# ቅዱስ ፡ ቁርአን ።

The Islamic Bulletin
PO Box 410186
San Francisco, CA 94141-0186 USA
www.islamicbulletin.org
info@islamicbulletin.org

# መግቢያ

የመጽሐፍ ዝግጅት እጅግ በጣም አድካሚና ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ሥራ ነው። ይልቁንም የሰው ልጆች ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ይመሩበት ዘንድ አስፈላጊ የሆነው መለኮታዊ ድንጋጌ፣ ግሳጼ፣ ማስጠንቀቂያና ብሥራት እንዲሁም የሩቁና የቅርቢቱ ዓለም ጥልቅ ምስጢራትና የፍጥረታትን እፁብ ድንቅ አፈጣጠር አካትቶ የያዘውን እንደ ቅዱስ ቁርአን ያለ አምላካዊ ቃል፣ በነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ላይ ከተወረደበት የዐረብኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ ቋንቋ ተርጉሞ ለሕትመት ማብቃት ምንኛ ከባድ እና ብርቱ ጥንቃቄን የሚሻ እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም።

በኢትዮጵያ አቆጣጠር ሐምሌ 18 ቀን 1958 ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፊት ቀርበው ቅዱስ ቁርአንን በአማርኛ ተርጉመው ለሕትመት ያበቁት ዘንድ ትእዛዝ የተቀበሉት የዚህ ቅዱስ ቁርአን ተርጓሚዎች ሥራው ምን ያህል በጥልቅ እውቀት፣ በጥልቅ ስሜትና በከፍተኛ ጥንቃቄ እንዳከናወኑት ሕያው ሥራቸው ራሱ ይመሰክራል።

ይህ የአማርኛ ቅዱስ ቁርአን በመቅድሙ ላይ በስም በተጠቀሱት ሙስሊም ሊቃውንት ተተርጉሞና ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በተመረጡ ሊቃውንት ታርሞ በዋና ተርጓሚዎቹ ሸህ ሰይድ ሙሐመድ ሳቢቅ እና በሐጅ ሙሐመድ ሣኒ ሐቢብ (አላህ የበጐ ሥራ ምንዳቸውን ይክፈላቸው) ተጠባባቂነትና አራሚነት በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት የታተመው በ1961 ነው። ነገር ግን ሕትመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በወጉ ተጠርዞ ለተጠቃሚው የኢትዮጵያ ሙስሊም ኅብረተሰብ የተሠራጨው እጅግ በጣም ጥቂት ቅጅ ብቻ ነበር። ይልቁንም ቁጥራቸው ከሃያ ሺህ የማያንስ እንደነበር የሚገመት የዚሁ የአማርኛ ቅዱስ ቁርአን ያልተጠረዙ ቅጂዎች በማተሚያ ቤቱ መጋዘን ውስጥ እንደተከመሩ ከሃያ አምስት ዓመት በላይ አስቆጥረው ነበር።

ከትርጉም ሥራውና ከእርማቱ ባሻገር የሕትመት ሂደቱን ጨምሮ ከሁለት ዓመት ላላነሰ ጊዜ ተደክሞበት በ1961 ለመጨረሻው ሕትመት የበቃው የቅዱስ ቁርአን የአማርኛ ትርጉም በሰፊው ላለመሠራጨቱ ከአፄው እና ከደርግ ሥርዓት አንጻር ሁለት አቢይ ምክኒያቶችን በእርግጠኝነት መጥቀስ ይቻላል። ከአፄ ኃይል ሥላሴ አንጻር ንጉሠ

ነገሥቱ ቅዱስ ቁርአን በአማርኛ እንዲተረጐም ያዘዙት ለመላው የኢትዮጵያ ሙስሊም ሕዝብ በማሰብ ሳይሆን በሰሜን አፍሪካም ሆነ በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ የኢስላም መንግሥታትን ወዳጅነት ለማግኘት ከሚል ዲፕሎማሲያዊ ዓላማ በመነጨ ብቻ በመሆኑ ነው። ይህንንም ሐቅ በትርጉም ሥራው ውስጥ ተካፋይ የነበሩት ሐጅ በሽር ዳውድ መስክረዋል። ይልቁንም የአፄ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓተ መንግሥት የአማርኛ ቅዱስ ቁርአን ይቅርና በዐረብኛ ቋንቋ የተዘጋጁ የእስልምና መጻሕፍት እንኳ የኢትዮጵያን የጠረፍ ድንበር አልፈው እንዳይገቡና ሙስሊሙ እንዳይነቃ ጥብቅ ትእዛዝ ያዘለ ቀላጤ ለየጠረፍ አገሩ አስተዳዳሪዎች ያስተላለፉት ቀን ይፋ ያወጣቸው ሠነዶች ያረጋገጡት ሐቅ ነው።

የደርግ ሥርዓትም ከአፄው ሥርዓት የተሻለ መስሎ ለመታየት፣ የሙስሊሞች ሃይማኖታዊ በዓላትን ብሔራዊ በዓል አድርጐ ማወጅን የመሰሉ ጥቂት እርምጃዎችን ከመውሰዱ በስተቀር የእምነት ነፃነትን የሚያከብር፣ ሃይማኖታዊ እውቀትና ትምህርትን በጽሑፍ ማሠራጨ ትን መፍቀድ ቀርቶ በአፄው የአካባቢ ሁኔታዎች አስገዳጅነት የታተ መውን ቅዱስ ቁርአን እንዲቃጠል አዞ ነበር። ለአሥራ ሰባት ዓመታት በዘለቀው የደርግ አገዛዝ ዘመን ለሕትመት የበቁት የእስልምና ማስተማሪያ መጻሕፍት ግማሽ ደርዘን እንኳ የማይሞሉ መሆናቸው ለዚህ በቂ ማስረጃ ነው።

በኢትዮጵያ በደርግ ሥርዓት ውድቀት ማግስት የሃይማኖቶች እኩልነ ትና የእምነት ነፃነት ከቀደሙት ሥርዓቶች ጋር ሊነጻጸሩ በማይችል ደረጃ የተከበረበት ሁኔታ በመፈጠሩ፣ በ1984 ነጃሺ ኢስላሚክ አሣታሚ ድርጅት በአገሪቱ የመጀመሪያው ሕጋዊ ኢስላማዊ አሣታሚ ድርጅት ሆኖ ሊቋቋም ችሏል። ድርጅቱ ኢስላማዊ ትምህርትና እውቀትን በአገር ቋንቋዎች በሕትመት እያዘጋጀ በማሰራጨት የሙስሊሙን ኅብረተሰብ ሃይማኖታዊ እውቀትና እሴት በማጐልበት ዓላማ ሁለት ዓመት ገደማ እንደተንቀሳቀሰ (በ1986 መጨረሻ አካባቢ) አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ከ25 ዓመት በፊት ያተመውን የአማርኛ ቅዱስ ቁርአን በግልጽ ጨረታ ለሽያጭ አቀረበ። ነጃሺ ኢስላሚክ አሣታሚ ድርጅት በጨረታው ላይ ተሳትፎ የቅዱስ ቁርአኑን የሽያጭ ጨረታ በማሸነፍ ባለበት ሁኔታ ገዝቷል። የአማርኛውን ቅዱስ ቁርአን በነበረበት ሁኔታ ሲገዛ አቢይ ዓላማ ያደረገው የቁርአኑ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ ለታለመው ኅብረተሰብ በስፋት ማሠራጨት ነው። በመሆኑም ላለፉት አሥር ዓመታት በተቻለ መጠን ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለተጠቃሚው አቅርቧል።

ከዚህ በተጓዳኝ ነጃሺ ኢስላሚክ አሣታሚ ድርጅት በ1961 የአማር ኛው ቅዱስ ቁርአን ባለፈበት የሕትመት ሂደት የተፈጠሩበትን በርካታ (የፊደላት ግድፈትን የመሰሉ) እንከኖችን በሥራው ባሕሪ ለማስተዋል የቻለ ከመሆኑም ባሻገር ቅጅዎቹን ገዝተው ከሚጠቀሙ አንባቢዎችም የተለያዩ የሕትመት ጉድለት ጥቆማዎች ደርሰውታል። እነኝህ ግድፈ ቶች በዋነኞቹ ተርጓሚዎች ተነቅሰው ወጥተው በመጀመሪያው ቅጅ የመጨረሻ ገጾች የግድፈት ማረሚያ ላይ ከተካተቱት ተጨማሪ በነጃሺ ኢስላሚክ አሣታሚ በተለያዩ ጊዜያት ለተሰበሰቡት ለእነዚህ ግድፈ ቶች ተጨማሪ የግድፈት ማረሚያ አትሞ ከጥራዙ ጋር በማያያዝ ሲያሰራጫቸው ቆይቷል።

በ1961 በታተመው የአማርኛ ቅዱስ ቁርአን ላይ ከበርካታ ተጠቃሚዎች የተሰነዘረው ሌላው አስተያየት ለገጽ፣ ለጁዝእ (ክፍል)፣ ለሱራ (ምዕራፍ) እንዲሁም ላአያ (አንቀጾች) መለያነት ጥቅም ላይ ውሎ የነበረው የግዕዝ ቁጥሮች ላይ ያተኮረ ነው። የግዕዝ ቁጥሮች በዛሬው ዘመን የአገራችን ኅብረተሰብ እጅግም አይታወቅም። ይህም ሁኔታ በዐረብኛም ሆነ በእንግሊዝኛ ቋንቋ በተዘጋጁ የእስልምና ትምህርት መጻሕፍት ላይ ከሚጠቀሱ የቁርአን አንቀጾች በመነሻነት የአማርኛውን ቅዱስ ቁርአን ለማጣቀስ የሚደረጉ ጥረቶችን አዳጋች እንዳደረገው ለመረዳት ተችሏል።

ይህ የቅዱስ ቁርአን የአማርኛ ትርጉም ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሁለት አበይት ችግሮች ለመፍታት፦ 1ኛ ከፊደል ግድፈት እርማት አኳያ ከዚህ ቀደም ከተሠራው ሥራ ለየት የሚለው አዲስ ነገር የግድፈት ማረሚያዎቹን ከጥራዙ በስተመጨረሻ በሰንጠረዥ ከማካ ተት ይልቅ ግድፈት ያለበትን ቃል እዚያው በሚገኝበት ሥፍራ ላይ በትክክለኛው ቃል የተተካ ሲሆን፣ 2ኛ የግዕዝ ቁጥሮቹም በዚሁ መልክ በመላው ሕዝብ በስፋት በሚታወቁት የዐረብኛ አኃዞች ተተክተዋል።

በ1961 ትርጉም ላይ ምዕራፍ 26 (ሱረቱል ሹዓራእ) በሕትመት ስህተት ተዘልሎ የነበረውን አንቀጽ 33 በተለየ ወረቀት ላይ በማተም ከአንቀጽ 32 በመቀጠል እንዲነበብና 'ከአንቀጽ 34 ጀምሮም እስከ

ምዕራፉ መጨረሻ አንድ አንድ ቁጥር እየተጨመረ እንዲነበብ" የሚገልጽ ማሳሰቢያ የነበረበት ሲሆን፥ ይህ አንቀጽና ማሳሰቢያው የሰፈረበት ገጽ ተቀዶ ቢጠፋ እርማቱም አብሮ የሚጠፋ መሆኑን በማስተዋል የተዘለለውን የሱረቱል ሹዓራእ 33ኛ አንቀጽ በቦታው አስገብተን አንቀጾቹንም ተራ ቁጥሩ በማሳሰቢያው ላይ በተጠቀሰው መሠረት አስተካክለነዋል።

ከዚህ ውጭ አገራችን ባፈራቻቸው ምርጥ ዓሊሞች ከ1958 እስከ 1961 ባለው ጊዜ ውስጥ በተተረጐመው የአማርኛ ቅዱስ ቁርአን ላይ የተጨመረም ሆነ የተቀነሰ አንዳችም ነገር የለም። የቅዱስ ቁርአን የ1961 የአማርኛ ትርጉም የራሱ የሆነ ወጥ የአተረጓጐም ሥልት፣ የቋንቋ ምጥቀትና ጥልቀት ያለው እንደመሆኑ ሥራውን ላከናወኑት ታላላቅ ዓሊሞቻችን የመልካም ሥራቸውን ምንዳ እንዲከፍላቸው አላህን እንለምነዋለን። የሥራቸውም ፍሬ ተጠቃሚዎች ለመሆን ያብቃን።

ይህ የቅዱስ ቁርአን የትርጉም ሥራ የተከተለው የቃል በቃል የአተረጓጐም ስልት በመሆኑና ትንታኔም የሌለው በመሆኑ በርካታ አንባቢያን ትንታኔ ያለው የትርጉም ሥራ እንዲሠራ ባቀረቡት ሐሳብ መነሻነት ነጃሺ ኢስላሚክ አሣታሚ ድርጅት አዲስ የትርጉም ሥራ አቅርቧል። ይኸው በአቶ ሐሰን ታጁ ዋና ተርጓሚነት በአቶ ኢድሪስ ሙሐመድ ረዳት ተረጓሚነትና ኤዲተርነት የተዘጋጀው የቁርአን ትርጉም ሥራው በ1991 ተጀምሮ 1997 የተጠናቀቀ ሲሆን በ11 ጥራዝ ታትሞ ለአንባቢያን ቀርቧል። የዚህ ትርጉም ሥራ ሰፊ የግርጌ ማስታወሻና ማብብሪያ ያለው ሲሆን ከአማርኛው ትርጉም ጐን ለጐን የዐረብኛውን ቁርአን አካቷል። ይህን በ11 ጥራዝ የቀረበውን የቅዱስ ቁርአን ትርጉም አባሪ በመጨመር በአንድ ጥራዝ የማውጣት ዕቅድ ያለን ሲሆን አላህ ይህንኑ እንዲያሳካልን እንለምነዋለን።

ነጃሺ ኢስላሚክ አሣታሚ ድርጅት

# መ ቅ ድ ም ።

ቁርኣን ፡ በማንበቡ ፡ የሚጸለይበት ፤ ያለፈው ፡ ታሪክና ፡ የጊዜው ፡ ድርጊት ፤ መጪውም፡ ትንቢት ፡ የተጠቀሰበት ፤ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ለሥጋዊና ፡ ለመንፈሳዊ ፡ አስፈላጊው ፡ ሕግ ፡ የተደነገገበት ፤ የወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ጽድቅና ፡ ኩነኔ ፡ ዝርዝር ፡ የተገለጸበት ፤ የታላላቆቹ ፡ ነቢያት ፡ የሃይማኖት ፡ ጥርሪ ፡ (ስብከት) ፡ የተነገረበት ፤ በአነጋገሩ ፡ ጠቅላላነትና ፡ በዐረፍተ ፡ ነገሩም ፡ ለሰካክ ፡ ስድም ፡ ቅኔም ፡ ሳይኾን ፤ ለየምዕራፎቹ ፡ የተለያዩ ፡ ተመሳሳይ ፡ የኾኑ ፡ ዜማዊ ፡ ማሳረፊያዎች ፡ ያሉት ፤ ሰዎችም ፡ ጋኔኖችም ፡ ሁሉ ፡ ቢተባበሩም ፡ እንኳ ፡ ከምዕራፎቹ ፡ የአንዲቱንም ፡ ምዕራፍ ፡ ተመሳሳይ ፡ ለማምጣት ፡ ፈጽሞ ፡ አይችሉም ፡ በማለት ፤ በሌሊት ፡ ጉዞና ፤ በላም ፤ በዩናስ ፡ . . . . . ምዕራፎች ፡ ውድድር ፡ የተደረገበት ፤ በነቢዩ ፡ ሙሐመድ ፡ ላይ ፡ የተወረደ ፤ አምላካዊ ፡ ቃል ፡ ነው ፤ እንጂ ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የማያውቀው ፡ ነቢይ ፡ ቃል ፡ አይደለም ።

ተመሳሳዩን ፡ ለማምጣት ፡ አይቻልም ፡ በማለት ፡ ውድድር ፡ የተደረገው ፡ በዐረብኛው ፡ አነጋገር ፡ በመኾኑ ፡ በሌላ ፡ ቋንቋ ፡ ሲተረጐም ፡ ታምርነቱ ፡ ይቀነሳል ፡ በማለት ፡ ከእስላም ፡ ሊቃውንት ፡ ከፊሎቹ ፡ መተርጐሙ ፡ ክልክል ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

እርግጠኛው ፡ ነገር ፡ ትርጉም ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ነው ፤ አንዱ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ትርጉም ፡ ሲኾን ፡ ሁለተኛው ፡ ፍቺውን ፡ መተርጐም ፡ ነው ። ለየቋንቋው ፡ የተለያየ ፡ ባህል ፡ ስላለው ፡ በዐረብኛው ፡ አቀማመጥ ፡ ተራ ፤ ቃል ፡ በቃል ፡ መተርጐሙ ፡ ሙሉ ፡ ስሜት ፡ ስለማይሰጥ ፡ ክልክል ፡ ቢኾንም ፡ ፍቺውን ፡ መተርጐም ፡ አይከለከልም ።

ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ሮበርት ፡ ኬኔት ፡ Robert Kennet በ1ሺሕ ፡ 143 ፡ ዓ ፡ ል ፡ በላቲን ፡ ቋንቋ ፡ ተርጕሞታል ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የምሥራቅን ፡ ባህል ፡ የመረመሩት ፡ ምዕራባውያን ፡ በፈረንሳዊና ፡ በእንግሊዝ ፤ በጀርመን ፤ በእስፓኝ ፤ በኢጣሊያ ፤ በግሪክ ፤ በፖርቱጊስ ፤ በሆላንድ ፤ በስዊድን ፤ በሩስያ ፡ ቋንቋዎች ፡ ተርጕመውታል ። በኢራን ፤ በህንዱስታን ፤ በፓክስታን ፤ በጃዋ ፤ በቱርክ ፤ እንዲሁም ፡ በዕብራይስጥ ፤ በሌሎችም ፡ ቋንቋዎች ፡ ተተርጕሟል ።

አብዛኛዎቹ ፡ ትርጕሞች ፡ ትክክል ፡ ባለመኾናቸው ፡ የአዝሃር ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የበላይ ፡ መሪ ፡ በ1936 ፡ ዓ ፡ ል ፡ ስሕተቱን ፡ ለማስወገድ ፡ *በሙስሊም፡ ሊቃውንት* ፡ መተርጐም ፡ ያስፈልጋል ፡ ሲሉ ፡ አትተዋል ። ገሚሶቹ ፡ የቁርኣን ፡ ታምራትነት ፡ በዐረብኛው ፡ አነጋገር ፡ በመኾኑና ፡ ዐረብኛም ፡ የእስልምና ፡ ምልክት ፡ በመኾኑ ፡ በሌላው ፡ ቋንቋ ፡ መተርጐሙ ፡ ክልክል ፡ ነው ፤ ቢሉም ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ፈቅደውታል ። በካይሮም ፡ በዐማንም ፡ የተሰበሰበው ፡ *ሙስሊም፡ ሊቃውንት* ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ጉባኤ ፡ ተስማምቶበታል ።

ኢትዮጵያ ፡ ልጆቿን ፡ በመካከላቸው ፡ ልዩነት ፡ ሳታደርግ ፡ አፍቅራና ፡ አስተባብራ ፡ ከመኖሯ ፡ በላይ ፡ እንግዶችንም ፡ ቢኾን ፡ በአክብሮት ፡ ተቀብላ ፡ የምታስተናግድ ፡ አገር ፡ መኾኗ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ነቢዩ ፡ ሙሐመድ ፡ በ610 ፡ ዓ ፡ ል ፡ በተነሱ ፡ ጊዜ ፡ ነገዶቻቸው ፡ ተከታዮቹን ፡ ስለአሠቃዩዋቸው ፡ «ሐበሻ ፡ (ኢትዮጵያ) ፡ የእውነት ፡ አገር ፡ ናት ፤ በውስጧም ፡ ሰውን ፡ የማይበድል ፡ እርሱም ፡ ዘንድ ፡ አንድም ፡ የማይበደል ፡ ንጉሥ ፡ አለና ፤ ወደዚያ ፡ ብትኼዱ ፡ መልካም ፡ ነው ›› በማለታቸው ፤ በመጀመሪያ ፡ በ615 ፡ ዓ ፡ ል ፡ የነቢዩ ፡ ሴት ፡ ልጅና ፡ ኸሊ

ፋው ፡ ዑስማን ፤ የአጐታቸው ፡ ልጅ ፡ ጃዕፈር ፡ የሚገኙባቸው ፡ 16፡ ስደተኞች ፤ ዳግመኛም ፡ ከመቶ ፡ በላይ ፡ የሚኾኑ ፡ የሃይማኖት ፡ ጥገኞች ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገብተው ፡ 15 ፡ ዓመት ፡ በመልካም ፡ ጥገኝነት ፡ ተቀምጠዋል ።

ጠላቶቻቸውም ፡ ስደተኞቹ ፡ ተይዘው ፡ እጃቸው ፡ እንዲመለስላቸው ፡ ቢጠይቁ ፤ ንጉ ሡ ፤ ገንዘብ ፡ ያላጠፋ ፡ ነፍስ ፡ ያልገደሉ ፡ መኾናቸውን ፡ አጣርቶ ፤ አሳልፌ ፡ አልሰጥም ፡ በማለቱ ፤ ጥገኛን ፡ አሳልፎ ፡ ያለመስጠት ፡ ሕግ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ተጀመረ ፡ እንደሚባል ፤ ነቢዩ ፡ ሙሐመድም ፡ ለተከታዮቻቸው ፡ «ሐበሾችን ፡ (ኢትዮጵያውያኖችን) ፡ ካልወጉዋችሁ ፡ አትውጉዋቸው ፡» ማለታቸው ፡ ይነገራል ። ንጉሡም ፡ ድርብ ፡ ምንዳ ፡ ያለው ፡ ጻድቅ ፡ ንጉሥ ፡ መኾኑ ፡ በቁርኣን ፡ በ3ም. 199 ፡ አንቀጽ ፡ በ28ም. 52-54 ፡ አንቀጽ ፡ ተገልጿል ።

ቁርኣን ፡ ሕያው ፡ በኾኑት ፡ ቋንቋዎች ፡ ሁሉ ፡ የተተረጐመ ፡ ጥቀስ ፡ ብዙ ፡ በመኾኑ ፡ ታላቁ ፡ መሪያችን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፤ ሙስሊም ዜጐቻቸው ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ በቋንቋቸው ፡ እንዲማሩ ፡ ለማድረግና ፡ የሃይማኖትም ፡ ነጻነት ፡ የሚታመንበት ፡ በመኾኑ ፡ መልካም ፡ ፈቃዳቸው ፡ ኾኖ ፡ ሐምሌ ፡ 18 ፡ ቀን ፡ 1958 ፡ ዓ ፡ ም ፡ (በ25 ፡ 7 ፡ 1966 ፡ ዓ ፡ ል ፡) በክቡር ፡ ዶክተር ፡ ምናሴ ፡ ኀይሌ ፡ አማካይነት ፡ ቀርበን ፡ በአማርኛ ፡ እንድንተረጕመው ፡ ስላዘዙን ፡ ከአሥራ ፡ አምስት ፡ ወሮች ፡ በማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ተርጕመነዋል ። የግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ትእዛዝ ፡ ከግቡ ፡ እንዲደርስ ፡ ክቡር ፡ ዶክተር ፡ ምናሴ ፡ ኀይሌ ፡ ሥራው ፡ እንዲቃና ፡ ያደረጉት ፡ ድካምና ፡ የፈጸሙት ፡ ቀን ፡ አገልግሎት ፡ ለሁልጊዜም ፡ የማይረሳ ፡ ነው ። የተረጐምነውም ፡ ከዚህ ፡ በሚከተለው ፡ አኳኋን ፡ ነው ።

1ኛ ፤ የአማርኛና ፡ የዐረብኛ ፡ ቋንቋዎች ፡ በጣም ፡ የተቀራረቡ ፡ በብዙ ፡ ቃላት ፡ ቤት ፤ ደም ፤ ነፍስ ፤ ዐፈር ፤ ፈረስ ፤ ዐንበሳ ፤ እነዚህን ፡ በመሳሰሉ ፡ ቃላትና ፡ በግሥ ፡ አረባብም ፡ የሚመሳሰሉ ፡ ቋንቋዎች ፡ ቢኾኑም ፡ በአነጋገር ፡ ስልታቸው ፡ የተለያዩ ፡ በመኾናቸው ፤ ባለቤትን ፡ ከግሥ ፡ ማስቀደምን ፡ በመሰለ ፡ በጠቀላላው ፡ በዐረፍተ ፡ ነገር ፡ አቀነባበርም ፡ የአማርኛውን ፡ ባህል ፡ ተከትለናል ።

2ኛ ፤ ዐረብኛው ፡ በአመልካች ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ መድረሻ ፡ ላይ ፡ አገናዛቢ ፡ አጸፋ ፡ ስለሚያስገባ ፤ ይህ ፡ በሚለው ፡ ላይ ፡ ይሃችሁ ፡ በሚለው ፡ ዓይነት ፡ የዐረብኛውን ፡ ጠባይ ፡ ተከትለናል ።

3ኛ ፤ በዐረብኛው ፡ አነጋገር ፡ ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ኾኖ ፡ ሳለ ፡ በአማርኛው ፡ መግለጽ ፡ በሚያስፈልገው ፡ ላይ ፡ የቁርኣን ፡ አታቾች ፡ በሰጡት ፡ ፍች ፡ መሠረት ፡ ገልጸን ፡ በቅንፍ ፡ አጥረነዋል ። አታቾቹ ፡ ሊቃውንት ፡ በሚለያዩበት ፡ ሁሉ ፤ ለሁሉም ፡ ተስማሚ ፡ በኾነ ፡ ቃል ፡ ተርጕመነዋል ። በአንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሐሳቡ ፡ ግልጽ ፡ ያልኾነውን ፡ በቍጥር ፡ እያወጣን ፡ በሕዳግ ፡ ላይ ፡ አብራርተነዋል ። በተቻለን ፡ መጠን ፡ ነጠላውን ፡ በነጠላ ፡ ብዙውን ፡ በብዙ ፤ ስሙን ፡ በስም ፡ ግ ሡን ፡ በግሥ ፡ ለመተርጐም ፡ ሞክረናል ።

4ኛ ፤ ገባ ፡ የሚለው ፡ ግሥ ፡ በአማርኛ ፡ ገቢርና ፡ ተገብሮ ፡ በመኾኑ ፡ ወላዋይ ፡ ግሥ ፡ ሲኾን ፡ በቁርአን ፡ ውስጥ ፡ ገቢር ፡ ብቻ ፡ ኾኖ ፡ ስለሚገኝ ፡ ይህንኑ ፡ ተከትለናል ።

5ኛ ፤ እኛ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በዐረብኛው ፡ ሕግ ፡ ከብዙዎች ፡ ጋር ፡ ኾኖ ፡ ለሚናገር ፡ ወይም ፡ ነፍሱን ፡ አክባሪ ፡ ለኾነ ፡ ነጠላ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሦች ፡ እኛ ፡ እያሉ ፡



እንደሚጠቀሙበት ፡ አምላክም ፡ ስለ ፡ ነፍሱ ፡ በነጠላ ፡ እንደሚናገር ፡ በብዙም ፡ ቃል ፡ እኛ ፡ ፈጠርናችሁ ፡ እኛ ፡ ቁርኣንን ፡ አወረድነው ፤ እኛም ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ነን ፡ ሲል ፡ ይናገርበታል ። ይህም ፡ አንድነቱን ፡ አይቃወምም ።

6ኛ ፤ ሐተታው ፡ እንዳይሰለች ፡ አነጋገርን ፡ ለማለዋወጥ ፡ (ኢልቲፋት) ፡ መገላመጥ ፡ የሚባለው ፡ አነጋገር ፡ በዐረብኛ ፡ ተወዳጅና ፤ የሚያነቃቃ ፡ ስለኾነ ፤ በቁርአን ፡ ውስጥ ፡ በብዛት ፡ ይገኛል ። ይህም ፡ በአንደኛ ፡ ወይም ፡ በሁለተኛ ፡ ወይም ፡ በሦስተኛ ፡ መደብ ፡ ሲያትት ፡ ከአንዱ ፡ መደብ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ አዛውሮ ፡ ማተት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ በ2ም. 57 ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ደመናን ፡ አጠለልን ፤ በናንተም ፡ ላይ ፡ መናን ፡ አወረድን ፤ እኛን ፡ አልበደሉንም ፤ ግን ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ ይበድሉ ፡ ነበር ፤ ሲል ፡ ከሁለተኛ ፡ ወደ ፡ ሦስተኛ፡ ተዛውሯል። በ3:195 ፡ ላይ ፡ ከናንተ ፡ ከወንድም ፡ ከሴትም ፡ የሠረን ፡ ሥራ ፡ አላጠፋም ፡ ሲል ፡ ጌታቸው ፡ ተቀበላቸው ፤ እነዚያም ፡ የተሰደዱ ፡ ከነሱ ፡ ኃጢአቶቻቸውን ፡ አብብሳለሁ ፡ ሲልም ፡ ከሦስተኛ ፡ ወደ ፡ አንደኛ ፡ ተዛውሯል ። ከሦስተኛ ፡ ወደ ፡ አንደኛ ፡ በመዛወርም ፡ በ20:53 ፡ ላይ ፡ እርሱ ፡ ያ ፡ ከሰማይ ፡ ውሃን ፡ ያወረደ ፡ ነው ፤ በርሱም ፡ ከተለያዩ ፡ በቃይ ፡ ዐይነቶች ፡ አወጣንላችሁ ፡ ይላል ። ምሳሌዎችም ፡ በሚያደርጋቸው ፡ ነገሮች ፡ አስተያየቱ ፡ ጥልቀ ፡ በመኾኑ ፡ አጥብቀ ፡ መመልከትን ፡ ይጠይቃል ።

7ኛ ፤ ቁርኣን ፡ 114 ፡ ሱራዎች ፡ (ምዕራፎች) ፡ 6ሺሕ፡ 236 ፡ አያት ፡ (አንቀጾች) ፡ አሉት ። በየወሩ ፡ ለመነበብ ፡ እንዲቻልም ፡ ተከክል ፡ ኾኖ ፡ በ30 ጁዝእ ፡ (ክፍል) ፡ ተከፍሏል ። ሱራህ ፤ መሠረተ ፡ ፍቹ ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምድር ፡ ወይም ፡ ከፍታ ፡ ያለው ፡ የከተማ ፡ አጥር ፡ ሲኾን ፤ ከቁርአን ፡ ክፍሎች ፡ ዐዋቂያቸው ፡ ከፍታ ፡ ለሚኖረው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ ስም ፡ ኾኗል ። አያት ፡ ማለትም ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ ታምር ፡ ማለት ፡ ሲኾን ፤ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ለያዘ ፡ ማረፊያ ፡ ወይም ፡ ቍጥር ፡ ስም ፡ ተደርጓል ። በአማርኛ ፡ ሌላ ፡ ትርጉም ፡ ስላጣንላቸው ፡ ሱራን ፡ በምዕራፍ ፤ አያትን ፡ በአንቀጽ ፤ ተርጕመናል ። ረዢሙ ፡ የላም ፡ ሱራ ፡ 286 ፡ አያት ፡ ሲኖረው ፡ ከሦስት ፡ አያት ፡ ያነሰ ፡ ሱራ ፡ የለም ። የቁርአን ፡ ሱራዎች ፡ አብዛኞዎቹ ፡ የዘረፋ ፤ የሌሊት ፡ ጉዞ ፤ የሮም ፤ የጣሃ ፤ የያሲን ፡ ..... ምዕራፎች ፡ የተባሉት ፡ በመክፈቻቸው ፤ ወይም ፡ በመጀመሪያቸው ፡ በሚገኘው ፡ ቃል ፡ ተሰይመዋል ፤ ጥቂቶቹ ፡ ደግሞ ፡ 35 ፡ የሚኾኑት ፡ በውስጣቸው ፡ በተነገረው ፡ ቃል ፡ ተጠርተዋል ። የላም ፡ ምዕራፍ ፡ ከ66 ፡ ቍጥር ፡ በኋላ ፤ የዒምራን ፡ ቤተሰብ ፡ ከ32 ፡ ቍጥር ፤ የማእድ ፡ ምዕራፍ ፡ ከመቶ ፡ ዐሥር ፡ ቍጥር ፡ በኋላ ፡ በተነገረው ፡ ቃል ፡ ተጠርተዋል ። የአንቀጾች ፡ ቍጥር ፡ በዐረብኛው ፡ በመድረሻው ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፤ እኛ ፡ በመነሻው ፡ አድርገነዋል ። የክፍሎቹንም ፡ ምልክት ፡ አምስት ፡ ማ[illegible] ፡ ያላቸው ፡ ሦስት ፡ ከዋክብት ፡ አድርገናል ።

8ኛ ፤ ቁርኣን ፡ ሁለት ፡ አወራረድ ፡ አለው ። መጀመሪያ ፡ ከተጠበቀው ፡ ሰሌዳ ፡ በቀርቢቱ ፡ ሰማይ ፤ ወደሚገኘው ፡ ወደ ፡ ልቅናው ፡ ቤት ፡ በረመዳን ፡ ወር ፡ በከፍተኛይቱ ፡ ሌሊት ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ለጂብሪል ፡ ወርዷል ። የመጽሐፉም ፡ ተራ ፡ አቀማመጥ ፡ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ነው ።

ሁለተኛው ፡ አወራረድ ፡ በጂብሪል ፡ አማካይነት ፡ በነቢዩ ፡ ሙሐመድ ፡ ላይ ፡ በ23 ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ እየተከፈለ ፡ ነው ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ መካዊና ፡ መዲናዊ ፡ በመባል ፡ ተከፍሏል ። ክፍያውም ፡ ጊዜን ፡ እንጂ ፡ ስፍራን ፡ አይመለከትም ። መካዊ ፡

የሚባለው ፡ ከነቢዩ ፡ ስደት ፡ በፊት ፡ የወረደው ፡ ሲኾን ፡ መዲናዊ ፡ የሚባለው ፡ በመካም ፡ ቢኾን ፡ ከነቢዩ ፡ ስደት ፡ በኋላ ፡ የወረደው ፡ ነው ፡ የሚሉትን ፡ ተከትለናል ።

ቁርኣን ፡ በብራናም ፡ በሰሌዳም ፡ በአጥንትም ፡ በሰሌንም ፡ በስስ ፡ ድንጋዮችም ፡ ላይ ፡ የአያቶቹ ፡ ተራ ፡ ተጠብቆ ፡ ተጽፎ ፡ በነቢዩ ፡ ቤት ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ፤ ብዙዎቹ ፡ ምእምናች ፡ በቃላቸው ፡ አጥንተውት ፡ ሲኖሩ ፡ ከነቢዩ ፡ እረፍት ፡ በኋላ ፡ በ12ኛው ፡ ዓመተ ፡ ስደት ፡ በየማማህ ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ በቃላቸው ፡ ካጠኑት ፡ ብዙዎቹ ፡ ስለ ፡ አለቁ ፡ እንዳይጠፋ ፡ በመስጋት ፡ በዑመር ፡ አልኸጣብ ፡ አስታዋሽነት ፡ አቡበክር ፡ አልሲዲቅ ፡ ዘይድ ፡ ሣቢትን ፡ አዘው ፡ ጽሑፎቹንና ፡ በቃል ፡ ያጠኑትን ፡ እያመሳከረ ፤ የአያቶቹን ፡ ተራ ፡ ጠብቆ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በአንድ ፡ ጥራዝ ፡ ሰበሰበው ። ስም ፡ አውጡለት ፡ ተብሎ ፡ ገሚሶቹ ፡ ሲፍር ፡ ይባል ፡ ቢሉ ፤ ይህ ፡ የአይሁድ ፡ አጠራር ፡ መኾኑን ፡ ጠልተው ፡ የሐበሻ ፡ (ኢትዮጵያ) ፡ ሰዎች ፡ መሰሉን ፡ መጽሐፍ ፡ ይሉታል ፡ በማለት ፡ መጽሐፍ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ፡ ማለትን ፡ ኢትቃን ፡ በ 1:89 ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ያስረዳል ።

ዳግመኛ ፡ ኸሊፋ ፡ ዑስማን ፡ በ25ኛው ፡ ዓመተ ፡ ስደት ፡ ባነባበቡ ፡ ግጭት ፡ ስለተገኘ ፡ በአራት ፡ የቁርአን ፡ ሊቃውንት ፡ በተከናወነ ፡ ጉባኤ ፡ የቃላቱን ፡ አጻጻፍ ፡ ያለነጥብ ፡ ለየን ባቡ ፡ ተስማሚ ፡ አድርገው ፡ በመጀመሪያው ፡ አወራረድ ፡ መሠረት ፡ የሱራዎቹንም ፡ ተራ ፡ ጠብቀው ፡ ሰበሰቡት ፤ ኸሊፋውም ፡ በአምስት ፡ ኮፒዎች ፡ አስጽፎ ፡ አንዱን ፡ ለራሱ ፡ አስቀርቶ ፡ አራቱን ፡ ለመካና ፡ ለደማስቆ ፤ ለበስራ ፤ ለኩፋ ፤ ከተሞች ፡ ልኮ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከነዚህ ፡ ብቻ ፡ እንዲገለበጥ ፡ አድርጐ ፡ የቀረውን ፡ ስለ ፡ አቃጠለው ፡ ቁርኣን ፡ አንድነቱን ፡ ጠብቆ ፡ ይኖራል ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ምንም ፡ መለዋወጥ ፡ አልደረሰበትም ።

9ኛ ፤ በመካ ፡ ከወረዱት ፡ 27ና ፡ በመዲና ፡ ከወረዱት ፡ ሁለቱ ፡ በጠቅላላው ፡ 29ኙ ፡ ሱራዎች ፡ በማኅጸረ ፡ ቃላት ፡ ተጀምረዋል ። በዐረብኛ ፡ መሠረተ ፡ ቃላት ፡ ከአምስት ፡ ፊደላት ፡ ስለማይበልጥ ፤ እነዚህም ፡ ቃላት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ በሚደርሱ ፡ ፊደላት ፡ ተቀናብረዋል ። ዐረብኛ ፡ ቀርጻቸው ፡ 13 ፡ ዐይነት ፡ ብቻ ፡ ሲኾን ፡ ያልተደጋገሙት ፡ ፊደላት ፡ 14 ፡ በመኾናቸው ፡ ከጠቅላላው ፡ ከ28 ፡ ፊደላት ፡ ግማሹ ፡ ናቸው ።

ፍቾቻቸው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አታቸች ፡ ተለያይተውባቸዋል ። ከፊሎቹ ፡ ፍቾቻቸውን ፡ ከአላህ ፡ በስተቀር ፡ የሚያውቀው ፡ የለም ፡ የሚሉ ፡ ሲኾኑ ፤ ሌሎቹ ፡ ከአላህ ፡ ስሞች ፡ የአንዳንድ ፡ ፊደል ፡ ጥቅስ ፡ ናቸው ፡ ይላሉ ። የምዕራፍ ፤ ወይም ፡ የመጽሐፉ ፡ ስሞች ፡ ናቸው ፡ የሚሉም ፡ አሉ ። ግን ፡ አብዛኛዎቹ ፡ እንደ ፡ አረጋገጡት ፡ የቁርአን ፡ አነጋገር ፡ አስደናቂ ፡ በመኾኑ ፡ ብዙዎቹ ፡ ዐረቦች ፡ ነቢዩ ፡ ሙሐመድ ፡ በመልካም ፡ ድምጽ ፡ ሲያነቡት ፡ ተሰብስበው ፡ እያዳመጡ ፡ በግሣጼው ፡ ተሸንፈው ፡ ስለ ፡ ተከተሉት ፡ ከሐዲዎቹ ፡ ድግምት ፡ ስለአለበት ፡ ይስባችኋልና ፡ አታዳምጡት ፡ እያሉ ፤ እንዳይሰሙት ፡ ይንጫጩ ፡ ስለነበረ ፡ እነዚህን ፡ ማህጸረ ፡ ቃላት ፡ ባሰሟቸው ፡ ቍጥር ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ንግግሮች ፡ ናቸው ፡ እያሉ ፡ በማሰላሰል ፡ ዝም ፡ ሲሉ ፡ ንባቡን ፡ አስከታትለው ፡ ብዙዎቹን ፡ ያሳመኑባቸው ፡ ምስጢረ ፡ ቃላት ፡ ናቸው ፡ ይላሉ ።

10ኛ ፤ ከ1ሺሕ ፡ 435 ፡ እስከ ፡ 1ሺሕ ፡ 505 ፡ ዓ ፡ ል ፡ የነበረው ፡ ሱዩጢ ፡ ኢትቃን ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ቁርአን ፡ በዐረብኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተወረደ ፡ ቢኾንም ፡ ከዕብራይስጥና ፡ ከሮም ፡ ከፋርስ ፡ አንዳንድ ፡ ቃላት ፡ አለበት ፡ ይላል ። ከዐረብኛ ፡ ግሥ ፡ መሠረት ፡ የሌላቸው ፡ ሃያ ፡ ስድስት ፡ ያክል ፡ የሚኾኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቃላት ፡ እንዳለበትም ፡ ያስረዳል ።



እነሆ ፤

ከዕብራይስጥ ፤

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጀሀነም ፡ | ገሃነም ፡ (ሲኦል) ፡ | ሪቢይ ፡ | መምህር ፡ |

ከፋርስ ፤

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሱንዱስ ፡ | ስስ ፡ ሐር ፡ | ኢስተብረቅ ፡ | ወፍራም ፡ ሐር ፡ |
| አባሪቅ ፡ | ኢብሪቆች ፡ | ሱራዲቅ ፡ | ምድራፍ ፡ |
| ዘንጀቢል ፡ | ዝንጅብል ፡ | | |

ከሮም ፤

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቂንጣር ፡ | ኩንታል ፡ | ረቂም ፡ | ጽሑፍ ፡ |

ከኢትዮጵያ ፤

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጂብት ፡ | ድግምት ፡ | ታቡት ፡ | ታቦት ፡ |
| ጣሃ ፡ | ጸሐይ ፡ | ቡርሃን ፡ | ብርሃን ፡ |
| ኢብሊስ ፡ | ዲያብሎስ ፡ | ጣጉት ፡ | ጣዖት ፡ |
| ሐዋሪይ ፡ | ሐዋሪያ ፡ | ሚሕራብ ፡ | ምኵራብ ፡ (የጸሎት ፡ ስፍራ) ፡ |
| አዋህ ፡ | የዋህ ፡ | ሚሽካት ፡ | መስኮት ፡ |
| ማኢዳ ፡ | ማእድ ፡ | ኪፍል ፡ | ክፍል ፡ |
| በግል ፡ | በቅሎ ፡ | ፈጠረ ፡ | ፈጥጠረ ፡ |
| ሙናፊቅ ፡ | መናፍቅ ፡ | ደምደመ ፡ | ደመደመ ፡ |
| ኢብለዒ ፡ | ብልዒ ፡ (በትግርኛ) ፡ | | |

ከሚለው ፡ የተወሰዱ ፡ ናቸው ፡ ይላል ። የቋንቋ ፡ መግባባት ፡ የተለመደ ፡ ስለኾነ ፡ የዐረቦችም ፡ ቃላት ፡ ናቸው ፡ የሚሉም ፡ አሉ ።

11 ፤ ቁርአን ፡ አዳምን ፡ (አደም) ፡ ሄኖክን ፡ (ኢድሪስ) ፡ አብርሃምን ፡ (ኢብራሂም) ፡ ይስሐቅን ፡ (ኢስሓቅ) ፡ ዮሴፍን ፡ (ዩሱፍ) ፡ ኢዮብን ፡ (አዩብ) ፡ ሙሴን ፡ (ሙሳ) ፡ አሮንን ፡ (ሃሩን) ፡ ቆሬንን ፡ (ቃሩን) ፡ ኢያሱን ፡ (አልየሰዕ) ፡ (1) ሳኦልን ፡ (ጣሉት) ፡ ጐልያድን ፡ (ጃሉት) ፡ ዳዊትን ፡ (ዳውድ) ፡ ሰሎሞንን ፡ (ሱለይማን) ፡ ዕዝራን ፡ (ዑዘይር) ፡ ኤልያስን ፡ (ኢልያስ) ፡ ዮናስን ፡ (ዩኑስ) ፡ ዘካርያስን ፡ (ዘከሪያ) ፡ ዮሐንስን ፡ (የሕያ) ፡ የሱስን ፡ ወይም ፡ የሱዕን ፡ (ዒሳ) ፡ ማርያምን ፡ (መርየም) ፡ (2) ገብሬልን ፡ (ጂብሪል) ፡ ኦሪትን ፡ (ተውራት) ፡ ወንጌልን ፡ (ኢንጂል) ፡ ብሎ ፡ ስለሚጠራቸው ፡ በጠቅላላው ፡ በተጸውዖ ፡ ስም ፡ አጠራሩን ፡ ተከትለናል ።

እንዲሁም ፡ የአምላክ ፡ ስም ፡ በአማርኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ (የዓለም ፡ አምላክ) ፡ ሲኾን ፡ በዐረብኛ ፡ ዋና ፡ ስሙ ፡ አልላህ ፡ ነው ። ሌሎቹም ፡ ዘጠና ፡ ዘጠኝ ፡ መልካም ፡ ስሞች ፡ አሉት ።

አላህ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ሊገዙት ፡ ለሚገባው ፤ ዘላለም ፡ ሕያው ፡ (መታጣት ፡ ያልቀደመው ፡ መሞት ፡ የማይከተለው) ፡ ራሱን ፡ ቻይ ፡ (አስገኝ ፡ ጌታ ፡ መገኛ ፡ ቦታ ፡ የማይፈልገው) ፡ ለኾነ ፡ አምላክ ፡ የተጸውዖ ፡ ስም ፡ በመኾኑ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ትርጉም ፡ ስላለው ፡ ሳንተረጉም ፡ እንዳለ ፡ አስገብተነዋል ።


1 የሙሴ ፡ አገልጋይ ፡ ወጣት ፡ የነበረው ፡ ዩሸዕም ፡ ይባላል ።
2 ከማርያም ፡ ሌላ ፡ የሴት ፡ ስም ፡ የሔዋን ፡ እንኳ ፡ በቁርአን ፡ አልተነገረም ።

12ኛ ፤ ከዘመነ ፡ ብሉይ ፡ እስከ ፡ አራተኛው ፡ ዘመነ ፡ ልደት ፡ ያለ ፡ አናባቢ ፡ በግእዝ ፡ ፊደል ፡ ብቻ ፡ ይጻፍ ፡ የነበረው ፡ የግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ አማርኛም ፡ የሴም ፡ ቋንቋዎች ፡ ስለኾኑ ፡ እንደ ፡ ዐረብኛና ፡ ዕብራይስጥ ፡ ከቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ይጻፉ ፡ እንደነበሩ ፡ በአክሱም ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጽሑፍ ፡ ይመራናል ።

ፍሬምናጦስና ፡ አብረውት ፡ የነበሩት ፡ ከያሬት ፡ ቋንቋ ፡ ጋር ፡ ለማስማማት ፡ ጥርጊያ ፡ መንገዱን ፡ ለውጠው ፡ አናባቢዎቹን ፡ በፊደሉ ፡ ወገብና ፡ ግርጌ ፡ በራሱም ፡ ላይ ፡ ቀጥለው ፡ ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ እንዲጻፍ ፡ አድርገዋል ። የአልፋቤት ፡ ወይም ፡ የአቡጊዳ ፡ ተራውንም ፡ ለውጠው ፡ በሀሌታው ፡ ሀና ፡ ለ ፡ እንዲጀመር ፡ ወስነዋል ። የጥቂቶቹ ፡ ፊደላት ፡ ድምፅ ፡ ተለዋውጧል ። በምላስ ፡ ጫፍ ፡ የሚነገረው ፡ ንጉሡ ፡ ሠ ፡ ድምጹ ፡ ጠፍቶ ፡ እንደ ፡ እሳቱ ፡ ሰ ፡ ይነበባል ። በቅርብ ፡ ጉረሮ ፡ የሚነገረው ፡ ብዙኃን ፡ ኀና ፡ በመሃል ፡ ጉረሮ ፡ የሚነገሩት ፡ ሐመሩ ፡ ሐና ፡ ዓይኑ ፡ ዓ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ በትግርኛ ፡ ተጠብቀው ፡ ሳሉ ፡ በአማርኛ ፡ ንባባቸው ፡ እየደከመ ፡ ሄዶ ፡ ጠፍቷል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ አገባባቸው ፡ ስለሚጠበቅ ፡ አንዳንድ ፡ በፍራ ፡ ቢያመልጥም ፡ በተቻለን ፡ መጠን ፡ አገባባቸውን ፡ ጠብቀናል ። ድምፅ ፡ ማለት ፡ በኃይል ፡ በመነካካት ፡ ወይንም ፡ በመለያየት ፡ የሚገኝ ፡ የአየር ፡ ግጭት ፡ ሲኾን ፡ ከሰውም ፡ ከእንስሳም ፡ ከግዑዝም ፡ ይገኛል ።

ፊደል ፡ ግን ፡ በመናገሪያ ፡ አካል ፡ ላይ ፡ የሚጋጭ ፡ ድምፅ ፡ ነው ። ፊደላትም ፡ የሚነገሩት ፡ በጉረሮና ፡ በትናጋ ፡ በምላስ ፡ በከንፈር ፡ ነው ። የሚከተለውን ፡ ሥዕል ፡ ተመልከት ።




በሦ፡ ጉን፡ የሚገኘው ፡ ዘ ፡ በላቲን ፡ the ነው ።

ከነዚህም ፡ ሌላ ፡ ከሁለት ፡ ፊደላት ፡ የሚወጡ ፡ ይገኛሉ ። ተና ፡ ሸ ፡ ቸ ፤ ነና ፡ የ ፡ ኘ ፤ ከና ፡ ጀ ፡ ገ ፤ ጀና ፡ ሸ ፡ ዠ ፤ ተና ፡ ጠ ፡ ጨ ፤ በና ፡ ፈ ፡ ፐ ፡ ጸ ፤ ፈና ፡ በ ፡ ቨ ፤ ይኾናሉ ። ለቃላት ፡ መለያ ፡ ሁለት ፡ ነጥብ ፡ (፡) ለዓረፍተ ፡ ነገር ፡ አነስተኛ ፡ መክፈያ ፡ ነጠላ፡ ሠረዝ ፡ (፣) ለከፍተኛ ፡ መክፈያ ፡ ድርብ ፡ ሠረዝ ፡ (፤) ለሙሉ ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ አራት ፡ ነጠብጣብ ፡ (።) ለጥያቄ ፡ ምልክት ፡ (?) ለአንክሮ ፡ (!) የተለመደውን ፡ ተከትለናል ። በመጥበቅና ፡ በመላላት፡



ፍቹ ፡ የሚያሻማ ፡ ለኾነው ፡ ቃል ፡ በሚጠብቅ ፡ ጊዜ ፡ በመነሻው ፡ በኩል ፡ ሳድሱን ፡ ፊደል ፡ በመጨመር ፡ ተጠቅመናል ። ኾናም ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ፊደል ፡ ጠብቆ ፡ እንዲነበብ ፡ ያስፈልጋል ፡ ምሳሌውም ፡ ሙሳ ፡ አለ ፡ ስንል ከመናገር ፡ የኾነው ፡ አለ ፡ በመላላት ፡ ሲነገር ፤ ብርሃን ፡ አልለ ፡ ስንል ፡ ከመገኘት ፡ የኾነው ፡ ጠብቆ ፡ ስለሚነገር ፡ ል ፡ እንዲጨመር ፡ አድርገናል ። የትርጉሙም ፡ ሥራ ፡ በአቶ ፡ ሽፈራው ፡ ወርቁ ፡ አስተባባሪነት ፡ ዘሙሴ ፡ ሰሊም ፡ ቡሸቀራ ፡ ተጠባባቂነት ፡

ሐጂ ፡ በሺር ፡ ዳውድ ፡ ቢ. ኤ. ኤም. ኤ. ከአዝሀር ፡ ዩኒቨርስቲ ፡
ሸህ ፡ ዐብዱልከሪም ፡ ኑር ፡ ሑሴን ፡ ቢ. ኤ. አዝሀር ፡ ኤም. ኤ. እስክንድሪያ ፡

ከኾኑት ፡ መምህሮች ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ተከናውኗል ። ከየአገሩም ፡ የተመረጡ ፡ ሊቃውንት ፡ እንዲያርሙት ፡ ያስፈልጋል ፡ ስለ ፡ ተባለ ፤

| | |
|---|---|
| ሸህ ፡ ቡሸረልከሪም ፡ ሙስጠፋ ፡ | ከወሎ ፡ |
| ሐጂ ፡ ዩሱፍ ፡ ዐብዱረሕማን ፡ | ከሐረር ፡ |
| ቃዲ ፡ ሙሐመድ ፡ ዐብዱረሕማን ፡ | ከትግሬ ፡ |
| ሐጂ ፡ አሕመድ ፡ ዳለቲ ፡ | ከሸዋ ፡ |
| ሐጂ ፡ መንዛረሁ ፡ ከቢር ፡ ሑሴን ፡ | ከዐሩሲ ፡ |

ተመርጠው ፡ አብረን ፡ አርመነዋል ። በመጨረሻም ፡ ሁለታችን ፡ ደጋግመን ፡ አርመን ፡ በኛው ፡ ተጠባባቂነትና ፡ አራሚነት ፡ በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታትሟል ።

## ተ ር ጓ ሚ ዎ ች ፤

ሰይድ ፡ ሙሐመድ ፡ ሳዲቅ ፡
ሐጂ ፡ ሙሐመድ ፡ ሣኒ ፡ ሐቢብ ፡

በዚህ ፡ ትርጉም ፡ ከቁርኣን ፡ ተፍሲር ፡ (ፍች) ፡ ከዚህ ፡ በሚከተሉት ፤

1ኛ ፤ ከጀላለይንና ፡ ከሳዊ ፤
2ኛ ፤ ከተንዊር ፡ አልሚቅባስ ፤
3ኛ ፤ ከአቡ ፡ አልሱዑድ ፤
4ኛ ፤ ከኢብን ፡ ጁዘይ ፤
5ኛ ፤ ከነሰፊ ፤
6ኛ ፤ ከመራሕ ፡ ለቢድ ፤
7ኛ ፤ ከኻዚን ፤
8ኛ ፤ ከኢብን ፡ ከሢር ፤
9ኛ ፤ ከበይዷዊ ፡ ተጠቅመናል ። ከሙፍረዳት ፡ አልራጊብም ፡ በብዙ ፡ ወስደናል።

ከነዚህ ፡ አይወጣም ።

## ምዕራፍ ፡ 1 ፡ አል-ፋቲሐህ ። ክፍል ፡ 1 ።

1ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ፋቲሐህ ፡ (የመክፈቻይቱ ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፡ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 7 ፡ ናቸው ።

1 በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በኾነው ።
2 ምስጋና ፡ ለአላህ ፡ ይገባው ፡ የዓለማት ፡ ጌታ ፡ ለኾነው ፤
3 እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡
4 የፍርዱ ፡ ቀን ፡ ባለቤት ፡ ለኾነው ።
5 አንተን ፡ ብቻ ፡ እንግገዛለን ፤ አንተንም ፡ ብቻ ፡ ርዳታን ፡ እንለምናለን ።
6 ቀጥተኛውን ፡ መንገድ ፡ ምራን ።
7 የነዚያን ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ በጎ ፡ የዋልክላቸውን ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ያልተቆጣህባቸውንና ፡ ያልተሳሳቱትንም ፡ ሰዎች ፡ መንገድ ፡ (ምራን ፤ በሉ) ።

## ምዕራፍ ፡ 2 ፡ አል-በቀራህ ። ክፍል ፡ 1 ።

2ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-በቀራህ ፡ (የላም ፡ ምዕራፍ) ፡ በመዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፡ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 286 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 አ.ለ.መ. (አሊፍ፡ላም፡ሚም) ፤ (1) ፡
2 ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ (ከአላህ ፡ ለመኾኑ) ፡ ጥርጥር ፡ የለበትም ፤ ለፈራህያን ፡ (2) መሪ ፡ ነው ።
3 ለነዚያ ፡ በሩቁ ፡ ነገር ፡ (3) የሚያምኑ ፡ ሶላትንም ፡ ደንቡን ፡ ጠብቀው ፡ የሚሰግዱ ፡ ከሰጠናቸውም ፡ ሲሳይ ፡ የሚቸሩ ፡ ለኾኑት ፤
4 ለነዚያም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ በተወረደው ፡ ና ፡ ከአንተ ፡ በፊትም ፡ በተወረደው ፡ የሚያምኑ ፡ በመጨረሻይቱም ፡ (ዓለም) ፡ እነርሱ ፡ የሚያረጋግጡ ፡ ለኾኑት ፡ (መሪ ፡ ነው) ።
5 እነዚያ ፡ ከጌታቸው ፡ በመመራት ፡

1 በዚህና ፡ በመሰሉ ፡ ትርጉም ፡ ብዙዎቹ ፡ ሊቃውንት ፡ ፍችውን ፡ ካላህ ፡ በስተቀር ፡ የሚያውቀው ፡ የለም ፡ ይላሉ ፤ እኔ ፡ አላህ ፡ ነኝ ፡ ዐውቃለሁ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የሚሉም ፡ አሉ ፤ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ነቢዩ ፡ ሙሐመድ ፡ ቁርአንን ፡ ሲያነቡ ፡ ዐረቦች ፡ እየተሰበሰቡ ፡ ድግምት ፡ ነው ፡ ይስባችኋል ፡ አታዳምጡት ፡ እያሉ ፡ ይሸሹ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ በነሱ ፡ ዘንድ ፡ ያልታወቀ ፡ አነጋገር ፡ ምህጻረ ፡ ቃላት ፡ አውርዶ ፡ ዝም ፡ ለማሰኘት ፡ ነው ፡ የሚሉም ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው

2 አላህን ፡ ለሚፈሩ ።

3 ከሕዋሳት ፡ በራቀው ፡ ነገር ።

ላይ ፡ ናቸው ፤ እነዚያም ፡ እነሱ ፡
ፍላጐታቸውን ፡ ያገኙ ፡ ናቸው ።
6 እነዚያ ፡ የካዱት ፡ (ሰዎች) ፡ ብታ
ስፈራራቸውም ፡ ባታስፈራራቸ
ውም ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ እኩል ፡
ነው ፤ አያምኑም ።
7 አላህ ፡ በልቦቻቸው ፡ ላይ ፡ በመ
ስሚያቸውም ፡ ላይ ፡ አትሞባቸ
ዋል ፤ በዓይኖቻቸውም ፡ ላይ ፡
መሸፈኛ ፡ አልለ፤ ለነሱም፡ ታላቅ፡
ቅጣት ፡ አላቸው ።
8 ከሰዎችም ፡ በአላህና ፡ በመጨረ
ሻው ፡ ቀን ፡ አምነናል ፡ የሚሉ ፡
አልሉ ፤ እነርሱም ፡ አማኞች ፡
አይደሉም ።
9 አላህንና ፡ እነዚያን ፡ ያመኑትን ፡
(ሰዎች) ፡ ያታልላሉ ፤ የማያውቁ ፡
ሲኾኑ ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ እንጅ ፡
ሌላን ፡ አያታልሉም ።
10 በልቦቻቸው ፡ ውስጥ ፡ (የንፍ
ቅና) ፡ በሺታ ፡ አለባቸው ፤ አላ
ህም ፡ በሺታን ፡ ጨመረባቸው ፤
ለነርሱም ፡ ይዋሹ ፡ በነበሩት ፡
ምክንያት ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡
አላቸው ።
11 ለነርሱም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አታ
በላሹ ፡ በተባሉ ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡
አሳማሪዎች ፡ ብቻ ፡ ነን ፡ ይላሉ ።
12 ንቁ ፡ እነሱ ፡ አጥፊዎቹ ፡ እነ
ሱው ፡ ናቸው ፤ ግን ፡ አያውቁም ።
13 ለነሱም ፡ ሰዎቹ ፡ እንዳመኑ ፡
እመኑ ፡ በተባሉ ፡ ጊዜ ፡ ቂሎቹ ፡
እንዳመኑ ፡ እናምናለን ? ይላሉ ፤
አዋጅ ፡ ንቁ ፡ እነርሱ ፡ ቂሎቹ ፡
እነርሱው ፡ ናቸው ፤ ግን ፡ አያ
ውቁም ።
14 እነዚያንም ፡ ያመኑትን ፡ በተገ
ናኙ ፡ ጊዜ ፡ አምነናል ፡ ይላሉ ፤
ወደ ፡ ሰይጣኖቻቸውም ፡ ባገለሉ ፡
ጊዜ ፡ እኛ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ነን ፤
እኛ ፡ (በነሱ) ፡ ተሳላቂዎች ፡
ብቻ ፡ ነን ፡ ይላሉ ።
15 አላህ ፡ በነሱ ፡ ይሳለቅባቸዋል ፤
(1) በጥመታቸውም፡ ውስጥ፡ የሚ
ዋልሉ ፡ ሲኾኑ ፡ ያዘገያቸዋል ።
16 እነዚህ ፡ እነዚያ ፡ ስሕተትን ፡ በቅ
ንነት ፡ የገዙ ፡ ናቸው ፤ ንግዳቸ
ውም ፡ አላተረፈችም ፤ ቀጥተኞ
ችም ፡ አልኾኑም ።
17 (በንፍቅና) ፡ ምሳሌያቸው ፡ እን
ደዚያ ፡ እሳትን ፡ እንዳነደደ ፡
ሰው ፡ በዙሪያው ፡ ያለውን ፡
ሁሉ ፡ ባበራች ፡ ጊዜም ፡ አላህ ፡
ብርሃናቸውን ፡ እንደወሰደባቸው ፡
በጨለማዎችም ፡ ውስጥ ፡ የማ
ያዩ ፡ ኾነው ፡ እንደተዋቸው ፡
(ሰዎች) ፡ ብጤ ፡ ነው ።
18 (እነሱ) ፡ ደንቆሮዎች ፡ ዲዳዎች ፡
ዕውሮች ፡ ናቸው ፤ ስለዚህ ፡
እነርሱ ፡ አይመለሱም ።
19 ወይም ፡ (ምሳሌያቸው) ፡ ከሰ
ማይ ፡ እንደ ፡ ወረደ ፡ ዝናም ፡
(ባለቤቶች) ፡ ነው ፤ በርሱ ፡ (በደ
መናው) ፡ ውስጥ ፡ ጨለማዎች ፡
ነጐድጓድም ፡ ብልጭታም ፡ ያሉ
በት ፡ ሲኾን ፡ ከመብረቆቹ ፡ ሞ
ትን ፡ ለመፍራት ፡ ጣቶቻቸውን ፡
በጆሮቻቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደሚያ
ደርጉ ፡ ብጤ ፡ ነው ፤ አላህም ፡
ከሓዲዎችን ፡ ከባቢ ፡ ነው ።
20 ብልጭታው ፡ ዓይኖቻቸውን ፡
ሊነጥቅ ፡ ይቀርባል ፤ ለነርሱ ፡
ባበራላቸው ፡ ቍጥር ፡ በርሱ ፡
ውስጥ ፡ ይኼዳሉ ፤ በነሱም ፡ ላይ፡
ባጨለመ ፡ ጊዜ ፡ ይቆማሉ ፤ አላ
ህም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ መስሚያቸው
ንና ፡ ማያዎቻቸውን ፡ በወሰደ ፡

1 በመሳለቃቸው ፡ ይቀጣቸዋል ።

ነበር ፤ አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ቻይ ፡ ነውና ።
21 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! የፈጠራ
ችሁን ፡ እነዚያንም ፡ ከናንተ ፡
በፊት ፡ የነበሩትን ፡ (የፈጠረ
ውን) ፡ ጌታችሁን ፡ ተገዙ ፤ (ቅጣ
ትን) ፡ ልትጠነቀቁ ፡ ይከጀላልና ።
22 (እርሱ) ፡ ያ ፡ ለናንተ ፡ ምድርን ፡
ምንጣፍ ፡ ሰማይንም ፡ ጣራ ፡
ያደረገ ፡ ነው ፤ ከሰማይም ፡ (ከደ
መና) ፡ ውሃን ፡ ያወረደ ፡ በርሱም፡
ከፍሬዎች ፡ ለናንተ ፡ሲሳይን ፡
ያወጣ ፡ ነው ፤ እናንተም ፡ (ፈጣሪ
ነቱን) ፡ የምታውቁ ፡ ስትኾኑ ፡
ለአላህ ፡ ባላንጣዎችን ፡ አታድ
ርጉ ።
23 በባሪያችንም ፡ ላይ ፡ ካወረድነው ፡
በመጠራጠር ፡ ውስጥ ፡ ብትኾኑ ፡
ከብጤው ፡ አንዲትን ፡ ምዕራፍ ፡
አምጡ ፤ ውነተኞችም ፡ እንደኾ
ናችሁ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ መስካሪ
ዎቻችሁን ፡ ጥሩ ።
(ይህንን) ፡ ባትሠሩ ፡ ፈጽሞም ፡
አትሠሩትምና ፡ ያችን ፡ መቀጣጠ
ያዋ ፡ ሰዎችና ፡ ደንጊያዎች ፡ የኾ
ኑችውን ፡ እሳት ፡ ተጠበቁ ፤ ለከ
ሓዲዎች ፡ ተደግሳለች ።
25 እነዚያን ፡ ያመኑትንና ፡ መልካም
ችንም ፡ የሠሩትን ፡ ለነርሱ ፡ ከ
ሥሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱባ
ቸው ፡ ገነቶች ፡ ያሏቸው ፡ መኾ
ኑን ፡ አብስራቸው ፤ ከርሷ ፡ ከፍሬ
(ዓይነቶች) ፡ ሲሳይን ፡ በተመገቡ ፡
ቍጥር ፡ (ፍሬዎችዋ ፡ ስለሚመ
ሳሰሉ) ፡ ይህ ፡ ያ ፡ ከአሁን ፡ በፊት
የተመገብነው ፡ ነው ፡ ይላሉ ፤
እርሱንም ፡ ተመሣሳይ ፡ ኾኖ ፡
ተሰጡት ፤ ለነሱም ፡ በውስጧ ፡
ንጹሕ ፡ የተደረጉ ፡ ሚስቶች ፡
አሏቸው ፤ እነሱም ፡ በውስጧ ፡
ዘውታሪዎች ፡ ናቸው ።
26 አላህ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ትን
ኝንም ፡ ኾነ ፡ (1) ከበላይዋ ፡ የኾ
ነንም ፡ ምሳሌ ፡ ለማድረግ ፡ አያ
ፍርም ፤ እነዚያ ፡ ያመኑትማ ፤
እርሱ ፡ (ምሳሌው) ፡ ከጌታቸው ፡
(የተገኘ) ፡ እውነት ፡ መኾኑን ፡
ያውቃሉ ፤ እነዚያም ፡ የካዱትማ ፡
አላህ ፡ በዚህ ፡ ምንን ፡ ምሳሌ ፡
ሻ ፡ ይላሉ ፤ በርሱ ፡ (በምሳሌው) ፡
ብዙዎችን ፡ ያሳስታል ፤ በርሱም ፡
ብዙዎችን ፡ ያቀናል ፤ በርሱም ፡
አመጠኞችን ፡ እንጅ ፡ ሌላን ፡
አያሳስትም ።
27 እነዚያ ፡ የአላህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
ከአጠበቀባቸው ፡ በኋላ ፡ የሚያፈ
ርሱ ፡ እንዲቀጠልም ፡ በርሱ ፡
ያዘዘውን ፡ ነገር ፡ የሚቆርጡ ፡
በምድርም ፡ ላይ ፡ የሚያበላሹ ፡
እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ ከሳሪዎቹ ፡
ናቸው ።
28 ሙታን ፡ የነበራችሁ ፡ ስትኾኑ ፡
ሕያው ፡ ያደረጋችሁ ፡ ከዚያም ፡
የሚገድላችሁ ፡ ከዚያም ፡ ሕያው ፡
የሚያደርጋችሁ ፡ ሲኾን ፡ ከዚ
ያም ፡ ወደርሱ ፡ የምትመለሱ ፡
ስትኾኑ ፡ በአላህ ፡ እንዴት ፡ ትክ
ዳላችሁ !
29 እርሱ ፡ ያ ፡ በምድር ፡ ያለውን ፡
ሁሉ ፡ ለናንተ ፡ የፈጠረ ፡ ነው ፤
ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አሰበ ፤
ሰባት ፡ ሰማያትም ፡ አደረጋቸው ፤
እርሱም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።
30 (ሙሐመድ ፡ ሆይ) ፡ ጌታህ ፡ ለመ
ላእክት ፡— እኔ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ምትክን ፡ አድራጊ ፡ ነኝ ፤ ባለ ፡

1 በትንሽነት ፡ ወይም ፡ በትልቅነት ።

ጊዜ ፡ (የኾነውን ፡ አስታውስ ፤
እነርሱም) ፡ እኛ ፡ ከማመስገን ፡
ጋር ፡ የምናጠራህ ፡ ላንተም ፡
የምንቀድስ ፡ ስንኾን ፡ በርሷ ፡
ውስጥ ፡ የሚያጠፋንና ፡ ደሞች
ንም ፡ የሚያፈስን ፡ ታደርጋለ
ህን ? አሉ ፤ (አላህ) ፡ እኔ ፡ የማታ
ውቁትን ፡ ነገር ፡ ዐውቃለሁ ፡
አላቸው ።
31 አደምንም ፡ ስሞችን ፡ ሁሏንም ፡
አስተማረው ፤ ከዚያም ፡ በመላ
እክት ፡ ላይ ፡ (ተጠሪዎቹን) ፡ አቀ
ረባቸው ፤ እውነተኞችም ፡ እንደ
ኾናችሁ ፡ የነዚህን ፡ (ተጠሪዎች)፡
ስሞች ፡ ንገሩኝ፥ አላቸው ።
32 ጥራት ፡ ይገባህ ፤ ከአስተማርከን ፡
ነገር ፡ በስተቀር ፡ ለኛ ፡ ዕውቀት ፡
የለንም ፤ አንተ ፡ ዐዋቂው ፡ ጥበበ
ኛው ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህና ፡
(አሉ) ።
33 ፡—አደም ፡ ሆይ ፡ ስሞቻቸውን ፡
ንገራቸው ፡ አለው ፤ ስሞቻቸውን፡
በነገራቸውም ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ የሰማ
ያትንና ፡ የምድርን ፡ ሩቅ ፡ ምስ
ጢር ፡ ዐውቃለሁ ፤ የምትገልጹ
ትንና ፡ ያንንም ፡ ትደብቁት ፡ የነ
በራችሁትን ፡ ዐውቃለሁ ፡ አላል
ኋችሁምን ? አላቸው ።
34 ለመላእክትም ፡ ለአደም ፡ ስገዱ ፡
ባልን ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፤
ሁሉም ፡ ወዲያውኑ ፡ ሰገዱ ፤
ኢብሊስ ፡ (ዲያብሎስ) ፡ ብቻ ፡
ሲቀር ፡ እምቢ ፡ አለ ፤ ኮራም ፡
ከከሓዲዎቹም ፡ ኾነ ።
35 አደም ፡ ሆይ ! አንተ ፡ ከነሚስ
ትህ ፡ በገነት ፡ ተቀመጥ ፤ ከር
ሷም ፡ በፈለጋችሁት ፡ ስፍራ ፡
በሰፊው ፡ ተመገቡ ፤ ግን ፡ ይህ
ችን ፡ ዛፍ ፡ አትቅረቡ ፤ ከበደለ
ኞች ፡ ትኾናላችሁና ፡ አልንም ።
36 ከርሷም ፡ ሰይጣን ፡ አንዳለጣቸው፤
በውስጡም ፡ ከነበሩበት ፡ (ድሎ
ት) ፡ አወጣቸው ፤ ከፊላችሁም ፡
ለከፊሉ ፡ ጠላት ፡ ሲኾን ፡ ውረ
ዱ ፤ ለናንተም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
እስከ ፡ ጊዜ ፡ (ሞታችሁ) ፡ ድረስ ፡
መርጊያና ፡ መጣቀሚያ ፡ አላ
ችሁ ፡ አልናቸው ።
37 አደምም ፡ ከጌታው ፡ ቃላትን ፡
ተቀበለ ፤ በርሱ ፡ ላይም ፡ (ጌታው፡
ጸጸትን ፡ በመቀበል) ፡ ተመለሰ
ለት ፤ እነሆ ፡ እርሱ ፡ ጸጸትን ፡
ተቀባይ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።
38 ሁላችሁም ፡ ኾናችሁ ፡ ከርሷ ፡
ውረዱ ፤ ከኔም ፡ የኾነ ፡ መምሪያ ፡
ቢመጣላችሁ ፡ ወዲያውኑ ፡ መም
ሪያዬን ፡ የተከተለ ፡ ሰው ፡ በነሱ ፡
ላይ ፡ ፍርሃት ፡ የለባቸውም ፤ እነ
ሱም ፡ አያዝኑም ፡ አልናቸው ።
39 እነዚያም ፡ (በመልክተኞቻችን) ፡
የካዱ ፡ በአንቀጾቻችንም ፡ ያስተ
ባበሉ ፡ እነዚያ ፡ የእሳት ፡ ጓዶች ፡
ናቸው ፤ እነርሱ ፡ በውስጧ ፡ ዘው
ታሪዎች ፡ ናቸው ።
40 የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ !
ያችን ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ የለገስኳ
ትን ፡ ጸጋዬን ፡ አስታውሱ ፤
በቃል ፡ ኪዳኔም ፡ ሙሉ ፤ በቃል ፡
ኪዳናችሁ ፡ እሞላለሁና ፤ እኔ
ንም ፡ ብቻ ፡ ፍሩ ።
41 ከናንተ ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ (መጽ
ሐፍ) ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ኾኖ ፡ ባወ
ረድኩትም ፡ (ቁርአን) ፡ እመኑ ፤
በርሱም ፡ የመጀመሪያ ፡ ከሓዲ ፡
አትኹኑ ፤ በአንቀጾቼም ፡ ጥቂ
ትን ፡ ዋጋ ፡ አትለውጡ ፤ እኔንም ፡
ብቻ ፡ ተጠንቀቁ ።



42 እውነቱንም ፡ በውሸት ፡ አትቀላ
ቅሉ ፤ እናንተም ፡ የምታውቁ ፡
ስትኾኑ ፡ እውነትን ፡ አትደብቁ ።
43 ሶላትንም ፡ ደንቡን ፡ ጠብቃችሁ ፡
ስገዱ ፤ ዘካንም ፡ (ግዴታ ፡ ምጽ
ዋትን) ፡ ስጡ ፤ (ለጌታችሁ) ፡ ከአ
ጐንባሾች ፡ ጋርም ፡ አጐንብሱ ።
44 እናንተ ፡ መጽሐፉን ፡ የምታነቡ ፡
ኾናችሁ ፡ ሰዎችን ፡ በበጐ ፡ ሥራ፡
ታዛላችሁን ? ነፍሶቻችሁንም ፡
ትረሳላችሁን ? (የሥራችሁን ፡
መጥፎነት) ፡ አታውቁምን ?
45 በመታገሥና ፡ በሶላትም ፡ ተረዱ ፤
እርሷም ፡ (ሶላት) ፡ በፈሪዎች ፡
ላይ ፡ እንጅ ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡
በእርግጥ ፡ ከባድ ፡ ናት ።
46 እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ ጌታቸውን ፡
የሚገናኙ ፡ እነሱም ፡ ወደርሱ ፡
ተመላሾች ፡ መኾናቸውን ፡ የሚ
ያረጋግጡ ፡ በኾኑት ፡ (ላይ ፡
እንጅ ፡ ከባድ ፡ ናት) ።
47 የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ !
ያችን ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ የለገስኳ
ትን ፡ ጸጋየንና ፡ እኔም ፡ በዓለ
ማት ፡ ላይ ፡ ያበለጥኳችሁ ፡ (1)
መኾኔን ፡ አስታውሱ ።
48 (ማንኛዋ) ፡ ነፍስም ፡ ከ(ሌላዋ) ፡
ነፍስ ፡ ምንንም ፡ የማትመነዳበ
ትን ፡ ከርሷም ፡ ምልጃን ፡ የማይ
ቀበሉባትን ፡ ከርሷም ፡ ቤዛ ፡ የማ
ይያዝባትን ፡ እነርሱም ፡ የማይረ
ዱበትን ፡ ቀን ፡ ተጠንቀቁ ።
49 ከፈርዖን ፡ ቤተሰቦች ፡ (ከጐሶ
ቹና ፡ ከወታደሮቹ) ፡ ብርቱን ፡
ቅጣት ፡ የሚያቀምሱዋችሁ ፡
ወንዶች ፡ ልጆቻችሁን ፡ የሚያ
ርዱ ፡ ሴቶቻችሁንም ፡ የሚተው ፡
ሲኾኑ ፡ ባዳንናችሁ ፡ ጊዜ ፡ (የኾነ
ውን ፡ አስታውሱ) ፤ በዚሃችሁም ፡
ከጌታችሁ ፡ ታላቅ ፡ ፈተና ፡ አለ
በት ።
50 በናንተም ፡ ምክንያት ፡ ባሕሩን ፡
በከፈልን ፡ ጊዜ ፡ (አስታውሱ) ፤
ወዲያውም ፡ አዳንናችሁ ፤ የፈር
ዖንንም ፡ ቤተሰቦች ፡ እናንተ ፡
የምትመለከቱ ፡ ኾናችሁ ፡ አሰ
ጠምናቸው ።
51 ሙሳንም ፡ አርባን ፡ ሌሊት ፡ በቀ
ጠርነው ፡ ጊዜ ፡ (የኾነውን ፡ አስ
ታውሱ) ፤ ከዚያም ፡ ከርሱ ፡
(መኼድ) ፡ በኋላ ፡ እላንተ ፡ በዳ
ዮች ፡ ስትኾኑ ፡ ወይፈንን ፡ (አም
ላክ ፡ አድርጋችሁ) ፡ ያዛችሁ ።
52 ከዚያም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እናንተ ፡
ታመሰግኑ ፡ ዘንድ ፡ ከናንተ ፡
ምሕረት ፡ አደረግን ።
53 ሙሳንም ፡ መጽሐፍንና ፡ (እውነ
ትና ፡ ውሸትን) ፡ መለያንም ፡
ትምመሩ፡ ዘንድ፡ በሰጠነው፡ ጊዜ፡
(አስታውሱ) ።
54 ሙሳም ፡ ለሕዝቦቹ ፡— ሕዝቦቼ ፡
ሆይ ! እናንተ ፡ ወይፈንን ፡ (አም
ላክ ፡ አድርጋችሁ) ፡ በመያዛችሁ ፡
ነፍሶቻችሁን ፡ በደላችሁ ፤ ወደ ፡
ፈጣሪያችሁም ፡ ተመለሱ ፤ ነፍሶ
ቻችሁንም ፡ ግደሉ ፤ (1) ይሃችሁ ፡
በፈጣሪያችሁ ፡ ዘንድ ፡ ለናንተ ፡
በላጭ ፡ ነው ፤ ባለ ፡ ጊዜ ፡ (አስታ
ውስ) ፤ በናንተም ፡ ላይ ፡ ጸጸትን ፡
በመቀበል ፡ ተመለሰላችሁ ፤ እነሆ
እርሱ ፡ ጸጸትን ፡ ተቀባይ ፡ አዛኝ ፡
ነውና ።
55 ሙሳ ፡ ሆይ ! አላህን ፡ በግልጽ ፡
እስከምናይ ፡ ድረስ ፡ ላንተ ፡ በፍ

1 አባቶቻችሁን ፡ በጊዜያቸው ፡ ከነበሩት ፡ ዓለማት ፡ ያበለጥኳቸው ።

1 ንጹሃችሁ ፡ አጥፊውን ፡ ይግደል ።

ጹም ፡ አናምንልህም ፡ ባላችሁም፡
ጊዜ ፡ (አስታውሱ) ፤ እናንተም ፡
እየተመለከታችሁ ፡ መብረቅ ፡
ያዘቻችሁ ፤ (1)
56 ከዚያም ፡ ታመሰግኑ ፡ ዘንድ ፡
ከሞታችሁ ፡ በኋላ ፡ አስነሳናችሁ።
57 በናንተም ፡ ላይ ፡ ደመናን ፡ አጠ
ለልን ፤ በናንተም ፡ ላይ ፡ (እንደ ፡
ነጭ፡ ማር፡ ያለ)፡ መንናን፡ እና፡ ድር
ጭትን ፡ አወረድን ፤ ከሰጠናች
ሁም ፡ ጣፋጮች ፡ ብሉ ፡ (አልን) ፤
አልበደሉንምም ፡ ግን ፡ ነፍሶቻ
ቸውን ፡ ይበድሉ ፡ ነበር ።
58 ይህችንም ፡ ከተማ ፡ ግቡ ፤ ከር
ሷም ፡ በሻችሁት ፡ ስፍራ ፡ ሰፊን ፡
(ምግብ) ፡ ተመገቡ ፤ በሩንም ፡
ያጐነበሳችሁ ፡ ኾናችሁ ፡ ግቡ ፤
(ጥያቄያችን ፡ የኃጢአታችን)፡
መርገፍ ፡ ነው ፡ በሉም ፤ ኃጢአ
ቶቻችሁን ፡ ለናንተ ፡ እንምራ
ለንና ፤ በጐ ፡ ሠሪዎችንም ፡ (ምን
ዳን) ፡ እንጨምርላቸዋለን ፡ ባልን
ጊዜ ፡ (አስታውሱ) ።
59 እነዚያም ፡ የበደሉት ፡ ሰዎች ፡
ከዚያ ፡ ለነሱ ፡ ከተባሉት ፡ ሌላ ፡
ቃልን ፡ ለወጡ ፤ በነዚያም ፡ በበ
ደሉት ፡ ላይ ፡ ያምመጡ ፡ በመኾ
ናቸው ፡ ምክንያት ፡ መቅሠፍ
ትን ፡ አወረድንባቸው ።
60 ሙሳም ፡ ለሕዝቦቹ ፡ መጠጥን ፡
በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ (የኾነውን ፡ አስ
ታውሱ) ፤ ደንጊያውንም ፡ በበ
ትርህ ፡ ምታ ፡ አልነው ፤ (መታ
ውም) ፡ ከርሱም ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት፡
ምንጮች ፡ ፈለቁ ፤ ሰዎቹ ፡ ሁሉ ፡
መጠጫቸውን ፡ በእርግጥ ፡ ዐወቁ፤
ከአላህ ፡ ሲሳይ ፡ ብሉ ፤ ጠጡም ፤
አመጠኞችም ፡ ኾናችሁ ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ አታበላሹ ፡ (አል
ናቸው) ።
61 ሙሳ ፡ ሆይ ፡— በአንድ ፡ (ዓይ
ነት) ፡ ምግብ ፡ ላይ ፡ በፍጹም ፡
አንታገሥም ፤ ስለዚህ ፡ ጌታህን ፡
ከዚያ ፡ ምድር ፡ ከምታበቅለው ፡
ሁሉ ፡ ከቅጠላቅጠልዋ ፡ ከዱባ
ዋም ፡ ከስንዴዋም ፡ ከምሥር
ዋም ፡ ከሽንኩርቷም ፡ ለኛ ፡
ያወጣ ፡ ዘንድ ፡ ለኛ ፡ ለምንልን ፡
ባላችሁም ፡ ጊዜ ፡ (የኾነውን ፡
አስታውሱ ፤ ሙሳም) ፡— ያንን ፡
እርሱ ፡ ዝቅተኛ ፡ የኾነውን ፡
በዚያ ፡ እርሱ ፡ በላጭ ፡ በኾነው ፡
ነገር ፡ ለውጥን ፡ ትፈልጋላችሁን?
ወደ ፡ ከተማ ፡ ውረዱ ፤ ለናንተም፡
የጠየቃችሁት ፡ ነገር ፡ አላችሁ ፡
አላቸው ፤ በነርሱም ፡ ላይ ፡ ውር
ደትና ፡ ድኽነት ፡ ተመታባቸው ፤
ከአላህም ፡ በኾነ ፡ ቁጣ ፡ ተመ
ለሱ ፤ ይህ ፡ (1) እነርሱ ፡ በአላህ ፡
ታምራቶች ፡ ይክዱና ፡ ነቢያት
ንም ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ ይገድሉ ፡ ስለ ፡
ነበሩ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ (2) በማመጣ
ቸውና ፡ ወሰን ፡ የሚያልፉ ፡ በመ
ኾናቸው ፡ ነው ።
62 እነዚያ ፡ ያመኑ ፡ እነዚያም ፡ ይሁ
ዳውያን ፡ የኾኑ ፡ ክርስቲያኖችም፡
ሳቢያኖችም ፡ (ከነርሱ) ፡ በአላ
ህና ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ያመነ፡
መልካምንም ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡
ለነርሱ ፡ በጌታቸው ፡ ዘንድ ፡ ምን
ዳቸው ፡ አላቸው ፤ በነርሱም ፡
ላይ ፡ ፍርሃት ፡ የለባቸውም ፤ እነ
ሱም ፡ አያዝኑም ።
63 ከበላያችሁም ፡ የጡርን ፡ ተራራ ፡
ያነሳን ፡ ኾነን ፡ የጠበቀ ፡ ቃል ፡

1 ሰባዎቹ ፡ ምርጦቻችሁ ፡ ሞቱ ።

1 ውርደትና ፡ ቁጣ ።
2 ክሕደትና ፡ መግደል ።



ኪዳናችሁን ፡ በያዝን ፡ ጊዜ ፡ (የኾ
ነውን ፡ አስታውሱ) ፤ ያንን ፡ የሰ
ጠናችሁን ፡ በኀይል ፡ ያዙ ፤ በው
ስጡ ፡ ያለውንም ፡ ነገር ፡ (ከእ
ሳት) ፡ ትጠበቁ ፡ ዘንድ ፡ አስታ
ውሱ ፡ (አልን) ።
64 ከዚያም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ (ኪዳ
ኑን) ፡ ተዋችሁ ፤ በናንተም ፡ ላይ ፡
የአላህ ፡ ችሮታና ፡ እዝነቱ ፡ ባል
ነበረ ፡ ኖሮ ፡ በእርግጥ ፡ ከጠፊ
ዎቹ ፡ በኾናችሁ ፡ ነበር ።
65 እነዚያንም ፡ ከናንተ ፡ ውስጥ ፡
በቅዳሜ ፡ (ቀን ፡ ዐሣን ፡ በማ
ደን) ፡ ወሰን ፡ ያለፉትንና ፡ ለነሱ ፡
ወራዳዎች ፡ ስትኾኑ ፡ ዝንጀሮ
ዎች ፡ ኹኑ፡ ያልናቸውን ፡ በእር
ግጥ ፡ ዐወቃችሁ ።
66 (ቅጣቲቱንም) ፡ ለነዚያ፡ በስተ
ፊትዋ ፡ ለነበሩትና ፡ ለነዚያም ፡
ከበኋላዋ ፡ ላሉት ፡ (ሕዝቦች) ፡
መቀጣጫ ፡ ለፈራህያንም ፡ መገ
ሠጫ ፡ አደረግናት ።
67 ሙሳም ፡ ለሕዝቦቹ ፡— አላህ ፡
ላምን ፡ እንድታርዱ ፡ ያዛችኋል ፡
ባለ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውሱ) ፤ መሳለ
ቂያ ፡ አድርገህ ፡ ትይዘናለህን ?
አሉት ፤— ከተሳላቂዎች ፡ ከመ
ኾን ፡ በአላህ ፡ እጠበቃለሁ ፡
አላቸው ።
68 ለኛ ፡ ጌታህን ፡ ጠይቅልን ፤ እርሷ፡
ምን ፡ እንደኾነች ፡ (ዕድሜዋን) ፡
ያብራራልን ፡ አሉ ፤ እርሱ ፡ እርሷ ፡
ያላረጀች ፡ ጥጃም ፡ ያልኾነች ፡
በዚህ ፡ መካከል ፡ ልከኛ ፡ የኾ
ነች ፡ ጊደር ፡ ናት ፡ ይላችኋል ፤
የታዘዛችሁትንም ፡ ሥሩ ፡ አላ
ቸው ።
69 ለኛ ፡ ጌታህን ፡ ጠይቅልን ፤
መልኳ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡
ለኛ ፡ ይገለጽልን ፡ አሉ ፤ እርሱ ፡
እርሷ ፡ መልኳ ፡ ደማቅ ፡ ተመል
ካቾችን ፡ የምታስደስት ፡ ዳለቻ ፡
ላም ፡ ናት ፡ ይላችኋል ፡ አላቸው ።
70 ለኛ ፡ ጌታህን ፡ ጠይቅልን ፤ እርሷ ፡
ምን ፡ እንደኾነች ፡ ይግለጽልን ፤
ከብቶች ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ተመሳሰሉ
ብን ፤ እኛም ፡ አላህ ፡ የሻ ፡ እንደ ፡
ኾነ ፡ በእርግጥ ፡ ተመሪዎች ፡
ነን ፡ አሉ ።
71 እርሱ ፡ እርሷ ፡ ያልተገራች ፡ ምድ
ርን ፡ (በማረስ) ፡ የማታስነሳ ፡
እርሻንም ፡ የማታጠጣ ፡ (ከነ
ውር) ፡ የተጠበቀች ፡ ልዩ ፡ ምል
ክት ፡ የሌለባት ፡ ናት ፡ ይላች
ኋል ፡ አላቸው ፤ አሁን ፡ በትክ
ክል ፡ መጣህ ፡ አሉ ፤ ሊሠሩ ፡
ያልተቃረቡም ፡ ሲኾኑ ፡ አረ
ዱዋት (1) ።
72 ነፍስንም ፡ በገደላችሁና ፡ በር
ሷም ፡ (ገዳይ) ፡ በተከራከራችሁ ፡
ጊዜ ፡ (አስታውሱ) ፤ አላህም ፡
ትደብቁት ፡ የነበራችሁትን ፡
ሁሉ ፡ ገላጭ ፡ ነው ።
73 (በድኑን) ፡ በከፊሏም ፡ ምቱት ፡
አልን ፤ (2) እንደዚሁ ፡ አላህ ፡
ሙታንን ፡ ያስነሳል ፤ ታውቁም ፡
ዘንድ ፡ ታምራቶችን ፡ ያሳያች
ኋል ።
74 ከዚያም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልቦቻ
ችሁ ፡ ደረቁ ፤ እርሷም ፡ እንደ ፡
ደንጊያዎች ፡ ወይም ፡ በድርቅና ፡
ይበልጥ ፡ የበረታች ፡ ናት ፤ ከደን
ጊያዎችም ፡ ከርሱ ፡ ጂረቶች ፡
የሚፈሱለት ፡ አልለ ፤ ከነርሱም ፡
በእርግጥ ፡ የሚሰነጠቅና ፡ ከርሱ ፡

1 የጠናቸው ፡ ኾነው ፡ እየከበዳቸው ፡ አረ
ዷት ።
2 መቱትምና ፡ ተነሳ ፡ ገዳዩንም ፡ ተናገረና ፡
ሞተ ።

ውሃ ፡ (ምንጭ) ፡ የሚወጣው ፡
አልለ ፤ ከነርሱም ፡ አላህን ፡ ከመ
ፍራት ፡ የተነሳ ፡ ወደ ፡ ታች ፡
የሚወርድ ፡ አልለ ፤ አላህም ፡
ከምትሠሩት ፡ ነገር ፡ ዘንጊ ፡ አይ
ደለም ።

75 (ይሁዶች) ፡ ከነሱ ፡ የኾኑ ፡ ጭፍ
ሮች ፡ የአላህን ፡ ቃል ፡ የሚሰ
ሙና ፡ ከዚያም ፡ ከተረዱት ፡
በኋላ ፡ እነርሱ ፡ እያወቁ ፡ የሚለ
ውጡት ፡ ሲኾኑ ፡ ለናንተ ፡ ማመ
ናቸውን ፡ ትከጅላላችሁን ?

76 እነዚያንም ፡ ያመኑትን ፡ ባገኙ ፡
ጊዜ ፡ አምነናል ፡ ይላሉ ፤ ከፊላቸ
ውም ፡ ወደ ፡ ከፊሉ ፡ ባገለለ ፡
ጊዜ ፡ አላህ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ በገለ
ጻላችሁ ፡ ነገር ፡ እጌታችሁ ፡ ዘንድ
በርሱ ፡ እንዲከራከሩዋችሁ ፡ ትነ
ግሩዋቸዋላችሁን ? አታውቁምን?
ይላሉ ።

77 አላህ ፡ የሚደበቁትንና ፡ የሚገል
ጹትን ፡ የሚያውቅ ፡ መኾኑን ፡
አያውቁምን ?

78 ከነሱም ፡ መጽሐፉን ፡ የማያውቁ፡
መሃይምናን ፡ አልሉ ፤ ግን ፡ ከንቱ
ምኞቶችን ፡ (ይመኛሉ) ፤ እነር
ሱም ፡ የሚጠራጠሩ ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አይደሉም ።

79 ለነዚያም ፡ መጽሐፉን ፡ በእጆቻ
ቸው ፡ ለሚጽፉና ፡ ከዚያም ፡
በርሱ ፡ ጥቂትን ፡ ዋጋ ፡ ሊገዙ
በት ፡ ይህ ፡ ከአላህ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡
ለሚሉ ፡ ወዮላቸው ፤ ለነርሱም ፡
ከዚያ ፡ እጆቻቸው ፡ ከጻፉት ፡
ወዮላቸው ፤ ለነሱም ፡ ከዚያ ፡
ከሚያፈሩት ፡ (ኃጢአት) ፡ ወዮ
ላቸው ።

80 እሳትም ፡ የተቆጠሩን ፡ ቀኖች ፡
እንጂ ፡ አትነካንም ፡ አሉ ፤ አላህ ፡
ዘንድ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይዛችኋ
ልን ? (ይህ ፡ ከኾነ) ፡ አላህም ፡
ኪዳኑን ፡ አያፈርስም ፤ በውነቱ ፡
በአላህ ፡ ላይ ፡ የማታውቁትን ፡
ትናገራላችሁ ፡ በላቸው ።

81 አይደለም ፡ (ትነካችኋለች) ፤ መጥ
ፎን ፡ (ክሕደትን) ፡ የሠራ ፡ በር
ሱም ፡ ኃጢአቱ ፡ የከበበችው ፡
ሰው ፡ እነዚያ ፡ የእሳት ፡ ጓዶች ፡
ናቸው ፤ እነርሱ ፡ በውስጧ ፡ ዘው
ታሪዎች ፡ ናቸው ።

82 እነዚያም ፡ ያመኑት ፡ በጐ ፡ ሥራ
ዎችንም ፡ የሠሩት ፡ እነዚያ ፡ የገ
ነት ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ፤ እነርሱ ፡
በውስጧ ፡ ዘላለም ፡ ዘውታሪዎች ፡
ናቸው ።

83 የእስራኤል ፡ ልጆችንም ፡ ጥብቅ ፡
ኪዳን ፡— አላህን ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡
አታምልኩ ፤ በወላጆችም ፡ በግ
ጐን ፡ ሥራ ፡ (አድርጉ) ፤ በዝም
ድና ፡ ባለ ፡ ቤቶችም ፡ በየቲሞ
ችም ፡ (አባት ፡ በሌላቸው ፡ ልጆ
ች) ፡ በምስኪኖችም ፡ (በጐ ፡
ዋሉ) ፤ ለሰዎችም ፡ መልካምን ፡
ተናገሩ ፤ ሶላትንም ፡ ደንቡን ፡
ጠብቃችሁ ፡ ስገዱ ፡ በማለት ፡
በያዝንባቸው ፡ ጊዜ ፡ (አስታ
ውሱ) ፤ ከዚያም ፡ ከናንተ ፡ ጥቂ
ቶች ፡ ሲቀሩ ፡ ሸሻችሁ ፤ እናን
ተም ፡ (ኪዳንን) ፡ የምትተው ፡
ናችሁ ።

84 ደሞቻችሁን ፡ አታፍስሱ ፡ ነፍሶ
ቻችሁንም ፡ (ከፊላችሁን) ፡ ከአገ
ሮቻችሁ ፡ አታውጡ ፡ የምንል ፡
ስንኾን ፡ የጠበቀ ፡ ቃል ፡ ኪዳና
ችሁን ፡ በያዝንባችሁ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውሱ) ፤ ከዚያም ፡ (በኪ
ዳኑ) ፡ አረጋገጣችሁ ፤ እናንተም ፡
ትመሰክራላችሁ ።



85 ከዚያም ፡ እናንተ ፡ እነዚያ ፡ ነፍ
ሶቻችሁን ፡ የምትገድሉ ፡ ከናን
ተም ፡ የኾኑ ፡ ጭፍሮችን ፡ በኃጢ
አትና ፡ በመበደል ፡ በነርሱ ፡
ላይ ፡ የምትረዳዱ ፡ ስትኾኑ ፡ ከአ
ገሮቻቸው ፡ የምታወጡ ፡ ምርኮ
ኞችም፡ ኾነው፡ ቢመጡዋችሁ፡
የምትበዠ ፡ ናችሁ ፡ እርሱ ፡
(ነገሩ) ፡ እነርሱን ፡ ማውጣት ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ የተከለከለ ፡ ነው ፤
በመጽሐፉ ፡ ከፊል ፡ ታምናላች
ሁን ? በከፊሉም ፡ ትክዳላችሁን ?
ከናንተም ፡ ይህንን ፡ የሚሠራ ፡
ሰው ፡ ቅጣት ፡ በቅርቢቱ ፡ ሕይ
ወት ፡ ውርደት ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡
አይደለም ፡ በትንሣኤ ፡ ቀንም ፡
ወደ ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ ይመለ
ሳሉ ፡ አላህም ፡ ከምትሠሩት ፡
ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ዘንጊ ፡ አይደለም ።

86 እነዚህ ፡ እነዚያ ፡ ቅርቢቱን ፡
ሕይወት ፡ በመጨረሻይቱ ፡ አገር፡
የገዙ ፡ ናቸው ፤ ከነሱም ፡ ቅጣቱ ፡
አይቀለልላቸውም ፤ እነሱም ፡ አ
ይርረዱም ።

87 ሙሳንም ፡ መጽሐፍን ፡ በእርግጥ፡
ሰጠነው ፤ ከበኋላውም ፡ መልክ
ተኞችን ፡ አስከታተልን ፤ የመር
የምን ፡ ልጅ ፡ ዒሳንም ፡ ግልጽ ፡
ታምራቶችን ፡ ሰጠነው ፤ በቅ
ዱሱ ፡ መንፈስም ፡ አበረታነው ፤
ነፍሶቻችሁ ፡ በማትወደው ፡ ነገር፡
መልክተኛ ፡ በመጣላችሁ ፡ ቍ
ጥር ፡ (ከመከተል) ፡ትኮራላች
ሁን ? ከፊሉን ፡ አስተባበላችሁ ፤
ከፊሉንም ፡ ትገድላላችሁ ።

88 ልቦቻችንም ፡ ሽፍኖች ፡ ናቸው ፡
አሉ ፤ አይደለም ፡ አላህ ፡ በክሕ
ደታቸው ፡ ምክንያት ፡ ረገማቸው፡
ጥቂትንም ፡ ብቻ ፡ ያምናሉ ።

89 ከነሱም ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ (መጽ
ሐፍ) ፡ አረጋጋጭ ፡ የኾነ ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ከአላህ ፡ ዘንድ ፡ በመጣላ
ቸው ፡ ጊዜ ፡ (ከመምጣቱ) ፡
በፊት ፡ በነዚያ ፡ በካዱት ፡ ላይ ፡
ይረዱበት ፡ የነበሩ ፡ ሲኾኑ ፡ (1)
ያወቁት ፡ ነገር ፡ በመጣላቸው ፡
ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ካዱ ፤ የአላህም ፡
ርግማን ፡ በከሓዲዎች ፡ ላይ ፡
ይኹን ።

90 ነፍሶቻቸውን ፡ በርሱ ፡ የሸጡ
በት ፡ ነገር ፡ ከፋ ! (እርሱም) ፡
አላህ ፡ ከባሮቹ ፡ በሚሻው ፡ ሰው ፡
ላይ ፡ ከችሮታው ፡ (ራእይን) ፡
ማውረዱን ፡ በመመቅኘት ፡ አላህ፡
ባወረደው ፡ ነገር ፡ መካዳቸው ፡
ነው ፤ በቁጣ ፡ ላይም ፡ ቁጣ ፡ (የተ
ረጋገጠባቸው ፡ ሲኾኑ) ፡ ተመ
ለሱ ፤ ለከሓዲዎችም ፡ አዋራጅ ፡
ቅጣት ፡ አላቸው ።

91 አላህም ፡ ባወረደው ፡ (ሁሉ) ፡ ለነ
ርሱ ፡ እመኑ ፡ በተባሉ ፡ ጊዜ ፡
በኛ ፡ ላይ ፡ በተወረደው ፡ (መጽ
ሐፍ ፡ ብቻ) ፡ እናምናለን፡ ይላሉ ፤
ከርሱ ፡ ኋላ ፡ ባለው ፡ (ቁርአን) ፡
እርሱ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ላለው ፡
(መጽሐፍ) ፡ አረጋጋጭ ፡ እውነ
ተኛ ፡ ሲኾን ፡ ይክዳሉ ፤ አማኞች፡
ከኾናችሁ ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡ የአ
ላህን ፡ ነቢያት ፡ ለምን ፡ ገደላ
ችሁ ፡ በላቸው ።

92 ሙሳም ፡ በታምራቶች ፡ በእር
ግጥ ፡ መጣላችሁ ፡ ከዚያም ፡ ከበ
ኋላው ፡ እላንተ ፡ በዳዮች ፡ ስት
ኾኑ ፡ ወይፈንን ፡ (አምላክ ፡ አድ
ርጋችሁ) ፡ ያዛችሁ ።

---

1 አላህ ፡ በመጨረሻ ፡ በሚመጣው ፡ ነቢይ ፡
ተማጥንንሃል ፡ በጠላቶቻችን ፡ ላይ ፡ እር
ዳን ፡ እያሉ ፡ ይረዱበት ፡ የነበሩ ፡ ሲኾኑ ፡

93 የጡርንም ፡ ጋራ ፡ ከበላያችሁ ፡
ያነሳን ፡ ስንኾን ፡ (በኦሪት ፡ ሕግ ፡
እንድትሠሩ) ፡ ኪዳናችሁን ፡ በያ
ዝን ፡ ጊዜ ፡ (አስታውሱ) ፤ የሰጠ
ናችሁን ፡ በኀይል ፡ ያዙ ፤ ስሙም ፤
(አልን) ፤ ሰማን ፡ አመጥንም ፡
አሉ ፤ የወይፈኑንም ፡ ውዴታ ፡
በክሕደታቸው ፡ ምክንያት ፡ በል
ቦቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ተጠጡ ፤
አማኞች ፡ እንደኾናችሁ ፡ እምነ
ታችሁ ፡ በርሱ ፡ የሚያዛችሁ ፡
ነገር ፡ ከፋ ! በላቸው ።

94 የመጨረሻይቱ ፡ አገር ፡ (ገነት) ፡
አላህ ፡ ዘንድ ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡
ሌላ ፡ የተለየች ፡ ስትኾን ፡ ለእና
ንተ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ እውነተ
ኞች ፡ ከኾናችሁ ፡ ሞትን ፡ ተመኙ ፡
በላቸው ።

95 እጆቻቸውም ፡ ባሳለፉት ፡ (በሠ
ሩት) ፡ ምክንያት ፡ ምንጊዜም ፡
ፈጽሞ ፡ አይመኙትም ፤ አላህም ፡
በዳዮችን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

96 ከሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ከነዚያም ፡
(ጣዖትን) ፡ ከአጋሩት ፡ ይበልጥ ፡
በሕይወት ፡ ላይ ፡ የሚጓጉ ፡ ኾነው
በእርግጥ ፡ ታገኛቸዋለህ ፤ አንዳ
ቸው ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡
ቢሰሰጥ ፡ ይወዳል ፤ እርሱም ፡
ዕድሜ ፡ መሰጠቱ ፡ ከቅጣት ፡
የሚያርቀው ፡ አይደለም ፤ አላ
ህም ፡ የሚሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ተመ
ልካች ፡ ነው ።

97 ለጂብሪል ፡ (ለገብሬል) ፡ ጠላት ፡
የኾነ ፡ ሰው ፡ (በቁጭት ፡ ይሙት)
በላቸው ፤ እርሱ ፡ (ቁርአኑን) ፡
ከበፊቱ ፡ ለነበሩት ፡ (መጻሕፍት) ፡
አረጋጋጭ ፡ ለምእመናን ፡ መሪና ፡
ብስራት ፡ ሲኾን ፡ በአላህ ፡ ፈቃድ ፡
በልብህ ፡ ላይ ፡ አውርዶታልና ።

98 ለአላህና ፡ ለመላእክቱ ፡ ለመልክ
ተኞቹም ፡ ለጂብሪልም ፡ ለሚካ
ልም ፡ (ሚካኤል) ፡ ጠላት ፡
የኾነ ፡ ሰው ፡ አላህ ፡ ለ(እነዚህ) ፡
ከሓዲዎች ፡ ጠላት ፡ ነው ።

99 ወደንተም ፡ ግልጽ ፡ የኾኑትን ፡
አንቀጾች ፡ በእርግጥ ፡ አውርደ
ናል ፤ በርሷም ፡ አመጠኞች ፡
እንጂ ፡ ሌላው ፡ አይክድም ፡

100 ቃል ፡ ኪዳንንም ፡ ቃል ፡ በገቡ ፡
ቍጥር ፡ ከነርሱ ፡ ከፊሉ ፡ ይጥለ
ዋልን ? (ያፈርሰዋልን) ፤ ይልቁ
ንም ፡ አብዛኞቻቸው ፡ አያም
ኑም ።

101 እነርሱ ፡ ጋርም ፡ ላለው ፡ (መጽ
ሐፍ) ፡ አረጋጋጭ ፡ የኾነ ፡ መል
ክተኛ ፡ ከአላህ ፡ ዘንድ ፡ በመጣ
ላቸው ፡ ጊዜ ፡ ከነዚያ ፡ መጽሐ
ፍን ፡ ከተሰጡት ፡ ከፊሉ ፡ እነ
ርሱ ፡ እንደማያውቁ ፡ ኾነው ፡
የአላህን ፡ መጽሐፍ ፡ ከጀርባዎቻ
ቸው ፡ ኋላ ፡ ጣሉ ።

102 ሰይጣናትም ፡ በሱለይማን ፡ (ሰሎ
ሞን) ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የሚ
ያነቡትን ፡ (ድግምት) ፡ ተከተሉ ፤
ሱለይማንም ፡ አልካደም ፤ (ድግ
ምተኛ ፡ አልነበረም) ፤ ግን ፡ ሰይ
ጣናት ፡ ሰዎችን ፡ ድግምትን ፡
የሚያስተምሩ ፡ ሲኾኑ ፡ ካዱ ፤
ያንንም ፡ በባቢል ፡ በሁለቱ ፡ መላ
እክት ፡ በሃሩትና ፡ ማሩት ፡ ላይ ፡
የተወረደውን ፡ ነገር ፡ (ያስተምሩ
ዋቸዋል) ፡- እኛ ፡ መፈተኛ ፡
ነንና ፡ አትካድ ፡ እስከሚሉም ፡
ድረስ ፡ አንድንም ፡ አያስተም
ሩም ፤ ከነሱም ፡ በሰውየውና ፡
በሚስቱ ፡ መካከል ፡ በርሱ ፡
የሚለዩበትን ፡ ነገር ፡ ይማራሉ ፡
እነርሱም ፡ በአላህ ፡ ፈቃድ ፡ ካል



ኾነ ፡ በርሱ ፡ አንድንም ፡ ጎጂ
ዎች ፡ አይደሉም ፤ የሚጎዳቸው
ንና ፡ የማይጠቅማቸውንም ፡ ይማ
ራሉ ፡ የገዛውም ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡
በመጨረሻይቱ ፡ አገር ፡ ምንም ፡
ዕድል ፡ የሌለው ፡ መኾኑን ፡ በእ
ርግጥ ፡ ዐወቁ ፤ ነፍሶቻቸውንም ፡
በርሱ ፡ የሸጡበት ፡ ዋጋ ፡ ከፋ !
የሚያውቁ ፡ በኾኑ ፡ ኖሮ ፡ (ባልሠ
ሩት ፡ ነበር) ።

103 እነርሱም ፡ (አይሁዶች) ፡ ባመ
ኑና ፡ በተጠነቀቁ ፡ ኖሮ ፡ (በተመ
ነዱ ፡ ነበር) ፤ የሚያውቁ ፡ ቢ
ኾኑ ፡ ከአላህ ፡ ዘንድ ፡ የኾነው ፡
ምንዳ ፡ (ነፍሶቻቸውን ፡ ከሚሸ
ጡበት) ፡ በላጭ ፡ ነው ።

104 እናንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! (ለነ
ቢዩ) ፡ ራዒና ፡ [1] አትበሉ ፤
ተመልከተን ፡ በሉም ፤ ስሙም ፤
ለከሓዲዎችም ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት
አላቸው ።

105 እነዚያ ፡ ከመጽሐፉ ፡ ባለቤቶ
ችና ፡ ከአጋሪዎቹም ፡ የካዱት ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ ከጌታችሁ ፡ የኾነ ፡
መልካም ፡ ነገር ፡ መወረዱን ፡
አይወዱም ፤ አላህም ፡ በችሮታው ፡
(በነቢይነት) ፡ የሚሻውን ፡ ይመ
ርጣል ፤ አላህም ፡ የታላቅ ፡ ችሮታ
ባለቤት ፡ ነው ።

106 ከአንቀጽ ፡ ብንለውጥ ፡ ወይም ፡
እርሷን ፡ ብናስረሳህ ፡ ከርሷ ፡ የሚ
በልጥን ፡ ወይም ፡ ብጤዋን ፡ እና
መጣለን ፤ አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ከሃሊ ፡ (ቻይ) ፡ መኾኑን ፡
አታውቅምን ?

107 አላህ ፡ የሰማያትና ፡ የምድር ፡
ንግሥና ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡
አታውቅምን ? ለናንተም ፡ ከአ
ላህ ፡ ሌላ ፡ ዘመድና ፡ ረዳት ፡
ምንም ፡ የላችሁም ።

108 በውነቱ ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡ ሙሳ ፡
እንደተጠየቀ ፡ ብጤ ፡ መልክተኛ
ችሁን ፡ ልትጠይቁ ፡ ትፈልጋላች
ሁን ? በእምነትም ፡ ክሕደትን ፡
የሚለውጥ ፡ ሰው ፡ ትክክለኛ
ውን ፡ መንገድ ፡ በእርግጥ ፡ ተሳ
ሳተ ።

109 ከመጽሐፉ ፡ ባለቤቶች ፡ ብዙ
ዎች ፡ እውነቱ ፡ ከተገለጸላቸው ፡
በኋላ ፡ ከነፍሶቻቸው ፡ በኾነው ፡
ምቀኝነት ፡ ከእምነታችሁ ፡ በኋላ ፡
ከሓዲዎች ፡ አድርገው ፡ ሊመልሱ
ዋችሁ ፡ ተመኙ ። አላህም ፡ ትእ
ዛዙን ፡ እስከሚያመጣ ፡ ድረስ ፡
ይቅርታ ፡ አድርጉ ፤ እለፏቸውም ፤
አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ከሃሊ ፡
ነውና ።

110 ሶላትንም ፡ አስተካክላችሁ ፡
ስገዱ ፤ ዘካንም ፡ ስጡ ፤ ለነፍሶ
ቻችሁም ፡ ከበጎ ፡ ሥራ ፡ የምታ
ስቀድሙትን ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡ ታገ
ኙታላችሁ ፡ አላህ ፡ የምትሠሩ
ትን ፡ ሁሉ ፡ ተመልካች ፡ ነውና ።

111 ገነትንም ፡ አይሁድን ፡ ወይም ፡
ክርስቲያኖችን ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይገባትም ፡ አሉ ፤
ይህቺ ፡ (ከንቱ) ፡ ምኞታቸው ፡
ናት ፡ እውነተኞች ፡ እንደኾና
ችሁ ፡ አስረጃችሁን ፡ አምጡ ፡
በላቸው ።

112 አይደለም ፡ (ሌላውም ፡ ይገባ
ታል) ፡ እርሱ ፡ በጎ ፡ ሠሪ ፡ ኾኖ ፡
ፊቱን ፡ ለአላህ ፡ የሰጠ ፡ [1]
ሰው ፡ ለርሱ ፡ በጌታው ፡ ዘንድ ፡
ምንዳው ፡ አለው ፤ በነሱም ፡ ላይ ፡

---

1 ጠብቀን ፡ ለማለትና ፡ ጂሉ ፡ ለማለት ፡
ማሸሞሪያ ፡ ቃል ፡ ነው ።

1 ፍጹም ፡ ታዛዥ ፡ የኾነ ።

ፍርሃት ፡ የለባቸውም ፡ እነሱም ፡
አያዝኑም ።
113 እነርሱ ፡ መጽሐፉን ፡ የሚያነቡ ፡
ሲኾኑ ፡ አይሁዶች ፡— ክርስቲያ
ኖች ፡ በምንም ፡ ላይ ፡ አይደሉም ፡
አሉ ፤ ክርስቲያኖችም ፡— አይ
ሁዶች ፡ በምንም ፡ ላይ ፡ አይደ
ሉም ፡ አሉ ፤ እንደዚሁ ፡ እነዚያ ፡
የማያውቁት ፡ (አጋሪዎች) ፡ የንግ
ግራቸውን ፡ ብጤ ፡ አሉ ፤ (1)
አላህም ፡ በዚያ ፡ በርሱ ፡ ይለያ
ዩበት ፡ በነበሩት ፡ ነገር ፡ በትን
ሣኤ ፡ ቀን ፡ በመካከላቸው ፡ ይፈ
ርዳል ።
114 የአላህንም ፡ መስጊዶች ፡ በውስ
ጣቸው ፡ ስሙ ፡ እንዳይወሳ ፡ ከከ
ለከለና ፡ እርሷንም ፡ በማበላሸት ፡
ከሮጠ ፡ ሰው ፡ ይበልጥ ፡ በዳይ ፡
ማነው ? እነዚያ ፡ ፈሪዎች ፡ ኾነው ፡
እንጂ ፡ ለነርሱ ፡ ሊገቡዋት ፡ የላ
ቸውም ፤ ለነርሱ ፡ በቅርቢቱ ፡
ዓለም ፡ ውርደት ፡ አላቸው ፤ ለነ
ርሱም ፡ በመጨረሻይቱ ፡ አገር ፡
ታላቅ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ።
115 ምሥራቁም ፡ ምዕራቡም ፡ የአ
ላህ ፡ ነው ፤ (ፊቶቻችሁን) ፡ ወደ ፡
የትም ፡ ብታዞሩ ፡ የአላህ ፡ ፊት ፡
እዚያ ፡ ነው ፡ አላህ ፡ ችሮታው ፡
ሰፊ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።
116 አላህም ፡ ልጅ ፡ አለው ፡ አሉ ፡
(ከሚሉት) ፡ ጥራት ፡ ተገባው ፡
አይደለም ፡ በሰማያትና ፡ በም
ድር ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ የርሱ ፡ ነው ፤
ሁሉም ፡ ለርሱ ፡ ታዛዦች ፡
ናቸው ።
117 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ ያለብጤ ፡
ፈጣሪ ፡ ነው ፤ ነገርንም ፡ (ማስገ
ኘት) ፡ በሻ ፡ ጊዜ ፡ ለርሱ ፡ የሚ
ለው ፡— ኹን ፡ ነው ፤ ወዲያውም ፡
ይኾናል ።
118 እነዚያም ፡ የማያውቁት ፡ (አንተ ፡
መልክተኛ ፡ ስለ ፡ መኾንህ) ፡
አላህ ፡ አያናግረንም ፡ ኖሮአልን ?
ወይም ፡ (ለውነተኛነትህ) ፡ ታምር
አትመጣልንም ፡ ኖሮአልን ? አሉ ፤
እንደዚሁ ፡ እነዚያ ፡ ከነሱ ፡
በፊት ፡ የነበሩት ፡ እንደ ፡ ንግግ
ራቸው ፡ ብጤ ፡ ብለዋል ፤ ልቦ
ቻቸው ፡ (በክሕደት) ፡ ተመሳ
ሰሉ ፤ ለሚያረጋግጡ ፡ ሕዝቦች ፡
አንቀጾችን ፡ በእርግጥ ፡ አብራር
ተናል ።
119 እኛ ፡ አብሳሪና ፡ አስፈራሪ ፡
ኾነህ ፡ በውነት ፡ ላክንህ ፤ ከእሳ
ትም ፡ ጓዶች ፡ አትጠየቅም ።
120 አይሁዶችና ፡ ክርስቲያኖችም ፡
ሃይማኖታቸውን ፡ እስከምትከተ
ል ፡ ድረስ ፡ ካንተ ፡ ፈጽሞ ፡ አይ
ወዱም ፤ የአላህ ፡ መምራት ፡
(ትክክለኛው) ፡ መምራት ፡ እርሱ ፡
ብቻ ፡ ነው ፡ በላቸው ፤ ከዚያም ፡
ዕውቀቱ ፡ ከመጣልህ ፡ በኋላ ፡ ዝን
ባሌያቸውን ፡ ብትከተል ፡ ለአ
ንተ ፡ ከአላህ ፡ (የሚከለክልህ) ፡
ዘመድና ፡ ረዳት ፡ ምንም ፡ የለ
ህም ።
121 እነዚያ ፡ መጽሐፉን ፡ የሰጠና
ቸው ፡ ተገቢ ፡ ንባቡን ፡ ያነቡ
ታል ፤ እነዚያ ፡ በርሱ ፡ ያምናሉ ፤
በርሱም ፡ የሚክዱ ፡ እነዚያ ፡
እነርሱ ፡ ከሳሪዎቹ ፡ ናቸው ።
122 የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፡ ያችን
በናንተ ፡ ላይ ፡ የለገስኋትን ፡ ጸጋ
የንና ፡ እኔም ፡ በዓለማት ፡ ላይ ፡
ያበለጥኋችሁ ፡ መኾኔን ፡ አስታ
ውሱ ።

1 ባለ ፡ ሃይማኖቶች ፡ በምንም ፡ ላይ ፡ አይደ
ሉም ፡ አሉ ።



123 (አማኝ) ፡ ነፍስም ፡ ከ(ከሓዲ) ፡
ነፍስ ፡ ምንንም ፡ የማትጠቅምበ
ትን ፡ ከርሷም ፡ ቤዛ ፡ የማይወሰድ
በትን ፡ ምልጃም ፡ ለርሷ ፡ የማት
ጠቅምበትን ፡ እነርሱም ፡ የማይረ
ዱበትን ፡ ቀን ፡ ተጠንቀቁ ።
124 ኢብራሂምንም ፡ ጌታው ፡ በቃ
ላት ፡ (በሕግጋት) ፡ በፈተነውና ፡
በፈጸማቸው ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፤
እኔ ፡ ለሰዎች ፡ መሪ ፡ አድራጊህ ፡
ነኝ ፡ አለው ፤ ከዘሮቼም ፡ (አድ
ርግ) ፡ አለ ፤ ቃል ፡ ኪዳኔ ፡ በዳ
ዮቹን ፡ አያገኝም ፡ አለው ።
125 ቤቱንም ፡ (1) ለሰዎች ፡ መመለ
ሻና ፡ ጸጥተኛ ፡ ባደረግን ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ) ፤ ከኢብራሂምም ፡
መቆሚያ ፡ መስገጃን ፡ አድርጉ ፤
ወደ ፡ ኢብራሂምና ፡ ወደ ፡ ኢስ
ማዒልም ፡ ቤቴን ፡ ለዘዋሪዎቹና ፡
ለተቀማጮቹም ፡ ለአጎንባሾች ፡
ሰጋጆቹም ፡ አጥሩ ፡ ስንል ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ ያዝን ።
126 ኢብራሂም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ (አስታ
ውስ) ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ይህንን ፡
ጸጥተኛ ፡ አገር ፡ አድርግ ፤ ቤተሰ
ቦቹንም ፡ ከነሱ ፡ በአላህና ፡ በመ
ጨረሻው ፡ ቀን ፡ ያመነውን ፡
ሰው ፡ ከፍሬዎች ፡ ስጠው ፤ (አላ
ህም) ፡ የካደውንም ፡ ሰው ፤ (እሰ
ጠዋለሁ) ፤ ጥቂትም ፡ እጠቅመ
ዋለሁ ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ እሳት ፡
ቅጣት ፡ አስጠጋዋለሁ ፤ ምን ፡
ትከፉም ፡ መመለሻ ! (አለ) ።
127 ኢብራሂምና ፡ ኢስማዒልም ፡
ጌታችን ፡ ሆይ ፡ ከኛ ፡ ተቀበል ፤
አንተ ፡ ሰሚውና ፡ ዐዋቂው ፡
አንተ ፡ ነህና ፡ የሚሉ ፡ ሲኾኑ ፡
ከቤቱ ፡ መሠረቶቹን ፡ ከፍ ፡ ባደ
ረጉ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ።
128 ጌታችን ፡ ሆይ ! ላንተ ፡ ታዛዥ
ችም ፡ አድርገን ፤ ከዘሮቻችንም ፡
ላንተ ፡ ታዛዦች ፡ ሕዝቦችን ፡
(አድርግ) ፤ ሕግጋታችንንም ፡
አሳየን ፤ (አሳውቀን) ፤ በኛም ፡
ላይ ፡ ተመለስልን ፤ አንተ ፡ ጸጸ
ትን ፡ ተቀባዩ ፡ ርኅሩኁ ፡ አንተ ፡
ብቻ ፡ ነህና ።
129 ጌታችን ፡ ሆይ ! በውስጣቸውም ፡
ከነሱው ፡ የኾነን ፡ መልክተኛ ፡
በነርሱ ፡ ላይ ፡ አንቀጾችህን ፡ የሚ
ያነብላቸውን ፡ መጽሐፍንና ፡
ጥበብንም ፡ የሚያስተምራቸውን ፡
(ከክሕደት) ፡ የሚያጠራቸውንም ፡
ላክ ፤ አንተ ፡ አሸናፊው ፡ ጥበበ
ኛው ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህና ። (የሚ
ሉም ፡ ሲኾኑ) ።
130 ከኢብራሂምም ፡ ሕግጋት ፡ ነፍ
ሱን ፡ ያቄለ ፡ ሰው ፡ ካልኾነ ፡
በስተቀር ፡ የሚያፈገፍግ ፡ ማነው ?
(የለም) ፤ በቅርቢቱም ፡ ዓለም ፡
በእርግጥ ፡ መረጥነው ፤ በመጨረ
ሻይቱም ፡ ዓለም ፡ እርሱ ፡ ከመል
ካሞቹ ፡ ነው ።
131 ጌታው ፡ ለርሱ ፡ ታዘዝ ፡ ባለው ፡
ጊዜ ፡ (መረጠው) ፤ ለዓለማት ፡
ጌታ ፡ ታዘዝኩ ፡ አለ ።
132 በርሷም ፡ (በሕግጋቲቱ) ፡ ኢብራ
ሂም ፡ ልጆቹን ፡ አዘዘ ፤ ያዕቁብም ፡
(እንደዚሁ ፡ ልጆቹን ፡ አዘዘ) ፤
ልጆቼ ፡ ሆይ ! አላህ ፡ ለናንተ ፡
ሃይማኖትን ፡ መረጠ ፤ ስለዚህ ፡
እናንተ ፡ ሙስሊሞች ፡ ኾናችሁ ፡
እንጂ ፡ አትሙቱ ፡ (አላቸው) ።
133 ያዕቁብን ፡ ሞት ፡ በመጣበት ፡
ጊዜ ፡ ለልጆቹ ፡ ከኔ ፡ በኋላ ፡ ማንን ፡
ትግገዛላችሁ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ቀራቢ

1 የአላህን ፡ መገገኘ ፡ ቤት ፡ ከዕባን ።

ዎች ፡ ነበራችሁን ? (እነርሱም) ፡
አምላክህንና ፡ የአባቶችህን ፡ የኢ
ብራሂምን ፡ የኢስማዒልንና ፡ የኢ
ስሐቅንም ፡ አምላክ ፡ አንድ ፡ የኾ
ነውን ፡ አምላክ ፡ እኛ ፡ ለርሱ ፡
ፍጹም ፡ ታዛዦች ፡ ኾነን ፡ እናመ
ልካለን ፡ አሉ ።
134 ይህች ፡ (የተወሳችው) ፡ በእር
ግጥ ፡ ያለፈች ፡ ሕዝብ ፡ ናት ፤
ለርሷ ፡ የሠራችው ፡ (ምንዳ) ፡
አላት ፡ ለናንተም ፡ የሠራችሁት ፡
(ምንዳ) ፡ አላችሁ ፡ ይሠሩትም ፡
ከነበሩት ፡ አትጠየቁም ።
135 አይሁድን ፡ ወይም ፡ ክርስቲያ
ኖችን ፡ ኹኑ ፤ (ቅኑን ፡ መንገድ) ፡
ትመራላችሁና ፡ አሉም ፤ አይደ
ለም ፡ የኢብራሂምን ፡ ሃይማኖት ፡
ቀጥተኛ ፡ ሲኾን ፡ እንከተላለን ፤
ከአጋሪዎችም ፡ አልነበረም ፡
በላቸው ።
136 በአላህና ፡ ወደኛ ፡ በተወረደው ፡
(ቁርአን) ፡ ወደ ፡ ኢብራሂምም ፡
ወደ ፡ ኢስማዒልና ፡ ወደ ፡ ኢስሐ
ቅም ፡ ወደ ፡ ያዕቁብና ፡ ወደ ፡ ነገ
ዶቹም ፡ በተወረደው ፡ በዚያም ፡
ሙሳና ፡ ዒሳ ፡ በተሰጡት ፡ በዚ
ያም ፡ ነቢያት ፡ ሁሉ ፡ ከጌታቸው ፡
በተሰጡት ፡ ከነርሱ ፡ በአንድም ፡
መካከል ፡ የማንለይ ፡ ስንኾን ፡
አመንን ፤ እኛም ፡ ለርሱ ፡ (ለአ
ላህ) ፡ ታዛዦች ፡ ነን ፡ በሉ ።
137 በርሱ ፡ ባመናችሁበት ፡ ብጤ ፡
ቢያምኑ ፡ በእርግጥ ፡ ተመሩ ፤
ቢዞሩም ፡ እነርሱ ፡ በጭቅጭቅ ፡
ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፤ እነርሱ
ንም ፡ አላህ ፡ ይበቃሃል ፤ እርሱም ፡
ሰሚው ፡ ዐዋቂው ፡ ነው ።
138 የአላህን ፡ (የተፈጥሮ) ፡ መንከር ፡
(እምነት) ፡ ያዙ ፤ በመንከርም ፡
ከአላህ ፡ ይበልጥ ፡ ያማረ ፡ ማነው?
(ማንም ፡ የለም) ፡ እኛም ፡ ለርሱ ፡
ብቻ ፡ ተገዢዎች ፡ ነን ፡ (በሉ) ።
139 እርሱ ፡ (አላህ) ፡ ጌታችንና ፡ ጌታ
ችሁ ፡ ሲኾን ፡ ለኛም ፡ ሥራችን ፡
ያለን ፡ ስንኾን ፡ ለናንተም ፡ ሥራ
ችሁ ፡ ያላችሁ ፡ ስትኾኑ ፡ እኛም ፡
ለርሱ ፡ ፍጹም ፡ ታዛዦች ፡ ስን
ኾን ፡ በአላህ ፡ (ሃይማኖት) ፡ ትከ
ራከሩናላችሁን ? በላቸው ።
140 ወይም ፡ ኢብራሂም ፡ ኢስማዒ
ልም ፡ ኢስሐቅም ፡ ያዕቁብም ፡
ነገዶቹም ፡ አይሁዶች ፡ ወይም ፡
ክርስቲያኖች ፡ ነበሩ ፡ ትላላች
ሁን ? እናንተ ፡ ታውቃላችሁን ?
ወይንስ ፡ አላህ ? በላቸው ፤ እር
ሱም ፡ ዘንድ ፡ ከአላህ ፡ የኾነችን ፡
ምስክርነት ፡ ከደበቀ ፡ ሰው ፡
ይበልጥ ፡ በዳይ ፡ ማነው ? አላ
ህም ፡ ከምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ዘንጊ ፡
አይደለም ።
141 ይህቺ ፡ በእርግጥ ፡ ያለፈች ፡
ሕዝብ ፡ ናት ፤ ለእርሷ ፡ የሠራ
ችው ፡ አላት ፤ ለናንተም ፡ የሠራ
ችሁት ፡ አላችሁ ፤ ይሠሩትም ፡
ከነበሩት ፡ አትጠየቁም ። (1)

* * *

142 ከሰዎቹ ፡ ቂሎቹ ፡ ከዚያች ፡ በርሷ ፡
ላይ ፡ ከነበሩባት ፡ ቂብላቸው ፡ (2)
ምን ፡ አዞራቸው ? ይላሉ ፤ ምሥራ
ቁም ፡ ምዕራቡም ፡ የአላህ ፡ ነው ፤
የሻውን ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ቀጥተኛው ፡
መንገድ ፡ ይመራል ፡ በላቸው ።
143 እንደዚሁም ፡ (እንደመራናችሁ) ፡
በሰዎች ፡ ላይ ፡ መስካሪዎች ፡
ልትሆኑና ፡ መልክተኛውም ፡ በና

1 በነርሱ ፡ ለምን ፡ ትመካላችሁ ።
2 በስግደት ፡ ከሚቅጣጩዋት ፡ ስፍራ ፡ ከቤተ
መቅደስ ።



ንተ ፡ ላይ ፡ መስካሪ ፡ ይሆን ፡
ዘንድ ፡ ምርጥ ፡ ሕዝቦች ፡ አደረግ
ናችሁ ፤ ያችንም ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡
የነበርክባትን ፡ አቅጣጫ ፡ መልክ
ተኛውን ፡ የሚከተለውን ፡ ሰው ፡
ወደ ፡ ክሕደት ፡ ከሚመለሰው ፡
ሰው ፡ ልናውቅ ፡ (ልንገልጥ) ፡
እንጅ ፡ ቂብላ ፡ አላደረግናትም ፡
እርሷም ፡ በነዚያ ፡ አላህ ፡ በመራ
ቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ በስተቀር ፡
በእርግጥ ፡ ከባድ ፡ ናት ፤ አላህም ፡
እምነታችሁን ፡ (ስግደታችሁን) ፡
የሚያጠፋ ፡ አይደለም ፤ አላህ ፡
ለሰዎች ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ አዛኝ ፡
ነውና ።
144 የፊትህን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ መገላ
በጥ ፡ በእርግጥ ፡ እናያለን ፤ ወደ
ምትወዳትም ፡ ቂብላ ፡ እናዞርሃ
ለን ፤ ስለዚህ ፡ ፊትህን ፡ ወደ ፡
ተከበረው ፡ መስጊድ ፡ (ወደ ፡
ካዕባ) ፡ አግጣጫ ፡ አዙር ፤ የትም ፡
ስፍራ ፡ ብትኾኑም ፡ (ስትሰግዱ) ፡
ፊቶቻችሁን ፡ ወደርሱ ፡ አግጣጫ ፡
አዙሩ ፤ እነዚያም ፡ መጽሐፉን ፡
የተሰጡት ፡ እርሱ ፡ ከጌታቸው ፡
ሲኾን ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ ያው
ቃሉ ፤ አላህም ፡ ከምትሠሩት ፡
ሥራ ፡ ዘንጊ ፡ አይደለም ።
145 እነዚያንም ፡ መጽሐፍን ፡ የተሰ
ጡትን ፡ በአስረጅ ፡ ሁሉ ፡ ብት
መጣቸው ፡ ቂብላህን ፡ አይከተ
ሉም ፤ አንተም ፡ ቂብላቸውን ፡
ተከታይ ፡ አይደለህም ፤ ከፊላቸ
ውም ፡ የከፊሉን ፡ ቂብላ ፡ ተከ
ታይ ፡ አይደሉም ፤ ከዕውቀትም ፡
(ከራዕይ) ፡ ከመጣልህ ፡ በኋላ ፡
ዝንባሌያቸውን ፡ ብትከተል ፡
አንተ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከበዳዮች ፡
ነህ ።
146 እነዚያ ፡ መጽሐፍን ፡ የሰጠና
ቸው ፡ ወንዶች ፡ ልጆቻቸውን ፡
እንደሚያውቁ ፡ (ሙሐመድን) ፡
ያውቁታል ፤ (1) ከነሱም ፡ የተ
ለዩ ፡ ክፍሎች ፡ እነርሱ ፡ የሚያ
ውቁ ፡ ሲኾኑ ፡ ውነቱን ፡ በእር
ግጥ ፡ ይደብቃሉ ።
147 (ይህ) ፡ ከጌታህ ፡ የኾነ ፡ እውነት ፡
ነው ፤ ከተጠራጣሪዎቹም ፡ አት
ሁን ።
148 ለሁሉም ፡ እርሱ ፡ (በስግደት ፡
ፊቱን) ፡ የሚያዞርባት ፡ አግጣጫ ፡
አለችው ፤ ወደ ፡ መልካም ፡ ሥራ
ዎችም ፡ ተሽቀዳደሙ ፤ የትም ፡
ስፍራ ፡ ብትኾኑ ፡ አላህ ፡ እናን
ተን ፡ የተሰበሰባችሁ ፡ ኾናችሁ ፡
ያመጣችኋል ፤ አላህ ፡ በነገሩ ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ ነውና ።
149 ከየትም ፡ (ለጉዞ) ፡ ከወጣህበት ፡
ስፍራ ፡ ፊትህን ፡ ወደ ፡ ተከበ
ረው ፡ መስጊድ ፡ አግጣጫ ፡
አዙር ፤ እርሱም ፡ ከጌታህ ፡ የኾነ ፡
እርግጠኛ ፡ ውነት ፡ ነው ፤ አላ
ህም ፡ ከምትሠሩት ፡ ሥራ ፡ ዘንጊ ፡
አይደለም ።
150 ከየትም ፡ ከወጣህበት ፡ ስፍራ ፡
ፊትህን ፡ ወደ ፡ ተከለለው ፡ መስ
ጊድ ፡ አቅጣጫ ፡ አዙር ፤ በየትም ፡
ስፍራ ፡ ብትኾኑ ፡ ለሰዎቹ ፡ እነ
ዚያ ፡ ከነሱ ፡ የበደሉት ፡ ሲቀሩ ፡
(ሃይማኖታችንን ፡ ይክዳሉ ፡ ቂብ
ላችንን ፡ ይከተላሉ ፡ በማለት) ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ መከራከሪያ ፡ እን
ዳይኖራቸው ፡ ፊቶቻችሁን ፡ ወደ ፡
አቅጣጫው ፡ አዙሩ ፤ አትፍሩዋ
ቸውም ፤ ፍሩኝም ፤ (በዚህም ፡
ያዘዝኳችሁ ፡ መከራከሪያ ፡ እንዳ
ይኖራቸው) ፡ በናንተም ፡ ላይ ፡

1 በመጽሐፋቸው ፡ ምልክቱ ፡ ተነግሮአልና ።

ጸጋዬን ፡ እንድሞላላችሁና ፡ (ወደ ፡
እውነትም) ፡ እንድትመሩ ፡ ነው ።

151 በውስጣችሁ ፡ ከናንተው ፡ የኾነን ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ አንቀጾቻችንን ፡
የሚያነብላችሁና ፡ የሚያጠራችሁ
መጽሐፍንና ፡ ጥበብንም ፡ የሚያ
ስተምራችሁ ፡ ታውቁት ፡ ያልነበ
ራችሁትንም ፡ ነገር ፡ የሚያሳው
ቃችሁ ፡ የኾነን ፡ መልክተኛ ፡
እንደላክን ፡ (ጸጋን ፡ ሞላንላችሁ) ።

152 አስታውሱኝም ፤ አስታውሳችኋ
ለሁና ፡ ለኔም ፡ አመስግኑ ፤ አት
ካዱኝም ።

153 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ፡ በመ
ታገሥና ፡ በሦላት ፡ ተረዱ ፤ አላህ ፡
(በእርዳታው) ፡ ከታጋሾች ፡ ጋር ፡
ነውና ።

154 በአላህ ፡ መንገድ ፡ (ለሃይማኖቱ) ፡
የሚገደሉትን ፡ ሰዎችም ፡ ሙታን ፡
ናቸው ፡ አትበሉ ፤ በውነቱ ፡ ሕያ
ዋን ፡ ናቸው ፤ ግን ፡ አታውቁም ።

155 ከፍርሃትና ፡ ከረኃብም ፡ በጥቂት ፡
ነገር ፡ ከገንዘቦችና ፡ ከነፍሶችም ፡
ከፍራፍሬዎችም ፡ በመቀነስ ፡
በእርግጥ ፡ እንሞክራችኋለን ፡
ታጋሾችንም ፡ (በገነት) ፡ አብ
ስር ።

156 እነዚያን ፡ መከራ ፤ በነካቻቸው ፡
ጊዜ ፡ እኛ ፡ ለአላህ ፤ ነን ፡ እኛም ፡
ወደርሱ ፡ ተመላሾች ፡ ነን ፡ የሚ
ሉትን ፡ (አብስር) ።

157 እነዚያ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ከጌታ
ቸው ፡ የኾኑ ፡ ምሕረቶች ፡ ችሮ
ታም ፡ አልሉ ፡ እነርሱም ፡ (ወደ
እውነት) ፡ ተመሪዎቹ ፡ እነርሱ ፡
ናቸው ።

158 ሶፋና ፡ መርዋ ፡ (1) ከአላህ ፡
(ትእዛዝ ፡ መፈጸሚያ) ፡ ምልክ
ቶች ፡ ናቸው ፤ ቤቱን ፡ (ከዕባን) ፡
በሐጅ ፡ ወይም ፡ በዑምራህ ፡
ሥራ ፡ የጎበኘ ፡ ሰው ፡ በሁለቱ ፡
(መካከል) ፡ በመመላለሱ ፡ በርሱ ፡
ላይ ፡ ኃጢአት ፡ የለበትም ፤ መል
ካምንም ፡ ሥራ ፡ በፈቃደኛነት ፡
የሠራ ፡ ሰው ፡ (አላህ ፡ ይመነዳ
ዋል) ፤ አላህ ፡ አመስጋኝ ፡ ዐዋቂ ፡
ነውና ።

159 እነዚያ ፡ ከአንቀጾችና ፡ ከቅን ፡
መምሪያ ፡ ያወረድነውን ፡ ለሰ
ዎች ፡ በመጽሐፉ ፡ ከገለጽነው ፡
በኋላ ፡ የሚደብቁ ፤ እነዚያ ፡
አላህ ፡ ይረግማቸዋል ፤ ረጋሚዎ
ችም ፡ ሁሉ ፡ ይረግሟቸዋል ።

160 እነዚያ ፡ (ከመደበቅ) ፡ የተጸጸቱና ፡
(ሥራቸውን) ፡ ያሳመሩም ፡ (የደ
በቁትን) ፡ የገለጹም ፡ ብቻ ፡
ሲቀሩ ፤ እነዚህም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
(ጸጸታቸውን) ፡ እቀበላለሁ ፤ እኔ
ም ፡ ጸጸትን ፡ በጣም ፡ ተቀባይ ፡
አዛኙ ፡ ነኝ።

161 እነዚያ ፡ የካዱ ፡ እነርሱ ፡ ከሐዲ
ዎች ፡ ኾነውም ፡ የሞቱ ፡ እነዚያ
በነርሱ ፡ ላይ ፡ የአላህና ፡ የመላ
እክት ፡ የሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ርግ
ማን ፡ አለባቸው ።

162 በውስጧ ፡ (በርግማንዋ ፡ ውስጥ) ፡
ሁልጊዜ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡
ቅጣቱ ፡ ከነሱ ፡ አይቀለልም ፤
እነርሱም ፡ አይቅቆዩም ፡ (ጊዜ ፡
አይሰጡም) ።

163 አምላካችሁም ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ ከርሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡
አምላክ ፡ የለም ፤ (እርሱ) ፡ እጅግ ፡
በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።

164 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ በመፍ
ጠር ፡ ሌሊትንና ፡ ቀንንም ፡ በማ

1 በመካ ፡ የሚገኙ ፡ ተራራዎች ፡ ናቸው ።



ተካካት ፡ በዚያችም ፡ ሰዎችን ፡
በሚጠቅም ፡ ነገር ፡ (ተጪና) ፡
በባሕር ፡ ላይ ፡ በምትንሻለለው ፡
ታንኳ ፡ አላህም ፡ ከሰማይ ፡ ባወ
ረደው ፡ ውሃና ፡ በርሱም ፡ ምድ
ርን ፡ ከሞተች ፡ በኋላ ፡ ሕያው ፡
በማድረጉ ፡ በርሷም ፡ ውስጥ ፡
ከተንቀሳቃሽ ፡ ሁሉ ፡ በመበተኑ ፡
ነፋሶችንም ፡ (በየአቅጣጫው) ፡
በማገለባበጥ ፡ በሰማይና ፡ በም
ድር ፡ መካከል ፡ በሚንነዳውም ፡
ደመና ፡ ለሚያውቁ ፡ ሕዝቦች ፡
እርግጠኛ ፡ ምልክቶች ፡ አልሉ ።

165 ከሰዎችም ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ባላን
ጣዎችን ፡ (ጣዖታትን) ፡ አላህን ፡
እንደሚወዱ ፡ የሚወዷቸው ፡
ኾነው ፡ የሚይዙ ፡ አልሉ ፡ እነ
ዚያ ፡ ያመኑትም ፡ አላህን ፡ በመ
ውደድ ፡ (ከነርሱ) ፡ ይበልጥ ፡ የበ
ረቱ ፡ ናቸው ፤ እነዚያም ፡ የበደ
ሉት ፡ ሰዎች ፡ ቅጣትን ፡ (በትን
ሣኤ ፡ ቀን) ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ኀይል ፡
ሁሉ ፡ ለአላህ ፡ ብቻ ፡ መኾኑንና ፡
አላህም ፡ ቅጣቱ ፡ ብርቱ ፡ መኾ
ኑን ፡ (በአዱኛ ፡ ዓለም) ፡ ቢያ
ውቁ ፡ኖሮ ፡ (ባላንጣዎችን ፡ በመ
ያዛቸው ፡ በተጸጸቱ ፡ ነበር) ።

166 እነዚያ ፡ አስከታዮቹ ፡ ቅጣትን ፡
ያዩ ፡ ሲኾኑ ፡ ከነዚያ ፡ ከተከታ
ዮች ፡ በተጥራሩና ፡ በነርሱም ፡
(መካከል) ፡ ምክንያቶች ፡ በተቆ
ረጡ ፡ ጊዜ ፡ (የሚኾኑትን ፡ ባወቁ
ኖሮ ፡ በተጸጸቱ ፡ ነበር) ።

167 እነዚያም ፡ የተከተሉት ፡ ለኛ ፡
(ወደ ፡ ቅርቢቱ ፡ ዓለም) ፡ አን
ዲት ፡ ጊዜ ፡ መመለስ ፡ በኖረች
ንና ፡ ከእኛ ፡ እንደተጥራሩ ፡ ከነ
ርሱ ፡ በተጥራራን ፡ እንመኛለን ፡
ይላሉ ፤ እንደዚሁ ፡ አላህ ፡ ሥራ
ዎቻቸውን ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ጸጸ
ቶች ፡ አድርጎ ፡ ያሳያቸዋል ፤ እነ
ርሱም ፡ ከእሳት ፡ ወጪዎች ፡ አይ
ደሉም ።

168 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! በምድር ፡
ካለው ፡ ነገር ፡ የተፈቀደ ፡ ጣፋጭ ፡
ሲኾን ፡ ብሉ ፤ የሰይጣንንም ፡ እር
ምጃዎች ፡ አትከታተሉ ፤ እርሱ ፡
ለናንተ ፡ ግልጽ ፡ ጠላት ፡ ነውና ።

169 (እርሱ) ፡ የሚያዛችሁ ፡ በኃጢ
አትና ፡ በጠያፍ ፡ ነገር ፡ በአላ
ህም ፡ ላይ ፡ የማታውቁትን ፡ እን
ድትናገሩ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

170 ለነርሱም ፡ አላህ ፡ ያወረደውን ፡
ተከተሉ ፡ በተባሉ ፡ ጊዜ ፡ አይደ
ለም ፡ አባቶቻችንን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
ያገኘንበትን ፡ ነገር ፡ እንከተላ
ለን ፡ ይላሉ ፡ አባቶቻቸው ፡
ምንም ፡ የማያውቁና ፡ (ወደ ፡
እውነት) ፡ የማይመሩም ፡ ቢኾኑ ፡
(ይከተሉዋቸዋልን ?)

171 የነዚያም ፡ የካዱት(ና ፡ ወደ ፡
ቅን ፡ መንገድ ፡ የሚጠራቸው ፡
ሰው) ፡ ምሳሌ ፡ እንደዚያ ፡ ድም
ጽንና ፡ ጥሪን ፡ በስተቀር ፡ ሌላን ፡
በማይሰማ ፡ (እንስሳ) ፡ ላይ ፡ እን
ደሚጮህ ፡ ብጤ ፡ ነው ፤ (እነ
ርሱ) ፡ ደንቆሮዎች ፡ ዲዳዎች ፤
ዕውሮች ፡ ናቸው ፤ ስለዚህ ፡ እነ
ርሱ ፡ አያውቁም ።

172 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ከነ
ዚያ ፡ ከሰጠናችሁ ፡ ጣፋጮች ፡
ብሉ ፡ ለአላህም ፡ እርሱን ፡ ብቻ ፡
የምትገዙ ፡ እንደኾናችሁ ፡ አመ
ስግኑ ፡

173 በናንተ ፡ ላይ ፡ እርም ፡ ያደረገው ፡
በክትንና ፡ ደምን ፡ የእሪያ ፡ ሥጋ
ንም ፡ በርሱም ፡ (ማረድ) ፡ ከአ
ላህ ፡ ስም ፡ ሌላ ፡ የተነሳበትን ፡

ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ሺፍታና ፡
ወሰን ፡ አላፊ ፡ ሳይኾን ፡ (ለመብ
ላት) ፡ የተገደደ ፡ ሰውም ፡ በርሱ ፡
ላይ ፡ ኃጢአት ፡ የለበትም ፡ አላህ፡
መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።

174 እነዚያ ፡ አላህ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ያወ
ረደውን ፡ የሚደብቁ ፡ በርሱም ፡
(በመደበቃቸው) ፡ ጥቂትን ፡ ዋጋ ፡
የሚገዙ ፡ እነዚያ ፡ በሆዶቻቸው ፡
ውስጥ ፡ እሳትን ፡ እንጂ ፡ አይበ
ሉም ፤ አላህም ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡
አያናግራቸውም ፤ (ከኃጢአት) ፡
አያጠራቸውምም ፤ ለነርሱም ፡
አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ።

175 እነዚያ ፡ ጥመትን ፡ በቅንነት ፡
ቅጣትንም ፡ በምሕረት ፡ የገዙ ፡
ናቸው ፤ በእሳት ፡ ላይም ፡ ምን ፡
ታጋሽ ፡ አደረጋቸው !

176 ይህ ፡ (ቅጣት) ፡ አላህ ፡ መጽሐ
ፍን ፡ በውነት ፡ ያወረደ ፡ በመ
ኾኑ ፡ ምክንያት(ና ፡ በርሱ ፡ በመ
ካዳቸው) ፡ ነው ፤ እነዚያም ፡ በመ
ጽሐፉ ፡ የተለያዩት ፡ (ከውነት) ፡
በራቀ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ውስጥ ፡
ናቸው ።

177 መልካም ፡ ሥራ ፡ ፊቶቻችሁን ፡
ወደ ፡ ምሥራቅና ፡ ምዕራብ ፡ አቅ
ጣጫ ፡ ማዞር ፡ አይደለም ፤ ግን ፡
መልካም ፡ ሥራ ፡ በአላህና ፡ በመ
ጨረሻው ፡ ቀን ፡ በመላእክትም ፡
በመጻሕፍትም ፡ በነቢያትም ፡
ያመነ ፡ ሰው ፡ ገንዘብንም ፡ ከመ
ውደዱ ፡ ጋር ፡ ለዝምድና ፡ ባለቤ
ቶችና ፡ ለየቲሞች ፡ (1) ለምስኪ
ኖችም ፡ ለመንገደኞችም ፡ ለለማ
ኞችም ፡ ለጫንቃዎችም ፡ (ማስለ
ቀቅ) ፡ የሰጠ ፡ ሰውና ፡ ሶላትንም ፡
ደንቡን ፡ ጠብቆ ፡ የሰገደ ፡ ዘካ
ንም ፡ የሰጠ ፡ ቃል ፡ ኪዳንም ፡
በገቡ ፡ ጊዜ ፡ በኪዳናቸው ፡ የሞሉ
(ሰዎች ፡ ሥራ) ፡ ነው ፤ በችግር ፡
በበሺታና ፡ በጦር ፡ ጊዜም ፡ ታጋ
ሾችን ፡ (እናወድሳለን) ፤ እነዚህ ፡
እነዚያ ፡ እውነትን ፡ የያዙ ፡ ናቸው፤
እነዚያም ፡ ተጠንቃቂዎቹ ፡ እነ
ርሱ ፡ ናቸው ።

178 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! በተ
ገደሉ ፡ ሰዎች ፡ ማመሳሰል ፡ በና
ንተ ፡ ላይ ፡ ተጻፈ ፤ ነጻ ፡ በነጻ ፡
ባሪያም ፡ በባሪያ ፡ ሴትም ፡ በሴት፡
(ይገደላሉ) ፤ ለርሱም ፡ (ለገዳዩ) ፡
ከወንድሙ ፡ (ደም) ፡ ትንሽ ፡
ነገር ፡ ምሕረት ፡ የተደረገለት ፡
ሰው ፡ (በመሐሪው ፡ ላይ ፡ ጉማ
ውን) ፡ በመልካም ፡ መከታተል ፡
ወደርሱም ፡ (ወደ ፡ መሐሪው ፡
ገዳዩ) ፡ በመልካም ፡ አኳኋን ፡
መክፈል ፡ አለባቸው ፤ ይህ ፡ ከጌ
ታችሁ ፡ የኾነ ፡ ማቃለልና ፡ እዝ
ነት ፡ ነው ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡
ሕግን ፡ የተላለፈ ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡
አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ አለው ።

179 ለናንተም ፡ ባለ ፡ አእምሮዎች፡
ሆይ ! በማመሳሰል ፡ (ሕግ) ፡
ውስጥ ፡ ሕይወት ፡ አላችሁ ፤ ትጠ
ነቀቁ ፡ ዘንድ ፡ (ገዳይን ፡ መግ
ደል ፡ ተደነገገላችሁ) ።

180 አንዳችሁን ፡ ሞት ፡ በመጣበት ፡
ጊዜ ፡ ሀብትን ፡ ቢተው ፡ ለወላ
ጆችና ፡ ለቅርብ ፡ ዘመዶች ፡
በበጎ ፡ መናዘዝ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
ተጻፈ ፤ (ይህ) ፡ በጥንቁቆች ፡ ላይ ፡
እርግጠኛ ፡ ድንጋጌ ፡ ተደነ
ገገ ። (1)

181 (ኑዛዜውን) ፡ ከሰማውም ፡ በኋላ ፡

1 የቲም ፤ ማለት ፡ አባቱ ፡ የሞተበት ፡ ሕፃን ፡
ነው ።

1 ይህ ፡ በውርስ ፡ አንቀጾች ፡ ተሽሮአል ።



የለወጠው ፡ ሰው ፡ ኃጢአቱ ፡
በነዚያ ፡ በሚለውጡት ፡ ላይ ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ አላህ ፡ ሰሚ ፡ ዐ
ዋቂ ፡ ነውና ።

182 ከተናዛገርም ፡ በኩል ፡ (ከውነት) ፡
መዘንበልን ፡ ወይም ፡ (ከሚስ) ፡
በመጨመር) ፡ ኃጢአትን ፡ ያወ
ቀና ፡ በመካከላቸው ፡ ያስታረቀ ፡
ሰው ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ኃጢአት ፡
የለበትም ፤ አላህ ፡ በጣም ፡ መሐሪ
አዛኝ ፡ ነውና ።

183 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ፡ ጾም ፡
በነዚያ ፡ ከናንተ ፡ በፊት ፡ በነበ
ሩት ፡ (ሕዝቦች) ፡ ላይ ፡ እንደ
ተጻፈ ፡ በናንተም ፡ ላይ ፡ ተጻፈ ፡
(ተደነባ) ፡ ልትጠነቀቁ ፡ ይከጀ
ላልና ።

184 የተቆጠሩን ፡ ቀኖች ፡ (ጹሙ) ፤
ከናንተም ፡ ውስጥ ፡ በሺተኛ ፡
ወይም ፡ በጉዞ ፡ ላይ ፡ የኾነ ፡ ሰው፡
ከሌሎች ፡ ቀኖች ፡ ቍጥሮችን ፡
መጾም ፡ አለበት ፤ በነዚያም ፡
ጾምን ፡ በማይችሉት ፡ ላይ ፡ ቤዛ ፡
ድኻን ፡ ማብላት ፡ አለባቸው ፤
(ቤዛን ፡ በመጨመር) ፡ መልካ
ምንም ፡ ሥራ ፡ የፈቀደ ፡ ሰው ፡
እርሱ ፡ (ፈቅዶ ፡ መጨመሩ) ፡
ለርሱ ፡ በላጭ ፡ ነው ፤ መጾማች
ሁም ፡ ለናንተ ፡ የበለጠ ፡ ነው ፤
የምታውቁ ፡ ብትኾኑ ፡ (ትመር
ጡታላችሁ) ።

185 (እንድትጾሙ ፡ የተጻፈባችሁ) ፡
ያ ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ለሰዎች ፡
መሪ ፡ ከቅን ፡ መንገድና ፡ (ውነ
ትን ፡ ከውሸት) ፡ ከሚለዩም ፡ ገላ
ጮች ፡ (አንቀጾች) ፡ ሲኾን ፡ ቁር
አን ፡ የተወረደበት ፡ የረመዳን ፡
ወር ፡ ነው ፤ ከናንተም ፡ ወሩን ፡
ያገኘ ፡ ሰው ፡ ይጹመው ፤ በሺ
ተኛ ፡ ወይም ፡ በጉዞ ፡ ላይ ፡ የኾ
ነም ፡ ሰው ፡ ከሌሎች ፡ ቀኖች ፡
ቍጥሮችን ፡ (በልኩ) ፡ መጾም ፡
አለበት ፤ አላህ ፡ በናንተ ፡ ገሩን ፡
(ነገር) ፡ ይሻል ፤ በናንተም ፡ ችግ
ሩን ፡ አይሻም ፤ ቍጥሮችንም ፡
ልትሞሉ ፡ አላህንም ፡ ቅኑን ፡ መን
ገድ ፡ ስለመራችሁ ፡ ታከብሩ
ትና ፡ ታመሰግኑት ፡ ዘንድ ፡ (ይህ
ንን ፡ ደነገግንላችሁ) ።

186 ባሮቼም ፡ ከኔ ፡ በጠየቁህ ፡ ጊዜ ፡
(እንዲህ ፡ በላቸው) ፡— እኔ ፡
ቅርብ ፡ ነኝ ፤ የለማኝን ፡ ጸሎት ፡
በለመነኝ ፡ ጊዜ ፡ እቀበለዋለሁ ፤
ስለዚህ ፡ ለኔ ፡ ይታዘዙ ፤ በኔም ፡
ይመኑ ፤ እነሱ ፡ ሊመሩ ፡ ይከጀ
ላልና ።

187 በጾም ፡ ሌሊት ፡ ወደ ፡ ሴቶቻችሁ፡
መድረስ ፡ ለናንተ ፡ ተፈቀደላ
ችሁ ፤ እነርሱ ፡ ለናንተ ፡ ልብ
ሶች ፡ ናቸው ፤ እናንተም ፡ ለነ
ርሱ ፡ ልብሶች ፡ ናችሁ ፤ አላህ ፡
እናንተ ፡ ነፍሶቻችሁን ፡ የምትበ
ድሉ ፡ መኾናችሁን ፡ ዐወቀ ፤
በናንተም ፡ ላይ ፡ ተመለሰላ
ችሁ ፤ (1) ከናንተም ፡ ይቅርታ ፡
አደረገ ፤ አሁን ፡ ተገናኙዋቸው ፤
አላህም ፡ ለናንተ ፡ የጻፈላችሁን ፡
ነገር ፡ (ልጅን) ፡ ፈልጉ ፤ ከጎህ ፡
የኾነው ፡ ነጭ ፡ ክርም ፡ ከጥቁሩ ፡
ክር ፡ (ከሌሊት ፡ ጨለማ) ፡ ለና
ንተ ፡ እስከሚገልጽላችሁ ፡ ድረስ፡
ብሉ ፤ ጠጡም ፤ ከዚያም ፡ ጾምን ፡
እስከሌሊቱ ፡ ድረስ ፡ ሙሉ ፤
እላንተም ፡ በመስጊዶች ፡ ተቀማ
ጮች ፡ ስትኾኑ ፡ አትገናኙዋቸው፤
ይህች ፡ የአላህ ፡ ሕግጋት ፡ ናትና ፡
(ለመተላለፍ) ፡ አትቅረቧት ፤ እን

1 ጸጸታችሁን ፡ ተቀበለ ።

ደዚሁ ፡ አላህ ፡ አንቀጾቹን ፡ ለሰ
ዎች ፡ ያብራራል ፤ እነርሱ ፡ (የተ
ከለከሉትን) ፡ ሊጠንቀቁ ፡ ይከጀ
ላልና ፡

188 ገንዘቦቻችሁንም ፡ በመካከላችሁ ፡
በከንቱ ፡ (ያለ ፡ አግባብ) ፡ አት
ብሉ ፤ እናንተም ፡ የምታውቁ ፡
ስትኾኑ ፡ ከሰዎች ፡ ገንዘቦች ፡
ከፊልን ፡ በኃጢአት ፡ ትበሉ ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ ዳኞች ፡ አትጣሏት ።

189 (ሙሐመድ ፡ ሆይ !) ከለጋ ፡ ጨረ
ቃች ፡ (መለዋወጥ) ፡ ይጠይቁሃል ፡
እነርሱ ፡ ለሰዎች ፡ ጥቅም ፡ ለሐ
ጅም ፡ (ማወቂያ) ፡ ጊዜያቶች ፡
(ምልክቶች) ፡ ናቸው ፡ በላቸው ፤
መልካም ፡ ሥራም ፡ ቤቶችን ፡
ከጀርባዎቻቸው ፡ በመምጣታችሁ
አይደለም ፤ ግን ፡ የመልካም ፡
ሥራ ፡ ባለቤት ፡ የተጠነቀቀ ፡
ሰው ፡ ነው ፤ ቤቶችንም ፡ ከደጃፎ
ቻቸው ፡ በኩል ፡ ግቧቸው ፤ አላ
ህንም ፡ ፍሩ ፡ ልትድኑ ፡ ይከጀ
ላልና ፡ (በላቸው) ።

190 እነዚያንም ፡ የሚጋደሉዋችሁን ፡
(ከሓዲዎች) ፡ በአላህ ፡ መንገድ ፡
ተጋደሉ ፤ ወሰንንም ፡ አትለፉ ፤
አላህ ፡ ወሰን ፡ አላፊዎችን ፡ አይ
ወድምና ።

191 ባገኛችኋቸውም ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡
ግደሉዋቸው ፤ ከአወጧችሁም ፡
ስፍራ ፡ አውጧቸው ፤ መከራም (1)
ከመግደል ፡ ይበልጥ ፡ የበረታች ፡
ናት ፤ በተከበረው ፡ መስጊድም ፡
ዘንድ ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ እስከሚ
ጋደሉዋችሁ ፡ ድረስ ፡ አትጋደሉ
ዋቸው ፤ ቢጋደሉዋችሁም ፡ ግደ
ሉዋቸው ፤ የከሓዲዎች ፡ ቅጣት ፡
እንደዚህ ፡ ነው ።

1 በክልከሉ፡ ወራት፡ ከአገር፡ መባረር።

192 ቢከለከሉም ፡ አላህ ፡ መሓሪ ፡
አዛኝ ፡ ነው ።

193 እውከት ፡ እስከማይገኝና ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ለአላህ ፡ ብቻ ፡ እስከሚ
ኾን ፡ ድረስ ፡ ተጋደሉዋቸው ፤
ቢከለከሉም ፡ ወሰንን ፡ ማለፍ ፤
በበዳዮች ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡ የለም ፡
(ወሰን ፡ አትለፉባቸው) ።

194 የተከበረው ፡ ወር ፡ በተከበረው ፡
ወር ፡ አንጻር ፡ ነው ፤ ክብሮችም ፡
ሁሉ ፡ ተመሳሳዮች ፡ ናቸው ፤
በናንተም ፡ ላይ ፡ (በተከበረው ፡
ወር) ፡ ወሰን ፡ ያለፈባችሁን ፡
ሰው ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ወሰን ፡ ባለ
ፈው ፡ ብጤ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ወሰን ፡
እለፉበት ፤ አላህንም ፡ ፍሩ ፤
አላህ ፡ ከሚፈሩት ፡ ጋር ፡ መኾ
ኑንም ፡ ዕወቁ ።

195 በአላህም ፡ መንገድ ፡ ለግሱ ፤
በእጆቻችሁም ፡ (ነፍሶቻችሁን) ፡
ወደ ፡ ጥፋት ፡ አትጣሉ ፤ በጎ ፡
ሥራንም ፡ ሥሩ ፤ አላህ ፡ በጎ ፡
ሠሪዎችን ፡ ይወዳልና ።

196 ሐጅንና ፡ ዑምራንም ፡ ለአላህ ፡
ሙሉ፤ ብትታገዱም ፡ ከሀድይ ፡
(ከመሥዋዕት) ፡ የተገራውን ፡
(መሠዋት) ፡ አለባችሁ ፤ ሀድዩም፡
(1) እስፍራው ፡ እስከሚደርስ ፡
ድረስ ፡ ራሶቻችሁን ፡ አትላጩ ፤
ከናንተም ፡ ውስጥ ፡ በሺተኛ ፡
ወይም ፡ በራሱ ፡ እውከት ፡ ያለ
በት ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ (ቢላጭ) ፡
ከጾም ፡ ወይም ፡ ከምጽዋት ፡
ወይም ፡ ከመሥዋዕት ፡ ቤዛ ፡ አለ
በት ፤ ጸጥታም ፡ ባገኛችሁ ፡ ጊዜ ፡
እስከ ፡ ሐጅ ፡ በዑምራ ፡ የተጣ
ቀመ ፡ ሰው ፡ ከሀድይ ፡ የተገራ

1 ሀድይ ፡ ማለት ፡ በካዕባ ፡ ለመሠዋት ፡ የሚ
ነዳ ፡ እንስሳ ፡ ነው ።



ውን ፡ (መሠዋት) ፡ አለበት ፤ ያላ
ገኘም ፡ ሰው ፡ ሦስትን ፡ ቀኖች ፡
በሐጅ ፡ ወራት ፤ ሰባትንም ፡ በተ
መለሳችሁ ፡ ጊዜ ፡ መጾም ፡ አለ
በት ፤ ይህች ፡ ሙሉ ፡ ዐሥር ፡
(ቀናት) ፡ ናት ፤ ይህም ፡ (ሕግ) ፡
ቤተሰቦቹ ፡ ከቅዱሱ፡ መስጊድ ፡
አቅራቢያ ፡ ላልኾኑ ፡ ነው ፤ አላህ
ንም ፡ ፍሩ ፤ አላህም ፡ ቅጣተ ፡
ብርቱ ፡ መኾኑን ፡ ዕወቁ ።

197 ሐጅ ፡ (ጊዜያቱ) ፡ የታወቁ ፡
ወሮች ፡ ናቸው ፤ በነርሱም ፡ ውስ
ጥ ፡ ሐጅን ፡ (እንዲሠራ) ፡ ነፍ
ሱን ፡ ያስገደደ ፡ ሰው ፡ በሐጅ ፡
ውስጥ ፡ ሴትን ፡ መገናኘት ፡ ማመ
ጥም ፡ ክርክርም ፡ የለም ፤ ከበ
ጎም ፡ ሥራ ፡ የምትሠሩትን ፡
ሁሉ ፡ አላህ ፡ ያውቀዋል ፤ ተሰነ
ቁም ፤ ከስንቅም ፡ ሁሉ ፡ በላጩ ፡
ጥንቃቄ ፡ ነው ፤ የአእምሮዎችም ፡
ባለቤቶች ፡ ሆይ ! ፍሩኝ ።

198 (በሐጅ ፡ ጊዜ ፡ በንግድ ፡ ሥራ) ፡
ከጌታችሁ ፡ ትርፍን ፡ በመፈለ
ጋችሁ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ኃጢአት ፡
የለባችሁም ፤ ከዐረፋትም ፡ በጎረ
ፋችሁ ፡ ጊዜ ፡ መሽዐረልሐራም ፡
ዘንድ ፡ አላህን ፡ አውሱ ፤ (ለሐጅ)
ስለመራችሁም ፡ አውሱት ፤ ከመ
ምራቱ ፡ በፊትም ፡ በእርግጥ ፡
ከተሳሳቾች ፡ ነበራችሁ ።

199 ከዚያም ፡ (ቁረይሾች ፡ ሆይ) ፡
ሰዎቹ ፡ ከጎረፉበት ፡ ስፍራ ፡
ጉረፉ ፤ (ተመለሱ) ፤ አላህንም ፡
ምሕረትን ፡ ለምኑ ፤ አላህ ፡ እጅግ፡
መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።

200 የሐጅ ፡ ሥራዎቻችሁንም ፡ በፈጸ
ማችሁ ፡ ጊዜ ፡ አባቶቻችሁን ፡
እንደምታወሱ ፡ ወይም ፡ ይበ
ልጥ ፡ የበረታን ፡ ማውሳት ፡ አላ
ህን ፡ አውሱ ፤ ከሰዎችም ፡ ውስጥ፡
፡- ጌታችን ፡ ሆይ ! በምድረ ፡
ዓለም ፡ መልካም ፡ ዕድልን ፡
ስጠን ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ አልለ ፤
ለርሱም ፡ በመጨረሻይቱ ፡ አገር ፡
ከዕድል ፡ ምንም ፡ የለውም ።

201 ከነርሱም ፡ ውስጥ ፡— ጌታችን ፡
ሆይ ! በምድረ ፡ ዓለም ፡ ደግን ፡
ነገር ፡ (ጸጋን) ፡ በመጨረሻይ
ቱም ፡ አገር ፡ ደግን ፡ ነገር ፡ (ገነ
ትን) ፡ ስጠን ፤ የእሳትንም ፡ ቅጣት
ጠብቀን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ አልሉ፤

202 እነዚያ ፡ ከሠሩት ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡
ለነርሱ ፡ ዕድል ፡ አላቸው ፤ አላ
ህም ፡ ምርመራው ፡ ፈጣን ፡ ነው ።

203 በተቆጠሩ ፡ ቀኖችም ፡ ውስጥ ፡
(በሚና ፡ ጠጠሮችን ፡ ስትወረ
ውሩ) ፡ አላህን ፡ አውሱ ፤ በሁ
ለት ፡ ቀኖችም ፡ ውስጥ ፡ (በመ
ኼድ) ፡ የተቻኮለ ፡ ሰው ፡ በርሱ ፡
ላይ ፡ ኃጢአት ፡ የለበትም ፤ የቆ
የም ፡ ሰው ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ኃጢ
አት ፡ የለበትም ፤ (ይህም) ፡ አላ
ህን ፡ ለፈራ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ አላህ
ንም ፡ ፍሩ ፤ እናንተ ፡ ወደርሱ ፡
የምትሰበሰቡ ፡ መኾናችሁንም ፡
ዕወቁ ።

204 ከሰዎችም ፡ ውስጥ ፡ እርሱ ፡ ክር
ክረ ፡ ብርቱ ፡ ሲኾን ፡ በቅርቢቱ ፡
ሕይወት ፡ ንግግሩ ፡ የሚደንቅህና፡
በልቡ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ነገር ፡
ላይ ፡ አላህን ፡ የሚያስመሰክር ፡
ሰው ፡ አልለ ።

205 (ካንተ) ፡ በዞረም ፡ ጊዜ ፡ በምድር፡
ላይ ፡ በውስጧ ፡ ሊያበላሽና ፡ አዝ
መራንና ፡ እንስሳዎችን ፡ ሊያ
ጠፋ ፡ ይሮጣል ፤ አላህም ፡ ማበ
ላሸትን ፡ አይወድም ።

206 ለርሱ ፡ አላህን ፡ ፍራ ፡ በተባለም ፡ ጊዜ ፤ ትዕቢቱ ፡ በኃጢአት ፡ (ሥራ) ፡ ላይ ፡ ትገፋፋዋለች ፤ ገሀነምም ፡ በቂው ፡ ናት ፤ (እርሷም) ፡ በእርግጥ ፡ የከፋች ፡ ምንጣፍ ፡ ናት ።

207 ከሰዎችም ፡ ውስጥ ፡ የአላህን ፡ ውዴታ ፡ ለመፈለግ ፡ ነፍሱን ፡ የሚሸጥ ፡ ሰው ፡ አልለ ፤ አላህም ፡ ለባሮቹ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ ነው ።

208 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ሁላችሁም ፡ በመታዘዝ ፡ ውስጥ ፡ ግቡ ፤ የሰይጣንንም ፡ እርምጃዎች ፡ አትከተሉ ፤ እርሱ ፡ ለናንተ ግልጽ ፡ ጠላት ፡ ነውና ።

209 ግልጽ ፡ ማስረጃዎችም ፡ ከመጡላችሁ ፡ በኋላ ፡ ብትዘነበሉ ፡ አላህ ፡ አሸናፊ ፡ ጥበበኛ ፡ መኾኑን ፡ ዕወቁ ።

210 አላህ ፡ (ቅጣቱ)ና ፡ መላእክቱ ፡ ከደመና ፡ በኾኑ ፡ ጥላዎች ፡ ውስጥ ፡ ሊመጡዋቸው ፡ እንጂ ፡ አይጠባበቁም ፤ ነገሩም ፡ ተፈጸመ ፤ ነገሮችም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ይመለሳሉ ።

211 የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከግልጽ ፡ ታምር ፡ ስንትን ፡ እንደሰጠናቸው ጠይቃቸው ፤ የአላህንም ፡ ጸጋ ፡ ከመጣችለት ፡ በኋላ ፡ የሚለውጥ ፡ ሰው ፡ አላህ ፡ ቅጣተ ፡ ብርቱ ፡ ነው ።

212 ለነዚያ ፡ ለካዱት ፡ ከነዚያ ፡ ካመኑት ፡ የሚሳለቁ ፡ ሲኾኑ ፡ ቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡ ተሸለመችላቸው ፤ እነዚያም ፡ የተጠነቀቁት ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ከበላያቸው ፡ ናቸው ፤ አላህም ፡ ለሚሻው ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ይሰጣል ።

213 ሰዎቹ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ነበሩ ፤ (ተለያዩ) ፤ አላህም ፡ ነቢያትን ፡ አብሳሪዎችና ፡ አስፈራሪዎች ፡ አድርጎ ፡ ላከ ፤ ከነርሱም ፡ ጋር ፡ መጻሕፍትን ፡ በሰዎቹ ፡ መካከል ፡ በዚያ ፡ በርሱ ፡ በተለያዩበት ፡ ነገር ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ በእውነት ፡ አወረደ ፤ በርሱም ፡ (በሃይማኖት) ፡ ግልጽ ፡ አስረጂዎች ፡ ከመጡላቸው ፡ በኋላ ፡ በመካከላቸው ፡ ለኾነው ፡ ምቀኝነት ፡ እነዚያው ፡ የተሰጡት ፡ እንጅ ፡ አልተለያዩበትም ፤ አላህም ፡ እነዚያን ፡ ያመኑትን ፡ ሰዎች ፡ ለዚያ፡ ከውነት ፡ በርሱ ፡ ለተለያዩበት ፡ በፈቃዱ ፡ መራቸው ፤ አላህም ፡ የሚሻውን ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ቀጥተኛው ፡ መንገድ ፡ ይመራል ።

214 በውነቱ ፡ የነዚያ ፡ ከበፊታችሁ ፡ ያለፉት ፡ (ምእምናን ፡ መከራ) ፡ ብጤ ፡ ሳይመጣባችሁ ፡ ገነትን ፡ ልትገቡ ፡ ታስባላችሁን ? መልክተኛውና ፡ እነዚያ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያመኑት ፡ የአላህ ፡ እርዳታ ፡ መቼ፡ ነው ? እስከሚሉ ፡ ድረስ ፡ መከራና ፡ ጉዳት ፡ ነካቻቸው ፤ ተርበደበዱም ፤ ንቁ ፡ የአላህ ፡ እርዳታ ፡ በእርግጥ ፡ ቅርብ ፡ ነው ፡ (ተባሉም) ።

215 ምንን ፡ (ለማንም) ፡ እንደሚለግሱ ፡ ይጠይቁሃል ፤ ከመልካም ፡ ነገር ፡ የምትለግሱት ፤ ለወላጆችና ፡ ለቅርብ ፡ ዘመዶች ፡ ለየቲሞችም ፡ ለድኾችም ፡ ለመንገደኞችም ፡ ነው ፤ ከበጎ ፡ ነገርም ፡ ማንኛውንም ፡ ብትሠሩ ፡ አላህ ፡ እርሱን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፡ በላቸው ።

216 (ከሓዲዎችን) ፡ መጋደል ፡ እርሱ፡ ለናንተ ፡ የተጠላ ፡ ሲኾን ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ተጻፈ ፤ አንዳች ፡ ነገርን ፡ እርሱ ፡ ለናንተ ፡ የበለጠ ፡ ሲኾን ፡ የምትጠሉት ፡ መኾናችሁ ፡ ተረጋገጠ ፤ አንዳችንም ፡ ነገር ፡ እርሱ ፡ ለናንተ ፡ መጥፎ ፡ ሲኾን ፡ የምትወዱት ፡ መኾናችሁ ፡ ተረጋገጠ ፤ አላህም ፡ (የሚሻላችሁን) ፡ ያውቃል ፤ ግን ፡ እናንተ ፡ አታውቁም ።

217 ከተከበረው ፡ ወር ፡ (ከረጀብ) ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ከመጋደል ፡ ይጠይቁሃል ፤ በላቸው ፡— በርሱ ፡ ውስጥ ፡ መጋደል ፡ ታላቅ ፡ (ኃጢአት) ፡ ነው ፤ ግን ፡ ከአላህ ፡ መንገድ ፡ (ሰዎችን) ፡ መከልከል ፡ በርሱም ፡ መካድ ፡ ከተከበረውም፡ መስጊድ ፡ (ማገድ) ፡ ባለቤቶቹንም ፡ ከርሱ ፡ ማውጣት ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡ ይበልጥ ፡ ታላቅ ፡ (ወንጀል) ፡ ነው ፤ ፈተናም ፡ (ማጋራት) ፡ ከመግደል ፡ ይበልጥ ፡ ከባድ ፡ ነው ፤ (ከሓዲዎች) ፡ ቢችሉ ፡ ከሃይማኖታችሁ ፡ እስከሚመልሳችሁ ፡ ድረስ ፡ የሚዋጉዋችሁ ፡ ከመኾን ፡ አይቦዝኑም ፤ ከናንተ ፡ ውስጥም ፡ ከሃይማኖቱ ፡ የሚመለስና ፡ እርሱም ፡ ከሓዲ ፡ ኾኖ ፡ የሚሞት ፡ ሰው ፡ እነዚያ ፡ (በጎ) ፡ ሥራቸው ፡ በቅርቢቱም ፡ በመጨረሻይቱም ፡ አገር ፡ ተበላሸች ፤ እነዚያ ፡ የእሳት ፡ ጓደኞች ፡ ናቸው ፤ እነርሱ ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ናቸው ።

218 እነዚያ ፡ ያመኑትና ፡ እነዚያም ፡ (ከአገራቸው) ፡ የተሰደዱት ፡ በአላህም ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ የተጋደሉት ፡ እነዚያ ፡ የአላህን ፡ እዝነት ፡ ይከጅላሉ ፤ አላህም ፡ እጅግ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።



219 አእምሮን ፡ ከሚቃወም ፡ መጠጥና ፡ ከቁማር ፡ ይጠይቁሃል ፤ በሁለቱም ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ኃጢአትና ፡ ለሰዎች ፡ ጥቅሞች ፡ አሉባቸው ፤ ግን ፡ ኃጢአታቸው ፡ ከጥቅማቸው ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ነው ፡ በላቸው ፤ ምንን ፡ እንደሚመጸውቱም ፡ (መጠኑን) ፡ ይጠይቁሃል ፤ ትርፍን ፡ (መጽውቱ) ፡ በላቸው ፤ እንደዚሁ ፡ ታስተነትኑ ፡ ዘንድ ፡ አላህ ፡ ለናንተ ፡ አንቀጾችን ፡ ይገልጽላችኋል ።

220 በቅርቢቱ ፡ ዓለምና ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ታስተነትኑ ፡ ዘንድ ፡ (ይገለጽላችኋል) ፤ ከየቲሞችም ፡ ይጠይቁሃል ፤ ለነርሱ ፡ (ገንዘባቸውን ፡ በማራባት) ፡ ማሳመር ፡ በላጭ ፡ ነው ፤ ብትቀላቀሏቸውም፡ ወንድሞቻችሁ ፡ ናቸው ፤ አላህም ፡ የሚያጠፋውን ፡ ከሚያበጀው ፡ (ለይቶ) ፡ ያውቃል ፤ አላህም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ ባስቸገራችሁ ፡ ነበር ፤ አላህ ፡ አሸናፊ ፡ ጥበበኛ ፡ ነውና ፡ በላቸው ።

221 (በአላህ) ፡ አጋሪ ፡ የሆኑ ፡ ሴቶች ፡ እስከሚያምኑ ፡ ድረስ ፡ አታግቡዋቸው ፤ ከአጋሪይቱ ፡ ምንም ፡ ብትደንቃችሁም ፡ እንኳ፡ ያመነችው ፡ ባሪያ ፡ በእርግጥ ፡ በላጭ ፡ ናት ፤ ለአጋሪዎቹም ፡ እስከሚያምኑ ፡ ድረስ ፡ አትዳሩላቸው ፤ ከአጋሪው ፡ (ጌታ) ፡ ምንም ፡ ቢደንቃችሁ ፡ ምእምኑ ፡ ባሪያ ፡ በላጭ ፡ ነው ፤ እነዚያ ፡ (አጋሪዎች) ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ይጠራሉ ፤ አላህም ፡ በፈቃዱ ፡ ወደ ፡ ገነትና ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ይጠራል ፤ ሕግጋቱንም ፡ ለሰዎች ፡ ይገልጻል ፡ እነርሱ ፡ ሊገሠጹ ፡ ይከጀላልና ።

222 ከወር፡ አበባም፡ ይጠይቁሃል፤
እርሱ፡ የተበከለ፡ ነው፤ ሴቶችን
ም፡ በወር፡ አበባ፡ ጊዜ፡ ራቋቸው፤
ንጹሕ ፡ እስከሚኾኑም ፡ ድረስ ፡
አትቅረቡዋቸው ፤ ንጹሕ ፡ በኾ
ኑም ፡ ጊዜ ፡ አላህ ፡ካዘዛችሁ ፡
ስፍራ ፡ ተገናኙዋቸው ፤ አላህ ፡
(ከኃጢአት) ፡ ተመላሾችን ፡ ይወ
ዳል ፤ ተጥራሪዎችንም ፡ ይወ
ዳል ፡ በላቸው ።

223 ሴቶቻችሁ ፡ ለናንተ ፡ እርሻ ፡
ናቸው ፤ እርሻችሁንም ፡ በፈለጋ
ችሁት ፡ ኹነታ ፡ ድረሱ ፤ ለነፍሶ
ቻችሁም ፡ (መልካም ፡ ሥራን) ፡
አስቀድሙ ፤ አላህንም ፡ ፍሩ ፤
እናንተም ፡ ተገናኝዎቹ ፡ መኾና
ችሁን ፡ ዕወቁ ፤ ምእመናንንም ፡
(በገነት) ፡ አብስር ።

224 መልካም ፡ እንዳትሠሩ ፡ አላህ
ንም ፡ እንዳትፈሩ ፡ በሰዎችም ፡
መካከል ፡ እንዳታስታርቁ ፡ አላ
ህን ፡ ለመሐሎቻችሁ ፡ ግርዶ ፡
አታድርጉ ፤ አላህም ፡ ሰሚ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።

225 በመሐሎቻችሁ ፡ በውድቁ ፡ (ሳታ
ስቡ ፡ በምትምሉት) ፡ አላህ ፡ አይ
ይዛችሁም ፤ ግን ፡ ልቦቻችሁ ፡
ባሰቡት ፡ ይይዛችኋል ፤ አላህም ፡
በጣም ፡ መሓሪ ፡ ታጋሽ ፡ ነው ።

226 ለነዚያ ፡ ከሴቶቻቸው ፡ (ላይቀ
ርቡ) ፡ ለሚምሉት ፡ አራትን ፡
ወሮች ፡ መጠበቅ፡ አለባቸው፤
(ከመሐላቸው) ፡ ቢመለሱም ፡
አላህ ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።

227 መፍታትንም ፡ ቁርጥ ፡ አሳብ ፡
ቢያደርጉ ፡ (ይፍቱ) ፤ አላህም ፡
ሰሚ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

228 የተፈቱ ፡ ሴቶችም ፡ ነፍሶቻቸ
ውን ፡ (ከማግባት) ፡ ሦስትን ፡
ቁርእ ፡ (1) ይጠብቁ ፤ በአላህና ፡
በመጨረሻውም ፡ ቀን ፡ የሚያ
ምኑ ፡ ቢኾኑ ፡ አላህ ፡ በማሕፀኖ
ቻቸው ፡ ውስጥ ፡ የፈጠረውን ፡
ሊደብቁ ፡ ለነርሱ ፡ አይፈቀድላ
ቸውም ፤ ባሎቻቸውም ፡ በዚህ ፡
ውስጥ ፡ እርቅን ፡ ቢፈልጉ ፡ በመ
ማለሳቸው ፡ ተገቢዎች ፡ ናቸው ፤
ለነርሱም ፡ (ለሴቶች) ፡ የዚያ ፡
በነርሱ ፡ ላይ ፡ ያለባቸው ፡ (ግዴ)
ብጤ ፡ በመልካም ፡ አኗኗር ፡
(በባሎቻቸው ፡ ላይ ፡ መብት) ፡
አላቸው ፤ ለወንዶችም ፡ (ጣጣቸ
ውን ፡ ስለሚሸከሙ) ፡ በነሱ ፡
ላይ ፡ ብልጫ ፡ አላቸው ፤ አላ
ህም ፡ አሸናፊ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።

229 ፍች ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤ (ከዚህ ፡
በኋላ) ፡ በመልካም ፡ መያዝ ፡
ወይም ፡ በበጎ ፡ አኳኋን ፡ ማሰና
በት ፡ ነው ፤ የአላህንም ፡ ሕግ
ጋት ፡ አለመጠበቃቸውን ፡ ካላ
ወቁ ፡ በስተቀር ፡ ከሰጣችኋቸው ፡
ነገር ፡ ምንንም ፡ ልትወስዱ ፡
ለናንተ ፡ (ለባሎች) ፡ አይፈቅድላ
ችሁም ፤ የአላህንም ፡ ሕግጋት ፡
አለመጠበቃቸውን ፡ ብታውቁ ፡
በርሱ ፡ (ነፍሷን) ፡ በተበዠችበት ፡
ነገር ፡ በሁለቱም ፡ ላይ ፡ ኃጢ
አት ፡ የለም ፤ ይህች ፡ የአላህ ፡
ሕግጋት ፡ ናት ፤ አትተላለፏትም ፤
የአላህንም ፡ ሕግጋት ፡ የሚተላ
ለፉ ፡ እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ በዳዮች ፡
ናቸው ።

230 (ሦስተኛ) ፡ ቢፈታትም ፡ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ሌላን ፡ ባል ፡ እስከምታ

1 ሦስት፡ የወር፡ አበባ፡ ወይም፡ ሦስት፡ የወር፡
አበባ፡ ጥራት።



ገባ ፡ ድረስ ፡ ለርሱ ፡ አትፈቀድ
ለትም ፤ (ሁለተኛው ፡ ባል) ፡ ቢፈ
ታትም ፡ የአላህን ፡ ሕግጋት ፡
መጠበቃቸውን ፡ ቢያውቁ ፡ በመ
ማለሳቸው ፡ በሁለቱም ፡ ላይ ፡
ኃጢአት ፡ የለባቸውም ፤ ይህ
ችም ፡ የአላህ ፡ ሕግጋት ፡ ናት ፡
ለሚያውቁ ፡ ሕዝቦች ፡ ያብራራ
ታል ።

231 ሴቶችን ፡ በፈታችሁና ፡ (የዒዳ) ፡
ጊዜያቸውን ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ (1)
በመልካም ፡ ያዙዋቸው ፤ (ተማለ
ሷቸው) ፤ ወይም ፡ በመልካም ፡
ኹነታ ፡ አሰናብቱዋቸው ፤ ለመጉ
ዳትም ፡ ወሰን ፡ ታልፉባቸው ፡
ዘንድ ፡ አትያዙዋቸው ፤ ይህን
ንም ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ ነፍሱን ፡
በእርግጥ ፡ በደለ ፤ የአላህንም ፡
አንቀጾች ፡ ማላገጫ ፡ አድርጋ
ችሁ ፡ አትያዙ ፤ የአላህንም ፡
ጸጋ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ያደረገውን ፡
ከመጽሐፍና ፡ ከጥበብም ፡ በርሱ ፡
የሚገሥጻችሁ ፡ ሲኾን ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ ያወረደውን ፡ አስታውሱ ፤
አላህንም ፡ ፍሩ ፤ አላህም ፡ ነገ
ሩን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ መኾኑን ፡
ዕወቁ ።

232 ሴቶችንም ፡ በፈታችሁና ፡ ጊዜ
ያቸውን ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በመካ
ከላቸው ፡ በሕግ ፡ በተዋደዱ ፡
ጊዜ ፡ ባሎቻቸውን ፡ ከማግባት ፡
አታስተንጉሏቸው ፡ ይህ ፡ (መከ
ልከል) ፡ ከናንተ ፡ በአላህና ፡ በመ
ጨረሻው ፡ ቀን ፡ የሚያምን ፡
ሰው ፡ በርሱ ፡ ይገሠጽበታል ፤
ይሄችሁ ፡ ለናንተ ፡ በላጭ ፡ ነው ፤
(ከመጠርጠር) ፡ አጥሪም ፡ ነው ፤
አላህም ፡ ያውቃል ፤ እናንተ ፡ ግን፡
አታውቁም ።

233 እናቶችም ፡ ልጆቻቸውን ፡ ሙሉ ፡
የኾኑን ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡
ያጥቡ ፤ (ይህም) ፡ ማጥባትን ፡
መሙላት ፡ ለሻ ፡ ሰው ፡ ነው ፤
ለርሱም ፡ በተወለደለት ፡ (አባት)፡
ላይ ፡ ምግባቸውና ፡ ልብሳቸው ፡
በችሎታው ፡ ልክ ፡ አለበት ፤
ነፍስ ፡ ችሎታዋን ፡ እንጂ ፡ አትገ
ደድም ፤ ወላጂት ፡ (እናት) ፡ በል
ጅዋ ፡ ምክንያት ፡ ለርሱ ፡ የተወ
ለደለትም ፡ (አባት) ፡ በልጁ ፡
ምክንያት ፡ አይጉዳዱ ፤ በወራ
ሽም ፡ ላይ ፡ እንደዚሁ ፡ ብጤ ፡
(1) አለበት ፤ (ወላጆቹ) ፡ ከሁለ
ቱም ፡ በኾነ ፡ መዋደድና ፡ መመ
ካከር ፡ (ልጁን ፡ ከጡት) ፡ መነ
ጠልን ፡ ቢፈልጉ ፡ በሁለቱም ፡
ላይ ፡ ኃጢአት ፡ የለባቸውም ፤
ልጆቻችሁንም ፡ ለሌሎች ፡ አጥ
ቢዎች ፡ ማስጠባትን ፡ ብትፈ
ልጉ ፡ ልትሰጡ ፡ የሻችሁትን ፡
በመልካም ፡ ኹነታ ፡ በሰጣችሁ ፡
ጊዜ ፡ (በማስጠባታችሁ) ፡ በና
ንተ ፡ ላይ ፡ ኃጢአት ፡ የለባች
ሁም ፤ አላህንም ፡ ፍሩ ፤ አላህም ፡
የምትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ተመል
ካች ፡ መኾኑን ፡ ዕወቁ ፡

234 እነዚያም ፡ ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ የሚ
ሞቱና ፡ ሚስቶችን ፡ የሚተዉ ፡
(ሚስቶቻቸው) ፡ በነፍሶቻቸው ፡
አራት ፡ ወሮች ፡ ከዐሥር ፡ (ቀናት፡
ከጋብቻ) ፡ ይታገሡ ፤ ጊዜያቸ
ውንም ፡ በጨረሱ ፡ ጊዜ ፡ በነፍ
ሶቻቸው ፡ በታወቀ ፡ ሕግ ፡ በሠ
ሩት ፡ ነገር ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ኃጢ

1 ለመጨረስ ፡ በተቃረቡ ፡ ጊዜ ።

1 መመገብና ፡ ማልበስ ።

አት ፡ የለባችሁም ፤ አላህም ፡
በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ውስጥ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ፡

235 ሴቶችንም ፡ ከማጨት ፡ በርሱ ፡
ባሸሞራችሁበት ፡ ወይም ፡ በነፍ
ሶቻችሁ ፡ ውስጥ ፡ (ለማግባት) ፡
በደበቃችሁት ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
ኃጢአት ፡ የለባችሁም ፡ አላህ ፡
እናንተ ፡ በእርግጥ ፡ የምታስታ
ውሷቸው ፡ መኾናችሁን ፡ ዐወቀ ፤
(ስለዚህ ፡ ማሸሞርንና ፡ ማሰብን ፡
ፈቀደላችሁ) ፤ ግን ፡ በሕግ ፡ የታ
ወቀን ፡ ንግግር ፡ የምትነጋገሩ ፡
ካልኾናችሁ ፡ በስተቀር ፤ ምስጢ
ርን ፡ (ጋብቻን) ፡ አትቃጠሩዋ
ቸው ፤ የተጻፈውም ፡ (ዒዳህ) ፡
ጊዜውን ፡ እስከሚደርስ ፡ ድረስ ፡
ጋብቻን ፡ ለመዋዋል ፡ ቁርጥ ፡
ሐሳብ ፡ አታድርጉ ፤ አላህም ፡
በነፍሶቻችሁ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡
የሚያውቅ ፡ መኾኑን ፡ ዕወቁ ፤
ተጠንቀቁትም ፤ አላህም ፡ መሐሪ፡
ታጋሽ ፡ መኾኑን ፡ ዕወቁ ።

236 ሴቶችን፡ ሳትነኳቸው፡ (ሳትገናኙ)፥
ወይም፡ ለነሱ፡ መህርን፡ ሳትወስኑላ
ቸው፥ ብትፈቷቸው፡ በናንተ፡ ላይ፡
ኃጢአት፡ የለባችሁም፤ (ዳረጐት፡
በመስጠት፡ መፍታት፡ ትችላላች
ሁ)፡ ጥቀሟቸውም፤ በሀብታም፡
ላይ፡ ችሎታው፡ በድኻም፡ ላይ፡ ችሎ
ታው፡ (አቅሙ፡ የሚፈቅደውን፡
መስጠት)፡ አለበት፤ በልካም፡ የኾ
ነን፡ መጥቀም፡ በበጐ፡ ሠሪዎች፡
ላይ የተረጋገጠን፤ (ጥቀሟቸው)።

237 ለነርሱም ፡ መወሰንን ፡ በእርግጥ ፡
የወሰናችሁላቸው ፡ ስትኾኑ ፡
ሳትነኳቸው ፡ በፊት ፡ ብትፈቷ
ቸው ፡ ካልማሩዋችሁ ፡ ወይም ፡
ያ ፡ የጋብቻው ፡ ውል ፡ በእጁ ፡
የኾነው ፡ (ባልየው) ፡ ካልማረ ፡
በስተቀር ፡ የወሰናችሁት ፡ ግማሹ ፡
አላቸው ፤ ምሕረትም ፡ ማድረጋ
ችሁ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ፍራቻ ፡ በ
ጣም ፡ የቀረበ ፡ ነው ፤ በመካከላ
ችሁም ፡ ችሮታን ፡ አትርሱ ፤ አ
ላህ ፡ የምትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ተመ
ልካች ፡ ነውና ።

238 በሶላቶች ፡ (በተለይ) ፡ በመካከለ
ኛይቱም ፡ ሶላት ፡ ላይ ፡ ተጠባ
በቁ ፤ ታዛዦች ፡ ኾናችሁም ፡ ለአ
ላህ ፡ ቁሙ ።

239 ብትፈሩም ፡ እግረኞች ፡ ወይም ፡
ጋላቢዎች ፡ ኾናችሁ ፡ (ስገዱ) ፡
ጸጥተኞችም ፡ በኾናችሁ ፡ ጊዜ ፡
ታውቁት ፡ ያልነበራችሁትን ፡
እንደ ፡ አሳወቃችሁ ፡ አላህን ፡
አውሱ ፡ (ስገዱ) ።

240 እነዚያ ፡ ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ የሚ
ሞቱ ፡ (1) ሚስቶችንም ፡ የሚ
ተዉ ፤ ለሚስቶቻቸው ፡ (ከቤታ
ቸው) ፡ የማይወጡ ፡ ሲኾኑ ፡
ዓመት ፡ ድረስ ፡ መጠቀምን ፡
ኑዛዜን ፡ (ይናዘዙ) ፤ በፈቃዳቸው ፡
ቢወጡም ፡ በሕግ ፡ ከታወቀው ፡
ነገር ፡ በነፍሶቻቸው ፡ በሠሩት ፡
በናንተ ፡ (በሟቹ ፡ ዘመዶች) ፡
ላይ ፡ ኃጢአት ፡ የለባችሁም ፡
አላህም ፡ አሸናፊ ፡ ጥበበኛ ፡
ነው ። (2)

241 ለተፈቱ ፡ ሴቶችም ፡ በችሎታ ፡
መጠን ፡ ዳረጐት ፡ አላቸው ፤ አላ
ህን ፡ በሚፈሩ ፡ ላይ ፡ ተደንግ
ጓል ።

1 ለመሞት ፡ የቀረቡ ።

2 ይህ ፡ አንቀጽ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ 234
አንቀጽና ፡ በምዕራፍ ፡ 4 ፡ አንቀጽ ፡ 12
ተሽሮአል ።



242 እንደዚሁ ፡ አላህ ፡ አንቀጾቹን ፡
ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ለናንተ ፡ ያብራ
ራላችኋል ።

243 ወደ ፡ እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ ብዙ ፡
ሺሕ ፡ ኾነው ፡ ሞትን ፡ ለመፍ
ራት ፡ ከሀገሮቻቸው ፡ ወደ ፡
ወጡት ፡ ሰዎች ፡ ዕውቀትህ ፡ አል
ደረሰምን ? አላህም ፡ ለነርሱ ፡
ሙቱ ፡ አላቸው ፤ (ሞቱም) ፤ ከዚ
ያም ፡ ሕያው ፡ አደረጋቸው ፤
አላህም ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ባለ ፡
ችሮታ ፡ ነው ፤ ግን ፡ አብዛኞዎቹ ፡
ሰዎች ፡ አያመሰግኑም ።

244 በአላህም ፡ መንገድ ፡ (ሃይማ
ኖት) ፡ ተጋደሉ ፤ አላህም ፡ ሰሚ ፡
ዐዋቂ ፡ መኾኑን ፡ ዕወቁ ።

245 ያ ፡ ለአላህ ፡ መልካም ፡ ብድርን ፡
የሚያበድርና ፡ ለርሱ ፡ (አላህ) ፡
ብዙ ፡ እጥፎች ፡ አድርጎ ፡ የሚያ
ነባብርለት ፡ ማነው ? አላህም ፡
ይጨብጣል ፤ ይዘረጋልም ፤ ወደ ፡
እርሱም ፡ ትመለሳላችሁ ።

246 ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከሙሳ ፡
በኋላ ፡ ወደ ፡ ነበሩት ፡ ጭፍሮች ፡
ለነቢያቸው ፡ (ለሳሙኤል) ፡—
ለኛ ፡ ንጉሥን ፡ አስነሳልን ፡ በአ
ላህ ፡ መንገድ ፡ እንዋጋለን ፤ ባሉ ፡
ጊዜ ፡ አላየህምን ? (አላወቅህ
ምን ?) ፡— መዋጋት ፡ ቢጻፍባ
ችሁ ፡ አትዋጉም ፡ ይኾናል ፡ አላ
ቸው ፤ ከሀገሮቻችንና ፡ ከልጆ
ቻችን ፡ የተባረርን ፡ ስንኾን ፡
በአላህ ፡ መንገድ ፡ የማንዋጋ ፡
ለኛ ፡ ምን ፡ አለን ? አሉ ፤ በነርሱ ፡
ላይ ፡ መዋጋት ፡ በተጻፈባቸውም ፡
ጊዜ ፡ ከነርሱ ፡ ጥቂቶች ፡ ሲቀሩ ፡
አፈገፈጉ ፤ አላህም ፡ በዳዮቹን ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።

247 ነቢያቸውም ፡ ለነርሱ ፡— አላህ ፡
ጧሉትን ፡ (ሳኦልን) ፡ ንጉሥ ፡ አድ
ርጎ ፡ በእርግጥ ፡ ላከላችሁ ፡ አላ
ቸው ፤ (እነርሱም) ፡— እኛ ፡ ከእ
ርሱ ፡ ይልቅ ፡ በንግሥና ፡ ተገቢ
ዎች ፡ ስንኾን ፡ ከሀብትም ፡ ስፋ
ትን ፡ ያልተሰጠ ፡ ሲኾን ፡ ለርሱ ፡
በኛ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ንግሥና ፡
ይኖረዋል ? አሉ ፤ (ነቢያቸውም)፡
፡— አላህ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ መረ
ጠው ፤ በዕውቀትና ፡ በአካልም ፡
ስፋትን ፡ ጨመረለት ፤ አላህም ፡
ንግሥናውን ፡ ለሚሻው ፡ ሰው ፡
ይሰጣል ፤ አላህም ፡ ችሮታው ፡
ሰፊ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፡ አላቸው ።

248 ነቢያቸውም ፡ ለነርሱ ፡— የንግ
ሥናው ፡ ምልክት ፡ ከጌታችሁ ፡
የኾነ ፡ እርጋታ ፡ የሙሳ ፡ ቤተሰ
ብና ፡ የሃሩን ፡ ቤተሰብ ፡ ከተው
ትም ፡ ቅርስ ፡ በውስጡ ፡ ያለበት ፡
መላእክት ፡ የሚሸከሙት ፡ ኾኖ ፡
ሳጥኑ ፡ ሊመጣላችሁ ፡ ነው ፤ አማ
ኞች ፡ ብትኾኑ ፡ በዚህ ፡ ለናንተ ፡
እርግጠኛ ፡ ምልክት ፡ አለለ ፡
አላቸው ።

249 ጧሉትም ፡ በሠራዊቱ ፡ (ታጅቦ) ፡
በወጣ ፡ ጊዜ ፡— አላህ ፡ በወንዝ ፡
(ውሃ) ፡ ፈታኛችሁ ፡ ነው ፡ ከር
ሱም ፡ የጠጣ ፡ ሰው ፡ ከእኔ ፡ አይ
ደለም ፤ ያልቀመሰውም ፡ ሰው ፡
በእጁ ፡ መዝገንን ፡ የዘገነ ፡ ሰው ፡
ብቻ ፡ ሲቀር ፡ እርሱ ፡ ከኔ ፡ ነው ፡
አለ ፤ ከነርሱም ፡ ጥቂቶች ፡ ሲቀሩ
ከርሱ ፡ ጠጡ ፤ እርሱና ፡ እነዚ
ያም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያመኑት ፡
(ወንዙን) ፡ ባለፉት ፡ ጊዜ ፡—
ጃሉትንና ፡ ሠራዊቱን ፡ በመዋ
ጋት ፡ ለኛ ፡ ዛሬ ፡ ችሎታ ፡ የለ
ንም ፡ አሉት ፤ እነዚያ ፡ እነርሱ ፡

አላህን ፡ ተገናኝዎች ፡ መኾናቸ
ውን ፡ የሚያረጋግጡት ፡— ከጥ
ቂት ፡ ጭፍራ ፡ በአላህ ፡ ፈቃድ ፡
ብዙን ፡ ጭፍራ ፡ ያሸነፈች ፡
ብዙ ፡ ናት ፤ አላህም ፡ ከታጋሾች ፡
ጋር ፡ ነው ፡ አሉ ።
250 ለጃሉትና ፡ ለሠራዊቱ ፡ በተሰለ
ፉም ፡ ጊዜ ፡— ጌታችን ፡ ሆይ !
በእኛ ፡ ላይ ፡ ትእግሥትን ፡ አን-
ቧቧ ፤ ጫማዎቻችንንም ፡ አደላ
ድል ፤ በከሓዲያን ፡ ሕዝቦችም ፡
ላይ ፡ እርዳን ፡ አሉ ።
251 በአላህም ፡ ፈቃድ ፡ ድል ፡ መቷ
ቸው ፤ ዳውድም ፡ ጃሉትን ፡ (1)
ገደለ ፤ ንግሥናንና ፡ ጥበብንም ፡
(ነቢይነትን) ፡ አላህ ፡ ሰጠው ፤
ከሚሻውም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አሳ
ወቀው ፤ አላህም ፡ ሰዎችን ፡ ከፊ
ላቸውን ፡ በከፊሉ ፡ መመለሱ ፡
ባልነበረ ፡ ኖሮ ፡ ምድር ፡ በተበ
ላሸች ፡ ነበር ፤ ግን ፡ አላህ ፡ በዓለ
ማት ፡ ላይ ፡ የችሮታ ፡ ባለቤት ፡
ነው ።
252 እነዚህ ፡ (አንቀጾች) ፡ በውነት ፡
በአንተ ፡ ላይ ፡ የምናነባቸው ፡
ሲኾኑ ፡ የአላህ ፡ አንቀጾች ፡
ናቸው ፤ አንተም ፡ በእርግጥ ፡
ከመልክተኞቹ ፡ ነህ ።

★ ★ ★

253 እነዚህን ፡ መልክተኞች ፡ ከፊላቸ
ውን ፡ በከፊሉ ፡ ላይ ፡ አበለጥን ፤
ከነርሱ ፡ ውስጥ ፡ አላህ ፡ ያነጋ
ገረው ፡ አልለ ፤ ከፊሎቻቸውንም ፡
በደረጃዎች ፡ ከፍ ፡ አደረገ ፤ የመ
ርየምን ፡ ልጅ ፡ ዒሳንም ፡ ግልጽ ፡
ታምራቶችን ፡ ሰጠነው ፤ በቅ
ዱሱ ፡ መንፈስም ፡ አበረታነው ፤
አላህም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ እነዚያ ፡
ከነርሱ ፡ (ከመልክተኞቹ) ፡ በኋላ ፡
የነበሩት ፡ ግልጽ ፡ ታምራቶች ፡
ከመጡላቸው ፡ በኋላ ፡ ባልተጋ
ደሉ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ተለያዩ ፤
ከነርሱም ፡ ውስጥ ፡ ያመነ ፡ ሰው ፡
አልለ ፤ ከነርሱም ፡ ውስጥ ፡ የካደ ፡
ሰው ፡ አልለ ፤ አላህም ፡ በሻ ፡
ኖሮ ፡ ባልተዋጉ ፡ (ባልተለያዩ) ፡
ነበር ፤ ግን ፡ አላህ ፡ የሚሻውን ፡
ይሠራል ።
254 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! በርሱ ፡
ውስጥ ፡ ሽያጭ ፡ (መበዠት) ፡ ወዳጅ
ነትም ፡ ምልጃም ፡ የሌለበት ፡ ቀን ፡
ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ ከሰጠና
ችሁ ፡ ነገር ፡ ለግሱ ፤ ከሓዲዎ
ችም ፡ በዳዮቹ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ።
255 አላህ ፡ ከእርሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡
አምላክ ፡ የለም ፤ ሕያው ፡ ራሱን ፡
ቻይ ፡ ነው ፤ ማንገላጀትም ፡ እን
ቅልፍም ፡ አትይዘውም ፤ በሰማ
ያት ፡ ውስጥና ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡
ያለው ፡ ሁሉ ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤
ያ ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡ በፈቃዱ ፡
ቢኾን ፡ እንጅ ፡ የሚያማልድ ፡
ማነው ? (ከፍጡሮች) ፡ በፊታ
ቸው ፡ ያለውንና ፡ ከኋላቸው ፡
ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል ፤ በሻ
ውም ፡ ነገር ፡ እንጂ ፡ ከዕውቀቱ ፡
በምንም ፡ ነገር ፡ አያካብቡም ፡
(አያውቁም) ፤ መንበሩ ፡ ሰማያ
ትንና ፡ ምድርን ፡ ሰፋ ፤ ጥበቃ
ቸውም ፡ አያቅተውም ፤ እርሱም ፡
የሁሉ ፡ በላይ ፡ ታላቅ ፡ ነው ።
256 በሃይማኖት ፡ ማስገደድ ፡ የለም ፤
ቅኑ ፡ መንገድ ፡ ከጠማማው ፡
በእርግጥ ፡ ተገለጠ ፤ በጣዖትም ፡
የሚክድና ፡ በአላህ ፡ የሚያምን ፡
ሰው ፡ ለርሷ ፡ መበጠስ ፡ የሌላ

1 ዳዊት ፡ ጐልያድን ።



ትን ፡ ጠንካራ ፡ ዘለበት ፡ በእር
ግጥ ፡ ጨበጠ ፤ አላህም ፡ ሰሚ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።
257 አላህ ፡ የእነዚያ ፡ ያመኑት ፡ ሰዎች
ረዳት ፡ ነው ፤ ከጨለማዎች ፡
ወደ ፡ ብርሃን ፡ ያወጣቸዋል ፤ እነ
ዚያም ፡ የካዱት ፡ ረዳቶቻቸው ፡
ጣዖታት ፡ ናቸው ፤ ከብርሃን ፡
ወደ ፡ ጨለማዎች ፡ ያወጧቸዋል ፤
እነዚያ ፡ የእሳት ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ፤
እነርሱ ፡ በውስጧ ፡ ዘውታሪዎች ፡
ናቸው ።
258 ወደ ፡ ዚያ ፡ አላህ ፡ ንግሥናን ፡ ስለ
ሰጠው ፡ ኢብራሂምን ፡ በጌታው ፡
ነገር ፡ ወደ ፡ ተከራከረው ፡ ሰው ፡
(1) አላየህምን ? ኢብራሂም ፡—
ጌታዬ ፡ ያ ፡ ሕያው ፡ የሚያደር
ግና ፡ የሚገድል ፡ ነው ፡ ባለ ፡
ጊዜ ፡ እኔ ፡ ሕያው ፡ አደርጋለሁ ፡
እገድላለሁም ፡ አለ ፤ ኢብራሂም ፡
፡— አላህ ፡ ፀሐይን ፡ ከምሥራቅ ፡
በኩል ፡ ያመጣል ፡ (አንተ) ፡ ከም
ዕራብ ፡ በኩል ፡ አምጣት ፡ አለው ፤
ያም ፡ የካደው ፡ ሰው ፡ ዋለለ ፤
(መልስ ፡ አጣ) ፡ አላህም ፡ በዳ
ዮች ፡ ሕዝቦችን ፡ አይመራም ።
259 ወይም ፡ ያንን ፡ በከተማ ፡ ላይ ፡
እርሷ ፡ በጣራዎችዋ ፡ ላይ ፡ የወ
ደቀች ፡ ስትኾን ፡ ያለፈውን ፡
ሰው ፡ ብጤ ፡ (አላየህምን ?) ፡—
ይህችን ፡ (ከተማ) ፡ ከሞተች ፡
በኋላ ፡ አላህ ፡ እንዴት ፡ ሕያው ፡
ያደርጋታል ? አለ ፤ አላህም ፡ ገደ
ለው ፡ መቶ ፡ ዓመትን ፡ (አቆየ
ውም) ፤ ከዚያም ፡ አስነሳው ፡—
ምን ፡ ያህል ፡ ቆየህ ? አለው ፤
አንድን ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ የቀንን ፡
ከፊል ፡ ቆየሁ ፡ አለ ፤ አይደለም ፡
መቶን ፡ ዓመት ፡ ቆየህ ፤ ወደ ፡
ምግብህና ፡ ወደ ፡ መጠጥህም ፡
ያልተለወጠ ፡ ሲኾን ፡ ተመል
ከት ፤ ወደ ፡ አህያህም ፡ ተመል
ከት ፤ ለሰዎችም ፡ አስረጅ ፡ እናደ
ርግህ ፡ ዘንድ ፡ (ይህንን ፡ ሠራን) ፤
ወደ ፡ ዐፅሞቹም ፡ እንዴት ፡ እን
ደምናስነሳት ፡ ከዚያም ፡ ሥጋን ፡
እንደምናለብሳት ፡ ተመልከት ፡
አለው ፤ ለርሱም ፡ (በማየት) ፡
በተገለጸለት ፡ ጊዜ ፡— አላህ ፡
በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ መኾ
ኑን ፡ ዐውቃለሁ ፡ አለ ።
260 ኢብራሂምም ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ !
ሙታንን ፡ እንዴት ፡ ሕያው ፡ እን
ደምታደርግ ፡ አሳየኝ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ ፤ አላህ) ፡— አላመን
ክምን ? አለው ፤ አይደለም ፡ (አም
ኛለሁ) ፤ ግን ፡ ልቤ ፡ እንዲረጋ ፡
ነው ፡ አለ ፤ (አላህም) ፡— ከበራ
ሪዎች ፡ (ከወፎች) ፡ አራትን ፡
ያዝ ፤ ወደ ፡ አንተም ፡ ሰብስባ
ቸው ፤ (ቆራርጣቸውም) ፤ ከዚ
ያም ፡ በየኮረብታው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ከነርሱ ፡ ቁራጭን ፡ አድርግ ፤ ከዚ
ያም ፡ ጥራቸው ፤ ፈጥነው ፡ ይመ
ጡሃልና ፤ አላህም ፡ አሸናፊ ፡ ጥበ
በኛ ፡ መኾኑን ፡ ዕወቅ ፡ አለው ።
261 የእነዚያ ፡ ገንዘቦቻቸውን ፡ በአ
ላህ ፡ መንገድ ፡ የሚለግሱ ፡ ሰዎች
(ልግስና) ፡ ምሳሌ ፡ በየዘለላው ፡
ሁሉ ፡ መቶ ፡ ቅንጣት ፡ ያለባቸ
ውን ፡ ሰባት ፡ ዘለላዎች ፡ እንደ ፡
አበቀለች ፡ እንዲት ፡ ቅንጣት ፡
ብጤ ፡ ነው ፤ አላህም ፡ ለሚሻው ፡
ሰው ፡ (ከዚህ ፡ በላይ) ፡ ያነባብ
ራል ፤ አላህም ፡ ችሮታው ፡ ሰፊ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።

1 ወደ ፡ ኑምሩድ ፡ ወይም ፡ ሐሙራቢ ።

262 እነዚያ ፡ ገንዘቦቻቸውን ፡ በአላህ፡ መንገድ ፡ የሚለግሱ ፡ ከዚያም ፡ የሰጡትን ፡ ነገር ፡ መመጣደቅንና ፡ ማስከፋትን ፡ የማያስከትሉ ፡ ለነርሱ ፡ በጌታቸው ፡ ዘንድ ፡ ምንዳቸው ፡ አላቸው ፤ በነርሱም ፡ ላይ ፡ ፍርሃት ፡ የለባቸውም ፤ እነርሱም ፡ አያዝኑም ።

263 መልካም ፡ ንግግርና ፡ ምሕረት ፡ ማድረግ ፡ ማስከፋት ፡ ከሚከተላት ፡ ምጽዋት ፡ በላጭ ፡ ነው ፤ አላህም ፡ ተብቃቂ ፡ ታጋሽ ፡ ነው ።

264 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! እንደዚያ ፡ ገንዘቡን ፡ ለሰዎች ፡ ማሳየት ፡ ሲል ፡ እንደሚሰጠውና ፡ በአላህና ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ እንደማያምነው ፡ ሰው ፡ ምጽዋቶቻችሁን ፡ በመመጣደቅና ፡ በማስከፋት ፡ አታበላሹ ፤ ምሳሌውም፡ በላዩ ፡ ዐፈር ፡ እንዳለበት ፡ ለንጣ ፡ ደንጊያ ፡ ኀይለኛም ፡ ዝናም ፡ እንዳገኘውና ፡ ምልጥ ፡ አድርጎ ፡ እንደተወው ፡ ብጤ ፡ ነው ፤ ከሠሩት ፡ ነገር ፡ በምንም ፡ ላይ ፡ (ሊጠቀሙ) ፡ አይችሉም ፤ አላህም ፡ ከሓዲያንን ፡ ሕዝቦች ፡ አይመራም ።

265 የእነዚያም ፡ የአላህን ፡ ውዴታ ፡ ለመፈለግና ፡ ከነፍሶቻቸው ፡ (እምነትን) ፡ ለማረጋገጥ ፡ ገንዘቦቻቸውን ፡ የሚለግሱ ፡ ሰዎች ፡ ምሳሌ ፡ በተስተካከለች ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ እንዳለች ፡ አትክልት ፡ ብዙ ፡ ዝናም ፡ እንደነካት ፡ ፍሬዋንም ፡ እጥፍ ፡ ኾና ፡ እንደሰጠች ፡ ዝናብም ፡ ባይነካት ፡ ካፊያ ፡ እንደሚበቃት ፡ ብጤ ፡ ነው ፤ አላህም ፡ የምትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ተመልካች ፡ ነው ።

266 (ከናንተ) ፡ አንዳችሁ ፡ ለርሱ ፡ ከዘምባባና ፡ ከወይኖች ፡ በሥርዋ ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱባት ፡ አትክልት ፡ ልትኖረው ፡ በውስጧም ፡ ለርሱ ፡ ከየፍሬው ፡ ሁሉ ፡ ሊኖረው ፡ እርጅናም ፡ ሊነካውና ፡ ለርሱ ፡ ደካማዎች ፡ ዝርያዎች ፡ ያሉት ፡ ሲኾን ፡ በውስጡ ፡ እሳት፡ ያለበት ፡ ውርጭ ፡ ሊያገኛትና ፡ ልትቃጠል ፡ ይወዳልን ? እንደዚሁ ፡ አላህ ፡ አንቀጾችን ፡ ለናንተ ፡ ያብራራል ፤ ልታስተነትኑ ፡ ይከጅላልና ።

267 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ካፈራችሁትና ፡ ከዚያም ፡ ለናንተ ፡ ከምድር ፡ ካወጣንላችሁ ፡ ከመልካሙ ፡ ለግሱ ፤ መጥፎውንም ፡ (ለመስጠት) ፡ አትሰቡ ፤ በርሱ ፡ ዓይኖቻችሁን ፡ ጨፍናችሁ ፡ እንጂ ፡ የማትወስዱት ፡ ስትኾኑ ፡ ከርሱ ፡ (ከመጥፎው) ፡ ትሰጣላችሁን ? አላህም ፡ ተብቃቂ ፡ ምስጉን ፡ መኾኑን ፡ ዕወቁ ።

268 ሰይጣን ፡ (እንዳትለግሱ) ፡ ድኽነትን ፡ ያስፈራራችኋል ፤ በመጥፎም ፡ ያዛችኋል ፤ አላህም ፡ ከርሱ፡ የኾነን ፡ ምሕረትና ፡ ችሮታን ፡ ይቀጥራችኋል ፤ አላህም ፡ ችሮታው ፡ ሰፊ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

269 ለሚሻው ፡ ሰው ፡ ጥበብን ፡ ይሰጣል ፤ ጥበብንም ፡ የሚሰሰጥ ፡ ሰው ፡ ብዙን ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ በእርግጥ ፡ ተሰጠ ፤ የአእምሮዎች ፡ ባለቤቶች ፡ እንጂ ፡ (ሌላው) ፡ አይገሠጽም ።

270 ከምጽዋትም ፡ ማንኛውንም ፡ የለገሳችሁትን ፡ ወይም ፡ ከስእለት ፡ የተሳላችሁትን ፡ አላህ ፡ ያውቀዋል ፤ ለበዳዮችም ፡ ከረዳቶች ፡ ምንም ፡ የላቸውም ።

271 ምጽዋቶችን ፡ ብትገልጹ ፡ እርሷ፡ ምንኛ ፡ መልካም ፡ ናት ፤ ብትደብቋትና ፡ ለድኾች ፡ ብትሰጧትም ፡ እርሱ ፡ ለናንተ ፡ በላጭ ፡ ነው ። ከኀጢአቶቻችሁም ፡ ከናንተ ፡ ያብሳል ፤ አላህም ፡ በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

272 እነርሱን ፡ ማቅናት ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ የለብህም ፤ ግን ፡ አላህ ፡ የሚሻውን ፡ ሰው ፡ ያቀናል ፤ ከገንዘብም ፡ የምትለግሱት ፡ (ምንዳው)፡ ለነፍሶቻችሁ ፡ ነው ፤ የአላህንም ፡ ፊት ፡ (ውዴታውን) ፡ ለመፈለግ ፡ እንጂ ፡ አትለግሱም ፡ ከገንዘብም ፡ የምትለግሱት ፡ ሁሉ ፡ (ምንዳው)፡ ወደናንተ ፡ ይሞላል ፤ እናንተም ፡ አትበደሉም ።

273 (የምትመጸውቱት) ፡ ለነዚያ ፡ በአላህ ፡ መንገድ ፡ (ለመታገል ፡ ሲሉ) ፡ ለታገዱት ፡ ድኾች ፡ ነው ፤ በምድር ፡ መኼድን ፡ አይችሉም ፤ (ልመናን) ፡ ከመጥጠበቃቸው ፡ (የተነሳ) ፡ የማያውቅ ፡ ሰው ፡ ሀብታሞች ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ይጠረጥራቸዋል ፤ በምልክታቸው ፡ ታውቃቸዋለህ ፤ ሰዎችን ፡ በችክታ ፡ አይለምኑም ፤ ከገንዘብም ፡ የምትለግሱት ፡ አላህ ፡ እርሱን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

274 እነዚያ ፡ ገንዘቦቻቸውን ፡ በሌሊትና ፡ በቀን ፡ በድብቅም ፡ በግልጽም ፡ የሚለግሱ ፡ ለነርሱ ፡ በጌታቸው ፡ ዘንድ ፡ ምንዳቸው ፡ አላቸው ፤ በነርሱም ፡ ላይ ፡ ፍርሃት ፡ የለባቸውም ፡ እነርሱም ፡ አያዝኑም ።

275 እነዚያ ፡ አራጣን ፡ የሚበሉ ፡ ያ ፡ ሰይጣን ፡ ከመንካቱ ፡ የተነሳ ፡ የሚጥለው ፡ ሰው ፡ (ከአውድቁ) ፡ እንደሚነሳ ፡ ብጤ ፡ እንጅ ፡ (ከመቃብራቸው) ፡ አይነሱም ፤ ይህ ፡ እነርሱ ፡ መሸጥ ፡ የአራጣ ፡ ብጤ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በማለታቸው ፡ ነው ፤ ግን ፡ መሸጥን ፡ አላህ ፡ ፈቅዷል፤ አራጣንም ፡ እርም ፡ አድርጓል ፤ ከጌታውም ፡ ግሣጼ ፡ የመጣለትና ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡ (ከመከልከሉ ፡ በፊት) ፡ ያለፈው ፡ አለው ፤ ነገሩም ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ነው ፤ (አራጣን ፡ ወደ ፡ መብላት) ፡ የተመለሰም ፡ ሰው ፡ እነዚያ ፡ የእሳት ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ፤ እነርሱ ፡ በውስጧ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ናቸው ።

276 አላህ ፡ አራጣን ፡ (በረከቱን) ፡ ያጠፋል ፤ ምጽዋቶችንም ፡ ያፋፋል ፤ አላህም ፡ ኃጢአተኛ ፡ ከሓዲን ፡ ሁሉ ፡ አይወድም ።

277 እነዚያ ፡ ያመኑ ፡ መልካም ፡ ሥራዎችንም ፡ የሠሩ ፡ ሶላትንም ፡ ያስተካከሉ ፡ ዘካንም ፡ የሰጡ ፡ ለነርሱ ፡ በጌታቸው ፡ ዘንድ ፡ ምንዳቸው ፡ አላቸው ፤ በነርሱም ፡ ላይ ፡ ፍርሃት ፡ የለባቸውም ፡ እነርሱም ፡ አያዝኑም ።

278 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላህን ፡ ፍሩ ፤ ከአራጣም ፡ የቀረውን ፡ ተዉ ፤ አማኞች ፡ እንደኾናችሁ ፡ (ተጠንቀቁ) ።

279 (የታዘዛችሁትን) ፡ ባትሠሩም ፡ ከአላህና ፡ ከመልክተኛው ፡ በኾነች ፡ ጦር ፡ (መወጋታችሁን) ፡ ዕወቁ ፤ ብትጸጸቱም ፡ ለናንተ ፡ የገንዘቦቻችሁ ፡ ዋናዎች ፡ አሏችሁ ፤ አትበድሉም ፡ አትበደሉም ።

280 የድኽነት ፡ ባለቤት ፡ የኾነም ፡ (ባለዕዳ) ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ እማግኘት ፡ ድረስ ፡ ማቆየት ፡ ነው ፤ (በመማር) ፡ መመጽወታችሁም ፡ ለናንተ ፡ በላጭ ፡ ነው ፤ የምታውቁ ፡ ብትኾኑ ፡ (ትሠሩታላችሁ) ።

281 በርሱም ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ የምትመለሱበትንና ፡ ከዚያም ፡ እነርሱ ፡ የማይበደሉ ሲሆኑ ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ የሠራችውን ፡ ሥራ ፡ የምትሞላበትን ፡ ቀን ፡ ተጠንቀቁ ።

282 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! እስከ ፡ ተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በዕዳ ፡ በተዋዋላችሁ ፡ ጊዜ ፡ ጻፉት ፤ ጸሐፊም ፡ በመካከላችሁ ፡ በትክክል ፡ ይጻፍ ፤ ጸሐፊም ፡ አላህ ፡ እንደ ፡ አሳወቀው ፡ መጻፍን ፡ እንቢ ፡ አይበል ፤ ይጻፍም ፤ ያም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ዕዳው ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ በቃሉ ፡ ያስጽፍ ፤ አላህንም ፡ ጌታውን ፡ ይፍራ ፤ ከርሱም ፡ (ካለበት ፡ ዕዳ) ፡ ምንንም ፡ አያጉድል ፤ ያም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ዕዳው ፡ ያለበት ፡ ቂል ፡ ወይም ፡ ደካማ ፡ ወይም ፡ በቃሉ ፡ ማስጣፍን ፡ የማይችል ፡ ቢኾን ፡ ዋቢው ፡ በትክክል ፡ ያስጥፍለት ፤ ከወንዶቻችሁም ፡ ሁለትን ፡ ምስክሮች ፡ አስመስክሩ ፤ ሁለትም ፡ ወንዶች ፡ ባይኾኑ ፡ ከምስክሮች ፡ ሲኾኑ ፡ ከምትወዱዋቸው ፡ የኾኑን ፡ አንድ ወንድና ፡ አንደኛዋ ፡ ስትረሳ ፡ አንደኛይቱ ፡ ሌላዋን ፡ ታስታውሳት ፡ ዘንድ ፡ ሁለት ፡ ሴቶች ፡ (ይመስክሩ) ፤ ምስክሮችም ፡ በተጠሩ ፡ ጊዜ ፡ እምቢ ፡ አይበሉ ፤ (ዕዳው) ፡ ትንሽ ፡ ወይም ፡ ትልቅ ፡ ቢኾንም ፡ እስከ ፡ ጊዜው ፡ ድረስ ፡ የምትጽፉት ፡ ከመኾን ፡ አትሰልቹ ፤ ይኻችሁ ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ ትክክል ፡ ለምስክርነትም ፡ አረጋጋጭ ፡ ላለመጠራጠራችሁም ፡ በጣም ፡ ቅርብ ፡ ነው ፡ ግን ፡ በመካከላችሁ ፡ እጅ ፡ በጅ ፡ የምትቀባበሏት ፡ ንግድ ፡ ብትኾን ፡ ባትጽፉዋት ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ኃጢአት ፡ የለባችሁም ፡ በተሻሻጣችሁም ፡ ጊዜ ፡ አስመስክሩ ፤ ጸሐፊም ፡ ምስክርም ፡ (ባለጉዳዩ ፡ ጋር) ፡ አይጐዳዱ ፤ (ይህንን) ፡ ብትሠሩም ፡ እርሱ ፡ በናንተ ፡ (የሚጠጋ) ፡ አመጥ ፡ ነው ፤ አላህንም ፡ ፍሩ ፤ አላህም ፡ ያሳውቃችኋል ፤ አላህም ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

283 በጉዞም ፡ ላይ ፡ ብትኾኑና ፡ ጸሐፊን ፡ ባታገኙ ፡ የተጨበጡ ፡ መተማመኛዎችን ፡ ያዙ ፤ ከፊላችሁም ፡ ከፊሉን ፡ ቢያምን ፡ ያ ፡ የታመነው ፡ ሰው ፡ አደራውን ፡ ያድርስ ፤ አላህንም ፡ ጌታውን ፡ ይፍራ ፤ ምስክርነትንም ፡ አትደብቁ ፤ የሚደብቃትም ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡ ልቡ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ነው ። አላህም ፡ የምትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

284 በሰማያት ፡ ውስጥና ፡ በምድርም ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ የአላህ ፡ ነው ። በነፍሶቻችሁ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ብትገልጹ ፡ ወይም ፡ ብትደብቁት ፡ አላህ ፡ በርሱ ፡ ይቆጣጠራችኋል ፤ ለሚሻውም ፡ ሰው ፡ ይምራል ፤ የሚሻውንም ፡ ሰው ፡ ይቀጣል ፤ አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ።

285 መልክተኛው ፡ ከጌታው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ በተወረደው ፡ አመነ ፤ ምእምኖቹም ፡ (እንደዚሁ) ፤ ሁሉም ፡



በአላህ ፡ በመላእክቱም ፡ በመጻሕፍቱም ፡ በመልክተኞቹም ፡ ከመልክተኞቹ ፡ በአንድም ፡ መካከል ፡ አንለይም ፡ (የሚሉ ፡ ሲኾኑ) ፡ አመኑ ፤ ሰማን ፤ ታዘዝንም ፤ ጌታችን ፡ ሆይ ! ምሕረትህን ፡ (እንሻለን) ፤ መመለሻም ፡ ወዳንተ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ አሉም ።

286 አላህ ፡ ነፍስን ፡ ከችሎታዋ ፡ በላይ ፡ አያስገድዳትም ፤ ለርስዋ ፡ የሠራቸው ፡ አላት ። በርስዋም ፡ ላይ ፡ ያፈራቺው ፡ (ኃጢአት) ፡ አለባት ። (በሉ) ፡— ጌታችን ፡ ሆይ ! ብንረሳ ፡ ወይም ፡ ብንስት ፡ አትያዘን ፤ (አትቅጣን) ፤ ጌታችን ፡ ሆይ ! ከባድ ፡ ሸክምን ፡ ከእኛ ፡ በፊት ፡ በነበሩት ፡ ላይ ፡ እንደ ጫንከው ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ አትጫንብን ፤ ጌታችን ፡ ሆይ ! ለኛም ፡ በርሱ ፡ ችሎታ ፡ የሌለንን ፡ ነገር ፡ አታሸክመን ፤ ከኛም ፡ ይቅርታ ፡ አድርግ ፤ ለኛም ፡ ምሕረት ፡ አድርግ ፤ እዘንልንም ፤ ዋቢያችን ፡ አንተ ፡ ነህና ፤ በከሓዲዎች ፡ ሕዝቦች ፡ ላይም ፡ እርዳን ።

## ምዕራፍ ፡ 3 አሊ-ዒምራን ። ክፍል ፡ 3 ።

**3ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አሊ-ዒምራን ፡ (የዒምራን ፡ ቤተሰብ ፡ ምዕራፍ) ፤ በመዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) 200 ናቸው ።**

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 አ. ለ. መ. (አሊፍ ፡ ላም ፡ ሚም) ፤ (1)

2 አላህ ፡ ከሱ ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ (እሱ) ፡ ሕያው ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ አስተናባሪ ፡ ነው ።

3 ከርሱ ፡ በፊት ፡ ያሉትን ፡ መጻሕፍት ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ሲኾን ፡ መጽሐፉን ፡ (ቁርአንን) ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ከፋፍሎ ፡ በውነት ፡ አወረደ ። ተውራትንና ፡ ኢንጂልንም ፡ (2) አውርዷል ።

4 (ከቁርአን) ፡ በፊት ፡ ለሰዎች ፡ መሪ ፡ አድርጎ ፡ (አወረዳቸው) ፤ ፉርቃንንም ፡ አወረደ ፤ እነዚያ ፡ በአላህ ፡ ታምራቶች ፡ የካዱ ፡ ለነርሱ ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ፤ አላህም ፡ አሸናፊ ፡ የመበቀል ፡ ባለቤት ፡ ነው ።

5 አላህ ፡ በምድርም ፡ በሰማይም ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አይሰወርም ።

6 እርሱ ፡ ያ ፡ በማሕፀኖች ፡ ውስጥ ፡ እንደሚሻ ፡ አድርጎ ፡ የሚቀርጻችሁ ፡ ነው ። ከርሱ ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ አሸናፊው ፡ ጥበበኛው ፡ ነው ።

7 እርሱ ፡ ያ ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ መጽ

1 ፍቹን ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ ተመልከት ።
2 ኦሪትንና ፡ ወንጌልን ።

ሐፉን ፡ ያወረደ ፡ ነው ፤ ከርሱ ፡
(ከመጽሐፉ) ፡ ግልጽ ፡ የኾኑ ፡
አንቀጾች ፡ አሉሉ ፤ እነሱ ፡ የመ
ጽሐፉ ፡ መሠረቶች ፡ ናቸው ፤
ሌሎችም ፡ ተመሳሳዮች ፡ አሉሉ ፤
እነዚያማ ፡ በልቦቻቸው ፡ ውስጥ ፡
ጥመት ፡ ያለባቸው ፡ ሰዎች ፡ ማሳ
ሳትን ፡ ለመፈለግና ፡ ትችቱን ፡
ለመፈለግ ፡ ከርሱ ፡ የተመሳሰለ
ውን ፡ ይከታተላሉ ። (ትክክለኛ) ፡
ትችቱንም ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡ እንጅ ፡
ሌላ ፡ አያውቀውም ። በዕውቀ
ትም ፡ የጠለቁት ፡ በርሱ ፡ አምነ
ናል ፤ ሁሉም ፡ ከጌታችን ፡ ዘንድ ፡
ነው ፡ ይላሉ ። የአእምሮ ፡ ባለቤ
ቶችም ፡ እንጅ ፡ (ሌላው) ፡ አይገ
ሠጽም ።

8 (እነሱም ፡ ይላሉ) ፡— ጌታችን ፡
ሆይ ! ቅኑን ፡ መንገድ ፡ ከመራ
ኸን ፡ በኋላ ፡ ልቦቻችንን ፡ አታ
ዘምብልብን ፤ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡
የኾነን ፡ ችሮታም ፡ ለኛ ፡ ስጠን ፤
አንተ ፡ በጣም ፡ ለጋስ ፡ ነህና ።

9 ጌታችን ፡ ሆይ ! አንተ ፡ (ለመም
ጣቱ) ፡ በርሱ ፡ ጥርጥር ፡ የሌለ
በት ፡ በኾነ ፡ ቀን ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡
ሰብሳቢ ፡ ነህ ፡ ምንጊዜም ፡ አላህ ፡
ቀጠሮውን ፡ አያፈርስምና ።

10 እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡ ገንዘቦ
ቻቸውና ፡ ልጆቻቸው ፡ ከአላህ ፡
(ቅጣት) ፡ ምንም ፡ አያስጥሉዋቸ
ውም ፤ እነዚያም ፡ እነርሱ ፡ የእ
ሳት ፡ ማገዶዎች ፡ ናቸው ።

11 (ልማዳቸው ፡ ሁሉ) ፡ እንደ ፡ ፈር
ዖን ፡ ቤተሰብና ፡ እንደነዚያ ፡
ከበፊታቸው ፡ እንደነበሩት ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ልማድ ፡ ነው ፤ በአንቀጾቻ
ችን ፡ አስተባበሉ ፤ አላህም ፡ በኃ
ጢአቶቻቸው ፡ ያዛቸው ፤ አላ
ህም ፡ ቅጣተ ፡ ብርቱ ፡ ነው ።

12 ለነዚያ ፡ ለካዱት ፡ ሰዎች ፡ በላ
ቸው ፡— በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ትሸነፋ
ላችሁ ፤ ወደ ፡ ገሀነምም ፡ ትሰበሰ
ባላችሁ ፤ ምንጣፊቱም ፡ ምን ፡
ትከፉ !

13 (የበድር ፡ ቀን) ፡ በተጋጠሙት ፡
ሁለት ፡ ጭፍሮች ፡ ለናንተ ፡ በእ
ርግጥ ፡ ታአምር ፡ አለ ፤ አንደኛዋ፡
ጭፍራ ፡ በአላህ ፡ መንገድ ፡ ትጋ
ደላለች ፤ ሌላይቱም ፡ ከሓዲ ፡
ናት ፡ ከሓዲዎቹ ፡ (አማኞቹን) ፡
በዓይን ፡ አስተያየት ፡ እጥፋቸ
ውን ፡ ኾነው ፡ ያዩዋቸዋል ፤ አላ
ህም ፡ በርዳታው ፡ የሚሻውን ፡
ሰው ፡ ያበረታል ፤ በዚህ ፡ ውስጥ ፡
ለማስተዋል ፡ ባለቤቶች ፡ በእር
ግጥ ፡ መገሠጫ ፡ አለበት ።

14 ከሴቶች ፡ ከወንዶች ፡ ልጆችም ፡
ከወርቅና ፡ ከብር ፡ ከተከማቹ ፡
ገንዘቦችም ፡ ከተሰማሩ ፡ ፈረሶ
ችም ፡ ከግመል ፡ ከከብትና ፡ ከፍ
የልም ፡ ከአዝመራም ፡ የኾኑ ፡
ፍላጎቶችን ፡ መውደድ ፡ ለሰዎች፡
ተሸለመ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የቅርቢቱ ፡
ሕይወት ፡ መጠቀሚያ ፡ ነው ፤
አላህም ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡ መል
ካም ፡ መመለሻ ፡ (ገነት) ፡ አለ ።

15 ከዚኻቹሁ ፡ የሚበልጥን ፡ ልንገራ
ችሁን ? በላቸው ፡— (እርሱም) ፡
ለነዚያ ፡ ለተጠነቀቁት ፡ ሰዎች ፡
በጌታቸው ፡ ዘንድ ፡ በሥራቸው ፡
ወንዞች ፡ የሚፈሱባቸው ፡ ገነ
ቶች ፡ በውስጧ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ነዋ
ሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ ንጹሕ ፡ የተደ
ረጉ ፡ ሚስቶችም ፡ ከአላህም ፡
የኾነ ፡ ውዴታ፡ አላቸው ፤ አላ



ህም ፡ ባሮቹን ፡ ተመልካች ፡
ነው ።

16 (እነርሱም) ፡ እነዚያ ፡— ጌታ
ችን ፡ ሆይ ! እኛ ፡ አመንን ፤ ኀጢ
አቶቻችንንም ፡ ለኛ ፡ ማር ፤ የእሳ
ትንም ፡ ቅጣት ፡ ጠብቀን ፡ የሚሉ
ናቸው ።

17 ታጋሾች ፡ እውነተኞችም ፡ ታዛ
ዦችም ፡ ለጋሶችና ፡ በሌሊት ፡
መጨረሻዎች ፡ ምሕረትን ፡ ለማ
ኞች ፡ ናቸው ።

18 አላህ ፡ በማስተካከል ፡ የቆመ ፡
(አስተናባሪ) ፡ ሲኾን ፡ ከእርሱ ፡
በስተቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የሌለ ፡
መኾኑን ፡ መሰከረ ፤ መላእክቶ
ችና ፡ የዕውቀት ፡ ባለቤቶችም ፡
(እንደዚሁ ፡ መሰከሩ) ፤ ከርሱ ፡
በስተቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፤
አሸናፊው ፡ ጥበበኛው ፡ ነው ።

19 አላህ ፡ ዘንድ ፡ (የተወደደ) ፡ ሃይ
ማኖት ፡ ኢስላም፡ ብቻ ፡ ነው ፤
እነዚያም ፡ መጽሐፉን ፡ የተሰ
ጡት ፡ ሰዎች ፡ በመካከላቸው ፡
ላለው ፡ ምቀኝነት ፡ ዕውቀቱ ፡
ከመጣላቸው ፡ በኋላ ፡ እንጅ ፡
አልተለያዩም ፤ በአላህም ፡ አን
ቀጾች ፡ የሚክድ ፡ አላህ ፡ ምርመ
ራው ፡ ፈጣን ፡ ነው ።

20 ቢከራከሩህም ፡— ፊቴን ፡ ለአ
ላህ ፡ ሰጠሁ ፤ የተከተሉኝም ፡
ሰዎች ፡ (እንደዚሁ ፡ ለአላህ ፡
ሰጡ) ፡ በላቸው ፤ ለእነዚያም ፡
መጽሐፍን ፡ ለተሰጡት ፡ ሰዎ
ችና ፡ ለመሀይሞቹ ፡— ሰለማች
ሁን ? በላቸው ፤ ቢሰልሙም ፡
በእርግጥ ፡ ተመሩ ፤ እምቢ ፡ ቢሉ
ም ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ ያለብህ ፡ ማድ
ረስ ፡ ብቻ ፡ ነው ። አላህም ፡ ባሮ
ቹን ፡ ተመልካች ፡ ነው ።

21 እነዚያ ፡ በአላህ ፡ አንቀጾች ፡ የሚ
ክዱ ፡ ነቢያትንም ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡
የሚገድሉ ፡ ከሰዎችም ፡ ውስጥ ፡
እነዚያን ፡ በትክክለኛነት ፡ የሚ
ያዙትን ፡ የሚገድሉ ፡ በአሳማሚ ፡
ቅጣት ፡ አብስራቸው ።

22 እነዚያ ፡ በቅርቢቱና ፡ በመጨረ
ሻይቱ ፡ ዓለም ፡ ሥራዎቻቸው ፡
የተበላሹ ፡ ናቸው ፤ ለእነርሱም ፡
ምንም ፡ ረዳቶች ፡ የሏቸውም ።

23 ወደ ፡ እነዚያ ፡ ከመጽሐፉ ፡ (ትም
ህርት) ፡ ዕድልን ፡ ወደ ፡ ተሰጡት፡
ሰዎች ፡ አላየህምን ? ወደ ፡ አላህ ፡
መጽሐፍ ፡ በመካከላቸው ፡ ይፈ
ርድ ፡ ዘንድ ፡ ይጠራሉ ፤ ከዚያም ፡
ከነሱ ፡ ገሚሶቹ ፡ እነርሱ ፡ (እውነ
ቱን) ፡ የተው ፡ ኾነው ፡ ይሸሻሉ ።

24 ይኸ ፡ እነርሱ ፡ እሳት ፡ የተቆጠሩ፡
ቀናችን ፡ እንጅ ፡ አትነካንም ፡
በማለታቸው ፡ ነው ። በሃይማኖ
ታቸውም ፡ ይቀጣጥፉት ፡ የነበ
ሩት ፡ ነገር ፡ አታለላቸው ።

25 በርሱ ፡ (መምጣት) ፡ ጥርጥር ፡
የሌለበት ፡ በኾነው ፡ ቀን ፡ በሰበ
ሰብናቸውና ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ የሠራ
ችውን ፡ ሥራ ፡ በተሞላች ፡ ጊዜ ፡
እንዴት ፡ ይኾናሉ ? እነርሱም ፡
አይበደሉም ።

26 (ሙሐመድ ፡ ሆይ !) በል ፡— የን
ግሥና ፡ ባለቤት ፡ የኾንክ ፡ አላህ ፡
ሆይ ! ለምትሻው ፡ ሰው ፡ ንግሥ
ናን ፡ ትሰጣለህ ፤ ከምትሻውም ፡
ሰው ፡ ንግሥናን ፡ ትገፍፋለህ ፤
የምትሻውንም ፡ ሰው ፡ ታልቃ
ለህ ፤ የምትሻውንም ፡ ሰው ፡ ታዋ
ርዳለህ ። መልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
በእጅህ ፡ (በችሎታህ) ፡ ነው ፤
አንተ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ቻይ ፡ ነህና ።

27 ሌሊቱን ፡ በቀን ፡ ውስጥ ፡ ታስገ
ባለህ ፤ ቀኑንም ፡ በሌሊቱ ፡ ውስጥ
ታስገባለህ ፤ ሕያውንም ፡ ከሙት ፡
ውስጥ ፡ ታወጣለህ ፤ ሙትንም ፡
ከሕያው ፡ ውስጥ ፡ ታወጣለህ ፡
ለምትሻውም ፡ ሰው ፡ ያለግምት ፡
ትሰጣለህ ።

28 ምእምናን ፡ ከሓዲዎችን ፡ ከምእ
ምናን ፡ ሌላ ፡ ረዳቶች ፡ አድር
ገው ፡ አይያዙ ፤ ይኽንንም ፡ የሚ
ሠራ ፡ ሰው ፡ ከአላህ ፡ (ሃይማኖት)
በምንም ፡ ውስጥ ፡ አይደለም ፤
ከነርሱ ፡ መጠበቅን ፡ ብትጠበቁ ፡
እንጂ ፤ አላህም ፡ ነፍሱን ፡ (ቁ
ጣውን) ፡ ያስጠነቅቃችኋል ። መ
መለሻም ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡
ነው ።

29 በደረቶቻችሁ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡
ነገር ፡ ብትደብቁ ፡ ወይም ፡ ብት
ገልጹት ፡ አላህ ፡ ያውቀዋል ፤
በሰማያት ፡ ያለውንና ፡ በምድ
ርም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል ።
አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ቻይ ፡ ነው ፡ (በል) ።

30 ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ ከመልካም ፡ ነገር ፡
የሠራችውን ፡ የቀረበ ፡ ኾኖ ፡ የም
ታገኝበትን ፡ ቀን ፡ (አስታውስ) ፤
ከመጥፎም ፡ የሠራችው ፡ በርስ
ዋና ፡ በርሱ ፡ (በኀጢአትዋ) ፡
መካከል ፡ በጣም ፡ የሰፋ ፡ ርቀት ፡
ቢኖር ፡ ትመኛለች ፤ አላህ ፡ ነፍ
ሱን ፡ ያስጠነቅቃችኋል ። አላ
ህም ፡ ለባሮቹ ፡ ርኅሩህ ፡ ነው ።

31 በላቸው ፡— አላህን ፡ የምትወዱ ፡
እንደኾናችሁ ፡ ተከተሉኝ ፤ አላህ ፡
ይወዳችኋልና ፤ ኀጢአቶቻችሁ
ንም ፡ ለናንተ ፡ ይምራልና ፤ አላ
ህም ፡ መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።

32 አላህንና ፡ መልክተኛውን ፡ ታዘዙ
ብትሸሹም ፡ አላህ ፡ ከሓዲዎችን ፡
አይወድም ፡ በላቸው ።

33 አላህ ፡ አደምን ፡ ኑሕንም ፡ የኢብ
ራሂምንም ፡ ቤተሰብ ፡ የዒምራ
ንንም ፡ ቤተሰብ ፡ በዓለማት ፡
ላይ ፡ መረጠ ።

34 ከፊልዋ ፡ ከከፊሉ ፡ የኾነች ፡
ዝርያ ፡ አድርጎ ፡ (መረጣት) ፤
አላህም ፡ ሰሚ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

35 የዒምራን ፡ ባለቤት ፡ (ሐና) ፡—
ጌታዬ ፡ ሆይ ! እኔ ፡ በሆዴ ፡
ውስጥ ፡ ያለውን ፡ (ፅንስ ፡ ከሥራ)
ነጻ ፡ የተደረገ ፡ ሲኾን ፡ ለአንተ ፡
ተሳልኩ ፤ ከኔም ፡ ተቀበል ፤
አንተ ፡ ሰሚው ፡ ዐዋቂው ፡ ነህና ፡
ባለች ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ።

36 በወለደቻትም ፡ ጊዜ ፡— ጌታዬ ፡
ሆይ ! እኔ ፡ ሴት ፡ ኾና ፡ ወለድ
ኋት ፤ አላህም ፡ የወለደችውን ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ፤ ወንድም ፡ እንደ ፡
ሴት ፡ አይደለም ፤ እኔም ፡ መር
የም ፡ ብዬ ፡ ስም ፡ አወጣሁላት ፡
እኔም ፡ እስዋንም ፡ ዝርያዋንም ፡
ከተረገመው ፡ ሰይጣን ፡ በአንተ ፡
እጠብቃቸዋለሁ ፡ አለች ።

37 ጌታዋም ፡ በደህና ፡ አቀባበል ፡
ተቀበላት ፤ በመልካም ፡ አስተዳ
ደግም ፡ አፋፋት ፤ ዘከሪያም ፡ (1)
አሳደጋት ፤ ዘከሪያ ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡
በምኵራቧ ፡ (2) በገባ ፡ ቍጥር ፡
እርስዋ ፡ ዘንድ ፡ሲሳይን ፡ አገኘ ፡-
መርየም ፡ ሆይ ! ይህ ፡ ለአንቺ ፡
ከየት ፡ ነው ? አላት ፤— እርሱ ፡
ከአላህ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ አላህ ፡
ለሚሻው ፡ ሰው ፡ ሲሳዩን ፡ ያለ
ድካም፡ ይሰጣል ፡ አለችው ።

1 ዘካሪያስ ።
2 በመጸለያ ፡ ስፍራዋ ።



38 እዚያ ፡ ዘንድ ፡ ዘከሪያ ፡ ጌታውን ፡
ለመነ ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ! ከአንተ ፡
ዘንድ ፡ መልካም ፡ ዘርን ፡ ለኔ ፡
ስጠኝ ፤ አንተ ፡ ጸሎትን ፡ ሰሚ ፡
ነህና ፡ አለ ።

39 እርሱም ፡ በጸሎት ፡ ማድረሻው ፡
ክፍል ፡ ቆሞ ፡ ሲጸልይ ፡ መላእ
ክት ፡ ጠራችው ። (1) አላህ ፡ በየ
ሕያ ፡ (2) ከአላህ ፡ በኾነ ፡ ቃል ፡
የሚያረጋግጥ ፡ ጌታም ፡ ድንግ
ልም፥ ከደጋጎቹ፡ ነቢይም፡ ሲኾን፡
ያበስርሃል፤ በማለት፥ (መላእክት፡
ጠራችው)።

40 ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ! እኔ ፡ እርጅና ፡
በእርግጥ ፡ የደረሰብኝ ፡ ስኾን ፡
ባልተቤቴም፡ መካን፡ ስትኾን፥ ለኔ፡
እንዴት ፡ ልጅ ፡ ይኖረኛል ? አለ ።
(መልአኩም) ፡ እንደዚሁ ፡ አላህ ፡
የሚሻውን ፡ ነገር ፡ ይሠራል ፡
አለው ፤

41 ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ! ለኔ ፡ ምልክ
ትን ፡ አድርግልኝ ፡ አለ ፤ ምልክ
ትህ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ በጥቅሻ ፡
ቢኾን ፡ እንጅ ፡ ሰዎችን ፡ አለማና
ገርህ ፡ ነው ፤ ጌታህንም ፡ በብዙ ፡
አውሳ ፤ በማታና ፡ በጧትም ፡ አወ
ድሰው ፡ አለው ።

42 መላእክትም ፡ ያሉትን ፡ (አስታ
ውስ) ፡— መርየም ፡ ሆይ ! አላህ ፡
በእርግጥ ፡ መረጠሽ ፡ አነጻሽም ፡
በዓለማት ፡ ሴቶችም ፡ ላይ ፡ መረ
ጠሽ ።

43 መርየም ፡ ሆይ ! ለጌታሽ ፡ ታዘዢ፤
ስገጂም ፤ ከአጐንባሾቹም ፡ ጋር ፡
አጐንብሺ ።

44 ይኽ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ የምናወር
ደው ፡ የኾነ ፡ ከሩቅ ፡ ወሬዎች ፡
ነው ፤ መርየምንም ፡ ማን ፡ እንደ
ሚያሳድግ ፡ ብርዖቻቸውን ፡ (ለዕ
ጣ) ፡ በጣሉ ፡ ጊዜ ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡
አልነበርክም ፤ በሚከራከሩም ፡
ጊዜ ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ አልነበ
ርክም ።

45 መላእክት ፡ ያሉትን ፡ (አስታ
ውስ) ፡— መርየም ፡ ሆይ ! አላህ ፡
ከርሱ ፡ በኾነው ፡ ቃል ፡ ስሙ ፡
አልመሲሕ ፡ ዒሳ ፡ የመርየም ፡
ልጅ ፡ በዚህ ፡ ዓለምና ፡ በመጨረ
ሻውም ፡ ዓለም ፡ የተከበረ ፡ ከባ
ለሟሎችም ፡ በኾነ ፡ (ልጅ) ፡ ያበ
ስርሻል ፤

46 በሕፃንነቱና ፡ በከፈኒሳነቱ ፡ (1)
ሰዎቹን ፡ ያነጋግራል ፤ ከመልካ
ሞቹም ፡ ነው ፡ (አላት) ።

47 ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ! ሰው ፡ ያልነ
ካኝ ፡ ስኾን ፡ ለኔ ፡ እንዴት ፡ ልጅ ፡
ይኖረኛል ? አለች ፤ ነገሩ ፡ እንደ
ዚህሽ ፡ ነው ፤ አላህ ፡ የሚሻውን ፡
ይፈጥራል ፤ አንዳችን ፡ በሻ ፡ ጊዜ ፡
ለርሱ ፡ ኹን ፡ ይለዋል ፤ ወዲያው
ኑም ፡ ይኾናል ፡ አላት ።

48 ጽሕፈትንና ፡ ጥበብንም ፡ ተውራ
ትንና ፡ ኢንጂልንም ፡ ያስተምረ
ዋል ።

49 ወደ ፡ እሥራኤልም ፡ ልጆች ፡
መልክተኛ ፡ ያደርገዋል ፤ (ይላ
ልም) ፡— እኔ ፡ ከጌታዬ ፡ ዘንድ ፡
በታምር ፡ መጣኋችሁ ። እኔ ፡
ለናንተ ፡ ከጭቃ ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡
ቅርጽ ፡ እፈጥራለሁ ፤ በርሱም ፡
እተነፍስበታለሁ ፤ በአላህም ፡
ፈቃድ ፡ ወፍ ፡ ይኾናል ። በአላ
ህም ፡ ፈቃድ ፡ ዕውር ፡ ኾኖ ፡ የተ
ወለደን ፡ ለምጸኛንም ፡ አድናለሁ፤
ሙታንንም ፡ አስነሳለሁ ። የምት

1 ጂብሪል ፡ ጠራው ።
2 ዮሐንስ፡ (መጥመቁ)።

1 የበሰለ ፡ ሰው ፡ ዕድሜው ፡ ከ፴—፶ ፡ የኾነ ።

በሉትንና ፡ በቤታችሁ ፡ የምታደ
ልቡትንም ፡ ሁሉ ፡ እነግራችኋ
ለሁ ፤ የምታምኑ ፡ እንደኾናችሁ ፡
ለእናንተ ፡ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ በእር
ግጥ ፡ ታምር ፡ አለበት ።

50 ከተውራትም ፡ ከኔ ፡ በፊት ፡ ያል
ለውን ፡ ያረጋገጥሁ ፡ ስኾን ፡ የዚ
ያንም ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ እርም ፡
የተደረገውን ፡ ከፊል ፡ ለናንተ ፡
እፈቅድ ፡ ዘንድ ፡ (መጣኋችሁ) ፡
ከጌታችሁም ፡ በኾነ ፡ ታምር ፡
መጣሁዋችሁ ። አላህንም ፡ ፍሩ ፤
ታዘዙኝም ።

51 አላህ ፡ ጌታየና ፡ ጌታችሁ ፡ ነው ፤
ስለዚህ ፡ ተገዙት ፤ ይህ ፡ ቀጥ
ተኛ ፡ መንገድ ፡ ነው ፡ (አላቸው) ።

52 ዒሳ ፡ ከነርሱ ፡ ክሕደት ፡ በተሰ
ማውም ፡ ጊዜ ፡- ወደ ፡ አላህ ፡
(ተጨምረው) ፡ ረዳቶቼ ፡ እነማን፡
ናቸው ? አለ ፤ ሐዋርያት ፡- እኛ ፡
የአላህ ፡ ረዳቶች ፡ ነን ፤ በአላህ ፡
አምነናል ፤ እኛም ፡ ትክክለኛ ፡
ታዛዦች ፡ መኾናችንን፡ መስ
ክር ፡ አሉ ።

53 ጌታችን ፡ ሆይ ! ባወረድኸው ፡
አመንን ፤ መልክተኛውንም ፡
ተከተልን ፤ ከመስካሪዎችም ፡
ጋር ፡ መዝግበን ፡ (አሉ) ።

54 (አይሁዶችም)፡ አደሙ፤ አላ
ህም ፡ አድማቸውን ፡ መለሰባ
ቸው ፤ አላህም ፡ ከአድመኞች ፡
ሁሉ ፡ በላጭ ፡ ነው ።

55 አላህም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ)፤
ዒሳ ፡ ሆይ ! እኔ ፡ ወሳጂህ ፡ ወደ ፡
እኔም ፡ አንሺህ ፡ ነኝ ፤ ከነዚያም ፡
ከካዱት ፡ ሰዎች ፡ አጥሪህ ፡ ነኝ ፤
(1) እነዚያንም ፡ የተከተሉህን ፡
እስከ ፡ ትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡
ከነዚያ ፡ ከካዱት ፡ በላይ ፡ አድ
ራጊ ፡ ነኝ ፤ ከዚያም ፡ መመለሻ
ችሁ ፡ ወደኔ ፡ ነው ፤ በርሱ ፡ ትለ
ያዩበትም ፡ በነበራችሁት ፡ ነገር ፡
በመካከላችሁ ፡ እፈርዳለሁ ።

56 እነዚያማ ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡ በቅ
ርቢቱ ፡ ዓለምና ፡ በመጨረሻ
ይቱ ፡ ዓለም ፡ ብርቱን ፡ ቅጣት ፡
እቀጣቸዋለሁ ፤ ለነርሱም ፡ ምን
ም ፡ ረዳቶች ፡ የሏቸውም ።

57 እነዚያም ፡ ያመኑትማ ፡ መል
ካም ፡ ሥራዎችንም ፡ የሠሩት ፡
ምንዳዎቻቸውን ፡ ይሞላላቸዋል፤
አላህም ፡ በዳዮችን ፡ አይወድም ።

58 ይህ ፡ ከታምራቶችና ፡ ጥበብን ፡
ከያዘው ፡ ተግሣጥ ፡ ሲኾን ፡ በእ
ንተ ፡ ላይ ፡ እናነበዋለን ።

59 አላህ ፡ ዘንድ ፡ የዒሳ ፡ ምሳሌ ፡
እንደ ፡ አዳም ፡ ብጤ ፡ ነው ፤ ከዐ
ፈር ፡ ፈጠረው ፤ ከዚያም ፡ ለርሱ፡
(ሰው) ፡ ኹን ፡ አለው ፡ ኾነም ።

60 ይህ ፡ ከጌታህ ፡ ዘንድ ፡ የኾነ ፡
እውነት ፡ ነው ፤ ከተጠራጣሪዎ
ቹም ፡ አትኹን ።

61 ዕውቀቱም ፡ ከመጣልህ ፡ በኋላ ፡
በርሱ ፡ (በዒሳ) ፡ የተከራከሩህን ፡
ሰዎች ፡— ኑ ፤ ልጆቻችንንና፡ልጆ
ቻችሁን ፤ ሴቶቻችንና ፡ ሴቶቻ
ችሁንም፡ ነፍሶቻችንንና፡ ነፍሶ
ቻችሁንም ፡ እንጥራ ፤ ከዚያም ፡
አጥብቀን ፡ አላህን ፡ እንለምን ፤
የአላህንም ፡ ቁጣ ፡ በውሸታሞቹ፡
ላይ ፡ እናድርግ ፡ በላቸው ።

62 ይህ ፡ እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ እውነ
ተኛ ፡ ታሪክ ፡ ነው ፤ አምላክም ፡
ከአላህ ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡
የለም ። አላህም ፡ እርሱ ፡ በእር

1 ከገርብትናቸው ፡ አራቂህ ፡ ነኝ ።



ግጥ ፡ አሸናፊው ፡ ጥበበኛው ፡
ነው ።

63 (ከማመን) ፡ እንቢ ፡ ቢሉም ፡
አላህ ፡ አጥፊዎቹን ፡ በእርግጥ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።

64 የመጽሐፉ ፡ ባለቤቶች ፡ ሆይ !
በኛና ፡ በናንተ ፡ መካከል ፡ ትክ
ክል ፡ ወደኾነች ፡ ቃል ፡ ኑ ፤ (እር
ሷም) ፡ አላህን ፡ እንጅ ፡ ሌላን ፡
ላንገዛ ፡ በርሱም ፡ ምንንም ፡ ላና
ጋራ ፡ ከፊላችንም ፡ ከፊሉን ፡
ከአላህ ፡ ሌላ ፡ አማልክት ፡ አድ
ርጎ ፡ ላይይዝ ፡ ነው ፤ በላቸው ።
እምቢ ፡ ቢሉም ፡- እኛ ፡ ሙስሊ
ሞች ፡ መኾናችንን ፡ መስክሩ ፡
በሏቸው ።

65 እላንተ ፡ የመጽሐፉ ፡ ሰዎች ፡
ሆይ ! በኢብራሂም ፡ ለምን ፡ ትከ
ራከራላችሁ ? ተውራትና ፡ ኢን
ጂልም ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ እንጅ ፡
አልተወረዱም ፤ ልብ ፡ አታደር
ጉምን ? በላቸው ።

66 ንቁ ፤ እናንተ ፡ እነዚያ ፡ ለናንተ ፡
በርሱ ፡ ዕውቀት ፡ ባላችሁ ፡ ነገር፡
የተከራከራችሁ ፡ ናችሁ ፤ ታዲያ፡
ለናንተ ፡ በርሱ ፡ ዕውቀት ፡ በሌላ
ችሁ ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ ትከራከራ
ላችሁ ? አላህም ፡ ያውቃል ። እና
ንተ ፡ ግን ፡ አታውቁም ።

67 ኢብራሂም ፡ ይሁዳዊም ፡ ክርስ
ቲያንም ፡ አልነበረም ፤ ግን ፡ ወደ፡
ቀጥተኛው ፡ ሃይማኖት ፡ የተዘነ
በለ ፡ ሙስሊም፡ ነበረ ፤ ከአጋሪዎ
ችም ፡ አልነበረም ።

68 ከሰው ፡ ሁሉ ፡ በኢብራሂም ፡
ተገቢዎቹ ፡ እነዚያ ፡ የተከተሉ
ትና ፡ ይህ ፡ ነቢይ ፡ እነዚያም ፡
ያመኑት ፡ ናቸው ፤ አላህም ፡ የም
እምናን ፡ ረዳት ፡ ነው ።

69 ከመጽሐፉ ፡ ባለቤቶች ፡ የኾኑ ፡
ጭፍሮች ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ እንጂ፡
የማያሳስቱ ፡ ሲኾኑ ፡ ሊያሳስቱ
ዋችሁ ፡ ተመኙ ፤ ግን ፡ አያው
ቁም ።

70 የመጽሐፉ ፡ ባለቤቶች ፡ ሆይ !
እናንተ ፡ የምታውቁ ፡ ስትኾኑ ፡
በአላህ ፡ አንቀጾች ፡ ለምን ፡ ትክ
ዳላችሁ ?

71 የመጽሐፉ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! እውነ
ቱን ፡ በውሸት ፡ ለምን ፡ ትቀላቅ
ላላችሁ ? እውነቱንም ፡ እናንተ ፡
የምታውቁ ፡ ስትኾኑ ፡ ለምን ፡
ትደብቃላችሁ ?

72 ከመጽሐፉ ፡ ባለቤቶች ፡ የኾኑ ፡
ጭፍሮችም ፡ አሉ ፡— በነዚያ ፡
በአመኑት ፡ ላይ ፡ በተወረደው ፡
(ቁርአን) ፡ በቀኑ ፡ መጀመሪያ ፡
ላይ ፡ እመኑበት ፤ በመጨረሻ
ውም ፡ ካዱት ፤ እነርሱ ፡ ሊመ
ለሱ ፡ ይከጀላልና ።

73 እናንተ ፡ የተሰጣችሁትን ፡ ብጤ፡
አንድም ፡ ሰው ፡ መሰጠቱን ፡
ወይም ፡ እጌታችሁ ፡ ዘንድ ፡ የሚ
ከራከሩዋችሁ ፡ መኾንን ፡ ሃይማ
ኖታችሁን ፡ ለተከተለ ፡ ሰው ፡
ቢኾን ፡ እንጂ ፡ አትመኑ ፡ (አት
ግለጹ ፡ አሉ) ፤ መምሪያው ፡ የአ
ላህ ፡ መምሪያ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በላ
ቸው ፤ ችሮታ ፡ በአላህ ፡ እጅ ፡
ነው ፡ ለሚሻው ፡ ይሰጠዋል ፤ አላ
ህም ፡ ችሮታው ፡ ሰፊ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ፡ በላቸው ።

74 በችሮታው ፡ (በነቢይነት) ፡ የሚሻ
ውን ፡ ይመርጣል ፡ አላህም ፡
የታላቅ ፡ ችሮታ ፡ ባለቤት ፡ ነው።

75 ከመጽሐፉ ፡ ሰዎችም ፡ በብዙ ፡
ገንዘብ ፡ ብታምነው ፡ ወዳንተ ፡
የሚመልስ፡ ሰው ፡ አልለ ። ከነ

ሱውም ፡ በአንድ ፡ ዲናር፡ እንኳ፡
ብታምነው ፤ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡
ላይ ፡ የምትጠባበቅ ፡ ካልኾንክ ፡
በስተቀር ፡ የማይመልስ ፡ ሰው ፡
አልለ ። ይኸ ፡ በመሃይምናን ፡
(በምናደርገው) ፡ በኛ ፡ ላይ ፡
ምንም ፡ መንገድ ፡ የለብንም ፡
ስለሚሉ ፡ ነው ፤ እነርሱ ፡ እያወ
ቁም ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ውሸትን ፡
ይናገራሉ ።
76 አይደለም ፡ (አለባቸው ፡ እንጅ) ፤
በቃል ፡ ኪዳኑ ፡ የሞላና ፡ የተጠ
ነቀቀ ፡ ሰው ፡ አላህ ፡ ጥንቁቆችን፡
ይወዳል ።
77 እነዚያ ፡ በአላህ ፡ ቃል ፡ ኪዳንና ፡
በመሐላዎቻቸው ፡ ጥቂትን ፡ ዋጋ
የሚለውጡ ፡ እነዚያ ፡ በመጨረ
ሻይቱ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ ዕድል ፡
የላቸውም ፤ በትንሣኤ ፡ ቀንም ፡
አላህ ፡ አያነጋግራቸውም ፤ ወደ
ነርሱም ፡ አይመለከትም ፡ አያነ
ጻቸውምም ፤ ለነሱም ፡ አሳማሚ፡
ቅጣት ፡ አላቸው ።
78 ከነሱም ፡ እርሱ ፡ ከመጽሐፉ ፡
ያይደለ ፡ ሲኾን ፡ ከመጽሐፉ ፡
መኾኑን ፡ እንድታስቡ ፡ በመጽ
ሐፉ ፡ ምላሶቻቸውን ፡ የሚያጣ
ምሙ ፡ ክፍሎች ፡ አልሉ ። እርሱ፡
ከአላህ ፡ ዘንድ ፡ ያልኾነ ፡ ሲኾን፡
እርሱ ፡ ከአላህ ፡ ዘንድ ፡ ነውም ፡
ይላሉ ። እነርሱ ፡ የሚያውቁ ፡
ሲኾኑም ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ውሸ
ትን ፡ ይናገራሉ ።
79 ለማንም ፡ ሰው ፡ አላህ ፡ መጽሐ
ፍንና ፡ ጥበብን ፡ ነቢይነትንም ፡
ሊሰጠውና ፡ ከዚያም ፡ ለሰዎች ፡
ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ለእኔ ፡ ባሮች ፡
ኹኑ ፡ ሊል ፡ አይገባውም ፤ ግን ፡
መጽሐፍን ፡ የምታስተምሩ ፡ በነ
በራችሁትና ፡ የምታጠኑም ፡ በነ
በራችሁት ፡ በዕውቀታችሁ ፡ ሠሪ
ዎች ፡ ኹኑ ፡ (ይላቸዋል) ።
80 መላእክትንና ፡ ነቢያትንም ፡ አማ
ልክቶች ፡ አድርጋችሁ ፡ እንድ
ትይዙ ፡ ሊያዛችሁ ፡ (አይገባ
ውም) ፤ እናንተ ፡ ሙስሊሞች፡ከኾ
ናችሁ ፡ በኋላ ፡ በክሕደት ፡ ያዛ
ችኋልን ?
81 አላህ ፡ የነቢያትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን፡
ከመጽሐፍና ፡ ከጥበብ ፡ ሰጥቻ
ችሁ ፡ ከዚያም ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡
ላለው ፡ (መጽሐፍ) ፡ የሚያረጋ
ግጥ ፡ መልክተኛ ፡ ቢመጣላችሁ፡
በርሱ ፡ በእርግጥ ፡ እንደምታም
ኑበት ፡ በእርግጥም ፡ እንድትረ
ዱት ፡ ሲል ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፡ (አስታ
ውስ) ፤ አረጋገጣችሁን ? በይሃ
ችሁ ፡ ላይ ፡ ኪዳኔን ፡ ያዛችሁ
ምን ? አላቸው ፤ አረጋገጥን ፡ አሉ
እንግዲያስ ፡ መስክሩ ፤ እኔም ፡
ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ከመስካሪዎቹ ፡
ነኝ ፡ አላቸው ።
82 ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የሸሹ ፡ ሰዎች ፡
እነዚያ ፡ እነሱ ፡ አመጠኞቹ ፡
ናቸው ።
83 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ያሉ ፡
ሁሉ ፤ በውድም ፡ በግድም ፡
ለርሱ ፡ የታዘዙ ፡ ወደርሱም ፡
የሚመለሱ ፡ ሲኾኑ ፡ (ከሓዲዎች)
ከአላህ ፡ ሃይማኖት ፡ ሌላን ፡ ይፈ
ልጋሉን ?
84 በአላህ ፡ አመንን ፤ በኛ ፡ ላይ ፡
በተወረደውም ፡ (በቁርአን) ፡
በኢብራሂምና ፡ በኢስማዒልም ፡
በኢስሓቅም ፡ በያዕቆብም ፡ በነገ
ዶችም ፡ ላይ ፡ በተወረደው ፤ ለሙ
ሳና ፡ ለዒሳም ፡ ለነቢያትም ፡
ሁሉ ፡ ከጌታቸው ፡ በተሰጠው ፡



(አመንን) ፤ ከነርሱ ፡ መካከል ፡
አንድንም ፡ አንለይም ፤ እኛ ፡
ለርሱ ፡ ታዛዦች ፡ ነን ፡ በል ።
85 ከኢስላም፡ ፡ ሌላ ፡ ሃይማኖትን ፡
የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ፈጽሞ ፡ ከርሱ
ተቀባይ ፡ የለውም ፤ እርሱም ፡
በመጨረሻይቱ ፡ ዓለም ፡ ከከሳሪ
ዎቹ ፡ ነው ።
86 ከእምነታቸውና ፡ መልክተኛው
ም ፡ እውነት ፡ መኾኑን ፡ ከመሰ
ከሩ ፡ የተብራሩ ፡ አንቀጾችም ፡
ከመጡላቸው ፡ በኋላ ፡ የካዱን ፡
ሕዝቦች ፡ አላህ ፡ እንዴት ፡ ያቀ
ናል ! አላህ ፡ በዳዮችንም ፡ ሕዝ
ቦች ፡ አያቀናም ።
87 እነዚያ ፡ ቅጣታቸው ፡ የአላህና ፡
የመላእክት ፡ የሰዎችም ፡ ሁሉ ፡
ርግማን ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ መኾን ፡
ነው ።
88 በውስጧ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፤
ቅጣቱም ፤ ከነሱ ፡ ላይ ፡ አይቃለ
ልላቸውም ፤ እነሱም ፡ ቀን ፡ አይ
ሰጡም ።
89 እነዚያ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንስሐ ፡
የገቡና ፡ (ሥራቸውን) ፡ ያሳመሩ፡
ሲቀሩ ፡ (እነዚህንስ ፡ ይምራቸ
ዋል) ፤ አላህ ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡
ነውና ።
90 እነዚያ ፡ ከእምነታቸው ፡ በኋላ ፡
የካዱ ፡ ከዚያም ፡ ክሕደትን ፡
የጨመሩ ፡ ጸጸታቸው ፡ ፈጽሞ ፡
ተቀባይ ፡ የላትም ፡ እነዚያም ፡
የተሳሳቱ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ።
91 እነዚያ ፡ የካዱና ፡ እነርሱም ፡ በክ
ሕደታቸው ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡
የሞቱ ፡ ከነሱ ፡ ከአንዳቸው ፡
በምድር ፡ ሙሉ ፡ የኾነ ፡ ወርቅ ፡
(ቢኖረውና) ፡ በርሱ ፡ ቢበዠበ
ትም ፡ እንኳ ፡ ፈጽሞ ፡ ተቀባይን፡
አያገኝም ፤ እነዚያ ፡ ለነርሱ ፡ የ
ሚያሰቃይ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ፤
ለነርሱም ፡ ምንም ፡ ረዳቶች ፡ የሏ
ቸውም ።

★ ★ ★

92 የምትወዱትን ፡ እስከምትለግሱ ፡
ድረስ ፡ በጐን ፡ ሥራ ፡ (ዋጋውን)፡
አታገኙም ፤ ከምንም ፡ ነገር ፡
ብትለግሱ ፡ አላህ ፡ ያውቀዋል ።
93 ተውራት ፡ ከመወረድዋ ፡ በፊት ፡
እስራኤል ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ እርም ፡
ካደረገው ፡ ነገር ፡ በስተቀር ፡
ምግብ ፡ ሁሉ ፡ ለእስራኤል ፡
ልጆች ፡ የተፈቀደ ፡ ነበር ፤ እው
ነተኞችም ፡ እንደኾናችሁ ፡ ተው
ራትን ፡ አምጡ ፡ አንብቡዋትም ፡
በላቸው ።
94 ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡
ውሸትን ፡ የቀጣጠፉ ፡ ሰዎች ፡
እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ በደለኞች ፡
ናቸው ።
95 አላህ ፡ውነትን ፡ ተናገረ ፤ የኢብ
ራሂምንም ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡
እውነት ፡ ያዘነበለ ፡ ሲኾን ፡ ተከ
ተሉ ፤ ከአጋሪዎቹም ፡ አልነበ
ረም ፡ በላቸው ።
96 ለሰዎች ፡ (መጸለያ) ፡ መጀመሪያ፡
የተኖረው ፡ ቤት ፡ ብሩክና ፡ ለዓ
ለማት ፡ ሁሉ ፡ መምሪያ ፡ ሲኾን ፡
ያ ፡ በበካህ ፡ (በመካ) ፡ ያለው ፡
ነው ።
97 በውስጡ ፡ ግልጽ ፡ የኾኑ ፡ ታም
ራቶች ፡ የኢብራሂም ፡ መቆሚያ ፡
አልለ ። የገባውም ፡ ሰው ፡ ጸጥ
ተኛ ፡ ይኾናል ፤ (1) ለአላህም ፡
በሰዎች ፡ ላይ ፡ ወደርሱ ፡ መኼ
ድን፡በቻለ፡ሁሉ፡ላይ፡ቤቱን ፡መጐ

1 ሰላምን ፡ ያገኛል ።

ብኘት ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ፤
የካደም ፡ ሰው ፡ አላህ ፡ ከዓለ
ማት ፡ ሁሉ ፡ የተብቃቃ ፡ ነው ።

98 የመጽሐፉ ፡ ባለቤቶች ፡ ሆይ !
አላህ ፡ በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ዐዋቂ ፡ ሲኾን ፡ በአላህ ፡ ታም
ራት ፡ ለምን ፡ ትክዳላችሁ ? በላ
ቸው ።

99 የመጽሐፉ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! እና
ንተ ፡ መስካሪዎች ፡ ኾናችሁ ፡
ከአላህ ፡ መንገድ ፡ መጥመሟን ፡
የምትፈልጓት ፡ ስትኾኑ ፡ ያመነን
ሰው ፡ ለምን ፡ ትከለክላላችሁ ?
አላህም ፡ ከምትሠሩት ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ ዘንጊ ፡ አይደለም ፡ በላ
ቸው ።

100 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ከነ
ዚያ ፡ መጽሐፉን ፡ ከተሰጡት ፡
ሰዎች ፡ ከፊሉን ፡ ብትታዘዙ ፡
ከእምነታችሁ ፡ በኋላ ፡ ከሓዲ
ዎች ፡ አድርገው ፡ ይመልሱዋ
ችኋል ።

101 የአላህም ፡ አንቀጾች ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ የሚነበቡ ፡ ሲኾኑ ፡ መል
ክተኛውም ፡ በውስጣችሁ ፡ ያለ፡
ሲኾን ፡ እናንተ ፡ እንዴት ፡ ትክ
ዳላችሁ ! በአላህም ፡ የሚጠበቅ ፡
ሰው ፡ ወደ ፡ ቀጥተኛው ፡ መን
ገድ ፡ በእርግጥ ፡ ተመራ ።

102 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላ
ህን ፡ ተገቢውን ፡ መጠንቀቅ ፡
ተጠንቀቁት ፤ እናንተም ፡ ሙስሊ
ሞች፡ ኾናችሁ፡ ፡ እንጅ ፡ አት
ሙቱ ።

103 የአላህንም ፡ (የማመን) ፡ ገመድ ፡
ሁላችሁም ፡ ያዙ ፤ አትለያዩም ፤
ጠበኞችም ፡ በነበራችሁ ፡ ጊዜ ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ (የዋለውን) ፡ የአ
ላህን ፡ ጸጋ ፡ አስታውሱ ፤ በልቦ
ቻችሁም ፡ መካከል ፡ አስማማ ፤
በጸጋውም ፡ ወንድማማቾች ፡
ኾናችሁ ፤ በእሳት ፡ ጉድጓድ ፡
አፋፍም ፡ ላይ ፡ ነበራችሁ ፤ ከእ
ርስዋም ፡ አዳናችሁ ፤ እንደዚሁ፡
ትመሩ ፡ ዘንድ ፡ አላህ ፡ ለናንተ ፡
አንቀጾቹን ፡ ያብራራል ።

104 ከናንተም ፡ ወደ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡
የሚጠሩ ፡ በመልካም ፡ ሥራም ፡
የሚያዙ ፡ ከክፉ ፡ ነገርም ፡ የሚከ
ለክሉ ፡ ሕዝቦች ፡ ይኑሩ ። እነዚ
ያም ፡ እነሱ ፡ የሚድኑ ፡ ናቸው ።

105 እንደነዚያም ፡ ግልጽ ፡ ታምራት፡
ከመጣላቸው ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡
ተለያዩትና ፡ እንደ ፡ ተጨቃጨ
ቁት ፡ አትኹኑ ፤ እነዚያም ፡ ለነ
ርሱ ፡ ታላቅ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ።

106 ፊቶች ፡ የሚያበሩበትን ፡ ፊቶ
ችም ፡ የሚጠቁሩበትን ፡ ቀን ፡
(አስታውስ) ፤ እነዚያ ፡ ፊቶቻ
ቸው ፡ የጠቆሩትማ ፡ ከእምነታ
ችሁ ፡ በኋላ ፡ ካዳችሁን ? ትክ
ዱት ፡ በነበራችሁት ፡ ነገር ፡ ቅጣ
ቱን ፡ ቅመሱ ። (ይባላሉ) ።

107 እነዚያም ፡ ፊቶቻቸው ፡ ያበሩ
ትማ ፡ በአላህ ፡ ችሮታ ፡ (ገ
ነት) ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ፤ እነ
ርሱ ፡ በውስጧ ፡ ዘውታሪዎች ፡
ናቸው ።

108 ይህች ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ በውነት ፡
የምናነባት ፡ ስትኾን ፡ የአላህ ፡
ታምራት ፡ ናት ፤ አላህም ፡ ለዓለ
ማት ፡ በደልን ፡ የሚሻ ፡ አይ
ደለም ።

109 በሰማያት ፡ ያለውና ፡ በምድር ፡
ያለውም ፡ ሁሉ ፡ የአላህ ፡ ነው ፤
ነገሮችም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡
ብቻ ፡ ይመለሳሉ ።



110 ለሰዎች ፡ ከተገለጸች ፡ ሕዝብ ፡
ሁሉ ፡ በላጭ ፡ ኾናችሁ ፤ በጽ
ድቅ ፡ ነገር ፡ ታዛላችሁ ፤ ከመጥ
ፎም ፡ ነገር ፡ ትከለክላላችሁ ፤
በአላህም ፡ (አንድነት) ፡ ታምና
ላችሁ ፤ የመጽሐፉም ፡ ሰዎች ፡
ባመኑ ፡ ኖሮ ፡ ለነርሱ ፡ የተሻለ ፡
በኾነ ፡ ነበር ፤ ከነርሱ ፡ አማኞች ፡
አልሉ ፤ አብዛኞቻቸው ፡ ግን ፡
አመጸኞች ፡ ናቸው ።

111 ማስከፋትን ፡ እንጅ ፡ ፈጽሞ ፡
አይጎዱዋችሁም ፤ ቢዋጉዋች
ሁም ፡ ጀርባዎችን ፡ ያዞሩላች
ኋል ፤ (ይሸሻሉ) ፤ ከዚያም ፡
አይረዱም ።

112 የትም ፡ በተገኙበት ፡ ስፍራ ፡ ከአ
ላህ ፡ በኾነ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከሰ
ዎችም ፡ በኾነ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
(የተጠበቁ) ፡ ካልኾኑ ፡ በስተቀር፡
በነርሱ ፡ ላይ ፡ ውርደት ፡ ተመ
ታችባቸው ፤ ከአላህም ፡ በኾነ ፡
ቁጣ ፡ ተመለሱ ፤ በነርሱም ፡ ላይ፡
ድኽነት ፡ ተመታችባቸው ፤ ይኸ፡
እነርሱ ፡ በአላህ ፡ ታምራት ፡
ይክዱ ፡ ስለ ፡ ነበሩና ፡ ነቢያት
ንም ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ ይገድሉ ፡ ስለ ፡
ነበሩ ፡ ነው ፤ ይህ÷፣ በማመጣቸ
ውና ፡ ወሰንን ፡ ይተላለፉ ፡ ስለ ፡
ነበሩ ፡ ነው ።

113 (የመጽሐፉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ) ፡
እኩል ፡ አይደሉም ፤ ከመጽሐፉ ፡
ሰዎች ፡ ቀጥ ፡ ያሉ ፡ በሌሊት ፡
ሰዓቶች ፡ እነርሱ ፡ የሚሰግዱ ፡
ኾነው ፡ የአላህን ፡ አንቀጾች ፡
የሚያነቡ ፡ ሕዝቦች ፡ አልሉ ።

114 በአላህና ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡
ያምናሉ ፤ በጽድቅ ፡ ነገርም ፡
ያዛሉ ፡ ከመጥፎ ፡ ነገርም ፡ ይከ
ለክላሉ ፤ በበጎ ፡ ሥራዎችም ፡
ይጣደፋሉ ። እነዚያም ፡ ከመል
ካሞቹ ፡ ናቸው ።

115 ከበጎ ፡ ሥራ ፡ ማንኛውንም ፡
ቢሠሩ ፡ አይካዱትም፤ (1) አላ
ህም ፡ ጥንቁቆቹን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

116 እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡ ገንዘቦ
ቻቸውና ፡ ልጆቻቸው ፡ ከአላህ ፡
(ቅጣት) ፡ እነርሱን ፡ ምንንም ፡
አያድኑዋቸውም ፤ እነዚያም ፡
የእሳት ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ፤ እነርሱ፡
በእርስዋ ፡ ውስጥ ፡ ዘውታሪዎች፡
ናቸው ።

117 የዚያ ፡ በዚች ፡ በቅርቢቱ ፡
ሕይወት ፡ የሚለግሱት ፡ ነገር ፡
ምሳሌ ፡ በውስጧ ፡ ውርጭ ፡ ያለ
ባት ፡ ነፋስ ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ የበ
ደሉን ፡ ሕዝቦች ፡ አዝመራ ፡
እንደ ፡ ነካችና ፡ እንዳጠፋችው ፡
ብጤ ፡ ነው ፤ አላህም ፡ አልበደ
ላቸውም ፡ ግን ፡ ነፍሶቻቸውን ፡
ይበድላሉ ።

118 እናንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ከና
ንተ ፡ ሌላ ፡ ምስጢረኛን ፡ አት
ያዙ ፤ ማበላሸትን ፡ አይገቱላች
ሁም ፤ ጉዳታችሁን ፡ ይወዳሉ ፡
ጥላቻይቱ ፡ ከአፎቻቸው ፡ በእ
ርግጥ ፡ ተገለጸች ። ልቦቻቸውም፡
የሚደብቁት ፡ ይበልጥ ፡ ትልቅ ፡
ነው ። ልብ ፡ የምታደርጉ ፡ እን
ደኾናችሁ ፡ ለናንተ ፡ ማብራሪያ
ዎችን ፡ በእርግጥ ፡ ገለጽን ።

119 እነሆ ፡ እናንተ ፡ እነዚያ ፡ የምት
ወዱዋቸው ፡ ናችሁ ፤ (እነሱ) ፡
ግን ፡ አይወዱዋችሁም ። በመጽ
ሐፉም ፡ በሁሉም ፡ ታምናላችሁ፤
ባገኙዋችሁም ፡ ጊዜ ፡ አምነናል፡
ይላሉ ፤ ባገለሉም ፡ ጊዜ ፡ ከቁጭ
ታቸው ፡ የተነሳ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡

---

1 ኢስላምን፡ ተቀብለው፡ በበጐ፡ ምግባራቸው፡ እስከቀጠሉ፡ ድረስ፡ ምንዳቸውን፡ አያጡም።

ዐጥቆቻቸውን ፡ ይነክሳሉ ፡- በቁ
ጭታችሁ ፡ ሙቱ ፤ አላህ ፡ ልቦች፡
የቋጠሩትን ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ፡ በላ
ቸው ።
120 ደግ ፡ ነገር ፡ ብትነካችሁ ፡ ታስከ
ፋቸዋለች ። መጥፎም ፡ ነገር ፡
ብታገኛችሁ ፡ በርሷ ፡ ይደሰታሉ፤
ብትታገሡና ፡ ብትጠነቀቁም ፡
ተንኮላቸው ፡ ምንም ፡ አይጐዳ
ችሁም ። አላህ ፡ በሚሠሩት ፡
ሁሉ ፡ (በዕውቀቱ) ፡ ከባቢ ፡
ነውና ።
121 ለምእምኖቹም ፡ ለውጊያ ፡ ስፍ
ራዎችን ፡ የምታዘጋጅ ፡ ኾነህ ፡
ከቤተሰብህ ፡ በማለድክ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ) ፡ አላህም ፡ ሰሚ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።
122 ከናንተ ፡ ሁለት ፡ ጭፍሮች ፡
አላህ ፡ ረዳታቸው ፡ ሲኾን ፡ ለመ
ፍራት ፡ ባሰቡ ፡ ጊዜ ፡ (አስታ
ውስ) ፤ በአላህም ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡
ምእምናኖች፡ ይመኩ ።
123 በበድርም ፡ እናንተ ፡ ጥቂቶች ፡
ኾናችሁ ፡ ሳለ ፡ አላህ ፡ በእርግጥ፡
ረዳችሁ ፤ አላህንም ፡ ታመሰግኑ ፡
ዘንድ ፡ ፍሩት ።
124 ለምእምናን፡ ጌታችሁ ፡ በሦስት፡
ሺሕ ፡ መላእክት ፡ የተወረዱ ፡
ሲኾኑ ፡ ቢረዳችሁ ፡ አይበቃች
ሁምን ? በምትል ፡ ጊዜ ፡ (አስ
ታውስ) ።
125 አዎን ፡ ብትታገሡና ፡ ብትጠነ
ቀቁ ፡ ከዚህም ፡ ፍጥነታቸው ፡
(ጠላቶቻችሁ) ፡ ቢመጡባችሁ ፡
ጌታችሁ ፡ ምልክት ፡ ባላቸው፡፡ አ
ምስት ፡ ሺሕ ፡ መላእክት ፡ ይረዳ
ችኋል ።
126 አላህም ፡ (እርዳታውን) ፡ ለናንተ ፡
ብስራትና ፡ ልቦቻችሁ ፡ በርሱ ፡
እንዲረኩ ፡ እንጂ ፡ አላደረገውም፤
ድልም ፡ መንሳት ፡ አሸናፊ ፡ ጥበ
በኛ ፡ ከኾነው ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡
እንጅ ፡ ከሌላ ፡ አይደለም ።
127 (ድልን ፡ ያጐናጸፋችሁ) ፡ ከነዚያ
ከካዱት ፡ ከፊልን ፡ ሊቆርጥ ፡
(ሊያጠፋ) ፡ ወይም ፡ ሊያዋርዳ
ቸውና ፡ ያፈሩ ፡ ኾነው ፡ እንዲ
መለሱ ፡ ነው ።
128 (አላህ) ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ይቅርታ፡
እስኪያደርግ ፡ ወይም ፡ እነርሱ ፡
በዳዮች ፡ ናቸውና ፡ እስኪቀጣ
ቸው ፡ ድረስ ፡ ላንተ ፡ ከነገሩ ፡
ምንም ፡ የለህም ።
129 በሰማያት ፡ ያለው ፡ በምድርም ፡
ያለው ፡ ሁሉ ፡ የአላህ ፡ ነው ፤ ለ
ሚሻው ፡ ሰው ፡ ይምራል ፤ የሚሻ
ውንም ፡ ሰው ፡ ይቀጣል ፤ አላ
ህም ፡ መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።
130 እናንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ፡ አራ
ጣን ፡ የተነባበሩ ፡ እጥፎች ፡
ሲኾኑ ፡ አትብሉ ፤ ትድኑም ፡
ዘንድ ፡ አላህን ፡ ፍሩ ።
131 ያችንም ፡ ለከሓዲዎች ፡ የተደገ
ሰችውን ፡ እሳት ፡ ተጠንቀቁ ።
132 ይታዘንላችሁም ፡ ዘንድ ፡ አላህ
ንና ፡ መልክተኛውን ፡ ታዘዙ ።
133 ከጌታችሁ ፡ ወደ ፡ ኾነችም ፡ ምሕ
ረትና ፡ ስፋትዋ ፡ እንደ ፡ ሰማያ
ትና ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ኾነች፡
ገነት ፡ አላህን ፡ ለሚፈሩ ፡ የተዘ
ጋጀች ፡ ስትኾን ፡ ተቻኮሉ ።
134 ለነዚያ ፡ በድሎትም ፡ ኾነ ፡ በች
ግር ፡ ለሚለግሱት ፡ ቁጭትንም ፡
ገቺዎች ፡ ከሰዎችም ፡ ይቅርታ ፡
አድራጊዎች ፡ ለኾኑት ፡ (ተደግ
ሳለች) ፤ አላህም ፡ በጐ ፡ ሠሪዎ
ችን ፡ ይወዳል ።



135 ለነዚያም ፡ መጥፎ ፡ ሥራን ፡
በሠሩ ፡ ወይም ፡ ነፍሶቻቸውን ፡
በበደሉ ፡ ጊዜ ፤ አላህን ፡ የሚያ
ስታውሱና ፡ ለኀጢአቶቻቸው ፡
ምሕረትን ፡ የሚለምኑ ፡ ለኾኑት፡
ከአላህም ፡ ሌላ ፡ ኀጢአቶችን ፡
የሚምር ፡ አንድም ፡ የለ ፤ (በስ
ሕተት) ፡ በሠሩትም ፡ ላይ ፡ እነ
ርሱ ፡ የሚያውቁ ፡ ሲኾኑ ፡ የማይ
ዘወትሩ ፡ ለኾኑት ፡ (ተደግሳለች)።
136 እነዚያ ፡ ምንዳቸው ፡ ከጌታቸው፡
ምሕረትና ፡ በውስጣቸው ፡ ዘው
ታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ በሥሮቻቸው ፡
ወንዞች ፡ የሚፈሱባቸው ፡ ገነቶ
ችም ፡ ናቸው ። የሠሪዎችም ፡
ምንዳ ፡ (ገነት) ፡ ምንኛ ፡ አማ
ረች ! ።
137 ከናንተ ፡ በፊት ፡ ድርጊቶች ፡
በእርግጥ ፡ አልፈዋል ። በምድ
ርም ፡ ላይ ፡ ኺዱ ፡ የአስተባባዮ
ችም ፡ ፍጻሜ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡
ነበረ ፡ ተመልከቱ ።
138 ይህ ፡ ለሰዎች ፡ ገላጭ ፤ ለጥንቁ
ቆች ፡ መሪና ፡ ገሣጭ ፡ ነው ።
139 እናንተም ፡ የበላዮች ፡ ስትኾኑ ፡
ምእምናን ፡ እንደኾናችሁ ፡ አት
ስነፉ ፤ አትዘኑም ።
140 ቁስል ፡ ቢያገኛችሁ ፡ ሰዎቹንም ፡
መሰሉ ፡ ቁስል ፡ አግኝቷቸዋል ፤
ይኽችንም ፡ ቀናት ፡ በሰዎች ፡
መካከል ፡ እናዘዋውራታለን ፤
(እንድትገሠጹና) ፡ አላህም ፡ እነ
ዚያን ፡ ያመኑትን ፡ እንዲያውቅ ፡
(እንዲለይ) ፡ ከናንተም ፡ ሰማዕ
ታትን ፡ እንዲይዝ ፡ ነው ፤ (1)
አላህም ፡ በዳዮችን ፡ አይወድም ።
141 አላህም ፡ እነዚያን ፡ ያመኑትን ፡

1 በሰማዕታትነት ፡ የሚገደሉን ፡ እንዲያ
ደርግ ።

(ከኀጢአት) ፡ ሊያነጻና ፡ ከሓዲ
ዎችንም ፡ ሊያጠፋ ፡ ነው ።
142 በውነቱ ፡ አላህ ፡ ከናንተ ፡ እነዚ
ያን ፡ የታገሉትን ፡ ሳያውቅ ፡
(ሳይለይ) ፡ ታጋሾቹንም ፡ ሳያ
ውቅ ፡ ገነትን ፡ ልትገቡ ፡ አሰባ
ችሁን ?
143 (በጦርነት ፡ ላይ) ፡ መሞትንም ፡
ሳታገኙት ፡ በፊት ፡ በርግጥ ፡ የም
ትመኙት ፡ ነበራችሁ ፡ እናንተም
የምትመለከቱ ፡ ስትኾኑ ፡ በር
ግጥ ፡ አያችሁት ፤ (ታዲያ ፡ ለምን
ሸሻችሁ ?)
144 ሙሐመድም ፡ ከበፊቱ ፡ መልክ
ተኞች ፡ በእርግጥ ፡ ያለፉ ፡ የኾነ፡
መልክተኛ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደ
ለም ፤ ታዲያ ፡ ቢሞት ፡ ወይም ፡
ቢገደል ፡ ወደኋላችሁ ፡ ትገለበ
ጣላችሁን ? (1) ወደኋላው ፡ የሚ
ገለበጥም ፡ ሰው ፡ አላህን ፡ ምንም
አይጐዳም ። አላህም ፡ አመስጋ
ኞቹን ፡ በእርግጥ ፡ ይመነዳል ።
145 ለማንኛይቱም ፡ ነፍስ ፡ በአላህ ፡
ፍርድ ፡ ቢኾን ፡ እንጅ ፡ ልትሞት
አይገባትም ፤ (ጊዜውም) ፡ ተወ
ስኖ ፡ ተጽፏል ፤ የቅርቢቱንም ፡
ምንዳ ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ከእ
ርስዋ ፡ እንሰጠዋለን ። የመጨ
ረሻይቱንም ፡ ምንዳ ፡ የሚፈልግ፡
ሰው ፡ ከእርስዋ ፡ እንሰጠዋለን ፤
አመስጋኞችንም ፡ በእርግጥ ፡
እንመነዳለን ።
146 ከነቢይም ፡ ብዙ ፡ ሊቃውንት ፡
ከርሱ ፡ ጋር ፡ ኾነው ፡ የተዋጉ ፡
ብዙ፡ ናቸው፤ በአላህም፡ መንገድ፡
ለሚደርስባቸው ፡ ነገር ፡ አልፈ
ሩም ፤ አልደከሙምም ፤ (ለጠ
ላት) ፡ አልተዋረዱምም ። አላ

1 ወደ ፡ ክሕደት ፡ ተመለሳችሁን ።

ህም ፡ ትዕግሥተኞችን ፡ ይወ
ዳል ።
147 ንግግራቸውም ፡-ጌታችን ፡ ሆይ ፡
ኃጢአቶቻችንንና ፡ በነገራችን ፡
ሁሉ ፡ ወሰን ፡ ማለፋችንን ፡ ለኛ ፡
ማር ፤ ይዞታችንንም ፡ አደላ
ድል ፤ (፩) በከሓዲዎችም ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ላይ ፡ እርዳን ፡ ማለታቸው ፡
እንጅ ፡ ሌላ ፡ አልነበረም ።
148 አላህም ፡ የቅርቢቱን ፡ ምንዳና ፡
የመጨረሻይቱን ፡ መልካም ፡
ምንዳ ፡ ሰጣቸው ። አላህም ፡
በጐ ፡ አድራጊዎችን ፡ ይወዳል ።
149 እናንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! እነ
ዚያን ፡ የካዱትን ፡ ሰዎች ፡ ብት
ታዘዙ ፡ ወደ ፡ ኋላችሁ ፡ ይመል
ሱዋችኋል ፤ ከሳሪዎች ፡ ኾናች
ሁም ፡ ትገለበጣላችሁ ።
150 (አይረዱችሁም) ፤ ይልቁን ፡ አ
ላህ ፡ ብቻ ፡ ረዳታችሁ ፡ ነው ።
እርሱም ፡ ከረዳቶች ፡ ሁሉ ፡ በ
ላጭ ፡ ነው ።
በነዚያ፡ በካዱት፡ ሰዎች፡ ልቦች፡
151 ውስጥ፤ አላህ፡ በርሱ፡ አስረጅ፡
ያላወረደበትን፡ ነገር፡ በአላህ፡
በማጋራታቸው፡ ምክንያት፡ ፍርሃ
ትን፡ እንጥላለን። መኖሪያቸውም፡
እሳት፡ ናት፤ የበዳዮችም፡ መኖሪያ፡
ምን፡ ትከፋ!
አላህም፡ በፈቃዱ፡ በምትጨፈጭ
152 ፏቸው፡ ጊዜ፡ ኪዳኑን፡ በእርግጥ፡
አረጋገጠላችሁ። የምትወዱትን
ም፡ ነገር፡ ካሳያችሁ፡ በኋላ፡ በፈራ
ችሁ፥ በትእዛዙም፡ በተጨቃጨቃ
ችሁና፡ ባምመጣችሁ፡ ጊዜ፥ (እርዳ
ታውን፡ ከለከላችሁ)፤ ከናንተ፡
ውስጥ፡ ቅርቢቱን፡ ዓለም፡ የሚሻ፡
አልለ፤ ከናንተም፡ የመጨረሻይ
ቱን፡ ዓለም፡ የሚሻ፡ አልለ፤ ከዚ
ያም፡ ሊሞክራችሁ፡ ከነርሱ፡ አዞራ
ችሁ፤ በእርግጥም፡ ከናንተ፡ ይቅ
ርታ፡ አደረገላችሁ። አላህም፡
በምእምናን፡ ላይ፡ የችሮታ፡
ባለቤት፡ ነው፡
153 መልክተኛው፡ ከኋላችሁ፡ የሚጠ
ራችሁ፡ ሲኾን፥ ርቃችሁ፡ በምትሸ
ሹና፡ በአንድም፡ ላይ፡ የማትዞሩ፡
በኾናችሁ፡ ጊዜ፥ (አስታውሱ)፤
ባመለጣችሁና፡ በደረሰባችሁም፡
ነገር፡ እንድታዝኑ፡ በሐሳብ፡ ላይ፡
ሐሳብን፡ መነዳችሁ፤ አላህም፡ በም
ትሠሩት፡ ሁሉ፡ ውስጠ፡ ዐዋቂ፡
ነው።
154 ከዚያም ፡ ከጭንቅ ፡ በኋላ ፡ ጸጥ
ታን ፡ ከናንተ ፡ ከፊሎችን ፡ የሚ
ሸፍንን ፡ እንቅልፍ ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ አወረደ ፤ ከፊሎቹም ፡ ነፍ
ሶቻቸው ፡ በእርግጥ ፡ አሳሰቧ
ቸው ። እውነት ፡ ያልኾነውን ፡
የመሃይምነትን ፡ መጠራጠር ፡
በአላህ ፡ ይጠራጠራሉ ፤ ከነገሩ ፡
ለኛ ፡ ምንም ፡ የለንም ፡ ይላሉ ፤
ነገሩ ፡ ሁሉም ፡ ለአላህ ፡ ነው ፡
በላቸው ። ለአንተ ፡ የማይገልጹ
ትን ፡ በነፍሶቻቸው ፡ ውስጥ ፡
ይደብቃሉ ፤ ከነገሩ ፡ ለኛ ፡ አን
ዳች ፡ በነበረን ፡ ኖሮ ፡ እዚህ ፡
ባልተገደልን ፡ ነበር ፡ ይላሉ ።
በቤታችሁ ፡ ውስጥ ፡ በኾናችሁም
ኖሮ ፡ እነዚያ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡
መገደል ፡ የተጻፈባቸው ፡ ወደ ፡
መውደቂያቸው ፡ በወጡ ፡ ነበር ፡
በላቸው ፤ አላህ ፡ (ፍርዱን ፡ ሊ
ፈጽምና) ፡ በደረቶቻችሁም ፡ ው
ስጥ ፡ ያለውን ፡ ሊፈትን ፡ በል
ቦቻችሁም ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡



ነገር ፡ ሊገልጽ ፡ (ይህን ፡ ሠራ) ፤
አላህም ፡ በደረቶች ፡ ውስጥ ፡
ያለን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
155 እነዚያ ፡ ሁለቱ ፡ ጭፍሮች ፡ በተ
ገናኙ ፡ ቀን ፡ ከእናንተ ፡ የሸሹት ፡
ሰዎች ፡ በዚያ ፡ በሠሩት ፡ ከፊል ፡
ምክንያት ፡ ያሳሳታቸው ፡ ሰይ
ጣን ፡ ነው ፤ አላህም ፡ ከነሱ ፡
በእርግጥ ፡ ይቅር ፡ አለ ፤ አላህ ፡
መሓሪ ፡ በቅጣት ፡ የማይቸኩል ፡
ነውና ።
156 እናንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! እን
ደነዚያ ፡ እንደ ፡ ካዱትና ፡ ስለ ፡
ወንድሞቻቸው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
በተጓዙ ፡ ወይም ፡ ዘማቾች ፡
በኾኑ ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ በነ
በሩ ፡ ኖሮ ፡ ባልሞቱም ፡ ባልተ
ገደሉም ፡ ነበር ፡ እንደሚሉት ፡
አትኹኑ ፤ አላህ ፡ ይኽንን ፡ በል
ቦቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ጸጸት ፡ ያደርግ
ባቸው ፡ ዘንድ ፡ (ይህንን ፡ አሉ) ።
አላህም ፡ ሕያው ፡ ያደርጋል ፤
ይገድላልም ። አላህም ፡ የምት
ሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ተመልካች ፡
ነው ።
157 በአላህም ፡ መንገድ ፡ ብትገደሉ ፡
ወይም ፤ ብትሞቱ ፡ ከአላህ ፡
የኾነው ፡ ምሕረትና ፡ እዝነት ፡
(እነርሱ) ፡ ከሚሰበስቡት ፡ ሀብት ፡
በእርግጥ ፡ በላጭ ፡ ነው ።
158 ብትሞቱም ፡ ወይም ፡ ብትገደሉ ፡
በእርግጥ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡
ትሰበሰባላችሁ ።
159 ከአላህም ፡ በኾነች ፡ ችሮታ ፡
ለዘብክላቸው ። ዐመለ ፡ መጥፎ ፡
ልበ ፡ ደረቅም ፡ በኾንክ ፡ ኖሮ ፡
ከዙሪያህ ፡ በተበተኑ ፡ ነበር ።
ከነርሱም ፡ ይቅር ፡ በል ። ለነር
ሱም ፡ ምሕረትን ፡ ለምንላቸው ።
በነገሩም ፡ ሁሉ ፡ አማክራቸው ።
ቁርጥ ፡ ሐሳብም ፡ ባደረግህ ፡
ጊዜ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ተመካ ።
አላህ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተመኪዎ
ችን ፡ ይወዳልና ።
160 አላህ ፡ ቢረዳችሁ ፡ ለናንተ ፡ አሸ
ናፊ ፡ የለም ፤ ቢያዋርዳችሁም ፡
ያ ፡ ከርሱ ፡ (ማዋረድ) ፡ በኋላ ፡
የሚረዳችሁ ፡ ማነው ? በአላህም ፡
ላይ ፡ ብቻ ፡ ምእምናን ፡ ይመኩ ።
161 ለነቢይም ፡ ሰለባን ፡ መደበቅ ፡
አይገባውም ። ሰላባንም ፡ የሚደ
ብቅ ፡ ሰው ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡
በደበቀው ፡ ነገር ፡ (ተሸክሞ) ፡
ይመጣል ። ከዚያም ፡ ነፍስ ፡
ሁሉ ፡ የሥራዋን ፡ ዋጋ ፡ ትሞላ
ለች ። እነርሱም ፡ አይበደሉም ።
162 የአላህን ፡ ውዴታ ፡ የተከተለ ፡
ሰው ፡ ከአላህ ፡ በኾነ ፡ ቁጣ ፡
እንደ ፡ ተመለሰና ፡ መኖሪያው ፡
ገሀነም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሰው ፡
ነውን ? መመለሻውም ፡ ምን ፡
ይከፋ !
163 እነርሱ ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡ ባለ ፡
ደረጃዎች ፡ ናቸው ፤ አላህም ፡
የሚሠሩትን ፡ ነገር ፡ ተመልካች ፡
ነው ።
164 አላህ ፡ በምእምናን ፡ ላይ ፡ ከጐ
ሳቸው ፡ የኾነን ፤ በነርሱ ፡ ላይ ፡
አንቀጾቹን ፡ የሚያነብ ፡ የሚያ
ጠራቸውም ፡ መጽሐፍንና ፡ ጥበ
ብን ፡ የሚያስተምራቸውም ፡ የኾ
ነን ፡ መልክተኛ ፡ በውስጣቸው ፡
በላከ ፡ ጊዜ ፤ በእርግጥ ፡ ለገሰላ
ቸው ፤ እነርሱም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡
በግልጽ ፡ ስሕተት ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ ።
165 ሁለት ፡ ብጤዎችዋን ፡ በእርግጥ ፡
ያገኛችሁ ፡ የኾነች ፡ መከራ ፡
(መጠቃት) ፡ ባገኛችችሁ ፡ ጊዜ ፡

ይህ ፡ ከየት ፡ ነው ፡ አላችሁን ?
እርሱ ፡ ከነፍሶቻችሁ ፡ ዘንድ ፡
ነው ። አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ
ቻይ ፡ ነውና ፡ በላቸው ።
166 ሁለቱ ፡ ጭፍሮችም ፡ በተጋጠሙ
ቀን ፡ የደረሰባችሁ ፡ በአላህ ፡
ፈቃድ ፡ ነው ፤ ምእምናንንም፡፡
(ሊፈትንና) ፡ ሊገልጽ ፡ ነው ።
167 እነዚያንም ፡ የነፈቁትንና ፡ ለነ
ርሱ ፡ ኑ ፤ በአላህ ፡ መንገድ ፡
ተጋደሉ ፤ ወይም ፡ ተከላከሉ ፤
የተባሉትን ፡ ሊገልጽ ፡ ነው ።
መዋጋትን ፡ (መኖሩን) ፡ ብናውቅ
ኖሮ ፡ በተከተልናችሁ ፡ ነበር ፡
አሉ ፤ እነርሱ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከእ
ምነት ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ ክሕደት ፡
የቀረቡ ፡ ናቸው ፤ በልቦቻቸው ፡
የሌለውን ፡ በአፎቻቸው ፡ ይናገ
ራሉ ። አላህም ፡ የሚደብቁትን ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።
168 እነዚያ ፡ (ከትግል) ፡ የቀሩ ፡ ሲ
ኾኑ ፡ ለወንድሞቻቸው ፡—በታዘ
ዙን ፡ ኖሮ ፡ ባልተገደሉ ፡ ነበር ፡
ያሉ ፡ ናቸው ፡ እውነተኞች ፡ እን
ደኾናችሁ ፡ ከነፍሶቻችሁ ፡ ላይ ፡
ሞትን ፡ ገፍትሩ ፡ በላቸው ።
169 እነዚያን ፡ በአላህ ፡ መንገድ ፡
የተገደሉትን ፡ ሙታን ፡ አድር
ገህ ፡ አትገምታቸው ። በእርግጥ ፡
እነርሱ ፡ እጌታቸው ፡ ዘንድ ፡
ሕያዋን ፡ ናቸው ፤ ይመገባሉ ።
170 አላህ ፡ ከችሮታው ፡ በሰጣቸው ፡
ነገር ፡ ተደሳቾች፡ ሲኾኑ ፡ (ይመ
ገባሉ) ፤ በነዚያም ፡ ከኋላቸው ፡
ገና ፡ በነርሱ ፡ ባልተከተሉት ፡
(1) በነርሱ ፡ ላይ ፡ ፍርሃት ፡ ባለ ፡
መኖሩና ፡ እነርሱም ፡ የማያዝኑ ፡
በመኾናቸው ፡ ይደሰታሉ ።

1 ባልሞቱት ፡ ወንድሞቻቸው ።

171 ከአላህ ፡ በኾነ ፡ ጸጋና ፡ ልግስና ፡
አላህም ፡ የምእምናንን ፡ ምንዳ ፡
የማያጠፋ ፡ በመኾኑ ፡ ይደሰታሉ።
172 እነዚያ ፡ መቁሰል ፡ ካገኛቸው ፡
በኋላ ፡ ለአላህና ፡ ለመልክተኛው
የታዘዙት ፡ ከነሱ ፡ ለነዚያ ፡ በጎ ፡
ለሠሩትና ፡ ለተጠነቀቁት ፡ ታ
ላቅ ፡ ምንዳ ፡ አላቸው ።
173 እነዚያ ፡ ሰዎቹ ፡ ለነርሱ ፡- ሰዎች
ለናንተ ፡ (ጦርን) ፡ አከማችተ
ዋልና ፡ ፍሩዋቸው ፡ ያሉዋቸውና
(ይህም) ፡ እምነትን ፡ የጨመረላ
ቸው ፡ በቂያችንም ፡ አላህ ፡ ነው ፡
ምን ፡ ያምርም ፡ መጠጊያ ! ፡ ያሉ
ናቸው ።
174 ከአላህም ፡ በኾነ ፡ ጸጋና ፡ ችሮታ ፡
ክፉ ፡ ነገር ፡ ያልነካቸው ፡ ኾነው ፡
ተመለሱ ፤ የአላህንም ፡ ውዴታ ፡
ተከተተሉ ፤ አላህም ፡ የታላቅ ፡
ችሮታ ፡ ባለቤት ፡ ነው ።
175 ይሃችሁ ፡ ሰይጣን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡
ወዳጆቹን ፡ ያስፈራራችኋል ፤
አትፍሩዋቸውም ፤ ምእምናንም ፡
እንደኾናችሁ ፡ ፍሩኝ ።
176 እነዚያም ፡ በክሕደት ፡ የሚቻ
ኮሉት ፡ አያሳዝኑህ ። እነርሱ ፡
ፈጽሞ ፡ አላህን ፡ በምንም ፡ አይ
ጐዱምና ፤ አላህ ፡ በመጨረሻ
ይቱ ፡ ዓለም ፡ ለነሱ ፡ ዕድልን ፡
ላያደርግ ፡ ይሻል ፤ ለነርሱም ፡
ታላቅ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ።
177 እነዚያ ፡ ክሕደትን ፡ በእምነት ፡
የለወጡ ፡ አላህን ፡ በምንም ፡
ነገር ፡ ፈጽሞ ፡ አይጐዱትም ፤
ለነሱም ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡
አላቸው ።
178 እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡ እነ
ርሱን ፡ ማዘግየታችንን ፡ ለነፍ
ሶቻቸው ፡ ደግ ፡ ነገር ፡ ነው ፡



ብለው ፡ አያስቡ ፡ እነርሱን ፡ የም
ናዘገያቸው ፡ ኃጢአትን ፡ እንዲ
ጨምሩ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ለነሱም ፡
አዋራጅ ፡ ስቃይ ፡ አላቸው ።
179 አላህ ፡ መጥፎውን ፡ ከመልካሙ ፡
እስከሚለይ ፡ ድረስ ፡ ምእምናንን
እናንተ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ባላችሁ
በት ፡ (ኹኔታ)፡ ላይ ፡ የሚተው ፡
አይደለም ፤ አላህም ፡ ሩቁን ፡
ነገር ፡ የሚያሳውቃችሁ ፡ አይ
ደለም ፤ ግን ፡ አላህ ፡ ከመልክተ
ኞቹ ፡ የሚሻውን ፡ ይመርጣል ፤
በአላህና ፡ በመልክተኞቹም ፡
እመኑ ። ብታምኑና ፡ ብትጠነቀ
ቁም ፡ ለናንተ ፡ ታላቅ ፡ ምንዳ ፡
አላችሁ ።
180 እነዚያም ፡ አላህ ፡ ከችሮታው ፡
በሰጣቸው ፡ ገንዘብ ፡ የሚነፍጉ ፡
እርሱ ፡ ለነሱ ፡ ደግ ፡ አይምሰላ
ቸው ፤ ይልቁንም ፤ እርሱ ፡ ለነሱ ፡
መጥፎ ፡ ነው ፤ ያንን ፡ በርሱ ፡
የነፈጉበትን ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡
(እባብ ፡ ኾኖ) ፡ ይጠለቃሉ ። የሰ
ማያትና ፡ የምድርም ፡ ውርስ ፡
ለአላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ አላህም ፡
በሚሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ውስጥ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።
181 የእነዚያን ፡ አላህ ፡ ድኻ ፡ ነው ፡
እኛ፡ ግን፡ ከበርቴዎች፡ ነን፡ ያሉ
ትን ፡ ሰዎች ፡ ቃል ፡ አላህ ፡ በእ
ርግጥ ፡ ሰማ ፤ ያንን ፡ ያሉትንና ፡
ነቢያትን ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ መግደላቸ
ውን ፡ በእርግጥ ፡ እንጽፋለን ፤
የእሳትንም ፡ ስቃይ ፡ ቅመሱ ፡
እንላቸዋለን ።
182 ያ ፡ (ስቃይ) ፡ እጆቻችሁ ፡ ባሳለ
ፉት ፡ ሥራ ፡ ነው ። አላህም ፡
ለባሮቹ ፡ በዳይ ፡ ባለመኾኑ ፡
ነው ።

183 እነዚያ ፡ ለማንኛውም ፡ መልክ
ተኛ ፡ እሳት ፡ የምትበላው ፡ የኾ
ነን ፡ ቁርባን ፡ እስከሚያመጣልን ፡
ድረስ ፡ ላናምን ፡ አላህ ፡ ወደኛ ፡
አዟል ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፤ መልክተ
ኞች ፡ ከኔ ፡ በፊት ፡ በታምራትና ፡
በዚያም ፡ ባላችሁት ፡ (ቁርባን) ፡
በእርግጥ ፡ መጥተውላችኋል ፡
እውነተኞች ፡ ከኾናችሁ ፡ ታዲያ ፡
ለምን ፡ ገደላችኋቸው ? በላቸው ።
184 ቢያስተባብሉህም ፡ ከአንተ ፡
በፊት ፡ በግልጽ ፡ ታምራትና ፡
በጽሑፎች ፡ በብሩህ ፡ መጽሐ
ፍም ፡ የመጡት ፡ መልክተኞች ፡
በእርግጥ ፡ ተስተባብለዋል ።
185 ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ ሞትን ፡ ቀማሽ ፡
ናት ፤ ምንዳዎቻችሁንም ፡ የምት
ሞሉት ፡ (1) በትንሣኤ ፡ ቀን ፡
ብቻ ፡ ነው ። ከእሳትም ፡ የተራ
ቀና ፡ ገነትን ፡ የተገባ ፡ (2) ሰው ፡
በእርግጥ ፡ ምኞቱን ፡ አገኘ ።
ቅርቢቱም ፡ ሕይወት ፡ የመታ
ለያ ፡ መሣሪያ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡
አይደለችም ።
186 በገንዘቦቻችሁና ፡ በነፍሶቻችሁ ፡
በእርግጥ ፡ ትፈተናላችሁ ፤ ከነ
ዚያም ፡ ከእናንተ ፡ በፊት ፡ መጽ
ሐፍን ፡ ከተሰጡትና ፡ ከነዚያም ፡
ከአጋሩት ፡ ብዙን ፡ ማስቃየት ፡
ትሰማላችሁ ፤ ብትታገሡና ፡ ብት
ጠነቀቁ ፡ ይህ ፡ ከጥብቅ ፡ ነገሮች ፡
ነው ።
187 አላህ ፡ የነዚያን ፡ መጽሐፉን ፡
የተሰጡትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለሰ
ዎች ፡ በእርግጥ ፡ ታብራሩታላ
ችሁ ፡ አትደብቁትምም ፡ በማለት ፡
የያዘባቸውን ፡ (አስታውሱ) ፤ በጀ

1 የምትሰጡት ።
2 እንዲገባ ፡ የተደረገ ።

ርባዎቻቸውም ፡ ኋላ ፡ ጣሉት ፤
በርሱም ፡ ጥቂትን ፡ ዋጋ ፡ ገዙ ፤
የሚገዙትም ፡ ነገር ፡ ከፋ !
188 እነዚያን ፡ በሠሩት ፡ ነገር ፡ የሚደ
ሰቱትንና ፡ ባልሠሩትም ፡ መመ
ስገንን ፡ የሚወዱትን ፡ አትሰብ ፤
ከቅጣት ፡ በመዳን ፡ ላይ ፡ ናቸው ፡
ብለህ ፡ አትሰባቸው ፤ ለነሱ ፡ አሳ
ማሚ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ።
189 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ንግሥና ፡
ለአላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ አላህም ፡
በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ።
190 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ በመፍ
ጠር ፡ ሌሊትና ፡ ቀንም ፡ በመተ
ካካት ፡ ለባለ ፡ አእምሮዎች ፡
በእርግጥ ፡ ምልክቶች ፡ አሉ ።
191 (እነርሱም) ፡ እነዚያ ፡ ቆመው ፡
ተቀምጠውም ፡ በጐኖቻቸው ፡
ተጋድመውም ፡ አላህን ፡ የሚያ
ወሱ ፡ በሰማያትና ፡ በምድር ፡
አፈጣጠርም ፡ የሚያስተነትኑ ፡—
ጌታችን ፡ ሆይ ! ይኸን ፡ በከንቱ ፡
አልፈጠርከውም ፤ ጥራት ፡ ይገ
ባህ ፤ ከእሳትም ፡ ቅጣት ፡ ጠብ
ቀን ፡ የሚሉ ፡ ናቸው ።
192 ጌታችን ፡ ሆይ ! አንተ ፡ እሳት ፡
የምታገባውን ፡ ሰው ፡ በእርግጥ ፡
አዋረድከው ፤ ለበደለኞችም ፡ ም
ንም ፡ ረዳቶች ፡ የሉዋቸውም ።
193 ጌታችን ፡ ሆይ ! እኛ ፡ በጌታችሁ ፡
እመኑ ፡ በማለት ፡ ወደ ፡ እምነት ፡
የሚጠራን ፡ ጠሪ ፡ ሰማን ፤ አመ
ንንም ፤ ጌታችን ፡ ሆይ ! ኃጢአቶ
ቻችንንም ፡ ለኛ ፡ ማር ፤ ክፉ ፡
ሥራዎቻችንንም ፡ ከኛ ፡ አብስ ፤
ከንጹሖቹም፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ግደ
ለን ፤
194 ጌታችን፡ ሆይ! በመልክተኞች
ህም፡ ላይ፡ ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡ ያደረ
ግክልንን ፡ ስጠን ፤ በትንሣኤ ፡
ቀንም ፡ አታዋርደን ፤ አንተ ፡ ቀጠ
ሮን ፡ አታፈርስምና ፤ (የሚሉ ፡
ናቸው) ።
195 ጌታቸውም ፡ እኔ ፡ ከናንተ ፡
ከወንድ ፡ ወይም ፡ ከሴት ፡ የሠ
ሪን ፡ ሥራ ፡ አላጠፋም ፤ ከፊላ
ችሁ ፡ ከከፊሉ ፡ ነው ፤ በማለት ፡
ለነርሱ ፡ ልመናቸውን ፡ ተቀበለ ፤
እነዚያም ፡ (1) የተሰደዱ ፡ ከአገሮ
ቻቸውም ፡ የተባረሩ ፡ በመንገ
ዴም ፡ የተጠቁ ፡ የተጋደሉም ፡
የተገደሉም ፡ ክፉ ፡ ሥራዎቻቸ
ውን ፡ ከነርሱ ፡ በእርግጥ ፡ አብሳ
ለሁ ፤ በሥሮቻቸውም ፡ ወንዞች ፡
የሚፈሱባቸውን ፡ ገነቶች ፡ በእር
ግጥ ፡ አገባቸዋለሁ ፤ ከአላህ ፡
ዘንድ ፡ የኾነን ፡ ምንዳ ፡ (ይመነ
ዳሉ) ፤ አላህም ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡
መልካም ፡ ምንዳ ፡ አለለ ።
196 የነዚያ ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡ በአገ
ሮች ፡ መንፈላሰስ ፡ አያታልህ ።
197 አነስተኛ ፡ ጥቅም ፡ ነው ፤ ከዚ
ያም ፡ መኖሪያቸው ፡ ገሀነም ፡
ናት ፤ ምን ፡ ትከፋም ፡ ምንጣፍ !
198 ግን ፡ እነዚያ ፡ ጌታቸውን ፡ የፈሩ ፡
ለነሱ ፡ ከስሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡
የሚፈሱባቸው ፡ ገነቶች ፡ በው
ስጧ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ ከአ
ላህ ፡ ዘንድ ፡ (የተሰጡ) ፡ መስተን
ግዶዎች፡ አሏቸው፤ አላህም ፡
ዘንድ ፡ ያለው ፡ (ምንዳ) ፡ ለበጐ ፡
ሠሪዎች ፡ በላጭ ፡ ነው ።
199 ከመጽሐፉም ፡ ባለቤቶች ፡ (2)
ለአላህ ፡ ፈሪዎች ፡ በአላህ ፡ አንቀ
ጾችም ፡ ጥቂትን ፡ ዋጋ ፡ የማይለ

1 ከመካ ፡ ወደ ፡ ሐበሻ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ መዲና
2 እንደ ፡ ዐብደላህ ፡ ሰላምና ፡ እንደ ፡ ሐበሻ ፡ ንጉሥ ።



ውጡ ፡ ሲኾኑ ፡ በአላህና ፡ በዚያ ፡
ወደ ፡ እናንተ ፡ በተወረደው ፡
በዚያም ፡ ወደነርሱ ፡ በተወረ
ደው ፡ የሚያምኑ ፡ ሰዎች ፡ አልሉ፤
እነዚያ ፡ ለነርሱ ፡ በጌታቸው ፡
ዘንድ ፡ ምንዳቸው ፡ አላቸው ፤
አላህ ፡ ምርመራው ፡ ፈጣን ፡
ነው ።
200 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ !
ታገሡ ፡ ተበራቱም ፡ (በጠር ፡
ኬላ ፡ ላይ) ፡ ተሰለፉም ፡ ትድ
ኑም ፡ ዘንድ ፡ አላህን ፡ ፍሩ ።

## ምዕራፍ ፡ 4 ፡ አል-ኒሳእ ። ክፍል ፡ 4 ።

4ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ኒሳእ ፡ (የሴቶች ፡ ምዕራፍ) ፤ በመዲና ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 176 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በኾነው ።
1 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! ያንን ፡
ከአንዲት ፡ ነፍስ ፡ (ከአዳም) ፡
የፈጠራችሁን ፡ ከርስዋም ፡ መቀ
ናጀዋን፡ (ሔዋንን) ፡ የፈጠረ
ውን ፡ ከነርሱም ፡ ብዙ ፡ ወንዶ
ችንና ፡ ሴቶችን ፡ የበተነውን ፡
ጌታችሁን ፡ ፍሩ ። ያንንም ፡ በር
ሱ ፡ የምትጠያየቁበትን ፡ አላህ
ንና ፡ ዝምድናዎችንም ፡ (ከመቁ
ረጥ) ፡ ተጠንቀቁ ፤ አላህ ፡ በእ
ናንተ ፡ ላይ ፡ ተጠባባቂ ፡ ነውና ።
2 የቲሞችንም ፡ ገንዘቦቻቸውን ፡
ስጡ ፤ መጥፎውንም ፡ በመል
ካሙ ፡ አትለውጡ ፤ ገንዘቦቻቸ
ውንም ፡ ወደ ፡ ገንዘቦቻችሁ ፡
(በመቀላቀል) ፡ አትብሉ ፤ እርሱ ፡
ታላቅ ፡ ኃጢአት ፡ ነውና ።
3 በየቲሞችም ፡ (ማግባት) ፡ አለማ
ስተካከላችሁን ፡ ብትፈሩ ፡ (ዝሙ
ትንና ፡ ከተወሰነላችሁ ፡ በላይ ፡
ማግባትንም ፡ ፍሩ) ፤ ከሴቶች ፡
ለናንተ ፡ የተዋበላችሁን ፡ ሁለት ፡
ሁለት ፡ ሦስት ፡ ሦስትም ፡ አራት፡
አራትም ፡ አግቡ ። አለማስተካከ
ልንም ፡ ብትፈሩ ፡ አንዲትን ፡
ብቻ ፡ ወይም ፡ እጆቻችሁ ፡ ንብ
ረት ፡ ያደረጉትን ፡ (1) ያዙ ፤
ይህ ፡ ወደ ፡ አለመበደል ፡ በጣም ፡
የቀረበ ፡ ነው ።
4 ሴቶችንም ፡ መህሮቻቸውን ፡ (2)
በደስታ ፡ ስጡ ፤ ለናንተም ፡
ከርሱ ፡ አንዳችን ፡ ነገር ፡ ነፍሶ
ቻቸው ፡ ቢለግሱ ፡ መልካም ፡
ምስጉን ፡ ሲኾን ፡ ብሉት ።
5 ቂሎችንም ፡ ያችን ፡ አላህ ፡ ለና
ንተ ፡ መተዳደሪያ ፡ ያደረጋትን ፡
ገንዘቦቻችሁን ፡ (የያዛችሁላቸው
ን) ፡ አትስጡዋቸው ፤ ከርሷም ፡
መግቡዋቸው ፤ አልብሱዋቸውም፤
ለነሱም ፡ መልካምን ፡ ንግግር ፡
ተናገሩ ።
6 የቲሞችንም ፡ ጋብቻን ፡ እስከ ፡

1 ሀብታችሁ ፡ የኾኑትን ፡ ዕቁባት ።
2 በ" ኒካሕ"፡ ወቅት፡ ለሴቷ፡ የሚሰጥ፡ ገንዘብ።

ደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ፈትኑዋ
ቸው ፤ ከነርሱም፡ ቅንነትን ፡
ብታውቁ ፡ ገንዘቦቻቸውን ፡ ወደ
ነርሱ ፡ ስጡ ። በማባከንና ፡ ማደ
ጋቸውንም ፡ በመሽቀዳደም ፡ አት
ብሏት ። (ከዋቢዎች) ፡ ሀብታ
ምም ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ይከልከል ፤
ድኻም፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ (ለድካሙ)፡
በአግባብ ፡ ይብላ ። ገንዘቦቻቸው
ንም ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ በሰጣችሁ ፡
ጊዜ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ አስመስክሩ ፤
ተጠባባቂነትም ፡ በአላህ ፡ በቃ ።
7 ለወንዶች ፡ ወላጆችና ፡ የቅርብ ፡
ዘመዶች ፡ ከተውት፡ (ንብረት)፡
ፈንታ ፡ አላቸው ። ለሴቶችም ፡
ወላጆችና ፡ የቅርብ ፡ ዘመዶች ፡
ከተውት ፡ ከርሱ ፡ ካነሰው ፡
ወይም ፡ ከበዛው ፡ ፈንታ ፡ አላ
ቸው ። የተወሰነ ፡ ድርሻ ፡ (ተደ
ርጓል) ።
8 ክፍያንም ፡ (ወራሽ ፡ ያልኾኑ) ፡
የዝምድና ፡ ባለቤቶችና ፡ የቲ
ሞች ፡ ምስኪኖችም ፡ በተገኙ
በት ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ዳርጓቸው ፤
መልካምንም ፡ ንግግር ፡ ተናገሩ
ዋቸው ።
9 እነዚያም ፡ ከኋላቸው ፡ ደካሞ
ችን ፡ ዝርያዎች ፡ ቢተው ፡ ኖሮ ፡
በነርሱ ፡ ላይ ፡ የሚፈሩ ፡ (በየቲ
ሞች ፡ ላይ) ፡ ይጠንቀቁ ፤ አላህ
ንም ፡ ይፍሩ ፤ (ለተናዛዡ) ፡ ትክ
ክለኛንም ፡ ቃል ፡ ይናገሩ ።
10 እነዚያ ፡ የየቲሞችን ፡ ገንዘብ፡
በመበደል ፡ የሚበሉ ፡ በሆዶቻ
ቸው ፡ ውስጥ ፡ የሚበሉት ፡ እሳ
ትን ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ እሳትንም ፡
በእርግጥ ፡ ይገባሉ ።
11 አላህ ፡ በልጆቻችሁ ፡ (ውርስ ፡
በሚከተለው) ፡ ያዛችኋል ፤ ለወ
ንዱ ፡ የሁለት ፡ ሴቶች ፡ ድርሻ ፡
ብጤ ፡ አለው ፤ (ሁለት ፡ ወይም) ፡
ከሁለት ፡ በላይም ፡ የኾኑ ፡ ሴቶች፡
ብቻ ፡ ቢኾኑ ፡ ለነቡ ፡ (ሟቹ) ፡
ከተወው ፡ ረጀት ፡ ከሦስት ፡
ሁለት ፡ እጁ ፡ አላቸው ። አንዲ
ትም ፡ ብትኾን ፡ ለርሷ ፡ ግማሹ ፡
አላት ። ለአባትና ፡ ለእናቱም ፡
ለርሱ ፡ ልጅ ፡ እንዳለው ፡ ከሁ
ለቱ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ከስድስት ፡
አንድ ፡ አላቸው ። ለርሱም ፡ ልጅ፡
ባይኖረውና ፡ ወላጆቹ ፡ ቢወር
ሱት ፡ ለእናቱ ፡ ሢሶው ፡ አላት ።
ለርሱም ፡ ወንድሞችና ፡ እኅቶች ፡
ቢኖሩት ፡ ለናቱ ፡ ከስድስት ፡
አንድ ፡ አላት ፤ (ይህም ፡ የተባ
ለው) ፡ በርሷ ፡ ከተናዘዘባት ፡
ኑዛዜ ፡ ወይም ፡ ከዕዳ ፡ በኋላ ፡
ነው ። አባቶቻችሁና ፡ ልጆቻ
ችሁ ፡ ለናንተ ፡ በመጥቀም ፡ ማን
ኛቸው ፡ ይበልጥ ፡ ቅርብ ፡ እንደ ፡
ኾኑ ፡ አታውቁም ። (ይኸም) ፡
ከአላህ ፡ የተደነገገ ፡ ነው ፤ አላህ ፡
ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነውና ።
12 ለናንተም ፡ ሚስቶቻችሁ ፡ ከተ
ውት ፡ ንብረት ፡ ለነርሱ ፡ ልጅ ፡
ባይኖራቸው ፡ ግማሹ ፡ አላችሁ ፤
ለነሱም ፡ ልጅ ፡ ቢኖራቸው ፡
ከተውት ፡ ሀብት ፡ ከአራት ፡
አንድ ፡ አላችሁ ፤ (ይህም) ፡ በርሷ ፡
ከሚናዘዙባት ፡ ኑዛዜ ፡ ወይም ፡
ከዕዳ ፡ በኋላ ፡ ነው ። ለናንተም ፡
ልጅ ፡ ባይኖራችሁ ፡ ከተዋችሁት፡
ንብረት ፡ ለነርሱ ፡ (ለሚስቶች) ፡
ከአራት ፡ አንድ ፡ አላቸው ፤ ለና
ንተም ፡ ልጅ ፡ ቢኖራችሁ ፡ ከተ
ዋችሁት ፡ ንብረት ፡ ለነርሱ ፡ ከስ
ምንት ፡ አንድ ፡ አላቸው ፤ (ይህም
በርሷ ፡ ከምትናዘዙባት ፡ ኑዛዜ ፡
ወይም ፡ ከዕዳ ፡ በኋላ ፡ ነው ።



ወላጅም ፡ ልጅም ፡ የሌለው ፡
በኾን ፡ ወራሾች ፡ የሚወርስ ፡
ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ቢገኝ ፡
ለርሱም ፡ (ለሟቹ) ፡ ወንድም ፡
ወይም ፡ እኅት ፡ (ከእናቱ ፡ በኩል ፡
ብቻ ፡ የኾነ) ፡ ቢኖር ፡ ከሁለቱ ፡
ለያንዳንዳቸው ፡ ከስድስት ፡ አን
ድ ፡ አላቸው ። ከዚህም ፡ (ከአ
ንድ) ፡ የበዙ ፡ ቢኾኑ ፡ እነርሱ ፡
በሢሶው ፡ ተጋሪዎች ፡ ናቸው ፤
(ይህም ፡ ወራሾችን) ፡ የማይጐዳ ፡
ኾኖ ፡ በርሷ ፡ ከሚናዘዙባት ፡
ኑዛዜ ፡ ወይም ፡ ከዕዳ ፡ በኋላ ፡
ነው ። ከአላህም ፡ የኾነን ፡ ኑዛዜ ፡
(ያዛችኋል) ፤ አላህም ፡ ዐዋቂ ፡
ቻይ ፡ ነው ።
13 እነዚህ ፡ የአላህ ፡ ውሳኔዎች ፡
ናቸው ። አላህንና ፡ መልክተኛው
ንም ፡ የሚታዘዙ ፡ ሰዎች ፡ ከስሮ
ቻቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱባቸ
ውን ፡ ገነቶች ፡ በውስጣቸው ፡
ዘውታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ ያገባቸ
ዋል ። ይህም፡ ትልቅ ፡ ዕድል ፡
ነው ።
14 አላህንና ፡ መልክተኛውንም ፡
የሚያምጥ ፡ ወሰኖቹንም ፡ የሚተ
ላለፍ ፡ በውስጧ፡ ዘውታሪ ፡
ሲኾን ፡ እሳትን ፡ ያገባዋል ፤ ለር
ሱም ፡ አዋራጅ ፡ ቅጣት ፡ አለው ።
15 እነዚያም ፡ ከሴቶቻችሁ ፡ መጥ
ፎን ፡ ሥራ ፡ (ዝሙትን) ፡ የሚ
ሠሩ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ከናንተ ፡
አራትን ፡ (ወንዶች) ፡ አስመስክ
ሩባቸው ። ቢመሰክሩም ፡ ሞት ፡
እስከሚደርስባቸው ፡ ወይም ፡
አላህ ፡ ለነርሱ ፡ መንገድን ፡
እስከሚያደርግ ፡ ድረስ ፡ በቤ
ቶች ፡ ውስጥ ፡ ያዙዋቸው ፡ (ጠብ
ቁዋቸው) ።
16 እነዚያንም ፡ ከእናንተ ፡ ውስጥ ፡
(ዝሙትን) ፡ የሚሠሩዋትን ፡
አሰቃዩዋቸው ፤ ቢጸጸቱና ፡ ሥራ
ቸውንም ፡ ቢያሳምሩ ፡ ከነርሱ ፡
ተገቱ ፡ (አታሰቃዩዋቸው) ፡ አ
ላህ ፡ ጸጸትን ፡ ተቀባይ ፡ አዛኝ ፡
ነውና ። (1)
17 ጸጸትን ፡ መቀበል ፡ በአላህ ፡
ላይ ፡ የሚገባው ፡ ለነዚያ ፡
ኀጢአትን ፡ በስሕተት ፡ ለሚሠ
ሩና ፡ ከዚያም ፡ ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡
ለሚጸጸቱት ፡ ብቻ ፡ ነው ። እነዚ
ያንም ፡ አላህ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡
ጸጸትን ፡ ይቀበላል ። አላህም ፡
ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።
18 ጸጸትንም ፡ መቀበል ፡ ለነዚያ ፡
ኀጢአቶችን ፡ ለሚሠሩ ፡ አንዳቸ
ውንም ፡ ሞት ፡ በመጣበት ፡
ጊዜ ፡ እኔ ፡ አሁን ፡ ተጸጸትኩ ፡
ለሚልና ፡ ለነዚያም ፡ እነርሱ ፡
ከሓዲዎች ፡ ኾነው ፡ ለሚሞቱ ፡
አይደለችም ። እነዚያ ፡ ለነሱ ፡ አሳ
ማሚን ፡ ቅጣት ፡ አዘጋጅተናል ።
19 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሰዎች ፡
ሆይ ! ሴቶችን ፡ ያስገደዳችሁ ፡
ኾናችሁ ፡ ልትወርሱና ፡ ግልጽን ፡
መጥፎ ፡ ሥራ ፡ ካልሠሩ ፡ በስተ
ቀር ፡ ከሰጣችኋቸው ፡ ከፊሉን ፡
ልትወስዱ ፡ ልታጉላሏቸውም ፡
ለናንተ ፡ አይፈቀድም ፤ በመል
ካምም ፡ ተኗኗሩዋቸው ፤ ብትጠሉ
ዋቸውም ፡ (ታገሡ) ፤ አንዳችን ፡
ነገር ፡ ልትጠሉ ፡ አላህም ፡ በርሱ፡
ብዙ ፡ ደግ ፡ ነገርን ፡ ሊያደርግ ፡
ይቻላልና ።
20 በሚስትም ፡ ስፍራ ፡ ሚስትን ፡
ለመለወጥ ፡ ብትፈልጉ ፡ ለአንደ

---

1 ይህ ፡ በ24ኛ፡ ምዕራፍ ፡ በ፪ኛ ፡ አንቀጽ ፡ ተብራርቷል ።

ኛይቱ ፡ (ለምትፈታው) ፡ ብዙን ፡
ገንዘብ ፡ የሰጣችኋት ፡ ስትኾኑ ፡
ከርሱ ፡ ምንንም ፡ አትውሰዱ ።
በመበደልና ፡ ግልጽ ፡ በኾነ ፡
ኀጢአት ፡ ትወስዱታላችሁን ?
21 ከፊላችሁ ፡ ወደ ፡ ከፊሉ ፡ በእር
ግጥ ፡ የደረሰ ፡ሲኾንና ፡ ከናንተ ፡
ላይም ፡ (ሴቶች) ፡ የጠበቀ ፡ ኪዳ
ንን ፡ የያዙባችሁ ፡ ሲኾኑ ፡ እን
ዴት ፡ ትወስዱታላችሁ !
22 ከሴቶችም ፡ አባቶቻችሁ ፡ ያገቡዋ
ቸውን ፡ አታግቡ ። (ትቀጡበታላ
ችሁ) ፡ ያለፈው ፡ ሲቀር ፡ እርሱ ፡
መጥፎና ፡ የተጠላ ፡ ሥራ ፡ ነውና
መንገድነቱም ፡ ከፋ !
23 እናቶቻችሁ ፡ ሴት ፡ ልጆቻች
ሁም ፡ እኅቶቻችሁም ፡ አክስቶቻ
ችሁም ፡ የሹሜዎቻችሁም ፡ (1)
የወንድም ፡ ሴቶች ፡ ልጆችም ፡
የእኅት ፡ ሴቶች ፡ ልጆችም ፡ እነ
ዚያም ፡ ያጠቡዋችሁ ፡ እናቶቻ
ችሁ ፡ ከመጥባት ፡ የኾኑትም ፡
እኅቶቻችሁ ፡ የሚስቶቻችሁም ፡
እናቶች ፡ እነዚያም ፡ በጉያዎቻ
ችሁ ፡ ያሉት ፡ የነዚያ ፡ በነርሱ ፡
የገባችሁባቸው ፡ ሚስቶቻችሁ ፡
ሴቶች ፡ ልጆች ፡ (ልታገቧቸው) ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ እርም ፡ ተደረጉ
ባችሁ ። በነርሱም ፡ (በሚስቶ
ቻችሁ) ፡ ያልገባችሁባቸው ፡
ብትኾኑ ፡ (በፈታችኋቸው ፡ ጊዜ ፡
ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ብታገቡ) ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ የለባ
ችሁም ። የነዚያ ፡ ከጀርባዎቻ
ችሁ ፡ የኾኑት ፡ ወንዶች ፡ ልጆቻ
ችሁ ፡ (2) ሚስቶችም ፡ በሁለት ፡
እኅትማማቾችም ፡ መካከል ፡
መሰብሰብ ፡ (እንደዚሁ ፡ እርም ፡
ነው) ፤ ግን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያለ
ፈው ፡ ሲቀር ፡ (እርሱንስ ፡ ተም
ራችኋል) ፡ አላህ ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡
ነውና ።

★ ★ ★

24 ከሴቶችም ፡ (በባል) ፡ ጥብቆቹ ፡
እጆቻችሁ ፡ (በምርኮ) ፡ የያዙዋ
ቸው ፡ ሲቀሩ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
እርም ፡ ናቸው ። (ይህን) ፡ አላህ ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ ጻፈ ፤ ከዚሃችሁም ፡
(ከተከለከሉት) ፡ ወዲያ ፡ ጥብ
ቆች ፡ ኾናችሁ ፡ ዝሙተኞች ፡
ሳትኾኑ ፡ በገንዘቦቻችሁ ፡ (1)
ልትፈልጉ ፡ ለናንተ ፡ ተፈቀደ ፤
ከነሱም ፡ በርሱ ፡ (በመገናኘት) ፡
የተጠቀማችሁባቸውን ፡ ሴቶች ፡
መህሮቻቸውን ፡ ግዴታ ፡ ሲኾን ፡
ስጧቸው ። ከመወሰንም ፡ በኋላ ፡
በተዋደዳችሁበት ፡ ነገር ፡ በና
ንተ ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ የለም ።
አላህ ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነውና ።
25 ከናንተም፡ ውስጥ፡ ጥብቆች፡ ምእ
ምናት፡ የኾኑትን፡ ለማግባት፡ ሀብ
ትን፡ ያልቻለ፡ ሰው፥ እጆቻችሁ፡
ንብረት፡ ካደረጓቸው፡ ከምእምናት፥
ወጣቶቻችሁ፥ (ባሪያን፡ ያግባ)፤
አላህም፡ እምነታችሁን፡ ዐዋቂ፡
ነው፤ ከፊላችሁ፡ ከከፊሉ፡ (የተራባ)፡
ነው። (ባሮችን)፡ በጌቶቻቸውም፡
ፈቃድ፡ አግቡዋቸው። መህሮቻቸ
ውንም፡ በመልካም፡ መንገድ፡ ስጧ
ቸው፤ ጥብቆች፡ ኾነው፡ ዝሙተ
ኞች፡ ያልኾኑ፡ የስርቆሽ፡ ወዳጆች
ንም፡ ያልያዙ፡ ሲኾኑ፥ (አግቧቸው)፤
በማግባት፡ በተጠበቁም፡ ጊዜ፥
መጥፎን፡ ሥራ፡ ቢሠሩ፥ በነርሱ፡

1 የእናት ፡ እኅት ።
2 የወለዳችሁአቸው ፡ ልጆቻችሁ ፡ ሚስቶች ።

1 በጋብቻ ፡ ወይም ፡ በግዥ ።



ላይ፥ ከቅጣት፡ በነጻዎቹ፡ ላይ፡
ያለው፡ ግማሽ፡ አለባቸው፤ ይኸ፡
(ባሪያን፡ ማግባቱ)፥ ከናንተ፡ ዝሙ
ትን፡ ለፈራ፡ ሰው፡ ነው። መታገ
ሳችሁም፡ ለናንተ፡ በላጭ፡ ነው።
አላህም፡ መሓሪ፡ አዛኝ፡ ነው።
26 አላህ ፡ (የሃይማኖታችሁን ፡ ሕግ
ጋት) ፡ ሊያብራራላችሁ ፡ ከናንተ ፡
በፊትም ፡ የነበሩትን ፡ ነቢያት ፡
ደንቦች ፡ ሊመራችሁ ፡ በናንተም ፡
ላይ ፡ ጸጸትን ፡ ሊቀበል ፡ ይሻል ።
አላህም ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።
27 አላህም ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ጸጸትን ፡
ሊቀበል ፡ ይሻል ። እነዚያም ፡
ፍላጎታቸውን ፡ የሚከተሉት ፡
(ከውነት) ፡ ትልቅን ፡ መዘንበል ፡
እንድትዘነበሉ ፡ ይፈልጋሉ ።
28 አላህ ፡ ከናንተ ፡ ሊያቃልላችሁ ፡
ይሻል ። ሰውም ፡ ደካማ ፡ ኾኖ ፡
ተፈጠረ ።
29 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ገንዘ
቉ቻችሁን ፡ በመካከላችሁ ፡ ያለ ፡
አግባብ ፡ አትብሉ ፤ ግን ፡ ከናንተ ፡
በመዋደድ ፡ የኾነችውን ፡ ንግድ ፡
(ብሉ) ፤ ነፍሶቻችሁንም ፡ አት
ግደሉ ። አላህ ፡ ለናንተ ፡ አዛኝ ፡
ነውና ።
30 ወሰን ፡ በማለፍና ፡ በመበደልም ፡
ይህንን ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ እሳትን ፡
እናገባዋለን ። ይኸም ፡ በአላህ ፡
ላይ ፡ ገር ፡ ነው ።
31 ከርሱ ፡ ከተከለከላችሁት ፡ ታላላ
ቆቹን ፡ ብትርቁ ፡ (ትናንሾቹን) ፡
ኀጢአቶቻችሁን ፡ ከናንተ ፡ እና
ብሳለን ፤ የተከበረንም ፡ ስፍራ ፡
(ገነትን) ፡ እናገባችኋለን ።
32 አላህም ፡ ከፊላችሁን ፡ በከፊሉ ፡
ላይ ፡ በርሱ ፡ ያበለጠበትን ፡ ጸጋ ፡
አትመኙ ። ለወንዶች ፡ ከሠሩት ፡
ሥራ ፡ ዕድል ፡ አላቸው ፤ ለሴቶ
ችም ፡ ከሠሩት ፡ ሥራ ፡ ዕድል ፡
አላቸው ። አላህንም ፡ ከችሮታው ፡
ለምኑት ፤ አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡
ዐዋቂ ፡ ነውና ።
33 ለሁሉም ፡ (ለወንዶችና ፡ ለሴ
ቶች) ፡ ወላጆችና ፡ የቅርብ ፡ ዘመ
ዶች ፡ ከተውት ፡ ሀብት ፡ ጠቅ
ላይ ፡ ወራሾችን ፡ አድርገናል ።
እነዚያንም ፡ (ለመረዳዳትና ፡ ለመ
ዋረስ) ፡ በመሐላዎቻችሁ ፡ የተዋ
ዋላችኋቸውን ፡ ድርሻቸውን ፡ (ከ
ስድስት ፡ አንድ) ፡ ስጧቸው (1) ።
አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።
34 ወንዶች ፡ በሴቶች ፡ ላይ ፡ ቋሚ
ዎች ፡ (አሳዳሪዎች) ፡ ናቸው ፤
አላህ ፡ ከፊላቸውን ፡ በከፊሉ ፡
ላይ ፡ በማብለጡና ፡ (ወንዶች) ፡
ከገንዘቦቻቸው ፡ (ለሴቶች) ፡ በመ
ስጠታቸው ፡ ነው ። መልካም
ቹም ፡ ሴቶች ፡ (ለባሎቻቸው) ፡
ታዛዦች ፡ አላህ ፡ ባስጠበቀው ፡
ነገር ፡ ሩቅን ፡ ጠባቂዎች ፡ (2)
ናቸው ። እነዚያንም ፡ ማመጣቸ
ውን ፡ የምትፈሩትን ፡ ገሥጹዋ
ቸው ፤ በመኝታዎችም ፡ ተለዩ
ዋቸው ፤ (ሳካ ፡ ሳታደርሱ) ፡ ም
ቱዋቸውም ። ቢታዘዟችሁም ፡
(ለመጨቆን) ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡
መንገድን ፡ አትፈልጉ ፤ አላህ ፡
የበላይ ፡ ታላቅ ፡ ነውና ።
35 (እላንተ ፡ ዋቢዎች) ፡ የመካከላቸ
ውንም ፡ ጭቅጭቅ ፡ ብታውቁ ፡
ከቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ ሽማግሌን ፡ ከቤ
ተሰቦችዋም ፡ ሽማግሌን ፡ ላኩ ።

1 በመሐላ ፡ መዋረስ ፡ በኋኛም ፡ ቋኟ ፡ አን
ቀጽ ፡ ተሽሯል ።
2 ባሎቻቸው ፡ በሩቁ ፡ ጊዜ ፡ መብታቸው ፡
እንዳይደፈርና ፡ ገንዘባቸውን ፡ ጠባቂዎች ።

ማስታረቅን ፡ ቢሹ ፡ አላህ ፡ በመ
ካከላቸው ፡ ያስማማል ። አላህ ፡
ግልጽን ፡ ዐዋቂ ፡ ውስጥንም ፡
ዐዋቂ ፡ ነውና ።
36 አላህንም ፡ ተገዙ ፤ በርሱም ፡
ምንንም ፡ አታጋሩ ፡ በወላጆችና ፡
በቅርብ ፡ ዝምድና ፡ ባለቤትም ፡
በየቲሞችም ፡ በምስኪኖችም ፡
በቅርብ ፡ ጎረቤትም ፡ በሩቅ ፡
ጎረቤትም ፡ በጐን ፡ ባልደረባም ፡
በመንገደኛም ፡ እጆቻችሁም ፡
ንብረት ፡ ባደረጓቸው ፡ (ባሮች) ፡
መልካምን ፡ (ሥሩ) ፤ አላህ ፡ ኩራ
ተኛ ፡ ጉረኛ ፡ የኾነን ፡ ሰው ፡
አይወድም ።
37 እነዚያ ፡ የሚሰስቱ ፡ ሰዎችንም ፡
በመሰሰት ፡ የሚያዙ ፡ አላህም ፡
ከችሮታው ፡ የሰጣቸውን ፡ ጸጋ ፡
የሚደብቁ ፡ (ብርቱን ፡ ቅጣት፡
ይቀጥጣሉ) ፤ ለከሓዲዎችም ፡
አዋራጅን ፡ ቅጣት ፡ አዘጋጅተ
ናል ።
38 እነዚያም ፡ ለሰዎች ፡ ይውልኝ ፡
ሲሉ ፡ ገንዘቦቻቸውን ፡ የሚሰጡ ፡
በአላህና ፡ በመጨረሻውም ፡ ቀን ፡
የማያምኑ ፡ (ይቀጥጣሉ) ፤ ሰይጣ
ንም ፡ ለሱ ፡ ጓደኛው ፡ የኾነ ፡
ሰው ፡ ጓደኛነቱ ፡ ከፋ !
39 በአላህና ፡ በመጨረሻውም ፡ ቀን ፡
ባመኑ ፡ አላህ ፡ ከሰጣቸውም ፡
(ሲሳይ) ፡ በለገሱ ፡ ኖሮ ፡ በነርሱ ፡
ላይ ፡ ምን ፡ (ጉዳት) ፡ ነበረ ? አላ
ህም ፡ በነርሱ ፡ (ኹነታ) ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።
40 አላህ ፡ የብናኝን ፡ ክብደት ፡ ያህል
አይበድልም ፤ መልካም ፡ ሥራ ፡
ብትኾንም ፡ ይደራርባታል ፤ ከር
ሱም ፡ ዘንድ ፡ ታላቅን ፡ ምንዳ ፡
ይሰጣል ።
41 ከሕዝቦችም ፡ ሁሉ ፡ መስካሪን ፡
ባመጣን ፡ ጊዜ ፡ አንተንም ፡ በነ
ዚህ ፡ ላይ ፡ መስካሪ ፡ አድርገን ፡
በምናመጣህ ፡ ጊዜ ፡ (የከሓዲ
ዎች ፡ ኹኔታ) ፡ እንዴት ፡ ይኾን ?
42 በዚያ ፡ ቀን ፡ እነዚያ ፡ የካዱትና ፡
መልክተኛውን ፡ ያልታዘዙት ፡
በነሱ ፡ ምድር ፡ ብትደፋባቸው ፡
ይመኛሉ ፤ ከአላህም ፡ ወሬን ፡
አይደብቁም ።
43 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! እና
ንተ ፡ የሰከራችሁ ፡ ኾናችሁ ፡
የምትሉትን ፡ ነገር ፡ እስከምታ
ውቁ ፡ የረከሳችሁም ፡ ስትኾኑ ፡
መንገድን ፡ አላፊዎች ፡ ካልኾና
ችሁ ፡ በስተቀር ፡ (አከላታችሁን)፡
እስከምትታጠቡ ፡ ድረስ ፡ ስግደ
ትን ፡ አትቅረቡ ። በሽተኞች ፡
ወይም ፡ በጉዞ ፡ ላይ ፡ ብትኾኑም ፡
ወይንም ፡ ከእናንተ ፡ አንዱ ፡ ከዓ
ይነምድር ፡ ቢመጣ ፡ ወይንም ፡
ሴቶችን ፡ ብትነካኩና ፡ ውሃን ፡
ባታገኙ ፡ ንጹሕ ፡ የኾነን ፡ የም
ድር ፡ ገጽ ፡ አስቡ ። ፊቶቻችሁ
ንና ፡ እጆቻችሁንም ፡ (በርሱ) ፡
አብሱ ። አላህ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡
መሓሪ ፡ ነውና ።
44 ወደነዚያ ፡ ከመጽሐፉ ፡ (ዕው
ቀት) ፡ ዕድልን ፡ ወደ ፡ ተሰጡት ፡
አላየህምን ? ጥመትን ፡ (በቅን
ነት) ፡ ይገዛሉ ፤ መንገድንም ፡
እንድትሳሳቱ ፡ ይፈልጋሉ ።
45 አላህም ፡ ጠላቶቻችሁን ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ፤ ጠባቂነትም ፡ በአላህ ፡
በቃ ፤ ረዳትነትም ፡ በአላህ ፡ በቃ።
46 ከነዚያ ፡ ይሁዳውያን ፡ ከኾኑት ፡
ሰዎች ፡ ንግግሮችን ፡ ከስፍራ
ዎቹ ፡ የሚያጣምሙ ፡ አልሉ ፤
ሰማንም ፡ አመጥንም ፡ የማትሰ



ማም ፡ ስትኾን ፡ ስማ ፡ ይላሉ ፤
በምላሶቻቸውም ፡ ለማጣመምና ፡
ሃይማኖትንም ፡ ለመዝለፍ ፡ ራዒ
ና ፡ ይላሉ ፤ (1) እነሱም ፡ ሰማን ፡
ታዘዝንም ፡ ስማም ፡ ተመልከተ
ንም ፡ ባሉ ፡ ኖሮ ፡ ለነሱ ፡ መልካ
ምና ፡ ትክክለኛ ፡ በኾነ ፡ ነበር ።
ግን ፡ በክሕደታቸው ፡ አላህ ፡
ረገማቸው ፤ ጥቂትንም ፡ እንጅ ፡
አያምኑም ።
47 እላንተ ፡ መጽሐፉን ፡ የተሰጣ
ችሁ ፡ ሆይ ! ፊቶችን ፡ ሳናብስና ፡
በጀርባዎች ፡ ላይ ፡ ሳንመልሳ
ቸው ፡ ወይም ፡ የሰንበትን ፡ ባለ
ቤቶች ፡ (ያፈረሱትን) ፡ እንደረገ
ምን ፡ ሳንረግማቸው ፡ በፊት ፡
ከናንተ ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ የሚያረ
ጋግጥ ፡ ኾኖ ፡ ባወረድነው ፡ (ቁር
አን) ፡ እመኑ ፤ የአላህም ፡ ትእ
ዛዝ ፡ ተፈጻሚ ፡ ነው ።
48 አላህ ፡ በርሱ ፡ ማጋራትን ፡ በፍ
ጹም ፡ አይምርም ፤ ከዚህ ፡ ሌላ ፡
ያለውንም፡ (ኀጢአት)፡ ለሚሻው፡
ሰው ፡ ይምራል ። በአላህም ፡ የሚ
ያጋራ ፡ ሰው ፡ ታላቅን ፡ ኀጢአት፡
በእርግጥ ፡ ቀጠፈ ።
49 ወደነዚያ ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ ወደ
ሚያጠሩት ፡ (የሚያወድሱት) ፡
አላየህምን ? አይደለም ፤ አላህ ፡
የሚፈልገውን፡ ያጠራል፤ የተምር፡
ፍሬ ፡ ክር ፡ ያህልም ፡ አይበደ
ሉም ።
50 በአላህ ፡ ላይ ፡ ውሸትን ፡ እንዴት፡
እንደሚቀጣጥፉ ፡ ተመልከት ፤
ግልጽ ፡ ወንጀልም ፡ በርሱ ፡ (በመ
ቅጠፍ) ፡ በቃ ።
51 ወደ ፡ እነዚያ ፡ ከመጽሐፉ ፡ ዕድ

1 ሁለት ፡ ትርጉም ፡ አለው ፡ ጠብቀን ፡
ወይም ፡ ጅል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ልን ፡ ወደ ፡ ተሰጡት ፡ አላየኸ
ምን ? በድግምትና ፡ በጣዖት ፡
ያምናሉ ። ለነዚያም ፡ ለካዱት ፡
፡-እናንተ ፡ በመንገድ ፡ (በሃይማ
ኖት) ፡ ከነዚያ ፡ ካመኑት ፡ ይበ
ልጥ ፡ የቀናችሁ ፡ ናችሁ ፡ ይላሉ ።
52 እነዚያ ፡ አላህ ፡ የረገማቸው ፡
ናቸው ። አላህም ፡ የረገመው ፡
ሰው ፡ ለርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ረዳትን ፡
አታገኝለትም ።
53 በውነቱ ፡ ለነሱ ፡ ከንግሥናው ፡
ፋንታ ፡ አላቸውን ? ያን ፡ ጊዜ ፡
ለሰዎች ፡ በተምር ፡ ፍሬ ፡ ላይ ፡
ያለችውን ፡ ነጥብ ፡ ያህል ፡ አይ
ሰጡም ፡ ነበር ።
54 ይልቁንም፡ ሰዎችን፥ አላህ፡
ከችሮታው፡ በሰጣቸው፡ ነገር፡
ላይ ይመቀኛሉን? ለኢብራ
ሂምም፡ ቤተሰቦች፡ መጽሐ
ፍንና፡ ጥበብን በእርግጥ፡
ሰጠን፤ ታላቅንም፡ ንግሥና፡
ሰጠናቸው።
55 ከነሱም ፡ (ከይሁዶች) ፡ በርሱ ፡
ያመነ ፡ አልለ ። ከነሱም ፡ ከእ
ርሱ ፡ ያፈገፈገ ፡ አልለ ፤ አቃጣይ
ነትም ፡ በገሀነም ፡ በቃ ።
56 እነዚያን ፡ በተአምራታችን ፡ የካ
ዱትን ፡ በእርግጥ ፡ እሳትን ፡ እና
ገባቸዋለን ፤ ስቃይን ፡ እንዲቀ
ምሱ ፡ ቆዳዎቻቸው ፡ በተቃጠሉ ፡
ቍጥር ፡ ሌሎችን ፡ ቆዳዎች ፡ እን
ለውጥላቸዋለን ፤ አላህ ፡ አሸናፊ ፡
ጥበበኛ ፡ ነውና ።
57 እነዚያንም ፡ ያመኑትንና ፡ መል
ካም ፡ ሥራዎችን ፡ የሠሩትን ፡
ከስራቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱ
ባቸውን ፡ ገነቶች ፡ ዘለዓለም ፡
በውስጣቸው ፡ ዘውታሪዎች ፡
ሲኾኑ ፡ በእርግጥ ፡ እናገባቸዋ

ለን ፤ ለነሱ ፡ በውስጥዋ ፡ ንጹሕ ፡
ሚስቶች፡ አሉዋቸው፤ የምታስ ጠ
ልልን፡ ጥላም፡ እናገባቸዋለን።
58 አላህ ፡ አደራዎችን ፡ ወደ ፡ ባለቤ
ቶቻቸው ፡ እንድታደርሱ ፡ ያዛ
ችኋል ። በሰዎችም ፡ መካከል ፡
በፈረዳችሁ ፡ ጊዜ ፡ በትክክል ፡
እንድትፈርዱ ፡ (ያዛችኋል) ፤ አላ
ህ ፡ በርሱ ፡ የሚገሥጻችሁ ፡ ነገር ፡
ምን ፡ ያምር ! አላህ ፡ ሰሚ ፡ ተመ
ልካች ፡ ነው ።
59 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላ
ህን ፡ ተገዙ ፤ መልክተኛውንና ፡
ከናንተም ፡ የሥልጣን ፡ ባለቤቶ
ችን ፡ ታዘዙ ፤ በማንኛውም ፡
ነገር ፡ ብትከራከሩ ፡ በአላህና ፡
በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ የምታምኑ ፡
ብትኾኑ ፡ (የተከራከራችሁበትን ፡
ነገር) ፡ ወደ ፡ አላህና ፡ ወደ ፡ መል
ክተኛው ፡ መልሱት ፤ ይህ ፡ የተ
ሻለ ፡ መጨረሻውም ፡ ያማረ ፡
ነው ።
60 ወደ ፡ እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ በአንተ ፡
ላይ ፡ በተወረደውና ፡ ከአንተ ፡
በፊትም ፡ በተወረደው ፡ አምነ
ናል ፡ ወደሚሉት ፡ አላየህምን ?
በርሱ ፡ እንዲክዱ ፡ በእርግጥ ፡
የታዘዙ ፡ ሲኾኑ ፡ ወደ ፡ ጣዖት ፡
መፋረድን ፡ ይፈልጋሉ ፤ ሰይጣ
ንም ፡ (ከውነት) ፡ የራቀን፡ መሳ
ሳት ፡ ሊያሳስታቸው ፡ ይፈልጋል።
61 ለነርሱም ፡— አላህ ፡ ወደ ፡ አወ
ረደው ፡ (ቁርአን)ና ፡ ወደ ፡ መል
ክተኛው ፡ ኑ ፡ በተባሉ ፡ ጊዜ ፡
መናፍቃን፡ ከአንተ ፡ መሸሽን ፡
ሲሸሹ ፡ ታያቸዋለህ ።
62 እጆቻቸውም ፡ ባስቀደሙት ፡
(ጥፋት) ፡ መከራ ፡ በደረሰችባቸ
ውና ፡ ከዚያም ፡ ደግን ፡ ሐሳብና ፡
ማስማማትን ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አል
ሻንም ፡ በማለት ፡ በአላህ ፡ የሚ
ምሉ ፡ ኾነው ፡ በመጡህ ፡ ጊዜ ፡
እንዴት ፡ ይኾናሉ ?
63 እነዚህ ፡ እነዚያ ፡ አላህ ፡ በልቦ
ቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡
የሚያውቅባቸው ፡ ናቸው ። እነር
ሱንም ፡ ተዋቸው ፤ ገሥጻቸውም ፤
ለነርሱም ፡ በነፍሶቻቸው ፡ ውስጥ
ስሜት፡ ያለውን፡ (የሚያጭር)፡
ቃል፡ ተናገራቸው።
64 ማንንም ፡ መልክተኛ ፡ በአላህ ፡
ፈቃድ ፡ ሊታዘዙት ፡ እንጅ ፡ አል
ላክንም ። እነሱም ፡ ነፍሶቻቸ
ውን ፡ በበደሉ ፡ ጊዜ ፡ በመጡህ ፡
አላህንም ፡ ምሕረትን ፡ በለመኑ ፡
መልክተኛውም ፡ ለነርሱ ፡ ምሕ
ረትን ፡ በለመነላቸው ፡ ኖሮ ፡ አላ
ህን ፡ ጸጸትን ፡ ተቀባይ ፡ አዛኝ ፡
ኾኖ ፡ ባገኙት ፡ ነበር ።
65 በጌታህም ፡ እምላለሁ ፡ (1) በመ
ካከላቸው ፡ በተከራከሩበት ፡ ፍ
ርድ ፡ እስከሚያስፈርዱህ ፡ ከዚ
ያም ፡ ከፈረድከው፡ ነገር ፡ በነፍ
ሶቻቸው ፡ ውስጥ፡ ጭንቀትን ፡
እስከማያገኙና ፡ ፍጹም ፡ መታዘዝ
ንም ፡ እስከሚታዘዙ ፡ ድረስ ፡ አያም
ኑም ፤ (ምእምን ፡ አይኾኑም) ።
66 እኛም ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡— ነፍሶቻ
ችሁን ፡ ግደሉ ፡ ወይም ፡ ከአገሮ
ቻችሁ ፡ ውጡ ፡ ማለትን ፡ በጻ
ፍን ፡ ኖሮ ፡ ከነሱ ፡ ጥቂቶቹ ፡
እንጅ ፡ ባልሠሩት ፡ ነበር ። እነ
ሱም ፡ በርሱ ፡ የሚገሠጹበትን ፡
ነገር ፡ በሠሩ ፡ ኖሮ ፡ ለነሱ ፡ መል
ካምና ፡ (በእምነታቸው ፡ ላይ) ፡
ለመርጋትም ፡ በጣም ፡ የበረታ ፡
በኾነ ፡ ነበር ።

1 አላህ ፡ በራሱ ፡ መማሉ ፡ ነው ።



67 ያንጊዜም ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅን፡
ምንዳ ፡ በሰጠናቸው ፡ ነበር ።
68 ቀጥተኛውንም ፡ መንገድ ፡ በእር
ግጥ ፡ በመራናቸው ፡ ነበር ።
69 አላህንና ፡ መልክተኛውንም ፡
የሚታዘዝ ፡ ሰው ፤ እነዚህ ፡ ከነ
ዚያ ፡ አላህ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ከለገ
ሰላቸው ፡ ከነቢያት ፡ ከጻድቃንም፡
ከሰማዕታትም ፡ ከመልካሞቹ ፡
ጋር ፡ ይኾናሉ ። የነዚያም ፡ ጓደ
ኝነት ፡ አማረ !
70 ይኸ ፡ ችሮታ ፡ ከአላህ ፡ ነው ።
ዐዋቂነትም፡ በአላህ፡ በቃ።
71 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ጥን
ቃቄያችሁን ፡ ያዙ ። ክፍልፍልም፡
ጓድ ፡ ኾናችሁ ፡ (ለዘመቻ) ፡
ውጡ ፤ ወይም ፡ ተሰብስባችሁ ፡
ውጡ ።
72 ከናንተም ፡ ውስጥ ፡ በእርግጥ ፡
(ከዘመቻ) ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የሚንጓ
ደድ ፡ ሰው ፡ አልለ ፤ አደጋም፡
ብታገኛችሁ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ተጣ
ጅ ፡ ባልኾንኩ ፡ ጊዜ ፡ አላህ ፡
በእኔ ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ ለገሰልኝ ፡
ይላል ።
73 ከአላህም ፡ የኾነ ፡ ችሮታ ፡ ቢያገ
ኛችሁ ፡ በናንተና ፡ በርሱ ፡ መካ
ከል ፡ ፍቅር ፡ እንዳልነበረች ፡
ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ ዕድልን ፡ አገኝ ፡
ዘንድ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ በኾንኩ ፡
ወይ ፡ ምኞቴ ! ይላል ።
74 እነዚያም ፡ ቅርቧን ፡ ሕይወት ፡
በመጨረሻይቱ ፡ ሕይወት ፡ የሚ
ለውጡ ፡ በአላህ ፡ መንገድ ፡ ይጋ
ደሉ ፤ በአላህም ፡ መንገድ ፡ የሚጋ
ደል ፡ የሚገደልም ፡ ወይም ፡ የሚ
ያሸንፍ ፡ ታላቅ ፡ ምንዳን ፡ በእ
ርግጥ ፡ እንሰጠዋለን ።
75 በአላህ ፡ መንገድና ፡ ከወንዶች ፡
ከሴቶችና ፡ ከልጆችም ፡ የኾኑ
ትን ፡ ደካሞች ፡ እነዚያን ፡— ጌታ
ችን ፡ ሆይ ! ከዚች ፡ ባለቤቶችዋ ፡
በዳይ ፡ ከኾኑት ፡ ከተማ ፡ አው
ጣን ፡ ከአንተም ፡ ዘንድ ፡ ለኛ ፡
አሳዳሪን ፡ አድርግልን ፡ ከአንተ ፡
ዘንድም ፡ ለኛ ፡ ረዳትን ፡ አድርግ
ልን ፡ የሚሉትን ፡ (ለማዳን) ፡ የማ
ትጋደሉት ፡ ለናንተ ፡ ምን ፡ አላ
ችሁ ?
76 እነዚያ ፡ ያመኑት ፡ ሰዎች ፡ በአ
ላህ ፡ መንገድ ፡ ይጋደላሉ ፤ እነ
ዚያ ፡ የካዱትም ፡ በጣዖት ፡ መን
ገድ ፡ ይጋደላሉ ፤ የሰይጣንንም ፡
ጭፍሮች ፡ ተጋደሉ ። የሰይጣን ፡
ተንኮል ፡ ደካማ ፡ ነውና ።
77 ወደነዚያ ፡ ለነርሱ ፡— እጆቻች
ሁን ፡ (ከመጋደል) ፡ ሰብስቡ ፡
ሶላትንም ፡ ደንቡን ፡ ጠብቃችሁ ፡
ስገዱ ፡ ግዴታ ፡ ምጽዋትንም ፡
ስጡ ፡ ወደ ፡ ተባሉት ፡ አላየህ
ምን ? በነርሱም ፡ ላይ ፡ መጋደል ፡
በተጻፈ ፡ ጊዜ ፡ ከነሱ ፡ ከፊሎቹ ፡
ወዲያውኑ ፡ ሰዎችን ፡ አላህን ፡
እንደሚፈሩ ፡ ወይም ፡ የበለጠ ፡
ፍራቻን ፡ ይፈራሉ ፤ ጌታችን ፡
ሆይ ! በኛ ፡ ላይ ፡ መጋደልን ፡
ለምን ፡ ደነገግክ ? እስከ ፡ ቅርብ ፡
ጊዜ ፡ ድረስ ፡ አታቆየንም ፡ ኖሮ
አልን ? ይላሉም ፤ የቅርቢቱ ፡
ሕይወት ፡ ጥቅም ፡ አነስተኛ ፡
ነው ፤ መጨረሻይቱም ፡ ዓለም ፡
አላህን ፡ ለሚፈራ ፡ ሰው ፡ በላጭ ፡
ናት ፤ በተምር ፡ ፍሬ ፡ ውስጥ ፡
ያለን ፡ ክር ፡ያህል ፡ እንኳ ፡ አት
በደሉም ፡ በላቸው ።
78 የትም ፡ ስፍራ ፡ ብትኾኑ ፡ በጠ
ነከሩ ፡ ሕንጻዎች ፡ ውስጥ ፡ ብት

ኾኑም ፡ እንኳ ፡ ሞት ፡ ያገኛች
ኋል ፤ ደግም ፡ ነገር ፡ ብታገኛ
ቸው ፡ ይህች ፡ ከአላህ ፡ ዘንድ ፡
ናት ፡ ይላሉ ፤ መከራም ፡ ብታ
ገኛቸው ፡ ይህቺ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ
ናት ፡ ይላሉ ፤ ሁሉም ፡ (ደጉም ፡
ክፉውም) ፡ ከአላህ ፡ ዘንድ ፡
ነው ፡ በላቸው ፤ ለነዚህም ፡
ሰዎች ፡ ንግግርን ፡ ሊረዱ ፡ የማይ
ቀርቡት ፡ ምን ፡ አላቸው ?
79 ከደግ ፡ ነገር ፡ የሚያገኝህ ፡ ከአ
ላህ ፡ (ችሮታ) ፡ ነው ፤ ከመከራም ፡
የሚደርስብህ ፡ ከራስህ ፡ (ጥፋት ፡
የተነሳ) ፡ ነው ፤ ለሰዎችም ፡ ሁሉ ፡
መልክተኛ ፡ ኾነህ ፡ ላክንህ ፤ መስ
ካሪም ፡ በአላህ ፡ በቃ ።
80 መልክተኛውን ፡ የሚታዘዝ ፡
ሰው ፡ በእርግጥ ፡ አላህን ፡ ታዘዘ ፤
ከትእዛዝም ፡ የሸሸ ፡ ሰው ፡ (አያ
ሳስብህ) ፤ በነሱ ፡ ላይ ፡ ጠባቂ ፡
አድርገን ፡ አልላክንህምና ።
81 (ነገራችን) ፡ መታዘዝ ፡ ነው ፡
ይላሉም ፤ ከአንተም ፡ ዘንድ ፡
በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ከነርሱ ፡ ከፊሎቹ ፡
ከዚያ ፡ (በፊትህ) ፡ ከሚሉት ፡
ሌላን ፡ (በልቦቻቸው) ፡ ያሳድራሉ ፤
አላህም ፡ የሚያሳድሩትን ፡ ነገር ፡
ይጽፋል ፤ ስለዚህ ፡ ተዋቸው ፤
በአላህም ፡ ላይ ፡ ተጠጋ ፤ መጠጊ
ያም ፡ በአላህ ፡ በቃ ።
82 ቁርአንን ፡ አያስተነትኑምን ?
ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ዘንድ ፡ በነበረ ፡
ኖሮ ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ብዙን ፡
መለያየት ፡ ባገኙ ፡ ነበር ።
83 ከጸጥታ ፡ ወይም ፡ ከፍርሃት ፡ አን
ዳች ፡ (ወሬ) ፡ በመጣላቸውም ፡
ጊዜ ፡ እርሱን ፡ ያጋንናሉ ፤ ወደ ፡
መልክተኛውና ፡ ከነርሱ ፡ ወደ ፡
ትእዛዙ ፡ ባለቤቶች ፡ (ወደ ፡ ዐዋ
ቂዎቹ) ፡ በመለሱት ፡ ኖሮ ፡ እነ
ዚያ ፡ ከነርሱ ፡ (ነገሩን) ፡ የሚያ
ውጣጡት ፡ (1) ባወቁት ፡ ነበር ።
በእናንተም ፡ ላይ ፡ የአላህ ፡ ችሮ
ታና ፡ እዝነቱ ፡ ባልነበረ ፡ ኖሮ ፡
ከጥቂቶች ፡ በስተቀር ፡ ሰይጣንን ፡
በተከተላችሁ ፡ ነበር ።
84 በአላህም ፡ መንገድ ፡ ተጋደል ፤
ራስህን ፡ እንጅ ፡ ሌላን ፡ አትገደ
ድም ፤ ምእምናንንም ፡ (በመጋ
ደል ፡ ላይ) ፡ አደፋፍር ፤ አላህ ፡
የነዚያን ፡ የካዱትን ፡ ኀይል ፡ ሊከ
ለክል ፡ ይከጀላል ፤ አላህም ፡ በኀ
ይል ፡ በመያዙ ፡ የበረታ ፡ ቅጣ
ቱም ፡ የጠነከረ ፡ ነው ።
85 መልካም ፡ መታደግን ፡ የሚታ
ደግ ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡ ከርስዋ ፡
ዕድል ፡ ይኖረዋል ፤ መጥፎ ፡ መታ
ደግንም ፡ የሚታደግ ፡ ሰው ፡
ለርሱ ፡ ከርስዋ ፡ ድርሻ ፡ ይኖረ
ዋል ። አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ቻይ ፡ ነው ።
86 በሰላምታ ፡ በተከበራችሁም ፡
ጊዜ ፡ ከርሷ ፡ ይበልጥ ፡ ባማረ ፡
(ሰላምታ) ፡ አክብሩ ፤ ወይም ፡
(እርሷኑ) ፡ መልሷት ። አላህ ፡ በነ
ገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ተቆጣጣሪ ፡
ነውና ።
87 አላህ ፡ ከርሱ ፡ በስተቀር ፡ አም
ላክ ፡ የለም ፤ ወደ ፡ ትንሣኤ ፡
ቀን ፡ በርሱ ፡ ጥርጥር ፡ የሌለበት ፡
ሲኾን ፡ በእርግጥ ፡ ይሰበስባች
ኋል ። በንግግርም ፡ ከአላህ ፡ ይበ
ልጥ ፡ እውነተኛ ፡ ማነው ?
88 በመናፍቃንም፡ (ነገር) ፡ አላህ ፡
በሥራዎቻቸው ፡ ወደ ፡ ክሕደት ፡
የመለሳቸው ፡ ሲኾኑ ፡ ሁለት ፡
ክፍሎች ፡ የኾናችሁት ፡ ለናንተ ፡

---

1 የሚደበቅ ፡ ወይም ፡ የሚነገር ፡ መኾኑን ።



ምን ፡ አላችሁ ? አላህ ፡ ያጠመመ
ውን ፡ ሰው ፡ ልታቀኑ ፡ ታስባላች
ሁን ? አላህም ፡ ያሳሳተውን ፡
ሰው ፡ ለርሱ ፡ መንገድን ፡ ፈጽሞ ፡
አታገኝለትም ።
89 (እነሱ) ፡ እንደ ፡ ካዱ ፡ ብትክዱና ፡
እኩል ፡ ብትኾኑ ፡ ተመኙ ! በአላ
ህም ፡ ሃይማኖት ፡ እስከሚሰደዱ ፡
ድረስ ፡ ከነሱ ፡ ወዳጆችን ፡ አት
ያዙ ፤ (ከእምነት) ፡ ቢያፈገፍጉም፡
ያዙዋቸው ፤ (ማርኩዋቸው) ።
ባገኛችሁበትም ፡ ስፍራ ፡ ግደሉ
ዋቸው ፤ ከነሱም ፡ ወዳጅንና ፡
ረዳትን ፡ አትያዙ ።
90 እነዚያ ፡ በናንተና ፡ በነርሱ ፡
መካከል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ወዳላ
ቸው ፡ ሕዝቦች ፡ የሚጠጉና ፡
ወይም ፡ እናንተን ፡ ለመጋደል ፡
ወይም ፡ ወገኖቻቸውን ፡ ለመጋ
ደል ፡ ልቦቻቸው ፡ የተጨነቁ ፡
ኾነው ፡ የመጧዋችሁ ፡ ሲቀሩ ፤
(እነዚያንስ ፡ አትጋደሉዋቸው) ፤
አላህም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ በእናንተ ፡
ላይ ፡ ኀይል ፡ በሰጣቸውና ፡ በተ
ጋደሉዋችሁ ፡ ነበር ፤ ቢተዋች
ሁና ፡ ባይጋደሉዋችሁም፥ ወደ ፡
እናንተም ፡ ዕርቅን ፡ ቢያቀርቡ ፡
አላህ ፡ ለናንተ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
(የመጋደል) ፡ መንገድን ፡ አላ
ደረገም ።
91 ሌሎችንም ፡ ከናንተ ፡ ለመዳን ፡
ከወገኖቻቸውም ፡ ለመዳን ፡ የሚ
ፈልጉን ፡ ታገኛላችሁ ፤ ወደ ፡
እውከት ፡ እንዲመለሱ ፡ በተ
ጠሩ ፡ ቍጥር ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡
ይመለሳሉ ፤ ባይተውዋችሁና ፡
እርቅንም ፡ ባያቀርቡላችሁ ፡ እጆ
ቻቸውንም ፡ ባይሰበስቡ ፡ ባገኛ
ችኋቸው ፡ ስፍራ ፡ ማርኩዋቸው ፤
ግደሉዋቸውም ፤ እነዚያችሁ ፡
ለእናንተ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ግልጽ ፡
ማስረጃን ፡ አድርገናል ።
92 ለምእምንም ፡ በስሕተት ፡ ካል
ኾነ ፡ በቀር ፡ ምእምንን ፡ መግ
ደል ፡ አይገባውም ። ምእምንንም፡
በስሕተት ፡ የገደለ ፡ ሰው ፡ ያመነ
ችን ፡ ጫንቃ ፡ ነጻ ፡ ማውጣትና ፡
ወደ ፡ ቤተሰቦቹም ፡ የምትሰጥ ፡
ጉማ ፡ ምሕረት ፡ ካላደረጉለት ፡
በስተቀር ፡ (መክፈል) ፡ አለበት ።
እርሱ ፡ (ተገዳዩ) ፡ ምእምን ፡
ሲኾን ፡ ለናንተ ፡ ጠላት ፡ ከኾኑ
ትም ፡ ሕዝቦች ፡ ቢኾን ፡ ያመነ
ችን ፡ ጫንቃ ፡ ነጻ ፡ ማውጣት ፡
(ብቻ) ፡ አለበት ፤ በናንተና ፡
በነሱ ፡ መካከል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
ካላቸውም ፡ ሕዝቦች ፡ ቢኾን ፡
ወደ ፡ ቤተሰቦቹ ፡ በእጅ ፡ የምት
ሰጥ ፡ ጉማና ፡ ያመነችን ፡ ጫንቃ ፡
ነጻ ፡ ማውጣት ፡ አለበት ፤ ያላገኘ ፡
ሰውም ፡ ተከታታዮችን ፡ ሁለት ፡
ወሮች ፡ መጾም ፡ አለበት ፤ አላህ ፡
መጸጸትን ፡ ለመቀበል ፡ (ደነገገ
ላችሁ) ፡ አላህም ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበ
በኛ ፡ ነው ።
93 ምእምንንም ፡ አስቦ ፡ የሚገድል ፡
ሰው ፡ ቅጣቱ ፡ በውስጧ ፡ ዘው
ታሪ ፡ ሲኾን ፡ ገሀነም ፡ ናት ፤ አላ
ህም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተቆጣ ፤ ረገ
መውም ፤ ለርሱም ፡ ከባድ ፡ ቅጣ
ትን ፡ አዘጋጀ ።
94 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! በአ
ላህ ፡ መንገድ ፡ (ለመጋደል) ፡
በተጓዛችሁ ፡ ጊዜ ፡ አስረግጡ ፤
ሰላምታንም ፡ ወደናንተ ፡ ላቀ
ረበ ፡ ሰው ፡ የቅርቢቱን ፡ ሕይ
ወት ፡ ጥቅም ፡ የምትፈልጉ ፡
ኾናችሁ ፡ ምእምን ፡ አይደለህም ፡

አትበሉ ፤ አላህም ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡
ዘረፋዎች ፡ አሉ ፤ ከዚህ ፡
በፊት ፡ እንደዚሁ ፡ ነበራችሁ ፤
አላህም ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ለገሰ ፤
ስለዚህ ፡ አስተውሉ ፤ አላህ ፡
በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ውስጠ ፡
ዐዋቂ ፡ ነውና ።
95 ከምእምናን ፡ የጉዳት ፡ ባለቤት ፡
ከኾኑት ፡ በቀር ፡ ተቀማጮቹና ፡
በአላህ ፡ መንገድ ፡ በገንዘቦቻቸ
ውና ፡ በነፍሶቻቸው ፡ የሚታገ
ሉት ፡ አይተካከሉም ፤ በገንዘቦቻ
ቸውና ፡ በነፍሶቻቸው ፡ የሚታገ
ሉትን ፡ አላህ ፡ በተቀማጮቹ ፡
ላይ ፡ በደረጃ ፡ አበለጠ ፤ ለሁ
ሉም ፡ አላህ ፡ መልካሚቱን ፡
(ገነት) ፡ ተስፋ ፡ ሰጠ ። ታጋዮ
ቹንም ፡ በተቀማጮቹ ፡ ላይ ፡
አላህ ፡ በታላቅ ፡ ምንዳ ፡ አበለጠ።
96 ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ በኾኑ ፡ ደረጃ
ዎች ፡ (አበለጠ) ፤ ምሕረትንም ፡
አደረገ ፤ እዝነትም ፡ አዘነላቸው ፤
አላህም ፡ መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።
97 እነዚያ ፡ (ለእምነት ፡ ባለመሰ
ደድ) ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ በዳዮች ፡
ኾነው ፡ መላእክት ፡ (በበድር) ፡
የገደሉዋቸው ፡ (መላእክት ፡ ለነ
ርሱ) ፡ በምን ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ነበራ
ችሁ ? አሏቸው ፤ በምድር ፡
ውስጥ ፡ ደካሞች ፡ ነበርን ፡ አሉ ፤
የአላህ ፡ ምድር ፡ ትሰደዱባት ፡
ዘንድ፡ ሰፊ፡ አልነበረችምን? አሉ
ዋቸው ፤ እነዚያም ፡ መኖሪያቸው፡
ገሀነም ፡ ናት ፤ በመመለሻነትም ፡
ከፋች !
98 ግን ፡ ከወንዶችና ፡ ከሴቶች ፡
ከሕፃናትም ፡ ሲኾኑ ፡ (ለመው
ጣት) ፡ መላን ፡ የማይችሉና ፡ መን
ገድንም ፡ የማይምመሩ ፡ (1) ደካ
ሞች ፡ (ቅጣት ፡ የለባቸውም) ፤
99 እነዚያም ፡ አላህ ፡ ከነርሱ ፡ ይቅ
ርታ ፡ ሊያደርግ ፡ ይሻል ፤ አላ
ህም ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ መሐሪ ፡
ነው ።
100 በአላህም ፡ መንገድ ፡ የሚሰደድ ፡
ሰው ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡
መሰደጃንና ፡ ምቾትን ፡ ያገኛል ።
ወደ ፡ አላህና ፡ ወደ ፡ መልክተ
ኛውም ፡ ስደተኛ ፡ ኾኖ ፡ ከቤቱ ፡
የሚወጣ ፡ ከዚያም ፡ (በመንገድ) ፡
ሞት ፡ የሚያገኘው ፡ ሰው ፡ ምን
ዳው ፡ በእርግጥ ፡ በአላህ ፡ ዘንድ ፡
ተረጋገጠ ። አላህም ፡ መሐሪ ፡
አዛኝ ፡ ነው ።
101 በምድርም፡ ላይ፡ በተጓዛችሁ፡
ጊዜ፥ እነዚያ፡ የካዱት፡ ያውኩ
ናል፡ ብላችሁ፡ ብትፈሩ፥ ከሶላት፡
(ባለአራት፡ ረከዓት፡ የኾኑትን)፡
ብታሳጥሩ፥ በናንተ፡ ላይ፡ ኀጢ
አት፡ የለም፤ ከሓዲዎች፡ ለናንተ፡
በእርግጥ፡ ግልጽ፡ ጠላቶች፡
ናቸውና።
102 በውስጣቸውም ፡ በኾንክና ፡ ሶላ
ትን ፡ ለነርሱ ፡ ባስሰገድካቸው ፡
ጊዜ ፡ ከነሱ ፡ አንዲት ፡ ጭፍራ ፡
ካንተ ፡ ጋር ፡ ትቁም ፤ መሣሪያ
ዎቻቸውንም ፡ ይያዙ ። በግንባራ
ቸውም ፡ በተደፉ ፡ ጊዜ ፡ ከስተኋ
ላችሁ ፡ ይኹኑ ፤ (እነዚህ ፡ ይኺ
ዱና) ፡ ያልሰገዱትም ፡ ሌሎቹ ፡
ጭፍሮች ፡ ይምጡ ፤ ከአንተም ፡
ጋር ፡ ይስገዱ ፤ ጥንቃቄያቸው
ንና ፡ መሣሪያዎቻቸውንም ፡ ይ
ያዙ ። እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ከመሣሪ
ያዎቻችሁና ፡ ከጓዞቻችሁ ፡ ብት
ዘነጉና ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ አንዲ

1 የማያውቁ ።



ትን ፡ መዘንበል ፡ ቢዘነበሉ ፡
ተመኙ ፤ ከዝናብም ፡ የኾነ ፡
ችግር ፡ በናንተ ፡ ቢኖር ፡ ወይም ፡
ሕመምተኞች ፡ ብትኾኑ ፡ መሣሪ
ያዎቻችሁን ፡ ብታስቀምጡ ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ የለም ፤
ጥንቃቄያችሁንም ፡ ያዙ ፡ አላህ ፡
ለከሓዲዎች ፡ አዋራጅን ፡ ቅጣት ፡
አዘጋጀ ።
103 ሶላትንም ፡ በፈጸማችሁ ፡ ጊዜ ፡
ቆማችሁም ፡ ተቀምጣችሁም ፡
በጐኖቻችሁም ፡ ላይ ፡ ተጋድ
ማችሁ ፡ አላህን ፡ አውሱ ። በረጋ
ችሁም ፡ ጊዜ ፡ ሶላትን ፡ (አሟል
ታችሁ) ፡ ስገዱ ። ሶላት ፡ በምእ
ምናን ፡ ላይ ፡ በጊዜያት ፡ የተወ
ሰነች ፡ ግዴታ ፡ ናትና ።
104 ሰዎቹንም ፡ በመፈለግ ፡ አትስ
ነፉ ፤ (ስትቃስሉ) ፡ የምትታመሙ
ብትኾኑ ፡ እናንተ ፡ እንደምትታ
መሙ ፡ እነሱም ፡ ይታመማሉ ፤
የማይከጅሉትንም ፡ ከአላህ ፡ ትከ
ጅላላችሁ ። አላህም ፡ ዐዋቂ ፡
ጥበበኛ ፡ ነው ።
105 እኛ ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ አላህ ፡
ባሳወቀህ ፡ ልትፈርድ ፡ ወደ ፡
አንተ ፡ መጽሐፉን ፡ በውነት ፡
አወረድን ፤ ለከዳተኞችም ፡ ተከ
ራካሪ ፡ አትኹን ።
106 አላህንም ፡ ምሕረትን ፡ ለምን ፤
አላህ ፡ መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።
107 ከነዚያም ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ ከሚ
በድሉት ፡ ላይ ፡ አትከራከር ፤
አላህ ፡ ከዳተኛ ፡ ኀጢአተኛ ፡ የኾ
ነን ፡ ሰው ፡ አይወድምና ።
108 ከሰው ፡ ይደበቃሉ ፤ አላህም ፡
እርሱ ፡ (በዕውቀቱ) ፡ ከነሱ ፡
ጋር ፡ ሲኾን ፡ ከንግግር ፡ የማይወ
ደውን ፡ ነገር ፡ (በልቦቻቸው) ፡
በሚያሳድሩ ፡ ጊዜ ፡ (ከርሱ) ፡ አይ
ደበቁም ። አላህም ፡ በሚሠሩት ፡
ሁሉ ፡ (በዕውቀቱ) ፡ ከባቢ ፡
ነው ።
109 እነሆ ፡ እናንተ ፡ እነዚያ ፡ በቅር
ቢቱ ፡ ሕይወት ፡ ከነሱ ፡ የተከራከ
ራችሁ ፡ ናችሁ ፤ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡
አላህን ፡ ስለነሱ ፡ የሚከራከር ፡
ማን ፡ ነው ? ወይስ ፡ ለነሱ ፡
ኃላፊና፡ መመኪያ ፡ የሚኾን ፡
ማን ፡ ነው ?
110 መጥፎም ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡
ወይም ፡ ነፍሱን ፡ የሚበድል ፡
ከዚያም ፡ (ተጸጽቶ) ፡ አላህን ፡
ምሕረትን ፡ የሚለምን ፡ አላህን ፡
መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ኾኖ ፡ ያገኘዋል ።
111 ኀጢአትንም ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡
የሚሠራው ፡ ጥፋት ፡ በራሱ ፡
ላይ ፡ ነው ፤ አላህም ፡ ዐዋቂ ፡
ጥበበኛ ፡ ነው ፤
112 ኀጢአትን ፡ ወይም ፡ አበሳን ፡
የሚሠራም ፡ ሰው ፡ ከዚያም ፡
በርሱ ፡ ንጹሕን ፡ ሰው ፡ የሚሰ
ድብ ፡ ቅጥፈትንና ፡ ግልጽ ፡ አበ
ሳን ፡ በቁርጥ ፡ ተሸከመ ።
113 የአላህም ፡ ችሮታና ፡ እዝነቱ ፡
ባንተ ፡ ላይ ፡ ባልነበረ ፡ ኖሮ ፡
ከነሱ ፡ የኾኑ ፡ ጭፍሮች ፡ ሊያሳ
ስቱህ ፡ ባሰቡ ፡ ነበር ፤ ነፍሶቻቸ
ውንም ፡ እንጅ ፡ ሌላን ፡ አያሳስ
ቱም ፤ በምንም ፡ አይጐዱህም ።
አላህም ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ መጽሐ
ፍንና ፡ ጥበብን ፡ አወረደ ፤ የማታ
ውቀውንም ፡ ሁሉ ፡ አስተማረህ ።
የአላህም ፡ ችሮታ ፡ በአንተ ፡
ላይ ፡ ታላቅ ፡ ነው ።
114 ከውይይታቸው ፡ በምጽዋት ፡
ወይም ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡
በሰዎች ፡ መካከል ፡ በማስታረቅ ፡

ከሚያዙ ፡ ሰዎች ፡ ውይይት ፡ በስ
ተቀር ፡ በብዙው ፡ ውስጥ ፡ ደግ ፡
ነገር ፡ የለበትም ። ይኸንንም ፡
(የተባለውን) ፡ የአላህን ፡ ውዴታ፡
ለመፈለግ ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡
ታላቅ ፡ ምንዳን ፡ እንሰጠዋለን ።
115 ቅኑም ፡ መንገድ ፡ ለርሱ ፡ ከተገ
ለጸ ፡ በኋላ ፡ መልክተኛውን ፡
የሚጨቃጨቅና ፡ ከምእምናኖቹ ፡
መንገድ ፡ ሌላ ፡ የኾነን ፡ የሚከ
ተል ፡ ሰው ፡ (በዚህ ፡ ዓለም) ፡
በተሾመበት ፡ (ጥመት) ፡ ላይ ፡
እንሾመዋለን ፣ (1) ገሀነምንም ፡
እናገባዋለን ፣ መመለሻይቱም ፡
ከፋች !
116 አላህ፡ በርሱ፡ የማጋራትን፡ (ወን
ጀል)፡ አይምርም፣ ከዚህም፡
ወዲያ፡ ያለውን፥ ለሚሻው፡ ሰው፡
ይምራል። በአላህም፡ የሚያጋራ፡
ሰው፣ (ከውነት)፡ የራቀን፡
መሳሳት፡ በእርግጥ፡ ተሳሳተ።
117 ከርሱ ፡ ሌላ ፡ እንስታትን ፡ (2)
እንጅ ፡ አይግገዙም ፣ አመጠኛ ፡
ሰይጣንንም ፡ እንጅ ፡ ሌላን ፡ አይ
ግገዙም ።
118 አላህ ፡ የረገመውን ፡ ከባሮችህም ፡
የተወሰነን ፡ ድርሻ ፡ በእርግጥ ፡
እይዛለሁ ፡ ያለውን ፡ (ሰይጣን ፡
እንጅ ፡ ሌላን ፡ አይከተሉም) ።
119 በእርግጥ ፡ አጠማቸዋለሁም ፣
(ከንቱን) ፡ አስመኛቸዋለሁም ፣
አዛቸውምና ፡ የእንስሶችን ፡ ጆሮ
ዎች ፡ ይተለትላሉ ፣ አዛቸውምና ፡
የአላህን ፡ ፍጥረት ፡ ይለውጣሉ ፣
(ያለውን ፡ ይከተላሉ) ፣ ከአላ
ህም ፡ ሌላ ፡ ሰይጣንን ፡ ረዳት ፡
አድርጎ ፡ የሚይዝ ፡ ሰው ፡ ግልጽ፡
ክስረትን፡ በእርግጥ፡ ከሰረ።
120 (የማይፈጸመውን) ፡ ተስፋ ፡ ይሰ
ጣቸዋል ፣ ያስመኛቸዋልም ፣ ሰይ
ጣንም ፡ ለማታለል ፡ እንጅ ፡ አይ
ቀጥራቸውም ።
121 እነዚያ ፡ መኖሪያቸው ፡ ገሀነም ፡
ናት ፣ ከርስዋም ፡ መሸሻን ፡ አያ
ገኙም ።
122 እነዚያም ፡ ያመኑና ፡ በጎ ፡ ሥራ
ዎችን ፡ የሠሩ ፡ በስራቸው ፡
ወንዞች ፡ የሚፈሱባቸውን ፡ ገነ
ቶች ፡ ዘላለም ፡ በውስጣቸው ፡
ዘውታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ እናገባቸዋ
ለን ፣ አላህ ፡ እውነተኛን ፡ ተስፋ ፡
ሰጣቸው ። በንግግርም ፡ ከአላህ ፡
ይበልጥ ፡ እውነተኛ ፡ ማን፡ ነው?
123 (ነገሩ) ፡ በምኞታችሁና ፡ በመጽ
ሐፉ ፡ ሰዎች ፡ ምኞት ፡ አይደ
ለም ፣ መጥፎን ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡
በርሱ ፡ ይቀጣል ፣ ለርሱም ፡ ከአ
ላህ ፡ ሌላ ፡ ጠባቂንም ፡ ረዳት
ንም ፡ አያገኝም ።
124 ከወንድ ፡ ወይም ፡ ከሴት ፡ እርሱ ፡
አማኝ ፡ ኾኖ ፡ ከበጎ ፡ ሥራዎች ፡
አንዳችን ፡ የሚሠራም ፡ ሰው ፡
እነዚያ ፡ ገነትን ፡ ይገባሉ ፣ በተ
ምር ፡ ፍሬ ፡ ላይ ፡ ያለችን ፡ ነጥብ ፡
ያክል ፡ እንኳ ፡ አይበደሉም ።
125 እርሱ ፡ መልካም ፡ ሠሪ ፡ ኾኖ ፡
ፊቱን ፡ ለአላህ ፡ ከሰጠና ፡ የኢብ
ራሂምንም ፡ መንገድ ፡ ቀጥተኛ ፡
ሲኾን ፡ ከተከተለ ፡ ሰው ፡ ይበ
ልጥ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ያማረ ፡ ማን ፡
ነው ? አላህም ፡ ኢብራሂምን ፡
ፍጹም ፡ ወዳጅ ፡ አድርጎ ፡ ያዘው ።
126 በሰማያት ፡ ያለውና ፡ በምድር ፡
ያለው ፡ ሁሉ ፡ የአላህ ፡ ነው ።

1 በመረጠው ፡ ላይ ፡ እንተወዋለን ።
2 በእንስት፡ ስም፡ የሚጠሩዋቸውን፡ ጣዖታት፡
ላት፥ ዑዛ፥ መናት፥ መላእክት፥...
ቸውን ።



አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ በዕው
ቀት ፡ ከባቢ ፡ ነው ።
127 በሴቶችም ፡ ነገር ፡ ያስተቹሃል ፤
አላህ ፡ በነርሱ ፡ ይነግራችኋል ፤
ያም ፡ በመጽሐፉ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
የሚነበበው ፡ በነዚያ ፡ ለነርሱ ፡
(ከውርስ) ፡ የተጻፈላቸውን ፡ በማ
ትሰጧቸውና ፡ ልታገቧቸው ፡ በ
ማትፈልጉት ፡ የቲሞች ፡ ሴቶች ፡
(ይህንን ፡ እንዳታደርጉ) ፡ ከሕፃና
ትም ፡ ለኾኑት ፡ ደካሞች ፡ መብ
ታቸውን ፡ እንድትሰጡ ፤ ለየቲሞ
ችም ፡ በትክክል ፡ እንድትቆሙ ፡
(ይነግራችኋል) ፡ በላቸው ። ከበጎ
ም ፡ ሥራ ፡ ማናቸውንም ፡ ብትሠ
ሩ ፡ አላህ ፡ እርሱን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
128 ሴትም ፡ ከባልዋ ፡ ጥላቻን ፡
ወይም ፡ ፊቱን ፡ ማዞርን ፡ ብታ
ውቅ ፡ በመካከላቸው ፡ መስማማ
ትን ፡ ቢስማሙ ፡ በሁለቱ ፡ ላይ ፡
ኀጢአት ፡ የለም ። መታረቅም ፡
መልካም ፡ ነው ። ነፍሶችም ፡
ንፍገት ፡ ተጣለባቸው ። መልካ
ምም ፡ ብትሠሩ ፡ ብትጠነቀቁም ፡
አላህ ፡ በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡
ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
129 በሴቶችም ፡ መካከል ፡ ምንም ፡
እንኳ ፡ ብትጓጉ ፡ (በፍቅር) ፡ ለማ
ስተካከል ፡ አትችሉም ። እንደ ፡
ተንጠለጠለችም ፡ አድርጋችሁ ፡
ትተዋት ፡ ዘንድ ፡ (ወደምትወ
ዱት) ፡ መዝዘንበልን፡ ሁሉ፣ አት
ዝዘንበሉ ፣ ብታበጁም ፡ ብትጠነ
ቀቁም ፡ አላህ ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡
ነው ።
130 ቢለያዩም ፡ አላህ ፡ ሁሉንም ፡
በችሮታው ፡ ያብቃቃቸዋል ።
አላህም ፡ ችሮታው ፡ ሰፊ ፡ ጥበ
በኛ ፡ ነው ።
131 በሰማያት ፡ ያለውና ፡ በምድርም ፡
ያለው ፡ ሁሉ ፡ የአላህ ፡ ነው ።
እነዚያንም ፡ ከበፊታችሁ ፡ መጽ
ሐፍን ፡ የተሰጡትን ፡ እናንተንም፡
አላህን ፡ ፍሩ ፡ በማለት ፡ በእር
ግጥ ፡ አዘዝን ፤ ብትክዱም ፡ በሰ
ማያትና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡ ሁሉ፡
የአላህ ፡ ነው ፤ (አትጎዱትም) ፤
አላህም ፡ ተብቃቂ ፡ ምስጉን ፡
ነው ።
132 በሰማያት ፡ ያለውና ፡ በምድርም ፡
ያለው ፡ ሁሉ ፡ የአላህ ፡ ነው ፤
መመኪያም ፡ በአላህ ፡ በቃ ።
133 ሰዎች ፡ ሆይ ! (አላህ) ፡ ቢሻ ፡
ያስወግዳችኋል ፤ ሌሎችንም ፡
ያመጣል ፤ አላህም ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡
ቻይ ፡ ነው ።
134 የቅርቢቱን ፡ ዓለም ፡ ምንዳ ፡ የሚ
ፈልግ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ አላህ ፡
ዘንድ ፡ የቅርቢቱና ፡ የመጨረሻ
ይቱ ፡ ምንዳ ፡ አለለ ። አላህም ፡
ሰሚ ፡ ተመልካች ፡ ነው ።
135 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! በት
ክክል ፡ (ፍትሕ) ፡ ቀዋሚዎች ፡
በነፍሶቻችሁ ፡ ወይም ፡ በወላጆ
ችና ፡ በቅርብ ፡ ዘመዶች ፡ ላይ ፡
ቢኾንም ፡ እንኳ ፡ ለአላህ ፡ መስካ
ሪዎች ፡ ኹኑ ። ሀብታም ፡ ወይም ፡
ድኻ ፡ ቢኾን ፡ አላህ ፡ በነርሱ ፡
(ከናንተ) ፡ ይበልጥ ፡ ተገቢ ፡
ነው ። እንዳታደሉም ፡ ዝንባሌን ፡
አትከተሉ ። ብታጣምሙም ፡
ወይም ፡ (መመስከርን) ፡ ብት
ተው ፡ አላህ ፡ በምትሠሩት ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።
136 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! በአ
ላህና ፡ በመልክተኛው ፡ በዚያም ፡
በመልክተኛው ፡ ላይ ፡ ባወረደው፡

መጽሐፍ ፡ በዚያም ፡ ከበፊቱ ፡
ባወረደው ፡ መጽሐፍ ፡ እመኑ ፤
በአላህና ፡ በመላእክቱም ፡ በመጽ
ሐፎቹም ፡ በመልክተኞቹም ፡
በመጨረሻውም ፡ ቀን ፡ የካደ ፡
ሰው ፡ (ከውነት) ፡ የራቀን ፡ መሳ
ሳት ፡ በእርግጥ ፡ ተሳሳተ ።
137 እነዚያ ፡ (በሙሳ) ፡ ያመኑና ፡ ከዚ
ያም ፡ (ወይፈንን ፡ በመግገዛት) ፡
የካዱ ፡ ከዚያም ፡ (በርሱ) ፡ ያመኑ ፡
ከዚያም ፡ (በዒሳ) ፡ የካዱ ፡ ከዚ
ያም ፡ (በሙሐመድ) ፡ ክሕደትን ፡
የጨመሩ ፡ አላህ ፡ ለነሱ ፡ የሚም
ራቸውና ፡ ቅኑን ፡ መንገድ ፡ የሚ
መራቸው ፡ አይደለም ።
138 መናፍቃንን ፡ ለነርሱ ፡ አሳማሚ ፡
ቅጣት ፡ ያላቸው ፡ መኾኑን ፡ አብ
ስራቸው ።
139 እነዚያ ፡ ከምእምናን ፡ ሌላ ፡ ከሐ
ዲዎችን ፡ ወዳጆች ፡ አድርገው ፡
የሚይዙ ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ ልቅ
ናን ፡ ይፈልጋሉን ? ልቅናም ፡
ሁሉ ፡ ለአላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
140 በእናንተም ፡ ላይ ፡ በመጽሐፉ ፡
ውስጥ (1) የአላህን ፡ አንቀጾች ፡
በርሷ ፡ ሲካድባትና ፡ በርሷም ፡
ሲላገጥባት ፡ በሰማችሁ ፡ ጊዜ ፡
በሌላ ፡ ወሬ ፡ ውስጥ ፡ እስከሚ
ገቡ ፡ ድረስ ፡ ከእነሱ ፡ ጋር ፡ አት
ቀመጡ ፡ ማለትን ፡ በእርግጥ ፡
አወረደ ፤ እናንተ ፡ ያንጊዜ ፡ ብጤ
ያቸው ፡ ናችሁና ፤ አላህ ፡ መናፍ
ቃንን፡ እና፡ ከሐዲዎችን፡ በሙሉ፡
በገሀነም፡ ውስጥ፡ ሰብሳቢ፡
ነውና።
141 እነዚያ ፡ በእናንተ ፡ (የጊዜን ፡
መዘዋወር) ፡ የሚጠባበቁ ፡ ናቸው ፤
ለናንተም ፡ ከአላህ ፡ የኾነ ፡ አሸና
ፊነት ፡ ቢኖራችሁ ፡ ከናንተ ፡
ጋር ፡ አልነበርንምን ? ይላሉ ፤
ለከሓዲዎችም ፡ ዕድል ፡ ቢኖር ፡
(ከአሁን ፡ በፊት) ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
አልተሾምንምን ? (እና ፡ አልተው
ናችሁምን ?) ከምእምናንም ፡
(አደጋ) ፡ አልከለከልናችሁምን ?
ይላሉ ። አላህም ፡ በትንሣኤ ፡
ቀን ፡ በመካከላችሁ ፡ ይፈርዳል ፤
አላህም ፡ ለከሓዲዎች ፡ በምእም
ናን ፡ ላይ ፡ መንገድን ፡ በፍጹም ፡
አያደርግም ።
142 መናፍቃን ፡ አላህን ፡ ያታልላሉ ፤
እርሱም ፡ አታላያቸው ፡ ነው ፤
(ይቀጣቸዋል) ፤ ወደ ፡ ሶላትም ፡
በቆሙ ፡ ጊዜ ፡ ታካቾች ፡ ሰዎ
ችን ፡ የሚያሳዩ ፡ ኾነው ፡ ይቆ
ማሉ ፤ አላህንም ፡ ጥቂትን ፡
እንጅ ፡ አያወሱም ።
143 በዚህ ፡ መካከል ፡ ወላዋዮች ፡
ኾነው ፡ (ያሳያሉ) ፡ ወደነዚህም ፡
ወደነዚያም ፡ አይደሉም ፤ አላ
ህም ፡ ያሳሳተውን ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡
(የቅንነት) ፡ መንገድን ፡ በፍጹም ፡
አታገኝለትም ።
144 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ከም
እምናን ፡ ሌላ ፡ ከሓዲዎችን ፡
ወዳጆች ፡ አድርጋችሁ ፡ አትያዙ ፤
ለአላህ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ግልጽ ፡
ማስረጃዎችን ፡ ልታደርጉ ፡ ትፈ
ልጋላችሁን ?
145 መናፍቃን ፡ በእርግጥ ፡ ከእሳት ፡
በታችኛው ፡ አዘቅት ፡ ውስጥ ፡
ናቸው ፤ ለነሱም ፡ ረዳትን ፡ አታ
ገኝላቸውም ።
146 እነዚያ ፡ የተመለሱ ፡ (ሥራቸ
ውን) ፡ ያሳመሩም ፤ በአላህም ፡
የተጠበቁ ፤ ሃይማኖታቸውንም ፡

---
1 በቁርአን ፡ በአንዓም ፡ ምዕራፍ ፡ አንቀጽ ፡ ፷፰ ፤



ለአላህ ፡ ፍጹም ፡ ያደረጉ ፡ ሲቀሩ ፡
እነዚያስ ፡ ከምእምናን ፡ ጋር ፡
ናቸው ፤ ለምእምናንም ፡ አላህ ፡
ታላቅን ፡ ምንዳ ፡ በእርግጥ ፡ ይሰ
ጣል ።
147 ብታመሰግኑና ፡ ብታምኑ ፡ አላህ ፡
እናንተን ፡ በመቅጣት ፡ ምን ፡
ያደርጋል ? አላህም ፡ ወረታን ፡
መላሽ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

★ ★ ★

148 አላህ ፡ ከንግግር ፡ በክፉው ፡ መጮ
ህን ፡ ከተበደለ ፡ ሰው ፡ (ጩኸት) ፡
በቀር ፡ አይወድም ፤ አላህ ፡ ሰሚ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።
149 ደግ ፡ ነገርን ፡ ብትገልጹ ፡ ወይም ፡
ብትደብቁት ፡ ወይም ፡ ከመጥፎ ፡
ነገር ፡ (ከበደል) ፡ ይቅርታ ፡ ብታ
ደርጉ ፡ አላህ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡
ኃያል፡ ነው።
150 እነዚያ ፡ በአላህና ፡ በመልክተ
ኞቹ ፡ የሚክዱ ፡ በአላህና ፡ በመ
ልክተኞቹም ፡ መካከል ፡ መለየ
ትን ፡ የሚፈልጉ ፡ በከፊሉም ፡
እናምናለን ፡ በከፊሉም ፡ እንክ
ዳለን ፡ የሚሉ ፡ በዚህም ፡ መካ
ከል ፡ መንገድን ፡ ሊይዙ ፡ የሚ
ፈልጉ ፤
151 እነዚያ ፡ በውነት ፡ ከሓዲዎቹ ፡
እነርሱ ፡ ናቸው ። ለከሓዲዎችም ፡
አዋራጅን ፡ ቅጣት ፡ አዘጋጅ
ተናል ።
152 እነዚያም ፡ በአላህና ፡ በመልክተ
ኞቹ ፡ ያመኑ ፡ ከነሱም ፡ በአን
ድም ፡ መካከል ፡ ያልለዩ ፡ እነ
ዚያ ፡ ምንዳዎቻቸውን ፡ በእር
ግጥ ፡ ይሰጣቸዋል ። አላህም ፡
መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።
153 የመጽሐፉ ፡ ሰዎች ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
ከሰማይ ፡ መጽሐፍን ፡ እንድታ
ወርድ ፡ ይጠይቁሃል ፤ ከዚያም ፡
የከበደን ፡ ሙሳን ፡ በእርግጥ ፡
ጠይቀዋል ፤ አላህንም ፡ በግልጽ ፡
አሳየን ፡ ብለዋል ፤ በበደላቸውም ፡
መብረቅ ፡ ያዘቻቸው ። ከዚያም ፡
ታምራቶች ፡ ከመጡዋቸው ፡ በ
ኋላ ፡ ወይፈኑን ፡ (አምላክ ፡ አድ
ርገው) ፡ ያዙ ፤ ከዚያም ፡ ይቅር ፡
አልን ። ሙሳንም ፡ ግልጽ ፡ ስል
ጣንን ፡ ሰጠነው ።
154 በቃል ፡ ኪዳናቸውም ፡ ምክን
ያት ፡ የጡርን ፡ ተራራ ፡ ከበላያ
ቸው ፡ አነሳን ፤ ለነሱም ፡ ደጃ
ፉን ፡ አጐንባሾች ፡ ኾናችሁ ፡
ግቡ ፡ አልን ፤ ለነርሱም ፡ በሰን
በት ፡ ቀን ፡ ትእዛዝን ፡ አትተላ
ለፉ ፡ አልን ፤ ከነሱም ፡ ከባድን ፡
ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያዝን ።
155 ቃል ፡ ኪዳናቸውንም ፡ በማፍረሳ
ቸው ፡ በአላህም ፡ አንቀጾች ፡ በመ
ካዳቸው ፡ ነቢያትንም ፡ ያለ ፡ አግ
ባብ ፡ በመግደላቸውና ፡ ልቦቻ
ችን ፡ ሽፍኖች ፡ ናቸው ፡ በማለታ
ቸው ፡ ምክንያት ፡ (ረገምናቸው) ፤
በውነቱ ፡ በክሕደታቸው ፡ ምክን
ያት ፡ አላህ ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ አተመ ፤
ስለዚህ ፡ ጥቂትን ፡ እንጅ ፡ አያ
ምኑም ።
156 በመካዳቸውም ፡ በመርየም ፡ ላይ ፡
ከባድ ፡ ቅጥፈትን ፡ በመናገራቸ
ውም ፡ ምክንያት ፡ (ረገምናቸው) ።
157 ፡—እኛ ፡ የአላህን ፡ መልክተኛ ፡
የመርየምን ፡ ልጅ ፡ አልመሲሕ ፡
ዒሳን ፡ ገደልን ፡ በማለታቸውም ፡
(ረገምናቸው) ፤ አልገደሉትም ፤
አልሰቀሉትምም ፤ ግን ፡ ለነሱ ፡
(የተገደለው ፡ ሰው ፡ በዒሳ) ፡

ተመሰለ ፤ እነዚያም ፡ በርሱ ፡
ነገር ፡ የተለያዩት ፡ ከርሱ ፡ (መገ
ደል) ፡ በመጠራጠር ፡ ውስጥ ፡
ናቸው ፤ ጥርጣሬን ፡ ከመከተል ፡
በስተቀር ፡ በርሱ ፡ ነገር ፡ ምንም
ዕውቀት ፡ የላቸውም ፤ በእርግ
ጥም ፡ አልገደሉትም ።
158 ይልቁንስ ፡ አላህ ፡ ወደርሱ ፡ አነ
ሳው ፤ አላህም ፡ አሸናፊ ፡ ጥበበኛ፡
ነው ።
159 ከመጽሐፉም ፡ ሰዎች ፡ ከመሞቱ ፡
በፊት ፡ በርሱ ፡ (በዒሳ) ፡ በእር
ግጥ ፡ የሚያምን ፡ እንጅ ፡ (አን
ድም) ፡ የለም ፤ በትንሣኤም ፡
ቀን ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ መስካሪ ፡ ይኾ
ናል ።
160 ከነዚያ ፡ ይሁዳውያን ፡ ከኾኑትም፡
በተገኘው ፡ በደል ፡ ሰዎችንም ፡
ከአላህ ፡ መንገድ ፡ በብዙ ፡ በመ
ከልከላቸው ፡ ምክንያት ፡ ለነሱ ፡
ተፈቅደው ፡ የነበሩትን ፡ ጣፋ
ጮች ፡ ምግቦች ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡
እርም ፡ አደረግንባቸው ።
161 ከርሱ ፡ በቁርጥ ፡ የተከለከሉ ፡
ሲኾኑ ፡ አራጣንም ፡ በመያዛቸ
ውና ፡ የሰዎችን ፡ ገንዘቦች ፡ ያለ ፡
አግባብ ፡ (በጉቦ) ፡ በመብላታ
ቸውም ፡ ምክንያት ፡ (የተፈቀደላ
ቸውን ፡ እርም ፡ አደረግንባቸው)።
ከነሱም ፡ ለከሓዲዎቹ ፡ አሳማ
ሚን ፡ ቅጣት ፡ አዘጋጀን ።
162 ግን ፡ ከነርሱ ፡ ውስጥ ፡ በዕው
ቀት ፡ የጠለቁትና ፡ ምእምናኖቹ ፡
በአንተ ፡ ላይ ፡ በተወረደውና ፡
ከአንተም ፡ በፊት ፡ በተወረደው ፡
መጽሐፍ ፡ የሚያምኑ ፡ ሲኾኑ ፤
ሶላትንም ፡ ደንቡን ፡ ጠብቀው ፡
ሰጋጆችን ፡ (እናመሰግናለን) ፡ ዘካ
ንም ፡ ሰጪዎቹ ፡ በአላህና ፡ በመ
ጨረሻውም ፡ ቀን ፡ አማኞቹ ፡
እነዚያ ፡ ታላቅ ፡ ምንዳን ፡ በእር
ግጥ ፡ እንሰጣቸዋለን ።
163 እኛ ፡ ወደ ፡ ኑሕና ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡
ወደ ፡ ነበሩት ፡ ነቢያት ፡ እንዳወ
ረድን ፡ ወደ ፡ አንተም ፡ አወረ
ድን ፤ ወደ ፡ ኢብራሂምም ፡ ወደ ፡
ኢስማዒልም ፡ ወደ ፡ ኢስሐቅም ፡
ወደ ፡ ያዕቆብም ፡ ወደ ፡ ነገዶ
ቹም ፡ ወደ ፡ ዒሳም ፡ ወደ ፡ አዮ
ብም ፡ ወደ ፡ ዩኑስም ፡ ወደ ፡ ሃሩ
ንና ፡ ወደ ፡ ሱለይማንም ፡ አወረ
ድን ፤ ለዳውድም ፡ ዘቡርን ፡
ሰጠነው ።
164 ከዚህም ፡ በፊት ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡
በእርግጥ ፡ የተረክናቸውን ፡ መል
ክተኞች ፡ ባንተ ፡ ላይም ፡ ያልተ
ረክናቸውን ፡ መልክተኞች ፡ (እን
ደላክን ፡ ላክንህ) ። አላህም ፡
ሙሳን ፡ ማነጋገርን ፡ አነጋገረው ።
165 ከመልክተኞቹ ፡ በኋላ ፡ ለሰዎች ፡
በአላህ ፡ ላይ ፡ አስረጅ ፡ እንዳይ
ኖር ፡ አብሳሪዎችና ፡ አስፈራሪ
ዎች ፡ የኾኑን ፡ መልክተኞች ፡
(ላክን) ፤ አላህም ፡ አሸናፊ ፡ ጥበ
በኛ ፡ ነው ።
166 ግን ፡ አላህ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ባወረ
ደው ፡ ይመሰክራል ፤ በዕውቀቱ ፡
አወረደው ፤ መላእክቱም ፡ ይመሰ
ክራሉ ፤ መስካሪም ፡ በአላህ ፡
በቃ ።
167 እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ከአላህም ፡ መን
ገድ ፡ ያገዱት ፡ (ከውነት) ፡ የራቀን ፡
መሳሳት ፡ በእርግጥ ፡ ተሳሳቱ ።
168 እነዚያ ፡ የካዱ ፡ የበደሉም ፡ አላህ፡
የሚምራቸውና ፡ (ቅን) ፡ መንገ
ድን ፡ የሚመራቸው ፡ አይደለም ።
169 ግን ፡ በውስጧ ፡ ዘለዓለም ፡ ዘው
ታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ የገሀነምን ፡



መንገድ ፡ (ይመራቸዋል) ፡ ይህም፡
በአላህ ፡ ላይ ፡ ገር ፡ ነው ።
170 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! መልክተ
ኛው ፡ እውነትን ፡ ከጌታችሁ ፡
አመጣላችሁ ፤ እመኑም ፤ ለናንተ ፡
የተሻለ ፡ (ይኾናል) ፤ ብትክዱም ፡
(አትጐዱትም) ፤ በሰማያትና ፡
በምድር ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ የአላህ ፡
ነውና ፤ አላህም ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡
ነው ።
171 እላንተ ፡ የመጽሐፉ ፡ ሰዎች ፡
ሆይ ! በሃይማኖታችሁ ፡ ወሰንን ፡
አትለፉ ፤ በአላህም ፡ ላይ ፡ እውነ
ትን ፡ እንጅ ፡ አትናገሩ ፤ የመር
የም ፡ ልጅ ፡ አልመሲሕ ፡ ዒሳ ፡
የአላህ ፡ መልክተኛ ፡ ወደ ፡ መር
የም ፡ የጣላት ፡ (የኹን) ፡ ቃሉም ፡
ከርሱ ፡ የኾነ ፡ መንፈስም ፡ ብቻ ፡
ነው ፤ በአላህና ፡ በመልክተኞ
ቹም ፡ እመኑ ፤ (አማልክት) ፡
ሦስት ፡ ናቸው ፡ አትበሉም ፤ ተከ
ልከሉ ፤ ለናንተ ፡ የተሻለ ፡ ይኾና
ልና ፤ አላህ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡
ብቻ ፡ ነው ። ለርሱ ፡ ልጅ ፡ ያለው
ከመኾን ፡ የጠራ ፡ ነው ። በሰማያ
ትና ፡ በምድር ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡
የርሱ ፡ ነው ። መመኪያም ፡ በአ
ላህ ፡ በቃ ።
172 አልመሲሕ ፡ ለአላህ ፡ ባሪያ ፡ ከመ
ኾን ፡ ፈጽሞ ፡ አይጠየፍም ፤ ቀረ
ቢዎች ፡ የኾኑት ፡ መላእክትም ፡
(አይጠየፉም) ፤ እርሱን ፡ ከመገ
ዛት ፡ የሚጠየፍና ፡ የሚኮራም ፡
ሰው ፡ (አላህ) ፡ ሁሉንም ፡ ወደ ፡
እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ ይሰበስባቸ
ዋል ።
173 እነዚያማ ፡ ያመኑት ፡ መልካሞች
ንም ፡ የሠሩት ፡ ምንዳዎቻቸውን ፡
ይሞላላቸዋል ፡ ከችሮታውም ፡
ይጨምርላቸዋል ። እነዚያን ፡
የተጠየፉትንና ፡ የኮሩትንማ ፡
አሳማሚን ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣቸ
ዋል ። ከአላህም ፡ ሌላ ፡ ለነሱ ፡
ዘመድንና ፡ ረዳትን ፡ አያገኙም ።
174 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! ከጌታ
ችሁ ፡ ዘንድ ፡ በእርግጥ ፡ አስረጅ ፡
መጣላችሁ ፤ ወደናንተም ፡ ገላጭ፡
የኾነን ፡ ብርሃን ፡ (ቁርአንን) ፡
አወረድን ።
175 እነዚያማ ፡ በአላህ ፡ ያመኑ ፡ በር
ሱም ፡ የተጠበቁ ፡ ከሱ ፡ በኾነው ፡
እዝነትና ፡ ችሮታ ፡ ውስጥ ፡ በእር
ግጥ ፡ ያስገባቸዋል ። ወደርሱም ፡
ቀጥተኛ ፡ መንገድን ፡ ይመራቸ
ዋል ።
176 ይጠይቁሃል ፤ በላቸው ፡— ወላ
ጅና ፡ ልጅ ፡ ሳይኖረው ፡ በሚወ
ረስ ፡ ሰው ፡ አላህ ፡ ይነግራች
ኋል ፤ ለርሱ ፡ ልጅ ፡ የሌለው ፡
ሰው ፡ ቢሞት ፡ ለርሱም ፡ እኅት ፡
ብትኖረው ፡ ለርስዋ ፡ ከተወው ፡
ረጅት ፡ ግማሹ ፡ አላት ። እርሱም ፡
ለርሷ ፡ ልጅ ፡ የሌላት ፡ እንደ ፡
ኾነች ፡ (በሙሉ) ፡ ይወርሳታል ።
ሁለት ፡ (እኅቶች ፡ ወይም ፡ ከሁ
ለት ፡ በላይ) ፡ ቢኾኑም ፡ ከተ
ወው ፡ ረጅት ፡ ከሦስት ፡ ሁለት ፡
እጁ ፡ አላቸው ። ወንድሞች ፡
(ና ፡ እኅቶች) ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች፡
ቢኾኑም ፡ ለወንዱ ፡ የሁለት ፡
ሴቶች ፡ ድርሻ ፡ ብጤ ፡ አለው ።
አላህ ፡ እንዳትሳሳቱ ፡ ለናንተ ፡
ያብራራል ። አላህም ፡ በነገሩ ፡
ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

5ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ማኢዳህ ፡ (የማእድ ፡ ምዕራፍ) ፡ በመዲና ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 120 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው።
1 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! በቃል
ኪዳኖች ፡ ሙሉ ፤ በናንተ ፡ ላይ ፡
የሚነበበው ፡ (1) ብቻ ፡ ሲቀር ፡
የግመል ፡ የከብት ፡ የበግና ፡ የፍ
የል ፡ እንስሳዎች ፡ እናንተ ፡
በሐጅ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ኾናችሁ ፡
ማደንን፡ የተፈቀደ፡ ሳታደርጉ፡
ለናንተ፡ ተፈቀዱ፤ አላህ፡
የሚሻውን፡ ይፈርዳል

2 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! የአላ
ህን ፡ (ክልክል ፡ ያደረጋቸውን) ፡
ምልክቶች ፡ የተፈቀዱ ፡ አታድ
ርጉ ፤ የተከበረውንም ፡ ወር ፡ በመ
ጋደል ፡ አትድፈሩ ፤ ወደ ፡ መካ ፡
የሚነዱትን ፡ መሥዋዕትና ፡ የሚ
ታበቱባቸውንም ፡ ገመዶች ፡ ከጌ
ታቸው ፡ ችሮታንና ፡ ውዴታን ፡
ፈልገው ፡ ወደ ፡ ተከበረው ፡ ቤት ፡
አሳቢዎችንም ፡ ሰዎች ፡ (አት
ንኩ) ፤ ከሐጅም ፡ ሥራ ፡ በወጣ
ችሁ ፡ ጊዜ ፡ ዕደኑ ፤ ከተከበረው ፡
መስጊድ ፡ ስለከለከሉዋችሁ ፡
ሰዎችን ፡ መጥላትም ፡ (በነሱ ፡
ላይ) ፡ ወሰን ፡ እንድታልፉ ፡ አይ
ገፋፋችሁ ፤ በበጎ ፡ ነገርና ፡ አላ
ህን ፡ በመፍራትም ፡ ተረዳዱ ፤
ግን ፡ በኃጢአትና ፡ ወሰንን ፡ በማ
ለፍ ፡ አትረዳዱ አላህንም ፡
ፍሩ ፤ አላህ ፡ ቅጣተ ፡ ብርቱ ፡
ነውና ።
3 በክት ፡ ፈሳሽ ፡ ደምም ፡ የእሪያ ፡
(እሣማ) ፡ ሥጋም ፤ በርሱ ፡ ከአ
ላህ ፡ (ስም) ፡ ሌላ ፡ የተነሳበትም ፤
የታነቀችም ፡ ተደብድባ ፡ የተገደ
ለችም ፡ ተንከባላ ፡ የሞተችም ፡
በቀንድ ፡ ተወግታ ፡ የሞተችም ፡
ክርቧ ፡ አውሬ ፡ የበላላትም ፡ (ከነ
ዚህ ፡ በሕይወት ፡ ደርሳችሁ) ፡
ያረዳችሁት ፡ ብቻ ፡ ሲቀር ፡ ለጣዖ
ታትም ፡ የታረደው ፡ በአዝላምም፤
(1) ዕድልን ፡ መፈለጋችሁ ፡ በና
ንተ ፡ ላይ ፡ እርም ፡ ተደረገ ፤ ይሃ
ችሁ ፡ አመጥ ፡ ነው ። ዛሬ ፡ (2)
እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ከሃይማኖታ
ችሁ ፡ ተስፋ ፡ ቆረጡ ፤ ስለዚህ ፡
አትፍሩዋቸው ፤ ፍሩኝም ፤ ዛሬ ፡
ሃይማኖታችሁን ፡ ለናንተ ፡ ሞላ
ሁላችሁ ። ጸጋዬንም ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ ፈጸምኩ ። ለእናንተም ፡ ኢስ
ላምን ፡ ከሃይማኖት ፡ በኩል ፡
ወደድኩ ፤ በረኃብ ፡ ወቅት ፡
ወደ ፡ ኃጢአት ፡ ያዘነበለ ፡ ሳይ
ሆን ፡ (እርም ፡ የኾኑትን ፡ ለመብ
ላት) ፡ የተገደደ ፡ ሰውም ፡ (ይብላ) ፤
አላህ ፡ መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።
4 ለነርሱ ፡ ምን ፡ እንደተፈቀደላ
ቸው ፡ ይጠይቁሃል ፤ በላቸው ፡—
ለእናንተ ፡ መልካሞች ፡ ሁሉና ፡
እነዚያም ፡ ከአዳኞች ፡ አሰልጣ

1 በ3ኛው አንቀጽ፡ ተገልጿል

1 የዕድል ፡ መፈለጊያ ፡ ዕንጨቶች ።

2 ይህ፡ የወረደው፡ በዐረፋ፡ ቀን፡ ነው።



ኞች ፡ ኾናችሁ ፡ ያስተማራችኋ
ቸው ፡ (ያደኑት) ፡ ተፈቀደላችሁ ፤
አላህ ፡ ከአስተማራችሁ ፡ ዕው
ቀት ፡ ታስተምሩዋቸዋላችሁ ፤
ለናንተም ፡ ከያዙላችሁ ፡ ነገር ፡
ብሉ ፡ በርሱም ፡ ላይ ፡ የአላህን ፡
ስም ፡ አውሱ ፤ አላህንም ፡ ፍሩ ፤
አላህ ፡ ምርመራው ፡ ፈጣን ፡
ነውና ።
5 ዛሬ ፡ መልካሞች ፡ ሁሉ ፡ ለናንተ ፡
ተፈቀዱ ፤ የነዚያም ፡ መጽሐፍን ፡
የተሰጡት ፡ ሰዎች ፡ ምግብ ፡
(ያረዱት) ፡ ለእናንተ ፡ የተፈቀደ ፡
ነው ፤ ምግባችሁም ፡ ለነሱ ፡ የተ
ፈቀደ ፡ ነው ፤ ከምእምናት ፡ ጥብ
ቆቹም ፡ ከነዚያ ፡ ከናንተ ፡
በፊት ፡ መጽሐፍን ፡ ከተሰጡት ፡
ሴቶች ፡ ጥብቆቹም ፤ ዘማዊዎ
ችና ፡ የምስጢር ፡ ወዳጅ ፡ ያዢ
ዎች ፡ ሳትኾኑ ፡ ጥብቆች ፡ ኾና
ችሁ ፡ መህሮቻችውን ፡ በሰጣች
ኋቸው ፡ ጊዜ ፡ (ሊታገቡዋቸው ፡
የተፈቀዱ ፡ ናቸው) ፤ ከእምነትም፤
የሚመለስ ፡ ሰው ፡ በእርግጥ ፡
ሥራው ፡ ተበላሸ ። በመጨረሻም፡
ቀን ፡ እርሱ ፡ ከከሳሪዎቹ ፡ ነው ።
6 እላንተ፡ ያመናችሁ፡ ሆይ! ወደ፡
ሶላት፡ በቆማችሁ፡ (ለመቆም፡ ባሰ
ባችሁ)፡ ጊዜ፥ ፊቶቻችሁን፥ እጆቻ
ችሁንም፡ እስከ፡ ክርኖች፡ እጠቡ።
ራሶቻችሁንም፡ (በውሃ)፡ እበሱ። እግ
ሮቻችሁንም፡ እስከ፡ ቁርጭምጭ
ሚቶች፡ (እጠቡ)፤ (ሴት፡ ጋር፡ በመ
ገናኘት፡ ወይም፡ በሌላ፡ ምክንያት፡
ጀናባ)፡ ብትኾኑ፡ (ገላችሁን)፡ ታጠ
ቡ። በሽተኞች፡ ወይም፡ በጉዞ፡ ላይ፡
ብትኾኑም፥ ወይም፡ ከእናንተ፡ አን
ዳችሁ፡ ከዓይነ፡ ምድር፡ ቢመጣ፥
ወይም ፡ ሴቶችን ፡ ብትነካኩና ፡
ውሃን ፡ ባታገኙ ፡ ንጹሕን ፡ የም
ድር ፡ ገጽ ፡ አስቡ ። ከሱም ፡
ፊቶቻችሁንና ፡ እጆቻችሁን ፡
እበሱ ። አላህ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡
ምንም ፡ ችግር ፡ ሊያደርግ ፡ አይ
ሻም ። ግን ፡ ታመሰግኑ ፡ ዘንድ ፡
ሊያጠራችሁና ፡ ጸጋውን ፡ በእና
ንተ ፡ ላይ ፡ ሊሞላ ፡ ይሻል ።
7 በእናንተ፡ም ፡ ላይ ፡ (የለገሰውን) ፡
የአላ ህን ጸጋ ፡ ያንንም ፡ ሰምተ
ናል ፡ ታዘናልም ፡ ባላችሁ ፡ ጊዜ ፡
በርሱ ፡ ያጠበቀባችሁን ፡ ቃል ፡
ኪዳኑን ፡ አስታውሱ ። አላህንም ፡
ፍሩ ። አላህ ፡ በደረቶች ፡ ውስጥ ፡
ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።
8 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ለአ
ላህ ፡ ቀጥተኞች ፡ በትክክል ፡ መስ
ካሪዎች ፡ ኹኑ ። ሕዝቦችንም ፡
መጥላት ፡ ባለማስተካከል ፡ ላይ ፡
አይገፋፋችሁ ፤ አስተካክሉ ፤
እርሱ ፡ (ማስተካከል) ፡ ለአላህ ፡
ፍራቻ ፡ በጣም ፡ የቀረበ ፡ ነው ።
አላህንም ፡ ፍሩ ። አላህ ፡ በምትሠ
ሩት ፡ ሁሉ ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።
9 እነዚያንም ፡ ያመኑትንና ፡ በጎ ፡
ሥራዎችን ፡ የሠሩትን ፡ አላህ ፡
(ገነትን) ፡ ተስፋ ፡ አደረገላቸው ፡
ለነርሱ ፡ ምሕረትና ፡ ታላቅ ፡
ምንዳ ፡ አላቸው ።
10 እነዚያም ፡ የካዱና ፡ በተአምራቶ
ቻችን ፡ ያስተባበሉ ፡ እነዚያ ፡
የእሳት ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ።
11 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ሕዝ
ቦች ፡ እጆቻቸውን ፡ ወደ ፡ እና
ንተ ፡ ሊዘረጉ ፡ ባሰቡና ፡ እጆቻቸ
ውን ፡ ከናንተ ፡ ላይ ፡ በከለከለ
ላችሁ ፡ ጊዜ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
(የዋለላችሁን) ፡ የአላህን ፡ ጸጋ ፡

አስታውሱ ፤ አላህንም ፡ ፍሩ ፡
ምእምናንም ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡
ይመኩ ።
12 አላህም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡
የጠበቀ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በእርግጥ፡
ያዘባቸው ። ከነሱም ፡ ዐሥራ ፡
ሁለትን ፡ አለቆች ፡ አስነሣን ፤
አላህም ፡ አላቸው ፤ እኔ ፡ ከና
ንተ ፡ ጋር ፡ ነኝ ፤ ሶላትን ፡ ብታ
ስተካክሉ ፡ ግዴታ ፡ ምጽዋት
ንም ፡ ብትሰጡ ፡ በመልክተኞ
ቼም ፡ ብታምኑ ፡ ብትረዱዋቸ
ውም ፡ ለአላህም ፡ መልካም ፡
ብድርን ፡ ብታበድሩ ፡ ኃጢአቶቻ
ችሁን ፡ ከናንተ ፡ በእርግጥ ፡ አብ
ሳለሁ ፤ ከስሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡
የሚፈሱባቸውን ፡ ገነቶችም ፡
በእርግጥ ፡ አገባችኋለሁ ። ከዚ
ህም ፡ በኋላ ፡ ከናንተ ፡ የካደ ፡
ሰው ፡ ቀጥተኛውን ፡ መንገድ ፡
በእርግጥ ፡ ተሳሳተ ።
13 ቃል ፡ ኪዳናቸውንም ፡ በማፍረ
ሳቸው ፡ ረገምናቸው ፤ ልቦቻቸ
ውንም ፡ ደረቆች ፡ አደረግን ፤
ቃላትን ፡ ከቦታዎቻቸው፡ ይለው
ጣሉ ። በርሱም ፡ ከታዘዙበት ፡
ነገር ፡ ፈንታን ፡ ተዉ ። ከነሱም ፡
ጥቂቶች ፡ ሲቀሩ ፡ ከነርሱ ፡ የኾ
ነን ፡ ክዳት ፡ የምታውቅባቸው ፡
ከመኾን ፡ አትወገድም ፤ ከነር
ሱም ፡ ይቅርታ ፡ አድርግ ፤ እለፋ
ቸውም ፤ አላህ ፡ መልካም ፡ ሠሪ
ዎችን ፡ ይወዳልና ።
14 ከነዚያም ፡ እኛ ፡ ክርስቲያኖች ፡
ነን ፡ ካሉት ፡ የጠበቀ ፡ ቃል ፡ ኪዳ
ናቸውን ፡ ያዝን ። በርሱም ፡ ከታ
ዘዙበት ፡ ነገር ፡ ፈንታን ፡ ተዉ ፡
ስለዚህ ፡ እስከ ፡ ትንሣኤ ፡ ቀን ፡
ድረስ ፡ በመካከላቸው ፡ ጠብንና ፡
ጥላቻን ፡ ጣልንባቸው ፤ አላህም ፡
ይሠሩት ፡ የነበሩትን ፡ ሁሉ ፡ በእ
ርግጥ ፡ ይነግራቸዋል ።
15 የመጽሐፉ ፡ ባለ ፡ ቤቶች ፡ ሆይ !
ከመጽሐፉ ፡ ትሸሽጉት ፡ ከነበራ
ችሁት ፡ ነገር ፡ ብዙውን ፡ ለእና
ንተ ፡ የሚገልጽ ፡ ከብዙውም ፡
የሚተው ፡ ሲኾን ፡ መልክተኛ
ችን ፡ (ሙሐመድ) ፡ በእርግጥ ፡
መጣላችሁ ። ከአላህ ፡ ዘንድ ፡
ብርሃንና ፡ ገላጭ ፡ መጽሐፍ ፡ በእ
ርግጥ ፡ መጣላችሁ ።
16 አላህ ፡ ውዴታውን ፡ የተከተሉ
ትን ፡ ሰዎች ፡ የሰላምን ፡ መንገ
ዶች ፡ በርሱ ፡ ይመራቸዋል ። በፈ
ቃዱም ፡ ከጨለማዎች ፡ ወደ ፡
ብርሃን ፡ ያወጣቸዋል ። ወደ ፡
ቀጥተኛም ፡ መንገድ ፡ ይመራቸ
ዋል ።
17 እነዚያ ፡ አላህ ፡ እርሱ ፡ የመር
የም ፡ ልጅ ፡ አልመሲሕ ፡ ነው ፡
ያሉ ፡ በእርግጥ ፡ ካዱ ፤ የመርየ
ምን ፡ ልጅ ፡ አልመሲሕን ፡ እናቱ
ንም ፡ በምድር ፡ ያለንም ፡ ሁሉ ፡
ለማጥፋት ፡ ቢሻ ፡ ከአላህ ፡ ማዳ
ንን ፡ የሚችል ፡ ማነው ? በላቸው።
የሰማያትና ፡ የምድር ፡ የመካከላ
ቸውም ፡ ንግሥና ፡ የአላህ ፡ ብቻ ፡
ነው ፤ የሚሻውን ፡ ይፈጥራል ።
አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ቻይ ፡ ነው ።
18 ይሁዶችና ፡ ክርስቲያኖችም ፡
እኛ ፡ የአላህ ፡ ልጆችና ፡ ወዳጆቹ ፡
ነን ፡ አሉ ። ታዲያ ፡ በኀጢአቶቻ
ችሁ ፡ ለምን ፡ ያሰቃያችኋል ?
አይደላችሁም ፡ እናንተ ፡ ከፈጠ
ራቸው ፡ ሰዎች ፡ ናችሁ ፡ በላቸው፤
ለሚሻው ፡ ሰው ፡ ይምራል ፤ የሚሻ
ውንም ፡ ሰው ፡ ይቀጣል ፤ የሰማያ



ትና ፡ የምድርም ፡ በመካከላቸ
ውም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ንግሥና ፡
የአላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ። መመለሻም፡
ወደርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
19 እላንተ ፡ የመጽሐፉ ፡ ሰዎች ፡
ሆይ ! አብሳሪና ፡ አስፈራሪ ፡ አል
መጣልንም ፡ እንዳትሉ ፡ ከመል
ክተኞች ፡ በመቋረጥ ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡
ሲኾን ፡ (ሕጋችንን) ፡ የሚያብ
ራራ ፡ ኾኖ ፡ መልክተኛችን ፡ በእ
ርግጥ ፡ መጣላችሁ ። አብሳሪና ፡
አስፈራሪም ፡ በእርግጥ ፡ መጣላ
ችሁ ። አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ።
20 ሙሳም ፡ ለሕዝቦቹ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ) ፡ ፡—ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ፡
የአላህን ፡ ጸጋ ፡ በውስጣችሁ ፡
ነቢያትን ፡ ባደረገና ፡ ነገሥታ
ትም ፡ ባደረጋችሁ ፡ ከዓለማትም ፡
ለአንድም ፡ ያልሰጠውን ፡ ችሮታ፡
በሰጣችሁ ፡ ጊዜ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
(ያደረገውን ፡ ጸጋ) ፡ አስታውሱ ።
21 ፡—ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ! ያችን ፡ አላህ ፡
ለእናንተ ፡ ያደረጋትን ፡ የተቀደሰ
ችውን ፡ መሬት ፡ ግቡ ፤ ወደኋላች
ሁም ፡ አትመለሱ ፤ ከሳሪዎች ፡
ኾናችሁ ፡ ትመለሳላችሁና ።
22 ፡—ሙሳ ፡ ሆይ ! በርስዋ ፡ ውስጥ ፡
ኀያላን ፡ ሕዝቦች ፡ አልሉ ፤ ከርስ
ዋም ፡ እስከሚወጡ ፡ ድረስ ፡
እኛ ፡ ፈጽሞ ፡ አንገባትም ፤ ከርስ
ዋም ፡ ቢወጡ ፡ እኛ ፡ ገቢዎች ፡
ነን ፡ አሉ ።
23 ከእነዚያ ፡ (አላህን) ፡ ከሚፈሩ
ትና ፡ አላህ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ከለገ
ሰላቸው ፡ የኾኑ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡
—(1) በነርሱ ፡ (በኀያሎቹ) ፡ ላይ፡
በሩን ፡ ግቡ ፤ በገባችሁትም ፡
ጊዜ ፡ እናንተ ፡ አሸናፊዎች ፡
ናችሁ ፤ ምእምናንም ፡ እንደ ፡
ኾናችሁ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ተመኩ ፡
አሉ ።
24 ሙሳ ፡ ሆይ ! በውስጧ ፡ እስካሉ ፡
ድረስ ፡ እኛ ፡ ፈጽሞ፡ምን ፡ ጊዜም ፡
አንገባትም ፤ ስለዚህ ፡ ኺድ ፤
አንተና ፡ ጌታህ ፡ ተጋደሉም ፤
እኛ ፡ እዚህ ፡ ተቀማጮች ፡ ነን ፡
አሉ ።
25 ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ ራሴንና ፡
ወንድሜን ፡ በቀር ፡ (ላስገድድ) ፡
አልችልም ፡ በእኛና ፡ በአመጠ
ኞቹም ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡
ለይ ፡ አለ ።
26 ፡—እርስዋም ፡ (የተቀደሰችው ፡
መሬት) ፡ በእነሱ ፡ ላይ ፡ አርባ ፡
ዓመት ፡ እርም ፡ ናት ፤ በምድረ ፡
በዳ ፡ ይንከራተታሉ ። በአመጠ
ኞችም ፡ ሕዝቦች ፡ ላይ ፡ አት
ዘን ፡ አለው ።
27 በነሱም ፡ ላይ ፡ የአደምን ፡ ሁለት ፡
ልጆች ፡ ወሬ ፡ ቁርባንን ፡ ባቀረ
ቡና ፡ (አላህ) ፡ ከአንደኛቸው ፡
ተቀብሎ ፡ ከሌላው ፡ ባልተቀበለ ፡
ጊዜ ፡ (የኾነውን) ፡ በውነት ፡
አንብብላቸው ፤ በእርግጥ ፡ እገድ
ልሃለሁ ፡ አለው ፤ (ተገዳዩ) ፡
አላህ ፡ የሚቀበለው ፡ እኮ ፡ ከጥን
ቁቆቹ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ አለ ።
28 ልትገድለኝ ፡ እጅህን ፡ ወደኔ ፡
ብትዘረጋ ፡ እኔ ፡ ልገድልህ ፡
እጄን ፡ ወዳንተ ፡ የምዘረጋ ፡ አይ
ደለሁም ፤ እኔ ፡ የዓለማትን ፡
ጌታ ፡ አላህን ፡ እፈራለሁና ፡ አለ ።
29 እኔ ፡ በኃጢአቴና ፡ በኃጢአትህ ፡
ልትመለስና ፡ ከእሳት ፡ ጓዶች ፡
ልትኾን ፡ እሻለሁ ፤ ይኸም ፡ የበ
ደለኞች ፡ ቅጣት ፡ ነው ፡ (አለ) ።

1 ዮሽዕና ፡ ካሌብ ።

30 ነፍሱም ፡ ወንድሙን ፡ መግደ
ልን ፡ ለርሱ ፡ ሸለመችለት ፤ ገደለ
ውም ፤ ከከሳሪዎቹም ፡ ኾነ ።
31 የወንድሙንም ፡ ሬሳ ፡ እንዴት ፡
እንደሚሸሽግ ፡ ያሳየው ፡ ዘንድ ፡
አላህ ፡ መሬትን ፡ የሚጭር ፡
ቁራን ፡ ላከለት ፤ ወይ ፡ እኔ ፡ የወን
ድሜን ፡ ሬሳ ፡ እሸሽግ ፡ ዘንድ ፡
እንደዚህ ፡ ቁራ ፡ ብጤ ፡ መኾን ፡
አቃተኝን ? አለ ፤ ከጸጸተኞችም ፡
ኾነ ።
32 በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በእስራኤል ፡
ልጆች ፡ ላይ ፡ እነሆ ያለ ፡ ነፍስ ፡
(መግደል) ፡ ወይም ፡ በምድር ፡
ላይ ፡ ያለማጥፋት ፡ ነፍስን ፡ የገ
ደለ ፡ ሰው ፡ ሰዎቹን ፡ ሁሉ ፡ እንደ
ገደለ ፡ ነው ፤ ሕያው ፡ ያደረጋ
ትም ፡ ሰው ፡ ሰዎቹን ፡ ሁሉ ፡
ሕያው ፡ እንዳደረገ ፡ ነው ፡ ማለ
ትን ፡ ጻፍን ፤ መልክተኞቻችንም ፡
በግልጽ ፡ ተአምራት ፡ በእርግጥ ፡
መጡዋቸው ፤ ከዚያም ፡ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ከነሱ ፡ ብዙዎቹ ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ ወሰንን ፡ አላፊዎች ፡
ናቸው ።
33 የነዚያ ፡ አላህንና ፡ መልክተኛ
ውን ፡ የሚዋጉ ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡
ለማጥፋት ፡ የሚተጉ ፡ ሰዎች ፡
ቅጣት ፡ (1) መገደል ፡ ወይም ፡ (2)
መሰቀል ፡ ወይም ፡ (3) እጆቻቸ
ውንና ፡ እግሮቻቸውን ፡ በማፈ
ራረቅ ፡ (4) መቆረጥ ፡ ወይም ፡ (5)

1 ነፍስ ፡ የገደሉ ፡ እንደ ፡ ኾነ ።
2 ነፍስ ፡ ገድለው ፡ ገንዘብም ፡ ቀምተው ፡
እንደ ፡ ኾነ ።
3 ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ወስደው ፡ እንደ ፡ ኾነ ።
4 ቀኝ ፡ እጅንና ፡ ግራ ፡ እግርን ።
5 ነፍስም ፡ ሳይገድሉ ፡ ገንዘብም ፡ ሳይወስዱ ፡
አስፈራርተው ፡ እንደ ፡ ኾነ ።

ከአገር ፡ መባረር ፡ (1) ነው ።
ይህ ፡ ለነሱ ፡ በቅርቢቱ ፡ ዓለም ፡
ውርደት ፡ ነው ፤ በመጨረሻይ
ቱም ፡ ለነርሱ ፡ ከባድ ፡ ቅጣት ፡
አላቸው ።
34 እነዚያ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ከመቻላ
ችሁ ፡ በፊት ፡ የተጸጸቱ ፡ ሲቀሩ ፤
አላህም ፡ መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ መኾ
ኑን ፡ ዕወቁ ።
35 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላ
ህን ፡ ፍሩ ፤ ወደርሱም ፡ መቃረ
ቢያን ፡ (መልካም ፡ ሥራን) ፡
ፈልጉ ፤ ትድኑ ፡ ዘንድም ፡ በርሱ ፡
መንገድ ፡ ታገሉ ።
36 እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ከር
ሱም ፡ ጋር ፡ ብጤው ፡ ከትንሣኤ ፡
ቀን ፡ ቅጣት ፡ በርሱ ፡ ሊበዡበት ፡
ለነርሱ ፡ በኖራቸው ፡ ኖሮ ፡ ከነሱ ፡
ተቀባይን ፡ ባላገኙ ፡ ነበር ፤ ለነ
ሱም ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ አላ
ቸው ።
37 ከእሳት ፡ ሊወጡ ፡ ይፈልጋሉ ፤
እነርሱም ፡ ከርስዋ ፡ ወጪዎች ፡
አይደሉም ፤ ለነርሱም ፡ ዘውታሪ ፡
ቅጣት ፡ አላቸው ።
38 ሰራቂውንና ፡ ሰራቂይቱንም ፡
በሠሩት ፡ ነገር ፡ ለቅጣት ፡ ከአ
ላህ ፡ የኾነን ፡ መቀጣጫ ፡ እጆቻ
ቸውን ፡ ቁረጡ ፤ አላህም ፡ አሸ
ናፊ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።
39 ከመበደሉም ፡ በኋላ ፡ የተጸጸተና ፡
ሥራውን ፡ ያሳመረ ፡ አላህ ፡ ጸጸ
ቱን ፡ ከርሱ ፡ ይቀበለዋል ፤ አላህ ፡
መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።
40 የሰማያትና፡ የምድር፡ ንግሥና፡
የሱ ፡ -የአላህ- ብቻ፡ መኾኑን፡

1 ወይም ፡ መታሰር ።



አላወቅከምን ? የሚሻውን ፡ ሰው ፡
ይቀጣል ፤ ለሚሻውም ፡ ሰው ፡ ይ
ምራል ፤ አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ።
41 አንተ ፡ መልክተኛ ፡ ሆይ ፡ እነ
ዚያ ፡ በክሕደት ፡ የሚቻኮሉት ፡
ከነዚያ ፡ ልቦቻቸው ፡ ያላመኑ ፡
ሲኾኑ ፡ በአፎቻቸው ፡ አመንን ፡
ካሉትና ፡ ከነዚያም ፡ አይሁድ ፡
ከኾኑት ፡ ሲኾኑ ፡ አያሳዝኑህ ፤
(እነርሱ) ፡ ውሸትን ፡ አዳማጮች ፡
ናቸው ፤ ለሌሎች ፡ ወዳንተ ፡ ላል
መጡ ፡ ሕዝቦች ፡ አዳማጮች ፡
ናቸው፥ ንግግሮችን፡ ከቦታቸው፡
ሌላ ፡ ያጣምማሉ ፤ ይህንን ፡
ንን ፡ (የተጣመመውን) ፡ ብትሰ
ሰጡ ፡ ያዙት ፤ ባትሰሰጡትም ፡
ተጠንቀቁ ፡ ይላሉ ። አላህም ፡
መፈተኑን ፡ የሚሻበትን ፡ ሰው ፡
ለርሱ ፡ ከአላህ ፡ (ለመከላከል) ፡
ምንንም ፡ አትችልም ። እነዚህ ፡
እነዚያ ፡ አላህ ፡ ልቦቻቸውን ፡
ማጥራትን ፡ ያልሻላቸው ፡ ናቸው ፤
ለነርሱ ፡ በቅርቢቱ ፡ ዓለም ፡
ውርደት ፡ አላቸው ፤ ለነርሱም ፡
በመጨረሻይቱ ፡ ዓለም ፡ ከባድ ፡
ቅጣት ፡ አላቸው ።
42 ውሸትን ፡ አዳማጮች ፡ እርምን ፡
በላተኞች ፡ ናቸው ፤ ቢመጡህም ፡
በመካከላቸው ፡ ፍረድ ፤ ወይም ፡
ተዋቸው ፤ ብትተዋቸውም ፡ ም
ንም ፡ አይጎዱህም ፤ ብትፈርድ
ም ፡ በመካከላቸው ፡ በትክክል ፡
ፍረድ ፤ አላህ ፡ በትክክል ፡ ፈራ
ጆችን ፡ ይወዳልና ።
43 እነርሱም ፡ ዘንድ ፡ ተውራት ፡
እያለች ፡ በውስጧ ፡ የአላህ ፡ ፍርድ
ያለባት ፡ ስትኾን ፡ እንዴት ፡
ያስፈርዱሃል ! ከዚያም ፡ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ እንዴት ፡ ይሸሻሉ ! እነዚ
ያም ፡ በፍጹም ፡ ምእምናን ፡ አይ
ደሉም ።
44 እኛ ፡ ተውራትን ፡ በውስጥዋ ፡
መምሪያና ፡ ብርሃን ፡ ያለባት ፡
ስትኾን ፡ አወረድን ፤ እነዚያ ፡
ትእዛዝን ፡ የተቀበሉት ፡ ነቢያት ፡
በነዚያ ፡ ይሁዳውያን ፡ በኾኑት ፡
ላይ ፡ በርሷ ፡ ይፈርዳሉ ፤ ሊቃው
ንቱና ፡ ዐዋቂዎቹም ፡ ከአላህ ፡
መጽሐፍ ፡ እንዲጠብቁ ፡ በተደረ
ጉትና ፡ በርሱም ፡ ላይ ፡ መስካሪ
ዎች ፡ በኾኑት ፡ (ይፈርዳሉ) ፤
ሰዎችንም ፡ አትፍሩ ፤ ፍሩኝም ፤
በአንቀጾቼም ፡ አነስተኛን ፡ ዋጋ ፡
አትለውጡ ፤ አላህም ፡ ባወረደው ፡
ነገር ፡ ያልፈረደ ፡ ሰው ፡ እነዚያ ፡
ከሓዲዎቹ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ።
45 በነርሱም ፡ ላይ ፡ በውስጧ ፡ ነፍስ ፡
በነፍስ ፡ ዓይንም ፡ በዓይን ፡ አፍን
ጫም ፡ በአፍንጫ ፡ ጆሮም ፡
በጆሮ ፡ ጥርስም ፡ በጥርስ ፡ (ይያ
ዛል) ፡ ቁስሎችንም ፡ ማመሳሰል ፡
አለባቸው ፡ ማለትን ፡ ጻፍን ፤
በርሱም ፡ የመጸወተ ፡ (የማረ) ፡
ሰው ፡ እርሱ ፡ ለርሱ ፡ (ለሠራው ፡
ኃጢአት) ፡ ማስተሰሪያ ፡ ነው ፤
አላህም ፡ ባወረደው ፡ ነገር ፡ የማ
ይፈርድ ፡ ሰው ፤ እነዚያ ፡ በደለ
ኞቹ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ።
46 በፈለጎቻቸውም ፡ (በነቢያቶቹ ፡
ፈለግ) ፡ ላይ ፡ የመርየምን ፡ ልጅ ፡
ዒሳን ፡ ከተውራት ፡ በስተፊቱ ፡
ያለውን ፡ አረጋጋጭ ፡ ሲኾን ፡
አስከተልን ፤ ኢንጂልንም ፡ በው
ስጡ ፡ ቀጥታና ፡ ብርሃን ፡ ያለ
በት ፡ በስተፊቱ ፡ ያለችውን ፡
ተውራትንም ፡ የሚያረጋግጥ ፡

ለጥንቁቆችም ፡ መሪና ፡ ገሣጭ ፡
ሲኾን ፡ ሰጠነው ።
47 የኢንጅልም ፡ ባለቤቶች ፡ በው
ስጡ ፡ አላህ ፡ ባወረደው ፡ ሕግ ፡
ይፍረዱ ፤ አላህም ፡ ባወረደው ፡
የማይፈርድ ፡ ሰው ፡ እነዚያ ፡
አመጠኞች ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ።
48 ወደ ፡ አንተም ፡ መጽሐፉን ፡ ከበ
ፊቱ ፡ ያለውን ፡ መጽሐፍ ፡ አረ
ጋጋጭና ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተጠባ
ባቂ ፡ ሲኾን ፡ በውነት ፡ አወረ
ድን ፤ በመካከላቸውም ፡ አላህ ፡
ባወረደው ፡ ሕግ ፡ ፍረድ ፤ እውነ
ቱም ፡ ከመጣልህ ፡ በኋላ ፡ ዝን
ባሌዎቻቸውን ፡ አትከተል ። ከና
ንተ ፡ ለሁሉም ፡ ሕግንና ፡ መን
ገድን ፡ አደረግን ፤ አላህም ፡ በሻ ፡
ኖሮ ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ባደረጋ
ችሁ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ በሰጣችሁ ፡
ሕግጋት ፡ ሊሞክራችሁ ፡ (ለያያ
ችሁ) ፤ በጎ ፡ ሥራዎችንም ፡
(ለመሥራት) ፡ ተሽቀዳደሙ ፤
መመለሻችሁ ፡ በጠቅላላ ፡ ወደ ፡
አላህ ፡ ነው ፤ በርሱም ፡ ትለያዩ
በት ፡ የነበራችሁትን ፡ ነገር ፡ ይነ
ግራችኋል ።
49 በመካከላቸውም ፡ አላህ ፡ ባወረ
ደው ፡ ሕግ ፡ ፍረድ ፤ ፍላጎቶቻቸ
ውንም ፡ አትከተል ፤ አላህም ፡
ወደ ፡ አንተ ፡ ካወረደው ፡ ከከ
ፊሉ ፡ እንዳያሳስቱህ ፡ ተጠንቀቃ
ቸው ፡ (ማለትን ፡ አወረድን) ፤
ቢዞሩም ፡ አላህ ፡ የሚሻው ፡ በከ
ፊሉ ፡ ኃጢአታቸው ፡ ሊቀጣ
ቸው ፡ መኾኑን ፡ ዕወቅ ፤ ከሰዎ
ቹም ፡ ብዙዎቹ ፡ አመጠኞች ፡
ናቸው ።
50 የማይምንነትን ፡ ፍርድ ፡ ይፈል
ጋሉን ? ለሚያረጋግጡም ፡ ሰዎች ፡
ከአላህ ፡ ይበልጥ ፡ ፍርዱ ፡ ያማረ ፡
ማን ፡ ነው ?
51 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ይሁ
ዶችንና ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ረዳ
ቶች ፡ አድርጋችሁ ፡ አትያዙ ፤
ከፊላቸው ፡ ለከፊሉ ፡ ረዳቶች ፡
ናቸው ፤ ከናንተም ፡ ውስጥ ፡ ረዳ
ቶች ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ሰው ፡
እርሱ ፡ ከነርሱ ፡ ነው ፤ አላህ ፡
አመጠኞችን ፡ ሕዝቦች ፡ አያቀ
ናም ።
52 እነዚያንም ፡ በልቦቻቸው ፡ ው
ስጥ ፡ (የንፍቅና) ፡ በሽታ ፡ ያለባ
ቸውን ፡ ሰዎች ፡ የጊዜ ፡ መለዋ
ወጥ ፡ እንዳያገኘን ፡ እንፈራለን ፡
የሚሉ ፡ ሲኾኑ ፡ በነርሱ ፡ (ለመረ
ዳት) ፡ ሲቻኮሉ ፡ ታያቸዋለህ ፤
አላህም ፡ ድል ፡ መንሳትን ፡
ወይም ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ የኾነን ፡
ነገር ፡ (ማጋለጥን) ፡ ሊያመጣ ፡
በነፍሶቻቸው ፡ ውስጥ ፡ በደበቁ
ትም ፡ ነገር ፡ ተጸጻቾች ፡ ሊኾኑ ፡
ተረጋገጠ ።
53 እነዚያም ፡ ያመኑት ፡ ሰዎች ፡—
እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡
ነን ፡ ብለው ፡ የጠነከረ ፡ መሐላ
ቸውን ፡ በአላህ ፡ የማሉት ፡ እነ
ዚህ ፡ ናቸውን ? ይላሉ ፤ ሥራዎ
ቻቸው ፡ ተበላሹ ፤ ከሳሪዎችም ፡
ኾኑ ።
54 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ከና
ንተ ፡ ውስጥ ፡ ከሃይማኖቱ ፡ የሚ
መለስ ፡ ሰው ፡ አላህ ፡ (በነርሱ ፡
ስፍራ) ፡ የሚወዳቸውንና ፡ የሚ
ወዱትን ፡ በምእምናን ፡ ላይ ፡
ትሑቶች ፡ በከሓዲዎች ፡ ላይ ፡
ኀያላን ፡ የኾኑን ፡ በአላህ ፡ መን
ገድ ፡ የሚታገሉን ፡ የወቃሽን ፡
ወቀሳ ፡ የማይፈሩን ፡ ሕዝቦች ፡



በእርግጥ ፡ ያመጣል ፤ ይኸ ፡ የአ
ላህ ፡ ችሮታ ፡ ነው ፤ ለሚሻው ፡
ሰው ፡ ይሰጠዋል ፤ አላህም ፡ ችሮ
ታው ፡ ሰፊ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
55 ረዳታችሁ ፡ አላህና ፡ መልክተ
ኛው ፡ እነዚያም ፡ ያመኑት ፡
ብቻ ፡ ናቸው ፤ (እነርሱ) ፡ እነ
ዚያ ፡ ሶላትን ፡ በደንቡ ፡ የሚሰ
ግዱ ፡ እነርሱም ፡ ያጐነበሱ ፡
ኾነው ፡ ምጽዋትን ፡ የሚሰጡ ፡
ናቸው ።
56 አላህንና ፡ መልክተኛውን ፡ እነዚ
ያንም ፡ ያመኑትን ፡ የሚወዳጅ ፡
ሰው ፡ (ከአላህ ፡ ጭፍሮች ፡ ይኾ
ናል) ፤ የአላህም ፡ ጭፍሮች ፡ እነ
ርሱ ፡ አሸናፊዎች ፡ ናቸው ።
57 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ከነ
ዚያ ፡ ከበፊታችሁ ፡ መጽሐፍን ፡
ከተሰጡት ፡ እነዚያን ፡ ሃይማኖ
ታችሁን ፡ ማላገጫና ፡ መጫ
ወቻ ፡ አድርገው ፡ የያዙትን ፡
ከሓዲዎችንም ፡ ረዳቶች ፡ አድር
ጋችሁ ፡ አትያዙ ፤ ምእምናንም ፡
እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ አላህን ፡ ፍሩ ።
58 ወደ ፡ ሶላትም ፡ በጠራችሁ ፡ ጊዜ ፡
(ጥሪይቱን) ፡ መሳለቂያና ፡ መጫ
ወቻ ፡ አድርገው ፡ ይይዟታል ፤
ይኸ ፡ እነርሱ ፡ የማያውቁ ፡ ሕዝ
ቦች ፡ በመኾናቸው ፡ ነው ።
59 ፡—የመጽሐፉ ፡ ባለቤቶች ፡ ሆይ !
በአላህና ፡ ወደኛ ፡ በተወረደው ፡
በፊትም ፡ በተወረደው ፡ ለማመ
ናችን ፡ አብዛኞቻችሁም ፡ አመጠ
ኞች ፡ በመኾናችሁ ፡ እንጅ ፡
(ሌላን ፡ ነገር) ፡ ከኛ ፡ ትጠላላች
ሁን ? በላቸው ።
60 ፡—አላህ ፡ ዘንድ ፡ ቅጣቱ ፡ ከዚህ ፡
የከፋን ፡ ነገር ፡ ልንገራችሁን ?
በላቸው ፤ (እርሱም) ፡ አላህ ፡
የረገመው ፡ ሰው ፡ በርሱም ፡ ላይ ፡
የተቆጣበት ፡ ከነርሱም ፡ ዝንጀሮ
ዎችንና ፡ ከርከሮዎችን፡ ያደረ
ገው ፡ ጣዖትንም ፡ የተገዛ ፡ ሰው ፡
(ሃይማኖት) ፡ ነው ፤ እነዚያ ፡
በጣም ፡ በከፉ ፡ ስፍራ ፡ ናቸው ፡
ከቀጥተኛውም ፡ መንገድ ፡ በጣም
የተሳሳቱ ፡ ናቸው ።
61 በመጡዋችሁም ፡ ጊዜ ፡ (ወደ
ናንተ) ፡ ከክሕደት ፡ ጋር ፡ በእር
ግጥ ፡ የገቡ ፡ እነርሱም ፡ ከርሱ ፡
ጋር ፡ በእርግጥ ፡ የወጡ ፡ ሲኾኑ ፡
አምነናል ፡ ይላሉ ፤ አላህም ፡ ይደ
ብቁት ፡ የነበሩትን ፡ ነገር ፡ በጣም
ዐዋቂ ፡ ነው ።
62 ከነርሱም ፡ ብዙዎቹን ፡ በኃጢአ
ትና ፡ በበደል ፡ እርምንም ፡ በመ
ብላታቸው ፡ የሚጣደፉ ፡ ሲኾኑ ፡
ታያለህ ፤ ይሠሩት ፡ የነበሩት ፡
ነገር ፡ በጣም ፡ ከፋ !
63 ቀሳውስቱና ፡ ሊቃውንቱ ፡ ከኃ
ጢአት ፡ ንግግራቸውና ፡ እርምን ፡
ከመብላታቸው ፡ አይከለክሏቸው
ም ፡ ኖሮአልን ? ይሠሩት ፡ የነበ
ሩት ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ከፋ !
64 ይሁዶችም ፡ የአላህ ፡ እጅ ፡ የታ
ሰረች ፡ ናት ፡ አሉ ፤ እጆቻቸው ፡
ይታሰሩ ፡ ባሉትም ፡ ነገር ፡ ይረ
ገሙ ፤ አይደለም ፡ እጆቹ ፡ የተዘ
ረጉ ፡ ናቸው ፤ እንደሚሻ ፡ ይለግ
ሳል ፤ ከጌታህም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡
የተወረደው ፡ (ቁርአን) ፡ ከነሱ ፡
ብዙዎቹን ፡ ትዕቢትንና ፡ ክሕደ
ትን ፡ በእርግጥ ፡ ይጨምራቸ
ዋል ፤ በመካከላቸውም ፡ ጠብ
ንና ፡ ጥላቻን ፡ እስከ ፡ ትንሣኤ ፡
ቀን ፡ ድረስ ፡ ጣልን ፤ ለጦር ፡
እሳትን ፡ ባያያዙ ፡ (ባጫሩ) ፡

ቍጥር ፡ አላህ ፡ ያጠፋታል ፤ በም
ድርም ፡ ውስጥ ፡ ለማበላሸት ፡
ይሮጣሉ ፤ አላህም ፡ አበላሺዎ
ችን ፡ አይወድም ።
65 የመጽሐፉም ፡ ባለቤቶች ፡ ባመ
ኑና ፡ (ከክሕደትም) ፡ በተጠነ
ቀቁ ፡ ኖሮ ፡ ከእነሱ ፡ ኃጢአቶቻ
ቸውን ፡ በእርግጥ ፡ ባበስንና ፡
የመጠቀሚያ ፡ ገነቶችንም ፡ በእ
ርግጥ ፡ ባገባናቸው ፡ ነበር ።
66 እነሱም ፡ ተውራትንና ፡ ኢንጂ
ልን ፡ ከጌታቸውም ፡ ወደነሱ ፡
የተወረደውን ፡ መጽሐፍ ፡ ባቋ
ቋሙ ፡ (በሠሩበት) ፡ ኖሮ ፡ ከበላ
ያቸውና ፡ ከእግሮቻቸው ፡ ስር ፡
በተመገቡ ፡ ነበር ፤ ከነሱ ፡ ውስጥ፡
ትክክለኞች ፡ ሕዝቦች ፡ አሉ ፤
ከነሱም ፡ ብዙዎቹ ፡ የሚሠሩት ፡
ነገር ፡ ከፋ !
67 አንተ ፡ መልክተኛ ፡ ሆይ ! ከጌ
ታህ ፡ ወዳንተ ፡ የተወረደውን ፡
አድርስ ፤ ባትሠራም ፡ (1) መልክ
ቱን፡ አላደረስክም፤ አላህም፡
ከሰዎች፡ ይጠብቅሃል፤ አላህ፡
ከሓዲዎችን ፡ ሕዝቦች ፡
አያቀናምና።
68 ፡—እላንተ ፡ የመጽሐፉ ፡ ባለቤ
ቶች ፡ ሆይ ! ተውራትንና ፡ ኢን
ጂልን ፡ ከጌታችሁም ፡ ወደናንተ ፡
የተወረደውን ፡ እስከምታቆሙ ፡
(እስከምትሠሩባቸው) ፡ ድረስ ፡
በምንም ፡ ላይ ፡ አይደላችሁም ፡
በላቸው ፤ ከጌታህም ፡ ወደ ፡ አንተ
የተወረደው ፡ ቁርአን ፡ ከነሱ ፡
ብዙዎቹን ፡ ትዕቢትንና ፡ ክሕደ
ትን ፡ በእርግጥ ፡ ይጨምርባቸ
ዋል ፤ በከሓዲያን ፡ ሕዝቦችም ፡
ላይ ፡ አትዘን ።
69 እነዚያ ፡ ያመኑና ፡ እነዚያም ፡
ይሁዳውያን ፡ የኾኑ ፡ ሳቢያና
ችም ፡ ክርስቲያኖችም ፡ (ከነርሱ)፡
በአላህና ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡
ያመነና ፡ መልካምን ፡ ሥራ ፡
የሠራ ፡ ሰው ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡
ፍርሃት ፡ የለባቸውም ፤ እነርሱም፡
አያዝኑም ።
70 የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ የጠበቀ ፡
ቃል ፡ ኪዳን ፡ በእርግጥ ፡ ያዝንባ
ቸው ፤ ወደነሱም ፡ መልክተኞ
ችን ፡ላክን ፤ ነፍሶቻቸው ፡ በማት
ወደው ፡ ነገር ፡ መልክተኛ ፡ በመ
ጣቸው ፡ ቍጥር ፡ ከፊሉን ፡ አስተ
ባበሉ ፤ ከፊሉንም ፡ ይገድላሉ ።
71 ፈተናም ፡ አለመኖርዋን ፡ ጠረ
ጠሩ ፤ ታወሩም ፤ ደነቆሩም ፤ ከዚ
ያም ፡ አላህ ፡ ከነርሱ ፡ ላይ ፡ ጸጸ
ትን ፡ ተቀበለ ፤ ከዚያም ፡ ከነሱ ፡
ብዙዎቹ ፡ ታወሩ ፤ ደነቆሩም ፤
አላህም ፡ የሚሠሩትን ፡ ሁሉ ፡
ተመልካች ፡ ነው ።
72 እነዚያ ፡ አላህ ፡ እርሱ ፡ የመር
የም ፡ ልጅ ፡ አልመሲሕ ፡ ነው ፡
ያሉ ፡ በእርግጥ ፡ ካዱ ፤ አልመሲ
ሕም ፡ አለ ፡— የእስራኤል ፡
ልጆች ፡ ሆይ ! ጌታዬንና ፡ ጌታ
ችሁን ፡ አላህን ፡ ተገዙ ፤ እነሆ !
በአላህ ፡ የሚያጋራ ፡ ሰው ፡ አላህ ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ ገነትን ፡ በእርግጥ ፡
እርም ፡ አደረገ ፤ መኖሪያውም ፡
እሳት ፡ ናት ፤ ለበዳዮችም ፡ ምንም
ረዳቶች ፡ የሏቸውም ።
73 እነዚያ ፡ አላህ ፡ የሦስት ፡ ሦስ
ተኛ ፡ ነው ፡ (1) ያሉ ፡ በእርግጥ ፡
ካዱ ፤ ከአምላክም ፡ አንድ ፡ አም
ላክ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ የለም ፤ ከሚ

1 ጥቂትንም ፡ ብታስቀር ።

1 ከሦስት፡ አማልክት፡ አንዱ፡ ነው፡ ያሉ፤ (በሥላሴ፡ የሚያምኑ)።



ሉትም ፡ ነገር ፡ ባይከለከሉ፥
ከነሱ ፡ እነዚያን ፡ የካዱትን ፡ አሳ
ማሚ ፡ ቅጣት ፡ በእርግጥ ፡ ይነካ
ቸዋል ።
74 ወደ ፡ አላህ ፡ አይመለሱምና ፡
ምሕረትን ፡ አይለምኑትምን ?
አላህም ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።
75 የመርየም ፡ ልጅ ፡ አልመሲሕ ፡
ከበፊቱ ፡ መልክተኞች ፡ በእርግጥ፡
ያለፉ ፡ የኾነ ፡ መልክተኛ ፡ እንጅ፡
ሌላ ፡ አይደለም ፤ እናቱም ፡ በጣ
ም ፡ እውነተኛ ፡ ናት ፤ (ሁለቱም)፡
ምግብን ፡ የሚበሉ ፡ ነበሩ ፤ አንቀ
ጾችን ፡ ለነርሱ ፡ (ለከሓዲዎች) ፡
እንዴት ፡ እንደምናብራራ ፡ ተመ
ልከት ፤ ከዚያም ፡ (ከውነት) ፡ እን
ዴት ፡ እንደሚመለሱ ፡ ተመል
ከት ።
76 ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ለናንተ ፡ መጉዳት
ንና ፡ መጥቀምን ፡ የማይችልን ፡ ት
ገዛላችሁን ? በላቸው ፤ አላህም ፡
እርሱ ፡ ሰሚው ፡ ዐዋቂው ፡ ነው ።
77 ፡—እላንተ ፡ የመጽሐፉ ፡ ባለቤ
ቶች ፡ ሆይ ! በሃይማኖታችሁ ፡
ከውነት ፡ ሌላ ፡ የኾነን ፡ (ማለፍ) ፡
ወሰንን ፡ አትለፉ ፤ በፊትም ፡ በእ
ርግጥ ፡ የተሳሳቱትንና ፡ ብዙዎ
ችን ፡ ያሳሳቱትን ፡ ከቀጥተኛው ፡
መንገድም ፡ (አሁን) ፡ የተሳሳ
ቱን ፡ ሕዝቦች ፡ ከንቱ ፡ ዝንባሌ
ዎች ፡ አትከተሉ ፡ በላቸው ።
78 ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እነዚያ ፡
የካዱት ፡ በዳውድና ፡ በመርየም ፡
ልጅ ፡ በዒሳ ፡ ምላስ ፡ ተረገሙ ፤
ይኸ ፡ ትእዛዝን ፡ በመጣሳቸውና ፡
ወሰንን ፡ የሚያልፉ ፡ በመኾና
ቸው ፡ ነው ።
79 ከሠሩት ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ አይከላ
ከሉም ፡ (1) ነበር ፤ ይሠሩት ፡ የነ
በሩት ፡ ነገር ፡ በእርግጥ ፡ ከፋ !
80 ከነሱ ፡ ብዙዎቹን ፡ እነዚያን ፡ የካ
ዱትን ፡ ሲወዳጁ ፡ ታያለህ ፤
በነሱ ፡ ላይ ፡ አላህ ፡ የተቆጣባ
ቸው ፡ በመኾኑ ፡ ለነርሱ ፡ ነፍሶ
ቻቸው ፡ ያስቀደሙት ፡ ሥራ ፡
በጣም ፡ ከፋ ፤ እነሱም ፡ በቅጣት ፡
ውስጥ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ናቸው ።
81 በአላህና ፡ በነቢዩ ፡ ወደርሱም ፡
በተወረደው ፡ ቁርአን ፡ የሚያ
ምኑ ፡ በኾኑ ፡ ኖሮ ፡ ወዳጆች ፡
አድርገው ፡ ባልያዙዋቸው ፡ ነበር፤
ግን ፡ ከነርሱ ፡ ብዙዎቹ ፡ አመጠ
ኞች ፡ ናቸው ።
82 ይሁዶችንና ፡ እነዚያን ፡ ያጋሩ
ትን ፡ ለነዚያ ፡ ለአመኑት ፡ በጠ
ላትነት ፡ ከሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይበ
ልጥ ፡ የበረቱ ፡ ኾነው ፡ በእርግጥ ፡
ታገኛለህ ፤ እነዚያንም ፡ እኛ ፡
ክርስቲያኖች ፡ ነን ፡ ያሉትን ፡ ለነ
ዚያ ፡ ለአመኑት ፡ በወዳጅነት ፡
በእርግጥ ፡ ይበልጥ ፡ የቀረቧቸው ፡
ኾነው ፡ ታገኛለህ ፤ ይህ ፡ ከነሱ ፡
ውስጥ ፡ ቀሳውስትና ፡ መነኮሳት ፡
በመኖራቸውና ፡ እነሱም ፡ የማ
ይኮሩ ፡ በመኾናቸው ፡ ነው ። (2)

★ ★ ★

83 ወደ ፡ መልክተኛውም ፡ የተወረ
ደውን ፡ (ቁርአን) ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡
እውነቱን ፡ ከማወቃቸው ፡ የተነሳ ፡
ዓይኖቻቸው ፡ እንባን ፡ ሲያፈሱ ፡
ታያለህ ፤ ጌታችን ፡ ሆይ ! አመ

1 አንዱ ፡ አንዱን ፡ አይከለከልም ፤ አይነቃ
ቀፉም ።

2 ይህ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነጋሢ ፡ ልዑካን ፡
የተነገረ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

ንን ፤ ከመስካሪዎቹም ፡ ጋር ፡
ጻፈን ፡ ይላሉ ።

84 በአላህና ፡ ከውነትም ፡ በመጣ
ልን ፡ ነገር ፡ የማናምን ፡ ጌታች
ንም ፡ ከመልካም ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡
ሊያስገባን ፡ የማንከጅል ፡ ለኛ ፡
ምን ፡ አለን ፡ (ይላሉ) ።

85 ባሉትም ፡ ምክንያት ፡ አላህ ፡
በስሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈ
ሱባቸውን ፡ ገነቶች ፡ በውስጣ
ቸው ፡ ዘውታሪዎች ፡ሲኾኑ ፡
መነዳቸው ፤ ይህም ፡ የበጎ ፡ ሠሪ
ዎች ፡ ዋጋ ፡ ነው ።

86 እነዚያም ፡ የካዱና ፡ በአንቀጾቻ
ችን ፡ ያስተባበሉ ፡ እነዚያ ፡ የእ
ሳት ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ።

87 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ !
አላህ ፡ ለናንተ ፡ የፈቀደላችሁን ፡
ጣፋጮች ፡ እርም ፡ አታድርጉ ፤
ወሰንንም ፡ አትለፉ ፤ አላህ ፡
ወሰን ፡ አላፊዎችን ፡ አይወድ
ምና ።

88 አላህም ፡ ከሰጣችሁ ፡ሲሳይ ፡ የተ
ፈቀደ ፡ ጣፋጭ ፡ ሲኾን ፡ ብሉ ፤
ያንንም ፡ እናንተ ፡ በርሱ ፡ አማ
ኞች ፡ የኾናችሁበትን ፡ አላህን ፡
ፍሩ ።

89 አላህ፡ በመሐላዎቻችሁ፡ በው
ድቁ ፡ አይዛችሁም ፤ ግን ፡ መሐ
ላዎችን ፡ ባሰባችሁት ፡ ይይዛች
ኋል ፤ ማስተስረያውም ፡ (ባፈረሳ
ችሁት ፡ ጊዜ) ፡ ቤተሰቦቻችሁን ፡
ከምትመግቡት ፡ ከመካከለኛው ፡
(ምግብ) ፡ ዐሥርን ፡ ምስኪኖች ፡
ማብላት ፡ ወይም ፡ እነሱን ፡ ማል
በስ ፡ ወይም ፡ ጫንቃን ፡ ነጻ ፡
ማውጣት ፡ ነው ፤ (ከተባሉት ፡
አንዱን) ፡ ያላገኘም ፡ ሰው ፡
ሦስት ፡ ቀኖችን ፡ መጾም ፡ ነው ፤
ይህ ፡ በማላችሁ ፡ ጊዜ ፡ የመሐሎ
ቻችሁ ፡ ማስተስረያ ፡ ነው ፤ መሐ
ሎቻችሁንም ፡ ጠብቁ ፤ እንደ
ዚሁ ፡ አላህ ፡ ለናንተ ፡ አንቀጾ
ችን ፡ ያብራራል ፤ እናንተ ፡ ልታ
መሰግኑ ፡ ይከጀላልና ።

90 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! የሚያ
ሰክር ፡ መጠጥ ፡ ቁማርም ፡ ጣዖታ
ትም ፡ አዝላምም ፡ (1) ከሰይጣን ፡
ሥራ ፡ የኾኑ ፡ እርኩስ ፡ ብቻ ፡ ና
ቸው ፤ (እርኩስን) ፡ ራቁትም ፤
ልትድኑ ፡ ይከጀላልና ።

91 ሰይጣን ፡ የሚፈልገው ፡ በሚያ
ሰክር ፡ መጠጥና ፡ በቁማር ፡ በመ
ካከላችሁ ፡ ጠብንና ፡ ጥላቻን ፡
ሊጥል ፡ አላህን ፡ ከማውሳትና ፡
ከስግደትም ፡ ሊያግዳችሁ ፡ ብቻ ፡
ነው ፡ ታዲያ ፡ እናንተ ፡ (ከነ
ዚህ) ፡ ተከልካዮች ፡ ናችሁን ?
(ተከልከሉ) ።

92 አላህንም ፡ ተገዙ ፤ መልክተኛው
ንም ፡ ታዘዙ ፤ ተጠንቀቁም ፤
ብትሸሹም ፡ በመልክተኛችን ፡
ላይ ፡ ያለበት ፡ ግልጽ ፡ ማድረስ ፡
ብቻ ፡ መኾኑን ፡ ዕወቁ ።

93 በነዚያ ፡ ባመኑትና ፡ በጎ ፡ ሥራ
ዎችን ፡ በሠሩት ፡ ላይ ፡ (ከሕደ
ትን) ፡ በተጠነቀቁና ፡ ባመኑ ፡
መልካም ፡ ሥራዎችንም ፡ በሠሩ ፡
ከዚያም ፡ (የሚያሰክርንና ፡ ቁማ
ርን) ፡ በተጠነቀቁና ፡ ባመኑ ፡
ከዚያም ፡ (ከተከለከለው ፡ ሁሉ) ፡
በተጠነቀቁና ፡ (ሥራን) ፡ ባሳ
መሩ ፡ ጊዜ ፡ (ከመከልከሉ ፡
በፊት) ፡ በተመገቡት ፡ ነገር ፡
ኃጢአት ፡ የለባቸውም ፤ አላህም ፡
በጎ ፡ ሠሪዎችን ፡ ይወዳል ።

1 የመጠንቆያ ፡ ዕንጨቶች ።



94 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ !
(በሐጅ ፡ ጊዜ) ፡ እጆቻችሁና ፡
ጦሮቻችሁ ፡ በሚያገኙት ፡ ታዳኝ፡
አውሬ ፡ አላህ ፡ ይሞክራችኋል ፤
በሩቅ ፡ ኾኖ ፡ የሚፈራውን ፡ ሰው፡
አላህ ፡ ሊገልጽ ፡ (ይሞክራች
ኋል) ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወሰንን ፡
ያለፈና ፡ ያደነ ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡
አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ አለው ።

95 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! እና
ንተ ፡ በሐጅ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡
ስትኾኑ ፡ አውሬን ፡ አትግደሉ ፤
ከናንተም ፡ እያወቀ ፡ የገደለው ፡
ሰው ፡ ቅጣቱ ፡ ከናንተ ፡ ሁለት ፡
የትክክለኛነት ፡ ባለቤቶች ፡ የሚ
ፈርዱበት ፡ የኾነ ፡ ወደ ፡ ካዕባ ፡
ደራሽ ፡ መሥዋዕት ፡ ሲኾን ፡
ከቤት ፡ እንስሳዎች ፡ የገደለውን ፡
ነገር ፡ ብጤ ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡
ምስኪኖችን ፡ ማብላት ፡ ወይም ፡
የዚህን ፡ ልክ ፡ መጾም ፡ ማስተስ
ረያ ፡ ነው ፤ (ይኸም) ፡ የሥራ
ውን ፡ ከባድ ፡ ቅጣት ፡ እንዲቀ
ምስ ፡ ነው ፤ (ሳይከለከል ፡ በፊት)፡
ካለፈው ፡ ነገር ፡ አላህ ፡ ይቅርታ ፡
አደረገ ፤ የተመለሰም ፡ ሰው ፡
አላህ ፡ ከርሱ ፡ ይበቀላል ፤ አላ
ህም ፡ አሸናፊ ፡ የመበቀል ፡ ባለ
ቤት ፡ ነው ።

96 የባሕር ፡ ታዳኝና ፡ ምግቡ ፡ (1)
ለናንተም ፡ ለመንገደኞችም ፡
መጠቀሚያ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ለና
ንተ ፡ ተፈቀደ ፤ በሐጅም ፡ ላይ ፡
እስካላችሁ ፡ ድረስ ፡ የየብስ ፡
አውሬ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ እርም ፡
ተደረገ ፤ ያንንም ፡ ወደርሱ ፡ የም
ትሰበሰቡበትን ፡ አላህን ፡ ፍሩ ።

97 ከዕባን ፡ የተከበረውን ፡ ቤት ፡
ከልክል ፡ የኾነውንም ፡ ወር ፡
መስዋዕቱንና ፡ ባለ ፡ ምልክቶ
ቹንም ፡ መንጋዎች ፡ አላህ ፡ ለሰ
ዎች ፡ መቋቋሚያ ፡ አደረገ ፤ ይኸ ፡
አላህ ፡ በሰማያት ፡ ያለውን ፡
ሁሉ ፡ በምድርም ፡ ያለውን ፡
ሁሉ ፡ የሚያውቅ ፡ መኾኑን ፡
አላህም ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡
መኾኑን ፡ እንድታውቁ ፡ ነው ።

98 አላህ ፡ ቅጣተ ፡ ብርቱ ፡ መኾኑን ፡
አላህም ፡ መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ መኾ
ኑን ፡ ዕወቁ ።

99 በመልክተኛው ፡ ላይ ፡ ማድረስ ፡
እንጅ ፡ ሌላ ፡ የለበትም ፤ አላ
ህም ፡ የምትገልጹትን ፡ ነገር ፡
የምትደብቁትንም ፡ ሁሉ ፡ ያው
ቃል ።

100 የመጥፎው ፡ (ገንዘብ) ፡ ብዛት ፡
ቢያስደንቃችሁም ፡ እንኳ ፡ መጥ
ፎውና ፡ ጥሩው ፡ አይተካከሉም ፡
ባለልቦች ፡ ሆይ ! አላህንም ፡
ፍሩ ፤ እናንተ ፡ ልትድኑ ፡ ይከጀ
ላልና ፤ በላቸው ።

101 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ለና
ንተ ፡ ቢገለጹ ፡ ከሚያስከፏችሁ ፡
ነገሮች ፡ አትጠይቁ ፤ ቁርአንም ፡
በሚወርድበት ፡ ጊዜ ፡ ከርሷ ፡
ብትጠይቁ ፡ ለናንተ ፡ ትገለጻለች ፤
ከርሷ ፡ (1) አላህ ፡ ይቅርታ ፡ አደ
ረገ ፤ አላህም ፡ መሐሪ ፡ ታጋሽ ፡
ነው ።

102 ከናንተም ፡ በፊት ፡ ሕዝቦች ፡ በእ
ርግጥ ፡ ጠየቋት ፤ ከዚያም ፡ በርሷ፡
(ምክንያት) ፡ ከሓዲዎች ፡ ኾኑ ።

103 ከበሒራ ፡ (2) ከሳኢባም ፡ (3)

1 በውስጡ ፡ ሞቶ ፡ የተገኘው ።

1 ከአለፈው ፡ ጥያቄያችሁ ።
2 ዐሥር ፡ የወለደችን ፡ ግመል ፡ ጆሮ ፡ መተ
ልተል ።
3 ዐሥር ፡ ሴቶች ፡ ወልዳ ፡ ስድ ፡ የተደረገች ።

ከወሲላም ፡ (1) ከሓምም ፡ (2) አላህ ፡ ምንንም ፡ (ሕግ) ፡ አላደረገም ፣ ግን ፡ እነዚያ ፡ የካዱት ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ውሸትን ፡ ይቀጣጥፋሉ ፣ አብዛኞቻቸውም ፡ አያውቁም ።

104 ለነርሱም ፡ አላህ ፡ ወደ ፡ አወረደው ና ፡ ወደ ፡ መልክተኛው ፡ ኑ ፡ በተባሉ ፡ ጊዜ ፡ አባቶቻችንን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ያገኘንበት ፡ ነገር ፡ ይበቃናል ፡ ይላሉ ፣ አባቶቻቸው ፡ ምንም ፡ የማያውቁና ፡ የማይምሩ ፡ ቢኾኑም ? (ይኸንን ፡ ማለት ፡ ይበቃቸዋልን ?)

105 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ነፍሶቻችሁን ፡ (ከእሳት) ፡ ያዙ ፣ (ጠብቁ) ፡ በተመራችሁ ፡ ጊዜ ፡ የተሳሳተ ፡ ሰው ፡ አይጐዳችሁም ፣ የሁላችሁም ፡ መመለሻ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፣ ትሠሩትም ፡ የነበራችሁትን ፡ ሁሉ ፡ ይነግራችኋል ።

106 እናንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አንዳችሁን ፡ ሞት ፡ በመጣበት ፡ ጊዜ ፡ በኑዛዜ ፡ ወቅት ፡ የመካከላችሁ ፡ ምስክርነት ፡ ከናንተ ፡ ሁለት ፡ የትክክለኛነት ፡ ባለቤቶች ፡ የኾኑ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ በምድር ፡ ብትጓዙና ፡ የሞት ፡ አደጋ ፡ ብትነካችሁ ፡ ከሌሎቻችሁ ፡ የኾኑ ፡ ሁለት ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ (መመስከር) ፡ ነው ። ብትጠራጠሩ ፡ ከሶላት ፡ (ከዐሱር) ፡ በኋላ ፡ ታቆሟቸውና ፡ (የሚመሰክርለት ፡ ሰው) ፡ የዝምድና ፡ ባለቤት ፡ ቢኾንም ፡ እንኳ ፡ በርሱ ፡ ዋጋን ፡ አንገዛም ፡ የአላህንም ፡ ምስክርነት ፡ አንደብቅም፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ (ደብቀን ፡ ብንገኝ) ፡ እኛ ፡ ከኃጢአተኞች ፡ ነን ፡ ብለው ፡ በአላህ ፡ ስም ፡ ይምላሉ ።

107 እነርሱም ፡ ኃጢአትን ፡ (በውሸት፡ መስክረው) ፡ የተገቡ ፡ መኾናቸው ፡ ቢታወቅ ፡ ከነዚያ ፡ (ለሟቹ) ፡ ቅርቦች ፡ በመኾን ፡ (ውርስ) ፡ ከተገባቸው ፡ የኾኑ ፡ ሁለት ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ በስፍራቸው ፡ (በምስክሮች ፡ ስፍራ) ፡ ይቆሙና ፡ ምስክርነታችን ፡ ከነሱ ፡ ምስክርነት ፡ ይልቅ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ወሰንም ፡ አላለፍንም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ ከበዳዮች ፡ ነን ፡ ሲሉ ፡ በአላህ ፡ ይምላሉ ።

108 ይህ ፡ ምስክርነትን ፡ በተገቢዋ ፡ ላይ ፡ ለማምጣታቸው ፡ ወይም ፡ ከመሐላዎቻቸው ፡ በኋላ ፡ የመሐላዎችን ፡ (ወደ ፡ ወራሾች) ፡ መመለስን ፡ ለመፍራት ፡ በጣም ፡ የቀረበ ፡ ነው ፣ አላህንም ፡ ፍሩ ፣ ስሙም ፣ አላህም ፡ አመጠኞች ፡ ሕዝቦችን ፡ አይመራም ።

109 አላህ ፡ መልክተኞቹን ፡ የሚሰበስብበትንና ፡ ምን ፡ መልስ ፡ ተሰጣችሁ ፡ የሚልበትን ፡ ቀን ፡ (አስታውስ) ፣ ለኛ ፡ ምንም ፡ ዕውቀት ፡ የለንም ፡ አንተ ፡ ሩቆችን ፡ በጣም፡ ዐዋቂ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህ ፡ ይላሉ።

110 አላህ ፡ በሚል ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፡— የመርየም ፡ ልጅ ፡ ዒሳ ፡ ሆይ ! በአንተና ፡ በእናትህ ፡ ላይ ፡ (የዋልኩላችሁን) ፡ ጸጋዬን ፡ አስታውስ ፣ በሕጻንነትና ፡ በከፈኒሳንነት ፡ (የበሰለ ፡ ሰው ፡ ኾነህ) ፡ ሰዎችን ፡ የምትናገር ፡ ስትኾን ፡

---

1 በሴት ፡ ተበክራ ፡ ሴት ፡ የቀጠለችን ፡ ለወንዶች ፡ ምግብ ፡ ብቻ ፡ መወሰን ።

2 ዐሥር ፡ ሴቶች ፡ ያስወለደን ፡ ኮርማ ፡ እንዳይጫን ፡ ማድረግን ።



በቅዱሱ ፡ መንፈስ ፡ (በገብሬል) ፡ ባበረታሁህ ፡ ጊዜ ፡ ጽሕፈትንና ፡ ጥበብንም ፡ ተውራትንና ፡ ኢንጂልንም ፡ ባስተማርኩህ ፡ ጊዜ ፡ ከጭቃም ፡ የወፍ ፡ ቅርጽ ፡ ብጤ ፡ በፈቃዴ ፡ በምትሠራና ፡ በውስጧ ፡ በምትነፋ ፡ በፈቃዴም ፡ ወፍ ፡ በምትኾን ፡ ጊዜ ፡ ዕውርም፡ ኾኖ ፡ የተወለደንና ፡ ለምጻምንም በፈቃዴ ፡ በምታሽር ፡ ጊዜ ፡ ሙታንንም ፡ በፈቃዴ ፡ (ከመቃብራቸው) ፡ በምታወጣ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ በተአምራት ፡ በመጣህባቸውና ፡ ከነሱ ፡ እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ይህ ፡ ግልጽ ፡ ድግምት ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ (ሊገድሉህ ፡ ሲያስቡህ) ፡ ከአንተ ፡ ላይ ፡ በከለከልኩልህም፡ ጊዜ ፡ (ያደረግሁልህን ፡ ውለታ ፡ አስታውስ) ።

111 ወደ ፡ ሐዋርያትም ፡ በኔና ፡ በመልክተኛዬ ፡ እመኑ ፡ በማለት ፡ ባዘዝኩ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፣ አመንን ፣ እኛም ፡ እስላሞች ፡ መኾናችንን ፡ መስክር ፡ አሉ ።

112 ሐዋርያት ፡— የመርየም ፡ ልጅ ፡ ዒሳ ፡ ሆይ ፡ ጌታህ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ከሰማይ ፡ ማእድን ፡ ሊያወርድልን፡ ይችላልን ? ባሉ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፣ ምእምናን ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ አላህን ፡ ፍሩ ፡ አላቸው ።

113 ከርሷ ፡ ልንበላ ፡ ልቦቻችንም ፡ ሊረኩ ፡ እውነት ፡ ያልከንም ፡ መኾንህን ፡ ልናውቅና ፡ በርሷም፡ ላይ ፡ ከመስካሪዎች ፡ ልንኾን ፡ እንፈልጋለን ፡ አሉ ።

114 የመርየም ፡ ልጅ ፡ ዒሳ ፡ አለ ፡— ጌታችን ፡ አላህ ፡ ሆይ ! ለኛ ፡ ለመጀመሪያዎቻችንና ፡ ለመጨረሻዎቻችን ፡ ባዕል ፡ (መደሰቻ) ፡ የምትኾንን ፡ ከአንተም ፡ ተአምር ፡ የኾነችን ፡ ማእድ ፡ ከሰማይ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ አውርድ ፣ ስጠንም ፣ አንተ ፡ ከሰጪዎች ፡ ሁሉ ፡ በላጭ ነህና ።

115 አላህ ፡— እኔ ፡ (ማእድዋን) ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ አውራጅዋ ፡ ነኝ ፣ በኋላም ፡ ከናንተ ፡ የሚክድ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ከዓለማት ፡ አንድንም ፡ የማልቀጣውን ፡ ቅጣት ፡ እቀጣዋለሁ ፡ አለ ።

116 አላህም ፡— የመርየም ፡ ልጅ ፡ ዒሳ ፡ ሆይ ፡ አንተ ፡ ለሰዎቹ ፡— እኔንና ፡ እናቴን ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ሁለት ፡ አምላኮች ፡ አድርጋችሁ ፡ ያዙ ፡ ብለሃልን ? በሚለው ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፣ ጥራት ፡ ይገባህ ፣ ለኔ ፡ ተገቢዬ ፡ ያልኾነን ፡ ነገር ፡ ማለት ፡ ለኔ ፡ አይገባኝም ፣ ብዬው እንደ ፡ ኾነም ፡ በእርግጥ ፡ ዐውቀኸዋል ፣ በነፍሴ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ታውቃለህ ፣ ግን ፡ አንተ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ አላውቅም ፣ አንተ ፡ ሩቆችን ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ዐዋቂ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህና ፡ ይላል ።

117 በርሱ ፡ ያዘዝከኝን ፡ ቃል ፡ ጌታዬንና ፡ ጌታችሁን ፡ አላህን ፡ ተገዙ ፡ ማለትን ፡ እንጂ ፡ ለነርሱ ፡ ሌላ ፡ አላልኩም ፣ በውስጣቸውም ፡ እስካለሁ ፡ ድረስ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ተጠባባቂ ፡ ነበርኩ ፣ በተሞላኸኝም ፡ ጊዜ ፡ (ባነሳኸኝ ፡ ጊዜ) ፡ አንተ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ተጠባባቂ ፡ ነበርክ ፣ አንተም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ዐዋቂ ፡ ነህ ።

118 ብትቀጣቸው ፡ እነርሱ ፡ ባሮችህ ፡ ናቸው ፣ ለነርሱ ፡ ብትምርም ፡

አንተ ፡ አሸናፊው ፡ ጥበበኛው ፡
ነህ ፡ (ይላል) ።
119 አላህ ፡ ይላል ፡— ይህ ፡ እውነተኞ
ችን ፡ እውነታቸው ፡ የሚጠቅም
በት ፡ ቀን ፡ ነው ፤ ለነርሱ ፡ በሥሮ
ቻቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱባቸው
በውስጣቸው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ዘው
ታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ የሚኖሩባቸው፡
ገነቶች ፡ አሉዋቸው ፤ አላህ ፡
ከነሱ ፡ (1) ወደደ ፤ እነርሱም ፡
ከርሱ ፡ (2) ወደዱ ፤ ይህ ፡ ታላቅ ፡
ዕድል ፡ ነው ።
120 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ በውስጣ
ቸውም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ንግሥና ፡
የአላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ እሱም ፡
በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ።

1 በእምነታቸውና ፡ በሥራቸው ።
2 በሰጣቸው ፡ ክብርና ፡ ምንዳ ።

## ምዕራፍ ፡ 6 ፡ አል-አንዓም ። ክፍል ፡ 7 ።

6ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-አንዓም ፡ (የቤት ፡ እንስሳዎች ፡ ምዕራፍ) ፤ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 165 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 ምስጋና ፡ ለዚያ ፡ ሰማያትንና ፡
ምድርን ፡ ለፈጠረው ፡ ጨለማዎ
ችንና ፡ ብርሃንንም ፡ ላደረገው ፡
ለአላህ ፡ የተገባ ፡ ነው ፤ ከዚያም ፡
እነዚያ ፡ የካዱት ፡ (ጣዖታትን) ፡
በጌታቸው ፡ ያስተካክላሉ ።
2 እርሱ ፡ ያ ፡ ከጭቃ ፡ የፈጠራችሁ ፡
ከዚያም ፡ (የሞት) ፡ ጊዜን ፡ የወ
ሰነ ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ ዘንድ ፡
(ለትንሣኤ) ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡
አልለ ፤ ከዚያም ፡ እናንተ ፡ (በመ
ቀስቀሳችሁ) ፡ ትጠራጠራላችሁ ።
3 እርሱም ፡ ያ ፡ በሰማያትና ፡ በም
ድር ፡ (ሊግገዙት ፡ የሚገባው) ፡
አላህ ፡ ነው ፤ ምስጢራችሁን ፡
ግልጻችሁንም ፡ ያውቃል ፤ የምት
ሠሩትንም ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል ።
4 ከጌታቸውም ፡ አንቀጾች ፡ አንዲ
ትም ፡ አንቀጽ ፡ አትመጣቸውም ፡
ከርሷ ፡ የሚሸሹ ፡ ቢኾኑ ፡ እንጅ ።
5 በውነቱም ፡ (በቁርአን) ፡ በመጣ
ላቸው ፡ ጊዜ ፡ በእርግጥ ፡ አስተ
ባበሉ ፤ በርሱም ፡ ይሳለቁበት ፡
የነበሩት ፡ ነገር ፡ ዜናዎች ፡ (ቅ
ጣት) ፡ በእርግጥ ፡ ይመጣባቸ
ዋል ።
6 ከበፊታቸው ፡ ከክፍለ ፡ ዘመናት ፡
ሕዝቦች ፡ ብዙዎችን ፡ ማጥፋታ
ችንን ፡ አላዩምን ? ለናንተ ፡ ያላስ
መቸነውን ፡ (ለነርሱ) ፡ በምድር ፡
ውስጥ ፡ አስመቸናቸው ፤ በነር
ሱም ፡ ላይ ፡ ዝናምን ፡ የተከታ
ተለ ፡ ሲኾን ፡ ላክን ፤ ወንዞች
ንም ፡ በስራቸው ፡ እንዲፈሱ ፡ አደ
ረግን ፤ በኃጢአቶቻቸውም ፡ አጠ
ፋናቸው ፤ ከኋላቸውም ፡ ሌሎ
ችን ፡ የክፍል ፡ ዘመን ፡ ሰዎች ፡
አስገኘን ።



7 ባንተም ፡ ላይ ፡ በወረቀት ፡ የተጻ
ፈን ፡ መጽሐፍ ፡ ባወረድንና ፡
በእጆቻቸው ፡ በነኩት ፡ ኖሮ ፡
እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡ ይህ ፡
ግልጽ ፡ ድግምት ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡
አይደለም ፡ ባሉ ፡ ነበር ።
8 በርሱም ፡ (በሙሐመድ) ፡ ላይ ፡
መልአክ ፡ አይወረድለትም ፡ ኖሮ
አልን ? አሉ ፤ መልአክን ፡ ባወረድ
ንም ፡ ኖሮ ፡ (ባያምኑ ፡ የጥፋታ
ቸው) ፡ ነገሩ ፡ በተፈረደ ፡ ነበር ፤
ከዚያም ፡ አይቆዩም ፡ ነበር ።
9 (መልክተኛውን) ፡ መልአክም ፡
ባደረግነው ፡ ኖሮ ፡ ወንድ ፡ (በሰ
ው ፡ ምስል) ፡ ባደረግነው ፡ ነበር ፤
በነርሱም ፡ ላይ ፡ የሚያመሳስ
ሉትን ፡ ነገር ፡ (1) ባመሳሰልን
ባቸው ፡ ነበር ።
10 ካንተ ፡ በፊትም ፡ በመልክተኞች ፡
በእርግጥ ፡ ተላገጢል ፤ በነዚያም፡
ከነሱ ፡ ባላገጡት ፡ ላይ ፡ በርሱ ፡
ያላግጡ ፡ የነበሩት ፡ ነገር ፡ (ቅ
ጣት) ፡ ወረደባቸው ።
11 በምድር ፡ ላይ ፡ ኺዱ ፡ የአስተባባ
ዮችም ፡ መጨረሻ ፡ እንዴት ፡
እንደ ፡ ነበረ ፡ ተመልከቱ ፡ በላ
ቸው ።
12 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡
ሁሉ ፡ የማን ፡ ነው ? በላቸው ፡
(ሌላ ፡ መልስ ፡ የለምና) ፡ የአላህ ፡
ነው ፡ በል ፤ በነፍሱ ፡ ላይ ፡ እዝነ
ትን ፡ ጻፈ ፤ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡
በርሱ ፡ ጥርጥር ፡ የሌለበት ፡
ሲኾን ፡ በእርግጥ ፡ ይሰበስባች
ኋል ፤ እነዚያ ፡ ነፍሶቻቸውን ፡
ያከሰሩ ፡ ናቸው ፤ እነርሱም ፡ አያ
ምኑም ።

1 ይህ ፡ ሰው ፡ እንጅ ፡ አይደለም ፡ በማለት ።

13 በሌሊትና ፡ በቀንም ፡ ጸጥ ፡ ያለው
ሁሉ ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ እር
ሱም ፡ ሰሚው ፡ ዐዋቂው ፡ ነው ።
14 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ ፈጣሪ ፡
ከኾነው ፡ አላህ ፡ እርሱ ፡ የሚመ
ግብ ፡ የማይመገብም ፡ ሲኾን ፡
ሌላን ፡ አምላክ ፡ እይዛለሁን ?
በላቸው ፤ እኔ ፡ መጀመሪያ ፡ ትእ
ዛዝን ፡ ከተቀበለ ፡ ሰው ፡ ልኾን ፡
ታዘዝኩ ፤ ከአጋሪዎችም ፡ ፈጽሞ፡
አትኹን ፡ (ተብያለሁ) ፡ በላቸው ።
15 እኔ ፡ በጌታዬ ፡ ባምጥ ፡ የታላቁን ፡
ቀን ፡ ቅጣት ፡ እፈራለሁ ፡ በላ
ቸው ።
16 በዚያ ፡ ቀን ፡ ከርሱ ፡ ላይ ፡ (ቅጣት
የሚመለስለት ፡ ሰው ፡ (አላህ) ፡
በእርግጥ ፡ አዘነለት ፤ ይህም ፡
ግልጽ ፡ ማግኘት ፡ ነው ።
17 አላህም ፡ በጉዳት ፡ ቢነካህ ፡
ለርሱ ፡ (ለጉዳቱ) ፡ ከእርሱ ፡
በቀር ፡ ሌላ ፡ አስወጋጅ ፡ የለም ፤
በበጎም ፡ ነገር ፡ ቢነካህ ፡ እርሱ ፡
በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ።
18 እርሱም ፡ ከባሮቹ ፡ በላይ ፡ ሲኾን፡
አሸናፊ ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ ጥበበ
ኛው ፡ ውስጥ ፡ ዐዋቂው ፡ ነው ።
19 በምስክርነት ፡ ከነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ይበ
ልጥ ፡ ታላቅ ፡ ማነው ? በላቸው ፤
(ሌላ ፡ መልስ ፡ የለምና) ፡ አላህ ፡
ነው ፤ በእኔና ፡ በናንተ ፡ መካከል ፡
መስካሪ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ቁርአን ፡
እናንተንና ፡ የደረሰውን ፡ ሰው ፡
ሁሉ ፡ በርሱ ፡ ላስፈራራበት ፡
ወደኔ ፡ ተወረደ ፤ ከአላህ ፡ ጋር ፡
ሌሎች ፡ አማልክት ፡ መኖራቸ
ውን ፡ እናንተ ፡ ትመሰክራላች
ሁን ? በላቸው ፤ እኔ ፡ አልመሰክ
ርም ፡ በላቸው ፤ እርሱ ፡ አንድ ፡
አምላክ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ እኔም ፡

ከምታጋሩት ፡ ነገር ፡ ንጹሕ፡ ነኝ ፡
በላቸው ።
20 እነዚያ ፡ መጽሐፍን ፡ የሰጠና
ቸው ፡ ልጆቻቸውን ፡ እንደሚያ
ውቁ ፡ (ሙሐመድን) ፡ ያውቁ
ታል ፤ እነዚያ ፡ ከነርሱ ፡ ውስጥ ፡
ነፍሶቻቸውን ፡ ያከሰሩት ፡ እነ
ርሱ ፡ አያምኑም ።
21 በአላህም ፡ ላይ ፡ ውሸትን ፡ ከቀጣ
ጠፈ ፡ ወይም ፡ በአንቀጾቹ ፡ ካስ
ተባበለ ፡ ሰው ፡ ይበልጥ ፡ በደ
ለኛ ፡ ማነው ? እነሆ ፡ በደለኞች ፡
አይድኑም ።
22 ሁላቸውንም ፡ የምንሰበስብበት
ንና ፡ ከዚያም ፡ ለነዚያ ፡ (ጣዖታ
ትን ፡ ለአጋሩት ፡-እነዚያ ፡ (ለአ
ላህ) ፡ ተጋሪዎች ፡ ናቸው ፡ ብላ
ችሁ ፡ ታስቧቸው ፡ የነበራችሁት ፡
ተጋሪዎቻችሁ ፡ የት ፡ ናቸው ?
የምንልበትን ፡ ቀን ፡ (አስታ
ውስ) ።
23 ከዚያም ፡ መልሳቸው ፡ በጌታ
ችን ፡ በአላህ ፡ ይኹንብን ፡ አጋሪ
ዎች ፡ አልነበርንም ፡ ማለት ፡
እንጅ ፡ ሌላ ፡ አትኾንም ።
24 በነፍሶቻቸወ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡
እንደ ፡ ዋሹና ፡ ይቀጣጥፉት ፡ የነ
በሩት ፡ ነገር ፡ ከነሱ ፡ እንዴት ፡
እንደ ፡ ተሰወረ ፡ ተመልከት ።
25 ከነርሱም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ የሚያዳ
ምጥ ፡ ሰው ፡ አልለ ፤ በልቦቻቸ
ውም ፡ ላይ ፡ እንዳያውቁት ፡ ሽፋ
ኖችን፡ በጆሮዎቻቸውም፡ ላይ ÷
ድንቁርናን ፡ አደረግን ፤ ታምር
ንም ፡ ሁሉ ፡ ቢያዩ ፡ በርሷ ፡ አያ
ምኑም ፤ በመጡህም ፡ ጊዜ ፡ የሚ
ከራከሩህ ፡ ሲኾኑ ፡ እነዚያ ፡ የካ
ዱት ፡ ይህ ፡ (ቁርአን) ፡ የቀድሞ
ዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ጽሑፍ ፡ ተረቶች ፡
እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፡ ይላሉ ።
26 እነርሱም ፡ (ሰዎችን) ፡ ከርሱ ፡
ይከለክላሉ ፤ ከርሱም ፡ ይርቃሉ ፤
ነፍሶቻቸውንም ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡
አያጠፉም ፤ ግን ፡ አያውቁም ።
27 በእሳትም ፡ ላይ ፡ በተቆሙ ፡ ጊዜ ፡
(ወደ ፡ ምድረ ፡ ዓለም) ፡ ምንነው ፡
በተመለስን ፡ በጌታችንም ፡ አን
ቀጾች ፡ ባላስተባበልን ፡ ከምእም
ናንም ፡ በኾንን ፡ ዋ ፡ ምኞታችን !
ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ብታይ ፡ ኖሮ ፡ (የሚ
ያስደነግጥን ፡ ነገር ፡ ባየህ ፡ ነበር)፤
28 ይልቁንም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ይደብ
ቁት ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ ለነርሱ ፡
ተገለጸ ፤ (ወደምድረ ፡ ዓለም) ፡
በተመለሱም ፡ ኖሮ ፡ ከርሱ ፡
ወደ ፡ ተከለከሉት ፡ ነገር ፡ በተመ
ለሱ ፡ ነበር ፤ እነሱም ፡ በእርግጥ ፡
ውሸታሞች ፡ ናቸው ።
29 እርሷም ፡ (ሕይወት) ፡ የቅርቢቱ ፡
ሕይወታችን ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይ
ደለችም ፡ እኛም ፡ ተቀስቃሾች ፡
አይደለንም ፡ አሉ ።
30 በጌታቸውም ፡ ላይ ፡ (ለምርመራ)፡
በተቆሙ ፡ ጊዜ ፡ ብታይ ፡ ኖሮ ፡
(አስደንጋጭን ፡ ነገር ፡ ባየህ ፡
ነበር) ። ይህ ፡ እውነት ፡ አይደለ
ምን ? ይላቸዋል ፤ በጌታችን ፡ ይኹ
ንብን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ይላሉ ።
ትክዱት ፡ በነበራችሁት ፡ ምክን
ያት ፡ ቅጣቱን ፡ ቅመሱ ፡ ይላቸ
ዋል ።
31 እነዚያ ፡ በአላህ ፡ መገናኘት ፡ ያስ
ተባበሉ ፡ በእርግጥ ፡ ከሰሩ ፤ ሰዓ
ቲቱም ፡ በድንገት ፡ በመጣች
ቸው ፡ ጊዜ ፡ እነሱ ፡ ኃጢአቶቻቸ
ውን ፡ በጀርባዎቻቸው ፡ ላይ ፡
የሚሸከሙ ፡ ሲኾኑ ፡ በርሷ ፡
(በምድረ ፡ ዓለም) ፡ ባጓደልነው ፡



ነገር ፡ ላይ ፡ ዋ ፡ ቁጪታችን ፡
ይላሉ ፤ ንቁ ፡ የሚሸከሙት ፡
ነገር ፡ ከፋ ።
32 የቅርቢቱም ፡ ሕይወት ፡ ጨዋ
ታና ፡ ላግጣ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደ
ለችም ፤ የመጨረሻይቱም ፡ አገር፡
(ገነት) ፡ ለነዚያ ፡ ለሚጠነቀቁት ፡
በጣም ፡ በላጭ ፡ ናት ፤ አታው
ቁምን ?
33 እነሆ ፡ ያ ፡ የሚሉህ ፡ ነገር ፡ እንደ
ሚያሳዝንህ ፡ በእርግጥ ፡ እናው
ቃለን ፤ እነርሱም ፡ (በልቦቻቸው)
አያስተባብሉህም ፡ ግን ፡ በዳዮቹ ፡
በአላህ ፡ አንቀጾች ፡ ይክዳሉ ።
34 ከበፊትህም ፡ መልክተኞች ፡ በእ
ርግጥ ፡ ተስተባበሉ ፤ በተስተባበ
ሉበትም ፡ ነገርና ፡ በተሰቃዩት ፡
ላይ ፡ እርዳታችን ፡ እስከመጣላ
ቸው ፡ ድረስ ፡ ታገሡ ፤ የአላህ
ንም ፡ ንግግሮች ፡ ለዋጭ ፡ የለም ፤
ከመልክተኞቹም ፡ ወሬ ፡ (የምትረ
ጋጋበት) ፡ በእርግጥ ፡ መጣልህ ።
35 (ኢስላምን)፡ መተዋቸውም ፡
ባንተ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ቢኾንብህ ፡
በምድር ፡ ውስጥ ፡ ቀዳዳን ፡
ወይም ፡ በሰማይ ፡ ውስጥ ፡ መሰ
ላልን ፡ ልትፈልግና ፡ በተአምር ፡
ልትመጣቸው ፡ ብትችል ፡ (አድ
ርግ) ፤ አላህም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡
በቅኑ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በሰበሰባ
ቸው ፡ ነበር ፤ ከተሳሳቱትም ፡ ሰ
ዎች ፡ በፍጹም ፡ አትኹን ።
36 ጥሪህን ፡ የሚቀበሉት ፡ እነዚያ ፡
የሚሰሙት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፤ ሙታ
ንንም ፡ አላህ ፡ ይቀሰቅሳቸዋል ፤
ከዚያም ፡ ወደርሱ ፡ ብቻ ፡ ይመለ
ሳሉ ።
37 ከጌታውም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡
ተአምር ፡ አልተወረደም ፡ አሉ ፤
አላህ ፡ ተአምርን ፡ በማውረድ ፡
ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ፡ በላቸው ፤ ግን ፡
አብዛኞቻቸው ፡ አያውቁም ።
38 ከተንቀሳቃሽም ፡ በምድር ፡ (የሚ
ኼድ) ፤ በሁለት ፡ ክንፎቹ ፡ የሚ
በርም ፡ በራሪ ፡ መሰሎቻችሁ ፡
ሕዝቦች ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደ
ሉም ፤ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ምን
ንም ፡ ነገር ፡ አልተውንም ፡ ከዚ
ያም ፡ ወደ ፡ ጌታቸው ፡ ይሰበሰ
ባሉ ።
39 እነዚያም ፡ በአንቀጾቻችን ፡ ያስ
ዋሹ ፡ ደንቆሮች ፡ ድዳዎችም ፡
በጨለማዎች ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡
ናቸው ፤ አላህ ፡ ማጥመሙን ፡ የሚ
ሻውን ፡ ሰው ፡ ያጠመዋል ፡ መም
ራቱን ፡ የሚሻውንም ፡ ሰው ፡ በቀ
ጥተኛ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ያደርገ
ዋል ።
40 የአላህ ፡ ቅጣት ፡ ቢመጣባችሁ ፡
ወይም ፡ ሰዓቲቱ ፡ (ትንሣኤ) ፡ ብ
ትመጣባችሁ ፡ ከአላህ ፡ ሌላን ፡
ትጠራላችሁን ? እውነተኞች ፡
እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ ንገሩኝ ፡ በላ
ቸው ።
41 አይደለም ፡ እርሱን ፡ ብቻ ፡ ትጠ
ራላችሁ ፤ ቢሻም ፡ ወደርሱ ፡ የም
ትጠሩበትን ፡ ነገር ፡ ያስወግዳል ፤
የምታጋሩትንም ፡ ነገር ፡ ትተዋ
ላችሁ ፡ (በላቸው) ።
42 ከበፊትህም ፡ ወደ ፡ ነበሩት ፡ ሕዝ
ቦች ፡ (መልክተኞችን) ፡ በእር
ግጥ ፡ ላክን ፤ እንዲዋደቁም ፡ በድ
ህነትና ፡ በበሽታ ፡ ያዝናቸው ።
43 ታዲያ ፡ ቅጣታችን ፡ በመጣባ
ቸው ፡ ጊዜ ፡ አይዋደቁም ፡ ኖሯ
ልን ? ግን ፡ ልቦቻቸው ፡ ደረቁ ፤
ይሠሩት ፡ የነበሩትንም ፡ ነገር ፡
ሰይጣን ፡ ለነሱ ፡ አሳመረላቸው ።

44 በርሱም ፡ ይገሠጹበት ፡ የነበረ
ውን ፡ ነገር ፡ በተው ፡ ጊዜ ፡ በነሱ ፡
ላይ ፡ የነገርን ፡ ሁሉ ፡ ደጃፎች ፡
ከፈትን ፤ (አስመቸናቸው) ፡ በተ
ሰጡትም ፡ ነገር ፡ በተደሰቱ ፡
ጊዜ ፡ በድንገት ፡ ያዝናቸው ፡
ወዲያውኑም ፡ እነርሱ ፡ ተስፋ ፡
ቆራጮች ፡ ኾኑ ።
45 የነዚያም ፡ የበደሉት ፡ ሕዝቦች ፡
መጨረሻ ፡ ተቆረጠ ፤ ምስጋናም ፡
ለዓለማት ፡ ጌታ ፡ ለአላህ ፡ ይገ
ባው ።
46 ፡—ንገሩኝ ፡ አላህ ፡ መስሚያች
ሁንና ፡ ማያዎቻችሁን ፡ ቢወስድ ፡
በልቦቻችሁም ፡ ላይ ፡ ቢያትም ፡
ከአላህ ፡ ሌላ ፡ እርሱን ፡ የሚያመ
ጣላችሁ ፡ አምላክ ፡ ማነው ?
በላቸው ፤ አንቀጾችን ፡ እንዴት ፡
እንደምናብራራ ፡ ከዚያም ፡ እነሱ ፡
እንዴት ፡ እንደሚመለሱ ፡ ተመ
ልከት ።
47 ፡—ንገሩኝ ፡ የአላህ ፡ ቅጣት ፡ በድ
ንገት ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ ቢመጣ
ባችሁ ፡ አመጠኞች ፡ ሕዝቦች ፡
እንጅ ፡ ሌላ ፡ ይጥጠፋልን ? በላ
ቸው ፡
48 መልክተኞችንም ፡ አብሳሪና ፡
አስፈራሪ ፡ አድርገን ፡ እንጅ ፡
አንልክም ፤ ያመኑና ፡ በጎን ፡
የሠሩ ፡ ሰዎችም ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡
ፍርሃት ፡ የለባቸውም ፤ እነሱም ፡
አያዝኑም ።
49 እነዚያም ፡ ባንቀጾቻችን ፡ ያስ
ዋሹ ፡ ያምጡ ፡ በነበሩት ፡ ምክ
ንያት ፡ ቅጣቱ ፡ ያገኛቸዋል ።
50 ፡—ለናንተ ፡ የአላህ ፡ ግምጃ ፡
ቤቶች ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ ናቸው ፡ አል
ልም ፡ ሩቅንም ፡ አላውቅም ፤
ለናንተም ፡ እኔ ፡ መልአክ ፡ ነኝ ፡
አልልም ፤ ወደኔ ፡ የሚወርድል
ኝን ፡ እንጅ ፡ ሌላን ፡ አልከተልም ፡
በላቸው ፤ ዕውርና ፡ የሚያይ ፡ ይተ
ካከላሉን ? አታስተነትኑምን ?
በላቸው ።
51 እነዚያንም ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ ረዳ
ትና ፡ አማላጅ ፡ የሌላቸው ፡
ሲኾኑ ፡ ወደ ፡ ጌታቸው ፡ መሰብ
ሰብን ፡ የሚፈሩትን ፡ ይጠነቀቁ ፡
ዘንድ ፡ በርሱ ፡ (በቁርአን) ፡ አስ
ፈራራ ።
52 እነዚያንም ፡ ጌታቸውን ፡ ፊቱን ፡
(ውዴታውን) ፡ የሚሹ ፡ ኾነው ፡
በጧትና ፡ በማታ ፡ የሚጠሩትን ፡
አታባር ፤ ታበራቸውና ፡ ከበደለ
ኞችም ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ እነሱን ፡
መቆጣጠር ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ም
ንም ፡ የለብህም ፤ አንተንም ፡ መ
ቆጣጠር ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡
የለባቸውም ።
53 እንደዚሁም ፡ ከመካከላችን ፡
አላህ ፡ የለገሰላቸው ፡ እነዚህ ፡
ናቸውን ? ይሉ ፡ ዘንድ ፡ ከፊላቸ
ውን ፡ በከፊሉ ፡ ሞከርን ፤ አላህ ፡
አመስጋኞቹን ፡ ዐዋቂ ፡ አይደ
ለምን ?
54 እነዚያም ፡ በተአምራታችን ፡ የሚ
ያምኑት ፡ በመጡህ ፡ ጊዜ ፡ ሰላም ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ ይኹን ፤ ጌታችሁ ፡
በነፍሱ ፡ ላይ ፡ እዝነትን ፡ ጻፈ ፤
እነሆ ፡ ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ በስሕ
ተት ፡ ክፉን ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡
ሰው ፡ ከዚያም ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡
የተጸጸተና ፡ ሥራውን ፡ ያሳመረ ፡
እርሱ ፡ (አላህ) ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡
ነው ፡ በላቸው ።
55 እንደዚሁም ፡ (እውነቱ ፡ እንዲገ
ለጽና) ፡ የወንጀለኞችም ፡ መን
ገድ ፡ ትብራራ ፡ ዘንድ ፡ አንቀ
ጾችን ፡ እንገልጻለን ።



56 እኔ ፡ እነዚያን ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡
የምትጠሩዋቸውን ፡ ከመገዛት ፡
ተከልክያለሁ ፡ በላቸው ። ዝንባሌ
ያችሁን ፡ አልከተልም ፤ ያን ፡
ጊዜ ፡ በእርግጥ ፡ ተሳሳትኩ ፤
እኔም ፡ ከተመሪዎቹ ፡ አይደለ
ሁም ፡ በላቸው ።
57 እኔ ፡ ከጌታዬ ፡ በኾነች ፡ ግልጽ ፡
ማስረጃ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፤ በርሱም ፡
አስተባበላችሁ ፤ በርሱ ፡ የምትቻ
ኮሉበት ፡ ቅጣት ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡
አይደለም ፤ ፍርዱ ፡ ለአላህ ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ እውነትን ፡ ይፈርዳል ፤
እርሱም ፡ ከፈራጆች ፡ ሁሉ ፡
በላጭ ፡ ነው ፡ በላቸው ።
58 በርሱ ፡ የምትቻኮሉበት ፡ ቅጣት ፡
እኔ ፡ ዘንድ ፡ በኾነ ፡ ኖሮ ፡ በኔና ፡
በናንተ ፡ መካከል ፡ ነገሩ ፡ (ቅጣ
ታችሁ) ፡ በተፈጸመ ፡ ነበር ፤ አላ
ህም ፡ በደለኞችን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፡
በላቸው ።
59 የሩቅ ፡ ነገርም ፡ መክፈቻዎች ፡
እርሱ ፡ ዘንድ ፡ ናቸው ፤ ከርሱ ፡
በቀር ፡ ማንም ፡ አያውቃቸውም ፤
በየብስና ፡ በባሕር ፡ ያለውንም ፡
ሁሉ ፡ ያውቃል ፤ ከቅጠልም ፡
አንዲትም ፡ አትረግፍም ፡ የሚያ
ውቃት ፡ ቢኾን ፡ እንጅ ፤ ከቅንጣ
ትም ፡ በመሬት ፡ ጨለማዎች ፡
ውስጥ ፡ የለም ፡ ከእርጥብም ፡
ከደረቅም ፡ አንድም ፡ የለም ፡
ግልጽ ፡ በኾነው ፡ መጽሐፍ ፡
ውስጥ ፡ (የተመዘገበ) ፡ ቢኾን ፡
እንጅ ።
60 እርሱም ፡ ያ ፡ በሌሊት ፡ የሚያስ
ተኛችሁ ፡ በቀንም ፡ የሠራችሁ
ትን ፡ ሁሉ ፡ የሚያውቅ ፡ ከዚ
ያም ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ይፈ
ጸም ፡ ዘንድ ፡ በርሱ ፡ (በቀን) ፡
ውስጥ ፡ የሚቀሰቅሳችሁ ፡ ነው ፤
ከዚያም ፡ መመለሻችሁ ፡ ወደ ፡
እርሱ ፡ ነው ፤ ከዚያም ፡ ትሠሩት ፡
የነበራችሁትን ፡ ሁሉ ፡ ይነግራ
ችኋል ።
61 እርሱም ፡ ከባሮቹ ፡ በላይ ፡ሲኾን ፡
ሁሉን ፡ አሸናፊ ፡ ነው ፤ በናን
ተም ፡ ላይ ፡ ጠባቂዎችን ፡ (መላ
እክት) ፡ ይልካል ፤ አንዳችሁንም ፡
ሞት ፡ በመጣበት ፡ ጊዜ ፡ (የሞት) ፡
መልክተኞቻችን ፡ እነርሱ ፡ (ትእ
ዛዛትን) ፡ የማያጓድሉ ፡ ሲኾኑ ፡
ይገድሉታል ።
62 ከዚያም ፡ እውነተኛ ፡ ወደ ፡ ኾነው ፡
ጌታቸው ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ይመለ
ሳሉ ፤ ንቁ ፡ ፍርዱ ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡
ነው ፤ እርሱም ፡ ከተቆጣጣሪዎች ፡
ሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ፈጣን ፡ ነው ።
63 ከየብስና ፡ ከባሕር ፡ ጨለማዎች ፡
(1) በግልጽና ፡ በምስጢር ፡ የም
ትጠሩት ፡ ስትኾኑ ፡ ከነዚህ ፡ (2)
ቢያድነን ፡ በእርግጥ ፡ ከአመስጋ
ኞች ፡ እንኾናለን ፡ (ስትሉ) ፡ የሚ
ያድናችሁ ፡ ማነው ? በላቸው ።
64 አላህ ፡ ከሷና ፡ ከጭንቅም ፡ ሁሉ ፡
ያድናችኋል ፤ ከዚያም ፡ እናንተ ፡
ታጋራላችሁ ፡ በላቸው ።
65 እርሱ ፡ (አላህ) ፡ ከበላያችሁ ፡
ወይም ፡ ከእግሮቻችሁ ፡ በታች ፡
ቅጣትን ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ሊልክ ፡
ወይም ፡ የተለያዩ ፡ ሕዝቦች ፡
ስትኾኑ ፡ ሊያደባልቃችሁና ፡ ከፊ
ላችሁን ፡ የከፊሉን ፡ ጭካኔ ፡ ሊያ
ቀምስ ፡ ቻይ ፡ ነው ፡ በላቸው ።
ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ አንቀጾችን ፡ እን

1 መከራዎች ።
2 ጨለማዎች ።

ዴት ፡ እንደምናብራራ ፡ ተመ
ልከት ።
66 በርሱም ፡ (በቁርአን) ፡ እርሱ ፡
እውነት ፡ ሲኾን ፡ ሕዝቦችህ ፡
አስተባበሉ ። በላቸው ፡— በና
ንተ ፡ ላይ ፡ ጠባቂ ፡ አይደለሁም ።
67 ለትንቢት ፡ ሁሉ ፡ (የሚደርስ
በት) ፡ መርጊያ ፡ አለው ፣ ወደፊ
ትም ፡ ታውቁታላችሁ ።
68 እነዚያንም ፡ በአንቀጾቻችን ፡ የሚ
ገቡትን ፡ ባየህ ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡
ሌላ ፡ በኾነ ፡ ወሬ ፡ እስከሚገቡ ፡
ድረስ ፡ ተዋቸው ፣ ሰይጣንም ፡
(መከልከልህን) ፡ ቢያስረሳህ ፡
ከትዝታ ፡ በኋላ ፡ ከበደለኞች ፡
ሕዝቦች ፡ ጋር ፡ አትቀመጥ ።
69 በነዚያም ፡ በሚጠነቀቁት ፡ ላይ ፡
ከሒሳባቸው ፡ (1) ምንም ፡ የለባ
ቸውም ፣ ግን ፡ ይጠነቀቁ ፡ ዘንድ ፡
መገሠጥ ፡ (አለባቸው) ።
70 እነዚያንም ፡ ሃይማኖታቸውን ፡
ጨዋታና ፡ ላግጣ፡ አድርገው ፡
የያዙትን ፡ ቅርቢቱም ፡ ሕይወት ፡
ያታለለቻቸውን ፡ ተዋቸው ፣ በር
ሱም ፡ (በቁርአን) ፡ ነፍስ ፡ በሠራ
ችው ፡ ሥራ ፡ እንዳትጠፋ ፡ አስታ
ውስ ፣ ለርሷ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ረዳ
ትና ፡ አማላጅ ፡ የላትም ፣ በመበ
ዢያም ፡ ሁሉ ፡ ብትበዥ ፡ ከርሷ ፡
አይወሰድም ፣ እነዚህ ፡ እነዚያ ፡
በሠሩት ፡ ሥራ ፡ የተጠፉት ፡ ና
ቸው ፣ ለነሱ ፡ ይከዱ ፡ በነበሩት ፡ ም
ክንያት ፡ ከፈላ ፡ ውሃ ፡ መጠጥና ፡
አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ።
71 ፡—ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የማይጠቅመ
ንን፡ እና፡ የማይጐዳንን፡ እንግገዛ
ለን ? አላህም ፡ ከመራን ፡ ጊዜ ፡
በኋላ ፡ የኋሊት ፡ እንመለሳለን ?
እንደዚያ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የዋ
ለለ ፡ ሲኾን ፡ ሰይጣናት ፡ እንዳሳ
ሳቱት ፡ ለርሱ ፡ ወደኛ ፡ ና ፡ እያሉ፡
ወደ ፡ ቅን ፡ መንገድ ፡ የሚጠሩ ፡
ወዳጆች ፡ እንዳሉት ፡ (እንደማይ
ከተላቸውም) ፡ ሰው ፡ እንኾና
ለን ? በላቸው ፣ የአላህ ፡ መንገድ ፡
እርሱ ፡ ቀጥተኛው ፡ መንገድ ፡
ነው ፣ ለዓለማት ፡ ጌታ ፡ ልንገ
ዛም ፡ ታዘዝን ፡ በላቸው ።
72 ሶላትንም ፡ በደንቡ ፡ ስገዱ ፡ ፍሩ
ትም ፣ (በማለት ፡ ታዘዝን) ፡ እር
ሱም ፡ ያ ፡ ወደርሱ ፡ ብቻ ፡ የም
ትሰበሰቡበት፡ ነው።
73 እርሱም ፡ ያ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድ
ርን ፡ በእውነት ፡ የፈጠረ ፡ ነው ፣
ኹን ፡ የሚልበትንና ፡ ወዲያውም፡
የሚኾንበትን ፡ ቀን ፡ (አስታ
ውስ) ፣ ቃሉ ፡ እውነት ፡ ነው ፣ በቀ
ንዱም ፡ በሚነፋ ፡ ቀን ፡ ንግሥ
ናው ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፣ ሩቁ
ንና ፡ ቅርቡን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፣ እር
ሱም ፡ ጥበበኛው ፡ ውስጠ ፡ ዐዋ
ቂው ፡ ነው ።
74 ኢብራሂምም ፡ ለአባቱ ፡ (1)
ለአዘር ፡ ጣዖታትን ፡ አማልክት ፡
አድርገህ ፡ ትይዛለህን ? እኔ ፣ አን
ተንም ፡ ሕዝቦችህንም ፡ በግልጽ ፡
መሳሳት ፡ ውስጥ ፡ ኾናችሁ ፡ አያ
ችኋለሁ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ)
75 እንደዚሁም ፡ ኢብራሂምን ፡ (እን
ዲያውቅና) ፡ ከአረጋጋጮቹም ፡
ይኾን ፡ ዘንድ ፡ የሰማያትንና ፡
የምድርን ፡ መለኮት ፡ (2) እሳ
የነው ።

1 ከላጋጮቹ ፡ ኀጢአት ።

1 የግል ፡ ስሙ ፡ ታሪህ ፡ ለኾነው ።
2 ግዛት ፡ ሥልጣን ።



76 ሌሊቱም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ባጨ
ለመ ፡ ጊዜ ፡ ኮከብን ፡ አየ ፣ ይህ ፡
ጌታዬ ፡ ነው ፡ አለ ፣ በጠለቀም ፡
ጊዜ ፡—ጠላቂዎችን ፡ አልወድም፡
አለ ።
77 ጨረቃንም ፡ ወጪ ፡ ኾኖ ፡ ባየ ፡
ጊዜ ፡—ይህ ፡ ጌታዬ ፡ ነው ፡ አለ ፣
በገባም ፡ ጊዜ ፡— ጌታዬ ፡ (ቅኑን ፡
መንገድ) ፡ ባይመራኝ ፡ በእርግጥ ፡
ከተሳሳቱት ፡ ሕዝቦች ፡ እኾና
ለሁ ፡ አለ ።
78 ፀሐይንም ፡ ጮራዋን ፡ ዘርግታ ፡
ባየ ፡ ጊዜ ፡— ይህ ፡ ጌታዬ ፡ ነው ፣
ይህ ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ነው ፡
አለ ፣ በገባችም ፡ ጊዜ ፡— ወገ
ኖቼ ፡ ሆይ ! እኔ ፡ ከምታጋሩት ፡
ሁሉ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ አለ ።
79 እኔ ፡ ለዚያ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድ
ርን ፡ ለፈጠረው ፡ (አምላክ) ፡
ቀጥተኛ ፡ ስኾን ፡ ፊቴን ፡ አዞርኩ ፣
እኔም ፡ ከአጋሪዎቹ ፡ አይደለሁም፡
(አለ) ።
80 ወገኖቹም ፡ ተከራከሩት ፣ በአ
ላህ ፡ (አንድነት) ፡ በእርግጥ ፡ የመ
ራኝ ፡ ሲኾን ፡ ትከራከሩኛላች
ሁን ? በርሱም ፡ የምታጋሩትን ፡
ነገር ፡ አልፈራም ፣ ግን ፡ ጌታዬ ፡
ነገርን ፡ ቢሻ ፡ (ያገኘኛል) ፣ ጌታ
ዬም ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ዕውቀቱ ፡
ሰፋ ፣ አትገነዘቡምን ? አላቸው ።
81 በናንተ ፡ ላይ ፡ በርሱ ፡ ማስረጃን ፡
ያላወረደበትን ፡ እናንተ ፡ ማጋራ
ታችሁን ፡ የማትፈሩ ፡ ስትኾኑ ፡
የምታጋሩትን ፡ (ጣዖታት) ፡ እን
ዴት ፡ እፈራለሁ ! የምታውቁም ፡
ብትኾኑ ፡ ከሁለቱ ፡ ክፍሎች ፡ (1)
በጸጥታ ፡ ይበልጥ ፡ ተገቢው ፡
ማንኛው ፡ ነው ? (አለ) ።
82 እነዚያ ፡ ያመኑና ፡ እምነታቸ
ውን ፡ በበደል ፡ ያልቀላቀሉ ፡
እነዚያ ፡ ለነርሱ ፡ ጸጥታ ፡ አላ
ቸው ፣ እነሱም ፡ የተመሩ ፡ ናቸው ፣
83 ይኽችም ፡ (1) ማስረጃችን ፡ ናት ፣
ለኢብራሂም ፡ በሕዝቦቹ ፡ ላይ ፡
(አስረጅ ፡ እንድትኾን) ፡ ሰጠ
ናት ፣ የምንሻውን ፡ ሰው ፡ በደረ
ጃዎች ፡ ከፍ ፡ እናደርጋለን ፣
ጌታህ ፡ ጥበበኛ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።
84 ለርሱም ፡ ኢስሐቅን ፡ (የልጅ ፡
ልጁን) ፡ የዕቁብንም ፡ ሰጠነው ፣
ሁሉንም ፡ መራን ፣ ኑሕንም ፡
በፊት ፡ መራን ፣ ከዘሮቹም ፡ ዳው
ድን ፡ ሱለይማንንም ፡ አዮብንም ፡
ዩሱፍንም ፡ ሙሳንም ፡ ሃሩንንም ፡
(መራን) ፡ እንደዚሁም ፡ በጎ ፡
ሠሪዎችን ፡ እንመነዳለን ።
85 ዘከሪያንም ፡ የሕያንም ፡ ዒሳንም ፡
ኢልያስንም ፡ (መራን) ፣ ሁሉም ፡
ከመልካሞቹ ፡ ናቸው ።
86 ኢስማዒልንም ፡ አልየስዕንም ፡
ዩኑስንም ፡ ሉጥንም ፡ (መራን) ፣
ሁሉንም ፡ በዓለማት ፡ ላይ ፡ አበ
ለጥናቸውም ።
87 ከአባቶቻቸውም ፡ ከዘሮቻቸውም፡
ከወንድሞቻቸውም ፡ (መራን) ፣
መረጥናቸውም ፣ ወደ ፡ ቀጥታ
ውም ፡ መንገድ ፡ መራናቸው ።
88 ይህ ፡ (2) የአላህ ፡ መምሪያ ፡
ነው ። በርሱ ፡ ከባሮቹ ፡ የሚሻ
ውን ፡ ሰው ፡ ይመራል ፣ ባጋሩም ፡
ኖሮ ፡ ይሠሩት ፡ የነበሩት ፡ ከነሱ ፡
በታበሰ ፡ ነበር ።

1 በአንድ ፡ አምላክ ፡ ከሚያምኑና ፡ ከሚያ
ጋሩ ።

1 የኮከብ ፡ የጨረቃና ፡ የፀሐይ ፡ መግባት ።
2 በአንድ ፡ አምላክ ፡ የማመን ፡ ሕግ ።

89 እነዚህ ፡ እነዚያ ፡ መጻሕፍትንና ፡
ጥበብን ፡ ነቢይነትንም ፡ የሰጠ
ናቸው ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ (የመካ ፡
ከሓዲዎች) ፡ በርሷ ፡ ቢክዱም ፡
በርሷ ፡ የማይክዱን ፡ ሕዝቦች ፡
ለርሷ ፡ በእርግጥ ፡ አዘጋጅተናል ።
90 እነዚህ ፡ (ነቢያት) ፡ እነዚያ ፡
አላህ ፡ የመራቸው ፡ ናቸው ፤
በመንገዳቸውም ፡ ተከተል ፤ ፦
በርሱ ፡ (በቁርአን) ፡ ላይ ፡ ምንም ፡
ዋጋ ፡ አልጠይቃችሁም ፤ እርሱ ፡
ለዓለማት ፡ ግሣጼ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡
አይደለም ፡ በላቸው ።
91 አላህ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ምንም ፡
አላወረደም ፡ ባሉም ፡ ጊዜ ፡ አላ
ህን ፡ ተገቢ ፡ ክብሩን ፡ አላከ
በሩትም ። (እንዲህ) ፡ በላቸው ፦
ያንን ፡ ብርሃንና ፡ ለሰዎች ፡ መሪ ፡
ኾኖ ፡ ሙሳ ፡ ያመጣውን ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ክፍልፍሎች ፡ የምታደር
ጉት ፡ ስትኾኑ ፡ ማን ፡ አወረደው ?
(የወደዳችኋትን) ፡ ትገልጿታላች
ሁ ፡ ብዙውንም ፡ ትደብቃላችሁ ፤
እናንተም ፡ አባቶቻችሁም ፡ ያላ
ወቃችሁትን ፡ ተስተማራችሁ ፤
92 አላህ ፡ (አወረደው) ፡ በላቸው ።
ከዚያም ፡ በውሽታቸው ፡ ውስጥ ፡
የሚጫወቱ ፡ ሲኾኑ ፡ ተዋቸው ።
ይህም ፡ ያወረድነው ፡ የኾነ ፡
ብሩክ ፡ ያንንም ፡ በፊቱ ፡ የነበረ
ውን ፡ (መጽሐፍ) ፡ አረጋጋጭ ፡
መጽሐፍ ፡ ነው ፤ የከተሞችን ፡
እናት፡ (መካን)፡ እና፡ በዙሪያዋ፡
ያሉትንም ፡ ሰዎች ፡ ልታስጠነቅ
ቅበት ፡ (አወረድነው) ፤ እነዚ
ያም ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ዓለም ፡
የሚያምኑት ፡ እነርሱ ፡ በሶላታ
ቸው ፡ ላይ ፡ የሚጠባበቁ ፡ ሲኾኑ ፡
በርሱ ፡ ያምናሉ ።
93 በአላህም ፡ ላይ ፡ እብለትን ፡ ከቀ
ጣጠፈ ፡ ወይም ፡ ወደርሱ ፡ ምን
ም ፡ ያልተወረደለት ፡ ሲኾን ፡
ወደኔ ፡ ተወረደልኝ ፡ ካለና ፦
አላህም ፡ ያወረደውን ፡ ብጤ ፡
በእርግጥ ፡ አወርዳለሁ ፡ ካለ ፡
ሰው ፡ ይበልጥ ፡ በዳይ ፡ ማን ፡
ነው ? በደለኞችንም ፡ በሞት ፡
መከራዎች ፡ ውስጥ ፡ በኾኑ ፡
ጊዜ ፡ መላእክት ፡ እጆቻቸውን ፡
ዘርጊዎች ፡ ኾነው ፡ (ለቅጥጥብ) ፡
ነፍሶቻችሁን ፡ አውጡ ፤ በአላህ ፡
ላይ ፡ እውነት ፡ ያልኾነን ፡ ነገር ፡
ትናገሩ ፡ በነበራችሁትና ፡ ከአን
ቀጾቹም ፡ ትኮሩ ፡ በነበራችሁት ፡
ምክንያት ፡ ዛሬ ፡ የውርደትን ፡
ቅጣት ፡ ትመነዳላችሁ ፡ (የሚሏ
ቸው ፡ ሲኾኑ) ፡ ብታይ ፡ ኖሮ ፡
(አስደናቂን ፡ ነገር ፡ ባየህ ፡ ነበር)።
94 መጀመሪያም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ፈጠ
ርናችሁ ፡ ኾናችሁ ፡ የሰጠናች
ሁን፡ ሁሉ፡ በጀርባዎቻችሁ፡ ኋላ፡
የተዋችሁ ፡ ስትኾኑ ፡ ለየብቻ
ችሁ ፡ ኾናችሁ ፡ በእርግጥ ፡ መጣ
ችሁን ፤ እነዚያንም ፡ እነሱ ፡ በና
ንተ ፡ ውስጥ ፡ (ለአላህ) ፡ ተጋሪ
ዎች ፡ ናቸው ፡ የምትሉዋቸውን ፡
አማላጆቻችሁን ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡
አናይም ፤ ግንኙነታችሁ ፡ በእር
ግጥ ፡ ተቋረጠ ፤ ከናንተም ፡ ያ ፡
(ያማልደናል) ፡ የምትሉት ፡ ጠፋ፡
(ይባላሉ) ።
95 አላህ ፡ ቅንጣትንና ፡ የፍሬን ፡ አጥ
ንት ፡ ፈልቃቂ ፡ ነው ፡ ሕያውን ፡
ከሙት ፡ ያወጣል ፤ ሙትንም ፡
ከሕያው ፡ አውጪ ፡ ነው ፤ ይኻ
ችሁ ፡ አላህ ፡ ነው ፤ ታዲያ ፡
(ከእምነት) ፡ እንዴት ፡ ትመለሳ
ላችሁ ?



96 እርሱም ፡ ጎህን ፡ (ከሌሊት ፡
ጨለማ) ፡ ፈልቃቂ ፡ ሌሊትንም ፡
ማረፊያ ፡ ፀሐይንና ፡ ጨረቃንም ፡
(ለጊዜ) ፡ መቍጠሪያ ፡ አድራጊ ፡
ነው ፤ ይህ ፡ የአሸናፊው ፡ የዐዋ
ቂው ፡ ድርጅት ፡ ነው ።
97 እርሱም ፡ ያ ፡ ከዋክብትን ፡ በየብ
ስና ፡ በባሕር ፡ ጨለማዎች ፡
ውስጥ ፡ በርሷ ፡ ትመሩ ፡ ዘንድ ፡
ለናንተ ፡ ያደረገ ፡ ነው ፤ ለሚያ
ውቁ ፡ ሕዝቦች ፡ አንቀጾችን ፡
በእርግጥ ፡ ዘረዘርን ።
98 እርሱም ፡ ያ ፡ ከአንዲት ፡ ነፍስ ፡
ያስገኛችሁ ፤ ነው ፤ (በማሕፀን) ፡
መርጊያና ፡ (በጀርባ) ፡ መቀመ
ጫም ፡ (አላችሁ) ፤ ለሚያውቁ ፡
ሕዝቦች ፡ አንቀጾችን ፡ በእርግጥ ፡
ዘረዘርን ።
99 እርሱም ፡ ያ ፡ ከሰማይ ፡ ውሃን ፡
ያወረደ ፡ ነው ፤ በርሱም ፡ የነገ
ሩን ፡ ሁሉ ፡ በቃይ ፡ አወጣን ፤
የተደራረበንም ፡ ቅንጣት ፡ ከርሱ፡
የምናወጣ ፡ የኾነን ፡ ለምለም ፡
(አዝመራ) ፡ ከርሱ ፡ አወጣን ፤
ከዘንባባም ፡ ከእንቡጧ ፡ የተቀራ
ረቡ ፡ የኾኑ ፡ ዘለላዎች ፡ አሉ ፤
ከወይኖችም ፡ ከወይራም ፡ ከሩ
ማንም ፡ (ቅጠላቸው) ፡ ተመሳሳ
ይና ፡ (ፍሬያቸው) ፡ የማይመሳ
ሰል ፡ ሲኾኑ ፡ አትክልቶችን ፡
(አወጣን) ፤ ባፈራ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡
ፍሬውና ፡ ወደ ፡ መብሰሉ ፡ ተመ
ልከቱ ፤ በይሃችሁ ፡ ለሚያምኑ ፡
ሕዝቦች ፡ ምልክቶች ፡ አሉ ።
100 ለአላህም ፡ አጋንንትን ፡ የፈጠራ
ቸው ፡ ሲኾን ፡ (በመታዘዝ) ፡ ተጋ
ሪዎች ፡ አደረጉ ፤ ወንዶች ፡ ልጆ
ችንና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችንም ፡ ያለ ፡
ዕውቀት ፡ ለርሱ ፡ቀጠፉ ፤ (አላህ)
ጥራት ፡ የተገባው ፡ ከሚሉት ፡
ነገር ፡ የላቀ ፡ ነው ።
101 (እርሱ) ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡
ያለ ፡ ብጤ ፡ ፈጣሪ ፡ ነው ፤ ለርሱ ፡
ሚስት ፡ የሌለችው ፡ ሲኾን ፡ እን
ዴት ፡ ለርሱ ፡ ልጅ ፡ ይኖረዋል ?
ነገርንም ፡ ሁሉ ፡ ፈጠረ ፤ እር
ሱም ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።
102 ይኻችሁ ፡ ጌታችሁ ፡ አላህ ፡ ነው፤
ከርሱ ፡ በቀር ፡ አምላክ ፡ የለም ፤
ነገርን ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡ ነው ፤
ስለዚህ ፡ ተገዙት ፤ እርሱም ፡
በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ተጠባባቂ ፡
ነው ።
103 ዓይኖች ፡ አያገኙትም ፤ (አያዩ
ትም) ፤ እርሱም ፡ ዓይኖችን ፡
ያያል ፤ እርሱም ፡ ርኅራኄው ፡
ረቂቁ ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂው ፡ ነው ።
104 ፦ከጌታችሁ ፡ ዘንድ ፡ ብርሃኖች፡
በእርግጥ ፡ መጡላችሁ ፤ የተመለ
ከተም ፡ ሰው ፡ (ጥቅሙ) ፡ ለነ
ፍሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ የታወረም ፡
ሰው ፡ (ጉዳቱ) ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ እኔም ፡ በናንተ ፡ ላይ፡
ጠባቂ ፡ አይደለሁም ፡ (በላቸው) ።
105 እንደዚሁም ፡ (እንዲገመግሙና ፡
ያለፉትን ፡ መጻሕፍት) ፡ አጥንተ
ሃልም ፡ እንዲሉ ፡ ለሚያውቁ ፡
ሕዝቦችም ፡ (ቁርአንን) ፡ እንድና
ብራራው ፡ አንቀጾችን ፡ እንገል
ጻለን ።
106 ከጌታህ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ የተወረደ
ውን ፡ ተከተል ፤ ከርሱ ፡ በቀር ፡
አምላክ ፡ የለም ፤ አጋሪዎችንም ፡
ተዋቸው ።
107 አላህም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ ባላጋሩ ፡
ነበር ፤ በነሱም ፡ ላይ ፡ ጠባቂ ፡

አላደረግንህም ፤ አንተም ፡ በነሱ ፡
ላይ ፡ ኀላፊ ፡ አይደለህም ።
108 እነዚያንም ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የሚ
ግገዙዋቸውን ፡ (ጣዖታትን) ፡ አት
ስደቡ ፡ ድንበርን ፡ በማለፍ ፡ ያለ ፡
ዕውቀት ፡ አላህን ፡ ይሰድቡሉና ፤
እንደዚሁ ፡ ለሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡
ሥራቸውን ፡ ደግ ፡ አስመሰልንላ
ቸው ፤ ከዚያም ፡ መመለሻቸው ፡
ወደ ፡ ጌታቸው ፡ ነው ፤ ይሠሩት ፡
የነበሩትንም ፡ ሁሉ ፡ ይነግራቸ
ዋል ።
109 ታምርም ፡ ብትመጣላቸው ፡ በ
ርሷ ፡ በቁርጥ ፡ ሊያምኑ ፡ ጥብቅ ፡
መሐሎቻቸውን ፡ በአላህ ፡ ማሉ ፤
ታምራት ፡ ሁሉ ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡
ናት ፡ በላቸው ፤ እርሷ ፡ በመጣች ፡
ጊዜም ፡ አለማመናቸውን ፡ (ወ
ይም ፡ ማመናቸውን) ፡ ምን ፡ አሳ
ወቃችሁ ?
110 በመጀመሪያም ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡
እንዳላመኑ ፡ ሁሉ ፡ ልቦቻቸው
ንና ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ እናገላብጣ
ለን ። (1) በጥመታቸውም ፡
ውስጥ ፡ የሚዋልሉ ፡ ሲኾኑ ፡
እንተዋቸዋለን ።

* * *

111 እኛም ፡ ወደነርሱ ፡ መላእክትን ፡
ባወረድን ፡ ሙታንም ፡ ባነጋገሩ
ዋቸው ፡ ነገሩንም ፡ ሁሉ ፡ ጭፍራ ፡
ጭፍራ ፡ አድርገን ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
በሰበሰብን ፡ ኖሮ ፡ አላህ ፡ ካልሻ ፡
በስተቀር ፡ የሚያምኑ ፡ ባልኾኑ ፡
ነበር ። ግን ፡ አብዛኞቻቸው ፡
(ይህንን) ፡ ይስታሉ ።
112 እንደዚሁም ፡ ለነቢዩ ፡ ሁሉ ፡ ከሰ
ውና ፡ ከጋኔን ፡ የኾኑን ፡ ሰይጣ
ናት ፡ ጠላት ፡ አደረግን ፤ ከፊላ
ቸው ፡ ወደ ፡ ከፊሉ ፡ ለማታለል ፡
ልብስብስን ፡ ቃል ፡ ይጥላሉ ፤
ጌታህም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ ባልሠሩት ፡
ነበር ። ከቅጥፈታቸውም ፡ ጋር ፡
ተዋቸው ።
113 (የሚጥሉትም ፡ ሊያታልሉና) ፡
የነዚያም ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ሕይ
ወት ፡ የማያምኑት ፡ ሰዎች ፡
ልቦች ፡ ወደርሱ ፡ እንዲያዘነብሉ ፡
እንዲወዱትም ፡ እነርሱ ፡ ይቀ
ጥፉ ፡ የነበሩትንም ፡ እንዲቀጣ
ጥፉ ፡ ነው ።
114 እርሱ ፡ ያ ፡ መጽሐፉን ፡ የተብ
ራራ ፡ ኾኖ ፡ ወደናንተ ፡ ያወረደ ፡
ሲኾን ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ዳኛን ፡ እፈ
ልጋለሁን ? (በላቸው) ፤ እነዚያም ፡
መጽሐፍን ፡ የሰጠናቸው ፡ እርሱ ፡
ከጌታህ ፡ ዘንድ ፡ በእውነት ፡ የተ
ወረደ ፡ መኾኑን ፡ ያውቃሉ ፡
ከተጠራጣሪዎቹም ፡ አትኹን ።
115 የጌታህም ፡ ቃላት ፡ እውነተኛና ፡
ትክክለኛ ፡ ስትኾን ፡ ተፈጸመች ፤
ለቃላቱ ፡ ለዋጭ ፡ የለም ፤ እር
ሱም ፡ ሰሚው ፡ ዐዋቂው ፡ ነው ።
116 በምድርም ፡ ካሉት ፡ ሰዎች ፡
አብዛኞቹን ፡ ብትከተል ፡ ከአ
ላህ ፡ መንገድ ፡ ያሳስቱሃል ።
ጥርጣሬን ፡ እንጅ ፡ ሌላን ፡ አይ
ከተሉም ። እነርሱም ፡ የሚዋሹ ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደሉም ።
117 ጌታህ ፡ እርሱ ፡ ከመንገዱ ፡ የሚሳ
ሳቱትን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ። እርሱም ፡
ተመሪዎቹን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
118 በአንቀጾቹም ፡ አማኞች ፡ እንደ
ኾናችሁ ፡ (ሲታረድ) ፡ የአላህ ፡
ስም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ከተወሳበት ፡
እንስሳ ፡ ብሉ ።

1 እውነትን ፡ አያውቁም ፡ አያዩምም ።



119 ወደርሱም ፡ (መብላት) ፡ ከተገደ
ዳችሁበት ፡ በስተቀር ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ እርም ፡ የተደረገውን ፡ ለና
ንተ ፡ (አላህ) ፡ በእርግጥ ፡ የዘረ
ዘረ ፡ ሲኾን ፡ ከዚያ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
የአላህ ፡ ስም ፡ ከተጠራበት ፡ የማ
ትበሉት ፡ ለናንተ ፡ ምን ፡ (ምክ
ንያት) ፡ አላችሁ ? ብዙዎቹም ፡
ያለ ፡ ዕውቀት ፡ በዝንባሌዎቻ
ቸው ፡ ያሳስታሉ ፤ ጌታህ ፡ እርሱ ፡
ወሰን ፡ አላፊዎቹን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው።
120 የኃጢአትንም ፡ ግልጹንም ፡ ድብ
ቁንም ፡ ተውዉ ፤ እነዚያ ፡ ኃጢ
አትን ፡ የሚሠሩ ፤ ይሠሩት ፡ በነ
በሩት ፡ ነገር ፡ በእርግጥ ፡ ይቅ
ቀጣሉ ።
121 በርሱም ፡ ላይ ፡ የአላህ ፡ ስም ፡
ካልተጠራበት ፡ ነገር ፡ አትብሉ ፤
እርሱም ፡ በእርግጥ ፡ አመጥ ፡
ነው ፤ ሰይጣናትም ፡ ወደ ፡ ወዳጆ
ቻቸው ፡ (በክትን ፡ በመብላት) ፡
ይከራከሯችሁ ፡ ዘንድ ፡ ያሾክሹ
ካሉ ፤ ብትታዘዙዋቸውም ፡ እና
ንተ ፡ በእርግጥ ፡ አጋሪዎች ፡
ናችሁ ።
122 ሙት ፡ የነበረና ፡ ሕያው ፡ ያደረ
ግነው ፡ ለርሱም ፡ በሰዎች ፡ መካ
ከል ፡ በርሱ ፡ የሚኼድበትን ፡
ብርሃን ፡ ያደረግንለት ፡ ሰው ፡
በጨለማዎች ፡ ውስጥ ፡ ከርሷ ፡
የማይወጣ፡ ኾኖ ፡ እንዳልለ ፡
ሰው ፡ ብጤ ፡ ነውን ? እንደዚሁ ፡
ለከሓዲዎች ፡ ይሠሩት ፡ የነበሩት፡
ነገር ፡ ተጌጠላቸው ።
123 እንደዚሁም ፡ (1) በየከተማይቱ ፡
በውስጧ ፡ ያሴሩ ፡ ዘንድ ፡ የተንኮ
ለኞችዋን ፡ ታላላቆች ፡ አደረግን ፤
በነፍሶቻቸውም ፡ ላይ ፡ እንጅ ፡
በሌላ ፡ ላይ ፡ አያሴሩም ፤ (1) ግን ፡
አያውቁም ።
124 ታምርም ፡ በመጣቻቸው ፡ ጊዜ ፡-
የአላህ ፡ መልክተኞች ፡ የተሰጡ
ትን ፡ ብጤ ፡ እስክንሰጥ ፡ ድረስ ፡
በፍጹም ፡ አናምንም ፡ አሉ ፤
አላህ ፡ መልክቱን ፡ የሚያደርግ
በትን ፡ ስፍራ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፤
እነዚያን ፡ ያምመጡትን ፡ ሰዎች ፡
ይዶልቱ ፡ በነበሩት ፡ ነገር ፡ አላህ፡
ዘንድ ፡ ውርደትና ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት
ያገኛቸዋል ።
125 አላህም ፡ ሊመራው ፡ የሚሻውን ፡
ሰው ፡ ደረቱን ፡ (ልቡን) ፡ ለኢስ
ላም ፡ ይከፍትለታል ፤ ሊያጠ
መውም ፡ የሚሻውን ፡ ሰው ፡ ደረ
ቱን ፡ ጠባብ ፡ ቸጋራ ፡ ወደ ፡
ሰማይ ፡ ለመውጣት ፡ እንደሚታ
ገል ፡ ያደርገዋል ። እንደዚሁ ፡
አላህ ፡ በነዚያ ፡ በማያምኑት ፡
ላይ ፡ ርክሰትን ፡ ያደርጋል ።
126 ይህም ፡ (ያለህበት) ፡ ቀጥተኛ ፡
ሲኾን ፡ የጌታህ ፡ መንገድ ፡ ነው ፤
ለሚያስታውሱ ፡ ሕዝቦች ፡ አንቀ
ጾችን ፡ በእርግጥ ፡ ዘርዝረናል ።
127 ለነርሱ ፡ በጌታቸው ፡ ዘንድ ፡ የሰ
ላም ፡ አገር ፡ አላቸው ፤ እርሱም ፡
(ጌታህ) ፡ ይሠሩት ፡ በነበሩት ፡
ምክንያት ፡ ረዳታቸው ፡ ነው ።
128 ሁሉንም ፡ የሚሰበስብባቸውንም ፡
ቀን ፡ (አስታውስ) ፡— ያጋንንት ፡
ጭፍሮች ፡ ሆይ ! ከሰዎች ፡ (ጭፍ
ራን ፡ በማጥመም) ፡ በእርግጥ ፡
አበዛችሁ ፡ (ይባላሉ) ፤ ከሰዎችም፡
የኾኑት ፡ ወዳጆቻቸው ፡— ጌታ
ችን ፡ ሆይ ! ከፊላችን ፡ በከፊሉ ፡

1 በመካ ፡ ታላላቅ ፡ አመጸኞችን ፡ እንዳደ
ረግን ።

1 ጉዳቱ ፡ ወደነሱው ፡ ይመለሳልና ።

ተጠቀመ ፤ (1) ያንንም ፡ ለኛ ፡ የወሰንክልንን ፡ ጊዜያችንን ፡ ደረስን ፡ ይላሉ ፤ እሳት ፡ አላህ ፡ የሻው ፡ ጊዜ ፡ ሲቀር ፡ በውስጧ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ስትኾኑ ፡ መኖሪያችሁ ፡ ናት ፡ ይላቸዋል ፤ ጌታህ ፡ ጥበበኛ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።

129 እንደዚሁም ፡ የበደለኞችን ፡ ከፊል ፡ በከፊሉ ፡ ላይ ፡ ይሠሩት ፡ በነበሩት ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ እንሾማለን ።

130 የጋኔንና ፡ የሰዎች ፡ ጭፍሮች ፡ ሆይ ! ፡—እንቀጾቼን ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ የሚተርኩ ፡ የዚህንም ፡ ቀናችሁን ፡ (ቅጣት) ፡ ማግኘትን ፡ የሚያስፈራሩዋችሁ ፡ ከናንተው ፡ የኾኑ ፡ መልክተኞች ፡ አልመጧችሁምን ? (ይባላሉ) ፤ በነፍሶቻችን ፡ ላይ ፡ መሰከርን ፤ (መጥተውልናል) ፡ ይላሉ ፤ የቅርቢቱም ፡ ሕይወት ፡ አታለለቻቸው ፤ በነፍሶቻቸውም ፡ ላይ ፡ እነርሱ ፡ ከሓዲዎች ፡ የነበሩ ፡ መኾናቸውን ፡ መሰከሩ ።

131 ይህ ፡ ጌታህ ፡ ከተሞችን ፡ ባለቤቶችዋ ፡ ዘንጊዎች ፡ ኾነው ፡ ሳሉ ፡ (2) በበደል ፡ ምክንያት ፡ አጥፊ ፡ ባለመኾኑ ፡ ነው ።

132 ለሁሉም ፡ ከሠሩት ፡ ሥራ ፡ (የተበላለጡ) ፡ ደረጃዎች ፡ አልሏቸው ፤ ጌታህም ፡ ከሚሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ዘንጊ ፡ አይደለም ።

133 ጌታህም ፡ ተብቃቂ ፡ የእዝነት ፡ ባለ ፡ ቤት ፡ ነው ፤ ቢሻ ፡ ያስወግዳችኋል ፤ (ያጠፋችኋል) ፤ ከሌሎች ፡ ሕዝቦችም ፡ ዘሮች ፡ እንዳስገኛችሁ ፡ ከበኋላችሁ ፡ የሚሻውን ፡ ይተካል ።

134 የምትቀጠሩት ፡ ሁሉ ፡ በእርግጥ ፡ መጪ ፡ ነው ፤ እናንተም ፡ አምላጮች ፡ አይደላችሁም ።

135 ፡—ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ! በችሎታችሁ ፡ ላይ ፡ ሥሩ ፤ እኔ ፡ (በችሎታዬ ፡ ላይ) ፡ ሠሪ ፡ ነኝና ፤ ምስጉኒቱም ፡ አገር ፡ (ገነት) ፡ ለርሱ ፡ የምትኾንለት ፡ ሰው ፡ ማን ፡ እንደኾነ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ታውቃላችሁ ፤ እነሆ ፡ በደለኞች ፡ አይድኑም ፡ በላቸው ።

136 ለአላህም ፡ ከፈጠረው ፡ ከአዝመራና ፡ ከግመል ፡ ከከብት ፡ ከፍየልም ፡ ድርሻን ፡ (1) አደረጉ ፤ በሐሳባቸውም ፡ ይህ ፡ ለአላህ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ለተጋሪዎቻችን ፡ ነው ፡ ለተጋሪዎቻቸውም ፡ (ለጣዖታት) ፡ የኾነው ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ አይደርስም ፤ ለአላህም ፡ የኾነው ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ ተጋሪዎቻቸው ፡ ይደርሳል ፡ አሉ ፤ የሚፈርዱት ፡ ፍርድ ፡ ከፋ !

137 እንደዚሁም ፡ ከአጋሪዎቹ ፡ ለብዙዎቹ ፤ ተጋሪዎቻቸው ፡ ሊያጠፉዋቸው ፡ ሃይማኖታቸውንም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ሊያቀላቅሉባቸው ፡ (ሊያመሳስሉባቸው) ፡ ልጆቻቸውን ፡ መግደልን ፡ አሳመሩላቸው ፤ አላህም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ ባልሠሩት ፡ ነበር ፤ ከቅጥፈታቸውም ፡ ጋር ፡ ተዋቸው ።

138 በሐሳባቸውም ፡ ይህች ፡ እርም ፡ የኾነች ፡ ለማዳ ፡ እንስሳና ፡ አዝመራ ፡ ናት ፤ የምንሻው ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይበላትም ፤ (ይህች) ፡ ጀርቦችዋ ፡ እርም ፡ የተደረገች ፡ ለማዳ ፡ እንስሳም ፡ ናት ፡

1 ጋኔኖች ፡ ስንጠበቅባቸው ፡ ይጠብቁናል ፡ እኛም ፡ እንታዘዛቸዋለን ።

2 አስጠንቃቂ ፡ መልክተኛ ፡ ሳይመጣቸው ።

1 ለሚያጋሩዋቸውም ፡ ጣዖታት ፡ ድርሻን ።



(አትጫኑም ፡ ይኸች) ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ የአላህን ፡ ስም ፡ (ስትታረድ) ፡ የማይጠሩባትም ፡ እንስሳ ፡ ናት ፡ አሉ ። በርሱ ፡ ላይ ፡ ለመቅጠፍ ፡ (ነገሩን ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ አስጠጉ) ፤ ይቀጥፉት ፡ በነበሩት ፡ ነገር ፡ በእርግጥ ፡ ይቀጣቸዋል ።

139 ፡—በነዚህም ፡ እንስሶች ፡ ሆዶች ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ለወንዶቻችን ፡ በተለይ ፡ የተፈቀደ ፡ ነው ፤ በሚስቶቻችንም ፡ ላይ ፡ እርም ፡ የተደረገ ፡ ነው ፤ ሙትም ፡ ቢኾን ፡ (ሙት ፡ ኾኖ ፡ ቢወለድ) ፡ እነርሱ ፡ (ወንዶቹም ፡ ሴቶቹም) ፡ በርሱ ፡ ተጋሪዎች ፡ ናቸው ፡ አሉ ፤ በመቅጠፋቸው ፡ አላህ ፡ በእርግጥ ፡ ይቀጣቸዋል ፤ እርሱ ፡ ጥበበኛ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።

140 እነዚያ ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ በሞኝነት ፡ ልጆቻቸውን ፡ የገደሉና ፡ አላህም ፡ የሰጣቸውን ፡ (ሲሳይ) ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ በመቅጠፍ ፡ እርም ፡ ያደረጉ ፡ በእርግጥ ፡ ከሰሩ ፤ በእርግጥ ፡ ተሳሳቱ ፤ ተመሪዎችም ፡ አልነበሩም ።

141 እርሱም ፡ ያ ፡ ዳስ ፡ የሚደረግላቸውንና ፡ ዳስ ፡ የማይደረግላቸውን ፡ አትክልቶች ፡ የፈጠረ ፡ ነው ፤ ዘምባባንም ፡ (የተምርን ፡ ዛፍ) ፡ አዝመራንም ፡ ፍሬዎቹ ፡ የተለያዩ ፡ ሲኾኑ ፡ ወይራንና ፡ ሩማንንም ፡ (ቅጠላቸው) ፡ ተመሳሳይና ፡ (ጣዕማቸው) ፡ የማይመሳሰል ፡ ሲኾኑ ፡ (ፈጠረ) ፤ ባፈራ ፡ ጊዜ ፡ ከፍሬው ፡ ብሉ ፤ ባጨዳውም ፡ ቀን ፡ ተገቢውን ፡ (ዘካ) ፡ ስጡ ፤ አታባክኑም ፤ እርሱ ፡ አባካኞችን ፡ አይወድምና ።

142 ከለማዳ ፡ እንስሳዎችም ፡ የሚጫኑትንና ፡ የማይጫኑትን ፡ (ፈጠረ) ፡ አላህ ፡ ከሰጣችሁ ፡ ሲሳይ ፡ ብሉ ፤ የሰይጣንንም ፡ እርምጃዎች ፡ አትከተሉ ፤ እርሱ ፡ ለናንተ ፡ ግልጽ ፡ ጠላት ፡ ነውና ።

143 ስምንትን ፡ ዓይነቶች ፡ ከበግ ፡ ሁለትን ፡ (ወንድና ፡ ሴትን) ፡ ከፍየልም ፡ ሁለትን ፡ (ፈጠረ ፤ ከሁለቱም ፡ ክፍሎች ፡ አላህ) ፡ ወንዶቹን ፡ እርም ፡ አደረገን ፡ ወይስ ፡ ሴቶቹን ? ወይስ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የሁለቱ ፡ ሴቶች ፡ ማሕፀኖች ፡ ያጠቃለሉትን ? እውነተኞች ፡ እንደሆናችሁ ፡ በዕውቀት ፡ (በአስረጅ) ፡ ንገሩኝ ፡ በላቸው ።

144 ከግመልም ፡ ሁለትን ፡ ከከብትም ፡ ሁለትን ፡ (ፈጠረ) ፤ አላህ ፡ (ከሁለቱ) ፡ ወንዶቹን ፡ እርም ፡ አደረገን ፡ ወይስ ፡ ሴቶቹን ? ወይስ ፡ የሁለቱ ፡ ሴቶች ፡ ማሕፀኖች ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ያጠቃለሉትን ? በውነቱ ፡ አላህ ፡ በዚህ ፡ ባዘዛችሁ ፡ ጊዜ ፡ የተጣዳችሁ ፡ ነበራችሁን ? ሰዎችንም ፡ ያለዕውቀት ፡ ሊያጠም ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ውሸትን ፡ ከቀጠፈ ፡ ሰው ፡ ይበልጥ ፡ በደለኛ ፡ ማን ፡ ነው ? አላህ ፡ በደለኞችን ፡ ሕዝቦች ፡ (ቅኑን ፡ መንገድ) ፡ አይመራም ።

145 (ሙሐመድ ፡ ሆይ!) በላቸው ፡— ወደኔ ፡ በተወረደው ፡ ውስጥ ፡ በክት ፡ ወይም ፡ ፈሳሽ ፡ ደም ፡ ወይም ፡ የአሳማ ፡ ስጋ ፡ እርሱ ፡ ርኩስ ፡ ነውና ፡ ወይም ፡ በአመጥ ፡ ከአላህ ፡ ስም ፡ ሌላ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የተወሳበት ፡ ካልኾነ ፡ በስተቀር ፡ በሚመገበው ፡ ተመጋቢ ፡ ላይ ፡ እርም ፡ የኾነን ፡ ነገር ፡ አላገኝም ፤

አመጠኛና ፡ ወሰን ፡ ያለፈ ፡ ሳይ
ኾንም ፡ የተገደደ ፡ ሰው ፡ (ከተወ
ሱት ፡ ቢበላ ፡ ኃጢአት ፡ የለበ
ትም) ፡ ጌታህ ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡
ነውና ።
146 በነዚያም ፡ ይሁዳውያን ፡ በኾኑት ፡
ላይ ፡ ባለ ፡ ጥፍርን ፡ (1) ሁሉ ፡
እርም ፡ አደረግን ፤ ከከብት ፡ ከፍ
የልና ፡ ከበግም ፡ ሞራዎቻቸውን ፡
ጀርባቸው ፡ ወይም ፡ አንጀቶቻ
ቸው ፡ የተሸከሙት ፡ ወይም ፡
በአጥንት ፡ የተቀላቀለው ፡ (ስብ) ፡
ሲቀር ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ እርም ፡
አደረግን ፤ ይህንን ፡ በአመጻቸው ፡
ምክንያት ፡ ቀጣናቸው ፤ እኛም ፡
እውነተኞች ፡ ነን ።
147 ቢያስተባብሉህም ፡— ጌታችሁ ፡
የሰፊ ፡ ችሮታ ፡ ባለቤት ፡ ነው ፤
ብርቱ ፡ ቅጣቱም ፡ ከአመጠኞች ፡
ሕዝቦች ፡ ላይ ፡ አይመለስም ፡
በላቸው ።
148 እነዚያ ፡ ያጋሩት ፡ አላህ ፡ በሻ ፡
ኖሮ ፡ እኛም ፡ አባቶቻችንም ፡
ባላጋራን ፡ ነበር ፤ አንዳችንም ፡
ነገር ፡ እርም ፡ ባላደረግን ፡ ነበር ፡
ይላሉ ፤ እንደዚሁ ፡ (እንዚህ ፡ እን
ደዋሹ) ፡ እንዚያ ፡ ከበፊታቸው ፡
የነበሩት ፡ ብርቱ ፡ ቅጣታችንን ፡
እስከቀመሱ ፡ ድረስ ፡ አስተባበ
ሉ ፤ ለኛ ፡ ታዘልቁልን ፡ ዘንድ ፡
(ማጋራታችሁን ፡ ለመውደዱ) ፡
እናንተ ፡ ዘንድ ፡ ዕውቀት ፡ አለን?
ጥርጣሬን ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አትከ
ተሉም ፤ እናንተ ፡ ዋሾዎች ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደላችሁም ፡
በላቸው ።
149 የተሟላው ፡ ማስረጃ ፡ የአላህ ፡
ነው ፤ በሻም ፡ ኖሮ ፡ ሁላችሁ

1 ያልተሰነጠቀ ፡ ሰኮና ፡ ያለውን ።

ንም ፡ ባቀናችሁ ፡ ነበር ፡ በላቸው ።
150 ፡—እነዚያን ፡ አላህ ፡ ይህን ፡
እርም ፡ ማድረጉን ፡ የሚመሰክሩ
ትን ፡ ምስክሮቻችሁን ፡ አምጡ ፡
በላቸው ፤ ቢመሰክሩም ፡ ከነርሱ ፡
ጋር ፡ አትመስክር ፤ (1) የነዚያ
ንም ፡ በአንቀጾቻችን ፡ ያስተባበ
ሉትን ፡ የነዚያንም ፡ እነርሱ ፡
በጌታቸው ፡ (ሌላን) ፡ የሚያስተ
ካክሉ ፡ ሲኾኑ ፡ በመጨረሻይቱ ፡
ዓለም ፡ የማያምኑትን ፡ ሰዎች ፡
ዝንባሌዎች ፡ አትከተል ።
151 ፡—ኑ ፤ ጌታችሁ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
እርም ፡ ያደረገውን ፡ ነገር ፡ (በር
ሱም ፡ ያዘዛችሁን) ፡ ላንብብላ
ችሁ ፡ በላቸው ፤ በርሱ ፡ (በአ
ላህ) ፡ ምንንም ፡ ነገር ፡ አታጋሩ ፤
ለወላጆችም ፡ በጎን ፡ ሥራ ፡
(ሥሩ) ፤ ልጆቻችሁንም ፡ ከድኽ
ነት ፡ (ፍራቻ) ፡ አትግደሉ ፤ እኛ ፡
እናንተንም ፡ እነርሱንም ፡ እንመ
ግባችኋለንና ፤ መጥፎ ፡ ሥራዎ
ችንም ፡ ከርሷ ፡ የተገለጸውንም ፡
የተደበቀውንም ፡ ሁሉ ፡ አትቅ
ረቡ ፤ ያችንም ፡ አላህ ፡ እርም ፡
ያረጋትን ፡ ነፍስ ፡ በሕግ ፡ ቢኾን ፡
እንጅ ፡ አትግደሉ ፤ ይሃችሁ ፡
ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ (አላህ) ፡ በርሱ ፡
አዘዛችሁ ።
152 የየቲምንም ፡ ገንዘብ ፡ ብርታ
ቱን ፡ (አካለ ፡ መጠን) ፡ እስኪደ
ርስ ፡ ድረስ ፡ በዚያች ፡ እርሷ ፡
መልካም ፡ በኾነች ፡ ኹኔታ ፡
እንጅ ፡ አትቅረቡ ፤ ስፍርንና ፡
ሚዛንንም ፡ በትክክሉ ፡ ሙሉ ፤
ነፍስን ፡ ችሎታዋን ፡ እንጂ ፡ አና
ስገድድም ፤ በተናገራችሁም ፡
ጊዜ ፡ በዘመዶቻችሁ ፡ ላይ ፡ ቢኾ

1 ምስክርነታቸውን ፡ አትቀበል ።



ንም ፡ እንኳ ፡ (እውነትን ፡ በመና
ገር) ፡ አስተካክሉ ፤ በአላህም ፡
ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሙሉ ፤ ይኻችሁ ፡
ትገሠጹ ፡ ዘንድ ፡ በርሱ ፡ አዘዛ
ችሁ ።
153 ይህም ፡ ቀጥተኛ ፡ ሲኾን ፡ መን
ገዴ ፡ ነው ፤ ተከተሉትም ፤ (የጥ
መት) ፡ መንገዶችንም ፡ አትከ
ተሉ ፤ ከ(ቀጥተኛው) ፡ መንገዱ ፡
እናንተን ፡ ይለያዩዋችኋልና ።
ይኻችሁ ፡ ትጠነቀቁ ፡ ዘንድ ፡
በርሱ ፡ አዘዛችሁ ።
154 ከዚያም ፡ ለሙሳ ፡ በዚያ ፡ መል
ካም ፡ በሠራው ፡ ላይ ፡ (ጸጋች
ንን) ፡ ለማሟላት ፡ ነገርንም ፡
ሁሉ ፡ ለመዘርዘር ፡ መጽሐፉን ፡
(ለእስራኤል ፡ ልጆች) ፡ መሪና ፡
እዝነት ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ሰጠ
ነው ፤ እነርሱ ፡ በጌታቸው ፡ መገ
ናኘት ፡ ሊያምኑ ፡ ይከጀላልና ።
155 ይህም ፡ ያወረድነው ፡ የኾነ ፡ የተ
ባረከ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፤ ተከተሉ
ትም ፤ ይታዘንላችሁም ፡ ዘንድ ፡
(ከክሕደት) ፡ ተጠንቀቁ ።
156 (ያወረድነውም) ፡ መጽሐፍ ፡ የተ
ወረደው ፡ ከፊታችን ፡ በሁለቱ ፡
ጭፍሮች ፡ (1) ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤
እኛም ፡ ከንባባቸው ፡ ዘንጊዎች ፡
ነበርን ፡ እንዳትሉ ፡ ነው ።
157 ወይም ፡ እኛ ፡ መጽሐፍ ፡ በኛ ፡
ላይ ፡ በተወረደ ፡ ኖሮ ፡ ከነሱ ፡
ይበልጥ ፡ የተመራን ፡ እንኾን ፡
ነበር ፡ እንዳትሉ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡
ከጌታችሁ ፡ ግልጽ ፡ ማስረጃ ፡
መምሪያም ፡ እዝነትም ፡ በእር
ግጥ ፡ መጣላችሁ ፤ በአላህም ፡
አንቀጾች ፡ ካስተባበለና ፡ ከር
ሷም ፡ ከዞረ ፡ ሰው ፡ ይበልጥ ፡

1 በይሁዶችና ፡ በክርስቲያኖች ።

በዳይ ፡ ማን ፡ ነው ? እነዚያን ፡
አንቀጾቻችንን ፡ የሚተውትን ፡
ይተውት ፡ በነበሩት ፡ ምክንያት ፡
ብርቱን ፡ ቅጣት ፡ በእርግጥ ፡ እን
ቀጣቸዋለን ።
158 መላእክት ፡ ልትመጣላቸው ፡
ወይም ፡ ጌታህ ፡ (ቅጣቱ) ፡ ሊመ
ጣ ፡ ወይም ፡ ከጌታህ ፡ ምልክ
ቶች ፡ ከፊሉ ፡ ሊመጣ ፡ እንጂ ፡
ይጠባበቃሉን ? ከጌታህ ፡ ምልክ
ቶች ፡ ከፊሉ ፡ በሚመጣ ፡ ቀን ፡
ከዚያ ፡ በፊት ፡ አማኝ ፡ ያልኾነ
ችን ፡ ነፍስ ፡ እምነትዋ ፡ ወይም ፡
በእምነትዋ ፡ (ጊዜ) ፡ በጎ ፡ ያልሠ
ራችን ፡ (ነፍስ ፡ ጸጸትዋ) ፡ አይጠ
ቅማትም ፡— ተጠባበቁ ፡ እኛ ፡
ተጠባባቂዎች ፡ ነንና ፡ በላቸው ።
159 እነዚያ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ የለ
ያዩ ፡ አሕዛብም ፡ የኾኑ ፡ በም
ንም ፡ ከነሱ ፡ አይደለህም ፤ ነገ
ራቸው ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
ከዚያም ፡ ይሠሩት ፡ የነበሩትን ፡
ሁሉ ፡ ይነግራቸዋል ።
160 በመልካም ፡ ሥራ ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡
ለርሱ ፡ ዐሥር ፡ ብጤዎችዋ ፡
አሉት ፤ በክፉ ፡ ሥራም ፡ የመጣ ፡
ሰው ፡ ብጤዋን ፡ እንጅ ፡ አይመነ
ዳም ፤ እነርሱም ፡ አይበደሉም ።
161 እኔ ፡ ጌታዬ ፡ ወደ ፡ ቀጥተኛው ፡
መንገድ ፡ ትክክለኛን ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ወደ ፡ እውነት ፡ አዘንባይ ፡
ሲኾን ፡ የአብርሃምን ፡ መንገድ ፡
መራኝ ፤ እርሱም ፡ ከአጋሪዎቹ ፡
አልነበረም ፡ በል ።
162 ስግደቴ ፡ መገዛቴም ፡ሕይወቴም ፡
ሞቴም ፡ ለዓለማት ፡ ጌታ ፡ ለአ
ላህ ፡ ነው ፡ በል ።
163 ለርሱ ፡ ተጋሪ ፡ የለውም ፤ በዚ
ህም ፡ (በማጥራት) ፡ ታዘዝኩ ፤

እኔም የሙስሊሞች፡ መጀመሪያ ፡ ነኝ ፡ (በል) ።

164 በላቸው ፡—እርሱ ፡ (አላህ) ፡ የሁሉ ፡ ጌታ ፡ ሲኾን ፡ ከአላህ ፡ በቀር ፡ ሌላን ፡ ጌታ ፡ እፈልጋለሁን ? ነፍስም ፡ ሁሉ ፡ በራሷ ፡ ላይ ፡ እንጅ ፡ (ከፉን) ፡ አትሠራም ፤ ተሸካሚም ፡ (ነፍስ) ፡ የሌላይቱን ፡ ሸክም ፡ (ኃጢአት) ፡ አትሸከምም ፤ ከዚያም ፡ መመለሻችሁ ፡ ወደ ፡ ጌታችሁ ፡ ነው ፤ ወዲያውም ፡ በርሱ ፡ ትለያዩበት ፡ የነበራችሁትን ፡ ሁሉ ፡ ይነግራችኋል ።

165 እርሱም ፡ ያ ፡ በምድር ፡ ምትኮች ፡ ያደረጋችሁ ፡ በሰጣችሁም ፡ ጸጋ ፡ ሊፈትናችሁ ፡ ከፊላችሁን ፡ ከከፊሉ ፡ በላይ ፡ በደረጃዎች ፡ ከፍ ፡ ያደረገ ፡ ነው ፤ ጌታህ ፡ ቅጣቱ ፡ ፈጣን ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ እጅግ ፡ መሓሪ ፡ ርኅሩህ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 7 ፡ አል-አዕራፍ ። ክፍል ፡ 8 ።

7ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-አዕራፍ ፡ (የአዕራፍ ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 206 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው።

1 አ . ለ . መ . ሰ. (አሊፍ ፡ ላም ፡ ሚም ፡ ሷድ) ። (1)

2 (ይህ) ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ የተወረደ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፤ በደረትህም ፡ ውስጥ ፡ ከርሱ ፡ ጭንቀት ፡ አይኑር ፤ (የተወረደውም) ፡ በርሱ ፡ ልታስፈራራበትና ፡ ለምእምናን ፡ መገሠጫ ፡ እንዲኾን ፡ ነው ።

3 ከጌታችሁ ፡ ወደናንተ ፡ የተወረደውን ፡ ተከተሉ ፤ ከአላህም ፡ ሌላ ፡ ረዳቶችን ፡ አትከተሉ ፤ ጥቂትን ፡ ብቻ ፡ ትገሠጻላችሁ ።

4 ከከተማም ፡ ልናጠፋት ፡ የሻነው ፡ ወዲያወ ም ፡ ብርቱ ፡ ቅጣታችን ፡ ሌሊት ፡ ወይም ፡ ቀን ፡ እነርሱ ፡ በቀትር ፡ አርፈው ፡ ሳሉ ፡ የመጣባቸው ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

5 ቅጣታችንም ፡ በመጣባቸው ፡ ጊዜ ፡ ጸሎታቸው ፡ እኛ ፡ በደለኞች ፡ ነበርን ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አልነበረም ።

6 እነዚያንም ፡ ወደነሱ ፡ የተላከባቸውን ፡ (ሕዝቦች) ፡ በእርግጥ ፡ መልክተኞቹንም፡ እንጠይቃለን።

7 በነርሱም ፡ ላይ ፡ (የነበሩበትን ፡ ሁሉ) ፡ ከዕውቀት ፡ ጋር ፡ በእርግጥ ፡ እንተርክላቸዋለን ፤ የራቅንም ፡ አልነበርንም ።

8 ትክክለኛውም ፡ ሚዛን ፡ የዚያን ፡ ቀን ፡ ነው ፤ ሚዛኖቻቸው ፡ የከበዱላቸው ፡ ሰዎችም ፡ እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ የፈለጉትን ፡ ያገኙ ፡ ናቸው ።

9 ሚዛኖቻቸው ፡ የቀለሉባቸው ፡ ሰዎችም ፡ እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ ታአምራቶቻችንን ፡ ይክዱ ፡ በነበሩት ፡ ምክንያት ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ ያከሰሩ ፡ ናቸው ።

10 በምድርም ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ አስመቸናችሁ ፤ በርሷም ፡ ላይ ፡ ለናንተ ፡ መኖሪያዎችን ፡ አደረግንላችሁ ፤ ምስጋናችሁ ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ነው ።

11 በእርግጥም ፡ ፈጠርናችሁ ፤ ከዚያም ፡ ቀረጽናችሁ ፤ ከዚያም ፡ ለመላእክቶች ፡ ለአዳም ፡ ስገዱ ፡ አልን ፤ ወዲያውም ፡ ሰገዱ ፤ ኢብሊስ ፡ (ዲያብሎስ) ፡ ሲቀር ፡ ከሰጋጆቹ ፡ አልኾነም ።

12 (አላህ) ፡ ባዘዝኩህ ፡ ጊዜ ፡ ከመስገድ ፡ ምን ፡ ከለከለህ ? አለው ፤ እኔ ፡ ከርሱ ፡ የበለጥኩ ፡ ነኝ ፤ ከእሳት ፡ ፈጠርከኝ ፤ እርሱን ፡ ግን ፡ ከጭቃ ፡ ፈጠርከው ፡ አለ ።

13 ከርሷ ፡ (1) ውረድ ፤ በርሲ ፡ ውስጥ ልትኮራ ፡ አይገባህምና ፡ ውጣም ፡ አንተ ፡ ከወራዶቹ ፡ ነህና ፡ አለው፤

14 ፡—እስከሚቀሰቀሱበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ አቆየኝ ፡ አለ ።

15 ፡—አንተ ፡ ከሚቆዩት ፡ ነህ ፡ አለው ።

16 ፡—ስለአጠመምከኝም ፡ ለነርሱ ፡ በቀጥተኛው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ እቀመጥባቸዋለሁ ፡ አለ ።

17 ከዚያም ፡ ከስተፊቶቻቸው ፡ ከኋላቸውም ፡ ከቀኞቻቸውም ፡ ከግራዎቻቸውም ፡ በእርግጥ ፡ እመጣባቸዋለሁ ፤ አብዛኞቻቸውንም ፡ አመስጋኞች ፡ ኾነው ፡ አታገኛቸውም ፡ (አለ) ።

18 ፡—የተጠላህ ፡ ብሩሪ ፡ ስትኾን ፡ ከርሷ ፡ ውጣ ፤ ከነርሱ ፡ የተከተለህ ፡ ከናንተ ፡ ከመላችሁም ፡ ገሀነምን ፡ በእርግጥ ፡ እሞላታለሁ ፡ አለው ።

19 አዳምም ፡ ሆይ ! አንተም ፡ ሚስትህም ፡ በገነት ፡ ተቀመጡ ፤ ከሻችሁትም ፡ ስፍራ ፡ ብሉ ፤ ግን ፡ ይህችን ፡ ዛፍ ፡ አትቅረቡ ፤ (ራሳቸውን) ፡ ከሚበድሉት ፡ ትኾናላችሁና ፡ (አላቸው) ።

20 ሰይጣንም ፡ ከዕፍረተ ፡ ገላቸው ፡ የተሸሸገውን ፡ ለነርሱ ፡ ሊገልጽባቸው ፡ በድብቅ ፡ ንግግር ፡ ጐተጐታቸው ፤ ጌታችሁም ፡ መልአኮች ፡ እንዳትኾኑ ፡ ወይም ፡ ከዘላለም ፡ ነዋሪዎች ፡ እንዳትኾኑ ፡ እንጂ ፡ ከዚች ፡ ዛፍ ፡ አልከለከላችሁም ፡ አላቸው ።

21 እኔ ፡ ለናንተ ፡ በእርግጥ ፡ ከሚመክሩዋችሁ ፡ ነኝ ፡ ሲልም ፡ ማለላቸው ።

22 በማታለልም ፡ አዋረዳቸው ፤ ከዛፊቱም ፡ በቀመሱ ፡ ጊዜ ፡ ዕፍረተ፡ ገላቸው ፡ ለሁለቱም ፡ ተገለጠችላቸው ፤ ከገነት ፡ ቅጠልም ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ ይደርቱ ፡ ጀመር ፤ ጌታቸውም ፡ ከዚቻችሁ ፡ ዛፍ ፡ አልከለከልኳችሁምን ? ሰይጣነም ለናንተ ፡ ግልጽ ፡ ጠላት ፡ ነው ፡ አላልኳችሁምን ? ሲል ፡ ጠራቸው ።

23 ፡—ጌታችን ፡ ሆይ ! ነፍሶቻችንን ፡ በደልን ፤ ለኛ ፡ ባትምር ፡ ባታዝንልንም ፡ በእርግጥ ፡ ከከሳሪዎቹ ፡ እንኾናለን ፡ አሉ ።

24 (አላህ) ፡— ከፊላችሁ ፡ ለከፊሉ ፡ ጠላት ፡ ሲኾን ፡ ውረዱ ፤ ለእናንተም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እስከ ፡

1 እኔ ፡ አላህ ፡ ነኝ ፡ ዐውቃለሁ ፡ እገልጻለሁ ።

1 ከገነት ፡ ወይም ፡ ከሰማያት ።

ተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ መርጊ
ያና ፡ መጠቀሚያ ፡ አላችሁ ፡
አላቸው ።
25 ፡—በርሷ ፡ ላይ ፡ ትኖራላችሁ ፤
በርሷም ፡ ላይ ፡ ትሞታላችሁ ፤
ከርሷም፡ ውስጥ ፡ ትወጣላችሁ ፡
አላቸው ።
26 የአዳም ፡ ልጆች ፡ ሆይ ! ኀፍረተ ፡
ገላችሁን ፡ የሚሸሽግን ፡ ልብስ ፡
ጌጥንም ፡ በእርግጥ ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ አወረድን ፤ አላህን ፡ የመፍ
ራትም ፡ ልብስ ፡ ይህ ፡ የተሻለ ፡
ነው ፤ ይህ ፡ ከአላህ ፡ ታምራቶች ፡
ነው ፤ ይገሠጹ ፡ ዘንድ ፡ (አወረደ
ላቸው) ።
27 የአዳም ፡ ልጆች ፡ ሆይ ! ሰይጣን ፡
አባትና ፡ እናታችሁን ፡ ዕፍረተ ፡
ገላቸውን ፡ ሊያሳያቸው ፡ ልብሶ
ቻቸውን ፡ ከነሱ ፡ የገፈፋቸው ፡
ሲኾን ፡ ከገነት ፡ እንዳወጣቸው ፡
ሁሉ ፡ እናንተን ፡ አይሞክራችሁ ፤
እነሆ ፡ እርሱ ፡ ከነሰራዊቱ ፡
ከማታዩዋቸው ፡ ስፍራ ፡ ያዩዋች
ኋልና ፤ እኛ ፡ ሰይጣናትን ፡ ለነ
ዚያ ፡ ለማያምኑት ፡ ወዳጆች ፡
አድርገናል ።
28 መጥፎንም ፡ ሥራ ፡ በሠሩ ፡ ጊዜ ፡
—በርሷ ፡ ላይ ፡ አባቶቻችንን ፡
አገኘን ፡ አላህም ፡ በርሷ ፡ አዞ
ናል ፡ ይላሉ ፤ ፡—አላህ ፡ በመ
ጥፎ ፡ ነገር ፡ አያዝም ፤ በአላህ ፡
ላይ ፡ የማታውቁትን ፡ ትናገራ
ላችሁን ? በላቸው ።
29 ፡—ጌታዬ ፡ በማስተካከል ፡ አዘዘ ፤
በየመስጊዱም ፡ ዘንድ ፡ ፊቶቻች
ሁን ፡ (እርሱን ፡ ለመገዛት) ፡ አስ
ተካክሉ ፤ ሃይማኖትንም ፡ ለርሱ ፡
ፍጹም ፡ አድርጋችሁ ፡ ተገዙት ፤
እንደጀመራችሁ ፡ (1) ትመለሳላ
ችሁ ፡ በላቸው ።
30 ከፊሉን ፡ ወደ ፡ ቅን ፡ መንገድ ፡
መራ ፤ ከፊሎቹም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
ጥመት ፡ ተረጋግጠባቸዋል ፤ እነ
ርሱ ፡ ሰይጣናትን ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡
ረዳቶች ፡ አድርገው ፡ ይዘዋልና ፤
እነርሱም ፡ (ቅኑን ፡ መንገድ) ፡ የተ
መራን ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ያስባሉ ።
31 የአዳም ፡ ልጆች ፡ ሆይ ! (ኀፍረተ ፡
ገላችሁን ፡ የሚሸፍኑትን) ፡ ጌጠ
ቻችሁን ፡ በመስገጃው ፡ ሁሉ ፡
ዘንድ ፡ (2) ያዙ ፤ ብሉም ፤ ጠጡ
ም ፤ አታባክኑም ፤ እርሱ ፡ አባካ
ኞችን ፡ አይወድምና ።
32 ፡—የአላህን ፡ ጌጥ ፡ ያችን ፡ ለባ
ሮቹ ፡ የፈጠራትን ፡ ከሲሳይም ፡
ጥሩዎቹን ፡ እርም ፡ ያደረገ ፡ ማን ፡
ነው ? በላቸው ፤ እርሷ ፡ በትን
ሣኤ ፡ ቀን ፡ ለነዚያ ፡ ላመኑት ፡
ብቻ ፡ ስትኾን ፡ በቅርቢቱ ፡ ሕይ
ወት ፡ ተገቢያቸው ፡ ናት ፡ በላ
ቸው ፤ እንደዚሁ ፡ ለሚያውቁ ፡
ሕዝቦች ፡ አንቀጾችን ፡ እናብራ
ራለን ።
33 ፡—ጌታዬ ፡ እርም ፡ ያደረገው ፡
መጥፎ ፡ ሥራዎችን ፡ ከርሷ ፡ የተ
ገለጸውንና ፡ የተደበቀውን ፡ ኃጢ
አትንም ፡ ያላግባብ ፡ መበደል
ንም ፡ በርሱም ፡ ማስረጃ ፡ ያላወረ
ደበትን ፡ (ጣዖት) ፡ በአላህ ፡ ማጋ
ራታችሁን ፡ በአላህም ፡ ላይ ፡
የማታውቁትን ፡ መናገራችሁን ፡
ብቻ ፡ ነው ፡ በላቸው ።
34 ለሕዝብም ፡ ሁሉ ፡ የተወሰነ ፡
ጊዜ ፡ አላቸው ፤ ጊዜያቸውም ፡

1 መጀመሪያ ፡ እንደ ፡ ፈጠራችሁ ፡ ይመልሳ
ችኋል ፤
2 በሶላትና ፡ ከዕባን ፡ በመዞር ፡ ጊዜ ፡ ሸፍኑ ።



በመጣ ፡ ወቅት ፡ አንዲትን ፡
ሰዓት ፡ አይቆዩም ፤ (ከጊዜያቱ) ፡
አይቀደሙምም ።
35 የአዳም ፡ ልጆች ፡ ሆይ ! ከናንተ ፡
ውስጥ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ አንቀጾ
ቼን ፡ የሚያነቡ ፡ መልክተኞች ፡
ቢመጧችሁ ፡ ከናንተ ፡ ከሕደ
ትን ፡ የተጠነቀቁና ፡ በግኀንም ፡
የሠሩ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ፍርሃት ፡
የለባቸውም ፤ እነሱም ፡ አይተክ
ዙም ።
36 እነዚያም ፡ በአንቀጾቻችን ፡ ያስ
ተባበሉ ፡ ከርሷም ፡ የኮሩ ፡ እነ
ዚያ ፡ የእሳት ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ፤
እነሱ ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ዘውታ
ሪዎች ፡ ናቸው ።
37 በአላህ ፡ ላይ ፡ ውሸትን ፡ ከቀ
ጠፈ ፡ ወይም ፡ በአንቀጾቹ ፡ ከአስ
ዋሸ ፡ ሰው ፡ ይበልጥ ፡ በዳይ ፡
ማን ፡ ነው ? እነዚያ ፡ (ከተጻፈላ
ቸው) ፡ ከመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡
ሲኾን ፡ ዕድላቸው ፡ ያገኛቸዋል ፤
(የሞት) ፡ መልክተኞቻችንም ፡
የሚገድሏቸው ፡ ኾነው ፡ በመጡ
ባቸው ፡ ጊዜ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ትግ
ገዟቸው ፡ የነበራችሁት ፡ የት ፡
አሉ ? ይሏቸዋል ፤ ከኛ ፡ ተሰወ
ሩን ፡ ይላሉ ፤ እነርሱም፡ ከሃዲ
ያን ፡ እንደነበሩ ፡ በነፍሶቻቸው ፡
ላይ ፡ ይመሰክራሉ ።
38 ፡—ከጋኔንም ፡ ከሰውም ፡ ከናንተ ፡
በፊት ፡ በእርግጥ ፡ ካለፉት ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ጋር ፡ ኾናችሁ ፡ እሳት ፡
ውስጥ ፡ ግቡ ፡ ይላቸዋል ፤ አን
ዲቱ ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ በገ
ባች ፡ ቍጥር ፡ (ያሳሳተቻትን) ፡
ብጤዋን ፡ ትረግማለች ፤ መላ
ውም ፡ በውስጧ ፡ ተሰብስበው ፡
በተገናኙም ፡ ጊዜ ፡ የኋለኛይቱ ፡
ለመጀመሪያይቱ ፡ (ተከታዮች ፡
ለአስከታዮች) ፡—ጌታችን ፡ ሆይ!
እነዚህ ፡ አሳሳቱን ፤ ከእሳትም ፡
ስቃይ ፡ ዕጥፍን ፡ ስጣቸው ፡ ትላ
ለች ፤ (አላህም) ፡— ለሁሉም ፡
ዕጥፍ ፡ አለው ፡ ግን ፡ አታውቁም፡
ይላቸዋል ።
39 ፡—መጀመሪያይቱም ፡ ለኋለኛይ
ቱ ፡ ለናንተ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡
ብልጫ ፡ አልነበራችሁም ፡ ትላ
ለች ፤ ትሠሩትም ፡ በነበራችሁት ፡
ቅጣቱን ፡ ቅመሱ ፡ (ይላቸዋል) ።
40 እነዚያ ፡ አንቀጾቻችንን ፡ ያስተ
ባበሉ ፡ ከርሷም ፡ የኮሩ ፡ ለነርሱ ፡
የሰማይ ፡ ደጃፎች ፡ አይከፈቱላ
ቸውም ፤ ግመል ፡ በመርፌ ፡
ቀዳዳ ፡ እስከሚገባም ፡ ድረስ ፡
ገነትን ፡ አይገቡም ፤ እንደዚሁም ፡
አጋሪዎችን ፡ እንቀጣለን ።
41 ለነርሱ ፡ ከገሀነም ፡ እሳት ፡ (በሥ
ራቸው) ፡ ምንጣፍ ፡ ከበላያቸ
ውም ፡ (የእሳት) ፡ መሸፈኛዎች ፡
አሏቸው ፤ እንደዚሁም ፡ በደለ
ኞችን ፡ እንቀጣለን ።
42 እነዚያም ፡ ያመኑና ፡ መልካሞ
ችን ፡ የሠሩ ፡ ነፍስን ፡ ችሎታ
ዋን ፡ እንጂ ፡ አናስገድድምና ፤
እነዚያ ፡ የገነት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፤
እነርሱ ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ዘውታ
ሪዎች ፡ ናቸው ።
43 በደረቶቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለው
ንም ፡ ጥላቻ ፡ እናስወግዳለን ፤
ወንዞች ፡ በሥሮቻቸው ፡ ይፈስ
ሳሉ ፤ ለዚያም ፡ ወደዚህ ፡ (ላደረ
ሰን ፡ ሥራ) ፡ ለመራን ፡ አላህ ፡
ምስጋና ፡ ይገባው ፤ አላህ ፡ ባልመ
ራንም ፡ ኖሮ ፡ አንመራም ፡ ነበር ፤
የጌታችን ፡ መልክተኞች ፡ በው
ነት ፡ ላይ ፡ ሲኾኑ ፡ በእርግጥ ፡

መጥተውልናል ፡ ይላሉ ፤ ይህቻ
ችሁም ፡ ገነት ፡ ትሠሩት ፡ በነበራ
ችሁት ፡ ተሰጣችኋት ፡ በማለት ፡
ይጠራሉ ።
44 የገነትም ፡ ሰዎች ፡ የእሳትን ፡
ሰዎች ፡ ጌታችን ፡ ቃል ፡ የገባል
ንን ፡ እውነት ፡ ኾኖ ፡ አገኘን ፤
ጌታችሁ ፡ የዛተባችሁንስ ፡ እው
ነት ፡ ኾኖ ፡ አገኛችሁትን ? ሲሉ ፡
ይጣራሉ ፤ አዎን ፡ አገኘን ፡ ይላሉ፤
በመካከላቸውም ፡ የአላህ ፡ ርግ
ማን ፡ በበደለኞች ፡ ላይ ፡ ይኹን ፡
ሲል ፡ ለፋፊ ፡ ይለፍፋል ።
45 (በደለኞች) ፡ እነዚያ ፡ ከአላህ ፡
መንገድ ፡ የሚከለክሉ ፤ እንድት
ጣመምም ፡ የሚፈልጉዋት ፡ እነር
ሱም ፡ በመጨረሻዋ ፡ ዓለም ፡
ከሓዲዎች ፡ የኾኑ ፡ ናቸው ።
46 በመካከላቸውም ፡ (1) ግርዶሽ ፡
አልለ ፤ በአዕራፍም ፡ ላይ ፡ (2)
ሁሉንም ፡ በምልክታቸው ፡ (3)
የሚያውቁ ፡ ሰዎች ፡ አልሉ ፤
የገነትንም ፡ ሰዎች ፡ ሰላም ፡ ለና
ንተ ፡ ይኹን፡ በማለት ፡ ይጣራሉ፤
እነርሱም ፡ (የአዕራፍ ፡ ሰዎች) ፡
የሚከጅሉ ፡ ሲኾኑ ፡ ገና ፡ አልገ
ቧትም ።
47 ዓይኖቻቸውም ፡ ወደ ፡ እሳት ፡
ሰዎች ፡ አግጣጫ ፡ በተዞሩ ፡
ጊዜ ፡—ጌታችን ፡ ሆይ ! ከበደ
ለኞች ፡ ጋር ፡ አታድርገን ፡ ይላሉ፤
48 የአዕራፍም ፡ ሰዎች ፡ በምልክታ
ቸው ፡ የሚያውቁዋቸውን ፡ (ታላ
ላቅ)፡ ሰዎች፡ ይጣራሉ፤ ስብስባ
ችሁና፡ በብዛታችሁ፥ የምትኮሩ፡
መኾናችሁም፡ ከናንተ፡ ምንም፡
አልጠቀማችሁ፡ ይሏቸዋል።
49 እነዚያ ፡ አላህ ፡ በችሮታው ፡ አያገ
ኛቸውም ፡ ብላችሁ ፡ የማላችሁት፡
(ደካሞች) ፡ እነዚህ ፡ ናቸውን ?
ገነትን ፡ ግቡ ፡ ፍርሃት ፡ የለባች
ሁም ፡ እናንተም ፡ አታዝኑም ፡
(ተባሉ ፡ ይሏቸዋል) ።
50 የእሳትም ፡ ሰዎች ፡ የገነትን ፡
ሰዎች ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ከውሃ ፡ አፍ
ስሱብን ፡ ወይም ፡ አላህ ፡ ከሰጣ
ችሁ ፡ሲሳይ ፡ (ጣሉልን) ፡ ብለው
ይጠሩዋቸዋል ፤ እነሱም ፡ አላህ ፡
በከሓዲዎች ፡ ላይ ፡ እርም ፡ አድ
ርጓቸዋል ፡ ይሏቸዋል ።
51 እነዚያ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ መሳ
ለቂያና ፡ መጫወቻ ፡ አድርገው ፡
የያዙ ፡ የቅርቢቱም ፡ ሕይወት ፡
ያታለለቻቸው ፡ ይህንን ፡ ቀናቸ
ውን ፡ መገናኘትን ፡ እንደርሱ ፡
በተአምራታችንም ፡ ይክዱ ፡
እንደ ፡ ነበሩ ፡ ዛሬ ፡ እንረሳቸ
ዋለን ።
52 ከዕውቀት ፡ ጋርም ፡ የዘረዘርነው ፡
የኾነን ፡ መጽሐፍ ፡ ለሚያምኑ ፡
ሕዝቦች ፡ መምሪያና ፡ እዝነት ፡
ሲኾን ፡ በእርግጥ ፡ አመጣንላ
ቸው ።
53 (የዛቻውን) ፡ ፍጻሜውን ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አይጠባበቁም ፤ ፍጻሜው ፡
በሚመጣበት ፡ ቀን ፡ እነዚያ ፡
ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ የረሱት ፡
ሰዎች ፡ የጌታችን ፡ መልክተኞች ፡
በእርግጥ ፡ በውነት ፡ መጥተዋል ፤
ለኛ ፡ ያማልዱም ፡ ዘንድ ፡ አማላ
ጆች ፡ አልሉን ? ወይስ ፡ ከዚያ ፡
እንሠራው ፡ ከነበርነው ፡ ሌላን ፡
ሥራ ፡ እንሠራ ፡ ዘንድ ፡ (ወደ ፡

1 በእሳትና ፡ በገነት ፡ መካከል ።
2 በገነትና ፡ በእሳት ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ኮረ
ብታ ፡ ነው ።
3 ከሓዲዎች ፡ ፊታቸው ፡ በመጥቆር ፡ ምእ
ምናኖች ፡ ፊታቸው ፡ በማብራት ።



ምድረ ፡ ዓለም) ፡ እንመለሳለን ?
ይላሉ ፤ ነፍሶቻቸውን ፡ በእርግጥ ፡
አከሰሩ ፤ ይቀጥፉት ፡ የነበሩትም ፡
ከነርሱ ፡ ጠፉቸው ።
54 ጌታችሁ ፡ ያ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድ
ርን ፡ በስድስት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡
የፈጠረ ፡ አላህ ፡ ነው ፤ ከዚያም ፡
(ስልጣኑ) ፡ በዐርሹ ፡ ላይ ፡ (1)
ተደላደለ ፤ (አላህ) ፡ ሌሊትን ፡
በቀን ፡ ፈጥኖ ፡ የሚፈልገው ፡
ሲኾን ፡ ይሸፍናል ፤ ፀሐይንና ፡
ጨረቃንም ፡ ከዋክብትንም ፡ በት
እዛዙ ፡ የተገሩ ፡ ሲኾኑ ፡ (ፈጠራ
ቸው) ፤ ንቁ ፤ መፍጠርና ፡ ማዘዝ ፡
የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ የዓለማት ፡
ጌታ ፡ አላህ ፡ (ክብሩ) ፡ ላቀ ።
55 ጌታችሁን ፡ ተዋርዳችሁ ፡ በድብ
ቅም ፡ ለምኑት ፤ እርሱ ፡ ወሰን ፡
አላፊዎችን ፡ አይወድምና ።
56 በምድርም ፡ ውስጥ ፡ ከተበጀች ፡
በኋላ ፡ አታበላሹ ፤ ፈርታችሁና ፡
ከጅላችሁም ፡ ተገዙት ፤ የአላህ ፡
ችሮታ ፡ ከበጎ ፡ አድራጊዎች ፡
ቅርብ ፡ ነውና ።
57 እርሱም ፡ ያ ፡ ነፋሶችን ፡ ከችሮ
ታው ፡ (ከዝናም) ፡ በፊት ፡ አብሳ
ሪዎች ፡ አድርጎ ፡ የሚልክ ፡
ነው ። ከባዳዎችንም ፡ ደመናዎች ፡
በተሸከሙ ፡ ጊዜ ፡ ሙት ፡ ወደ ፡
ኾነ ፡ አገር ፡ እንነዳዋለን ፤ በር
ሱም ፡ ውሃን ፡ እናወርዳለን ፤ ከፍ
ሬዎችም ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡ እናወ
ጣለን ፤ እንደዚሁ ፡ ትገነዘቡ ፡
ዘንድ ፡ ሙታንን ፡ (ከመቃብር) ፡
እናወጣለን ።
58 መልካሙም ፡ አገር ፡ በጌታው ፡
ፈቃድ ፡ በቃዩ ፡ (ያማረ ፡ ኾኖ) ፡
ይወጣል ፤ ያም ፡ መጥፎ ፡ የኾ
ነው ፡ (በቃዩ) ፡ ደካማ ፡ ኾኖ ፡
እንጂ ፡ አይወጣም ፤ እንደዚሁ ፡
ለሚያመሰግኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ታምራ
ትን ፡ እናብራራለን ። (1)
59 ኑሕን ፡ ወደ ፡ ወገኖቹ ፡ በእርግጥ ፡
ላክነው ፤ አላቸውም ፡— ወገኖቼ ፡
ሆይ ! አላህን ፡ ተገዙ ፤ ለናንተ ፡
ከርሱ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ አምላክ ፡
የላችሁም ፤ እኔ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
የከባድ ፡ ቀንን ፡ ቅጣት ፡ እፈራላ
ችኋለሁ ።
60 ከሕዝቦቹ ፡ (የካዱት) ፡ መሪ
ዎቹ ፡— እኛ ፡ በግልጽ ፡ መሳ
ሳት ፡ ውስጥ ፡ ኾነህ ፡ በእርግጥ ፡
እናይሃለን ፡ አሉት ።
61 አላቸው ፡— ወገኖቼ ፡ ሆይ !
ምንም ፡ መሳሳት ፡ የለብኝም ፤
ግን ፡ እኔ ፡ ከዓለማት ፡ ጌታ ፡
መልክተኛ ፡ ነኝ ።
62 የጌታዬን ፡ መልክቶች ፡ አደርስላ
ችኋለሁ ፤ ለናንተም ፡ እመክራ
ችኋለሁ ፤ ከአላህም ፡ በኩል ፡
የማታውቁትን ፡ ዐውቃለሁ ።
63 አላህን ፡ ልትፈሩና ፡ ይታዘንላች
ሁም ፡ ዘንድ ፡ ከናንተው ፡ (ጐሳ) ፡
በኾነ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ እንዲያስጠ
ነቅቃችሁ ፡ ከጌታችሁ ፡ ግሣጼ ፡
ቢመጣላችሁ ፡ ትደነቃላችሁን ?
(አላቸው) ።
64 ወዲያውም ፡ አስተባበሉት ፤ እር
ሱንና ፡ እነዚያንም ፡ ከርሱ ፡
ጋር ፡ ያሉትን ፡ (አማኞች) ፡ በታ
ንኳዋ ፡ ውስጥ ፡ አዳንናቸው ፤
እነዚያንም ፡ በአንቀጾቻችን ፡ ያስ
ተባበሉትን ፡ አሰጠምን ፤ እነ
ርሱ ፡ (ልበ) ፡ ዕውራን ፡ ሕዝቦች ፡
ነበሩና ።

1 በዙፋኑ ፡ ላይ ።

1 ይህ ፡ ለአማኝና ፡ ለከሓዲ ፡ የተሰጠ ፡ ምሳሌ
ነው ።

65 ወደ ፡ ዓድም ፡ ወንድማቸውን ፡
ሁድን ፡ ላክን ፤ ፡— ወገኖቼ ፡
ሆይ ! አላህን ፡ ተገዙ ፤ ከርሱ ፡
ሌላ ፡ ምንም ፡ አምላክ ፡ የላች
ሁም ፤ (የአላህን ፡ ቅጣት) ፡ አት
ፈሩምን ? አላቸው ።
66 ከሕዝቦቹ ፡ እነዚያ ፡ የካዱት ፡
መሪዎች ፡— እኛ ፡ በሞኝነት ፡
ላይ ፡ ኾነህ ፡ በእርግጥ ፡ እናይሃ
ለን ፤ እኛም ፡ ከውሸተኞቹ ፡ ነህ ፡
ብለን ፡ እንጠረጥርሃለን፡ አሉት ።
67 (እርሱም) ፡ አላቸው ፡— ወገኖቼ ፡
ሆይ ! እኔ ፡ ሞኝነት ፡ የለብኝም ፤
ግን ፡ እኔ ፡ ከዓለማት ፡ ጌታ ፡ የተ
ላክሁ ፡ ነኝ ፤
68 የጌታዬን ፡ መልክቶች ፡ አደርስላ
ችኋለሁ ፤ እኔም ፡ ለናንተ ፡ ታማኝ
መካሪ ፡ ነኝ ፤
69 ከጌታችሁ ፡ የኾነ ፡ ግሣጼ ፡ ከናን
ተው ፡ ውስጥ ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡
ላይ ፡ ያስጠነቅቃችሁ ፡ ዘንድ ፡
ቢመጣባችሁ ፡ ትደነቃላችሁን ?
ከኑሕም ፡ ሕዝቦች ፡ በኋላ ፡ ምት
ኮች ፡ ባደረጋችሁና ፡ በፍጥረ
ትም ፡ ግዙፍነትን ፡ በጨመረላ
ችሁ ፡ ጊዜ ፡ አስታውሱ ፤ የሻችሁ
ትንም ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ፡ የአላህን ፡
ጸጋዎች ፡ አስታውሱ ።
70 ፡- አላህን ፡ አንድ ፡ ብቻውን ፡ እን
ድንግገዛ ፡ አባቶቻችንም ፡ ይግገ
ዙት ፡ የነበረውን ፡ (አማልክት) ፡
እንድንተው ፡ መጣህብን ? ከው
ነተኞች ፡ ከኾንክ ፡ የምታስፈራ
ራብንን ፡ (ቅጣት) ፡ አምጣብን ፡
አሉ ።
71 ፡—ከጌታችሁ ፡ የኾነ ፡ ቅጣትና ፡
ቁጣ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ በውነት ፡
ተረጋገጠ ፤ እናንተና ፡ አባቶቻ
ችሁ ፡ (አማልክት ፡ ብላችሁ) ፡
በጠራችኋቸው ፡ ስሞች ፡ አላህ ፡
በርሷ ፡ ምንም ፡ ማስረጃ ፡ ያላወረ
ደባት ፡ ስትኾን ፡ ትከራከሩኛላች
ሁን ? ተጠባበቁም ፡ እኔ ፡ ከናንተ፡
ጋር ፡ ከተጠባባቂዎቹ ፡ ነኝና ፡
አለ ።
72 እርሱንና ፡ እነዚያንም ፡ አብረ
ውት ፡ የነበሩትን ፡ ከኛ ፡ በኾ
ነው ፡ ችሮታ ፡ (ከቅጣት) ፡ አዳን
ናቸው ፤ የነዚያንም ፡ በተአምራ
ታችን ፡ ያስተባበሉትንና ፡ አማ
ኞች ፡ ያልነበሩትን ፡ መሠረት ፡
ቆረጥን ።
73 ወደ ፡ ሠሙድም ፡ ወንድማቸ
ውን ፡ ሷሊህን ፡ ላክን ፤ አላቸው ፡
—ወገኖቼ ፡ ሆይ ! አላህን ፡ ተገዙ፤
ከርሱ ፡ ሌላ ፡ ለናንተ ፡ ምንም ፡
አምላክ ፡ የላችሁም ፤ (እውነተኛ ፡
ለመኾኔ) ፡ ከጌታችሁ ፡ የኾነች ፡
ምልክት ፡ በእርግጥ ፡ መጥታላች
ኋለች ፤ ይህች ፡ ለናንተ ፡ ታምር ፡
ስትኾን ፡ የአላህ ፡ ግመል ፡ ናትና ፡
ተውዋት ፤ በአላህ ፡ ምድር ፡ ውስ
ጥ ፡ ትብላ ፤ (ትጠጣም) ፤ በክፉ ፡
አትንኳትም ፤ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡
ይይዛችኋልና ።
74 ከዓድም ፡ በኋላ ፡ ምትኮች ፡ ባደረ
ጋችሁና ፡ በምድሪቱም ፡ ላይ ፡
ባስቀመጣችሁ ፡ ጊዜ ፡ አስታ
ውሱ ፤ ከሜዳዎቿ ፡ (ሸክላ) ፡ ሕን
ጻዎችን ፡ ትገነባላችሁ ፤ ከተራራ
ዎችም ፡ ቤቶችን ፡ ትጠርባላችሁ ፤
ስለዚህ ፡ የአላህን ፡ ጸጋዎች ፡
አስታውሱ ፤ በምድርም ፡ ውስጥ ፡
አጥፊዎች ፡ ኾናችሁ ፡ አታበ
ላሹ ።
75 ከወገኖቹ ፡ እነዚያ ፡ የኮሩት ፡
መሪዎች ፡ ለነዚያ ፡ ለተሸነፉት ፡
ከነሱ ፡ ላመኑት ፡—ሷሊህ ፡ ከጌ
ታው ፡ መላኩን ፡ ታውቃላች
ሁን ? አሏቸው ፤ (አዎን) ፡—እኛ ፡
እርሱ ፡ በተላከበት ፡ ነገር ፡ አማ
ኞች ፡ ነን ፡ አሉ ።
76 እነዚያ ፡ የኮሩት ፡— እኛ ፡ በዚያ ፡
እናንተ ፡ በርሱ ፡ ባመናችሁበት ፡
ከሓዲዎች ፡ ነን ፡ አሉ ።
77 ወዲያውም ፡ ግመሊቱን ፡ ወጓት ፤
ከጌታቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ወጡ ፤
አሉም ፡— ሷሊህ ፡ ሆይ ! ከመል
ክተኞቹ ፡ እንደኾንክ ፡ የምታስ
ፈራራብንን ፡ (ቅጣት) ፡ አምጣ
ብን ።
78 ወዲያውም ፡ የምድር ፡ መንቀጥ
ቀጥ ፡ (ጩኸትም) ፡ ያዘቻቸው ፤
በቤቶቻቸውም ፡ ውስጥ ፡ ተንከፍ
ርረው ፡ አነጉ ።
79 (ሷሊህ) ፡ ከነርሱም ፡ ዞረ ፤ አለም ፡
—ወገኖቼ ፡ ሆይ ! የጌታየን ፡
መልክት ፡ በእርግጥ ፡ አደረስኩ
ላችሁ ፤ ለናንተም ፡ መከርኳችሁ ፤
ግን ፡ መካሪዎችን ፡ አትወዱም ።
80 ሉጥንም ፡ ለሕዝቦቹ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ) ፤ አስቀያሚን ፡ ሥራ፡
ትሠራላችሁን ? በርሷ ፡ ከዓለማት፡
አንድም ፡ አልቀደማችሁም ።
81 እናንተ ፡ ከሴቶች ፡ ሌላ ፡ ወንዶ
ችን ፡ በመከጀል ፡ በእርግጥ ፡
ትመጡባቸዋላችሁ ፤ በውነቱ ፡
እናንተ ፡ ወሰንን ፡ አላፊዎች ፡
ሕዝቦች ፡ ናችሁ ።
82 የሕዝቦቹም ፡ መልስ ፡ (ሉጥንና ፡
ተከታዮቹን) ፡ ከከተማችሁ ፡
አውጧቸው ፡ እነሱ ፡ የሚጥራሩ ፡
ሰዎች ፡ ናቸውና ፡ ማለት ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አልነበረም ።
83 እርሱንና ፡ ቤተሰቦቹንም ፡ አዳንና
ቸው ፡ ሚስቱ ፡ ብቻ ፡ ስትቀር ፡ እ
ርሷ ፡ (ለጥፋት)፡ ከቀሩት ፡ ኾነች ።
84 በነሱም ፡ ላይ ፡ (የእሳት) ፡ ዝና
ምን ፡ አዘነምንባቸው ፤ የኃጢአ
ተኞችም ፡ መጨረሻ ፡ እንዴት ፡
እንደ ፡ ነበረ ፡ ተመልከት ።
85 ወደ ፡ መድየንም ፡ (ምድያን) ፡
ወንድማቸውን ፡ ሹዓይብን ፡ (ላ
ክን) ፤ አላቸው ፡— ወገኖቼ ፡
ሆይ ! አላህን ፡ ተገዙ ፤ ከርሱ ፡
በቀር ፡ ምንም ፡ አምላክ ፡ የላች
ሁም ፤ ከጌታችሁ ፡ ዘንድ ፡ ግልጽ፡
ማስረጃ ፡ በእርግጥ ፡ መጥታላች
ኋለች ፤ ስፍርንና ፡ ሚዛንን ፡
ምሉ ፤ ሰዎችንም ፡ አንዳቾቻቸ
ውን ፡ (ገንዘቦቻቸውን) ፡ አታጉድ
ሉባቸው ፤ በምድርም ፡ ውስጥ ፡
ከተበጀች ፡ በኋላ ፡ አታበላሹ ፤
ይሃችሁ ፡ ምእምናን ፡ እንደኾና
ችሁ ፡ ለናንተ ፡ የተሻለ ፡ ነው ።
86 (ሰዎችን) ፡ የምታስፈራሩና ፡
ከአላህም ፡ መንገድ ፡ በርሱ ፡
ያመኑትን ፡ የምታግዱ ፡ መጥመ
ሟንም ፡ የምትፈልጉዋት ፡ ኾና
ችሁ ፡ በየመንገዱ ፡ አትቀመጡ ፤
ጥቂቶችም ፡ በነበራችሁና ፡ ባበዛ
ችሁ ፡ ጊዜ ፡ አስታውሱ ፤ የአጥፊ
ዎችም ፡ መጨረሻ ፡ እንዴት ፡
እንደ ፡ ነበረ ፡ ተመልከቱ ፤
87 ከናንተም ፡ በዚያ ፡ እኔ ፡ በርሱ ፡
በተላከሁበት ፡ ያመኑ ፡ ጭፍሮ
ችና ፡ ያላመኑ ፡ ጭፍሮችም ፡
ቢኖሩ ፡ በመካከላችን ፡ አላህ ፡
እስከሚፈርድ ፡ ታገሡ ፤ እርሱም፡
ከፈራጆች ፡ ሁሉ ፡ በላጭ ፡ ነው ።

* * *

88 ከሕዝቦቹ ፡ እነዚያ ፡ የኮሩት ፡
መሪዎች ፡— ሹዓይብ ፡ ሆይ !
አንተንና ፡ እነዚያን ፡ ካንተ ፡
ጋር ፡ ያመኑትን ፡ ከከተማችን ፡

በእርግጥ ፡ እናወጣችኋለን ፤ ወ
ይም ፡ ወደ ፡ ሃይማኖታችን ፡
መመለስ ፡ አለባችሁ ፡ አሉ ፤ የጠ
ላንም ፡ ብንኾን ? አላቸው ።

89 አላህ ፡ ከርሷ ፡ ከአዳነን ፡ በኋላ ፡
ወደ ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ ብንመ
ለስ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡
ውሸትን ፡ ቀጠፍን ፤ አላህ ፡ ጌታ
ችን ፡ ካልሻም ፡ በስተቀር ፡ ለኛ ፡
ወደርሷ ፡ ልንመለስ ፡ አይገባንም ፤
ጌታችን ፡ ዕውቀቱ ፡ ሁሉን ፡
ነገር ፡ ሰፋ ፤ በአላህ ፡ ላይ ፡ ተጠ
ጋን ፤ ጌታችን ፡ ሆይ ! በኛና ፡
በወገኖቻችን ፡ መካከል ፡ በውነት ፡
ፍረድ ፤ አንተም ፡ ከፈራጆቹ ፡
ሁሉ ፡ በላጭ ፡ ነህ ፡ (አለ) ።

90 ከወገኖቹም ፡ እነዚያ ፡ የካዱት ፡
መሪዎች ፡ ሹዓይብን ፡ ብትከተሉ ፡
እናንተ ፡ ያንጊዜ ፡ ከሳሪዎች ፡
ናችሁ ፡ አሉ ።

91 ወዲያውም ፡ የምድር ፡ መንቀጥ
ቀጥ ፡ (ጩኸትም) ፡ ያዘቻቸው ፤
በከተማቸውም ፡ ውስጥ ፡ ተንከፍ
ርረው ፡ አነጉ ።

92 እነዚያ ፡ ሹዓይብን ፡ ያስተባበ
ሉት ፡ በርሷ ፡ እንዳልነበሩባት ፡
ኾኑ ፤ እነዚያ ፡ ሹዓይብን ፡ ያስተ
ባበሉት ፡ እነሱ ፡ ከሳሪዎች ፡
ኾኑ ።

93 ከነርሱም ፡ (ትቷቸው) ፡ ዞረ ፡—
ወገኖቼ ፡ ሆይ ! የጌታዬን ፡ መል
ክቶች ፡ በእርግጥ ፡ አደረስኩላ
ችሁ ፤ ለናንተም ፡ መከርኩ ፤
ታዲያ ፡ በከሓዲዎች ፡ ሰዎች ፡
ላይ ፡ እንዴት ፡ አዝናለሁ ?
አለም ።

94 በከተማ ፡ አንድንም ፡ ነቢይ ፡
አልላክንም ፡ ሰዎችዋን ፡ ይዋ
ደቁ ፡ ዘንድ ፡ በድህነትና ፡ በጉ
ዳት ፡ የያዝናቸው ፡ ብንኾን ፡
እንጂ ።

95 ከዚያም ፡ እስከበዙና ፡ አባቶቻ
ችንን ፡ ድህነትና ፡ በሺታ ፡ በእር
ግጥ ፡ ነክቷቸዋል ፡ (ይኸም ፡
የጊዜ ፡ ልማድ ፡ ነው) ፡ እስካሉ ፡
ድረስ ፡ በመጥፎው ፡ ስፍራ ፡
በጎውን ፡ ለወጥን ፤ ወዲያውም ፡
እነርሱ ፡ የማያውቁ ፡ ኾነው ፡ በድ
ንገት ፡ ያዝናቸው ።

96 የከተማዋም ፡ ሰዎች ፡ ባመኑና ፡
በተጠነቀቁ ፡ ኖሮ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
ከሰማይም ፡ ከምድርም ፡ በረከ
ቶችን ፡ በከፈትንላቸው ፡ ነበር ፤
ግን ፡ አስተባበሉ ፤ ይሠሩት ፡ በነ
በሩትም ፡ ኃጢአት ፡ ያዝናቸው ።

97 የከተማዋ ፡ ሰዎችም ፡ እነሱ ፡
የተኙ ፡ ኾነው ፡ ቅጣታችን ፡
ሌሊት ፡ ሊመጣባቸው ፡ አይፈ
ሩምን ?

98 የከተማዋ ፡ ሰዎችም ፡ እነሱ ፡
የሚጫወቱ ፡ ኾነው ፡ ሳሉ ፡ ቅጣ
ታችን ፡ ቀን ፡ በረፋድ ፡ ሊመጣባ
ቸው ፡ አይፈሩምን ?

99 የአላህንም ፡ ማዘናጋት ፡ (1) አይ
ፈሩምን ? የአላህንም ፡ ማዘናጋት ፡
ከከሳሪዎች ፡ ሕዝቦች ፡ በስተቀር ፡
የሚተማመን ፡ የለም ።

100 ለነዚያ ፡ ምድርን ፡ ከባለቤቶ
ችዋ ፡ (ጥፋት) ፡ በኋላ ፡ ለሚወር
ሱት ፡ ብንሻ ፡ ኖሮ ፡ በኃጢአቶቻ
ቸው ፡ የምንቀጣቸው ፡ መኾና
ችን ፡ አልተገለጸላቸውምን ? በል
ቦቻቸውም ፡ ላይ ፡ እናትማለን ፤
ስለዚህ ፡ እነርሱ ፡ አይሰሙም ።

101 እነዚህ ፡ ከተሞች ፡ (ከኑሕ ፡ እስከ ፡
ሹዓይብ ፡ ሰዎች ፡ የተነገሩት) ፡

1 አስመችቶ ፡ በድንገት ፡ መያዙን ።



ከወሬዎቻቸው ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡
እንተርካለን ፤ መልክተኞቻቸው
ም ፡ በግልጽ ፡ ታምራት ፡ በእር
ግጥ ፡ መጥተዋቸዋል ፤ ከመምጣ
ታቸው ፡ በፊት ፡ ባስተባበሉትም ፡
ነገር ፡ የሚያምኑ ፡ አልኾኑም ፤
እንደዚሁ ፡ አላህ ፡ በከሓዲያን ፡
ልቦች ፡ ላይ ፡ ያትማል ።

102 ለብዙዎቻቸውም ፡ በቃል ፡ ኪዳ
ናቸው ፡ መሙላትን ፡ አላገኘንም ፤
አብዛኞቻቸውንም ፡ በእርግጥ ፡
አመጠኞች ፡ ኾነው ፡ አገኘና
ቸው ።

103 ከዚያም ፡ ከበኋላቸው ፡ ሙሳን ፡
ወደ ፡ ፈርዖንና ፡ ወደ ፡ መማከር
ቶቹ ፡ በታአምራታችን ፡ ላክነው ፤
በርሷም ፡ ካዱ ፤ ያጥፊዎችም ፡
መጨረሻ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡
ነበረ ፡ ተመልከት ።

104 ሙሳም ፡ አለ ፡— ፈርዖን ፡ ሆይ !
እኔ ፡ ከዓለማት ፡ ጌታ ፡ የተላከሁ ፡
መልክተኛ ፡ ነኝ ፤

105 በአላህ ፡ ላይ ፡ ከእውነት ፡ በቀር ፡
አለመናገር ፡ ተገቢዬ ፡ ነው ፤
ከጌታችሁ ፡ በታምር ፡ በእርግጥ ፡
መጣኋችሁ ፤ የእስራኤልንም ፡
ልጆች ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ልቀቅ ።

106 (ፈርዖንም) ፡— በታምር ፡ የመ
ጣህ ፡ እንደኾንክ ፡ ከውነተኞቹ ፡
ከኾንክ ፡ እርሷን ፡ አምጣት ፡
አለው ።

107 በትሩንም ፡ ጣለ ፤ እርስዋም ፡
ወዲያውኑ ፡ ግልጽ ፡ እባብ ፡
ኾነች ።

108 እጁንም ፡ አወጣ ፤ እርሷም ፡ ወዲ
ያውኑ ፡ ለተመልካቾች ፡ ነጭ ፡
ኾነች ።

109 ከፈርዖን ፡ ሰዎች ፡ መማከር
ቶቹ ፡— ይህ ፡ በእርግጥ ፡ ዐዋቂ ፡
ድግመተኛ ፡ ነው ፡ አሉ ።

110 ከምድራችሁ ፡ ሊያወጣችሁ ፡
ይሻል ፡ (አሉ) ፤ ታዲያ ፡ ምን ፡
ታዛላችሁ ? (አለ) ።

111 (እነርሱም) ፡ አሉ ፡— እርሱንና ፡
ወንድሙን ፡ አቆይ ፤ ወደ ፡ ከተ
ሞቹም ፡ ሁሉ ፡ ሰብሳቢዎችን ፡
(ዘበኞች) ፡ ላክ ፤

112 ዐዋቂ ፡ ድግምተኛ ፡ የኾነን ፡
ሁሉ ፡ ያመጡልሃልና ።

113 ድግምተኞቹም ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡
መጡ ፤ እኛ ፡ አሸናፊዎች ፡ ብን
ኾን ፡ ለኛ ፡ በእርግጥ ፡ ዋጋ ፡
አለን ? አሉ ።

114 ፡—አዎን ፡ እናንተም ፡ በእርግጥ ፡
ከባለሟሎቹ ፡ ትኾናላችሁ ፡ አላ
ቸው ።

115 ሙሳ ፡ ሆይ ! (በትርህን) ፡ ወይም ፡
(በፊት) ፡ ትጥላለህ ፡ ወይም ፡
እኛ ፡ ጣዮች ፡ እንኾናለን ፡ አሉት ፤

116 ፡—ጣሉ ፡ አላቸው ፤ (ገመዶቻቸ
ውን) ፡ በጣሉም ፡ ጊዜ ፡ የሰዎ
ቹን ፡ ዓይኖች ፡ ደገሙባቸው ፤
አስፈራሩዋቸውም ፤ ትልቅ ፡ ድግ
ምትንም ፡ አመጡ ።

117 ወደ ፡ ሙሳም ፡— በትርህን ፡
ጣል ፡ ስንል ፡ ላክን ፤ (ጣላትም) ፡
ወዲያውኑም ፡ የሚቀጣጥፉትን ፡
(ማታለያ) ፡ ትውጣለች ።

118 እውነቱም ፡ ተገለጸ ፤ ይሠሩት ፡ የነ
በሩትም ፡ (ድግምት) ፡ ተበላሸ ።

119 እዚያ ፡ ዘንድ ፡ ተሸነፉም ፤ ወራ
ዶችም ፡ ኾነው ፡ ተመለሱ ።

120 ድግምተኞቹም ፡ ሰጋጆች ፡ ኾነው
ወደቁ ።

121 አሉ ፡— በዓለማት ፡ ጌታ ፡ አመ
ንን ፤
122 በሙሳና ፡ በሃሩን ፡ ጌታ ።
123 ፈርዖን ፡ አለ ፡— እኔ ፡ ለናንተ ፡
ሳልፈቅድላችሁ ፡ በፊት ፡ በርሱ ፡
አመናችሁን ? ይህ ፡ በከተማይቱ ፡
ውስጥ ፡ ሰዎቿን፡ ከርሷ ፡ ለማ
ውጣት ፡ በእርግጥ ፡ የተስማማች
ሁበት ፡ ተንኮል ፡ ነው ፤ ወደፊ
ትም ፡ (የሚደርስባችሁን) ፡ ታው
ቃላችሁ ፤
124 እጆቻችሁንና ፡ እግሮቻችሁን ፡
በማፈራረቅ ፡ በእርግጥ ፡ እቆራር
ጣለሁ ፤ ከዚያም ፡ ሁላችሁንም ፡
በእርግጥ ፡ እሰቅላችኋለሁ ።
125 አሉ ፡— እኛ ፡ ወደ ፡ ጌታችን ፡
ተመላሾች ፡ ነን ፤
126 የጌታችንም ፡ ታምራቶች ፡ በመ
ጡልን ፡ ጊዜ ፡ ከማመናችን ፡
በቀር ፡ ከኛ ፡ አትጠላም ፤ ጌታ
ችን ፡ ሆይ ! በኛ ፡ ላይ ፡ ትእግሥ
ትን ፡ አፍስስ ፤ ሙስሊሞች፡
ኾነን ፡ ግደለን ።
127 ከፈርዖንም ፡ ሰዎች ፡ ታላላቆቹ ፡
(ለፈርዖን) ፡— ሙሳንና ፡ ሰዎ
ቹን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንዲያበላ
ሹና ፡ (ሙሳም) ፡ አንተንና ፡ አማ
ልክቶችህን ፡ እንዲተው ፡ ትተዋ
ቸዋለህን ? አሉ ፤ ፡— ወንዶች ፡
ልጆቻቸውን ፡ እንገድላለን ፤ ሴቶ
ቻቸውንም ፡ እናስቀራለን ፤ እኛም
ከበላያቸው ፡ ነን ፤ አሸናፊዎች ፡
(ነን) ፡ አለ ።
128 ሙሳ ፡ ለሰዎቹ ፡— ለአላህ ፡
ተገዙ ፡ ታገሡም ፤ ምድር ፡ ለአ
ላህ ፡ ናትና ፤ ከባሮቹ ፡ ለሚሻው ፡
ያወርሳታል ፤ ምስጉንዋም ፡ ፍ
ጻሜ ፡ ለጥንቁቆቹ ፡ ናት ፡ አላ
ቸው ።
129 ፡—ከመምጣትህም ፡ በፊት ፡ ከመ
ጣኸልንም ፡ በኋላ ፡ ተሰቃየን፡
አሉት ፤ ጌታችሁ ፡ ጠላቶቻች
ሁን ፡ ሊያጠፋ ፡ እንዴት ፡ እንደ
ምትሠሩም ፡ ይመለከት ፡ ዘንድ ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ ሊተካችሁ ፡
ይሻል ፡ አላቸው ።
130 የፈርዖንንም ፡ ቤተሰቦች ፡ እንዲ
ገሠጹ ፡ በድርቅ ፡ ዓመታትና ፡
ከፍሬዎችም ፡ በመቀነስ ፡ በእር
ግጥ ፡ ያዝናቸው ።
131 ደጊቱም ፡ ነገር ፡ (ምቾት) ፡ በመ
ጣችላቸው ፡ ጊዜ ፡ ይህች ፡ ለኛ ፡
(ተገቢ) ፡ ናት ፡ ይላሉ ፤ ክፉትም ፡
ብታገኛቸው ፡ በሙሳና ፡ አብረ
ውት ፡ ባሉት ፡ ገደቢስነት ፡ ያመ
ካኛሉ ፤ ንቁ ፤ ገደቢስነታቸው ፡
አላህ ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ግን ፡
አብዛኞዎቻቸው ፡ አያውቁም ።
132 (ለሙሳም) ፡— በማንኛይቱም ፡
ታምር ፡ በርሷ ፡ ልትደግምብን ፡
ብትመጣብን ፡ እኛ ፡ ለአንተ ፡
የምናምንልህ ፡ አይደለንም ፡ አሉ፤
133 ወዲያውም ፡ የውሃን ፡ ማጥለቅ
ለቅ ፡ አንበጣንም ፡ ነቀዝንም ፡
እንቁራሪቶችንም ፡ ደምንም ፡
የተለያዩ ፡ ታምራት ፡ ሲኾኑ ፡
በነሱ ፡ ላይ ፡ ላክን ፤ ኮሩም ፤ ተን
ኮለኞችም ፡ ሕዝቦች ፡ ነበሩ ።
134 በነርሱም ፡ ላይ ፡ ቅጣቱ ፡ በወደ
ቀባቸው ፡ ጊዜ ፡— ሙሳ ፡ ሆይ !
ጌታህን ፡ ላንተ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
በገባልህ ፡ ነገር ፡ ለኛ ፡ ለምንልን ፤
ከኛ ፡ ቅጣቱን ፡ ብታነሳልን ፡ ለአ
ንተ ፡ በእርግጥ ፡ እናምንልሃለን ፤
የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ከአ



ንተ ፡ ጋር ፡ በእርግጥ ፡ እንለቃ
ለን ፤ አሉ ።
135 እነርሱም ፡ ደራሾቹ ፡ እኾኑበት ፡
ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ቅጣትን ፡ ከነሱ ፡
ላይ ፡ ባነሳን ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡
እነርሱ ፡ ቃላቸውን ፡ ያፈርሳሉ ።
136 እነርሱ ፡ በታምራታችን ፡ ስለአስ
ተባበሉም ፡ ከርሷ ፡ ዘንጊዎች ፡
ስለኾኑም ፤ ከነሱ ፡ ተበቀልን ፤
በባሕርም ፡ ውስጥ ፡ አሰጠምና
ቸው ።
137 እነዚያንም ፡ ደካሞች ፡ የነበሩ
ትን ፡ ሕዝቦች ፡ ያችን ፡ በውስጧ ፡
በረከት ፡ ያደረግንባትን ፡ ምድር ፡
ምሥራቆቿዋንም ፡ ምዕራቦቿንም
አወረስናቸው ፤ የጌታህም ፡ መል
ካሚቱ ፡ ቃል ፡ በእስራኤል ፡
ልጆች ፡ ላይ ፡ በመታገሣቸው ፡
ተፈጸመች ፤ ፈርዖንና ፡ ሰዎቹም ፡
ይሠሩት ፡ የነበረውን ፡ (ሕንጻ) ፡
ዳስ ፡ ያደርጉትም ፡ የነበረውን ፡
አፈረስን ።
138 የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ባሕ
ሩን ፡ አሻገርናቸው ፤ ለነርሱ ፡
በኾኑ ፡ ጣዖታት ፡ (መግገዛት) ፡
ላይ ፡ በሚዘወትሩ ፡ ሕዝቦች ፡
ላይ ፡ አለፉም ፤ ሙሳ ፡ ሆይ ፡—
ለነርሱ ፡ (ለሰዎቹ) ፡ አማልክት ፡
እንዳሏቸው ፡ ለኛም ፡ አምላክን ፡
አድርግልን ፡ አሉት ፤ እናንተ ፡
የምትሳሳቱ ፡ ሕዝቦች ፡ ናችሁ ፤
አላቸው ።
139 እነዚህ ፡ እነርሱ ፡ በውስጡ ፡ ያሉ
በት ፡ ነገር ፡ ጠፊ ፡ ነው ፡ ይሠ
ሩት ፡ የነበሩትም ፡ ብልሹ ፡ ነው ፡
(አላቸው) ፤
140 ከአላህ ፡ ሌላ ፡ እርሱ ፡ ከዓለማት ፡
ያበለጣችሁ ፡ ሲኾን ፡ (የምትግገ
ዙት) ፡ አምላክን ፡ እፈልግላችኋ
ለሁን ? አለ ።
141 ከፈርዖንም ፡ ቤተሰቦች ፡ ብር
ቱን ፡ ቅጣት ፡ የሚያቀምሱዋ
ችሁ ፡ ወንዶች ፡ ልጆቻችሁን ፡
የሚገድሉ ፡ ሴቶቻችሁንም ፡ የሚ
ተው ፡ ሲኾኑ ፡ ባዳንናችሁ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውሱ) ፤ በይኸችሁም ፡
ውስጥ ፡ ከጌታችሁ ፡ ዘንድ ፡
የኾነ ፡ ከባድ ፡ ፈተና ፡ አለበት ።
142 ሙሳንም ፡ ሠላሳን ፡ ሌሊት ፡
(ሊጾምና ፡ ልናነጋግረው) ፡ ቀጠር
ነው ፤ በዐሥርም ፡ (ሌሊት) ፡ ሞላ
ናት ፤ የጌታውም ፡ ቀጠሮ ፡ አርባ ፡
ሌሊት ፡ ሲኾን ፡ ተፈጸመ ፤ ሙ
ሳም ፡ ለወንድሙ ፡ ሃሩን ፡— በሕ
ዝቦቼ ፡ ላይ ፡ ተተካኝ ፤ አሳም
ርም ፡ የአጥፊዎችንም ፡ መንገድ ፡
አትከተል ፡ አለው ።
143 ሙሳም ፡ ለቀጠሯችን ፡ በመ
ጣና ፡ ጌታውም ፡ ባነጋገረው ፡
ጊዜ ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ! (ነፍስ
ህን) ፡ አሳየኝ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እመ
ለከታለሁና ፡ አለ ፤ (አላህም) ፡—
በፍጹም ፡ አታየኝም ፡ ግን ፡ ወደ ፡
ተራራው ፡ ተመልከት ፤ በስፍራ
ውም ፡ ቢረጋ ፡ በእርግጥ ፡ ታየኛ
ለህ ፡ አለው ፤ ጌታውም ፡ ለተራ
ራው ፡ በተገለጸ ፡ ጊዜ ፡ ንኩት
ኩት ፡ አደረገው ፤ ሙሳም ፡ ጮሆ ፡
ወደቀ ፤ በአንሰራራም ፡ ጊዜ ፡
ጥራት ፡ ይገባህ ፤ ወዳንተ ፡ ተመ
ለስኩ ፤ እኔም ፡ (በወቅቱ)፡ የም
እምናን ፡ መጀመሪያ ፡ ነኝ ፡ አለ ።
144 (አላህም) ፡ አለው ፡— ሙሳ ፡
ሆይ ! እኔ ፡ በመልክቶቼና ፡ በማ
ናገሬ ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ (1) መረጥ

1 በዘመንህ ፡ ካሉት ።

ኩህ ፤ የሰጠሁህንም ፡ ያዝ ፤ ከአ
መስጋኞቹም ፡ ኹን ።
145 ለርሱም ፡ በሰሌዳዎቹ ፡ ላይ ፡ ከነ
ገሩ ፡ ሁሉ ፡ ግሣጼንና ፡ ለነገሩም ፡
ሁሉ ፡ ማብራራትን ፡ ጻፍንለት ፤
(አልንም) ፦ በብርታትም ፡ ያዛት ፡
ሕዝቦችህንም ፡ በመልካሟ ፡ እ
ንዲይዙ ፡ እዘዛቸው ፤ የአመጠ
ኞቹን ፡ አገር ፡ በእርግጥ ፡ አሳያ
ችኋለሁ ።
146 እነዚያን ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ በምድር ፡
ላይ ፡ የሚኮሩትን ፡ ከአንቀጾቼ ፡
በእርግጥ፡ አዞራቸዋለሁ፤ ታምርን
ም፡ ሁሉ፡ ቢያዩ፥ በርሷ፡ አያምኑም፤
ቅንንም ፡ መንገድ ፡ ቢያዩ ፡ መን
ገድ ፡ አድርገው ፡ አይዙትም ፤
ግን ፡ የጥመትን ፡ መንገድ ፡ ቢያዩ
መንገድ ፡ አድርገው ፡ ይይዙ
ታል ፤ ይኽ ፡ እነርሱ ፡ በአንቀጾ
ቻችን ፡ ስለ ፡ አስተባበሉና ፡ ከር
ሷም ፡ ዘንጊዎች ፡ ስለኾኑ ፡ ነው ።
147 እነዚያም ፡ በአንቀጾቻችንና ፡
መጨረሻይቱን ፡ ዓለም ፡ በመገና
ኘት ፡ ያስተባበሉት ፡ ሥራዎቻ
ቸው ፡ ተበላሹ ፤ ይሠሩት ፡ የነበረ
ውን ፡ እንጂ ፡ ይመነዳሉን ?
148 የሙሳም ፡ ሕዝቦች ፡ ከርሱ ፡
(መኼድ) ፡ በኋላ ፡ ከጌጦቻቸው ፡
ወይፈንን ፡ አካልን ፡ ለርሱ ፡ ማግ
ሳት ፡ ያለውን ፡ (አምላክ ፡ አድ
ርገው) ፡ ያዙ ፤ እርሱ ፡ የማያናግራ
ቸው ፡ መንገድንም ፡ የማይመራ
ቸው ፡ መኾኑን ፡ አይመለከቱ
ምን ? (አምላክ ፡ አድርገው) ፡
ያዙት ፤ በዳዮችም ፡ ኾኑ ።
149 በተጸጸቱና ፡ እነሱም ፡ በእርግጥ ፡
የተሳሳቱ ፡ መኾናቸውን ፡ ባዩ ፡
ጊዜ ፦ ጌታችን ፡ ባያዝንልንና ፡
ባይምረን ፡ በእርግጥ ፡ ከከሳሪ
ዎቹ ፡ እንኾናለን ፡ አሉ ።
150 ሙሳም ፡ እየተቆጣና ፡ እያዘነ ፡
ወደ ፡ ሕዝቦቹ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡
-ከኔ፡ በኋላ፡ በኔ፡ ላይ፡ የተካችሁት፡
ነገር ፡ ከፋ ! የጌታችሁን ፡ ትእ
ዛዝ ፡ ተቻኮላችሁን ? አላቸው ፤
ሰሌዳዎቹንም ፡ ጣላቸው ፤ የወን
ድሙንም ፡ ራስ ፡ (ጸጉር) ፡ ወደ
ርሱ ፡ የሚጐትተው ፡ ሲኾን ፡
ያዘ ፤ (ወንድሙም) ፦ የናቴ ፡
ልጅ ፡ ሆይ ! ሕዝቦቹ ፡ ናቁኝ ፤
ሊገድሉኝም ፡ ተቃረቡ ፤ ስለዚህ ፡
በኔ ፡ ጠላቶችን ፡ አታስደስትብኝ ፤
ከአመጠኞች ፡ ሕዝቦችም ፡ ጋር ፡
አታድርገኝ ፡ አለው ።
151 (ሙሳም) ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ! ለእ
ኔም ፡ ለወንድሜም ፡ማር ፤ በእዝ
ነትህም ፡ ውስጥ ፡ አግባን ፤ አን
ተም ፡ ከአዛኞች ፡ ሁሉ ፡ ይበ
ልጥ ፡ አዛኝ ፡ ነህ ፡ አለ ።
152 እነዚያ ፡ ወይፈኑን ፡ (አምላክ ፡
አድርገው) ፡ የያዙ ፡ ከጌታቸው ፡
ዘንድ ፡ ቁጣ ፤ በቅርቢቱም ፡ ሕይ
ወት ፡ ውርደት ፡ በእርግጥ ፡ ያገኛ
ቸዋል ፤ እንዲሁም ፡ ቀጣፊዎ
ችን ፡ እንቀጣለን ።
153 እነዚያም ፡ ኃጢአቶችን ፡ የሠሩ ፡
ከዚያም ፡ ከርሷ ፡ በኋላ ፡ የተጸ
ጸቱ ፡ ያመኑም ፡ ጌታህ ፡ ከርሷ ፡
በኋላ ፡ በእርግጥ ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡
ነው ።
154 ከሙሳም ፡ ቁጣው ፡ በበረደ ፡ ጊዜ፡
ሰሌዳዎቹን ፡ በግልባጫቸው ፡
ውስጥ ፡ ለነዚያ ፡ እነርሱ ፡ ጌታቸ
ውን ፡ የሚፈሩ ፡ ለኾኑት ፡ መምሪ
ያና ፡ እዝነት ፡ ያለባቸው ፡ ሲኾኑ ፡
ያዘ ።



155 ሙሳም ፡ ከሕዝቦቹ ፡ ውስጥ ፡ ለቀ
ጠሮዋችን ፡ ሰባን ፡ ሰዎች ፡ መረ
ጠ ፤ ብርቱ ፡ የምድር ፡ እንቅጥ
ቃጤ ፡ በያዘቻቸውም ፡ ጊዜ ፡
ሙሳ ፡ አለ ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ !
በሻህ ፡ ኖሮ ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡
በአጠፋሃቸው ፡ ነበር ፤ እኔንም ፡
(ባጠፋኸኝ ፡ ነበር) ፤ ከኛ ፡ ቂሎቹ፡
በሠሩት ፡ ነገር ፡ ታጠፋናለህን ?
እርሷ ፡ (ፈተናይቱ) ፡ ያንተ ፡ ፈተ
ና ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለችም ፤
በርሷ ፡ የምትሻውን ፡ ታሳስታ
ለህ ፤ የምትሻውንም ፡ ታቀናለህ ፤
አንተ ፡ ረዳታችን ፡ ነህና ፡ ለኛ ፡
ምሕረት ፡ አድርግልን ፤ እዘንል
ንም ፤ አንተም ፡ ከመሓሪዎች ፡
ሁሉ ፡ በላጭ ፡ ነህ ።
156 ለኛም ፡ በዚች ፡ በቅርቢቱ ፡
ዓለም ፡ መልካሚን ፡ በመጨረሻ
ይቱም ፡ (መልካሚን) ፡ ጻፍልን ፤
እኛ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ተመለስን ፤
(ሲል ፡ ሙሳ ፡ ጸለየ ፤ አላህም) ፡
አለ ፦ ቅጣቴ ፡ በርሱ ፡ የምሻ
ውን ፡ ሰው ፡ እቀጣበታለሁ ፤
ችሮታየም ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ሰፋች፤
ለነዚያም ፡ ለሚጠነቀቁ ፡ ዘካ
ንም ፡ ለሚሰጡ ፡ ለነዚያም ፡
እነሱ ፡ በአንቀጾቻችን ፡ ለሚያ
ምኑ ፡ በእርግጥ ፡ እጽፋታለሁ ።
157 ለነዚያ ፡ ያንን ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡
በተውራትና ፡ በኢንጂል ፡ ተጽፎ፡
የሚያገኙትን ፡ የማይጽፍና ፡ የማ
ያነብ ፡ ነቢይ ፡ የኾነውን ፡ መልክ
ተኛ ፡ የሚከተሉ ፡ ለኾኑት ፡ (በእ
ርግጥ ፡ እጽፋታለሁ) ፤ በበጎ ፡
ሥራ ፡ ያዛቸዋል ፤ ከክፉም ፡
ነገር ፡ ይከለክላቸዋል ፤ መልካም ፡
ነገሮችንም ፡ ለነርሱ ፡ ይፈቅድላ
ቸዋል ፤ መጥፎ ፡ ነገሮችንም ፡
በነሱ ፡ ላይ ፡ እርም ፡ ያደርግባቸ
ዋል ። ከነሱም ፡ ላይ ፡ ሸክማቸው
ንና ፡ እነዚያንም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
የነበሩትን ፡ እንዛዝላዎች ፡ (ከባድ
ሕግጋቶች) ፡ ያነሳላቸዋል ፤ እነዚ
ያም ፡ በርሱ ፡ ያመኑ ፡ ያከበሩ
ትም ፡ የረዱትም ፡ ያንንም ፡ ከርሱ
ጋር ፡ የተወረደውን ፡ ብርሃን ፡
የተከተሉ ፡ እነዚያ ፡ እነሱ ፡ የሚ
ድኑ ፡ ናቸው ።
158 (ሙሐመድ ፡ ሆይ !) በላቸው ፦
እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! እኔ ፡ ወደ
ናንተ ፡ ወደሁላችሁም ፡ የአላህ ፡
መልክተኛ ፡ ነኝ ፤ (እርሱም) ፡
ያ ፡ የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ንግ
ሥና ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡ የኾነ ፡ ነው ፤
እርሱ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡
የለም ፤ ሕያው ፡ ያደርጋል ፤ ይገድ
ላልም ፤ በአላህ ፡ በዚያም ፡ በአላ
ህና ፡ በቃላቶቹ ፡ በሚያምነው ፡
የማይጽፍ ፡ የማያነብ ፡ ነቢይ ፡
በኾነው ፡ መልክተኛው ፡ እመኑ ፤
ቅንንም ፡ መንገድ ፡ ትመሩ ፡
ዘንድ ፡ ተከተሉት ።
159 ከሙሳም ፡ ሕዝቦች ፡ በውነት ፡
የሚመሩና ፡ በርሱም ፡ (ፍርድን) ፡
የሚያስተካክሉ ፡ ጭፍሮች ፡ አ
ሉ ።
160 ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ነገዶች ፡ ሕዝ
ቦች ፡ አድርገንም ፡ ከፋፈልና
ቸው ፤ ወደ ፡ ሙሳም ፡ ወገኖቹ ፡
መጠጣትን ፡ በፈለጉበት ፡ ጊዜ ፡
ደንጊያውን ፡ በበትርህ ፡ ምታው ፡
ስንል ፡ ላክን ፤ (መታውም) ፡
ከርሱ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ምንጮ
ችም ፡ ፈለቁ ፤ ሰዎቹ ፡ ሁሉ ፡
መጠጫቸውን ፡ በእርግጥ ፡ ዐወቁ፤
በነሱም ፡ ላይ ፡ ደመናን ፡ አጠለ
ልን ፤ በነሱም ፡ ላይ ፡ መናንና ፡

ድርጭትን ፡ አወረድን ፤ ከሰጠና
ችሁም ፡ መልካም ፡ ሲሳይ ፡ ብሉ ፡
(አልን ፤ ጸጋችንን ፡ በመካዳቸው)፡
አልበደሉንምም ፤ ግን ፡ ነፍሶቻቸ
ውን ፡ የሚበድሉ ፡ ነበሩ ።
161 ለነርሱም ፡ በተባሉ ፡ ጊዜ ፡ (አስ
ታውስ) ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ተቀ
መጡ ፤ ከርሷም ፡ በሻችሁት ፡
ስፍራ ፡ ብሉ ፤ (የምንፈልገው) ፡
የኃጢአታችንን ፡ መርገፍ ፡ ነው ፡
በሉም ፤ የከተማይቱንም ፡ በር ፡
አጎንብሳችሁ ፡ ግቡ ፤ ኃጢአቶቻ
ችሁን ፡ ለእናንተ ፡ እንምራለንና ፤
በጎ ፡ ለሠሩት ፡ በእርግጥ ፡ እን
ጨምራለን ።
162 ከነሱም ፡ ውስጥ ፡ እነዚያ ፡ (ራሳ
ቸውን) ፡ የበደሉት ፡ ሰዎች ፡
ከዚያ ፡ ለነርሱ ፡ ከተባለው ፡ ሌላ ፡
የኾነን ፡ ቃል ፡ ለወጡ ፤ በነርሱም
ላይ ፡ ይበድሉ ፡ በነበሩት ፡ በደል ፡
መዐትን ፡ ከሰማይ ፡ ላክንባቸው ።
163 ከዚያችም ፡ በባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ከነ
በረችው ፡ ከተማ ፡ በቅዳሜ ፡
(ቀን) ፡ ወሰን ፡ ባለፉ ፡ ጊዜ ፡
በሰንበታቸው ፡ ቀን ፡ ዐሣዎቻ
ቸው ፡ የተከማቹ ፡ ኾነው ፡ በሚ
መጡላቸው ፡ ጊዜ ፡ (የኾነውን) ፡
ጠይቃቸው ፤ ሰንበትንም ፡ በማያ
ከብሩበት ፡ (በሌላው) ፡ ቀን ፡ አይ
መጡላቸውም ፤ እንደዚሁ ፡ ያም
ጡበት ፡ በነበሩት ፡ ምክንያት ፡
እንሞክራቸዋለን ።
164 ከነሱም ፡ (ከፊሎቹ) ፡ ሕዝቦች ፡—
አላህ ፡ አጥፊያቸው ፡ ወይም ፡
በብርቱ ፡ ቅጣት ፡ ቀጪአቸው ፡
የኾኑትን ፡ ሕዝቦች ፡ ለምን ፡ ትገ
ሥጻላችሁ ? ባሉ ፡ ጊዜ ፡ (ገሳ
ጮቹ) ፡— ወደ ፡ ጌታችሁ ፡ በቂ ፡
ምክንያት ፡ እንዲኾንና ፡ እነር
ሱም ፡ ቢከለከሉ ፡ ብለን ፡ ነው ፡
አሉ ።
165 በርሱም ፡ የተገሠጹበትን ፡ ነገር ፡
በተው ፡ ጊዜ ፡ እነዚያን ፡ ከከፉ ፡
የሚከለክሉትን ፡ አዳን ፤ እነዚ
ያንም ፡ የበደሉትን ፡ ያምጡ ፡ በነ
በሩት ፡ ምክንያት ፡ በብርቱ ፡
ቅጣት ፡ ያዝናቸው ።
166 ከርሱም ፡ ከተከለከሉት ፡ ነገር ፡
በኰሩ ፡ ጊዜ ፡ ለነሱ ፡ ወራዶች ፡
ዝንጀሮዎች ፡ ኹኑ ፡ አልን ፤
(ኾኑም) ።
167 ጌታህም ፡ እስከ ፡ ትንሣኤ ፡ ቀን ፡
ክፉ ፡ ቅጣትን ፡ የሚያቀምሳቸ
ውን ፡ ሰው ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ በእር
ግጥ ፡ የሚልክ ፡ መኾኑን ፡ ባስታ
ወቀ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውሳቸው) ፤
ጌታህ ፡ በእርግጥ ፡ ቅጣተ ፡ ፈጣን፡
ነው ፤ እርሱም ፡ በእርግጥ ፡
እጅግ ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።
168 (የእስራኤልን ፡ ልጆች) ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ የተለያዩ ፡ ሕዝቦች ፡
አድርገንም ፡ ከፋፈልናቸው ፤
ከነሱ ፡ መልካሞች ፡ አሉ ፤
ከነሱም ፡ ከዚያ ፡ ሌላ ፡ አሉ ፤
ይመለሱ ፡ ዘንድም ፡ በተድላዎ
ችም ፡ በመከራዎችም ፡ሞከርና
ቸው ።
169 ከኋላቸውም ፡— መጽሐፉን ፡
የወረሱ ፡ መጥፎ ፡ ምትኮች ፡
ተተኩ ፤ የዚህን ፡ የቅርቡን ፡
ጠፊ ፡ ጥቅም ፡ ይይዛሉ ፤ ብጤ
ውም ፡ ጥቅም ፡ ቢመጣላቸው ፡
የሚይዙት ፡ ሲኾኑ ፡ (በሠራ
ነው) ፡— ለኛ ፡ ምሕረት ፡ ይደረ
ግልናል ፡ ይላሉ ፤ በአላህ ፡ ላይ ፡
ከውነት ፡ በቀር ፡ እንዳይናገሩ ፡
በነርሱ ፡ ላይ ፡ የመጽሐፉ ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ አልተያዘባቸውምን ? በ



ርሱ ፡ ውስጥ ፡ ያለውንም ፡ አላነ
በቡምን ? የመጨረሻይቱም ፡
አገር ፡ ለነዚያ ፡ ጌታቸውን ፡ ለሚ
ፈሩት ፡ በላጭ ፡ ናት ፤ አታውቁ
ምን ?
170 እነዚያም ፡ መጽሐፉን ፡ ጠብ
ቀው ፡ የሚይዙ ፡ ሦላትንም ፡
በደንቡ ፡ የሰገዱ ፡ እኛ ፡ የመል
ካም ፡ ሠሪዎችን ፡ ዋጋ ፡ አናጠ
ፋም ።
171 የጡርን ፡ ተራራ ፡ ነቅለን ፡ ከበላ
ያቸው ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ኾኖ ፡ በአነ
ሳነውና ፡ እርሱም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
ወዳቂ ፡ መኾኑን ፡ ባረጋገጡ ፡
ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፤ የሰጠናች
ሁን ፡ በብርታት ፡ ያዙ ፤ ትጠነ
ቀቁም ፡ ዘንድ ፡ በውስጡ ፡ ያለ
ውን ፡ ተገንዘቡ ፡ (አልን) ።
172 ጌታህም ፡ ከአደም ፡ ልጆች ፡ ከጀ
ርባቻቸው ፡ ዘሮቻቸውን ፡ ባወ
ጣና ፡ ጌታችሁ ፡ አይደለሁምን ?
ሲል ፡ በነፍሶቻቸው ፡ ላይ ፡ ባስ
መሰከራቸው ፡ ጊዜ ፡ (የኾነውን ፡
አስታውስ) ፤ ጌታችን ፡ ነህ ፡ መሰ
ከርን ፡ አሉ ፤ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡
ከዚህ ፡ (ኪዳን) ፡ ዘንጊዎች ፡ ነበ
ርን ፡ እንዳትሉ ፤
173 ወይም ፤ (ጣዖታትን) ፡ ያጋሩት ፡
ከኛ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ አባቶ
ቻችን ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፤ እኛም ፡
ከነሱ ፡ በኋላ ፡ የኾን ፡ ዘሮች ፡ ነበ
ርን ፤ አጥፊዎቹ ፡ በሠሩት ፡ ታጠ
ፋናለህን ? እንዳትሉ ፤ (አስመሰ
ከርናችሁ) ።
174 እንደዚሁም ፡ (እንዲያስቡ) ፡ እን
ዲመለሱም ፡ አንቀጾችን ፡ እናብ
ራራለን ።
175 የዚያንም ፡ ታምራታችንን ፡ የሰ
ጠነውንና ፡ ከርሷ ፡ የወጣውን ፡
ሰይጣንም ፡ ያስከተለውን ፡ ከጠ
ማሞቹም ፡ የኾነውን ፡ ሰው ፡
ወሬ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ አንብብ
ላቸው ።
176 በሻንም ፡ ኖሮ ፡ በርሷ ፡ ከፍ ፡ ባደ
ረግነው ፡ ነበር ፤ እርሱ ፡ ግን ፡
ወደ ፡ ምድር ፡ ተዘነበለ ፤ ፍላጐ
ቱንም ፡ ተከተለ ፤ ብጤውም ፡
ብታባርረው ፡ ምላሱን ፡ አው
ጥቶ ፡ የሚያለኽልህ ፡ ወይም ፡
ብትተወው ፡ ምላሱን ፡ አውጥቶ ፡
የሚያለኽልህ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡
ውሻ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ የነዚያ ፡ በአ
ንቀጾቻችን ፡ ያስተባበሉት ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፤ ያስተነት
ኑም ፡ ዘንድ ፡ ታሪኮችን ፡ ተርክ
ላቸው ።
177 የነዚያ ፡ በአንቀጾቻችን ፡ ያስተባ
በሉትና ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ ይበ
ድሉ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ምሳሌ ፡
ከፋ !
178 አላህ ፡ የሚያቀናው ፡ ሰው ፡ ቅን ፡
እርሱ ፡ ነው ፤ የሚያጠመውም ፡
ሰው ፡ እነዚያ ፡ ከሳሪዎቹ ፡ እነሱ ፡
ናቸው ።
179 ከጋኔንም ፡ ከሰዎችም ፡ ብዙዎ
ችን ፡ ለገሀነም ፡ በእርግጥ ፡ ፈጠ
ርን ፤ ለነርሱ ፡ በርሳቸው ፡ የማያ
ውቁባቸው ፡ ልቦች ፡ አሏቸው ፤
ለነሱም ፡ በሳቸው ፡ የማያዩባ
ቸው ፡ ዓይኖች ፡ አሉዋቸው ፤
ለነሱም ፡ በሳቸው ፡ የማይሰሙ
ባቸው ፡ ጆሮዎች ፡ አሉዋቸው ፤
እነዚያ ፡ እንደ ፡ እንስሳዎች ፡
ናቸው ፤ ይልቁንም ፡ እነርሱ ፡
በጣም ፡ የተሳሳቱ ፡ ናቸው ፤ እነ
ዚያ ፡ ዘንጊዎቹ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው፤
180 ለአላህም ፡ መልካም ፡ ስሞች ፡
አሉት ፤ (ስትጸልዩ) ፡ በርሷም፡

ጥሩት ፤ እነዚያንም ፡ ስሞቹን ፡
የሚያጣምሙትን ፡ ተውዋቸው ፤
ይሠሩት ፡ የነበሩትን ፡ ነገር ፡ በእ
ርግጥ ፡ ይመነዳሉ ።

181 ከፈጠርናቸውም ፡ ሰዎች ፡ በው
ነት ፡ የሚመሩ ፡ በርሱም ፡ (ፍር
ድን) ፡ የሚያስተካክሉ ፡ ሕዝ
ቦች ፡ አሉ ፤

182 እነዚያንም ፡ በአንቀጾቻችን ፡
ያስተባበሉትን ፡ ከማያውቁት ፡
ስፍራ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ (ምቾትን ፡
በመጨመር) ፡ እናዘነጋቸዋለን ።

183 ለነርሱም ፡ ጊዜ ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡
ጥበቤ ፡ ብርቱ ፡ ነውና ።

184 በነቢያቸው ፡ (በሙሐመድ) ፡
ምንም ፡ ዕብደት ፡ የሌለበት ፡
መኾኑን ፡ አያስተውሉምን ? እ
ርሱ፡ ግልጽ፡ አስጠንቃቂ፡ እንጅ፡
ሌላ ፡ አይደለም ።

185 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ግዛት ፡
ውስጥ ፡ ከማንኛው ፡ ነገር ፡ አላህ ፡
በፈጠረውም ፡ ሁሉ ፡ የሞት ፡ ጊዜ
ያቸውም ፡ በእርግጥ ፡ መቅረቡ ፡
የሚፈራ ፡ መኾኑን ፡ አያስተውሉ
ምን ? ከርሱም ፡ (ከቁርአን) ፡
ወዲያ ፡ በየትኛው ፡ ንግግር ፡ ያም
ናሉ ።

186 አላህ ፡ የሚያጠመው ፡ ሰው ፡ ለር
ሱ ፡ ምንም ፡ አቅኝ ፡ የለውም ፤
በጥመታቸውም ፡ ውስጥ ፡ እየዋ
ለሉ ፡ ይተዋቸዋል ።

187 ከሰዓቲቱ ፡ መቼ ፡ እንደምትረጋ ፡
(እንደምትመጣ) ፡ ይጠይቁሃል ፤
ዕውቀቷ ፡ በጌታዬ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤
በጊዜዋ ፡ እርሱ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡
አይገልጣትም ፤ በሰማያትና ፡
በምድርም ፡ ከበደች ፤ በድንገት ፡
ቢኾን ፡ እንጂ ፡ አትመጣችሁም ፡
በላቸው ፤ ከርሷ ፡ አጥብቀህ ፡
እንደ ፡ ተረዳህ ፡ አድርገው ፡
ይጠይቁሃል ፤ ዕውቀቷ ፡ አላህ ፡
ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ግን ፡ አብዛ
ኞዎቹ ፡ ሰዎች ፡ አያውቁም ፤
በላቸው ።

188 አላህ፡ የሻውን፡ በስተቀር፡ ለራሴ፡
ጥቅምንም፥ ጉዳትንም፥ ማም
ጣት፡ አልችልም፥ ሩቅንም፡ (ምስ
ጢር) ፡ የማውቅ ፡ በነበርኩ ፡
ኖሮ ፡ ከመልካም ፡ ነገር ፡ ባበዛ
ሁና ፡ ክፉም ፡ ነገር ፡ ባልነካኝ ፡
ነበር ፤ እኔ ፡ ለሚያምኑ ፡ ሕዝቦች ፡
አስፈራሪና ፡ አብሳሪ ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አይደለሁም ፡ በላቸው ።

189 እርሱ ፡ ያ ፡ ከአንዲት ፡ ነፍስ ፡
(ከአደም) ፡ የፈጠራችሁ ፡ ከር
ሷም ፡ መቀናጀዋን ፡ ወደርሷ ፡
ይረካ ፡ ዘንድ ፡ ያደረገ ፡ ነው ።
በተገናኛትም ፡ ጊዜ ፡ ቀላልን ፡
እርግዝና ፡ አረገዘች ፤ እርሱንም ፡
(ፅንሱን) ፡ ይዛው ፡ ኼደች፤ በከበ
ደችም ፡ ጊዜ ፦ ደግን ፡ ልጅ ፡
ብትሰጠን ፡ በእርግጥ ፡ ከአመስ
ጋኞቹ ፡ እንኾናለን ፤ ሲሉ ፡ ጌታ
ቸውን ፡ አላህን ፡ ለመኑ ።

190 መልካምን ፡ ልጅ ፡ በሰጣቸውም ፡
ጊዜ ፡ በሰጣቸው ፡ ልጅ ፡ (ስም) ፡
ለርሱ ፡ ተጋሪዎችን ፡ አደረጉ
ለት ፤ (1) አላህም ፡ ከሚያጋሩት ፡
ሁሉ ፡ ላቀ ።

191 ምንንም ፡ የማይፈጥሩትንና ፡ እነ
ርሱም ፡ የሚፈጠሩትን ፡ (በአ
ላህ) ፡ ያጋራሉን ?

192 ለነርሱም ፡ መርዳትን ፡ የማይች
ሉትን ፡ ነፍሶቻቸውንም ፡ የማይ
ረዱትን ፡ (ያጋራሉን ?)

1 ስሙን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አስጠግተው ፡ በመ
ጥራት ።



193 (ጣዖቶቹን) ፡ ወደ ፡ ቅን ፡ መን
ገድ ፡ ብትጠሩዋቸውም ፡ አይከተ
ሉዋችሁም ፤ ብትጠሩዋቸው ፡
ወይም ፡ እናንተ ፡ ዝምተኞችም ፡
ብትኾኑ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ እኩል ፡
ነው ፤

194 እነዚያ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የምትግገ
ዙዋቸው ፡ ብጤዎቻችሁ ፡ ተገገዢ
ዎች ፡ ናቸው ፤ እውነተኞችም ፡
እንደኾናችሁ ፡ ጥሩዋቸውና ፡
ለናንተ ፡ ይመልሱላችሁ ፤ (አይ
ችሉም) ።

195 ለነርሱ ፡ በርሳቸው ፡ የሚኼዱ
ባቸው ፡ እግሮች ፡ አሉዋቸውን ?
ወይስ ፡ ለነሱ ፡ በርሳቸው ፡ የሚ
ጨብጡባቸው ፡ እጆች ፡ አሉዋ
ቸውን ? ወይስ ፡ ለነሱ ፡ በርሳ
ቸው ፡ የሚያዩባቸው ፡ ዓይኖች ፡
አሉዋቸውን ? ወይስ ፡ ለነሱ ፡
በርሳቸው ፡ የሚሰሙባቸው ፡
ጆሮዎች ፡ አሉዋቸውን ?፦ ያጋ
ራችኋቸውን ፡ ጥሩ ፡ ከዚያም ፡
ተተናኮሉኝ ፤ ጊዜም ፡ አትስጡኝ ፤
(አልፈራችሁም) ፡ በላቸው ።

196 የኔ ፡ ረዳቴ ፡ ያ ፡ መጽሐፉን ፡
(ቁርአንን) ፡ ያወረደልኝ ፡ አላህ ፡
ነውና ፤ እርሱም ፡ መልካም ፡ ሠሪ
ዎችን ፡ ይረዳል ፡ (በላቸው) ።

197 እነዚያም ፡ ከርሱ ፡ በቀር ፡ የምት
ግገዙዋቸው ፡ ሊረዱዋችሁ ፡ አይ
ችሉም ፤ ነፍሶቻቸውንም ፡ አይ
ረዱም ።

198 ወደ ፡ ቅንም ፡ መንገድ ፡ (እንዲመ
ሩዋችሁ) ፡ ብትጠሩዋቸው ፡ አይ
ሰሙም ፤ (በላቸው) ፤ እነርሱንም ፡
የማያዩ ፡ ሲኾኑ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡
ሲመለከቱ ፡ ታያቸዋለህ ።

199 ገርን ፡ ጠባይ ፡ ያዝ ፤ በመልካ
ምም ፡ እዘዝ ፡ ባለጌዎቹንም ፡
ተዋቸው ።

200 ከሰይጣንም ፡ (በኩል) ፡ ጉትጎታ ፡
ቢያገኝህ ፡ በአላህ ፡ ተጠበቅ ፤
እርሱ ፡ ሰሚው ፡ ዐዋቂው ፡
ነውና ።

201 እነዚያ ፡ የተጠነቀቁት ፡ ከሰይ
ጣን ፡ የኾነ ፡ ዘዋሪ ፡ በነካቸው ፡
ጊዜ ፡ (ጌታቸውን) ፡ ይገነዘባሉ ፤
ወዲያውም ፡ እነሱ ፡ ተመልካ
ቾች ፡ ይኾናሉ ።

202 ወንድሞቻቸውም ፡ (1) ጥመትን ፡
ይጨምሩላቸዋል ፤ ከዚያም ፡
(እነርሱ) ፡ አይገቱም ።

203 በታምርም ፡ ባልመጣሃቸው ፡
ጊዜ ፡ (በራስህ) ፦ ለምን ፡ አት
ፈጥራትም ፡ ይላሉ ፤ ከጌታዬ ፡
ወደኔ ፡ የተወረደውን ፡ ብቻ ፡
እከተላለሁ ፤ ይህ ፡ (ቁርአን) ፡ ከጌ
ታችሁ ፡ ሲኾን ፡ ለሚያምኑ ፡
ሕዝቦች ፡ መረጃዎችና ፡ መም
ሪያ ፡ እዝነትም ፡ ነው ፡ በላቸው ።

204 ቁርአንም ፡ በተነበበ ፡ ጊዜ ፡ እር
ሱን ፡ አዳምጡ ፤ ጸጥም ፡ በሉ ፤
ይታዘንላችኋልና ።

205 ጌታህንም ፡ በምስጢር ፡ ተዋድ
ቀህና ፡ ፈርተህ ፡ ከጩኸት ፡ በታ
ችም ፡ በኾነ ፡ ቃል ፡ በጧትም ፡
በማታም ፡ አውሳው ፤ ከዘንጊዎ
ቹም ፡ አትኹን ።

206 እነዚያ ፡ እጌታህ ፡ ዘንድ ፡ ያሉት ፡
(መላእክት) ፡ እርሱን ፡ ከመግገ
ዛት ፡ አይኮሩም ፤ ያወድሱታልም፤
ለርሱም ፡ ብቻ ፡ ይሰግዳሉ ።

1 የከሓዲያን ፡ ወንድሞች ፡ ሰይጣናት ።

8ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-አንፋል ፡ (የጦር ፡ ዘረፋዎች ፡ ምዕራፍ) ፡
በመዲና፡የወረደች፡ናት፤አያትዋ፡(አንቀጾችዋ)፡75፤፡ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 ከጦር ፡ ዘረፋ ፡ ገንዘቦች ፡ ይጠይ
ቁሃል ፤ የዘረፋ ፡ ገንዘቦች ፡ የአላ
ህና ፡ የመልክተኛው ፡ ናቸው ፤
ስለዚህ ፡ አላህን ፡ ፍሩ ፤ በመካከ
ላችሁ ፡ ያለችውንም ፡ ኹኔታ ፡
አሳምሩ ፤ አማኞችም ፡ እንደኾና
ችሁ ፡ አላህንና ፡ መልክተኛውን ፡
ታዘዙ ፡ በላቸው ።
2 ፍጹም ፡ ምእምናን ፡ እነዚያ ፡
አላህ ፡ በተወሳ ፡ ጊዜ ፡ ልቦቻ
ቸው ፡ የሚፈሩት ፤ በነሱም ፡
ላይ ፡ አንቀጾቻችን ፡ በተነበቡ ፡
ጊዜ ፡ እምነትን ፡ የሚጨምሩላ
ቸው ፡ በጌታቸውም ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡
የሚመኩት ፡ ናቸው ።
3 እነዚያ ፡ ሶላትን ፡ ደንቡን ፡ አሟ
ልተው ፡ የሚሰግዱ፥ ከሰጠና
ቸውም ፡ ሲሳይ ፡ የሚለግሱ ፡
ናቸው ።
4 እነዚያ ፡ በውነት ፡ አማኞች ፡
እነሱ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፤ ለነሱ ፡
በጌታቸው ፡ ዘንድ ፡ ደረጃዎች ፡
ምሕረትና ፡ የከበረ ፡ ሲሳይም ፡
አላቸው ።
5 (ይህ ፡ በዘረፋ ፡ ክፍያ ፡ የከፊሉ ፡
ሰው ፡ መጥላት) ፡ ከምእምናን ፡
ከፊሉ ፡ የጠሉ ፡ ሲኾኑ ፡ ጌታህ ፡
ከቤትህ ፡ በውነት ፡ ላይ ፡ ኾነህ ፡
እንዳወጣህ ፡ ነው ።
6 እነርሱ ፡ እያዩ ፡ ወደሞት ፡ እንደ
ሚነዱ ፡ ኾነው ፡ በውነቱ ፡ ነገር ፡
(በመጋደል ፡ ግዴታነት) ፡ ከተገ
ለጸላቸው ፡ በኋላ ፡ ይከራከሩሃል ።
7 አላህም ፡ ከሁለቱ ፡ ጭፍሮች ፡ (1)
አንደኛዋን ፡ እርሷ ፡ ለናንተ ፡
ናት ፡ ሲል ፡ ተስፋ ፡ በሰጣችሁ ፡
ጊዜ ፤ የኀይል ፡ ባለቤት ፡ ያልኾነ
ችውም ፡ (ነጋዴይቱ) ፡ ለናንተ ፡
ልትኾን ፡ በወደዳችሁ ፡ ጊዜ ፡
አላህም ፡ በተስፋ ፡ ቃላቱ ፡ እውነ
ትን ፡ ማረጋገጡን ፡ ሊገልጽና ፡
የከሓዲዎችንም ፡ መጨረሻ ፡ ሊቆ
ርጥ ፡ በሻ ፡ ጊዜ ፡ (የኾነውን ፡ አስ
ታውስ) ።
8 (ይህንንም ፡ ያደረገው) ፡ አጋሪ
ዎቹ ፡ ቢጠሉም ፡ እውነቱን ፡ ሊያ
ረጋግጥ ፡ ክሕደትንም ፡ ሊያጠፋ ፡
ነው ።
9 ከጌታችሁ ፡ ርዳታን ፡ በፈለጋ
ችሁ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ በሺሕ ፡ መላእ
ክት ፡ ተከታታዮች ፡ ሲኾኑ ፡
እረዳችኋለሁ ፡ ሲል ፡ ለናንተ ፡
የተቀበላችሁን ፡ (አስታውሱ) ።
10 አላህም ፡ (ይኸንን ፡ ርዳታ) ፡ ለብ
ስራትና ፡ ልቦቻችሁ ፡ በርሱ ፡
ሊረኩበት ፡ እንጂ ፡ ለሌላ ፡ አላደ
ረገውም ፤ ድልም ፡ መንሳት ፡
ከአላህ ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፡ ከሌላ ፡
አይደለም ፤ አላህ ፡ አሸናፊ ፡
ጥበበኛ ፡ ነውና ።
11 ከርሱ ፡ በኾነው ፡ ጸጥታ ፡ (በጦር ፡
ግንባር) ፡ በእንቅልፍ ፡ በሸፈና

1 ከቁረይሽ ፡ ሲራራና ፡ ከጦረኛዋ ።



ችሁና ፡ ውሃንም ፡ በርሱ ፡ ሊያጠ
ራችሁ ፡ የሰይጣንንም ፡ ጉትጎታ ፡
ከናንተ ፡ ሊያስወግድላችሁ ፡
ልቦቻችሁንም ፡ (በትዕግሥት) ፡
ሊያጠነክርላችሁ ፡ በርሱም ፡
ጫሞችን ፡ (በአሸዋው ፡ ላይ) ፡
ሊያደላድልላችሁ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
ከሰማይ ፡ ባወረደላችሁ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውሱ) ።
12 ጌታህ ፡ ወደ ፡ መላእክቱ ፡—
እኔ ፡ (በርዳታዬ) ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡
ነኝና ፡ እነዚያን ፡ ያመኑትን ፡
አጥናኑ ፤ በነዚያ ፡ በካዱት ፡
ልቦች ፡ ውስጥ ፡ ፍርሃትን ፡ በእር
ግጥ ፡ እጥላለሁ ፤ ከአንገቶችም ፡
በላይ ፡ (ራሶችን) ፡ ምቱ ፤ ከነ
ሱም ፡ የቅርንጫፎችን ፡ መለ
ያልይ ፡ ሁሉ ፡ ምቱ ፤ ሲል ፡ ያወረ
ደውን ፡ (አስታውስ) ።
13 ይህ ፡ እነርሱ ፡ አላህንና ፡ መልክ
ተኛውን ፡ ስለተቃወሙ ፡ ነው ፤
አላህንና ፡ መልክተኛውንም ፡
የሚቃወም ፡ ሁሉ ፡ አላህ ፡
ቅጣቱ ፡ ብርቱ ፡ ነው ።
14 ይኻችሁ ፡ (ቅጣታችሁ ፡ ነው) ፡
ቅመሱትም ፡ ለከሓዲዎችም ፡
የእሳት ፡ ቅጣት ፡ በእርግጥ ፡
አለባቸው ።
15 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! እነዚ
ያን ፡ የካዱትን ፡ ሰዎች ፡ (ለጦር) ፡
ሲጓዙ ፡ ባገኛችኋቸው ፡ ጊዜ ፡
ጀርባዎችን ፡ አታዙሩላቸው ።
16 ያን ፡ ጊዜም ፡ ለግድያ ፡ ለመዘ
ዋወር ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሠራዊት ፡
ለመቀላቀል ፡ ሳይኾን ፡ ጀርባ
ውን ፡ የሚያዞርላቸው ፡ ሰው ፡
ከአላህ ፡ በኾነ ፡ ቁጣ ፡ በእርግጥ ፡
ተመለሰ ፤ መኖሪያውም ፡ ገሀነም ፡
ናት ፤ መመለሻይቱም ፡ ከፋች ።
17 አልገደላችኋቸውም ፡ ግን ፡ አላህ ፡
ገደላቸው ፤ (ጭብጥን ፡ ዐፈር) ፡
በወረወርክም ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡
አልወረወርክም ፤ ግን ፡ አላህ ፡
ወረወረ ፤ (ወደ ፡ ዓይኖቻቸው ፡
አደረሰው) ፤ ለአማኞችም ፡ ከርሱ ፡
የኾነን ፡ መልካም ፡ ጸጋ ፡ ለመስ
ጠት ፡ (ይህን ፡ አደረገ) ። አላህ ፡
ሰሚ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።
18 ይኻችሁ ፡ (ዕውነት ፡ ነው) ፡ አላ
ህም ፡ የከሓዲዎችን ፡ ተንኮል ፡
አድካሚ ፡ ነው ።
19 ፍትሕን ፡ (ፍርድን) ፡ ብትጠይቁ ፡
ፍትሑ ፡ በእርግጥ ፡ መጥቶላች
ኋል ፤ (ክሕደትንና ፡ መዋጋትን) ፡
ብትከለከሉም ፡ እርሱ ፡ ለናንተ ፡
የተሻለ ፡ ነው ፤ (ወደ ፡ መጋደል) ፡
ብትመለሱም ፡ እንመለሳለን ፤ ሰራ
ዊታችሁም ፡ ብትበዛም ፡ እንኳ ፡
ከናንተ ፡ ምንም ፡ አትጠቅማች
ሁም ፤ አላህም ፡ ከምእምናን ፡
ጋር ፡ ነው ።
20 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላህ
ንና ፡ መልክተኛውን ፡ ታዘዙ ፤
እናንተም ፡ የምትሰሙ ፡ ስትኾኑ ፡
ከርሱ ፡ አትሽሹ ።
21 እንደነዚያም ፡ እነሱ ፡ የማይሰሙ ፡
ሲኾኑ ፡ ሰማን ፡ እንደ ፡ አሉት ፡
አትኹኑ ።
22 ከተንቀሳቃሾች ፡ ሁሉ ፡ አላህ ፡
ዘንድ ፡ መጥፎ ፡ ተንኮለኞች ፡
እነዚያ ፡ የማያውቁት ፡ ደንቆሮ
ዎቹ ፡ ዲዳዎቹ ፡ ናቸው ።
23 በውስጣቸውም ፡ ደግ ፡ መኖሩን ፡
አላህ ፡ ባወቀ ፡ ኖሮ ፡ (የመረዳ
ትን ፡ መስማት) ፡ ባሰማቸው ፡
ነበር ፤ (ደግ ፡ የሌለባቸው ፡ መኾ
ኑን ፡ ሲያውቅ) ፡ ባሰማቸውም ፡

ኖሮ ፡ እነሱ ፡ እወነትን ፡ የተዉ ፡
ኾነው ፡ በሸሹ ፡ ነበር ።
24 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! (መል
ክተኛው) ፡ ሕያው ፡ ወደሚያደር
ጋችሁ ፡ እምነት ፡ በጠራችሁ ፡
ጊዜ ፡ ለአላህና ፡ ለመልክተኛው ፡
ታዘዙ ፤ አላህም ፡ በሰውየውና ፡
በልቡ ፡ መካከል ፡ የሚጋርድ ፡
መኾኑን ፡ ወደርሱም ፡ የምትሰበ
ሰቡ ፡ መኾናችሁን ፡ ዕወቁ ።
25 ከናንተም ፡ ውስጥ ፡ እነዚያን ፡
የበደሉትን ፡ ብቻ ፡ ለይታ ፡ የማ
ትነካን ፡ ፈተና ፡ ተጠንቀቁ ፤
አላህም ፡ ቅጣቱ ፡ ብርቱ ፡ መኾ
ኑን ፡ ዕወቁ ።
26 እናንተም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የተና
ቃችሁ ፡ ጥቂቶች ፡ ኾናችሁ ፡ ሳላ
ችሁ ፡ ሰዎች ፡ ሊነጥቁዋችሁ ፡
የምትፈሩ ፡ ስትኾኑ ፡ ያስጠጋች
ሁን ፡ በእርዳታውም ፡ ያበረታች
ሁን ፡ ከመልካሞች ፡ ሲሳዮችም ፡
ታመሰግኑ ፡ ዘንድ ፡ የሰጣችሁን ፡
አስታውሱ ።
27 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላህ
ንና ፡ መልክተኛውን ፡ አትክዱ ፤
አደራዎቻችሁንም ፡ እናንተ ፡
እያወቃችሁ ፡ አትክዱ ።
28 ገንዘቦቻችሁና ፡ ልጆቻችሁም ፡
ፈተና ፡ ብቻ ፡ መኾናቸውንና ፡
አላህም ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡
ምንዳ ፡ ያለው ፡ መኾኑን ፡ ዕወቁ ።
29 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላ
ህን ፡ ብትፈሩ ፡ የውነት ፡ መለ
ያን ፡ ብርሃን ፡ ያደርግላችኋል ፤
ክፉ ፡ ሥራዎቻችሁንም ፡ ከናንተ ፡
ላይ ፡ ያብስላችኋል ፤ ለናንተም ፡
ይምራችኋል ፤ አላህም ፡ የታላቅ ፡
ችሮታ ፡ ባለቤት ፡ ነው ።
30 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ሊያስሩህ ፡
ወይም ፡ ሊገድሉህ ፡ ወይም ፡
(ከመካ) ፡ ሊያወጡህ ፡ ባንተ ፡
ላይ ፡ በመከሩብህ ፡ ጊዜ ፡ (አስታ
ውስ) ፤ ይመክራሉም ፡ አላህም ፡
ተንኮላቸውን ፡ ይመልስባቸዋል ፤
አላህም ፡ ከመካሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡
በላይ ፡ ነው ።
31 አንቀጾቻችንም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
በተነበቡ ፡ ጊዜ ፡— በእርግጥ ፡
ሰምተናል ፤ በሻን ፡ ኖሮ ፡ የዚህን ፡
ብጤ ፡ ባልን ፡ ነበር ፤ ይህ ፡ የመ
ጀመሪያዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ጽሑፍ ፡
ተረቶች ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደ
ለም ፡ ይላሉ ።
32 ፡—ጌታችን ፡ ሆይ ! ይህ ፡ እርሱ ፡
ካንተ ፡ ዘንድ ፡ (የተወረደ) ፡ እው
ነት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡
ከሰማይ ፡ ድንጋዮችን ፡ አዝን
ምብን ፡ ወይም ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣ
ትን ፡ አምጣብን ፡ ባሉም ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ) ።
33 አላህም ፡ አንተ ፡ በውስጣቸው ፡
እያለህ ፡ (ደንጊያ ፡ በማዝነምና ፡
ባሳማሚ ፡ ቅጣት) ፡ የሚቀጣ
ቸው ፡ አይደለም ፤ አላህም ፡ እነሱ
ምሕረትን ፡ የሚለምኑ ፡ ሲኾኑ ፡
የሚቀጣቸው ፡ አይደለም ።
34 እነሱ ፡ ከተከበረው ፡ መስጊድ ፡
የሚከለክሉ ፡ ሲኾኑም ፡ አላህ ፡
(በሰይፍ) ፡ የማይቀጣቸው ፡ ለነሱ
ምን ፡ አላቸው ፤ (የቤቱ) ፡ ጠባቂ
ዎችም: አልነበሩም ፤ ጠባቂዎቹ ፡
(ከሕይትን) ፡ ተጠንቃቂዎቹ ፡
እንጂ ፡ ሌሎቹ ፡ አይደሉም ፤ ግን ፡
አብዛኞዎቻቸው: አያውቁም::
35 በቤቱ ፡ ዘንድም ፡ (በከዕባ) ፡ ስግ
ደታቸው ፡ ማፏጨትና: ማጨብ
ጨብ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አልነበረም ፤



ትክዱት ፡ በነበራችሁትም ፡ ነገር ፡
ቅጣትን ፡ ቅመሱ ፡ (ይባላሉ) ።
36 እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ከአላህ ፡ መን
ገድ ፡ ሊከለክሉ ፡ ገንዘቦቻቸውን ፡
ያወጣሉ ፤ በእርግጥም ፡ ያወጡ
ዋታል ፤ ከዚያም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
ጸጸት ፡ ትኾንባቸዋለች ፤ ከዚ
ያም ፡ ይሸነፋሉ ፤ እነዚያም ፡
የካዱት ፡ ወደ ፡ ገሀነም ፡ ይሰበሰ
ባሉ ።
37 አላህ ፡ መጥፎውን ፡ ከመልካሙ ፡
ሊለይ ፡ መጥፎውንም ፡ ከፊሉን ፡
በከፊሉ ፡ ላይ ፡ ሊያደርግና ፡
ባንድ ፡ ላይ ፡ ሊያነባብረው ፡ በገ
ሀነም ፡ ውስጥም ፡ ሊያደርገው ፡
(ይሰበሰባሉ) ፤ እነዚያ ፡ እነሱ ፡
ከሳሪዎቹ ፡ ናቸው ።
38 ለነዚያ ፡ ለካዱት ፡ በላቸው ፡—
ቢከለከሉ ፡ ለነሱ ፡ በእርግጥ ፡
ያለፈውን ፡ (ሥራ) ፡ ምሕረት ፡
ይደረግላቸዋል ፤ (ወደ ፡ መጋ
ደል) ፡ ቢመለሱም ፡ (እናጠፋቸ
ዋለን) ፤ የቀድሞዎቹ ፡ ሕዝቦች ፡
ልማድ ፡ በእርግጥ ፡ አልፋለችና ።
39 እውከትም ፡ እስከማትገኝ ፡ ሃይ
ማኖትም ፡ ሁሉ ፡ ለአላህ ፡ ብቻ ፡
እስከሚኾን ፡ ድረስ ፡ ተጋደሉዋ
ቸው ፤ ቢከለከሉም ፡ አላህ ፡ የሚ
ሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ተመልካች ፡
ነው ።
40 (ከእምነት) ፡ ቢዞሩም ፡ አላህ ፡
ረዳታችሁ ፡ መኾኑን ፡ ዕወቁ ፤
(እርሱ) ፡ ምን ፡ ያምር ፡ ጠባቂ !
ምን ፡ ያምርም ፡ ረዳት !

* * *

41 ከማንኛውም ፡ ነገር ፡ በጦር ፡
(ከከሓዲዎች) ፡ የዘረፋችሁትም ፡
አንድ ፡ አምስተኛው ፡ ለአላህና ፡
ለመልክተኛው ፤ (ለነቢዩ) ፡ የዝ
ምድና ፡ ባለቤቶችም ፤ ለየቲሞ
ችም ፤ ለምስኪኖችም ፤ ለመንገደ
ኛም ፡ የተገባ ፡ መኾኑን ፡ ዕወቁ ፤
በአላህና ፡ በዚያም ፡ እውነትና ፡
ውሸት ፡ በተለየበት ፡ ቀን ፡ ሁለቱ
ጭፍሮች ፡ በተገናኙበት ፡ (በበ
ድር) ፡ ቀን ፡ በባሪያችን ፡ ላይ ፡
ባወረድነው ፡ የምታምኑ ፡ እንደ ፡
ኾናችሁ ፡ (ይህንን ፡ ዕወቁ) ፡
አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ቻይ ፡ ነው ።
42 እናንተ ፡ በቅርቢቱ ፡ ዳርቻ ፡ (1)
ኾናችሁ ፡ እነርሱም ፡ በሩቂቱ ፡
ዳርቻ ፡ ኾነው ፡ የነጋዴዎቹም ፡
ጭፍራ ፡ ከናንተ ፡ በታች ፡ ሲኾኑ ፡
በሰፈራችሁ ፡ ጊዜ ፡ (ያደረግንላ
ችሁን ፡ አስታውሱ) ፤ በተቃጠራ
ችሁም ፡ ኖሮ ፡ በቀጠሮው ፡ በተ
ለያያችሁ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ አላህ ፡
ሊሠራው ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡
ሊፈጽም ፡ የሚጠፋ ፡ ሰው ፡ ከአ
ስረጅ ፡ በኋላ ፡ እንዲጠፋ ፡ ሕያው
የሚኾንም ፡ ሰው ፡ ከአስረጅ ፡
በኋላ ፡ ሕያው ፡ እንዲኾን ፡ (ያለ
ቀጠሮ ፡ አጋጠማችሁ) ፤ አላህም ፡
በእርግጥ ፡ ሰሚ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
43 አላህ ፡ በሕልምህ ፡ እነሱን ፡
ጥቂት ፡ አድርጎ ፡ ባሳየህ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ) ፤ እነሱን ፡ ብዙ ፡
አድርጎ ፡ ባሳየህም ፡ ኖሮ ፡ በፈራ
ችሁና ፡ በነገሩ ፡ በተጨቃጨቃ
ችሁ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ አላህ ፡ አዳና
ችሁ ፤ እርሱ ፡ በደረቶች ፡ ውስጥ ፡
ያለን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።
44 አላህም: ሊሠራው: የሚገባን: ነገር:
ይፈጽም: ዘንድ: በተጋጠማችሁ:
ጊዜ: እነርሱን: በዓይኖቻችሁ:

1 ከሸለቆው ፡ ወደ ፡ መዲና ።

ጥቂት፡ አድርጐ፡ ያሳያችሁንና፡ በዓ
ይኖቻቸውም፡ ላይ፡ ያሳነሳችሁን፡
(አስታውሱ)፤ ነገሮቹም፡ ሁሉ፡
ወደ፡ አላህ፡ ብቻ፡ ይመለሳሉ።

45 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ሰራ
ዊትን ፡ በገጠማችሁ ፡ ጊዜ ፡
እርጉ ፤ (መክቱ) ፤ አላህንም ፡
በብዙ ፡ አውሱ ፤ በእርግጥ ፡ ትድ
ናላችሁና ።

46 አላህንና ፡ መልክተኛውንም ፡
ታዘዙ ፤ አትጨቃጨቁም ፤ ትፈራ
ላችሁና ፡ ኃይላችሁም ፡ ትኼዳ
ለችና ፤ ታገሡም ፤ አላህ ፡ ከትዕ
ግሥተኞች ፡ ጋር ፡ ነውና ።

47 እንደነዚያ ፡ ለትዕቢትና ፡ ለሰ
ዎች ፡ ይውልኝ ፡ ሲሉ ፡ ከአላ
ህም ፡ መንገድ ፡ ለማገድ ፡ ከአገራ
ቸው ፡ እንደ ፡ ወጡት ፡ አትኹኑ ፤
አላህም ፡ በሚሠሩት ፡ ሁሉ ፡
(በዕውቀቱ) ፡ ከባቢ ፡ ነው ።

48 ሰይጣንም ፡ ሥራዎቻቸውን ፡ ለነ
ርሱ ፡ ባሳመረላቸውና ፡ ዛሬ ፡
ለናንተ ፡ ከሰዎች ፡ አሸናፊ ፡ የላ
ችሁም ፡ እኔም ፡ ለናንተ ፡ ረዳት ፡
ነኝ ፡ ባለ ፡ ጊዜም ፡ (አስታውስ) ፤
ሁለቱ ፡ ጭፍሮችም ፡ በተያዩ ፤
ጊዜ ፡ ወደኋላው ፡ አፈገፈገ ፡
እኔ ፡ ከናንተ ፡ ንጹህ ፡ ነኝ ፤ እኔ ፤
እናንተ ፡ የማታዩትን ፡ አያለሁ ፡
እኔ ፡ አላህን ፡ እፈራለሁ ፤ አላ
ህም ፡ ቅጣተ ፡ ብርቱ ፡ ነው ፡
አላቸውም ።

49 መናፍቃንና ፡ እነዚያ ፡ በልቦቻ
ቸው ፡ ውስጥ ፡ በሽታ ፡ ያለባ
ቸው ፡ እነዚህን ፡ (ሙስሊሞች)፡
ሃይማኖታቸው ፡ አታለላቸው ፡
ባሉ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፤ በአላ
ህም ፡ ላይ ፡ የሚጠጋ ፡ (ያሸን
ፋል) ፤ አላህ ፡ አሸናፊ ፡ ጥበበኛ ፡
ነውና ።

50 እነዚያንም ፡ የካዱትን ፡ መላእ
ክት ፡ ፊቶቻቸውንና ፡ ጀርባቻቸ
ውን ፡ እየመቱ ፡ የቃጠሎንም ፡
ስቃይ ፡ ቅመሱ ፡ (እያሉ) ፡ በሚገ
ድሏቸው ፡ ጊዜ ፡ ብታይ ፡ ኖሮ ፡
(አስደንጋጭን ፡ ነገር ፡ ታይ ፡
ነበር) ።

51 ይህ ፡ እጆቻችሁ ፡ ባስቀደሙት ፡
ምክንያት ፡ አላህም ፡ ለባሮቹ ፡
በዳይ ፡ ባለመኾኑ ፡ ነው ፡ (ይባ
ላሉ) ።

52 (የነዚያ ፡ ልማድ) ፡ እንደ ፡ ፈር
ዖን ፡ ቤተሰብና ፡ እንደነዚያም ፡
ከነሱ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡
ልማድ ፡ ነው ፤ በአላህ ፡ አንቀ
ጾች ፡ ካዱ ፤ አላህም ፡ በኃጢአቶ
ቻቸው ፡ ያዛቸው ፤ አላህ ፡ ኀይ
ለኛ ፡ ቅጣተ ፡ ብርቱ ፡ ነውና ።

53 ይኸ ፡ (ቅጣት) ፡ አላህ ፡ በሕዝ
ቦች ፡ ላይ ፡ የለገሰውን ፡ ጸጋ ፡ በነ
ፍሶቻቸው ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡
እስከሚለውጡ ፡ ድረስ ፡ የማይለ
ውጥ ፡ በመኾኑ፡ ምክንያት ፡
ነው ፤ አላህም ፡ ሰሚ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።

54 እንደ ፡ ፈርዖን ፡ ቤተሰቦችና ፡
እንደነዚያም ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡
እንደ ፡ ነበሩት ፡ ልማድ ፡ (እስከ
ሚለውጡ ፡ ድረስ ፡ አይለውጥባ
ቸውም) ፤ በጌታቸው ፡ ታምራት ፡
አስተባበሉና ፡ በኃጢአቶቻቸው ፡
አጠፋናቸው ፤ የፈርዖንንም ፡ ቤተ
ሰቦች ፡ አሰጠምናቸው ፤ ሁሉም ፡
በዳዮች ፡ ነበሩም ።

55 ከሚንቀሳቀሱ ፡ እንስሳዎች ፡
ሁሉ ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡ ይበልጥ ፡
ከፉዎቹ ፡ እነዚያ ፡ ዘወትር ፡



የካዱት ፡ ናቸው ፤ ስለዚህ ፡ እነሱ ፡
አያምኑም ።

56 እነዚያ ፡ ከነሱ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
የያዝክባቸው ፡ ከዚያም ፡ በየጊ
ዜው ፡ ቃል ፡ ኪዳናቸውን ፡ የሚ
ያፈርሱ ፡ ናቸው ፤ እነሱም ፡ አይ
ጠንቀቁም ።

57 በጦርም ፡ ላይ ፡ ብታገኛቸው ፡
በነርሱ ፡ ቅጣት ፡ ምክንያት ፡
(ሌሎቹ ፡ ከሐዲዎች) ፡ ይገሠጡ ፡
ዘንድ ፡ ከኋላቸው ፡ ያሉትን ፡
በትንባቸው ።

58 ከሕዝቦችም ፡ ክዳትን ፡ ብትፈራ ፡
(የኪዳኑን ፡ መፍረስ ፡ በማወቅ) ፡
በመተካከል ፡ ላይ ፡ ኾናችሁ ፡ (1)
ኪዳናቸውን ፡ ወደነሱ ፡ ጣልላ
ቸው ፤ አላህ ፡ ከዳተኞችን ፡ አይ
ወድምና ።

59 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ከአላህ ፡
ቅጣት ፡ ያመለጡ ፡ መኾናቸውን ፡
አያስቡ ፤ እነሱ ፡ አያቅቱምና ።

60 ለነሱም ፡ ከማንኛውም ፡ ኀይልና ፡
ከታጀበ ፡ ፈረሶችም ፡ የቻላችሁ
ትን ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡ የአላህን ፡
ጠላትና ፡ ጠላታችሁን ፡ ሌሎች
ንም ፡ ከነርሱ ፡ በቀር ፡ ያሉትን ፡
የማታውቋዋቸውን ፡ አላህ ፡ የሚ
ያውቃቸውን ፡ (መናፍቃን) ፡ የም
ታሸብሩበት ፡ ስትኾኑ ፡ አዘጋጁ
ላቸው ። ከማንኛውም ፡ ነገር ፡
በአላህ ፡ መንገድ ፡ የምትለግሱ
ትም ፡ ምንዳው ፡ ወደናንተ ፡
በሙሉ ፡ ይሰጣል ፤ እናንተም ፡
አትበደሉም ።

61 ወደ ፡ ዕርቅም ፡ ቢያዘነብሉ፡
ወደ ፡ እርሷ ፡ አዘንብል፤ በአላ
ህም ፡ ላይ ፡ ተጠጋ ፤ እነሆ ፡ እርሱ
ሰሚ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።

62 ሊያታልሉህም ፡ ቢፈልጉ ፡ በቂህ፡
አላህ ፡ ነው ፤ እርሱ ፡ ያ ፡ በርዳታ
ውና ፡ በምእምናን ፡ ያበረታህ ፡
ነው ።

63 በልቦቻቸውም ፡ መካከል ፡ ያስ
ማማ ፡ ነው ፤ በምድር ፡ ያለውን ፡
ሁሉ ፡ (ሀብት) ፡ በለገስክ ፡ ኖሮ ፡
በልቦቻቸው ፡ መካከል ፡ ባላስማ
ማህ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ አላህ ፡ በመካ
ከላቸው ፡ አስማማ ፤ እርሱ ፡ አሸ
ናፊ ፡ ጥበበኛ ፡ ነውና ።

64 አንተ ፡ ነቢዩ ፡ ሆይ ፡ በቂህ ፡
አላህ ፡ ነው ፤ ለተከተሉህም ፡
ምእምናን ፡ (በቂያቸው ፡ ነው) ።

65 አንተ ፡ ነቢዩ ፡ ሆይ ! ምእምና
ንን ፡ በመዋጋት ፡ ላይ ፡ አደፋፍ
ራቸው ፤ ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ ሃያ ፡
ታጋሾች ፡ ቢኖሩ ፡ ሁለት ፡ መቶን
ያሸንፉሉ ፤ ከናንተም ፡ መቶ ፡
ቢኖሩ ፡ ከነዚያ ፡ ከካዱት ፡ እነሱ ፡
የማያውቁ ፡ ሕዝቦች ፡ ስለኾኑ ፡
ሺሕን ፡ ያሸንፉሉ ፤ (1)

66 አሁን ፡ አላህ ፡ ከናንተ ፡ ላይ ፡
አቀለለላችሁ ፤ በናንተ ፡ ውስ
ጥም ፡ ድክመት ፡ መኖሩን ፡
ዐወቀ ፤ ስለዚህ ፡ ከናንተ ፡ መቶ ፡
ታጋሾች ፡ ቢኖሩ ፡ ሁለት ፡ መቶን
ያሸንፉሉ ፤ ከናንተም ፡ ሺሕ ፡
ቢኖሩ ፡ በአላህ ፡ ፈቃድ ፡ ሁለት ፡
ሺሕን፡ ያሸንፉሉ ፤ አላህም ፡ ከታ
ጋሾቹ ፡ ጋር ፡ ነው ።

67 ለነቢይ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እስኪ
ያደክም ፡ ድረስ ፡ ለርሱ ፡ ምርኮ
ኞች ፡ ሊኖሩት ፡ አይገባም ፤ የቅር
ቢቱን ፡ ዓለም ፡ ጠፊ ፡ ጥቅም ፡
ትፈልጋላችሁ ፤ አላህም ፡ መጪ

---

1 የኪዳኑን ፡ መፍረስ ፡ አስታውቀሃቸው ፤

1 ሃያው ፡ ሁለት ፡ መቶን ፡ መቶው ፡ ሺህን ፡
ይመክቱ ፡ የሚለው ፡ በሚቀጥለው ፡ አን
ቀጽ ፡ ተሻሽሎአል ።

ረሻይቱን ፣ ይሻል ፤ አላህም ፣
አሸናፊ ፣ ጥበበኛ ፣ ነው ።
68 ከአላህ ፣ ያለፈ ፣ ፍርድ ፣ ባልነ
በረ ፣ ኖሮ ፣ በወሰዳችሁት ፣ (ቤዛ)፣
ከባድ ፣ ቅጣት ፣ በነካችሁ ፣
ነበር ።
69 (ከጠላት)፡ ከዘረፋችሁትም፡
(ሀብት)፡ የተፈቀደ፡ መልካም፡
ሲኾን፡ ብሉ፤ አላህንም፡ ፍሩ፤
አላህ፡ መሓሪ፡ አዛኝ፡ ነውና፡፡
70 አንተ ፣ ነቢዩ ፣ ሆይ ! ከምርኮ
ኞች ፣ በእጆቻችሁ ፣ ላሉት ፣ በላ
ቸው ፣— አላህ ፣ በልቦቻችሁ ፣
ውስጥ ፣ በጎን ፣ ነገር ፣ (እምነ
ትን) ፣ ቢያውቅ ፣ ከናንተ ፣ ከተወ
ሰደባችሁ ፣ የተሻለን ፣ ይሰጣች
ኋል ፤ ለናንተም ፣ ይምራችኋል ፤
አላህም ፣ መሓሪ ፣ አዛኝ ፣ ነው ።
71 ሊከዱህም ፣ ቢፈልጉ ፣ ከዚህ ፣
በፊት ፣ አላህን ፣ በእርግጥ ፣ ከድ
ተዋል ፤ ከነሱም ፣ አስመችቶሃል ፤
አላህም ፣ ዐዋቂ ፣ ጥበበኛ ፣ ነው ።
72 እነዚያ ፣ ያመኑና ፣ የተሰደዱ ፣
በአላህም ፣ መንገድ ፣ ላይ ፣ በገን
ዘቦቻቸውና ፣ በነፍሶቻቸው ፣
የታገሉ ፣ እነዚያም ፣ (ስደተኞ
ቹን) ፣ ያስጠጉና ፣ የረዱ ፣ እነዚያ ፣
ከፊሎቻቸው ፣ ለከፊሉ ፣ ረዳቶች ፣
ናቸው ፤ እነዚያም ፣ ያመኑና ፣ ያል
ተሰደዱ ፣ እስከሚሰደዱ ፣ ድረስ ፣
ከነሱ ፣ ምንም ፣ ዝምድና ፣ የላች
ሁም ፤ በሃይማኖትም ፣ እርዳታን ፣
ቢፈልጉባችሁ ፣ በናንተና ፣ በነሱ፣
መካከል ፣ ቃል ፣ ኪዳን ፣ ባላችሁ ፣
ሕዝቦች ፣ ላይ ፣ ካልኾነ ፣ በስተ
ቀር ፣ በናንተ ፣ ላይ ፣ መርዳት ፣
አለባችሁ ፤ አላህም ፣ የምትሠሩ
ትን ፣ ሁሉ ፣ ተመልካች ፣ ነው ።
73 እነዚያም ፣ የካዱት ፣ ከፊሎቻ
ቸው ፣ ለከፊሉ ፣ ረዳቶች ፣ ናቸው ፤
(ከምእምናን ፣ መረዳዳትን ፣ ከከ
ሓዲያን ፣ መቆራረጥን) ፣ ባትሠ
ሩት ፣ በምድር ፣ ላይ ፣ እውከትና ፣
ታላቅ ፣ ጥፋት ፣ ይኾናል ።
74 እነዚያም ፣ ያመኑና ፣ የተሰደዱ ፣
በአላህም ፣ መንገድ ፣ ላይ ፣ የታ
ገሉ ፣ እነዚያም ፣ ያስጠጉና ፣
የረዱ ፣ እነዚያ ፣ እነሱ ፣ በውነት ፣
አማኞች ፣ ናቸው ፤ ለነሱም ፣
ምሕረትና ፣ የከበረ ፣ ሲሳይ ፣
አላቸው ።
75 እነዚያም ፣ በኋላ ፣ ያመኑና ፣ የተ
ሰደዱ ፣ ከናንተም ፣ ጋር ፣ ኾነው ፣
የታገሉ ፣ እነዚያ ፣ ከናንተው ፣
ናቸው ፤ የዝምድናዎች ፣ ባለቤ
ቶችም ፣ በአላህ ፣ መጽሐፍ ፣ ከፊ
ሎቻቸው ፣ በከፊሉ ፣ (መውረስ) ፣
የተገቡ ፣ ናቸው ፤ አላህ ፣ በነገሩ ፣
ሁሉ ፣ ዐዋቂ ፣ ነው ።



9ኛ ፣ ሱረቱ ፣ አል-ተውባህ ፣ (የንስሓ ፣ ምዕራፍ) ፣ በመዲና ፣
የወረደች ፣ ናት ፤ አያትዋ ፣ (አንቀጾችዋ) ፣ 129 ፣ ናቸው ።

1 (ይህች) ፣ ከአላህና ፣ ከመልክ
ተኛው ፣ ወደነዚያ ፣ ቃል ፣ ኪዳን ፣
ወደ ፣ ተጋባችኋቸው ፣ አጋሪዎች ፣
የምትደርስ ፣ ንጽሕና ፣ ናት ።
2 በምድር ፣ ላይም ፣ አራት ፣ ወሮ
ችን ፣ (ጸጥተኞች ፣ ስትኾኑ) ፣
ኺዱ ፤ እናንተም ፣ ከአላህ ፣ (ቅጣ
ት) ፣ የማታመልጡ ፣ መኾናችሁ
ንና ፣ አላህም ፣ ከሓዲዎችን ፣ አዋ
ራጅ ፣ መኾኑን ፣ ዕወቁ ፤ (በሏ
ቸው) ።
3 (ይህ) ፣ ከአላህና ፣ ከመልክተ
ኛው ፣ በታላቁ ፣ ሐጅ ፣ ቀን ፣
የወጣ ፣ አላህ ፣ ከአጋሪዎቹ ፣
ንጹሕ ፣ ነው ፣ መልክተኛውም ፣
(እንደዚሁ) ፤ (ከክሕደት) ፣ ብት
ጸጸቱም ፣ እርሱ ፣ ለናንተ ፣ በላ
ጭ ፣ ነው ፤ (ከእምነት) ፣ ብትሸ
ሹም ፣ እናንተ ፣ አላህን ፣ የማታ
ቅቱት ፣ መኾናችሁን ፣ ዕወቁ ፤
በማለት ፣ ወደ ፣ ሰዎች ፣ የሚደርስ
ማስታወቂያ ፣ ነው ፤ (1) እነዚ
ያን ፣ የካዱትንም ፣ በአሳማሚ ፣
ቅጣት ፣ አብስራቸው ።
4 ከአጋሪዎቹ ፣ እነዚያ ፣ ቃል ፣
ኪዳን ፣ የተጋባችኋቸውና ፣ ከዚ
ያም ፣ ምንም ፣ ያላጐደሉባችሁ ፣
በናንተ ፣ ላይም ፣ አንድንም ፣
ያልረዱባችሁ ፣ ሲቀሩ ፤ (እነዚ
ህን) ፣ ቃል ፣ ኪዳናቸውን ፣ እስከ ፣
ጊዜያታቸው ፣ (መጨረሻ) ፣ ሙሉ
ላቸው ፤ አላህ ፣ ጥንቁቆችን ፣
ይወዳልና ።
5 የተከበሩትም ፣ ወሮች ፣ ባለቁ ፣
ጊዜ ፣ አጋሪዎቹን ፣ በአገኛችሁባ
ቸው ፣ ስፍራ ፣ ግደሉዋቸው ፤
ያዙዋቸውም ፤ ክበቡዋቸውም ፤
ለነሱም ፣ (መጠባበቅ) ፣ በየመን
ገዱ ፣ ተቀመጡ ፤ ቢጸጸቱም ፣
ሶላትንም ፣ በደንቡ ፣ ቢሰግዱ ፣
ግዴታ ፣ ምጽዋትንም ፣ ቢሰጡ ፣
መንገዳቸውን ፣ ልቀቁላቸው ፤
አላህ ፣ መሓሪ ፣ አዛኝ ፣ ነውና ።
6 ከአጋሪዎችም ፣ አንዱ ፣ ጥገኝነ
ትን ፣ ቢጠይቅ ፣ የአላህን ፣ ቃል ፣
ይሰማ ፣ ዘንድ ፣ አስጠጋው ፤ ከዚ
ያም ፣ ወደ ፣ መጠበቂያው ፣ ስፍራ
አድርሰው ፤ ይህ ፣ እነሱ ፣ የማያ
ውቁ ፣ ሕዝቦች ፣ በመኾናቸው ፣
ነው ።
7 ለአጋሪዎቹ ፣ አላህ ፣ ዘንድና ፣
እመልክተኛው ፣ ዘንድ ፣ ቃል ፣
ኪዳን ፣ እንዴት ፣ ይኖራቸዋል ?
እነዚያ ፣ በተከበረው ፣ መስጊድ ፣
ዘንድ ፣ ኪዳን ፣ የተጋባችኋቸው ፣
ብቻ ፣ (1) ሲቀሩ ፣ (እነዚህ) ፣ በኪ
ዳናቸው ፣ ለናንተ ፣ ቀጥ ፣ እስካሉ
ላችሁ ፣ ድረስ ፣ ለነርሱም ፣ ቀጥ ፣
በሉላቸው ፤ አላህ ፣ ጥንቁቆችን ፣
ይወዳልና ።

1 ከዚህ ፣ ዓመት ፣ በኋላ ፣ ከሓዲ ፣ ከዕባን ፣
አይጐበኝም ፣ ራቁቱንም ፣ አይዞርም ።

1 በኒ ፣ ዶምራ ።

8 በናንተ ፡ ላይ ፡ ቢያይሉም ፡ በና
ንተ ፡ ውስጥ ፡ ዝምድናንና ፡ ቃል፡
ኪዳንን ፡ የማይጠብቁ ፡ ሲኾኑ ፡
እንዴት ? (ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይኖራ
ቸዋል) ፡ በአፎቻቸው ፡ ያስወድ
ዷችኋል ፤ ልቦቻቸውም ፡ እንቢ ፡
ይላሉ ፤ አብዛኞቻቸውም ፡ አመ
ጠኞች ፡ ናቸው ።
9 በአላህ ፡ አንቀጾች ፡ ጥቂትን ፡
ዋጋ ፡ ገዙ ፤ ከመንገዱም ፡ አገዱ ፤
እነርሱ ፡ ይሠሩት ፡ የነበሩት ፡
ሥራ ፡ ከፋ !
10 በምእምን ፡ ነገር ፡ ዝምድናንም ፡
ኪዳንንም ፡ አይጠብቁም ፤ እነ
ዚያም ፡ እነሱ ፡ ወሰን ፡ አላፊዎች፡
ናቸው ።
11 ቢጸጸቱም ፡ ሶላትንም ፡ ቢሰግዱ ፡
ዘካንም ፡ ቢሰጡ ፡ የሃይማኖት ፡
ወንድሞቻችሁ ፡ ናቸው ፤ ለሚያ
ውቁ ፡ ሕዝቦችም ፡ አንቀጾችን ፡
እናብራራለን ።
12 ከቃል ፡ ኪዳናቸው ፡ በኋላ ፡ መሐ
ላዎቻቸውን ፡ ቢያፈርሱ ፡ ሃይማ
ኖታችሁንም ፡ ቢያነውሩ ፡ የክሕ
ደት ፡ መሪዎችን ፡ (ከክሕደት) ፡
ይከለክሉ ፡ ዘንድ ፡ ተዋጉዋቸው ፤
እነርሱ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የላቸ
ውምና ።
13 መሐላዎቻቸውን ፡ ያፈረሱትን ፡
መልክተኛውንም ፡ ለማውጣት ፡
ያሰቡትን ፡ ሕዝቦች ፡ እነሱ ፡ ለመ
ጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የጀመሩዋችሁ ፡
ሲኾኑ ፡ ለምን ፡ አትዋጉዋቸውም፤
ትፈሩዋቸዋላችሁን ? ምእምናን ፡
እንደ ፡ ኾናችሁም ፡ አላህ ፡ ይበ
ልጥ ፡ ልትፈሩት ፡ የተገባው ፡
ነው ።
14 ተጋደሉዋቸው ፤ አላህ ፡ በእጆ
ቻችሁ ፡ ያሰቃያቸዋል ፤ ያዋርዳ
ቸዋልም ፤ በነሱም ፡ ላይ ፡ ይረዳ
ችኋል ፤ የምእምናን ፡ ሕዝቦች
ንም ፡ ልቦች ፡ ያሽራል ።
15 የልቦቻችሁንም ፡ ቁጭት ፡ ያስወ
ግዳል፤ አላህም ፡ ከሚሻው ፡ ሰው፡
ላይ ፡ ጸጸትን ፡ ይቀበላል ፤ አላ
ህም ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።
16 እነዚያን ፡ ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ የታ
ገሉትንና ፡ ከአላህም ፡ ከመልክ
ተኛውም ፡ ከምእምናንም ፡ ሌላ ፡
ምስጢረኛ ፡ ወዳጅ ፡ ያልያዙትን ፡
አላህ ፡ ሳይገልጽ ፡ ልትተዉ ፡
ታስባላችሁን ? አላህም ፡ በምት
ሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።
17 ለከሓዲዎች ፡ በነፍሶቻቸው ፡
ላይ ፡ በክሕደት ፡ የሚመሰክሩ ፡
ሲኾኑ ፡ የአላህን ፡ መስጊዶች ፡
ሊሠሩ ፡ አይገባቸውም ፤ እነዚያ ፡
ሥራዎቻቸው ፡ ተበላሹ ፤ እነ
ሱም ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ዘውታ
ሪዎች ፡ ናቸው ።
18 የአላህን ፡ መስጊዶች ፡ የሚሠ
ራው ፡ በአላህና ፡ በመጨረሻው ፡
ቀን ፡ ያመነ ፡ ሶላትንም ፡ በደ
ንቡ ፡ የሰገደ ፡ ግዴታ ፡ ምጽዋ
ትንም ፡ የሰጠ ፡ ከአላህም ፡ ሌላ ፡
(ማንንም) ፡ ያልፈራ ፡ ሰው ፡ ብቻ፡
ነው ፤ እነዚያም ፡ ከተመሩት ፡
ጭምር ፡ መኾናቸው ፡ ተረጋገጠ ።
19 ካዕባን ፡ ኀብኘዎችን ፡ ማጠጣት
ንና ፡ የተከበረውን ፡ መስጊድ ፡
መሥራትን ፡ በአላህና ፡ በመጨ
ረሻው ፡ ቀን ፡ እንዳመነና ፡ በአ
ላህ ፡ መንገድ ፡ እንደታገለ ፡
ሰው ፡ (እምነትና ፡ ትግል) ፡ አደረ
ጋችሁን ? አላህ ፡ ዘንድ ፡ አይተካ
ከሉም ፤ አላህም ፡ በዳዮች ፡ ሕዝ
ቦችን ፡ አይመራም ።



20 እነዚያ ፡ ያመኑት ፡ ከአገራቸ
ውም ፡ የተሰደዱት ፡ በገንዘቦቻቸ
ውና ፡ በነፍሶቻቸውም ፡ በአላህ ፡
መንገድ ፡ ላይ ፡ የታገሉት ፡ አላህ ፡
ዘንድ ፡ በደረጃ ፡ በጣም ፡ የላቁ ፡
ናቸው ፤ እነዚያም ፡ እነሱ ፡ ፍላጐ
ታቸውን ፡ ያገኙ ፡ ናቸው ።
21 ጌታቸው ፡ ከርሱ ፡ በኾነው ፡ እዝ
ነትና ፡ ውዴታ ፡ በገነቶችም ፡
ለነሱ ፡ በውስጥዋ ፡ የማያቋርጥ ፡
መጠቀሚያ ፡ ያለባት ፡ ስትኾን ፡
ያበስራቸዋል ።
22 በውስጧ ፡ ዘላለም ፡ ዘውታሪዎች ፡
ሲኾኑ ፡ (ያበስራቸዋል) ፤ አላህ ፡
እርሱ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ምንዳ ፡
አለና ።
23 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አባቶ
ቻችሁና ፡ ወንድሞቻችሁ ፡ ክሕ
ደትን ፡ ከእምነት ፡ አብልጠው ፡
ቢወዱ ፡ ወዳጆች ፡ አድርጋችሁ ፡
አትያዙዋቸው ፤ ከናንተም ፡ ው
ስጥ ፡ ወዳጅ ፡ የሚያደርጋቸው ፡
እነዚያ ፡ እነሱ ፡ በዳዮች ፡ ናቸው ፤
24 ፡—አባቶቻችሁና ፡ ወንዶች ፡
ልጆቻችሁ ፡ ወንድሞቻችሁም ፡
ሚስቶቻችሁም ፡ ዘመዶቻችሁም፡
የሰበሰባችኋቸው ፡ ሀብቶችም ፡
መክሰሩዋን ፡ የምትፈሩዋት ፡
ንግድም ፡ የምትወዷቸው፡ መኖሪ
ያዎችም ፡ እናንተ ፡ ዘንድ ፡ ከአላ
ህና ፡ ከመልክተኛው ፡ በርሱ ፡
መንገድም ፡ ከመታገል ፡ ይበ
ልጥ ፡ የተወደዱ ፡ እንደኾኑ ፡
አላህ ፡ ትእዛዙን ፡ እስከሚያመጣ፡
ድረስ ፡ ተጠባበቁ ፡ በላቸው ፤
አላህም ፡ አመጠኞች ፡ ሕዝቦችን ፡
አይመራም ።
25 አላህም ፡ በብዙ ፡ስፍራዎች ፡ በእ
ርግጥ ፡ ረዳችሁ ፤ የሑነይንም ፡
ቀን ፡ ብዛታችሁ ፡ በአስደነቀቻች
ሁና ፡ ከናንተም ፡ ምንም ፡ ባልጠ
ቀመቻችሁ ፡ ጊዜ ፡ ምድርም ፡
ከስፋቷ ፡ ጋር ፡ በጠበበቻችሁና ፡
ከዚያም ፡ ተሸናፊዎች ፡ ኾናችሁ ፡
በዞራችሁ ፡ ጊዜ ፡ (ረዳችሁ) ።
26 ከዚያም ፡ አላህ ፡ እርጋታውን ፡
በመልክተኛውና ፡ በምእምናኖቹ፡
ላይ ፡ አወረደ ፤ ያላያችኋቸውንም፡
ሰራዊት ፡ አወረደ ፤ እነዚያን ፡
የካዱትንም ፡ በመገደልና ፡ በመ
ማረክ ፡ አሰቃየ ፤ ይህም ፡ የከሓዲ
ያን ፡ ፍዳ ፡ ነው ።
27 ከዚያም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አላህ ፡
በሚሻው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጸጸትን ፡
ይቀበላል ፤ አላህም ፡ እጅግ ፡ መ
ሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።
28 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አጋ
ሪዎች ፡ እርኩሶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፤
ከዚህም ፡ ዓመታቸው ፡ (1)
በኋላ ፡ የተከበረውን ፡ መስጊድ ፡
አይቅረቡ ፤ ድኽነትንም ፡ ብት
ፈሩ ፡ አላህ ፡ ቢሻ ፡ ከችሮታው ፡
በእርግጥ ፡ ያከብራችኋል ፤ አላህ ፡
ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነውና ።
29 ከነዚያ ፡ መጽሐፍን ፡ ከተሰጡት ፡
ሰዎች ፡ እነዚያን ፡ በአላህና ፡ በመ
ጨረሻው ፡ ቀን ፡ የማያምኑትን ፡
አላህና ፡ መልክተኛው ፡ እርም ፡
ያደረጉትንም ፡ እርም ፡ የማያደር
ጉትንና ፡ እውነተኛውንም ፡ ሃይ
ማኖት ፡ የማይቀበሉትን ፡ እነ
ርሱ ፡ የተዋረዱ ፡ ኾነው ፡ ግብ
ርን ፡ በእጆቻቸው ፡ እስከሚሰጡ ፡
ድረስ ፡ ተዋጉዋቸው ።
30 አይሁድ ፡ ዑዘይር ፡ የአላህ ፡
ልጅ ፡ ነው ፡ አሉ ፤ ክርስቲያኖ

1 ዘጠነኛ ፡ ዓመተ ፡ ስደት ።

ችም ፡ አልመሲሕ ፡ የአላህ ፡ ልጅ፡
ነው ፡ አሉ ፤ ይህ ፡ በአፎቻቸው ፡
(የሚናገሩት) ፡ ቃላቸው ፡ ነው ፤
የነዚያን ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡ የካዱ
ትን ፡ ሰዎች ፡ ቃል ፡ ያመሳስላሉ ፤
አላህ ፡ ያጥፋቸው ፤ (ከእውነት) ፡
እንዴት ፡ ይመለሳሉ !
31 ከርሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የ
ሌለውን ፡ አንድን ፡ አምላክ ፡ ሊግ
ገዙ ፡ እንጂ ፡ ያልታዘዙ ፡ ሲኾኑ
ሊቃውንቶቻቸውንና ፡ መነኮሳታ
ቸውን ፡ የመርየምን ፡ ልጅ ፡ አል
መሲሕንም ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ አማ
ልክት ፡ አድርገው ፡ ያዙ ፤ ከሚያ
ጋሩት ፡ ሁሉ ፡ የጠራ ፡ ነው ።
32 የአላህን ፡ ብርሃን ፡ በአፎቻቸው ፡
ለማጥፋት ፡ ይፈልጋሉ ፤ አላህም ፡
ከሓዲዎች ፡ ቢጠሉም ፡ እንኳ ፡
ብርሃኑን ፡ መሞላትን ፡ እንጅ ፡
ሌላን ፡ አይሻም ።
33 እርሱ ፡ ያ ፡ አጋሪዎቹ ፡ ቢጠሉም ፡
መልክተኛውን ፡ (ሙሐመድን) ፡
በቅን ፡ መንገድና ፡ በእውነተኛ ፡
ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ ከሃይማኖት ፡
ሁሉ ፡ በላይ ፡ ይፋ ፡ ያደርገው ፡
ዘንድ ፡ የላከው ፡ ነው ።
34 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ከሊ
ቃውንትና ፡ ከመነኮሳት ፡ ብዙ
ዎቹ ፡ የሰዎችን ፡ ገንዘቦች ፡ በው
ሸት ፡ በእርግጥ ፡ ይበላሉ ፤ ከአላ
ህም ፡ መንገድ ፡ ያግዳሉ ፤ እነዚ
ያንም ፡ ወርቅንና ፡ ብርን ፡ የሚያ
ደልቡትን ፡ በአላህም ፡ መንገድ ፡
ላይ ፡ የማያወጧትን ፡ በአሳማሚ፡
ቅጣት ፡ አብስራቸው ።
35 በርሷ፡ ላይ፡ በገሀነም፡ እሳት፡ ውስጥ፡
በሚጋልባትና፡ ግንባሮቻቸውም፡
ጐኖቻቸውም፥ ጀርባዎቻቸውም፥
በርሷ፡ በሚተኮሱ ቀን፥ (አሳማሚ፡
በኾነ፡ ቅጣት፡ አብስራቸው)፤ ይህ፡
ለነፍሶቻችሁ፡ ያደለባችሁት፡ ነው፤
ታደልቡት፡ የነበራችሁትንም፡
ቅመሱ፤ (ይባላሉ)።
36 የወሮች ፡ ቍጥር ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡
በአላህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ሰማ
ያትንና ፡ ምድርን ፡ በፈጠረበት ፡
ቀን ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡
ነው ፤ ከነሱ ፡ አራቱ ፡ የተከበሩ ፡
ናቸው ፤ ይህ ፡ ቀጥተኛው ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ነው ፤ በነርሱ ፡ ውስጥም ፡
ነፍሶቻችሁን ፡ አትበድሉ ፤ አጋሪ
ዎችንም ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ኾነው ፡
እንደሚዋጉዋችሁ ፡ በአንድ ፡
ላይ ፡ ኾናችሁ ፡ ተጋደሉዋቸው ፤
አላህም ፡ ከሚፈሩት ፡ ጋር ፡ መኾ
ኑን ፡ ዕወቁ ።
37 የአንዱን ፡ ወር ፡ ክብር ፡ ወደ ፡
ሌላው ፡ ማዘግየት ፡ በክሕደት ፡
ላይ ፡ (ክሕደትን) ፡ መጨመር ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ በርሱ ፡ እነዚያ ፡ የካ
ዱት ፡ ሰዎች ፡ ይሳሳቱበታል ፤
በአንድ ፡ ዓመት ፡ የተፈቀደ ፡ ያደ
ርጉታል ፤ በሌላው ፡ ዓመትም ፡
ያወግዙታል ፤ (ይህ) ፡ አላህ ፡ ያከ
በራቸውን ፡ ወሮች ፡ ቍጥር ፡
ሊያስተካክሉ ፡ አላህም ፡ እርም ፡
ያደረገውን ፡ የተፈቀደ ፡ ሊያደ
ርጉ ፡ ነው ፤ የሥራዎቻቸው ፡
መጥፎው ፡ ለነርሱ ፡ ተዋበላቸው፤
አላህም ፡ ከሓዲያን ፡ ሕዝቦችን ፡
አይመራም ።
38 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! በአ
ላህ ፡ መንገድ ፡ (ለመታገል) ፡
ውጡ ፡ በተባላችሁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡
ምድር ፡ የምትወዘፉት ፡ ለእና
ንተ ፡ ምን ፡ አላችሁ ? የቅርቢ
ቱን ፡ ሕይወት ፡ ከመጨረሻይቱ ፡
ይበልጥ ፡ ወደዳችሁን ? የቅርቢ



ቱም ፡ ሕይወት ፡ ጥቅም ፡ በመጨ
ረሻይቱ ፡ (አንጻር) ፡ ጥቂት ፡
እንጂ ፡ አይደለም ።
39 ለዘመቻ ፡ ባትወጡ ፡ (አላህ) ፡ አሳ
ማሚን ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣችኋል ፤
ከናንተ ፡ ሌላ ፡ የኾኑንም ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ይለውጣል ፤ በምንም ፡ አት
ጐዱትምም ፤ አላህም ፡ በነገሩ ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ።
40 (ነቢዩን) ፡ ባትረዱት ፡ እነዚያ ፡
የካዱት ፡ ሕዝቦች ፡ የሁለት ፡
(ሰዎች) ፡ ሁለተኛ ፡ ኾኖ ፡ (ከመ
ካ) ፡ ባወጡት ፡ ጊዜ ፡ አላህ ፡ በእ
ርግጥ ፡ ረድቶታል ፤ ሁለቱም ፡
በዋሻው ፡ ሳሉ ፡ ለጓደኛው ፡ አት
ዘን ፡ አላህ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ነውና ፡
ባለ ፡ ጊዜ ፡ አላህ ፡ እርካታውን ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ አወረደ ፤ ባላያችኋ
ቸውም ፡ ሰራዊት ፡ አበረታው ፤
የነዚያንም ፡ የካዱትን ፡ ሰዎች ፡
ቃል ፡ ዝቅተኛ ፡ አደረገ ፤ የአላ
ህም ፡ ቃል ፡ እርሷ ፡ ከፍተኛ ፡
ናት ፤ አላህም ፡ አሸናፊ ፡ ጥበበኛ ፡
ነው ።
41 ቀላሎችም ፡ ከባዶችም ፡ ኾናችሁ፡
ዝመቱ ፤ በአላህም ፡ መንገድ ፡ በገ
ንዘቦቻችሁ ፡ በነፍሶቻችሁም ፡
ታገሉ ፤ ይሃችሁ ፡ የምታውቁ ፡
ብትኾኑ ፡ ለናንተ ፡ በጣም ፡ የተ
ሻለ ፡ ነው ።
42 (የጠራሀባቸው ፡ ነገር) ፡ ቅርብ ፡
ጥቅምና ፡ መካከለኛ ፡ ጉዞ ፡ በኾነ፡
ኖሮ ፡ በተከተሉህ ፡ ነበር ፤ ግን ፡
በነሱ ፡ ላይ ፡ መንገዲቱ ፡ ራቀች
ባቸው ፤ በቻልንም ፡ ኖሮ ፡ ከና
ንተ ፡ ጋር ፡ በወጣን ፡ ነበር ፡
ሲሉ ፡ በአላህ ፡ ይምላሉ ፤ ነፍሶ
ቻቸውን ፡ ያጠፋሉ ፤ አላህም ፡
እነሱ ፡ ውሸታሞች ፡ መኾናቸ
ውን ፡ በእርግጥ ፡ ያውቃል ።
43 አላህ ፡ ከአንተ ፡ ይቅር ፡ አለ ፤
እነዚያ ፡ እውነተኞዎቹ ፡ ላንተ ፡
እስከሚገለጹልህና፡ ፡ ውሸታሞ
ቹንም ፡ እስከምታውቅ ፡ ድረስ ፡
ለነርሱ ፡ (እንዲቀሩ) ፡ ለምን ፡
ፈቀድክላቸው ?
44 እነዚያ ፡ በአላህና ፡ በመጨረ
ሻው ፡ ቀን ፡ የሚያምኑት ፡ በገን
ዘቦቻቸውና ፡ በነፍሶቻቸው ፡
ከመታገላቸው ፡ (ለመቅረት) ፡
ፈቃድን ፡ አይጠይቁህም ፤ አላ
ህም ፡ የሚፈሩትን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
45 ፈቃድን ፡ የሚጠይቁህ ፡ እነዚያ ፡
በአላህና ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡
የማያምኑት ፡ ልቦቻቸውም ፡ የተ
ጠራጠሩት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፤ እነ
ሱም ፡ በጥርጣሬያቸው ፡ ውስጥ ፡
ይዋልላሉ ።
46 መውጣትንም ፡ ባሰቡ ፡ ኖሮ ፡
ለርሱ ፡ ዝግጅትን ፡ ባሰናዱ ፡
ነበር ፤ ግን ፡ አላህ ፡ (ለመውጣት)፡
እንቅስቃሴያቸውን ፡ ጠላ ፤ (አል
ሻውም) ፤ አሰነፋቸውም ፤ ከተቀ
ማጮቹም ፡ ጋር ፡ (1) ተቀመጡ ፡
ተባሉ ።
47 ከናንተ ፡ ጋር ፡ በወጡ ፡ ኖሮ ፡
ጥፋትን ፡ እንጂ ፡ አይጨምሩላች
ሁም ፡ ነበር ፤ እውከትንም ፡ የሚ
ፈልጉላችሁ ፡ ሲኾኑ ፡ በመካከላ
ችሁ ፡ (በማሳበቅ) ፡ ይቻኮሉ ፡
ነበር ፤ በናንተም ፡ ውስጥ ፡ ለነሱ ፡
አዳማጮች ፡ አሏቸው ፤ አላህም ፡
በዳዮችን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
48 እነርሱ ፡ ጠይዎች ፡ ሲኾኑ ፡ እው
ነቱ ፡ እስከመጣና ፡ የአላህም ፡

1 ከሕፃናትና ፡ ከሴቶች ፡ ጋር ።

ትእዛዝ ፡ እስከ ፡ ተገለጸ ፡ ድረስ ፡
ከዚህ ፡ በፊት ፡ እውከትን ፡ በእር
ግጥ ፡ ፈለጉ ፤ ነገሮችንም ፡ ሁሉ ፡
አገላበጡልህ ። (1)

49 ከነሱም ፡ ውስጥ ፡— ለኔ ፡ ፍቀ
ድልኝ ፡ አትሞክረኝም ፡ የሚል ፡
ሰው ፡ አልለ ፤ ንቁ ፡ በመከራ ፡
ውስጥ ፡ ወደቁ ፤ ገሀነምም ፡ ከሓ
ዲዎችን ፡ በእርግጥ ፡ ከባቢ ፡
ናት ።

50 መልካም ፡ ነገር ፡ ብታገኝህ ፡ ታስ
ከፋቸዋለች ፤ መከራም ፡ ብታገ
ኝህ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በእርግጥ ፡
ጥንቃቄያችንን ፡ ይዘናል ፡ ይላሉ ፤
እነርሱም ፡ ተደሳቾች ፡ ኾነው ፡
ይሸሻሉ ።

51 ፡—አላህ ፡ ለኛ ፡ የጻፈልን ፡
(ጥቅም) ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይነካ
ንም ፤ እርሱ ፡ ረዳታችን ፡ ነው ፤
በአላህ ፡ ላይም ፡ ምእምናን ፡
ይመኩ ፡ በላቸው ።

52 በኛ ፡ ላይ ፡ ከሁለቱ ፡ መልካሞች ፡
(2) አንደኛዋን ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡
ትጠባበቃላችሁን ? እኛም ፡ አላህ፡
ከርሱ ፡ በኾነው ፡ ቅጣት ፡ ወይም፡
በእጆቻችን ፡ የሚያጠፋችሁ ፡
መኾኑን ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ እንጠ
ባበቃለን ፤ ተጠባበቁም ፤ እኛ ፡
ከናንተ ፡ ጋር ፡ ተጠባባቂዎች ፡
ነንና ፡ በላቸው ።

53 ወዳችሁም ፡ ኾነ ፡ ጠልታችሁ ፡
ለግሱ ፤ ከናንተ ፡ ተቀባይ ፡ የላች
ሁም ፤ እናንተ ፡ አመጠኞች ፡
ሕዝቦች ፡ ናችሁና ፡ በላቸው ።

54 ልግስናዎቻቸውን ፡ ከነሱ ፡ ተቀ
ባይ ፡ የሚያገኙ፡ ከመኾን ፡ እነሱ፡
በአላህና ፡ በመልክተኛው ፡ የካዱ፡
ሶላትንም ፡ እነሱ ፡ ታካቾች ፡
ኾነው ፡ በስተቀር ፡ የማይሰግዱ ፡
እነሱም ፡ ጠይዎች ፡ ኾነው ፡ በስ
ተቀር ፡ የማይሰጡ ፡ መኾናቸው ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ አልከለከላቸውም ።

55 ገንዘቦቻቸውና ፡ ልጆቻቸውም ፡
አይድንቁህ ፤ አላህ ፡ የሚሻው ፡
በቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡ በነርሱ ፡
(በገንዘቦቻቸውና ፡ በልጆቻቸው)፡
ሊቀጣቸው ፡ ነፍሶቻቸውም ፡
እነሱ ፡ ከሓዲዎች ፡ ኾነው ፡
ሊወጡ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

56 እነሱም ፡ በእርግጥ ፡ ከናንተ ፡
ለመኾናቸው ፡ በአላህ ፡ ይምላሉ ፤
እነርሱም ፡ ከናንተ ፡ አይደሉም ፤
ግን ፡ እነሱ ፡ (አጋሪዎችን ፡ ያገኘ ፡
እንዳያገኛቸው) ፡ የሚፈሩ ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ናቸው ።

57 መጠጊያን ፡ ወይም ፡ ዋሻዎችን ፡
ወይም ፡ መግቢያን ፡ (ቀዳዳ) ፡
ባገኙ ፡ ኖሮ ፡ እነርሱ ፡ እየገሠ
ገሡ ፡ ወደርሱ ፡ በሸሹ ፡ ነበር ።

58 ከነሱም ፡ ውስጥ ፡ በምጽዋቶች ፡
የሚዘልፉህ ፡ ሰዎች ፡ አልሉ ።
ከርሷም ፡ (የሚሹትን) ፡ ቢሰሰጡ፡
ይደሰታሉ ፤ ከርሷም ፡ ባይሰሰጡ፡
እነሱ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይጠላሉ ።

59 እነሱም ፡ አላህና ፡ መልክተኛው ፡
የሰጣቸውን ፡ በወደዱ ፡ አላህም ፡
በቂያችን ፡ ነው ፡ አላህ ፡ ከችሮ
ታው ፡ በእርግጥ ፡ ይሰጠናል ፡
መልክተኛውም ፡ (ይሰጠናል) ፡
እኛ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ከጃዮች ፡ ነን ፡
ባሉ ፡ ኖሮ ፡ (ለነሱ ፡ በተሻላቸው ፡
ነበር) ።

60 ግዴታ ፡ ምጽዋቶች ፡ (የሚከፈ
ሉት) ፡ ለድኾች ፡ ለምስኪኖችም ፡
በርሷም ፡ ላይ ፡ ለሚሠሩ ፡ ሠራ

1 መከሩብህ ።
2 ድል ፡ ከመንሳትና፡ ከሰማዕትነት ።



ተኞች ፡ ልቦቻቸውም ፡ (በእስል
ምና) ፡ ለሚለማመዱት ፡ ጫንቃ
ዎችንም ፡ ነጻ ፡ በማውጣት ፡
በባለ ፡ ዕዳዎችም ፡ በአላህ ፡ መን
ገድም ፡ በሚሠሩ ፡ በመንገደኛም ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ ከአላህ ፡ የተደነገ
ገች ፡ ግዴታ ፡ ናት ፤ አላህም ፡
ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።

61 ከነሱም ፡ (ከመናፍቃን) ፡ እነ
ዚያ ፡ ነቢዩን ፡ የሚያሰቃዩ ፡ እር
ሱም ፡ ጆሮ ፡ ነው ፡ (ወሬ ፡ ሰሚ ፡
ነው) ፡ የሚሉ ፡ አልሉ ፤ በላቸው ፡
፡—ለናንተ ፡ የበጎ ፡ (ወሬ) ፡
ሰሚ ፡ ነው ፤ በአላህ ፡ ያምናል ፤
ምእምናንንም ፡ ያምናቸዋል ፤
ከናንተም ፡ ውስጥ ፡ ለነዚያ ፡
ላመኑት ፡ እዝነት ፡ ነው ፤ እነዚ
ያም ፡ የአላህን ፡ መልክተኛ ፡ የሚ
ያሰቃዩ ፡ ለነሱ ፡ አሳማሚ ፡
ቅጣት ፡ አላቸው ።

62 አላህንና ፡ መልክተኛውን ፡ ሊያስ
ወድዱ ፡ ተገቢያቸው ፡ ሲኾን ፡
እናንተን ፡ ያስወድዱ ችሁ ፡ ዘንድ፡
በአላህ ፡ ይምሉላችኋል ፤ ምእም
ናኖች ፡ ቢኾኑ ፡ (አላህንና ፡ መል
ክተኛውን ፡ ያስወድዱ) ።

63 አላህንና ፡ መልክተኛውን ፡ የሚ
ከራከር ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡ የገሀነም ፡
እሳት ፡ በውስጧ ፡ ዘውታሪ ፡
ሲኾን ፡ የተገባቿው ፡ መኾኑን ፡
አያውቁምን ? ይህ ፡ ታላቅ ፡
ውርደት ፡ ነው ።

64 መናፍቃን ፡ በልቦቻቸው ፡ ውስጥ፡
ያለውን ፡ ነገር ፡ የምትነግራቸው ፡
ሱራ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ መወረዷን ፡
ይፈራሉ ፤ አልላግጡ ፡ አላህ ፡
የምትፈሩትን ፡ ሁሉ ፡ ገላጭ ፡
ነው ፡ በላቸው ።

65 በእርግጥ ፡ ብትጠይቃቸው ፡ እኛ ፡
የምንዘባርቅና ፡ የምንጫወት ፡
ብቻ ፡ ነበርን ፡ ይላሉ ፤ በአላህና ፡
በአንቀጾቹ ፡ በመልክተኛውም ፡
ታላግጡ ፡ ነበራችሁን ? በላቸው ።

66 አታመካኙ ፤ ከእምነታችሁ ፡
በኋላ ፡ በእርግጥ ፡ ካዳችሁ ፤ ከና
ንተ ፡ አንዷን ፡ ጭፍራ ፡ ብንምር ፡
(ሌላዋን) ፡ ጭፍራ ፡ እነሱ ፡ ኃጢ
አተኞች ፡ በመኾናቸው ፡ እንቀ
ጣለን ።

67 መናፍቃንና ፡ መናፍቃት ፡ ከፊሎ
ቻቸው ፡ ከከፊሉ ፡ ናቸው ፤ በመ
ጥፎ ፡ ነገር ፡ ያዛሉ ፤ ከደግም ፡
ነገር ፡ ይከለክላሉ ፤ እጆቻቸው
ንም ፡ (ከልግስና) ፡ ይሰበስባሉ ፤
አላህን ፡ ረሱ ፤ ስለዚህ ፡ (እርሱ) ፡
ተዋቸው ፤ መናፍቃን ፡ አመጠ
ኞቹ ፡ እነሱ ፡ ናቸው ።

68 መናፍቃንንና ፡ መናፍቃትን ፡
ከሓዲዎችንም ፡ አላህ ፡ የገሀነ
ምን ፡ እሳት ፡ በውስጧ ፡ ዘውታ
ሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ ቃል ፡ ገብቶላቸ
ዋል ፤ እርሷ ፡ በቂያቸው ፡ ናት ፡
አላህም ፡ ረግሟቸዋል ፤ ለነርሱም
ዘውታሪ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ።

69 እንደነዚያ ፡ ከናንተ ፡ በፊት ፡
እንደ ፡ ነበሩት ፡ ናችሁ ፤ ከናንተ ፡
ይበልጥ ፡ በኀይል ፡ የበረቱ ፡ በገ
ንዘቦችም ፡ በልጆችም ፡ ይበልጥ ፡
የበዙ ፡ ነበሩ ፡ በዕድላቸውም ፡
ተጠቀሙ ፤ እነዚያም ፡ ከናንተ ፡
በፊት ፡ የነበሩት ፡ በዕድላቸው ፡
እንደ ፡ ተጠቀሙ ፡ በዕድላችሁ ፡
ተጠቀማችሁ ፡ እንደነዚያም ፡
እንደ ፡ ዘባረቁት ፡ ዘባረቃችሁ ፡
እነዚያ ፡ ሥራዎቻቸው ፡ በቅርቢ
ቱም ፡ በመጨረሻይቱም ፡ ዓለም ፡

ተበላሹ ፤ እነዚያም ፡ ከሳሪዎቹ ፡ እነሱ ፡ ናቸው ።

70 የነዚያ ፡ ከናንተ ፡ በፊት የነበሩት ፡ የኑሕ ፡ ሕዝቦች ፡ የዓድና ፡ የሠሙድም ፡ የኢብራሂምም ፡ ሕዝቦች ፡ የመድየን ፡ ባለቤቶችና ፡ የተገልባጮቹም ፡ ከተሞች ፡ ወሬ ፡ አልመጣላቸውምን ? መልክተኞቻቸው ፡ በታምራት ፡ መጧቸው ፤ አላህም ፡ የሚበድላቸው ፡ አልነበረም ፤ ግን ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ የሚበድሉ ፡ ነበሩ ።

71 ምእምናንና ፡ ምእምናትም ፡ ከፊሎቻቸው ፡ ለከፊሉ ፡ ረዳቶች ፡ ናቸው ፤ በደግ ፡ ነገር ፡ ያዛሉ ፤ ከክፉም ፡ ይከለክላሉ ፤ ሶላትንም ፡ ይሰግዳሉ ፤ ዘካንም ፡ ይሰጣሉ ፤ አላህንና ፡ መልክተኛውንም ፡ ይታዘዛሉ ፤ እነዚያን ፡ አላህ ፡ በእርግጥ ፡ ያዝንላቸዋል ፤ አላህ ፡ አሸናፊ ፡ ጥበበኛ ፡ ነውና ።

72 አላህ ፡ ምእምናንንና ፡ ምእምናትን ፡ ከስሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱባቸውን ፡ ገነቶች ፡ በውስጣቸው ፡ ዘውታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ በመኖሪያ ፡ ገነቶችም ፡ ውስጥ ፡ መልካም ፡ መኖሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ቃል ፡ ገብቶላቸዋል ፤ ከአላህም ፡ የኾነው ፡ ውዴታ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ እርሱ ፡ ታላቅ ፡ ዕድል ፡ ነው ።

73 አንተ ፡ ነቢዩ ፡ ሆይ ፡ ከሓዲዎችንና ፡ መናፍቃንን ፡ ታገል ፤ በነሱም ፡ ላይ ፡ ጨክን ፤ መኖሪያቸውም ፡ ገሀነም ፡ ናት ፤ መመለሻይቱም ፡ ከፋች ።

74 ምንም ፡ ያላሉ ፡ ለመኾናቸው ፡ በአላህ ፡ ይምላሉ ፤ የክሕደትንም ፡ ቃል ፡ በእርግጥ ፡ አሉ ፤ ከእስልምናቸውም ፡ በኋላ ፡ ካዱ ፤ ያላገኙትንም ፡ ነገር ፡ (1) አሰቡ፡ አላህም ፡ ከችሮታው ፡ መልክተኛውም ፡ (እንደዚሁ) ፡ ያከበራቸው ፡ መኾኑን ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡ አልጠሉም ፤ ቢጸጸቱም ፡ ለነሱ ፡ የተሻለ ፡ ይኾናል ፤ ቢሸሹም ፡ አላህ ፡ በቅርቢቱና ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ዓለም ፡ አሳማሚን ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣቸዋል ፤ ለነሱም ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ወዳጅና ፡ ረዳት ፡ የላቸውም ።

75 ከነሱም ፡ አላህን ፡ ከችሮታው ፡ ቢሰጠን ፡ በእርግጥ ፡ እንመጸውታለን ፡ ከመልካሞቹም ፡ በእርግጥ ፡ እንኾናለን ፡ ሲል ፡ ቃል ፡ የተጋባ ፡ አልለ ፤

76 ከችሮታውም ፡ በሰጣቸው ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ሰሰቱ ፡ እነሱ ፡ (ኪዳናቸውን) ፡ የተዉ ፡ ኾነውም ፡ ዞሩ ።

77 አላህንም ፡ ቃል ፡ የገቡለትን ፡ በማፍረሳቸውና ፡ ይዋሹትም ፡ በነበሩት ፡ ምክንያት ፡ እስከሚገናኙት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ንፍቅናን ፡ አስከተላቸው ።

78 አላህ ፡ ምስጢራቸውንና ፡ ውይይታቸውን ፡ የሚያውቅ ፡ መኾኑን ፡ አላህም ፡ ሩቆችን ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ዐዋቂ ፡ መኾኑን ፡ አያውቁምን ?

79 እነዚያ ፡ ከምእምናን ፡ በምጽዋቶች ፡ ፈቃደኛ ፡ የኾኑትን ፡ እነዚያንም ፡ የችሎታቸውን ፡ ያክል ፡ እንጅ ፡ የማያገኙትን ፡ ሰዎች ፡ የሚያነውሩ ፡ ከነሱም ፡ የሚሳለቁ ፡ አላህ ፡ ከነሱ ፡ ይሳለቅባቸዋል ፤ (ይቀጣቸዋል) ፡ ለነሱም ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ።

1 ነቢዩን ፡ መግደልን ።



80 ለነርሱ ፡ ምሕረትን ፡ ለምንላቸው ፤ ወይም ፡ ለነሱ ፡ ምሕረትን ፡ አትለምንላቸው ፤ (እኩል ፡ ነው) ። ለነሱ ፡ ሰባ ፡ ጊዜ ፡ ምሕረትን ፡ ብትለምንላቸው ፡ አላህ ፡ ለነሱ ፡ በፍጹም ፡ አይምርም ፡ ይኽ ፡ እነርሱ ፡ በአላህና ፡ በመልክተኛው ፡ በመካዳቸው ፡ ነው ፤ አላህም ፡ አመጠኞች ፡ ሕዝቦችን ፡ አያቀናም ።

81 እነዚያ ፡ ከዘመቻ ፡ የቀሩት ፡ ከአላህ ፡ መልክተኛ ፡ በኋላ ፡ በመቀመጣቸው ፡ ተደሰቱ ፤ በአላህም ፡ መንገድ ፡ በገንዘቦቻቸውና ፡ በነፍሶቻቸው ፡ መታገልን ፡ ጠሉ ፤ በሐሩር ፡ አትኺዱ ፡ አሉም ፤ የገሀነም ፡ እሳት ፡ ተኳሳነቱ ፡ በጣም ፡ የበረታ ፡ ነው ፡ በላቸው ። የሚያውቁ ፡ ቢኾኑ ፡ ኖሮ ፡ (አይቀሩም ፡ ነበር) ።

82 ጥቂትንም ፡ ይሳቁ ፤ ይሠሩት ፡ በነበሩትም ፡ ዋጋ ፡ ብዙን ፡ ያለቅሱ ፤

83 ከነሱም ፡ ወደ ፡ ኾነችው ፡ ጭፍራ ፡ አላህ ፡ ቢመልስህ ፡ (ከአንተ ፡ ጋር) ፡ ለመውጣትም ፡ ቢያስፈቅዱህ ፡— ከኔ ፡ ጋር ፡ በፍጹም ፡ አትወጡም ፤ ከኔም ፡ ጋር ፡ ጠላትን ፡ አትዋጉም ፤ እናንተ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ መቀመጥን ፡ ወዳችኋልና ፤ ከተቀማጮቹ ፡ ጋርም ፡ ተቀመጡ ፡ በላቸው ።

84 ከነሱም ፡ በአንድም ፡ በሞተ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ፈጽሞ ፡ አትስገድ ፤ በመቃብሩም ፡ ላይ ፡ አትቁም ፤ እነሱ ፡ በአላህና ፡ በመልክተኛው ፡ ክደዋልና ፤ እነሱም ፡ አመጠኞች ፡ ኾነው ፡ ሞተዋልና ።

85 ገንዘቦቻቸውና ፡ ልጆቻቸውም ፡ አይድነቁህ ፤ አላህ ፡ የሚሻው ፡ በቅርቢቱ ፡ ዓለም ፡ በነሱ ፡ ሊቀጣቸውና ፡ ከሓዲዎችም ፡ ኾነው ፡ ነፍሶቻቸው ፡ እንዲወጡ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

86 በአላህ ፡ እመኑ ፤ ከመልክተኛውም ፡ ጋር ፡ ኾናችሁ ፡ ታገሉ ፤ በማለት ፡ ምዕራፍ ፡ በተወረደች ፡ ጊዜ ፡ ከነሱ ፡ የሰፊ ፡ ሀብት ፡ ባለቤቶች ፡ የኾኑት ፡ (ለመቅረት) ፡ ፈቃድ ፡ ይጠይቁሃል ፤ ከተቀማጮቹ ፡ ጋርም ፡ እንኹን ፤ ተዎን ፤ ይሉሃል ።

87 በቤት ፡ ከሚቀሩት ፡ ጋር ፡ መኾናቸውን ፡ ወደዱ ፤ በልቦቻቸውም ፡ ላይ ፡ (ዝገት) ፡ ታተመባቸው ፤ ስለዚህ ፡ እነሱ ፡ አያውቁም ።

88 ግን ፡ መልክተኛው ፡ እነዚያም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያመኑት ፡ በገንዘቦቻቸውም ፡ በነፍሶቻቸውም ፡ ታገሉ ፤ እነዚያም ፡ መልካሞች ፡ ሁሉ ፡ ለነሱ ፡ ናቸው ፤ እነዚያም ፡ እነሱ ፡ ምኞታቸውን ፡ ያገኙ ፡ ናቸው ።

89 ለነሱም ፡ ገነቶችን ፡ በሥራቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱባቸውን ፡ በውስጣቸው ፡ ዘውታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ አላህ ፡ አዘጋጅቶላቸዋል ፤ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ማግኘት ፡ ነው ።

90 ከአዕራቦችም ፡ (1) ይቅርታ ፡ ፈላጊዎቹ ፡ ለነሱ ፡ እንዲፈቀድላቸው ፡ መጡ ፤ እነዚያ ፡ አላህንና ፡ መልክተኛውን ፡ የዋሹትም ፡ ተቀመጡ ፤ ከነሱ ፡ እነዚያን ፡ የካዱትን ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ በእርግጥ ፡ ይነካቸዋል ።

1 ከዓረብ ፡ ዘላኖች ።

91 በደካሞች ፡ ላይ ፡ በበሽተኞችም ፡ ላይ ፡ በነዚያም ፡ የሚያወጡት ፡ ገንዘብ ፡ በማያገኙት ፡ ላይ ፡ ለአላህና ፡ ለመልክተኛው ፡ ፍጹም ፡ ታዛገሮች ፡ ከኾኑ ፡ (ባይወጡም) ፡ ኃጢአት ፡ የለባቸውም ፤ በበጎ ፡ አድራጊዎች ፡ ላይ ፡ (የወቀሳ) ፡ መንገድ ፡ ምንም ፡ የለባቸውም ፡ አላህም ፡ መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።

92 በነዚያም ፡ ልትጫናቸው ፡ (1) በመጡህ ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የምጭናችሁ ፡ (አጋሰስ) ፡ አላገኝም ፤ ያልካቸው ፡ ስትኾን ፡ የሚያወጡት ፡ ገንዘብ ፡ ባለማግኘታቸው ፡ ለማዘናቸው ፡ ዓይኖቻቸው ፡ እንባን ፡ እያፈሰሱ ፡ በዞሩት ፡ ላይ ፡ (የወቀሳ ፡ መንገድ) ፡ የለባቸውም) ።

93 (የወቀሳ) ፡ መንገዱ ፡ በነዚያ ፡ እነሱ ፡ ባለጸጋዎች ፡ ኾነው ፡ ሳሉ ፡ ለመቅረት ፡ ፈቃድ ፡ በሚጠይቁህ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ከቀሪዎቹ ፡ ጋር ፡ መኾናቸውን ፡ ወደዱ ፤ አላህም ፡ በልቦቻቸው ፡ ላይ ፡ አተመባቸው ፤ ስለዚህ ፡ እነሱ ፡ አያውቁም ።

★ ★ ★

94 ወደነሱ ፡ በተመለሳችሁ ፡ ጊዜ ፡ ምክንያታቸውን ፡ ያቀርቡላችኋል፤ አታመካኙ ፤ እናንተን ፡ ፈጽሞ ፡ አናምንም ፤ አላህ ፡ ከወሬዎቻችሁ ፡ በእርግጥ ፡ ነግሮናልና ፡ አላህም ፡ ሥራችሁን ፡ በእርግጥ ፡ ያያል ፤ መልክተኛውም ፡ (እንደዚሁ) ፤ ከዚያም ፡ ሩቅንና ፡ ቅርብን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ወደ ፡ ኾነው ፡ (አላህ) ፡ ትመለሳላችሁ ፡ ወዲያውም ፡ ትሠሩት ፡ የነበራችሁትን ፡ ሁሉ ፡ ይነግራችኋል ፡ በላቸው ።

95 ወደነሱ ፡ በተመለሳችሁ ፡ ጊዜ ፡ እንድትተውዋቸው ፡ ለናንተ ፡ በእርግጥ ፡ በአላህ ፡ ይምላሉ ፤ እነሱንም ፡ ተውዋቸው ፤ እነሱ ፡ እርኩሶች፡ ናቸውና ፤ ይሠሩትም ፡ በነበሩት ፡ ዋጋ ፡ መኖሪያቸው ፡ ገሀነም ፡ ነው ።

96 ከነሱ ፡ ትወዱላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለናንተ ፡ ይምሉላችኋል ፤ ከነሱ ፡ ብትወዱም ፡ አላህ ፡ ከአመጠኞች ፡ ሕዝቦች ፡ አይወድም ።

97 አዕራቦች ፡ በክሕደትና ፡ በንፍቅና ፡ በጣም ፡ የበረቱ ፤ አላህም ፡ በመልክተኛው ፡ ላይ ፡ ያወረደውን ፡ ሕግጋት ፡ ባለማወቅ ፡ የተገቡ ፡ ናቸው ፡ አላህም ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።

98 ከአዕራቦችም ፡ (በአላህ ፡ መንገድ) ፡ የሚያወጣውን ፡ (ገንዘብ) ፡ ዕዳ ፡ አድርጎ ፡ የሚይዝ ፡ በናንተም ፡ ላይ ፡ የጊዜን ፡ መገለባበጥ ፡ የሚጠባበቅ ፡ ሰው ፡ አልለ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ጥፋቱ ፡ ይዞርባቸው ፤ አላህም ፡ ሰሚ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

99 ከአዕራቦችም ፡ በአላህና ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ የሚያምን ፡ የሚሰጣቸውንም ፡ (ምጽዋቶች) ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡ መቃረቢያዎችና ፡ ወደ ፡ መልክተኛው ፡ ጸሎቶች ፡ መዳረሻ ፡ አድርጎ ፡ የሚይዝ ፡ ሰው ፡ አልለ ፤ ንቁ ፤ እርሷ ፡ ለነሱ ፡ በእርግጥ ፡ አቃራቢ ፡ ናት ፤ አላህ ፡ በችሮታው ፡ ውስጥ ፡ (በገነቱ) ፡ በእርግጥ ፡ ያስገባቸዋል ፤ አላህ ፡ መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።

1 የሚጭኑበት ፡ አጋሠሥ ፡ ልትሰጣቸው ።



100 ከስደተኞቹና ፡ ከረዳቶቹም ፡ ሲኾኑ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ቀዳሚዎች ፡ እነዚያም ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡ የተከተሏቸው ፡ አላህ ፡ ከነሱ ፡ ወዷል ፤ (1) ከርሱም ፡ ወደዋል ፤ (2) በሥሮቻቸውም ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱባቸውን ፡ ገነቶች ፡ በውስጣቸው ፡ ዘለዓለም ፡ ነዋሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ ለነርሱ ፡ አዘጋጅቶላቸዋል ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ዕድል ፡ ነው ።

101 በዙሪያችሁም ፡ ካሉት ፡ ከዐረብ ፡ ዘላኖች ፡ መናፍቃን ፡ አልሉ ፤ ከመዲና ፡ ሰዎችም ፡ በንፍቅና ፡ ላይ ፡ በማመጽ ፡ የዘወተሩ ፡ አልሉ ፤ አታውቃቸውም ፤ እኛ ፡ እናውቃቸዋለን ፤ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ (3) እንቀጣቸዋለን ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ታላቅ ፡ ቅጣት ፡ ይመለሳሉ ።

102 ሌሎችም ፡ በኃጢአቶቻቸው ፡ የተናዘዙ ፡ (4) መልካም ፡ ሥራንና ፡ ሌላን ፡ መጥፎ ፡ ሥራ ፡ የቀላቀሉ ፡ አልሉ ፤ አላህ ፡ ከነሱ ፡ ጸጸታቸውን ፡ ሊቀበል ፡ ይከጀላል ፤ አላህ ፡ መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።

103 ከገንዘቦቻቸው ፡ ስትኾን ፡ በርሷ ፡ የምታጠራቸውና ፡ የምታፋፋቸው ፡ የኾነችን ፡ ምጽዋት ፡ ያዝ ፡ ለነሱም ፡ ጸልይላቸው ፤ ጸሎትህ ፡ ለነሱ ፡ እርካታ ፡ ነውና ፤ አላህም ፡ ሰሚ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

104 አላህ ፡ እርሱ ፡ ከባሮቹ ፡ ንስሓን ፡ የሚቀበል ፡ ምጽዋቶችንም ፡ የሚወስድ ፡ መኾኑን ፡ አላህም ፡ እርሱ ፡ ጸጸትን ፡ ተቀባይ ፡ አዛኝ ፡ መኾኑን ፡ አያውቁምን ?

105 በላቸውም ፡— ሥሩ ፤ አላህ ፡ ሥራችሁን ፡ በእርግጥ ፡ ያያልና ፡ መልክተኛውና ፡ ምእምናንም ፡ (እንደዚሁ ፡ ያያሉ) ። ሩቁንና ፡ ቅርቡን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ወደ ፡ ኾነውም ፡ (አላህ) ፡ በእርግጥ ፡ ትመለሳላችሁ ፡ ትሠሩትም ፡ የነበራችሁትን ፡ ሁሉ ፡ ይነግራችኋል ።

106 ሌሎችም ፡ ለአላህ ፡ ትእዛዝ ፡ የተቆዩ ፡ ሕዝቦች ፡ አልሉ ፤ ወይ ፡ ይቀጣቸዋል ፡ ወይም ፡ ከነሱ ፡ ላይ ፡ ጸጸትን ፡ ይቀበላል ፤ አላህም ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።

107 እነዚያም ፡ (ምእምናንን) ፡ ለመጉዳት ፡ ክሕደትንም ፡ ለማበርታት ፡ በምእምናንም ፡ መካከል ፡ ለመለያየት ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡ አላህንና ፡ መልክተኛውን ፡ የተዋጋውንም ፡ ሰው ፡ ለመጠባበቅ ፡ መስጊድን ፡ የሠሩት ፡ (ከነሱ ፡ ናቸው) ፤ መልካምን ፡ ሥራ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አልሻንም ፡ ሲሉም ፡ በእርግጥ ፡ ይምላሉ ፤ አላህም ፡ እነሱ ፡ በእርግጥ ፡ ውሸታሞች ፡ መኾናቸውን ፡ ይመሰክራል ።

108 በርሱ ፡ ውስጥ ፡ በፍጹም ፡ አትስገድ ፤ ከመጀመሪያ ፡ ቀን ፡ ይዞ ፡ በአላህ ፡ ፍራቻ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ (የቁባ) ፡ መስጊድ ፡ በውስጡ ፡ ልትሰግድበት ፡ ይልቅ ፡ የተገባው ፡ ነው ፤ በሱ ፡ ውስጥ ፡ መጥራራትን ፡ የሚወዱ ፡ ወንዶች ፡ አልሉ ፤ አላህም ፡ ተጥራሪዎችን ፡ ይወዳል ።

109 አላህን ፡ በመፍራትና ፡ ውዴታውን ፡ በመፈለግ ፡ ላይ ፡ ግንቡን ፡

1 ሥራቸውን ፡ ተቀብሏል ።
2 በተሰጣቸው ፡ ምንዳ ፡ ተደስተዋል ።
3 በወቀሳና ፡ በመቃብር ፡ ስቃይ ።
4 በአጥፊነታቸው ፡ ያመኑ ።

የመሠረተው ፡ ሰው ፡ ይበልጣ
ልን ? ወይስ ፡ ጕርፍ ፡ በሸረሸ
ረው ፡ ለመናድ ፡ በተቃረበ ፡
ገደል ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ግንቡን ፡
የመሠረተውና ፡ በርሱ ፡ (ይዞት) ፡
በገሀነም ፡ እሳት ፡ ውስጥ ፡ የወ
ደቀ ፡ (ይበልጣል ?) አላህም ፡ በደ
ለኞች ፡ ሕዝቦችን ፡ አይመራም ።
110 ያ ፡ የካቡት ፡ ግንባቸው ፡ ልቦቻ
ቸው ፡ (በሞት) ፡ ካልተቆራረጡ ፡
በቀር ፡ በልቦቻቸው ፡ ውስጥ ፡
የመጠራጠር ፡ ምክንያት ፡ ከመ
ኾን ፡ አይወገድም ፤ አላህም ፡
ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።
111 አላህ ፡ ከምእምናን ፡ ነፍሶቻቸ
ውንና ፡ ገንዘቦቻቸውን ፡ ገነት ፡
ለነሱ ፡ ብቻ ፡ ያላቸው ፡ በመኾን ፡
ገዛቸው ፤ በአላህ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡
ይጋደላሉ ፤ ይገድላሉም ፤ ይገደ
ላሉም ፤ በተውራት ፡ በኢንጅ
ልና ፡ በቁርአንም ፡ (የተነገረውን)
ተስፋ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አረጋገጠ ፡
ከአላህም ፡ የበለጠ ፡ በኪዳኑ ፡
የሚሞላ ፡ ማነው ? በዚያም ፡
በርሱ ፡ በተሻሻጣችሁበት ፡ ሽያ
ጫችሁ ፡ ተደሰቱ ፤ ይህም ፡ እርሱ፡
ታላቅ ፡ ዕድል ፡ ነው ።
112 (እነርሱ) ፡ ተጸጻቾዎች ፡ ተገዢ
ዎች ፡ አመስጋኞች ፡ ጿሚዎች፥
አጎንባሾች ፡ በግንባር ፡ ተደፊ
ዎች ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡ አዛዦች ፡
ከክፉም ፡ ከልካዮች ፡ የአላህንም ፡
ሕግጋት ፡ ጠባቂዎች ፡ ናቸው ፡
ምእምናንንም ፡ አብስር ።
113 ለነቢዩና ፡ ለነዚያ ፡ ላመኑት ፡
ለአጋሪዎቹ ፡ የዝምድና ፡ ባለቤ
ቶች ፡ ቢኾኑም ፡ እንኳ ፡ እነሱ ፡
(ከሐዲዎቹ) ፡ የእሳት ፡ ጓዶች ፡
መኾናቸው ፡ ከተገለጸላቸው ፡
በኋላ ፡ ምሕረትን ፡ ሊለምኑ ፡
የሚገባ ፡ አልነበረም ።
114 የኢብራሂምም ፡ ለአባቱ ፡ ምሕረ
ትን ፡ መለመን ፡ ለርሱ ፡ ገብቶ
ለት ፡ ለነበረችው ፡ ቃል ፡ (ለመም
ላት) ፡ እንጂ ፡ ለሌላ ፡ አልነበ
ረም ። እርሱም ፡ የአላህ ፡ ጠላት ፡
መኾኑ ፡ ለርሱ ፡ በተገለጸለት ፡
ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ራቀ ፤ (ተወው) ፤
ኢብራሂም ፡ በእርግጥ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ ታጋሽ ፡ ነውና ።
115 አላህም ፡ ሕዝቦችን ፡ ከአቀና
ቸው ፡ በኋላ ፡ የሚጠነቀቁትን ፡
(ሥራ) ፡ ለነሱ ፡ እስከሚገልጽላ
ቸው ፡ (እስከሚተውትም) ፡ ድረ
ስ ፡ ጥፋተኛ ፡ የሚያደርግ ፡ አይደ
ለም ፤ አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡
ዐዋቂ ፡ ነውና ።
116 አላህ ፡ የሰማያትና ፡ የምድር ፡
ንግሥና ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤
ሕያው ፡ ያደርጋል ፤ ይገድላልም ፤
ለናንተም ፡ ከርሱ ፡ በቀር ፡ ጠባ
ቂም ፡ ረዳትም ፡ የላችሁም ።
117 በነቢዩ ፡ በነዚያም ፡ በችግሪቱ ፡
ጊዜያት ፡ (በተቡክ ፡ ዘመቻ) ፡
ከነሱ ፡ የከፊሎቹ ፡ ልቦች ፡ (ለመ
ቅረት) ፡ ሊዘነበሉ ፡ ከተቃረቡ ፡
በኋላ ፡ በተከተሉት ፡ ስደተኞችና፡
ረዳቶች ፡ ላይ ፡ አላህ ፡ በእርግጥ ፡
ጸጸታቸውን ፡ ተቀበለ ፤ ከዚያም ፡
ከነሱ ፡ ንስሐ ፡ መግባታቸውን ፡
ተቀበለ ፤ እርሱ ፡ ለነሱ ፡ ርኅሩህ ፡
አዛኝ ፡ ነውና ።
118 በነዚያም ፡ በሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡
ምድር ፡ ከስፋትዋ ፡ ጋር ፡ በነሱ ፡
ላይ ፡ እስከ ፡ ጠበበች ፡ ነፍሶቻቸ
ውም ፡ በርሳቸው ፡ ላይ ፡ እስከ ፡
ተጠበበ ፡ ከአላህም ፡ ወደርሱ ፡
ቢኾን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ መጠጊያ ፡



አለመኖሩን ፡ እስከ ፡ አረጋገጡ ፡
ድረስ ፡ በተቆዩት ፡ ላይ ፡ (አላህ ፡
ጸጸትን ፡ ተቀበለ) ። ከዚያም ፡
ይጸጸቱ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ጸጸት ፡
መራቸው ፤ አላህ ፡ እርሱ ፡ ጸጸ
ትን ፡ ተቀባይ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።
119 እናንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላ
ህን ፡ ፍሩ ፤ ከውነተኞቹም ፡ ጋር ፡
ኹኑ ።
120 ለመዲና ፡ ሰዎችና ፡ ከአዕራብም ፡
በዙሪያቸው ፡ ላሉት ፡ ሰዎች ፡
ከአላህ ፡ መልክተኛ ፡ ወደኋላ ፡
ሊቀሩ ፡ ነፍሶቻቸውንም ፡ ከነ
ፍሱ ፡ አብልጠው ፡ ሊወዱ ፡
አይገባቸውም ፡ ነበር ፤ ይህ ፡
(ከመቅረት ፡ መከልከል) ፡ ለነ
ርሱ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ የሚጻፍ
ላቸው ፡ ቢኾን ፡ እንጅ ፡ በአላህ ፡
መንገድ ፡ ላይ ፡ ጥምም ፡ ድካ
ምም ፡ ረኃብም ፡ የማይነካቸው ፡
ከሐዲዎችንም ፡ የሚያስቆጭን ፡
ስፍራ ፡ የማይረግጡ ፡ ከጠላትም ፡
የሚጐዳን ፡ ነገር ፡ (መግደልን ፡
መማረክን ፡ መዝረፍን) ፡ የማያ
ገኙ ፡ በመኾናቸው ፡ ነው ። አላህ ፡
የመልካም ፡ ሠሪዎችን ፡ ምንዳ ፡
አያጠፋምና ።
121 ትንሽንም ፡ ትልቅንም ፡ ልግስና ፡
አይለግሱም ፡ ወንዝንም ፡ አያቋ
ርጡም ፡ አላህ ፡ ይሠሩት ፡ ከነበ
ረው ፡ የበለጠን ፡ ምንዳ ፡ ይመነ
ዳቸው ፡ ዘንድ ፡ ለነሱ ፡ የሚጻፍላ
ቸው ፡ ቢኾን ፡ እንጅ ።
122 ምእምናንም ፡ (ነቢዩ ፡ ጋር ፡ ካል
ኾኑ) ፡ በሙሉ ፡ ሊወጡ ፡ አይገ
ባም ፤ ከነሱ ፡ ውስጥ ፡ ከየክፍሉ ፡
አንዲት ፡ ጭፍራ ፡ ለምን ፡ አት
ወጣም ፤ (ሌሎቹ) ፡ ሃይማኖትን ፡
እንዲማሩና ፡ ወገኖቻቸውን ፡
ወደነርሱ ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡
እንዲጠነቀቁ ፡ ይገሥጹዋቸው ፡
ዘንድ ፡ (ለምን ፡ አይቀሩም) ።
123 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! እነዚ
ያን ፡ በአቅራቢያችሁ ፡ ያሉትን ፡
ከሓዲዎች ፡ ተዋጉ ፤ ከናንተም ፡
ብርታትን ፡ ያግኙ፤ አላህም ፡ ከሚ
ጠነቀቁት ፡ ጋር ፡ መኾኑን ፡
ዕወቁ ።
124 ሱራም ፡ (ምዕራፍ) ፡ በተወረደች ፡
ጊዜ ፡ ከነሱ ፡ (ከመናፍቃን) ፡
ውስጥ ፡ ማንኛችሁ ፡ ነው ? ይህቺ፤
(ምዕራፍ) ፡ እምነትን ፡ የጨመረ
ችለት ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ አልለ ፤
እነዚያ ፡ ያመኑትማ ፡ የሚደሰቱ ፡
ሲኾኑ ፡ እምነትን ፡ ጨመረችላ
ቸው ።
125 እነዚያም ፡ በልቦቻቸው ፡ ውስጥ ፡
በሽታ ፡ ያለባቸውማ ፡ በርክሰታ
ቸው ፡ ላይ ፡ ርክሰትን ፡ ጨመረ
ችላቸው ፤ እነሱም ፡ ከሓዲዎች ፡
ኾነው ፡ ሞቱ ።
126 በየዓመቱ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡
ሁለት ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ የሚሞ
ከሩ ፡ መኾናቸውን ፡ አያዩምን ?
ከዚያም ፡ አይጸጸቱምን ? እነሱም፡
አይገሠጹምን ?
127 (እነሱን ፡ የምታነሳ) ፡ ምዕራ
ፍም) ፡ በተወረደች ፡ ጊዜ ፡ አንድ፡
ሰው ፡ ያያችኋልን ? እያሉ ፡ ከፊ
ሎቻቸው ፡ ወደ ፡ ከፊሉ ፡ ይመለ
ከታሉ ፤ ከዚያም ፡ (ተደብቀው) ፡
ይኼዳሉ ፤ እነርሱ ፡ የማያውቁ ፡
ሕዝቦች ፡ በመኾናቸው ፡ አላህ ፡
ልቦቻቸውን ፡ አዞረ ።
128 ከጐሳችሁ ፡ የኾነ ፡ ችግራችሁ ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ ጥኑ ፡ የኾነ ፡ በና
ንተ ፡ (እምነት) ፡ ላይ ፡ የሚጓጓ ፡
በምእምናን ፡ ርኅሩህ ፡ አዛኝ ፡

የኾነ ፡ መልክተኛ ፡ በእርግጥ ፡
መጣላችሁ ።
129 ቢያፈገፍጉም ፡ አላህ ፡ በቂዬ ፡
ነው ፤ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡
የለም ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተጠጋሁ ፤
እርሱም ፡ የታላቁ ፡ ዐርሽ ፡ ጌታ ፡
ነው ፡ በላቸው ።

## ምዕራፍ ፡ 10፡ ዩኑስ ። ክፍል ፡ 11 ።

10ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ዩኑስ ፡ (የዮናስ ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡ የወ
ረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 109 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 አ. ለ. ረ. (አሊፍ ፡ ላም ፡ ራ) ፡
(1) ይህቺ ፡ (ሱራ) ፡ ጥበብ ፡ ከተ
መላው ፡ መጽሐፍ ፡ (ከቁርአን) ፡
አንቀጾች ፡ ናት ።
2 ሰዎችን ፡ አስፈራራ ፤ እነዚያንም ፡
ያመኑትን ፡ ለነሱ ፡ ከጌታቸው ፡
ዘንድ ፡ መልካም ፡ ምንዳ ፡ ያላ
ቸው ፡ መኾኑን፡ አብስር ፡ በማ
ለት ፡ ከነርሱው ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ ራእይን ፡ ማውረ
ዳችን ፡ ለሰዎች ፡ ድንቅ ፡ ኾነባ
ቸውን ? ከሓዲዎቹ ፡— ይህ ፡ በእ
ርግጥ ፡ ግልጽ ፡ ድግምተኛ ፡
ነው ፡ አሉ ።
3 ጌታችሁ ፡ ያ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድ
ርን ፡ በስድስት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡
የፈጠረ ፡ አላህ ፡ ነው ፤ ከዚያም ፡
ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ የሚያስተናብር ፡
ሲኾን ፡ በዐርሹ ፡ ላይ ፡ (ስል
ጣኑ) ፡ ተደላደለ ፤ ከርሱ ፡ ፈቃድ ፡
በኋላ፡ ቢኾን ፡ እንጂ ፡ አንድም ፡
አማላጅ ፡ የለም ፤ ይሃችሁ ፡ አላህ ፡

1 እኔ ፡ አላህ ፡ ነኝ ፡ እያለሁ ።

ጌታችሁ ፡ ነውና ፡ ተገዙት ፤ አት
ገሠጹምን ?
4 ሁላችሁም ፡ ኾናችሁ ፡ መመለሻ
ችሁ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ነው ፤ (ይህ
ም) ፡ የተረጋገጠ ፡ የአላህ ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ ነው ፤ እርሱ ፡ መፍጠርን ፡
ይጀምራል ፤ ከዚያም ፡ እነዚያን ፡
ያመኑትንና ፡ መልካም ፡ የሠሩ
ትን ፡ በትክክል ፡ ይመነዳ ፡
ዘንድ ፡ ይመልሰዋል ፤ እነዚያ ፡
የካዱትም ፡ ይክዱት ፡ በነበሩት ፡
ነገር ፡ ለነርሱ ፡ ከፈላ ፡ ውሃ ፡
የኾነ ፡ መጠጥና ፡ አሳማሚ ፡
ቅጣት ፡ አላቸው ።
5 እርሱ ፡ ያ ፡ ፀሐይን ፡ አንጸባራቂ ፡
ጨረቃንም ፡ አብሪ ፡ ያደረገ ፡
ነው ፤ የዓመታትን ፡ ቍጥርና ፡
ሒሳብን ፡ ታውቁ ፡ ዘንድም ፡
ለርሱ ፡ መስፈሪያዎችን ፡ (1)
የለካ ፡ ነው ፤ አላህ ፡ ይህንን ፡ በእ
ውነት ፡ እንጂ ፡ (በከንቱ) ፡ አልፈ
ጠረውም ፤ ለሚያውቁ ፡ ሕዝቦች ፡
አንቀጾችን ፡ ያብራራል ።
6 ሌሊትና ፡ ቀን ፡ በመተካካታ

1 በ28 ፡ ሌሊት ፡ ማደሪያዎችን ።



ቸው ፡ አላህም ፡ በሰማያትና ፡
በምድር ፡ ውስጥ ፡ በፈጠረው ፡
ሁሉ ፡ ለሚጠነቀቁ ፡ ሕዝቦች ፡
ምልክቶች ፡ አሉሉ ።
7 እነዚያ ፡ መገናኘታችንን ፡ የማይ
ፈሩ ፡ ቅርቢቱንም ፡ ሕይወት ፡
የወደዱ ፡ በሷም ፡ የረኩ ፡ እነዚ
ያም ፡ እነሱ ፡ ከአንቀጾቻችን ፡
ዘንጊዎች ፡ የኾኑ ፡
8 እነዚያ ፡ ይሠሩት ፡ በነበሩት ፡
ምክንያት ፡ መኖሪያቸው ፡ በእሳት
ውስጥ ፡ ነው ።
9 እነዚያ ፡ ያመኑና ፡ መልካም ፡
ሥራዎችን ፡ የሠሩ ፡ ጌታቸው ፡
በእምነታቸው ፡ ምክንያት ፡ (የገ
ነትን ፡ መንገድ) ፡ ይመራቸዋል ፤
ከሥራቸው ፡ ወንዞች ፡ ይፈስሳሉ ፤
በመጠቀሚያ ፡ ገነቶች ፡ ውስጥ ፡
ይኖራሉ ።
10 በርሷም ፡ ውስጥ ፡ ጸሎታቸው ፡
ጌታችን ፡ ሆይ ! ጥራት ፡ ይገባህ ፡
(ማለት) ፡ ነው ፤ በርሷ ፡ ውስጥ ፡
መከባበሪያቸውም ፡ ሰላም ፡ መባ
ባል ፡ ነው ፤ የመጨረሻ ፡ ጸሎታ
ቸውም ፡ ምስጋና ፡ ለዓለማት ፡
ጌታ ፡ ይኹን ፡ (ማለት) ፡ ነው ።
11 አላህ ፡ ለሰዎች ፡ ደግን ፡ ነገር ፡
ለማግኘት ፡ እንደ ፡ መቻኮላቸው ፡
(አጥፋን ፡ ሲሉት) ፡ ክፉን ፡
ነገር ፡ ቢያስቸኩል ፡ ኖሮ ፡ ጊዜያ
ቸው ፡ ወደነሱ ፡ በተፈጸመ ፡
ነበር ፡ እነዚያንም ፡ መገናኘታ
ችንን ፡ የማይፈሩትን ፡ በጥመታ
ቸው ፡ ውስጥ ፡ የሚዋልሉ ፡
ሲኾኑ ፡ እንተዋቸዋለን ።
12 ሰውንም ፡ ጉዳት ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡
በጐኑ ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ ወይም ፡
ተቀምጦ ፡ ወይም ፡ ቆሞ ፡ ይለም
ነናል ፤ ጉዳቱንም ፡ ከሱ ፡ ላይ ፡
በገለጥንለት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አገ
ኘው ፡ ጉዳት ፡ እንዳልጠራን ፡
ኾኖ ፡ ያልፋል ፤ እንደዚሁ ፡ ለድ
ንበር ፡ አላፊዎች ፡ ይሠሩት ፡ የነ
በሩት ፡ ሥራ ፡ ተሸለመላቸው ።
13 ከናንተ ፡ በፊት ፡ የነበሩትንም ፡
የክፍል ፡ ዘመናት ፡ ሰዎች ፡ መል
ክተኞቻቸው ፡ በማስረጃዎች ፡
የመጧቸው ፡ ሲኾኑ ፡ በበደሉና ፡
የማያምኑም ፡ በኾኑ ፡ ጊዜ ፡
በእርግጥ ፡ አጠፋናቸው ፤ እንደ
ዚሁ ፡ ተንኮለኞችን ፡ ሕዝቦች ፡
እንቀጣለን ።
14 ከዚያም ፡ እንዴት ፡ እንደምት
ሠሩ ፡ ልንመለከት ፡ ከነሱ ፡
በኋላ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ምትኮች ፡
አደረግናችሁ ።
15 አንቀጾቻችንም ፡ ግልጽ ፡ ኾነው ፡
በነርሱ ፡ ላይ ፡ በተነበቡላቸው ፡
ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ መገናኘታችንን ፡
የማይፈሩት ፤ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ የኾ
ነን ፡ ቁርአን ፡ አምጣልን ፡ ወይም
ለውጠው ፡ ይላሉ ፡ ፡— እኔ ፡
ከራሴ ፡ በኩል ፡ ልለውጠው ፡
አይገባኝም ፤ ወደኔ ፡ የሚወርደ
ውን ፡ እንጂ ፡ አልከተልም ፡
እኔ ፡ ከጌታዬ ፡ ባምጽ ፡ የታላ
ቅን ፡ ቀን ፡ ቅጣት ፡ እፈራለሁ ፡
በላቸው ።
16 አላህ ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
ባላነበብኩትም ፡ (አላህ) ፡ እር
ሱን ፡ ባላሳወቃችሁም ፡ ነበር ፡
በናንተም ፡ ውስጥ ፡ ከርሱ ፡
በፊት ፡ (ምንም ፡ ሳልል) ፡ ብዙን ፡
ዕድሜ ፡ (1) በእርግጥ ፡ ኖሬአ
ለሁ ፤ አታውቁምን ?
17 በአላህም ፡ ላይ ፡ እብለትን ፡ ከቀ
ጣጠፈ ፡ ወይም ፡ በአንቀጾቹ ፡ ከአ

1 አርባ ፡ ዓመት ።

ስተባበለ ፡ ይበልጥ ፡ በዳይ ፡
ማን ፡ ነው ? እነሆ ፡ አመጠኞች ፡
አይድኑም ።
18 ከአላህም ፡ ሌላ ፡ የማይጐዳቸ
ውን ፡ የማይጠቅማቸውንም ፡
ይገገዛሉ ፤ እነዚህም ፡ አላህ ፡
ዘንድ ፡ አማላጆቻችን ፡ ናቸው ፡
ይላሉ ፤ አላህን ፡ በሰማያትና ፡
በምድር ፡ ውስጥ ፡ የማያውቀው ፡
ነገር ፡ ኖሮ ፡ ትነግሩታላችሁን ?
በላቸው ፤ ከሚያጋሩት ፡ ሁሉ ፡
ጠራ ፤ ላቀም ።
19 ሰዎችም ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አልነበሩም ፤ ተለያዩም ፤
ከጌታህ ፡ ያለፈች ፡ ቃልም ፡ ባል
ነበረች ፡ ኖሮ ፡ በርሱ ፡ በሚለያዩ
በት ፡ ነገር ፡ በመካከላቸው ፡ በእ
ርግጥ ፡ (በቶሎ) ፡ በተፈረደ ፡
ነበር ።
20 በርሱ ፡ ላይም ፡ ከጌታው ፡ የኾ
ነች ፡ ታምር ፡ ለምን ፡ አትወረድ
ለትም ፡ ይላሉ ፤ ፡—ሩቅ ፡ ነገርም ፡
ሁሉ ፡ የአላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ተጠ
ባበቁም ፤ እኔ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡
ከሚጠባበቁት ፡ ነኝና ፡ በላቸው ።
21 ሰዎችንም ፡ ካገኛቸው ፡ ጉዳት ፡
በኋላ ፡ እዝነትን ፡ (ዝናምና ፡
ምቾትን) ፡ ባቀመስናቸው ፡ ጊዜ ፡
ወዲያውኑ ፡ ለነሱ ፡ በታምራቶ
ቻችን ፡ (በማላገጥ) ፡ ተንኮል ፡
ይኖራቸዋል ፤ አላህ ፡ ቅጣተ ፡
ፈጣን ፡ ነው ፤ መልክተኞቻችን ፡
(1) የምትመክሩትን ፡ ነገር ፡ በእ
ርግጥ ፡ ይጽፋሉ ፡ በላቸው ።
22 እርሱ ፡ (አላህ) ፡ ያ ፡ በየብስና ፡
በባሕር ፡ የሚያስኼዳችሁ ፡ ነው ፤
በመርከቦችም ፡ ውስጥ ፡ በኾናች
ሁና ፡ በነርሱም ፡ (1) በመልካም ፡
ነፋስ ፡ በርሷ ፡ የተደሰቱ ፡ ኾነው ፡
(መርከቦቹ) ፡ በተንሻለሉ ፡ ጊዜ ፡
ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ትመጣባታለች ፤
ከየስፍራውም ፡ ማዕበል ፡ ይመጣ
ባቸዋል ፤ እነሱም ፡ (ለጥፋት) ፡ የ
ተከበቡ ፡ መኾናቸውን ፡ ያረጋግ
ጣሉ ፤ (ያንጊዜ) ፡ አላህን ፡ ከዚች ፡
(ጭንቀት) ፡ ብታድነን ፡ በእር
ግጥ ፡ ከአመስጋኞቹ ፡ እንኾና
ለን ፡ ሲሉ ፡ ሃይማኖትን ፡ ለርሱ ፡
ብቻ ፡ ያጠሩ ፡ ኾነው ፡ ይለምኑ
ታል ።
23 በአዳናቸውም ፡ ጊዜ ፡ እነሱ ፡
ወዲያውኑ ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ ወሰን ፡ ያልፋሉ ፤
እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ወሰን ፡
ማለፋችሁ ፡ (ጥፋቱ) ፡ በነፍሶ
ቻችሁ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ (እር
ሱም) ፡ የቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡
መጠቀሚያ ፡ ነው ፤ ከዚያም ፡
መመለሻችሁ ፡ ወደኛ ፡ ነው ፤
ትሠሩት ፡ የነበራችሁትንም ፡
ሁሉ ፡ እንነግራችኋለን ።
24 የቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡ ምሳሌ ፡ (2)
ከሰማይ ፡ እንዳወረድነው ፡ ውሃ ፡
በርሱም ፡ ሰውና ፡ እንስሳዎች ፡
ከሚበሉት ፡ የምድር ፡ በቃይ ፡
ተቀላቅሎበት ፡ (እንደ ፡ ፋፋ ፡)
ምድርም ፡ ውበትዋን ፡በያዘችና ፡
ባጌጠች ፡ ጊዜ ፡ ባለቤቶችዋም ፡
በርሷ ፡ ላይ ፡ እነርሱ ፡ ቻዮች ፡
መኾናቸውን ፡ ባሰቡ ፡ ጊዜ ፡ ትእ
ዛዛችን ፡ ሌሊት ፡ ወይም ፡ ቀን ፡
መጥቶባት ፡ ትላንት ፡ እንዳልነ
በረች ፡ የታጨደች ፡ እንዳደረ
ግናት ፡ ብጤ ፡ ነው ፤ እንደዚሁም ፡

1 ተጠባባቂዎቹ ፡ መላእክት ።

1 በተሳፋሪዎቹ ።

2 ጊዜዋ ፡ በማጠርና ፡ በመጥፋት ።



ለሚያስተነትኑ ፡ ሕዝቦች ፡ አንቀ
ጾችን ፡ እናብራራለን ።
25 አላህም ፡ ወደ ፡ ሰላም ፡ አገር ፡ (1)
ይጠራል ፤ የሚሻውንም ፡ ሰው ፡
ወደ ፡ ቀጥተኛው ፡ መንገድ ፡
ይመራል ።
26 ለነዚያ ፡ መልካም ፡ ለሠሩት ፡
መልካም ፡ ነገርና ፡ ጭማሪም ፡
አላቸው ፤ ፊቶቻቸውንም ፡ ጥቁ
ረትና ፡ ውርደት ፡ አይሸፍናቸ
ውም ፤ እነዚያ ፡ የገነት ፡ ሰዎች ፡
ናቸው ፤ እነርሱ ፡ በውስጧ ፡ ዘው
ታሪዎች ፡ ናቸው ።
27 ለነዚያም ፡ ኃጢአቶችን ፡ ለሠ
ሩት ፡ የኃጢአቲቱ ፡ ቅጣት ፡ በብ
ጤዋ ፡ አለቻቸው ፤ ውርደትም ፡
ትሸፍናቸዋለች ፤ ለነሱ ፡ ከአላህ ፡
(ቅጣት) ፡ ጠባቂ ፡ የላቸውም ፤
ፊቶቻቸው ፡ ከጨለመ ፡ ሌሊት ፡
ቁራጮች ፡ እንደ ፡ ተሸፈኑ ፡ ይኾ
ናሉ ፤ እነዚያ ፡ የእሳት ፡ ሰዎች ፡
ናቸው ፤ እነርሱ ፡ በውስጧ ፡ ዘለ
ዓለም ፡ ነዋሪዎች ፡ ናቸው ።
28 ሁሉንም ፡ የምንሰበስባቸውን ፡
ከዚያም ፡ ለነዚያ ፡ ለአጋሩት ፡
እናንተም ፡ ተጋሪዎቻችሁም ፡ (2)
ስፍራችሁን ፡ ያዙ ፡ የምንልበ
ትን ፡ ተጋሪዎቻቸውም ፡ እኛን ፡
ትገገዙ ፡ አልነበራችሁም ፡ የሚሉ
ዋቸው ፡ሲኾኑ ፡ በመካከላቸው ፡
የምንለይበትን ፡ ቀን ፡ (አስታ
ውስ) ።
29 (ጣዖታቶቹ ፡ ለኛ) ፡ ከመገዛታ
ችሁ ፡ በእርግጥ ፡ ዘንጊዎች ፡
ለመኾናችንም ፡ በኛና ፡ በናንተ ፡
መካከል ፡ የአላህ ፡ መስካሪነት ፡
በቃ ፡ (ይሏቸዋል) ።
30 በዚያ ፡ ቀን ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ ያሳለ
ፈችውን ፡ ሥራ ፡ ታውቃለች ፤
(አጋሪዎች) ፡ ወደ ፡ አላህም ፡ እው
ነተኛ ፡ ወደኾነው ፡ ጌታቸው ፡ ይ
መለሳሉ ፤ ከነሱም ፡ ይቀጣጥፉት ፡
የነበሩት ፡ ነገር ፡ ይጠፉቸዋል ።
31 ከሰማይና ፡ ከምድር ፡ ሲሳይን ፡
የሚሰጣችሁ ፡ ማን ፡ ነው ? መስ
ሚያዎችንና ፡ ማያዎችንስ ፡ የፈ
ጠረ ፡ ማን ፡ ነው ? ከሙትም ፡
ሕያውን ፡ የሚያወጣ ፡ ከሕያ
ውም ፡ ሙትን ፡ የሚያወጣስ ፡
ማን ፡ ነው ? ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ የሚያ
ስተናብርስ ፡ ማን ፡ ነው ? በላ
ቸው ፤ በእርግጥም ፡ አላህ ፡ ነው ፡
ይሉሃል ፤ ታዲያ ፡ (ለምን ፡ ታጋ
ራላችሁ ?) አትፈሩትምን ? በላ
ቸው ።
32 ይሃችሁም ፡ እውነተኛ ፡ ጌታችሁ ፡
አላህ ፡ ነው ፤ ከእውነትም ፡ በኋላ ፡
ጥመት ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡
አለለ ? (ከውነት) ፡ እንዴት ፡
ትዝዞራላችሁ ?
33 እንደዚሁ ፡ የጌታህ ፡ ቃል ፡ በነ
ዚያ ፡ ባምመጡት ፡ ላይ ፡ እነርሱ ፡
የማያምኑ ፡ መኾናቸው ፡ ተረጋ
ገጠች ።
34 ፡—ከምታጋሩዋቸው ፡ (ጣዖታት) ፡
ውስጥ ፡ መፍጠርን ፡ የሚጀምር ፡
ከዚያም ፡ የሚመልሰው ፡ አለለን?
በላቸው ፡— አላህ ፡ መፍጠርን ፡
ይጀምራል ፤ (1) ከዚያም ፡ ይመ
ልሰዋል ፤ ታዲያ ፡ (ከእምነት) ፡
እንዴት ፡ ትዝዞራላችሁ ? በላቸው ።
35 ፡—ከምታጋሩዋቸው ፤ (2) ወደ ፡ እ
ውነት ፡ የሚመራ ፡ አለን ? በላቸው ፤

1 ወደ ፡ ገነት ።

2 ጣዖታቶቻችሁ ።

1 ያልነበረን ፡ ያስገኛል ።

2 ለአላህ ፡ ባላጋራ ፡ ከምታደርጓቸው ፡ ጣዖ
ታት ።

አላህ ፡ ወደ ፡ እውነቱ ፡ ይመራል ፤
ወደ ፡ እውነት ፡ የሚመራው ፡
ሊከተሉት ፡ የተገባው ፡ ነውን ?
ወይስ ፡ ካልተመራ ፡ በስተቀር ፡
የማይመራው ? ለናንተም ፡ ምን ፡
(አስረጅ) ፡ አላችሁ ? እንዴት ፡
(በውሸት) ፡ ትፈርዳላችሁ ? በላ
ቸው ።
36 አብዛኞቻቸውም ፡ ጥርጣሬን ፡
እንጂ ፡ አይከተሉም ፤ ጥርጣሬ ፡
ከእውነት ፡ ምንም፡ አያብቃቃም፤
አላህ ፡ የሚሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ዐ
ዋቂ ፡ ነው ።
37 ይህም ፡ ቁርአን ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡
(ከኾነ ፡ ፍጡር) ፡ የተቀጠፈ ፡
ሊኾን ፡ አይገባውም ፤ ግን ፡ ያንን፡
ከርሱ ፡ በፊት ፡ ያለውን ፡ (መጽ
ሐፍ) ፡ የሚያረጋግጥና ፡ በመጽ
ሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የሚዘረ
ዝር ፡ በርሱ ፡ ጥርጣሬ ፡ የሌለ
በት ፡ ሲኾን ፡ ከዓለማት ፡ ጌታ ፡
(የተወረደ) ፡ ነው ።
38 በእውነትም ፡ (ሙሐመድ) ፡ ቀጣ
ጠፈው ፡ ይላሉን ? ይህ ፡ ከኾነ ፡
መሰሉን ፡ (አንዲት) ፡ ሱራ ፡
አምጡ ፤ ከአላህም ፡ ሌላ ፡ የቻላ
ችሁትን ፡ ሁሉ ፡ (ረዳት) ፡ ጥሩ ፤
እውነተኞች ፡ እንደኾናችሁ ፡ (ተ
ጋግዛችሁ ፡ አምጡ) ፡ በላቸው ።
39 ይልቁንም ፡ (ከቁርአን) ፡ እውቀ
ቱን ፡ ባላዳረሱት ፡ ፍቹም ፡ ገና ፡
ባልመጣቸው ፡ ነገር ፡ አስተባ
በሉ ፤ እንደዚሁ ፡ እነዚያ ፡ ከነሱ ፡
በፊት ፡ የነበሩት ፡ አስተባብለ
ዋል ፤ የበዳዮችም ፡ መጨረሻ ፡
እንዴት ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ተመ
ልከት ።
40 ከነርሱም ፡ ውስጥ ፡ (ወደፊት) ፡
በርሱ ፡ የሚያምኑ ፡ አሉ ፤ ከነር
ሱም ፡ በርሱ ፡ የማያምኑ ፡ አሉ ፡
ጌታህም ፡ አጥፊዎቹን ፡ በጣም ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።
41 ቢያስተባብሉህም ፡ ለኔ ፡ ሥራዬ ፡
አለኝ ፤ ለናንተም ፡ ሥራችሁ ፡
አላችሁ ፤ እናንተ ፡ ከምሠራው ፡
ነገር ፡ ንጹሕ ፡ ናችሁ ፤ እኔም ፡
ከምትሠሩት ፡ ነገር ፡ ንጹሕ ፡
ነኝ ፡ በላቸው ።
42 ከነሱም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ የሚያ
ዳምጡ (ና ፡ የማያምኑ) ፡ አሉ ፡
አንተ ፡ ደንቆሮዎችን ፡ የማያ
ውቁ ፡ ቢኾኑም ፡ ታሰማለህን ?
43 ከእነሱም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ የሚመ
ለከቱ ፡ አሉ ፤ አንተ ፡ (ልበ) ፡
ዕውራንን ፡ የማያዩ ፡ ቢኾኑም ፡
ትመራለህን ?
44 አላህ ፡ ሰዎችን ፡ ምንም ፡ አይበ
ድልም ፤ ግን ፡ ሰዎች ፡ ነፍሶቻቸ
ውን ፡ ይበድላሉ ።
45 (ከሓዲዎችን) ፡ ከቀን ፡ አንዲ
ትን ፡ ሰዓት ፡ እንጂ ፡ እንዳል
ቆዩ ፡ መስለው ፡ በመካከላቸው ፡
የሚተዋወቁ ፡ ሲኾኑ ፡ በምንሰበ
ስባቸው ፡ ቀን ፡ (አስታውስ) ።
እነዚያ ፡ በአላህ ፡ መገናኘት ፡
ያስተባበሉት፥ በእርግጥ ፡ ከሰሩ ፡
የተመሩም ፡ አልነበሩም ።
46 የዚያንም ፡ የምናስፈራራቸውን ፡
ከፊሉን ፡ (በሕይወትህ) ፡ ብናሳ
ይህ ፡ (መልካም ፡ ነው) ፤ ወይም ፡
(ሳናሳይህ) ፡ ብንገድልህ ፡ መመ
ለሻቸው ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ነው ፤ ከዚ
ያም ፡ አላህ ፡ በሚሠሩት ፡ ሥራ ፡
ላይ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
47 ለሕዝቦችም ፡ ሁሉ ፡ መልክተኛ ፡
አላቸው ፤ መልክተኛቸውም ፡ በ
መጣ ፡ ጊዜ ፡ (ሲያስተባብሉ) ፡



በመካከላቸው ፡ በትክክል ፡ ይፈ
ረዳል ፤ እነርሱም ፡ አይበደሉም ።
48 ፡—እውነተኞችም ፡ ከኾናችሁ ፡
ይህ ፡ (የቅጣቱ) ፡ ቀጠሮ ፡ መቼ ፡
ነው ? ይላሉ ።
49 ፡—ለራሴ ፡ ጉዳትንም ፡ ጥቅም
ንም ፡ አላህ ፡ ከሻው ፡ በስተቀር ፡
አልችልም ፤ ለሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡
የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ አላቸው ፤ ጊዜያ
ቸው ፡ በመጣ ፡ ወቅት ፡ አንዲ
ትን ፡ ሰዓት ፡ አይቆዩም ፤ አይቀደ
ሙምም ፤ በላቸው ።
50 ቅጣቱ ፡ በሌሊት ፡ ወይም ፡ በቀን፡
ቢመጣባችሁ ፤ አጋሪዎቹ ፡ ከርሱ፡
የሚቻኮሉበት ፡ ነገር ፡ ምንድን ፡
ነው ? ንገሩኝ ፡ በላቸው ።
51 ከዚያም ፡ (ቅጣቱ) ፡ በወደቀ ፡
ጊዜ ፡ በርሱ ፡ አመናችሁበትን ?
በእርግጥ ፡ በርሱ ፡ የምትቻኮሉ ፡
የነበራችሁ ፡ ስትኾኑ ፡ አሁን ?
(ይባላሉ) ።
52 ከዚያም ፡ ለነዚያ ፡ ለበደሉት ፡—
ዘውታሪን ፡ ቅጣት ፡ ቅመሱ ፤
ትሠሩት ፡ የነበራችሁትን ፡ ዋጋ ፡
እንጂ ፡ አትመነዱም ፡ ይባላሉ ።
53 እርሱም ፡ (1) እውነት ፡ ነውን ?
(ሲሉ) ፡ ይጠይቁሃል ፤ አዎን ፤
በጌታዬ ፡ እምላለሁ ፤ እርሱ ፡ እ
ውነት ፡ ነው ፤ እናንተም ፡ አምላ
ጮች ፡ አይደላችሁም ፤ በላቸው ።
54 ለበደለችም ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ቢኖ
ራት ፡ ኖሮ ፡ በእርግጥ ፡ በተበዠ
ችበት ፡ ነበር፤ ቅጣቱንም ፡ ባዩ ፡
ጊዜ ፡ ጸጸትን ፡ ይገልጻሉ ፤ በመካ
ከላቸውም ፡ በትክክል ፡ ይፈረ
ዳል ፤ እነርሱም ፡ አይበደሉም ።

1 የምታስፈራራብን ፡ ነገር ።

55 ንቁ ፤ በሰማያትና ፡ በምድር ፡
ያለው ፡ ሁሉ ፡ የአላህ ፡ ነው ፤
ንቁ ፡ የአላህ ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡ እር
ግጥ ፡ ነው ፤ ግን ፡ አብዛኞቻቸው ፡
አያውቁም ።
56 እርሱ ፡ ሕያው ፡ ያደርጋል ፤ ይገ
ድላልም ፡ ወደ ፡ እርሱም ፡ ትመ
ለሳላችሁ ።
57 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! ከጌታ
ችሁ ፡ ግሣጼ ፡ በደረቶች ፡ ውስ
ጥም ፡ ላለው ፡ (የመጠራጠር ፡
በሽታ) ፡ መድኃኒት ፡ ለምእም
ናንም ፡ ብርሃንና ፡ እዝነት ፡ በእ
ርግጥ ፡ መጣችላችሁ ።
58 ፡—በአላህ ፡ ችሮታና ፡ በእዝነቱ ፡
(ይደሰቱ) ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡
ይደሰቱ ፤ እርሱ ፡ ከሚሰበስቡት፡፡
ሀብት ፡ በላጭ ፡ ነው ፤ በላቸው ።
59 ፡—አላህ ፡ ከሲሳይ ፡ ለናንተ ፡
ያወረደውን ፡ ከርሱም ፡ እርምና ፡
የተፈቀደ ፡ ያደረጋችሁትን ፡ አያ
ችሁን ? በላቸው ፤ አላህ ፡ (ይህ
ንን) ፡ ለናንተ ፡ ፈቀደላችሁን ?
ወይስ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ትቀጣጥ
ፋላችሁ ? በላቸው ።
60 የነዚያም ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ውሸ
ትን ፡ የሚቀጣጥፉ ፡ (ሰዎች) ፡
በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ (በአላህ) ፡ ጥር
ጣሬያቸው ፡ ምንድን ፡ ነው ?
አይቀጡም ፡ ይመስላቸዋልን ?)
አላህ ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ (ቅጣትን ፡
ባለማቻኮል) ፡ የልግስና ፡ ባለ
ቤት ፡ ነው ፤ ግን ፡ አብዛኞዎቹ ፡
አያመሰግኑም ።
61 (ሙሐመድ ፡ ሆይ !) በማንኛ
ውም ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ አትኾንም ፤
ከርሱም ፡ ከቁርአን ፡ አታነብም ፡
ማንኛውንም ፡ ሥራ ፡ (አንተም ፡
ሰዎቹም) ፡ አትሠሩም ፡ በገባችሁ

በት ፡ ጊዜ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ተጠ
ባባቂዎች ፡ ብንኾን ፡ እንጂ ፤
በምድርም ፡ ኾነ ፡ በሰማይ ፡ የብ
ናኝ ፡ ክብደት ፡ ያክል ፡ ከጌታህ ፡
(ዕውቀት) ፡ አይርቅም ፤ ከዚያም ፡
ያነሰ ፡ የተልለቀም ፡ የለም ፡ በግ
ልጹ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የተ
ጻፈ ፡ ቢኾን ፡ እንጂ ።
62 ንቁ ፡ የአላህ ፡ ወዳጆች ፡ በነሱ ፡
ላይ ፡ ፍርሃት ፡ የለባቸውም ፤
እነሱም ፡ አያዝኑም ።
63 (እነሱም) ፡ እነዚያ ፡ ያመኑትና ፡
ይፈሩት ፡ የነበሩት ፡ ናቸው ።
64 ለነሱ ፡ በቅርቢቱ ፡ ሕይወትም ፡
በመጨረሻይቱም ፡ ብስራት ፡
አላቸው ፤ የአላህ ፡ ቃላት ፡ መል
ለወጥ ፡ የላትም ፤ ይህ ፡ እርሱ ፡
ታላቅ ፡ ዕድል ፡ ነው ።
65 ንግግራቸውም ፡ (1) አያሳዝንህ ፤
ኀይል ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ የአላህ ፡
ብቻ ፡ ነውና ፤ እርሱ ፡ ሰሚው ፡
ዐዋቂው ፡ ነው ።
66 ንቁ ፤ በሰማያት ፡ ያሉትና ፡ በምድ
ርም ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ በእርግጥ ፡
የአላህ ፡ ናቸው ፤ እነዚያ ፡ ከአ
ላህ ፡ ሌላ ፡ ተጋሪዎችን ፡ የሚ
ጠሩ ፡ ምንን ፡ ይከተላሉ ? ጥርጣ
ሬን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይከተሉም ፤
እነሱም ፡ የሚዋሹ ፡ እንጂ ፡ አይ
ደሉም ።
67 እርሱ ፡ ያ ፡ ሌሊትን ፡ በውስጡ ፡
ልታርፉበት ፡ (ጨለማ) ፡ ቀንንም፡
(ልትሠሩበት) ፡ ብርሃን ፡ ያደረገ
ላችሁ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ ውስጥ ፡
ለሚሰሙ ፡ ሕዝቦች ፡ በእርግጥ ፡
ታምራቶች ፡ አልሉ ።
68 አላህ ፡ ልጅን ፡ ያዘ ፡ (ወለደ) ፡
አሉ ፤ (ከሚሉት) ፡ ጥራት ፡ ተገ
ባው ፤ እርሱ ፡ ተብቃቂ ፡ ነው ፡
በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡
ሁሉ ፡ የርሱ ፡ ነው ፤ እናንተ ፡
ዘንድ ፡ በዚህ ፡ (በምትሉት) ፡
ምንም ፡ አስረጅ ፡ የላችሁም ፡
በአላህ ፡ ላይ ፡ የማታውቁትን ፡
ትናገራላችሁን ?
69 ፡—እነዚያ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ውሸ
ትን ፡ የሚቀጣጥፉ ፡ ፈጽሞ ፡ አይ
ድኑም ፤ በላቸው ።
70 (ለነሱ) ፡ በቅርቢቱ ፡ ዓለም ፡ መጠ
ቀም ፡ አልላቸው ፤ ከዚያም ፡ መመ
ለሻቸው ፡ ወደኛ ፡ ነው ፤ ከዚያም ፡
ይክዱ ፡ በነበሩት ፡ ምክንያት ፡
ብርቱን ፡ ቅጣት ፡ እናቀምሳቸዋ
ለን ።
71 የኑሕንም ፡ ወሬ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
አንብብላቸው ፤ ለሕዝቦቹ ፡ ባለ ፡
ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፤ ፡—ሕዝቦቼ ፡
ሆይ ! በናንተ ፡ ውስጥ ፡ ብዙን ፡
ጊዜ ፡ መቆየቴ ፡ በአላህም ፡ ታም
ራት ፡ ማስታወሴ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
የከበደ ፡ ቢኾን ፤ በአላህ ፡ ላይ ፡
ተጠግቻለሁ ፡ ነገራችሁንም ፡
ከምታጋሩዋቸው ፡ (ጣዖታት) ፡
ጋር ፡ ኾናችሁ ፡ ቁረጡ ፤ ከዚ
ያም ፡ ነገራችሁ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
ድብቅ ፡ አይኹን ፤ (ግለጹት) ፤
ከዚያም ፡ (የሻችሁትን) ፡ ወደኔ ፡
አድርሱ ፤ ጊዜም ፡ አትስጡኝ ፤
(ከምንም ፡ አልቆጥራችሁም) ።
72 ብትሸሹም ፡ (አትጐዱኝም) ፡ ከም
ንዳ ፡ ምንንም ፡ አልለምናችሁ
ምና ። ምንዳዬ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡
እንጂ ፡ በሌላ ፡ ላይ ፡ አይደለም ፤
ከሙስሊሞች፡ እንድኾንም ፡ ታዝ
ዣለሁ ።
73 አስተባበሉትም ፤ እርሱንና ፡ ከ
ርሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩትንም ፡ በታን

---
1 መልከተኛ ፡ አይደለህም ፡ ማለታቸው ።



ኳይቱ ፡ ውስጥ ፡ አዳንናቸው ፤
(ለጠፉት) ፡ ምትኮችም ፡ አደረግ
ናቸው ፤ እነዚያንም ፡ በአንቀጾቻ
ችን ፡ ያስተባበሉትን ፡ አሰጠ
ምን ፤ የተስፈራሩትም ፡ ሕዝቦች ፡
መጨረሻ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡
ነበረ ፡ ተመልከት ።
74 ከዚያም ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ መልክተ
ኞችን ፡ ወደየሕዝቦቻቸው ፡ ላ
ክን ፤ በግልጽ ፡ ማስረጃዎችም ፡
መጧቸው ፤ (ከመላካቸው) ፡ በ
ፊት ፡ በርሱ ፡ ባስተባበሉበትም ፡
ነገር ፡ የሚያምኑ ፡ አልኾኑም ፤
እንደዚሁ ፡ በወሰን ፡ አላፊዎች ፡
ልቦች ፡ ላይ ፡ እናትማለን ።
75 ከዚያም ፡ ከነሱ ፡ ኋላ ፡ ሙሳንና ፡
ሃሩንን ፡ ወደ ፡ ፈርዖንና ፡ ወደ ፡
መማክርቱ ፡ በታምራታችን ፡
ላክን ፤ ኮሩም ፡ ትዕቢተኞች ፡
ሕዝቦችም ፡ ነበሩ ።
76 ከኛም ፡ ዘንድ ፡ እውነቱ ፡ በመጣላ
ቸው ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ በእርግጥ ፡
ግልጽ ፡ ድግምት ፡ ነው ፡ አሉ ።
77 ሙሳ ፡ አለ ፡-እውነቱን ፡ በመጣላ
ችሁ ፡ ጊዜ ፡ ድግምተኞች ፡ የማይ
ድኑ ፡ ሲኾኑ ፡ (እርሱ ፡ ድግምት ፡
ነው) ፡ ትላላችሁን ? ይህ ፡ ድግ
ምት ፡ ነውን ?
78 (እነርሱም) ፡ አሉ ፡—አባቶቻች
ንን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ካገኘንበት ፡
ሃይማኖት ፡ ልታዞረን ፡ ለናንተም፡
በምድር ፡ ውስጥ ፡ ኩራት ፡ (ሹ
መት) ፡ ልትኖራችሁ ፡ መጣህ
ብን ? እኛም ፡ ለናንተ ፡ አማኞች ፡
አይደለንም ።
79 ፈርዖንም ፡—ዐዋቂ ፡ ድግምተ
ኛን ፡ ሁሉ ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ።
80 ድግምተኞቹም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡
ሙሳ ፡ ለነርሱ ፡—እናንተ ፡ የምት
ጥሉትን ፡ ነገር ፡ ጣሉ ፡ አላቸው ።
81 (ገመዶቻቸውን) ፡ በጣሉም ፡
ጊዜ ፡ ሙሳ ፡ አለ ፡— ያ ፡ በርሱ ፡
የመጣችሁበት ፡ ነገር ፡ ድግምት ፡
ነው ፤ አላህ ፡ በእርግጥ ፡ ያፈርሰ
ዋል ፤ አላህ ፡ የአጥፊዎችን ፡ ሥራ
ፈጽሞ ፡ አያበጅምና ።
82 አላህም ፡ ከሓዲዎች ፡ ቢጠሉም ፡
እውነትን ፡ በቃላቱ ፡ ያረጋግጣል ።
83 ለሙሳም ፡ ከፈርዖንና ፡ ከሹማም
ንቶቻቸው ፡ ማሰቃየትን ፡ ከመፍ
ራት ፡ ጋር ፡ ከወገኖቹ ፡ የኾኑ ፡
ጥቂቶች ፡ ትውልዶች ፡ እንጂ ፡
አላመኑለትም ፤ ፈርዖንም ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ የኮራ ፡
ነበር ፤ እርሱም ፡ በእርግጥ ፡ ወሰን
ካለፉት ፡ ነበር ።
84 ሙሳም ፡ አለ ፡—ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ፡
በአላህ ፡ አምናችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ ተጠጉ ፤ ታዛዦች ፡
እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ (በአላህ ፡ ላይ ፡
ትመካላችሁ) ።
85 አሉም ፡— በአላህ ፡ ላይ ፡ ተጠ
ጋን ፤ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ ለበደለ
ኞች ፡ ሕዝቦች ፡ መፈተኛ ፡ አታ
ድርገን ።
86 በእዝነትህም ፡ ከከሓዲዎች ፡ ሕዝ
ቦች ፡ አድነን ።
87 ወደ ፡ ሙሳና ፡ ወደ ፡ ወንድሙ ፡—
ለሕዝቦቻችሁ ፡ በምሥር ፡ ቤቶ
ችን ፡ ሥሩ ፤ ቤቶቻችሁንም ፡ መስ
ገጃ ፡ አድርጉ ፤ ሶላትንም ፡ በደ
ንቡ ፡ ስገዱ ፤ (ለሙሳ) ፡ ምእምናኖ
ቹንም ፡ አብስር ፡ ስንል ፡ ላክን ።
88 ሙሳም ፡ አለ ፡— ጌታችን ፡ ሆይ ፡
አንተ ፡ ለፈርዖንና ፡ ለሹሞቹ ፡
በቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡ ጌጥን ፡
ብዙ ፡ ገንዘቦችንም ፡ በእርግጥ ፡
ሰጠህ ፤ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ ከመንገ

ድህ ፡ ያሳስቱ ፡ ዘንድ ፡ (ሰጠሃ
ቸው) ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ገንዘቦቻ
ቸውን ፡ አጥፋ ፤ በልቦቻቸውም ፡
ላይ ፡ አትም ፤ አሳማሚን ፡
ቅጣት ፡ እስከሚያዩ ፡ አያምኑ
ምና ።
89 (አላህም) ፡- ጸሎታችሁ ፡ በእር
ግጥ ፡ ተሰምታለች ፤ ቀጥም ፡ በሉ፤
የነዚያንም ፡ የማያውቁትን ፡ ሰ
ዎች ፡ መንገድ ፡ አትከተሉ ፡
አላቸው ።
90 የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ባሕ
ሩን ፡ አሳለፍናቸው ፤ ፈርዖንና ፡
ሰራዊቱም ፡ ወሰን ፡ ለማለፍና ፡
ለመበደል ፡ ተከተሏቸው ፤ መስጠ
ምም ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡— አመ
ንኩ ፤ እነሆ ፡ ከዚያ ፡ የእስራኤል ፡
ልጆች ፡ በርሱ ፡ ከአመኑበት ፡
በስተቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፡
እኔም ፡ ከታዛዦቹ ፡ ነኝ ፡ አለ ።
91 ፡-ከአሁን፡ በፊት፡ በእርግጥ፡ ያመ
ጥክ፡ ከአጥፊዎችም፡ የነበርክ፡ ስት
ኾን፥ አሁን፡ (አመንኩ፡ ትላለህ)?
92 ዛሬማ ፡ ከኋላህ ፡ ላሉት ፡ ታምር ፡
ትኾን ፡ ዘንድ ፡ በድን ፡ ኾነህ ፡
(ከባሕሩ) ፡ እናወጣሃለን ፡ (ተባለ)፤
ከሰዎችም ፡ ብዙዎቹ ፡ ከታምራታ
ችን ፡ በእርግጥ ፡ ዘንጊዎች ፡
ናቸው ።
93 የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ምስጉ
ንን ፡ ስፍራ ፡ በእርግጥ ፡ አሰፈርና
ቸው ፤ ከመልካም ፡ ሲሳዮችም ፡
ሰጠናቸው ፤ ዕውቀትም ፡ (ቁር
አን) ፡ እስከ ፡ መጣቸው ፡ ድረስ ፡
አልተለያዩም ፤ ጌታህ ፡ በርሱ ፡
ይለያዩበት ፡ በነበሩት ፡ ነገር ፡
በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ በመካከላቸው ፡
ይፈርዳል ።
94 ወደ ፡ አንተም ፡ ካወረድነው ፡
በመጠራጠር ፡ ውስጥ ፡ ብትኾን ፡
እነዚያን ፡ ከአንተ ፡ በፊት ፡ መጽ
ሐፉን ፡ የሚያነቡትን ፡ ጠይቅ ፤
እውነቱ ፡ ከጌታህ ፡ ዘንድ ፡ በእር
ግጥ ፡ መጥቶልሃል ፤ ከተጠራጣሪ
ዎቹም ፡ አትኹን ።
95 ከእነዚያም ፡ የአላህን ፡ አንቀጾች ፡
ከአስተባበሉት ፡ አትኹን ፤ ከከሳ
ሪዎቹ ፡ ትኾናለህና ።
96 እነዚያ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ የጌታህ ፡
ቃል ፡ የተረጋገጠባቸው ፡ አያም
ኑም ።
97 ታምር ፡ ሁሉ ፡ ብትመጣላቸውም፡
አሳማሚን ፡ ቅጣት ፡ እስከሚያዩ ፡
ድረስ ፡ (አያምኑም) ።
98 (ከዩኑስ ፡ በፊት ፡ ካለፉት ፡ ከተ
ሞች) ፡ ያመነችና ፡ እምነትዋ ፡
የጠቀማት ፡ ከተማ ፡ ለምን ፡ አል
ኖረችም ፡ ግን ፡ የዩኑስ ፡ ሕዝቦች ፡
ባመኑ ፡ ጊዜ ፡ በቅርቢቱ ፡ ሕይ
ወት ፡ የውርደትን ፡ ቅጣት ፡
ከነሱ ፡ ላይ ፡ አነሳንላቸው ፤
እስከ ፡ ጊዜም ፡ ድረስ ፡ አጣቀም
ናቸው ።
99 ጌታህም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ በምድር ፡
ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉም ፡ የተሰበ
ሰቡ ፡ ኾነው ፡ ባመኑ ፡ ነበር ፤
ታዲያ ፡ አንተ ፡ ሰዎችን ፡ አማ
ኞች ፡ እንዲኾኑ ፡ ታስገድዳለህን?
100 ለማንኛዋም ፡ ነፍስ ፡ በአላህ ፡
ፈቃድ ፡ ቢኾን ፡ እንጂ ፡ ልታ
ምን ፡ (ችሎታ) ፡ የላትም ፤ (አላህ ፡
ለከፊሎቹ ፡ እምነትን ፡ ይሻል) ፡
በነዚያም ፡ በማያውቁት ፡ ላይ ፡
ርክሰትን ፡ ያደርጋል ።
101 ፡—በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ያለ
ውን ፡ (ታምር) ፡ ተመልከቱ ፡
በላቸው ፤ ታምራቶችና ፡ አስፈራ



ሪዎችም ፡ ለማያምኑ ፡ ሕዝቦች ፡
አይጠቅሙም ።
102 የነዚያን ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡ ያለፉ
ትን ፡ ሕዝቦች ፡ ቀኖች ፡ ብጤ ፡
እንጂ ፡ ሌላን ፡ ይጠባበቃሉን ?
፡—ተጠባበቁ ፤ እኔ ፡ ከናንተ ፡
ጋር ፡ ከሚጠባበቁት ፡ ነኝ ፡ በላ
ቸው ።
103 ከዚያም ፡ መልክተኞቻችንን ፡
እነዚያንም ፡ ያመኑትን ፡ እናድና
ለን ፤ እንደዚሁም ፡ ምእምናንን ፡
(ከጭንቅ ፡ ሁሉ) ፡ እናድናለን ፡
(ይህ) ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ተረጋገጠ ።
104 ፡—እናንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! ከኔ ፡
ሃይማኖት ፡ በመጠራጠር ፡ ውስጥ ፡
ብትኾኑ ፡ እነዚያን ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡
የምትግገዟቸውን ፡ አልግገዛም ፡
ግን ፡ ያንን ፡ የሚገድላችሁን ፡
አላህን ፡ እግገዛለሁ ፤ ከምእምናን ፡
እንድኾንም ፡ ታዝዣለሁ ፡ በላ
ቸው ።
105 ፊትህንም ፡ (ወደ ፡ ቀጥታ) ፡ ያዘነ
በልክ ፡ ስትኾን ፡ ለሃይማኖት ፡
ቀጥ ፡ አድርግ ፤ ከአጋሪዎቹም ፡
አትኹን ።
106 ከአላህም ፡ በቀር ፡ የማይጠቅም
ንና ፡ የማይጐዳን ፡ አትግገዛ ፤ ብት
ሠራም ፡ አንተ ፡ ያንጊዜ ፡ ከበደ
ለኞቹ ፡ ትኾናለህ ፡ (ተብያለሁ ፡
በላቸው) ።
107 አላህም ፡ ጉዳትን ፡ ቢያደርስብህ ፡
ከርሱ ፡ ሌላ ፡ ለርሱ ፡ ገላጭ ፡ የለ
ውም ፤ በግጎንም ፡ ነገር ፡ ቢሻ
ልህ ፡ ለችሮታው ፡ መላሽ ፡ የለም፤
ከባሮቹ ፡ የሚሻውን ፡ በርሱ ፡ ይለ
ይበታል ፤ እርሱም ፡ መሐሪ ፡
አዛኝ ፡ ነው ።
108 ፡—እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! እው
ነቱ ፡ ከጌታችሁ ፡ በእርግጥ ፡ መጣ
ላችሁ ፡ (በርሱ) ፡ የተመራም ፡
ሰው ፡ የሚመራው ፡ ለራሱ ፡ ነው፤
የተሳሳተም ፡ ሰው ፡ የሚሳሳተው ፡
(ጉዳቱ) ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነው ፤
እኔም ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ተጠባባቂ ፡
አይደለሁም ፡ በላቸው ።
109 ወዳንተም ፡ የሚወረደውን ፡ ነገር፡
ተከተል ፤ አላህም ፡ (በነሱ ፡ ላይ) ፡
እስከሚፈርድ ፡ ድረስ ፡ ታገሥ ፤
እርሱም ፡ ከፈራጆቹ ፡ ሁሉ ፡
በላጭ ፡ ነው ።

11ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ሁድ ፡ (የሁድ ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡ የወ
ረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 123 ፡ ናቸው ።

★ ★ ★

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በኾነው ።

1 አ. ለ. ረ. (አሊፍ ፡ ላም ፡ ራ ፤
ይህ ፡ ቁርአን ፡) አንቀጾቹ ፡ በጥ
ንካሬ ፡ የተሰከኩ ፡ ከዚያም ፡ የተ
ዘረዘሩ ፡ የኾነ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፤
ጥበበኛ ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡ ከኾ
ነው ፡ ዘንድ ፡ (የተወረደ) ፡ ነው ።

2 (እንዲህ ፡ በላቸው) ፡- አላህን ፡
እንጂ ፡ ሌላን ፡ አትገዙ ፤ እኔ ፡
ለናንተ ፡ ከርሱ ፡ (የተላክሁ) ፡
አስፈራሪና ፡ አብሳሪ ፡ ነኝ ።

3 ጌታችሁንም ፡ ምሕረትን ፡ ለም
ኑት ፤ ከዚያም ፡ ወደርሱ ፡ ተመ
ለሱ ፤ እስከ ፡ ተወሰነ ፡ ጊዜ ፡
ድረስ ፡ መልካምን ፡ መጥቀም ፡
ይጠቅማችኋልና ፤ የትሩፋትንም ፡
ባለቤት ፡ ሁሉ ፡ ችሮታውን ፡
(ምንዳውን) ፡ ይሰጠዋል ፤ ብትሸ
ሹም ፡ እኔ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ የታላ
ቅን ፡ ቀን ፡ ቅጣት ፡ እፈራላች
ኋለሁ ።

4 መመለሻችሁ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡
ነው ፤ እርሱም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ።

5 ንቁ ፡ እነሱ ፡ ከርሱ ፡ (ከአላህ) ፡
ይደበቁ ፡ ዘንድ ፡ ደረቶቻቸውን ፡
ያጥፋሉ ፤ ንቁ ፡ ልብሶቻቸውን ፡
በሚከናነቡ ፡ ጊዜ ፡ የሚደብቁ
ትን ፡ የሚገልጹትንም ፡ ሁሉ ፡
ያውቃል ፤ እርሱ ፡ በደረቶች ፡
ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡
ነውና ።

6 በምድርም ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ተንቀ
ሳቃሽ ፡ የለችም ፡ ምግቧ ፡ በአ
ላህ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ቢኾን ፡ እንጂ ፤
ማረፊያዋንም ፡ መርጊያዋንም ፡
ያውቃል ፤ ሁሉም ፡ ግልጽ ፡ በኾ
ነው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

7 እርሱም ፡ ያ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድ
ርን ፡ በስድስት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡
የፈጠረ ፡ ነው ፤ ዐርሹም ፡ በውሃ ፡
ላይ ፡ ነበር ፤ የትኛችሁ ፡ ሥራው ፡
ያማረ ፡ መኾኑን ፡ ይፈትናችሁ ፡
ዘንድ ፡ (ፈጠራቸው) ፡— እናንተ ፡
ከሞት ፡ በኋላ ፡ በእርግጥ ፡ ተቀስ
ቃሾች ፡ ናችሁ ፡ ብትልም ፡ እነ
ዚያ ፡ የካዱት ፡ ይህ ፡ ግልጽ ፡ ድግ
ምት ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፡
ይላሉ ። (1)

8 ቅጣቱንም ፡ ወደ ፡ ተቆጠሩ ፡
(ጥቂት) ፡ ጊዜያቶች ፡ ከነርሱ ፡
ብናቆይላቸው ፡ (ከመውረድ) ፡
የሚከለክለው ፡ ምንድን ፡ ነው?
ይላሉ ፤ ንቁ ፡ በሚመጣባቸው ፡
ቀን ፡ ከነሱ ፡ ላይ ፡ ተመላሽ ፡
አይደለም ፤ በርሱ ፡ ይሳለቁበት ፡
የነበሩትም ፡ (ቅጣት) ፡ በነርሱ ፡
ላይ ፡ ይወርድባቸዋል ።

9 ሰውንም ፡ ከኛ ፡ ችሮታን ፡ ብናቀ
ምሰው ፡ ከዚያም ፡ ከርሱ ፡ ብንወ
ስዳት ፡ እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ ተስፋ ፡
ቆራጭ ፡ ከሕደተ ፡ ብርቱ ፡ ነው ።

---

1 ይህ ፡ ቃል ፡ ብልሹ ፡ በመኾን ፡ እንደ ፡
ድግምት ፡ ነው ፡ ይላሉ ።



10 ከነኘችውም ፡ ችግር ፡ በኋላ ፡ ጠጋ
ዎችን ፡ ብናቀምሰው ፡ ችግሮች ፡
ከኔ ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ ተወገዱ ፡
ይላል ፤ (አያመሰግንም) ፡ እርሱ ፡
ተደሳች ፡ ጉረኛ ፡ ነውና ።

11 ግን ፡ እነዚያ ፡ የታገሡ ፡ መል
ካም ፡ ሥራዎችንም ፡ የሠሩ ፡ እነ
ዚያ ፡ ለነሱ ፡ ምሕረትና ፡ ታላቅ ፡
ምንዳ ፡ አላቸው ።

12 በርሱ ፡ ላይ ፡ የገንዘብ ፡ ድልብ ፡
ለምን ፡ አልተወረደም ፡ ወይም ፡
ከርሱ ፡ ጋር ፡ መልአክ ፡ ለምን ፡
አልመጣም ፡ ማለታቸውንም ፡
በመፍራት ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ከሚወ
ርደው ፡ ከፊሉን ፡ ልትተው ፡
በርሱም ፡ ልብህ ፡ ጠባብ ፡ ሊኾን ፡
ይፈራልሃል ፤ አንተ ፡ አስፈራሪ ፡
ብቻ ፡ ነህ ፤ አላህም ፡ በነገሩ ፡
ሁሉ ፡ ተጠባባቂ ፡ ነው ።

13 ይልቁንም ፡ (ቁርአንን) ፡ ቀጣጠ
ፈው ፡ ይላሉን? ፡- እውነተኞች ፡
እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ ብጤው ፡ የኾ
ኑን ፡ ዐሥር ፡ የተቀጣጠፉ ፡ ሱራ
ዎች ፡ አምጡ ፤ ከአላህም ፡ ሌላ ፡
የቻላችሁትን ፡ (ረዳት) ፡ ጥሩ ፡
በላቸው ።

14 ለናንተም ፡ (ጥሪውን) ፡ ባይቀበሏ
ችሁ ፡ የተወረደው ፡ በአላህ ፡ ዕው
ቀት ፡ ብቻ ፡ መኾኑንና ፡ ከርሱ ፡
ሌላ ፡ አምላክ ፡ አለመኖሩን ፡
ዕወቁ ፤ ታዲያ ፡ እናንተ ፡ የምትሰ
ልሙ ፡ ናችሁን ? (ስለሙ ፡ በላ
ቸው) ።

15 ቅርቢቱን ፡ ሕይወትና ፡ ጌጧን ፡
የሚሹ ፡ የኾኑትን ፡ ሰዎች ፡ ሥራ
ዎቻቸውን ፡ (ምንዳዋን) ፡ በርሷ ፡
ውስጥ ፡ ወደኛሱ ፡ እንሞላላቸዋ
ለን ፤ እኛሱም ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡
ምንም ፡ አይጐደልባቸውም ።

16 እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ በመጨረሻ
ይቱ ፡ ዓለም ፡ ለነርሱ ፡ ከእሳት ፡
በቀር ፡ የሌላቸው ፡ ናቸው ፤ የሠ
ሩትም ፡ ሥራ ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡
ተበላሸ ፤ (በቅርቢቱ ፡ ዓለም) ፡
ይሠሩት ፡ የነበሩትም ፡ በኀ ፡
ሥራ ፡ ብልሹ ፡ ነው ።

17 ከጌታው ፡ ከአስረጅ ፡ ጋር ፡ የኾነ ፡
ሰው ፡ ከርሱም ፡ (ከአላህ) ፡ የኾነ ፡
መስካሪ ፡ የሚከተለው ፡ ከርሱ ፡
በፊትም ፡ የሙሳ ፡ መጽሐፍ ፡
መሪና ፡ እዝነት ፡ ሲኾን ፡ (የመሰ
ከረለት) ፡ የቅርቢቱን ፡ ሕይወት ፡
እንደሚሻው ፡ ሰው ፡ ነውን ? እነ
ዚያ ፡ በርሱ ፡ (በቁርአን) ፡ ያም
ናሉ ፤ ከአሕዛቦቹም ፡ በርሱ ፡
የሚክድ ፡ ሰው ፡ እሳት ፡ መመለ
ሻው ፡ ናት ፤ ከርሱም ፡ በመጠ
ራጠር ፡ ውስጥ ፡ አትኹን ፤ እርሱ ፡
ከጌታህ ፡ የኾነ ፡ እውነት ፡ ነው ፤
ግን ፡ አብዛኞቹ ፡ ሰዎች ፡ አያም
ኑም ።

18 በአላህ ፡ ላይ ፡ እብለትን ፡ ከሚቀ
ጣጥፍም ፡ ይበልጥ ፡ በዳይ ፡
ማነው ? እነዚያ ፡ በጌታቸው ፡
ላይ ፡ ይቀረባሉ ፤ መስካሪዎ
ቹም ፡— እነዚህ ፡ በጌታቸው ፡
ላይ ፡ የዋሹት ፡ ናቸው ፡ ይላሉ ፤
ንቁ ፡ የአላህ ፡ ርግማን ፡ በበዳ
ዮች ፡ ላይ ፡ ይኹን ።

19 (እነሱም) ፡ እነዚያ ፡ ከአላህ ፡
መንገድ ፡ የሚከለክሉ ፡ መጥመሟ
ንም ፡ የሚፈልጓት ፡ ናቸው ፤ እነ
ሱም ፡ መጨረሻይቱን ፡ ዓለም ፡
እነሱ ፡ ከሓዲዎች ፡ ናቸው ።

20 እነዚያ ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ (ከአ
ላህ) ፡ የሚያመልጡ ፡ አልነበ
ሩም ፤ ከአላህም ፡ ሌላ ፡ ለነርሱ ፡
ረዳቶች ፡ አልነበሯቸውም ፤ ለነሱ ፡

ቅጣቱ ፡ ይደራረብላቸዋል ፣ (እው
ነትን) ፡ መስማትን ፡ የሚችሉ ፡
አልነበሩም ፤ የሚያዩም ፡ አልነ
በሩም ።
21 እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ ነፍሶቻቸውን ፡
ያከሰሩ ፤ ከነሱም ፡ ይቀጣጥፉት ፡
የነበሩት ፡ ነገር ፡ የጠፉቸው ፡
ናቸው ።
22 እነርሱ ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ዓለም ፡
በጣም ፡ ከሳሪዎቹ ፡ እነሱ ፡ መኾ
ናቸው ፤ ጥርጥር ፡ የለውም ።
23 እነዚያ ፡ ያመኑትና ፡ በጎ ፡ ሥራዎ
ችን ፡ የሠሩት ፤ ወደ ፡ ጌታቸውም ፡
የተዋረዱት ፤ እነዚያ ፡ የገነት ፡
ሰዎች ፡ ናቸው ፣ እነሱ ፡ በው
ስጧ ፡ ዘላለም ፡ ዘውታሪዎች ፡
ናቸው ።
24 የሁለቱ ፡ ክፍሎች ፡ (1) ምሳሌ ፡
እንደ ፡ ዕውርና ፡ እንደ ፡ ደንቆሮ ፡
እንደሚያይና ፡ እንደሚሰማም ፤
ብጤ ፡ ነው ፣ በምሳሌ ፡ ይተካከ
ላሉን ? አትገሠጹምን ?
25 ኑሕንም ፡ ወደ ፡ ሕዝቦቹ ፡ በእር
ግጥ ፡ ላክን ፣ (አላቸውም) ፡—
እኔ ፡ ለናንተ ፡ ግልጽ ፡ አስፈራሪ ፡
ነኝ ።
26 አላህን ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡ አትገዙ ፣
እኔ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ የአሳማሚን ፡
ቀን ፡ ቅጣት ፡ እፈራላችኋለሁና ።
27 ከሕዝቦቹም ፡ እነዚያ ፡ የካዱት ፡
መሪዎቹ ፤ ብጤያችን ፡ ሰው ፡
ኾነህ ፡ እንጂ ፡ አናይህም ፣ እነዚ
ያም ፡ እነሱ ፡ ሐሳበ ፡ ጥሬዎች ፡
የኾኑት ፡ ወራዶቻችን ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ ተከትሎህ ፡ አናይህም ፣
ለናንተም ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡
ብልጫን ፡ አናይም ፣ ከቶውንም ፡
ውሸታሞች ፡ መኾናችሁን ፡ እን
ጠረጥራችኋለን ፡ አሉ ።
28 ፡-ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ፡ ንገሩኝ ፤ ከጌ
ታዬ ፡ በግልጽ ፡ ማስረጃ ፡ ላይ ፡
ብኾን ፤ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ የኾ
ነን ፡ ችሮታ ፤ (ነቢይነት) ፡ ቢሰ
ጠኝና ፤ በናንተ ፡ ላይ ፡ ብትደበቅ
ባችሁ ፤ እናንተ ፡ ለርሷ ፡ ጠይ
ዎች ፡ ስትኾኑ ፤ እርሷን ፡ (በመ
ቀበል) ፡ እናስገድዳችኋለን ? አላ
ቸው ።
29 ሕዝቦቼም ፡ ሆይ ! በርሱ ፡ (በተላ
ከሁበት ፡ ማድረስ) ፡ ላይ ፡ ገንዘ
ብን ፡ አልጠይቃችሁም ፣ ምን
ዳዬ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡
በሌላ ፡ ላይ ፡ አይደለም ፣ እኔም ፡
እነዚያን ፡ ያመኑትን ፡ አባራሪ ፡
አይደለሁም ፣ እነርሱ ፡ ጌታቸ
ውን ፡ የሚገናኙ ፡ ናቸውና ፣ ግን ፡
እኔም ፡ የምትሳሳቱ ፡ ሕዝቦች ፡
ኾናችሁ ፡ አያችኋለሁ ።
30 ሕዝቦቼም ፡ ሆይ ፡ ባባርራቸው ፤
ከአላህ ፡ (ቅጣት) ፡ የሚያድነኝ ፡
ማን ፡ ነው ? አትገሠጹምን ?
31 ለእናንተም ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ የአ
ላህ ፡ ግምጃ ፡ ቤቶች ፡ አሉ ፤
ሩቅንም ፡ ዐውቃለሁ ፡ አልላች
ሁም ፣ እኔም ፡ መልአክ ፡ ነኝ ፡
አልላችሁም ፣ ለነዚያም ፡ ዓይኖቻ
ችሁ ፡ ለሚያዋርዷቸው ፤ አላህ ፡
ደግ ፡ ነገርን ፡ (እምነትን) ፡ አይሰ
ጣቸውም ፡ አልልም ፣ አላህ ፡
በነፍሶቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡
ነገር ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፣ እኔ ፡ ያን ፡
ጊዜ ፡ ከበደለኞች ፡ እኾናለሁና ፡
(አላቸው) ።
32 ፡—ኑሕ ፡ ሆይ ፡ በእርግጥ ፡ ተከራ
ከርከን ፣ እኛን ፡ መከራከርህንም ፡
አበዛኸው ፤ ከእውነተኞቹም ፡ እን

1 የከሓዲዎችና ፡ የምእምናን ።



ደኾንክ ፡ የምታስፈራራብንን ፡
ቅጣት ፡ አምጣው ፡ አሉ ።
33 ፡—እርሱን ፡ የሚያመጣባችሁ ፡
የሻ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡
ነው ፣ እናንተም ፡ የምታቅቱ ፡
አይደላችሁም ፡ አላቸው ።
34 ለናንተም ፡ ልመክራችሁ ፡ ብሻ ፡
አላህ ፡ ሊያጠማችሁ ፡ ሽቶ ፡
እንደ ፡ ኾነ ፡ ምክሬ ፡ አይጠቅማ
ችሁም ፣ እርሱ ፡ ጌታችሁ ፡ ነው ፣
ወደ ፡ እርሱም ፡ ትመለሳላችሁ ፡
(አላቸው) ።
35 ይልቁንም ፡ ቀጠፈው ፡ ይላሉን ?
ብቀጥፈው ፡ ኃጢአቴ ፡ (ቅጣቱ) ፡
በኔ ፡ ላይ ፡ ነው ፣ እኔም ፡ ከምታ
ጠፉት ፡ (ጥፋት) ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡
በላቸው ።
36 ወደ ፡ ኑሕም ፡ እነሆ ፡- ከሕዝቦ
ችህ ፡ በእርግጥ ፡ ካመኑት ፡ በስተ
ቀር ፡ (ወደፊት) ፡ አያምኑም ፡
ይሠሩትም ፡ በነበሩት ፡ (ክሕ
ደት) ፡ አትዘን ፡ ማለት ፡ ተወ
ረደ ።
37 (አላህም) ፡ በጥበቃችንና ፡ በትእ
ዛዛችንም ፡ ኾነህ ፡ መርከቢቱን ፡
ሥራ ፣ በነዚያም ፡ በበደሉት ፡
ሰዎች ፡ ነገር ፡ አታናግረኝ ፣
እነሱ ፡ በእርግጥ ፡ የሚሰጠሙ ፡
ናቸውና ፡ (አለው) ።
38 ከወገኖቹም ፡ መሪዎቹ ፡ በርሱ ፡
አጠገብ ፡ ባለፉ ፡ ቁጥር ፡ ከርሱ ፡
እየተሳለቁ ፤ መርከቢቱን ፡ ይሠ
ራል ። ከኛ ፡ ብትሳለቁ ፤ እኛም ፡
እንደተሳለቃችሁብን ፡ ከናንተ ፡
እንሳለቅባችኋለን ፡ አላቸው ።
39 የሚያዋርደው ፡ ቅጣት ፡ የሚመ
ጣበትን ፤ በርሱም ፡ ላይ ፡ ዘው
ታሪ ፡ ቅጣት ፡ የሚሰፍርበትን ፡
ሰው ፤ (ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ) ፡ ወደ
ፊት ፡ ታውቃላችሁ ፡ (አላቸው) ።
40 ትእዛዛችንም ፡ በመጣና ፡ እቶ
ኑም ፡ በገነፈለ ፡ ጊዜ ፡ በርሷ ፡
ውስጥ ፡ ከየዓይነቱ ፡ ሁሉ ፡ ሁለት
ሁለት ፤ (ወንድና ፡ ሴት) ፣ ቤተ ፡
ሰቦችህንም ፡ ቃል ፡ ያለፈበት ፡
ብቻ ፡ ሲቀር ፡ ያመነንም ፡ ሰው ፡
ሁሉ ፡ ጫን ፡ አልነው ፣ ከርሱም ፡
ጋር ፡ ጥቂቶች ፡ እንጂ ፡ አላመ
ኑም ።
41 ፡—መኼዷም ፡ መቆሚያም ፡ በአ
ላህ ፡ ስም ፡ ነው ፤ እያላችሁም ፡
በውስጧ ፡ ተሳፈሩ ፣ ጌታዬ ፡
መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ፡ አላቸው ።
42 እርሷም ፡ እንደ ፡ ተራራዎች ፡
በኾነ ፡ ማዕበል ፡ ውስጥ ፡ በነርሱ ፡
(ይዛቸው) ፡ የምትንሻለል ፡ ስት
ኾን ፤ (በአላህ ፡ ስም ፡ ተቀመጡ
ባት) ፣ ኑሕም ፡ ልጁን ፡ ከመርከ
ቢቱ ፡ የራቀ ፡ ኾኖ ፡ ሳለ ፡—
ልጄ ፡ ሆይ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ተሳፈር ፤
ከከሓዲዎቹም ፡ አትኹን ፡ ሲል ፡
ጠራው ።
43 (ልጁም) ፡— ከውሃው ፡ ወደሚ
ጠብቀኝ ፡ ተራራ ፡ እጠጋለሁ ፡
አለ ፣ (አባቱም) ፡— ዛሬ ፡ ከአላህ ፡
ትእዛዝ ፡ ምንም ፡ ጠባቂ ፡ የለም ፣
(እርሱ) ፡ ያዘነለት ፡ ካልኾነ ፡
በቀር ፡ አለው ፣ ማዕበሉም ፡ በመ
ካከላቸው ፡ ጋረደ ፣ ከሰጣሚዎ
ቹም ፡ ኾነ ።
44 ተባለም ፡— ምድር ፡ ሆይ ፡ ውሃ
ሽን ፡ ዋጪ ፣ ሰማይም ፡ ሆይ ፡
(ዝናምሽን) ፡ ያዢ ፣ ውሃውም ፡
ሠረገ ፣ ቅጣቱም ፡ ተፈጸመ ፣
ጁዲይ ፡ በሚባልም ፡ ተራራ ፡
ላይ ፡ (መርከቢቱ) ፡ ተደላደለች ፣
ለከሓዲዎችም ፡ ሰዎች ፡ ጥፋት ፡
ተገባቸው ፡ (ጠፉ) ፡ ተባለ ።

45 ኑሕም ፡ ጌታውን ፡ ጠራ ፣ አለም ፡
፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ልጄ ፡ ከቤተ
ሰቤ ፡ ነው ፣ ኪዳንህም ፡ እውነት ፡
ነው ፣ አንተም ፡ ከፈራጆች ፡
ሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ዐዋቂ ፡ ነህ ።
46 (አላህም) ፡ ኑሕ ፡ ሆይ ፡ እርሱ ፡
ከቤተ ፡ ሰብህ ፡ አይደለም ፣ እርሱ፡
መልካም ፡ ያልኾነ ፡ ሥራ ፡ ነው ፣
በርሱ ፡ ዕውቀት ፡ የሌለህንም ፡
ነገር ፡ አትጠይቀኝ ፣ እኔ ፡ ከሚ
ሳሳቱት ፡ ሰዎች ፡ እንዳትኾን ፡
እገሥጽሃለሁ ፡ አለ።
47 ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ በርሱ ፡ ለኔ ፡
ዕውቀት ፡ የሌለኝን ፡ ነገር ፡ የም
ጠይቅህ ፡ ከመኾን ፡ እኔ ፡ ባንተ ፡
እጠበቃለሁ ፣ ለኔም ፡ ባትምረ
ኝና ፡ ባታዝንልኝ ፡ ከከሳሪዎቹ ፡
እኾናለሁ ፡ አለ ።
48 ፡— ኑሕ ፡ ሆይ ፡ ከኛ ፡ በኾነ ፡
ሰላም ፡ ባንተ ፡ ላይና ፡ አንተም ፡
ጋር ፡ ባሉት ፡ ሕዝቦች ፡ (ትው
ልድ) ፡ ላይ ፡ በኾኑ ፡ በረከቶችም ፡
የተጐናጸፍክ ፡ ኾነህ ፡ ውረድ ፣
(ከነሱው ፡ ዘሮች ፡ የኾኑ) ፡ ሕዝ
ቦችም ፡ በቅርቢቱ ፡ ዓለም ፡ በእ
ርግጥ ፡ እናስመቻቻቸዋለን ፣ ከዚ
ያም ፡ ከኛ ፡ የኾነ ፡ አሳማሚ ፡
ቅጣት ፡ ይነካቸዋል ፡ ተባለ ።
49 ይህቺ ፡ ከሩቁ ፡ ወሬዎች ፡ ናት ፣
ወደ ፡ አንተ ፡ እናወርዳታለን ፣
አንተም ፡ ሕዝቦችህም ፡ ከዚህ ፡
በፊት ፡ የምታውቋት ፡ አልነበራ
ችሁም ፣ ታገሥም ፣ ምስጉን ፡ የኾ
ነችው ፡ ፍጻሚ ፡ ለሚጠነቀቁት ፡
ናትና ።
50 ወደ ፡ ዓድም ፡ ወንድማቸውን ፡
ሁድን ፡ (ላክን) ፣ አላቸው ፡—
ወገኖቼ ፡ ሆይ ፡ አላህን ፡ ተገዙ ፣
ከእርሱ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ አምላክ ፡
የላችሁም ፣ እናንተም ፡ ቀጣፊ
ዎች ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደላች
ሁም ።
51 ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ፡ በርሱ ፡ (በማድ
ረሴ) ፡ ላይ ፡ ምንዳን ፡ አልጠይቃ
ችሁም ፣ ምንዳዬ ፡ በዚያ ፡ በፈጠ
ረኝ ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ ላይ ፡
አይደለም ፣ አታውቁምን ?
52 ሕዝቦቼም ፡ ሆይ ፡ ጌታችሁን ፡
ምሕረትን ፡ ለምኑት ፣ ከዚያም ፡
ወደርሱ ፡ ተጸጸቱ ፣ ዝናምን ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ ተከታታይ ፡ አድ
ርጎ ፡ ይልክላችኋልና ፣ ወደ ፡
ኀይላችሁም ፡ ኀይልን ፡ ይጨምር
ላችኋል ፣ አመጠኞችም ፡ ኾና
ችሁ ፡ አትሽሹ ።
53 አሉ ፡— ሁድ ፡ ሆይ ፡ በአስረጅ ፡
አልመጣህልንም ፣ እኛም ፡ ላንተ ፡
ንግግር ፡ ብለን ፡ አማልክቶቻ
ችንን ፡ የምንተው ፡ አይደለንም ፣
እኛም ፡ ለአንተ ፡ አማኞች ፡ አይ
ደለንም ።
54 ከፊሎቹ ፡ አማልክቶቻችን ፡ በ
ክፉ፡ ነገር ፡ (በዕብደት) ፡ ለክፈ
ውሃል ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡ አንልም ፡
(አሉ) ፣ እኔ ፡ አላህን ፡ አስመሰክ
ራለሁ ፣ ከምታጋሩትም ፡ እኔ ፡
ንጹሕ ፡ መኾኔን ፡ መስክሩ ፡ አላ
ቸው ።
55 ከርሱ ፡ ሌላ ፡ (አማልክትን ፡ ከም
ታጋሩት ፡ ንጹህ ፡ ነኝ) ፣ ሁላች
ሁም ፡ ኾናችሁ ፡ ተንኮልን ፡
ሥሩብኝ ፣ ከዚያም ፡ አታቆዩኝ ፣
56 እኔ ፡ በጌታዬና ፡ በጌታችሁ ፡ በአ
ላህ ፡ ላይ ፡ ተጠጋሁ ፣ በምድር ፡
ላይ ፡ ምንም ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ የለ
ችም ፡ እርሱ ፡ አናትዋን ፡ የያዛት ፡
ብትኾን ፡ እንጂ ፣ ጌታዬ ፡ (ቃ
ሉም ፡ ሥራውም) ፡ በቀጥተኛው ፡



መንገድ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ (አላቸው) ።
57 ብትዞሩም ፡ በርሱ ፡ ወደናንተ ፡
የተላክሁበትን ፡ ነገር ፡ በእርግጥ ፡
አድርሼላችኋለሁ ፣ ጌታዬም ፡
ሌላችሁን ፡ ሕዝብ ፡ ይተካል ፣
ምንም ፡ አትጐዱትምም ፣ ጌታዬ ፡
በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ተጠባባቂ ፡
ነውና ፡ (አላቸው) ።
58 ትእዛዛችንም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡
ሁድንና ፡ እነዚያን ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡
ያመኑትን ፡ ከኛ ፡ በኾነው ፡
ችሮታ ፡ አዳን ፣ ከብርቱ ፡ ቅጣ
ትም ፡ አዳናቸው ።
59 ይህች ፡ (ነገድ) ፡ ዓድ ፡ ናት ፣ በጌ
ታቸው ፡ ታምራት ፡ ካዱ ፣ መል
ክተኞቹንም ፡ አምመጡ ፣ የኀ
ያል ፡ ሞገደኛን ፡ ሁሉ ፡ ትእዛ
ዝም ፡ ተከተሉ ።
60 በዚች በቅርቢቱ ፡ ዓለምም ፡
ርግማን እንዲከተላቸው ፡ ተደ
ረጉ ፣ በትንሣኤም ፡ ቀን ፡ (እን
ደዚሁ) ፣ ንቁ ፡ ዓዶች ፡ ጌታቸ
ውን ፡ ካዱ ፣ ንቁ ፡ የሁድ ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ለኾኑት ፡ ዓዶች ፡ (ከእዝ
ነት) ፡ መራቅ ፡ ይገባቸው ።
61 ወደ ፡ ሠሙዶችም ፡ ወንድማቸ
ውን ፡ ሷሊህን ፡ (ላክን) ፣ ፡—ሕዝ
ቦቼ ፡ ሆይ ፡ አላህን ፡ ተገዙ ፣
ከርሱ ፡ ሌላ ፡ ለናንተ ፡ አምላክ ፡
የላችሁም ፣ እርሱ ፡ ከምድር ፡
ፈጠራችሁ ፣ በውስጧ ፡ እንድታለ
ሟትም ፡ አደረጋችሁ ፣ ምሕረቱ
ንም ፡ ለምኑት ፣ ከዚህም ፡ ወደ
ርሱ ፡ ተመለሱ ፣ ጌታዬ ፡ ቅርብ ፡
(ለለመነው) ፡ ተቀባይ ፡ ነውና ፡
አላቸው ።
62 ፡—ሷሊህ ፡ ሆይ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡
በኛ ፡ ውስጥ ፡ (መሪ ፡ ልትኾን) ፡
በእርግጥ ፡ የምትከጀል ፡ ነበርክ ፣
አባቶቻችን ፡ የሚግገዙትን ፡ ከመ
ገዛት ፡ ትከለክለናለህን ? እኛም ፡
ወደርሱ ፡ ከምትጠራን ፡ ነገር ፡
በእርግጥ ፡ አወላዋይ ፡ በኾነ ፡ መጠ
ራጠር ፡ ውስጥ ፡ ነን ፡ አሉ ።
63 ፡—ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ፡ ንገሩኝ ፡ ከጌ
ታዬ ፡ በኾነ ፡ ማስረጃ ፡ ላይ ፡
ብኾን ፡ ከርሱም ፡ የኾነን ፡ ችሮታ
(ነቢይነት) ፡ ቢሰጠኝና ፡ ባልታ
ዘዘው ፡ ከአላህ ፡ (ቅጣት) ፡ የሚያ
ድነኝ ፡ ማነው ? ከማሳሳትም ፡ በስ
ተቀር ፡ ምንም ፡ አትጨምሩል
ኝም ፡ አላቸው ።
64 ሕዝቦቼም ፡ ሆይ ፡ ይህቺ ፡ ለና
ንተ ፡ ታምር ፡ ስትኾን ፡ የአላህ ፡
ግመል ፡ ናት ፣ ተውዋትም ፣ በአ
ላህ ፡ ምድር ፡ ውስጥ ፡ ትብላ ፣
በክፉም ፡ አትንኳት ፣ ቅርብ ፡
የኾነ ፡ ቅጣት ፡ ይይዛችኋልና ፡
(አላቸው) ።
65 ወግተው ፡ ገደሏትም ፣ (ሷሊህ) ፡
በአገራችሁም ፡ ሦስትን ፡ ቀናት ፡
(ብቻ) ፡ ተጠቀሙ ፡ ይህ ፡ የማይ
ዋሽ ፡ ቀጠሮ ፡ ነው ፡ አላቸው ።
66 ትእዛዛችንም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡
ሷሊህንና ፡ እነዚያን ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡
ያመኑትን ፡ ከእኛ ፡ በኾነው ፡
እዝነት ፡ አዳን ፣ ከዚያም ፡ ቀን ፡
ውርደት ፡ (አዳንናቸው) ፣ ጌታህ ፡
እርሱ ፡ ብርቱው ፡ አሸናፊው ፡
ነውና ።
67 እነዚያንም ፡ የበደሉትን ፡ ጩኸት
ያዛቸው ፣ በቤቶቻቸውም ፡ ው
ስጥ ፡ የተንበረከኩ ፡ ኾነው ፡
ሞተው ፡ አነጉ ።
68 በሷ ፡ ውስጥ ፡ እንዳልኖሩባት ፡
ኾኑ ፣ ንቁ ፡ ሠሙዶች ፡ ጌታቸ
ውን ፡ በእርግጥ ፡ ካዱ ፣ ንቁ ፣

ለሠሙዶች ፡ (ከአላህ ፡ እዝነት) ፡
መራቅ ፡ ተገባቸው ።
69 መልክተኞቻችንም ፡ ኢብራሂምን
በ(ልጅ) ፡ ብስራት ፡ በእርግጥ ፡
መጡት ፤ ሰላም ፡ አሉት ፤ ሰላም ፡
አላቸው ፤ ጥቂትም ፡ ሳይቆይ ፡
ወዲያውኑ ፡ የተጠበሰን ፡ የወይ
ፈን ፡ ስጋ ፡ አመጣ ፤
70 እጆቻቸውም ፡ ወደርሱ ፡ የማይደ
ርሱ ፡ መኾናቸውን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡
ሸሻቸው፡ ከነሱም ፡ ፍርሃት ፡
ተሰማው ፤ ፡—አትፍራ ፡ እኛ ፡
ወደ ፡ ሉጥ ፡ ሕዝቦች ፡ ተልከና
ልና ፡ አሉት ።
71 ሚስቱም ፡ የቆመች ፡ ስትኾን ፡
(አትፍራ ፡ አሉት) ፡ ሳቀችም ፤
በኢስሐቅም ፡ አበሰርናት ፤ ከኢስ
ሐቅም ፡ በኋላ ፡ (በልጁ) ፡ በያዕ
ቁብ ፡ (አበሰርናት) ።
72 (እርሷም) ፡ ዋልኝ ! እኔ ፡ አሮጊት ፡
ይህም ፡ ባሌ ፡ ሽማግሌ ፡ ኾኖ ፡
ሳለ ፡ እወልዳለሁን ? ይህ ፡ በእር
ግጥ ፡ አስደናቂ ፡ ነገር ፡ ነው ፡
አለች ፤
73 ፡—ከአላህ ፡ ትእዛዝ ፡ ትደነቂያ
ለሽን ? የአላህ ፡ ችሮታና ፡ በረከ
ቶቹ ፡ በናንተ ፡ በኢብራሂም ፡
ቤተሰቦች ፡ ላይ ፡ ይኹን ፡ እርሱ ፡
ምስጉን ፡ ለጋስ ፡ ነውና ፡ አሉ ።
74 ከኢብራሂም ፡ ፍራቻው ፡ በኼደለ
ትና ፡ ብስራት ፡ በመጣችለትም ፡
ጊዜ ፡ በሉጥ ፡ ሕዝቦች ፡ (ነገር) ፡
ይከራከረን ፡ ጀመር ።
75 ኢብራሂም ፡ በእርግጥ ፡ ታጋሽ ፡
አልቃሻ ፡ መላሳ ፡ ነውና ።
76 ፡—ኢብራሂም ፡ ሆይ ፡ ከዚህ ፡
(ክርክር) ፡ ተው ፤ እነሆ ፡ የጌታህ ፡
ትእዛዝ ፡ በእርግጥ ፡ መጥቷል ፤ እነ
ሱም ፡ የማይመለስ ፡ ቅጣት ፡ የሚ
መጣባቸው ፡ ናቸው ፡ (አሉት) ።
77 መልክተኞቻችንም ፡ ሉጥን ፡ በመ
ጡት ፡ ጊዜ ፡ በነሱ ፡ (ምክንያት) ፡
አዘነ ፤ ልቡም ፡ በነሱ ፡ ተጨነቀ ፤
ይህ ፡ ብርቱ ፡ ቀን ፡ ነውም ፡ አለ ።
78 ሕዝቦቹም ፡ ወደርሱ ፡ እየተጣ
ደፉ ፡ መጡት ፤ ከዚህም ፡ በፊት ፡
መጥፎ ፡ ሥራዎችን ፡ ይሠሩ ፡
ነበር ፤ ፡—ሕዝቦቼ ፡ ሆይ እኻህ፡
ሴቶች ፡ ልጆቼ ፡ ናቸው ፤ እነሱ ፡
ለናንተ ፡ ይልቅ ፡ በጣም ፡ የጠዱ ፡
ናቸው ፤ (አግቧቸው) ፤ አላህንም ፡
ፍሩ ፤ በእንግዶቼም ፡ አታሳፍ
ሩኝ ፤ ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ ቅን ፡
ሰው ፡ የለምን ? አላቸው ።
79 ፡—ከሴቶች ፡ ልጆችህ ፡ ለኛ ፡
ምንም ፡ ጉዳይ ፡ የለንም ፤ አን
ተም ፡ የምንሻውን ፡ በእርግጥ ፡
ታውቃለህ ፡ አሉት ።
80 ፡—በናንተ ፡ ላይ ፡ ለኔ ፡ ኀይል ፡
በኖረኝ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ብርቱ ፡
ወገን ፡ ብጠጋ ፡ ኖሮ ፡ (የምሠራ
ውን ፡ በሠራሁ ፡ ነበር) ፡ አላቸው።
81 ፡—ሉጥ ፡ ሆይ ፡ እኛ ፡ የጌታህ ፡
መልክተኞች ፡ ነን ፤ (ሕዝቦችህ) ፡
ወደ ፡ አንተ ፡ (በክፉ) ፡ አይደርሱ
ብህም ፤ ቤተሰብህንም ፡ ይዘህ ፡
ከሌሊቱ ፡ በከፊሉ ፡ ውስጥ ፡
ኺድ ፤ ከናንተም ፡ አንድም ፡
(ወደ ፡ ኋላው) ፡ አይገላመጥ ፤
ሚስትህ ፡ ብቻ ፡ ስትቀር ፤ እነሆ ፡
እርሷን ፡ የሚያገኛቸው ፡ ስቃይ ፡
ያገኛታልና ፤ ቀጠሯቸው ፡ እን
ጋቱ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ ንጋቱ ፡ ቅርብ ፡
አይደለምን ? አሉት ።
82 ትእዛዛችንም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡
(ከተማይቱን) ፡ ላያዋን ፡ ከታ
ችዋ ፡ አደረግን ፤ (ገለበጥናት) ፡



ተከታታይም ፡ የኾነን ፡ የሸክላ ፡
ድንጊያ ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ አዘነምን ።
83 ከጌታህ ፡ ዘንድ ፡ ምልክት ፡ የተ
ደረገባት ፡ ስትኾን ፡ (አዘነምናት) ፡
እርሷም ፡ ከበደለኞቹ ፡ ሩቅ ፡ አይ
ደለችም ።
84 ወደ ፡ መድየንም ፡ ወንድማቸ
ውን ፡ ሹዐይብን ፡ (ላክን) ፤ አላ
ቸው ፡ ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ! አላህን ፡
ተገዙ ፤ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ ለናንተ ፡
አምላክ ፡ የላችሁም ፤ ስፍርንና ፡
ሚዛንንም ፡ አታጉድሉ ፤ እኔ ፡ በ
ጸጋ ፡ ላይ ፡ ኾናችሁ ፡ አያችኋለሁ ፤
እኔም ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ የከባቢን ፡
ቀን ፡ ቅጣት ፡ እፈራለሁ ።
85 ሕዝቦቼም ፡ ሆይ ! ስፍርንና ፡
ሚዛንን ፡ በትክክል ፡ ምሉ ፤ ሰዎ
ችንም ፡ እንዳቾቻቸውን ፡ አታጉ
ድሉባቸው ፤ በምድርም ፡ ውስጥ ፡
አጥፊዎች ፡ ኾናችሁ ፡ አታበላሹ።
86 አላህ ፡ ያስቀረላችሁ ፡ (1) ለና
ንተ ፡ የተሻለ ፡ ነው ፤ ምእምናን ፡
እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ (አላህ ፡ በሰጣ
ችሁ ፡ ውደዱ) ፡ እኔም ፡ (መካሪ ፡
እንጅ) ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ተጠባባቂ
አይደለሁም ።
87 ፡—ሹዐይብ ፡ ሆይ ! ስግደትህ ፡
አባቶቻችን ፡ የሚገገዙትን ፡ ጣዖ
ታት ፡ እንድንተው ፡ ወይም ፡ በገ
ንዘቦቻችን ፡ የምንሻውን ፡ መሥ
ራትን ፡ (እንድንተው) ፡ ታዝሃለ
ችን ? አንተ ፡ በእርግጥ ፡ ታጋሹ ፡
ቅኑ ፡ (2) አንተ ፡ ነህና ፡ አሉት ።
88 ፡—ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ! ንገሩኝ ፤ ከጌ
ታዬ ፡ በኾነ ፡ አስረጅ ፡ ላይ ፡
ብኾንና ፡ ከርሱም ፡ የኾነን ፡ መል
ካም ፡ ሲሳይ ፡ ቢሰጠኝ ፡ (በቅጥ
ፈት ፡ ልቀላቅለው ፡ ይገባልን ?)
ከርሱ ፡ ወደ ፡ ከለከልኳችሁም ፡
ነገር ፡ ልለያችሁ ፡ (1) አልሻም ፤
በተቻለኝ ፡ ያክል ፡ ማበጀትን ፡
እንጂ ፡ አልሻም ፤ (ለደግ ፡ ሥራ) ፡
መገጠሜም ፡ በአላህ ፡ እንጂ ፡
በሌላ ፡ አይደለም ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡
ተመካሁ ፤ ወደርሱም ፡ እመለሳ
ለሁ ፤ አላቸው ።
89 ወገኖቼም ፡ ሆይ ! እኔን ፡ መከራከ
ራችሁ ፡ የኑሕን ፡ ሕዝቦች ፡
ወይም ፡ የሁድን ፡ ሕዝቦች ፡
ወይም ፡ የሷሊሕን ፡ ሕዝቦች ፡
ያገኛቸው ፡ (ቅጣት) ፡ ብጤ ፡ እን
ዲያገኛችሁ ፡ አይገፋፋችሁ ፤ የሉ
ጥም ፡ ሕዝቦች ፡ ከናንተ ፡ ሩቅ ፡
አይደሉም ።
90 ጌታችሁንም ፡ ምሕረትን ፡ ለም
ኑት ፤ ከዚያም ፡ ወደርሱ ፡ ተመ
ለሱ ፤ ጌታዬ ፡ አዛኝ ፡ ወዳድ ፡
ነውና ፡ (አላቸው) ።
91 ፡—ሹዐይብ ፡ ሆይ ! ከምትለው ፡
ነገር ፡ ብዙውን ፡ አናውቀውም ፤
እኛም ፡ አንተን ፡ በኛ ፡ ውስጥ ፡
ደካማ ፡ ኾነህ ፡ እናይሃለን ፤ ጐሶ
ችህም ፡ ባልኖሩ ፡ ኖሮ ፡ በወገር
ንህ ፡ ነበር ፤ አንተም ፡ በኛ ፡ ላይ ፡
የተከበርክ ፡ አይደለህም ፡ አሉት ።
92 ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ! ጐሶቼ ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ ከአላህ ፡ ይልቅ ፡ የከበሩ ፡
ናቸውን ? (አላህን) ፡ ከኋላችሁ ፡
ወደ ፡ ጀርባ ፡ አድርጋችሁም ፡
ያዛችሁት ፤ ጌታዬ ፡ በምትሠሩት ፡
ሁሉ ፡ ከባቢ ፡ ነው ፡ አላቸው ።
93 ሕዝቦቼም ፡ ሆይ ! በችሎታችሁ ፡
ልክ ፡ ሥሩ ፤ እኔ ፡ ሠሪ ፡ ነኝና ፤
የሚያዋርደው ፡ ቅጣት ፡ የሚመ

1 ስፍርንና ፡ ሚዛንን ፡ ሞልታችሁ ፡ የተረ
ፈው ፡ ሲሳይ ።
2 መቀጣጠባቸው ፡ ነው ።

1 እናንተን ፡ ከልክየ ፡ እኔ ፡ ልሠራው ።

ጣበትና ፡ እርሱ ፡ ውሸታም ፡ የኾ
ነው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወደ ፡
ፊት ፡ ታውቃላችሁ ፤ ጠብቁም ፤
እኔ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ተጠባባቂ ፡
ነኝና ፡ (አላቸው) ።
94 ትእዛዛችንም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡
ሹዐይብንና ፡ እነዚያን ፡ ከርሱ ፡
ጋር ፡ ያመኑትን ፡ ከኛ ፡ በኾነው ፡
ችሮታ ፡ አዳን ፤ እነዚያን ፡ የበደ
ሉትንም ፡ (የጂብሪል) ፡ ጩኸት ፡
ያዘቻቸው ፤ በቤቶቻቸውም ፡
ውስጥ ፡ ተንከፍርረው ፡ አደሩ ።
95 በርሷ ፡ ውስጥ ፡ እንዳልነበሩ ፡
ኾኑ ፤ ንቁ ፤ ሠሙድ ፡ (ከአላህ ፡
እዝነት) ፡ እንደ ፡ ራቀች ፡ መድ
የንም ፡ ትራቅ ።
96 ሙሳንም ፡ በታምራታችንና ፡
በግልጽ ፡ ብርሃን ፡ በእርግጥ ፡
ላክነው ።
97 ወደ ፡ ፈርዖንና ፡ ወደ ፡ ሰዎቹ ፡
(ላክነው) ፤ የፈርዖንንም ፡ ነገር ፡
(ሕዝቦቹ) ፡ ተከተሉ ፤ የፈርዖን ፡
ነገርም ፡ ቀጥተኛ ፡ አልነበረም ።
98 በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ሕዝቦቹን ፡ ይቀ
ድማል ፤ ወደ ፡ እሳትም ፡ ያወርዳ
ቸዋል ፤ የሚገቡትም ፡ አገባብ ፡
ምንኛ ፡ ከፋ !
99 በዚችም ፡ (በቅርቢቱ ፡ ዓለም) ፡
እርግማንን ፡ አስከተልናቸው ፤
በትንሣኤም ፡ ቀን ፡ (እንደዚሁ) ፤
የተሰጡት: ስጦታ: ምንኛ: ከፋ!
100 ይህ: (የተነገረው): ከከተሞቹ:
ወሬዎች: ነው፤ ባንተ: ላይ
እንተርከዋለን፤ ከርሷ: ፋናው:
የቀረና: ሙሉ: በሙሉ: የተደ
መሰሰ: አልለ።
101 እኛም ፡ አልበደልናቸውም ፤ ግን ፡
ነፍሶቻቸውን ፡ በደሉ ፤ የአላህም ፡
ትእዛዝ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡
ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የሚግገዙዋቸው ፡
አማልክቶቻቸው ፡ በምንም ፡ አላ
ዳኑዋቸውም ፤ ከማክሰርም ፡ በቀር
ምንም ፡ አልጨመሩላቸውም ።
102 የጌታህም ፡ ቅጣት ፡ የከተሞችን ፡
ሰዎች ፡ እነሱ ፡ በዳዮች ፡ ሲኾኑ ፡
በቀጣቸው ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡
ነው ፤ ቅጣቱ ፡ በእርግጥ ፡ አሳ
ማሚ ፡ ብርቱ ፡ ነው ።
103 በዚህ ፡ (1) ውስጥ ፡ የመጨረሻ
ውን ፡ ቀን ፡ ቅጣት ፡ ለሚፈሩ ፡
ሁሉ ፡ መገሠጫ ፡ አልለ ። ይህ ፡
(የትንሣኤ ፡ ቀን) ፡ ሰዎች ፡ በ
ርሱ ፡ የሚሰበሰቡበት ፡ ቀን ፡
ነው ፤ ይህም ፡ የሚጣዱት ፡ ቀን ፡
ነው ።
104 (ይህንን ፡ ቀን) ፡ ለተቆጠረም ፡
ጊዜ ፡ እንጂ ፡ አናቆየውም ።
105 በሚመጣ ፡ ቀን ፡ ማንኛዋም ፡
ነፍስ ፡ በርሱ ፡ ፈቃድ ፡ ቢኾን ፡
እንጂ ፡ አትናገርም ፤ ከነሱም ፡
መናጢና ፡ ዕድለኛም ፡ አልለ ።
106 እነዚያ: መናጢ: የሆኑትማ፥
በእሳት: ውስጥ: ናቸው፤ ለነርሱ:
በርሷ: ውስጥ: ማናፋትና:
መንሰቅሰቅ: አላቸው።
107 ጌታህ ፡ ከሻው ፡ (ጭማሬ) ፡ ሌላ ፡
ሰማያትና ፡ ምድር ፡ እስከ ፡ ዘወ
ተሩ ፡ ድረስ ፡ በውስጧ ፡ ዘውታሪ
ዎች ፡ ሲኾኑ ፡ (በእሳት ፡ ይኖ
ራሉ) ፤ ጌታህ ፡ የሚሻውን ፡ ሠሪ ፡
ነውና ።
108 እነዚያም ፡ ዕድለኞቹማ ፡ ጌታህ ፡
ከሻው ፡ (ጭማሬ) ፡ ሌላ ፡ ሰማያ
ትና ፡ ምድር ፡ እስከ ፡ ዘወተሩ ፡
ድረስ ፡ በውስጧ ፡ ዘውታሪዎች ፡
ኾነው ፡ በገነት ፡ ውስጥ ፡ ይኖ

1 ባለፈው ፡ ሰባት ፡ ታሪክ ።



ራሉ ፤ የማይቋረጥ ፡ ስጦታን ፡
ተሰጡ ።
109 እነዚህ ፡ (ከሓዲዎች) ፡ ከሚግገ
ዙት ፡ ጣዖት ፡ በመጠራጠር ፡
ውስጥ ፡ አትኹን ፤ አባቶቻቸው ፡
ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደሚግገዙት ፡
እንጂ ፡ አይግገዙም ፤ እኛም ፡
(እነዚህን) ፡ ፈንታቸውን ፡ የማይ
ጓደል ፡ ሲኾን ፡ የምንሞላላቸው ፡
ነን ።
110 ለሙሳም ፡ መጽሐፍን ፡ በእርግጥ፡
ሰጠነው ፤ በርሱም ፡ ተለያዩበት ፤
ከጌታህም ፡ ያለፈች ፡ ቃል ፡ ባል
ነበረች ፡ ኖሮ ፡ በመካከላቸው ፡
(አሁን) ፡ ይፈረድ ፡ ነበር ፤ እነ
ሱም ፡ ከርሱ ፡ (ከቁርአን) ፡ አወ
ላዋይ ፡ በኾነ ፡ መጠራጠር ፡
ውስጥ ፡ ናቸው ።
111 ሁሉንም ፡ ጌታህ ፡ ሥራዎቻቸ
ውን ፡ (ምንዳቸውን) ፡ በእርግጥ ፡
ይሞላላቸዋል ፤ እርሱ ፡ በሚሠ
ሩት ፡ ሁሉ ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡
ነውና ።
112 እንደ ፡ ታዘዝከውም ፡ ቀጥ ፡ በል ፤
ከአንተ ፡ ጋር ፡ ያመኑትም ፡
(ቀጥ ፡ ይበሉ) ፤ ወሰንንም ፡ አት
ለፉ ፤ እርሱ ፡ የምትሠሩትን ፡
ሁሉ ፡ ተመልካች ፡ ነውና ።
113 ወደነዚያም ፡ ወደ ፡ በደሉት ፡ አት
ጠጉ ፤ እሳት ፡ ትነካችኋለችና ፤
ከአላህም ፡ ሌላ ፡ ጠባቂዎች ፡ የሏ
ችሁም ፤ ከዚያም ፡ አትረዱም ።
114 ሶላትንም ፡ በቀን ፡ ጫፎች ፤ (1)
ከሌሊትም ፡ ክፍሎች ፡ ፈጽም ፤
መልካም ፡ ሥራዎች ፡ ኀጢአቶ
ችን ፡ ያስወግዳሉና ፤ ይህ ፡ ለተገሣ
ጮች ፡ ግሣጤ ፡ ነው ።
115 ታገሥም ፤ አላህ ፡ የበጎ ፡ ሠሪዎ
ችን ፡ ምንዳ ፡ አያጠፋምና ።
116 ከናንተም ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ከክ
ፍለ ፡ ዘመናት ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ ከማበላሸት ፡ የሚ
ከለክሉ ፡ የመልካም ፡ ቀሪ ፡ ሥራ
ዎች ፡ ባለቤቶች ፡ ለምን ፡ አልነበ
ሩም ፤ ግን ፡ ከነሱ ፡ ያዳንናቸው ፡
ጥቂቶቹ ፡ (ከለከሉና ፡ ዳኑ) ። እነ
ዚያም ፡ የበደሉት ፡ ሰዎች ፡ (አል
ከለከሉም) ፤ በርሱ ፡ የተቀማጠሉ
በትን ፡ ተድላ ፡ ተከተሉ ፤ አመጠ
ኞችም ፡ ነበሩ ።
117 ጌታህም ፡ ከተሞችን ፡ ባለ ፡ ቤቶ
ቻቸው ፡ መልካም ፡ ሠሪዎች ፡
ኾነው ፡ ሳሉ ፡ በመበደል ፡ የሚያ
ጠፋቸው ፡ አልነበረም ።
118 ጌታህም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ ሰዎችን ፡
ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ባደረጋ
ቸው ፡ ነበር ፤ የተለያዩም ፡ ከመ
ኾን ፡ አይወገዱም ።
119 ጌታህ ፡ ያዘነለት ፡ ብቻ ፡ ሲቀር ፤
(ከመለያየት ፡ አይወገዱም) ፤ ለዚ
ሁም ፡ ፈጠራቸው ፤ (1) የጌታ
ህም ፡ ቃል ፡ ገሀነምን ፡ ከአጋንን
ትና ፡ ከሰዎች ፡ ከሁሉም ፡ በእር
ግጥ ፡ እሞላታለሁ ፡ በማለት ፡
ተፈጸመች ።
120 ከመልክተኞቹም ፡ ዜናዎች ፡ (ተፈ
ላጊውን) ፡ ሁሉንም ፡ ልብህን ፡
በርሱ ፡ የምናረካበትን ፡ እንተርክ
ልሃለን ፤ በዚችም ፡ (ሱራ) ፡ እ
ውነቱ ፡ ነገር ፡ ለምእምናን ፡ ግሣ
ጼና ፡ ማስታወሻ ፡ መጥቶልሃል ።
121 ለነዚያም ፡ ለማያምኑት ፡- ባላችሁ
በት ፡ ኹኔታ ፡ ላይ ፡ ሥሩ ፤ እኛ ፡
ሠሪዎች ፡ ነንና ፡ በላቸው ።

1 ጥዋትና ፡ ከቀትር ፡ በኋላ ።

1 መጨረሻቸው ፡ ይህ ፡ ኾነ ።

122 ተጠባበቁም ፡ እኛ ፡ ተጠባባቂዎች ፡ ነንና ፡ (በላቸው) ።

123 በሰማያትና ፡ በምድርም ፡ ያለው ፡ ምስጢር ፡ ሁሉ ፡ የአላህ ፡ ነው ፤ ነገሩ ፡ ሁሉም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይመለሳል ፤ ስለዚህ ፡ ተገዛው ፤ በርሱም ፡ ላይ ፡ ተጠጋ ፤ ጌታህም ፡ ከሚሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ዘንጊ ፡ አይደለም ።

## ምዕራፍ ፡ 12 ፡ ዩሱፍ ። ክፍል ፡ 12 ።

12ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ዩሱፍ ፡ (የዮሴፍ ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 111 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 አ.ለ.ረ. (አሊፍ ፡ ላም ፡ ራ) ፡ እነዚህ ፡ የገላጩ ፡ መጽሐፍ ፡ አንቀጾች ፡ ናቸው ።

2 እኛ ፡ (ፍቹን) ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ዐረብኛ ፡ ቁርአን ፡ ሲኾን ፡ በእርግጥ ፡ አወረድነው ።

3 እኛ ፡ ይህንን ፡ ቁርአን ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ በማውረዳችን ፡ በጣም ፡ መልካም ፡ ዜናዎችን ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ እንተርክልሃለን ፤ እነሆ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ (ካለፉት ፡ ሕዝቦች ፡ ታሪክ) ፡ በእርግጥ ፡ ከዘንጊዎቹ ፡ ነበርክ ።

4 ዩሱፍ ፡ ለአባቱ ፡— አባቴ ፡ ሆይ! እኔ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ከዋክብትን ፡ ፀሐይንና ፡ ጨረቃንም ፡ (በሕልሜ) ፡ አየሁ ፤ ለእኔ ፡ ሰጋጆች ፡ ኾነው ፡ አየኋቸው ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ።

5 (አባቱም) ፡ አለ ፡— ልጄ ፡ ሆይ! ሕልምህን ፡ ለወንድሞችህ ፡ አታውራ ፤ ላንተ ፡ ተንኮልን ፡ ይሠሩብሃልና ፤ ሰይጣን ፡ ለሰው ፡ ግልጽ ፡ ጠላት ፡ ነውና ።

6 እንደዚሁም ፡ (እንዳየኸው) ፡ ጌታህ ፡ ይመርጥሃል ፤ ከንግግርችም ፡ ፍች ፡ ያስተምርሃል ፤ ጸጋውንም ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡ በሁለቱ ፡ አባቶችህ ፡ በኢብራሂምና ፡ በኢስሐቅ ፡ ላይ ፡ እንደአሟላት ፡ በአንተ ፡ ላይና ፡ በያዕቆብ ፡ ዘሮችም ፡ ላይ ፡ ይሞላታል ፤ ጌታህ ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነውና ።

7 በዩሱፍና ፡ በወንድሞቹ ፡ (ታሪኮች) ፡ ውስጥ ፡ ለጠያቂዎች ፡ ሁሉ ፡ በእርግጥ ፡ አስደናቂ ፡ ምልክቶች ፡ ነበሩ ፤

8 (ወንድሞቹ) ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፤ ፡—እኛ ፡ ጭፍሮች ፡ ስንኾን ፡ ዩሱፍና ፡ ወንድሙ ፡ (ብንያም) ፡ ወደ ፡ አባታችን ፡ ከኛ ፡ ይበልጥ ፡ የተወደዱ ፡ ናቸው ፡ አባታችን ፡ በግልጽ ፡ ስሕተት ፡ ውስጥ ፡ ነው ፤

9 ዩሱፍን ፡ ግደሉ ፤ ወይም ፡ በ(ሩቅ) ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ጣሉት ፤ ያባታችሁ ፡ ፊት ፡ ለናንተ ፡ የግል ፡ ይኾናልና ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ መልካም ፡ ሕዝቦች ፡ ትኾናላችሁና ፡ (ተባባሉ) ።



10 ከነሱ ፡ አንድ ፡ ተናጋሪ ፡— ዩሱፍን ፡ አትግደሉ ፤ ግን ፡ በጉድጓድ ፡ አዘቅት ፡ ጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ጣሉት ፤ ከተጓዦች ፡ አንዱ ፡ ያነሳዋልና ፤ ሠሪዎች ፡ ብትኾኑ ፡ (በዚሁ ፡ ተብቃቁ) ፡ አላቸው ።

11 (እነሱም) ፡ አሉ ፡— አባታችን ፡ ሆይ ! በዩሱፍ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ አታምነንም ? እኛም ፡ ለርሱ ፡ በእርግጥ ፡ አዛኞች ፡ ነን ፤

12 ነገ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ላከውና ፡ ይደሰት ፤ ይጫወትም ፤ እኛም ፡ ለርሱ ፡ ጠባቂዎች ፡ ነን ።

13 ፡— እኔ ፡ እርሱን ፡ (ዩሱፍን) ፡ ይዛችሁ ፡ መኼዳችሁ ፡ በእርግጥ ፡ ያሳዝነኛል ፤ እናንተም ፡ ከርሱ ፡ ዘንጊዎች ፡ ስትኾኑ ፡ ተኵላ ፡ ይበላዋል ፡ ብዬ ፡ እፈራለሁ ፡ አላቸው ።

14 ፡— እኛ ፡ ጭፍራዎች ፡ ኾነን ፡ ሳለን ፡ ተኵላ ፡ ቢበላውማ ፡ እኛ ፡ ያንጊዜ ፡ በእርግጥ ፡ ከሳሪዎች ፡ ነን ፡ አሉት ።

15 እርሱንም ፡ ይዘውት ፡ በኼዱና ፡ በጉድጓዱ ፡ ጨለማ ፡ አዘቅት ፡ ውስጥ ፡ እንዲያደርጉት ፡ በቆረጡ ፡ ጊዜ ፡ (ሐሳባቸውን ፡ ፈጸሙበት) ፤ ወደርሱም ፡ እነሱ ፡ የማያውቁ ፡ ሲኾኑ ፡ ይህንን ፡ ሥራቸውን ፡ በእርግጥ ፡ ትነግራቸዋለህ ፡ ስንል ፡ ላክንበት ።

16 አባታቸውንም ፡ በምሽት ፡ እያለቀሱ ፡ መጡት ፤

17 ፡—አባታችን ፡ ሆይ ! እኛ ፡ (ለሩጫና ፡ ለውርወራ) ፡ ልንሽቀዳደም ፡ ኼድን ፤ ዩሱፍንም ፡ ዕቃችን ፡ ዘንድ ፡ ተውነው ፤ ወዲያውም ፡ ተኵላ ፡ በላው ፤ አንተም ፡ እውነተኞች ፡ ብንኾንም ፡ የምታምነን ፡ አይደለህም ፡ አሉ ።

18 በቀሚሱም ፡ ላይ ፡ የውሸትን ፡ ደም ፡ አመጡ ፤ (አባታቸው) ፡ አይደለም ፤ ነፍሶቻችሁ ፡ (ውሸት) ፡ ነገርን ፡ ለናንተ ፡ ሸለሙላችሁ ፤ ስለዚህ ፡ መልካም ፡ ትእግሥት ፡ (ማድረግ ፡ አለብኝ) ፡ በምትሉትም ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ መታገገሪው ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ አለ ።

19 መንገደኞችም ፡ መጡ ፤ ውሃ ፡ ቀጂያቸውንም ፡ ላኩ ፤ አኮሊውንም ፡ (ወደ ፡ ጉድጓዱ) ፡ ሰደደ ፤ [1] ፡—የምስራች ! ይህ ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ አለ ፤ ሸቀጥ ፡ አድርገውም ፡ ደበቁት ፤ አላህም ፡ የሚሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

20 በርካሽ ፡ ዋጋም ፡ በሚቆጠሩ ፡ ዲርሃሞች ፡ ሸጡት ፤ በርሱም ፡ ከቸልተኞቹ ፡ ነበሩ ።

21 ያም ፡ ከምስር ፡ የገዛው ፡ ሰው ፡ ለሚስቱ ፡— መኖሪያውን ፡ አክብሪ ፤ ሊጠቅመን ፡ ወይም ፡ ልጅ ፡ አድርገን ፡ ልንይዘው ፡ ይከጀላልና ፤ አላት ፤ እንደዚሁም ፡ ለዩሱፍ ፡ (ገዥ ፡ ልናደርገውና) ፡ የሕልሞችንም ፡ ፍች ፡ ልናስተምረው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አስመቸነው ፤ አላህም ፡ በነገሩ ፡ ላይ ፡ አሸናፊ ፡ ነው ፤ ግን ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ሰዎች ፡ አያውቁም ።

22 ጥንካሬውንም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ጥበብንና ፡ ዕውቀትን ፡ ሰጠነው ፤

---

1 ዩሱፍም ፡ አኮሌው ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ወጣ ።

እንደዚሁም ፡ መልካም ፡ ሠሪዎ
ችን ፡ ሁሉ ፡ እንመነዳለን ።
23 ያቺም ፡ እርሱ ፡ በቤትዋ ፡ የነበረ
ባት ፡ ሴት ፡ ከነፍሱ ፡ አባበለችው፤
ደጃፎቹንም ፡ ዘጋች ፤ ላንተ ፡ ተዘ
ጋጂቸልሃለሁና ፡ ቶሎ ፡ ናም ፡
አለች ፤ በአላህ ፡ እጠበቃለሁ ፤
እርሱ ፡ (የገዛኝ) ፡ ጌታዬ ፡ ኑሮ
ዬን ፡ ያሳመረልኝ ፡ ነውና ፤ (አል
ከዳውም) ፤ እነሆ ! በደለኞች ፡
አይድኑም ፤ አላት ።
24 በርሱም ፡ በእርግጥ ፡ አሰበች ፤
በርሷም ፡ አሰበ ፤ የጌታውን ፡ ማስ
ረጃ ፡ ባላዬ ፡ ኖሮ ፡ (የተፈጥሮ ፡
ፍላጎቱን ፡ ባረካ ፡ ነበር ፤) እንደ
ዚሁ ፡ መጥፎ ፡ ነገርንና ፡ ኀጢአ
ትን ፡ ከርሱ ፡ ላይ ፡ ልንመልስለ
ት ፡ (አስረጃችንን ፡ አሳየነው) ፤ እ
ርሱ ፡ ከተመረጡት ፡ ባሮቻችን ፡
ነውና ።
25 በሩንም ፡ ተሽቀዳደሙ ፤ (1) ፡
ቀሚሱንም ፡ ከስተኋላው ፡ ቀደደ
ችው ፤ ጌታዋንም ፡ (ባለቤትዋን) ፡
እበሩ ፡ አጠገብ ፡ አገኙት ፤ (ቀ
ደም ፡ ብላ) ፡ በባለቤትህ ፡ መጥ
ፎን ፡ ያሰበ ፡ ሰው ፡ ቅጣቱ ፡ መታ
ሰር ፡ ወይም ፡ አሳማሚ ፡ ስቃይ ፡
እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፡ አለ
ችው ።
26 (ዩሱፍም) ፡ እርሷ ፡ ከነፍሴ ፡ አባ
በለችኝ ፡ አለ ፤ ከቤተሰቦችዋም ፡
መስካሪ ፡ (እንዲህ ፡ ሲል) ፡ መሰ
ከረ ፤ ቀሚሱ ፡ ከስተፊት ፡ ተቀዶ ፡
እንደ ፡ ኾነ ፡ እውነት ፡ ተናገረች ፤
እርሱም ፡ ከውሸታሞቹ ፡ ነው ።
27 ቀሚሱም ፡ ከስተኋላ ፡ ተቀዶ ፡
እንደ ፡ ኾነ ፡ ዋሸች ፤ እርሱም ፡
ከእውነተኞቹ ፡ ነው ።
28 ቀሚሱንም ፡ ከስተኋላ ፡ ተቀዶ ፡
ባየ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ (የተናገር
ሺው) ፡ ከተንኮላችሁ ፡ ነው ፤
(ሴቶች) ፡ ተንኮላችሁ ፡ በእርግጥ ፡
ብርቱ ፡ ነውና ፡ አላት ።
29 ፡—ዩሱፍ ፡ ሆይ ! ከዚህ ፡ (ወሬ) ፡
ተከልከል ፤ ለኃጢአትሽም ፡ ማር
ታን ፡ ለምኝ ፤ አንቺ ፡ ከስሕተተ
ኞቹ ፡ ኾነሻልና ፡ (አለ) ።
30 በከተማው ፡ ያሉ ፡ ሴቶችም ፡ የዐ
ዚዝ ፡ (1) ሚስት ፡ ብላቴናዋን ፡
ከነፍሱ ፡ ታባብለዋለች ፤ በወ
ነቱ ፡ ፍቅሩ ፡ ልቧን ፡ መቷታል ፤
እኛ ፡ በግልጽ ፡ ስሕተት ፡ ውስጥ፡
ኾና ፡ በእርግጥ ፡ እናያታለን ፡
አሉ ።
31 ኑሜታቸውንም ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡
ወደነሱ ፡ ላከችባቸው ፤ ምግብ
ንም ፡ ለነርሱ ፡ አዘጋጀችላቸው ፤
ከነሱ ፡ ለያንዳንዳቸውም ፡ ቢላ
ዋን ፡ ሰጠች ፤ በነሱም ፡ ላይ ፡
ውጣ ፡ አለችው ፤ ባዩትም ፡ ጊዜ ፡
አደነቁት ፤ እጆቻቸውንም ፡ ቆ
ረጡ ፤ አላህም ፡ ጥራት ፡ ይገባው ፤
ይህ ፡ ሰው ፡ አይደለም ፤ ይህ ፡
የማረ ፡ መልአክ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡
አይደለም ፡ አሉ ።
32 ፡—ታዲያ ፡ ይኻችሁ ፡ ያ ፡ በርሱ ፡
(ፍቅር) ፡ የዘለፋችሁኝ ፡ ነው ፤
በእርግጥም ፡ ከነፍሱ ፡ አባበል
ኩት ፤ እንቢ ፡ አለም ፤ የማዘወ
ንም ፡ ነገር ፡ ባይሠራ ፡ በእርግጥ ፡
ይታሰራል ፤ ከወራዶቹም ፡ ይኾ
ናል ፡ አለች ፤
33 ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ! ወደርሱ ፡ ከሚ
ጠሩኝ ፡ ነገር ፡ (ከዝሙት) ፡
ይልቅ ፡ መታሰር ፡ ለኔ ፡ የተወ

1 እርሱ ፡ ለማምለጥ ፡ እርሷ ፡ ለመያዝ ።

1 የማዕረግ ፡ ስሙ ፡ ነው ፤ የተጸውዖ ፡ ስሙ ፡ ቂጥፊር ፡ ነው ።



ደደ ፡ ነው ፤ ተንኮላቸውንም ፡
ከኔ ፡ ላይ ፡ ባትመልስልኝ ፡ ወደ
ነሱ ፡ እዘነበላለሁ ፤ ከስሕተተኞ
ቹም ፡ እኾናለሁ ፡ አለ ።
34 ጌታውም ፡ ጸሎቱን ፡ ተቀበለው ፤
ተንኮላቸውንም ፡ ከርሱ ፡ መለሰ
ለት ፤ እነሆ ! እርሱ ፡ ሰሚው ፡
ዐዋቂው ፡ ነውና ።
35 ከዚያም ፡ ማስረጃዎቹን ፡ ካዩ ፡
በኋላ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ እንዲ
ያስሩት ፡ ለነሱ ፡ ታያቸው ።
36 ከሱም ፡ ጋር ፡ ሁለት ፡ ጐበዞች ፡
እስር ፡ ቤቱ ፡ ገቡ ፤ አንደኛቸው ፡
እኔ ፡ በሕልሜ ፡ የወይን ፡ ጠጅን ፡
ስጠምቅ ፡ አየሁ ፡ አለ ፤ ሌላ
ውም ፡— እኔ ፡ በራሴ ፡ ላይ ፡ እን
ጀራን ፡ ተሸክሜ ፡ ከሱ ፡ በራሪ ፡
(አሞራ) ፡ ስትበላ ፡ አየሁ ፤ ፍቹን ፡
ንገረን ፤ እኛ ፡ ከአሳማሪዎች ፡
ኾነህ ፡ እናይሃለንና ፡ አሉት ።
37 (ዩሱፍም) ፡ አለ ፡— ማንኛውም ፡
የምትሰሰጡት ፡ ምግብ ፡ ለናንተ ፡
ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ ፍቹን ፡ የምነ
ግራችሁ ፡ ቢኾን ፡ እንጅ ፡ አይመ
ጣላችሁም ፤ ይሃችሁ ፡ ጌታዬ ፡
ካሳወቀኝ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ እኔ ፡ በአ
ላህ ፡ የማያምኑን ፡ እነርሱም ፡
መጨረሻይቱን ፡ ዓለም ፡ እነርሱ ፡
ከሓዲዎች ፡ የኾኑትን ፡ ሕዝቦች ፡
ሃይማኖት ፡ ትቻለሁ ፤
38 የአባቶቼንም ፡ የኢብራሂምንና፥
የኢስሐቅን ፡ የያዕቆብንም ፡ ሃይ
ማኖት ፡ ተከትያለሁ ፤ ለኛ ፡ በአ
ላህ ፡ ምንንም ፡ ማጋራት ፡ አይገባ
ንም ፤ ያ ፡ (አለማጋራት) ፡ በኛ ፡
ላይና ፡ በሰዎቹ ፡ ላይ ፡ የአላህ ፡
ችሮታ ፡ ነው ፤ ግን ፡ አብዛኞቹ ፡
ሰዎች ፡ አያመሰግኑም ።
39 የእስር ፡ ቤት ፡ ጓደኞቼ ፡ ሆይ !
የተለያዩ ፡ (1) አምላኮች ፡ ይሻላ
ሉን ፡ ወይስ ፡ አሸናፊው ፡ አንዱ ፡
አላህ ?
40 ከርሱ ፡ ሌላ ፡ እናንተና ፡ አባቶቻ
ችሁ ፡ (አማልክት ፡ ብላችሁ) ፡
የጠራችኋቸውን ፡ ስሞች ፡ እንጅ ፡
አትግገዙም ፤ አላህ ፡ በርሷ ፡
ምንም ፡ አስረጅ ፡ አላወረደም ፤
ፍርዱ ፡ የአላህ ፡ እንጅ ፡ የሌላ ፡
አይደለም ፤ እርሱን ፡ እንጅ ፡
ሌላን ፡ እንዳትግገዙ ፡ አዟል ፤
ይህ ፡ ትክክለኛው ፡ ሃይማኖት ፡
ነው ፤ ግን ፡ አብዛኞቹ ፡ ሰዎች ፡
አያውቁም ።
41 የወህኒ ፡ ቤት ፡ ጓደኞቼ ፡ ሆይ !
አንደኛችሁማ ፡ ጌታውን ፡ (ንጉ
ሡን) ፡ ጠጅ ፡ ያጠጣል ፤ ሌላ
ውማ ፡ ይሰቀላል ፤ ከራሱም ፡
በራሪ ፡ (አሞራ) ፡ ትበላለች ፤ ያ ፡
ፍቹን ፡ የምትጠይቁት ፡ ነገር ፡
ተፈጸመ ፤ (አላቸው) ።
42 ለዚያም ፡ ከሁለቱ ፡ እርሱ ፡ የሚ
ድን ፡ መኾኑን ፡ ለተጠራጠረው ፡
እጌታህ ፡ ዘንድ ፡ አስታውሰኝ ፡
አለው ፤ ጌታውንም ፡ ከማስታ
ወስ ፡ ሰይጣን ፡ አስረሳው ፤ ለጥ
ቂት ፡ ዓመታትም ፡ በወህኒ ፡ ቤቱ፡
ውስጥ ፡ ቆዬ ።
43 ንጉሡም ፡ እኔ ፡ ሰባትን ፡ የሰቡ ፡
ላሞች ፡ ሰባት ፡ ከሲታዎች ፡ ሲበ
ሉዋቸው ፡ ሰባትንም ፡ ለምለም ፡
ዘለላዎች ፡ ሌሎችንም፡ ደረቆችን፡
(ሲጠመጠሙባቸው ፡ በሕልሜ) ፡
አያለሁ ፤ እናንተ ፡ ታላላቅ ፡ ሰ
ዎች ፡ ሆይ ! ሕልምን ፡ የምትፈቱ፡
እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ ሕልሜን ፡ ፍቱ
ልኝ ፡ አላቸው ።

1 ከብር ፡ ከወርቅ ፡ ከዕንጨት ፡ የተሠሩ ።

44 ፡—የሕልሞች ፡ ቅዠቶች፡ ናቸው፤
እኛም ፡ የሕልሞችን ፡ ፍቺ ፡ ዐዋ
ቂዎች ፡ አይደለንም ፡ አሉት ።
45 ያም ፡ ከሁለቱ ፡ የዳነውና ፡ ከብዙ፡
ጊዜ ፡ በኋላ ፡ (ዩሱፍን) ፡ ያስታወ
ሰው ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ፍቹን ፡ እነግራ
ችኋለሁና ፡ ላኩኝ ፡ አለ ፤ (ወደ ፡
ዩሱፍ ፡ ኼደም) ።
46 ፡—አንተ ፡ እውነተኛው ፡ ዩሱፍ፡
ሆይ ! ሰባትን ፡ የሰቡ ፡ ላሞች ፡
ሰባት ፡ ከሲታዎች ፡ ላሞች ፡ ሲበ
ሉዋቸው ፡ ሰባትን ፡ ለምለም ፡ ዘለ
ላዎችም ፡ ሌሎችንም ፡ ደረቆች ፡
(በነሱ ፡ ላይ ፡ ሲጠመጠሙባቸው
ያየን ፡ ሰው ፡ ሕልም ፡ ፍች) ፡ ተች
ልን ፤ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
ሰዎቹ ፡ ልመለስ ፡ እከጅላለሁና ፡
(አለው) ።
47 (እርሱም) ፡ አለ ፡— ሰባትን ፡ የተ
ከታተሉ ፡ ዓመታት ፡ ትዘራላ
ችሁ ፤ ያጨዳችሁትንም ፡ ሁሉ ፡
ከምትበሉት ፡ ጥቂት ፡ በስተቀር ፡
በዘለላው ፡ ውስጥ ፡ ተዉት ።
48 ከዚያም ፡ ከነዚያ ፡ በኋላ ፡ ካደለ
ባችሁት ፡ ጥቂት ፡ ሲቀር ፡ ለነሱ ፡
ያደለባችሁትን ፡ ሁሉ ፡ የሚበሉ ፡
ሰባት ፡ የችግሮች ፡ ዓመታት ፡
ይመጣሉ ።
49 ከዚያም ፡ ከነዚያ ፡ በኋላ ፡ ሰዎቹ ፡
በርሱ ፡ የሚዘነቡበት፥ በርሱም ፡
(ወይንን) ፡ የሚጨምቁበት ፡ ዓ
መት ፡ ይመጣል ።
50 ንጉሡም ፡— እርሱን ፡ አምጡ
ልኝ ፡ አለ ፤ መልክተኛውም ፡
(ዩሱፍን) ፡ በመጣው ፡ ጊዜ ፡ ወደ፡
ጌታህ ፡ ተመለስ ፤ የነዚያንም ፡
እጆቻቸውን ፡ የቆረጡትን ፡ ሴ
ቶች ፡ ኹኔታ ፡ ጠይቀው ፤ ጌታዬ፡
ተንኮላቸውን ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ፡
አለው ።
51 (ንጉሡም) ፡— ዩሱፍን ፡ ከነፍሱ ፡
ባባበላችሁት ፡ ጊዜ ፡ ነገራችሁ ፡
ምንድን ፡ ነው? አላቸው ፤ ለአ
ላህ ፡ ጥራት ፡ ይገባው ፤ በርሱ ፡
ላይ ፡ ምንም ፡ መጥፎን ፡ ነገር ፡
አላወቅንም ፡ አሉት ፤ የዐዚዝ ፡
ሚስት ፡- አሁን ፡ እውነቱ ፡ ተገ
ለጸ ፤ እኔ ፡ ከነፍሱ ፡ አባበልኩት ፤
እርሱም ፡ ከውነተኞቹ ፡ ነው ፡
አለች ።
52 (ዩሱፍ) ፡ ይህ ፡ (1) (ጌታዬ) ፡
ሩቅ ፡ ኾኖ ፡ ሳለ ፡ ያልከዳሁት ፡
መኾኔን ፡ አላህም ፡ የከዳተኞችን ፡
ተንኮል ፡ የማያቃና ፡ መኾኑን ፡
እንዲያውቅ ፡ ነው ፤ (አለ) ።

★ ★ ★

53 ነፍሴንም ፡ (ከስሕተት) ፡ አላጠ
ራም ፤ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ ጌታዬ ፡ የጠ
በቃት ፡ ካልኾነች ፡ በስተቀር ፡
በመጥፎ ፡ ነገር ፡ በእርግጥ ፡
አዛዥ ፡ ናትና ፡ ጌታዬ ፡ በጣም ፡
መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ፡ (አለ) ።
54 ንጉሡም ፡ እርሱን ፡ አምጡልኝ ፤
ለራሴ ፡ ግለኛ ፡ አደርገዋለሁና ፡
አለ ፤ ባናገረውም ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡
ዛሬ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ ባለሟል ፡
ታማኝ ፡ ነህ ፡ አለው ።
55 በምድር ፡ ግምጃ ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡
(ሹም) ፡ አድርገኝ ፤ እኔ ፡ ጠባቂ ፡
ዐዋቂ ፡ ነኝና ፡ አለ ።
56 እንደዚሁም ፡ ለዩሱፍ ፡ በምድር ፡
ላይ ፡ ከርሷ ፡ በፈለገው ፡ ስፍራ ፡
የሚሰፍር ፡ ሲኾን ፡ አስመቸነው ፤
በችሮታችን ፡ የምንሻውን ፡ ሰው ፡

1 ጥራቴን ፡ መፈለጌ ።



እንለያለን ፤ የበጎ ፡ ሠሪዎችንም ፡
ዋጋ ፡ አናጠፋም ።
57 የመጨረሻይቱም ፡ ዓለም ፡ ምንዳ፡
ለነዚያ ፡ ላመኑትና ፡ ይጠነቀቁ ፡
ለነበሩት ፡ የበለጠ ፡ ነው ።
58 የዩሱፍ ፡ ወንድሞችም ፡ መጡ ፤
በርሱም ፡ ላይ ፡ ገቡ ፤ እነሱም ፡
እርሱን ፡ የሳቱት ፡ ሲኾኑ ፡ ዐወቃ
ቸው ።
59 (ጉዳያቸውን ፡ ፈጽሞ) ፡ በንቃቸ
ውንም ፡ ባዘጋጀላቸው ፡ ጊዜ ፡
አለ ፡— ከአባታችሁ ፡ በኩል ፡
የኾነውን ፡ ወንድማችሁን ፡ አም
ጡልኝ ፤ እኔ ፡ ከአስተናጋጆች ፡
ሁሉ ፡ በላጭ ፡ ስኾን ፤ ስፍርን ፡
የምሞላ ፡ መኾኔን ፡ አታዩምን ?
60 እርሱንም ፡ ባታመጡልኝ ፡ እኔ ፡
ዘንድ ፡ ለናንተ ፡ ስፍር ፡ የላች
ሁም ፤ አትቀርቡኝምም ።
61 ፡—ስለርሱ ፡ አባቱን ፡ በጥብቅ ፡
እንጠይቃለን ፤ እኛም ፡ (ይህንን) ፡
በእርግጥ ፡ ሠሪዎች ፡ ነን ፡ አሉት።
62 ለአሽከሮቹም ፡— ሸቀጣቸውን ፡
ወደ ፡ ቤተሰቦቻቸው ፡ በተመለሱ፡
ጊዜ ፡ ያውቋት ፡ ዘንድ ፡ በየጓዞቻ
ቸው ፡ ውስጥ ፡ አድርጉላቸው ፤
ሊመለሱ ፡ ይከጀላልና ፡ አላቸው ።
63 ወደ ፡ አባታቸውም ፡ በተመለሱ ፡
ጊዜ ፡- አባታችን ፡ ሆይ ! (ወንድ
ማችንን ፡ እስከምንወስድ) ፡ ስፍር
ከኛ ፡ ተከልክሏል ፤ ስለዚህ ፡ ወን
ድማችንን ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ላከው ፤
ይሰፈርልናልና ፡ እኛም ፡ ለርሱ ፡
ጠባቂዎች ፡ ነን ፡ አሉ ።
64 ፡—ከአሁን ፡ በፊት ፡ በወንድሙ ፡
ላይ ፡ እንዳመንኳችሁ ፡ እንጅ ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ አምናችኋለሁን ?
አላህም ፡ በጠባቂነት ፡ (ከሁሉ) ፡
የበለጠ ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ ከአዛ
ኞች ፡ ሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ አዛኝ ፡
ነው ፤ አላቸው ።
65 ዕቃቸውንም ፡ በከፈቱ ፡ ጊዜ ፡
ሸቀጣቸውን ፡ ወደነርሱ ፡ ተመ
ልሳ ፡ አገኙ ፡—አባታችን ፡ ሆይ !
ምን ፡ እንፈልጋለን ? ይህቺ ፡ ሸቀ
ጣችን ፡ ናት ፤ ወደኛ ፡ ተመልሳል
ናለች ፤ (እንረዳባታለን) ፡ ለቤተ
ሰቦቻችንም ፡ እንሸምታለን ፤ ወን
ድማችንንም ፡ እንጠብቃለን ፤
የግመልንም ፡ ጭነት ፡ እንጨምራ
ለን ፤ ይህ ፡ (በንጉሡ ፡ ላይ) ፡
ቀላል ፡ ስፍር ፡ ነው ፡ አሉ ።
66 ፡—ካልተከበባችሁ ፡ በስተቀር ፡
እርሱን ፡ በእርግጥ ፡ የምታመጡ
ልኝ ፡ ለመኾናችሁ ፡ ከአላህ ፡ የኾ
ነን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ መተማመኛ ፡
እስከምትሰጡኝ ፡ ድረስ ፡ ከናንተ፡
ጋር ፡ ፈጽሞ ፡ አልልከውም ፡ አላ
ቸው ፤ መተማመኛቸውንም ፡ በሰ
ጡት ፡ ጊዜ ፡ ፡—አላህ ፡ በምን
ለው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ነው ፡
አላቸው ።
67 አለም ፡— ልጆቼ ፡ ሆይ ! ባንድ ፡
በር ፡ አትግቡ ፤ ግን ፡ በተለያዩ ፡
በሮች ፡ ግቡ ፤ ከአላህም ፡ (ፍርድ)፡
በምንም ፡ አልጠቅማችሁም ፤
(አልመልስላችሁም) ፤ ፍርዱ ፡
የአላህ ፡ እንጅ ፡ የሌላ ፡ አይደለም፤
በርሱ ፡ ላይ ፡ ተመካሁ ፤ ተመኪዎ
ችም ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡ ብቻ ፡
ይመኩ ።
68 አባታቸውም ፡ካዘዛቸው ፡ ስፍራ ፡
በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ከአላህ ፡ (ፍርድ) ፡
ምንም ፡ ነገር ፡ ከነርሱ ፡ የሚከለ
ክልላቸው ፡ አልነበረም ፤ ግን ፡
በያዕቆብ ፡ ነፍስ ፡ ውስጥ ፡ የነበ
ረች ፡ ጉዳይ ፡ ናት ፤ ፈጸማት ፤ እ

ርሱም ፡ ስላሳወቅነው ፡ የዕው
ቀት ፡ ባለ ፡ ቤት ፡ ነው ፤ ግን ፡
አብዛኞቹ ፡ ሰዎች ፡ አያውቁም ።

69 በዩሱፍ ፡ ላይ ፡ በገቡ ፡ ጊዜም ፡ ወ
ንድሙን ፡ ወደርሱ ፡ አስጠጋው ፦
እነሆ ፡ እኔ ፡ ወንድምህ ፡ ነኝ ፡
ይሠሩት ፡ በነበሩትም ፡ ሁሉ ፡
አትቆላጭ ፡ አለው ።

70 ዕቃቸውንም ፡ ባዘጋጀላቸው ፡
ጊዜ ፤ ዋንጫይቱን ፡ (1) በወን
ድሙ ፡ ዕቃ ፡ ውስጥ ፡ አደረገ ፤
ከዚያም ፡— እላንተ ፡ ባለ ፡ ግመ
ሎች ፡ ሆይ ! እናንተ ፡ በእርግጥ ፡
ሌቦች ፡ ናችሁ ፡ ሲል ፡ ጠሪ ፡
ተጣራ ።

71 ወደነሱ ፡ ዞረውም ፡— ምንድን ፡
ጠፋችሁ ? አሉ ።

72 ፡—የንጉሡ ፡ መስፈሪያ ፡ ጠፍቶ
ናል ፤ እርሱንም ፡ ላመጣ ፡ ሰው ፡
የግመል ፡ ጭነት ፡ አለው ፤ እኔም ፡
በርሱ ፡ ተያዥ ፡ ነኝ ፡ አለ ።

73 ፡—በአላህ ፡ እንምላለን ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ ለማጥፋት ፡ እንዳልመ
ጣን ፡ በእርግጥ ፡ ዐውቃችኋል ፤
ሌቦችም ፡ አልነበርንም ፡ አሉ ።

74 ፡—ውሸታሞች ፡ ብትኾኑ ፡ ቅጣቱ
ምንድን ፡ ነው ? አሏቸው ።

75 ቅጣቱ ፡ (በያዕቆብ ፡ ሕግ) ፡
ዕቃው ፡ በጓዙ ፡ ውስጥ ፡ የተገኘ
በት ፡ ሰው ፡ (ራሱ ፡ መወሰድ) ፡
ነው ፤ እርሱም ፡ ቅጣቱ ፡ ነው ፤
እንደዚሁ ፡ በደለኞችን ፡ እንቀጣ
ለን ፤ አሉ ።

76 (ምርመራውን) ፡ ከወንድሙም ፡
ዕቃ ፡ በፊት ፡ በዕቃዎቻቸው ፡
ጀመረ ፤ ከዚያም ፡ (ዋንጫይቱን) ፡
ከወንድሙ ፡ ዕቃ ፡ ውስጥ ፡ አወ
ጣት ፤ እንደዚሁ ፡ ለዩሱፍ ፡ ብል
ሃትን ፡ አስተማርነው ፤ አላህ ፡
ባልሻ ፡ ኖሮ ፡ በንጉሡ ፡ ሕግ ፡
ወንድሙን ፡ ሊይዝ ፡ አይገባውም
ነበር ፤ የምንሻውን ፡ ሰው ፡ በደረ
ጃዎች ፡ ከፍ ፡ እናደርጋለን ፡ ከዕ
ውቀት ፡ ባለቤቶች ፡ ሁሉ ፡ በላ
ይም ፡ ዐዋቂ ፡ አልለ ።

77 ፡—ቢሰርቅ ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡
የርሱው ፡ ወንድም ፡ በእርግጥ ፡
ሰርቋል ፡ አሉ ፤ ዩሱፍም ፡ (ይህ
ችን ፡ ንግግር) ፡ በነፍሱ ፡ ውስጥ ፡
ደበቃት ፤ ለነሱም ፡ አልገለጣ
ትም ፤ (በልቡ) ፦ እናንተ ፡ ሥራ
ችሁ ፡ የከፋ ፡ ነው ፤ አላህም ፡ የም
ትሉትን ፡ ሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ፡ አለ ።

78 አንተ ፡ የተከበርከው ፡ ሆይ !
፡—ለርሱ ፡ በእርግጥ ፡ ታላቅ ፡
ሽማግሌ ፡ አባት ፡ አልለው ፤ ስለ
ዚህ ፡ በርሱ ፡ ስፍራ ፡ አንድኛች
ንን ፡ ያዝ ፤ እኛ ፡ ከመልካም ፡
ሠሪዎች ፡ ኾነህ ፡ እናይሃለንና ፡
አሉት ።

79 ፡—ዕቃችንን ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡
ያገኘንበትን ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ ሌላን
ከመያዝ ፡ በአላህ ፡ እንጠበቃለን ፤
እኛ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በእርግጥ ፡ በዳ
ዮች ፡ ነን ፤ አለ ።

80 ከርሱም ፡ ተስፋን ፡ በቆረጡ ፡
ጊዜ ፡ የሚመካከሩ ፡ ኾነው ፡
ገለል ፡ አሉ ፤ ታላቃቸው ፡ አለ ፡—
አባታችሁ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ከአ
ላህ ፡ የኾነን ፡ መታመኛ ፡ ኪዳን ፡
በእርግጥ ፡ የያዘባችሁ ፡ መኾኑን ፡
ከዚህም ፡ በፊት ፡ በዩሱፍ ፡ ላይ ፡
ግፍ ፡ የሠራችሁትን ፡ አታውቁ
ምን ? ስለዚህ ፡ አባቴ ፡ ለኔ ፡ እስከ
ሚፈቅድልኝ ፡ ወይም ፡ አላህ ፡

1 መጠጫና ፡ መስፈሪያውን ።



ለኔ ፡ እስከሚፈርድልኝ ፡ ድረስ ፡
የምስርን ፡ ምድር ፡ አልለይም ፤
እርሱም ፡ ከፈራጆች ፡ ሁሉ ፡
በላጭ ፡ ነው ።

81 ወደ ፡ አባታችሁ ፡ ተመለሱ ፤ በሉ
ትም ፡— አባታችን ፡ ሆይ ! ልጅህ
ሰረቀ ፡ ባወቅነውም ፡ ነገር ፡
እንጂ ፡ አልመሰከርንም ፤ ሩቁ
ንም ፡ ነገር ፡ (ምስጢሩን) ፡ ዐዋቂ
ዎች ፡ አልነበርንም ፤

82 ያችንም ፡ በውስጧ ፡ የነበርንባ
ትን ፡ ከተማ ፡ ያችንም ፡ በውስጧ ፡
የመጣነውን ፡ ባለ ፡ ግመል ፡ ጓድ ፡
ጠይቅ ፤ እኛም ፡ በእርግጥ ፡ እውነ
ተኞች ፡ ነን ።

83 (ያዕቆብ) ፡— አይደለም ፡ ነፍሶቻ
ችሁ ፡ አንዳች ፡ ነገርን ፡ ለናንተ ፡
ሸለሙላችሁ ፤ (ሠራችሁትም) ፤
መልካምም ፡ ትእግሥት ፡ (ማድ
ረግ) ፡ አለብኝ ፤ እነርሱን ፡ (ሦስቱ
ንም) ፡ የተሰበሰቡ ፡ ኾነው ፡
አላህ ፡ ሊያመጣልኝ ፡ ይከጀላል ፤
እነሆ ፡ እርሱ ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡
ነውና ፡ አላቸው ።

84 ከነሱም ፡ ዘወር ፡ አለና ፡— በዩ
ሱፍ ፡ ላይ ፡ ዋ ፡ ሐዘኔ ! አለ ፤ ዓይ
ኖቹም ፡ ከሐዘን ፡ (ለቅሶ)፡ የተ
ነሳ ፡ ነጡ ፤ እርሱም ፡ በትካዜ ፡
የተመላ ፡ ነው ።

85 (እነርሱም) ፦ በአላህ ፡ እንምላ
ለን ፤ ለጥፋት ፡ የቀረብክ ፡ እስክ
ምትኾን ፡ ወይም ፡ ከጠፊዎቹ ፡
እስከምትኾን ፡ ድረስ ፡ ዩሱፍን ፡
ከማውሳት ፡ አትወገድም ፤ አሉ ።

86 ፡—ጭንቀቴንና ፡ ሐዘኔን ፡ የማሰ
ሙተው ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡
ነው ፤ ከአላህም ፡ በኩል ፡ የማታ
ውቁትን ፡ ነገር ፡ ዐውቃለሁ ፡
አላቸው ።

87 ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ ኺዱ ፤ ከዩሱፍና ፡
ከወንድሙም ፡ (ወሬ) ፡ ተመራ
መሩ ፤ ከአላህም ፡ እዝነት ፡ ተስፋ ፡
አትቍረጡ ፤ እነሆ ፡ ከአላህ ፡ እዝ
ነት ፡ ከሐዲዎች ፡ ሕዝቦች ፡
እንጂ ፡ ተስፋ ፡ አይቆርጥም ፡
(አለ) ።

88 በርሱም ፡ ላይ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡
አንተ ፡ የተከበርከው ፡ ሆይ ! እኛ
ንም ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻችንንም ፡
ጉዳት ፡ ደረሰብን ፤ ርካሽ ፡ ሸቀ
ጥም ፡ ይዘን ፡ መጥተናል ፤ ስፍር
ንም ፡ ለኛ ፡ ሙላልን ፤ በኛም ፡
ላይ ፡ መጽውት ፤ አላህ ፡ መጽዋቾ
ችን ፡ ይመነዳልና ፡ አሉት ።

89 ፡—እናንተ ፡ የማታውቁ ፡ በነበራ
ችሁ ፡ ጊዜ ፡ በዩሱፍና ፡ በወን
ድሙ ፡ ላይ ፡ የሠራችሁትን ፡ ግፍ ፡
ዐወቃችሁን ? አላቸው ።

90 ፡—አንተ ፡ በእርግጥ ፡ አንተ ፡
ዩሱፍ ፡ ነህን? አሉት ፤ እኔ ፡ ዩሱፍ
ነኝ ፤ ይህም ፡ ወንድሜ ፡ ነው ፡
አላህ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ ለገ
ሰልን ፤ እነሆ ! የሚጠነቀቅና ፡
የሚታገሥ ፡ ሰው ፡ (አላህ ፡ ይክሰ
ዋል) ፤ አላህ ፡ የበጎ ፡ አድራጊዎ
ችን ፡ ዋጋ ፡ አያጠፋምና ፡ አለ ።

91 ፡—በአላህ ፡ እንምላለን ፤ አላህ ፡
በኛ ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ አበለጠህ ፤
እኛም ፡ በእርግጥ ፡ አጥፊዎች ፡
ነበርን ፡ አሉ ።

92 ፡—ዛሬ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ወቀሳ ፡
የለባችሁም ፤ አላህ ፡ ለናንተ ፡
ይምራል ፤ እርሱም ፡ ከአዛኞች ፡
ሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ አዛኝ ፡ ነው ፡
አላቸው ።

93 ይህንን ፡ ቀሚሴን ፡ ይዛችሁ ፡
ኺዱ ፤ በአባቴ ፡ ፊትም ፡ ጣሉት ፡
የሚያይ ፡ ኾኖ ፡ ይመጣልና ፤ ቤተ

ሰቦቻችሁንም ፡ ሰብስባችሁ ፡ አም
ጡልኝ ፡ (አላቸው) ።

94 ግመል ፡ ጫኞቹም ፡ (ምስርን) ፡
በተለዩ ፡ ጊዜ ፡ አባታቸው ፡
፡—እኔ ፡ የዩሱፍን ፡ ሽታ ፡ በእር
ግጥ ፡ አገኛለሁ ፤ ባታቄሉኝ ፡
ኖሮ ፡ (ታምኑኝ ፡ ነበር) ፡ አለ ።

95 ፡—በአላህ ፡ እንምላለን ፤ አንተ ፡
በእርግጥ ፡ በቀድሞው ፡ ስሕተ
ትህ ፡ ውስጥ ፡ ነህ ፤ አሉት ።

96 አብሳሪውም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡
(ቀሚሱን) ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ጣለው፤
ወዲያውም ፡ የሚያይ ፡ ኾነ ፤ እኔ ፡
ለናንተ ፡— ከአላህ ፡ በኩል ፡ የማ
ታውቁትን ፡ ዐውቃለሁ ፡ አላልኋ
ችሁምን ? አላቸው ።

97 ፡—አባታችን ፡ ሆይ ፡ ለኀጢአቶ
ቻችን ፡ ምሕረትን ፡ ለምንልን ፤
እኛ ፡ ጥፋተኞች ፡ ነበርንና ፡ አሉ።

98 ፡—ወደፊት ፡ ለናንተ ፡ ጌታዬን ፡
ምሕረትን ፡ እለምንላችኋለሁ ፡
እነሆ ! እርሱ ፡ መሓሪው ፡ አዛኙ ፡
ነውና ፡ አላቸው ።

99 በዩሱፍ ፡ ላይም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡
ወላጆቹን ፡ ወደርሱ ፡ አስጠጋ
ቸው ፤ በአላህም ፡ ፈቃድ ፡ ጥብ
ቆች ፡ ስትኾኑ ፡ ምስርን ፡ ግቡ ፡
አላቸው ።

100 ወላጆቹንም ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ አወ
ጣቸው ፤ ለርሱም ፡ ሰጋጆች ፡
ኾነው ፡ ወረዱለት ፤ አባቴም ፡
ሆይ ፡ ይህ ፡ ፊት ፡ ያየኋት ፡
ሕልሜ ፡ ፍች ፡ ነው ፤ ጌታዬ ፡ በእ
ርግጥ ፡ እውነት ፡ አደረጋት ፤ ከወ
ህኒ ፡ ቤትም ፡ ባወጣኝና ፡ ሰይጣ
ንም ፡ በኔና ፡ በወንድሞቼ ፡ መካ
ከል ፡ ከአበላሸ ፡ በኋላ ፡ እናንተን ፡
ከገጠር ፡ ባመጣችሁ ፡ ጊዜ ፡ በእር
ግጥ ፡ ለኔ ፡ መልካም ፡ ዋለልኝ ፤
ጌታዬ ፡ ለሚሻው ፡ ነገር ፡ እዝነቱ፡
ረቂቅ ፡ ነው ፤ እነሆ ፡ እርሱ ፡ ዐዋ
ቂው ፡ ጥበበኛው ፡ ነው ፤ አለ ።

101 ጌታዬ ፡ ሆይ ! ከንግሥና ፡ በእር
ግጥ ፡ ሰጠኸኝ ፤ ከሕልሞችም ፡
ፍች ፡ አስተማርከኝ ፤ የሰማያትና ፡
የምድር ፡ ፈጣሪ ፡ ሆይ ! አንተ ፡
በቅርቢቱና ፡ በመጨረሻይቱ ፡
ዓለም ፡ ረዳቴ ፡ ነህ፤ ሙስሊም፡
ሆኜ ፡ ግደለኝ ፤ በመልካሞቹም ፡
አስጠጋኝ ፤ (አለ) ።

102 (ሙሐመድ ፡ ሆይ) ፡ ይህ ፡ ወዳ
ንተ ፡ የምናወርደው ፡ ሲኾን ፤
ከሩቅ ፡ ወሬዎች ፡ ነው ፤ አንተም ፡
እነርሱ ፡ (በዩሱፍ) ፡ የሚመከሩ ፡
ኾነው ፡ ነገራቸውን ፡ በቆረጡ ፡
ጊዜ ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ አልነበር
ክም ።

103 አብዛኛዎቹም ፡ ሰዎች ፡ (ለማመና
ቸው) ፡ ብትጓጓም ፡ የሚያምኑ ፡
አይደሉም ።

104 በርሱም ፡ (በቁርአን) ፡ ላይ ፡
ምንም ፡ ዋጋ ፡ አትጠይቃቸውም ፤
እርሱ ፡ ለዓለማት ፡ ግሣጼ ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ።

105 በሰማያትና ፡ በምድርም ፡ ካለ
ችው ፡ ምልክት ፡ ብዙይቱ ፡
እነሱ ፡ ከርሷ ፡ ዘንጊዎች ፡ ኾነው፡
በርሷ ፡ ላይ ፡ ያልፉሉ ።

106 አብዛኞቻቸውም ፤ እነሱ ፡ አጋሪ
ዎች ፡ ኾነው ፡ እንጂ ፡ በአላህ ፡
አያምኑም ።

107 ከአላህ ፡ ቅጣት ፡ ሽፋኝ ፡ አደጋ ፡
የምትመጣባቸው ፡ ወይም ፡ ሰዓ
ቲቱ ፡ እነሱ ፡ የማያውቁ ፡ ሲኾኑ ፡
በድንገት ፡ የምትመጣባቸው ፡
መኾኑዋን ፡ አይፈሩምን ?



108 ፡—ይህች ፡ መንገዴ ፡ ናት ፤ ወደ ፡
አላህ ፡ እጠራለሁ ፤ እኔም ፡ የተከ
ተለኝም ፡ ሰው ፡ በግልጽ ፡ ማስ
ረጃ ፡ ላይ ፡ ነን ፤ ጥራትም ፡ ለአ
ላህ ፡ ይገባው ፤ እኔም ፡ ከአጋሪ
ዎቹ ፡ አይደለሁም ፡ በል ።

109 ካንተ ፡ በፊትም ፡ ከከተሞች ፡
ሰዎች ፡ ወደነርሱ ፡ ራእይ ፡ የምና
ወርድላቸው ፡ የኾኑን ፡ ወንዶችን፡
እንጂ ፡ አልላክንም ፤ በምድር ፡
ላይ ፡ አይኼዱምና ፡ የነዚያን ፡
ከነሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡
ሰዎች ፡ መጨረሻ ፡ አይመለከ
ቱምን ? የመጨረሻይቱም ፡ አገር፡
ለነዚያ ፡ ለተጠነቀቁት ፡ በእር
ግጥ ፡ የተሻለች ፡ ናት ፤ አታውቁ
ምን ?

110 መልክተኞቹም ፡ ተስፋ ፡ በቆረ
ጡና ፡ እነርሱ ፡ በእርግጥ ፡ የተ
ዋሹ ፡ መኾናቸውን ፡ በተጠራ
ጠሩ ፡ ጊዜ ፡ እርዳታችን ፡ መጣላ
ቸው ፤ (እኛ) ፡ የምንሻውም ፡ ሰው
እንዲድን ፡ ተደረገ ፤ ቅጣታች
ንም ፡ ከአጋሪዎቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ላይ
አይመለስም ።

111 በታሪካቸው ፡ ውስጥ ፡ ለአእምሮ ፡
ባለ ፡ ቤቶች ፡ በእርግጥ ፡ መገ
ሠጫ ፡ ነበረ ፤ (ይህ ፡ ቁርአን) ፡
የሚቀጣጠፍ ፡ ወሬ ፡ አይደለም ፤
ግን ፡ ያንን ፡ በስተፊቱ ፡ ያለውን ፡
አረጋጋጭ ፡ ለነገርም ፡ ሁሉ ፡
ገላጭ ፡ ለሚያምኑ ፡ ሕዝቦችም ፡
መሪና ፡ ችሮታ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 13 ፡ አል-ረዕድ ። ክፍል ፡ 13 ።

13ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ረዕድ ፡ (የነጎድጓድ ፡ ምዕራፍ) ፡ በመ
ዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 43 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፤ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው።

1 አ.ለ.መ.ረ. (አሊፍ ፡ ላም ፡ ሚም ፡
ራ) ፡ (1) ይህች ፡ (አናቅጽ) ፡ ከመ
ጽሐፉ ፡ አንቀጾች ፡ ናት ፤ ያም ፡
ከጌታህ ፡ ወዳንተ ፡ የተወረደው ፡
እውነት ፡ ነው ፤ ግን ፡ አብዛኛ
ዎቹ ፡ ሰዎች ፡ አያምኑም ።

2 አላህ ፡ ያ ፡ ሰማያትን ፡ የምታዩ
ዋት ፡ አዕማድ ፡ ሳትኖር ፡ ያነ
ሳት ፡ ከዚያም ፡ በዐርሹ ፡ (ዙፋኑ)፡
ላይ ፡ (ስልጣኑ) ፡ የተደላደለ ፡ ፀሐ
ይንና ፡ ጨረቃንም ፡ የገራ ፡ ነው ፤
ሁሉም ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ይሮ
ጣሉ ፤ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ያስተናብ
ራል ፤ በጌታችሁ ፡ መገናኘት ፡
ታረጋግጡ ፡ ዘንድ ፡ ታምራቶ
ችን ፡ ይዘረዝራል ።

3 እርሱም ፡ ያ ፡ ምድርን ፡ የዘረጋ ፡
በሷም ፡ ተራራዎችንና ፡ ወንዞ
ችን ፡ ያደረገ ፡ በውስጧም ፡ ከፍሬ
ዎች ፡ ሁሉ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡
ዓይነቶችን ፡ ያደረገ ፡ ነው ፤ ሌሊ
ትን ፡ በቀን ፡ ይሸፍናል ፤ በዚ

1 እኔ ፡ አላህ ፡ነኝ ፡ ዐውቃለሁ ፡ እያለሁም ።

ህም ፡ ውስጥ ፡ ለሚያስተንትኑ ፡
ሕዝቦች ፡ ምልክቶች ፡ አልሉ ።

4 በምድርም ፡ የተጐራበቱ ፡ ቁርጥ
ራጮች ፡ አልሉ ፤ ከወይኖችም ፡
አትክልቶች ፡ አዝርዕቶችም ፡ መን
ታዎችና ፡ መንታዎች ፡ ያልኾኑ ፡
ዘንባባዎችም ፡ አልሉ ፡ በአንድ ፡
ውሃ ፡ ይጠጣሉ ፤ (በጣዕምም ፡
ይለያያሉ) ፤ ከፊሉዋንም ፡ በከ
ፊሉ ፡ ላይ ፡ በሚበላው ፡ ሰብል ፡
እናበልጣለን ፤ በዚህም ፡ ውስጥ ፡
ለሚያውቁ ፡ ሕዝቦች ፡ ታምራት ፡
አለበት ።

5 ብትደነቅም ፡ ዐፈር ፡ በኾንን ፡ ጊዜ ፡
እኛ ፡ አዲስ ፡ ፍጥረት ፡ እንኾና
ለን ? ማለታቸው ፡ (ታላቅ) ፡ ድን
ቅ ፡ ነው ፤ እነዚህ ፡ እነዚያ ፡ በጌታ
ቸው ፡ የካዱት ፡ ናቸው ፡ እነዚ
ህም ፡ እንዛዝላዎች ፡ በአንገቶቻ
ቸው ፡ ላይ ፡ ያሉባቸው ፡ ናቸው ፤
እነዚህም ፡ የእሳት ፡ ጓዶች ፡
ናቸው ፤ እነሱ ፡ በውስጧ ፡ ዘው
ታሪዎች ፡ ናቸው ።

6 ከነሱ ፡ በፊት ፡ የመሰሎቻቸው ፡
ቅጣቶች ፡ በእርግጥ ፡ ያለፉ ፡
ሲኾኑ ፡ ከመልካሙ ፡ በፊት ፡
በመጥፎው ፡ ያስቸኩሉሃል ፤ ጌታ
ህም ፡ ለሰዎች ፡ ከመበደላቸው ፡
ጋር ፡ በእርግጥ ፡ የምሕረት ፡ ባለ
ቤት ፡ ነው ፤ ጌታህም ፡ በእርግጥ ፡
ቅጣተ ፡ ብርቱ ፡ ነው ።

7 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
ከጌታው ፡ ታምር ፡ ለምን ፡ አልተ
ወረደለትም ፡ ይላሉ ፤ አንተ ፡
አስፈራሪ ፡ ብቻ ፡ ነህ ፡ ለሕዝብም
ሁሉ ፡ መሪ ፡ አላቸው ።

8 አላህ ፡ ሴት ፡ ሁሉ ፡ የምታረግዘ
ውን ፡ ያውቃል ፤ ማሕፀኖችም ፡
የሚያጐድሉትን ፡ የሚጨምሩት
ንም ፡ (ያውቃል) ፤ ነገሩም ፡ ሁሉ ፡
እርሱ ፡ ዘንድ ፡ በልክ ፡ የተወሰነ ፡
ነው ።

9 ሩቁንና ፡ ቅርቡን ፡ ዐዋቂ ፡ ታላቅ ፡
የላቀ ፡ ነው ።

10 ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ ቃሉን ፡ ዝቅ ፡
ያደረገ ፡ ሰው ፡ በርሱ ፡ የጮኸም ፡
ሰው ፡ እርሱ ፡ በሌሊት ፡ ተደባ
ቂም ፡ በቀን ፡ (ተገልጾ) ፡ ኺያጅም ፡
የኾነ ፡ ሰው ፡ (እርሱ ፡ ዘንድ) ፡
እኩል ፡ ነው ።

11 ለርሱ ፡ (ለሰው) ፡ ከስተፊቱም ፡
ከኋላውም ፡ በአላህ ፡ ትእዛዝ ፡
(ከክፉ) ፡ የሚጠብቁት ፡ ተተካኪ
ዎች ፡ (መላእክት) ፡ አልሉት ፡
አላህ ፡ በሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ ያለ
ውን ፡ ጸጋ ፡ በነፍሶቻቸው ፡ ያለ
ውን ፡ (ኹኔታ) ፡ እስከሚለውጡ ፡
ድረስ ፡ አይለውጥም ፤ አላህም ፡
በሰዎች ፡ ላይ ፡ ክፉን ፡ በሻ ፡ ጊዜ ፡
ለርሱ ፡ መመለስ ፡ የለውም ፤ ለነ
ርሱም ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡
ተከላካይ ፡ የላቸውም ።

12 እርሱ ፡ ያ ፡ የምትፈሩና ፡ የምትከ
ጅሉም ፡ ስትኾኑ ፡ ብልጭታን ፡
የሚያሳያችሁ ፡ ከባዶች ፡ ደመና
ዎችንም ፡ የሚያስገኝ ፡ ነው ።

13 ነጐድጓድም ፡ አላህን ፡ በማመስ
ገን ፡ ያጠራል ፡ መላእክትም ፡
እርሱን ፡ ለመፍራት ፡ (ያጠሩ
ታል) ፤ መብረቆችንም ፡ ይልካል ፡
እነርሱም ፡ (ከሓዲዎች)፡ በአ
ላህ ፡ የሚከራከሩ ፡ ሲኾኑ ፡ በርሷ ፡
የሚሻውን ፡ ሰው ፡ ይመታል ፡ እር
ሱም ፡ ኀይለ ፡ ብርቱ ፡ ነው ።

14 ለርሱ ፡ (ለአላህ) ፡ የውነት ፡ መጥ
ሪያ ፡ አልለው ፡ እነዚያም ፡ ከርሱ ፡
ሌላ ፡ የሚግገዙዋቸው ፡ (ጣዖታ
ት) ፡ ወደ ፡ አፉ ፡ ይደርስ ፡ ዘንድ ፡
ወደ ፡ ውሃ ፡ መዳፎቹን ፡ (በሩቅ ፡
ኾኖ) ፡ እንደሚዘረጋ ፡ (ሰው ፡
መልስ) ፡ እንጂ ፡ ለነርሱ ፡ በም
ንም ፡ አይመልሱላቸውም ፤ (1)
እርሱም ፡ ወደ ፡ አፉ ፡ ደራሽ ፡
አይደለም ፤ የከሓዲዎችም ፡ ጥሪ ፡
በከንቱ ፡ እንጂ ፡ አይደለም ።



15 በሰማያትና ፡ በምድርም ፡ ያሉት ፡
ሁሉ ፡ በውድም ፡ ኾነ ፡ በግድ ፡
ለአላህ ፡ ይሰግዳሉ ፤ ጥላዎቻቸ
ውም ፡ በጧቶችና ፡ በሠርኮች ፡ (2)
(ይሰግዳሉ) ።

16 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ጌታ ፡ ማን
ነው ? በላቸው ፤ አላህ ፡ ነው ፡
በል ፤ ለነፍሶቻቸው ፡ ጥቅምንም ፡
ጉዳትንም ፡ የማይችሉን ፡ ረዳ
ቶች ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ ያዛችሁን ?
በላቸው ፤ ዕውርና ፡ የሚያይ ፡ ይተ
ካከላሉን ? ወይስ ፡ ጨለማዎችና ፡
ብርሃን ፡ ይተካከላሉን ? ወይስ ፡
ለአላህ ፡ እንደርሱ ፡ አፈጣጠር ፡
የፈጠሩን ፡ ተጋሪዎች ፡ አደረጉለ
ትና ፡ ፍጥረቱ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ተመ
ሳሰለባቸውን ? በል ፤ አላህ ፡ ሁለመ
ናውን ፡ ፈጣሪ ፡ ነው ፤ እርሱም ፡
አንዱ ፡ አሸናፊው ፡ ነው ፡ በል ።

17 ከሰማይ ፡ ውሃን ፡ አወረደ ፤ ሸለቆ
ዎቹም ፡ በመጠናቸው ፡ ፈሰሱ ፤
ጎርፉም ፡ አሰፋፊውን ፡ ኮረፋት ፡
ተሸከመ ፤ ለጌጥ ፡ ወይም ፡ ለዕቃ ፡
ፍላጐት ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ እሳት ፡
የሚያነዱበትም ፡ (ማዕድን) ፡
ብጤው ፡ የኾነ ፡ ኮረፋት ፡ አል
ለው ፤ እንደዚሁ ፡ አላህ ፡ ለውነ
ትና ፡ ለውሸት ፡ ምሳሌን ፡ ያደር
ጋል ፤ ኮረፋቱማ ፡ ግብስብስ ፡
ኾኖ ፡ ይጠፋል ፤ ለሰዎች ፡ የሚጠ
ቅመውማ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይቆ
ያል ፤ እንደዚሁ ፡ አላህ ፡ ምሳሌ
ዎችን ፡ ይገልጻል ።

18 ለነዚያ ፡ ለጌታቸው ፡ ለታዘዙት ፡
መልካም ፡ ነገር ፡ (ገነት) ፡ አላ
ቸው ፤ እነዚያም ፡ ለርሱ ፡ ያልታ
ዘዙት ፡ ለነሱ ፡ በምድር ፡ ያለው ፡
ሁሉ ፡ ከርሱም ፡ ጋር ፡ ብጤው ፡
ቢኖራቸው ፡ ኖሮ ፡ በርሱ ፡ በተበ
ዡበት ፡ ነበር ፤ እነዚያ ፡ ለነሱ ፡
ክፉ ፡ ምርመራ ፡ አለባቸው ፤ መኖ
ሪያቸውም ፡ ገሀነም ፡ ናት ፤ ፍራሻ
ቸውም ፡ ከፉች !

19 ከጌታህ ፡ ወዳንተ ፡ የተወረደው ፡
እውነት ፡ መኾኑን ፡ የሚያውቅ ፡
ሰው ፡ እንደዚያ ፡ እርሱ ፡ ዕውር ፡
እንደ ፡ ኾነው ፡ ሰው ፡ ነውን ?
የሚገሠጹት ፡ የአእምሮ ፡ ባለ ፡
ቤቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

20 እነዚያ ፡ በአላህ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
የሚሞሉ ፡ የጠበቀውንም ፡ ኪዳን ፡
የማያፈርሱ ፡ ናቸው ።

21 እነዚያም ፡ አላህ ፡ እንዲቀጠል ፡
በርሱ ፡ ያዘዘውን ፡ ነገር ፡ የሚቀ
ጥሉ ፡ ጌታቸውንም ፡ የሚያከ
ብሩ ፡ መጥፎንም ፡ ቁጥጥር ፡ የሚ
ፈሩ ፡ ናቸው ።

22 እነዚያም ፡ የጌታቸውን ፡ ውዴታ ፡
ለመፈለግ ፡ የታገሡ ፡ ሶላትንም ፡
አዘውትረው ፡ የሰገዱ ፡ እኛ ፡ ከሰ
ጠናቸው ፡ ሲሳይም ፡ በምስጢ
ርም ፡ ኾነ ፡ በግልጽ ፡ የመጸወቱ ፡
ክፉውንም ፡ ነገር ፡ በበጎ ፡ የሚገ
ፈትሩ ፡ ናቸው ፤ እነዚያ ፡ ለነሱ ፡
መጨረሻይቱ ፡ ምስጉን ፡ አገር ፡
አለቻቸው ።

---

1 ውሃው ፡ በእጁ ፡ ቢጠቅሰው ፡ ወደ ፡ አፉ ፡ እንደማይመጣ ፡ ጣዖታቶቹም ፡ ጸሎታቸውን ፡ አይሰሙቸውም ።

2 ሠርክ ፡ ከዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

23 (እርሷም) ፡ የመኖሪያ ፡ ገነቶች ፡
ናት ፤ ይገቡባታል ፤ ከአባቶቻቸ
ውም ፡ ከሚስቶቻቸውም ፡ ከዝር
ያቸውም ፡ መልካም ፡ የሠራ ፡
ሰው ፡ (ይገባታል) ፤ መላእክትም ፡
በነሱ ፡ ላይ ፡ ከየደጃፉ ፡ ሁሉ ፡
ይገባሉ ።
24 ሰላም ፡ ለናንተ ፡ ይኹን ፡ (ይህ ፡
ምንዳ) ፡ በመታገሣችሁ ፡ ነው ፡
የመጨረሻይቱም ፡ አገር ፡ ምን ፡
ታምር ! (ይሏቸዋል) ።
25 እነዚያም ፡ የአላህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
ከጠበቀ ፡ በኋላ ፡ የሚያፈርሱ ፡
አላህም ፡ እንዲቀጠል ፡ በርሱ ፡
ያዘዘውን ፡ ነገር ፡ የሚቆርጡ ፡
በምድርም ፡ ላይ ፡ የሚያበላሹ ፡
እነዚያ ፡ ለነሱ ፡ ርግማን ፡ አለባ
ቸው ፤ ለነሱም ፡ መጥፎ ፡ አገር ፡
(ገሀነም) ፡ አላቸው ።
26 አላህ ፡ ለሚሻው ፡ ሰው ፡ ሲሳይን ፡
ያሰፋል ፤ ያጠባልም ፤ (ከሓዲ
ዎች) ፡ በቅርቢቱም ፡ ሕይወት ፡
ተደሰቱ ፤ የቅርቢቱም ፡ ሕይወት ፡
በመጨረሻይቱ ፡ አንጻር ፡ (ትን
ሽ ፡ መጠቀሚያ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡
አይደለችም ።
27 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
ከጌታው ፡ ታምር ፡ ለምን ፡ አል
ተወረደም ፡ ይላሉ ፤ አላህ ፡ የሚ
ሻውን ፡ ያጠማል ፤ የተመለሰው
ንም ፡ ሰው ፡ ወደርሱ ፡ ይመራል ፡
በላቸው ።
28 (እነሱም) ፡ እነዚያ ፡ ያመኑ ፡ ልቦ
ቻቸውም ፡ አላህን ፡ በማውሳት ፡
የሚረኩ ፡ ናቸው ፤ ንቁ ፡ አላህን ፡
በማውሳት ፡ ልቦች ፡ ይረካሉ ።
29 እነዚያ ፡ ያመኑትና ፡ መልካም ፡
ሥራዎችን ፡ የሠሩት ፡ ለነሱ ፡
ደግ ፡ ኑሮ ፡ መልካም ፡ መመለ
ሻም ፡ አላቸው ።
30 እንደዚሁ ፡ ከበፊትዋ ፡ ብዙ ፡ ሕዝ
ቦች ፡ በእርግጥ ፡ ያለፉ ፡ ወደ ፡
ኾነችው ፡ ሕዝብ ፡ እነርሱ ፡ በአል
ረሕማን ፡ (1) የሚክዱ ፡ ሲኾኑ ፡
ያንን ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ያወረድነ
ውን ፡ ቁርአን ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡
ታነብላቸው ፡ ዘንድ ፡ ላክንህ ፤
እርሱ ፡ (አልረሕማን) ፡ ጌታዬ ፡
ነው ፤ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡
የለም ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተጠጋሁ ፤
መመለሻየም ፡ ወደርሱ ፡ ብቻ ፡
ነው ፡ በላቸው ።
31 ቁርአንም ፡ በርሱ ፡ ተራራዎች ፡
በተነዱበት ፡ ወይም ፡ በርሱ ፡
ምድር ፡ በተቆራረጠችበት ፡ ወ
ይም ፡ በርሱ ፡ ሙታን ፡ እንዲና
ገሩ ፡ በተደረጉበት ፡ ኖሮ ፡ (የመካ ፡
ከሓዲዎች ፡ ባላመኑ ፡ ነበር) ፤
በውነቱ ፡ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ የአላህ ፡
ነው ፤ እነዚያ ፡ ያመኑት ፡ ሰዎች ፡
እነሆ ፡ አላህ ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ ሰዎ
ችን ፡ በመላ ፡ በእርግጥ ፡ ይመራ
ቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አያውቁ
ምን ? እነዚያም ፡ የካዱት ፡ በሥራ
ቸው ፡ ምክንያት ፡ (አጥፊ) ፡
ዐደጋ ፡ የምታገኛቸው ፡ ከመኾን ፡
ወይም ፡ የአላህ ፡ቀጠሮ ፡ እስኪ
መጣ ፡ በአገራቸው ፡ አቅራቢያ ፡
(አንተ) ፡ የምትሰፍርባቸው ፡ ከመ
ኾን ፡ አይወገዱም ፤ አላህ ፡ ቀጠ
ሮውን ፡ አያፈርስምና ።
32 ከአንተ ፡ በፊት ፡ በነበሩትም ፡
መልክተኞች ፡ በእርግጥ ፡ ተላግጠ
ባቸዋል ፤ ለነዚያም ፡ ለካዱት ፡
ጊዜን ፡ ሰጠኋቸው ፤ ከዚያም ፡

---

1 አልረሕማን ፡ የአላህ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ ነው ።



(በቅጣት) ፡ ያዝኩዋቸው ፤ ቅጣ
ቴም ፡ እንዴት ፡ ነበር !
33 እርሱ ፡ በነፍስ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በሠ
ራችው ፡ ሥራ ፡ ተጠባባቂ ፡ የኾ
ነው ፡ (አላህ ፡ እንደዚህ ፡ እንዳል
ኾነው ፡ ጣዖት ፡ ብጤ ፡ ነውን ?)
ለአላህም ፡ ተጋሪዎችን ፡ አደረጉ ፤
ጥሯቸው ፡ (1) አላህን ፡ በምድር ፡
ውስጥ ፡ የማያውቀው ፡ኖሮ ፡ ትነ
ግሩታላችሁን ? ወይስ ፡ ከቃል ፡
በግልጽ ፡ (ፍቺ ፡ በሌለው ፡ ከንቱ ፡
ቃል ፡ ተጋሪዎች ፡ በማለት ፡ ትጠ
ሩዋቸዋላችሁን ?) በላቸው ፤ በው
ነቱ ፡ ለነዚያ ፡ ለካዱት ፡ ተንኮላ
ቸው ፡ ተሸለመላቸው ፤ ከውነቱ ፡
መንገድም ፡ ታገዱ ፤ አላህም ፡
ያጠመመው ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡
ምንም ፡ አቅኚ ፡ የለውም ።
34 ለነሱ ፡ በቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡
ቅጣት ፡ አላቸው ፤ የመጨረሻይ
ቱም ፡ (ዓለም) ፡ ቅጣት ፡ በጣም ፡
የበረታ ፡ ነው ፤ ለነሱም ፡ ከአላህ ፡
(ቅጣት) ፡ ምንም ፡ ጠባቂ ፡ የላቸ
ውም ።
35 ያች ፡ ጥንቁቆቹ ፡ ተስፋ ፡ የተሰ
ጧ ፡ ገነት ፡ ምጣኔዋ ፡ (እንደሚ
ነገራችሁ ፡ ነው) ፤ ከሥርዋ ፡ወን
ዞች ፡ ይፈሳሉ ፤ ምግቧ ፡ (ሁል
ጊዜ) ፡ የማይቋረጥ ፤ ነው ፤ ጥላ
ዋም ፡ (እንደዚሁ) ፡ ይህች ፡ የነ
ዚያ ፡ የተጠነቀቁት ፡ መጨረሻ ፡
ናት ፤ የከሓዲዎችም ፡ መጨረሻ ፡
እሳት ፡ ናት ።
36 እነዚያም ፡ መጽሐፉን ፡ የሰጠና
ቸው ፡ ወዳንተ ፡ በተወረደው ፡
ይደሰታሉ ፤ ከአሕዛብም ፡ ከፊ
ሉን ፡ የሚክዱ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፤
እኔ ፡ የታዘዝኩት ፡ አላህን ፡ ብቻ ፡
እንድግገዛ ፡ በርሱም ፡ እንዳላጋራ ፡
ነው ፤ ወደርሱ ፡ እጠራለሁ ፤ መመ
ለሻየም ፡ ወደርሱ ፡ ነው ፡ በላ
ቸው ።
37 እንደዚሁ ፡ በዐረብኛ ፡ የተነገረ ፡
ፍትሕ ፡ ሲኾን ፡ አወረድነው ፤
ዕውቀቱ ፡ ከመጣልህም ፡ በኋላ ፡
ዝንባሌዎቻቸውን ፡ ብትከተል ፡
ከአላህ ፡ ቅጣት ፡ ምንም ፡ ረዳ
ትም ፡ ጠባቂም ፡ የለህም ።
38 ከአንተ ፡ በፊትም ፡ መልክተኞ
ችን ፡ በእርግጥ ፡ ልከናል ፤ ለነ
ሱም ፡ ሚስቶችንና ፡ ልጆችን ፡
አድርገናል ፤ ለማንኛውም ፡ መል
ክተኛ ፡ በአላህ ፡ ፈቃድ ፡ እንጂ ፡
ታምር ፡ ሊያመጣ ፡ አይገባውም ፤
ለጊዜው ፡ ሁሉ ፡ ጽሑፍ ፡ አለው ።
39 አላህ ፡ የሚሻውን ፡ ያብሳል ፤ ያጸ
ድቃልም ፤ የመጽሐፉ ፡ መሠረ
ትም ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።
40 የዚያንም ፡ ያስፈራራናቸውን ፡
ከፊሉን ፡ ብናሳይህ ፡ (መልካም ፡
ነው) ፤ ወይም ፡ ብንገድልህ ፡
(ወቀሳ ፡ የለብህም) ፤ በአንተ ፡
ላይ ፡ ያለብህ ፡ ማድረስ ፡ ብቻ ፡
ነው ፤ ምርመራውም ፡ በኛ ፡ ላይ ፡
ነው ።
41 እኛ ፡ ምድርን ፡ ከጫፎችዋ ፡ የም
ናጎድላት ፡ ኾነን ፡ የምንመጣባት ፡
መኾናችንን ፡ አላዩምን ? አላህም ፡
ይፈርዳል ፤ ለፍርዱም ፡ ገልባጭ ፡
የለውም ፤ እርሱም ፡ ምርመራው ፡
ፈጣን ፡ ነው ።
42 እነዚያም ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡ የነበ
ሩት ፡ በእርግጥ ፡ መከሩ ፤ አዘንግ
ቶም ፡ የመያዙ ፡ ዘዴ ፡ በሙሉ ፡
የአላህ ፡ ነው ፤ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ የም
ትሠራውን ፡ ያውቃል ፤ ከሓዲዎ

---

1 የአምላክነት ፡ ባሕርይ ፡ እንዳላቸው ፡ መጥ
ኑዋቸው ።

ኙም ፡ የመጨረሻይቱ ፡ አገር ፡
ለማን ፡ እንደምትኾን ፡ ወደፊት ፡
ያውቃሉ ።
43 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡ መል
ክተኛ ፡ አይደለህም ፡ ይላሉ ፤
በኔና ፡ በናንተ ፡ መካከል ፡ መስ
ካሪ ፡ በአላህና ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡
የመጽሐፉ ፡ ዕውቀት ፡ ባለው ፡
ሰው ፡ በቃ ፡ በላቸው ።

## ምዕራፍ ፡ 14 ፡ ኢብራሂም ። ክፍል ፡ 13 ።

14ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ኢብራሂም ፡ (የአብርሃም ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 52 ፡ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 አ.ለ.ረ. (አሊፍ ፡ ላም፡ ራ ፤ ይህ ፡
ቁርአን) ፤ ሰዎችን ፡ በጌታቸው ፡
ፈቃድ ፡ ከጨለማዎች ፡ ወደ ፡
ብርሃን ፡ አሸናፊ ፡ ምስጉን ፡ ወደ ፡
ኾነው ፡ ጌታ ፡ መንገድ ፡ ታወጣ ፡
ዘንድ ፡ ወዳንተ ፡ ያወረድነው ፡
መጽሐፍ ፡ ነው ።
2 አላህ ፡ ያ ፡ በሰማያት ፡ ያለው ፡
በምድርም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ የርሱ ፡
ብቻ ፡ የኾነ ፡ ነው ፤ ለከሓዲዎ
ችም ፡ ከብርቱ ፡ ቅጣት ፡ ወዮላ
ቸው ።
3 እነዚያ ፡ የቅርቢቱን ፡ ሕይወት ፡
ከመጨረሻይቱ ፡ ሕይወት ፡ ይበ
ልጥ ፡ የሚወዱ ፡ ከአላህም ፡ መን
ገድ ፡ የሚያግዱ ፡ መጥመሟንም ፡
የሚፈልጉዋት ፡ ናቸው ፤ እነዚያ ፡
በሩቅ ፡ ስሕተት ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።
4 ከመልክተኛ ፡ ማንኛውንም ፡ ለነ
ርሱ ፡ ያብራራላቸው ፡ ዘንድ ፡ በወ
ገኖቹ ፡ ቋንቋ ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ አ
ልላክንም ፤ አላህም ፡ የሚሻውን ፡
ያጠማል ፤ የሚሻውንም ፡ ያቀ
ናል ፤ እርሱም ፡ አሸናፊው ፡ ጥበበ
ኛው ፡ ነው ።
5 ሙሳንም ፡ ወገኖችህን ፡ ከጨለማ
ዎች ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ አውጣ ፤
የአላህንም ፡ ቀኖች ፡ (1) አስገንዝ
ባቸው ፤ በማለት ፡ በታምራታ
ችን ፡ በእርግጥ ፡ ላክነው ፤ በዚህ ፡
ውስጥ ፡ በብዙ ፡ ታጋሽና ፡ በብዙ ፡
አመስጋኝ ፡ ለኾኑት ፡ ሁሉ ፡ በእር
ግጥ ፡ ታምራቶች ፡ አልሉ ።
6 ሙሳም ፡ ለሕዝቦቹ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ) ፤ ከፈርዖን ፡ ቤተ
ሰቦች ፡ መጥፎን ፡ ቅጣት ፡ የሚያ
ቀምሱዋችሁ ፡ ወንዶች ፡ ልጆቻ
ችሁንም ፡ የሚያርዱ ፡ ሴቶቻችሁ
ንም ፡ የሚተዉ ፡ ሲኾኑ ፡ በአዳና
ችሁ ፡ ጊዜ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ (የዋ
ለላችሁን) ፡ የአላህን ፡ ጸጋ ፡ አስ
ታውሱ ፤ በዚሃችሁ ፡ ከጌታችሁ ፡
የኾነ ፡ ታላቅ ፡ ፈተና ፡ አለበት ።
7 ጌታችሁም ፡— ብታመሰግኑ ፡
በእርግጥ ፡ እጨምርላችኋለሁ ፡

1 ያለፉትን ፡ ሕዝቦች ፡ ድርጊቶች ።



ብትክዱም ፡ (እቀጣችኋለሁ) ፤ ቅ
ጣቴ ፡ በእርግጥ ፡ ብርቱ ፡ ነውና ፡
በማለት ፡ ባስታወቀ ፡ ጊዜ ፡ (አስ
ታውሱ) ።
8 ሙሳም ፡ አለ ፡— እናንተም ፡ በም
ድር ፡ ያለውም ፡ ሁሉ ፡ በመላ ፡
ብትክዱ ፡ አላህ ፡ በእርግጥ ፡ ተብ
ቃቂ ፡ ምስጉን ፡ ነው ።
9 የነዚያ ፡ ከናንተ ፡ በፊት ፡ የነበ
ሩት ፡ የኑሕ ፡ ሕዝቦች ፡ የዓድም ፡
የሠሙድም ፡ የነዚያም ፡ ከነሱ ፡
በኋላ ፡ የነበሩት ፡ ከአላህ ፡ በስተ
ቀር ፡ ሌላ ፡ የማያውቃቸው ፡ (ሕዝ
ቦች) ፡ ወሬ ፡ አልመጣላችሁምን ?
መልክተኞቻቸው፡ በማስረጃዎች፡
መጧቸው፤ እጆቻቸውንም ፡ (በቁ
ጭት ፡ ሊነክሱ) ፡ ወደ ፡ አፎቻ
ቸው ፡ መለሱ ፤ አሉም ፡— እኛ ፡
እናንተ ፡ በርሱ ፡ በተላካችሁበት ፡
ነገር ፡ ካድን ፤ እኛም ፡ ወደርሱ ፡
ከምትጠሩን ፡ ነገር ፡ አወላዋይ ፡
በኾነ ፡ ጥርጣሬ ፡ ውስጥ ፡ ነን ።
10 መልክተኞቻቸው ፡— ከኀጢአቶ
ቻችሁ ፡ እንዲምራችሁ ፡ ወደ ፡
ተወሰነ ፡ ጊዜም ፡ (ያለ ፡ ቅጣት) ፡
እንዲያቆያችሁ ፡ የሚጠራችሁ ፡
ሲኾን ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡
ፈጣሪ ፡ በኾነው ፡ አላህ ፡ (በመ
ኖሩ) ፡ ጥርጣሬ ፡ አለን ? አሏቸው ፡
(ሕዝቦቹም) ፡— እናንተ ፡ ብጤያ
ችን ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ አይደላች
ሁም ፤ አባቶቻችን ፡ ይግገዙት ፡
ከነበሩት ፡ ልትከለክሉን ፡ ትሻላ
ችሁ ፤ ግልጽንም ፡ አስረጅ ፡ (ካመ
ጣችሁት ፡ ሌላ) ፡ አምጡልን ፡
አሉ ።
11 መልክተኞቻቸው ፡ ለነርሱ ፡
አሉ ፡— እኛ ፡ ብጤያችሁ ፡ ሰው ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለንም ፤ ግን ፡
አላህ ፡ ከባሮቹ ፡ በሚሻው ፡ ሰው ፡
ላይ ፡ ይለግሳል ፤ ለኛም ፡ በአላህ ፡
ፈቃድ ፡ እንጂ ፡ ማስረጃን ፡ ልናመ
ጣላችሁ ፡ አይገባንም ፤ በአላህም ፡
ላይ ፡ ምእምናኖች ፡ ይጠጉ ።
12 መንገዳችንንም ፡ በእርግጥ ፡ የመ
ራን ፡ ሲኾን ፡ በአላህ፡ ላይ ፡ የማ
ንመካ ፡ ለኛ ፡ ምን ፡ አለን ? በማስ
ቃየታችሁም ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡
እንታገሣለን ፤ በአላህም ፡ ላይ ፡
ተመኪዎች ፡ ሁሉ ፡ ይመኩ ።
13 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ለመልክተኞ
ቻቸው ፡— ከምድራችን ፡ በእር
ግጥ ፡ እናወጣችኋለን ፤ ወይም ፡
ወደ ፡ ሃይማኖታችን ፡ በእርግጥ ፡
ትመለሳላችሁ ፡ አሉ ፤ ወደነር
ሱም ፡ ጌታቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
ላከ ፡— ከሓዲዎችን ፡ በእርግጥ ፡
እናጠፋለን ።
14 ከነሱም ፡ በኋላ ፡ ምድሪቱን ፡ በእ
ርግጥ ፡ እናስቀምጣችኋለን ፤ ይኽ፡
በፊቴ ፡ መቆሙን ፡ ለሚፈራ ፡
ዛቻየንም ፡ ለሚፈራ ፡ ሰው ፡ ነው።
15 እርዳታንም ፡ (ከአላህ) ፡ ፈለጉ ፤
(ተረዱም) ፤ ጨካኝ ፡ ሞገደኛ ፡
የኾነም ፡ ሁሉ ፡ አፈረ ።
16 ከስተፊቱ ፡ ገሀነም ፡ አለበት ፡
እኸር ፡ ከኾነም ፡ ውሃ ፡ ይጋታል ።
17 ይጎነጨዋል፤ ሊውጠውም ፡
አይቀርብም ፤ ሞትም ፡ ከየስፍ
ራው ፡ ሁሉ ፡ ይመጣበታል ፤ እር
ሱም ፡ የሚሞት ፡ አይደለም ፤ ከስ
ተፊቱም፡ ከባድ ፡ ቅጣት፡ አለለ ።
18 የነዚያ ፡ በጌታቸው ፡ የካዱት ፡
ሰዎች ፡ ምሳሌ ፡ (መልካም) ፡ ሥራ
ዎቻቸው ፡ በነፋሻ ፡ ቀን ፡ ነፋስ ፡
በርሱ ፡ እንደ ፡ በረታችበት ፡ አ
መድ ፡ ነው ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡
በምንም ፡ ላይ ፡ (ሊጠቀሙ) ፡ አይ

ችሉም ፤ ይህ ፡ እርሱ ፡ ሩቅ ፡
ጥፋት ፡ ነው ።
19 አላህ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡
በውነት ፡ የፈጠረ ፡ መኾኑን ፡ አታ
ይምን ? ቢሻ ፡ ያጠፋችኋል ፤
አዲስ ፡ ፍጡርንም ፡ ያመጣል ።
20 ይህም ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ አስቸጋሪ ፡
አይደለም ።
21 የተሰበሰቡም ፡ ኾነው ፡ ለአላህ ፡
ይገለጻሉ ፤ (ሐሳበ) ፡ ደካማዎቹም፡
(ተከታዮች) ፡ ለነዚያ ፡ ለኮሩት፡—
እኛ ፡ ለናንተ ፡ ተከታዮች ፡ ነበ
ርን ፤ እናንተ ፡ ከአላህ ፡ ቅጣት ፡
ከኛ ፡ ላይ ፡ አንዳችን ፡ ነገር ፡ ተከ
ላካዮች ፡ ናችሁን ? ይላሉ ፤ (አስከ
ታዮቹም) ፡— አላህ ፡ ባቀናን ፡
ኖሮ ፡ በእርግጥ ፡ በመራናችሁ ፡
ነበር ፤ ይኋቸዋል ፤ ብንበሳጭ ፡
ወይም ፡ ብንታገሥም ፡ በኛ ፡ ላይ፡
እኩል ፡ ነው ፤ ለኛ ፡ ምንም ፡ መጠ
ጊያ ፡ የለንም ፡ ይላሉ ።
22 ነገሩም ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ሰይ
ጣን ፡ ይላቸዋል ፡— አላህ ፡ እውነ
ተኛውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገባላ
ችሁ ፤ ቃል ፡ ኪዳንም ፡ ገባሁ
ላችሁ ፤ አፈረስኩባችሁም ፤ ለ
ኔም ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡
ሥልጣን ፡ አልነበረኝም ፤ ግን ፡
ጠራኋችሁ ፤ ለኔም ፡ ታዘዛችሁ ፤
ስለዚህ ፡ አትውቀሱኝ ፤ ነፍሶቻች
ሁንም ፡ ውቀሱ ፤ እኔ ፡ የምረዳ
ችሁ ፡ አይደለሁም ፤ እናንተም ፡
የምትረዱኝ ፡ አይደላችሁም ፤
እኔ ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡ ለአላህ ፡
ተጋሪ ፡ በአደረጋችሁት ፡ ነገር ፡
ካድኩ ፤ በዳዮቹ ፡ ለነርሱ ፡ በእር
ግጥ ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ አልላ
ቸው ።
23 እነዚያም ፡ ያመኑና ፡ መልካም ፡
ሥራዎችን ፡ የሠሩ ፡ ከሥሮቻ
ቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱባቸውን፡
ገነቶች ፡ በውስጣቸው ፡ ዘውታሪ
ዎች ፡ ሲኾኑ ፡ በጌታቸው፡ ፈቃድ፡
እንዲገቡ ፡ ይደረጋሉ ፤ በውስጣ
ቸው ፡ መከባበሪያቸው ፡ ሰላም ፡
(ለናንተ ፡ ይኹን ፡ መባባል) ፡ ነው።
24 አላህ ፡ መልካምን፡ ቃል ፡ ሥርዋ፡
(በምድር ፡ ውስጥ) ፡ የተደላደ
ለች ፡ ቅርንጫፍዋም ፡ ወደ ፡
ሰማይ ፡ (የረዘመች) ፡ እንደ ፡
ኾነች ፡ መልካም ፡ ዛፍ ፡ አድርጎ ፡
ምሳሌን ፡ እንዴት ፡ እንደገለጸ ፡
አላየኸምን ?
25 ምግቧን ፡ (ፍሬዋን) ፡ በጌታዋ ፡
ፈቃድ ፡ በየጊዜው ፡ ትሰጣለች ፤
አላህም ፡ ለሰዎች ፡ ይገሠጹ ፡
ዘንድ ፡ ምሳሌዎችን ፡ ይገልጻል ።
26 የመጥፎም ፡ ቃል ፡ ምሳሌ ፡ ከም
ድር ፡ በላይ ፡ የተጐለሰሰች ፡
ለርሷ ፡ ምንም ፡ መደላደል ፡ የሌ
ላት ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ መጥፎ ፡
ዛፍ ፡ ነው ።
27 አላህ ፡ እነዚያን ፡ ያመኑትን ፡ በቅ
ርቢቱም ፡ ሕይወት ፡ በመጨረሻ
ይቱም ፡ (በመቃብር) ፡ በተረጋገ
ጠው ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ ያረጋቸዋል ፤
ከሓዲዎችንም ፡ አላህ ፡ ያሳስታቸ
ዋል ፤ አላህም ፡ የሚሻውን ፡ ይሠ
ራል ።
28 ወደነዚያ ፡ የአላህን ፡ ጸጋ ፡ በክሕ
ደት ፡ ወደ ፡ ለወጡት ፡ ሕዝቦቻቸ
ውንም ፡ በጥፋት ፡ አገር ፡ ወደ ፡
አሰፈሩት ፡ (ወደ ፡ ቁረይሾች) ፡
አላየህምን ?
29 (አገሪቱም) ፡ የሚገቧት ፡ ስት
ኾን ፡ ገሀነም ፡ ናት ፤ ምን ፡ ትከ
ፉም ፡ መርጊያ !



30 ለአላህም ፡ ከመንገዱ ፡ ያሳስቱ ፡
ዘንድ ፡ ባላንጣዎችን ፡ አደረጉ
ለት ፤ (ጥቂትን) ፡ ተጠቀሙ ፡
መመለሻችሁም ፡ ወደ ፡ እሳት ፡
ነው ፡ በላቸው ።
31 ለነዚያ ፡ ላመኑት ፡ ባሮቼ ፡ በርሱ ፡
ውስጥ ፡ ሽያጭና ፡ ወዳጂነት ፡ የሌ
ለበት ፡ ቀን ፡ ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡
ሶላትን ፡ በደንቡ ፡ ይሰግዳሉ ፤
ከሰጠናቸውም ፡ ሲሳይ ፡ በምስጢ
ርም ፡ በግልጽም ፡ ይለግሳሉ ።
(ስገዱ ፡ ለግሱም) ፡ በላቸው ።
32 አላህ ፡ ያ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡
የፈጠረ ፡ ከሰማይም ፡ ውሃን ፡ ያወ
ረደ ፡ በርሱም ፡ ከፍሬዎች ፡ ሲሳ
ይን ፡ ለናንተ ፡ ያወጣ ፡ መርከቦች
ንም ፡ በፈቃዱ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡
ይንሻለሉ ፡ ዘንድ ፡ ለናንተ ፡
የገራ ፡ ወንዞችንም ፡ ለናንተ ፡
የገራ ፡ ነው ።
33 ፀሐይንና ፡ ጨረቃንም ፡ ዘወትር ፡
ኼያጆች ፡ ሲኾኑ ፡ ለናንተ ፡ የገራ፡
ሌሊትንና ፡ ቀንንም ፡ ለናንተ ፡
የገራላችሁ ፡ ነው ።
34 ከለመናችሁትም ፡ ሁሉ ፡ የሰጣ
ችሁ ፡ ነው ፤ የአላህንም ፡ ጸጋ ፡
ብትቆጥሩ ፡ አትዘልቋትም ፤ ሰው ፡
በጣም ፡ በደለኛ ፡ ከሓዲ ፡ ነው ።
35 ኢብራሂምም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ (አስታ
ውስ) ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ! ይህንን ፡
አገር ፡ (መካን) ፡ ጸጥተኛ ፡ አድር
ገው ፤ እኔንም ፡ ልጆቼንም ፡ ጣዖ
ታትን ፡ ከመገዛት ፡ አርቀን ፤
36 ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እነርሱ ፡ (ጣዖ
ታት) ፡ ከሰዎች ፡ ብዙዎችን ፡ አሳ
ስተዋልና ፤ የተከተለኝም ፡ ሰው ፡
እርሱ ፡ ከኔ ፡ ነው ፤ ትእዛዜንም ፡
የጣሰ ፡ ሰው ፡ አንተ ፡ መሓሪ ፡
አዛኝ ፡ ነህ ፤
37 ጌታችን ፡ ሆይ ! እኔ ፡ አዝመራ ፡
በሌለው ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ በተከ
በረው ፡ ቤት ፡ (በከዕባ) ፡ አጠ
ገብ ፡ ከዘሮቼ ፡ አስቀምጥሁ ፤ ጌታ
ችን ፡ ሆይ ! ሶላትን ፡ ያቋቁሙ ፡
ዘንድ ፡ (አስቀመጥኳቸው) ፤ ከሰ
ዎችም ፡ ልቦችን ፡ ወደነሱ ፡ የሚ
ናፍቁ ፡ አድርግ ፤ ያመሰግኑህም ፡
ዘንድ ፡ ከፍሬዎች ፡ ስጣቸው ፤
38 ጌታችን ፡ ሆይ ! አንተ ፡ የምንደብ
ቀውንም ፡ የምንገልጸውንም ፡
ሁሉ ፡ በእርግጥ ፡ ታውቃለህ ፤
በአላህም ፡ ላይ ፡ በምድርም ፡ በሰ
ማይም ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አይደበ
ቅም ፤
39 ለዚያ ፡ ከሽምግልና ፡ በኋላ ፡ ኢስ
ማዒልን ፡ ኢስሐቅንም ፡ ለኔ ፡ ለሰ
ጠኝ ፡ አላህ ፡ ምስጋና ፡ ይገባው ፤
ጌታዬ ፡ ልመናን ፡ በእርግጥ ፡
ሰሚ ፡ ነውና ፤
40 ጌታዬ ፡ ሆይ ! ሶላትን ፡ አዘው
ትሬ ፡ የምሰግድ ፡ አድርገኝ ፤ ከዘ
ሮቼም ፡ (አድርግ) ፤ ጌታችን ፡
ሆይ ፡ ጸሎቴንም ፡ ተቀበለኝ ፤
41 ጌታችን ፡ ሆይ ! ለኔም ፡ ለወላጆ
ቼም ፡ ለምእመናንም ፡ ሁሉ ፡
ምርመራ ፡ በሚደረግበት ፡ ቀን ፡
ማር ።
42 አላህንም ፡ በደለኞች ፡ ከሚሠ
ሩት ፡ ግፍ ፡ ዘንጊ ፡ አድርገህ ፡
አታስብ ፤ የሚያቆያቸው ፡ ዓይ
ኖች ፡ በርሱ ፡ እስከሚፈጡበት ፡
ቀን ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
43 (ወደ ፡ ጠሪው ፡ መልአክ) ፡ ቸኳ
ዮች ፡ ራሶቻቸውን ፡ አንጋጣጮች
ኾነው ፡ (ዓይኖቻቸው ፡ ይፈጣሉ)፤
ዓይኖቻቸው ፡ ወደነርሱ ፡ አይመ
ለሱም ፤ ልቦቻቸውም ፡ ባዶዎች ፡
ናቸው ።

44 ሰዎችንም ፡ ቅጣቱ ፡ የሚመጣባቸውን ፡ ቀን ፡ አስፈራራቸው ፤ እነዚያም ፡ የበደሉት ፡— ጌታችን ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ አቆየን ፤ ጥሪህን ፡ እንቀበላለንና ፡ መልክተኞቹንም ፡ እንከተላለንና ፡ ይላሉ ፤ ከአሁን ፡ በፊት ፡ (በምድረ ፡ ዓለም) ፤ ለናንተ ፡ ምንም ፡ መወገድ ፡ የላችሁም ፡ በማለት ፡ የማላችሁ ፡ አልነበራችሁምን ? (ይባላሉ) ።

45 በነዚያም ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ በበደሉት ፡ ሰዎች ፡ መኖሪያ ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጣችሁ ፤ በነሱም ፡ እንዴት እንደ ፡ ሠራንባቸው ፡ ለናንተ ፡ ተገለጸላችሁ ፤ ለናንተም ፡ ምሳሌዎችን ፡ ገለጽንላችሁ ።

46 (በነቢዩ ፡ ላይ) ፡ ሴራቸውንም ፡ በእርግጥ ፡ አሴሩ ፤ ሴራቸውም ፡ (ቅጣቱ) ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ ሴራቸውም ፡ ኮረብታዎች ፡ (ሕግጋቶች) ፡ በርሱ ፡ የሚወገዱበት ፡ አልነበረም ።

47 አላህንም ፡ መልክተኞቹን ፡ (የገባላቸውን) ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ አፍራሽ ፡ አድርገህ ፡ አታስብ ፤ አላህ ፡ አሸናፊ ፡ የመበቀል፡ ባለቤት ፡ ነው ።

48 ምድር ፡ በሌላ ፡ ምድር ፡ የምትለወጥበትን ፡ ሰማያትም ፡ (እንደዚሁ)፡ አንድ ፡ አሸናፊ ፡ ለኾነው ፡ አላህም ፡ (ፍጡራን ፡ ሁሉ)፡ የሚገለጹበትን ፡ ቀን ፡ (አስታውሱ) ።

49 አመጠኞችንም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ በሰንሰለቶች ፡ ተቆራኝተው ፡ ታያቸዋለህ ።

50 ቀሚሶቻቸው፡ ከካትራም፡ ናቸው፡ ፊቶቻቸውንም ፡ እሳት ፡ ትሸፍናቸዋለች ።

51 አላህ ፡ ነፍስን ፡ ሁሉ ፡ የሠራችውን ፡ ይመነዳ ፡ ዘንድ ፡ (ይህንን ፡ አደረገ) ፤ አላህ ፡ ምርመራው ፡ ፈጣን ፡ ነው ።

52 ይህ ፡ (ቁርአን) ፡ ለሰዎች ፡ ገላጭ ፡ ነው ፤ (ሊመከሩበት) ፡ በርሱም ፡ ሊስፈራሩበት ፡ እርሱም ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ ሊያውቁበት ፡ የአእምሮ ፡ ባለ ፡ ቤቶችም ፡ ሊገሠጡበት ፡ (የተወረደ) ፡ ነው ።



15ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሒጅር ፡ (የሒጅር ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 99 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በኾነው ።

1 አ.ለ.ረ. (አሊፍ ፡ ላም ፡ ራ) ፡ ይህች ፡ (አናቅጽ) ፡ ከመጽሐፉ ፡ አንቀጾችና ፡ ገላጭ ፡ ከኾነው ፡ ቁርአን ፡ ናት ።

★ ★ ★

2 እነዚያ ፡ የካዱት ፡ (በትንሣኤ ፡ ቀን) ፡ ሙስሊሞች፡ ኾኑ ፡ ና ፡ : ፡ በብዛት ፡ ይመኛሉ ።

3 ተዋቸው ፡ ይብሉ ፤ ይጠቀሙም ፤ ተስፋም ፡ ያዘናጋቸው ፡ በእርግጥም ፡ (መጥፎ ፡ ፍጻሜያቸውን) ፡ ያውቃሉ ።

4 ማንኛይቱንም ፡ ከተማ ፡ ለርሷ ፡ የተወሰነ ፡ መጽሐፍ ፡ (ጊዜያት) ፡ ያላት ፡ ኾና ፡ እንጂ ፡ አላጠፋንም፤

5 ማንኛይቱም ፡ ሕዝብ ፡ ጊዜዋን ፡ ምንም ፡ አትቀድምም ፤ (ከርሱ) ፡ አይቆዩምም ።

6 ፡—አንተ ፡ ያ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ቁርአን ፡ የተወረደለት ፡ ሆይ ! አንተ፡ በእርግጥ ፡ ዕብድ ፡ ነህ ፡ አሉም ።

7 ከውነተኞቹ ፡ እንደ ፡ ኾንክ ፡ በመላእክት ፡ (መስካሪ) ፡ ለምን ፡ አትመጣንም ፡ (አሉ) ፤

8 መላእክትን ፡ በውነት ፡ (በቅጣት) ፡ እንጂ ፡ አናወርድም ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ የሚቆዩ ፡ አይደሉም ።

9 እኛ ፡ ቁርአንን ፡ እኛው ፡ አወረድነው ፤ እኛም ፡ ለርሱ ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ነን ።

10 ከአንተም ፡ በፊት ፡ በነበሩት ፡ በመጀመሪያዎቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ውስጥ ፡ (መልክተኞችን) ፡ በእርግጥ ፡ ልከናል ።

11 ማንኛውም ፡ መልክተኛ ፡ በርሱ ፡ የሚያላግጡበት ፡ ኾነው ፡ እንጅ ፡ አይመጣቸውም ፡ ነበር ።

12 እንደዚሁ ፡ (ማስተባበልን) ፡ በአመጠኞቹ ፡ ልቦች ፡ ውስጥ ፡ እናገባዋለን ።

13 በርሱ ፡ አያምኑበትም ፤ የቀድሞዎቹም ፡ ድርጊት ፡ በእርግጥ ፡ አልፋለች ፤ (እንደ ፡ ጠፉ ፡ ይጠፋሉ) ።

14 በነርሱም ፡ ላይ ፡ ከሰማይ ፡ ደጃፍን ፡ በከፈትንላቸውና ፡ በርሱ ፡ ሲወጡ ፡ በዋሉ ፡ ኖሮ ፤

15 ፡—የተዘጉት ፡ ዓይኖቻችን ፡ ናቸው ፤ እንዲያውም ፡ እኛ ፡ የተደገመብን ፡ ሰዎች ፡ ነን ፤ ባሉ ፡ ነበር ።

16 በሰማይም ፡ ላይ ፡ ቡርጆችን ፡ (1) በእርግጥ ፡ አድርገናል ፤ ለተመልካቾችም ፡ (በከዋክብት) ፡ አጊጠናታል ።

17 ከተባረረ ፡ ሰይጣንም ፡ ሁሉ ፡ ጠብቀናታል ።

18 ግን ፡ (ወሬ) ፡ መስማትን ፡ የሚሰርቅ ፡ ወዲያውኑ ፡ አብሪ ፡ ችቦ ፡ ይከተለዋል ። (ያቃጥለዋል) ።

1 በሥራ ፡ ሁሉት ፡ የተከፈሉ ፡ የከዋክብት ፡ መዞሪያዎች ፡ ናቸው ።

19 ምድርንም ፡ ዘረጋናት ፤ በውስ
ጧም ፡ ኮረብታዎችን ፡ ጣልንባት፤
በውስጧም ፡ (የተለካን) ፡ በቃይ፡
ሁሉ ፡ አበቀልንባት ።

20 በርሷም ፡ ውስጥ ፡ ለናንተ ፡ መኖ
ሪያዎችንና ፡ ለርሱ ፡ መጋቢዎቹ ፡
ያልኾናችሁትንም ፡ (እንስሳትን) ፡
አደረግንላችሁ ።

21 መካዚኖቹም ፡ (መክፈቻቸው) ፡
እኛ ፡ ዘንድ ፡ ያልኾነ ፡ ምንም ፡
ነገር ፡ የለም ፤ በተወሰነም ፡ ልክ ፡
እንጂ ፡ አናወርደውም ።

22 ነፋሶችንም ፡ (ደመናን) ፡ ተሸካ
ሚዎች ፡ አድርገን ፡ ላክን ፤ ከሰማ
ይም ፡ (ከደመና) ፡ ዝናምን ፡ አወ
ረድን ፤ እርሱንም ፡ አጠጣናችሁ ፤
እናንተም ፡ ለርሱ ፡ አድላቢዎች ፡
አይደላችሁም ።

23 እኛም ፡ ሕያው ፡ የምናደርግና ፡
የምንገድል ፡ እኛው ፡ ብቻ ፡ ነን ፤
እኛም ፡ (ፍጡርን ፡ ሁሉ) ፡ የምን
ወርስ ፡ (ቀሪ) ፡ ነን ።

24 ከናንተም ፡ ተቀዳሚዎቹን ፡ በእር
ግጥ ፡ ዐውቀናል ፤ ወደ ፡ ኋላም ፡
ቀሪዎቹን ፡ በእርግጥ ፡ ዐውቀናል።

25 ጌታህም ፡ እርሱ ፡ ይሰበስባችኋል፤
እርሱ ፡ ጥበበኛ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።

26 ሰውንም ፡ ከሚቅጨለጨል ፡
ሸክላ ፡ ከሚገማ ፡ ጥቁር ፡ ጭቃ ፡
በእርግጥ ፡ ፈጠርነው ።

27 ጃንንም ፡ (ከሰው) ፡ በፊት ፡ ከእ
ሳት ፡ ነበልባል ፡ ፈጠርነው ።

28 ጌታህም ፡ ለመላእክት ፡ ባለ ፡
ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፡— እኔ ፡
ሰውን ፡ ከሚቅጨለጨል ፡ ሸክላ ፡
ከሚገማ ፡ ጭቃ ፡ እፈጥራለሁ ።

29 (ፍጥረቱን) ፡ ባስተካከልኩትና ፡
በውስጡ ፡ ከመንፈሴ ፡ በነፋሁበ
ትም ፡ ጊዜ ፡ (1) ለርሱ ፡ ሰጋጆች ፡
ኾናችሁ ፡ ውደቁ ።

30 መላእክትም ፡ መላውም ፡ ተሰብ
ስበው ፡ ሰገዱ ።

31 ኢብሊስ ፡ (ዲያብሎስ) ፡ ብቻ ፡
ሲቀር ፤ ከሰጋጆቹ ፡ ጋር ፡ ከመ
ኾን ፡ እንቢ ፡ አለ ።

32 (አላህም) ፡— ኢብሊስ ፡ ሆይ !
ከሰጋጆቹ ፡ ጋር ፡ የማትኾን ፡
ላንተ ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ አለህ ፡
አለው ።

33 ፡—ከሚቅጨለጨል ፡ ሸክላ ፡
ከግም ፡ ጭቃ ፡ ለፈጠርከው ፡
ሰው ፡ ልሰግድ ፡ አይገባኝም ፡
አለ ።

34 (አላህ) ፡ አለው ፡— ከርሷም ፡ (2)
ውጣ ፤ አንተ ፡ የተባረርክ ፡
ርጉም ፡ ነህና ፤

35 ባንተ ፡ ላይም ፡ እስከ ፡ ፍርዱ ፡
ቀን ፡ ድረስ ፡ ርግማን ፡ አለብህ ።

36 ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እንግዲያስ ፡
(ሰዎች) ፡ እስከሚቀሰቀሱበት ፡
ቀን ፡ ድረስ ፡ አቆየኝ ፡ አለ ።

37 (አላህም) ፡ አለ ፡— አንተ ፡ ከሚ
ቆዩት ፡ ነህ ፡

38 እስከ ፡ ታወቀው ፡ ወቅት ፡ ቀን ፡
ድረስ ።

39 (ኢብሊስ) ፡ አለ ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ!
እኔን ፡ በማጥመምህ ፡ ይኹንብኝ፡
ለነርሱ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ (ኀጢአ
ትን) ፡ እሸልምላቸዋለሁ ፤ መላ
ቸውን ፡ አጠማቸውም ፡ አለሁ ፤

40 ከነርሱ ፡ ፍጹሞቹ ፡ ባሮችህ ፡
ብቻ ፡ ሲቀሩ ።

41 (አላህም) ፡ አለ ፡— ይህ ፡ በኔ ፡

1 ነፍስ ፡ በዘራሁበት ፡ ጊዜ ።
2 ከገነት ፡ ወይም ፡ ከሰማያት ።



ላይ ፡ (መጠበቁ ፡ የተገባ) ፡ ቀጥ
ተኛ ፡ መንገድ ፡ ነው ።

42 እነሆ ፡ ባሮቼ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡
ላንተ ፡ ስልጣን ፡ የለህም ፤ ከጠማ
ሞቹ ፡ የተከተለህ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡
ሲቀር ።

43 ገሀነምም ፡ (ለርሱና ፡ ለተከተ
ሉት) ፡ ለመላውም ፡ በእርግጥ ፡
ቀጠሯቸው ፡ ናት ፤

44 ለርሷ ፡ ሰባት ፡ ደ[illegible]ፎች ፡ አሏት ፤
ለየደጃፉም ፡ ሁ[illegible] ከነሱ ፡ የተከ
ፈለ ፡ ፋንታ ፡ [illegible]

45 እነዚያ ፡ (ከኀ[illegible]ት) ፡ የተጠነቀ
ቁት ፡ በአትክል[illegible]ና ፡ በምን
ጮች ፡ ውስጥ ፡ [illegible]

46 ጸጥተኞች ፡ ኾናችሁ ፡ በሰላም ፡
ግቧት ፡ (ይባላሉ) ።

47 ባልጋዎችም ፡ ላይ ፡ ፊት ፡ ለ
ፊት ፡ የሚቅጣጩ ፡ ወንድማማ
ቾች ፡ ኾነው ፡ በደረቶቻቸው ፡
ውስጥ ፡ ከቂም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡
እናስወግዳለን ።

48 በርሷም ፡ ውስጥ ፡ ድካም ፡ አይነካ
ቸውም ፤ እነሱም ፡ ከርሷ ፡ የሚወ
ጥጡ ፡ አይደሉም ።

49 ባሮቼን ፡ እኔ ፡ መሓሪው ፡ አዛኙ ፡
እኔው ፡ ብቻ ፡ መኾኔን ፡ ንገራቸው ፤

50 ቅጣቴም ፡ እርሱ ፡ አሳማሚ ፡
ቅጣት ፡ መኾኑን ፡ (ንገራቸው) ።

51 ከኢብራሂም፡እንግዶችም፡(ወሬ) ፡
ንገራቸው ።

52 በርሱ ፡ ላይ ፡ በገቡና ፡ ሰላም ፡
ባሉት ፡ ጊዜ ፡ የኾነውን ፡ (አስታ
ውስ) ። (እርሱም) ፡— እኛ ፡ ከና
ንተ ፡ ፈሪዎች ፡ ነን ፡ አላቸው ።

53 ፡—አትፍራ ፤ እኛ ፡ ዐዋቂ ፡ በኾነ ፡
ወንድ ፡ ልጅ ፡ እናበስርሃለን ፤
አሉት ።

54 ፡—እርጅና ፡ የደረሰብኝ ፡ ከመ
ኾኔ ፡ ጋር ፡ አበሰራችሁኝን ?
በምን ፡ ታበስሩኛላችሁ ? አለ ።

55 ፡—በውነት ፡ አበሰርንህ ፤ ከተ
ስፋ ፡ ቆራጮችም ፡ አትኹን ፡
አሉ ።

56 ከጠማማዎችም ፡ በስተቀር ፡ ከጌ
ታው ፡ እዝነት ፡ ተስፋን ፡ የሚቆ
ርጥ ፡ ማነው ? አለ ።

57 ፡—እላንተ ፡ መልክተኞች ፡ ሆይ !
እረ ፡ ለመኾኑ ፡ ነገራችሁ ፡ ምን
ድን ፡ ነው ? አለ ።

58 ፡—እኛ ፡ አመጠኞች ፡ ወደ፡ኾኑ፡
ሕዝቦች ፡ ተልከናል ፡ አሉት ፤

59 የሉጥ ፡ ቤተሰቦች ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ ፡
(እነርሱን) ፡ እኛ ፡ ሁላቸውንም ፡
በእርግጥ ፡ የምናድናቸው ፡ ነን ፤

60 ሚስቱ ፡ ብቻ ፡ ስትቀር ፤ እርሷን ፡
(በቅጣቱ ፡ ውስጥ) ፡ ከሚቀሩት ፡
መኾኗን ፡ ወስነናል ፡ (አሉ) ።

61 መልክተኞቹም ፡ የሉጥን ፡ ቤተ
ሰቦች ፡ በመጡባቸው ፡ ጊዜ ፤

62 (ሉጥ) ፡— እናንተ ፡ የተሳታችሁ ፡
(1) ሕዝቦች ፡ ናችሁ ፡ አላቸው ።

63 አይደለም ፡ እኛ ፡ ሕዝቦችህ ፡
በርሱ ፡ ይጠራጠሩበት ፡ በነበ
ሩት ፡ ቅጣት ፡ መጣንህ ፡ አሉት ።

64 እውነትንም ፡ ይዘን ፡ መጣንህ ፤
እኛም ፡ በእርግጥ ፡ እውነተኞች ፡
ነን ።

65 ከቤተሰብህም ፡ ጋር ፡ በሌሊቱ ፡
ከፊል ፡ ኺድ ፤ ከኋላቸውም ፡ ተከ
ተል ፤ ከናንተም ፡ አንድም ፡ ሰው፡
ወደ ፡ ኋላው ፡ አይገላመጥ ፤ ወደ ፡
ታዘዛችሁበትም ፡ ስፍራ ፡ እለፉ ፡
(አሉት) ።

1 የማናውቃችሁ ።

66 ወደርሱም ፡ ያንን ፡ ትእዛዝ ፡ አወ
ረድን ፤ (እርሱም) ፡ የነዚህ ፡ (ሕዝ
ቦች) ፡ መጨረሻ ፡ ያነጉ ፡ ሲኾኑ ፡
(ስራቸው) ፡ መቆረጥ ፡ ነው ።
67 የከተማይቱም ፡ ሰዎች ፡ የሚበሳ
ሰሩ ፡ ኾነው ፡ መጡ ።
68 (ሉጥም) ፡ አለ ፡— እነዚህ ፡ እንግ
ዶቼ ፡ ናቸውና ፡ አታጋልጡኝ ፤
69 አላህንም ፡ ፍሩ ፤ አታሳፍሩኝም ።
70 ፡—ከዓለማት ፡ (ማንንም ፡ እንዳታ
ስተናግድ) ፡ አልከለከልንህምን ?
አሉት ።
71 (ሉጥም) ፡— እነኛህ፥ ሴቶች፡
ልጆቼ ፡ ናቸው ፤ ሠሪዎች ፡ ብት
ኾኑ ፡ (አግቧቸው) ፡ አለ ።
72 በዕድሜህ ፡ እንምላለን ፡ እነሱ ፡
በእርግጥ ፡ በስካራቸው ፡ ውስጥ ፡
ይዋልላሉ ።
73 ጩኸቲቱም ፡ ፀሐይ ፡ የወጣችባ
ቸው ፡ ሲኾኑ ፡ ያዘቻቸው ።
74 ላይዋንም ፡ ከታችዋ ፡ አደረግን ፤
በነሱም ፡ ላይ ፡ የሸክላ ፡ ደንጊ
ያዎችን ፡ አዘነብንባቸው ።
75 በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ለተመልካቾች ፡
በእርግጥ ፡ መገምገሚያዎች ፡ አሉ
በት ።
76 እሷም ፡ (ከተማይቱ) ፡ በቀጥታ ፡
መንገድ ፡ ላይ ፡ ናት ።
77 በዚህ ፡ ውስጥ ፡ በእርግጥ ፡ ለምእ
ምናን ፡ መገሰጫ ፡ አለ ።
78 እነሆ ፡ የአይከት ፡ (1) ሰዎችም ፡
በእርግጥ ፡ በዳዮች ፡ ነበሩ ፤
79 ከነሱም ፡ ተበቀልን ፡ (2) ሁለ
ቱም ፡ (የሉጥና ፡ የአይከት ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ከተሞች) ፡ በእርግጥ ፡ በግ
ልጽ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ናቸው ።
80 የሒጅርም ፡ (1) ሰዎች ፡ መልክተ
ኞቹን ፡ በእርግጥ ፡ አስተባበሉ ።
81 ታምራታችንንም ፡ ሰጠናቸው ፤
ከርሷም ፡ ዘንጊዎች ፡ ነበሩ ።
82 ከኮረብታዎችም ፡ ቤቶችን ፡ ጸጥ
ተኞች ፡ ኾነው ፡ ይጠርቡ ፡ ነበር ።
83 ያነጉም ፡ ሲኾኑ ፡ ጩኸት ፡ ያዘ
ቻቸው ፤ (ወደሙ) ።
84 ይሠሩትም ፡ የነበሩት ፡ ሕንጻ ፡
ምንም ፡ አልጠቀማቸውም ።
85 ሰማያትንና ፡ ምድርንም ፡ በመካከ
ላቸው ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ በው
ነት ፡ እንጂ ፡ (በላግጣ) ፡ አልፈጠ
ርንም ፤ ሰዓቲቱም ፡ በእርግጥ ፡
መጪ ፡ ናት ፤ መልካምንም ፡ ይቅ
ርታ ፡ አድርግላቸው ።
86 ጌታህ ፡ እርሱ ፡ (ያልነበረን) ፡
ፈጣሪው ፡ ዐዋቂው ፡ ነው ።
87 ከሚደጋገሙ ፡ የኾኑን ፡ ሰባትንና፡
ታላቁንም ፡ ቁርአን ፡ (በሙሉ) ፡
በእርግጥ ፡ ሰጠንህ ።
88 ከነርሱ ፡ (ከከሓዲዎች) ፡ ብዙዎ
ችን ፡ ወገኖች ፡ በርሱ ፡ ወደ ፡ አጣ
ቀምንበት ፡ ጸጋ ፡ ዓይኖችህን ፡
አትዘርጋ ፤ በነሱም ፡ ላይ ፡ (ባያ
ምኑ) ፡ አትዘን ፤ ክንፍህንም ፡ ለም
እምናን ፡ አለዝብ ።
89 በልም ፡— እኔ ፡ ግልጽ ፡ አስፈራ
ሪው ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤
90 (ሰዎችን ፡ ለማገድ ፡ የመካን ፡
በሮች) ፡ በተከፋፈሉት ፡ ላይ ፡
እንደ ፡ አወረድነው ፡ (በኾነ ፡
ቅጣት ፡ አስፈራሪያችሁ ፡ ነኝ ፡
በል) ።

1 የዛፍ ፡ ወይም ፡ የጫካ ፡ ወይም ፡ የከተማ ፡ ስም ፡ ናት ።
2 በሙቀትና ፡ በእሳት ፡ ዝናም፡ ቀሠፍናቸው።

1 በመዲናና ፡ በሻም ፡ መካከል ፡ የሚገኝ ፡ ሸለቆ ፡ ነው ።



91 (እነርሱም)፡ እነዚያ ፡ ቁርአንን፡ ክ
ፍልፍሎች ፡ ያደረጉ ፡ ናቸው ። (1)
92 በጌታህም ፡ እንምላለን ፤ ሁላቸው
ንም ፡ እንጠይቃቸዋለን ፤
93 ይሠሩት ፡ ከነበሩት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ።
94 የታዘዝክበትንም ፡ ነገር ፡ በይፋ ፡
ግለጽ ፤ አጋሪዎችንም ፡ ተዋቸው።
95 ተሳላቂዎችን ፡ ሁሉ ፡ እኛ ፡ በቅተ
ንሃል ።
96 (እነሱም) ፡ እነዚያ ፡ ከአላህ ፡
ጋር ፡ ሌላ ፡ አምላክን ፡ ያደረጉ ፡
ናቸው ፤ በእርግጥም ፡ (ፍጻሜያቸ
ውን) ፡ወደፊት ፡ ያውቃሉ ።
97 አንተም ፡ በሚሉት፡ ነገር ፡ ልብህ፡
የሚጠብ ፡ መኾኑን ፡ በእርግጥ ፡
እናውቃለን ።
98 ጌታህንም ፡ ከማመስገን ፡ ጋር ፡
አጥራው ፡ ከሰጋጆቹም ፡ ኹን ።
99 እውነቱም ፡ (ሞት) ፡ እስኪመ
ጣህ ፡ ድረስ ፡ ጌታህን ፡ ተገዛ ።

1 ከፊሉ ፡ ድግምት ፡ ከፊሉ ፡ ጥንቆላ ፡ ከፊሉ ፡ ቅኔ ፡ በማለት ።

## ምዕራፍ ፡ 16 ፡ አል-ነሕል ። ክፍል ፡ 14 ።

16ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ነሕል ፡ (የንብ ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 128 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ፡ በጣም፡ አዛኝ፡ በሆነው ።
1 የአላህ ፡ ትእዛዝ ፡ መጣ ፤ ስለዚህ ፡
አታስቸኩሉት ፤ ከማይገባው ፡
ሁሉ ፡ ጠራ ፤ ከሚያጋሩትም ፡
ሁሉ ፡ ላቀ ፤
2 ከባሮቹ ፡ በሚሻው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡
መላእክትን ፡ ከራእይ ፡ ጋር ፡ በፈ
ቃዱ ፡ ያወርዳል ፤ (ከሓዲዎችን ፡
በቅጣት) ፡ አስጠንቅቁ ፤ እነሆ ፡
ከኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም፤
ፍሩኝም ፡ ማለትን ፡ (አስታውቁ ፡
በማለት ፡ ያወርዳል) ።
3 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ በውነት ፡
ፈጠረ ፤ ከሚያጋሩት ፡ ሁሉ ፡
ጠራ ።
4 ሰውን ፡ ከፍትወት ፡ ጠብታ ፡
ፈጠረው ፤ ከዚያም ፡ እርሱ ፡ ወዲ
ያውኑ ፡ (ትንሣኤን ፡ በመካድ) ፡
ግልጽ ፡ ተከራካሪ ፡ ይኾናል ።
5 ግመልን ፡ ከብትን ፡ ፍየልንም ፡
በርሷ ፡ (ብርድ ፡ መከላከያ) ፡
ሙቀት ፡ ጥቅሞችም ፡ ያሉባት ፡
ስትኾን ፡ ለናንተ ፡ ፈጠረላችሁ ፤
ከርሷም ፡ ትበላላችሁ ።
6 ለናንተም ፡ በርሷ ፡ ወደ ፡ ማረፊ
ያዋ ፡ በምትመለሷት ፡ ጊዜ ፡ በም
ታሰማሩዋትም ፡ ጊዜ ፡ ውበት ፡
አላችሁ ።
7 ጉዋዞቻችሁንም ፡ በነፍሶች ፡ ች
ግር ፡ እንጂ ፡ ወደማትደርሱበት ፡
አገር ፡ ትሸከማለች ፤ ጌታችሁ ፡
በእርግጥ ፡ ርኅሩኅ ፡ አዛኝ ፡
ነውና ።
8 ፈረሶችንም፥ በቅሎዎችንም፥ አህ
ዮችንም፥ ልትቀመጡዋቸውና፡

ልታጌጡባቸው ፡ (ፈጠረላችሁ) ፤
የማታውቁትንም ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡
ይፈጥራል ።
9 በአላህም ፡ ላይ ፡ (በችሮታው) ፡
ቀጥተኛውን ፡ መንገድ ፡ መግ
ለጽ ፡ አለበት ፤ ከርሷም ፡ (ከመን
ገድ) ፡ ጠማማ ፡ አልለ ፤ በሻም ፡
ኖሮ ፡ ሁላችሁንም ፡ በእርግጥ ፡
ባቀናችሁ ፡ ነበር ።
10 እርሱ ፡ ያ ፡ ከሰማይ ፡ ውሃን ፡ ያወ
ረደ ፡ ነው ፤ ከርሱ ፡ ለናንተ ፡ መ
ጠጥ ፡ አላችሁ ፤ ከርሱም ፡ (እንስ
ሳዎችን) ፡ በርሱ ፡ የምታሰማሩ
በት ፡ ዛፍ ፡ (ይበቅልበታል) ።
11 በርሱ ፡ ለናንተ ፡ አዝመራን ፡
(የዘይት) ፡ ወይራንም ፡ ዘምባባዎ
ችንም ፡ (ተምርን) ፡ ወይኖችንም ፡
ከፍሬዎችም ፡ ሁሉ ፡ ያበቅልላች
ኋል ፤ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ለሚያስተነ
ትኑ ፡ ሕዝቦች ፡ በእርግጥ ፡ ታ
ምር ፡ አልለ ።
12 ለናንተም ፡ ሌሊትንና ፡ ቀንን ፡
ፀሐይንና ፡ ጨረቃንም ፡ ገራላ
ችሁ ፤ ከዋክብትም ፡ በፈቃዱ ፡
የተገሩ ፡ ናቸው ፤ በዚህ ፡ ውስጥ ፡
ለሚያውቁ ፡ ሕዝቦች ፡ በእርግጥ ፡
ታምራቶች ፡ አልሉ ።
13 በምድርም ፡ ላይ ፡ መልኮቹ ፡ የተ
ለያዩ ፡ ኾኖ ፡ ለናንተ ፡ የፈጠረላች
ሁን ፡ ሁሉ ፡ (ገራላችሁ) ፤ በዚህ ፡
ውስጥ ፡ ለሚገሠጡ ፡ ሕዝቦች ፡
በእርግጥ ፡ ታምር ፡ አልለ ።
14 እርሱም ፡ ያ ፡ ባሕርን ፡ ከርሱ ፡
እርጥብ ፡ ስጋን ፡ ልትበሉና ፡ ከር
ሱም ፡ የምትለብሱትን ፡ ጌጣጌጥ ፡
ታወጡ ፡ ዘንድ ፡ የገራ ፡ ነው ፤
መርከቦችንም ፡ በውስጡ ፡ (ውሃ
ውን) ፡ ቀዳጆች ፡ ኾነው ፡ (ሲንሻ
ለሉ) ፡ ታያለህ ፤ ከችሮታው ፡
ልትፈልጉና ፡ ልታመሰግኑም ፡
(ገራላችሁ) ።
15 በምድርም ፡ ውስጥ ፡ በናንተ ፡ እን
ዳታረገርግ ፡ ተራራዎችን ፡ ጣለ
ባት ፤ ጂረቶችንም ፡ መንገዶችን
ም ፡ ትመሩ ፡ ዘንድ ፡ (አደረገ) ።
16 ምልክቶችንም ፡ (አደረገ) ፤ በከዋ
ክብትም ፡ እነሱ ፡ ይመራሉ ።
17 የሚፈጥር ፡ እንደማይፈጥር ፡
ነውን ? አትገሠጹምን ?
18 የአላህንም ፡ ጸጋ ፡ ብትቆጥሩ ፡
አትዘልቋትም ፤ አላህ ፡ በእርግጥ ፡
መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።
19 አላህም ፡ የምትደብቁትንና ፡ የም
ትገልጹትን ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል ።
20 እነዚያም ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የምትግ
ገዟቸው ፡ ምንንም ፡ አይፈጥሩም ፤
እነርሱም ፡ ይፈጠራሉ ፤
21 ሕያው ፡ ያልኾኑ ፡ ሙታን ፡
ናቸው ፤ መቼ ፡ እንደሚቀሰቀ
ሱም ፡ አያውቁም ።
22 አምላካችሁ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ እነዚያም ፡ በመጨረ
ሻይቱ ፡ ዓለም ፡ የማያምኑት ፡
ልቦቻቸው ፡ ከሓዲዎች ፡ ናቸው ፤
እነሱም ፡ የኮሩ ፡ ናቸው ፤ (አያም
ኑም) ።
23 አላህ ፡ የሚደብቁትንና ፡ የሚገ
ልጹትን ፡ ሁሉ ፡ የሚያውቅ ፡
ለመኾኑ ፡ ጥርጣሬ ፡ የለበትም ፤
እርሱ ፡ ኩሩዎችን ፡ አይወድም ።
24 ለነርሱም ፡ ጌታችሁ ፡ (በሙሐ
መድ ፡ ላይ) ፡ ምንን ፡ አወረደ ፡
በተባሉ ፡ ጊዜ ፡ (እርሱ) ፡ የመጀ
መሪያዎቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ተረቶች ፡
ነው ፡ ይላሉ ።
25 (ይህንንም ፡ የሚሉት) ፡ በትን
ሣኤ ፡ ቀን ፡ ኀጢአቶቻቸውን ፡



በሙሉ ፡ ከነዚያም ፡ ያለ ፡ ዕው
ቀት ፡ ኾነው ፡ ከሚያጠሟቸው ፡
ሰዎች ፡ ኀጢአቶች ፡ ከፊሉን ፡
ሊሸከሙ ፡ ነው ፤ ንቁ ፡ የሚሸከ
ሙት ፡ ኃጢአት ፡ ምንኛ ፡ ከፋ !
26 እነዚያ ፡ ከነሱ ፡ (ከቁረይሾች)
በፊት ፡ የነበሩት ፡ በእርግጥ ፡ መ
ከሩ ፤ አላህም ፡ ሕንጻዎቻቸውን ፡
ከመሠረቶቻቸው ፡ አፈረሰ ፤ ጣሪ
ያውም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ከበላያቸው፡
ወደቀባቸው ፤ ቅጣቱም ፡ ከማያው
ቁት ፡ ስፍራ ፡ መጣባቸው ።
27 ከዚያም ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ያዋር
ዳቸዋል ፤ እነዚያም ፡ በነሱ ፡
(ጉዳይ) ፡ ትከራከሩኝ ፡ የነበራች
ሁት ፡ ተጋሪዎቼ ፡ የት ፡ ናቸው ?
ይላቸዋል ፤ እነዚያ ፡ ዕውቀትን ፡
የተሰጡት ፡ ፡-ዛሬ ፡ ሐፍረቱና ፡
ቅጣቱ ፡ በእርግጥ ፡ በከሓዲዎች ፡
ላይ ፡ ነው ፡ ይላሉ ።
28 (እነርሱ) ፡ እነዚያ ፡ ነፍሶቻቸ
ውን ፡ በዳይ ፡ ኾነው ፡ መላእክት ፡
የሚገድሏቸው ፡ ናቸው ፤ ከክፉ ፡
ሥራ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የምንሠ
ራም ፡ አልነበርን ፡ (ሲሉ) ፡ ታዛ
ዥነታቸውን ፡ ይገልጻሉ ፤ በው
ነት ፡ አላህ ፡ ትሠሩት ፡ የነበራች
ሁትን ፡ ነገር ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፡ (ይባ
ላሉ) ።
29 የገሀነምንም ፡ ደጃፎች ፡ በውስጧ፡
ዘውታሪዎች ፡ ስትኾኑ ፡ ግቡ ፡
(ይባላሉ) ። የኩሩዎችም ፡ መኖ
ሪያ ፡ (ገሀነም) ፡ በእርግጥ ፡
ከፋች !
30 ለነዚያም ፡ ለተጠነቀቁት ፡ ጌታ
ችሁ ፡ ምንን ፡ ነገር ፡ አወረደ ?
ተባሉ ፤ መልካምን ፡ ነገር ፡ አሉ ፤
ለነዚያ ፡ ደግ ፡ ለሠሩት ፡ በዚህች ፡
በቅርቢቱ ፡ ዓለም ፡ መልካም ፡
ኑሮ ፡ አላቸው ፤ የመጨረሻይ
ቱም ፡ አገር ፡ በእርግጥ ፡ በላጭ ፡
ናት ፤ የጥንቁቆቹም ፡ አገር ፡ ምን ፡
ታምር !
31 (እርሷም) ፡ የሚገቡዋትና ፡ በሥ
ርዋ ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱባት ፡ ስት
ኾን ፡ የመኖሪያ ፡ አትክልቶች ፡
ናት ፤ ለነሱም ፡ በውስጧ ፡ የሚ
ሹት ፡ ሁሉ ፡ አላቸው ፤ እንደዚሁ፡
አላህ ፡ ጥንቁቆችን ፡ ይመነዳል ።
32 እነዚያ ፡ በመልካም ፡ ኹኔታ ፡
ላይ ፡ ኾነው ፡ መላእክት ፡ ሰላም ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ እያሉ ፡ የሚገድሏ
ቸው ፡ ናቸው ፤ ትሠሩት ፡ በነበራ
ችሁት ፡ ሥራ ፡ ገነትን ፡ ግቡ ፡
(ይባላሉ) ።
33 (ከሓዲዎች) ፡ መላእክት ፡ ወደ
ነሱ ፡ መምጣትን ፡ ወይም ፡ የጌ
ታህ ፡ ትእዛዝ ፡ መምጣቱን ፡
እንጂ ፡ አይጠባበቁም ፤ ከነሱ ፡
በፊት ፡ የነበሩት ፡ እንደዚህ ፡ ሠር
ተዋል ፤ አላህም ፡ አልበደላቸ
ውም ፤ ግን ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ የሚ
በድሉ ፡ ነበሩ ።
34 የሠሩዋቸውም ፡ ኀጢአቶች ፡
(ቅጣት) ፡ አገኛቸው ፤ በርሱም ፡
ይሳለቁበት ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡
በነሱ ፡ ላይ ፡ ወረደባቸው ።
35 እነዚያም ፡ (ጣዖታትን) ፡ ያጋ
ሩት ፡ አላህ ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ ከርሱ ፡
ሌላ ፡ እኛም ፡ አባቶቻችንም ፡
ምንንም ፡ ባልተገዛን፡ ነበር ፤
ያለርሱም ፡ (ትእዛዝ) ፡ ምንንም ፡
እርም ፡ ባላደረግን ፡ ነበር ፡ አሉ ፤
እነዚያም ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡ የነበ
ሩት ፡ እንደዚሁ ፡ ሠሩ ፤ በመልክ
ተኞቹም ፡ ላይ ፡ ግልጽ ፡ ማድረስ ፡
ብቻ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የለባቸውም ።

36 በየሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ውስጥ ፡ አላ
ህን ፡ ተገዙ ፤ ጣዖትንም ፡ ራቁ ፤
በማለት ፡ መልክተኛን ፡ በእር
ግጥ ፡ ልከናል ፤ ከነሱም ፡ ውስጥ ፡
አላህ ፡ ያቀናው ፡ ሰው ፡ አልለ ፤
ከነሱም ፡ ውስጥ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
ጥመት ፡ የተረጋገጠበት ፡ ሰው ፡
አልለ ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ ኺዱ ፤
የአስተባባዮችም ፡ መጨረሻ ፡
እንዴት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ተመል
ከቱ ።
37 በመቅናታቸው ፡ ላይ ፡ ብትጓጓ ፡
(ምንም ፡ ልታደርግ ፡ አትችልም)፤
አላህ ፡ የሚጠመውን ፡ ሰው ፡ (1)
አያቀናውምና ፤ ለነሱም ፡ ከረዳ
ቶች ፡ ምንም ፡ የላቸውም ።
38 ጥብቅ ፡ መሐሎቻቸውንም ፡ አ
ላህ ፡ የሚሞትን ፡ ሰው ፡ አያስነ
ሳም ፡ሲሉ ፡ በአላህ ፡ ስም ፡ ማሉ ፤
ሐሰት ፡ ነው ፡ (ያስነሳቸዋል) ፤
በርሱ ፡ ላይ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብ
ቷል ፤ አረጋግጧል ፤ ግን ፡ አብዛ
ኞቹ ፡ ሰዎች ፡ አያውቁም ።
39 (የሚቀሰቅሳቸውም) ፡ ለነሱ ፡
ያንን ፡ በርሱ ፡ የሚልለያዩበትን ፡
ሊገልጽላቸው ፤ እነዚያ ፡ የካዱ
ትም ፡ እነሱ ፡ ውሸታሞች ፡ የነ
በሩ ፡ መኾናቸውን ፡ እንዲያውቁ ፡
ነው ።
40 ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ (መኾኑን) ፡
በሻነው ፡ ጊዜ ፡ ቃላችን ፡ ለርሱ ፡
ኹን ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ወዲያ
ውም ፡ ይኾናል ።
41 እነዚያም ፡ ከተበደሉ ፡ በኋላ ፡
በአላህ ፡ (መንገድ ፡ ላይ) ፡ የተሰ
ደዱት ፡ በቅርቢቱ ፡ ዓለም ፡ መል
ካሚቱን ፡ አገር ፡ (መዲናን) ፡
በእርግጥ ፡ እናሰፍራቸዋለን ፤ የመ
ጨረሻይቱም ፡ ዓለም ፡ ምንዳ ፡
ታላቅ ፡ ነው ፤ (ከሓዲዎች) ፡ ቢያ
ውቁ ፡ ኖሮ ፡ (በተከተሏቸው ፡
ነበር) ።
42 (እነርሱ) ፡ እነዚያ ፡ የታገሡት ፡
በጌታቸውም ፡ ላይ ፡ የሚጠጉት ፡
ናቸው ።
43 ከአንተም ፡ በፊት ፡ ወደነሱ ፡ ወሕ
ይን ፡ (ራእይን) ፡ የምናወርድላቸ
ውን ፡ ሰዎችን ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡
አልላክንም ፤ የማታውቁም ፡ ብት
ኾኑ ፡ የዕውቀትን ፡ ባለቤቶች ፡
ጠይቁ ።
44 በግልጽ ፡ ማስረጃዎችና ፡ በመጻሕ
ፍት ፡ (ላክናቸው) ፤ ወደ ፡ አን
ተም ፡ ለሰዎች ፡ ወደነሱ ፡ የተወ
ረደውን ፡ (ፍች) ፡ ልትገልጽላቸ
ውና ፡ ያስተነትኑም ፡ ዘንድ ፡ ቁር
አንን ፡ አወረድን ።
45 እነዚያ፡ መጥፎዎችን፡ የዶለቱ፥
አላህ ፡ በነሱ ፡ ምድርን ፡ የሚገለ
ብጥባቸው ፡ ወይም ፡ ከማያው
ቁት ፡ ስፍራ ፡ ቅጣት ፡ የሚመጣ
ባቸው ፡ መኾኑን ፡ አይፈሩምን ?
46 ወይም ፡ (ካገር ፡ ወደ ፡ አገር) ፡
በሚዛወሩበት ፡ ጊዜ ፡ የሚይዛ
ቸው ፡ መኾኑን ፡ (አይፈሩምን ?)
እነሱም ፡ አሸናፊዎች ፡ አይደ
ሉም ።
47 ወይም ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ በማጉደል ፡
ላይ ፡ የሚይዛቸው ፡ መኾኑን ፡
(አይፈሩምን ?) ጌታችሁም ፡ በእር
ግጥ ፡ ርኅሩኅ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።
48 ወደዚያ ፡ ከማንኛውም ፡ ነገር ፡
አላህ ፡ ወደ ፡ ፈጠረው ፡ ጥላዎቹ ፡
እነርሱ ፡ የተዋረዱ ፡ ሲኾኑ ፡ ለአ
ላህ ፡ ሰጋጆች ፡ ኾነው ፡ ከቀኝና ፡
ከግራዎች ፡ወደሚዛወሩት ፡ አላዩ
ምን ?

1 እንዲጠም ፡ የሻውን ፡ ሰው ።



49 ለአላህም ፡ በሰማያት ፡ ያለው ፡
ከተንቀሳቃሽም ፡ በምድር ፡ ያ
ለው ፡ ሁሉ ፡ መላእክትም ፡ ይሰ
ግዳሉ ፤ እነርሱም ፡ አይኮሩም ።
50 ጌታቸውን ፡ ከበላያቸው ፡ ሲኾን ፡
ይፈሩታል ፤ የታዘዙትንም ፡ ሁሉ፡
ይሠራሉ ።
51 አላህም ፡ አለ ፡— ሁለት ፡ አማል
ክትን ፡ አትያዙ ፤ እርሱ ፡ አንድ ፡
አምላክ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ እኔንም ፡
ብቻ ፡ ፍሩ ።
52 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡
ሁሉ ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ መገዛ
ትም ፡ ዘወትር ፡ ሲኾን ፡ ለርሱ ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ ከአላህም ፡ ሌላ ፡
ያለን ፡ ትፈራላችሁን ?
53 ማንኛውም ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ያ
ለው ፡ ጸጋ ፡ ከአላህ ፡ ነው ፤ ከዚ
ያም ፡ ችግር ፡ በደረሰባችሁ ፡ ጊዜ፡
ወደርሱ ፡ ብቻ ፡ ትጮሃላችሁ ።
54 ከዚያም ፡ ከናንተ ፡ ላይ ፡ ችግርን ፡
ባነሳላችሁ ፡ ጊዜ ፡ ከናንተው ፡
የኾኑ ፡ ጭፍሮች ፡ ወዲያውኑ ፡
በጌታቸው ፡ (ጣዖትን) ፡ ያጋራሉ።
55 (የሚያጋሩትም) ፡ በሰጠናቸው ፡
ሊክዱ ፡ ነው ፤ ተጠቀሙም ፡ ወደ፡
ፊትም ፡ (የሚደርስባችሁን) ፡ በእ
ርግጥ ፡ ታውቃላችሁ ።
56 ለማያውቁትም ፡ (ጣዖታት) ፡ ከሰ
ጠናቸው ፡ ሲሳይ ፡ ፈንታን ፡ ያደ
ርጋሉ ፤ በአላህ ፡ እምላለሁ ፤ ትቀ
ጣጥፉት ፡ ከነበራችሁት ፡ ሁሉ ፡
በእርግጥ ፡ ትጠየቃላችሁ ።
57 ለአላህም ፡ (ከመላእክት) ፡ ሴቶች፡
ልጆችን ፡ ያደርጋሉ ፤ ጥራት ፡
ተገባው ፤ ለነርሱም ፡ የሚፈልጉ
ትን ፡ (ወንዶች ፡ ልጆችን) ፡ ያደር
ጋሉ ።
58 አንዳቸውም ፡ በሴት ፡ ልጅ ፡ በተ
በሰረ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ የተቆጨ ፡
ኾኖ ፡ ፊቱ ፡ ጠቊሮ ፡ ይውላል ።
59 በርሱ ፡ ከተበሰረበት ፡ ነገር ፡ መጥ
ፎነት ፡ በውርደት ፡ ላይ ፡ ኾኖ ፡
ይያዘውን ? ወይስ ፡ በዐፈር ፡
ውስጥ ፡ ይደብቀውን ? (በማለት ፡
እያምታታ) ፡ ከሰዎች ፡ ይደበቃል፤
ንቁ ፡ የሚፈርዱት ፡ (ፍርድ) ፡
ምንኛ ፡ ከፋ !
60 ለነዚያ ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ዓለም ፡
ለማያምኑት ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡
አላቸው ፤ ለአላህም ፡ ታላቅ ፡ ባሕ
ርይ ፡ አለው ፤ እርሱም ፡ አሸና
ፊው ፡ ጥበበኛው ፡ ነው ።
61 አላህም ፡ ሰዎችን ፡ በበደላቸው ፡
በያዛቸው ፡ ኖሮ ፡ በርሷ ፡ (በም
ድር) ፡ ላይ ፡ ከተንቀሳቃሽ ፡ ምን
ንም ፡ ባልተወ ፡ ነበር ፤ ግን ፡
እስከ ፡ ተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡
ያቆያቸዋል ፤ ጊዜያቸውም ፡ በ
መጣ ፡ ወቅት ፡ አንዲትን ፡ ሰዓት ፡
አይቆዩም ፤ አይቀደሙምም ።
62 ለአላህም ፡ የሚጠሉትን ፡ ነገር ፡
ያደርጋሉ ፡ (1) ለነሱም ፡ መልካ
ሚቱ ፡ (አገር) ፡ አለቻቸው ፡ በማ
ለት ፡ ምላሶቻቸው ፡ ውሸትን ፡
ይናገራሉ ፤ ለነሱ ፡ እሳት ፡ ያለቻ
ቸው ፡ መኾናቸውና ፡ እነሱም ፡
(ወደርሷ) ፡ በቅድሚያ ፡ የሚነዱ ፡
መኾናቸው ፡ ጥርጥር ፡ የለበትም ።
63 በአላህ ፡ እንምላለን ፡ ካንተ ፡
በፊት ፡ ወደ ፡ ነበሩት ፡ ሕዝቦች ፡
በእርግጥ ፡ (መልክተኞችን) ፡
ልከናል ፤ ሰይጣንም ፡ ለነርሱ ፡
ሥራዎቻቸውን ፡ ሸለመላቸው ፤
እርሱም ፡ ዛሬ ፡ ረዳታቸው ፡ ነው ፤

1 ሴት ፡ ልጅ ፡ ተጋሪዎች ፡ አለው ፡ ይላሉ ።

ለነሱም ፡ (ኋላ) ፡ አሳማሚ ፡
ቅጣት ፡ አላቸው ።
64 ባንተም ፡ ላይ ፡ መጽሐፉን ፡ አላ
ወረድንም ፤ ያንን ፡ በርሱ ፡ የተለ
ያዩበትን ፡ ለነርሱ ፡ ልታብራራላ
ቸውና ፡ ለሚያምኑትም ፡ ሕዝ
ቦች ፡ መሪና ፡ እዝነት ፡ ሊኾን ፡
እንጂ ።
65 አላህም ፡ ከሰማይ ፡ ውሃን ፡ አወ
ረደ ፤ በርሱም ፡ ምድርን ፡ ከሞ
ተች ፡ በኋላ ፡ ሕያው ፡ አደረገ ፤
በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ለሚሰሙ ፡ ሕዝበ
ች ፡ በእርግጥ ፡ ታምር ፡ አልለ ።
66 ለናንተም ፡ በግመል ፡ በከብት ፡
በፍየል ፡ በእርግጥ ፡ መገምገሚያ ፡
አልላችሁ ፤ በሆዶቹ ፡ ውስጥ ፡
ካለው ፡ ከፈርስና ፡ ከደም ፡ መካ
ከል ፡ ጥሩ ፡ ወተትን ፡ ለጠጪ
ዎች ፡ ተዋጭ ፡ ሲኾን ፡ እናጠጣ
ችኋለን ።
67 ከዘምባባዎችና ፡ ከወይኖችም ፡
ፍሬዎች ፡ (እንመግባችኋለን) ፤
ከርሱ ፡ ጠጅንና ፡ መልካም ፡ ምግ
ብንም ፡ ትሠራላችሁ ። በዚህም ፡
ውስጥ ፡ ለሚያስቡ ፡ ሕዝቦች ፡
በእርግጥ ፡ ታምር ፡ አልለ ።
68 ጌታህም ፡ ወደ ፡ ንብ ፡ እንዲህ ፡
ሲል ፡ አስታወቀ ፡— ከተራራ
ዎች ፡ ከዛፍም ፡ (ሰዎች) ፡ ከሚሠ
ሩትም ፡ (ቀፎ) ፡ ቤቶችን ፡ ያዝ ።
69 ከዚያም ፡ ከፍሬዎች ፡ ሁሉ ፡ ብይ፤
የጌታሽንም ፡ መንገዶች ፡ (ላንቺ)፡
የተገሩ ፡ ሲኾኑ ፡ ግቢ ፤ ከሆዶ
ችዋ ፡ መልኮቹ ፡ የተለያዩ ፡ መ
ጠጥ ፡ ይወጣል ፤ በርሱ ፡ ውስጥ ፡
ለሰዎች ፡ መድኀኒት ፡ አለበት ፤
በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ለሚያስተነትኑ ፡
ሕዝቦች ፡ በእርግጥ ፡ ታምር ፡ አለ
በት ።

70 አላህም ፡ ፈጠራችሁ ፤ ከዚያም ፡
ይገድላችኋል ፤ ከናንተም ፡ ከዕው
ቀት ፡ በኋላ ፡ ምንንም ፡ ነገር ፡
እንዳያውቅ ፡ ወደ ፡ ወራዳ ፡
ዕድሜ ፡ የሚመለስ ፡ ሰው ፡ አልለ፤
አላህ ፡ ዐዋቂ ፡ ቻይ ፡ ነው ።
71 አላህም ፡ ከፊላችሁን ፡ በከፊሉ ፡
ላይ ፡ በሲሳይ ፡ አበለጠ ፤ እነዚ
ያም ፡ በላጭ ፡ የተደረጉት ፡ ሲሳያ
ቸውን ፡ እጆቻቸው ፡ በያዙዋ
ቸው ፡ (ባሮች)፡ ላይ ፡ እነሱ ፡
በርሱ ፡ ይተካከሉ፡ ዘንድ ፡ መላ
ሾች ፡ አይደሉም ፤ (1) ታዲያ ፡
በአላህ ፡ ጸጋ ፡ (ለርሱ ፡ ተጋሪ ፡
በማድረግ) ፡ ይክዳሉን ?
72 አላህም ፡ ከነፍሶቻችሁ ፡ (ከጐሶ
ቻችሁ) ፡ ለናንተ ፡ ሚስቶችን ፡
አደረገ ፤ ለናንተም ፡ ከሚስቶቻ
ችሁ ፡ ወንዶች ፡ ልጆችን ፡ የልጅ ፡
ልጆችንም ፡ አደረገላችሁ ፤ ከመል
ካሞችም ፡ ጸጋዎች ፡ ሰጣችሁ ፤
ታዲያ ፡ በውሸት ፡ (በጣዖት) ፡
ያምናሉን ? በአላህም ፡ ጸጋ ፡
እነሱ ፡ ይክዳሉን ?
73 ከአላህም ፡ ሌላ ፡ ከሰማያትም ፡
ከምድርም ፡ ምንንም ፡ ሲሳይ ፡
የማይሰጧቸውን ፡ (ምንንም) ፡
የማይችሉትንም ፡ ይግገዛሉ ።
74 ለአላህም ፡ አምሳያዎችን ፡ አታድ
ርጉ ፤ አላህ ፡ (መሳይ ፡ እንደሌ
ለው) ፡ ያውቃል ፤ እናንተ ፡ ግን ፡
አታውቁም ።
75 በምንም ፡ ላይ ፡ የማይችለውን ፡
በይዞታ ፡ ያለውን ፡ ባሪያና ፡ ከኛ ፡
መልካም ፡ ሲሳይን ፡ የሰጠነውን ፡
እርሱም ፡ ከርሱ ፡ (ከሰጠነው) ፡
በምስጢርና ፡ በግልጽ ፡ የሚለግስ

1 በሲሳያቸው ፡ አገልጋዮቻቸውን ፡ አያጋሩ
ዋቸውም ።



ውን ፡ (ነጻ) ፡ ሰው ፡ አላህ ፡ (ለጣ
ዖትና ፡ ለርሱ) ፡ ምሳሌ ፡ አደረገ ፤
(ሁለቱ) ፡ ይተካከላሉን ? ምስ
ጋና ፡ ለአላህ ፡ ይኹን ፤ በውነቱ፡
አብዛኞቻቸው ፡ አያውቁም ።
76 አላህም ፡ ሁለትን ፡ ወንዶች ፡
(ለከሓዲና ፡ ለምእመናን) ፡ ምሳሌ
አደረገ ፤ አንደኛቸው ፡ በምንም ፡
ነገር ፡ ላይ ፡ የማይችል ፡ ዲዳ ፡
ነው ፤ እርሱም ፡ በጌታው ፡ ላይ ፡
ሸክም ፡ ነው ፤ ወደ ፡ የትም ፡ ቢያ
ዞረው ፡ በደግ ፡ ነገር ፡ አይመጣም፤
እርሱና ፡ ያ ፡ እርሱ ፡ በቀጥተኛው
መንገድ ፡ ላይ ፡ ኾኖ በማስተካ
ከል ፡ የሚያዘው ፡ ሰው ፡ ይስተካ
ከላሉን ?
77 በሰማያትና ፡ በምድርም ፡ ያለው ፡
ሩቅ ፡ ምስጢር ፡ የአላህ ፡ ነው ፤
የሰዓቲቱም ፡ ነገር ፡ (መምጣቷ) ፡
እንደ ፡ ዓይን ፡ ቅጽበት ፡ እንጂ ፡
አይደለም ፤ ወይም ፡ እርሱ ፡ ይበ
ልጥ ፡ የቀረበ ፡ ነው ፤ አላህ ፡ በነ
ገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ።
78 አላህም ፡ ከናቶቻችሁ ፡ ሆዶች ፡
ምንም ፡ የማታውቁ ፡ ሆናችሁ ፡
አወጣችሁ ፤ ታመሰግኑም ፡ ዘንድ፡
ለናንተ ፡ መስሚያን ፡ ማያዎች
ንም ፡ ልቦችንም ፡ አደረገላችሁ ።
79 ወደ ፡ በራሪዎች ፡ በሰማይ ፡ አየር ፡
ውስጥ ፡ (ለመብረር) ፡ የተገሩ ፡
ሲኾኑ ፡ (ከመውደቅ) ፡ አላህ ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ የማይዛቸው ፡ ኾነው
አይመለከቱምን ? በዚህ ፡ ውስጥ ፡
ለሚያምኑ ፡ ሕዝቦች ፡ በእርግጥ ፡
ታምራቶች ፡ አልሉ ።
80 አላህም ፡ ከቤቶቻችሁ ፡ ለናንተ ፡
መርጊያን ፡ አደረገላችሁ ፤ ከእንስ
ሳዎችም ፡ ቆዳዎች ፡ በጉዟችሁ ፡
ቀን ፡ በመቀመጫችሁም ፡ ቀን ፡

የምታቀልሏቸውን ፡ (1) ቤቶች ፡
ለናንተ ፡ አደረገላችሁ ፤ ከበግዋ ፡
ሱፎች ፡ ከግመልዋም ፡ ጠጉሮች ፡
ከፍየልዋም ፡ ጠጉሮች ፡ የቤት ፡
ዕቃዎችን ፡ እስከ ፡ ጊዜም ፡ ድረስ፡
መጠቃቀሚያን ፡ (አደረገላችሁ) ።
81 አላህም ፡ ከፈጠረው ፡ ነገር ፡ ለና
ንተ ፡ ጥላዎችን ፡ አደረገላችሁ ፤
ከጋራዎችም ፡ ለናንተ ፡ መከከለያ
ዎችን ፡ አደረገላችሁ ፤ ሐሩርንም ፡
(ብርድንም) ፡ የሚጠብቋችሁን ፡
ልብሶች ፡ የጦራችሁንም ፡ አደጋ ፡
የሚጠብቋችሁን ፡ ጥሩሮች ፡ ለና
ንተ ፡ አደረገላችሁ ፤ እንደዚሁ ፡
ትሰልሙ ፡ ዘንድ ፡ ጸጋውን ፡ በና
ንተ ፡ ላይ ፡ ይሞላል ።
82 (ከኢስላም)፡ ቢሸሹም ፡ ባንተ ፡
ላይ ፡ ያለብህ ፡ ግልጽ ፡ ማድረስ ፡
ብቻ ፡ ነው ።
83 የአላህን ፡ ጸጋ ፡ ያውቃሉ ፤ ከዚ
ያም ፡ ይክዷታል ፤ አብዛኞቻቸ
ውም ፡ ከሓዲዎቹ ፡ ናቸው ።
84 ከየሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ መስካሪን ፡
የምንቀሰቅስበትን ፡ ቀን ፡ (አስታ
ውስ) ፤ ከዚያም ፡ ለነዚያ ፡ ለካ
ዱት ፡ (ንግግር) ፡ አይፈቀድላቸ
ውም ፤ እነሱም ፡ በወቀሳ ፡ አይታ
ለፉም ።
85 እነዚያም ፡ የበደሉት ፡ ቅጣቱን ፡
ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከነሱ ፡ (ቅጣቱ) ፡ አይ
ቀለልላቸውም ፤ እነሱም ፡ ጊዜ ፡
አይሰጡም ።
86 እነዚያም ፡ ያጋሩት ፡ የሚያጋሩዋ
ቸውን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡
ሆይ ፡ እነዚህ ፡ ከአንተ ፡ ሌላ ፡
እንግገዛቸው ፡ የነበርነው ፡ ተጋሪ
ዎቻችን ፡ ናቸው ፡ ይላሉ ፤ (አማል

1 ቀላል ፡ ኾነው ፡ የምታገኙዋቸውን ፡ ድን
ኳኖች ።

ክቶቹ) ፡ እናንተ ፡ በእርግጥ ፡ ውሸ
ታሞች ፡ ናችሁ ፡ የማለትንም ፡
ቃል ፡ ወደነሱ ፡ ይጥላሉ ።

87 (አጋሪዎቹ) ፡ በዚያ ፡ ቀንም ፡ ታዛ
ዥነታቸውን ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ያቀ
ርባሉ ፤ ይቀጣጥፉት ፡ የነበሩትም፡
ሁሉ ፡ ከነርሱ ፡ ይጠፉቸዋል ።

88 እነዚያ ፡ የካዱ ፡ ከአላህም ፡ መን
ገድ ፡ የከለከሉ ፡ ያጠፉ ፡ በነበ
ሩት ፡ ምክንያት ፡ ቅጣትን ፡ በቅ
ጣት ፡ ላይ ፡ ጨመርንባቸው ።

89 በየሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ውስጥ ፡ ከጐ
ሳቸው ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ መስካሪን ፡
የምንቀሰቅስበትን ፡ አንተንም ፡
በነዚህ ፡ (ሕዝቦች) ፡ ላይ ፡ መስ
ካሪ ፡ አድርገን ፡ የምናመጣህን ፡
ቀን ፡ (አስታውስ) ፤ መጽሐፉ
ንም ፡ ለሁሉ ፡ ነገር ፡ አብራሪ ፡
መሪም፡ እዝነትም፥ ለሙስሊሞ
ችም፡ አብሳሪ፡ ኾኖ፡ ባንተ፡ ላይ፡
አወረድነው።

90 አላህ ፡ በማስተካከል ፡ በማሳመ
ርም ፡ ለዝምድና ፡ ባለ ፡ ቤት ፡
በመስጠትም ፡ ያዛል ፤ ከአስከ
ፊም ፡ (ከማመንዘር) ፡ ከሚጠ
ላም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከመበደልም ፡
ይከለክላል ፤ ትገነዘቡ ፡ ዘንድ ፡
ይገሥጻችኋል ።

91 ቃል ፡ ኪዳንም ፡ በገባችሁ ፡ ጊዜ ፡
በአላህ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሙሉ ፤
መሓሎቻችሁንም ፡ ከአጠነከራች
ኋት ፡ በኋላ ፡ አላህን ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ በእርግጥ ፡ መስካሪ ፡ ያደረጋ
ችሁ ፡ ስትኾኑ ፡ አታፍርሱ ፤
አላህ ፡ የምትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡
ያውቃልና ።

92 (ቃል ፡ ኪዳናችሁን ፡ በማፍረስ ፡
እንዲቱ) ፡ ሕዝብ ፡ እርሷ ፡ ከ(ሌላ
ይቱ) ፡ ሕዝብ ፡ የበዛች ፡ ለመኾ
ንዋ ፡ በመካከላችሁ ፡ መሓሎቻች
ሁን ፡ (ለክዳት) ፡ መግቢያ ፡ አድ
ርጋችሁ ፡ የምትይዙ ፡ ስትኾኑ ፡
እንደዚያች ፡ ፈትልዋን ፡ ከጠነ
ከረ ፡ በኋላ ፡ ትርትሮች ፡ አድርጋ ፡
እንዳፈረሰችው ፡ (ሴት) ፡ አት
ኹኑ። አላህ ፡ በርሱ ፡ (1) ይሞክራ
ችኋል ፤ በትንሣኤ ፡ ቀንም ፡ በርሱ
ትለያዩበት ፡ የነበራችሁትን ፡
ነገር ፡ ለናንተ ፡ በእርግጥ ፡ ያብራ
ራላችኋል ።

93 አላህም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ አንዲት ፡
ሕዝብ ፡ ባደረጋችሁ ፡ ነበር ፤ ግን ፡
የሚሻውን ፡ ሰው ፡ ያጠማል ፤
የሚሻውንም ፡ ሰው ፡ ያቀናል ፤
ትሠሩት ፡ ከነበራችሁትም ፡ ሁሉ፡
በእርግጥ ፡ ትጠየቃላችሁ ።

94 መሓላዎች ፡ ከተደላደሉ ፡ በኋላ ፡
እንዳይንዳለጡ ፡ ከአላህም ፡ መን
ገድ ፡ በመከልከላችሁ ፡ ምክን
ያት ፡ ቅጣትን ፡ እንዳትቀምሱ ፡
መሓሎቻችሁን ፡ በመካከላችሁ ፡
ለክዳት ፡ መግቢያ ፡ አድርጋችሁ ፡
አትያዙ ፤ ለናንተም ፡ (ያን ፡ ጊዜ) ፡
ታላቅ ፡ ቅጣት ፡ አላችሁ ።

95 በአላህም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ጥቂ
ትን ፡ ዋጋ ፡ አትግዙ ፤ የምታ
ውቁ ፡ ብትኾኑ ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡
ያለው ፡ ምንዳ ፡ እርሱ ፡ ለናንተ ፡
በላጭ ፡ ነውና ።

96 እናንተ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡
ያልቃል ፤ አላህ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡
ግን ፡ (ዘለዓለም) ፡ ቀሪ ፡ ነው ፤
እነዚያንም ፡ የታገሡትን ፡ ይሠ
ሩት ፡ በነበሩት ፡ በመልካሙ ፡
ምንዳቸውን ፡ እንመነዳቸዋለን ።

97 ከወንድ ፡ ወይም ፡ ከሴት ፡ እርሱ ፡
አማኝ ፡ ኾኖ ፡ በጎን ፡ የሠራ ፡

---
1 ቃል ፡ ኪዳንን ፡ በመሙላት፡ በማዘዙ ።



መልካም ፡ ኑሮን ፡ በእርግጥ ፡ እና
ኖረዋለን ፤ ይሠሩትም ፡ ከነበሩት ፡
ነገር ፡ በመልካሙ ፡ ምንዳቸውን ፡
እንመነዳቸዋለን ።

98 ቁርአንንም ፡ ባነበብህ ፡ ጊዜ ፡
ርጉም ፡ ከኾነው ፡ ሰይጣን ፡ በአ
ላህ ፡ ተጠበቅ ፤

99 እርሱ ፡ በነዚያ ፡ ባመኑትና ፡ በጌ
ታቸው ፡ ላይ ፡ በሚጠጉት ፡ ላይ ፡
ለርሱ ፡ ሥልጣን ፡ የለውምና ።

100 ሥልጣኑ ፡ በነዚያ ፡ በሚታዘዙት፡
ላይና ፡ በነዚያም ፡ እነርሱ ፡ በርሱ
(ምክንያት) ፡ አጋሪዎች ፡ በኾ
ኑት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

101 በአንቀጽም ፡ ስፍራ ፡ አንቀጽን ፡
በለወጥን ፡ ጊዜ ፡ አላህም ፡ የሚያ
ወርደውን ፡ ነገር ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፤
አንተ ፡ ቀጣፊ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይ
ደለህም ፡ ይላሉ ፤ በውነቱ ፡ አብዛ
ኞቻቸው ፡ አያውቁም ።

102 እነዚያን ፡ ያመኑትን ፡ ለማረጋ
ጋት ፡ ሙስሊሞቹንም፡ ለመምራ
ትና ፡ ለማብሰር ፡ (ቁርአንን) ፡
ቅዱሱ ፡ መንፈስ ፡ (ጂብሪል) ፡
እውነተኛ ፡ ሲኾን ፡ ከጌታህ ፡ አወ
ረደው ፡ በላቸው ።

103 እነሱም ፡ እርሱን ፡ (ቁርአንን) ፡
የሚያስተምረው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡
ነው ፡ ማለታቸውን ፡ በእርግጥ ፡
እናውቃለን ፤ የዚያ ፡ ወደርሱ ፡
የሚያስጠጉበት ፡ ሰው ፡ ቋንቋ ፡
ዐጀም ፡ ነው ፤ (1) ይህ ፡ (ቁር
አን) ፡ ግን ፡ ግልጽ ፡ ዐረብኛ ፡
ቋንቋ ፡ ነው ።

104 እነዚያን ፡ በአላህ ፡ አንቀጾች ፡
የማያምኑትን ፡ አላህ ፡ አይመራቸ
ውም ፤ ለነሱም ፡ አሳማሚ ፡
ቅጣት ፡ አላቸው ።

105 ውሸትን ፡ የሚቀጣጥፉት ፡ እነዚያ ፡
በአላህ ፡ አንቀጾች ፡ የማያምኑት ፡
ብቻ ፡ ናቸው ፤ እነዚያም ፡ ውሸታ
ሞቹ ፡ እነሱ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

106 ከእምነቱ ፡ በኋላ ፡ በአላህ ፡ የካደ ፡
ሰው ፡ (ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ አል
ለው) ፤ ልቡ ፡ በእምነት ፡ የረጋ፡
ኾኖ ፡ (በክሕደት ፡ ቃል ፡ በመና
ገር) ፡ የተገደደ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡
ሲቀር ፤ ግን ፡ ልባቸውን ፡ በክሕ
ደት ፡ የከፈቱ ፡ ሰዎች ፡ በነሱ ፡
ላይ ፡ ከአላህ ፡ ቁጣ ፡ አልለባ
ቸው ፤ ለነሱም ፡ ታላቅ ፡ ቅጣት ፡
አልላቸው ።

107 ይህ ፡ (ቅጣት) ፡ እነሱ ፡ ቅርቢ
ቱን ፡ ሕይወት ፡ ከመጨረሻይቱ ፡
በመምረጣቸው ፡ ምክንያትና ፡
አላህም ፡ ከሓዲዎችን ፡ ሕዝቦች ፡
የማያቀና ፡ በመኾኑ ፡ ነው ።

108 እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ በልቦቻቸው ፡
በዓይኖቻቸውም፤ በጆሮዎቻቸ
ውም፤ ላይ፡ አላህ፡ ያተማባቸው፡
ናቸው ፤ እነዚያም ፡ ዝንጉዎቹ ፡
እነሱ ፡ ናቸው ።

109 እነርሱ ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ዓለም ፡
ከሳሪዎቹ ፡ እነሱ ፡ ለመኾናቸው ፡
ጥርጥር ፡ የለም ።

110 ከዚያም ፡ ጌታህ ፡ ለነዚያ ፡ ከተፈ
ተኑ ፡ በኋላ ፡ ለተሰደዱት ፡ ከዚ
ያም ፡ ለታገሉትና ፡ ለታገሡት ፡
(መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው) ፤ ጌታህ ፡
ከርሷ ፡ (ከፈተናዋ) ፡ በኋላ ፡ በእር
ግጥ ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።

111 ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ ከራሷ ፡ ላይ ፡ የምት
ከራከር ፡ ኾና ፡ የምትመጣበትን ፡
ነፍስም ፡ ሁሉ ፡ የሠራችውን ፡
(ዋጋ) ፡ የምትቀበልበትን ፡ ቀን
(አስታውስ) ፤ እነርሱም ፡ አይበ
ሉም ።

---
1 ከዐረብኛ ፡ ሌላ ፡ የኾነ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ።

112 አላህ ፡ጸጥተኛ ፡ የረካች ፡ሲሳ
ይዋ ፡ ሰፊ ፡ ኾኖ ፡ ከየሥፍራው ፡
ይመጣላት ፡ የነበረችውንና ፡ በአ
ላህ ፡ ጸጋዎች ፡ የካደችውን ፡ አላ
ህም ፡ ይሠሩት ፡ በነበሩት ፡ ኃጢ
አት ፡ የረኃብንና ፡ የፍርሃትን ፡
ቅጣቶች ፡ ያቀመሳትን ፡ ከተማ ፡
(መኮን) ፡ ምሳሌ ፡ አደረገ ።
113 ከነርሱ ፡ ውስጥ ፡ የኾነ ፡ መልክ
ተኛም ፡ በእርግጥ ፡ መጣላቸው ፤
አስተባበሉትም ፤ እነሱም ፡ በዳ
ዮች ፡ ኾነው ፡ ቅጣቱ ፡ ያዛቸው ።
114 አላህም ፡ ከሰጣችሁ ፡ ሲሳይ ፡
የተፈቀደ ፡ ንጹሕ ፡ ሲኾን ፡ ብሉ ፤
የአላህንም ፡ ጸጋ ፡ እርሱን ፡ የምት
ግገዙት ፡ ብትኾኑ ፡ አመስግኑ ።
115 በናንተ ፡ ላይ ፡ እርም ፡ ያደረገው ፡
በክትንና ፡ ደምን ፡ የአሳማንም ፡
ሥጋ ፡ ያንንም ፡ (በመታረድ ፡
ጊዜ) ፡ በርሱ ፡ ከአላህ ፡ ስም ፡
ሌላ ፡ የተነሳበትን ፡ ብቻ ፡ ነው ፤
አመጠኛም ፡ ወሰን ፡ አላፊም ፡
ሳይኾን ፡ (ለመብላት) ፡ የተገደደ ፡
ሰው ፡ (ይፈቀድለታል) ፤ አላህ ፡
መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።
116 በአላህም ፡ ላይ ፡ ውሸትን ፡ ልትቀ
ጣጥፉ ፡ ምላሶቻችሁ ፡ በሚመጥ
ኑት ፡ ውሸት ፡- ይህ ፡ የተፈቀደ ፡
ነው ፤ ይህም ፡ እርም ፡ ነው ፡ አት
በሉ ፤ እነዚያ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡
ውሸትን ፡ የሚቀጣጥፉ ፡ አይድ
ኑም ።
117 ጥቂት ፡ መጣቀም ፡ አላቸው ፡
ለነሱም ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡
አላቸው ።
118 በነዚያም ፡ ይሁዳውያን ፡ በኾ
ኑት ፡ ላይ ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡ በአ
ንተ ፡ ላይ ፡ የተረክነውን ፡ ነገር ፡
እርም ፡ አድርገንባቸዋል ፤ እኛም ፡
አልበደልናቸውም ፤ ግን ፡ ነፍሶቻ
ቸውን ፡ ይበድሉ ፡ ነበሩ ።
119 ከዚያም ፡ ጌታህ ፡ ለነዚያ ፡ በስሕ
ተት ፡ መጥፎን ፡ ለሠሩና ፡ ከዚ
ያም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለተጸጸቱ ፡
ሥራቸውንም ፡ ላበጁ ፡ ጌታህ ፡
ከርሷ ፡ በኋላ ፡ በእርግጥ ፡ መሐሪ ፡
አዛኝ ፡ ነው ።
120 ኢብራሂም ፡ ለአላህ ፡ ታዛዥ ፡
ወደ ፡ ቀጥተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ተዘን
ባይ ፡ ሕዝብ ፡ ነበር ፤ ከአጋሪዎ
ቹም ፡ አልነበረም ።
121 ለጸጋዎቹ ፡ አመስጋኝ ፡ ነበር ፤
መረጠው ፤ ወደ ፡ ቀጥተኛውም ፡
መንገድ ፡ መራው ።
122 በቅርቢቱም ፡ ዓለም ፡ በጎን ፡
ነገር ፡ ሰጠነው ፤ እርሱም ፡ በመ
ጨረሻይቱ ፡ ዓለም ፡ በእርግጥ ፡
ከመልካሞቹ ፡ ነው ።
123 ከዚያም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ የኢብራሂ
ምን ፡ ሃይማኖት ፡ ቀጥተኛ ፡ ሲ
ኾን ፡ ተከተል ፤ ከአጋሪዎቹም ፡
አልነበረም ፡ ማለትን ፡ አወረድን ።
124 ሰንበት ፡ (ክልክል) ፡ የተደረገው ፡
በነዚያ ፡ በርሱ ፡ በተለያዩበት ፡
ሰዎች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ጌታ
ህም ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ይለያዩ
በት ፡ በነበሩት ፡ ነገር ፡ በመካከላ
ቸው ፡ በእርግጥ ፡ ይፈርዳል ።
125 ወደ ፡ ጌታህ ፡ መንገድ ፡ በብልሃ
ትና ፡ በመልካም ፡ ግሣጼ ፡ (በለዘ
ብታ ፡ ቃል) ፡ ጥራ ፤ በዚያችም ፡
እርሷ ፡ መልካም ፡ በኾነችው ፡
(ዘዴ) ፡ ተከራከራቸው ፤ ጌታህ ፡
እርሱ ፡ ከመንገዱ ፡ የተሳሳተውን ፡
ሰው ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፤ እርሱም ፡
ቅን ፡ የኾኑትን ፡ ሰዎች ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።



126 ብትበቀሉም ፡ በርሱ ፡ በተቀጣች
ሁበት ፡ ብጤ ፡ ተበቀሉ ፤ ብትታገ
ሡም ፡ እርሱ ፡ ለታጋሾች ፡ በእ
ርግጥ ፡ በላጭ ፡ ነው ።
127 ታገሥም ፤ መታገሥህም ፡ በአ
ላህ ፡ (ማስቻል) ፡ እንጂ ፡ አይደ
ለም ፤ በነርሱም ፡ ላይ ፡ (ባያምኑ) ፡
አትተክዝ ፤ (ባንተ ፡ ላይ) ፡ ከሚ
መክሩትም ፡ ተንኮል ፡ በጭን
ቅት ፡ ውስጥ ፡ አትኹን ።
128 አላህ ፡ ከነዚያ ፡ ከሚፈሩትና ፡
ከነዚያም ፡ እነሱ ፡ መልካም ፡
ሠሪዎች ፡ ከኾኑት ፡ ጋር ፡ ነውና ።

## ምዕራፍ ፡ 17 ፡ አል-ኢስራእ ። ክፍል ፡ 15 ።

★ ★ ★

17ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ኢስራእ ፡ (የሌሊት ፡ ጉዞ ፡ ምዕራፍ) ፡ በ
መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 111 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 ያ ፡ ባሪያውን ፡ (1) ከተከበረው ፡
መስጊድ ፡ ወደዚያ ፡ ዙሪያውን ፡
ወደ ፡ ባረክነው ፡ ወደ ፡ሩቁ ፡
መስጊድ ፡ በሌሊት ፡ ውስጥ ፡ ያስ
ኼደው ፡ (ጌታ) ፡ ጥራት ፡ ይገ
ባው ፤ ከታምራቶቻችን ፡ ልናሳ
የው ፡ (አስኼድነው) ፤ እነሆ ፡
እርሱ ፡ (አላህ) ፡ ሰሚው ፡ ተመል
ካቹው ፡ ነው ።
2 ሙሳንም ፡ መጽሐፉን ፡ ሰጠነው ፤
ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ መሪ ፡
አደረግነው ፤ ከኔ ፡ ሌላ ፡ መጠጊ
ያን ፡ አትያዙ ፤ (አልናቸውም) ።
3 እላንተ ፡ ከኑሕ ፡ ጋር ፡ (በመርከ
ቢቱ) ፡ የጫናቸው ፡ ዘሮች ፡ ሆይ !
(አላህን ፡ ተገዙ) ፡ እርሱ ፡ በብዙ ፡
አመስጋኝ ፡ ባሪያ ፡ ነበርና ።
4 ወደ ፡ እስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በመ
ጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ (እንዲህ ፡ በማ
ለት) ፡ አወረድን ፤ በምድር ፡ ላይ ፡
በእርግጥ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ታጠፋላ
ችሁ ፤ ትልቅንም ፡ ኩራት ፡ ትኮራ
ላችሁ ፤
5 ከሁለቱ ፡ (ጊዜያቶች) ፡ የመጀመ
ሪያይቱ ፡ ቀጠሮ ፡ በመጣም ፡
ጊዜ ፡ ለኛ ፡ የኾኑን ፡ ባሮች ፡ የብ
ርቱ ፡ ኃይል ፡ ባለቤቶች ፡ የኾኑ
ትን ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ እንልካለን ፤
በቤቶችም ፡ መካከል ፡ ይመላለ
ሳሉ ፤ (ይበረብሩታል ፤ ይህ) ፡
ተፈጻሚ ፡ ቀጠሮም ፡ ነበር ።
6 ከዚያም ፡ (በኋላ) ፡ ለናንተ ፡
በነሱ ፡ ላይ ፡ ድልን ፡ መለስንላ
ችሁ ፡ በገንዘቦችና ፡ በወንዶች ፡
ልጆችም ፡ ጨመርንላችሁ ፤ በወገ
ንም ፡ የበዛችሁ ፡ አደረግናችሁ ።
7 መልካም ፡ ብትሠሩ ፡ ለነፍሶቻ
ችሁ ፡ መልካምን ፡ ሠራችሁ ፤
መጥፎንም ፡ ብትሠሩ ፡ በነርሱ ፡
(በነፍሶቻችሁ)፡ ላይ ፡ ነው ፤
(አልን) ፤ የኋለኛይቱም ፡ (ጊዜ) ፡

1 ሙሐመድን ።

ቀጠሮ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ፊቶቻች
ሁን ፡ ሊያስከፉ ፡ መስጊዱንም ፡
በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡
ገቡት ፡ ሊገቡ ፡ ያሸነፉትንም ፡
ሁሉ ፡ (ፈጽመው) ፡ ማጥፋትን ፡
እንዲያጠፉ ፡ (እንልካቸዋለን) ።
8 (በመጽሐፉም ፡ አልን ፡ ብትጸ
ጸቱ) ፡— ጌታችሁ ፡ ሊያዝንላ
ችሁ ፡ ይከጀላል ፤ (ወደ ፡ ማጥ
ፋት) ፡ ብትመለሱም ፡ እንመለሳ
ለን ፤ ገሀነምንም ፡ ለከሓዲዎች ፡
ማሰሪያ ፡ አድርገናል ።
9 ይህ ፡ ቁርአን ፡ ወደዚያች ፡ እርሷ ፡
ቀጥተኛ ፡ ወደ ፡ ኾነችው ፡ መን
ገድ ፡ ይመራል ፤ እነዚያንም ፡
በጎ ፡ የሚሠሩትን ፡ ምእመናን ፡
ለነሱ ፡ ታላቅ ፡ ምንዳ ፡ ያላቸው ፡
መኾኑን ፡ ያበስራል ።
10 እነዚያም ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ዓ
ለም ፡ የማያምኑት ፡ ለነሱ ፡ አሳ
ማሚ ፡ ቅጣትን ፡ አዘጋጅተንላ
ቸዋል ፤
11 ሰው ፡ መልካምን ፡ ነገር ፡ እንደ
ሚለምን ፡ ሁሉ ፤ መጥፎንም ፡
ነገር ፡ ይለምናል ፤ ሰውም ፡
ቸኳላ ፡ ነው ።
12 ሌሊትንና ፡ ቀንንም ፡ (ለችሎታ
ችን) ፡ ምልክቶች ፡ አደረግን ፤
የሌሊትን ፡ ምልክትም ፡ አበስን ፤
የቀንን ፡ ምልክትም ፡ የምታሳይ ፡
አደረግን ፤ (ይህም ፡ የኾነበት) ፡
ከጌታችሁ፡ ትርፍን፡ ልትፈልጉ፡
የዓመታትንም፡ ቁጥርና፡ ሒሳብን
ም፡ ታውቁ፡ ዘንድ፡ ነው፤ ነገሩንም፡
ሁሉ፡ ለያይተን፡ ዘረዘርነው።
13 ሰውንም ፡ ሁሉ ፡ በራሪውን ፡
(ሥራውን) ፡ በአንገቱ ፡ አስያዝ
ነው ፤ ለርሱም ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡
የተዘረጋ ፡ ኾኖ ፡ የሚያገኘው ፡
የኾነን ፡ መጽሐፍ ፡ እናወጣለታ
ለን ።
14 መጽሐፍህን ፡ አንብብ ፤ ዛሬ ፡
ባንተ ፡ ላይ ፡ ተቆጣጣሪነት ፡ በነ
ፍስህ ፡ በቃ ፡ (ይባላል) ።
15 የተመራ ፡ ሰው ፡ የሚመራው ፡
ለራሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ የተሳሳተም ፡
ሰው ፡ የሚሳሳተው ፡ (ጉዳቱ) ፡
በርሷ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ ተሸካሚም ፡
(ነፍስ) ፡ የሌላይቱን ፡ ኃጢአት ፡
አትሸከምም ፤ መልክተኛንም ፡
እስከምንልክ ፡ ድረስ ፡ የምንቀጣ ፡
አይደለንም ።
16 ከተማንም ፡ ለማጥፋት ፡ በፈለ
ግን ፡ ጊዜ ፡ ባለ ፡ ጸጋዎችዋን ፡ እና
ዛለን ፤ በውስጧም ፡ ያምጣሉ ፤ በር
ሷም ፡ ላይ ፡ ቃሉ ፡ (ቅጣቱ) ፡
ይፈጸምባታል ፤ ማጥፋትንም ፡
እናጠፋታለን ።
17 ከኑሕም ፡ በኋላ ፡ ከክፍለ ፡ ዘመ
ናት ፡ ሰዎች ፡ ያጠፋናቸው ፡ ብዙ
ዎች ፡ ናቸው ፤ የባሮቹንም ፡ ኃጢ
አቶች ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡ ተመል
ካች ፡ መኾን ፡ በጌታህ ፡ በቃ ።
18 ቸኳይቱን ፡ ዓለም ፡ (በሥራው) ፡
የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡ በርሷ ፡
ውስጥ ፡ የሻነውን ፡ (ጸጋ) ፡ ለምን
ሻው ፡ ሰው ፡ እናስቸኩልለታ
ለን ፤ ከዚያም ፡ ለርሱ ፡ ገሀነምን ፡
(መኖሪያ) ፡ አድርገንለታል ፤ ተወ
ቃሽ ፡ ብራሪ ፡ ኾኖ ፡ ይገባታል ።
19 መጨረሻይቱንም ፡ ዓለም ፡ የፈ
ለገ ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡ አማኝ ፡ ኾኖ ፡
ለርሷ ፡ (ተገቢ) ፡ ሥራዋን ፡ የሠ
ራም ፡ ሰው ፡ እነዚህ ፡ ሥራቸው ፡
የተመሰገነ ፡ ይኾናል ።
20 ሁሉንም ፡ እነዚህንና ፡ እነዚያን ፡
ከጌታህ ፡ ስጦታ ፡ (በዚህ ፡ ዓ
ለም) ፡ እንጨምርላቸዋለን ፤ የጌ



ታህም ፡ ስጦታ ፡ (በዚች ፡ ዓለም)፡
ክልክል ፡ አይደለም ።
21 ከፊላቸውን ፡ በከፊሉ ፡ ላይ ፡ እን
ዴት ፡ እንዳበለጥን ፡ ተመልከት ፤
የመጨረሻይቱም ፡ አገር ፡ በማዕረ
ጎች ፡ በጣም ፡ የከበረችና ፡ በመብ
ለጥም ፡ የተለቀች ፡ ናት ።
22 ከአላህ ፡ ጋር ፡ ሌላን ፡ አምላክ ፡
አታድርግ ፤ የተወቀስክ ፡ ረዳት ፡
የሌለህ ፡ ትኾናለህና ፤
23 ጌታህም ፡ (እንዲህ ፡ ሲል) ፡
አዘዘ ፤— እርሱን ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡
አትገዙ ፤ በወላጆቻችሁም ፡ መል
ካምን ፡ ሥሩ ፤ በአንተ ፡ ዘንድ ፡
ኾነው ፡ አንዳቸው ፡ ወይም ፡ ሁለ
ታቸው ፡ እርጅናን ፡ ቢደርሱ ፡
ፎሀ ፡ አትበላቸው ፤ አትገላምጣ
ቸውም ፤ ለነርሱም ፡ መልካምን ፡
ቃል ፡ ተናገራቸው ።
24 ለሁለቱም ፡ ከእዝነትህ ፡ የመዋረ
ድን ፡ ክንፍ ፡ ዝቅ ፡ አድርግላቸው ፤
ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ በሕጻንነቴ ፡ (በር
ኅራሄ) ፡ እንዳሳደጉኝ ፡ እዘንላቸ
ውም ፡ በል ።
25 ጌታችሁ ፡ በነፍሶቻችሁ ፡ ውስጥ ፡
ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
ታዛዦችም ፡ ብትኾኑ ፡ (በመሳሳ
ትም ፡ ብታጠፉ) ፡ እርሱ ፡ ለተመ
ላሾች ፡ መሓሪ ፡ ነው ።
26 ለዝምድና ፡ ባለቤትም ፡ መብ
ቱን ፡ ስጥ ፤ ለምስኪንና ፡ ለመን
ገደኛም ፡ (ስጥ) ፤ ማባከንንም ፡
አታባክን ።
27 አባካኞች ፡ የሰይጣናት ፡ ወንድ
ሞች ፡ ናቸውና ፤ ሰይጣንም ፡ ለጌ
ታው ፡ ብርቱ ፡ ከሓዲ ፡ ነው ።
28 ከጌታህም ፡ የምትከጅላትን ፡
ጸጋ ፡ ለማጣት ፡ ከነርሱ ፡ ብት
ዞር ፡ ለነሱ ፡ ልዝብን ፡ ቃል ፡
ተናገራቸው ።
29 እጅህንም ፡ ወደ ፡ አንገትህ ፡ የታ
ሠረች ፡ አታድርግ ፤ መዘርጋት
ንም ፡ ሁሉ ፡ አትዘርጋት ፤ የተወቀ
ስክ ፡ የተቆጨህ ፡ ትኾናለህና ።
30 ጌታህ ፡ ሲሳይን ፡ ለሚሻው ፡
ሰው ፡ ያሰፋል ፤ ያጠባልም ፤
እርሱ ፡ በባሮቹ ፡ ኹኔታ ፡ ውስጠ፡
ዐዋቂ ፡ ተመልካች ፡ ነውና ።
31 ልጆቻችሁንም ፡ ድኽነትን ፡ ለመ
ፍራት ፡ አትግደሉ ፤ እኛ ፡ እንመ
ግባቸዋለን፤ እናንተንም፥ (እን
መግባለን) ፤ እነሱን ፡ መግደል ፡
ታላቅ ፡ ኃጢአት ፡ ነውና ።
32 ዝሙትንም ፡ አትቅረቡ ፤ እርሱ ፡
በእርግጥ ፡ መጥፎ ፡ ሥራ ፡ ነውና ፤
መንገድነቱም ፡ ከፋ !
33 ያቺንም ፡ አላህ ፡ ያወገዛትን ፡
ነፍስ ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ አትግደሉ ፤
የተበደለም ፡ ኾኖ ፡ የተገደለ ፡
ሰው ፡ ለዘመዱ ፡ (በገዳዩ ፡ ላይ) ፡
በእርግጥ ፡ ስልጣንን ፡ አድርገ
ናል ፤ በመግደልም ፡ ወሰንን ፡ አይ
ለፍ ፤ እርሱ ፡ የተረዳ ፡ ነውና ።
34 የየቲምንም ፡ ገንዘብ ፡ የብርታ
ቱን ፡ ጊዜ ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡
በዚያች ፡ እርሷ ፡ መልካም ፡ በኾ
ነች ፡ ኹኔታ ፡ እንጂ ፡ አትቅረቡ ፤
በኪዳናችሁም ፡ ሙሉ ፤ ኪዳን ፡
የሚጠየቁበት ፡ ነውና ።
35 በሰፈራችሁም ፡ ጊዜ ፡ ስፍርን ፡
ሙሉ፡ በትክክለኛው ፡ ሚዛንም ፡
መዝኑ ፤ ይህ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡
ነው ፤ መጨረሻውም ፡ ያማረ ፡
ነው ።
36 ለአንተም ፡ በርሱ ፡ ዕውቀት ፡
የሌለህን ፡ ነገር ፡ አትከተል ፤
መስሚያ ፡ ማያም ፡ ልብም ፡ እነ

ዚህ ፡ ሁሉ ፡ (ባለቤታቸው) ፡
ከነሱ ፡ ተጠያቂ ፡ ነውና ።
37 በምድርም ፡ ላይ ፡ የተንበጣረርክ ፡
ሆነህ ፡ አትኺድ ፤ አንተ ፡ ፈጽሞ ፡
ምድርን ፡ አትሰረጉድምና ፤ በርዝ
መትም ፡ ፈጽሞ ፡ ጋራዎችን ፡
አትደርስምና ።
38 ይህ ፡ ሁሉ ፡ (1) መጥፎው ፡ (2)
እጌታህ ፡ ዘንድ ፡ የተጠላ ፡ ነው ።
39 ይህ ፡ ጌታህ ፡ ከጥበቡ ፡ ወደ ፡
አንተ ፡ ካወረደው ፡ ነገር ፡ ነው ፤
ከአላህም ፡ ጋር ፡ ሌላን ፡ አምላክ ፡
አታድርግ ፤ የተወቀስክ ፡ የተባረ
ርክ ፡ ኾነህ ፡ በገሀነም ፡ ውስጥ ፡
ትጣላለህና ።
40 ጌታችሁ ፡ በወንዶች ፡ ልጆች ፡
መረጣችሁና ፡ ከመላእክት ፡ ሴቶ
ችን ፡ (ልጆች) ፡ ያዘን ? እናንተ ፡
ከባድን ፡ ቃል ፡ በእርግጥ ፡ ትናገ
ራላችሁ ።
41 ይገሠጹም ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ቁር
አን ፡ ውስጥ ፡ ደጋግመን ፡ በእር
ግጥ ፡ ገለጽን ፡ መበርገግንም ፡
እንጂ ፡ ሌላን ፡ አይጨምርላቸ
ውም ።
42 (ሙሐመድ ፡ ሆይ) ፡ በላቸው ፡—
እንደምትሉት ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ አማ
ልክት ፡ በነበሩ ፡ ኖሮ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡
ወደ ፡ ዐርሹ ፡ (3) ባለቤት ፡ መንገ
ድን ፡ በፈለጉ ፡ ነበር ።
43 ጥራት ፡ ይገባው ፤ ከሚሉትም ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ ያለን ፡ ልቅና ፡
ላቀ ።
44 ሰባቱ ፡ ሰማያትና ፡ ምድርም ፡
በውስጣቸውም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡
ለርሱ ፡ ያጠራሉ ፤ ከነገርም ፡
ሁሉ ፡ ከማመስገን ፡ ጋር ፡ የሚያ
ጠራው ፡ (1) እንጂ ፡ አንድም ፡
የለም ፤ ግን ፡ ማጥራታቸውን ፡
አታውቁትም ፤ እርሱ ፡ ታጋሽ ፡
መሓሪ ፡ ነው ።
45 ቁርአንንም ፡ ባነበብክ ፡ ጊዜ ፤
ባንተና ፡ በነዚያ ፡ በመጨረሻ
ይቱ ፡ ዓለም ፡ በማያምኑት ፡
ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚሸሽግን ፡
ግርዶሽ ፡ አድርገናል ።
46 እንዳያውቁትም ፡ በልቦቻቸው ፡
ላይ፡ ሽፋንን፥ በጆሮዎቻቸውም፡
ውስጥ ፡ ድንቁርናን ፡ አደረግን ፤
ጌታህንም ፡ ብቻውን ፡ ኾኖ ፡ በቁ
ርአን ፡ ባወሳኸው ፡ ጊዜ ፤ የሚ
ሸሹ ፡ ኾነው፡ በጀርባቻቸው፡
ላይ ፡ ይዞራሉ ።
47 እኛ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ በሚያዳምጡ፡
ጊዜ ፥ እነሱም ፡ የሚንሾካሾኩ፡
ጊዜ ፤ በዳዮች ፡ (እርስ ፡ በርሳ
ቸው) ፡ የተደገመበትን ፡ ሰው ፡
እንጂ ፡ አትከተሉም ፡ በሚሉ ፡
ጊዜ ፤ በርሱ ፡ የሚያዳምጡበትን ፡
ምክንያት ፡ ዐዋቂ ፡ ነን ።
48 ምሳሌዎችን ፡ ለአንተ ፡ እንዴት ፡
እንዳደረጉልህና ፡ (2) እንደ ፡ ተሳ
ሳቱ ፡ ተመልከት ፤ (ወደ ፡ እው
ነቱ ፡ ለመድረስ) ፡ መንገድንም ፡
አይችሉም ።
49 አሉም ፡— እንዴት ? አጥንቶችና ፡
ብስብሶች ፡ በኾን ፡ ጊዜ ፤ እኛ ፡
አዲስ ፡ ፍጥረት ፡ ኾነን ፡ በእር
ግጥ ፡ ተቀስቃሾች ፡ ነን?
50 በላቸው ፡— ድንጊያዎችን ፡ ወ
ይም ፡ ብረትን ፡ ኹኑ ፡

---

1 ከሃያ ፡ አምስቱ ፡ ጠባዮች ፡ ውስጥ ።
2 አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ክልክሎች ።
3 ወደ፡ ዙፋኑ።

1 የሚያወድሰው ።
2 የተደገመበት ፡ ነው ፡ ጠንቋይ ፡ ነው ፡
ገጣሚ ፡ ነው ፡ በማለት ።



51 ወይም ፡ በልቦቻችሁ ፡ ውስጥ ፡
የሚተልቅን ፡ ፍጥረት ፤ (ኹኑ ፤
መቀስቀሳችሁ ፡ አይቀርም) ፤
የሚመልሰንም ፡ ማነው ? ይላሉ ፤
ያ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የፈጠራ
ችሁ ፡ ነው ፤ በላቸው ፤ ወደ ፡ አን
ተም ፡ ራሶቻቸውን ፡ ይነቀንቃሉ ፤
እርሱም ፡ መቼ ፡ ነው ? ይላሉ ፤
(እርሱ) ፡ ቅርብ ፡ ሊኾንን ፡ ይቻ
ላል ፡ በላቸው ።
52 (እርሱም) ፡ የሚጠራችሁና ፡ (አላ
ህን) ፡ አመስጋኞቹ ፡ ኾናችሁ ፡
ጥሪውን ፡ የምትቀበሉበት ፤ ጥቂ
ትንም ፡ (ቀኖች) ፡ እንጂ ፡ ያልቆያ
ችሁ ፡ መኾናችሁን ፡ የምትጠራጠ
ሩበት ፡ ቀን ፡ ነው ፤ (በላቸው) ።
53 ለባሮቼም ፡ በላቸው ፡— ያችን ፡
እርሷ ፡ መልካም ፡ የኾነችውን ፡
(ቃል) ፡ ይናገሩ ፤ ሰይጣን ፡ በመካ
ከላቸው ፡ ያበላሻልና ፤ ሰይጣን ፡
ለሰው ፡ ግልጽ ፡ ጠላት ፡ ነውና ።
54 ጌታችሁ ፡ በናንተ ፡ (ኹኔታ) ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ፤ ቢሻ ፡ ያዝንላች
ኋል ፤ ወይም ፡ ቢሻ ፡ ይቀጣች
ኋል ፤ በነሱም ፡ ላይ ፡ ኃላፊ ፡
ኾነህ ፡ አላክንህም ። (አታስገድዳ
ቸውም) ።
55 ጌታህም ፡ በሰማያትና ፡ በምድር ፡
ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፤ ከፊ
ሉንም ፡ ነቢያት ፤ በከፊሉ ፡ ላይ ፡
በእርግጥ ፡ አብልጠናል ፤ ዳው
ድንም ፡ ዘቡርን ፡ ሰጥተነዋል ።
56 እነዚያን ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ (አማል
ክት) ፡ የምትሏቸውን ፡ ጥሩ ፤
ከናንተም ፡ ላይ ፡ጉዳትን ፡ ማስወ
ገድን ፡ (ወደ ፡ ሌላ) ፡ ማዞርንም ፤
አይችሉም ፡ በላቸው ።
57 እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ የሚግገዟቸው ፡
ማንኛቸውም ፡ (ወደ ፡ አላህ) ፡
በጣም ፡ ቀራቢያቸው ፡ ወደ ፡
ጌታቸው ፡ መቃረቢያን ፡ (ሥራ) ፡
ይፈልጋሉ ፤ እዝነቱንም ፡ ይከጀ
ላሉ ፤ ቅጣቱንም ፡ ይፈራሉ ፤ የጌ
ታህ ፡ ቅጣት ፡ የሚፈራ ፡ ነውና ።
58 አንዲትም ፡ ከተማ ፡ የለችም ፡
እኛ ፡ ከትንሣኤ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡
አጥፊዎችዋ ፤ ወይም ፡ ብርቱን ፡
ቅጣት ፡ ቀጭዎችዋ ፡ ብንኾን ፡
እንጂ ፡ ይህ ፡ በመጽሐፉ ፡ የተ
ጻፈ ፡ ነው ።
59 ታምራቶችንም ፡ ከመላክ ፤ የቀድ
ሞዎቹ፡ ሰዎች፡ በርሷ፡ ማስተባ
በልና ፡ (መጥፋት) ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡
አልከለከለንም ፤ ለሠሙድም ፡
ግመልን ፡ ግልጽ ፡ ታምር ፡ ኾና ፡
ሰጠናቸው ፤ በርሷም ፡ በደሉ ፤
ታምራቶችንም ፡ ለማስፈራራት ፡
እንጂ ፡ አንልክም ።
60 ላንተም ፡ ጌታህ ፡ (ዕውቀቱ) ፡ በሰ
ዎቹ ፡ ከበበ ፡ ባልንህ ፡ ጊዜ ፤ (አስ
ታውስ) ። ያችንም ፡ (በሌሊቱ ፡
ጉዞ ፡ በዓይንህ) ፡ ያሳየንህን ፡ ትር
ዕይት ፤ ለሰዎች ፡ ፈተና ፡ እንጂ ፡
አላደረግናትም ፤ በቁርአንም ፡
የተረገሙችውን ፡ ዛፍ ፤ (እንደዚሁ
ፈተና ፡ እንጂ ፡ አላደረግንም) ፤
እናስፈራራቸዋለንም ፤ ታላቅንም፡
ጥመት ፡ እንጂ ፡ አይጨምርላቸ
ውም ።
61 ለመላእክትም ፡ ለአደም ፡ ስገዱ ፡
ባልናቸው ፡ ጊዜ ፤ (አስታውስ) ፤
ወዲያውም ፡ ሰገዱ ፤ ኢብሊስ ፡
ብቻ ፡ ሲቀር ፤ ከጭቃ ፡ ለፈጠር
ከው ፡ ሰው ፤ እሰግዳለሁን? አለ ።
62 ንገረኝ ፤ ይህ ፡ ያ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ያበ
ለጥከው ፡ ነውን? እስከ ፡ ትንሣኤ ፡
ቀን ፡ ድረስ ፡ ብታቆየኝ ፤ ዘሮ
ቹን ፡ ጥቂቶች ፡ ሲቀሩ ፤ ወደ ፡

ስሕተት ፡ በእርግጥ ፡ እስባቸዋ
ለሁ ፡ አለ ።
63 (አላህም) ፡ አለው ፡— ኺድ ፤ ከነ
ሱም ፡ የተከተለህ ፡ ገሀነም ፡ የተ
ሟላች ፡ ቅጣት ፡ ስትኾን ፡ ፍዳ
ችሁ ፡ ናት ።
64 ከነሱ ፡ የቻልከውንም ፡ ሰው ፡
በድምጽህ ፡ አታል ፤ በነሱም ፡
ላይ ፡ በፈረሰኞችህ ፡ በእግረኞች
ህም ፡ ኾነህ ፡ ለልብ ፤ በገንዘቦቻ
ቸውም ፡ በልጆቻቸውም ፡ ተጋራ
ቸው ፤ ተስፋ ፡ ቃልም ፡ ግባላ
ቸው ፤ ሰይጣንም ፡ ማታለልን ፡
እንጂ ፡ ተስፋ ፡ ቃልን ፡ አይገባላ
ቸውም ።
65 ባሮቼ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ፈጽሞ ፡
ላንተ ፡ ስልጣን ፡ የለህም ፤ መጠ
ጊያም ፡ በጌታህ ፡ በቃ ።
66 ጌታችሁ ፡ ያ ፡ ከችሮታው ፡ ትፈ
ልጉ ፡ ዘንድ ፡ መርከቦችን ፡ በባ
ሕር ፡ ላይ ፡ ለናንተ ፡ የሚነዳላ
ችሁ ፡ ነው ፤ እነሆ ፡ እርሱ ፡ ለና
ንተ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።
67 በባሕሩም ፡ ውስጥ ፡ ጉዳት ፡ ባገ
ኛችሁ ፡ ጊዜ ፡ የምትጠሩዋቸው ፡
(አማልክት) ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ (ከአ
ላህ) ፡ በቀር ፡ ይጠፋሉ ፡ ወደ ፡
የብስም ፡ በማድረስ ፡ ባዳናችሁ ፡
ጊዜ ፡ (እምነትን) ፡ ትተዋላችሁ ፤
ሰውም ፡ በጣም ፡ ከሓዲ ፡ ነው ።
68 የየብሱን ፡ በኩል ፡ (ምድርን) ፡
በናንተ ፡ መገልበጡን ፡ ወይም ፡
ጠጠርን ፡ የያዘ ፡ ነፋስን ፡ በና
ንተ ፡ ላይ ፡ መላኩን ፡ ከዚያም ፡
ለናንተ ፡ ጠባቂ ፡ አለማግኘታች
ሁን ፡ አትፈሩምን?
69 ወይስ ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡
(ወደ ፡ ባሕር) ፡ የሚመልሳችሁ ፡
ወዲያውም ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ብር
ቱን ፡ ነፋስ ፡ የሚልክ ፡ በክሕደታ
ችሁም ፡ ምክንያት ፡ የሚያስጥማ
ችሁ ፡ መኾኑን ፡ ከዚያም ፡ በኛ ፡
ላይ ፡ በርሱ ፡ ተከታይን ፡ (ረዳ
ትን) ፡ ለናንተ ፡ የማታገኙ ፡ መኾ
ናችሁን ፡ አትፈሩምን ?
70 የአደምንም ፡ ልጆች ፡ በእርግጥ ፡
(ከሌላው ፡ ፍጡር) ፡ አከበርናቸው
በየብስና ፡ በባሕርም ፡ አስሳፈር
ናቸው ፤ ከመልካሞችም ፡ (ሲሳ
ዮች) ፡ ሰጠናቸው ፤ ከፈጠርናቸ
ውም ፡ ፍጡሮች ፡ በብዙዎቹ ፡
ላይ ፡ ማብለጥን ፡ አበለጥናቸው ።
71 ሰዎችን ፡ ሁሉ ፡ በመሪያቸው ፡
የምንጠራበትን ፡ ቀን ፡ (አስታ
ውስ) ፤ መጽሐፉንም ፡ በቀኙ ፡
የተሰጠ ፡ ሰው ፡ እነዚያ ፡ መጽሐ
ፋቸውን ፡ ያነባሉ ፤ በተምር ፡
ፍሬ ፡ ስንጥቅ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡
ክር ፡ ያክል ፡ እንኳ ፡ አይበደሉም።
72 በዚህችም ፡ ዓለም ፡ (ልበ) ፡
ዕውር ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡
በመጨረሻይቱም ፡ (ዓለም) ፡ ይበ
ልጥ ፡ ዕውር ፡ ነው ፤ መንገድንም ፡
በጣም ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ።
73 እነሆ ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡
ካወረድነው ፡ ሌላን ፡ በኛ ፡ ላይ ፡
ትዋሽ ፡ ዘንድ ፡ ሊፈትኑህ ፡ በእር
ግጥ ፡ ተቃረቡ ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡
ወዳጅ ፡ አድርገው ፡ በያዙህ ፡
ነበር ።
74 ባላረጋንህም ፡ኖሮ ፡ ወደነሱ ፡
ጥቂትን ፡ (ዝንባሌ) ፡ ልትዘነበል ፡
በእርግጥ ፡ በተቃረብክ ፡ ነበር ።
75 ያን ፡ ጊዜ ፡ የሕይወትን ፡ ድርብ ፡
(ቅጣት) ፡ የሞትንም ፡ ድርብ ፡
(ቅጣት) ፡ ባቀመስንህ ፡ ነበር ፤
ከዚያም ፡ ላንተ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ረዳ
ትን ፡ አታገኝም ፡ ነበር ።



76 ከምድሪቱም ፡ (ከዓረብ ፡ ምድር) ፡
ከርሷ ፡ ያወጡህ ፡ ዘንድ ፡ ሊያሸብ
ሩህ ፡ በእርግጥ ፡ ተቃረቡ ፤ ያን ፡ ጊ
ዜም ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ ጥቂትን ፡
ጊዜ ፡ እንጂ ፡ አይቆዩም ፡ ነበር ።
77 ከመልክተኞቻችን ፡ ካንተ ፡ በ
ፊት ፡ በእርግጥ ፡ እንደ ፡ ላክና
ቸው ፡ ሰዎች ፡ ልማድ ፡ ብጤ ፡
(ይጠፉ ፡ ነበር) ፤ ለልማዳችንም ፡
መለወጥን ፡ አታገኝም ።
78 ሶላትን ፡ ከፀሐይ ፡ መዘንበል ፡
እስከ ፡ ሌሊት ፡ ጨለማ ፡ ድረስ ፡
ስገድ ፤ የጎህንም ፡ ሶላት ፡ ስገድ ፤
የጎህ ፡ ሶላት ፡ (መላእክት) ፡ የሚ
ጣዱት ፡ ነውና ።
79 ከሌሊትም ፡ ላንተ ፡ ተጨማሪ ፡
የኾነችን ፡ ሶላት ፡ በርሱ ፡ (በቁር
አን) ፡ ስገድ ፤ ጌታህ ፡ ምስጉን ፡
በኾነ ፡ ስፍራ ፡ በእርግጥ ፡ ያቆም
ሃል ።
80 በልም ፡- ጌታዬ ፡ ሆይ ! የተወደ
ደን ፡ ማግባት ፡ አግባኝ ፤ የተወደ
ደንም ፡ ማውጣት ፡ አውጣኝ ፤
ለኔም ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ የተረዳን፡
ስልጣን ፡ አድርግልኝ ።
81 በልም ፡- እውነት ፡ መጣ ፡ ውሸ
ትም ፡ ተወገደ ፤ እነሆ ፡ ውሸት ፡
ተወጋጅ ፡ ነውና ፡
82 ከቁርአንም ፡ ለምእመናን ፡ መድ
ኃኒትና ፡ እዝነት ፡ የኾነን ፡ እናወ
ርዳለን ፤ በዳዮችንም ፡ ከሳራን ፡
እንጂ ፡ ሌላ፡ አይጨምርላቸውም።
83 በሰውም ፡ ላይ ፡ ጸጋችንን ፡ በለገ
ስን ፡ ጊዜ ፡ (ከምስጋና) ፡ ይዞራል ፤
ጎኑንም ፡ (ከውነት) ፡ ያርቃል ፤
ችግርም ፡ በነካው ፡ ጊዜ ፡ ተስፋ ፡
ቆራጭ ፡ ይኾናል ።
84 ፡- ሁሉም ፡ በሚመስለው ፡ መን
ገዱ ፡ ላይ ፡ ይሠራል ፡ ጌታችሁም፡
እርሱ ፡ መንገዱ ፡ ቀጥተኛ ፡ የኾነ
ውን ፡ ሰው ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፡ በላ
ቸው ።
85 ከሩሕም ፡ (1) ይጠይቁሃል ፤ ሩሕ ፡
ከጌታዬ ፡ ነገር ፡ (2) ነው ፡ ከዕው
ቀትም ፡ ጥቂትን ፡ እንጂ ፡ አልተሰ
ጣችሁም ፤ በላቸው ።
86 ብንሻም ፡ ያንን ፡ ወዳንተ ፡ ያወረ
ድነውን ፡ በእርግጥ ፡ እናስወግዳ
ለን ፤ ከዚያም ፡ ላንተ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡
በርሱ ፡ (ለማስመለስ) ፡ ተያዢን ፡
አታገኝም ።
87 ግን ፡ ከጌታህ ፡ በኾነው ፡ እዝነት ፡
(ጠበቅነው) ፤ ችሮታው ፡ ባንተ ፡
ላይ ፡ ታላቅ ፡ ነውና ።
88 ፡—ሰዎችም ፡ ጋኔኖችም ፡ የዚ
ህን ፡ ቁርአን ፡ ብጤ ፡ በማምጣት ፡
ላይ ፡ ቢሰበሰቡ ፡ ከፊላቸው ፡
ለከፊሉ ፡ ረዳት ፡ ቢኾንም ፡
እንኳ ፡ ብጤውን ፡ አያመጡም ፤
በላቸው ።
89 በዚህም ፡ ቁርአን ፡ ውስጥ ፡ ከምሳ
ሌው ፡ ሁሉ ፡ ለሰዎች ፡ በእርግጥ ፡
መላለስን ፤ አብዛኞቹም ፡ ሰዎች ፡
ክሕደትን ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡ እምቢ፡
አሉ ።
90 አሉም ፡— ለኛ ፡ ከምድር ፡ ምን
ጭን ፡ እስከምታፈነዳልን ፡ ለአ
ንተ ፡ አናምንም ፤
91 ወይም ፡ ከዘምባባዎችና ፡ ከወይን፡
የኾነች ፡ አትክልት ፡ ለአንተ ፡
እስከምትኖርህና ፡ በመካከልዋም፡
ጂረቶችን ፡ በብዛት ፡ እስከምታ
ንቧቧ ፤
92 ወይም ፡ እንደምትለው ፡ ከሰማይ ፡
ቁራጮችን ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ እስከም

---

1 አካል ፡ ሕያው ፡ ከሚኾንባት ፡ ነፍስ ።
2 በዕውቀቱ ፡ የተለየበት ፡ ነገር ፡ ነው ።

ታወድቅ ፤ ወይም ፡ አላህንና ፡
መላእክትን ፡ በግልጽ ፡ እስከምታ
መጣ ፤

93 ወይም ፡ ከወርቅ ፡ የኾነ ፡ ቤት ፡
ላንተ ፡ እስከሚኖርህ ፤ ወይም ፡
በሰማይ ፡ እስከምትወጣ ፤ ለመው
ጣትህም ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ የምናነ
በው ፡ የኾነን ፡ መጽሐፍ ፡ እስከ
ምታወርድልን ፡ ድረስ ፡ ፈጽሞ ፡
አናምንልህም ፤ (አሉ) ። ጌታዬ ፡
ጥራት ፡ ይገባው ፤ እኔ ፡ ሰው ፡
መልክተኛ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለ
ሁም ፤ በላቸው ።

94 ሰዎችንም ፡ መሪ ፡ (ቁርአን) ፡
በመጣላቸው ፡ ጊዜ ፡ ከማመን ፡
አላህ ፡ ሰውን ፡ መልክተኛ ፡ አድ
ርጎ ፡ላከን ? ማለታቸው ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አልከለከላቸውም ።

95 ፡—በምድር ፡ ላይ ፡ ረግተው ፡
የሚኼዱ ፡ መላእክት ፡ በነበሩ ፡
ኖሮ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ (ከጐሳቸው) ፡
የመልአክን ፡ መልክተኛ ፡ ባወረ
ድን ፡ ነበር ፡ በላቸው ።

96 ፡—በኔና ፡ በናንተ ፡ መካከል ፡
መስካሪ ፡ በአላህ ፡ በቃ ፤ እርሱ ፡
በባሮቹ ፡ (ነገር) ፡ ውስጥ ፡ ዐዋቂ ፡
ተመልካች ፡ ነውና ፤ በላቸው ።

97 አላህም ፡ ያቀናው ፡ ሰው ፡ ቅኑ ፡
እርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ያጠመማቸ
ውም ፡ ሰዎች ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ ለነ
ርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ረዳት ፡ አታገኝላቸ
ውም ፤ በትንሣኤ ፡ ቀንም ፡ ዕው
ሮች፡ ዲዳዎችም፥ ደንቀሮዎችም፡
ኾነው ፡ በፊቶቻቸው ፡ ላይ ፡ (እየ
ተጐተቱ) ፡ እንሰበስባቸዋለን ፤
መኖሪያቸው ፡ ገሀነም ፡ ናት ፤
(ነዲድዋ) ፡ በደከመች ፡ ቍጥር ፡
መንቀልቀልን ፡ እንጨምርባቸዋ
ለን ።

98 ይህ ፡ (ቅጣት) ፤ እነርሱ ፡ በአንቀ
ጾቻችን ፡ ስለ ፡ ካዱና ፡ አጥንቶ
ችና ፡ ብስብሶች ፡ በኾን ፡ ጊዜ ፡
እኛ ፡ አዲስ ፡ ፍጥረት ፡ ኾነን ፡
ተቀስቃሾች ፡ ነን? ስላሉም፡ ፍዳ
ቸው ፡ ነው ።

99 ያ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ የፈ
ጠረ ፡ አላህ ፡ ብጤያቸውን ፡ በመ
ፍጠር ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ መኾኑን ፡
በርሱ ፡ ጥርጣሬ ፡ የሌለበትንም ፡
ጊዜ ፡ (ለሞትም ፡ ለትንሣኤም) ፡
ለነርሱ ፡ የወሰነ ፡ መኾኑን ፡ አላወ
ቁምን? በደለኞችም ፡ ከክሕደት ፡
በቀር ፡ እምቢ ፡ አሉ ።

100 እናንተ ፡ የጌታየን ፡ የችሮታ ፡
መካዚኖች ፡ ብትይዙ ፡ ኖሮ ፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ በማውጣታችሁ ፡
ማለቋን ፡ በመፍራት ፡ በጨበጣ
ችሁ ፡ ነበር ፤ ሰውም ፡ በጣም ፡
ቆጣቢ ፡ ነው ።

101 ለሙሳም ፡ ግልጽ ፡ የኾኑን ፡
ዘጠኝ ፡ ታምራቶች ፡ በእርግጥ ፡
ሰጠነው ፤ በመጣቸውም ፡ ጊዜ ፡
የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ (ከፈር
ዖን ፡ እንዲለቀቁ) ፡ ጠይቅ ፡ (አል
ነው) ፤ ፈርዖንም ፡— ሙሳ ፡ ሆይ!
እኔ ፡ የተደገመብህ ፡ መኾንህን ፡
በእርግጥ ፡ እጠረጥርሃለሁ ፡ አ
ለው ።

102 (ሙሳም) ፡— እነዚህን ፡ (ታምራ
ቶች) ፡ መገሰጫዎች ፡ ሲኾኑ ፡
የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ጌታ ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ እንዳላወረዳቸው ፡
በእርግጥ ፡ ዐውቀሃል ፤ እኔም ፡
ፈርዖን ፡ ሆይ ! የምትጠፋ ፡ መኾ
ንህን ፡ በእርግጥ ፡ እጠረጥርሃ
ለሁ ፡ አለው ።

103 ከምድርም፡ ሊቀሰቅሳቸው፡ አሰበ፤
እርሱንና ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩት



ንም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉንም ፡ አሰጠም
ናቸው ።

104 ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ለእስራኤል ፡
ልጆች ፡— ምድሪቱን ፡ ተቀመጡ
ባት ፡ የኋለኛይቱም ፡ (ሰዓት) ፡
ቀጠሮ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እናንተን ፡
የተከማቻችሁ ፡ ስትኾኑ ፡ እናመ
ጣችኋለን ፤ አልናቸው ።

105 (ቁርአንን) ፡ በውነትም ፡ አወረድ
ነው ፤ በውነትም ፡ ወረደ ፤ አንተ
ንም፡ አብሳሪና፡ አስጠንቃቂ፡ አድ
ርገን፡ እንጂ፡ አልላክንህም።

106 ቁርአንንም ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ በዝ
ግታ ፡ ላይ ፡ ኾነህ ፡ ታነበው ፡
ዘንድ ፡ ከፋፈልነው ፤ ቀስ ፡ በቀስ፡
ማውረድንም ፡ አወረድነው ።

107 ፡—በርሱ ፡ እመኑ ፡ ወይም ፡ አት
መኑ ፡ በላቸው ፤ (1) እነዚያ ፡
ከርሱ ፡ በፊት ፡ ዕውቀትን ፡ የተሰ
ጡት ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ በተነበበ ፡
ጊዜ ፡ ሰጋጆች ፡ ኾነው ፡ በሽንጐ
በቶቻቸው ፡ (2) ላይ ፡ ይወድቃሉ፤

108 ይላሉም ፡— ጌታችን ፡ ጥራት ፡
ይገባው ! እነሆ ፡ የጌታችን ፡
ተስፋ ፡ ተፈጻሚ ፡ ነው ።

109 እያለቀሱም ፡ በሽንጐበቶቻቸው ፡
ላይ፡ ይወድቃሉ፤ (አላህን)፡ መፍ
ራትንም፡ ይጨምራላቸዋል።

110 ፡—አላህን ፡ ጥሩ ፤ ወይም ፡ አልረ
ሕማንን ፡ ጥሩ ፤ (ከሁለቱ) ፡ ማን
ኛውንም ፡ ብትጠሩ ፡ (መልካም ፡
ነው) ፤ ለርሱ ፡ መልካም ፡ ስሞች ፡
አሉትና ፡ በላቸው ፤ በስግደትህም፡
(ስታነብ) ፡ አትጮህ ፤ በርሷም ፡
ድምፅህን ፡ ዝቅ ፡ አታድርግ ፤
በዚህም ፡ መካከል ፡ መንገድን ፡
ፈልግ ።

111 ፡—ምስጋና ፡ ለአላህ ፡ ለዚያ ፡
ልጅን ፡ ላልያዘው ፡ ለርሱም ፡
በንግሥናው ፡ ተጋሪ ፡ ለሌለው ፡
ለርሱም ፡ ከውርደት ፡ ረዳት ፡
ለሌለው ፡ ይገባው ፡ በልም ፤ ማክ
በርንም ፡ አክብረው ።

---

1 ዛቻ ፡ ነው ፤ ውጤቱን ፡ ታገኙታላችሁ ፡
ማለት ፡ ነው ።

2 በአገጮቻቸው ።

## 18ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ከህፍ ፡ (የዋሻው ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 110፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው።

1 ምስጋና ፡ ለአላህ ፡ ለዚያ ፡ መጽሐፉን ፡ በውስጡ ፡ መጣመምን ፡ (1) ያላደረገበት ፡ ሲኾን ፡ በባሪያው ፡ ላይ ፡ ላወረደው ፡ ይገባው ።

2 ቀጥተኛ ፡ ሲኾን ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ የኾነን ፡ ብርቱን ፡ ቅጣት ፡ ሊያስፈራራበት ፡ እነዚያንም ፡ በጎ ፡ ሥራዎችን ፡ የሚሠሩትን ፡ ምእመናን ፡ ለነሱ ፡ መልካም ፡ ምንዳ ፡ ያልላቸው ፡ መኾኑን ፡ ሊያበስርበት ፤ (አወረደው) ።

3 በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ዘለዓለም ፡ የሚቆዩበት ፡ ሲኾኑ ፤ (ያላቸው ፡ መኾኑን) ፤

4 እነዚያንም ፡—አላህ ፡ ልጅን ፡ ይዟል ፡ ያሉትን ፡ ሊያስፈራራበት ፡ (አወረደው) ።

5 ለነሱም፡ ለአባቶቻቸውም፡ በርሱ፡ ምንም ፡ ዕውቀት ፡ የላቸውም ፤ ከአፎቻቸው ፡ የምትወጣውን ፡ ቃል ፡ ምን ፡ አከበዳት! ውሸትን ፡ እንጂ ፡ አይናገሩም ።

6 በዚህም ፡ ንግግር ፡ (በቁርአን) ፡ ባያምኑ ፡ በፈለጎቻቸው ፡ ላይ ፡ (2) በቁጭት ፡ ነፍስህን ፡ አጥፊ ፡ ልትኾን ፡ ይፈራልሃል ።

7 እኛ ፡ ማንኛቸው ፡ ሥራው ፡ ያማረ ፡ መኾኑን ፡ ልንፈትናቸው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያለን ፡ ሁሉ ፡ ለርሷ ፡ ጌጥ ፡ አደረግን ፤

8 እኛም ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ (በመጨረሻ) ፡ በእርግጥ ፡ በቃይ ፡ የሌለበት ፡ ምልጥ ፡ ዐፈር ፡ አድራጊዎች ፡ ነን ።

9 የዋሻውና ፡ የሰሌዳው ፡ (1) ባለቤቶች ፡ ከታምራቶቻችን ፡ ሲኾኑ ፡ ግሩም ፡ መኾናቸውን ፡ አሰብክን ?

10 ጎበዞቹ ፡ ወደ ፡ ዋሻው ፡ በተጠጉና ፡— ጌታችን ፡ ሆይ ! ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ እዝነትን ፡ ስጠን ፤ ለኛም ፡ ከነገራችን ፡ ቅንን ፡ አዘጋጅልን ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ።

11 በዋሻውም ፡ ውስጥ ፡ የተቆጠሩን፡ ዓመታት፡ በጆሮዎቻቸው፡ ላይ ፡ መታንባቸው ። (2)

12 ከዚያም ፡ ከሁለቱ ፡ ክፍሎች ፡ (3) ለቆዩት ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ ያረጋገጠው ፡ ማንኛው ፡ መኾኑን ፡ ልናውቅ ፡ አስነሳናቸው ።

13 እኛ ፡ ወሬያቸውን ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ በውነት ፡ እንተርካለን ፤ እነሱ ፡ በጌታቸው ፡ ያመኑ ፡ ጎበዞች ፡ ናቸው ፤ መመራትንም ፡ ጨመርንላቸው ።

1 ተቃርኖን፣ ጥበብ፡ አልባ፡ መኾንን።
2 ከእምቢታቸው ፡ በኋላ ።

1 በላዩ ፡ ላይ ፡ ስማቸው ፡ የተጻፈበት ።
2 መስማትን ፡ የሚከለክልን ፡ ግርዶሽ ፡ እንቅልፍን ፡ ጣልንባቸው ።
3 የቆዩት ፡ ጊዜያት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ከተከራከሩት ።



14 (በንጉሣቸው ፡ ፊት) ፡ በቆሙና ፡- ጌታችን ፡ የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ጌታ ፡ ነው ፤ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ አምላክን ፡ አንግገዛም ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ (ሌላን ፡ ብናመልክ) ፡ ወሰን ፡ ያለፈን ፡ (ንግግር) ፡ በእርግጥ ፡ ተናገርን ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ልቦቻቸውን ፡ አጠነከርን ።

15 እነዚህ ፡ ሕዝቦቻችን ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ አማልክትን ፡ ያዙ ፤ (እውነተኞች ፡ ከኾኑ) ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ግልጽ ፡ ማስረጃን ፡ ለምን ፡ አያመጡም ፤ በአላህም ፡ ላይ ፡ ውሸትን፡ ከሚቀጣጥፍ ፡ ይበልጥ ፡ በዳይ ፡ ማነው? (አሉ) ።

16 ፡—እነርሱንና ፡ ያንን ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የሚግገዙትን ፡ በተለያችሁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ዋሻው ፡ ተጠጉ ፤ ጌታችሁ ፡ ለናንተ ፡ ከችሮታው ፡ ይዘረጋላችኋልና ፤ ከነገራችሁም ፡ ለናንተ ፡ መጠቃቀሚያን ፡ ያዘጋጅላችኋል ፤ (ተባባሉ) ።

17 ፀሐይንም ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡ ከዋሻቸው ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ጐን ፡ ስታዘነብል ፡ ታያታለህ ፤ በገባችም ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ከርሱ ፡ በሰፊው ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ኾነው ፡ ሳሉ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ በኩል ፡ ትተዋቸዋለች ፤ ይህ ፡ ከአላህ ፡ ታምራቶች ፡ ነው ፤ አላህ ፡ የሚያቀናው ፡ ሰው ፡ ቅኑ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ የሚያጠመውም ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡ አቅኝን ፡ ረዳት ፡ አታገኝለትም ።

18 እነሱም ፡ የተኙ ፡ ኾነው ፡ ሳሉ ፡ (ዓይኖቻቸው ፡ በመከፈታቸው) ፡ ንቁዎች ፡ ናቸው ፡ ብለህ ፡ ታስባቸዋለህ ፤ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ጎንና ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ጎንም ፡ እናገላብጣቸዋለን ፤ ውሻቸውም ፡ ሁለት ፡ ክንዶቹን ፡ በዋሻው ፡ በር ፡ ላይ ፡ ዘርግቷል ፤ በነሱ ፡ ላይ ፡ ዘልቀህ ፡ ብታይ ፡ ኖሮ ፡ የምትሸሽ ፡ ኾነህ ፡ በዞርክ ፡ ነበር ፡ ከነሱም ፡ በእርግጥ ፡ ፍርሃትን ፡ በተመላህ ፡ ነበር ።

19 እንዲሁም ፡ በመካከላቸው ፡ እንዲጠያየቁ ፡ ቀሰቀስናቸው ፤ ከነሱ ፡ አንድ ፡ ተናጋሪ ፡— ምን ፡ ያክል ፡ ቆያችችሁ ? አለ ፤ አንድን ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ የቀንን ፡ ከፊል ፡ ቆየን ፡ አሉ ፤ (1) ጌታችሁ ፡ የቆያችሁትን ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፤ ከዚችም ፡ ብራችሁ ፡ ጋር ፡ አንዳችሁን ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ ላኩ ፤ ከምግቦችዋ ፡ የትኛዋ ፡ ንጹሕ ፡ መኾንዋንም ፡ ይመልከት ፤ ከርሱም ፡ (ከንጹሑ) ፡ ምግብን ፡ ያምጣላችሁ ፤ ቀስም ፡ ይበል ፤ በናንተም ፡ አንድንም ፡ ሰው ፡ አያሳውቅ ፡ አሉ ።

20 እነሱ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ቢዘልቁ ፡ ይቀጠቅጧችኋልና፤ ወይም፡ ወደ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ይመልሷችኋል ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ በፍጹም ፡ ፍላጎታችሁን ፡ አታገኙም ፡ (ተባባሉ) ።

21 እንደዚሁም ፡ የአላህ ፡ ቀጠሮ ፡ እርግጠኛ ፡ መኾኑን ፡ ሰዓቲቱም ፡ በርሷ ፡ ጥርጣሬ ፡ የሌለ ፡ መኾኑን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ (ሰዎችን) ፡ አሳወቅን ፤ (አማኞቹና ፡ ከሓዲዎቹ) ፡ ነገራቸውን ፡ በመካከላቸው ፡ ሲከራከሩ ፡ (የኾነውን ፡ አስታውስ ፤ ከሓዲዎቹ) ፡—በነሱ ፡ ላይም ፡ ግንብን ፡ ገንቡ ፡ አሉ ፤ ጌታቸው ፡ በነሱ ፡

1 እዋሻው ፡ የገቡት ፡ ፀሐይ ፡ ስትወጣ ፡ የተቀሰቀሱት ፡ ፀሐይ ፡ ስትገባ ፡ ነበርና ፡ ያው ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ መሰላቸው ፡ ነው ።

ይበልጥ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፤ እነዚያ ፡
በነገራቸው ፡ ላይ ፡ ያሸነፉት ፡ (ምእ
መናን) ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡
መስጊድን ፡ እንሠራለን ፡ አሉ ።
22 በሩቅ ፡ ወርዋሪዎች ፡ ኾነው ፡
(በጥርጣሬ) ፡— ሦስት ፡ ናቸው ፤
አራተኛቸው ፡ ውሻቸው ፡ ነው ፡
ይላሉ ፤ አምስት ፡ ናቸው ፤ ስድስ
ተኛቸው ፡ ውሻቸው ፡ ነውም ፡
ይላሉ ፤ ሰባት ፡ ናቸው ፤ ስምንተ
ኛቸውም ፡ ውሻቸው ፡ ነው ፡ ይላ
ሉም ፤ ጌታዬ ፡ ቍጥራቸውን ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ፤ ጥቂት ፡ (ሰው) ፡
እንጂ ፡ አያውቃቸውም ፡ በላ
ቸው ፤ በነሱም ፡ ነገር ፡ ግልጽን ፡
ክርክር ፡ እንጂ ፡ (ጠልቀህ) ፡ አት
ከራከር ፤ በነሱም ፡ ጉዳይ ፡ ከነሱ ፡
(ከመጽሐፉ ፡ ሰዎች) ፡ አንድንም ፡
አትጠይቅ ።
23 ለማንኛውም ፡ ነገር ፡— እኔ ፡ ይህ
ንን ፡ ነገ ፡ ሠሪ ፡ ነኝም ፡ አትበል ።
24 አላህ ፡ የሻ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ (እሠራ
ዋለሁ ፡ ብትል) ፡ እንጂ ፤ በረሳ
ህም ፡ ጊዜ ፡ ጌታህን ፡ አውሳ ፤
ጌታዬም ፡ ከዚህ ፡ ይበልጥ ፡ ለቀ
ጥታ ፡ የቀረበን ፡ ሊመራኝ ፡ ይከ
ጀላል ፡ በላቸው ።
25 በዋሻቸውም ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡
መቶ ፡ ዓመታትን ፡ቆዩ ፤ ዘጠኝ
ንም ፡ ጨመሩ ።
26 ፡—አላህ ፡ የቆዩትን ፡ ልክ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ፡ በላቸው ፤ የሰማያትና ፡ የም
ድር ፡ ምስጢር ፡ የሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤
እርሱ ፡ ምን ፡ ያይ ! ምን ፡ ይሰ
ማም ! ለነርሱ ፡ ከርሱ ፡ በቀር ፡
ምንም ፡ ረዳት ፡ የላቸውም ፤ በፍር
ዱም ፡ አንድንም ፡ አያጋራም ።
27 ከጌታህም ፡ መጽሐፍ ፡ ወደ ፡
አንተ ፡ የተወረደውን ፡ አንብብ ፤
ለቃላቶቹ ፡ ለዋጭ ፡ የላቸውም ፤
ከርሱም ፡ በቀር ፡ መጠጊያን ፡
በፍጹም ፡ አታገኝም ።
28 ነፍስህንም ፤ ከነዚያ ፡ ጌታቸውን ፡
ፊቱን ፡ (ውዴታውን) ፡ የሚሹ ፡
ኾነው ፡ በጧትና ፡ በማታ ፡ ከሚግ
ገዙት ፡ ጋር ፡ አስታግሥ ፤ የቅርቢ
ቱንም ፡ ሕይወት ፡ ሽልማት ፡ የም
ትሻ ፡ ኾነህ ፡ ዓይኖችህ ፡ ከነሱ ፡
(ወደ ፡ ሌላ) ፡ አይለፉ ፤ ልቡንም ፡
እኛን ፡ ከማስታወስ ፡ ያዘነጋነ
ውን ፡ ፍላጎቱንም ፡ የተከተለ
ውን ፡ ነገሩም ፡ ሁሉ ፡ ወሰን ፡
ማለፍ ፡ የኾነውን ፡ ሰው ፡ አትታ
ዘዝ ።
29 ፡—እውነቱም ፡ ከጌታችሁ ፡ ነው ፤
የሻም ፡ ሰው ፡ ይመን ፤ የሻም ፡
ሰው ፡ ይካድ ፡ በላቸው ፤ እኛ ፡
ለበደለኞች ፡ አጥርዋ ፡ በነሱ ፡
የከበበ ፡ የኾነችውን ፡ እሳት ፡ አዘ
ጋጅተናል ፤ (ከጥም) ፡ እርዳታ
ንም ፡ ቢፈልጉ ፡ እንደ ፡ ዘይት ፡
ዝቃጭ ፡ ባለ ፡ ፊቶችን ፡ በሚጠ
ብስ ፡ ውሃ ፡ ይረዳሉ ፤ መጠጡ ፡
ከፋ ! መደገፊያይቱም ፡ ምንኛ ፡
አስከፋች !
30 እነዚያ ፡ ያመኑና ፡ መልካም ፡
ሥራዎችንም ፡ የሠሩ ፡ እኛ ፡
ሥራን ፡ ያሳመረን ፡ ሰው ፡ ምንዳ ፡
አናጠፋም ።
31 እነዚያ ፡ ለነሱ ፡ የመኖሪያ ፡ ገነ
ቶች ፡ ከስሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡
የሚፈሱባቸው ፡ አሏቸው ፤ በርሷ ፡
ውስጥ ፡ ከወርቅ ፡ የኾኑን ፡ አንባ
ሮች ፡ ይሸለማሉ ፤ ከቀጭን ፡
ሐርና ፡ ከወፍራም ፡ ሐርም ፡ አረን
ጓዴን ፡ ልብሶች ፡ ይለብሳሉ ፤
በውስጧ ፡ በባለ ፡ አጐበር ፡ አልጋ
ዎች ፡ ላይ ፡ የተደገፉ ፡ ኾነው ፡



(ይቀመጣሉ) ፤ ምንዳቸው ፡ ምን ፡
ያምር ! መደገፊያይቱም ፡ ምንኛ ፡
አማረች !
32 ለነሱም ፡ የሁለትን ፡ ሰዎች ፡
ምሳሌ ፡ ግለጽላቸው ፤ ለአንደኛ
ቸው ፡ (ለከሓዲው) ፡ ከወይኖች ፡
የኾኑን ፡ ሁለት ፡ አትክልቶች ፡
አደረግንለት ፤ በዘምባባም ፡ አከበ
ብናቸው ፤ በመካከላቸውም ፡ አዝ
መራን ፡ አደረግን ።
33 ሁለቱም ፡ አትክልቶች ፡ ሰብላቸ
ውን ፡ ሰጡ ፤ ከርሱም ፡ ምንም ፡
አላጐደሉም ፤ በመካከላቸውም ፡
ወንዝን ፡ አፈሰስን ።
34 ለርሱም ፡ (ከአትክልቶቹ ፡ ሌላ ፡
ፍሬያማ)፡ ሀብት፡ ነበረው፤ ለጓደ
ኛውም ፡ (ለአማኙ) ፡ እርሱ ፡ የሚ
ወዳደረው ፡ ሲኾን ፡— እኔ ፡ ካ
ንተ ፡ በገንዘብ ፡ ይበልጥ ፡ የበ
ዛሁ ፡ በወገንም ፡ ይበልጥ ፡ የበረ
ታሁ ፡ ነኝ ፡ አለው ።
35 እርሱም ፡ ነፍሱን ፡ በዳይ ፡ ኾኖ ፡
ወደ ፡ አትክልቱ ፡ ገባ ፤ ይህች ፡
ዘለዓለም ፡ ትጠፋለች ፡ ብዬ ፡
አልጠረጥርም ፡ አለ ።
36 ሰዓቲቱንም ፡ ቋሚ ፡ (ኳኝ) ፡ ናት ፡
ብዬ ፡ አልጠረጥርም ፤ (እንደምት
ለው) ፡ ወደ ፡ ጌታዬም ፡ ብመለስ ፡
ከርሷ ፡ የበለጠን ፡ መመለሻ ፡
በእርግጥ ፡ አገኛለሁ ፡ (አለው) ።
37 ጓደኛው ፡ (አማኙ) ፡ እርሱ ፡ ለ
ርሱ ፡ የሚመላለሰው ፡ ሲኾን ፡—
በዚያ ፡ ከዐፈር ፡ ከዚያም ፡ ከፍ
ቶት ፡ ጠብታ ፡ በፈጠረህ ፡ ከዚ
ያም ፡ ሰው ፡ ባደረገህ ፡ (አም
ላክ) ፡ ካድህን ? አለው ።
38 እኔ ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ አላህ ፡ ጌታዬ ፡
ነው ፤ (እላለሁ) ፤ በጌታዬም ፡ አን
ድንም ፡ አላጋራም ።
39 አትክልትህንም ፡ በገባህ ፡ ጊዜ ፡
አላህ ፡ የሻው ፡ ይኾናል ፤ በአ
ላህ ፡ ቢኾን ፡ እንጂ ፡ ኀይል ፡
የለም ፤ አትልም ፡ ነበርን ?
እኔን ፡ በገንዘብም ፡ በልጅም ፡
ካንተ ፡ በጣም ፡ ያነስኩ ፡ ኾኜ ፡
ብታየኝ ፡
40 ጌታዬ ፡ ከአትክልትህ ፡ የበለጠን ፡
ሊሰጠኝ ፡ በርሷም ፡ (በአትክል
ትህ) ፡ ላይ ፡ ከሰማይ ፡ መብረቆ
ችን ፡ ሊልክባትና ፡ የምታንዳ
ልጥ ፡ ምልጥ ፡ ምድር ፡ ልትኾን ፡
ይቻላል ።
41 ወይም ፡ ውሃው ፡ ሠራጊ ፡ ሊኾን ፡
(ይችላል) ፤ ያንጊዜ ፡ ለርሱ ፡ መፈ
ለግን ፡ ፈጽሞ ፡ አትችልም ፡
(አለው) ።
42 ሀብቱም ፡ ተጠፋ ፤ እርሷ ፡ በዳሶ
ችዋ ፡ ላይ ፡ የወደቀች ፡ ኾና ፡
በርሷ ፡ ባወጣው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡
(እየተጸጸተ) ፡ መዳፎቹን ፡ የሚያ
ገላብጥና ፡ ወይ ፡ ጸጸቴ ! በጌታዬ ፡
አንድንም ፡ ባላጋራሁ ፡ የሚል ፡
ኾነ ።
43 ለርሱም ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የሚረ
ዱት ፡ ጭፍሮች ፡ አልነበሩትም ፤
ተረጂም ፡ አልነበረም ።
44 እዚያ ፡ ዘንድ ፡ (በትንሣኤ ፡ ቀን) ፡
ስልጣኑ ፡ እውነተኛ ፡ ለኾነው ፡
አላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ እርሱ ፡ በመ
መንዳት ፡ የበለጠ ፡ ፍጻሜንም ፡
በማሳመር ፡ የበለጠ ፡ ነው ።
45 ለነሱም ፡ የቅርቢቱን ፡ ሕይወት ፡
ምሳሌ ፡ አውሳላቸው ፤ (እርስዋ) ፡
ከሰማይ ፡ እንዳወረድነው ፡ ውሃ ፡
በርሱም ፡ የምድር ፡ በቃይ ፡
እንደ ፡ ተቀላቀለበት ፡ (ከተዋበ ፡
በኋላ ፡ ደርቆ) ፡ ነፋሶችም ፡ የሚያ
በኑት ፡ ደቃቅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ብጤ

ናት ፤ አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ።

46 ገንዘብና ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ የቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡ ጌጦች ፡ ናቸው ፤ መልካሞቹም ፡ ቀሪዎች ፡ (ሥራዎች) ፡ እጌታህ ፡ ዘንድ ፡ በምንዳ ፡ በላጭ ፡ ናቸው ፤ በተስፋም ፡ በላጭ ፡ ናቸው ።

47 ተራራዎችንም ፡ የምናስኼድበትን ፡ ቀን ፡ (አስታውስ) ፤ ምድርንም ፡ ግልጽ ፡ ኾና ፡ ታያታለህ ፤ እንሰበስባቸዋለንም ፤ ከነሱም ፡ አንድንም ፡ አንተውም ።

48 የተሰለፉም ፡ ኾነው ፡ በጌታህ ፡ ላይ ፡ ይቀረባሉ ፤ (ይባላሉም) ፦ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ፈጠርናችሁ ፡ (ራቁታችሁን) ፡ በእርግጥ ፡ መጣችሁን ፤ በውነቱ ፡ ለናንተ ፡ (ለመቀስቀሻ) ፡ ጊዜን ፡ አናደርግም ፡ መስሏችሁ ፡ ነበር ።

49 (ለሰው ፡ ሁሉ) ፡ መጽሐፉም ፡ ይቀረባል ፤ ወዲያውም ፡ ከሓዲዎችን ፡ በውስጡ ፡ ካለው ፡ ነገር ፡ ፈሪዎች ፡ ኾነው ፡ ታያቸዋለህ ፤ ዋ ፡ ጥፋታችን ! ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ (ከሥራ) ፡ ትንሽንም ፡ ትልቅንም ፡ የቆጠራት ፡ ቢኾን ፡ እንጂ ፡ የማይተወው ፡ ምን ፡ አለው ? ይላሉም ፤ የሠሩትንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ቀራቢ ፡ ኾኖ ፡ ያገኙታል ፤ ጌታህም ፡ አንድንም ፡ አይበድልም ።

50 ለመላእክትም ፡ ለአደም ፡ ስገዱ ፡ ባልናቸው ፡ ጊዜ ፡ (የኾነውን ፡ አስታውስ) ። ወዲያውም ፡ ሰገዱ ፤ ኢብሊስ ፡ ብቻ ፡ ሲቀር ፤ ከጋኔን ፡ (ጐሳ) ፡ ነበር ፤ ከጌታውም ፡ ትእዛዝ ፡ ወጣ ፤ እርሱንና ፡ ዘሮቹን ፡ እነሱ ፡ ለናንተ ፡ ጠላቶች ፡ ሲኾኑ ፡ ከኔ ፡ ሌላ ፡ ረዳቶች ፡ አድርጋችሁ ፡ ትይዛላችሁን ? ለበዳዮች ፡ ልዋጭነቱ ፡ ከፋ ! (1)

51 የሰማያትንና ፡ የምድርን ፡ አፈጣጠር ፡ አላሳየኋቸውም ፤ የነፍሶቻቸውንም ፡ አፈጣጠር ፡ (እንደዚሁ) ፤ አሳሳቾችንም ፡ ረዳቶች ፡ አድርጌ ፡ የምይዝ ፡ አይደለሁም ።

52 እነዚያንም ፡ (አምላክ) ፡ የምትሏቸውን ፡ ተጋሪዎቼን ፡ ጥሩ ፡ የሚልበትን ፡ ቀን ፡ (አስታውስ) ፤ ይጠሩዋቸዋልም ፤ ግን ፡ አይመልሱላቸውም ፤ በመካከላቸውም ፡ መጥፊያን ፡ ስፍራ ፡ (ገሀነምን) ፡ አደረግን ።

53 ከሓዲዎችም ፡ እሳትን ፡ ያያሉ ፤ እነርሱም ፡ በውስጥዋ ፡ ወዳቂዎች ፡ መኾናቸውን ፡ ያረጋግጣሉ ፤ ከርሷም ፡ መሸሻን ፡ አያገኙም ።

54 በዚህም ፡ ቁርአን ፡ ውስጥ ፡ ከየምሳሌው ፡ ሁሉ ፡ ለሰዎች ፡ መላልሰን ፡ ገለጽን ፤ ሰውም ፡ ከነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ክርክረ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

55 ሰዎችንም ፡ መምሪያ ፡ በመጣላቸው ፡ ጊዜ ፡ ከማመንና ፡ ጌታቸውንም ፡ ምሕረትን ፡ ከመለመን ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ (ሕዝቦች) ፡ ልማድ ፡ (መጥፋት) ፡ ልትመጣባቸው ፡ ወይም ፡ ቅጣቱ ፡ በያይነቱ ፡ ሊመጣባቸው ፡ (መጠባበቅ) ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አልከለከላቸውም ።

56 መልክተኞችንም ፡ አብሳሪዎችና ፡ አስፈራሪዎች ፡ ኾነው ፡ እንጂ ፡ አንልክም ፤ እነዚያ ፡ የካዱትም ፡ በውሸት ፡ እውነቱን ፡ በሱ ፡ ሊያበላሹ ፡ ይከራከራሉ ፤ አንቀጾቼ

1 ኢብሊስን ፡ በአላህ ፡ ለውጥ ፡ መያዛቸው ፡ ከፋ።



ንና ፡ በርሱ ፡ የተስፈራሩበትንም ፡ ነገር ፡ ማላገጫ ፡ አድርገው ፡ ያዙ ።

57 በጌታውም ፡ አንቀጾች ፡ ከተገሠጸና ፡ ከርሷ ፡ ከዞረ ፡ እጆቹም ፡ ያስቀደሙትን ፡ ነገር ፡ ከረሳ ፡ ሰው ፡ ይበልጥ ፡ በዳይ ፡ ማነው? እኛ ፡ በልቦቻቸው ፡ ላይ ፡ እንዳያውቁት፡ ሺፋኖችን፥ በጆሮዎቻቸውም ፡ ውስጥ ፡ ድንቁርናን ፡ አደረግን ፤ ወደ ፡ መመራትም ፡ ብትጠራቸው ፡ ያንጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ አይመሩም ።

58 ጌታህም ፡ በጣም ፡ መሓሪው ፡ የእዝነት ፡ ባለቤቱ ፡ ነው ፤ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ ቢይዛቸው ፡ ኖሮ ፡ ቅጣቱን ፡ ለነሱ ፡ ባስቸኮለባቸው ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ለነሱ ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ መጠጊያን ፡ ፈጽሞ ፡ የማያገኙበት ፡ ቀጠሮ ፡ አላቸው ።

59 እነዚህ ፡ ከተሞችም ፡ በበደሉ ፡ ጊዜ ፡ አጠፋናቸው ፤ ለመጥፊያቸውም ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜን ፡ አደረግን ።

60 ሙሳም ፡ ለወጣቱ ፡ (1) የሁለቱን ፡ ባሕሮች ፡ መገናኛ ፡ እስከምደርስ ፡ ወይም ፡ ብዙን ፡ ጊዜ ፡ እስከምኼድ ፡ ድረስ ፡ (ከመጓዝ) ፡ አልወገድም ፡ ያለውን ፡ (አስታውስ) ።

61 የሁለቱን ፡ መገናኛ ፡ በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ ዐሣቸውን ፡ ረሱ ፤ (ዐሣው)፡ መንገዱንም ፡ በባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ቀዳዳ ፡ አድርጎ ፡ ያዘ ።

62 ባለፉም ፡ ጊዜ ፡ ለወጣቱ ፡— ምሳችንን ፡ ስጠን ፤ ከዚህ ፡ ጉዟችን ፡ እርግጥ ፡ ድካምን ፡ አግኝተናልና ፡ አለ ።

1 ለዩሻዕ ፡ (ለኢያሱ) ።

63 ፡—አየህን ? ወደ ፡ ቋጥኝዋ ፡ በተጠጋን ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ዐሣውን ፡ ረሳሁ ፤ ማስታወሱንም ፡ ሰይጣን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አላስረሳኝም ፤ በባሕሩም ፡ ውስጥ ፡ መንገዱን ፡ አስደናቂ ፡ (መንገድ) ፡ አድርጎ ፡ ያዘ ፡ አለ ። (1)

64 (ሙሳም) ፡ ይህ ፡ እንፈልገው ፡ የነበርነው ፡ ነው ፡ አለው ፤ በፈለጎቻቸውም ፡ ላይ ፡ እየተከተሉ ፡ ተመለሱ ።

65 ከባሮቻችንም ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ችሮታን ፡ የሰጠነውን ፡ ከኛም ፡ ዘንድ ፡ ዕውቀትን ፡ ያስተማርነውን ፡ አንድን ፡ ባሪያ ፡ (ኸድርን)፡ አገኙ ።

66 ሙሳ ፡ ለርሱ ፡— ከተማርከው ፡ ነገር ፡ ቀጥተኛን ፡ (ዕውቀት) ፡ ታስተምረኝ ፡ ዘንድ ፡ ልከተልህን ? አለው ።

67 (ባሪያውም) ፡ አለ ፡— አንተ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ መታገሥን ፡ በጭራሽ ፡ አትችልም ።

68 በዕውቀትም ፡ በርሱ ፡ ባላዳረስከው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ትታገሣለህ ?

69 (ሙሳ) ፡ አላህ ፡ የሻ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታጋሽና ፡ ላንተ ፡ ትእዛዝን ፡ የማልጥስ ፡ ኾኜ ፡ ታገኘኛለህ ፡ አለው ።

70 ብትከተለኝም ፡ ለአንተ ፡ ከርሱ ፡ ማውሳትን ፡ እስከምጀምርልህ ፡ ድረስ ፡ ከምንም ፡ ነገር ፡ አትጠይቀኝ ፡ አለው ።

71 ኼዱም ፤ በመርከቢቱም ፡ በተሳፈሩ ፡ ጊዜ ፡ ቀደዳት ፤ ባለ ፡ ቤቶች

1 ግማሽ ፡ ጐኑን ፡ ከበሉለት ፡ በኋላ ፡ ሕያው ፡ ኾኖ ፡ ባሕሩን ፡ ቀዶ ፡ መኼዱ ፡ አስደናቂ ፡ አካኼድ ፡ ነው ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

ዋን ፡ ልታሰጥም ፡ ቀደድካትን ?
ትልቅ ፡ ነገርን ፡ በእርግጥ ፡
ሠራህ ፡ አለው ።

72 ፡—አንተ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ትእግሥ
ትን ፡ ፈጽሞ ፡ አትችልም ፡ አላል
ኩምን ? አለ ።

73 ፡—በረሳሁት ፡ ነገር ፡ አትያዘኝ ፡
ከነገሬም ፡ ችግርን ፡ አታሸክመኝ፡
አለው ።

74 (ወርደው) ፡ ተጓዙም ፤ ወጣት
ንም ፡ ልጅ ፡ ባገኙና ፡ በገደለው ፡
ጊዜ ፡ ያለ ፡ ነፍስ ፡ (መግደል) ፡
ንጹሕን ፡ ነፍስ ፡ ገደልክን ? በእር
ግጥ ፡ መጥፎን ፡ ነገር ፡ ሠራህ ፡
አለው ።

* * *

75 ፡—አንተ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ትእግሥ
ትን ፡ ፈጽሞ ፡ አትችልም ፡ አላል
ኩህምን ? አለ ።

76 ከርሷ ፡ (ከአሁኒቱ ፡ ጊዜ) ፡ በኋላ ፡
ከምንም ፡ ነገር ፡ ብጠይቅህ ፡ አት
ጐዳኝኝ ፤ ከኔ ፡ የይቅርታን ፡
መጨረሻ ፡ በእርግጥ ፡ ደርሰሃል ፡
አለው ።

77 ኼዱም ፤ ወደ ፡ አንዲት ፡ ከተማ ፡
ሰዎች ፡ በመጡም ፡ ጊዜ ፡ ነዋሪዎ
ችዋን ፡ ምግብን ፡ ጠየቁ ፤ ከማስተ
ናገዳቸውም ፡ እምቢ ፡ አሉ ፤ በር
ሷም ፡ ውስጥ ፡ ለመውደቅ ፡ የተ
ቃረበን ፡ ግድግዳ ፡ አገኙ ፡ (ኸድ
ር) ፡ አቆመውም ፤ (ሙሳም) ፡- በ
ሻህ ፡ ኖሮ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ዋጋን ፡
በተቀበልክ ፡ ነበር ፡ አለው ።

78 (ኸድር) ፡ አለ ፡- ይህ ፡ በኔና ፡
በአንተ ፡ መካከል ፡ መለያያ ፡
ነው ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ መታገሥን ፡
ያልቻልክበትን ፡ ፍች ፡ እነግርሃ
ለሁ ፡

79 መርከቢቱማ ፡ በባሕር ፡ ለሚ
ሠሩ ፡ ምስኪኖች ፡ ነበረች ፡ ከኋ
ላቸውም ፡ መርከብን ፡ ሁሉ ፡
በቅሚያ ፡ የሚይዝ ፡ ንጉሥ ፡
ነበረና ፡ (እንዳይቀማቸው) ፡ ላነ
ውራት ፡ (1) ፈቀድኩ ፤

80 ወጣቱም ፡ ልጅማ ፡ ወላጆቹ ፡
ምእምናን ፡ ነበሩ ፤ (ቢያድግ) ፡
ትእቢትንና ፡ ክሕደትንም ፡ የሚ
ያስገድዳቸው ፡ መኾኑን ፡ ፈራን ፤

81 ጌታቸውም ፡ በንጹሕነት ፡ ከርሱ ፡
በላጭን ፡ በእዝነትም ፡ ከርሱ ፡
በጣም ፡ ቀራቢን ፡ ልጅ ፡ ሊለው
ጥላቸው ፡ ፈለግን ።

82 ግድግዳውማ ፡ በከተማይቱ ፡ ው
ስጥ ፡ የነበሩ ፡ የሁለት ፡ የቲሞች ፡
(2) ወጣቶች ፡ ነበር ፤ በስሩም ፡
ለነርሱ ፡ የኾነ ፡ (የተቀበረ) ፡
ድልብ ፡ ነበረ ፤ አባታቸውም ፡
መልካም ፡ ሰው ፡ ነበር ፤ ጌታ
ህም ፡ ለአካለ ፡ መጠን ፡ እንዲደር
ሱና ፡ ከጌታህ ፡ ችሮታ ፡ ድልባቸ
ውን ፡ እንዲያወጡ ፡ ፈቀደ ፤ በፈ
ቃዴም ፡ አልሠራሁትም ፤ ይህ ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ መታገሥን ፡ ያልቻ
ልከው ፡ ነገር ፡ ፍች ፡ ነው ፤
(አለው) ።

83 ከዙልቀርነይንም ፡ (3) ይጠይቁ
ሃል ፤ በናንተ ፡ ላይ ፡ ከርሱ ፡
ወሬን ፡ አነባለሁ ፡ በላቸው ።

84 እኛ ፡ ለርሱ ፡ በምድር ፡ አስመቸ
ነው ፤ ከነገሩም ፡ ሁሉ ፡ (መዳ
ረሻ) ፡ መንገድን ፡ ሰጠነው ።

85 መንገድንም ፡ (ወደ ፡ ምዕራብ) ፡
ተከተለ ።

---

1 ነውረኛ ፡ ላደርጋት ።
2 ድኻ,አደጐች ።
3 ከባለ ፡ ሁለት ፡ ቀንድ ።



86 ወደ ፡ ፀሐይ ፡ መግቢያም ፡ በደ
ረሰ ፡ ጊዜ ፡ ጥቁር ፡ ጭቃ ፡
ባላት ፡ ምንጭ ፡ ውስጥ ፡ ስትጠ
ልቅ ፡ (1) አገኛት ፤ ባጠገቧም ፡
ሕዝቦችን ፡ አገኘ ፤ ዙልቀርነይን ፡
ሆይ ! ወይም ፡ (በመግደል) ፡ ትቀ
ጣለህ ፡ ወይም ፡ በነርሱ ፡ መል
ካም ፡ ነገርን ፡ (መማረክን) ፡ ትሠ
ራለህ ፡ አልነው ።

87 የበደለውን ፡ ሰውማ ፡ ወደፊት ፡
እንቀጣዋለን ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡
ጌታው ፡ ይመለሳል ፤ ብርቱንም ፡
ቅጣት ፡ ይቀጣዋል ፡ አለ ።

88 ያመነም ፡ ሰውማ ፡ መልካምንም ፡
ሥራ ፡ የሠራ ፡ ለርሱ ፡ ከምንዳ ፡
በኩል ፡ መልካሚቱ ፡ (ገነት) ፡ አ
ለችው ፤ ለርሱም ፡ ከትእዛዛችን ፡
ገርን ፡ ነገር ፡ እናዘዋለን ፤ (አለ) ።

89 ከዚያም ፡ መንገድን ፡ (ወደ ፡
ምሥራቅ) ፡ ቀጠለ ።

90 ወደ ፡ ፀሐይ ፡ መውጫ ፡ በደረ
ሰም ፡ ጊዜ ፡ ለነሱ ፡ ከበታችዋ ፡
መከለያን ፡ ባላደረግንላቸው ፡ ሕ
ዝቦች ፡ ላይ ፡ ስትወጣ ፡ አገኛት ።

91 (ነገሩ) ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፤ እርሱ
ም ፡ ዘንድ ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
በእርግጥ ፡ በዕውቀት ፡ ከበብን ።

92 ከዚያም ፡ (ወደ ፡ ሰሜን ፡ አቅ
ጣጫ) ፡ መንገድን ፡ ቀጠለ ።

93 በሁለቱ ፡ ጋራዎችም ፡ መካከል ፡
በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በአቅራቢያቸው ፡
ንግግርን ፡ ለማወቅ ፡ የማይቃረቡ፡
ሕዝቦችን ፡ አገኘ ።

94 ዙልቀርነይን ፡ ሆይ ! የእጁጅና ፡
መእጁጅ ፡ (2) በምድር ፡ ላይ ፡
አበላሺዎች ፡ ናቸውና ፡ በኛና ፡
በነሱ ፡ መካከል ፡ ግድብን ፡ ታደ
ርግልን ፡ ዘንድ ፡ ግብርን ፡ እናድ
ርግልህን ? አሉ ።

95 አለ ፡— ጌታዬ ፡ በርሱ ፡ ያስመ
ቼኝ ፡ ሀብት ፡ (ከናንተ ፡ ግብር) ፡
በላጭ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ በጉል
በት ፡ እገዙኝ ፤ በናንተና ፡ በነሱ ፡
መካከል ፡ ብርቱን ፡ ግድብ ፡ አደር
ጋለሁና ።

96 የብረትን ፡ ታላላቅ ፡ ቁራጮች ፡
ስጡኝ ፡ (አላቸው) ፤ በሁለቱ ፡
ኮረብታዎች ፡ (ጫፍ) ፡ መካከ
ልም ፡ ባስተካከለ ፡ ጊዜ ፡ እናፉ ፡
አላቸው ፤ (ብረቱን) ፡ እሳትም ፡
ባደረገው ፡ ጊዜ ፡ የቀለጠውን ፡
ነሐስ ፡ ስጡኝ ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ አፈ
ስበታለሁና ፤ አላቸው ።

97 (የእጁጅና ፡ መእጁጅ) ፡ ሊወጡ
ትም ፡ አልቻሉም ፤ ለርሱ ፡ መሸን
ቆርንም ፡ አልቻሉም ።

98 ይህ ፡ (ግድብ) ፡ ከጌታዬ ፡ ችሮታ ፡
ነው ፤ የጌታየም ፡ ቀጠሮ ፡
በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ትክክል ፡ ምድር ፡
ያደርገዋል ፤ የጌታዬም ፡ ቀጠሮ ፡
የተረጋገጠ ፡ ነው ፤ አለ ።

99 በዚያም ፡ ቀን ፡ ከፊላቸውን ፡ በከ
ፊሉ ፡ የሚቀላቀሉ ፡ አድርገን ፡
እንተዋቸዋለን ፤ በቀንዱም ፡ ይነ
ፋል ፡ መሰብሰብንም ፡ እንሰበስባ
ቸዋለን ።

100 ገሀነምንም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ለከሓዲ
ዎች፡ በጣም ፡ ማቅረብን ፡ እናቀር
ባታለን ።

101 ለነዚያ፡ ዓይኖቻቸው ፡ ከግሣ
ጼዬ ፡ በሺፋን ፡ ውስጥ ፡ ለነበሩ
ትና ፡ መስማትንም ፡ የማይችሉ ፡
ለነበሩት ፡ (እናቀርባታለን) ።

---

1 በዓይን ፡ አስተያየት ፡ በወሃው ፡ ውስጥ ፡
የምትጠልቅ ፡ መስላ ።
2 ጎግ ፡ ማጎግ ፡ የተባሉት ፡ ሕዝቦች ።

102 እንዚያ ፡ የካዱት ፡ ባሮቼን ፡ ከኔ ፡ ሌላ ፡ አማልክት ፡ አድርገው ፡ መያዛቸውን ፡ (የማያስቆጣኝ ፡ አድርገው) ፡ አሰቡን ? እኛ ፡ ገሀነ ምን ፡ ለከሓዲዎች ፡ መስተንግዶ ፡ አዘጋጅተናል ።

103 ፡—በሥራዎች ፡ በጣም ፡ ከሳሪዎ ቹን ፡ እንንገራችሁን ? በላቸው ።

104 እነዚያ ፡ እነሱ ፡ ሥራን ፡ የሚያሳ ምሩ ፡ የሚመስላቸው ፡ ሲኾኑ ፡ በቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡ ሥራቸው ፡ የጠፋባቸው ፡ ናቸው ።

105 እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ በጌታቸው ፡ ማስረጃዎችና ፡ በመገናኘቱ ፡ የካ ዱት ፡ ናቸው ፤ ሥራዎቻቸውም ፡ ተበላሹ ፤ ለነሱም ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ (ጠቃሚ) ፡ ሚዛንን ፡ አናቆ ምላቸውም ።

106 (ነገሩ) ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በክሕደታ ቸው ፡ አንቀጾቼንና ፡ መልክተኞ ቼንም ፡ መሳለቂያ ፡ አድርገው ፡ በመያዛቸው ፡ ፍዳቸው ፡ ገሀነም ፡ ነው ።

107 እነዚያ ፡ ያመኑና ፡ መልካም ፡ ሥራዎችን ፡ የሠሩ ፡ የፊርደውስ ፡ ገነቶች ፡ (1) ለነሱ ፡ መስፈሪያ ፡ ናቸው ።

108 በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ከርሷ ፡ መዛወርን ፡ የማይፈልጉ ፡ ሲኾኑ ፤ (መስፈሪያቸው ፡ ነው) ።

109 ባሕሩ ፡ ለጌታዬ ፡ ቃላት ፡ (መጻ ፊያ) ፡ ቀለሞችን ፡ በኾነ ፡ ኖሮ ፡ ብጤውን ፡ ጭማሬ ፡ ብናመጣም ፡ እንኳ ፡ የጌታዬ ፡ ቃላት ፡ ከማለቋ ፡ በፊት ፡ ባሕሩ ፡ ባለቀ ፡ ነበር ፤ በላቸው ።

110 ፡—እኔ ፡ አምላካችሁ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ወደኔ ፡ የሚወረድልኝ ፡ ቢጤያ ችሁ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነኝ ፤ የጌታው ንም ፡ መገናኘት ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፤ መልካም ፡ ሥራን ፡ ይሥራ፤ በጌታውም ፡ መገዛት ፡ አንድንም፡ አያጋራ ፡ በላቸው ።

---

1 የወይን ፡ አትክልት ፡ የሞላባቸው ፡ ምርጥ ፡ ገነቶች ፡ ናቸው ።



19ኛ ፡ ሱረቱ ፡ መርየም ፡ (የማርያም ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 98 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 ከ.ሀ.የ.ዐ.ጸ ፡ (ካፍ ፡ ሃ ፡ ያ ፡ ዓይን ፡ ሷድ) ፡ (1)

2 (ይህ) ፡ ጌታህ ፡ ባሪያውን ፡ ዘከሪ ያን ፡ (2) በችሮታው ፡ ያወሳበት ፡ ነው ።

3 ጌታውን ፡ የምስጢርን ፡ ጥሪ ፡ በተጣራ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ።

4 አለ ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ! እኔ ፡ አጥ ንቴ ፡ ደከመ ፤ ራሴም ፡ በሺበት ፡ ተንቀለቀለ ፤ አንተንም ፡ በመለ መኔ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ! (ምንጊዜም)፡ ዕድለ ፡ ቢስ ፡ አልኾንኩም ።

5 እኔም ፡ ከበኋላዬ ፡ ዘመዶቼን ፡ (3) በእርግጥ ፡ ፈራሁ ፤ ሚስቴም ፡ መካን ፡ ነበረች ፡ ስለዚህ ፡ ከአ ንተ ፡ ዘንድ ፡ ለኔ ፡ ልጅን ፡ ስጠኝ ፤

6 የሚወርሰኝ ፡ ከያዕቆብ ፡ ቤተ ፡ ሰቦችም ፡ የሚወርስ ፡ የኾነን ፡ (ልጅ) ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ ! ተወዳ ጅም ፡ አድርገው ።

7 ፡—ዘከሪያ ፡ ሆይ ! እኛ ፡ በወንድ ፡ ልጅ ፡ ስሙ ፡ የሕያ ፡ (4) በኾነ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ሞክሼን ፡ ባላደረ ግንለት ፡ እናበስርሃለን ፤ (አለው) ።

8 ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ! ሚስቴ ፡ መ ካን ፡ የነበረች ፡ ስትኾን ፡ እኔም ፡ ከእርጅና ፡ ድርቀትን ፡ በእርግጥ ፡ የደረስኩ ፡ ስኾን ፡ እንዴት ፡ ልጅ ፡ ይኖረኛል ! አለ ።

9 (ጅብሪል) ፡ አለ ፡— (ነገሩ) ፡ እን ደዚሁ ፡ ነው ፤ ጌታህ ፡— ከአ ሁን ፡ በፊት ፡ ምንም ፡ ያልነበር ከውን ፡ የፈጠርኩህ ፡ ስኾን ፡ እርሱ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ቀላል ፡ ነው ፤ አለ ።

10 ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ! (እንግዲያስ) ፡ ለኔ ፡ ምልክትን ፡ አድርግልኝ ፡ አለ ፤ ምልክትህ ፡ ጤናማ ፡ ሆነህ ፡ ሳለህ ፡ ሦስት ፡ ሌሊትን ፡ (ከነቀ ናቸው) ፡ ሰዎችን ፡ ለማነጋገር ፡ አለመቻልህ ፡ ነው ፤ አለው ።

11 ከምኩራቡም ፡ በሕዝቦቹ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፤ በጧትና ፡ በማታ ፡ (ጌታች ሁን) ፡ አወድሱ ፡ በማለትም ፡ ወደ ነሱ ፡ ጠቀሰ ።

12 ፡—የሕያ ፡ ሆይ ! መጽሐፉን ፡ በጥብቅ ፡ ያዝ ! (አልነው) ፤ ጥበብ ንም ፡ በሕጻንነቱ ፡ ሰጠነው ።

13 ከኛም ፡ የኾነን ፡ ርኅራኄ ፡ ንጽሕ ናንም ፡ (ሰጠነው) ፤ ጥንቁቅም ፡ ነበር ።

14 ለወላጆቹም ፡ በጎ ፡ ሠሪ ፡ ነበር ፤ ትዕቢተኛ ፡ አመጠኛም ፡ አልነበ ረም ።

15 በተወለደበት ፡ ቀንና ፡ በሚሞትበ ትም ፡ ቀን ፡ ሕያው ፡ ኾኖ ፡ በሚነ

---

1 ለባሮቼ ፡ በቂ ፡ መሪ ፡ እጇ ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ዐዋቂ ፤ እውነተኛ ፡ ነኝ ።

2 ዘካሪያስን ።

3 ሃይማኖትህን ፡ ይበድላሉ ፡ ብዬ ።

4 ዮሐንስ ።

ሳበትም ፡ ቀን ፡ ሰላም ፡ በሱ ፡
ላይ ፡ ይኹን ።
16 በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ መርየም
ንም ፡ ከቤተ ፡ ሰቧ ፡ ወደ ፡ ምሥራ
ቃዊ ፡ ስፍራ ፡ በተለየች ፡ ጊዜ ፡
(የኾነውን ፡ ታሪኳን) ፡ አውሳ ።
17 ከነሱም ፡ መጋረጃን ፡ አደረገች ፡
መንፈሳችንንም ፡ (ጂብሪልን) ፡
ወደርሷ ፡ ላክን ፤ ለርሷም ፡ ትክክ
ለኛ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ተመሰለላት ።
18 ፡—እኔ ፡ ከአንተ ፡ በአልረሕማን ፡
እጠበቃለሁ ፤ ጌታህን ፡ ፈሪ ፡
እንደ ፡ ኾንክ ፡ (አትቅረበኝ) ፡
አለች ።
19 ፡—እኔ ፡ ንጹሕን ፡ ልጅ ፡ ለአንቺ ፡
ልሰጥሽ ፡ የጌታሽ ፡ መልክተኛ ፡
ነኝ ፡ አላት ።
20 (በጋብቻ) ፡ ሰው ፡ ያልነካኝ ፡
ኾኜ ፡ አመንዝራም ፡ ሳልኾን ፡
ለኔ ፡ እንዴት ፡ ልጅ ፡ ይኖረኛል !
አለች ።
21 አላት ፡— (ነገሩ) ፡ እንደዚህሽ ፡
ነው ፤ ጌታሽ ፡ ፡—እርሱ ፡ በእኔ ፡
ላይ ፡ ገር ፡ ነው ፤ ለሰዎችም ፡
ታምር ፡ ከኛም ፡ ችሮታ ፡ ልናደር
ገው ፡ (ይህንን ፡ ሥራን) ፡ የተፈረ
ደም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ አለ ፤ (ነፋባ
ትም) ።
22 ወዲያውኑም ፡ አረገዘችው ፤ በር
ሱም ፡ (በሆድዋ፡ ይዛው) ፡ ወደ ፡
ሩቅ ፡ ስፍራ ፡ ገለል ፡ አለች ።
23 ምጡም ፡ ወደ ፡ ዘንባባይቱ ፡
ግንድ ፡ አስጠጋት ፡ ዋ ፡ ምኞቴ !
ምነው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በሞትኩ ፤
ተረስቼም ፡ የቀረሁ ፡ በኾንኩ ፤
አለች ።
24 ከበታቿም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠ
ራት ፡— አትዘኝ ፤ ጌታሽ ፡ ከበታ
ችሽ ፡ ትንሽን ፡ ወንዝ ፡ በእርግጥ ፡
አድርጓል ።
25 የዘምባባይቱንም ፡ ግንድ ፡ ወዳ
ንቺ ፡ ወዝውዢት ፤ ባንቺ ፡ ላይ ፡
የበሰለን ፡ የተምር ፡ እሸት ፡ ታረግ
ፍልሻለችና ።
26 ብይም ፡ ጠጪም ፤ ተደሰችም ፤
ከሰዎችም ፡ አንድን ፡ ብታይ ፡—
እኔ ፡ ለአልረሕማን ፡ ዝምታን ፡
ተስያለሁ ፤ ዛሬም ፡ ሰውን ፡ በፍ
ጹም ፡ አላነጋግርም ፡ በይ ።
27 በርሱም ፡ የተሸከመቺው ፡ ኾና ፡
ወደ ፡ ዘመዶችዋ ፡ መጣች ፤—
መርየም ፡ ሆይ ፡ ከባድን ፡ ነገር ፡
በእርግጥ ፡ ሠራሽ ፡ አሏት ።
28 የሃሩን ፡ (1) እኅት ፡ ሆይ ! አባ
ትሽ ፡ መጥፎ ፡ ሰው ፡ አልነበረም፤
እናትሽም ፡ አመንዝራ ፡ አልነበረ
ችም ፡ አሉዋት ።
29 ወደርሱም ፡ ጠቀሰች ፤ በአንቀ
ልባ ፡ ያለን ፡ ሕፃን ፡ እንዴት ፡
እናናግራለን ! አሉ ።
30 (ሕፃኑም) ፡ አለ ፡— እኔ ፡ የአላህ ፡
ባሪያ ፡ ነኝ ፤ መጽሐፍን ፡ ሰጥቶ
ኛል ፡ ነቢይም ፡ አድርጎኛል ።
31 በየትም ፡ ስፍራ ፡ ብኾን ፡ ብሩክ ፡
አድርጎኛል ፤በሕይወትም ፡ እስከ፡
አለሁ ፡ ሶላትን ፡ በመስገድ ፡ ዘካ
ንም ፡ በመስጠት ፡ አዞኛል ።
32 ለእናቴም ፡ ታዛዥ ፡ (አድርጎ
ኛል) ፤ ትዕቢተኛ ፡ እምቢተኛም ፡
አላደረገኝም ።
33 ሰላምም ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ በተወ
ለድሁ ፡ ቀን ፡ በምሞትበትም ፡
ቀን ፡ ሕያው ፡ ኾኘ ፡ በምቀሰቀስ
በትም ፡ ቀን ፤

1 የአባትዋ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ የሙሳ ፡ ወንድም ፡
ሃሩን ፡ አይደለም ።



34 ይህ ፡ የመርየም ፡ ልጅ ፡ ዒሳ ፡
ነው ፤ ያ ፡ በርሱ ፡ የሚጠራጠሩ
በት ፡ እውነተኛ ፡ ቃል ፡ ነው ።
35 ለአላህ ፡ ልጅን ፡ መያዝ ፡ አይገባ
ውም ፤ (ከጉድለት ፡ ሁሉ) ፡ ጠራ ፤
ነገርን ፡ በሻ ፡ ጊዜ ፡ ለርሱ ፡ የሚ
ለው ፡ ኹን ፡ ነው ፡ ወዲያውም ፡
ይኾናል ።
36 (ዒሳ ፡ አለ) ፡-አላህም ፡ ጌታዬ ፡
ጌታችሁም ፡ ነውና ፡ ተገዙት ፤
ይህ ፡ ቀጥተኛ ፡ መንገድ ፡ ነው ።
37 ከመካከላቸውም ፡ አሕዛቦቹ ፡
በርሱ ፡ ነገር ፡ ተለያዩ ፤ ለነዚ
ያም ፡ ለካዱት ፡ ሰዎች ፡ ከታላቁ ፡
ቀን ፡ መጋፈጥ ፡ ወዮላቸው ።
38 በሚመጡን ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ሰሚ ፡
ምንስ ፡ ተመልካች ፡ አደረጋቸው!
ግን ፡ አመጠኞች ፡ ዛሬ ፡ (በዚህ ፡
ዓለም) ፡ በግልጽ ፡ ስሕተት ፡
ውስጥ ፡ ናቸው ።
39 እነሱም ፡ (አሁን) ፡ በዝንጋቴ ፡
ላይ ፡ ኾነው ፡ ሳሉ ፡ እነሱም ፡
የማያምኑ ፡ ሲኾኑ ፡ ነገሩ ፡ በሚፈ
ረድበት ፡ ጊዜ ፡ የቁልጭቱን ፡
ቀን ፡ አስፈራራቸው ።
40 እኛ ፡ ምድርን ፡ በርሷም ፡ ላይ ፡
ያለውን ፡ ሁሉ ፡ እኛ ፡ እንወርሳ
ለን ፤ ወደኛም ፡ ይመለሳሉ ።
41 በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ኢብራሂም
ንም ፡ አውሳ ፤ እርሱ ፡ በጣም ፡
እውነተኛ ፡ ነቢይ ፡ ነበርና ።
42 ላባቱ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ (አስታ
ውስ) ፡ ፡—አባቴ ፡ ሆይ ! የማይሰ
ማንና ፡ የማያይን ፡ ከአንተም ፡
ምንንም ፡ የማይጠቅምህን ፡ (ጣ
ዖት) ፡ ለምን ፡ ትግገዛለህ ?
43 አባቴ ፡ ሆይ! እኔ፡ ከዕውቀት፡ ያል
መጣልህ ፡ ነገር ፡ በእርግጥ ፡ መጥ
ቶልኛልና ፡ ተከተለኝ ፤ ቀጥተኛ
ውን ፡ መንገድ ፡ እመራሃለሁና ።
44 አባቴ ፡ ሆይ ! ሰይጣንን ፡ አት
ግገዛ ፤ ሰይጣን ፡ ለአልረሕማን ፡
አመጠኛ ፡ ነውና ።
45 አባቴ ፡ ሆይ! እኔ ፡ ከአልረሕማን ፡
ቅጣት ፡ ሊያገኝህ ፡ ለሰይጣንም ፡
ጓደኛ ፡ ልትኾን ፡ እፈራለሁ ።
46 (አባቱም) ፡— ኢብራሂም ፡ ሆይ !
አንተ ፡ ከአምላኮቼ ፡ ትተህ ፡ የም
ትዞር ፡ ነህን ? ባትከለከል ፡ በእር
ግጥ ፡ እወግርሃለሁ ፤ ረዢም ፡
ጊዜንም ፡ ተዎኝ ፡ አለ ።
47 ፡—ደህና ፡ ኹን ፤ ወደፊት ፡ ከጌ
ታየ ፡ ምሕረትን ፡ እለምንልሃ
ለሁ ፤ እርሱ ፡ ለኔ ፡ በጣም ፡ ርኅ
ሩህ ፡ ነውና ፡ አለ ፤
48 እናንተንም ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የምት
ግገዙትንም ፡ እርቃለሁ ፤ ጌታየ
ንም ፡ እግገዛለሁ ፤ ጌታየን ፡ በመገ
ዛት ፡ የማፍር ፡ አለመኾኔን ፡ እከ
ጅላለሁ ።
49 እነሱንም ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የሚግገ
ዙትንም ፡ በራቀ ፡ ጊዜ ፡ ለርሱ ፡
ኢስሐቅንና ፡ ያዕቆብን ፡ ሰጠነው፤
ሁሉንም ፡ ነቢይ ፡ አደረግንም ።
50 ለነሱም ፡ ከችሮታችን ፡ ሰጠና
ቸው ፤ ለነሱም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስ
ጉን ፡ ዝናን ፡ አደረግንላቸው ።
51 በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ሙሳንም ፡
አውሳ ፤ እርሱ ፡ ምርጥ ፡ ነበርና ፡
መልክተኛ ፡ ነቢይም ፡ ነበር ።
52 ከጡር ፡ ቀኝ ፡ ጐን ፡ በኩልም ፡
ጠራነው ፤ ያነጋገርነውም ፡ ሲኾን
አቀረብነው ።
53 ከችሮታችንም ፡ ወንድሙን ፡
ሃሩንን ፡ ነቢይ ፡ አድርገን ፡ ሰጠ
ነው ።

54 በመጽሐፉ ፡ ኢስማዒልንም ፡
አውሳ ፤ እርሱ ፡ ቀጠሮን ፡ አክ
ባሪ ፡ ነበረና ፤ መልክተኛ ፡ ነቢ
ይም ፡ ነበር ።
55 ቤተሰቦቹንም ፡ በሶላትና ፡ በዘካ ፡
ያዝ ፡ ነበር ፤ እጌታውም ፡ ዘንድ ፡
ተወዳጅ ፡ ነበር ።
56 በመጽሐፉ ፡ ኢድሪስንም ፡ (ሄኖ
ክን) ፡ አውሳ ፤ እርሱ ፡ እውነተኛ ፡
ነቢይ ፡ ነበርና ።
57 ወደ ፡ ከፍተኛም ፡ ስፍራ ፡ አነሳ
ነው ።
58 እነዚህ ፡ (ዐሥሩ) ፡ እነዚያ ፡
አላህ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ የለገሰላቸው ፡
ከነቢያት ፡ ከአዳም ፡ ዘር ፡ ከኑሕ ፡
ጋር ፡ (በመርከቢቱ ፡ ላይ) ፡ ከጫ
ናቸውም ፡ (ዘሮች) ፡ ከኢብራሂ
ምና ፡ ከእስራኤልም ፡ ዘሮች ፡
ከመራናቸውና ፡ ከመረጥናቸውም
የኾኑት ፡ የአልረሕማን ፡ አንቀ
ጾች ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ በተነበቡ ፡
ጊዜ ፡ ሰጋጆችና ፡ አልቃሾች ፡
ኾነው ፡ ይወድቃሉ ።
59 ከነሱም ፡ በኋላ ፡ ሶላትን ፡ ያጓ
ደሉ ፡ (የተው) ፡ ፍላጎቶችንም ፡
የተከተሉ ፡ መጥፎ ፡ ምትኮች ፡
ተተኩ! የገሀነምንም ፡ ሸለቆ ፡
በእርግጥ ፡ ያገኛሉ ።
60 ግን ፡ የተጸጸተና ፡ ያመነም ፡ በጎ
ንም ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ እነ
ዚህ ፡ ገነትን ፡ ይገባሉ ፤ አንዳች
ንም ፡ አይበደሉም ።
61 የመኖሪያን ፡ ገነቶች ፡ ያችን ፡
አልረሕማን ፡ ለባሮቹ ፡ በሩቅ ፡
ኾነው ፡ ሳሉ ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡ የገባ
ላቸውን ፡ (ይገባሉ) ፤ እርሱ ፡ ተስ
ፋው ፡ ተፈጻሚ ፡ ነውና ፤
62 በርሷ ፡ ሰላምን ፡ እንጂ ፡ ውድ
ቅን ፡ ነገር ፡ አይሰሙም ፤ ለነሱም፡
በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ጧትም ፡ ማታም ፡
ሲሳያቸው ፡ አላቸው ።
63 ይህች ፡ ያቺ ፡ ከባሮቻችን ፡ ጥንቁ
ቆች ፡ ለኾኑት ፡ የምናወርሳት ፡
ገነት ፡ ናት ።
64 (ጂብሪል ፤ አለ) ፡ በጌታህም ፡ ት
እዛዝ ፡ እንጅ ፡ አንወርድም ፤ በፊ
ታችን ፡ ያለው ፡ በኋላችንም ፡
ያለው ፡ በዚህም ፡ መካከል ፡ ያለ
ው ፡ ሁሉ ፡ የርሱ ፡ ነው ፤ ጌታ
ህም ፡ ረሺ ፡ አይደለም ።
65 (እርሱ) ፡ የሰማያትና ፡ የምድር፡ በ
ሁለቱም ፡ መካከል፡ ላለው፡ ሁሉ፡
ጌታ ፡ ነውና ፡ ተገዛው ፤ እርሱን ፡
በመገገዛትም ፡ ላይ ፡ ታገሥ ፤ ለ
ርሱ ፡ ሞክሼን ፡ ታውቃለህን ?
66 ሰውም፡ በሞትኩ፡ ጊዜ ፡ ወደፊት ፡
ሕያው ኾኜ ፡ (ከመቃብር) ፡ እወጥ
ጣለሁን ? ይላል ።
67 ሰው ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡ ምንም ፡
ነገር ፡ ያልነበረ ፡ ሲኾን ፡ እኛ ፡
የፈጠርነው ፡ መኾኑን ፡ አያስታ
ውስምን ?
68 በጌታህ ፡ እንምላለን ፡ ሰይጣናት ፡
ጋር ፡ በእርግጥ ፡ እንሰበስባቸዋ
ለን ፤ ከዚያም ፡ በገሀነም ፡ ዙሪያ ፡
የተንበረከኩ ፡ ኾነው ፤ በእርግጥ ፡
እናቀርባቸዋለን ።
69 ከዚያም ፡ ከየጭፍሮቹ ፡ ሁሉ ፡
ከነርሱ ፡ ያንን ፡ (እርሱ) ፡ በአልረ
ሕማን ፡ ላይ ፡ በድፍረት ፡ በጣም ፡
ብርቱ ፡ የኾነውን ፡ እናወጣለን ፡
70 ከዚያም ፡ እኛ ፡ እነዚያን ፡ እነሱ ፡
በርሷ ፡ ለመግባት ፡ ተገቢ ፡ የኾ
ኑትን ፡ እናውቃለን ።
71 ከእናንተም ፡ ወደ ፡ እርሷ ፡ ወራጅ
እንጂ ፡ አንድም ፡ የለም ፤ (መውረ
ዷም) ፡ ጌታህ ፡ የፈረደው ፡ ግዴታ
ነው ።



72 ከዚያም ፡ እነዚያን ፡ የተጠነቀቁ
ትን ፡ እናድናለን ፤ አመጠኞቹ
ንም ፡ የተንበረከኩ ፡ ኾነው ፡ በው
ስጧ ፡ እንተዋቸዋለን ።
73 በነሱም ፡ ላይ ፡ አንቀጾቻችን ፡
ግልጽ ፡ ማስረጃዎች ፡ ኾነው ፡
በተነበቡ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ የካ
ዱት ፡ ለነዚያ ፡ ላመኑት ፡-ከሁ
ለቱ ፡ ክፍሎች ፡ መኖሪያው ፡ የሚ
በልጠውና ፡ ሸንጎውም ፡ ይበ
ልጥ ፡ የሚያምረው ፡ ማንኛው ፡
ነው ፡ ይላሉ ።
74 ከነሱም ፡ በፊት ፡ ከክፍለ ፡ ዘመ
ናት ፡ ሕዝቦች ፡ እነሱ ፡ በቁሳቁ
ስና ፡ በትርኢትም ፡ በጣም ፡ ያማ
ሩትን ፡ ብዙዎችን ፡ አጥፍተናል ።
75 ፡—በስሕተት ፡ ውስጥ ፡ የኾነ ፡
ሰው ፡ አልረሕማን ፡ ለርሱ ፡ ማዘ
ግየትን ፡ ያዘገየዋል ፡ (1) የሚዛት
ባቸውንም ፡ ወይም ፡ ቅጣቱን ፡
ወይም ፡ ሰዓቲቱን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡
እርሱ ፡ ስፍራው ፡ መጥፎና ፡ ሰራ
ዊቱ ፡ ደካማ ፡ የኾነው ፡ ሰው ፡
ማን ፡ እንደኾነ ፡ በእርግጥ ፡ ያው
ቃሉ ፤ በላቸው ።
76 እነዚያንም ፡ የቀኑትን ፡ ሰዎች ፡
አላህ ፡ ቅንነትን ፡ ይጨምርላቸ
ዋል ፤ መልካሞቹ ፡ ቀሪዎች ፡
(ሥራዎች) ፡ እጌታህ ፡ ዘንድ ፡
በምንዳ ፡ በላጭ ፡ ናቸው ፤ በመመ
ለሻም ፡ የተሻሉ ፡ ናቸው ።
77 ያንንም ፡ በአንቀጾቻችን ፡ የካደ
ውን ፡ (በትንሣኤ ፡ ቀን) ፡ ገንዘ
ብም ፡ ልጅም ፡ በእርግጥ ፡ እሰጣ
ለሁ ፡ ያለውንም ፡ አየህን?
78 ሩቁን ፡ ምስጢር ፡ ዐወቀን ?
ወይስ ፡ አልረሕማን ፡ ዘንድ ፡
ቃል ፡ ኪዳንን ፡ ያዘ?
79 ይከልከል ፤ (አይሰጠውም) ፡ የሚ
ለውን ፡ ሁሉ ፡ በእርግጥ ፡ እንጽ
ፋለን ፤ ለርሱም ፡ ከቅጣት ፡ ጪማ
ሬን ፡ እንጨምርለታለን ።
80 (አልለ'ኝ) ፡ የሚለውንም ፡ ሁሉ ፡
እንወርሰዋለን ፤ ብቻውንም ፡ ኾኖ
ይመጣናል ።
81 ከአላህም ፡ ሌላ ፡ አማልክትን ፡
ለነሱ ፡ መከበሪያ ፡ (አማላጅ) ፡
እንዲኾኑዋቸው ፡ ያዙ ፤
82 ይከልከሉ ፤ መገዛታቸውን ፡ በእር
ግጥ ፡ ይክዷቸዋል ፤ በነሱም ፡
ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ ይኾኑባቸዋል ።
83 እኛ ፡ ሰይጣናትን ፡ በከሓዲዎች ፡
ላይ ፡ (በመጥፎ ፡ ሥራ) ፡ ማወባ
ራትን ፡ የሚያወባሩዋቸው ፡ ሲ
ኾኑ ፡ የላክን ፡ መኾናችንን ፡ አላ
የህምን ?
84 በነሱም ፡ (መቀጣት) ፡ ላይ ፡ አት
ቻኮል ፤ ለነሱ ፡ (ቀንን) ፡ መቁጠ
ርን ፡ እንቆጥርላቸዋለንና ።
85 ምእምናንን ፡ የተከበሩ ፡ ጭፍ
ሮች ፡ ኾነው ፡ ወደ ፡ አልረሕማን ፡
የምንሰበስብበትን ፡ ቀን ፡ (አስ
ታውስ) ።
86 ከሓዲዎችንም ፡ የተጠሙ ፡ ኾ
ነው ፡ ወደ ፡ ገሀነም ፡ የምንነዳበ
ትን ፡ (ቀን ፡ አስታውስ) ።
87 አልረሕማን ፡ ዘንድ ፡ ቃል ፡ ኪዳ
ንን ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ እንጂ ፡
ማማለድን ፡ አይችሉም ።
88 ፡—አልረሕማንም ፡ ልጅን ፡ ያዘ ፡
(ወለደ) ፡ አሉ ፤
89 ከባድ ፡ መጥፎን ፡ ነገር ፡ በእር
ግጥ ፡ አመጣችሁ ፤

---
1 አዘናግቶ ፡ ለመያዝ ፡ ጊዜ ፡ ይሰጠዋል ,
ሀብቱንም ፡ ያፋፋለታል ።

90 ከርሱ ፡ (ከንግግራቸው) ፡ ሰማያት ፡ ሊቀደዱ ፡ ምድርም ፡ ልትሰነጠቅ ፡ ጋራዎችም ፡ ተንደው ፡ ሊወድቁ ፡ ይቃረባሉ ፤

91 ለአልረሕማን ፡ ልጅ ፡ አለው ፡ ስለ ፡ አሉ ።

92 ለአልረሕማን ፡ ልጅን ፡ መያዝ ፡ አይገባውም ።

93 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ (በትንሣኤ ፡ ቀን) ፡ ለአልረሕማን ፡ ባሪያ ፡ ኾነው ፡ የሚመጡ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደሉም ።

94 በእርግጥ ፡ (በዕውቀቱ) ፡ ከቧቸዋል ፤ መቍጠርንም ፡ ቆጥሯቸዋል ።

95 ሁሉም ፤ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ለየብቻ ፡ ኾነው ፡ ወደርሱ ፡ መጪዎች ፡ ናቸው ።

96 እነዚያ ፡ ያመኑና ፡ በጎ ፡ ሥራዎችን ፡ የሠሩ ፡ አልረሕማን ፡ ለነሱ ፡ ውዴታን ፡ ይሰጣቸዋል ።

97 በምላስህም ፡ (ቁርአንን) ፡ ያገራነው ፡ በርሱ ፡ ጥንቁቆቹን ፡ ልታበስርበት ፡ በርሱም ፡ ተከራካሪዎችን ፡ ሕዝቦች ፡ ልታስፈራራበት ፡ ነው ።

98 ከነሱም ፡ በፊት ፡ ከክፍለ ፡ ዘመናት ፡ ሕዝቦች ፡ ብዙዎችን ፡ አጥፍተናል ፤ ከነሱ ፡ አንድን ፡ እንኳ ፡ ታያለህን ? ወይስ ፡ ለነሱ ፡ ሹክሹክታን ፡ ትሰማለህን ?

## ምዕራፍ ፡ 20 ፡ ጣሃ ። ክፍል ፡ 16 ።

20ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ጣሃ ፡ (የጣሃ ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 135 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 ጠ. ሀ. (ጣ ፡ ሃ) ፡ (1)

2 ቁርአንን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ እንድትቸገር ፡ አላወረድንም ።

3 ግን ፡ አላህን ፡ ለሚፈራ ፡ ሰው ፡ መገሠጫ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ (አወረድነው) ።

4 ምድርንና ፡ የላይኞዎቹን ፡ ሰማያት ፡ ከፈጠረ ፡ አምላክ ፡ ተወረደ ።

1 አንተ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ምድርን ፡ እርገጣት ።

5 (እርሱ) ፡ አልረሕማን ፡ ነው ፡ በዐርሹ ፡ ላይ ፡ (ሥልጣኑ) ፡ ተደላደለ ።

6 በሰማያት ፡ ያለው ፡ በምድርም ፡ ያለው ፡ በመካከላቸውም ፡ ያለው ፡ ከዐፈር ፡ በታችም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

7 በንግግር ፡ ብትጮህ ፡ (አላህ ፡ ከጩኸቱ ፡ የተብቃቃ ፡ ነው) ፤ እርሱ ፡ ምስጢርን ፡ በጣም ፡ የተደበቀንም ፡ ያውቃልና ።

8 አላህ ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ ለርሱ ፡ መልካሞች ፡ የኾኑ ፡ ስሞች ፡ አሉት ።



9 የሙሳም ፡ ወሬ ፡ በእርግጥ ፡ መጥቶሃል ፤

10 እሳትን ፡ ባየና ፡ ለቤተሰቦቹ ፡— (እዚህ) ፡ ቆዩ ፤ እኔ ፡ እሳትን ፡ አየሁ ፤ ከርሷ ፡ ችቦን ፡ ላመጣላችሁ ፤ ወይም ፡ እሳቲቱ ፡ ዘንድ ፡ መሪን ፡ ላገኝ ፡ እከጅላለሁ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ።

11 በመጣትም ፡ ጊዜ ፡ ሙሳ ፡ ሆይ ፡ በማለት ፡ ተጠራ ፤

12 እኔ ፡ ጌታህ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ መጫሚያዎችህንም ፡ አውልቅ ፤ አንተ ፡ በተቀደሰው ፡ ሸለቆ ፡ በጡዋ ፡ ነህና ፤

13 እኔም ፡ መረጥኩህ ፤ የሚወረድልህንም ፡ ነገር ፡ አዳምጥ ፤

14 እኔ ፡ አላህ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ያለ ፡ እኔ ፡ አምላክ ፡ የለምና ፡ ተገዛኝ ፤ ሶላትንም ፡ (በርሷ) ፡ እኔን ፡ ለማውሳት ፡ ስገድ ።

15 ሰዓቲቱ ፡ (1) በእርግጥ ፡ መጪ ፡ ናት ፤ ልደብቃት ፡ እቃረባለሁ ፤ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ በምትሠራው ፡ ነገር ፡ ትመነዳ ፡ ዘንድ ፡ (መጪ ፡ ናት) ።

16 በርሷ ፡ የማያምነውና ፡ ዝንባሌውን ፡ የተከተለውም ፡ ሰው ፡ ከርሷ ፡ (2) አያግድህ ፡ ትጠፋለህና ።

17 ሙሳ ፡ ሆይ ! ይህችም ፡ በቀኝ ፡ እጅህ ፡ ያለችው ፡ ምንድን ፡ ናት? (ተባለ) ።

18 ፡—እርሷ ፡ በትሬ ፡ ናት ፤ በርሷ ፡ ላይ ፡ እደገፍባታለሁ ፤ በርሷም ፡ ለፍየሎቼ ፡ ቅጠልን ፡ አረግፍባታለሁ ፤ ለኔም ፡ በርሷ ፡ ሌሎች ፡ ጉዳዮች ፡ አሉኝ ፡ አለ ።

1 ዕለተ ፡ ትንሣኤ ።
2 በርሷ ፡ ከማመን ።

19 (አላህም) ፡ ሙሳ ፡ ሆይ ! ጣላት ፡ አለው ።

20 ጣላትም ፤ ወዲያውም ፡ እርሷ ፡ የምትሮጥ ፡ እባብ ፡ ኾነች ።

21 ፡—ያዛት ፤ አትፍራም ፤ ወደ ፡ መጀመሪያ ፡ ጠባይዋ ፡ እንመልሳታለን ፡ አለው ።

22 እጅህንም ፡ ወደ ፡ ብብትህ ፡ አግባ ፡ ሌላ ፡ ታምር ፡ ስትኾን ፡ ያለ ፡ ነውር ፡ ነጭ ፡ ኾና ፡ ትወጣለችና ።

23 ከታምራቶቻችን ፡ ታላቋን ፡ እናሳይህ ፡ ዘንድ ፡ (ይህን ፡ ሠራን) ።

24 ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ኺድ ፤ እርሱ ፡ ወሰን ፡ አልፏልና ።

25 (ሙሳም) ፡ አለ ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ! ልቤን ፡ አስፋልኝ ።

26 ነገሬንም ፡ ለኔ ፡ አግራልኝ ።

27 ከምላሴም ፡ መኮላተፍን ፡ ፍታልኝ ።

28 ንግግሬን ፡ ያውቃሉና ።

29 ከቤተሰቦቼም ፡ ለኔ ፡ ረዳትን ፡ አድርግልኝ ፤

30 ሃሩንን ፡ ወንድሜን ።

31 ኀይሌን ፡ በርሱ ፡ አበርታልኝ ።

32 በነገሬም ፡ አጋራው ።

33 በብዙ ፡ እናጠራህ ፡ ዘንድ ።

34 በብዙም ፡ እንድናወሳህ ።

35 አንተ ፡ በኛ ፡ ነገር ፡ ዐዋቂ ፡ ነህና ።

36 (አላህም) ፡ አለ ፡— ሙሳ ፡ ሆይ! ልመናህን ፡ በእርግጥ ፡ ተሰጠህ ።

37 በሌላም ፡ ጊዜ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ ለግሰናል ፤

38 ወደናትህ ፡ በልብ ፡ የሚፈስን ፡ ነገር ፡ ባሳወቅን ፡ ጊዜ ፤

39 (ሕፃኑን) ፡ በሳጥኑ ፡ ውስጥ ፡ ጣ
ይው ፤ እርሱንም ፡ (ሳጥኑን) ፡
በባሕር ፡ ላይ ፡ ጣይው ፤ ባሕ
ሩም ፡ በዳርቻው ፡ ይጣለው ፤
ለኔ ፡ ጠላት ፡ ለርሱም ፡ ጠላት ፡
የኾነ ፡ ሰው ፡ ይይዘዋልና ፡ በማ
ለት ፡ (ባሳወቅን ፡ ጊዜ ፡ ለገስን
ልህ) ፤ ባንተ ፡ ላይም ፡ ከኔ ፡ የኾ
ነን ፡ መወደድ ፡ ጣልኩብህ ፤
(ልትወደድና) ፡ በኔም ፡ ጥበቃ ፡
ታድግ ፡ ዘንድ ፤
40 እኅትህም ፡ በምትኼድና ፡ የሚያሳ
ድገውን ፡ ሰው ፡ ላመላከታችሁን ?
በምትል ፡ ጊዜ ፡ (መወደድን ፡ ጣ
ልኩብህ) ፤ ወደ ፡ እናትህም ፡ ዓይ
ንዋ ፡ እንዲረጋ ፡ (እርሷ) ፡ እንዳታ
ዝንም ፡ መለስንህ ፤ ነፍስንም ፡ ገደ
ልክ ፤ ከጭንቅም ፡ አዳንንህ ፤ ፈተ
ናዎችንም ፡ ፈተንህ ፤ በመድየን ፡
ቤተሰቦችም ፡ ውስጥ ፡ (ብዙ) ፡ ዓ
መታትን ፡ ተቀመጥክ ፤ ከዚያም ፡
ሙሳ ፡ ሆይ! በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡
መጣህ ።
41 ለነፍሴም ፡ (በመልክቴ) ፡ መረጥ
ኩህ ።
42 አንተም ፡ ወንድምህም ፡ በታምራ
ቶቼ ፡ ኺዱ ፤ እኔንም ፡ ከማው
ሳት ፡ አትቦዝኑ ።
43 ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ኺዱ ፤ እርሱ ፡
ወሰን ፡ አልፏልና ።
44 እርሱም ፡ ይገሠጥ ፡ ወይም ፡
ይፈራ ፡ ዘንድ ፤ ለርሱ ፡ ልዝብን ፡
ቃል ፡ ተናገሩት ።
45 ፡—ጌታችን ፡ ሆይ ! እኛ ፡ በኛ ፡
ላይ ፡ ክፋት ፡ በመሥራት ፡ መቸ
ኮሉን ፡ ወይም ፡ ኩራትን ፡ መጨ
መሩን ፡ እንፈራለን ፡ አሉ ።
46 (አላህም) ፡ አለ ፡— አትፍሩ ፤
እኔ ፡ በእርግጥ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡
ንኝና ፤ እሰማለሁ ፤ አያለሁም ።
47 ወደርሱም ፡ ኺዱ ፤ በሉትም ፡—
እኛ ፡ የጌታህ ፡ መልክተኞች ፡
ነን ፤ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡
ከኛ ፡ ጋር ፡ ልቀቅ ፤ አታሰቃያቸ
ውም ፤ ከጌታህ ፡ በኾነው ፡ ታ
ምር ፡ በእርግጥ ፡ መጥተንሃልና ፤
ሰላምም ፡ ቀጥታን ፡ በተከተለ ፡
ሰው ፡ ላይ ፡ ይኹን ።
48 እኛ ፡ ቅጣቱ ፡ ባስተባበለና ፡ እምቢ ፡
ባለ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ማለት ፡
በእርግጥ ፡ ተወረደልን ።
49 (ፈርዖንም) ፡— ሙሳ ፡ ሆይ ፡ ጌታ
ችሁ ፡ ማነው? አለ ።
50 ጌታችን ፡ ያ ፡ ለፍጥረቱ ፡ ነገርን ፡
ሁሉ ፡ (የሚያስፈልገውን) ፡ የ
ሰጠ ፡ ከዚያም ፡ የመራው ፡ ነው ፡
አለው ።
51 (ፈርዖንም) ፡ የመጀመሪያይቱ ፡
ዘመናት ፡ ሕዝቦች ፡ ኹኔታ ፡ ምን
ድን ፡ ነው ? አለ ።
52 (ሙሳም) ፡ ዕውቀትዋ ፡ እጌታዬ ፡
ዘንድ ፡ በመጽሐፍ ፡ የተመዘገበ ፡
ነው ፤ ጌታዬ ፡ አይሳሳትም ፡ አይረ
ሳምም ፡ አለው ።
53 (እርሱ) ፡ ያ ፡ ምድርን ፡ ለናንተ ፡
ምንጣፍ ፡ ያደረገላችሁ ፡ በር
ሷም ፡ ውስጥ ፡ ለናንተ ፡ መን
ገድን ፡ ያገራላችሁ ፡ ውሃንም ፡
ከሰማይ ፡ ያወረደ ፡ ነው ፡ (አለ) ።
በርሱም ፡ ከተለያየ ፡ በቃይ ፡ ዓይ
ነቶችን ፡ አወጣንላችሁ ፤
54 ብሉ ፡ እንስሳዎቻችሁንም ፡ አ
ግጡ ፤ (ባዮች ፡ ኾነን ፡ አወጣንላ
ችሁ) ፡ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ለአእምሮ ፡
ባለቤቶች ፡ በእርግጥ ፡ ታምራት ፡
አለበት ።
55 ከርሷ ፡ (ከምድር) ፡ ፈጠርናችሁ ፤
በርሷም ፡ ውስጥ ፡ እንመልሳችኋ



ለን ፤ ከርሷም ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ እና
ወጣችኋለን ።
56 ታምራቶቻችንንም ፡ ሁሏንም ፡ (ለ
ፈርዖን) ፡ በእርግጥ ፡ አሳየነው ፤
አስተባበለም ፤ እምቢም ፡ አለ ።
57 ከምድራችን ፡ በድግምትህ ፡ ልታ
ወጣን ፡ መጣህብን? ሙሳ ፡ ሆይ!
አለ ።
58 መሰሉንም ፡ ድግምት ፡ እናመጣ
ብሃለን ፤ በኛና ፡ ባንተም ፡ መካ
ከል ፡ እኛም ፡ አንተም ፡ የማንጥ
ሰው ፡ የኾነ ፡ ቀጠሮን ፡ በመካከ
ለኛ ፡ ስፍራ ፡ አድርግልን ፡ አለ ።
59 ቀጠሯችሁ ፡ በማጌጫው ፡ ቀን ፡
ሰዎቹም ፡ በረፋድ ፡ በሚሰበሰቡ
በት ፡ ነው ፡ አለ ።
60 ፈርዖንም ፡ ዞረ ፤ ተንኮሉንም ፡
ሰበሰበ ፤ ከዚያም ፡ መጣ ።
61 ሙሳ ፡ ለነሱ ፡ አላቸው ፡— ወዮላ
ችሁ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ውሸትን ፡
አትቅጠፉ ፤ በቅጣት ፡ ያጠፋችኋ
ልና ፤ የቀጠፈም ፡ ሰው ፡ በእር
ግጥ ፡ አፈረ ።
62 (ድግምተኞቹ) ፡ በመካከላቸውም ፡
ነገራቸውን ፡ ተጨቃጨቁ ፤ ውይ
ይትንም ፡ ደበቁ ።
63 እነዚህ ፡ በእርግጥ ፡ ደጋሚዎች ፡
ናቸው ፤ ከምድራችሁ ፡ በድግም
ታቸው ፡ ሊያወጧችሁ ፡ በላጪ
ቱንም ፡ መንገዳችሁን ፡ ሊያስወ
ግዱባችሁ ፡ ይሻሉ ፡ አሉ ።
64 ተንኮላችሁንም ፡ አጠንክሩ ፤ ከዚ
ያም ፡ ተሰልፋችሁ ፡ ኑ ፤ ዛሬ ፡
ያሸነፈም ፡ ሰው ፡ ምኞቱን ፡
አገኘ ፡ (ተባባሉ) ።
65 ሙሳ ፡ ሆይ ! ወይ ፡ ትጥላለህ ፡
ወይም ፡ በመጀመሪያ ፡ የምንጥል ፡
እንኾናለን ፡ (ምረጥ) ፡ አሉ ።
66 አይደለም ፡ ጣሉ ፡ አላቸው ፤ ወዲ
ያውም ፡ ገመዶቻቸውና ፡ ዘንጎቻ
ቸው ፡ ከድግምታቸው ፡ የተነሳ ፡
እነርሱ ፡ የሚሮጡ ፡ (እባቦች) ፡
ኾነው ፡ ወደርሱ ፡ ተመሰሉ ።
67 ሙሳም ፡ በነፍሱ ፡ ውስጥ ፡ ፍር
ሃትን ፡ አሳደረ ።
68 ፡—አትፍራ ፡ አንተ ፡ የበላዩ ፡
አንተ ፡ ነህና ፡ አልነው ።
69 በቀኝ ፡ እጅህ ፡ ያለችውንም ፡
በትር ፡ ጣል ፤ ያንን ፡ የሠሩትን ፡
ትውጣለችና ፤ ያ ፡ የሠሩት ፡ ሁሉ ፡
የድግምተኛ ፡ ተንኮል ፡ ነውና ፤
ድግምተኛም ፡ በመጣበት ፡ ስፍራ ፡
ሁሉ ፡ አይቀናውም ፡ (አልን) ።
70 ድግምተኞቹም ፡ ሰጋጆች ፡ ኾነው
ወደቁ ፤ በሃሩንና ፡ በሙሳ ፡ ጌታ ፡
አመንን ፡ አሉ ።
71 (ፈርዖንም) ፡ ለናንተ ፡ ሳልፈቅድ
ላችሁ ፡ በፊት ፡ ለርሱ ፡ አመናች
ሁን ? እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ ያ ፡ ድግ
ምትን ፡ ያስተማራችሁ ፡ ትልቃ
ችሁ ፡ ነው ፤ እጆቻችሁንና ፡ እግ
ሮቻችሁን ፡ በማናጋት ፡ (ግራና ፡
ቀኝን ፡ በማፈራረቅ) ፡ እቆራርጣ
ችኋለሁ ፤ በዘምባባም ፡ ግንዶች ፡
ላይ ፡ እሰቅላችኋለሁ ፤ ማንኛች
ንም ፡ ቅጣቱ ፡ በጣም ፡ ብርቱ ፡
የሚቆይም ፡ መኾኑን ፡ ታውቃላ
ችሁ ፡ አላቸው ።
72 ከመጡልን ፡ ታምራቶችና ፡ ከዚ
ያም ፡ ከፈጠረን ፡ (አምላክ) ፡
ፈጽሞ ፡ አንመርጥህም ፤ አንተም ፡
የምትፈርደውን ፡ ፍረድ ፤ የምትፈ
ርደው ፡ በዚች ፡ በአነስተኛይቱ ፡
ሕይወት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ አሉ ።
73 ኃጢአቶቻችንንና ፡ ከድግምትም ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ ያስገደድከንን ፡
ለኛ ፡ ይምረን ፡ ዘንድ ፡ እኛ ፡

በጌታችን ፡ አምነናል ፤ አላህም ፡
በጣም ፡ በላጭ ፡ ነው ፤ (ቅጣ
ቱም) ፡ በጣም ፡ የሚዘወትር ፡
ነው ፡ አሉ ።
74 እነሆ ፡ ከሓዲ ፡ ኾኖ ፡ ወደ ፡
ጌታው ፡ የሚመጣ ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡
ገሀነም ፡ አለችው ፤ በውስጧም ፡
አይሞትም ፡ ሕያውም ፡ አይኾን ።
75 በጎ ፡ ሥራዎችን ፡ በእርግጥ ፡
የሠራ ፡ ምእምን ፡ ኾኖ ፡ የመጣ
ውም ፡ ሰው ፡ እነዚያ ፡ ለነሱ ፡
ከፍተኛ ፡ ደረጃዎች ፡ አሏቸው ።
76 ከስሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱ
ባቸው ፡ የመኖሪያ ፡ ገነቶች ፡ በው
ስጣቸው ፡ ዘውታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡
(አሏቸው) ፤ ይህም ፡ የተጥራራ ፡
ሰው ፡ ምንዳ ፡ ነው ።
77 ወደ ፡ ሙሳም ፡ ባሮቼን ፡ ይዘህ ፡
በሌሊት ፡ ኺድ ፤ ለነሱም ፡ በባ
ሕር ፡ ውስጥ ፡ ደረቅ ፡ መንገድን ፡
አድርግላቸው ፤ መገኘትን ፡ አት
ፍራ ፤ (ከመስጠም) ፡ አትጨነቅ
ቅም ፡ ስንል ፡ በእርግጥ ፡ ላክን
በት ።
78 ፈርዖንም ፡ ከሰራዊቱ ፡ ጋር ፡
ኾኖ ፡ ተከተላቸው ፤ ከባሕሩም ፡
የሚሸፍን ፡ ሸፈናቸው ።
79 ፈርዖንም ፡ ሕዝቦቹን ፡ አሳሳታ
ቸው ፤ ቅኑንም ፡ መንገድ ፡ አልመ
ራቸውም ።
80 የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፡ ከጠ
ላታችሁ ፡ በእርግጥ ፡ አዳንናችሁ ፤
በጡርም ፡ ቀኝ ፡ ጐን ፡ ቀጠሮ ፡
አደረግንላችሁ ፤ በናንተም ፡ ላይ ፡
መናንና ፡ ድርጭትን ፡ አወረድን
ላችሁ ።
81 ከሰጠናችሁ ፡ ሲሳይ ፤ ከመል
ካሙ ፡ ብሉ ፤ በርሱም ፡ ወሰንን ፡
አትለፉ ፤ ቁጣዬ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
ይወርድባችኋልና ፤ በርሱም ፡
ላይ ፡ ቁጣዬ ፡ የሚወርድበት ፡
ሰው ፡ በእርግጥ ፡ ይጠፋል ።
82 እኔም ፡ ለተጸጸተ ፡ ላመነም ፡ መል
ካምንም ፡ ለሠራ ፡ ከዚያም ፡ ለተ
መራ ፡ ሰው ፡ በእርግጥ ፡ መሓሪ ፡
ነኝ ።
83 ሙሳ ፡ ሆይ ! ከሕዝቦችህ ፡ ምን ፡
አስቸኮለህም ? (ተባለ) ።
84 እነሱ ፡ እነዚህ ፤ በዱካዬ ፡ ላይ ፡
ያሉ ፡ ናቸው ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ ! ትወ
ድልኝም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡
ቸኮልኩ ፡ አለ ።
85 (አላህ) ፡ እኛም ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፤
ሰዎችህን ፡ በእርግጥ ፡ ፈትተን ፤
ሳምራዊውም ፡ አሳሳታቸው ፡
አለው ።
86 ሙሳም ፡ ወደ ፡ ሰዎቹ ፡ የተቆጣ ፡
ያዘነ ፡ ኾኖ ፡ ተመለሰ ፤ ሕዝቦቼ ፡
ሆይ ፡ ጌታችሁ ፡ መልካም ፡ ተስ
ፋን ፡ አልቀጠራችሁምን ? ቀጠ
ሮው ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ረዘመባች
ሁን ? ወይስ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
ከጌታችሁ ፡ ቅጣት ፡ ሊወርድባ
ችሁ ፡ ፈለጋችሁና፡ ቀጠሮየን ፡
አፈረሳችሁን ? አላቸው ።
87 ቀጠሮህን ፡ በፈቃዳችን ፡ አልጣስ
ንም ፤ ግን ፡ እኛ ፡ ከሕዝቦቹ ፡
ጌጥ ፡ ሸክሞችን ፡ ተጫንን ፡ (1)
(በእሳት ፡ ላይ) ፡ ጣልናትም ፤ ሳም
ራዊውም ፡ እንደዚሁ ፡ ጣለ ፡
አሉት ።
88 ለነሱም ፡ አካል ፡ የኾነ ፡ ጥጃን ፡
ለርሱ ፡ መንጎር ፡ ያለውን ፡ አወጣ
ላቸው ፤ (ተከታዮቹ) ፡ ይህ ፡ አም

1 ተሸከምን ።



ላካችሁ ፡ የሙሳም ፡ አምላክ ፡
ነው ፤ ግን ፡ ረሳው ፡ አሉም ።
89 ወደነሱ ፡ ንግግርን ፡ የማይመልስ፡
ለነሱም ፡ ጉዳትንና ፡ ጥቅምን ፡
የማይችል ፡ መኾኑን ፡ አያዩምን?
90 ሃሩንም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ በእር
ግጥ ፡ አላቸው ፡- ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ፡
(ይህ) ፡ በርሱ ፡ የተሞከራችሁበት ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ ጌታችሁም ፡ አልረ
ሕማን ፡ ነው ፤ ተከተሉኝም ፤ ትእ
ዛዜንም ፡ ስሙ ።
91 ሙሳ ፡ ወደኛ ፡ እስከሚመለስ ፡
በርሱ ፡ (መገዛት) ፡ ላይ ፡ ከመቆ
የት ፡ ፈጽሞ ፡ አንወገድም ፡ አሉ ።
92 (ሙሳ) ፡ አለ ፡- ሃሩን ፡ ሆይ ፡ ተሳ
ስተው ፡ ባየሃቸው ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡
ከለከለህ ?
93 እኔን ፡ ከመከተል ፤ ትእዛዜን ፡
ጣስክን ?
94 የእናቴ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ጢሜንም ፡
ራሴንም ፡ አትያዝ ፤ እኔ ፡ በእስራ
ኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ለያየህ ፡
ቃሌንም ፡ አልጠበቅህም ፡ ማለት
ህን ፡ ፈራሁ ፡ አለው ።
95 (ሙሳ) ፡ ሳምራዊው ፡ ሆይ ፡ ነገር
ህም ፡ ምንድን ፡ ነው ? አለ ።
96 ያላዩትን፡ ነገር ፡ (1) አየሁ ፤ ከመ
ልክተኛው ፡ (ከፈረሱ ፡ ኮቴ) ፡
ዱካም ፡ ጭብጥ ፡ ዐፈርን ፡ ዘገ
ንኩ ፤ (በቅርፁ ፡ ላይ) ፡ ጣልኳ
ትም ፤ እንደዚሁም ፡ ነፍሴ ፡ ሸለ
መችልኝ ፡ አለ ።
97 አለው ፡— ኺድ ፤ ላንተም ፡ በሕይ
ወትህ ፡ (ለአየኸው ፡ ሰው ፡ ሁሉ)፡
መነካካት ፡ የለም ፡ ማለት ፡ አለህ፤
ለአንተም ፡ ፈጽሞ ፡ የማትጣሰው፡
(1) ቀጠሮ ፡ አለህ ፤ ወደዚያም ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ ተገገርው ፡ ኾነህ ፡
ወደ ፡ ቆየህበት ፡ አምላክህ ፡ ተመ
ልከት ፤ በእርግጥ ፡ እናቃጥለዋ
ለን ፤ ከዚያም ፡ በባሕሩ ፡ ውስጥ ፡
መበተንን ፡ እንበትነዋለን ።
98 ጌታችሁ ፡ ያ ፡ ከርሱ ፡ በቀር ፡
ሌላ ፡ አምላክ ፡ የሌለ ፡ የኾነው ፡
አላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ዕውቀቱ ፡
ነገርን ፡ ሁሉ ፡ አዳረሰ ።
99 እንደዚሁ ፡ በእርግጥ ፡ ካለፉት ፡
ወሬዎች ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ እንተርካ
ለን ፤ ከኛም ፡ ዘንድ ፡ ቁርአንን ፡
በእርግጥ ፡ ሰጠንህ ።
100 ከርሱ ፡ ያፈገፈገ ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡
በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ከባድን ፡ ቅጣት
ይሸከማል ።
101 በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ዘውታሪዎች ፡
ኾነው ፡ (ይሸከማሉ) ፤ በትንሣ
ኤም ፡ ቀን ፡ ለነሱ ፡ የኾነው ፡
ሸክም ፡ ከፋ !
102 በቀንዱ ፡ በሚነፋ ፡ ቀን ፡ (ሸክማ
ቸው ፡ ከፋ) ፤ ከሓዲዎችንም ፡
በዚያ ፡ ቀን ፡ (ዓይኖቻቸው) ፡ ሰማ
ያዊዎች ፡ ኾነው ፡ እንሰበስባቸዋ
ለን ።
103 ዐሥርን ፡ (ቀን) ፡ እንጂ ፡ አልቆያ
ችሁም ፡ በመባባል ፡ በመካከላ
ቸው ፡ ይንሾካሾካሉ።
104 በሐሳብ ፡ ቀጥተኛቸው ፡ አንድን ፡
ቀን ፡ እንጅ ፡ አልቆያችሁም ፡
በሚል ፡ ጊዜ ፡ የሚሉትን ፡ ነገር ፡
እኛ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ነን ።
105 ከጋራዎችም ፡ ይጠይቁሃል ፤ በላ
ቸው ፡- ጌታዬ ፡ መበተንን ፡ ይበ
ትናቸዋል ።

1 የጂብሪል ፡ ባዝራ ፡ ፈረስ ፡ የረገጠችው ፡
መለምለሙን ።

1 አላህ ፡ የማይጥሰው ፡ የማይቀር ፡ ቀጠሮ ፡
አለህ ።

106 ትክክል ፡ ሜዳም ፡ ኾና ፡ ይተዋ
ታል ።
107 በርሷ ፡ ዝቅታና ፡ ከፍታን ፡ አታ
ይም ።
108 በዚያ ፡ ቀን ፡ (ለመሰብሰብ) ፡ ጠሪ
ውን ፡ ለርሱ ፡ መጣመም ፡ የሌለ
ውን ፡ መከተል ፡ ይከተላሉ ፤ ድም
ጾችም ፡ ለአልረሕማን ፡ ጸጥ ፡
ይላሉ ፡ ስለዚህ ፡ ሹክሹክታን ፡
እንጂ ፡ አትሰማም ።
109 በዚያ ፡ ቀን ፡ ለርሱ ፡ አልረሕ
ማን ፡ የፈቀደለትንና ፡ ለርሱም ፡
ቃልን ፡ የወደደለትን ፡ ሰው ፡
ቢኾን ፡ እንጅ ፡ ምልጃ ፡ (አንድ
ንም) ፡ አትጠቅምም ።
110 በስተፊታቸው ፡ ያለውን ፡ በስተ
ኋላቸውም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ያው
ቃል ፤ በርሱም ፡ ዕውቀትን ፡ አያ
ካብቡም ፤ (አያውቁም) ።
111 ፊቶችም ፡ ሁሉ ፡ ሕያው ፡ አስተና
ባሪ ፡ ለኾነው ፡ (አላህ) ፡ ተዋረዱ ፤
በደልንም ፡ የተሸከመ ፡ ሰው ፡
በእርግጥ ፡ ከሰረ ።
112 እርሱ ፡ አማኝ ፡ ኾኖ ፡ ከመል
ካም ፡ ሥራዎችም ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡
በደልንም ፡ መጉደልንም ፡ አይፈ
ራም ።
113 እንደዚሁም ፡ ዐረብኛ ፡ ቁርአን ፡
ኾኖ ፡ አወረድነው ፤ አላህንም ፡
ይፈሩ ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ ለነሱ ፡
ግሣጼን ፡ ያድስላቸው ፡ ዘንድ ፡
ከዛቻ ፡ ደጋግመን ፡ በውስጡ ፡
ገለጽን ።
114 እውነተኛው ፡ ንጉሥ ፡ አላህም ፡
(ከሓዲዎች ፡ ከሚሉት) ፡ ላቀ ፤
ወደ ፡ አንተ ፡ መወረዱም ፡ ከመፈ
ጸሙ ፡ በፊት ፡ በማንበብ ፡ አትቸ
ኩል ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ! ዕውቀትንም፡
ጨምርልኝ ፡ በል ።
115 ወደ ፡ አደምም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡
ኪዳንን ፡ በእርግጥ ፡ አወረድን ፤
ረሳም ፤ ለርሱም ፡ ቆራጥነትን ፡
አላገኘንለትም ።
116 ለመላእክትም ፡ ለአዳም ፡ ስገዱ ፡
ባልን ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፤ ሰገ
ዱም ፤ ኢብሊስ ፡ ብቻ ፡ ሲቀር ፡
እምቢ ፡ አለ ።
117 አልንም ፡— አደም ፡ ሆይ ! ይህ ፡
ላንተም ፡ ለሚስትህም ፡ በእር
ግጥ ፡ ጠላት ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡
ከገነት ፡ አያውጣችሁ ፤ ትለፋለ
ህና ፤
118 ለአንተ ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ አለመ
ራብና ፡ አለመታረዝ ፡ አለህ ።
119 አንተም ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ አትጥ
ጠማም ፤ በፀሐይም ፡ አትተኰ
ስም ።
120 ሰይጣንም ፡ ወደርሱ ፡ ጐተ
ጐተ ፡— አደም ፡ ሆይ ! በመዘው
ተሪያ ፡ ዛፍ ፡ (1) በማይጠፋ ፡
ንግሥናም ፡ ላይ ፡ ላመለከትህን ?
አለው ።
121 ከርሷም ፡ በሉ ፤ ለነርሱም ፡
ኅፍረተ፡ ገላቸው ፡ ተገለጸች ፤
ከገነትም ፡ ቅጠል ፡ በላያቸው ፡
ላይ ፡ ይለጥፉ ፡ ጀመር ፤ አደምም፡
የጌታውን ፡ ትእዛዝ ፡ (ረስቶ) ፡
ጣሰ ፤ (ከፈለገው ፡ መዘውተር) ፡
ተሳሳተም ።
122 ከዚያም ፡ ጌታው ፡ መረጠው ፡
ከርሱም ፡ ጸጸቱን ፡ ተቀበለው ፡
መራውም ።
123 አላቸው ፡— ከፊላችሁም ፡ ለከ
ፊሉ ፡ ጠላት ፡ ሲኾን ፡ ሁላች
ሁም ፡ ከርሷ ፡ ውረዱ ፤ ከኔም ፡

1 የበላት ፡ ሁልጊዜ ፡ ሕያው ፡ ኾኖ ፡ የሚዘወ
ትርባት ፡ በኾነች ።



የኾነ ፡ መሪ ፡ ቢመጣላችሁ ፡ መሪ
የን ፡ የተከተለ ፡ አይሳሳትም ፤
አይቸገርምም ።
124 ከግሣጼየም ፡ የዞረ ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡
ጠባብ ፡ ኑሮ ፡ አልለው ፤ በትንሣ
ኤም ፡ ቀን ፡ ዕውር ፡ ኾኖ ፡ እንቀሰ
ቅሰዋለን ።
125 ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ለምን ፡ ዕውር ፡
አድርገህ ፡ አስነሳኸኝ ? በእርግጥ ፡
የማይ ፡ የነበርኩ ፡ ስኾን ፡ ይላል ።
126 (ነገሩ) ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፤ ታምራ
ታችን ፡ መጣችልህ ፤ ተውካትም ፡
እንደዚሁም ፡ ዛሬ ፡ ትተዋለህ ፡
ይለዋል ።
127 እንደዚሁም ፡ ያጋራንና ፡ በጌ
ታው ፡ አንቀጾች ፡ ያላመነን ፡
ሰው ፡ እንቀጣዋለን ፤ የመጨ
ረሻይቱም ፡ ዓለም ፡ ቅጣት ፡
በጣም ፡ ብርቱ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ዘው
ታሪም ፡ ነው ።
128 (ቁረይሾች) ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡ ከክ
ፍለ ፡ ዘመናት ፡ ሕዝቦች ፡ ብዙዎ
ችን ፡ ያጠፋን ፡ መኾናችን ፡ በመ
ኖሪያዎቻቸው ፡ የሚኼዱ ፡ ኾነው ፡
ሳሉ ፡ ለነርሱ ፡ አልተገለጸላቸው
ምን ? በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ለአእምሮ ፡
ባለ ፡ ቤቶች ፡ በእርግጥ ፡ መልክ
ቶች ፡ አሉበት ።
129 ከጌታህ ፡ ያለፈች ፡ ቃልና ፡ የተወ
ሰነ ፡ ጊዜ ፡ ባልነበረ ፡ ኖሮ ፡
(ቅጣቱ ፡ አሁኑ) ፡ የሚይዛቸው ፡
ይኾን ፡ ነበር ።
130 በሚሉትም ፡ ላይ ፡ ታገሥ ፤ ጌታ
ህንም ፡ ፀሐይ ፡ ከመውጣትዋ ፡
በፊት ፡ ከመግባትዋም ፡ በፊት ፡
የምታመሠግን ፡ ኾነህ ፡ አጥራው ፤
(ስገድ) ፤ ከሌሊት ፡ ሰዓቶችም ፡
በቀን ፡ ጫፎችም ፡ አጥራው ፤
(በሚሰጥህ ፡ ምንዳ) ፡ ልትወድ ፡
ይከጀላልና ።
131 ዓይኖችህንም ፡ ከነርሱ ፡ (ከሰ
ዎቹ) ፡ ክፍሎችን ፡ በርሱ ፡ ልንፈ
ትናቸው ፡ ወደ ፡ አጣቀምንበት ፡
ወደ ፡ ቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡ ጌጦች፡
አትዘርጋ ። የጌታህ ፡ ሲሳይም ፡
በጣም ፡ በላጭ ፡ ዘውታሪም ፡
ነው ።
132 ቤተሰብህንም ፡ በስግደት ፡ እዘዝ ፤
በርሷም ፡ ላይ ፡ ዘውትር ፤ ሲሳ
ይን ፡ አንጠይቅህም ፤ እኛ ፡ እንሰ
ጥሃለን ፤ መልካሚቱ ፡ መጨረ
ሻም ፡ ለጥንቁቆቹ ፡ ናት ።
133 ከጌታውም ፡ በኾነ ፡ ታምር ፡ አይ
መጣንምን ? አሉ ፤ በመጀመሪያ
ዎቹ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ያለ
ችው ፡ ማስረጃ ፡ አልመጣቻቸ
ውምን ?
134 እኛም ፡ ከርሱ ፡ (ከሙሐመድ ፡
መላክ) ፡ በፊት ፡ በቅጣት ፡ ባጠ
ፋናቸው ፡ ኖሮ ፡—ጌታችን ፡ ሆይ!
ከመዋረዳችንና ፡ ከማፈራችን ፡
በፊት ፡ አንቀጾችህን ፡ እንከተል ፡
ዘንድ ፡ ወደኛ ፡ መልክተኛን ፡
አትልክም ፡ ነበርን ? ባሉ ፡ ነበር ።
135 ሁሉም ፡ ተጠባባቂ ፡ ነው ፡ ተጠ
ባበቁም ፤ የቀጥታውም ፡ መንገድ፡
ባለቤቶች ፡ እነማን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡
እነማንም ፡ እንደ ፡ ተመሩ ፡ ወደ
ፊት ፡ ታውቃላችሁ ፡ በላቸው ።

★ ★ ★

21ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-አንቢያ ፡ (የነቢያት ፡ ምዕራፍ) ፤ በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 112 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።

1 ለሰዎች ፡ እነሱ ፡ በዝንጋቴ ፡
ውስጥ ፡ (መሰናዳትን) ፡ የተው ፡
ኾነው ፡ ሳሉ ፡ ምርመራቸው ፡
ቀረበ ፤

2 ከጌታቸው ፡ አዲስ ፡ የተወረደ ፡
ቁርአን ፡ አይመጣላቸውም ፡ እ
ነሱ ፡ የሚያላግጡ ፡ ኾነው ፡ የሚ
ያደምጡት ፡ ቢኾኑ ፡ እንጂ ።

3 ልቦቻቸው ፡ ዝንጉዎች ፡ ኾነው ፡
(የሚያዳምጡት ፡ ቢኾኑ ፡ እንጅ)፤
እነዚያም ፡ የበደሉት ፡ ሰዎች ፡
መንሾካሾክን ፡ ደበቁ፤ ይህ ፡ ብጤ
ያችሁ ፡ ሰው ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡
ነውን ? እናንተም ፡ የምታዩ ፡
ስትኾኑ ፡ ድግምትን ፡ ለመቀበል ፡
ትመጣላችሁን ? (አሉ) ።

4 (ሙሐመድም) ፡ ጌታዬ ፡ ቃልን ፡
ሁሉ ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡
ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሲኾን ፡ ያውቃል ፤
እርሱም ፡ ሰሚው ፡ ዐዋቂው ፡
ነው ፡ አለ ።

5 ፡-በውነቱ ፡ (ቁርአኑ) ፡ የሕል
ሞች ፡ ቅዠቶች ፡ ነው ፤ ይልቁ
ንም ፡ቀጠፈው ፤ እንዲያውም ፡
እርሱ ፡ ቅኔን ፡ ገጣሚ ፡ ነው ፤
የቀድሞዎቹም ፡ እንደ ፡ ተላኩ ፥
(መልክተኛ ፡ ከኾነ) ፡ በታምር ፡
ይምጣብን ፡ አሉ ።

6 ከነሱ ፡ በፊት ፡ ያጠፋናት ፡
ከተማ ፡ አላመነችም ፤ ታዲያ ፡
እነሱ ፡ ያምናሉን ?

7 ከአንተም ፡ በፊት ፡ ወደነሱ ፡ የም
ናወርድላቸው ፡ የኾኑ ፡ ሰዎችን ፡
እንጂ ፡ ሌላን ፡ አልላክንም ፤ የማ
ታውቁም ፡ ብትኾኑ ፡ የመጽሐ
ፉን ፡ ባለቤቶች ፡ ጠይቁ ።

8 ምግብን ፡ የማይበሉ ፡ አካልም ፡
አላደረግናቸውም ፤ ዘውታሪዎ
ችም ፡ አልነበሩም ።

9 ከዚያም ፡ ቀጠሮን ፡ ሞላንላቸው ፡
አዳናቸውም ፤ የምንሻውንም ፡
ሰው ፡ (አዳን) ፤ ወሰን ፡ አላፊዎቹ
ንም ፡ አጠፋን ።

10 ክብራችሁ ፡ በውስጡ ፡ ያለበትን ፡
መጽሐፍ ፡ ወደናንተ ፡ በእርግጥ ፡
አወረድን ፤ አታውቁምን ?

11 በዳይም ፡ ከነበረች ፡ ከተማ ፡ ያጠ
ፋናትና ፡ ከኋላዋም ፡ ሌሎችን ፡
ሕዝቦች ፡ ያስገኘነው ፡ ብዙ ፡
ናት ።

12 ቅጣታችንም ፡ በተሰማቸው ፡
ጊዜ ፡ እነሱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ከርሷ ፡
(ለመሸሽ) ፡ ይገሠግሣሉ ።

13 አትገሥግሡ ፤ ትልለመኑም ፡ ይ
ኾናልና ፡ በርሱ ፡ ወደ ፡ ተቀማ
ጠላችሁበት ፡ ጸጋ ፡ ወደ ፡ መኖ
ሪያዎቻችሁም ፡ ተመለሱ ፡ (ይባ
ላሉ) ። (1)

14 ፡—ዋ ፡ ጥፋታችን ! እኛ ፡ በእር
ግጥ ፡ በዳዮች ፡ ነበርን ፡ ይላሉ ።

15 የታጨዱ ፡ ሬሳዎችም ፡ እስካደረ
ግናቸው ፡ ድረስ ፡ ይህቺ ፡ ጥሪያ
ቸው ፡ ከመኾን ፡ አልተወገደችም ።

16 ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በመካከላ
ቸው ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ ቀላ
ጆች ፡ ኾነን ፡ አልፈጠርንም ።

17 መጫወቻን ፡ (ሚስትን ፡ ልጅን) ፡
ልንይዝ ፡ በሻን ፡ ኖሮ ፡ ከኛ ፡
ዘንድ ፡ በያዝነው ፡ ነበር ፡ (ግን) ፡
ሠሪዎች ፡ አይደለንም ።

18 በእርግጥ ፡ እውነትን ፡ በውሸት ፡
ላይ ፡ እንጥላለን ፤ አንጐሉን ፡
ያፈርሰዋልም ፤ ወዲያውም ፡ እ
ርሱ ፡ ጠፊ ፡ ነው ፤ ለናንተም ፡
ከዚያ ፡ (ሚስትና ፡ ልጅ ፡ አለው ፡
በማለት) ፡ ከምትመጥኑት ፡ ነገር ፡
ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ አላችሁ ፤ (ወዮ
ላችሁ) ።

19 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡
ሁሉም ፡ የርሱ ፡ ነው ፤ እርሱ ፡
ዘንድ ፡ ያሉትም ፡ (መላእክት) ፡
እርሱን ፡ ከመገዛት ፡ አይኮሩም ፤
አይሰለቹምም ።

20 በሌሊትና ፡ በቀንም ፡ ያጠሩታል ፤
አያርፉም ።

21 ይልቁንም ፡ ከምድር ፡ የኾኑን ፡
እነሱ ፡ ሙታንን ፡ የሚያስነሱን ፡
አማልክት ፡ ያዙን ? (የለም) ።

22 በሁለቱ ፡ (በሰማያትና ፡ በምድር)፡
ውስጥ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ አማል
ክት ፡ በነበሩ ፡ ኖሮ ፡ በተበላሹ ፡
ነበር ፤ የዐርሹ ፡ ጌታ ፡ አላህም ፡
ከሚሉት ፡ ሁሉ ፡ ጠራ ።

23 ከሚሠራው ፡ ሁሉ ፡ አይጠየቅም ፤
እነሱ ፡ (ፍጥረቶቹ) ፡ ግን ፡ ይጠየ
ቃሉ ።

24 ይልቁንም ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ አማል
ክትን ፡ ያዙን ? አስረጃችሁን ፡
አምጡ ፤ ይህ ፡ (ቁርአን) ፡ እኔ ፡
ዘንድ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ መገ
ሠጫ ፡ ከኔ ፡ በፊትም ፡ የነበሩት ፡
ሕዝቦች ፡ መገሠጫ ፡ ነው ፡ በላ
ቸው ። በውነቱ ፡ አብዛኞቻቸው ፡
እውነቱን ፡ አያውቁም ። ስለዚህ ፡
እነሱ ፡ እንቢተኞች ፡ ናቸው ።

25 ከአንተ ፡ በፊትም ፡ እነሆ ፡ ከኔ ፡
ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለምና ፡ ተገዙኝ ፡
በማለት ፡ ወደርሱ ፡ የምናወርድ
ለት ፡ ቢኾን ፡ እንጅ ፡ ከመልክ
ተኛ ፡ አንድንም ፡ አልላክንም ።

26 አልረሕማንም ፡ (ከመላእክት) ፡
ልጅን ፡ ያዘ ፡ አሉ ፤ ጥራት ፡ ተገ
ባው ፤ አይደለም ፡ (መላእክት) ፡
የተከበሩ ፡ ባሮች ፡ ናቸው ።

27 በንግግር ፡ አይቀድሙትም ፤ (ያላ
ለውን ፡ አይሉም) ፤ እነሱም ፡ በት
እዛዙ ፡ ይሠራሉ ።

28 በፊታቸው ፡ ያለውንና ፡ በኋላ
ቸው ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ ያው
ቃል ፤ ለወደደውም ፡ ሰው ፡
እንጅ ፡ ለሌላው ፡ አያማልዱም ፤
እነሱም ፡ እርሱን ፡ ከመፍራታ
ቸው ፡ የተነሳ ፡ ተጨናቂዎች ፡
ናቸው ።

29 ከነሱም ፡ እኔ ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ አም
ላክ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ያንን ፡ ገሀነ
ምን ፡ እንመነዳዋለን ፤ እንደዚሁ ፡
በዳዮችን ፡ እንመነዳለን ።

30 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ሰማያትና ፡
ምድር ፡ የተጣበቁ ፡ የነበሩና ፡
የለያየናቸው ፡ መኾናችንን ፡ አያ
ውቁምን ? ሕያው ፡ የኾነንም ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከውሃ ፡ ፈጠርን ፤
አያምኑምን ?

1 ይህንን ፡ የሚባሉት ፡ ለቅጥጥብ ፡ ነው ።

31 በምድርም ፡ ውስጥ ፡ በነሱ ፡ እን
ዳታረገርግ ፡ ጋራዎችን ፡ አደረግን ፤
ይመሩም ፡ ዘንድ ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡
ሰፋፊ ፡ መንገዶችን ፡ አደረግን ።
32 ሰማይንም ፡ (ከመውደቅ) ፡ የተጠ
በቀ ፡ ጣራ ፡ አደረግን ፤ እነሱም ፡
ከታምራቶቿ ፡ ዘንጊዎች ፡ ናቸው ።
33 እርሱም ፡ ሌሊትንና ፡ ቀንን ፡
ፀሐይንና ፡ ጨረቃንም ፡ የፈጠረ ፡
ነው ፤ ሁሉም ፡ በፈለካቸው ፡ (1)
ውስጥ ፡ ይዋኛሉ ።
34 (ሙሐመድ ፡ ሆይ !) ካንተ ፡
በፊት ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ ዘለዓ
ለም ፡ መኖርን ፡ አላደረግንም ፤
ታዲያ ፡ ብትሞት ፡ እነሱ ፡ ዘውታ
ሪዎች ፡ ናቸውን ?
35 ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ ሞትን ፡ ቀማሽ ፡
ናት ፤ ለመፈተንም ፡ በክፉም ፡
በበጎም ፡ እንሞክራችኋለን ፤ ወደ
ኛም ፡ ትመለሳላችሁ ።
36 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡
ባዩህ ፡ ጊዜ ፡ መሳለቂያ ፡ አድር
ገው ፡ እንጂ ፡ አይይዙህም ፤
እነሱ ፡ በአልረሕማን ፡ መወሳት ፡
እነርሱ ፡ ከሓዲዎች ፡ ሲኾኑ ፡ ያ ፡
አማልክቶቻችሁን ፡ (በክፉ) ፡ የሚ
ያነሳው ፡ ይህ ፡ ነውን ? (ይላሉ) ።
37 ሰው ፡ ቸኳይ ፡ ኾኖ ፡ ተፈጠረ ፤
ታምራቶቼን ፡ በእርግጥ ፡ አሳያች
ኋለሁና ፡ አታቻኩሉኝ ።
38 ይህ ፡ ቀጠሮም ፡ መቼ ፡ ነው ?
እውነተኞች ፡ ከኾናችሁ ፡ (አም
ጡት) ፡ ይላሉ ።
39 እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ከፊቶቻቸውና ፡
ከጀርባዎቻቸው ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡
የማይከለክሉበትን ፡ እነሱም ፡
የማይረዳዱበትን ፡ ጊዜ ፡ ቢያ
ውቁ ፡ ኖሮ ፡ (ይህንን ፡ አይሉም ፡
ነበር) ።
40 ይልቁንም ፡ (ሰዓቲቱ) ፡ በድን
ገት ፡ ትመጣቸዋለች ፤ ታዋልላቸ
ዋለችም ፤ መመለሷንም ፡ አይች
ሉም ፤ እነሱም ፡ አይቆዩም ።
41 ከአንተ ፡ በፊትም ፡ የነበሩት ፡
መልክተኞች ፡ በእርግጥ ፡ ተቀለ
ደባቸው ፤ በነዚያም ፡ ከነሱ ፡ ይቀ
ልዱ ፡ በነበሩት ፡ በርሱ ፡ ይሳለቁ
በት ፡ የነበሩት ፡ (ቅጣት) ፡ ሰፈረ
ባቸው ።
42 ከአልረሕማን ፡ (ቅጣት) ፡ በሌሊ
ትና ፡ በቀን ፡ የሚጠብቃችሁ ፡
ማነው ? በላቸው ፤ በውነቱ ፡
እነሱ ፡ ከጌታቸው ፡ ግሣጼ ፡ (ከቁ
ርአን) ፡ ዘንጊዎች ፡ ናቸው ።
43 ለነሱ ፡ ከኛ ፡ ሌላ ፡ የምትከላከልላ
ቸው ፡ አማልክት ፡ አለቻቸውን ?
ነፍሶቻቸውን ፡ መርዳትን ፡ አይች
ሉም ፤ እነሱም ፡ (ከሓዲዎቹ) ፡
ከኛ ፡ አይጠበቁም ።
44 በውነትም ፡ እነዚህንና ፡ አባቶቻ
ቸውን ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ዕድሜ ፡
እስከ ፡ ረዘመባቸው ፡ ድረስ ፡ አጣ
ቀምናቸው ፤ (ተታለሉም) ፡ እኛ ፡
ምድርን ፡ ከጫፎችዋ ፡ የምናጐድ
ላት ፡ ኾነን ፡ ስንመጣባት ፡ አያዩ
ምን ? እነሱ ፡ አሸናፊዎች ፡ ናቸ
ውን ?
45 ፡-የማስፈራራችሁ ፡ በተወረደ
ልኝ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ግን ፡ ደንቆ
ሮዎች ፡ በሚስፈራሩ ፡ ጊዜ ፡ ጥሪን ፡
አይሰሙም ፡ በላቸው ።
46 ከጌታህ ፡ ቅጣትም ፡ ወላፈን ፡ ብት
ነካቸው ፡ ዋ ፡ ጥፋታችን ! እኛ ፡
በዳዮች ፡ ነበርን ፡ ይላሉ ።
47 በትንሣኤም ፡ ቀን ፡ ትክክለኛ ፡
ሚዛኖችን ፡ እናቆማለን ፡ ማንኛይ

1 በመዞሪያቸው ።



ቱም ፡ ነፍስ ፡ ምንንም ፡ አትበደ
ልም ፤ (ሥራው) ፡ የሰናፍጭ ፡
ቅንጣት ፡ ያክል ፡ ቢኾንም ፡ እር
ሷን ፡ እናመጣታለን ፤ ተቆጣጣሪ
ዎችም ፡ በኛ ፡ በቃ ።
48 ለሙሳና ፡ ለሃሩንም ፡ እውነትንና ፡
ውሸትን ፡ የሚለይን ፡ ብርሃንንም ፡
ለጥንቁቆችም ፡ መገሠጫን ፡ በእ
ርግጥ ፡ ሰጠናቸው ።
49 ለነዚያ ፡ ጌታቸውን ፡ በሩቅ ፡ ለሚ
ፈሩት ፡ እነሱም ፡ ከሰዓቲቱ ፡ ተጨ
ናቂዎች ፡ ለኾኑት ፡ (መገሠጫን ፡
ሰጠን) ።
50 ይህም ፡ (ቁርአን) ፡ ያወረድነው ፡
የኾነ ፡ ብሩክ ፡ መገሠጫ ፡ ነው ፤
ታዲያ ፡ እናንተ ፡ ለርሱ ፡ ከሓዲ
ዎች ፡ ናችሁን ?
51 ለኢብራሂምም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡
ቅን ፡ መንገዱን ፡ በእርግጥ ፡ ሰጠ
ነው ፤ እኛም ፡ በርሱ ፡ (ተገቢ
ነት) ፡ ዐዋቂዎች ፡ ነበርን ።
52 ለአባቱና ፡ ለሕዝቦቹ ፡—ይህቺ ፡
ቅርጻቅርጽ ፡ ያቺ ፡ እናንተ ፡
ለርሷ ፡ ተገገርዎች ፡ የኾናችሁት ፡
ምንድን ፡ ናት ? ባለ ፡ ጊዜ ፡ (መራ
ነው) ።
53 ፡—አባቶቻችንን ፡ ለርሷ ፡ ተገገር
ዎች ፡ ኾነው ፡ አገኘን ፡ አሉት ።
54 እናንተም ፡ አባቶቻችሁም ፡ በእር
ግጥ ፡ በግልጽ ፡ስሕተት ፡ ውስጥ ፡
ነበራችሁ ፡ አላቸው ።
55 በምሩ ፡ መጣህልን ? ወይንስ ፡
አንተ ፡ ከሚቀልዱት ፡ ነህ ?
አሉት ።
56 አይደለም ፡ ጌታችሁ ፡ የሰማያ
ትና ፡ የምድር ፡ ጌታ ፡ ያ ፡ የፈጠ
ራቸው ፡ ነው ፤ እኔም ፡ በይሃችሁ ፡
ላይ ፡ ከመስካሪዎቹ ፡ ነኝ ፡ አለ ።
57 በአላህም ፡ እምላለሁ ፡ ዟሪዎች ፡
ኾናችሁ ፡ ከኼዳችሁ ፡ በኋላ ፡
ጣዖቶቻችሁን ፡ ተንኮል ፡ እሠራ
ባቸዋለሁ ፡ (አለ) ።
58 (ዘወር ፡ ሲሉ) ፡ ስብርብሮችም ፡
አደረጋቸው ፤ ለነሱ ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡
ታላቅ ፡ (ጣዖት) ፡ ብቻ ፡ ሲቀር ፡
ወደርሱ ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ (እር
ሱን ፡ ተወው) ።
59 ፡—በአማልክቶቻችን ፡ ይህንን ፡
የሠራ ፡ ማነው ? እርሱ ፡ በእርግጥ ፡
ከበደለኞች ፡ ነው ፡ አሉ ።
60 ኢብራሂም ፡ የሚባል ፡ ጎበዝ ፡
(በመጥፎ) ፡ ሲያነሳቸው ፡ ሰምተ
ናል ፡ ተባባሉ ።
61 ይመሰክሩበት ፡ ዘንድ ፡ በሰዎቹ ፡
ዓይን ፡ (ፊት) ፡ ላይ ፡ አምጡት ፡
አሉ ።
62 ኢብራሂም ፡ ሆይ ! በአማልክቶቻ
ችን ፡ ይህንን ፡ የሠራህ ፡ አንተ ፡
ነህን ? አሉት ።
63 አይደለም ፡ ይህ ፡ ትልቃቸው ፡
ሠራው ፤ ይናገሩም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡
ጠይቋቸው ፡ አለ ።
64 ወደ ፡ ነፍሶቻቸውም ፡ ተመለሱ ።
እናንተ ፡ (በመጠየቃችሁ) ፡ በዳ
ዮቹ ፡ እናንተው ፡ ናችሁም ፡
ተባባሉ ።
65 ከዚያም ፡ በራሶቻቸው ፡ ላይ ፡ ተገ
ለበጡ ፤ (1) እነዚህ ፡ የሚናገሩ ፡
አለመኾናቸውን ፡ በእርግጥ ፡ ዐው
ቀሃል ፤ (አሉ) ።
66 ታዲያ ፡ ለናንተ ፡ ምንም ፡ የማይ
ጠቅማችሁንና ፡ የማይጐዳችሁን ፡
ነገር ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ትግገዛላች
ሁን ? አላቸው ።

1 ወደ ፡ መጥፎው ፡ ኹኔታቸው ፡ ተመለሱ ።

67 ፎህ ! ለናንተ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ለም
ትግገዙትም ፡ ነገር ፤ አታውቁ
ምን ? (አለ) ።
68 ፡-ሠሪዎች ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ አቃ
ጥሉት ፡ አማልክቶቻችሁንም ፡
እርዱ ፡ አሉ ። (በእሳት ፡ ላይ ፡
ጣሉትም) ።
69 ፡-እሳት ፡ ሆይ ! በኢብራሂም ፡ ላይ ፡
ቀዝቃዛ ፤ ሰላምም ፡ ኹኚ ፡ አልን ።
70 በርሱም ፡ ተንኮልን ፡ አሰቡ ፤
በጣም ፡ ከሳሪዎችም ፡ አደረግና
ቸው ።
71 እርሱንና ፡ ሉጥንም ፡ ወደዚያች ፤
በውስጧ ፡ ለዓለማት ፡ በረከትን ፡
ወደ ፡ አደረግንባት ፡ ምድር ፡
(በመውሰድ) ፡ አዳን ።
72 ለርሱም ፡ ኢስሐቅን ፡ ያዕቆብ
ንም ፡ ተጨማሪ ፡ አድርገን ፡ ሰጠ
ነው ፤ ሁሉንም ፡ መልካሞች ፡
አደረግን ።
73 በትእዛዛችንም ፡ ወደ ፡ በጎ ፡
ሥራ ፡ የሚመሩ ፡ መሪዎች ፡ አደ
ረግናቸው ፤ ወደነሱም ፡ መል
ካም ፡ ሥራዎችን ፡ መሥራትን ፡
ሶላትንም ፡ መስገድን ፡ ዘካንም ፡
መስጠትን ፡ አወረድን ፤ ለኛ ፡
ተገዢዎችም ፡ ነበሩ ።
74 ሉጥንም ፡ ፍርድንና ፡ ዕውቀትን ፡
ሰጠነው ፤ ከዚያችም ፡ መጥፎ ፡
ሥራዎችን ፡ ትሠራ ፡ ከነበረችው ፡
ከተማ ፡ አዳንነው ፤ እነሱ ፡ ክፉ ፡
ሰዎች ፡ አመጠኞች ፡ ነበሩና ።
75 በችሮታችንም ፡ ውስጥ ፡ አገባ
ነው ፤ እርሱ ፡ ከመልካሞቹ ፡
ነውና ።
76 ኑሕንም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ (ጌታ
ውን) ፡ በጠራ ፡ ጊዜ ፡ (አስታ
ውስ) ፤ ለርሱም ፡ (ጥሪውን) ፡
ተቀበልነው ፤ እርሱንም ፡ ቤተሰቦ
ቹንም ፡ ከከባድ ፡ ጭንቅ ፡ አዳን ።
77 ከነዚያም ፡ በታምራቶቻችን ፡
ከአስተባበሉት ፡ ሕዝቦች ፡ (ተን
ኮል) ፡ ጠበቅነው ፤ እነሱ ፡ ክፉ ፡
ሕዝቦች ፡ አመጠኞች ፡ ነበሩና ፤
ሁሉንም ፡ አሰጠምናቸውም ።
78 ዳውድንና ፡ ሱለይማንንም ፡ በአዝ
መራው ፡ ነገር ፡ በሚፈርዱ ፡ ጊዜ ፡
የሕዝቦቹ ፡ ፍየሎች ፡ ሌሊት ፡
በርሱ ፡ ውስጥ ፡ በተሠማሩ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ) ፤ ፍርዳቸውንም ፡
ዐዋቂዎች ፡ ነበርን ።
79 ለሱለይማንም ፡ (ትክክለኛይቱን ፡
ፍርድ) ፡ አሳወቅናት ፤ ለሁሉም ፡
ጥበብንና ፡ ዕውቀትን ፡ ሰጠን ፤
ተራራዎችንም ፡ ከዳውድ ፡ ጋር ፡
የሚያወድሱ ፡ ሲኾኑ ፡ ገራን ፤ አ
እዋፍንም ፡ (እንደዚሁ ፡ ገራን) ፡
ሠሪዎችም ፡ ነበርን ።
80 የብረት ፡ ልብስንም ፡ ሥራ ፡ ለና
ንተ ፡ ከጦራችሁ ፡ ትጠብቃችሁ ፡
ዘንድ ፡ አስተማርነው ፤ እናንተ ፡
አመስጋኞች ፡ ናችሁን ?
81 ለሱለይማንም ፡ ነፋስን ፡ በኀይል ፡
የምትነፍስ ፡ በትእዛዙ ፡ ወደዚ
ያች ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ በረከትን ፡
ወደ ፡ አደረግንባት ፡ ምድር ፡
(ወደ ፡ ሻም) ፡ የምትፈስ ፡ ስት
ኾን ፡ (ገራንለት) ፤ በነገሩ ፡ ሁ
ሉም ፡ ዐዋቂዎች ፡ ነበርን ።
82 ከሰይጣናትም ፡ ለርሱ ፡ (ሉልን ፡
ለማውጣት) ፡ የሚጠልሙንና ፡
ከዚያም ፡ ሌላ ፡ ያለን ፡ ሥራ ፡
የሚሠሩን ፡ (ገራንለት) ፤ ለነሱም ፡
ተጠባባቂዎች ፡ ነበርን ።
83 አዩብንም ፡ (እዮብን) ፡ ጌታ
ውን ፡— እኔ ፡ መከራ ፡ አገኘኝ ፡



አንተም ፡ ከአዛኞች ፡ ሁሉ ፡ ይበ
ልጥ ፡ አዛኝ ፡ ነህ ፡ ሲል ፡ በተ
ጣራ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ።
84 ለርሱም ፡ ጥሪውን ፡ ተቀበልነው ፤
ከጉዳትም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የነበረ
ውን ፡ ሁሉ ፡ አስወገድን ፤ ቤተ
ሰቦቹንም ፡ ከነሱም ፡ ጋር ፡ መሰላ
ቸውን ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ለችሮታና ፡
ለተገዢዎች ፡ ለማስገንዘብ ፡ ሰጠ
ነው ።
85 ኢስማዒልንም ፡ ኢድሪስንም ፡
ዙልኪፍልንም ፡ (አስታውስ) ፤
ሁሉም ፡ ከታጋሾቹ ፡ ናቸው ።
86 በችሮታችንም ፡ ውስጥ ፡ አገባና
ቸው ፤ እነሱ ፡ ከመልካሞቹ ፡ ናቸ
ውና ።
87 የዐሣውንም ፡ ባለቤት ፡ (1) ተቆ
ጥቶ ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፤
በርሱም ፡ ላይ ፡ ፈጽሞ ፡ የማንፈ
ርድበት ፡ መኾናችንን ፡ ጠረጠረ ፤
(ዐሳም ፡ ዋጠው) ፤ በጨለማዎ
ችም ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡-ከአንተ ፡
በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፤
ጥራት ፡ ይገባህ ፤ እኔ ፡ በእርግጥ ፡
ከበዳዮቹ ፡ ነበርኩ ፡ በማለት ፡ ተ
ጣራ ።
88 ለርሱም ፡ ጥሪውን ፡ ተቀበልነው ፤
ከጭንቅም ፡ አዳነው ፤ እንደዚ
ሁም ፡ ምእምናንን ፡ እናድናለን ።
89 ዘከሪያንም ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ! ብቻ
ዬን ፡ አትተዎኝ ፤ አንተም ፡ ከወ
ራሾች ፡ ሁሉ ፡ በላጭ ፡ ነህ ፡
ሲል ፡ ጌታውን ፡ በተጣራ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ) ፤
90 ለርሱም ፡ ጥሪውን ፡ ተቀበልነው ፤
ለርሱም ፡ የሕያን ፡ ሰጠነው ፤ ለር

1 ዮናስን ።

ሱም ፡ ሚስቱን ፡ አበጀንለት ፤ (1)
እነሱ ፡ በበጎ ፡ ሥራዎች ፡ የሚቻ
ኮሉ ፡ ከጃዮችና ፡ ፈሪዎች ፡
ኾነው ፡ የሚለምኑንም ፡ ነበሩ ፤
ለኛ ፡ ተዋራጆችም ፡ ነበሩ ፤
91 ያችንም ፡ ብልቷን ፡ የጠበቀቺ
ውን ፡ በርሷም ፡ ውስጥ ፡ ከመንፈ
ሳችን ፡ የነፋንባትን ፡ እርሷንም ፡
ልጅዋንም ፡ (እንደዚሁ) ፡ ለዓለ
ማት ፡ ታምር ፡ ያደረግናትን ፡
(መርየምን ፡ አስታውስ) ።
92 ይህች ፡ (ሕግጋት) ፡ አንዲት ፡
መንገድ ፡ ስትኾን ፡ በእርግጥ ፡
ሃይማኖታችሁ ፡ ናት ፤ እኔም ፡
ጌታችሁ ፡ ነኝና ፡ ተገዙኝ ።
93 በሃይማኖታቸውም ፡ ነገር ፡ በመካ
ከላቸው ፡ ተለያዩ ፤ ሁሉም ፡
ወደኛ ፡ ተመላሾች ፡ ናቸው ።
94 እርሱ ፡ ያመነ ፡ ኾኖ ፡ ከበጎ ፡
ሥራዎች ፡ ማንኛውንም ፡ የሚሠ
ራም ፡ ሰው ፤ ምንዳውን ፡ አይነፈ
ግም ፤ እኛም ፡ ለርሱ ፡ መዝጋቢ
ዎች ፡ ነን ።
95 ባጠፋናትም ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡
እነሱ ፡ (ወደኛ) ፡ የማይመለሱ ፡
መኾናቸው ፡ እብለት ፡ ነው ፤
(ይመለሳሉ) ።
96 የእጁጅና ፡ መእጁጅም ፡ እነርሱ ፡
ከየተረተሩ ፡ የሚንደረደሩ ፡ ሲ
ኾኑ ፡ (ግድባቸው) ፡ በተከፈተች ፡
ጊዜ ፡
97 እውነተኛውም ፡ ቀጠሮ ፡ በቀረበ ፡
ጊዜ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ የነዚያ ፡
የካዱት ፡ ሰዎች ፡ ዓይኖች ፡ ይፈጥ
ጣሉ ፤ ዋ ፡ ጥፋታችን ! ከዚህ ፡
(ቀን) ፡ በእርግጥ ፡ በዝንጋቴ ፡

1 እንድትወልድ ፡ አደረግንለት ።

ላይ ፡ ነበርን ፤ በውነትም ፡ በዳ
ዮች ፡ ነበርን ፤ (ይላሉ) ።
98 እናንተ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የምትግገ
ዟቸውም ፡ (ጣዖታት) ፡ የገሀነም ፡
ማገዶዎች ፡ ናችሁ ፤ እናንተ ፡
ለርሷ ፡ ወራጆች ፡ ናችሁ ።
99 እነዚህ ፡ (ጣዖታት) ፡ አማልክት ፡
በነበሩ ፡ ኖሮ ፡ አይገቡዋትም ፡
ነበር ፤ ግን ፡ ሁሉም ፡ በርስዋ ፡
ውስጥ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ናቸው ።
100 ለነርሱ ፡ በርስዋ ፡ ውስጥ ፡ መንሰ
ቅሰቅ ፡ አላቸው ፤ እነርሱም ፡ በው
ስጧ ፡ (ምንንም) ፡ አይሰሙም ።
101 እነዚያ ፡ ከኛ ፡ መልካምዋ ፡ ቃል ፡
ለነርሱ ፡ ያለፈችላቸው ፡ እነዚያ ፡
ከርሷ ፡ የተራቁ ፡ ናቸው ።
102 ድምጽዋን ፡ አይሰሙም ፤ እነ
ሱም ፡ ነፍሶቻቸው ፡ በሚሹት ፡
ነገር ፡ ውስጥ ፡ ዘውታሪዎች ፡
ናቸው ።
103 ታላቁ ፡ ድንጋጤ ፡ አያስተክዛቸ
ውም ፤ መላእክትም ፡ ይህ ፡ ያ ፡
ትቀጠሩት ፡ የነበራችሁት ፡ ቀና
ችሁ ፡ ነው ፤ እያሉ ፡ ይቀበሏቸ
ዋል ።
104 ለመጽሐፎች ፡ የኾኑ ፡ ገጾች ፡ እን
ደሚጠቀለሉ ፡ ሰማይን ፡ የምንጠ
ቀልልበትን ፡ ቀን ፡ (አስታውስ) ፤
የመጀመሪያን ፡ ፍጥረት ፡ እንደ ፡
ጀመርን ፡ እንመልሰዋለን ፤ (መፈ
ጸሙ) ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ የኾነን ፡
ቀጠሮ ፡ ቀጠርን ፤ እኛ ፡ (የቀጠ
ርነውን) ፡ ሠሪዎች ፡ ነን ።
105 ምድርንም ፡ መልካሞቹ ፡ ባሮቼ ፡
ይወርሷታል ፡ ማለትን ፡ ከመጽ
ሐፉ ፡ (ከተጠበቀው ፡ ሰሌዳ) ፡ በ
ኋላ ፡ በመጽሐፎቹ ፡ በእርግጥ ፡
ጽፈናል ።
106 በዚህ ፡ (ቁርአን) ፡ ውስጥ ፡ ለተገ
ዢዎች ፡ ሕዝቦች ፡ በቂነት ፡
አለ ።
107 (ሙሐመድ ፡ ሆይ !) ለዓለማትም ፡
እዝነት ፡ አድርገን ፡ እንጅ ፡ አልላ
ክንህም ።
108 ያ ፡ ወደኔ ፡ የሚወረደው ፡ አምላካ
ችሁ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡
ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ታዲያ ፡
እናንተ ፡ ፍጹም ፡ ታዛዦች ፡ ናች
ሁን ? በላቸው ።
109 እምቢም ፡ ቢሉ ፡ (በማወቅ) ፡ በእ
ኩልነት ፡ ላይ ፡ ኾነን ፡ (የታዘዝ
ኩትን) ፡ አስታወቅኋችሁ ፤ የም
ትስፈራሩበትም ፡ ነገር ፡ ቅርብ ፡
ወይም ፡ ሩቅ ፡ መኾኑን ፡ አላው
ቅም ፤ በላቸው ።
110 እርሱ ፡ ከንግግር ፡ ጩኸትን ፡
ያውቃል ፤ የምትደብቁትንም ፡
ሁሉ ፡ ያውቃል ።
111 እርሱም ፡ (ቅጣትን ፡ ማቆየት) ፡
ምናልባት ፡ ለናንተ ፡ ፈተናና ፡
እስከ ፡ ጊዜው ፡ መጣቀሚያ ፡
እንደ ፡ ኾነም ፡ አላውቅም ፤ (በላ
ቸው) ።
112 ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ በውነት ፡ ፍ
ረድ ፤ ጌታችንም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በምትሉት ፡ ነገር ፡ ላይ ፡
መታገገኛ ፡ ነው ፤ አለ ።



22ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሐጅ ፡ (የሐጅ ፡ ምዕራፍ) ፡ በመዲና ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 78 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በኾ
ነው ።
1 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! ጌታች
ሁን ፡ ፍሩ ፡ የሰዓቲቱ ፡ (1) እንቅ
ጥቃጤ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡
ነውና ።
2 በምታዩዋት ፡ ቀን ፡ አጥቢ ፡ ሁሉ ፡
ከአጠባችው ፡ ልጅ ፡ ትፈዝዛ
ለች ፤ የእርግዝና ፡ ባለቤት ፡ የኾነ
ችም ፡ ሁሉ ፡ እርጉዝዋን ፡ ትጨነ
ግፋለች ፤ ሰዎቹንም ፡ (በድንጋጤ ፡
ብርታት) ፡ የሰከሩ ፡ ኾነው ፡ ታያ
ለህ ፤ እነሱም ፡ (ከመጠጥ) ፡ የሰ
ከሩ ፡ አይደሉም ፤ ግን ፡ የአላህ ፡
ቅጣት ፡ ብርቱ ፡ ነው ።
3 ከሰዎቹም ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ በአ
ላህ ፡ ነገር ፡ የሚከራከር ፤ ሞገ
ደኛ ፡ ሰይጣንንም ፡ ሁሉ ፡ የሚከ
ተል ፡ ሰው ፡ አለ ።
4 እነሆ ! የተከተለውን ፡ ሰው ፡
እርሱ ፡ ያጠመዋል ፤ ወደ ፡ ነዳጅ ፡
እሳት ፡ ስቃይም ፡ ይመራዋል ፡
ማለት ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተጽፏል ።
5 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! ከመቀሰ
ቀስ ፡ በመጠራጠር ፡ ውስጥ ፡
እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ (አፈጣጠራች
ሁን ፡ ተመልከቱ) ፤ እኛም ፡ ከዐ
ፈር ፡ ፈጠርናችሁ ፤ ከዚያም ፡
ከፍቶት ፡ ጠብታ ፡ ከዚያም ፡
ከረጋ ፡ ደም ፡ ከዚያም ፡ ከቁራጭ ፡
ሥጋ ፡ ፍጥረትዋ ፡ ሙሉ ፡ ከኾነ
ችና ፡ ሙሉ ፡ ካልኾነች ፡ (ችሎታ
ችንን) ፡ ለናንተ ፡ ልንገልጽላችሁ ፡
ፈጠርናችሁ ፤ የምንሻውንም ፡
እስከ ፡ ተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡
በማሕፀን ፡ ውስጥ ፡ እናረጋዋለን ፤
ከዚያም ፡ ሕፃን ፡ ኾናችሁ ፡ እናወ
ጣችኋለን ፤ ከዚያም ፡ ሙሉ ፡ ጥን
ካሬያችሁን ፡ ትደርሱ ፡ ዘንድ ፡
(እናሳድጋችኋለን) ፤ ከናንተም ፡
የሚሞት ፡ ሰው ፡ አለ ፤ ከናንተም ፡
ከዕውቀት ፡ በኋላ ፡ ምንንም ፡ እን
ዳያውቅ ፡ ወደ ፡ ወራዳ ፡ ዕድሜ ፡
የሚመለስ ፡ ሰው ፡ አልለ ፤ ምድር
ንም ፡ ደረቅ ፡ ኾና ፡ ታያታለህ ፤
በርሷም ፡ ላይ ፡ ውሃን ፡ ባወረ
ድን ፡ ጊዜ ፡ ትላወሳለች ፤ ትነፋለ
ችም ፤ ውበት ፡ ካለው ፡ ጐሳ ፡
ሁሉ ፡ ታበቅላለችም ።
6 ይህ ፡ አላህ ፡ እርሱ ፡ መኖሩ ፡ የተ
ረጋገጠ ፤ እርሱም ፡ ሙታንን ፡
ሕያው ፡ የሚያደርግ ፤ እርሱም ፡
በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ በመ
ኾኑ ፡ ነው ።
7 ሰዓቲቱም ፡ መጪ ፡ በርሷ ፡ ፈ
ጽሞ ፡ ጥርጣሬ ፡ የሌለባት ፡ በመ
ኾኗ ፡ አላህም ፡ በመቃብሮች ፡
ውስጥ ፡ ያለን ፡ ሁሉ ፡ የሚቀሰ
ቅስ ፡ በመኾኑ ፡ ነው ።
8 ከሰዎችም ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ዕው
ቀት ፡ ያለ ፡ ማስረጃም ፡ ያለ ፡
አብራሪ ፡ መጽሐፍም ፡ በአላህ ፡
ነገር ፡ የሚከራከር ፡ ሰው ፡ አልለ ።
9 ጐኑን ፡ ያጠፈ ፡ ኾኖ ፡ ከአላህ ፡

1 የትንሣኤ ፡ ቀን ።

መንገድ ፡ ሊያሳስት ፡ (ይከራከ
ራል) ፤ በቅርቢቱ ፡ ዓለም ፡ ለርሱ ፡
ውርደት ፡ አለው ፤ በትንሣኤ ፡
ቀንም ፡ አቃጣይን ፡ ቅጣት ፡ እና
ቀምሰዋለን ።
10 ይህ ፡ እጆችህ ፡ ባስቀደሙት ፡
ኃጢአት ፡ አላህም ፡ ለባሮቹ ፡
ፈጽሞ ፡ በዳይ ፡ ባለመኾኑ ፡ ነው ፡
(ይባላል) ።
11 ከሰዎችም ፡ (ከሃይማኖት) ፡ በ
ጫፍ ፡ ላይ ፡ ኾኖ ፡ አላህን ፡ የሚግ
ገዛ ፡ ሰው ፡ አለ ፤ ታዲያ ፡ መል
ካም ፡ ነገር ፡ ቢያገኘው ፡ በርሱ ፡
ይረጋል ፤ መከራም ፡ ብታገኘው ፡
በፊቱ ፡ ላይ ፡ ይገለበጣል ፡ የቅር
ቢቱን ፡ ዓለምም ፡ የመጨረሻይቱ
ንም ፡ ከሰረ ፤ ይህ ፡ እርሱ ፡ ግልጽ፡
ከሳራ ፡ ነው ።
12 ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የማይጎዳውንና ፡
የማይጠቅመውን ፡ ይግገዛል ፤
ይህ ፡ እርሱ ፡ (ከእውነት) ፡
የራቀ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።
13 ያንን ፡ ከጥቅሙ ፡ ይልቅ ፡ ጉዳቱ ፡
የሚቀርብን ፡ ይግገዛል ፤ ረዳቱ ፡
ምንኛን ፡ ከፉ ! ወዳጁም ፡ ምንኛ ፡
ከፋ !
14 አላህ ፡ እነዚያን ፡ ያመኑትንና ፡
መልካም ፡ ሥራዎችን ፡ የሠሩ
ትን ፡ በስሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡
የሚፈሱባቸውን ፡ ገነቶች ፡ ያገባ
ቸዋል ፤ አላህ ፡ የሚሻውን ፡ ነገር ፡
በእርግጥ ፡ ይሠራል ።
15 አላህ ፡ (መልክተኛውን) ፡ በቅር
ቢቱም ፡ በመጨረሻይቱም ፡ ዓ
ለም ፡ አይረዳውም ፡ ብሎ ፡ የሚያ
ስብ ፡ ሰው ፡ ገመድን ፡ ወደ ፡
ሰማይ ፡ ይዘርጋ ፤ ከዚያም ፡ (ትን
ፋሹ ፡ እስኪቆረጥ) ፡ ይታነቅ ፤
ተንኮሉ ፡ የሚያስቆጨውን ፡
ነገር ፡ ያስወግድለት ፡ እንደ ፡
ሆነም ፡ ይመልከት ።
16 እንደዚሁም ፡ (ቁርአንን) ፡ የተብ
ራሩ ፡ አንቀጾች ፡ አድርገን ፡ አወ
ረድነው ፤ አላህም ፡ የሚሻውን ፡
ሰው ፡ ይመራል ።
17 እነዚያ ፡ ያመኑ ፡ እነዚያም ፡ ይሁ
ዳውያን ፡ የኾኑ ፡ ሳቢያኖችም ፡
ክርስቲያኖችም ፡ መጁሶችም ፡
(1) እነዚያም ፡ (ጣዖታትን ፡ በአ
ላህ) ፡ ያጋሩ ፡ አላህ ፡ በትንሣኤ ፡
ቀን ፡ በመካከላቸው ፡ በፍርድ ፡
ይለያል ፤ አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ በእርግጥ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።
18 አላህ ፡ በሰማያት ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡
በምድርም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ፀሐ
ይና ፡ ጨረቃም ፡ ከዋክብትም ፡
ተራራዎችም ፡ ዛፎችም ፡ ተንቀሳ
ቃሾችም ፡ ከሰዎች ፡ ብዙዎችም ፡
ለርሱ ፡ የሚሰግዱለት ፡ መኾኑን ፡
አታውቁምን ? ብዙውም ፡ በርሱ ፡
ላይ ፡ ቅጣት ፡ ተረጋገጠበት ፤
አላህ ፡ የሚያዋርደውም ፡ ሰው ፡
ለርሱ ፡ ምንም ፡ አክባሪ ፡ የለውም ፤
አላህ ፡ የሻውን ፡ ይሠራልና ።
19 እነዚህ ፡ (2) በጌታቸው ፡ የተከራ
ከሩ ፡ ሁለት ፡ ባላጋራዎች ፡
ናቸው ፤ እነዚያም ፡ የካዱት ፡
ለነርሱ ፡ የእሳት ፡ ልብሶች ፡ ተለ
ክተውላቸዋል ፤ ከራሶቻቸው ፡
በላይ ፡ የፈላ ፡ ውሃ ፡ ይምቧቧባቸ
ዋል ።
20 በሆዶቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡
ቆዳዎቻቸውም ፡ በርሱ ፡ ይቀለ
ጣሉ ።

1 በፀሐይና ፡ በጨረቃ ፡ በእሳት ፡ የሚያመ
ልኩ ።
2 ያመኑትና ፡ እምቢቱ ፡ ክፍሎች ፡ ከሓዲ
ያኖች ።



21 ለነሱም ፡ (መቅጫ) ፡ ከብረት ፡
የኾኑ ፡ መዶሻዎች ፡ አሉ ።
22 ከጭንቀት ፡ ብርታት ፡ የተነሣ ፡
ከርሷ ፡ ለመውጣት ፡ በፈለጉ ፡
ቍጥር ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ እንዲመ
ለሱ ፡ ይደረጋሉ ፤ በጣም ፡ የሚያ
ቃጥልንም ፡ ቅጣት ፡ ቅመሱ ፡
(ይባላሉ) ።
23 አላህ ፡ እነዚያን ፡ ያመኑትንና ፡
መልካም ፡ ሥራዎችን ፡ የሠሩ
ትን ፡ ሰዎች ፡ በስሮቻቸው ፡ ወን
ዞች ፡ የሚፈስሱባቸውን ፡ ገነ
ቶች ፡ ያገባቸዋል ፤ በርሷ ፡ ውስጥ፡
ከወርቅ ፡ የኾኑን ፡ አንባሮችና ፡
ሉልን ፡ ይሸለማሉ ፤ በርሷ ፡
ውስጥ ፡ ልብሶቻቸውም ፡ ሐር ፡
ናቸው ።
24 ከንግግርም ፡ ወደ ፡ መልካሙ ፡
ተመሩ ፤ ወደ ፡ ምስጉንም ፡ መን
ገድ ፡ ተመሩ ።
25 እነዚያ ፡ የካዱ ፡ ከአላህም ፡ መን
ገድና ፡ ከዚያም ፡ ለሰዎች ፡ በው
ስጡ ፡ ነዋሪ ፡ ለኾኑትም ፡ ከሩቅ ፡
ለሚመጡትም ፡ እኩል ፡ ካደረግ
ነው ፡ ከተከበረው ፡ መስጊድ ፡
(ሰዎችን) ፡ የሚከለክሉ ፡ (አሳማ
ሚን ፡ ቅጣት ፡ እናቀምሳቸዋ
ለን) ። በርሱም ፡ ውስጥ ፡ (ከትክ
ክለኛ ፡ መንገድ) ፡ በመዘንበል ፡
በዳይ ፡ ኾኖ ፡ (ማንኛውንም ፡
ነገር) ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ከአሳ
ማሚ ፡ ቅጣት ፡ እናቀምሰዋለን ።
26 ለኢብራሂምም ፡ የቤቱን ፡ (የከዕ
ባን) ፡ ስፍራ ፡ መመለሻ ፡ ባደረግ
ንለት ፡ ጊዜ ፡ በኔ ፡ ምንንም ፡ አታ
ጋራ ፤ ቤቴንም ፡ ለሚዞሩትና ፡
ለሚቆሙበት ፡ ለሚያጎነብሱትና
በግንባራቸውም ፡ ለሚደፉት ፡
ንጹሕ ፡ አድርግላቸው ፡ (ባል
ነው ፡ ጊዜ ፡ አስታውስ) ።
27 (አልነውም) ፡— በሰዎችም ፡
ውስጥ ፡ በሐጅ ፡ ትእዛዝ ፡ ጥራ ፤
እግረኞች ፡ ከየሩቅ ፡ መንገድ ፡
በሚመጡ ፡ ከሲታ ፡ ግመሎችም ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ ኾነው ፡ ይመጡሃ
ልና ።
28 ለነሱ ፡ የኾኑ ፡ ጥቅሞችን ፡ ይጣዱ
ዘንድ ፡ በታወቁ ፡ ቀኖችም ፡
ውስጥ ፡ ከለማዳ ፡ እንስሳዎች ፡
በሰጣቸው ፡ ሲሳይ ፡ ላይ ፡ የአላ
ህን ፡ ስም ፡ ያወሱ ፡ ዘንድ ፡ (ይመ
ጡሃል) ፤ ከርሷም ፡ ብሉ ፤ ችግ
ረኛ ፡ ድኻንም ፡ አብሉ ።
29 ከዚያም ፡ (እንደ ፡ ጠጉርና ፡
ጥፍር ፡ ያሉትን) ፡ ትርፍ ፡ አካላ
ቸውንና ፡ ዕድፋቸውን ፡ ያስወ
ግዱ ፤ ስለቶቻቸውንም ፡ ይሙሉ ፤
በጥንታዊውም ፡ ቤት ፡ ይዙሩ ።
30 (ነገሩ) ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የአላህንም ፡
ሕግጋት ፡ የሚያከብር ፡ ሰው ፡
እርሱ ፡ እጌታው ፡ ዘንድ ፡ ለርሱ ፡
በጣም ፡ የተሻለ ፡ ነው ፤ የቤት ፡
እንስሳትም ፡ (1) በናንተ ፡ ላይ ፡
(እርም ፡ መኾኑ) ፡ ከሚነበብላ
ችሁ ፡ በስተቀር ፡ ለናንተ ፡ ተፈቅ
ዳላችኋለች ። ከጣዖታትም ፡ ርክ
ሰት ፡ ተጠንቀቁ ፤ ሐሰትንም ፡
ቃል ፡ ራቁ ።
31 ለአላህ ፡ ታዛዦች ፡ በርሱ ፡ የማታ
ጋሩ ፡ ኾናችሁ ፡ (ከሐሰት ፡ ራቁ) ፤
በአላህም ፡ የሚያጋራ ፡ ሰው ፤
ከሰማይ ፡ እንደ ፡ ወደቀና ፡ በራሪ ፡
እንደምትነጥቀው ፡ ወይም ፡ ነ
ፋስ ፡ እርሱን ፡ በሩቅ ፡ ስፍራ ፡
እንደምትጥለው ፡ ብጤ ፡ ነው ።

1 ግመል ፡ ከብት ፡ በግና ፡ ፍየል ።

32 (ነገሩ) ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የአላህንም ፡
የሃይማኖት ፡ ምልክቶች ፡ (1)
የሚያከብር ፡ ሰው ፡ እርሷ ፡ ከል
ቦች ፡ የኾነች ፡ ጥንቃቄ ፡ ናት ።
33 ለናንተ ፡ በርሷ ፡ እስከ ፡ ተወሰነ ፡
ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ጥቅሞች ፡ አሏ
ችሁ ፤ ከዚያም ፡ (የማረጃ) ፡ ስፍ
ራዋ ፡ እጥንታዊው ፡ ቤት ፡ አጠ
ገብ ፡ ነው ።
34 ለሕዝብም ፡ ሁሉ ፡ (ወደ ፡ አላህ) ፡
መሥዋዕት ፡ ማቅረብን ፡ ደነገ
ግን ፤ ከቤት ፡ እንስሳት ፡ በሰጣ
ቸው ፡ ሲሳይ ፡ ላይ ፡ የአላህን ፡
ስም ፡ ብቻ ፡ ያወሱ ፡ ዘንድ ፡ (አዘ
ዝናቸው) ፤ አምላካችሁም ፡ አ
ንድ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ለር
ሱም ፡ ብቻ ፡ ታዘዙ ፤ ለአላህ ፡
ተዋራጆችንም ፡ አብስራቸው ።
35 እነዚያን ፡ አላህ ፡ በተወሳ ፡ ጊዜ ፡
ልቦቻቸው ፡ የሚጨነቁትን ፡ በደ
ረሰባቸውም ፡ (መከራ) ፡ ላይ ፡
ታጋሾችን ፡ ሶላትንም፡ አስተካክ
ለው ፡ ሰጋጆችን ፡ ከሰጠናቸውም ፡
ሲሳይ ፡ የሚለግሱትን ፡ (አብ
ስር) ።
36 ግመሎችንም ፡ ለናንተ ፡ ከአላህ ፡
ሃይማኖት ፡ ምልክቶች ፡ አደረግና
ቸው ፤ በርሷ ፡ ለናንተ ፡ መል
ካም ፡ ጥቅም ፡ አላችሁ ፤ በርሷም ፡
ላይ ፡ (ስታርዷት) ፡ በሦስት ፡
እግሮችዋ ፡ ቆማ ፡ የተሰለፈች ፡
ኾና ፡ የአላህን ፡ ስም ፡ አውሱ ፤
ጐኖቻቸውም ፡ በወደቁ ፡ ጊዜ ፡
ከርሷ ፡ ብሉ ፤ ለማኙንም ፡ ለል
መና ፡ የሚያገዳድምንም ፡ አብሉ ፤
እንደዚሁ ፡ ታመሰግኑ ፡ ዘንድ ፡
ለናንተ ፡ ገራናት ።

1 ወደ ፡ መካ ፡ የሚነዱትን ፡ መሥዋዕት ።

37 አላህን ፡ ስጋዎቿም ፡ ደሞቿም ፡
ፈጽሞ ፡ አይደርሰውም ፤ ግን ፡ ከና
ንተ ፡ የኾነው ፡ ፍራቻ ፡ ይደርሰ
ዋል ፤ እንደዚሁ ፡ አላህን ፡ በመ
ራችሁ ፡ ላይ ፡ ልታከብሩት ፡ ለና
ንተ ፡ ገራት ፤ በጎ ፡ ሠሪዎችንም ፡
አብስር ።
38 አላህ ፡ ከነዚያ ፡ ካመኑት ፡ ላይ ፡
ይከላከልላቸዋል ፤ አላህ ፡ ከዳተ
ኛን ፡ ውለታቢስን ፡ ሁሉ ፡ አይወ
ድም ።
39 ለነዚያ ፡ ለሚገደሉት ፡ (ምእመ
ናን) ፡ እነርሱ ፡ የተበደሉ ፡ በመኾ
ናቸው ፡ (መጋደል) ፡ ተፈቀደላ
ቸው ፤ አላህም ፡ እነርሱን ፡ በመር
ዳት ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ ቻይ ፡ ነው ።
40 ለነዚያ ፡ ጌታችን ፡ አላህ ፡ ነው ፡
ከማለታቸው ፡ በስተቀር ፡ ያለ ፡
አግባብ ፡ ከአገራቸው ፡ የተባረሩ ፡
ለኾኑት ፡ (ተፈቀደ) ፤ አላህ ፡ ሰዎ
ችን ፡ ከፊላቸውን ፡ በከፊሉ ፡
መገፍተሩ ፡ ባልነበረ ፡ ኖሮ ፡
ገዳማት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖችም ፡
ምኩራቦችም ፡ (1) በውስጣቸው ፡
የአላህ ፡ ስም ፡ በብዛት ፡ የሚወሳ
ባቸው ፡ መስጊዶችም ፤ በተፈ
ረሱ ፡ ነበር ፤ አላህም ፡ ሃይማኖ
ቱን ፡ የሚረዳውን ፡ ሰው ፡ በእር
ግጥ ፡ ይረዳዋል ፤ አላህ ፡ ብርቱ ፡
አሸናፊ ፡ ነውና ።
41 (እነርሱም) ፡ እነዚያ ፡ በምድር ፡
ላይ ፡ ብናስመቻቸው ፡ ሶላትን ፡
እንደሚገባ ፡ የሚያስተካክሉ ፡
ዘካንም ፡ የሚሰጡ ፡ በደግ ፡ ነገ
ርም ፡ የሚያዝዙ ፡ ከመጥፎ ፡ ነገ
ርም ፡ የሚከለክሉ ፡ ናቸው ፤ የነገ
ሮቹም ፡ ሁሉ ፡ መጨረሻ ፡ ወደ ፡
አላህ ፡ ነው ።

1 የይሁዶች ፡ ቤተ ፡ ጸሎት ።



42 ቢያስተባብሉህም ፡ ከነሱ፡ በፊት ፡
የኑሕ ፡ ሕዝቦች ፡ ዓድና ፡ ሠሙ
ድም ፡ በእርግጥ ፡ አስተባብለ
ዋል ፤
43 የኢብራሂምም ፡ ሕዝቦች ፡ የሉ
ጥም ፡ ሕዝቦች ፡ (አስተባብለ
ዋል) ፤
44 የመድየንም ፡ ሰዎች ፡ (አስተባብ
ለዋል) ፤ ሙሳም ፡ ተስተባብሏል ፤
ለከሓዲዎቹም ፡ ጊዜ ፡ ሰጠኋ
ቸው ፤ ከዚያም ፡ ያዝኩዋቸው ፤
ጥላቻየም ፡ እንዴት ፡ ነበረ !
45 ከከተማም ፡ እርሷ ፡ በደለኛ ፡
ኾና ፡ ያጠፋናትና ፡ እርሷ ፡ በጣሪ
ያዎችዋ ፡ ላይ ፡ ወዳቂ ፡ የኾነ
ችው ፡ ብዙ ፡ ናት ፤ ከተራቆተ
ችም ፡ የውሃ ፡ጉድጓድ ፡ ከተገነ
ባም ፡ ሕንጻ ፡ (ያጠፋነው ፡ ብዙ ፡
ነው) ።
46 ለነርሱም ፡ በነርሱ ፡ የሚያውቁባ
ቸው ፡ ልቦች ፡ ወይም ፡ በነርሱ ፡
የሚሰሙባቸው ፡ ጆሮዎች ፡ ይኖ
ሩዋቸው ፡ ዘንድ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
አይኼዱምን ? እነሆ ፡ ዓይኖች ፡
አይታወሩም ፡ ግን ፡ እነዚያ ፡ በደ
ረቶች ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ልቦች ፡
ይታወራሉ ።
47 አላህም ፡ ቀጠሮውን ፡ በፍጹም ፡
የማይጥስ ፡ ሲኾን ፡ በቅጣት ፡ ያቻ
ኩሉሃል ፤ እጌታህም ፡ ዘንድ ፡
አንዱ ፡ ቀን ፡ ከምትቆጥሩት ፡
(ቀን) ፡ እንደ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡
ነው ።
48 ከከተማ ፡ እርሷ ፡ በዳይ ፡ ኾና ፡
ለርሷ ፡ ጊዜ ፡ የሰጠኋትና ፡ ከዚ
ያም ፡ የያዝኳት ፡ ብዙ ፡ ናት ፤
መመለሻም ፡ ወደኔ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
49 ፡—እላንታ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! እኔ ፡
ለናንተ፡ ግልጽ፡ አስጠንቃቂ፡ ብቻ፡
ነኝ ፡ በላቸው ።
50 እነዚያም ፡ ያመኑ ፡ መልካም ፡
ሥራዎችንም ፡ የሠሩ ፡ ለነርሱ ፡
ምሕረትና ፡ ያማረ ፡ ሲሳይ ፡ አላ
ቸው ።
51 እነዚያም ፡ የሚያመልጡ ፡ መስሏ
ቸው ፡ ታምራቶቻችንን ፡ በመን
ቀፍ ፡ የተጉ ፡ እነሱ ፡ የእሳት ፡
ጓዶች ፡ ናቸው ።
52 ከመልክተኛና ፡ ከነቢይም ፡ ከአ
ንተ ፡ በፊት ፡ አንድንም ፡ አልላ
ክንም ፡ ባነበበ(ና ፡ ዝም ፡ ባለ) ፡
ጊዜ ፡ ሰይጣን ፡ በንባቡ ፡ ላይ ፡
(ማጥመሚያን ፡ ቃል) ፡ የሚጥል ፡
ቢኾን ፡ እንጅ ፤ ወዲያውም ፡
አላህ ፡ ሰይጣን ፡ የሚጥለውን ፡
ያስወግዳል ፤ ከዚያም ፡ አላህ ፡
አንቀጾቹን ፡ ያጠነክራል ፤ አላ
ህም ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።
53 ሰይጣን ፡ የሚጥለውን ፡ ነገር ፡
ለነዚያ ፡ በልቦቻቸው ፡ ውስጥ ፡
በሺታ ፡ ላለባቸው ፡ ልቦቻቸውም፡
ደረቆች ፡ ለኾኑት ፡ ፈተና ፡ ሊያደ
ርግ ፡ (ይጥላል) ፤ በዳዮችም ፡ ከው
ነት ፡ በራቀ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ውስጥ ፡
ናቸው ።
54 እነዚያም ፡ ዕውቀትን ፡ የተሰ
ጡት ፡ እርሱ ፡ (ቁርአን) ፡ ከጌ
ታህ ፡ የኾነ ፡ እውነት ፡ መኾኑን ፡
እንዲያውቁና ፡ በርሱ ፡ እንዲያ
ምኑ ፡ ልቦቻቸውም ፡ ለርሱ ፡ እን
ዲረኩ ፡ (ያጠነክራል) ፤ አላህም ፡
እነዚያን ፡ ያመኑትን ፡ ወደ ፡ ቀጥ
ተኛው ፡ መንገድ ፡ በእርግጥ ፡
መሪ ፡ ነው ።
55 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡ ሰዓ
ቲቱ ፡ በድንገት ፡ እስከምትመጣባ

ቸው ፡ ወይም ፡ (ከደግ ፡ ነገር) ፡
መካን ፡ የኾነው ፡ ቀን ፡ ቅጣት ፡
እስከሚመጣባቸው ፡ ድረስ ፡
ከርሱ ፡ (ከቁርአን) ፡ በመጠራጠር
ውስጥ ፡ ከመኾን ፡ አይወገዱም ።

56 በዚያ ፡ ቀን ፡ ንግሥናው ፡ የአ
ላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በመካከላቸው ፡
ይፈርዳል ፤ እነዚያም ፡ ያመኑት ፡
መልካም ፡ ሥራዎችንም ፡ የሠ
ሩት ፡ በመደሰቻ ፡ ገነቶች ፡ ው
ስጥ ፡ ናቸው ።

57 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ በአንቀጾቻች
ንም ፡ ያስተባበሉት ፡ እነዚያ ፡ ለነ
ርሱ ፡ አዋራጅ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ፤

58 እነዚያም ፡ በአላህ ፡ ሃይማኖት ፡
የተሰደዱ ፡ ከዚያም ፡ የተገደሉ ፡
ወይም ፡ የሞቱ ፡ አላህ ፡ መልካ
ምን ፡ ሲሳይ ፡ በእርግጥ ፡ ይሰጣቸ
ዋል ፡ አላህም ፡ እርሱ ፡ ከሰጪ
ዎች ፡ ሁሉ ፡ በላጭ ፡ ነው ።

59 የሚወዱትን ፡ መግቢያ ፡ (ገነ
ትን) ፡ በእርግጥ ፡ ያገባቸዋል ፤
አላህም ፡ በእርግጥ ፡ ዐዋቂ ፡
ታጋሽ ፡ ነው ።

60 (ነገሩ) ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በሱ ፡ በተበ
ደለበትም ፡ ብጤ ፡ የተበቀለ ፡
ሰው ፡ ከዚያም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
ግፍ ፡ የተዋለበት ፡ አላህ ፡ በእር
ግጥ ፡ ይረዳዋል ፤ አላህ ፡ ይቅር ፡
ባይ ፡ መሐሪ ፡ ነውና ፤

61 ይህ ፡ አላህ ፡ ሌሊትን ፡ በቀን ፡
ውስጥ ፡ የሚያስገባ ፡ ቀንንም ፡
በሌሊት ፡ ውስጥ ፡ የሚያስገባ ፡
(ቻይ) ፡ አላህም ፡ ሰሚ ፡ ተመል
ካች ፡ በመኾኑ ፡ ነው ።

62 ይህ ፡ አላህ ፡ እርሱ ፡ እውነት ፡
በመኾኑ ፡ ከርሱም ፡ ሌላ ፡ የሚገ
ዙት ፡ ነገር ፡ እርሱ ፡ ፍጹም ፡
ውሸት ፡ በመኾኑ ፡ አላህም ፡
እርሱ ፡ የሁሉ ፡ በላይ ፡ ታላቅ ፡
በመኾኑ ፡ ነው ።

63 አላህ ፡ ከሰማይ ፡ ውሃን ፡ ማውረ
ዱንና ፡ ምድር ፡ የምትለመልም ፡
መኾኗን ፡ አታይምን ? አላህ ፡
ርኅሩኅ ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

64 በሰማያት ፡ ውስጥ ፡ ያለውና ፡ በም
ድር ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡
የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ አላህም ፡
እርሱ ፡ ተብቃቂው ፡ ምስጉኑ ፡
ነው ።

65 አላህ ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ያለን ፡
ሁሉ ፡ ለናንተ ፡ የገራላችሁ ፡ መር
ከቦችንም ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ በፈ
ቃዱ ፡ የሚንሻለሉ ፡ ሲኾኑ ፡ (የገ
ራላችሁ) ፡ መኾኑን ፡ ሰማይንም ፡
በፈቃዱ ፡ ካልኾነ ፡ በምድር ፡
ላይ ፡ እንዳትወድቅ ፡ የሚይዛት ፡
መኾኑን ፡ አላየህምን ? አላህ ፡ ለሰ
ዎች ፡ በእርግጥ ፡ ርኅሩኅ ፡ አዛኝ ፡
ነው ።

66 እርሱም ፡ ያ ፡ ሕያው ፡ ያደረጋ
ችሁ ፡ ነው ፤ ከዚያም ፡ ይገድላች
ኋል ፤ ከዚያም ፡ ሕያው ፡ ያደርጋ
ችኋል ፤ ሰው ፡ በእርግጥ ፡ በጣም ፡
ከሓዲ ፡ ነው ።

67 ለየሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ እነሱ ፡ የሚሠ
ሩበት ፡ የኾነን ፡ ሥርዓተ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ አድርገናል ፤ ስለዚህ ፡ በነ
ገሩ ፡ አይከራከሩህ ፤ ወደ ፡ ጌታህ ፡
መንገድም ፡ ጥራ ፤ አንተ ፡ በእር
ግጥ ፡ በቅኑ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡
ነህና ።

68 ቢከራከሩህም ፡ አላህ ፡ የምትሠሩ
ትን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፡ በላ
ቸው ።

69 አላህ ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ በዚያ ፡
በርሱ ፡ ትለያዩበት ፡ በነበራች



ሁት ፡ ሁሉ ፡ በመካከላችሁ
ይፈርዳል ።

70 አላህ ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡
ውስጥ ፡ ያለን ፡ ሁሉ ፡ በእርግጥ ፡
የሚያውቅ ፡ መኾኑን ፡ አታውቅ
ምን ? ይህ ፡ በመጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡
(የተመዘገበ) ፡ ነው ፤ ይህ ፡ በአ
ላህ ፡ ላይ ፡ ገር ፡ ነው ።

71 ከአላህ ፡ ሌላም ፡ በርሱ ፡ ማስረ
ጃን ፡ ያላወረደበትን ፡ ለነርሱም ፡
በርሱ ፡ ዕውቀት ፡ የሌላቸውን ፡
ነገር ፡ ይግገዛሉ ፤ ለበዳዮችም ፡
ምንም ፡ ረዳት ፡ የላቸውም ።

72 አንቀጾቻችንም ፡ የተብራሩ ፡
ኾነው ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ በሚነበቡ ፡
ጊዜ ፡ በነዚያ ፡ በካዱት ፡ ሰዎች ፡
ፊቶች ፡ ላይ ፡ ጥላቻን ፡ ታውቃ
ለህ ፤ በነዚያ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ አንቀ
ጾቻችንን ፡ በሚያነቡት ፡ ላይ ፡
በኀይል ፡ ሊዘልሉባቸው ፡ ይቃረ
ባሉ ፤ ከዚሃችሁ ፡ ይልቅ ፡ የከፋን ፡
ነገር ፡ ልንገራችሁን ? በላቸው ፤
(እርሱም) ፡ እሳት ፡ ናት ፤ አላህ ፡
ለነዚያ ፡ ለካዱት ፡ ሰዎች ፡ ቀጥሯ
ታል ፤ ምን ፡ ትከፋም ፡ መመለሻ!

73 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! አስደናቂ ፡
ምሳሌ ፡ ተገለጸላችሁ ፤ ለርሱም ፡
አድምጡት ፤ እነዚያ ፡ ከአላህ ፡
ሌላ ፡ የምትግገዟቸው ፡ (ጣዖ
ታት) ፡ ዝምብን ፡ ፈጽሞ ፡ አይፈ
ጥሩም ፤ ለርሱ ፡ (ለመፍጠር) ፡
ቢሰበሰቡም ፡ እንኳ ፡ (አይች
ሉም) ፤ አንዳችንም ፡ ነገር ፡
ዝንቡ ፡ ቢነጥቃቸው ፡ ከርሱ ፡
አያስጥሉትም ፤ ፈላጊውም ፡ ተፈ
ላጊውም ፡ ደከሙ ። (1) ፤

74 አላህን ፡ ተገቢ ፡ ክብሩን ፡ አላከበ
ሩትም ፤ አላህ ፡ በጣም ፡ ኀያል ፡
አሸናፊ ፡ ነው ።

75 አላህ ፡ ከመላእክት ፡ ውስጥ ፡ መል
ክተኞችን ፡ ይመርጣል ፤ ከሰዎ
ችም ፡ (እንደዚሁ) ፤ አላህ ፡ ሰሚ ፡
ተመልካች ፡ ነው ።

76 በስተፊታቸው ፡ ያለን ፡ በስተኋላ
ቸውም ፡ ያለን ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል ፤
ወደ ፡ አላህም ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡
ይመለሳሉ ።

77 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሰዎች ፡
ሆይ ! (በስግደታችሁ) ፡ አጐን
ብሱ ፡ በግንባራችሁም ፡ ተደፉ ፤
ጌታችሁንም ፡ ተገዙ ፤ በጎንም ፡
ነገር ፡ ሥሩ ፤ ልትድኑ ፡ ይከጀልላ
ችኋልና ።

78 በአላህም ፡ ሃይማኖት ፡ ተገቢውን
ትግል ፡ ታገሉ ፤ እርሱ፡ መርጧች
ኋል ፤ በናንተም ፡ ላይ ፡ በሃይማ
ኖቱ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ችግር ፡
አላደረገባችሁም ፤ የአባታችሁን ፡
የኢብራሂምን ፡ ሃይማኖት ፡ ተከ
ተሉ ፤ እርሱ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡
ሙስሊሞች፡ ብሎ፡ ሰይሟችኋል፤
በዚህም ፡ (ቁርአን) ፤ መልክተ
ኛው ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ መስካሪ ፡
እንዲኾን ፡ እናንተም ፡ በሰዎቹ ፡
ላይ ፡ መስካሪዎች ፡ እንድትኾኑ ፡
(ሙስሊሞች፡ ብሎ፡ ሰይሟችኋል)፤
ሶላትንም ፡ አስተካክላችሁ ፡ ስ
ገዱ ፡ ዘካንም ፡ ስጡ ፤ በአላህም ፡
ተጠበቁ ፤ እርሱ ፡ ረዳታችሁ ፡
ነው ፤ (እርሱ) ፡ ምን ፡ ያምር ፡
ጠባቂ! ምን ፡ ያምርም ፡ ረዳት!

1 ገዢውም ፡ ተገዢውም ፡ ደካሞች ፡ ናቸው።

★ ★ ★

23ኛ ፡ ሱረቱ፡ አል-ሙእሚኑን ፡ (የምእምናን፡ ምዕራፍ)። በመካ፡ የወረደች፡ ናት ፤ አያትዋ፡ (አንቀጾችዋ)፡ 118 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 ምእምናን ፡ ፍላጎታቸውን ፡ ሁሉ በእርግጥ ፡ አገኙ ፡ (ዳኑ) ።

2 እነዚያ ፡ እነሱ ፡ በስግደታቸው ፡ ውስጥ ፡ (አላህን) ፡ ፈሪዎች ፤

3 እነዚያም ፡ እነሱ ፡ ከውድቅ ፡ ንግግር ፡ ራቂዎች ፤

4 እነዚያም ፡ እነሱ ፡ ዘካን ፡ ሰጭዎች ፤

5 እነዚያም ፡ እነሱ ፡ ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች ፡ የኾኑት ፡ (አገኙ) ።

6 በሚስቶቻቸው ፡ ወይም ፡ እጆቻቸው ፡ በያዟቸው ፡ (ባሪያዎች) ፡ ላይ ፡ ሲቀር ፡ እነሱ ፡ (በነዚህ) ፡ የማይወቀሱ ፡ ናቸውና ።

7 ከዚህም ፡ ወዲያ ፡ የፈለጉ፡ ሰዎች፡ እነዚያ ፡ እነሱ ፡ ወሰን ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ።

8 እነዚያም ፡ እነሱ ፡ ለአደራዎቻቸውና ፡ ለቃል ፡ ኪዳናቸው ፡ ጠባቂዎች ፤

9 እነዚያም ፡ እነሱ ፡ በስግደቶቻቸው ፡ ላይ ፡ የሚጠባበቁ ፤ የኾኑት ፡ (አገኙ) ፤

10 እነዚያ ፡ ወራሾቹ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ፤

11 እነዚያ ፡ ፊርደውስን ፡ (ላዕላይ ፡ ገነትን) ፤ የሚወርሱ ፡ ናቸው ፤ እነሱ ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ናቸው ።

12 በእርግጥም ፡ ሰውን ፡ ከነጠረ ፡ ጭቃ ፡ ፈጠርነው ።

13 ከዚያም ፡ በተጠበቀ ፡ መርጊያ ፡ ውስጥ ፡ የፍቶት ፡ ጠብታ ፡ አደረግነው ።

14 ከዚያም ፡ ጠብታዋን ፡ (በአርባ ፡ ቀን) ፡ የረጋ ፡ ደም ፡ አድርገን ፡ ፈጠርን ፤ የረጋውንም ፡ ደም ፡ ቁራጭ ፡ ሥጋ ፡ አድርገን ፡ ፈጠርን ፤ ቁራጭዋንም ፡ ሥጋ ፡ አጥንቶች ፡ አድርገን ፡ ፈጠርን ፤ አጥንቶቹንም ፡ ሥጋን ፡ አለበስናቸው ፤ ከዚያም ፡ (ነፍስን ፡ በመዝራት) ፡ ሌላ ፡ ፍጥረትን ፡ አድርገን ፡ አስገኘነው ፤ ከሰዓሊዎችም ፡ ሁሉ ፡ በላጭ ፡ የኾነው ፡ አላህ ፡ ላቀ ።

15 ከዚያም ፡ እናንተ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በእርግጥ ፡ ሟቾች ፡ ናችሁ ።

16 ከዚያም ፡ እናንተ ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ትቀሰቀሳላችሁ ።

17 በእርግጥም ፡ ከበላያችሁ ፡ ሰባትን ፡ ሰማያት ፡ ፈጠርን ፤ ከፍጥረቶቹም ፡ ዘንጊዎች ፡ አይደለንም ።

18 ከሰማይም ፡ ውሃን ፡ በልክ ፡ አወረድን ፤ በምድርም ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጥነው ፤ እኛም ፡ እርሱን ፡ በማስወገድ ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ ቻዮች ፡ ነን ።



19 በርሱም ፡ ከዘምባባዎችና ፡ ከወይኖች ፡ የኾኑን ፡ አትክልቶች ፡ ለናንተ ፡ አስገኘንላችሁ ፤ በውስጧ ፡ ለናንተ ፡ ብዙ ፡ ፍራፍሬዎች ፡ አሏችሁ ፤ ከርሷም ፡ ትበላላችሁ ።

20 ከሲና ፡ ተራራም ፡ የምትወጣን ፡ ዛፍ ፡ በቅባትና ፡ ለበይዎችም ፡ መባያ ፡ በሚኾን ፡ (ዘይት) ፡ ተቀላቅላ ፡ የምትበቅልን ፡ (አስገኘንላችሁ) ።

21 ለናንተም ፡ በግመል ፡ በከብት ፡ በፍየልና ፡ በበግ ፡ መገምገሚያ ፡ አላችሁ ፤ በሆዶችዋ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ (ወተት) ፡ እናጠጣችኋለን ፤ ለናንተም ፡ በርሷ ፡ ብዙ ፡ ጥቅሞች ፡ አሏችሁ ፤ ከርሷም ፡ ትበላላችሁ ።

22 በርሷም ፡ ላይ ፡ በመርከብም ፡ ላይ ፡ ትጫናላችሁ ።

23 ኑሕንም ፡ ወደ ፡ ሕዝቦቹ ፡ በእርግጥ ፡ ላክነው ፤ ወዲያውም ፡— ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ! አላህን ፡ ተገዙ ፤ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ አምላክ ፡ የላችሁም ፤ አትጠነቀቁምን ? አላቸው ።

24 ከሕዝቦቹም ፡ እነዚያ ፡ ታላላቆቹ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፡— ይህ ፡ ብጤያችሁ ፡ ሰው ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፤ በናንተ ፡ ላይ ፡ መብለጥን ፡ ይፈልጋል ፤ አላህም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ መላእክትን ፡ ባወረደ ፡ ነበር ፤ ይህንንም ፡ (የሚለውን) ፡ በመጀመሪያዎቹ ፡ አባቶቻችን ፡ አልሰማንም ።

25 እርሱ ፡ በርሱ ፡ ዕብደት ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፤ በርሱም ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ (ሞቱ) ፡ ድረስ ፡ ተጠባበቁ ፡ (አሉ) ።

26 (ኑሕም) ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ! ባስተባበሉኝ ፡ ምክንያት ፡ እርዳኝ ፡ አለ ።

27 ወደርሱም ፡ (እንዲህ ፡ ስንል) ፡ ላክን ፡— በተመልካችነታችንና ፡ በትእዛዛችን ፡ ታንኳን ፡ ሥራ ፤ ትእዛዛችንም ፡ በመጣና ፡ እቶኑ ፡ በፈለቀ ፡ ጊዜ ፡ በውስጧ ፡ ከሁሉም ፡ ሁለት ፡ ዓይነቶችን ፡ ቤተሰቦችህንም ፡ ከነሱ ፡ (ጠፊ ፡ በመኾን) ፡ ቃል ፡ ያለፈበት ፡ ብቻ ፡ ሲቀር ፤ አግባ ፤ በነዚያም ፡ በበደሉት ፡ ሰዎች ፡ ነገር ፡ አታነጋግረኝ ፤ እነሱ ፡ ተሰጣሚዎች ፡ ናቸውና ።

28 አንተም ፡ አብረውህ ፡ ካሉት ፡ ጋር ፡ በታንኳይቱ ፡ ላይ ፡ በተደላደልክ ፡ ጊዜ ፡ ምስጋና ፡ ለዚያ ፡ ከበደለኞች ፡ ሕዝቦች ፡ ላዳነን ፡ አላህ ፡ ይገባው ፡ በል ።

29 በልም ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ! ብሩክ ፡ የኾነን ፡ ማውረድ ፡ አውርደኝ ፤ አንተም ፡ ከአውራጆች ፡ ሁሉ ፡ በላጭ ፡ ነህ ።

30 በዚህ ፡ ውስጥ ፡ (ለከሃሊነታችን) ፡ ምልክቶች ፡ አሉበት ፤ እነሆ ! (የኑሕን ፡ ሰዎች) ፡ በእርግጥም ፡ ፈታታኞች ፡ ነበርን ።

31 ከዚያም ፡ ከኋላቸው ፡ ሌሎችን ፡ የክፍለ ፡ ዘመን ፡ ሕዝቦች ፡ አስገኘን ።

32 በውስጣቸውም ፡ ከነሱ ፡ የኾነን ፡ መልክተኛ ፡ አላህን ፡ ተገዙ ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የላችሁም፡ አትጠነቀቁምን ? በማለት ፡ ላክን፤

33 ከሕዝቦቹም ፡ እነዚያ ፡ የካዱት ፡ በመጨረሻይቱም ፡ ቀን ፡ መገናኘት ፡ ያስተባበሉት ፡ በቅርቢ

ቱም ፡ ሕይወት ፡ ያቀማጠልና
ቸው ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡— ይህ ፡
ብጤያችሁ ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡
አይደለም ፤ ከርሱ ፡ ከምትበሉት ፡
ምግብ ፡ ይበላል ፤ ከምትጠጡ
ትም ፡ ውሃ ፡ ይጠጣል ፡ አሉ ።
34 ብጤያችሁም ፡ የኾነን ፡ ሰው ፡
ብትታዘዙ ፡ እናንተ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡
በእርግጥ ፡ የተሞኛችሁ ፡ ናችሁ ፤
(አሉ) ።
35 እናንተ ፡ በሞታችሁና ፡ ዐፈርና ፡
አጥንቶችም ፡ በኾናችሁ ፡ ጊዜ ፡
እናንተ ፡ (ከመቃብር) ፡ ትውወጣ
ላችሁ ፡ በማለት ፡ ያስፈራራችኋ
ልን ?
36 ያ ፡ የምትስፈራሩበት ፡ ነገር ፡
ራቀ ፤ በጣም ፡ ራቀ ።
37 እርሷ ፡ (ሕይወት) ፡ ቅርቢቱ ፡
ሕይወታችን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደ
ለችም ፤ እንሞታለን ፤ (ልጆቻችን፡
ስለሚተኩ) ፡ ሕያውም ፡ እንኾና
ለን ፤ እኛም ፡ ተቀስቃሾች ፡ አይደ
ለንም ።
38 እርሱ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ውሸትን ፡
የቀጠፈ ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይ
ደለም ፤ እኛም ፡ ለርሱ ፡ አማኞች ፡
አይደለንም ፤ (አሉ) ።
39 (መልክተኛውም) ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ !
ስላስተባበሉኝ ፡ እርዳኝ ፤ አለ ።
40 (አላህም) ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡
(በጥፋታቸው) ፡ በእርግጥ ፡ ተጸጸ
ቾች ፡ ይኾናሉ ፡ አለው ።
41 ወዲያውም ፡ (የጥፋት) ፡ ጩኸ
ቲቱ ፡ በውነት ፡ ያዘቻቸው ፤
እንደ ፡ ጉርፍ ፡ ግብስባሽም ፡ አደ
ረግናቸው ፤ ለበደለኞች ፡ ሕዝቦ
ችም ፡ (ከእዝነት) ፡ መራቅ ፡ ተገ
ባቸው ።
42 ከዚያም ፡ ከነሱ ፡ በኋላ ፡ ሌሎችን፡
የክፍለ ፡ ዘመናት ፡ ሕዝቦች ፡ አስ
ገኘን ።
43 ማንኛይቱም ፡ ሕዝብ ፡ ጊዜያዋን ፡
አትቀድምም ፤ አይቆቆዩምም ።
44 ከዚያም ፡ መልክተኞቻችንን ፡
የሚከታተሉ ፡ ኾነው ፡ ላክን ፤ ማን
ኛይቱንም ፡ ሕዝብ ፡ መልክተ
ኛዋ ፡ በመጣላት ፡ ቍጥር ፡ አስ
ተባበሉት ፡ ከፊላቸውንም ፡ በከ
ፊሉ ፡ (በጥፋት) ፡ አስከታተልን ፤
ወሬዎችም ፡ አደረግናቸው ፤ ለማያ
ምኑም ፡ ሕዝቦች ፡ (ከእዝነታ
ችን) ፡ መራቅ ፡ ተገባቸው ።
45 ከዚያም ፡ ሙሳንና ፡ ወንድሙን ፡
ሃሩንን ፡ በታምራታችንና ፡ በግ
ልጽ ፡ አስረጅ ፡ ላክን ።
46 ወደ ፡ ፈርዖንና ፡ ወደ ፡ ሹማምቹ ፡
(ላክናቸው) ፤ ኮሩም ፤ የተንበጣ
ረሩ ፡ ሕዝቦችም ፡ ነበሩ ።
47 ብጤያችንም ፡ ለኾኑ ፡ ሁለት ፡
ሰዎች ፡ ሕዝቦቻቸው ፡ ለኛ ፡
ተገገርዎች ፡ ኾነው ፡ ሳሉ ፡ እና
ምናለን ? አሉ ።
48 አስተባበሉዋቸውም ፤ ከጠፊዎ
ቹም ፡ ኾኑ ።
49 ሙሳንም ፡ (ነገዶቹ) ፡ ይምመሩ ፡
ዘንድ ፡ መጽሐፍን ፡ በእርግጥ ፡
ሰጠነው ።
50 የመርየምን ፡ ልጅና ፡ እናቱንም ፡
ታምር ፡ አደረግናቸው ፤ የመደላ
ደልና ፡ የምንጭ ፡ ባለቤት ፡ ወደ ፡
ኾነች ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራም ፡ አስ
ጠጋናቸው ።
51 እላንተ ፡ መልክተኞች ፡ ሆይ !
ከተፈቀዱት ፡ ምግቦች ፡ ብሉ ፤
በጎ ፡ ሥራንም ፡ ሥሩ ፤ እኔ ፡ የም
ትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነኝ ።



52 ይህችም ፡ (በአንድ ፡ አምላክ ፡
የማመን ፡ ሕግጋት) ፡ አንድ ፡ መን
ገድ ፡ ስትኾን ፡ ሃይማኖታችሁ ፡
ናት ፤ እኔም ፡ ጌታችሁ ፡ ነኝና ፡
ፍሩኝ ፤
53 (ከዚያ ፡ ተከታዮቻቸው) ፡ የሃይ
ማኖት ፡ ነገራቸውንም ፡ በመካከ
ላቸው ፡ ክፍልፍሎች ፡ አድርገው፡
ቆራረጡ ፤ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ እነሱ ፡
ዘንድ ፡ ባለው ፡ ሃይማኖት ፡ ተደሳ
ቾች ፡ ናቸው ፤
54 እስከ ፡ ጊዜያቸውም ፡ ድረስ ፡ በጥ
መታቸው ፡ ውስጥ ፡ ተዋቸው ።
55 ከገንዘብና ፡ ከልጆች ፡ በርሱ ፡
የምንጨምርላቸውን ፡ ያስባሉን ?
56 በበጎ ፡ ነገሮች ፡ የምንቻኮልላ
ቸው ፡ መኾንን ፡ (ያስባሉን ?)
አይደለም ፤ (ለማዘንጋት ፡ መኾ
ኑን) ፡ አያውቁም ።
57 እነዚያ ፡ እነሱ ፡ ጌታቸውን ፡ ከመ
ፍራት ፡ የተነሳ ፡ ተጨናቂዎች ፡
የኾኑት ፡
58 እነዚያም ፡ እነሱ ፡ በጌታቸው ፡
ታምራቶች ፡ የሚያምኑት ፡
59 እነዚያም ፡ እነሱ ፡ በጌታቸው ፡
(ጣዖትን) ፡ የማያጋሩት ፡
60 እነዚያም ፡ የሚሰጡትን ፡ ነገር ፡
እነርሱ ፡ ወደ ፡ ጌታቸው ፡ ተመላ
ሾች ፡ መኾናቸውን ፡ ልቦቻቸው ፡
የሚፈሩ ፡ ኾነው ፡ የሚሰጡት ።
61 እነዚያ ፡ በመልካም ፡ ሥራዎች ፡
ይጣደፋሉ ፤ እነሱም ፡ ለርሷ ፡ ቀዳ
ሚዎች ፡ ናቸው ።
62 ማንኛይቱንም ፡ ነፍስ ፡ ችሎታ
ዋን ፡ እንጂ ፡ አናስገድዳትም ፤
እኛም ፡ ዘንድ ፡ በውነት ፡ የሚና
ገር ፡ መጽሐፍ ፡ አለለ ፤ እነሱም ፡
አይበደሉም ።
63 በውነቱ ፡ (ከሓዲዎች) ፡ ልቦቻ
ቸው ፡ ከዚህ ፡ (መጽሐፍ) ፡ በዝን
ጋቴ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ፤ ለነርሱም ፡
ከዚህ ፡ ሌላ ፡ እነሱ ፡ ለርሷ ፡ ሠሪ
ዎችዋ ፡ የኾኑ ፡ (መጥፎ) ፡ ሥራ
ዎች ፡ አሏቸው ።
64 ቅምጥሎቻቸውንም ፡ በቅጣት ፡
በያዝናቸው ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡
እነሱ ፡ ይወተውታሉ ።
65 ፡—ዛሬ ፡ አትወትውቱ ፤ እናንተ ፡
ከኛ ፡ ዘንድ ፡ አትረዱም ።
66 አንቀጾቼ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ በእር
ግጥ ፡ ይነበቡላችሁ ፡ ነበር ፤ በተረ
ከዞቻችሁም ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ኋላ
ችሁ ፡ ትመለሱ ፡ ነበራችሁ ።
67 በርሱ ፡ (በክልሉ ፡ ቤት) ፡ ኩሩ
ዎች ፡ ሌሊት ፡ ተጫዋቾች ፡ (ቁር
አንንም) ፡ የምትተው ፡ ኾናችሁ ፡
(ትመለሱ ፡ ነበራችሁ ፡ ይባላሉ) ።
68 (የቁርአንን) ፡ ንግግሩንም ፡ አያስ
ተነትኑምን? ወይስ ፡ ለመጀመሪያ
ዎቹ ፡ አባቶቻቸው ፡ ያልመጣ ፡
ነገር ፡ መጣባቸውን?
69 ወይስ ፡ መልክተኛቸውን ፡ አላወ
ቁምን ? ስለዚህ ፡ እነርሱ ፡ ለርሱ ፡
ከሓዲዎች ፡ ናቸውን?
70 ወይስ ፡ በርሱ ፡ ዕብደት ፡ አለ
በት ፡ ይላሉን? አይደለም ፤ እውነ
ትን ፡ ይዞ ፡ መጣላቸው ፤ አብዛኞ
ቻቸውም ፡ እውነትን ፡ ጠይዎች ፡
ናቸው ።
71 አላህም ፡ ዝንባሌዎቻቸውን ፡ በተ
ከተለ ፡ ኖሮ ፡ ሰማያትና ፡ ምድር ፡
በውስጣቸውም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡
በእርግጥ ፡ በተባላሸ ፡ ነበር ፤ ይልቁ
ንም ፡ ክብራቸው ፡ ያለበትን ፡
ቁርአን ፡ አመጣንላቸው ፤ እነሱም ፡
ከክብራቸው ፡ ዘንጊዎች ፡ ናቸው ።

72 ወይስ ፡ ግብርን ፡ ትጠይቃቸዋ
ለህን ? የጌታህም ፡ ችሮታ ፡ በላጭ
ነው ፤ እርሱም ፡ ከሰጪዎች ፡
ሁሉ ፡ በላጭ ፡ ነው ።
73 አንተም ፡ ወደ ፡ ቀጥተኛው ፡ መን
ገድ ፡ በእርግጥ ፡ ትጠራቸዋለህ ።
74 እነዚያም ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ዓ
ለም ፡ የማያምኑት ፡ ከትክክለ
ኛው ፡ መንገድ ፡ ተዘንባዮች ፡
ናቸው ።
75 ባዘንንላቸውና ፡ ከጉዳትም ፡ በነ
ርሱ ፡ ያለውን ፡ ባነሳንላቸው ፡
ኖሮ ፡ በጥመታቸው ፡ ውስጥ ፡
የሚዋልሉ ፡ ኾነው ፡ ይዘወትሩ ፡
ነበር ።
76 በእርግጥም ፡ በቅጣት ፡ ያዝናቸው
ታዲያ ፡ ለጌታቸው ፡ አልተናነ
ሱም ፤ አይዋደቁምም ።
77 በነሱም ፡ ላይ ፡ የብርቱ ፡ ቅጣት ፡
ባለቤት ፡ የኾነ ፡ ደጃፍን ፡ በከፈት
ንባቸው ፡ ጊዜ ፡ እነሱ ፡ ያን ፡ ጊዜ፡
በርሱ ፡ ተስፋ ፡ ቆራጮች ፡
ናቸው ።
78 እርሱም ፡ ያ ፡ መስሚያዎችንና ፡
ማያዎችን ፡ ልቦችንም ፡ ለናንተ ፡
የፈጠረላችሁ ፡ ነው ፤ ጥቂትን ፡
እንጅ ፡ አታመሰግኑም ።
79 እርሱም ፡ ያ ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡
የበተናችሁ ፡ ነው ፤ ወደርሱም ፡
ትሰበሰባላችሁ ።
80 እርሱም ፡ ያ ፡ ሕያው ፡ የሚያደ
ርግ ፡ የሚገድልም ፡ ነው ፤ የሌሊ
ትና ፡ የቀን ፡ መተካካትም ፡ የርሱ፡
ነው ፤ አታውቁምን?
81 ይልቁንም ፡ (የመካ ፡ ከሓዲዎች) ፡
የፊተኞቹ ፡ ሕዝቦች ፡ እንዳሉት ፡
ብጤ ፡ አሉ ።
82 ፡-በሞትንና ፡ ዐፈርና ፡ አጥንቶች ፡
በኾን ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ ተቀስቃሾች ፡
ነን ? አሉ ።
83 ይህንን ፡ እኛም ፡ ከእኛ ፡ በፊትም፡
የነበሩት ፡ አባቶቻችን ፡ በእርግጥ፡
ተቀጥረናል ፤ ይህ ፡ የመጀመሪያ
ዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ተረቶች ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አይደለም ፡ (አሉ) ።
84 ፡—ምድርና ፡ በውስጥዋ ፡ ያለው ፡
ሁሉ ፡ የማን ፡ ነው ? የምታውቁ ፡
ብትኾኑ ፡ (ንገሩኝ) ፤ በላቸው ።
85 በእርግጥ ፡ የአላህ ፡ ነው ፡ ይሉ
ሃል ፤ ታዲያ ፡ አትገሠጹምን ?
በላቸው ።
86 ፡—የሰባቱ ፡ ሰማያት ፡ ጌታና ፡
የታላቁ ፡ ዐርሽ ፡ ጌታ ፡ ማን ፡
ነው ? በላቸው ።
87 በእርግጥ ፡ አላህ ፡ ነው ፡ ይሉሃል ፤
እንግዲያ ፡ አትፈሩትምን ? በላ
ቸው ።
88 ፡—የነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ግዛት ፡ በእጁ ፡
የኾነ ፡ እርሱ ፡ የሚጠብቅ ፡ በርሱ፡
ላይ ፡ የማይጠበቅ ፡ ማን ፡ ነው ?
የምታውቁ ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡
(መልሱልኝ) ፤ በላቸው ።
89 በእርግጥ ፡ አላህ ፡ ነው ፡ ይሉሃል ፤
ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ትታለላላችሁ?
በላቸው ።
90 ይልቁንም ፡ እውነትን ፡ አመጣ
ንላቸው ፡ እነርሱም ፡ (በመካዳ
ቸው) ፡ ውሸታሞች ፡ ናቸው ።
91 አላህ ፡ ምንም ፡ ልጅን ፡ አልያ
ዘም ፡ (አልወለደም) ፤ ከርሱም ፡
ጋር ፡ አንድም ፡ አምላክ ፡ የለም ፤
ያን ፡ ጊዜ ፡ (ሌላ ፡ አምላክ ፡ በነ
በረ) ፡ አምላክ ፡ ሁሉ ፡ በፈጠ
ረው ፡ ነገር ፡ በተለየ ፡ ነበር ፤
ከፊላቸውም ፡ በከፊሉ ፡ ላይ ፡



በላቀ ፡ ነበር ፤ አላህ ፡ ከሚመጥ
ኑት ፡ ሁሉ ፡ ጠራ ።
92 ሩቁንና ፡ ቅርቡንም ፡ ሁሉ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ፤ (በርሱ) ፡ ከሚያጋ
ሩትም ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ አለ ።
93 (ሙሐመድ ፡ ሆይ !) በል ፡—
ጌታዬ ፡ ሆይ ! የሚስፈራሩበትን ፡
(ቅጣት) ፡ ብታሳየኝ ፡
94 ጌታዬ ፡ ሆይ ! በበደለኞች ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ውስጥ ፡ አታድርገኝ ።
95 እኛም ፡ የምናስፈራራቸውን ፡
ነገር ፡ ልናሳይህ ፡ በእርግጥ ፡
ቻዮች ፡ ነን ።
96 በዚያች ፡ እርስዋ ፡ መልካም ፡
በኾነችው ፡ (ጠባይ) ፡ መጥፎይ
ቱን ፡ ነገር ፡ ገፍትር ፤ እኛ ፡ የሚ
ሉትን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ነን ።
97 በልም ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ! ከሰይ
ጣናት ፡ ጉትጎታዎች ፡ በአንተ ፡
እጠበቃለሁ ።
98 ባንተም ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ! (በነገ
ሮቼ) ፡ ወደኔ ፡ ከመጣዳቸው ፡ እጠ
በቃለሁ ።
99 አንዳቸውንም ፡ ሞት ፡ በመጣ
በት ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—
ጌታዬ ፡ ሆይ ! (ወደ ፡ ምድረ ፡
ዓለም) ፡ መልሱኝ ፤
100 በተውኩት ፡ ነገር ፡ በጎን ፡ ሥራ ፡
ልሠራ ፡ እከጅላለሁና ፤ (ይህን ፡
ከማለት) ፡ ይከልከል ፤ እርስዋ ፡
(1) እርሱ ፡ ተናጋሪዋ ፡ የኾነች ፡
ከንቱ ፡ ቃል ፡ ናት ፤ ከስተፊታቸ
ውም ፡ እስከሚቀሰቀሱበት ፡ ቀን ፡
ድረስ ፡ ግርዶ ፡ አለ ።
101 በቀንዱም ፡ በተነፋ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ፡
ቀን ፡ በመካከላቸው ፡ ዝምድና ፡
የለም ፤ አይጠያየቁምም ።
102 ሚዛኖቹም ፡ የከበዱለት ፡ ሰው ፡
እነዚያ ፡ እነሱ ፡ ፍላጐታቸውን ፡
ያገኙ ፡ ናቸው ።
103 ሚዛኖቹም ፡ የቀለሉበት ፡ ሰው ፡
እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ ነፍሶቻቸውን ፡
ያከሰሩ ፡ ናቸው ፤ በገሀነም ፡
ውስጥ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ናቸው ።
104 ፊቶቻቸውን ፡ እሳት ፡ ትገርፋቸዋ
ለች ፤ እነሱም ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡
ከንፈሮቻቸው ፡ የተኮማተሩ ፡ ና
ቸው ።
105 አንቀጾቼ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ የሚነበ
ቡላችሁና ፡ በነርሱ ፡ የምታስተባ
ብሉ ፡ አልነበራችሁምን? (ይባ
ላሉ) ።
106 ይላሉ ፡— ጌታችን ፡ ሆይ! በኛ ፡
ላይ ፡ መናጢነታችን ፡ አሸነፈ
ችን ፤ ጠማማዎችም ፡ ሕዝቦች ፡
ነበርን ፤
107 ጌታችን ፡ ሆይ! ከርሷ ፡ አውጣን ፤
(ወደ ፡ ክሕደት) ፡ ብንመለስም ፡
እኛ ፡ በዳዮች ፡ ነን ።
108 (አላህም) ፡ ወራዶች ፡ ኾናችሁ ፡
በውስጥዋ ፡ እርጉ ፤ አታናግሩ
ኝም ፤ ይላቸዋል ።
109 እነሆ ፡ ከባሮቼ ፡-ጌታችን ፡ ሆይ !
አምነናልና ፡ ማረን ፤ እዘንልንም ፤
አንተም ፡ ከአዛኞች ፡ ሁሉ ፡ ይበ
ልጥ ፡ አዛኝ ፡ ነህ ፡ የሚሉ ፡ ክፍ
ሎች ፡ ነበሩ ።
110 እኔን ፡ ማውሳትን ፡ እስካስረሷ
ችሁ ፡ ድረስም ፡ ማላገጫ ፡ አድር
ጋችሁ ፡ ያዛችኋቸው ፤ በነርሱም ፡
የምትስቁ ፡ ነበራችሁ ።
111 እኔ ፡ ዛሬ ፡ በትዕግሥታቸው ፡ ምክ
ንያት ፡ እነሱ ፡ ፍላጐታቸውን ፡
የሚያገኙት ፡ እነርሱ ፡ ብቻ ፡

1 ጌታዬ ፡ መልሱኝ ፡ ማለቱ ።

በመኾን ፡ መነዳኂቻቸው ፤ (ይላቻ
ዋል) ።
112 በምድር ፡ ውስጥ ፡ ከዓመታት ፡
ቊጥር ፡ ስንትን ፡ ቆያችሁ ፤ ይላቻ
ዋል ።
113 አንድ ፡ ቀንን ፡ ወይም ፡ ከፊል ፡
ቀንን ፡ ቆየን ፤ ቆጣሪዎቹንም ፡
ጠይቅ ፤ ይላሉ ።
114 እናንተ ፡ (የቆያችሁትን ፡ መጠን)፡
የምታውቁ ፡ ብትኾኑ ፡ ኖሮ ፡
(በእሳት ፡ ውስጥ ፡ በምትቆዩት ፡
አንጻር) ፡ ጥቂትን ፡ ጊዜ ፡ እንጂ ፡
አልቆያችሁም ፡ ይላቸዋል ።
115 የፈጠርናችሁ ፡ ለከንቱ ፡ መኾ
ኑን ፡ እናንተም ፡ ወደኛ ፡ የማትመ
ለሱ፡ መኾናችሁን፡ ጠረጠራችሁን?
(ለከንቱ፡የፈጠርናችሁ፡መሰላችሁን?)
116 የውነቱም ፡ ንጉሥ ፡ አላህ ፡ ከፍተ
ኛነት ፡ ተገባው ፤ ከርሱ ፡ ሌላ ፡
አምላክ ፡ የለም ፤ የሚያምረው ፡
ዐርሽ ፡ ጌታ ፡ ነው ።
117 ከአላህም ፡ ጋር ፡ ሌላን ፡ አምላክ ፡
ለርሱ ፡ በርሱ ፡ ማስረጃ ፡ የሌለ
ውን ፡ የሚገዛ ፡ ሰው ፡ ምርመ
ራው ፡ እጌታው ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡
ነው ፤ እነሆ ፡ ከሓዲዎች ፡ አይድ
ኑም ።
118 በልም ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ማር ፤
እዘንም ፤ አንተም ፡ ከአዛኞች ፡
ሁሉ ፡ በላጭ ፡ ነህ ።

## ምዕራፍ ፡ 24 ፡ አል-ኑር ። ክፍል ፡ 18 ።

24ኛ ፡ ሱረት ፡ አል-ኑር ፡ (የብርሃን ፡ ምዕራፍ) ። በመዲና ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 64 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፤ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 (ይህች) ፡ ያወረድናትና ፡ የደነገ
ግናት ፡ ምዕራፍ ፡ ናት ፤ በርሷም፡
ውስጥ ፡ ትገሠጹ ፡ ዘንድ ፡ ግል
ጾችን ፡ አንቀጾች ፡ አውርደናል ።
2 ዝሙተኛይቱና ፡ ዝሙተኛው ፡
ከሁለቱ ፡ እያንዳንዳቸውን ፡ (ያላ
ገቡ ፡ እንደኾኑ) ፡ መቶ ፡ ግርፋ
ትን ፡ ግረፋዋቸው፤ በነርሱም ፡
በአላህ ፡ ፍርድ ፡ ርኅራኄ ፡ አትያ
ዛችሁ ፤ በአላህና ፡ በመጨረሻው፡
ቀን ፡ የምታምኑ ፡ እንደ ፡ ኾና
ችሁ ፡ (አትራሩ) ፤ ቅጣታቸው
ንም ፤ ከምእምናን ፡ ጭፍሮች ፡
ይገኙበት ።
3 ዝሙተኛው ፡ ዝሙተኛይቱን ፡
ወይም ፡ አጋሪቱን ፡ እንጂ ፡ አያ
ገባም ፤ ዝሙተኛይቱንም ፡ ዝሙ
ተኛ ፡ ወይም ፡ አጋሪ ፡ እንጂ ፡
አያገባትም ፤ ይህም ፡ በምእም
ምናን ፡ ላይ ፡ ተከልክሏል ።
4 እነዚያም ፡ ጥብቆችን ፡ ሴቶች ፡
(በዝሙት) ፡ የሚሰድቡ ፡ ከዚ
ያም ፡ አራትን ፡ ምስክሮች ፡ ያላ
መጡ ፡ ሰማኒያን ፡ ግርፋት ፡
ግረፏቸው ፤ ከነርሱም ፡ ምስክር



ነትን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አትቀበሉ ፤
እነዚያም ፡ እነሱ ፡ አመጠኞች ፡
ናቸው ።
5 እነዚያ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የተጸጸ
ቱና ፡ ሥራቸውን ፡ ያሳመሩ ፡
ሲቀሩ ፤ አላህ ፡ በጣም ፡ መሓሪ ፡
አዛኝ ፡ ነውና ።
6 እነዚያም ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ (በዝ
ሙት) ፡ የሚሰድቡ ፡ ለነሱም ፡
ከነፍሶቻቸው ፡ በስተቀር ፡ ምስ
ክሮች ፡ የሌሏቸው ፡ የኾኑ ፡ የአን
ዳቸው ፡ ምስክርነት ፡ እርሱ ፡
ከውነተኞች ፡ ለመኾኑ ፡ በአላህ ፡
ስም ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ ምሎ ፡ መመ
ስከር ፡ ነው ።
7 አምስተኛይቱም ፡ ከውሸታሞች ፡
ቢኾን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የአላህ ፡
እርግማን ፡ ይኑርበት ፡ (ብሎ ፡
መመስከር) ፡ ነው ።
8 እርሱም ፡ ከውሸታሞች ፡ ነው ፡
ብላ ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ መመስከሮ
ችን ፡ በአላህ ፡ ስም ፡ መመስከ
ርዋ ፡ ከርስዋ ፡ ላይ ፡ ቅጣትን ፡
ይገፈትርላታል ።
9 አምስተኛይቱም ፡ እርሱ ፡ ከው
ነተኞች ፡ ቢኾን ፡ በርስዋ ፡ ላይ ፡
የአላህ ፡ ቁጣ ፡ ይኑርባት ፡ (ብላ ፡
መመስከርዋ) ፡ ነው ።
10 በናንተም ፡ ላይ ፡ የአላህ ፡ ችሮ
ታና ፡ እዝነቱ ፡ ባልነበረ ፡ አላ
ህም ፡ ጸጸትን ፡ ተቀባይ ፡ ጥበበኛ፡
ባልኾነ ፡ ኖሮ ፡ (ውሸታሙን ፡
ይገልጸው ፡ ነበር) ።
11 እነዚያ ፡ መጥፎን ፡ ውሸት ፡ (1)
ያመጡ ፡ ከናንተው ፡ የኾኑ ፡
ጭፍሮች ፡ ናቸው ፤ ለናንተ ፡
ክፉ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡
አታስቡት ፤ በውነቱ ፡ እርሱ ፡
ለናንተ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ነው ፤
ከነርሱ ፡ (ከጭፍሮቹ) ፡ ለያንዳ
ንዱ ፡ ሰው ፡ ከኀጢአት ፡ የሠራው ፡
ሥራ ፡ ዋጋ ፡ አለው ፤ ያም ፡ ከነሱ ፡
ትልቁን ፡ ኀጢአት ፡ የተሸከመው ፡
(1) ለርሱ ፡ ከባድ ፡ ቅጣት ፡
አለው ።
12 (ውሸቱን) ፡ በሰማችሁት ፡ ጊዜ ፡
ምእምናንና ፡ ምእምናት ፡ በነ
ፍሶቻቸው ፡ ለምን ፡ ደግን ፡ ነገር ፡
አልጠረጠሩም ? ለምንስ ፡ ይህ ፡
ግልጽ ፡ ውሸት ፡ ነው ፡ አላሉም?
13 በርሱ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ አራትን ፡
ምስክሮች ፡ አላመጡም ? ምስክ
ሮቹንም ፡ ካላመጡ ፡ እነዚያ ፡
አላህ ፡ ዘንድ ፡ ውሸታሞቹ ፡
እነሱ ፡ ናቸው ።
14 በቅርቢቱም ፡ በመጨረሻይቱም ፡
ዓለም ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ የአላህ ፡
ችሮታና ፡ እዝነቱ ፡ ባልነበረ ፡
ኖሮ ፡ በውስጡ ፡ በገባችሁበት ፡
ወሬ ፡ ምክንያት ፡ ታላቅ ፡ ቅጣት፡
በእርግጥ ፡ በደረሰባችሁ ፡ ነበር ።
15 በምላሶቻችሁ ፡ በምትቀባበሉት ፡
ጊዜ ፡ ለናንተም ፡ በርሱ ፡ ዕው
ቀት ፡ በሌላችሁ ፡ ነገር ፡ በአፎ
ቻችሁ ፡ በተናገራችሁና ፡ እርሱ ፡
አላህ ፡ ዘንድ ፡ ከባድ ፡ ኀጢአት ፡
ኾኖ ፡ ሳለ ፡ ቀላል ፡ አድርጋችሁ ፡
ባሰባችሁት ፡ ጊዜ ፡ (ከባድ ፡
ቅጣት ፡ በነካችሁ ፡ ነበር) ።
16 በሰማችሁትም ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡
ልንናገር ፡ ለኛ ፡ አይገባንም ፤
ጥራት ፡ ይገባህ ፤ ይህ ፡ ከባድ ፡
ቅጥፈት ፡ ነው ፤ አትሉም ፡ ነበ
ርን?

1 ዓኢሻን ፡ በመስደብ ።

1 ነገሩን ፡ ያጋነነው ።

17 ምእምናን ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡
ወደ ፡ ብጤው ፡ በፍጹም ፡ እንዳ
ትመለሱ ፡ አላህ ፡ ይገሥጻችኋል ።
18 ለናንተም ፡ አላህ ፡ አንቀጾችን ፡
ይገልጽላችኋል ፤ አላህም ፡ ዐዋቂ፡
ጥበበኛ ፡ ነው ።
19 እነዚያ ፡ በነዚያ ፡ ባመኑት ፡
ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ መጥፎ ፡ ወሬ ፡
እንድትስፋፋ ፡ የሚወዱ ፡ ለነሱ ፡
በቅርቢቱም ፡ በመጨረሻይቱም ፡
ዓለም ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ አላ
ቸው ፤ አላህም ፡ ያውቃል ፤ እና
ንተ ፡ ግን ፡ አታውቁም ።
20 በናንተም ፡ ላይ ፡ የአላህ ፡ ችሮ
ታውና ፡ እዝነቱ ፡ ባልነበረ ፡
አላህም ፡ ርኅሩኅና ፡ አዛኝ ፡ ባል
ኾነ ፡ ኖሮ ፡ (ቶሎ ፡ ባጠፋችሁ ፡
ነበር) ።
21 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! የሰ
ይጣንን ፡ እርምጃዎች ፡ አትከ
ተሉ ፤ የሰይጣንንም ፡ እርምጃ ፡
ዎች ፡ የሚከተል ፡ ሰው ፡ (ኀጢ
አትን ፡ ተሸከመ) ፤ እርሱ ፡ በመ
ጥፎና ፡ በሚጠላ ፡ ነገር ፡ ያዝዛ
ልና ፡ በናንተም ፡ ላይ ፡ የአላህ ፡
ችሮታና ፡ እዝነቱ ፡ ባልነበረ ፡
ኖሮ ፡ ከናንተ ፡ አንድም ፡ ፈጽሞ፡
ባልጠራ ፡ ነበር ፤ (1) ፡ ግን ፡ አ
ላህ ፡ የሚሻውን ፡ ሰው ፡ ያጠራል ፤
አላህም ፡ ሰሚ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
22 ከናንተም ፡ የችሮታና ፡ የክብረት፡
ባለ ፡ ቤቶች ፡ የኾኑት ፡ ለቅርብ ፡
ዘመዶችና ፡ ለድኾች ፡ በአላህም ፡
መንገድ ፡ ለተሰደዱ ፡ ሰዎች ፡
ላይሰጡ ፡ አይማሉ ፤ ይቅርታም ፡
ያድርጉ ፤ (ጥፋተኞቹን) ፡ ይለ
ፉም ፤ አላህ ፡ ለናንተ ፡ ሊምር ፡
አትወዱምን ? አላህም ፡ መሐሪ ፡
አዛኝ ፡ ነው ።
23 እነዚያ ፡ ጥብቆቹን ፡ ከዝሙት ፡
ዘንጊዎቹን ፡ ምእምናት ፡ የሚሰ
ድቡ ፤ በቅርቢቱም ፡ በመጨረ
ሻይቱም ፡ ዓለም ፡ ተረገሙ ፤
ለነርሱም ፡ ታላቅ ፡ ቅጣት ፡ አላ
ቸው ።
24 በነሱ ፡ ላይ ፡ ምላሶቻቸው ፡ እጆ
ቻቸውና ፡ እግሮቻቸውም ፡ ይሠ
ሩት ፡ በነበሩት ፡ ነገር ፡ በሚመ
ሰክሩባቸው ፡ ቀን ፡ (ከባድ ፡
ቅጣት ፡ አላቸው) ።
25 በዚያ ፡ ቀን ፡ አላህ ፡ እውነተኛ ፡
ዋጋቸውን ፡ ይመላላቸዋል ፤ አላ
ህም ፡ እርሱ ፡ መኖሩ ፡ የተረጋገጠ
(ሁሉን ፡ ነገር) ፡ ገላጭ ፡ መኾ
ኑን ፡ ያውቃሉ ።
26 መጥፎዎቹ ፡ ሴቶች ፡ ለመጥፎ
ዎች ፡ ወንዶች ፡ መጥፎዎቹ ፡ ወን
ዶችም ፡ ለመጥፎዎች ፡ ሴቶች ፡
የተገቡ ፡ ናቸው ፤ ጥሩዎቹ ፡ ሴቶ
ችም ፡ ለጥሩዎቹ ፡ ወንዶች ፡ ጥሩ
ዎቹ ፡ ወንዶችም ፡ ለጥሩዎቹ ፡
ሴቶች ፡ የሚገቡ ፡ ናቸው ፤ እነ
ዚያ ፡ (1) (መጥፎዎቹ) ፡ ከሚ
ሉት ፡ ነገር ፡ ንጹሕ ፡ የተደረጉ ፡
ናቸው ፤ ለነርሱ ፡ ምሕረትና ፡
መልካም ፡ ሲሳይ ፡ አላቸው ።
27 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! እስከ
ምታስፈቅዱና ፡ በባለ ፡ ቤቶቿ ፡
ላይ ፡ ሰላምታን ፡ እስከምታቀርቡ
ድረስ ፤ ከቤቶቻችሁ ፡ ሌላ ፡ የኾ
ኑን ፡ ቤቶች ፡ አትግቡ ፤ ይሃችሁ ፡
ለናንተ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ እና
ንተ ፡ ትገነዘቡ ፡ ዘንድ ፡ (በዚህ ፡
ታዘዛችሁ) ።

1 ንጹሕ ፡ ባልኾነ ፡ ነበር ።

1 እነ ፡ ዓኢሻህ ።



28 በውስጧም ፡ አንድንም ፡ ሰው ፡
ባታገኙ ፡ ለናንተ ፡ እስከሚፈቀ
ድላችሁ ፡ ድረስ ፡ አትግቧት ፤
ለናንተ ፡ ተመለሱ ፡ ብትባሉም ፡
ተመለሱ ፤ እርሱ ፡ ለናንተ ፡ የተ
ሻለ ፡ ነው ፤ አላህም ፡ የምትሠ
ሩትን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
29 መኖሪያ ፡ ያልኾኑን ፡ ቤቶች ፡
በውስጣቸው ፡ ለናንተ ፡ ጥቅም ፡
ያላችሁን ፡ (ሳታስፈቅዱ) ፡ ብት
ገቡ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡
የለባችሁም ፤ አላህም ፡ የምትገ
ልጹትንና ፡ የምትደብቁትን ፡
ሁሉ ፡ ያውቃል ።
30 ለምእምናን ፡ ንገራቸው ፡— ዓይ
ኖቻቸውን ፡ (ያልተፈቀደን ፡ ከማ
የት) ፡ ይከልክሉ ፤ ብልቶቻቸ
ውንም ፡ ይጠብቁ ፤ ይህ ፡ ለነሱ ፡
የተሻለ ፡ ነው ፤ አላህ ፡ በሚሠ
ሩት ፡ ሁሉ ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።
31 ለምእምናትም ፡ ንገራቸው ፡—
ዓይኖቻቸውን ፡ ይከልክሉ ፤ ብል
ቶቻቸውንም ፡ ይጠብቁ ፤ ጌጣቸ
ውንም ፡ ከርሷ ፡ ግልጽ ፡ ከኾነው ፡
በስተቀር ፡ አይግለጡ ፤ ጉፍታዎ
ቻቸውንም ፡ በአንገትጌዎቻቸው ፡
ላይ ፡ ያጣፉ ፤ (የውስጥ) ፡ ጌጣቸ
ውንም ፡ ለባሎቻቸው ፡ ወይም ፡
ለአባቶቻቸው ፡ ወይም ፡ ለባሎ
ቻቸው ፡ አባቶች ፡ ወይም ፡ ለወ
ንዶች ፡ ልጆቻቸው ፡ ወይም ፡
ለባሎቻቸው ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡
ወይም ፡ ለወንድሞቻቸው ፡ ወ
ይም ፡ ለወንድሞቻቸው ፡ ወን
ዶች ፡ ልጆች ፡ ወይም ፡ ለእኅቶ
ቻቸው ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡
ወይም ፡ ለሴቶቻቸው ፡ (1) ወይም
እጆቻቸው ፡ ለያዙት ፡ (ባሪያ) ፡
ወይም ፡ ከወንዶች ፡ ለሴት ፡
ጉዳይ ፡ የሌላቸው ፡ ለኾኑ ፡ ተከ
ታዮች ፡ ወይም ፡ ለነዚያ ፡ በሴ
ቶች ፡ ሐፍረተ ፡ ገላ ፡ ላይ ፡ ላላ
ወቁ ፡ (1) ሕጻኖች ፡ ካልኾነ ፡
በስተቀር ፡ አይግለጹ ፤ ከጌጣቸ
ውም ፡ የሚሸፍኑት ፡ ይታወቅ ፡
ዘንድ ፡ በእግሮቻቸው ፡ አይምቱ፤
ምእምናኖች ፡ ሆይ ! ትድኑ ፡
ዘንድ ፡ ሁላችሁም ፡ ወደ ፡ አላህ ፡
(በመመለስ) ፡ ተጸጸቱ ።
32 ከናንተም ፡ ትዳር ፡ የሌላቸውን ፡
አጋቡ ፤ ከወንዶች ፡ ባሮቻችሁና ፡
ከሴቶች ፡ ባሮቻችሁም ፡ ለጋብቻ፡
ብቁ ፡ የኾኑትን ፡ (አጋቡ) ፤ ድኾች ፡
ቢኾኑ ፤ አላህ ፡ ከችሮታው ፡ ያከ
ብራቸዋል ፤ አላህም ፡ ስጦታው ፡
ሰፊ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
33 እነዚያም ፡ የማግቢያን ፡ ጣጣ ፡
የማያገኙ ፡ አላህ ፡ ከችሮታው ፡
እስከሚያከብራቸው ፡ ድረስ ፡
ይጠበቁ ፤ እነዚያንም ፡ እጆቻ
ችሁ ፡ ከጨበጧቸው ፡ አገልጋ
ዮች ፡ (ገንዘብ ፡ ሰጥተው ፡ ነጻ ፡
ለመውጣት) ፡ መጻጻፍን ፡ የሚፈ
ልጉትን ፡ ከነሱ ፡ መልካምን ፡
ነገር ፡ ብታውቁ ፡ ተጻጻፉዋቸው ፤
ከአላህም ፡ ገንዘብ ፡ ከዚያ ፡
ከሰጣችሁ ፡ ስጧቸው ፤ ሴቶች ፡
ባሮቻችሁንም ፡ መጠበቅን ፡ ቢፈ
ልጉ ፡ የቅርቢቱን ፡ ሕይወት ፡
ጥቅም ፡ ለመፈለግ ፡ ብላችሁ ፡
በዝሙት ፡ ላይ ፡ አታስገድዱዋ
ቸው ፤ የሚያስገድዳቸውም ፡ ሰው
አላህ ፡ ከመገደዳቸው ፡ በኋላ ፡
(ለተገደዱት) ፡ መሐሪ ፡ አዛኝ ፡
ነው ።

1 ለሃይማኖት ፡ ወገኖቻቸው ።

1 አካለ ፡ መጠን ፡ ላልደረሱ ።

34 ወደናንተም ፡ አብራሪ ፡ የኾኑን ፡
አንቀጾች ፡ ከነዚያ ፡ ከበፊታ
ችሁ ፡ ካለፉትም ፡ (ምሳሌዎ
ች ፡ ዓይነት) ፡ ምሳሌን ፡ ለጥን
ቁቆቹ ፡ መገሰጫንም ፡ በእርግጥ፡
አወረድን ።
35 አላህ፡ የሰማያትና፡የምድር፡አብሪ፡
ነው፤ የብርሃኑ፡ ምሳሌ፥ በውስጧ፡
መብራት፡ እንዳለባት፡(ዝግ)፡ መስ
ኮት፥ መብራቱ፡ በብርጭቆ፡ ውስ
ጥ፡ የኾነ፥ ብርጭቆይቱ፡ ፍጹም፡
ሉላዊ፡ ኮከብ፡የምትመስል፥ ምሥ
ራቃዊም፡ ምዕራባዊም፡ካልኾነች፥
ከተባረከች፡ የወይራ፡ ዛፍ፥ ዘይቷ፡
እሳት፡ ባይነካውም፡ እንኳ፡ ሊያ
በራ፡የሚቀርብ፡ ከኾነች፥ (ዘይት)፡
የሚቃጠል፡ እንደ፡ ኾነ፡ (መብ
ራት)፡ ነው፤ (ይህ)፥ በብርሃን፡
ላይ፡ የኾነ፡ ብርሃን፡ ነው፤ አላህ፡
ወደ፡ ብርሃኑ፡ የሚሻውን፡ ሰው፡
ይመራል፤ አላህም፡ ለሰዎች፡
ምሳሌዎችን፡ ያቀርባል። አላህም፡
በነገሩ፡ ሁሉ፡ ዐዋቂ፡ ነው።
36 አላህ ፡ እንድትከበርና ፡ ስሙ ፡
በውስጧ ፡ እንዲወሳ ፡ ባዘዘው ፡
ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ (አወድሱት) ፤
በውስጧ ፡ በጧትና ፡ በማታ ፡
ለርሱ ፡ ያጠራሉ ፡
37 አላህን ፡ ከማውሳትና ፡ ሶላትን ፡
ከመስገድ ፡ ዘካንም ፡ ከመስጠት ፡
ንግድም ፡ ሽያጭም ፡ የማያታል
ላቸው ፡ ልቦችና ፡ ዓይኖች ፡
በርሱ ፡ የሚገላበጡበትን ፡ ቀን ፡
የሚፈሩ ፡ የኾኑ ፡ ሰዎች ፡ (ያጠ
ሩታል) ።
38 አላህ ፡ የሠሩትን ፡ ሥራ ፡ መልካ
ሙን ፡ ሊመነዳቸው ፡ ከችሮታ
ውም ፡ ሊጨምርላቸው ፡ (ያጠ
ሩታል) ፤ አላህም ፡ ለሚሻው ፡
ሰው ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ይሰጣል ።
39 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡ ሥራ
ዎቻቸው ፡ (መልካሞቹ) ፡ በበ
ረሃ ፡ ሜዳ ፡ እንዳለ ፡ ሲሪብዱ ፡
(1) የጠማው ፡ ሰው ፡ ውሃ ፡ ነው ፡
ብሎ ፡ እንደሚያስበው ፡ በመ
ጣውም ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡
ኾኖ ፡ እንደማያገኘው ፡ ነው ፤
(ከሓዲው) ፡ አላህንም ፡ እሥራው
ዘንድ ፡ ያገኘዋል ፡ ምርመራው
ንም ፡ (ቅጣቱን) ፡ ይመላለታል ፤
አላህም ፡ ምርመራው ፡ ፈጣን ፡
ነው ።
40 ወይም ፡ (መጥፎ ፡ ሥራዎቻቸው) ፡
ከበላዩ ፡ ማዕበል ፡ ከበላዩ ፡ ደመና
ያለበት ፡ ማዕበል ፡ በሚሸፈነው ፡
ጥልቅ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ እንዳሉ ፡
ጨለማዎች ፡ ነው ፤ (እነዚያ) ፡
ከፊላቸው ፡ ከከፊሉ ፡ በላይ ፡
ድርብርብ ፡ የኾኑ ፡ ጨለማዎች ፡
ናቸው ፤ (በዚህች ፡ የተሞከረ ፡
(ሰው) ፡ እጁን ፡ ባወጣ ፡ ጊዜ ፡
ሊያያት ፡ አይቀርብም ፤ አላህም ፡
ለርሱ ፡ ብርሃንን ፡ ያላደረገለት ፡
ሰው ፡ ለርሱ ፡ ምንም ፡ ብርሃን ፡
የለውም ።
41 አላህ ፡ በሰማያትና ፡ በምድር ፡
ያለ ፡ ሁሉ ፡ በራሪዎችም ፡ ክን
ፎቻቸውን ፡ (በአየር ፡ ላይ) ፡
ያንሳፈፉ ፡ ኾነው ፡ ለርሱ ፡ የሚ
ያጠሩ ፡ (የሚያወድሱ) ፡ መኾ
ናቸውን ፡ አላወቅህምን ? ሁሉም፡
ስግደቱንና ፡ ማጥራቱን ፡ በእር
ግጥ ፡ ዐወቀ ፤ አላህም ፡ የሚሠ
ሩትን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

1 አሻዋማ ፡ በረሃ ፡ ላይ ፡ በፀሐይ ፡ ሲያዩት ፡
የተንጋለለ ፡ ባሕር ፡ መስሎ ፡ የሚታይ ፡
ነው ።



42 የሰማያትና ፡ የምድርም ፡ ግዛት ፡
የአላህ ፡ ነው ፤ መመለሻም ፡
ወደ ፡ አላህ ፡ ነው ።
43 አላህ ፡ ደመናን ፡ የሚነዳ ፡ መኾ
ኑን ፡ አላየህምን ? ከዚያም ፡ ከፊ
ሉን ፡ ከከፊሉ ፡ ያገናኛል ፤ ከዚ
ያም ፡ የተደራረበ ፡ ያደርገዋል ፤
ዝናሙንም ፡ ከመካከሉ ፡ የሚ
ወጣ ፡ ኾኖ ፡ ታየዋለህ ፤ ከሰማ
ይም ፡ (ከደመና) ፡ በውስጧ ፡
ካሉት ፡ ጋራዎች ፡ በረዶን ፡
ያወርዳል ፤ በርሱም ፡ የሚሻውን ፡
ሰው ፡ (በጉዳት) ፡ ይነካል ፤ ከሚ
ሻውም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይመልሰ
ዋል ፤ የብልጭታው ፡ ብርሃን ፡
ዓይኖችን ፡ ሊወስድ ፡ ይቀርባል ።
44 አላህ ፡ ሌሊትንና ፡ ቀንን ፡ ያገላ
ብጣል ፤ በዚህም ፡ ለባለ ፡ ውስጥ፡
ዓይኖች ፡ በእርግጥ ፡ ማስረጃ ፡
አለበት ።
45 አላህም ፡ ተንቀሳቃሽን ፡ ሁሉ ፡
ከውሃ ፡ ፈጠረ ፤ ከነሱም ፡ በሆዱ ፡
ላይ ፡ የሚኼድ ፡ አለለ ፤ ከነሱም ፡
በሁለት ፡ እግሮች ፡ ላይ ፡ የሚ
ኼድ ፡ አለለ ፤ ከነሱም ፡ በአራት ፡
ላይ ፡ የሚኼድ ፡ አለለ ፤ አላህ ፡
የሚሻውን ፡ ሁሉ ፡ ይፈጥራል ፤
አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡
ነውና ።
46 አብራሪን ፡ አንቀጾች ፡ በእርግጥ ፡
አወረድን ፤ አላህም ፡ የሚሻውን ፡
ሰው ፡ ወደ ፡ ቀጥተኛ ፡ መንገድ ፡
ይመራዋል ።
47 በአላህና ፡ በመልክተኛውም ፡
አምነናል ፡ ታዘናልም ፡ ይላሉ ፤
ከዚያም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከነሱ ፡
ከፊሉ ፡ ይሸሻል ፤ እነዚያም ፡
ምእምናን ፡ አይደሉም ፤
48 ወደ ፡ አላህና ፡ ወደ ፡ መልክተ
ኛውም ፡ በመካከላቸው ፡ ሊፈ
ርድ ፡ በተጠሩ ፡ ጊዜ ፡ ከነሱ ፡
ከፊሉ ፡ ወዲያውኑ ፡ ይሸሻሉ ።
49 እውነቱም ፡ (ሐቁ) ፡ ለነሱ ፡ ቢ
ኾን ፡ ወደርሱ ፡ ታዛዦች ፡ ኾነው ፡
ይመጣሉ ።
50 በልቦቻቸው ፡ ውስጥ ፡ በሽታ ፡
አለን ? ወይስ ፡ (በነቢይነቱ) ፡
ተጠራጠሩን ? ወይስ ፡ አላህና ፡
መልክተኛው ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ የሚ
በድሉ ፡ መኾንን ፡ ይፈራሉን ?
ይልቁንም ፤ እነዚያ ፡ እነሱ ፡
በዳዮቹ ፡ ናቸው ።
51 የምእምናን ፡ ቃል ፡ የነበረው ፡
ወደ ፡ አላህና ፡ ወደ ፡ መልክተ
ኛው ፡ በመካከላቸው ፡ ሊፈርድ ፡
በተጠሩ ፡ ጊዜ ፡ ሰማን ፤ ታዘዝ
ንም ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ እነ
ዚህም ፡ እነሱ ፡ የፈለጉትን ፡
የሚያገኙ ፡ ናቸው ።
52 አላህንና ፡ መልክተኛውን ፡ የሚ
ታዘዝም ፡ ሰው ፤ አላህንም ፡ የሚ
ፈራና ፡ የሚጠነቀቀው ፡ ሰው ፤
እነዚያ ፡ እነሱ ፡ ፍላጎታቸውን ፡
የሚያገኙ ፡ ናቸው ።
53 (ለዘመቻ) ፡ ብታዛቸውም ፡ በእ
ርግጥ ፡ ሊወጡ ፡ የጠነከሩ ፡ መሓ
ሎቻቸውን ፡ በአላህ ፡ ስም ፡ ይም
ላሉ ፤ አትማሉ ፤ የታወቀች ፡
(የንፍቅና) ፡ መታዘዝ ፡ ናትና ፤
አላህ ፡ በምትሠሩት ፡ ነገር ፡ ሁሉ፡
ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፡ በላቸው ።
54 ፡—አላህን ፡ ተገዙ ፤ መልክተኛ
ውንም ፡ ታዘዙ ፤ ብትሸሹም ፡
(አትጐዱትም) ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡
ያለበት ፡ የተገደደውን ፡ ማድረስ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ በናንተም ፡ ላይ ፡
ያለባችሁ ፡ የተገደዳችሁት ፡ (መ

ታዘዝ) ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ብትታዘ
ዙትም ፡ ትምመራላችሁ ፤ በመ
ልክተኛውም ፡ ላይ ፡ ግልጽ ፡
ማድረስ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የለበትም፤
በላቸው ።

55 አላህ ፡ እነዚያን ፡ ከናንተ ፡ ያመ
ኑትንና ፡ መልካም ፡ ሥራዎችን ፡
የሠሩትን ፡ እነዚያን ፡ ከነሱ ፡
በፊት ፡ የነበሩትን ፡ እንደተካ ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ ሊተ
ካቸው ፡ ለነሱም ፡ ያንን ፡ የወደ
ደላቸውን ፡ ሃይማኖታቸውን ፡
ሊያደላድልላቸው ፤ ከፍርሃታቸ
ውም ፡ በኋላ ፡ ጸጥታን ፡ ሊለው
ጥላቸው ፡ ተስፋን ፡ ቃል ፡ ሰጥቷ
ቸዋል ፤ በኔ ፡ ምንንም ፡ የማያጋሩ፡
ኾነው ፡ ይገዙኛል ፤ ከዚያም ፡
በኋላ ፡ የካደ ፡ ሰው ፡ እነዚያ ፡
እነሱ ፡ አመጠኞች ፡ ናቸው ።

56 ሶላትንም ፡ አስተካክላችሁ ፡
ስገዱ ፤ ምጽዋትንም ፡ ስጡ ፤
መልክተኛውንም ፡ ታዘዙ ፤ ለና
ንተ ፡ ሊታዘንላችሁ ፡ ይከጀላ
ልና ።

57 እነዚያን ፡ የካዱትን ፡ በምድር ፡
ውስጥ ፡ የሚያቅቱ ፡ አድርገህ ፡
አታስብ ፤ መኖሪያቸውም ፡ እሳት
ናት ፤ በእርግጥም ፡ የከፋች ፡
መመለሻ ፡ ናት ።

58 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! እነ
ዚያ ፡ እጆቻችሁ ፡ የጨበጧቸው ፡
(ባሮች) ፡ እነዚያም ፡ ከናንተ ፡
ለአካለ ፡ መጠን ፡ ያልደረሱት ፡
ከጐህ ፡ ስግደት ፡ በፊት ፡ በቀት
ርም ፡ ልብሶቻችሁን ፡ በምታወ
ልቁ ፡ ጊዜ ፡ ከምሽት ፡ ስግደትም፡
በኋላ ፡ ሦስት ፡ ጊዜያት ፡ (ለመ
ግባት ፡ ሲፈልጉ) ፡ ያስፈቅዷችሁ፤
(እነዚህ) ፡ ለናንተ ፡ የኾኑ ፡ ሦስት
የሐፍረተ ፡ ገላ ፡ መገለጫ ፡
ጊዜያቶች ፡ ናቸውና ፤ ከነዚህ ፡
በኋላ ፡ በናንተም ፡ በነሱም ፡
ላይ ፡ (ያለፈቃድ ፡ በመግባት) ፡
ኀጢአት ፡ የለም ፤ በናንተ ፡ ላይ ፡
(ለማገልገል) ፡ ዙዋሪዎች ፡ ናቸ
ውና ፤ ከፊላችሁ ፡ በከፊሉ ፡ ላይ ፡
ዙዋሪ ፡ ነው ፤ እንደዚሁ ፡ አላህ ፡
ለናንተ ፡ ሕግጋትን ፡ ይገልጽላ
ችኋል ፤ አላህም ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ፡
ነው ።

59 ከናንተም ፡ ሕፃናቶቹ ፡ አቅመ ፡
አዳምን ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡
ከነሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ (ታላላ
ቆቹ) ፡ እንዳስፈቀዱ ፡ ያስፈቅዱ ፤
እንደዚሁ ፡ አላህ ፡ ለናንተ ፡ አን
ቀጾቹን ፡ ያብራራል ፤ አላህም ፡
ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።

60 ከሴቶችም ፡ እነዚያ ፡ ጋብቻን ፡
የማይፈልጉት ፡ ተቀማጮች፥
(ባልቴቶች) ፤ በጌጥ ፡ የተገለጹ ፡
ሳይኾኑ ፡ የላይ ፡ ልብሶቻቸውን ፡
ቢጥሉ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡
የለባቸውም ፤ ግን ፡ መጥጠበቃ
ቸው ፡ ለነርሱ ፡ የተሻለ ፡ ነው ፤
አላህም ፡ ሰሚ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

61 (ከሰዎች ፡ ጋር ፡ በመብላት) ፡
በዕውር ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ የለበ
ትም ፤ በአንካሳም ፡ ላይ ፡ ኀጢ
አት ፡ የለበትም ፤ በበሽተኛም ፡
ላይ ፡ ኀጢአት ፡ የለበትም ፤ በነ
ፍሶቻችሁም ፡ ላይ ፡ ከቤቶቻችሁ፡
ወይም ፡ ከአባቶቻችሁ ፡ ቤቶች ፡
ወይም ፡ ከናቶቻችሁ ፡ ቤቶች ፡
ወይም፡ከወንድሞቻችሁ፡ቤቶች፡
ወይም ፡ ከእኅቶቻችሁ ፡ ቤቶች ፡
ወይም ፡ ከአጐቶቻችሁ ፡ ቤቶች ፡
ወይም ፡ ከአክስቶቻችሁ ፡ ቤቶች፡
ወይም ፡ ከየሹሞቻችሁ ፡ ቤቶች ፡



ወይም ፡ ከየሹሜዎቻችሁ ፡ ቤቶች
(1) ወይም ፡ መክፈቻዎቹን ፡
ከያዛችሁት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡
ከወዳጃችሁ ፡ ቤት ፡ (ብትበሉ) ፡
ኀጢአት ፡ የለባችሁም ፤ ተሰብ
ስባችሁ ፡ ወይም ፡ ተለያይታ
ችሁ ፡ ብትበሉ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
ኀጢአት ፡ የለባችሁም ፤ ቤቶች
ንም ፡ በገባችሁ ፡ ጊዜ ፤ ከአላህ ፡
ዘንድ ፡ የኾነችን ፡ የተባረከች ፡
መልካም ፡ ሰላምታ ፡ በነፍሶቻ
ችሁ ፡ ላይ ፡ ሰላም ፡ በሉ ፤ እንደ
ዚሁ ፡ አላህ ፡ አንቀጾችን ፡ ለና
ንተ ፡ ያብራራል ፤ ልታውቁ ፡
ይከጀላልና ።

62 ምእምናን ፡ ማለት ፡ እነዚያ ፡
በአላህና ፡ በመልክተኛው ፡ ያመ
ኑት ፤ ከርሱ ፡ ጋር ፡ በሚሰበሰብ ፡
ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በኾኑ ፡ ጊዜ ፡ እስ
ከሚያስፈቅዱት ፡ ድረስ ፡ የማይ
ኼዱት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፤ እነዚያ ፡
የሚያስፈቅዱህ ፡ እነርሱ ፡ እነ
ዚያ ፡ በአላህና ፡ በመልክተኛው ፡
የሚያምኑት ፡ ናቸው ፤ ለግል ፡
ጉዳያቸውም ፡ ፈቃድ ፡ በጠየ
ቁህ ፡ ጊዜ ፡ ከነሱ ፡ ለሻኸው ፡
ሰው ፡ ፍቀድለት ፤ ለነሱም ፡
አላህን ፡ ምሕረትን ፡ ለምንላ
ቸው ፡ አላህ ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡
ነውና ።

63 በመካከላችሁ ፡ የመልክተኛውን፡
ጥሪ ፡ ከፊላችሁ ፡ ከፊሉን ፡ እንደ፡
መጥራት ፡ አታድርጉት ፤ ከናንተ፡
ውስጥ ፡ እነዚያን ፡ እየተከለሉ ፡
በመስለክለክ ፡ የሚወጡትን ፡
አላህ ፡ በእርግጥ ፡ ያውቃቸዋል ፤
እነዚያም ፡ ትእዛዙን ፡ የሚጥሱ ፡
መከራ ፡ እንዳትደርስባቸው ፡
ወይም ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡
እንዳያገኛቸው ፡ ይጠንቀቁ ።

64 ንቁ ፡ በሰማያትና ፡ በምድር ፡
ያለው ፡ ሁሉ ፡ የአላህ ፡ ብቻ ፡
ነው ፤ እናንተ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
ያላችሁበትን ፡ ኹኔታ ፡ በእርግጥ፡
ያውቃል ፤ ወደርሱ ፡ የሚመለ
ሱበትን ፡ ቀንም ፡ (ያውቃል) ፤
የሠሩትንም ፡ ሁሉ ፡ ይነግራቸ
ዋል ፤ አላህም ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።

---

1 የሹማ ፡ የእናት ፡ ወንድም ፤ የሹሜ ፡ የእናት
እኅት ።

25ኛ ፡ ሱረቱ፡ አልፉርቃን፤ (እውነትን፡ ከውሸት፡ የመለየት፡ ምዕ
ራፍ)፤ በመካ፡ የወረደች፡ ናት፤ አያትዋ፡ (አንቀጾችዋ)፡ 77 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በኾነው ፡
1 ያ ፡ ፉርቃንን ፡ (1) በባሪያው ፡
ላይ ፡ ለዓለማት ፡ አስፈራሪ ፡
ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ያወረደው ፡ (አም
ላክ) ፡ ክብርና ፡ ጥራት ፡ ተገባው ።
2 (እርሱ) ፡ ያ ፡ የሰማያትና ፡ የም
ድር ፡ ንግሥና ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡
የኾነ ፡ ልጅንም ፡ ያልያዘ ፡ በን
ግሥናውም ፡ ተጋሪ ፡ የሌለው ፡
ነገሩንም ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረና ፡
በትክክልም ፡ ያዘጋጀው ፡ ነው ።
3 (ከሓዲዎች) ፡ ከርሱም ፡ ሌላ ፡
ምንንም ፡ የማይፈጥሩን ፡ እነ
ሱም ፡ የሚፈጠሩን ፡ ለነፍሶቻ
ቸውም ፡ ጉዳትን ፡ ለመከላከል ፡
ጥቅምንም ፡ ለማምጣት ፡ የማ
ይችሉን ፡ ሞትንና ፡ ሕይወትንም ፡
መቀስቀስንም ፡ የማይችሉን ፡
አማልክት ፡ ያዙ ።
4 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ይህ ፡ (ቁር
አን ፡ ሙሐመድ) ፡ የቀጠፈው ፡
በርሱም ፡ ላይ ፡ ሌሎች ፡ ሕዝቦች ፡
ያገዙት ፡ የኾነ ፡ ውሸት ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አይደለም ፡ አሉ ፤ በእር
ግጥም ፡ በደልንና ፡ እብለትን ፡
ሠሩ ።
5 አሉም ፡— የመጀመሪያዎቹ ፡
ሰዎች ፡ ተረቶች ፡ ናት ፤ አስጣ
ፋት ፤ እርሷም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
ጧትና ፡ ማታ ፡ ትነበብለታለች ።
6 ያ ፡ በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ው
ስጥ ፡ ያለን ፡ ምስጢር ፡ የሚያ
ውቀው ፡ አወረደው ፤ እርሱ ፡ መ
ሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ፤ በላቸው ።
7 ለዚህም ፡ መልክተኛ ፡ ምግብን ፡
የሚበላ ፡ በገበያዎችም ፡ የሚ
ኼድ ፡ ሲኾን ፡ ምን ፡ (መልክተ
ኛነት) ፡ አለው ? ከርሱ ፡ ጋር ፡
አስፈራሪ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ወደ
ርሱ ፡ መልአክ ፡ (ገሃድ)፡ አይ
ወረድም ፡ ኖሯልን ? አሉ ።
8 ወይም ፡ ወደርሱ ፡ ድልብ ፡ አይ
ጣልለትምን ? ወይም ፡ ከርሷ ፡
የሚበላላት ፡ አትክልት ፡ ለርሱ ፡
አትኖረውምን ? (አሉ) ፤ በዳዮ
ቹም ፡ (ላመኑት) ፡ የተደገመበ
ትን ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡
አትከተሉም ፡ አሉ ።
9 ላንተ ፡ ምሳሌዎችን ፡ እንዴት ፡
እንዳደረጉልህና ፡ እንደ ፡ ተሳሳቱ
ተመልከት ፤ (ወደ ፡ እውነት ፡ ለመ
ድረስ) ፡ መንገድንም ፡ አይች
ሉም ።
10 ያ ፡ ቢሻ ፡ ከዚህ ፡ (ካሉት) ፡ የተ
ሻለን ፡ ከሥሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡
የሚፈሱባቸውን ፡ አትክልቶች ፡
ላንተ ፡ የሚያደርግልህ ፡ ሕንጻ ፡
ቤቶችንም ፡ ላንተ ፡ የሚያደርግ
ልህ ፡ ጌታ ፡ ችሮታው ፡ በዛ ።
11 ይልቁንም ፡ በትንሣኤ ፡ አስተ
ባበሉ ፤ በትንሣኤ ፡ ላስተባበ
ለም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ነዳጅን ፡
እሳት ፡ አዘጋጅተናል ።

1 ውነትን ፡ ከውሸት ፡ ለይውን ፡ መጽሐፍ ፤
የቁርአን ፡ ስሙ ፡ ነው ።



12 ከሩቅ ፡ ስፍራ ፡ ባየቻቸው ፡ ጊዜ ፡
ለርሷ ፡ የቁጭት ፡ መገንፈልንና ፡
ማናፋትን ፡ ይሰማሉ ።
13 እጅ ፡ ከፍንጅ ፡ የታሠሩ ፡ ኾነው
ም ፡ ከርሷ ፡ በጠባብ ፡ ስፍራ ፡
በተጣሉ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ ስፍራ ፡
ጥፋትን ፡ ይጠራሉ ፤ (ዋ ፡ ጥፋታ
ችን ፡ ይላሉ) ።
14 ፡— ዛሬ ፡ አንድን ፡ ጥፋት ፡ ብቻ ፡
አትጥሩ ፡ ብዙንም ፡ ጥፋት ፡
ጥሩ ፡ (ይባላሉ) ።
15 (እንዲህ) ፡ በላቸው ፡— ይህ ፡
የተሻለ ፡ ነውን ? ወይስ ፡ ጥንቁ
ቆቹ ፡ ተስፋ ፡ የተሰጧት ፡ የዘለ
ዓለሟ ፡ ገነት ? ለነርሱ ፡ ምንዳና ፡
መመለሻ ፡ ኾነች ።
16 ለነሱ ፡ በውስጧ ፡ ዘውታሪዎች ፡
ኾነው ፡ የሚፈልጉት ፡ ሁሉ ፡
አላቸው ፤ (ይህም) ፡ ተስፋ ፡
ከጌታህ ፡ ተለማኝ ፡ ተስፋ ፡ ነው ።
17 እነርሱንና ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የሚ
ገገዟቸውንም ፡ የሚሰበስብባቸው
ንና ፡ እናንተ ፡ እነዚህን ፡ ባሮ
ቼን ፡ አሳሳታችሁን ? ወይስ ፡
እነሱው ፡ መንገድን ፡ ሳቱ ?
የሚልበትን ፡ ቀን ፡ (አስታውስ)።
18 ጥራት ፡ ይገባህ ፤ ካንተ ፡ ሌላ ፡
ረዳቶችን ፡ ልንይዝ ፡ ለኛ ፡ ተገ
ቢያችን ፡ አልነበረም ፤ ግን ፡ እነ
ሱንም ፡ አባቶቻቸውንም ፡ መገን
ዘብን ፡ እስከተዉ ፡ ድረስ ፡
አጣቀምካቸው ፤ ጠፊ ፡ ሕዝቦ
ችም ፡ ኾኑ ፤ ይላሉ ።
19 በምትሉትም ፡ (አማልክቶቻችሁ)
አስዋሹዋችሁ ፤ ቅጣቱን ፡ መገ
ፍተርንም ፡ መርዳትንም ፡ አት
ችሉም ፤ ከናንተም ፡ የሚበድለ
ውን ፡ ታላቅን ፡ ቅጣት ፡ እናቀ
ምሰዋለን ፤ (ይባላሉ) ።
20 ካንተ ፡ በፊትም ፡ ከመልክተ
ኞች ፡ እነሱ ፡ በእርግጥ ፡ ምግ
ብን ፡ የሚበሉ ፡ በገበያዎችም ፡
የሚኼዱ ፡ ኾነው ፡ በስተቀር ፡
አልላክንም ፤ ከፊላችሁንም ፡
ለከፊሉ ፡ ፈተና ፡ አድርገናል ፤
ትታገሣላችሁን ? ጌታህም ፡ ተመ
ልካች ፡ ነው ።

★ ★ ★

21 እነዚያም ፡ መገናኘታችንን ፡ የማ
ይፈሩት ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡
መላእክት ፡ አልወረደም ፤ ወይም ፡
ጌታችንን ፡ ለምን ፡ አናይም ?
አሉ ፤ በነፍሶቻቸው ፡ ውስጥ ፡ በእ
ርግጥ ፡ ኮሩ ፤ ታላቅንም ፡ አመጥ ፡
አመጡ ።
22 መላእክትን ፡ በሚያዩበት ፡ ቀን ፡
በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ለአመጠኞች ፡ ምስ
ራች ፡ የላቸውም ፤ የተከለከለ ፡
ክልክልም ፡ አድርገን ፡ ይላሉ ።
23 ከሥራም ፡ ወደ ፡ ሠሩት ፡ እናስ
ባለን ፤ የተበተነ ፡ ትቢያም ፡
እናደርገዋለን ።
24 የገነት ፡ ሰዎች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡
በመርጊያ ፡ የተሻሉ ፡ በማረፊ
ያም ፡ በጣም ፡ ያማሩ ፡ ናቸው ።
25 ሰማይም ፡ በደመና ፡ የምትቀደ
ድበትንና ፡ መላእክትም ፡ መወ
ረድን ፡ የሚወርዱበትን ፡ ቀን ፡
(አስታውስ) ።
26 እውነተኛው ፡ ንግሥና ፡ በዚያ ፡
ቀን ፡ ለአልረሕማን ፡ (1) ብቻ ፡
ነው ፤ በከሓዲዎችም ፡ ላይ ፡
አስቸጋሪ ፡ ቀን ፡ ነው ።
27 በዳይም ፡— ከመልክተኛው ፡
ጋር ፡ ቀጥተኛን ፡ መንገድ ፡ ይዤ፡

1 ለአላህ ፡ የተለየ ፡ ስሙ ፡ ነው ፤ እጅግ ፡
በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ ማለት ፡ ነው ።

በኾነ ፡ ዋ ፡ ምኞቴ! እያለ ፡ (በጸ
ጸት) ፡ ሁለት ፡ እጆቹን ፡ የሚነ
ክስበትን ፡ ቀን ፡ (አስታውስ) ።
28 ዋ ፡ ጥፋቴ ! እገሌን ፡ ወዳጅ ፡
ባልያዝኩ ፡ ኖሮ ፡ እመኛለሁ ፤
29 (የእምነት ፡ ቃልን) ፡ ከመጣልኝ ፡
በኋላ ፡ ከማስታወስ ፡ በእርግጥ ፡
አሳሳተኝ ፤ (ይላል) ፤ ሰይጣንም ፡
ለሰው ፡ አጋላጭ ፡ ነው ።
30 መልክተኛውም ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ!
ሕዝቦቼ ፡ ይህንን ፡ ቁርአን ፡
የተተወ ፡ ነገር ፡ አድርገው ፡
ያዙት ፡ አለ ።
31 እንደዚሁም ፡ ለነቢዩ ፡ ሁሉ ፡
ከአመጠኞች ፡ የኾነ ፡ ጠላትን ፡
አድርገናል ፤ መሪና ፡ ረዳትም ፡
በጌታህ ፡ በቃ ።
32 እነዚያ ፡ የካዱትም ፡— ቁርአን ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ በጠቅላላ ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ አልተወረደም ?
አሉ ፤ እንደዚሁ ፡ በርሱ ፡ ልብ
ህን ፡ ልናረጋ ፡ (ከፋፍለን ፡ አወ
ረድነው) ፤ ቀስ ፡ በቀስ ፡ መለ
ያየትንም ፡ ለየነው ።
33 በጥያቄም ፡ አይመጡብህም ፡
እውነተኛውን ፡ (መልስ) ፡ መል
ካምን ፡ ፍችም ፡ የምናመጣልህ ፡
ብንኾን ፡ እንጅ ።
34 እነዚያ ፡ በፊቶቻቸው ፡ ላይ ፡
(እየተጎተቱ) ፡ ወደ ፡ ገሀነም ፡
የሚሰበሰቡ ፡ ናቸው ፤ እነዚያ ፡
ስፍራቸው ፡ የከፋ ፡ መንገዳቸ
ውም ፡ የጠመመ ፡ ናቸው ።
35 በእርግጥም ፡ ለሙሳ ፡ መጽሐ
ፍን ፡ ሰጠነው ፤ ከርሱም ፡ ጋር ፡
ወንድሙን ፡ ሃሩንን ፡ ረዳት ፡
አደረግንለት ።
36 ወደነዚያም ፡ በታምራቶቻችን ፡
ወደ ፡ አስተባበሉት ፡ ሕዝቦች ፡
ኺዱ ፡ አልናቸው ፤ (አስዋሿቸ
ውም) ፡ ማጥፋትንም ፡ አጠፋና
ቸው ።
37 የኑሕን ፡ ሰዎችም ፡ መልክተኞ
ችን ፡ ባስተባበሉ ፡ ጊዜ ፡ አሰጠ
ምናቸው ፤ ለሰዎችም ፡ መገሰጫ ፡
አደረግናቸው ፤ ለበደለኞችም ፡ አሳ
ማሚን ፡ ቅጣት ፡ አዘጋጅተናል ።
38 ዓድንም ፡ ሠሙድንም ፡ የረሰን ፡
ሰዎችም ፡ በዚህ ፡ መካከል ፡
የነበሩትንም ፡ ብዙን ፡ የክፍለ ፡
ዘመናት ፡ ሕዝቦች ፡ (አጠፋን) ።
39 ሁሉንም ፡ (ገሠጽን) ፡ ለነሱ ፡
ምሳሌዎችን ፡ ገለጽን ፤ ሁሉንም ፡
ማጥፋትን ፡ አጠፋናቸውም ።
40 በዚያችም ፡ ክፉ ፡ ዝናምን ፡
(1) በተዘነመችው ፡ ከተማ ፡
ላይ ፡ (የመካ ፡ ከሐዲዎች) ፡
በእርግጥ ፡ መጥተዋል ፤ የሚያ
ዩዋት ፡ አልነበሩምን ? በውነቱ ፡
መቀስቀስን ፡ የማይፈሩ ፡ ነበሩ ።
41 ባዩህም ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ አላህ ፡ መል
እክተኛ ፡ አድርጐ ፡ የላከው ፡
ይህ ፡ ነውን ? እያሉ ፡ መሳለቂያ ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ አያደርጉህም ።
42 እነሆ ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ መታገሣ
ችን ፡ ባልነበረ ፡ ኖሮ ፡ ከአማል
ክቶቻችን ፡ ሊያሳስተን ፡ ቀርቦ ፡
ነበር ፡ (ሲሉም ፡ ይሳለቃሉ) ፤
ወደፊትም ፡ ቅጣቱን ፡ በሚያዩ ፡
ጊዜ ፡ መንገድን ፡ በጣም ፡ ተሳ
ሳቹ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በእር
ግጥ ፡ ያውቃሉ ።
43 ፍላጐቱን ፡ አምላኩ ፡ አድርጐ ፡
የያዘውን ፡ ሰው ፡ አየህን ? አንተ ፡

1 የጋለ ፡ ሸክላ ፡ ደንጊያን ።



በርሱ ፡ ላይ ፡ ጠባቂ ፡ ትኾናለ
ህን ?
44 ይልቁንም ፡ አብዛኞዎቻቸው ፡
የሚሰሙ ፡ ወይም ፡ የሚያውቁ ፡
መኾናቸውን ፡ ታስባለህን ? እነ
ርሱ ፡ እንደ ፡ እንስሳዎች ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አይደሉም ፡ ከቶውንም ፡
እነሱ ፡ ይልቅ ፡ መንገድን ፡ የተ
ሳሳቱ ፡ ናቸው ።
45 ወደ ፡ ጌታህ ፡ (ሥራ) ፡ ጥላን ፡
እንዴት ፡ እንደ ፡ ዘረጋ ፡ አላየ
ህምን ? በሻም ፡ ኖሮ ፡ የረጋ ፡
ባደረገው ፡ ነበር ፤ ከዚያም ፡
ፀሐይን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡
አደረግን ።
46 ከዚያም ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ወደኛ ፡
ሰበሰብነው ፤
47 እርሱም ፡ ያ ፡ ለናንተ ፡ ሌሊትን ፡
ልብስ ፡ እንቅልፍንም ፡ ማረፊያ ፡
ያደረገ ፤ ቀንንም ፡ መበተኛ ፡
ያደረገላችሁ ፡ ነው ።
48 እርሱም ፡ ያ ፡ ነፋሶችን ፡ አብሳ
ሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ ከዝናሙ ፡ በስተ
ፊት ፡ የላከ ፡ ነው ፤ ከሰማይም ፡
አጥሪ ፡ ውሃን ፡ አወረድን ፤
49 በርሱ ፡ የሞተችን ፡ አገር ፡ ሕያው
ልናደርግበት ፡ ከፈጠርነውም ፡
ፍጡር ፡ እንስሳዎችንና ፡ ብዙ ፡
ሰዎችንም ፡ ልናጠጣው ፡ (አወ
ረድነው) ።
50 (ጸጋችንን) ፡ ይገነዘቡም ፡ ዘንድ ፡
በመካከላቸው ፡ ከፋፈልነው ፤
ግን ፡ አብዛኞዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ክሕ
ደትን ፡ እንጂ ፡ እንቢ ፡ አሉ ።
51 በሻንም ፡ ኖሮ ፡ በየከተማይቱ ፡
አስፈራሪን ፡ በላክን ፡ ነበር ።
52 ከሓዲዎችንም ፡ አትታዘዛቸው ፤
በርሱም ፡ (በቁርአን) ፡ ታላቅን ፡
ትግል ፡ ታገላቸው ።
53 እርሱም ፡ ያ ፡ ሁለቱን ፡ ባሕ
ሮች ፡ አጐራብቶ ፡ የለቀቀ ፡ ነው ፤
ይህ ፡ ጥምን ፡ የሚቆርጥ ፡ ጣፋጭ
ነው ፤ ይህም ፡ የሚመረግግ ፡
ጨው ፡ ነው ፤ በመካከላቸውም ፡
(ከመቀላቀል) ፡ መለያንና ፡ የተ
ከለለን ፡ ክልል ፡ ያደረገ ፡ ነው ።
54 እርሱም ፡ ያ ፡ ከውሃ ፡ ሰውን ፡
የፈጠረ ፡ የዝምድናና ፡ የአማ
ችም ፡ ባለቤት ፡ ያደረገው ፡
ነው ፤ ጌታህም ፡ ቻይ ፡ ነው ።
55 ከአላህም ፡ ሌላ ፡ የማይጠቅማ
ቸውንና ፡ የማይጎዳቸውን ፡ ይግ
ገዛሉ ፤ ከሓዲም ፡ በጌታው ፡
ላይ ፡ (በማመጥ ፡ ለሰይጣን) ፡
ረዳት ፡ ነው ።
56 አብሳሪና ፡ አስፈራሪም ፡ አድር
ገን ፡ እንጂ ፡ አልላክንህም ።
57 በርሱ ፡ ላይ ፡ ዋጋን ፡ በፍጹም ፡
አልጠይቃችሁም ፤ ግን ፡ ወደ ፡
ጌታው ፡ (መልካም) ፡ መንገድን ፡
ለመያዝ ፡ የሻ ፡ ሰው ፡ (ይሥራ) ፤
በላቸው ።
58 በዚያም ፡ በማይሞተው ፡ ሕያው ፡
አምላክ ፡ ላይ ፡ ተመካ ፤ ከማመ
ስገንም ፡ ጋር ፡ አጥራው ፤ በባ
ሮቹ ፡ ኀጢአቶችም ፡ ውስጠ ፡
ዐዋቂ ፡ በርሱ ፡ በቃ ።
59 ያ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ በመካ
ከላቸው ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ በስድ
ስት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ የፈጠረ ፤
ከዚያም ፡ በዐርሹ ፡ ላይ ፡ (ስል
ጣኑ) ፡ የተደላደለ ፡ አልረሕማን ፡
ነው ፤ ከርሱም ፡ ዐዋቂን ፡ ጠይቅ።
60 ለነርሱም ፡ ለአልረሕማን ፡ ስገዱ፡
በተባሉ ፡ ጊዜ ፡ አልረሕማን ፡
ማነው ? ለምታዘን(ና ፡ ለማናው
ቀው) ፡ እንሰግዳለን ? ይላሉ ፤

(ይህ) ፡ መራቅንም ፡ ጨመራቸው ።

61 ያ ፡ በሰማይ ፡ ቡሩጆችን ፡ (1) ያደረገና ፡ በርሷም ፡ አንጸባራቂን ፡ (ፀሐይ) ፡ አብሪ ፡ ጨረቃንም ፡ ያደረገ ፡ ጌታ ፡ ክብሩ ፡ በጣም ፡ ላቀ ።

62 እርሱም ፡ ያ ፡ (ያመለጠውን ፡ ሥራ) ፡ ማስታወስን ፡ ለሚፈልግ ፡ ወይም ፡ ማመስገንን ፡ ለሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ሌሊትንና ፡ ቀንን ፡ ተተካኪ ፡ ያደረገ ፡ ነው ።

63 የአልረሕማንም ፡ ባሮች ፡ እነዚያ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በዝግታ ፡ የሚኼዱት ፡ ባለጌዎችም ፡(በክፉ) ባነጋገሩዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ሰላም ፡ የሚሉት ፡ ናቸው ።

64 እነዚያም ፡ ለጌታቸው ፡ በግንባራቸው ፡ ተደፊዎችና ፡ ቋሚዎች ፡ ኾነው ፡ የሚያድሩት ፡ ናቸው ።

65 እነዚያም ፡— ጌታችን ፡ ሆይ ! የገሀነምን ፡ ቅጣት ፡ ከኛ ፡ ላይ ፡ መልስልን ፤ ቅጣቷ ፡ የማያለቅ ፡ ነውና ፤ የሚሉት ፡ ናቸው ።

66 እርሷ ፡ መርጊያና ፡ መቀመጫ ፡ በመኾን ፡ ከፋች ! (ይላሉ) ።

67 እነዚያም ፡ በለገሱ ፡ ጊዜ ፡ የማያባክኑት ፡ የማይቆጥቡትም ፡ ናቸው ፤ በዚህም ፡ መካከል ፡ (ልግስናቸው) ፡ ትክክለኛ ፡ የኾነ ፡ ነው ።

68 እነዚያም ፡ ከአላህ ፡ ጋር ፡ ሌላን ፡ አምላክ ፡ የማይግገዙት ፤ ያችንም ፡ አላህ ፡ እርም ፡ ያደረጋትን ፡ ነፍስ ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ የማይገድሉት ፤ የማያመነዝሩትም ፡ ናቸው ፤ ይህንንም ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ ቅጣትን ፡ ያገኛል ።

69 በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ቅጣቱ ፡ ለርሱ ፡ ይደራረብል ፤ በርሱም ፡ ውስጥ ፡ የተዋረደ ፡ ኾኖ ፡ ይኖራል ።

70 ተጸጽቶ ፡ የተመለሰና ፡ ያመነ ፡ መልካምንም ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ሲቀር ፤ እነዚያም ፡ አላህ ፡ መጥፎ ፡ ሥራዎቻቸውን ፡ በመልካም ፡ ሥራዎች ፡ ይለውጣል ፤ አላህም ፡ እጅግ ፡ መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።

71 ተጸጽቶ ፡ የተመለሰም ፡ ሰው ፡ መልካምንም ፡ የሠራ ፡ እርሱ ፡ የተወደደን ፡ መመለስ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ይመለሳል ።

72 እነዚያም ፡ እብለትን ፡ የማይመሰክሩ ፤ በውድቅ ፡ ቃልም ፡ (ተናጋሪ ፡ አጠገብ) ፡ ባለፉ ፡ ጊዜ ፡ የከበሩ ፡ ኾነው ፡ የሚያልፉት ፡ ናቸው ።

73 እነዚያም ፡ በጌታቸው ፡ አንቀጾች ፡ በተገሠጹ ፡ ጊዜ ፡ (የተረዱ ፡ ተቀባዮች ፡ ኾነው ፡ እንጂ) ፡ ደንቆሮዎችና ፡ ዕውሮች ፡ ኾነው ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ የማይደፉት ፡ ናቸው ።

74 እነዚያም ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ! ከሚስቶቻችንና ፡ ከዘሮቻችን ፡ ለዓይኖች ፡ መርጊያን ፡ ለኛ ፡ ስጠን ፤ አላህን ፡ ለሚፈሩትም ፡ መሪ ፡ አድርገን ፤ የሚሉት ፡ ናቸው ።

75 እነዚያ ፡ በመታገሣቸው ፡ የገነትን ፡ ሰገነቶች ፡ ይመነዳሉ ፤ በርሷም ፡ ውስጥ ፡ ውዳሴንና ፡ ሰላምታን ፡ ይስሰጣሉ ።

76 በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ኾነው ፡ (ይስሰጣሉ) ፤ መርጊያና ፡ መኖሪያይቱ ፡ አማረች ።

77 ፡-ጸሎታችሁ ፡ ባልነበረ ፡ ኖሮ ፡ ጌታዬ ፡ እናንተን ፡ ከምንም ፡ አይቆጥራችሁም ፡ ነበር ፤ በእርግጥም ፡ አስተባበላችሁ ፤ ወደ ፊትም ፡ (ቅጣቱ) ፡ ያዣችሁ ፡ ይኾናል ፡ በላቸው ።

1 12 ፡ ቡሩጆች ፤ የፈለክ ፡ ክፍሎችናቸው ፤ ሀሐይ ፡ በወር ፡ የምታቋርጠው ፡ አንድ ፡ ቡርጅ ፡ ይባላል ።



## ምዕራፍ ፡ 26 ፡ አል-ሹዐራ ። ክፍል ፡ 19 ።

26ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አልሹዐራ ፡ (የባለ ፡ ቅኔዎች ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 227 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 ጠ. ሰ. መ. (ጧ ሲን ፡ ሚም) ። (1)

2 ይህች ፡ ግልጽ ፡ ከኾነው ፡ መጽሐፍ ፡ አንቀጾች ፡ ናት ።

3 አማኞች ፡ ባለ ፡ መኾናቸው ፤ (በቁጭት) ፡ ነፍስህን ፡ ገዳይ ፡ መኾን ፡ ይፈራልሃል ፤

4 ብንሻ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ከሰማይ ፡ ታምርን ፡ እናውርድና ፡ አንገቶቻቸው ፡ (መሪዎቻቸው) ፡ ለርሷ ፡ ተዋራጆች ፡ ይኾናሉ ።

5 ከአልረሕማንም ፡ ዘንድ ፡ አዲስ ፡ የተወረደ ፡ ቁርአን ፡ አይመጣላቸውም ፤ ከርሱ ፡ የሚሸሹ ፡ ቢኾኑ ፡ እንጂ ።

6 በእርግጥም ፡ አስተባበሉ ፤ የዚያም ፡ በርሱ ፡ ይሳለቁበት ፡ የነበሩት ፡ ወሬዎች ፡ (ፍጻሜ) ፡ ይመጣባቸዋል ።

7 ወደ ፡ ምድርም ፡ በውስጧ ፡ ከመልካም ፡ (በቃይ) ፡ ጐሳ ፡ ሁሉ ፡ ብዙን ፡ እንዳበቀልን ፡ አላዩምን ።

8 በዚህ ፡ አስደናቂ ፡ ምልክት ፡ አለበት ፤ አብዛኞቻቸውም ፡ አማኞች ፡ አልነበሩም ።

9 ጌታህም ፡ እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ አሸናፊ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።

10 ጌታህም ፡ ሙሳን ፡ ወደ ፡ በደለኞቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ኺድ ፡ በማለት ፡ በጠራው ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ።

11 ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ሕዝቦች ፡ (ኺድ) ፡ አላህን ፡ አይፈሩምን ? (አለው) ።

12 (ሙሳም) ፡ አለ ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ! እኔ ፡ ሊያስተባብሉኝ ፡ እፈራለሁ ።

13 ልቤም ፡ ይጠብባል ፤ ምላሴም ፡ አይፈታም ፤ ስለዚህ ፡ ወደ ፡ ሃሩን ፡ ላክ ።

14 ለነርሱም ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ (የደም) ፡ ወንጀል ፡ አለ ፤ ስለዚህ ፡ እንዳይገድሉኝ ፡ እፈራለሁ ።

15 (አላህ) ፡ አለ ፡—ተው ! (አይነኩህም) ፤ በታምራቶቻችንም ፡ ኺዱ ፤ እኛ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ሰሚዎች ፡ ነንና ።

1 በችሮታዬ ፡ በልቅናዬ ፡ በንጉሥነቴ ፡ እምላለሁ ።

16 ወደ ፡ ፈርዖንም ፡ ኺዱ ፤ በሉ
ትም ፡—እኛ ፡ የዓለማት ፡ ጌታ ፡
መልክተኞች ፡ ነን ፤
17 የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከኛ ፡
ጋር ፡ ልቀቅ ።
18 (ፈርዖንም) ፡ አለ ፡—ልጅ ፡ ኾነህ፡
በኛ ፡ ውስጥ ፡ አላሳደግንህምን ?
በኛ ፡ ውስጥም ፡ ከዕድሜህ ፡
ብዙ ፡ ዓመታትን ፡ አልተቀመ
ጥክምን ?
19 ያችንም ፡ የሠራሃትን ፡ ሥራህን ፡
አልሠራህምን ? አንተም ፡ ከው
ለታ ፡ ቢሶቹ ፡ ነህ ፤ (አለ) ።
20 (ሙሳም) ፡ አለ ፡- ያን ፡ ጊዜ ፡
እኔም ፡ ከተሳሳቱት ፡ ኾኜ ፡ ሠራ
ኋት ።
21 በፈራኋችሁም ፡ ጊዜ ፡ ከናንተ ፡
ሸሸሁ ፤ ጌታየም ፡ ለኔ ፡ ጥበብን ፡
ሰጠኝ ፤ ከመልክተኞቹም ፡ አደ
ረገኝ ።
22 ይህችም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡
ባሪያ ፡ በማድረግህ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡
የምትመጻደቅባት ፡ ጸጋ ፡ ናት ።
23 ፈርዖን ፡ አለ ፡-(ላከኝ ፡ የምት
ለው) ፡ የዓለማትም ፡ ጌታ ፡ ምን
ድነው ?
24 (ሙሳ)፡ የሰማያትና ፡ የምድር ፡
በመካከላቸውም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡
ጌታ ፡ ነው ፤ የምታረጋግጡ ፡
ብትኾኑ ፡ (ነገሩ ፡ ይህ ፡ ነው) ፤
አለው ።
25 (ፈርዖንም) ፡ በዙሪያው ፡ ላሉት ፡
ሰዎች ፡— አትሰሙምን ? አለ ።
26 (ሙሳ) ፡— ጌታችሁና ፡ የመጀመ
ሪያዎቹ ፡ አባቶቻችሁም ፡ ጌታ ፡
ነው ፡ አለው ።

27 (ፈርዖን)፡- ያ፡ ወደናንተ፡ የተላ
ከው፡ መልክተኛችሁ፥ በእርግጥ፡
ዕብድ፡ ነው፤ አለ።
28 (ሙሳ)፡- የምሥራቅና፡ የምዕራብ፡
በመካከላቸውም፡ ያለው፡ ነገር፡
ሁሉ፡ ጌታ፡ ነው፥ ታውቁ፡ እንደ፡
ኾናችሁ፥ (እመኑበት)፡ አለው።
29 (ፈርዖን)፡- ከኔ፡ ሌላ፡ አምላክን፡
ብትይዝ፥ በውነቱ፡ ከእስረኞቹ፡
አደርግሃለሁ፡ አለ።
30 (ሙሳ)፡- በግልጽ፡ አስረጅ፡ ብመ
ጣህም፡ እንኳ? አለው።
31 እንግዲያውስ፡ ከውነተኞች፡ እንደ፡
ኾንክ፡ (አስረጅን)፡ አምጣው፡ አለ።
32 በትሩንም፡ ጣለ፤ እርሷም፡ ወዲያ
ውኑ፡ ግልጽ፡ እባብ፡ ኾነች።
33 እጁንም፡ አወጣ፤ ወዲያውም
እርሷ፡ ለተመልካቾች፡ (የምታ
በራ)፡ ነጭ፡ ኾነች።
34 (ፈርዖን)፡ በዙሪያው፡ ላሉት፡ መማ
ክርት፥ ይህ፡ በእርግጥ፡ ዐዋቂ፡
ድግምተኛ፡ ነው፤ አለ።
35 ከምድራችሁ፡ በድግምቱ፡ ሊያወ
ጣችሁ፡ ይፈልጋልና፡ ምንን፡
ታዛላችሁ? (አላቸው)።
36 አሉት፡- እርሱን፡ ወንድሙንም፥
አቆይና፡ በየከተሞቹ፥ ሰብሳቢዎ
ችን፡ ላክ።
37 በጣም፡ ዐዋቂ፡ ድግምተኞችን፡
ሁሉ፡ ያመጡልሃልና።
38 ድግምተኞቹም፥ በታወቀ፡ ቀን፡
ቀጠሮ፡ ተሰበሰቡ።
39 ለሰዎቹም፡- እናንተ፡ ተሰብስባች
ኋልን? ተባለ።
40 ድግምተኞቹን፡ እነሱ፡ አሸናፊ
ዎች፡ ቢኾኑ፥ እንከተል፡ ዘንድ፡
(ተባለ)።



41 ድግምተኞቹም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡
ለፈርዖን ፡— እኛ ፡ አሸናፊዎች ፡
ብንኾን ፡ ለኛ ፡ በርግጥ ፡ ዋጋ ፡
አለን ? አሉት ።
42 አዎን ፤ እናንተም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡
ከባለሟሎቹ ፡ ትኾናላችሁ ፡ አላ
ቸው ።
43 ሙሳ ፡— ለነርሱ ፡ እናንተ ፡ የም
ትጥሉትን ፡ ጣሉ ፡ አላቸው ።
44 ገመዶቻቸውንና ፡ በትሮቻቸው
ንም ፡ ጣሉ ፤ በፈርዖንም ፡ ክብር ፡
ይኹንብን ፤ እኛ ፡ በእርግጥ ፡
አሸናፊዎቹ ፡ እኛ ፡ ነን ፤ አሉ ።
45 ሙሳም ፡ በትሩን ፡ ጣለ ፤ ወዲ
ያውም ፡ እርሷ ፡ የሚያስመስ
ሉትን ፡ ሁሉ ፡ ትውጣለች ።
46 ድግምተኞቹም ፡ ሰጋጆች ፡ ኾነው ፡
ወደቁ ።
47 (እነሱም) ፡ አሉ ፡- በዓለማት ፡
ጌታ ፡ አመንን ፤
48 በሙሳና ፡ በሃሩን ፡ ጌታ ።
49 ፈርዖንም) ፡ ለናንተ ፡ ሳልፈቅድ
ላችሁ ፡ በፊት ፡ ለርሱ ፡ አመና
ችሁን ? እርሱ ፡ ያ ፡ ድግምትን ፡
ያስተማራችሁ ፡ ታላቃችሁ ፡
ነው ፤ ወደፊትም ፡ (የሚያገኛ
ችሁን) ፡ በእርግጥ ፡ ታውቃላ
ችሁ ፤ እጆቻችሁንና ፡ እግሮቻ
ችሁን ፡ (ቀኝና ፡ ግራን) ፡ በማ
ናጋት ፡ እቆራርጣለሁ፤ ሁላች
ሁንም ፡ እሰቅላችኋለሁም ፡
አለ ።
50 (እነርሱም) ፡ አሉ ፡— ጉዳት ፡
የለብንም ፤ እኛ ፡ ወደ ፡ ጌታችን ፡
ተመላሾች ፡ ነን ።
51 እኛ ፡ የምእምናን ፡ መጀመሪያ ፡
በመኾናችን ፡ ጌታችን ፡ ኀጢአ
ቶቻችንን ፡ ለኛ ፡ ሊምር ፡ እን
ከጅላለን ።
52 ወደ ፡ ሙሳም ፡—ባሮቼን ፡ ይዘህ፡
ሌሊት ፡ ኺድ ፡ እናንተ ፡ የሚከ
ተሉዋችሁ ፡ ናችሁና ፡ ስንል ፡
ላክን ።
53 ፈርዖንም ፡ በየከተሞቹ ፡ ሰብሳ
ቢዎችን ፡ (እንዲህ ፡ ሲል) ፡
ላከ ፤
54 ፡—እነዚህ ፡ ጥቂቶች ፡ ጭፍ
ሮች ፡ ናቸው ።
55 እነርሱም ፡ ለኛ ፡ አስቆጪዎች ፡
ናቸው ።
56 እኛም ፡ ብዙዎች ፡ ጥንቁቆች ፡
ነን ፤ (አለ) ።
57 አወጣናቸውም ፤ ከአትክልቶችና፡
ከምንጮች ፤
58 ከድልቦችም ፡ ከመልካም ፡ መቀ
መጫዎችም ።
59 እንደዚሁ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡
አወረስናትም ።
60 ፀሐይዋ ፡ ስትወጣም ፡ ተከተሉ
ዋቸው ።
61 ሁለቱ ፡ ጭፍሮችም ፡ በተያዩ ፡
ጊዜ ፡ የሙሳ ፡ ጓዶች ፡ እኛ ፡ (የፈ
ርዖን ፡ ሰዎች) ፡ የሚደርሱብን ፡
ነን ፡ አሉ ።
62 (ሙሳ) ፡— ተውዉ ! ጌታዬ ፡ ከኔ ፡
ጋር ፡ ነው ፤ በእርግጥ ፡ ይመራ
ኛል ፤ አለ ።
63 ወደ ፡ ሙሳም ፡ ባሕሩን ፡ በበት
ርህ ፡ ምታው ፡ ስንል ፡ ላክንበት ፡
(መታውና) ፡ ተከፈለም ፤ ክፍ
ሉም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ጋራ፡
ኾነ ።
64 እዚያም ፡ ዘንድ ፡ ሌሎችን ፡ አቀ
ረብን ።

65 ሙሳንና ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያሉት
ንም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉንም ፡ አዳን ።
66 ከዚያም ፡ ሌሎቹን ፡ አሰጠምን ።
67 በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ታምር ፡
አለበት ፤ አብዛኞቻቸውም ፡ አማ
ኞች ፡ አልነበሩም ።
68 ጌታህም ፡ እርሱ ፡ አሸናፊው ፡
አዛኙ ፡ ነው ።
69 በነሱም ፡ (በሕዝቦችህ) ፡ ላይ ፡
የኢብራሂምን ፡ ወሬ ፡ አንብብ
ላቸው ።
70 ለአባቱና ፡ ለሕዝቦቹ ፡ ምንን ፡
ትግገዛላችሁ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡
71 ጣዖታትን ፡ እንግገዛለን ፤ እርሷ
ንም ፡ በመግገዛት ፡ ላይ ፡ እንቆ
ያለን ፤ አሉ ።
72 (እርሱም) ፡ አለ ፡— በጠራች
ኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ይሰሟችኋልን?
73 ወይስ ፡ ይጠቅሟችኋልን ? ወይስ ፡
ይጐዷችኋልን ?
74 የለም ፡ አባቶቻችን ፡ እንደዚሁ ፡
ሲሠሩ ፡ አገኘን ፡ አሉት ።
75 ትግገዙት ፡ የነበራችሁትን ፡ አስ
ተዋላችሁን ?
76 እናንተም ፡ የቀድሞዎቹ ፡ አባቶ
ቻችሁም ፡ (የተገዛችሁትን) ፤
77 እነሱም ፡ (ጣዖቶቹ) ፡ ለኔ ፡ ጠላ
ቶች ፡ ናቸው ፤ ግን ፡ የዓለማት ፡
ጌታ ፡ ሲቀር ፡ (እርሱ ፡ ወዳጄ ፡
ነው) ።
78 (እርሱ) ፡ ያ ፡ የፈጠረኝ ፡ ነው ፤
እርሱም ፡ ይመራኛል ።
79 ያም ፡ እርሱ ፡ የሚያበላኝና ፡
የሚያጠጣኝ ፡ ነው ።
80 በታመምኩም ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡
ያሽረኛል ።
81 ያም ፡ የሚገድለኝ ፡ ከዚያም ፡
ሕያው ፡ የሚያደርገኝ ፡ ነው ።
82 ያም ፡ በፍርዱ ፡ ቀን ፡ ኀጢአቴን ፡
ለኔ ፡ ሊምር ፡ የምከጅለው ፡ ነው ።
83 ጌታዬ ፡ ሆይ ! ዕውቀትን ፡ ስጠኝ፤
በደጋጎቹም ፡ ሰዎች ፡ አስጠጋኝ።
84 በኋለኞቹም ፡ ሕዝቦች ፡ ውስጥ ፡
ለኔ ፡ መልካም ፡ ዝናን ፡ አድር
ግልኝ ።
85 የጸጋይቱን ፡ ገነት ፡ ከሚወርሱ
ትም ፡ አድርገኝ ።
86 ለአባቴም ፡ ማር ፤ እርሱ ፡ ከተሳ
ሳቱት ፡ ነበረና ።
87 በሚቀሰቀሱበት ፡ ቀንም ፡ አታ
ዋርደኝ ፤
88 ገንዘብም ፡ ልጆችም ፡ በማይጠ
ቅሙበት ፡ ቀን ፤
89 ወደ ፡ አላህ ፡ በንጹህ ፡ ልብ ፡
የመጣ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ እንጅ ።
90 ገነትም ፡ ለፈሪዎች ፡ በምትቀረ
ብበት ፡ (ቀን) ፤
91 ገሀነምም ፡ ለጠማሞች ፡ በምት
ገለጽበት ፡ (ቀን) ፤
92 ለነሱም ፡ በሚባል ፡ ቀን ፡- ትግገ
ዟቸው ፡ የነበራችሁት ፡ የት ፡
ናቸው ?
93 ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ሲኾኑ ፡ ይረዱ
ዋችኋልን ? ወይስ ፡ (ለራሳቸው) ፡
ይረዳሉን ?
94 በውስጧም ፡ እነሱና ፡ ጠማሞቹ፡
በፊቶቻቸው ፡ ተጥለው ፡ ይንከ
ባለላሉ ፤
95 የሰይጣንም ፡ ሰራዊቶች ፡ መላ
ውም ፡ (ይጣላሉ) ።
96 እነርሱም ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ የሚ
ከራከሩ ፡ ኾነው ፡ ይላሉ ፡-



97 በአላህ ፡ እንምላለን ፤ እኛ ፡ በግ
ልጽ ፡ መሳሳት ፡ ውስጥ ፡ ነበ
ርን ።
98 (ጣዖቶቹን) ፡ በዓለማት ፡ ጌታ ፡
ባስተካከልናችሁ ፡ ጊዜ ።
99 አመጠኞቹም ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አላ
ሳሳተንም ።
100 ከአማላጆችም ፡ ለኛ ፡ ምንም ፡
የለንም ።
101 አዛኝ ፡ ወዳጂም ፡ (የለንም) ።
102 ለኛም ፡ አንዲት ፡ ጊዜ ፡ መመ
ለስ ፡ በኖረችንና ፡ ከአማኞቹ ፡
በኾን ፡ እንመኛለን ፡ (ይላሉ) ።
103 በዚህ ፡ ውስጥ ፡ አስደናቂ ፡ ግ
ሣጼ ፡ አለበት ፤ አብዛኞቻቸውም፡
አማኞች ፡ አልነበሩም ።
104 ጌታህም ፡ እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ አሸ
ናፊው ፡ አዛኙ ፡ ነው ።
105 የኑሕ ፡ ሕዝቦች ፡ መልክተኞችን ፡
አስተባበሉ ።
106 ወንድማቸው ፡ ኑሕ ፡ ለነሱ ፡ ባላ
ቸው ፡ ጊዜ ፡- አትጠነቀቁምን ?
107 እኔ ፡ ለናንተ ፡ ታማኝ ፡ መልክ
ተኛ ፡ ነኝ ።
108 አላህንም ፡ ፍሩ ፤ ታዘዙኝም ።
109 በርሱም ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡
አልጠይቃችሁም ፤ ዋጋዬ ፡ በዓለ
ማት ፡ ጌታ ፡ ላይ ፡ እንጅ ፡ በሌላ ፡
ላይ ፡ አይደለም ።
110 አላህንም ፡ ፍሩ ፤ ታዘዙኝም ።
111 (እነርሱም) ፡ ወራዶቹ ፡ የተከተ
ሉህ ፡ ኾነህ ፡ ለአንተ ፡ እናምና
ለን ? አሉት ።
112 (እርሱም) ፡ አላቸው ፡— ይሠ
ሩት ፡ በነበሩት ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ዕው
ቀት ፡ አለኝ ፤
113 ምርመራቸው ፡ በጌታዬ ፡ ላይ ፡
እንጅ ፡ በሌላ ፡ ላይ ፡ አይደለም ፤
ብታውቁ ፡ ኖሮ ፡ (ይህንን ፡ ትረዱ ፡
ነበር) ፤
114 እኔም ፡ አማኞችን ፡ አባራሪ ፡
አይደለሁም ፤
115 እኔ ፡ ግልጽ ፡ አስፈራሪ ፡ እንጅ ፡
ሌላ ፡ አይደለሁም ።
116 ፡— ኑሕ ፡ ሆይ ! (ከምትለው) ፡
ባትከለከል ፡ በእርግጥ ፡ ከሚወገ
ሩት ፡ ትኾናለህ ፡ አሉት ።
117 (እርሱም) ፡ አለ ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ!
ሕዝቦቼ ፡ አስተባበሉኝ ፤
118 በኔና ፡ በነርሱም ፡ መካከል ፡
(ተገቢ) ፡ ፍርድን ፡ ፍረድ ፤ አድነ
ኝም ፤ ከኔ ፡ ጋር ፡ ያሉትንም ፡
ምእምናን ።
119 እርሱንም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያለው
ንም ፡ ሁሉ ፡ በተመላው ፡ መር
ከብ ፡ ውስጥ ፡ አዳን ።
120 ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ቀሪዎቹን ፡ አሰ
ጠምን ።
121 በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ግሣጼ ፡
አለበት ፤ አብዛኞቻቸውም ፡ አማ
ኞች ፡ አልነበሩም ።
122 ጌታህም ፡ እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ አሸ
ናፊው ፡ አዛኙ ፡ ነው ።
123 ዓድ ፡ መልክተኞችን ፡ አስተባበ
ለች ፤
124 ወንድማቸው ፡ ሁድ ፡ ለነርሱ ፡
ባላቸው ፡ ጊዜ ፡— አትጠነቀቁ
ምን ?
125 እኔ ፡ ለናንተ ፡ ታማኝ ፡ መልክ
ተኛ ፡ ነኝ ።
126 አላህንም ፡ ፍሩ ፡ ታዘዙኝም ።
127 በርሱም ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡
አልለምናችሁም ፤ ዋጋዬ ፡ በዓለ

ማት ፡ ጌታ ፡ ላይ ፡ እንጅ ፡ በሌላ ፡ ላይ ፡ አይደለም ።

128 የምትጫወቱ ፡ ኾናችሁ ፡ በከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ምልክትን ፡ ትገነባላችሁን ?

129 የውሃ ፡ ማጠራቀሚያዎችንና ፡ ሕንጻዎችንም ፡ ዘላለም ፡ መኖርን ፡ የምትከጅሉ ፡ ኾናችሁ ፡ ትሠራላችሁን ?

130 በቀጣችሁም ፡ ጊዜ ፡ ጨካኞች ፡ ኾናችሁ ፡ ትቀጣላችሁን ?

131 አላህንም ፡ ፍሩ ፤ ታዘዙኝም ።

132 ያንንም ፡ በምታውቁት ፡ (ጸጋ) ፡ ያጣቀማችሁን ፡ ፍሩ ።

133 በእንስሳዎችና ፡ በልጆች ፡ ያጣቀማችሁን ፤

134 በአትክልቶችና ፡ በምንጮችም ፤

135 እኔ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ የታላቅን ፡ ቀን ፡ ቅጣት ፡ እፈራለሁና ።

136 (እነርሱም) ፡ አሉ ፡— ብትገሥጽም ፡ ወይም ፡ ከገሣጮቹ ፡ ባትኾንም ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ እኩል ፡ ነው ፤ (ያለንበትን ፡ አንለቅም) ፤

137 ይህ ፡ የፊተኞቹ ፡ ሰዎች ፡ ጠባይ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ።

138 እኛም ፡ የምንቀቀጣ ፡ አይደለንም ፡ (አሉ) ።

139 አስተባበሉትም ፤ አጠፋናቸውም፤ በዚህም ፡ ውስጥ ፡ እርግጠኛ ፡ ግሣጼ ፡ አለበት ፤ አብዛኞቻቸውም፡ ምእምናን ፡ አልነበሩም ።

140 ጌታህም ፡ እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ አሸናፊው ፡ አዛኙ ፡ ነው ።

141 ሠሙድ ፡ መልክተኞችን ፡ አስተባበለች ፤

142 ወንድማቸው ፡ ሷሊሕ ፡ ለነርሱ ፡ ባላቸው ፡ ጊዜ ፡— አትጠነቀቁምን ?

143 እኔ ፡ ለናንተ ፡ ታማኝ ፡ መልክተኛ ፡ ነኝ ፤

144 አላህንም ፡ ፍሩ ፤ ታዘዙኝም ።

145 በርሱም ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ አልለምናችሁም ፤ ዋጋዬ ፡ በዓለማት ፡ ጌታ ፡ ላይ ፡ እንጅ ፡ በሌላ ፡ ላይ ፡ አይደለም ።

146 በዚያ ፡ እዚህ ፡ ባለው ፡ (ጸጋ) ፡ ውስጥ ፡ የረካችሁ ፡ ኾናችሁ ፡ ትትተዋላችሁን ?

147 በአትክልቶችና ፡ በምንጮች ፡ ውስጥ ፤

148 በአዝመራዎችም ፡ ፍሬዋ ፡ የበሰለ ፡ በኾነች፡ ዘንባባም፤ (ውስጥ፡ ትትተዋላችሁን?)

149 ብልሆች ፡ ኾናችሁ ፡ ከጋራዎች ፡ ቤቶችንም ፡ ትጠርባላችሁ ።

150 አላህንም ፡ ፍሩ ፤ ታዘዙኝም ።

151 የወሰን ፡ አላፊዎችንም ፡ ትዕዛዝ ፡ አትከተሉ ፤

152 የነዚያን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚያጠፉትንና ፡ የማያበጁትን ።

153 (እነሱም) ፡ አሉ ፡— አንተ ፡ በብዙ ፡ ከተደገመባቸው ፡ ሰዎች፡ ብቻ ፡ ነህ ፤

154 አንተ ፡ ብጤያችን ፡ ሰው ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለህም ፤ ከውነተኞቹም፡ እንደ፡ ኾንክ፡ ተአምርን ፡ አምጣ ።

155 (እርሱም) ፡ አለ ፡- ይህች ፡ ግመልናት ፤ ለርሷ ፡ የመጠጥ ፡ ፋንታ ፡ አላት ፤ ለናንተም ፡ የታወቀ ፡ ቀን ፡ ፋንታ ፡ አላችሁ ፤



156 በክፉም ፡ አትንኳት ፤ የታላቅ ፡ ቀን ፡ ቅጣት ፡ ይይዛችኋልና ።

157 ወጓትም ፤ ወዲያውም ፡ ተጸጻቾች ፡ ኾነው ፡ አነጉ ።

158 ቅጣቱም ፡ ያዛቸው ፤ በዚህም ፡ ውስጥ ፡ ግሣጼ ፡ አለበት ፤ አብዛኞቻቸውም ፡ ምእምናን ፡ አልነበሩም ።

159 ጌታህም ፡ እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ አሸናፊው ፡ አዛኙ ፡ ነው ።

160 የሉጥ ፡ ሕዝቦች ፡ መልክተኞችን ፡ አስተባበሉ ፤

161 ወንድማቸው ፡ ሉጥ ፡ ለነርሱ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡— አትጠነቀቁምን?

162 እኔ ፡ ለናንተ ፡ ታማኝ ፡ መልክተኛ ፡ ነኝ ።

163 አላህንም ፡ ፍሩ ፤ ታዘዙኝም ።

164 በርሱም ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ አልለምናችሁም ፤ ዋጋዬ ፡ በዓለማት ፡ ጌታ ፡ ላይ ፡ እንጅ ፡ በሌላ ፡ ላይ ፡ አይደለም ፤

165 ከዓለማት ፡ ሰዎች ፡ ወንዶችን ፡ ትመጣላችሁን ?

166 ከሚስቶቻችሁም ፡ ጌታችሁ ፡ ለናንተ ፡ የፈጠረላችሁን ፡ ትተዋላችሁን ? በውነቱ ፡ እናንተ ፡ ወሰን ፡ አላፊዎች ፡ ሕዝቦች ፡ ናችሁ ።

167 (እነርሱም) ፡ አሉ ፡— ሉጥ ፡ ሆይ ! ባትከለከል ፡ በእርግጥ ፡ (ከአገር) ፡ ከሚወጉጡት ፡ ትኾናለህ ፤

168 (እርሱም) ፡ አለ ፡— እኔ ፡ ሥራችሁን ፡ ከሚጠሉት ፡ ሰዎች ፡ ነኝ ።

169 ጌታዬ ፡ ሆይ ! እኔንም ፡ ቤተሰቦቼንም ፡ ከሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ (ቅጣት) ፡ አድነን ።

170 እርሱንም ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹንም ፡ በጠቅላላ ፡ አዳንናቸው ።

171 በቀሪዎቹ ፡ ውስጥ ፡ የኾነች ፡ አሮጊት ፡ ብቻ ፡ ስትቀር ፡ (እርሷ፡ ጠፋች) ።

172 ከዚያም ፡ ሌሎቹን ፡ አጠፋን ።

173 በነሱም ፡ ላይ ፡ (የደንጊያ) ፡ ዝናምን ፡ አዘነምንባቸው ፤ የተስፈራሪዎቹም ፡ ዝናም ፡ ከፋ ።

174 በዚህ ፡ ውስጥ ፡ አስደናቂ ፡ ታምር ፡ አለበት ፤ አብዛኞቻቸውም ፡ ምእምናን ፡ አልነበሩም ።

175 ጌታህም ፡ እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ አሸናፊው ፡ አዛኙ ፡ ነው ።

176 የአይከት ፡ ሰዎች ፡ መልክተኞችን ፡ አስተባበሉ ፤

177 ሹዐይብ ፡ ለነርሱ ፡ ባላቸው ፡ ጊዜ ፡-አትጠነቀቁምን ?

178 እኔ ፡ ለናንተ ፡ ታማኝ ፡ መልክተኛ ፡ ነኝ ፤

179 አላህንም ፡ ፍሩ ፤ ታዘዙኝም ፤

180 በርሱም ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ አልጠይቃችሁም ፤ ዋጋዬ ፡ በዓለማት ፡ ጌታ ፡ ላይ ፡ እንጅ ፡ በሌላ ፡ ላይ ፡ አይደለም ።

181 ስፍርን ፡ ምሉ ፤ ከአጉዳዮቹም ፡ አትኹኑ ።

182 በትክክለኛ ፡ ሚዛንም ፡ መዝኑ ።

183 ሰዎችንም ፡ ነገሮቻቸውን ፡ አታጉድሉባቸው ። በምድርም ፡ ላይ ፡ አጥፊዎች ፡ ኾናችሁ ፡ አታበላሹ።

184 ያንንም ፡ የፈጠራችሁን ፡ የቀድሞዎቹንም ፡ ፍጡሮች ፡ (የፈጠረውን) ፡ ፍሩ ።

185 አሉ ፡— አንተ ፡ በብዛት ፡ ከተደገመባቸው ፡ ሰዎች ፡ ነህ ፤

186 አንተም ፡ ብጤያችን ፡ ሰው ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለህም ፤ እነሆ፡ ከውሸታሞች ፡ ነህ ፡ ብለን ፡ እንጠረጥርሃለን ፤

187 ከውነተኞቹም ፡ እንደኾንክ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ከሰማይ ፡ ቁራጭን ፡ ጣልብን ።

188 ፡—ጌታዬ ፡ የምትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፤ አላቸው ።

189 አስተባበሉትም ፤ የጥላይቱ ፡ ቀን ፡ ቅጣትም ፡ ያዛቸው ፤ እርሱ ፡ የከባድ ፡ ቀን ፡ ቅጣት ፡ ነበርና ።

190 በዚህ ፡ ውስጥ ፡ አስደናቂ ፡ ታምር ፡ አለበት ፤ አብዛኞቻቸውም ፡ ምእምናን ፡ አልነበሩም ።

191 ጌታህም ፡ እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ አሸናፊው ፡ አዛኙ ፡ ነው ።

192 እርሱም ፡ (ቁርአን) ፡ በእርግጥ ፡ ከዓለማት ፡ ጌታ ፡ የተወረደ ፡ ነው ።

193 እርሱን ፡ ታማኙ ፡ መንፈስ ፡ (ጂብሪል) ፡ አወረደው ፤

194 ከአስፈራሪዎቹ ፡ (ነቢያት) ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ በልብህ ፡ ላይ ፡ (አወረደው) ፤

195 ግልጽ ፡ በኾነ ፡ ዐረብኛ ፡ ቋንቋ ።

196 እርሱም ፡ (ቁርአን) ፡ በቀድሞዎቹ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ (የተወሳ) ፡ ነው ።

197 የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሊቃውንት ፡ የሚያውቁት ፡ መኾኑ ፡ ለነርሱ ፡ (ለመካ ከሓዲዎች)፡ ምልክት ፡ አይኾናቸውምን ?

198 ከአዕጀሞች ፡ (1) ባንዱ ፡ ላይ ፡ ባወረድነውም ፡ ኖሮ ፡

199 በነርሱ ፡ ላይ ፡ ባነበበውም ፡ በርሱ ፡ አማኞች ፡ አይኾኑም ፡ ነበር ።

200 እንደዚሁ ፡ (ማስተባበልን) ፡ በተንኮለኞች ፡ ልቦች ፡ ውስጥ ፡ አስገባነው ።

201 አሳማሚ ፡ ቅጣትን ፡ እስከሚያዩ፡ ድረስ ፡ በርሱ ፡ አያምኑም ።

202 እነርሱ ፡ የማያውቁ ፡ ሲኾኑ ፡ (ቅጣቱ) ፡ ድንገት ፡ እስከሚመጣባቸውም ፡ ድረስ ፡ (አያምኑም) ።

203 (በመጣባቸው ፡ ጊዜ) ፡ እኛ ፡ የምንቅቆይ ፡ ነን ? እስከሚሉም ፤ (አያምኑም) ።

204 በቅጣታችን ፡ ያቻኩላሉን ?

205 አየህን ? ብዙ ፡ ዓመታትን ፡ ብናጣቅማቸው ፤

206 ከዚያም ፡ ያ ፡ ይስፈራሩበት ፡ የነበሩት ፡ ቢመጣባቸው ፤

207 ይጣቀሙበት ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ ከነሱ ፡ ምንም ፡ አያብቃቃቸውም ።

208 አንዲትንም ፡ ከተማ ፡ ለርሷ ፡ አስፈራሪዎች ፡ ያሏት (ና ፡ ያስተባበለች) ፡ ኾና ፡ እንጅ ፡ አላጠፋንም ።

209 (ይህች) ፡ ግሣጼ ፡ ናት ፤ በዳዮችም ፡ አልነበርንም ።

210 ሰይጣናትም ፡ እርሱን ፡ (ቁርአንን ፡ አላወረዱትም ።

211 ለነርሱም ፡ አይገባቸውም ፤ አይችሉምም ።

212 እነርሱ ፡ (የመላእክትን ፡ ንግግር)፡ ከመስማት ፡ የተከለከሉ ፡ ናቸው ።

1 ዐረብ ፡ ካልኾኑት ።



213 ከአላህም ፡ ጋር ፡ ሌላን ፡ አምላክ ፡ አትገዛ ፤ ከሚቀጥጡት ፡ ትኾናለህና ።

214 ቅርቦች ፡ ዘመዶችህንም ፡ አስጠንቅቅ ።

215 ከምእምናንም ፡ ለተከተሉህ ፡ ሰዎች ፡ክንፍህን ፡ ዝቅ ፡ አድርግ ፤ (ልዝብ ፡ ኹን) ።

216 እንቢ ፡ ቢሉህም ፡ እኔ ፡ ከምትሠሩት ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ በላቸው ።

217 አሸናፊ ፡ አዛኝ ፡ በኾነው ፡ (ጌታህ) ፡ ላይም ፡ ተጠጋ ።

218 በዚያ ፡ ለሶላት ፡ በምትቆም ፡ ጊዜ ፡ በሚያይህ ፤

219 በሰጋጆች ፡ ውስጥ ፡ መዘዋወርህንም ፡ (በሚያየው ፡ ጌታህ ፡ ላይ ፡ ተጠጋ) ፤

220 እነሆ ፡ እርሱ ፡ ሰሚው ፡ ዐዋቂው ፡ ነውና ።

221 ሰይጣናት ፡ በማን ፡ ላይ ፡ እንደሚወርዱ ፡ ልንገራችሁን ?

222 በውሸታም ፡ ኀጢአተኛ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይወርዳሉ ።

223 የሰሙትን ፡ (ወደ ፡ ጠንቋዮች) ፡ ይጥላሉ ፤ አብዛኞቻቸውም ፡ ውሸታሞች ፡ ናቸው ።

224 ባለ ፡ ቅኔዎችንም ፡ ጠማማዎቹ ፡ ይከተሉዋቸዋል ።

225 እነርሱ ፡ በ(ንግግር) ፡ ሸለቆ ፡ ሁሉ ፡ የሚዋልሉ ፡ መኾናቸውን ፡ አታይምን ?

226 እነሱም ፡ የማይሠሩትን ፡ ነገር ፡ የሚናገሩ ፡ መኾናቸውን ፡ (አታይምን) ፤

227 እነዚያ ፡ ያመኑና ፡ መልካም ፡ ሥራዎችን ፡ የሠሩ ፡ አላህንም ፡ በብዛት ፡ ያወሰሱ ፡ ከተበደሉም ፡ በኋላ ፡ (በቅኔ) ፡ የተከላከሉ ፡ ሲቀሩ ፤ (እነርሱ ፡ አይወቀሱም)፤ እነዚያም ፡ የበደሉ ፡ (ከሞቱ ፡ በኋላ) ፡ እንዴት ፡ ያለን ፡ መመለስ ፡ እንደሚመለሱ ፡ በእርግጥ ፡ ያውቃሉ ።

## ምዕራፍ ፡ 27 ፡ አል-ነምል ። ክፍል ፡ 19 ።

27ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ነምል ፡ (የጉንዳን ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 93 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በኾነው ።

1 ጠ. ሰ. (ጣ ፡ ሲን) ፡ ይህቺ ፡ ከቁርአኑና ፡ ከገላጩ ፡ መጽሐፍ ፡ አንቀጾች ፡ ናት ።

2 ለምእምናን ፡ መሪና ፡ ብስራት ፡ ናት ።

3 ለነዚያ ፡ ሶላትን ፡ ለሚሰግዱት ፡ ዘካንም ፡ ለሚሰጡት ፡ እነሱም ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ሕይወት ፡ እነሱ ፡ የሚያረጋግጡ ፡ ለኾኑት ።

4 እነዚያ ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ዓለም ፡
የማያምኑት ፡ ለነሱ ፡ (ክፉ) ፡
ሥራዎቻቸውን ፡ ሸለምንላቸው ፤
(1) ስለዚህ ፡ እነርሱ ፡ ይዋልላሉ ።

5 እነርሱ ፡ እነዚያ ፡ ክፉ ፡ ቅጣት ፡
ለነርሱ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ፤ እነ
ሱም ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ዓለም ፡
እነርሱ ፡ በጣም ፡ ከሳሪዎቹ ፡
ናቸው ።

6 አንተም ፡ ቁርአንን ፡ ጥበበኛና ፡
ዐዋቂ ፡ ከኾነው ፡ (ጌታህ) ፡
ዘንድ ፡ በእርግጥ ፡ ትስሰጣለህ ።

7 ሙሳ ፡ ለቤተሰቦቹ ፦እኔ ፡ እሳ
ትን ፡ አየሁ ፡ ከርሷ ፡ ወሬን ፡
አመጣላችኋለሁ ፤ ወይም ፡ ትሞቁ
ዘንድ ፡ የተለኮሰ ፡ ችቦን ፡ አመጣ
ላችኋለሁ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ (የኾነ
ውን ፡ አውሳላቸው) ።

8 በመጣትም ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡
በማለት ፡ ተጠራ ፤ ፦በእሳቲቱ ፡
ያለው ፡ ሰውና ፡ በዙሪያዋ ፡
ያሉም ፡ ሁሉ ፡ ተባረኩ ፤ የዓለ
ማትም ፡ ጌታ ፡ አላህ ፡ ጥራት ፡
ይገባው ፤

9 ሙሳ ፡ ሆይ ! እነሆ ፡ እኔ ፡ አሸ
ናፊው ፡ ጥበበኛው ፡ አላህ ፡ ነኝ ።

10 በትርህንም ፡ ጣል ፡ (ተባለ ፤
ጣለም) ፤ እርሷ ፡ እንደ ፡ ትንሽ ፡
እባብ ፡ በፍጥነት ፡ ስትስለከለክ ፡
ባያትም ፡ ጊዜ ፤ ፊቱን ፡ ዞሮ ፡
ሸሸ ፤ አልተመለሰምም ፤ ሙሳ ፡
ሆይ ! አትፍራ ፤ እኔ ፡ መልክተ
ኞቹ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ አይፈሩምና ፤

11 ግን ፡ የበደለ ፡ ሰው ፡ ከዚያም ፡
ከመጥፎ ፡ ሥራው ፡ በኋላ ፡ መል
ካምን ፡ የለወጠ ፡ እኔ ፡ መሓሪ ፡
አዛኝ ፡ ነኝ ፤

12 እጅህንም ፡ በአንገትጌህ ፡ ውስጥ ፡
አግባ ፤ ያለነውር ፡ (ያለ ፡ ለምጽ) ፡
ነጭ ፡ ኾና ፡ ትወጣለችና ፤ በዘ
ጠኝ ፡ ታምራት ፡ ወደ ፡ ፈርዖንና ፡
ወደ ፡ ሕዝቦቹ ፡ (ኺድ) ፤ እነርሱ ፡
አመጠኞች ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸውና ።

13 ታምራታችንም ፡ ግልጽ ፡ ኾና ፡
በመጣቻቸው ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ግልጽ
ድግምት ፡ ነው ፤ አሉ ።

14 ነፍሶቻቸውም ፡ ያረጋገጧት ፡
ሲኾኑ ፡ ለበደልና ፡ ለኩራት ፡
በርሷ ፡ ካዱ ፤ የአመጸኞችም ፡
ፍጻሜ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡
ተመልከት ።

15 ለዳውድና ፡ ለሱለይማንም ፡ ዕው
ቀትን ፡ በእርግጥ ፡ ሰጠናቸው ፤
አሉም ፦ምስጋና ፡ ለአላህ ፡
ለዚያ ፡ ከምእምናን ፡ ባሮቹ ፡
በብዙዎቹ ፡ ላይ ፡ ላበለጠን ፡
ይገባው ።

16 ሱለይማንም ፡ ዳውድን ፡ ወረሰ ፤
አለም ፦ሰዎች ፡ ሆይ ! የበራ
ሪን ፡ ንግግር ፡ (የወፍን ፡ ቋንቋ) ፡
ተስተማርን ፤ ከነገሩም ፡ ሁሉ ፡
ተሰጠን ፤ ይህ ፡ እርሱ ፡ በእርግጥ ፡
ግልጽ ፡ የኾነ ፡ ችሮታ ፡ ነው ።

17 ለሱለይማንም ፡ ሰራዊቶቹ ፡ ከጋ
ኔን ፡ ከሰውም ፡ ከበራሪም ፡ የኾ
ኑት ፡ ተሰበሰቡ ፤ እነሱም ፡ ይከ
መከማሉ ።

18 በጉንዳንም ፡ ሸለቆ ፡ በመጡ ፡
ጊዜ ፡ አንዲት ፡ ጉንዳን ፦እላ
ንተ ፡ ጉንዳኖች ፡ ሆይ ! ወደ ፡
መኖሪያዎቻችሁ ፡ ግቡ ፤ ሱለይ
ማንና ፡ ሰራዊቱ ፡ እነርሱ ፡
የማያውቁ ፡ ሲኾኑ ፡ አይሰባብ
ሩዋችሁ ፡ አለች ።

19 ከንግግርዋም ፡ እየሳቀ ፡ ጥርሱን ፡
ፈገግ ፡ አደረገ ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ !

1 መልካም ፡ አስመስለን ፡ አሳየናቸው ።



ያቺን ፡ በኔና ፡ በወላጆቼ ፡ ላይ ፡
የለገስካትን ፡ ጸጋህን ፡ እንዳመ
ሰግን ፡ የምትወደውንም ፡ በጎ ፡
ሥራ ፡ እንድሠራ ፡ ምራኝ ፤ በች
ሮታህም ፡ በመልካሞቹ ፡ ባሮ
ችህ ፡ ውስጥ ፡ አግባኝ ፡ አለ ።

20 በራሪዎቹንም ፡ ተመለከተ ፤ አ
ለም ፦ ሁድሁድን ፡ (1) ለምን ፡
አላየውም ! በውነቱ ፡ ከራቁት ፡
ነበርን ?።

21 ብርቱን ፡ ቅጣት ፡ በእርግጥ ፡ እቀ
ጣዋለሁ ፤ ወይም ፡ በእርግጥ ፡
ዐርደዋለሁ ፤ ወይም ፡ ግልጽ ፡
በኾነ ፡ አስረጅ ፡ ይመጣኛል ፡
(አለ) ።

22 (ወፉ) ፡ ዕሩቅ ፡ ያልኾነንም ፡ ጊዜ ፡
ቆዬ ፤ አለም ፦ ያላወቅከውን ፡
ነገር ፡ አወቅኩ ፤ ከሰበእም ፡ እር
ግጠኛን ፡ ወሬ ፡ አመጣሁልህ ፤

23 እኔ ፡ የምትገዛቸው ፡ የኾነችን ፡
ሴት ፡ ከነገሩም ፡ ሁሉ ፡ የተሰጠ
ችን ፡ አገኘሁ ፤ ለርሷም ፡ ታላቅ ፡
ዙፋን ፡ አላት ፤

24 እርስዋንም ፡ ሕዝቦችዋንም ፡
ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ለፀሐይ ፡ ሲሰግዱ ፡
አገኘኋቸው ፤ ሰይጣንም ፡ ለነሱ ፡
ሥራዎቻቸውን ፡ ሸልሞላቸዋል ፤
ከውነተኛውም ፡ መንገድ ፡ አግ
ዷቸዋል ፤ ስለዚህ ፡ እነሱ ፡
(ወደ ፡ እውነት) ፡ አይመሩም ።

25 ለዚያ ፡ በሰማያትና ፡ በምድር ፡
የተደበቀውን ፡ ለሚያወጣው ፤
የምትሸሽጉትንና ፡ የምትገልጹ
ትንም ፡ ሁሉ ፡ ለሚያውቀው ፡
አላህ ፡ እንዳይሰግዱ ፡ (ሰይጣን ፡
አግዷቸዋል) ።

26 አላህ ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡
የለም ፤ የታላቁ ፡ ዐርሽ ፡ (ዙፋን) ፡
ጌታ ፡ ነው ።

27 (ሱለይማንም) ፡ አለ ፦እውነት ፡
እንደ ፡ ተናገርክ ፡ ወይም ፡ ከው
ሸታሞቹ ፡ እንደ ፡ ኾንክ ፡ ወደ ፡
ፊት ፡ እናያለን ፤

28 ይህንን ፡ ደብዳቤዬን ፡ ይዘህ ፡
ኺድ ፤ ወደነርሱም ፡ ጣለው ፤
ከዚያም ፡ ከነሱ ፡ ዘወር ፡ በል ፤
ምን ፡ እንደሚመልሱም ፡ ተመ
ልከት ።

29 (እርሷም ፡ በደረሳት ፡ ጊዜ) ፡
አለች ፦ እላንተ ፡ መማክርቶች ፡
ሆይ ! እኔ ፡ ክብር ፡ ያለው ፡ ጽ
ሑፍ ፡ ወደኔ ፡ ተጣለ ፤

30 እርሱ ፡ ከሱለይማን ፡ ነው ፤ እር
ሱም ፡ በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡
በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡
በኾነው ፤

31 በኔ ፡ ላይ ፡ አትኩሩ ፤ ታዛዥ
ችም ፡ ኾናችሁ ፡ ወደኔ ፡ ኑ ፤
(የሚል ፡ ነው) ።

32 እላንተ ፡ መማክርቶች ፡ ሆይ !
በነገሬ ፡ (የሚበጀውን) ፡ ንገሩኝ ፤
እስከምትገኙልኝ ፡ ድረስ ፡ አን
ድንም ፡ ነገር ፡ ቆራጭ ፡ አይደ
ለሁምና ፡ አለች ።

33 እኛ ፡ የኀይል ፡ ባለ ፡ ቤቶች ፡
የብርቱ ፡ ጦርም ፡ ባለ ፡ ቤቶች ፡
ነን ፤ ግን ፡ ትእዛዙ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡
ነው ፤ ምን ፡ እንደምታዢም ፡
አስተውሊ ፡ አሏት ።

34 (እርሷም) ፡ አለች ፦ንጉሦች ፡
ከተማን ፡ (በኀይል) ፡ በገቡባት ፡
ጊዜ ፡ ያበላሹዋታል ፤ የተከበሩ ፡
ሰዎችዋንም ፡ ወራዶች ፡ ያደር
ጋሉ ፤ እንደዚሁም ፡ (እነዚህ) ፡
ይሠራሉ ፤

1 የዝናብ ፡ ወፍን ።

35 እኔም ፡ ወደነርሱ ፡ ገጸ ፡ በረከትን
የምልክና ፡ መልክተኞቹ ፡ በምን፡
እንደሚመለሱ ፡ የምጠባበቅ ፡
ነኝ ።

36 (መልክተኛው) ፡ ሱለይማንንም ፡
በመጣው ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡—በገን
ዘብ ፡ ትረዱኛላችሁን ? አላህም ፡
የሰጠኝ ፡ ከሰጣችሁ ፡ የበለጠ ፡
ነው ፤ ይልቁንም ፡ እናንተ ፡ በገጸ፡
በረከታችሁ ፡ ትደሰታላችሁ ።

37 ወደነሱ ፡ ተመለስ ፤ ለነሱም ፡
በርሷ ፡ ችሎታ ፡ በሌላቸው ፡
ሰራዊት ፡ እንመጣባቸዋለን ፤
ከርሷም ፡ እነርሱ ፡ የተዋረዱ ፡
ኾነው ፡ በእርግጥ ፡ እናወጣቸ
ዋለን ፡ (አለ) ።

38 ፡—እናንተ ፡ መኳንንቶች ፡ ሆይ !
ሙስሊሞች፡ ኾነው፡ ሳይመጡኝ፡
በፊት ፡ ዙፋንዋን ፡ የሚያመጣ
ልኝ ፡ ማንኛችሁ ፡ ነው ? አለ ።

39 ከጋኔን ፡ ኀይለኛው ፡—ከችሎ
ትህ ፡ ከመነሳትህ ፡ በፊት ፡ እኔ ፡
እርሱን ፡ አመጣልሃለሁ ፤ እኔም ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ታማኝ ፡
ነኝ ፤ አለ ።

40 ያ ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡ ከመጽሐፉ ፡
ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ (የተገ
ለጸው) ፡ ዓይንህ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡
ከመመለሱ ፡ በፊት ፡ እኔ ፡ እር
ሱን ፡ አመጣልሃለሁ፡ አለ ፤
(እንደዚሁም ፡ አደረገ) ፤ እርሱ ፡
ዘንድ ፡ ረግቶ ፡ ባየውም ፡ ጊዜ ፡
ይህ ፡ ከጌታዬ ፡ ችሮታ ፡ ነው ፤
የማመሰግን ፡ ወይም ፡ የምክድ ፡
መኾኔን ፡ ሊሞክረኝ ፡ (ቸረልኝ) ፤
ያመሰገነም ፡ ሰው ፡ የሚያመሰ
ግነው ፡ ለራሱ ፡ ነው ፤ የካደም ፡
ሰው ፡ ጌታዬ ፡ ከርሱ ፡ ተብቃቂ ፡
ቸር ፡ ነው ፡ አለ ።

41 ዙፋንዋን ፡ ለርሷ ፡ አሳስቱ ፤
ታውቀው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡
ከነዚያ ፡ ከማያውቁት ፡ ትኾን ፡
እንደ ፡ ኾነ ፡ እናያለን ፤ አላቸው ።

42 በመጣችም ፡ ጊዜ ፡— ዙፋንሽ ፡
እንደዚህ ፡ ነውን ? ተባለች ፤
እርሱ ፡ ልክ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡
መሰለኝ ፡ አለች ፤ (ሱለይማን) ፡
ከርሷ ፡ በፊትም ፡ ዕውቀትን ፡
ተሰጠን፤ ሙስሊሞችም፡ ነበርን፤
(አለ) ።

43 ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ትግገዛው ፡ የነበረ
ችውንም ፡ ከለከላት ፤ እርሷ ፡
ከከሓዲዎች ፡ ሕዝቦች ፡ ነበረ
ችና ።

44 ሕንጻውን ፡ ግቢ ፡ ተባለች ፤
ባየቺውም ፡ ጊዜ ፡ ባሕር ፡ ነው ፡
ብላ ፡ ጠረጠረችው ፤ ከባቶች
ዋም ፡ ገለጠች ፤ እርሱ ፡ ከመስ
ተዋት ፡ የተለሰለሰ ፡ ሕንጸ ፡ ነው፡
አላት ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ ነፍ
ሴን ፡ በደልኩ ፤ ከሱለይማንም ፡
ጋር ፡ ሆኜ ፡ ለዓለማት ፡ ጌታ ፡
ለአላህ ፡ ታዘዝኩ ፡ አለች ።

45 ወደ ፡ ሠሙድም ፡ ወንድማቸ
ውን ፡ ሷሊሕን ፡ አላህን ፡ ተገዙ ፡
በማለት ፡ በእርግጥ ፡ ላክነው ፤
ወዲያውም ፡ እነሱ ፡ የሚነታ
ረኩ ፡ ሁለት ፡ ጭፍሮች ፡ ኾኑ ።

46 ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ! ከመልካሙ ፡
በፊት ፡ በክፉው ፡ (ቅጣትን ፡
አምጣብን ፡ በማለት) ፡ ለምን ፡
ታስቸኩላላችሁ ፤ ይታዘንላችሁ ፡
ዘንድ ፡ አላህን ፡ ምሕረትን ፡ አት
ለምኑምን ፡ አላቸው ።

47 ባንተና ፡ ካንተም ፡ ጋር ፡ ባሉት፡
ሰዎች ፡ ምክንያት ፡ ገደ ፡ ቢሶች ፡
ኾን ፡ አሉት ፤ ገደ ፡ ቢስነታችሁ ፡
አላህ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ ይልቁንም ፡



እናንተ ፡ የምትፈተኑ ፡ ሕዝቦች ፡
ናችሁ ፡ አላቸው ።

48 በከተማይቱም ፡ ውስጥ ፡ በም
ድር ፡ ውስጥ ፡ የሚያበላሹና ፡
የማያሳምሩ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዎች ፡
ነበሩ ።

49 እርሱንና ፡ ቤተሰቦቹን ፡ ሌሊት ፡
ልንገድል ፡ ከዚያም ፡ ለዘመዱ ፡
የቤተሰቦቹን ፡ ጥፋት ፡ (መገደላቸ
ውን) ፡ አላየንም ፤ እኛም ፡ እውነ
ተኞች ፡ ነን ፡ ልንል ፡ በአላህ ፡ ተ
ማማሉ ፡ አሉ ።

50 ትንኮልንም ፡ መከሩ ፤ እነርሱም ፡
የማያውቁ ፡ ሲኾኑ ፡ በተንኮላ
ቸው ፡ አጠፋናቸው ።

51 የተንኮላቸውም ፡ መጨረሻ ፡
እንዴት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እኛ ፡
እነሱንም ፡ ሕዝቦቻቸውንም ፡
በሙሉ ፡ እንዴት ፡ እንዳጠፋ
ናቸው ፡ ተመልከት ።

52 እሊህም ፡ በበደላቸው ፡ ምክን
ያት ፡ ባዶዎች ፡ ሲኾኑ ፡ ቤቶቻ
ቸው ፡ ናቸው ፤ በዚህም ፡ ውስጥ ፡
ለሚያውቁ ፡ ሕዝቦች ፡ አስደናቂ፡
ታምር ፡ አለበት ።

53 እነዚያንም ፡ ያመኑትንና ፡ ከክ
ሕደት ፡ ይጠነቀቁ ፡ የነበሩትን ፡
አዳን ።

54 ሉጥንም ፡ ለሕዝቦቹ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ) ፤ እናንተ ፡ የምታዩ ፡
ስትኾኑ ፡ ጠያፍን ፡ ነገር ፡ ትሠ
ራላችሁን ?

55 እናንተ ፡ ከሴቶች ፡ አልፋችሁ ፡
ወንዶችን ፡ ለመከጀል ፡ ትመ
ጣላችሁን ? በውነቱ ፡ እናንተ ፡
የምትሳሳቱ ፡ ሕዝቦች ፡ ናችሁ ።

56 የሕዝቦቹም ፡ መልስ ፡ የሉጥን ፡
ቤተሰቦች፡ ከከተማችሁ ፡ አውጡ፡
እነርሱ ፡ የሚጥራሩ ፡ ሰዎች ፡
ናቸውና ፡ ማለት ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡
አልነበረም ።

57 እርሱንና ፡ ቤተሰቦቹንም ፡ አዳን ፤
ሚስቱ ፤ ብቻ ፡ ስትቀር ፤ (በጥ
ፋቱ ፡ ውስጥ) ፡ ከቀሪዎቹ ፡ አደ
ረግናት ።

58 በነርሱም ፡ ላይ ፡ (የደንጊያ) ፡
ዝናምን ፡ አዘነምንባቸው ፤ የተስ
ፈራሪዎቹም ፡ ዝናም ፡ ከፋ ።

59 (ሙሐመድ ፡ ሆይ) ፡ በል ፡-ምስ
ጋና ፡ ለአላህ ፡ ይግባው ፤ በነዚ
ያም ፡ በመረጣቸው ፡ ባሮቹ ፡
ላይ ፡ ሰላም ፡ ይውረድ ፤ አላህ ፡
በላጭ ፡ ነውን ? ወይስ ፡ ያ ፡
የሚያጋሩት ? (ጣዖት) ።

60 ወይም ፡ ያ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድ
ርን ፡ የፈጠረና ፡ ከሰማይም ፡
ለናንተ ፡ ውሃን ፡ ያወረደው ?
(ይበልጣል ? ወይስ ፡ የሚያጋሩ
ት) ፤ በርሱም ፡ ባለ ፡ ውበት ፡ የኾ
ኑትን ፡ የታጠሩ ፡ አትክልቶችን ፡
ዛፍዋን ፡ ልታበቅሉ ፡ ለናንተ ፡
ችሎታ ፡ ያልነበራችሁን ፡ አበ
ቀልን ፤ ከአላህ ፡ ጋር ፡ ሌላ ፡ አም
ላክ ፡ አለን ? (የለም) ፤ ግን ፡ እነሱ
(ከውነት) ፡ የሚያዘነብሉ ፡ ሕዝቦች
ናቸው ።

★ ★ ★

61 ወይም ፡ ያ ፡ ምድርን ፡ መርጊያ ፡
ያደረገና ፡ በመካከሏም ፡ ወንዞ
ችን ፡ ያደረገ ፡ ለርሷም ፡ ጋራዎ
ችን ፡ ያደረገ ፡ በሁለቱ ፡ ባሕሮ
ችም ፡ (በጣፋጩና ፡ በጨው ፡
ባሕር) ፡ መካከል ፡ ግርዶን ፡
ያደረገ ፡ (ይበልጣልን ? ወይስ ፡
የሚያጋሩት)? ከአላህ ፡ ጋር ፡

ሌላ ፡ አምላክ ፡ አለን ? ግን ፡
አብዛኞቻቸው ፡ አያውቁም ።

62 ወይም ፡ ያ ፡ ችግረኛን ፡ በለመ
ነው ፡ ጊዜ ፡ የሚቀበል ፡ መከራ
ንም ፡ የሚያስወግድ ፡ በምድርም ፡
ላይ ፡ ምትኮች ፡ የሚያደርጋችሁ ፤
(ይበልጣልን ? ወይስ ፡ የሚያጋ
ሩት?) ከአላህ ፡ ጋር ፡ ሌላ ፡ አም
ላክ ፡ አለን ? ጥቂትንም ፡ አት
ገሠጹም ።

63 ወይም ፡ ያ ፡ በየብስና ፡ በባሕር ፡
ጨለማዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚመ
ራችሁ ፡ ነፋሶችንም ፡ ከዝናሙ ፡
በፊት ፡ አብሳሪ ፡ ኾነው ፡ የሚ
ልክ ፡ (ይበልጣልን ? ወይስ ፡
የሚያጋሩት?) ከአላህ ፡ ጋር ፡
ሌላ ፡ አምላክ ፡ አለን ? አላህ ፡
(በርሱ) ፡ ከሚያጋሩዋቸው ፡ ሁሉ
ላቀ ።

64 ወይም ፡ ያ ፡ መፍጠርን ፡ የሚ
ጀምር ፡ ከዚያም ፡ የሚመልሰው ፡
ከሰማይና ፡ ከምድርም ፡ ሲሳይን ፡
የሚሰጣችሁ ፡ አምላክ ፡ (ይበ
ልጣልን ? ወይስ ፡ የሚያጋሩት ?)
ከአላህ ፡ ጋር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡
አለን ? እውነተኞች ፡ እንደ ፡ ኾና
ችሁ ፤ አስረጃችሁን ፡ አምጡ ፡
በላቸው ።

65 ፦በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡
ሁሉ ፡ ሩቅን ፡ ምስጢር ፡ አያው
ቅም ፤ ግን ፡ አላህ ፡ (ያውቀዋል) ፤
መቼ ፡ እንደሚቀሰቀሱም ፡ አያ
ውቁም ፡ በላቸው ።

66 በውነት ፡ የመጨረሻይቱን ፡ ዓ
ለም ፡ (ኹኔታ) ፡ ማወቃቸው ፡
ተሟላን ? አይደለም ፡ እነሱ ፡
ከርሷ ፡ በመጠራጠር ፡ ውስጥ ፡
ናቸው ፤ በውነትም ፡ እነሱ ፡
ከርሷ ፡ ዕውሮች ፡ ናቸው ።

67 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ አሉ ፡—
እኛም ፡ አባቶቻችንም ፡ ዐፈር ፡
በኾን ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ (ከመቃብር)፡
የምንወጣ ፡ ነን ?

68 ይህንን ፡ እኛም ፡ ከፊት ፡ የነበ
ሩት ፡ አባቶቻችንም ፡ በእርግጥ ፡
ተቀጥረንበታል ፤ ይህ ፡ የመጀ
መሪያዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ተረቶች ፡
እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፡ (አሉ) ።

69 ፦በምድር ፡ ላይ ፡ ኺዱ ፤ የአመጠ
ኞችም ፡ መጨረሻ ፡ እንዴት ፡
እንደ ፡ ነበረ ፡ ተመልከቱ ፡ በላ
ቸው ።

70 በነሱም ፡ ላይ ፡ አትዘን ፤ ከሚመ
ክሩብህም ፡ ነገር ፡ በጭንቀት ፡
ውስጥ ፡ አትኹን ።

71 ፦እውነተኞችም ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡
ይህ ፡ ቀጠሮ ፡ መቼ ፡ ነው ? ይላሉ ፤

72 ፦የዚያ ፡ የምትቻኮሉበት ፡ ከፊሉ ፡
ለናንተ ፡ የቀረበ ፡ መኾኑ ፡ ተረጋ
ግጧል ፡ በላቸው ።

73 ጌታህም ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ በእር
ግጥ ፡ የችሮታ ፡ ባለቤት ፡ ነው ፤
ግን ፡ አብዛኛዎቻቸው ፡ አያመ
ሰግኑም ።

74 ጌታህም ፡ ልቦቻቸው ፡ የሚደብቁ
ትንና ፡ የሚገልጹትን ፡ ያውቃል ።

75 በሰማይና ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡
ምንም ፡ የተደበቀ ፡ ነገር ፡ የለም ፡
ገላጭ ፡ በኾነው ፡ መጽሐፍ ፡
ውስጥ ፡ ያለ ፡ ቢኾን ፡ እንጅ ።

76 ይህ ፡ ቁርአን ፡ በእስራኤል ፡
ልጆች ፡ ላይ ፡ የዚያን ፡ እነሱ ፡
በርሱ ፡ የሚለያዩበትን ፡ አብዛኛ
ውን ፡ ይነግራል ።

77 እርሱም ፡ ለምእምናን ፡ መምሪ
ያና ፡ እዝነት ፡ ነው ።



78 ጌታህ ፡ በመካከላቸው ፡ በትክ
ክል ፡ ፍርዱ ፡ ይፈርዳል ፤ እር
ሱም ፡ አሸናፊው ፡ ዐዋቂው ፡
ነው ።

79 በአላህም ፡ ላይ ፡ ተጠጋ ፤ አንተ ፡
ግልጽ ፡ በኾነው ፡ እውነት ፡ ላይ ፡
ነህና ።

80 አንተ ፡ ሙታንን ፡ አታሰማም ፤
ደንቆሮችንም ፡ የሚተው ፡ ኾነው ፡
በዞሩ ፡ ጊዜ ፡ ጥሪን ፡ አታሰማም ።

81 አንተም ፡ (ልበ) ፡ ዕውሮችን ፡ ከጥ
መታቸው ፡ አቅኚ ፡ አይደለህም ፤
በአንቀጾቻችን ፡ የሚያምኑትን ፡
በስተቀር ፡ አታሰማም ፤ እነሱ ፡
ፍጹም ፡ ታዛዦች ፡ ናቸውና ።

82 በነሱም ፡ ላይ ፡ (የቅጣት) ፡ ቃሉ ፡
በተረጋገጠ ፡ ጊዜ ፡ ሰዎቹ ፡ በአን
ቀጾቻችን ፡ የማያረጋግጡ ፡ እንደ ፡
ነበሩ ፡ የምትነግራቸውን ፡ እን
ስሳ ፡ ለነርሱ ፡ ከምድር ፡ እናወ
ጣለን ።

83 ከሕዝቦቹም ፡ ሁሉ ፡ በአንቀጾቻ
ችን ፡ የሚያስተባብሉትን ፡ ጭፍ
ሮች ፡ የምንሰበስብበትን ፡ ቀን ፡
(አስታውስ) ፤ እነሱም ፡ ይከመከ
ማሉ ።

84 በመጡም ፡ ጊዜ ፡ (አላህ) ፡ ይላቸ
ዋል ፡— በአንቀጾቼ ፡ እርሷን ፡
በማወቅ ፡ ያላዳረሳችሁ ፡ ስትኾኑ ፡
አስተባበላችሁን ? ወይስ ፡ ምንን ፡
ትሠሩ ፡ ነበራችሁ ?

85 በመበደላቸውም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
ቃሉ ፡ ይፈጸምባቸዋል ፤ እነርሱም
አይናገሩም ።

86 እኛ ፡ ሌሊትን ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡
እንዲያርፉበት ፡ ቀንንም ፡ የሚያ
ሳይ ፡ እን፡ደረግን ፡ አያዩምን ?
ለሚያምኑ ፡ ሕዝቦች ፡ በዚህ ፡
ውስጥ ፡ ታምራቶች ፡ አሉበት ።

87 በቀንዱም ፡ በሚነፋ ፡ ቀን ፡ በሰማ
ያት ፡ ውስጥ ፡ ያሉትና ፡ በምድ
ርም ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡
አላህ ፡ የሻው ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡
ሲቀር ፡ በሚደነግጡ ፡ ጊዜ ፡ (የሚ
ኾነውን ፡ አስታውስ) ፤ ሁሉም ፡
የተናነሱ ፡ ኾነውም ፡ ወደርሱ ፡
ይመጣሉ ።

88 ጋራዎችንም ፡ እርሷ ፡ እንደ ፡
ደመና ፡ አስተላለፍ ፡ የምታልፍ ፡
ስትኾን ፡ የቆመች ፡ ናት ፡ ብለህ ፡
የምታስባት ፡ ኾና ፡ ታያታለህ ፤
የዚያን ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ያጠነከረ
ውን ፡ የአላህን ፡ ጥበብ ፡ (ተመል
ከት) ፤ እርሱ ፡ በምትሠሩት ፡
ሁሉ ፡ ውስጥ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

89 በመልካም ፡ ሥራ ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡
ለርሱ ፡ ከርስዋ ፡ የበለጠ ፡ ምንዳ ፡
አለው ፤ እነርሱም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡
ከድንጋጤ ፡ ጸጥተኞች ፡ ናቸው ።

90 በመጥፎም ፡ የመጡ ፡ ሰዎች ፡
ፊቶቻቸው ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡
ይደፋሉ ፤ ትሠሩት ፡ የነበራችሁ
ትን ፡ እንጅ ፡ አትመነዱም ፡ (ይባ
ላሉ) ።

91 የታዘዝኩት ፡ የዚህችን ፡ አገር ፡
ጌታ ፡ ያንን ፡ ክልል ፡ ያደረጋትን ፡
እንድግገዛ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ነገሩም ፡
ሁሉ ፡ የርሱ ፡ ነው ፤ ከእስላሞ
ችም ፡ እንድኾን ፡ ታዝዣለሁ ፡
(በላቸው) ።

92 ቁርአንንም ፡ እንዳነብ ፡ (ታዝዣ
ለሁ) ፤ የተመራም ፡ ሰው ፡ የሚመ
ራው ፡ ለራሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ የተሳ
ሳተም፡ ሰው፥ እኔ፡ ከአስጠንቃ

ቂዎች፡ ነኝ፡ እንጅ፡ ሌላ፡ አይደ
ለሁም፡ በለው።
93 ምስጋናም ፡ ለአላህ ፡ ነው ፤ ታም
ራቶቹን ፡ ወደፊት ፡ ያሳያችኋል ፤
ታውቋትምአላችሁ ፡ በላቸው ፤
ጌታህም ፡ ከምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡
ዘንጊ ፡ አይደለም ።

## ምዕራፍ ፡ 28 ፡ አል-ቀሶስ ። ክፍል ፡ 20 ፤

28ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አልቀሶስ ፡ (የዜናዎች ፡ ምዕራፍ) ፤ በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 88 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ፡ በኾነው።
1 ጠ.ሰ.መ. (ጣ ፡ ሲን ፡ ሚም) ።
2 ይህቺ ፡ ገላጭ ፡ ከሆነው ፡ መጽ
ሐፍ ፡ አንቀጾች ፡ ናት ።
3 ከሙሳና ፡ ከፈርዖን ፡ ዜና ፡ እውነተ
ኞች ፡ ስንኾን ፡ ለሚያምኑ ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ እናነባለን ።
4 ፈርዖን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተንበጣ
ረረ ፤ ነዋሪዎችዋንም ፡ የተከፋፈሉ ፡
ጓዶች ፡ አደረጋቸው ፤ ከነሱ ፡
ጭፍሮችን ፡ ያዳክማል ፤ ወንዶች ፡
ልጆቻቸውን ፡ በብዛት ፡ ያርዳል ፤
ሴቶቻቸውንም ፡ ይተዋል ፤ እርሱ ፡
ከሚያበላሹት ፡ ሰዎች ፡ ነበርና ።
5 በነዚያም ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ በተ
ጨቆኑት ፡ ላይ ፡ ልንለግስ ፤ መሪ
ዎችም ፡ ልናደርጋቸው ፡ ወራሾ
ችም ፡ ልናደርጋቸው ፡ እንሻለን ።
6 ለነርሱም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ልናስ
መች ፡ ፈርዖንንና ፡ ሃማንንም ፡
ሰራዊቶቻቸውንም ፡ ከነሱ ፡ ይፈ
ሩት ፡ የነበሩትን ፡ ነገር ፡ ልናሳ
ያቸው ፡ (እንሻለን) ።
7 ወደ ፡ ሙሳም ፡ እናት ፡— አጥ
ቢው ፤ በርሱም ፡ ላይ ፡ በፈራሽ ፡
ጊዜ ፡ በባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ጣይው ፤
አትፍሪም ፤ አትዘኚም ፤ እኛ ፡ ወዳ
ንቺ ፡ መላሾቹና ፡ ከመልክተኞ
ቹም ፡ አድራጊዎቹ ፡ ነንና ፡ ማለ
ትን ፡ አመለከትን ።
8 የፈርዖን ፡ ቤተሰቦችም ፡ (መጨረ
ሻው) ፡ ለነርሱ ፡ ጠላት ፡ ሐዘንም ፡
ይኾን ፡ ዘንድ ፡ አነሱት ፤ ፈርዖ
ንና ፡ ሃማንም ፡ ሰራዊቶቻቸውም ፡
ኀጢአተኞች ፡ ነበሩ ።
9 የፈርዖንም ፡ ሚስት ፡ ለኔ ፡ የዓ
ይኔ ፡ መርጊያ ፡ ነው ፤ ለአንተም ፤
አትግደሉት ፤ ሊጠቅመን ፡ ወ
ይም ፡ ልጅ ፡ አድርገን ፡ ልንይ
ዘው ፡ ይከጀላልና ፡ አለች ፤ እነር
ሱም ፡ (ፍጻሜውን) ፡ የማያውቁ ፡
ኾነው ፡ (አነሱት) ።
10 የሙሳም ፡ እናት ፡ ልብ ፡ ባዶ ፡
ኾነ ፤ ከምእምናን ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡
በልቧ ፡ ላይ ፡ ባላጠነከርን ፡ ኖሮ ፡
ልትገልጸው ፡ ቀርባ ፡ ነበር ።
11 ለእኅቱም ፡ ተከታተይው ፡ አለቻት ፤
እርሱንም ፡ እነሱ ፡ የማያውቅ ፡
ሲኾኑ ፡ በሩቅ ፡ ኾና ፡ አየችው ።



12 (ወደናቱ ፡ ከመመለሱ) ፡ በፊትም ፡
አጥቢዎችን ፡ (መጥባትን) ፡ በርሱ
ላይ ፡ እርም ፡ አደረግን ፤ (እኅቱ) ፡
ለናንተ ፡ የሚያሳድጉላችሁን ፡ እነ
ርሱም ፡ ለርሱ ፡ ቅን ፡ አገልጋ
ዮች ፡ የኾኑን ፡ ቤተሰቦች ፡ ላመል
ክታችሁን ? አለችም ።
13 ወደናቱም ፡ ዓይንዋ ፡ እንድት
ረጋ ፡ እንዳታዝንም ፡ የአላህም ፡
የተስፋ ፡ ቃል ፡ እርግጥ ፡ መኾ
ኑን ፡ እንድታውቅ ፡ መለስነው ፤
ግን ፡ አብዛኞቻቸው ፡ አያውቁም።
14 ብርታቱንም ፡ በደረሰና ፡ በተስተ
ካከለ ፡ ጊዜ ፡ ጥበብንና ፡ ዕውቀ
ትን ፡ ሰጠነው ፤ እንዲሁም ፡ መል
ካም ፡ ሠሪዎችን ፡ እንመነዳለን ።
15 ከተማይቱንም ፡ ሰዎችዋ ፡ በዝን
ጋቴ ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ ኾነው ፡ ሳሉ ፡
ገባ ፤ በርሷም ፡ ውስጥ ፡ የሚጋደ
ሉን ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ አገኘ ፤
ይህ ፡ ከወገኑ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ከጠ
ላቱ ፡ ነው ፤ ያም ፡ ከወገኑ ፡ የኾ
ነው ፡ ሰው ፡ በዚያ ፡ ከጠላቱ ፡
በኾነው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ እርዳታን ፡
ጠየቀው ፤ ሙሳም ፡ በጡጫ ፡
መታው ፤ ገደለውም ፤ ይህ ፡ ከሰ
ይጣን ፡ ሥራ ፡ ነው ፤ እርሱ ፡
ግልጽ ፡ አሳሳች ፡ ጠላት ፡ ነውና ፡
አለ ።
16 ጌታዬ ፡ ሆይ ! እኔ ፡ ነፍሴን ፡ በደ
ልኩ ፤ ለኔም ፡ ማር ፡ አለ ፤ ለር
ሱም ፡ ምሕረት ፡ አደረገለት ፤
እርሱ ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።
17 ጌታዬ ፡ ሆይ ! በኔ ፡ ላይ ፡ በመለገ
ስህ ፡ ይኹንብኝ ፡ (ከስሕተቴ ፡
እጸጸታለሁ) ፤ ለአመጠኞችም ፡
ፈጽሞ ፡ረዳት ፡ አልኾንም ፡ አለ ።
18 በከተማይቱም ፡ ውስጥ ፡ ፈሪ ፡
የሚጠባበቅ ፡ ኾኖ ፡ አደረ ፤ በድ
ንገትም ፡ ያ ፡ ትላንት ፡ እርዳታን ፡
የጠየቀው ፡ ሰው ፡ በጩኸት ፡
እርዳታን ፡ ይጠይቀዋል ፤ ሙሳ ፡
ለርሱ ፡— አንተ ፡ በእርግጥ ፡
ግልጽ ፡ ጠማማ ፡ ነህ ፡ አለው ።
19 (ሙሳ) ፡ ያንን ፡ እርሱ ፡ ለሁለ
ቱም ፡ ጠላት ፡ የኾነውን ፡ ሰው ፡
በኀይል ፡ ሊይዘው ፡ በፈለገም ፡
ጊዜ ፡ ሙሳ ፡ ሆይ ! በትላንትናው፡
ቀን ፡ ነፍስን ፡ እንደ ፡ ገደልክ ፡
ልትገድለኝ ፡ ትፈልጋለህን ? በም
ድር ፡ ላይ ፡ ጨካኝ ፡ መኾንን ፡
እንጅ ፡ ሌላ ፡ አትፈልግም ፤ ከመ
ልካም ፡ ሠሪዎችም ፡ መኾንን ፡
አትፈልግም ፤ አለው ።
20 ከከተማይቱም ፡ ዳርቻ ፡ አንድ ፡
ሰው ፡ እየሮጠ ፡ መጣ ፤ ሙሳ ፡
ሆይ ! ሹማምንቶቹ ፡ ሊገድሉህ ፡
ባንተ ፡ ይመካከራሉና ፡ ውጣ ፤
እኔ ፡ ላንተ ፡ ከመካሪዎች ፡ ነኝና ፡
አለው ።
21 የፈራና ፡ የሚጠባበቅ ፡ ኾኖም ፡
ከርሷ ፡ ወጣ ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ !
ከበደለኞቹ ፡ ሕዝቦች ፡ አድነኝ ፡
አለ ።
22 ወደ ፡ መድየን ፡ አግጣጫ ፡
ፊቱን ፡ ባዞረ ፡ ጊዜም ፡ ጌታዬ ፡
ቀጥተኛውን ፡ መንገድ ፡ ሊመ
ራኝ ፡ እከጅላለሁ ፡ አለ ።
23 ወደ ፡ መድየንም ፡ ውሃ ፡ በመጣ ፡
ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ከሰዎች ፡
ጭፍሮችን ፡ (መንጋዎቻቸውን ፡)
የሚያጠጡ ፡ ኾነው ፡ አገኘ ፤
ከነሱ ፡ በታችም ፡ (ከውሃው ፡
መንጎቻቸውን) ፡ የሚከለክሉን ፡
ሁለት ፡ ሴቶች ፡ አገኘ ፤ ነገራ
ችሁ ፡ ምንድን ፡ ነው ? አላቸው ፤
እረኞቹ ፡ ሁሉ ፡ (መንጋዎቻቸ
ውን) ፡ እስከሚመልሱ ፡ አናጠ

ጣም ፤ አባታችንም ፡ ትልቅ ፡
ሺማግሌ ፡ ነው ፡ አሉት ።
24 ለሁለቱም ፡ አጠጣላቸው ፤ ከዚ
ያም ፡ ወደ ፡ ጥላው ፡ ዞወር ፡ አለ ፤
ጌታዬ ፡ ሆይ ! እኔ ፡ ከመልካም ፡
ነገር ፡ ወደኔ ፡ ለምታወርደው ፡
ፈላጊ ፡ ነኝ ፡ አለ ።
25 ከሁለቱ ፡ አንደኛይቱም ፡ ከሕ
ፍረት ፡ ጋር ፡ የምትኼድ ፡ ኾና ፡
መጣችው ፤ አባቴ ፡ ለኛ ፡ ያጠ
ጣህልንን ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጥህ ፡ ይጠ
ራሃል ፤ አለችው ፤ ወደርሱ ፡ በመ
ጣና ፡ ወሬውን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
በተረከለትም ፡ ጊዜ ፡ አትፍራ ፤
ከበደለኞቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ድነሃል ፡
አለው ።
26 ከሁለቱ ፡ አንደኛይቱም ፡ አባቴ ፡
ሆይ ፡ ቅጠረው ፤ ከቀጠርከው ፡
ሰው ፡ ሁሉ ፡ በላጩ ፡ ብርቱው ፡
ታማኙ ፡ ነውና ፡ አለችው ።
27 ስምንትን ፡ ዓመታት ፡ ልታገለ
ግለኝ ፡ እኔ ፡ ከነዚህ ፡ ሁለት ፡
ሴቶች ፡ ልጆቼ ፡ አንዲቱን ፡
ላጋባህ ፡ እሻለሁ ፤ ዐሥርን ፡
ብትሞላም ፡ ከአንተ ፡ ነው ፤
ባንተ ፡ ላይ ፡ ማስቸገርንም ፡
አልሻም ፤ አላህ ፡ የሻ ፡ እንደ ፡
ኾነ ፡ ከመልካሞቹ ፡ ሰዎች ፡
ኾኜ ፡ ታገኘኛለህ ፡ አለው ።
28 (ሙሳም) ፡ ይህ ፡ (ውለታ) ፡ በኔና ፡
ባንተ ፡ መካከል ፡ (ረጊ) ፡ ነው ፤
ከሁለቱ ፡ ጊዜያቶች ፡ ማንኛው
ንም ፡ ብፈጽም ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ወሰን
ማለፍ ፡ የለም ፤ አላህም ፡ በምን
ለው ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ነው ፡ አለ ።
29 ሙሳም ፡ ጊዜውን ፡ በጨረሰና ፡
ከቤተሰቦቹ ፡ ጋር ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡
ከጡር ፡ ተራራ ፡ ጐን ፡ እሳትን ፡
አየ ፤ ለቤተሰቡ ፡ (እዚህ) ፡ ቆዩ ፤
እኔ ፡ እሳትን ፡ አየሁ ፤ ከርሷ ፡
ወሬን ፡ ወይም ፡ ትሞቁ ፡ ዘንድ ፡
ከእሳት ፡ ትንታግን ፡ አመጣላ
ችኋለሁ ፡ አለ ።
30 በመጣትም ፡ ጊዜ ፡ ከሸለቆው ፡
ቀኝ ፡ ዳርቻ ፡ ከዛፊቱ ፡ በኩል ፡
በተባረከችው ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡
ሙሳ ፡ ሆይ ! እኔ ፡ የዓለማት ፡
ጌታ ፡ አላህ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡
ተጠራ ።
31 በትርህንም ፡ ጣል ፡ (ተባለ) ፤
እንደ ፡ ትንሽ ፡ እባብ ፡ ስትስለ
ከለክ ፡ ባያትም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡
ኋላ ፡ ዞሮ ፡ ሸሸ ፤ አልተመለሰ
ምም ፤ ሙሳ ፡ ሆይ ! ተመለስ ፤
አትፍራም ፤ አንተ ፡ ከጥብቆቹ ፡
ነህና ፡ (ተባለም) ።
32 እጅህን ፡ በአንገትጌህ ፡ ውስጥ ፡
አግባ ፤ ያለ ፡ ነውር ፡ ነጭ ፡ ኾና ፡
ትወጣለችና ፤ ክንፍህንም ፡ ከፍ
ርሃት ፡ (ለመዳን) ፡ ወዳንተ ፡
አጣብቅ ፤ እነዚህም ፡ ከጌታህ ፡
የኾኑ ፡ ወደ ፡ ፈርዖንና ፡ ወደ ፡
መኳንንቶቹ ፡ የሚደርሱ ፡ ሁለት ፡
አስረጅዎች ፡ ናቸው ፤ እነርሱ ፡
አመጠኞች ፡ ሕዝቦች ፡ ነበሩና ።
33 (ሙሳ) ፡ አለ ፡- ጌታዬ ፡ ሆይ !
እኔ ፡ ከነሱ ፡ ነፍስን ፡ ገድያለሁ ፡
ስለዚህ ፡ እንዳይገድሉኝ ፡ እፈ
ራለሁ ፤
34 ወንድሜም ፡ ሃሩን ፡ እርሱ ፡
ምላሱ ፡ ከኔ ፡ የተባ ፡ ነው ፤ እው
ነተኛነቴንም ፡ የሚያረጋግጥልኝ ፡
ረዳት ፡ ኾኖ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ላከው ፡
እኔ ፡ ሊያስተባብሉኝ ፡ እፈራ
ለሁና ።
35 (አላህም) ፡- ጡንቻህን ፡ በወንድ
ምህ ፡ በእርግጥ ፡ እናበረታለን ፤
ለሁለታችሁም ፡ ስልጣንን ፡ እና



ደርጋለን ፡ ወደናንተም ፡ (በመ
ጥፎ) ፡ አይደርሱም ፤ በታምራቶ
ቻችን ፡ (ኺዱ) ፤ እናንተና ፡ የተ
ከተላችሁም ፡ ሁሉ ፡ አሸናፊ
ዎች ፡ ናችሁ ፡ አላቸው ።
36 ሙሳም ፡ በታምራቶቻችን ፡ ግል
ጽ ፡ ኾነው ፡ በመጣባቸው ፡ ጊዜ ፡
ይህ ፡ የተቀጠፈ ፡ ድግምት ፡
እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፤ ይህን
ንም ፡ በመጀመሪያዎቹ ፡ አባቶቻ
ችን ፡ ውስጥ ፡ አልሰማንም ፡ አሉ ።
37 ሙሳም ፡ ጌታዬ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡
በቀጥታው ፡ መንገድ ፡ የመጣ
ውን ፡ ሰው ፡ ምስጉኒቱም ፡ አገር ፡
ለርሱ ፡ የምትኾንለትን ፡ ሰው ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ፤ እነሆ ፡ በደለኞቹ ፡
አይድኑም ፡ አለ ።
38 ፈርዖንም ፡ እናንተ ፡ ጭፍሮች ፡
ሆይ ! ከኔ ፡ ሌላ ፡ ለናንተ ፡ አም
ላክን ፡ ምንም ፡ አላወቅሁም ፤
ሃማንም ፡ ሆይ ! ጭቃን ፡ ለኔ ፡
አቃጥልልኝ ፤ (ጡብ ፡ ሥራልኝ) ፤
ለኔም ፡ ከፍተኛ ፡ሕንጻን ፡ ሥራ
ልኝ ፤ ወደ ፡ ሙሳ ፡ አምላክ ፡
ልወጣ ፡ እከጅላለሁና ፤ እኔም ፡
ከውሸታሞቹ ፡ መኾኑን ፡ እጠረ
ጥረዋለሁ ፡ አለ ።
39 እርሱም ፡ ሰራዊቶቹም ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ ኮሩ ፤
እነርሱም ፡ ወደኛ ፡ የማይመለሱ ፡
መኾናቸውን ፡ ጠረጠሩ ።
40 እርሱንም ፡ ሰራዊቱንም ፡ በጥ
ብቅ ፡ ያዝናቸው ። በባሕርም ፡
ውስጥ ፡ ጣልናቸው ፤ የበደለ
ኞች ፡ መጨረሻም ፡ እንዴት ፡
እንደ ፡ ነበረ ፡ ተመልከት ።
41 ወደ ፡ እሳት ፡ የሚጠሩ ፡ መሪዎ
ችም ፡ አደረግናቸው ፤ በትንሣ
ኤም ፡ ቀን ፡ አይረዱም ።
42 በይህችም ፡ በቅርቢቱ ፡ ዓለም ፡
ውስጥ ፡ እርግማንን ፡ አስከተል
ናቸው ፤ በትንሣኤም ፡ ቀን ፡
እነሱ ፡ ከሚባረሩት ፡ ናቸው ።
43 የፊተኞቹን ፡ የክፍል ፡ ዘመናት ፡
ሕዝቦችም ፡ ከአጠፋን ፡ በኋላ ፡
ለሰዎች ፡ የልብ ፡ ብርሃን ፡ መሪም
እዝነትም ፡ ሲኾን ፡ ይገሠጹ ፡
ዘንድ ፡ ለሙሳ ፡ መጽሐፉን ፡
በእርግጥ ፡ ሰጠነው ።
44 ወደ ፡ ሙሳም ፡ ትእዛዝን ፡ ባወረድ
ንለት ፡ ጊዜ ፡ (ከተራራው) ፡ በም
ዕራባዊው ፡ ጎን ፡ አልነበርክም ፤
ከተጣዱትም ፡ አልነበርክም ።
45 ግን ፡ እኛ ፡ (ከርሱ ፡ ኋላ) ፡ የክ
ፍለ ፡ ዘመናትን ፡ ሰዎች ፡ አስገ
ኘን ፤ በነሱም ፡ ላይ ፡ ዕድሜዎች ፡
ተራዘሙ ፤ በመድየንም ፡ ሰዎች ፡
ውስጥ ፡ ተቀማጭ ፡ በነሱ ፡
ላይ ፡ አንቀጾቻችንን ፡ የምታነብ ፡
አልነበርክም ፤ ግን ፡ እኛ ፡ ላኪ
ዎችህ ፡ ኾን ፤
46 በጠራነውም ፡ ጊዜ ፡ በጡር ፡
ጐን ፡ አልነበርክም ፤ ግን ፡ ከአ
ንተ ፡ በፊት ፡ ምንም ፡ አስፈራሪ ፡
ያልመጣቸውን ፡ ሕዞቦች ፡ ታስ
ፈራራ ፡ ዘንድ ፡ ከጌታህ ፡ በኾነ ፡
ችሮታ ፡ (ላክንህ) ፡ ሊገሠጹ ፡
ይከጀላልና ።
47 እጆቻቸውም ፡ ባሳለፉት ፡ ምክ
ንያት ፡ መከራ ፡ የምትነካቸውና ፡
ጌታችን ፡ ሆይ ! አንቀጾችህን ፡
እንድንከተል ፡ ከምእምናንም ፡
እንድንኾን ፡ ወደኛ ፡ መልክተ
ኛን ፡ አትልክም ፡ ኖሯልን ? የሚ
ሉ ፡ ባልኾኑ ፡ ኖሮ ፡ (አንልክም ፡
ነበር) ።
48 እውነቱም ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ በመጣ
ላቸው ፡ ጊዜ ፡ ለሙሳ ፡ የተሰ

ጠው ፡ ብጤ ፡ አይሰሰጠውም ፡
ኖሯልን ? አሉ ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡
ሙሳ ፡ በተሰጠው ፡ አልካዱምን?
የተረዳዱ ፡ ሁለት ፡ ድግምቶች ፡
ናቸው ፡ አሉ ፤ እኛ ፡ በሁሉም ፡
ከሐዲዎች ፡ ነንም ፡ አሉ ።
49 ከአላህ ፡ ዘንድ ፡ የኾነን ፡ መጽ
ሐፍ ፡ እርሱ ፡ ከሁለቱም ፡ ይበ
ልጥ ፡ ቅን ፡ የኾነን ፡ አምጡ ፤
እውነተኞች ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡
(ብታመጡት) ፡ እከተለዋለሁ ፡
በላቸው ።
50 እሺ ፡ ባይሉህም ፤ (1) ፡ የሚከተ
ሉት ፤ ዝንባሌዎቻቸውን ፡ ብቻ ፡
መኾኑን ፡ ዕወቅ ፤ ከአላህም ፡
የኾነ ፡ መምሪያ ፡ ሳይኖረው ፡
ዝንባሌውን ፡ ከተከተለ ፡ ሰው ፡
ይበልጥ ፡ የጠመመ ፡ አንድም ፡
የለም ፤ አላህ ፡ በደለኞች ፡ ሕዝ
ቦችን ፡ አይመራምና ።
51 ይገሠጹም ፡ ዘንድ ፡ ቃልን ፡ (ቁር
አንን ፡ በያይነቱ) ፡ ለነርሱ ፡ በእ
ርግጥ ፡ አስከታተልን ።
52 እነዚያ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ መጽ
ሐፍን ፡ የሰጠናቸው ፡ እነርሱ ፡
በርሱ ፡ ያምናሉ ።
53 በነሱ ፡ ላይ ፡ በሚነበብላቸውም ፡
ጊዜ ፡ በርሱ ፡ አምነናል ፤ እርሱ ፡
ከጌታችን፡ የኾነ፡ እውነት ፡ ነው ፤
እኛ፡ ከርሱ፡ በፊት፡ ሙስሊሞች፡
ነበርን ፡ ይላሉ ።
54 እነዚያ ፡ በመታገሣቸው ፡ ዋጋ
ቸውን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ይሰሰ
ጣሉ ፤ ክፉውንም ፡ ነገር ፡ በበጎ ፡
ምግባር ፡ ይገፈትራሉ ፤ ከሰጠ
ናቸውም ፡ ሲሳይ ፡ ይለግሳሉ ።
55 ውድቅንም ፡ ቃል ፡ በሰሙ ፡
ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ይርቃሉ ፤ ለኛ ፡
ሥራዎቻችን ፡ አሉን ፤ ለናን
ተም ፡ ሥራዎቻችሁ ፡ አሏችሁ ፤
ሰላም ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ (ይኹን) ፤
ባለጌዎችን ፡ አንፈልግም ፡ ይላሉ፤
56 አንተ ፡ የወደድከውን ፡ ሰው ፡
ፈጽሞ ፡ አታቀናም ፤ ግን ፡ አላህ ፡
የሚሻውን ፡ ሰው ፡ ያቀናል ፤
እርሱም ፡ ቅኖቹን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
57 ከአንተ ፡ ጋር ፡ ቅንን ፡ መንገድ ፡
ብንከተል ፡ ከምድራችን ፡ እንባ
ረራለን ፡ አሉም ፤ ከኛ ፡ ዘንድ ፡
(የተሰጠ) ፡ ሲሳይ ፡ ሲኾን ፡ የነ
ገሩ ፡ ሁሉ ፡ ፍሬዎች ፡ ወደርሱ ፡
የሚነዱበትን ፡ ጸጥተኛ ፡ ክልል ፡
(መካን) ፡ ለነሱ ፡ አላስመቸናቸ
ውምን ? ግን ፡ አብዛኞቻቸው ፡
አያውቁም ።
58 ከከተማም ፡ ኑሮዋን ፡ (ምቾት
ዋን) ፡ የካደችን ፡ (ከተማ) ፡ ያጠ
ፋናት ፡ ብዙ ፡ ናት ፤ እነዚህም ፡
ከነሱ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡
እንጅ ፡ ያልተኖረባቸው ፡ ሲኾኑ፡
መኖሪያዎቻቸው ፡ ናቸው ፤ እኛ
ም ፡ (ከነሱ) ፡ ወራሾች ፡ ነበርን ።
59 ጌታህም ፡ ከተሞችን ፡ በዋናዋ ፡
(ከተማ) ፡ ውስጥ ፡ አንቀጾቻች
ንን ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ የሚያነብ ፡
መልክተኛን ፡ እስከሚልክ ፡ ድ
ረስ ፡ አጥፊ ፡ አልነበረም ፤ ከተ
ሞችንም ፡ ባለ ፡ ቤቶችዋ ፡ በዳ
ዮች ፡ ኾነው ፡ እንጅ ፡ አጥፊ
ዎች ፡ አልነበርንም ።
60 ከማንኛውም ፡ ነገር ፡ የተሰጣ
ችሁት ፤ የቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡
ጥቅምና ፡ ጌጧ ፡ ነው ፤ አላህ ፡
ዘንድ ፡ ያለውም ፡ (ምንዳ) ፡
በጣም ፡ በላጭና ፡ ዘውታሪ ፡
ነው ፤ አታውቁምን ?

1 መጽሐፉን ፡ ባያምኑ ።



61 መልካምን ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡ የገ
ባንለትና ፡ እርሱም ፡ አግኚው ፡
የኾነ ፡ ሰው ፡ የቅርቢቱን ፡ ሕይ
ወት ፡ ጥቅም ፡ እንዳስመቸነውና፡
ከዚያም ፡ እርሱ ፡ በትንሣኤ ፡
ቀን ፡ (ለእሳት) ፡ ከሚቀረቡት ፡
እንደ ፡ ኾነው ፡ ሰው ፡ ነውን ?
62 (አላህ) ፡ የሚጠራባቸውንና ፡
እነዚያ ፡ ተጋሪዎቼ ፡ ትሉዋቸው ፡
የነበራችሁት ፡ የት ፡ ናቸው ?
የሚልበትን ፡ ቀን ፡ (አስታውስ)።
63 እነዚያ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ቃሉ ፡
የተረጋገጠባቸው ፡ ይላሉ ፡—ጌታ
ችን ፡ ሆይ ፡ እነዚህ ፡ እነዚያ ፡
ያጠመምናቸው ፡ ናቸው ፤ እንደ ፡
ጠመምን ፡ አጠመምናቸው ፤
(ከነሱ) ፡ ወዳንተ ፡ ተጥራራን ፤
(1) እኛን ፡ ይግገዙ ፡ አልነበሩም።
64 (ለአላህ) ፡ የምታጋሩዋቸውንም ፡
ጥሩ ፡ ይባላሉ ፤ ይጠሩዋቸዋልም፤
ግን ፡ ለነርሱ ፡ አይመልሱላቸ
ውም ፤ ቅጣቱንም ፡ ያያሉ ፤
እነሱ ፡ ይመሩ ፡ በነበሩ ፡ ኖሮ ፡
(አያዩትም ፡ ነበር) ።
65 የሚጠራባቸውንና ፡ ለመልክተ
ኞቹም ፡ ምንን ፡ መለሳችሁ ፡
የሚልበትን ፡ ቀን ፡ (አስታውስ)።
66 በዚያም ፡ ቀን ፡ ወሬዎቹ ፡ ሁሉ ፡
በነርሱ ፡ ላይ ፡ ይሰውሩባቸዋል ፤
እነሱም ፡ አይጠያየቁም ።
67 የተጸጸተና ፡ ያመነ ፡ ሰውማ ፡
መልካምንም ፡ የሠራ ፡ ከሚድ
ኑት ፡ ሊኾን ፡ ይከጀላል ።
68 ጌታህም ፡ የሚሻውን ፡ ይፈጥ
ራል ፤ ይመርጣልም ፤ ለነሱ ፡
(ለሰዎቹ) ፡ ምርጫ ፡ የላቸውም ፤
አላህ፡ ከማይግገባው፡ ሁሉ፡ ጠራ፤
ከሚያጋሩዋቸውም ፡ ላቀ ።
69 ጌታህም ፡ ልቦቻቸው ፡ የሚደብ
ቁትንና ፡ የሚገልጹትን ፡ ሁሉ ፡
ያውቃል ።
70 እርሱም ፡ አላህ ፡ ነው ፤ ከርሱ ፡
ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ ምስጋና ፡
በመጀመሪያይቱም ፡ በመጨረሻ
ይቱም ፡ ዓለም ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡
ነው ፤ ፍርዱም ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡
ነው ፤ ወደርሱም ፡ ትመለሳላ
ችሁ ።
71 አያችሁን ? (ንገሩኝ) ፡ አላህ ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ ሌሊትን ፡ እስከ ፡
ትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ዘው
ታሪ ፡ ቢያደርገው ፡ ከአላህ ፡
ሌላ ፡ ብርሃንን ፡ የሚያመጣላ
ችሁ ፡ አምላክ ፡ ማነው ? አትሰ
ሙምን ? በላቸው ።
72 አያችሁን ? አላህ ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ ቀንን ፡ እስከ ፡ ትንሣኤ ፡
ቀን ፡ ድረስ ፡ ዘውታሪ ፡ ቢያደ
ርገው ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ በውስጡ ፡
የምታርፉበትን ፡ ሌሊት ፡ የሚያ
መጣላችሁ ፡ አምላክ ፡ ማን፡ ነው?
(ንገሩኝ) ፡ አታስተውሉምን ?
በላቸው ።
73 ከችሮታውም ፡ ለናንተ ፡ ሌሊት
ንና ፡ ቀንን ፡ በውስጡ ፡ ልታር
ፉበት ፡ ከትሩፋቱም ፡ ልትፈል
ጉበት ፡ አመስጋኞችም ፡ ልት
ኾኑ ፡ አደረገላችሁ ።
74 የሚጠራባቸውንም ፡ ቀንና ፡ እነ
ዚያ ፡ ተጋሪዎቼ ፡ ትሉዋቸው ፡
የነበራችሁት ፡ የት ፡ ናቸው ?
የሚልበትን ፡ (አስታውስ) ፤
75 ከሕዝቦችም ፡ ሁሉ ፡ መስካሪን ፡
እናወጣለን፤ (ያን፡ ጊዜ)፡ እውነተ

1 ከነሱ ፡ ንጹሕነታችንን ፡ ለአንተ ፡ እንገል
ጻለን ።

ኛውም ፡ አምላክነት ፡ ለአላህ ፡
ብቻ ፡ መኾኑን ፡ ያውቃሉ ፤
ይቀጣጥፉት ፡ የነበሩትም ፡ ከነሱ፡
ይጠፋቸዋል ።
76 ቃሩን ፡ ከሙሳ ፡ ነገዶች ፡ ነበር ፤
በነርሱም ፡ ላይ ፡ አመጠ ፤ ከድ
ልቦችም ፡ ያንን ፡ መከፈቻዎቹ ፡
ብቻ ፡ የኃይል ፡ ባለቤቶች ፡
የኾኑ ፡ ጭፍሮችን ፡ (ሸክሙ) ፡
የሚከብድን ፡ ሰጠነው ፤ ወገ
ኖቹ ፡ ለርሱ ፡ አትኩራ ፤ አላህ ፡
ኩራተኞችን ፡ አይወድምና ፡
ባሉት ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ።
77 አላህም ፡ በሰጠህ ፡ ሀብት ፡ የመ
ጨረሻይቱን ፡ አገር ፡ ፈልግ ፤
ከቅርቢቱም ፡ ዓለም ፡ ፋንታህን ፡
አትርሳ ፤ አላህም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡
መልካምን ፡ እንዳደረገልህ ፡ (ለሰ
ዎች) ፡ መልካምን ፡ አድርግ ፤
በምድርም ፡ ውስጥ ፡ ማጥፋትን ፡
አትፈልግ ፤ አላህ ፡ አጥፊዎችን ፡
አይወድምና ፡ (አሉት) ።
78 (ሀብቱን) ፡-የተሰጠሁት ፡ እኔ ፡
ዘንድ ፡ ባለው ፡ ዕውቀት ፡ ብቻ ፡
ነው ፡ አለ ፤ አላህ ፡ ከርሱ ፡ በፊት፡
ከክፍለ ፡ ዘመናት ፡ ሰዎች ፡ በኀ
ይል ፡ ከርሱ ፡ ይበልጥ ፡ የበረቱ
ትን ፡ (ሀብትን) ፡ በመሰብሰብም፡
ይበልጥ ፡ የበዙትን ፡ በእርግጥ ፡
ያጠፋ ፡ መኾኑን ፡ አያውቅምን ?
አመጠኞችም ፡ ከኀጢአቶቻቸው፡
(ምሕረት ፡ የሚከተለውን ፡ ጥ
ያቄ) ፡ አይጠየቁም ።
79 በሕዝቦቹም ፡ ላይ ፡ በጌጡ ፡ ው
ስጥ ፡ ኾኖ ፡ ወጣ ፤ እነዚያ ፡ ቅር
ቢቱን ፡ ሕይወት ፡ የሚፈልጉት ፡
ወይ ፡ ምኞታችን ! ቃሩን ፡ የተ
ሰጠው ፡ ብጤ ፡ ምነው ፡ ለኛ ፡
በኖረን ፤ እርሱ ፡ የታላቅ ፡ ዕድ
ል ፡ ባለቤት ፡ ነውና ፡ አሉ ።
80 እነዚያም ፡ ዕውቀትን ፡ የተሰ
ጡት ፡— ወዮላችሁ ! የአላህ ፡
ምንዳ ፡ ለአመነ ፡ ሰው ፡ መልካ
ምንም ፡ ለሠራ ፡ በላጭ ፡ ነው ፤
ታጋሾችም ፡ እንጅ ፡ ሌላው ፡
አያገኛትም ፡ አሉ ።
81 በርሱም ፡ በቤቱም ፡ ምድርን ፡
ደረባን ፤ ለርሱም ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡
የሚረዱት ፡ ጭፍሮች ፡ ምንም ፡
አልነበሩትም ፤ ከሚርረዱትም ፡
አልነበረም ።
82 እነዚያም ፡ በትላንትናው ፡ ቀን ፡
ስፍራውን ፡ ይመኙ ፡ የነበሩት ፡
ወይ ፡ጉድ ! ለካ ፡ አላህ ፡ ከባ
ሮቹ ፡ ለሚሻው ፡ ሰው ፡ ሲሳይን ፡
ያሰፋል ፤ ያጠባልም ፤ አላህ ፡
በኛ ፡ ላይ ፡ (በእምነት) ፡ ባልለ
ገሰልን ፡ኖሮ ፡ ምድርን ፡ በኛ ፡
ላይ ፡ በገለበጠብን ፡ ነበር ፤ ወይ ፡
ጉዱ ! ከሓዲዎች ፡ አይድኑም ፡
የሚሉ ፡ ኾነው ፡ አነጉ ።
83 ይህች ፡ የመጨረሻይቱ ፡ አገር ፡
ለነዚያ ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ኩራ
ትንና ፡ ማመጥን ፡ ለማይፈልጉት፡
እናደርጋታለን ፤ ምስጉኒቱም ፡
መጨረሻ ፡ ለጥንቁቆቹ ፡ ናት ።
84 በደግ ፡ ሥራ ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡
ለርሱ ፡ ከርሷ ፡ በላጭ ፡ ምንዳ ፡
አለው ፤ በክፉም ፡ ሥራ ፡ የመጡ፡
ሰዎች ፡ እነዚያ ፡ መጥፎዎችን ፡
የሠሩ ፡ ይሠሩት ፡ የነበሩትን ፡
እንጅ ፡ አይመነዱም ።
85 ያ ፡ ቁርአንን ፡ የተከፋፈለ ፡ ኾኖ ፡
ባንተ ፡ ላይ ፡ ያወረደው ፡ (አም
ላክ) ፡ ወደ ፡ መመለሻ ፡ (ወደ ፡
መካ) ፡ በእርግጥ ፡ መላሺህ ፡ ነው፤



ጌታዬ ፡ በቅን ፡ መንገድ ፡ የመ
ጣውን ፡ ሰውና ፡ እርሱም ፡ በግ
ልጽ ፡ ስሕተት ፡ ውስጥ ፡ የኾነ
ውን ፡ ሰው ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፡ በላ
ቸው ።
86 መጽሐፉ ፡ ወዳንተ ፡ መወረዱን ፡
ተስፋ ፡ የምታደርግ ፡ አልነበር
ክም ፤ ግን ፡ ከጌታህ ፡ ችሮታ ፡
(ተወረደልህ) ፤ ለከሓዲዎችም ፡
በፍጹም ፡ ረዳት ፡ አትኹን ።
87 ከአላህም ፡ አንቀጾች ፡ ወዳንተ ፡
ከተወረዱ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ አያ
ግዱህ ፤ ወደ ፡ ጌታህም ፡ (ሰዎ
ችን) ፡ ጥራ ፤ ከአጋሪዎቹም ፡ አት
ኹን ፤
88 ከአላህም ፡ ጋር ፡ ሌላን ፡ አም
ላክ ፡ አትግገዛ ፤ ከርሱ ፡ በቀር ፡
አምላክ ፡ የለም ፤ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡
ከአላህ ፡ በቀር ፡ ጠፊ ፡ ነው ፤
ፍርዱ ፡ የርሱ ፤ ብቻ ፡ ነው ፤
ወደርሱም ፡ ትመለሳላችሁ ።

## ምዕራፍ ፡ 29 ፡ አል-ዐንከቡት ። ክፍል ፡ 20 ።

29ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ዐንከቡት ፡ (የሸረሪት ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 69 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው፡
1 አ. ለ. መ. (አሊፍ ፡ ላም ፡ ሚም)፡
2 ሰዎቹ ፡ አምነናል ፡ በማለታቸው፡
ብቻ ፡ እነሱ ፡ ሳይፈተኑ ፡ የሚ
ትተዉ ፡ መኾናቸውን ፡ ጠረ
ጠሩን ?
3 እነዚያንም ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡
የነበሩትን ፡ በእርግጥ ፡ ፈትነ
ናል ፤ እነዚያንም ፡ እውነት ፡ የተ
ናገሩትን ፡ አላህ ፡ በእርግጥ ፡
ያውቃል ፤ ውሸታሞቹንም ፡ ያው
ቃል ።
4 ይልቁንም ፡ እነዚያ ፡ መጥፎዎ
ችን ፡ ሥራዎች ፡ የሚሠሩት ፡
ሊያመልጡን ፡ ይጠረጥራሉን ?
ያ ፡ የሚፈርዱት ፡ (ፍርድ) ፡
ከፋ ።
5 የአላህን ፡ መገናኘት ፡ ተስፋ ፡
የሚያደርግ ፡ ሰው ፡ (ይዘጋጅ) ፤
የአላህ ፡ ቀጠሮ ፡ በእርግጥ ፡
መጪ ፡ ነውና ፤ እርሱም ፡ ሰሚው
ዐዋቂው ፡ ነው ።
6 የታገለ ፡ ሰውም ፡ የሚታገለው ፡
ለነፍሱ ፡ ነው ፤ አላህ ፡ ከዓለማት፡
በእርግጥ ፡ ተብቃቂ ፡ ነውና ።
7 እነዚያም ፡ ያመኑ ፤ መልካሞች
ንም ፡ የሠሩ ፡ መጥፎዎቹን ፡ ሥራ
ዎቻቸውን ፡ ከነሱ ፡ ላይ ፡ እናብ
ሰላቸዋለን ፤ በዚያም ፡ ይሠሩት ፡
በነበሩት ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ በእ
ርግጥ ፡ እንመነዳቸዋለን ።
8 ሰውንም ፡ በወላጆቹ ፡ መልካም ፡
አድራጎትን ፡ አዘዝነው ፤ ላን
ተም ፡ በርሱ ፡ ዕውቀት ፡ የሌለ
ህን ፡ (ጣዖት) ፡ በእኔ ፡ እንድታ
ጋራ ፡ ቢታገሉህ ፡ አትታዘዛ

ቻው ፤ መመለሻችሁ ፡ ወደኔ ፡
ነው ፤ ትሠሩት ፡ የነበራችሁት
ንም ፡ ሁሉ ፡ እነግራችኋለሁ ።
9 እነዚያም ፡ ያመኑ ፤ መልካም ፡
ሥራዎችንም ፡ የሠሩ ፡ በደጋ
ጎቹ ፡ ውስጥ ፡ በእርግጥ ፡ እናገ
ባቸዋለን ።
10 ከሰዎችም ፡ በአላህ ፡ አመንን ፡
የሚል ፡ ሰው ፡ አለለ ፤ በአላህም ፡
(በማመኑ) ፡ በተሰቃዬ ፡ ጊዜ ፡
የሰዎችን ፡ ማሰቃየት ፡ እንደ ፡
አላህ ፡ ቅጣት ፡ ያደርጋል ፤ ከጌ
ታህም፡ እርዳታ፡ ቢመጣ፥ እኛ፡
በእርግጥ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ነበርን፡
ይላሉ ፤ አላህ ፡ በዓለማት ፡
ሕዝብ ፡ ልቦች ፡ ውስጥ ፡ ያለ
ውን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ አይደለ
ምን ?
11 አላህም ፡ እነዚያን ፡ ያመኑትን ፡
በእርግጥ ፡ ያውቃል ፤ መናፍቆቹ
ንም ፡ ያውቃል ።
12 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡ ለነ
ዚያ ፡ ላመኑት ፡ መንገዳችንን ፡
ተከተሉ ፤ ኀጢአቶቻችሁንም ፡
እንሸከማለን ፡ አሉ ፤ እነሱም ፡
ከኀጢአቶቻቸው ፡ ምንንም ፡ ተሸ
ካሚዎች ፡ አይደሉም ፤ እነርሱ ፡
በእርግጥ ፡ ውሸታሞች ፡ ናቸው ።
13 ሸክሞቻቸውንና ፡ ከሸክሞቻቸው፡
ጋር ፡ (ሌሎች) ፡ ሸክሞችንም ፡
በእርግጥ ፡ ይሸከማሉ ፤ በትንሣ
ኤም ፡ ቀን ፡ ይቀጥፉት ፡ ከነበ
ሩት ፡ በእርግጥ ፡ ይጠየቃሉ ።
14 ኑሕንም ፡ ወደ ፡ ሕዝቦቹ ፡ በእር
ግጥ ፡ ላክነው ፤ በውስጣቸውም ፡
ሺሕ ፡ ዓመትን ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡
ሲቀር ፡ ተቀመጠ ፤ እነርሱ ፡ በዳ
ዮች ፡ ኾነው ም ፡ የውሃው ፡ ማጥ
ለቅለቅ ፡ ያዛቸው ።
15 ኑሕንና ፡ የመርከቢቱንም ፡ ጓዶች ፡
አዳናቸው ፤ እርሷንም ፡ ለዓለማት ፡
ታምር ፡ አደረግናት ።
16 ኢብራሂምንም ፡ ለሕዝቦቹ ፡ ባለ ፡
ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፡— አላህን ፡
ተገዙ ፤ ፍሩትም ፤ ይሃችሁ ፡ የም
ታውቁ ፡ ብትኾኑ ፡ ለናንተ ፡
በላጭ ፡ ነው ።
17 ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የምትግገዙት ፡
ጣዖታትን ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ውሸት
ንም ፡ ትቀጣጥፋላችሁ ፤ እነዚያ ፡
ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የምትግገዙዋቸው ፡
ለናንተ ፡ ሲሳይን ፡ ሊሰጧችሁ ፡
አይችሉም ፤ ስለዚህ ፡ ሲሳይን ፡
ከአላህ ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ፈልጉ ፤
ተገዙትም ፤ ለርሱም ፡ አመስግኑ ፤
ወደርሱ ፡ ትመለሳላችሁ ።
18 ብታስተባብሉም ፡ ከፊታችሁ ፡
የነበሩት ፡ ሕዝቦች ፡ በእርግጥ ፡
አስተባብለዋል ፤ በመልክተኛ
ውም ፡ ላይ ፡ ግልጽ ፡ ማድረስ ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ የለበትም ።
19 አላህ ፡ መፍጠርን ፡ እንዴት ፡ እን
ደሚጀምር ፡ ከዚያም ፡ እንዴት ፡
እንደሚመልሰው ፡ አይመለከቱ
ምን? ይህ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ቀላል ፡
ነው ።
20 ፡—በምድር ፡ ላይ ፡ ኺዱ ፤ መፍጠ
ርንም ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ጀመረ ፡
ተመልከቱ ፤ ከዚያም ፤ አላህ ፡
የመጨረሻይቱን ፡ መነሳት ፡ ያስ
ነሳል ፤ አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ፡
ቻይ ፡ ነውና ፡ በላቸው ።
21 የሚሻውን ፡ ሰው ፡ ይቀጣል ፤
የሚሻውንም ፡ ሰው ፡ ያዝንለ
ታል ፤ ወደርሱም ፡ ትመለሳላችሁ፤
22 እናንተም ፡ በምድርም ፡ ኾነ ፡
በሰማይ ፡ የምታቅቱ ፡ አይደላ



ችሁም ፤ ከአላህም ፡ ሌላ ፡ ረዳ
ትም ፡ ተከላካይም ፡ ምንም ፡ የላ
ችሁም ።
23 እነዚያም ፡ በአላህ ፡ አንቀጾችና ፡
በመገናኘቱ ፡ የካዱ ፡ እነዚያ ፡
ከእዝነቴ ፡ ተስፋን ፡ ቆረጡ ፤ እነዚ
ያም ፡ ለነሱ ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡
አላቸው ።
24 የሕዝቦቹም ፡ (1) መልስ ፡— ግደ
ሉት ፤ ወይም ፡ አቃጥሉት ፡ ማ
ለት ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አልነበረም ፤
ከእሳቲቱም ፡ አላህ ፡ አዳነው ፤
በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ለሚያምኑ ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ታምራቶች ፡ አሉበት ።
25 (ኢብራሂም) ፡ አለም ፡— ከአላህ ፡
ሌላ ፡ ጣዖታትን ፡ (አማልክት) ፡
የያዛችሁት ፡ በቅርቢቱ ፡ ሕይ
ወት ፡ በመካከላችሁ ፡ ለመዋ
ደድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ከዚያም ፡
በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ከፊላችሁ ፡
በከፊሉ ፡ ይክዳል ፤ ከፊላችሁም ፡
ከፊሉን ፡ ይረግማል ፤ መኖሪያች
ሁም ፡ እሳት ፡ ናት ፤ ለናንተም ፡
ከረዳቶች ፡ ምንም ፡ የላችሁም ።
26 ሉጥም ፡ ለርሱ ፡ አመነ ፤ (ኢብ
ራሂም) ፡—እኔ ፡ ወደ ፡ ጌታዬ ፡
ተሰዳጅ ፡ ነኝ ፤ እነሆ ፡ እርሱ ፡
አሸናፊው ፡ ጥበበኛው ፡ ነውና ፡
አለም ።
27 ለርሱም ፡ ኢስሐቅንና ፡ ያዕቆ
ብን ፡ ሰጠነው ፤ በዘሩም ፡ ውስጥ ፡
ነቢይነትንና ፡ መጽሐፍን ፡ አደ
ረግን ፤ ምንዳውንም ፡ በቅርቢቱ ፡
ዓለም ፡ ሰጠነው ፤ (2) እርሱም ፡
በመጨረሻይቱ ፡ ዓለም ፡ ከደ
ጋጎቹ ፡ ነው ።
28 ሉጥንም ፡ ለሕዝቦቹ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ) ፡ —እናንተ ፡ ጠያ
ፍን ፡ ሥራ ፡ ትሠራላችሁን ?
በርሷ ፡ ከዓለማት ፡ አንድም ፡
አልቀደማችሁም ፤
29 እናንተ ፡ በእርግጥ ፡ ወንዶችን ፡
ትመጣላችሁን ? መንገድንም ፡
ትቆርጣላችሁን ? በሸንጓችሁም ፡
የሚነወርን ፡ ነገር ፡ ትሠራላች
ሁን ? (አላቸው) ፤ የሕዝቦቹም ፡
መልስ ፡ ከውነተኞቹ ፡ እንደ ፡
ኾንክ ፡ የአላህን ፡ ቅጣት ፡ አም
ጣብን ፡ ማለት ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡
አልነበረም ።
30 ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ በአመጠኞች ፡
ሕዝቦች ፡ ላይ ፡ እርዳኝ ፡ አለ ።
31 መልክተኞቻችንም ፡ ኢብራሂምን
በብስራት ፡ በመጡት ፡ ጊዜ ፡
እኛ ፡ የዚችን ፡ ከተማ ፡ ሰዎች ፡
አጥፊዎች ፡ ነን ፤ ሰውዎችዋ ፡
በዳዮች ፡ ነበሩና ፡ አሉት ።
32 በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ሉጥ ፡ አለለ ፡
እኮ ፡ አላቸው ፤ እኛ ፡ በውስጧ ፡
ያለውን ፡ ይበልጥ ፡ ዐዋቂ ፡ ነን ፤
(እርሱን) ፡ በእርግጥ ፡ እናድነ
ዋለን ፤ ቤተሰቦቹንም ፡ ጭምር ፤
ሚስቱ ፡ ብቻ ፡ ስትቀር ፤ እርሷ ፡
በጥፋቱ ፡ ውስጥ ፡ ከሚቀሩት ፡
ናት ፡ አሉት ።
33 መልክተኞቻችንም ፡ ሉጥን ፡
በመጡት ፡ ጊዜ ፡ በነሱ ፡ ምክ
ንያት ፡ አዘነ ፤ በነርሱም ፡ ልቡ ፡
ተጨነቀ ፤ አትፍራ ፤ አትዘንም ፤
እኛ ፡ አዳኞችህ ፡ ነን ፤ ቤተሰቦ
ችህንም ፤ ሚስትህ ፡ ብቻ ፡ ስት
ቀር ፤ እርሷ ፡ በጥፋቱ ፡ ውስጥ ፡
ከቀሪዎቹ ፡ ናት ፡ አሉትም ።
34 እኛ ፡ በይህች ፡ ከተማ ፡ ሰዎች ፡
ላይ ፡ ያምጡ ፡ በነበሩት ፡ ምክ

---

1 የኢብራሂም ፡ ሕዝቦች ፡ መልስ ።
2 ማንኛውም ፡ ባለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይወደዋል ፡
ያወድሰዋል ።

ንያት ፡ ከሰማይ ፡ ቅጣትን ፡ አው
ራጆች ፡ ነን ።
35 በእርግጥም ፡ ለሚያስቡ ፡ ሰዎች ፡
ከርሷ ፡ ግልጽ ፡ ምልክትን ፡
ተውን ፡ (አስቀረን) ።
36 ወደ ፡ መድየንም ፡ ወንድማቸ
ውን ፡ ሹዐይብን ፡ (ላክን ፤)ሕዝ
ቦቼ ፡ ሆይ ! አላህን ፡ ተገዙ ፤
የመጨረሻውንም ፡ ቀን ፡ ፍሩ ፤
በምድርም ፡ ውስጥ ፡ የምታጠ
ፉ ፡ ኾናችሁ ፡ አታበላሹ ፡ አላ
ቸውም ።
37 አስተባበሉትም ፤ የምድር ፡ መን
ቀጥቀጥም ፡ ያዘቻቸው ፤ ባገራ
ቸውም ፡ ውስጥ ፡ ተንከፍርረው ፡
አነጉ ።
38 ዓድንና ፡ ሠሙድንም ፡ (አጠፋን)፤
ከመኖሪያዎቻቸውም ፡ (ፍርራሾች
በኩል ፡ መጥፋታቸው) ፡ ለናንተ፡
በውነት ፡ ተገለጠላችሁ ፤ ሰይ
ጣንም ፡ ሥራዎቻቸውን፡ ለነ
ርሱ ፡ ሸለመላቸው ፤ ከመንገ
ድም ፡ አገዳቸው ፤ የማስተዋልም፡
ባለ ፡ ቤቶች ፡ ነበሩ ፤ (ግን ፡ አላስ
ተዋሉም) ።
39 ቃሩንንም ፡ ፊርዖንንም ፡ ሃማ
ንንም ፡ (አጠፋን) ፤ ሙሳም ፡
በታምራቶች ፡ በእርግጥ ፡ መጣባ
ቸው ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ ኮሩ ፤
አምላጪዎችም ፡ አልነበሩም ።
40 ሁሉንም ፡ በኀጢአቱ ፡ ያዝነው ፤
ከነሱም ፡ ውስጥ፡ ጠጠርን፡ ያዘለ፡
ነፋስን ፡ የላክንበት ፡ አልለ ፡ ከነ
ሱም ፡ ውስጥ ፡ ጩኸት ፡ የያዘ
ችው ፡ አልለ ፤ ከነሱም ፡ ውስጥ ፡
በርሱ ፡ ምድርን ፡ የደረባንበት ፡
አልለ ፤ ከነሱም ፡ ውስጥ ፡ ያሰጠ
ምነው ፡ አልለ ፤ አላህም ፡ የሚበድ
ላቸው ፡ አልነበረም ፤ ግን ፡ ነፍሶ
ቻቸውን ፡ የሚበድሉ ፡ ነበሩ ።
41 የነዚያ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ረዳቶ
ችን ፡ (ጣዖታትን) ፡ የያዙ ፡ ሰዎች
ምሳሌ ፡ ቤትን ፡ እንደ ፡ ሠራች ፡
ሸረሪት ፡ ብጤ ፡ ነው ፤ ከቤቶ
ችም ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ደካማው ፡
የሸረሪት ፡ ቤት ፡ ነው ፤ ቢያውቁ ፡
ኖሮ ፡ (አማልክት ፡ አድርገው ፡
አይግገዟቸውም ፡ ነበር) ።
42 አላህ ፡ ያንን ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ የሚ
ግገዙትን ፡ ማንኛውንም ፡ ያው
ቃል ፤ እርሱም ፡ አሸናፊው ፡
ጥበበኛው ፡ ነው ።
43 እነዚህንም ፡ ምሳሌዎች ፡ ለሰ
ዎች ፡ እንገልጻቸዋለን ፤ ከሊቃ
ውንቶቹም ፡ በስተቀር ፡ ሌሎቹ ፡
አያውቋትም ።
44 አላህ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡
እውነተኛ ፡ ኾኖ ፡ ፈጠረ ፤ በዚህ ፡
ውስጥ ፡ ለምእምናን ፡ ታምር ፡
አለበት ።

★ ★ ★

45 ከመጽሐፉ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ የተ
ወረደውን ፡ አንብብ ፤ ሶላትንም ፡
ደንቡን ፡ ጠብቀህ ፡ ስገድ ፤
ሶላት ፡ ከመጥፎና ፡ ከሚጠላ ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ትከለክላለችና ፤
አላህንም ፡ ማውሳት ፡ ከሁሉ ፡
ነገር ፡ በላጭ ፡ ነው ፤ አላህም ፡
የምትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል ።
46 የመጽሐፉን ፡ ባለ ፡ ቤቶችም ፡
በዚያች ፡ እርሷ ፡ መልካም ፡ በኾነ
ችው ፡ ክርክር ፡ እንጂ ፡ አትከራ
ከሩ ፤ ከነሱ ፡ እነዚያን ፡ የበደሉ
ትን ፡ ሲቀር ፤ በሉም ፡— በዚያ ፡
ወደኛ ፡ በተወረደው ፡ ወደናን
ተም ፡ በተወረደው ፡ አመንን ፤



አምላካችንም ፡ አምላካችሁም ፡
አንድ ፡ ነው ፤ እኛም ፡ ለርሱ ፡
ታዛዦች ፡ ነን ።
47 እንደዚሁም ፡ ወዳንተ ፡ መጽሐ
ፍን ፡ አወረድን ፤ እነዚያም ፡ መጽ
ሐፍን ፡ የሰጠናቸው ፤ በርሱ ፡
ያምናሉ ፤ ከነዚህም ፡ (ከመካ ፡
ሰዎች) ፡ በርሱ ፡ የሚያምኑ ፡
አልሉ ፤ በታምራቶቻችንም ፡ ከሓ
ዲዎቹ ፡ እንጂ ፡ ማንም ፡ አይክ
ድም ።
48 ከርሱ ፡ በፊትም ፡ መጽሐፍን ፡
የምታነብ ፡ በቀኝህም ፡ የምትጽ
ፈው ፡ አልነበርክም ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡
አጥፊዎቹ ፡ በእርግጥ ፡ በተጠራ
ጠሩ ፡ ነበር ።
49 አይደለም ፡ እርሱ ፡ (ቁርአን) ፡
በነዚያ ፡ ዕውቀትን ፡ በተሰጡት ፡
ሰዎች ፡ ልቦች ፡ ውስጥ ፡ (የጠ
ለቀ) ፡ ግልጾች ፡ አንቀጾች ፡ ነው ፤
በአንቀጾቻችንም ፡ በዳዮቹ ፡ እ
ንጂ ፡ ሌላው ፡ አይክድም ።
50 በርሱ ፡ ላይም ፡ ከጌታው ፡ ዘንድ ፡
ታምራቶች ፡ ለምን ፡ አልተወረ
ዱም ፡ አሉ ፤ ታምራቶች ፡ አላህ ፡
ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፤ እኔም ፡
ግልጽ ፡ አስፈራሪ ፡ ብቻ ፡ ነኝ ፡
በላቸው ።
51 እኛ ፡ መጽሐፉን ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
የሚነበብ ፡ ኾኖ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡
ማውረዳችን ፡ አይበቃቸውምን ?
በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ለሚያምኑ ፡
ሕዝቦች ፡ ችሮታና ፡ ግሣጼ ፡
አለበት ።
52 በኔና ፡ በናንተ ፡ መካከል ፡ መስ
ካሪ ፡ በአላህ ፡ በቃ ፤ በሰማያትና ፡
በምድርም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ያው
ቃል ፡ በላቸው ፤ እነዚያም ፡ በብ
ላሽ ፡ ነገር ፡ ያመኑ ፡ በአላህም ፡
የካዱ ፡ እነዚያ ፡ እነሱ ፡ ከሳሪ
ዎች ፡ ናቸው ።
53 በቅጣትም ፡ ያስቸኩሉሃል ፤ የተ
ወሰነም ፡ ጊዜ ፡ ባልነበረ ፡ ኖሮ ፡
ቅጣቱ ፡ በመጣባቸው ፡ ነበር ፤
እነሱ ፡ የማያውቁ ፡ ሲኾኑም ፡
በድንገት ፡ በእርግጥ ፡ ይመጣባ
ቸዋል ።
54 በቅጣት ፡ ያስቸኩሉሃል ፤ ገሀነ
ምም ፡ በከሓዲዎች ፡ በእርግጥ ፡
ከባቢ ፡ ናት ።
55 ቅጣቱ ፡ ከበላያቸው ፡ ከእግሮቻ
ቸውም ፡ ሥር ፡ በሚሸፍናቸው ፡
ቀን ፡ ትሠሩት ፡ የነበራችሁትን ፡
ቅመሱ ፡ በሚላቸውም ፡ (ቀን ፡
ትከባቸዋለች) ።
56 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ባሮቼ ፡
ሆይ ! ምድሬ ፡ በእርግጥ ፡ ሰፊ ፡
ናት ፤ (ብትቸገሩ ፡ ተሰደዱ) ፤
እኔንም ፡ ብቻ ፡ ተገዙኝ ።
57 ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ ሞትን ፡ ቀማሽ ፡
ናት ፤ ከዚያም ፡ ወደኛ ፡ ትመለ
ሳላችሁ ።
58 እነዚያም ፡ ያመኑና ፡ መልካም ፡
ሥራዎችን ፡ የሠሩ ፡ ከገነት ፡
በሥሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈ
ሱባቸውን ፡ ሰገነቶች ፡ በውስጣ
ቸው ፡ ዘውታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ በእ
ርግጥ ፡ እናሰፍራቸዋለን ፤ የሠራ
ተኞች ፡ ምንዳ ፡ ምንኛ ፡ አማረ !
59 (እነሱ) ፡ እነዚያ ፡ የታገሡ ፡ በጌ
ታቸውም ፡ ላይ ፡ የሚመኩ ፡
ናቸው ።
60 ከተንቀሳቃሺም ፡ ምግቧን ፡ ለመ
ሸከም ፡ የማትችለው ፡ ብዙ ፡
ናት ፡ አላህ ፡ ይመግባታል ፤ እና
ንተንም ፡ (ይመግባል) ፤ እርሱ
ሰሚው ፡ ዐዋቂው ፡ ነውና ።

61 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ የፈጠረ ፡
ፀሐይንና ፡ ጨረቃንም ፡ የገራ ፡
ማን ፡ እንደኾነ ፡ ብትጠይቃቸው ፡
በእርግጥ ፡ አላህ ፡ ነው ፡ ይሉሃል ፤
ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ይመለሳሉ ።
62 አላህ ፡ ከባሮቹ ፡ ለሚሻው ፡ ሲሳ
ይን ፡ ያሰፋል ፤ ለርሱም ፡ ያጠ
ባል ፤ አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ዐ
ዋቂ ፡ ነውና ።
63 ከሰማይም ፡ ውሃን ፡ ያወረደና ፡
በርሱም ፡ ምድርን ፡ ከሞተች ፡
በኋላ ፡ ሕያው ፡ ያደረጋት ፡ ማን ፡
እንደ ፡ ኾነ ፡ ብትጠይቃቸው ፡
አላህ ፡ ነው ፡ ይሉሃል ፤ ምስጋና ፡
ለአላህ ፡ ነው ፡ በላቸው ፤ ግን ፡
አብዛኞቻቸው ፡ አያውቁም ።
64 ይህችም ፡ የቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡
መታለያና ፡ ጨዋታ ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አይደለችም ፤ የመጨረሻ
ይቱም ፡ አገር ፡ እርሷ ፡ በእርግጥ ፡
የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ አገር ፡
ናት ፤ የሚያውቁ ፡ ቢኾኑ ፡ ኖሮ ፤
(ጠፊይቱን ፡ ሕይወት ፡ አይመ
ርጡም ፡ ነበር) ።
65 በመርከቦች ፡ ውስጥ ፡ በተሳፈሩ ፡
ጊዜም ፡ አላህን ፡ መግገዛትን ፡
ለርሱ ፡ ብቻ ፡ ያጠሩ ፡ ኾነው ፡
ይጠሩታል ፡ ወደ ፡ የብስ ፡ (በማ
ውጣት) ፡ ባዳናቸው ፡ ጊዜም ፡
ወዲያውኑ ፡ እነርሱ ፡ (ጣዖትን) ፡
ያጋራሉ ።
66 በሰጠናቸው ፡ ጸጋ ፡ ሊክዱና ፡
ሊጠቃቀሙ ፡ (ያጋራሉ) ፤ ወደ
ፊትም ፡ (የሚጠብቃቸውን) ፡
ያውቃሉ ።
67 ሰዎቹ ፡ ከዙሪያቸው ፡ ሲነጠቁ ፡
እኛ ፡ (አገራቸውን) ፡ ጸጥተኛ ፡
ክልል ፡ ማድረጋችንን ፡ አያዩ
ምን ? በውድቅ ፡ ነገር ፡ ያምና
ሉን ? በአላህም ፡ ጸጋ ፡ ይክዳ
ሉን ?
68 በአላህ ፡ ላይም ፡ ውሸትን ፡ ከቀ
ጣጠፈ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ እውነቱ ፡
በመጣለት ፡ ጊዜ ፡ ከአስዋሸ ፡
ይበልጥ ፡ በዳይ ፡ ማነው ? በገሀ
ነም ፡ ውስጥ ፡ ለከሓዲዎች ፡ መኖ
ሪያ ፡ የለምን ?
69 እነዚያም ፡ በኛ ፡ መንገድ ፡ የታ
ገሉ ፡ መንገዳችንን ፡ በእርግጥ ፡
እንመራቸዋለን ፤ አላህም ፡ በእ
ርግጥ ፡ ከበጎ ፡ ሠሪዎች ፡ ጋር ፡
ነው ።



30ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሩም ፡ (የሮም ፡ ምዕራፍ) ፤ በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 60 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 አ. ለ. መ. (አሊፍ ፡ ላም ፡ ሚም) ።
2 ሩም ፡ ተሸነፈች ፤
3 በጣም ፡ ቅርብ ፡ በኾነችው ፡
ምድር ። እነርሱም ፡ ከመሸነፋ
ቸው ፡ በኋላ ፡ በእርግጥ ፡ ያሸን
ፋሉ ።
4 በጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ (ያሸ
ንፋሉ) ፤ ትእዛዙ ፡ በፊትም ፡
በኋላም ፡ የአላህ ፡ ነው ። በዚያ ፡
ቀንም ፡ ምእምናን ፡ ይደሰታሉ ፤
5 በአላህ ፡ እርዳታ ፤ (ይደሰታሉ) ፤
የሚሻውን ፡ ሰው ፡ ይረዳል ፤ እር
ሱም ፡ አሸናፊው ፡ አዛኙ ፡ ነው ።
6 አላህ ፡ እርዳታን ፡ ቀጠረ ፤ አላህ ፡
ቀጠሮውን ፡ አያፈርስም ፤ ግን ፡
አብዛኞዎቹ ፡ ሰዎች ፡ አያውቁም ።
7 ከቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡ ግልጹን ፡
ብቻ ፡ ያውቃሉ ፤ እነርሱም ፡
ከኋለኛይቱ ፡ ዓለም ፡ እነርሱ ፡
ዘንጊዎች ፡ ናቸው ።
8 በነፍሶቻቸው ፡ (ኹኔታ) ፡ አያስ
ተውሉምን ? ሰማያትንና ፡ ምድ
ርን ፡ በመካከላቸው ፡ ያለውንም ፡
ሁሉ ፡ አላህ ፡ በውነትና ፡ በተወ
ሰነ ፡ ጊዜ ፡ እንጂ ፡ አልፈጠራ
ቸውም ፤ ከሰዎቹም ፡ ብዙዎቹ ፡
በጌታቸው ፡ መገናኘት ፡ ከሓዲ
ዎች ፡ ናቸው ።
9 በምድር ፡ ላይ ፡ አይኼዱምና ፡
የነዚያን ፡ ከበፊታቸው ፡ የነበሩ
ትን ፡ ሰዎች ፡ ፍጻሜ ፡ እንዴት ፡
እንደ ፡ ነበረ ፡ አይመለከቱምን ?
በኀይል ፡ ከነርሱ ፡ ይበልጥ ፡
የጠነከሩ ፡ ነበሩ ፤ ምድርንም ፡
አረሱ ፤ (እነዚህ) ፡ ከአለሟትም ፡
የበዛ ፡ አለሟት ፤ መልክተኞቻ
ቸውም ፡ በታምራቶች ፡ መጡባ
ቸው ፤ (አስተባበሉምና ፡ ጠፉ) ፤
አላህም ፡ የሚበድላቸው ፡ አልነ
በረም ፤ ግን ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ ይበ
ድሉ ፡ ነበሩ ።
10 ከዚያም ፡ የነዚያ ፡ ያጠፉት ፡
ሰዎች ፡ መጨረሻ ፡ በአላህ ፡
አንቀጾች ፡ በማስተባበላቸውና ፡
በርሷ ፡ የሚሳለቁ ፡ በመኾናቸው ፡
ምክንያት ፡ መጥፎ ፡ ቅጣት ፡
ኾነች ።
11 አላህ ፡ መፍጠርን ፡ ይጀምራል ፤
ከዚያም ፡ ይመልሰዋል ፤ ከዚያም ፡
ወደርሱ ፡ ትመለሳላችሁ ።
12 ሰዓቲቱም ፡ በምትቆምበት ፡ ቀን ፡
አመጠኞች ፡ ጭጭ ፡ ይላሉ ።
13 ለነርሱም ፡ ከሚያጋሩዋቸው ፡ (ጣ
ዖታት) ፡ አማላጆች ፡ አይኖሩ
ዋቸውም ፤ በሚያጋሩዋቸውም ፡
(ጣዖታት) ፡ ከሓዲዎች ፡ ይኾ
ናሉ ።
14 ሰዓቲቱ ፡ በምትቆምበት ፡ ቀንም ፡
በዚያ ፡ ቀን ፡ ይለያያሉ ።
15 እነዚያ ፡ ያመኑትና ፡ መልካሞችን ፡
ሥራዎች ፡ የሠሩትማ ፡ እነርሱ ፡

በገነት ፡ ጨፌ ፡ ውስጥ ፡ ይደሰ
ታሉ ።
16 እነዚያም ፡ የካዱትማ ፡ በአንቀ
ጾቻችንና ፡ በኋለኛይቱም ፡ ዓለም፥
መገናኘት ፡ ያስተባበሉት ፡ እነ
ዚያ ፡ በቅጣቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚ
ጣዱ ፡ ናቸው ።
17 አላህንም ፡ በምታመሹ ፡ ጊዜ ፡
በምታነጉም ፡ ጊዜ ፡ አጥሩት ፤
(ስገዱለት)።
18 ምስጋናም ፡ በሰማያትና ፡ በም
ድር ፡ ውስጥ ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡
(የተገባው) ፡ ነው ። በሠርክም ፤
(1) በቀትር ፡ ውስጥ ፡ በምትገ
ቡም ፡ ጊዜ ፤ (አጥሩት) ።
19 ሕያውን ፡ ከሙት ፡ ያወጣል ፤
ሙትንም ፡ ከሕያው ፡ ያወጣል ፤
ምድርንም ፡ ከሞተች ፡ በኋላ ፡
ሕያው ፡ ያደርጋታል ፤ እንደዚ
ሁም ፡ (ከመቃብር) ፡ ትወጥጣ
ላችሁ ።
20 እናንተንም ፡ ከዐፈር ፡ መፍጠሩ ፡
ከዚያም ፡ እናንተ ፡ ወዲያውኑ ፡
የምትበታተኑ ፡ ሰዎች ፡ መኾና
ችሁ ፡ ከአስደናቂ ፡ ምልክቶቹ ፡
ነው ።
21 ለናንተም ፡ ከነፍሶቻችሁ ፡ (ከጐ
ሶቻችሁ) ፡ ሚስቶችን ፡ ወደነ
ርሱ ፡ ትረኩ ፡ ዘንድ ፡ መፍጠሩ ፤
በመካከላችሁም ፡ ፍቅርንና ፡
እዝነትን ፡ ማድረጉ ፡ ከአስደናቂ፡
ምልክቶቹ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ ውስጥ፡
ለሚያስተውሉ ፡ ሕዝቦች ፡ ታም
ራቶች ፡ አልሉ ።
22 ሰማያትንና ፡ ምድርንም ፡ መፍ
ጠሩ ፡ የቋንቋዎቻችሁና ፡ የመል
ኮቻችሁም ፡ መለያየት ፡ ከአስ
ደናቂ ፡ ምልክቶቹ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡
ውስጥ ፡ ለዐዋቂዎች ፡ ታምራ
ቶች ፡ አሉበት ።
23 በሌሊትና ፡ በቀንም ፡ መተኛታ
ችሁ ፡ ከችሮታውም ፡ መፈለጋ
ችሁ ፡ ከምልክቶቹ ፡ ነው ፤ በዚህ፡
ውስጥ ፡ ለሚሰሙ ፡ ሕዝቦች ፡
ታምራቶች ፡ አሉበት ።
24 ብልጭታንም ፡ ፈሪዎችና ፡ ከጀ
ዮች ፡ ስትኾኑ ፡ ለናንተ ፡ ማሳ
የቱ ፡ ከሰማይም ፡ ውሃን ፡ ማው
ረዱ ፡ በርሱም ፡ ምድርን ፡ ከሞ
ተች ፡ በኋላ ፡ ሕያው ፡ ማድረጉ ፡
ከአስደናቂ ፡ ምልክቶቹ ፡ ነው ፤
በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ለሚያስቡ ፡
ሕዝቦች ፡ ታምራቶች ፡ አሉበት ።
25 ሰማይና ፡ ምድርም ፡ (ያለ ፡ ም
ሰሶ) ፡ በትእዛዙ ፡ መቆማቸው ፡
ከዚያም ፡ (መልአኩ ፡ ለትንሣኤ)
ከምድር ፡ ጥሪን ፡ በጠራችሁ ፡
ጊዜ ፡ እናንተ ፡ ወዲያውኑ ፡ የም
ትወጡ ፡ መኾናችሁ ፡ ከአስደ
ናቂ ፡ ምልክቶቹ ፡ ነው ።
26 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡
ሁሉ ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ሁሉ
ም ፡ ለርሱ ፡ ታዛዦች ፡ ናቸው ።
27 እርሱም ፡ ያ ፡ መፍጠርን ፡ የሚ
ጀምር ፡ ከዚያም ፡ የሚመልሰው ፡
ነው ፤ እርሱም ፡ (መመለሱ) ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ ገር ፡ ነው ፤
ለርሱም ፡ በሰማያትም ፡ በምድ
ርም ፡ ከፍተኛ ፡ ባሕርይ ፡ (አን
ድነትና ፡ ለርሱ ፡ ብጤ ፡ የሌለው፡
መኾን) ፡ አልለው ፤ እርሱም ፡
አሸናፊ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።
28 ለናንተ ፡ ከነፍሶቻችሁ ፡ የኾነን ፡
ምሳሌ ፡ አደረገላችሁ ፤ (እርሱም)
እጆቻችሁ ፡ ከያዙዋቸው ፡ (ባ

1 ሠርክ ፡ ከዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ እስከ ፡ ምሺት ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ነው ።



ሮች) ፡ ውስጥ ፡ በሰጠናችሁ ፡
ጸጋ ፡ ለናንተ ፡ ተጋሪዎች ፡ አሏ
ችሁን ? ታዲያ ፡ እናንተና ፡ እነ
ርሱ ፡ በርሱ ፡ ትክክል ፡ ናችሁን ?
ነፍሶቻችሁን ፡ (ብጤዎቻችሁን)፡
እንደምትፈሩ ፡ ትፈሩዋቸዋላች
ሁን? እንደዚሁ ፡ ለሚያስተውሉ፡
ሕዝቦች ፤ አንቀጾችን ፡ እንገል
ጻለን ።
29 ይልቁንም ፡ እነዚያ ፡ የበደሉ ፡
ሰዎች ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ ዝንባሌ
ዎቻቸውን ፡ ተከተሉ ፤ አላህም ፡
ያጠመመውን ፡ ሰው ፡ የሚያቀ
ናው ፡ ማነው ? ለነርሱም ፡ ከረ
ዳቶች ፡ ምንም ፡ የላቸውም ።
30 ወደ ፡ እውነት ፡ ተዘንባይ ፡ ኾነ
ህም ፡ ፊትህን ፡ ለሃይማኖት ፡
ቀጥ ፡ አድርግ ፤ የአላህን ፡ ፍጥ
ረት ፡ ያችን ፡ አላህ ፡ ሰዎችን ፡
በርስዋ ፡ ላይ ፡ የፈጠረባትን ፡
(ሃይማኖት ፡ ያዙዋት) ፤ የአላህን፡
ፍጥረት ፡ መለወጥ ፡ የለም ፤ ይህ ፡
ቀጥተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፤ ግን ፡
አብዛኛዎቹ ፡ ሰዎች ፡ አያውቁም።
31 ወደርሱ ፡ ተመላሾች ፡ ኾናችሁ ፡
(የአላህን ፡ ሃይማኖት ፡ ያዙ) ፤
ፍሩትም ፤ ሶላትንም ፡ አስተካክ
ላችሁ ፡ ስገዱ ፤ ከአጋሪዎቹም ፡
አትኹኑ ።
32 ከነዚያ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ከለ
ያዩትና ፡ ክፍልፍሎችም ፡ ከኾ
ኑት ፡ (አትኹኑ) ፤ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡
እነሱ ፡ ዘንድ ፡ ባለው ፡ ነገር ፡
ተደሳቾች ፡ ናቸው ።
33 ሰዎችንም ፡ ችግር ፡ ባገኛቸው ፡
ጊዜ ፡ ጌታቸውን ፡ ወደርሱ ፡
ተመላሾች ፡ ኾነው ፡ ይጠሩታል ፤
ከዚያም ፡ ከርሱ ፡ ችሮታን ፡ ባቀ
መሳቸው ፡ ጊዜ ፡ ከነሱ ፡ ከፊ
ሎቹ ፡ ወዲያውኑ ፡ በጌታቸው ፡
(ጣዖትን) ፡ ያጋራሉ ፤
34 በሰጠናቸው ፡ ጸጋ ፡ ሊክዱ ፡
(ያጋራሉ) ፤ ተጣቀሙም ፤ በእ
ርግጥም ፡ (መጨረሻችሁን) ፡
ወደፊት ፡ ታውቃላችሁ ።
35 በነሱ ፡ ላይ ፡ አስረጅን ፡ አወረ
ድን ? ታዲያ ፡ እርሱ ፡ በዚያ ፡
በርሱ ፡ ያጋሩ ፡ በነበሩት ፡ ነገር ፡
ይናገራልን ? (የለም) ።
36 ሰዎችንም ፡ ችሮታን ፡ ባቀመስ
ናቸው ፡ ጊዜ ፡ በርሷ ፡ ይደሰታሉ፤
እጆቻቸውም ፡ ባሳለፉት ፡ ምክ
ንያት ፡ መከራ ፡ ብታገኛቸው ፡
ወዲያውኑ ፡ እነርሱ ፡ ተስፋ ፡
ይቆርጣሉ ።
37 አላህ ፡ ለሚሻው ፡ ሰው ፡ ሲሳ
ይን ፡ የሚያሰፋ ፡ የሚያጠብም ፡
መኾኑን ፡ አያዩምን ? በዚህ ፡
ውስጥ ፡ ለሚያምኑ ፡ ሕዝቦች ፡
አስደናቂ ፡ ምልክቶች ፡ አሉበት።
38 የዝምድናን ፡ ባለቤት ፡ ተገቢ
ውን ፡ ስጠው ፤ ለድኻም ፡ ለመን
ገደኛም ፡ (እርዳ) ፤ ይህ ፡ ለነዚያ ፡
የአላህን ፡ ፊት ፡ (ውዴታውን) ፡
ለሚሹ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ እነ
ዚያም ፡ እነሱ ፡ የፈለጉትን ፡ የሚ
ያገኙ ፡ ናቸው ።
39 ከበረከትም ፡ በሰዎች ፡ ገንዘቦች ፡
ውስጥ ፡ ይጨመር ፡ ዘንድ ፡ (1)
የምትሰጡት ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡
አይጨምርም ፤ ከምጽዋትም ፡
የአላህን ፡ ፊት ፡ የምትሹ ፡ ኾና
ችሁ ፡ የምትሰጡት ፡ እነዚያ ፡
(ሰጪዎች) ፡ አበርካቾች ፡ እነሱ ፡
ናቸው ።
40 አላህ ፡ ያ ፡ የፈጠራችሁ ፡ ከዚ

1 ጥቂት ፡ ሰጥታችሁ ፡ ብዙ ፡ ለማግኘት ።

ያም ፡ ሲሳይን ፡ የሰጣችሁ ፡ ከዚ
ያም ፡ የሚያሞታችሁ ፡ ከዚያም ፡
ሕያው ፡ የሚያደርጋችሁ ፡ ነው ፣
ከምታጋሩዋቸው ፡ (ጣዖታት) ፡
ውስጥ ፡ ከዚኸችሁ ፡ አንዳችን ፡
የሚሠራ ፡ አልለን ? ለአላህ ፡ ጥራ
ትይገባው ፣ (በርሱ) ፡ ከሚያጋሩ
ትም ፡ ሁሉ ፡ ላቀ ።
41 የሰዎች ፡ እጆች ፡ በሠሩት ፡
ኃጣአት ፡ ምክንያት ፡ የዚያን ፡
የሠሩትን ፡ ከፊሉን ፡ ያቀምሳ
ቸው ፡ ዘንድ ፡ መከራው ፡ በየብ
ስና ፡ በባሕር ፡ ተገለጠ ፣ (ተሰ
ራጨ) ፣ እነርሱ ፡ ሊመለሱ ፡ ይከ
ጀላልና ።
42 ፡—በምድር ፡ ላይ ፡ ኺዱ ፡ የነዚ
ያንም ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎ
ች ፡ መጨረሻ ፡ እንዴት ፡ እንደ
ነበረ ፡ ተመልከቱ ፡ በላቸው ፣ አብ
ዛኞቻቸው ፡ አጋሪዎች ፡ ነበሩ ።
43 ለርሱ ፡ መመለስ ፡ የሌለው ፡ ቀን ፡
(የትንሣኤ ፡ ቀን) ፡ ከአላህ ፡ ሳይ
መጣ ፡ በፊት ፡ ፊትህን ፡ ወደ ፡
ቀጥተኛው ፡ ሃይማኖት ፡ ቀጥ ፡
አድርግ ፣ በዚያ ፡ ቀን ፡ (ወደ ፡
ገነትና ፡ ወደ ፡ እሳት) ፡ ይለያያሉ ፣
44 የካደ ፡ ሰው ፡ ክሕደቱ ፡ (ጠንቁ) ፡
በርሱው ፡ ላይ ፡ ነው ፣ መልካ
ምም ፡ የሠሩ ፡ ለነፍሶቻቸው ፡
(ማረፊያዎችን) ፡ ያዘጋጃሉ ።
45 እነዚያን ፡ ያመኑትንና ፡ መልካ
ሞችንም ፡ የሠሩትን ፡ ከችሮታው
ይመነዳ ፡ ዘንድ ፡ (ይለያያሉ) ፣
እርሱ ፡ ከሓዲዎችን ፡ አይወድ
ምና ።
46 ነፋሶችንም ፡ (በዝናም) ፡ ልታበ
ስራችሁ ፣ ከችሮታውም ፡ (በርሷ) ፡
ሊያቀምሳችሁ ፣ መርከቦችም ፡
በትእዛዙ ፡ እንዲንሻለሉ ፡ ከች
ሮታውም ፡ እንድትፈልጉ ፡ ታመ
ሰግኑትም ፡ ዘንድ ፡ መላኩ ፡ ከአ
ስደናቂ ፡ ምልክቶቹ ፡ ነው ።
47 ከአንተ ፡ በፊትም ፡ መልክተኞ
ችን ፡ ወደየ ፡ ሕዝቦቻቸው ፡ በእ
ርግጥ ፡ ላክን ፣ በግልጽ ፡ ማስረ
ጃዎችም ፡ መጡባቸው ፣ ከነዚያ ፡
ካምመጡትም ፡ ተበቀልን ፣ ምእ
ምኖቹንም ፡ መርዳት ፡ በኛ ፡ ላይ ፡
ተገቢ ፡ ኾነ ።
48 አላህ ፡ ያ ፡ ነፋሶችን ፡ የሚልክ ፡
ነው ፣ ደመናንም ፡ ይቀሰቅሳሉ ፣
በሰማይ ፡ ላይም ፡ እንደሚሻ ፡
ይዘረጋዋል ፣ ቁርጥራጮችም ፡
ያደርገዋል ፣ ዝናሙንም ፡ ከደመ
ናው ፡ መካከል ፡ ሲወጣ ፡ ታያ
ለህ ፣ በርሱም ፡ ከባሮቹ ፡ የሚሻ
ውን ፡ በለየ ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡
እነሱ ፡ ይደሰታሉ ።
49 በነሱም ፡ ላይ ፡ ከመወረዱ ፡
በፊት ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ በእርግጥ ፡
ተስፋ ፡ ቆራጮች ፡ ነበሩ ።
50 ምድርንም ፡ ከሞተች ፡ በኋላ ፡
እንዴት ፡ ሕያው ፡ እንደሚያደ
ርጋት ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ችሮታ ፡
ፈለጎች ፡ ተመልከት ፣ ይህ ፡
(አድራጊ) ፡ ሙታንንም ፡ በእር
ግጥ ፡ ሕያው ፡ አድራጊ ፡ ነው ፣
እርሱም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ቻይ ፡ ነው ።
51 ነፋስንም ፡ (በአዝመራዎች ፡ ላይ) ፡
ብንልክና ፡ ገርጥቶ ፡ ቢያዩት ፡
ከርሱ ፡ በኋላ ፡ በእርግጥ ፡ (ችሮ
ታውን) ፡ የሚክዱ ፡ ይኾናሉ ።
52 አንተም ፡ ሙታንን ፡ አታሰማም ፣
ደንቆሮዎችንም ፡ ሂሪዎች ፡ ኾነው ፡
በሸሹ ፡ ጊዜ ፡ ጥሪን ፡ አታሰማም ።
53 አንተ ፡ ዕውሮችንም ፡ ከጥመታ
ቸው ፡ የምታቀና ፡ አይደለህም ፣



በአንቀጾቻችን ፡ የሚያምኑትን ፡
ሰዎች ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡ አታሰ
ማም ፣ እነሱም ፡ ታዛዦች ፡
ናቸው ።
54 አላህ ፡ ያ ፡ ከደካማ ፡ (ፍትወት ፡
ጠብታ) ፡ የፈጠራችሁ ፡ ነው ፣
ከዚያም ፡ ከደካማነት ፡ በኋላ ፡
ኀይልን ፡ አደረገ ፣ ከዚያም ፡ ከብ
ርቱነት ፡ በኋላ ፡ ደካማነትንና ፡
ሺበትን ፡ አደረገ ፣ የሚሻውን ፡
ይፈጥራል ፣ እርሱም ፡ ዐዋቂው ፡
ቻዩ ፡ ነው ።
55 ሰዓቲቱ ፡ በምትኾንበት ፡ ቀን ፡
ከሓዲዎች ፡ ከአንዲት ፡ ሰዓት ፡
በስተቀር ፡ (በመቃብር) ፡ አልቆ
የንም ፡ ብለው ፡ ይምላሉ ፣ እንደ
ዚሁ ፡ (ከውነት) ፡ ይመለሱ ፡
ነበሩ ።
56 እነዚያም ፡ ዕውቀትንና ፡ እምነ
ትን ፡ የተሰጡት ፡ በአላህ ፡ መጽ
ሐፍ ፡ (ፍርድ) ፡ እስከ ፡ ትንሣኤ ፡
ቀን ፡ በእርግጥ ፡ ቆያችሁ ፣ ይህም ፡
(የካዳችሁት) ፡ የትንሣኤ ፡ ቀን ፡
ነው ፣ ግን ፡ እናንተ ፡ የማታውቁ ፡
ነበራችሁ ፡ ይሏቸዋል ።
57 በዚያም ፡ ቀን ፡ እነዚያን ፡ የበደ
ሉትን ፡ ማመካኘታቸው ፡ አይጠ
ቅማቸውም ። እነሱም ፡ በወቀሳ ፡
አይታለፉም ፣
58 በዚህም ፡ ቁርአን ፡ ውስጥ ፡ ከም
ሳሌ ፡ ሁሉ ፡ ለሰዎች ፡ በእርግጥ ፡
ገለጽን ፣ በታምርም ፡ ብትመጣ
ባቸው ፡ እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡
እናንተ ፡ አበላሺዎች ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አይደላችሁም ፡ ይላሉ ፣
59 እንደዚሁ ፡ አላህ ፡ በነዚያ ፡ በማ
ያውቁት ፡ ሰዎች ፡ ልቦች ፡ ላይ ፡
ያትማል ።
60 ስለዚህ ፡ ታገሥ ፣ የአላህ ፡ ቀጠሮ ፡
እውነት ፡ ነውና ፣ እነዚያም ፡ በት
ንሣኤ ፡ የማያረጋግጡት ፡ አያ
ቅልሉህ ። (1)

1 ትዕግሥትን ፡ በማሳጣት ፡ ቀላል ፡ ሰው ፡ አያድርጉህ ።

## ምዕራፍ ፡ 31 ፡ ሉቅማን ። ክፍል ፡ 21 ።

31ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ሉቅማን ፣ (የሉቅማን ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፣ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 34 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 አ. ለ. መ. (አሊፍ ፡ ላም ፡ ሚም) ።
2 ይህች ፡ ጥበብ ፡ ከተመላው ፡
መጽሐፍ ፡ አንቀጾች ፡ ናት ።
3 ለበጎ ፡ አድራጊዎች ፡ መሪና ፡
እዝነት ፡ ስትኾን ፣
4 ለነዚያ ፡ ሶላትን ፡ አስተካክለው ፡
ለሚያደርሱት ፣ ዘካንም ፡ ለሚ
ሰጡት ፣ እነሱም ፡ በመጨረሻ
ይቱ ፡ ዓለም ፡ እነሱ ፡ የሚያረ
ጋግጡ ፡ ለኾኑት ።
5 እነዚያ ፡ ከጌታቸው ፡ በኾነ ፡
ቅን ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ናቸው ፣

እነዚያም ፡ እነሱ ፡ ምኞታቸውን ፡
ያገኙ ፡ ናቸው ።
6 ከሰዎችም ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ ኾኖ ፡
ከአላህ ፡ መንገድ ፡ ሊያሳስትና ፡
ማላገጫ ፡ አድርጐ ፡ ሊይዛት ፡
አታላይ ፡ ወሬን ፡ የሚገዛ ፡ አልለ ፤
እነዚያ ፡ ለነሱ ፡ አዋራጅ ፡ ቅጣት ፡
አላቸው ።
7 አንቀጾቻችንም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
በሚነበቡ ፡ ጊዜ ፡ እንዳልሰማ
ትና ፡ በጆሮቹ ፡ ድንቁርና ፡ እን
ዳለበት ፡ የኵራ ፡ ኾኖ ፡ ይዞራል ፤
በአሳማሚ ፡ ቅጣትም ፡ አብስረው ።
8 እነዚያ ፡ ያመኑና ፡ መልካሞች
ንም ፡ የሠሩ ፡ ለነሱ ፡ የጸጋ ፡ ገነ
ቶች ፡ አሏቸው ።
9 በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ሲ
ኾኑ ፤ አላህም ፡ እውነተኛን ፡ ተስ
ፋ ፡ ቃል ፡ ገባላቸው ፤ እርሱም ፡
አሸናፊው ፡ ጥበበኛው ፡ ነው ።
10 ሰማያትን ፡ ያለምታዩዋት ፡ አዕ
ማድ ፡ (ምሰሶዎች) ፡ ፈጠረ ፤
በምድርም ፡ ውስጥ ፡ በናንተ ፡
እንዳታረገርግ ፡ ተራራዎችን ፡
ጣለ ፤ በርሷም ፡ ላይ ፡ ከተንቀሳ
ቃሽ ፡ ሁሉ ፡ በተነ ፤ ከሰማይም ፡
ውሃን ፡ አወረድን ፤ በርሷም ፡
ውስጥ ፡ ከመልካም ፡ ዓይነት ፡
ሁሉ ፡ አበቀልን ።
11 ይህ ፡ የአላህ ፡ ፍጡር ፡ ነው ፤
እነዚያ ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ ያሉት ፡
ምንን ፡ እንደ ፡ ፈጠሩ ፡ እስኪ ፡
አሳዩኝ ፤ በውነቱ ፡ በዳዮቹ ፡ በግ
ልጽ ፡ ጥመት ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።
12 ለሉቅማንም ፡ ጥበብን ፡ በእር
ግጥ ፡ ሰጠነው ፤ (አልነውም) ፡-
አላህን ፡ አመስግን ፤ ያመሰገነም ፡
ሰው ፡ የሚያመሰግነው ፡ ለራሱ ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ የካደም ፡ ሰው ፡
(በራሱ ፡ ላይ ፡ ነው) ፤ አላህ ፡
ተብቃቂ ፡ ምስጉን ፡ ነውና ።
13 ሉቅማንም ፡ ለልጁ ፡ እርሱ ፡
የሚገሥጸው ፡ ሲኾን ፡— ልጄ ፡
ሆይ ! በአላህ ፡ (ጣዖትን) ፡ አታ
ጋራ ፤ ማጋራት ፡ ታላቅ ፡ በደል ፡
ነውና ፡ ያለውን ፡ (አስታውስ) ።
14 ሰውንም ፡ በወላጆቹ ፡ (በጎ ፡ እን
ዲያደርግ) ፡ በጥብቅ ፡ አዘዝነው ፤
እናቱ ፡ ከድካም ፡ በላይ ፡ በኾነ ፡
ድካም ፡ አረገዘችው ፤ ጡት ፡
መጣያውም ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡
ውስጥ ፡ ነው ፤ ለኔም ፡ ለወላጆ
ችህም ፡ አመስግን ፡ በማለት ፡
(አዘዝነው) ፤ መመለሻው ፡ ወደኔ ፡
ነው ።
15 ለአንተ ፡ በርሱ ፡ ዕውቀት ፡ የሌ
ለህን ፡ ነገር ፡ በኔ ፡ እንድታጋራ ፡
ቢታገሉህም ፡ አትታዘዛቸው ፤
በቅርቢቱም ፡ ዓለም ፡ በመል
ካም ፡ ሥራ ፡ ተወዳጃቸው ፤ ወደ
ኔም ፡ የተመለሰን ፡ ሰው ፡ መን
ገድ ፡ ተከተል ፤ ከዚያም ፡ መመለ
ሻችሁ ፡ ወደኔ ፡ ነው ፤ ትሠሩት ፡
የነበራችሁትንም ፡ ሁሉ ፡ እነግራ
ችኋለሁ ፤ (አልነው) ።
16 (ሉቅማንም ፡ አለ) ፡— ልጄ ፡
ሆይ ! እርሷ ፡ (1) የሰናፍጭ ፡ ቅን
ጣት ፡ ክብደት ፡ ያህል ፡ ብትኾ
ንና ፡ በቋጥኝ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡
በሰማያት ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡
በምድር ፡ ውስጥ ፡ ብትኾን ፡
አላህ ፡ ያመጣታል ፤ አላህ ፡ ርኅ
ሩኅ ፡ ውስጥ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።
17 ልጄ ፡ ሆይ ! ሶላትን ፡ አስተካ
ክለህ ፡ ስገድ ፤ በበጎ ፡ ነገርም ፡

1 ደጊቱም ፡ ክፉይቱም ፡ ሥራ ።



እዘዝ ፤ ከሚጠላም ፡ ሁሉ ፡ ከል
ክል ፤ በሚያገኝህም ፡ መከራ ፡
ላይ ፡ ታገሥ ፤ ይህ ፡ በምር ፡ ከሚ
ይያዙ ፡ ነገሮች ፡ ነው ።
18 ጉንጭህንም ፡ (በኩራት) ፡ ከሰ
ዎች ፡ አታዙር ፤ በምድርም ፡
ላይ ፡ ተንበጥርረህ ፡ አትኺድ ፤
አላህ ፡ ተንበጥራሪን ፡ ጉረኛን ፡
ሁሉ ፡ አይወድምና ።
19 በአካኼድህም ፡ መካከለኛ ፡ ኹን ፡
ከድምጽህም ፡ ዝቅ ፡ አድርግ ፤
ከድምጾች ፡ ሁሉ ፡ አስከፊው ፡
የአህዮች ፡ ድምጽ ፡ ነውና ።
20 አላህ ፡ በሰማያት ፡ ያለውንና ፡
በምድርም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡
ለናንተ ፡ ያገራላችሁ ፡ ጸጋዎቹ
ንም ፡ ግልጽም ፡ ድብቅም ፡
ሲኾኑ ፡ የሞላላችሁ ፡ መኾኑን ፡
አታዩምን ? ከሰዎችም ፡ ያለ ፡
ዕውቀትና ፡ ያለ ፡ መሪ ፡ ያለ ፡
ግልጽ ፡ መጽሐፍም ፡ በአላህ ፡
የሚከራከር ፡ አልለ ።
21 ለነሱም ፡ አላህ ፡ ያወረደውን ፡
ተከተሉ ፡ በተባሉ ፡ ጊዜ ፡ አይደ
ለም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አባቶቻችንን ፡
ያገኘንበትን ፡ እንከተላለን ፡ ይላሉ ፤
ሰይጣን ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ቅጣት ፡
የሚጠራቸው ፡ ቢኾንም ፡ (ይከተ
ሉዋቸዋልን ?)
22 እርሱ ፡ መልካም ፡ ሠሪ ፡ ኾኖ ፡
ፊቱን ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ የሚሰጥም ፡
ሰው ፡ ጠንካራን ፡ ገመድ ፡ በእር
ግጥ ፡ ጨበጠ ፤ የነገሩም ፡ ሁሉ ፡
ፍጻሜ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ነው ።
23 የካደም ፡ ሰው ፡ ክሕደቱ ፡ አያሳ
ዝንህ ፤ መመለሻቸው ፡ ወደኛ ፡
ነው ፤ የሠሩትንም ፡ ሁሉ ፡ እንነ
ግራቸዋለን ፤ አላህ ፡ በልቦች ፡
ውስጥ ፡ ያለን ፡ ሁሉ ፡ ያውቃ
ልና ።
24 ጥቂትን ፡ እናጣቅማቸዋለን ፤
ከዚያም ፡ ወደ ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት ፡
እናስገድዳቸዋለን ፤
25 ሰማያትንና ፡ ምድርንም ፡ የፈ
ጠረ ፡ ማን ፡ እንደኾነ ፡ ብትጠይ
ቃቸው ፡ በእርግጥ ፡ አላህ ፡ ነው ፡
ይላሉ ፤ ምስጋና ፡ ለአላህ ፡ ይገ
ባው ፡ በላቸው ፤ ይልቁንም ፡
አብዛኞዎቹ ፡ አያውቁም ።
26 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡
ሁሉ ፡ የአላህ ፡ ነው ፤ አላህ ፡
እርሱ ፡ ተብቃቂ ፡ ምስጉን ፡
ነው ።
27 ከዛፍም ፡ በምድር ፡ ያለጡ ፡ ሁሉ ፡
ብርዖች ፡ ቢኾኑ ፡ ኖሮ ፡ ባሕሩም ፡
ከርሱ ፡ (ማለቅ) ፡ በኋላ ፡ ሰባት ፡
ባሕሮች ፡ የሚጨመሩለት ፡ ኾኖ ፡
(ቀለም ፡ ቢኾንና ፡ ቢጻፍባቸው) ፡
የአላህ ፡ ቃላት ፡ ባላለቀች ፡ ነበር ፤
አላህ ፡ አሸናፊ ፡ ጥበበኛ ፡ ነውና ።
28 እናንተን ፡ መፍጠርና ፡ እናን
ተን ፡ መቀስቀስ ፡ እንደ ፡ አንዲት ፡
ነፍስ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፤
አላህ ፡ ሰሚ ፡ ተመልካች ፡ ነውና ።
29 አላህ ፡ ሌሊትን ፡ በቀን ፡ ውስጥ ፡
የሚያስገባ ፡ ቀንንም ፡ በሌሊት ፡
ውስጥ ፡ የሚያስገባ ፡ ፀሐይንና ፡
ጨረቃንም ፡ የገራ ፡ መኾኑን ፡
አታይምን ? ሁሉም ፡ እስከ ፡ ተወ
ሰነ ፡ ጊዜ ፡ድረስ ፡ ይሮጣሉ ፤
አላህም ፡ በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡
ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
30 ይህ ፡ አላህ ፡ እርሱ ፡ እውነት ፡
ከርሱም ፡ ሌላ ፡ የሚገዙት ፡
(ጣዖት) ፡ ውሸት ፡ በመኾኑና ፡
አላህም ፡ እርሱ ፡ የበላይ ፡ ታላቅ ፡
በመኾኑ ፡ ነው ።

31 ከአስደናቂ ፡ ምልክቶቹ ፡ ሊያሳ
ያችሁ ፡ መርከቦች ፡ በአላህ ፡
ችሮታ ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ የሚን
ሻለሉ ፡ መኾናቸውን ፡ አታይ
ምን ? በዚህ ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡
ታጋሽ፡ አመስጋኝ ፡ ለኾኑ ፡ ሁሉ ፡
ታምራቶች ፡ አሉበት ።
32 እንደ ፡ ጥላዎችም ፡ የኾነ ፡ ማዕ
በል ፡ በሸፈናቸው ፡ ጊዜ ፡ አላ
ህን ፡ ሃይማኖትን ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡
ያጠሩ ፡ ኾነው ፡ ይጠሩታል ፤
ወደ ፡ የብስም ፡ ባዳናቸው ፡ ጊዜ ፡
ከነሱ ፡ ትክክለኛም ፡ አልለ ፤
(ከነሱም ፡ የሚከድ ፡ አልለ) ፤
በአንቀጾቻችንም ፡ አታላይ ፡ ከዳ
ተኛ ፡ ሁሉ ፡ እንጂ ፡ ሌላው ፡
አይክድም ።
33 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! ጌታች
ሁን ፡ ፍሩ ፤ ወላጅም ፡ ከልጁ ፡
(በምንም) ፡ የማይጠቅምበትን ፤
ተወላጅም ፡ እርሱ ፡ ወላጅን ፡
በምንም ፡ ጠቃሚ ፡ የማይኾንበ
ትን ፡ ቀን ፡ ፍሩ ፤ የአላህ ፡ ቀጠሮ ፡
እውነት ፡ ነውና ፤ ቅርቢቱም ፡
ሕይወት ፡ አትሸንግላችሁ ፤ በአ
ላህም ፡ (መታገስ) ፡ አታላዩ ፡
(ሰይጣን) ፡ አያታልላችሁ ።
34 አላህ ፡ የሰዓቲቱ ፡ ዕውቀት ፡
እርሱ ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ዝና
ምንም ፡ ያወርዳል ፤ በማሕፀኖ
ችም ፡ ውስጥ ፡ ያለን ፡ ሁሉ ፡ ያው
ቃል ፤ ማንኛይቱ ፡ ነፍስም ፡ ነገ ፡
የምትሠራውን ፡ አታውቅም ፤
ማንኛይቱ ፡ ነፍስም ፡ በየትኛው ፡
ምድር ፡ እንደምትሞት ፡ አታው
ቅም ፤ አላህ ፡ ዐዋቂ ፡ ውስጠ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 32 ፡ አል-ሰጅዳህ ። ክፍል ፡ 21 ።

32ኛ ፡ ሱረቱ፡ አል-ሰጅዳህ ፡ (የስግደት ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 30፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው።
1 አ. ለ. መ. (አሊፍ ፡ ላም ፡ ሚም) ።
2 የመጽሐፉ ፡ መወረድ ፡ ጥርጥር ፡
የለበትም ፤ ከዓለማት ፡ ጌታ ፡
ነው ።
3 ይልቁንም ፡ ቀጠፈው ፡ ይላሉን ?
አይደለም ፤ እርሱ ፡ ከጌታህ ፡
ዘንድ ፡ የኾነ ፡ እውነት ፡ ነው ፤
በርሱ ፡ ከአንተ ፡ በፊት ፡ ከአስ
ፈራሪ ፡ (ነቢይ) ፡ ያልመጣባቸ
ውን ፡ ሕዝቦች ፡ ልታስፈራራ
በት ፡ (ያወረደልህ ፡ ነው) ፤ እነ
ርሱ ፡ ሊምመሩ ፡ ይከጀላልና ።
4 አላህ ፡ ያ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድ
ርን ፡ በመካከላቸውም ፡ ያለውን ፡
ሁሉ ፡ በስድስት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ፡
የፈጠረ ፡ ከዚያም ፡ በዐርሹ ፡
ላይ ፡ (ሥልጣኑ) ፡ የተዳለደለ ፡
ነው ፤ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ ለናንተ ፡ ረዳ



ትም ፡ አማላጅም ፡ ምንም ፡ የላ
ችሁም ፤ አትገሠጹምን ?
5 ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ከሰማይ ፡ ወደ ፡
ምድር ፡ ያዘጋጃል ፤ ከዚያም ፡
ከምትቆጥሩት ፡ (ዘመን) ፡ ልኩ ፡
ሺሕ ፡ ዓመት ፡ በኾነ ፡ ቀን ፡
ውስጥ ፡ ወደርሱ ፡ ይወጣል ፤
(ይመለሳል) ።
6 ይህ ፡ (ይህንን ፡ የሠራው) ፡ ሩቁ
ንም ፡ ቅርቡንም ፡ ሁሉ ፡ ዐዋ
ቂው ፡ አሸናፊው ፡ አዛኙ ፡ (ጌታ)፡
ነው ።
7 ያ ፡ የፈጠረውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
ያሳመረው ፡ የሰውንም ፡ ፍጥረት ፡
ከጭቃ ፡ የጀመረው ፡ ነው ።
8 ከዚያም ፡ ዘሮቹን ፡ ከተጣለለ ፡
ከደካማ ፡ ውሃ ፡ ያደረገ ፡ ነው ።
9 ከዚያም ፡ (ቅርጹን) ፡ አስተካከ
ለው ፤ በርሱ ፡ ውስጥም ፡ ከመን
ፈሱ ፡ ነፋበት ፤ (ነፍስ ፡ ዘራበት) ፤
ለናንተም ፡ ጆሮዎችን፥ ዓይኖች
ንና ፡ ልቦችንም ፡ አደረገላችሁ ፡
በጣም ፡ ጥቂትን ፡ ብቻ ፡ ታመሰ
ግናላችሁ ።
10 በምድርም ፡ ውስጥ ፡ (በስብሰን) ፡
በጠፋን ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ በአዲስ ፡
መፈጠር ፡ ውስጥ ፡ እንኾናለን ?
አሉ ፤ በውነቱ ፡ እነሱ ፡ በጌታ
ቸው ፡ መገናኘት ፡ ከሓዲዎች ፡
ናቸው ።
11 ፡—በናንተ ፡ የተወከለው ፡ መል
አከ ፡ ሞት ፡ ይገድላችኋል ፤ ከዚ
ያም ፡ ወደ ፡ ጌታችሁ ፡ ትመለሳ
ላችሁ ፡ በላቸው ።
12 አመጠኞችም ፡ በጌታቸው ፡ ዘንድ
ራሶቻቸውን ፡ ያቀረቀሩ ፡ ኾነው፡
፡—ጌታችን ፡ ሆይ ! አየን ፤ ሰማ
ንም ፤ መልካምን ፡ እንሠራለንና ፡
(ወደ ፡ ምድረ ፡ ዓለም) ፡ መልሰን ፤
እኛ ፡ አረጋጋጮች ፡ ነን ፤ (የሚሉ፡
ሲኾኑ) ፡ ብታይ ፡ ኖሮ ፡ (አስደን
ጋጪን ፡ ነገር ፡ ታይ ፡ ነበር)።
13 በሻንም ፡ ኖሮ ፡ ነፍስን ፡ ሁሉ ፡
ቅንነቷን ፡ (እምነቷን) ፡ በሰጠ
ናት ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ገሀነምን ፡
ከአጋንንትና ፡ ከሰዎች ፡ የተሰበ
ሰቡ ፡ ኾነው ፡ በእርግጥ ፡ እመ
ላለሁ ፡ ማለት ፡ ቃሉ ፡ ከኔ ፡ ተረ
ጋግጧል ።
14 ይህንንም ፡ ቀናችሁን ፡ መገናኘ
ትን ፡ በመርሳታችሁ ፡ ምክንያት ፡
(ቅጣትን) ፡ ቅመሱ ! እኛ ፡ ተው
ናችሁ ፤ ትሠሩት ፡ በነበራችሁ
ትም ፡ ጥፋት ፡ ዘውታሪን ፡ ቅጣት
ቅመሱ ፡ (ይባላሉ) ።
15 በአንቀጾቻችን ፡ የሚያምኑት ፡
እነዚያ ፡ በርሷ ፡ በተገሠጹ ፡ ጊዜ፡
ሰጋጆች ፡ ኾነው ፡ የሚወድቁ
ትና ፡ እነሱም ፡ የማይኮሩ ፡
ኾነው ፡ በጌታቸው ፡ ምስጋና ፡
(ተጐናጽፈው) ፡ የሚያወድሱት ፡
ብቻ ፡ ናቸው ።
16 ጌታቸውን ፡ ለመፍራትና ፡ ለመ
ከጀል ፡ የሚጠሩት ፡ ኾነው ፡ ጐኖ
ቻቸው ፡ ከመጋደሚያ ፡ ስፍራ
ዎች ፡ ይራራቃሉ ፤ ከሰጠናቸ
ውም ፡ (ጸጋ) ፡ ይለግሳሉ ።
17 ይሠሩትም ፡ በነበሩት ፡ ለመመን
ዳት ፡ ከዓይኖች ፡ መርጊያ ፡ ለነሱ፡
የተደበቀላቸውን ፡ (ጸጋ) ፡ ማን
ኛይቱም ፡ ነፍስ ፡ አታውቅም ።
18 አማኝ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ አመጠኛ ፡
እንደ ፡ ኾነ ፡ ሰው ፡ ነውን ? አይ
ተካከሉም ።
19 እነዚያ ፡ ያመኑና ፡ መልካሞችን ፡
የሠሩማ ፡ ለነሱ ፡ ይሠሩት ፡ በነ

በሩት ፡ ምክንያት ፡ መስተንግዶ ፡
ሲኾኑ ፡ መኖሪያ ፡ ገነቶች ፡ አሏ
ቸው ።
20 እነዚያ ፡ ያምመጡትማ ፤ መኖሪ
ያቸው ፡ እሳት ፡ ናት ፤ ከርሷ ፡
መውጣትን ፡ በፈለጉ ፡ ቍጥር ፡
በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ይመለሳሉ ፤ ለነ
ርሱም ፡ ያንን ፡ በርሱ ፡ ታስተባ
ብሉበት ፡ የነበራችሁትን ፡ የእ
ሳት ፡ ቅጣት ፡ ቅመሱ ፡ ይባላሉ ።
21 ይመለሱ ፡ ዘንድም ፡ ከትልቁ ፡
ቅጣት ፡ በፊት ፡ (በዚህ ፡ ዓለም) ፡
ከትንሹ ፡ ቅጣት ፡ በእርግጥ ፡ እና
ቀምሳቸዋለን ።
22 በጌታውም ፡ አንቀጾች ፡ ከተገ
ሠጸና ፡ ከዚያም ፡ ከተዋት ፡ ሰው ፡
ይበልጥ ፡ በደለኛ ፡ ማነው ?
(የለም) ፤ እኛ ፡ ከተንኮለኞቹ ፡
ተበቃዮች ፡ ነን ።
23 ሙሳንም ፡ መጽሐፍን ፡ በእርግጥ ፡
ሰጠነው ፤ እርሱን ፡ ከመገናኘት
ህም ፡ በመጠራጠር ፡ ውስጥ ፡ አ
ትኹን ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆችም ፡
መሪ ፡ አደረግነው ።
24 በታገሡና ፡ በታምራቶቻችን ፡
የሚያረጋግጡ ፡ በኾኑም ፡ ጊዜ ፡
ከነርሱ ፡ በትእዛዛችን ፡ የሚመሩ ፡
መሪዎችን ፡ አደረግን ፤
25 ጌታህ ፡ እርሱ ፡ በዚያ ፡ በርሱ ፡
ይለያዩበት ፡ በነበሩት ፡ ነገር ፡
በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ በመካከላቸው ፡
(በፍርድ) ፡ ይለያል ፤
26 ከክፍለ ፡ ዘመናት ፡ ሰዎች ፡ ብዙ
ዎችን ፡ ያጠፋን ፡ መኾናችን ፡
በመኖሪያዎቻቸው ፡ የሚኼዱ ፡
ሲኾኑ ፡ ለነርሱ ፡ አልተገለጸላቸ
ውምን ? በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ምል
ክቶች ፡ አሉበት ፤ አይሰሙምን ?
27 እኛ ፡ ውሃን ፡ ወደ ፡ ደረቅ ፡ ምድር
የምንነዳ ፡ እንስሶቻቸውና ፡ ነፍ
ሶቻቸው ፡ ከርሱ ፡ የሚበሉለት
ንም ፡ አዝመራ ፡ በርሱ ፡ የምና
ወጣ ፡ መኾናችንን ፡ አያዩምን ?
አይመለከቱምን ?
28 ከውነተኞችም ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡
ይህ ፡ ፍርድ ፡ መቼ ፡ ነው ? ይላሉ ።
29 በፍርዱ ፡ ቀን ፡ እነዚያን ፡ የካዱ
ትን ፡ ሰዎች ፡ እምነታቸው ፡ አይ
ጠቅማቸውም ፤ እነሱም ፡ ጊዜን ፡
አይሰጡም ፤ በላቸው ።
30 እነሱንም ፡ ተዋቸው ፤ ተጠባበ
ቅም ፤ እነሱ ፡ ተጠባባቂዎች ፡
ናቸውና ።



33ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-አሕዛብ ፤ (የአሕዛቦች ፡ ምዕራፍ) ፤ በመዲ
ና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 73 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 አንተ ፡ ነቢዩ ፡ ሆይ ! አላህን ፡
ፍራ ፤ ከሓዲዎችንና ፡ መናፍቃ
ንንም ፡ አትታዘዝ ። አላህ ፡
ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነውና ።
2 ከጌታህም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ የሚወ
ረደውን ፡ ተከተል ፤ አላህ ፡ በምት
ሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡
ነውና ።
3 በአላህም ፡ ላይ ፡ ተመካ ፤ መመ
ኪያም ፡ በአላህ ፡ በቃ ።
4 አላህ ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ በሆዱ ፡
ውስጥ ፡ ሁለትን ፡ ልቦች ፡ አላደረ
ገም ፤ ሚስቶቻችሁንም ፡ እነዚ
ያን ፡ ከነርሱ ፡ እንደናቶቻችሁ ፡
ጀርባዎች ፡ ይኹኑብን ፡ የምትሏ
ቸውን ፡ እናቶቻችሁ ፡ አላደረ
ገም ፤ ልጅ ፡ በማድረግ ፡ የምታስ
ጠጓቸውንም ፡ ልጆቻችሁ ፡ አላ
ደረገም ፤ ይሃችሁ ፡ በአፎቻችሁ ፡
የምትሉት ፡ ነው ፤ አላህም ፡ እው
ነቱን ፡ ይናገራል ፤ እርሱም ፡ ትክ
ክለኛውን ፡ መንገድ ፡ ይመራል ።
5 ለአባቶቻቸው ፡ (በማስጠጋት) ፡
ጥሩዋቸው ፤ እርሱ ፡ አላህ ፡
ዘንድ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፤ አባቶ
ቻቸውንም ፡ ባታውቁ ፡ በሃይማ
ኖት ፡ ወንድሞቻችሁና ፡ ዘመዶ
ቻችሁ ፡ ናቸው ፤ በርሱ ፡ በተሳሳ
ታችሁበት ፡ ነገርም ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ ኀጢአት ፡ የለባችሁም ፤
ግን ፡ ልቦቻችሁ ፡ ዐውቀው ፡
በሠሩት ፡ (ኀጢአት ፡ አለባችሁ) ፤
አላህም ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።
6 ነቢዩ ፡ በምእምናን ፡ ከነፍሶቻ
ቸው ፡ ይበልጥ ፡ ተገቢ ፡ ነው ፤
ሚስቶቹም ፡ እናቶቻቸው ፡ ናቸው ፤
የዝምድና ፡ ባለ ፡ ቤቶችም ፡ ከፊ
ላቸው ፡ በከፊሉ ፡ (ውርስ) ፡ በአ
ላህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከምእ
ምናንና ፡ ከስደተኞቹ ፡ ይልቅ ፡
የተገባቸው ፡ ናቸው ፤ ግን ፡ ወደ ፡
ወዳጆቻችሁ ፡ (በኑዛዜ) ፡ መል
ካምን ፡ ብትሠሩ ፡ (ይፈቀዳል) ፤
ይህ ፡ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ የተመ
ዘገበ ፡ ነው ።
7 ከነቢዮችም ፡ የጠበቀ ፡ ኪዳናቸ
ውን ፡ ከአንተም ፡ ከኑሕም ፡ ከኢ
ብራሂምም ፡ ከሙሳም ፡ ከመር
የም ፡ ልጅ ፡ ዒሳም ፡ በያዝን ፡
ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፤ ከነሱም ፡
የከበደን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያዝን ።
8 (አላህ) ፡ እውነተኞችን ፡ ከውነታ
ቸው ፡ ሊጠይቅ ፡ (ይህንን ፡ ሠራ) ፤
ለከሓዲዎችም ፡ አሳማሚን ፡
ቅጣት ፡ አዘጋጀ ።
9 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ብዙ ፡
ሰራዊት ፡ በመጣችባችሁና ፡
በነሱ ፡ ላይ ፡ ነፋስንና ፡ ያላያች
ኋትን ፡ ሰራዊት ፡ በላክን ፡ ጊዜ ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ (ያደረገላችሁን) ፡
የአላህን ፡ ጸጋ ፡ አስታውሱ ፤ አላ
ህም ፡ የምትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡
ተመልካች ፡ ነው ።

10 ከበላያችሁም ፡ ከናንተ ፡ በታ
ችም ፡ በመጡባችሁ ፡ ጊዜ ፡ ዓይ
ኖችም ፡ በቃበዙ ፡ ልቦችም ፡
እላንቃዎች ፡ በደረሱና ፡ በአላ
ህም ፡ ጥርጣሬዎችን ፡ በጠረጠ
ራችሁ ፡ ጊዜ ፡ (ያደረገላችሁን ፡
አስታውሱ) ።
11 እዚያ ፡ ዘንድ ፡ ምእምናን ፡ ተሞ
ከሩ ፤ ብርቱን ፡ መንቀጥቀጥም ፡
ተንቀጠቀጡ ።
12 መናፍቆችና ፡ እነዚያ ፡ በልቦቻ
ቸው ፡ ውስጥ ፡ በሽታ ፡ ያለባቸ
ውም ፡ አላህና ፡ መልክተኛው ፡
ማታለልን ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡ አል
ቀጠሩንም ፡ በሚሉ ፡ ጊዜ ፡ (ያደ
ረገላችሁን ፡ አስታውሱ) ።
13 ከነሱም ፡ የኾኑ ፡ ጭፍሮች ፡ የየ
ሥሪብ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! ለናንተ ፡
ስፍራ ፡ የላችሁምና ፡ ተመለሱ ፡
ባሉ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውሱ) ፤ ከነ
ሱም ፡ ከፊሎቹ ፡ እርሷ ፡ ነውረኛ ፡
ሳትኾን ፡ ቤቶቻችን ፡ ነውረኛ ፡
ናቸው ፡ (1) የሚሉ ፡ ኾነው ፡
ነቢዩን ፡ (ከጦሩ ፡ ለመመለስ) ፡
ፈቃድን ፡ ይጠይቃሉ ፤ መሸሽን ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይፈልጉም ።
14 በነርሱም ፡ ላይ ፡ (ቤቶቻቸው) ፡
ከየቀበሌዋ ፡ በተገባባት ፡ ከዚ
ያም ፡ ከኢስላም፡ መመለስን ፡
በተጠየቁ ፡ ኖሮ ፡ በሠሩዋት ፡
ነበር ፤ በርሷም ፡ ጥቂትን ፡ ጊዜ ፡
እንጂ ፡ አይቆዩም ፡ ነበር ።
15 ጀርባዎችንም ፡ ላያዞሩ ፡ ከዚያ ፡
በፊት ፡ በእርግጥ ፡ አላህን ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ የተጋቡ ፡ ነበሩ ፤ የአላ
ህም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የሚጥጠየ
ቁበት ፡ ነው ።

1 ጠንካራ ፡ ያልኾኑ ፡ ያልታጠሩ ፡ ናቸው ።

16 ከሞት ፡ ወይም ፡ ከመገደል ፡ ብት
ሸሹ ፡ መሸሻችሁ ፡ ፈጽሞ ፡ አይ
ጠቅማችሁም ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡
ጥቂትን ፡ እንጂ ፡ የምትጣቀሙ ፡
አትደረጉም ፡ በላቸው ።
17 ፡—(አላህ) ፡ በናንተ ፡ ክፉን ፡
ነገር ፡ ቢሻ ፡ ያ ፡ ከአላህ ፡ የሚጠ
ብቃችሁ ፡ ማነው ? ወይም ፡ ለና
ንተ ፡ ችሮታን ፡ ቢሻ ፤ (በክፉ ፡
የሚነካችሁ ፡ ማነው ?) በላቸው ፤
ከአላህም ፡ ሌላ ፡ ለነርሱ ፡ ወዳ
ጅም ፡ ረዳትም ፡ አያገኙም ።
18 ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ የሚያሳንፉ
ትን ፡ ለወንድሞቻቸውም ፡ ወደኛ
ኑ ፡ የሚሉትን ፡ ውጊያንም ፡
ጥቂትን ፡ እንጂ ፡ የማይመጡ
ትን ፡ በእርግጥ ፡ አላህ ፡ ያውቃ
ቸዋል ።
19 በናንተ ፡ ላይ ፡ (ርዳታን) ፡ የነፈጉ ፡
ኾነው ፡ እንጅ ፡ (የማይመጡትን) ፤
ሽብሩም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እን
ደዚያ ፡ ከሞት ፡ (መከራ) ፡ በርሱ ፡
ላይ ፡ የሚሸፍን ፡ ዐደጋ ፡ እንደ ፡
ወደቀበት ፡ ዓይኖቻቸው ፡ ወዲ
ያና ፡ ወዲህ ፡ የምትዞር ፡ ኾና ፡
ወዳንተ ፡ ሲመለከቱ ፡ ታያቸዋ
ለህ ፤ ሽብሩም ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡
በገንዘብ ፡ ላይ ፡ የሚሳሱ ፡ ኾነው ፡
በተቡ ፡ ምላሶች ፡ ይነድፏችኋል ፤
እነዚያ ፡ አላመኑም ፤ ስለዚህ ፡
አላህ ፡ ሥራዎቻቸውን ፡ አበላሸ ፤
ይህም ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ገር ፡
ነው ።
20 (መናፍቆች) ፡ አሕዛብን ፡ አልኼ
ዱም ፡ ብለው ፡ ያስባሉ ፤ አሕዛቦ
ቹም ፡ ቢመጡ ፡ እነሱ ፡ በዘላ
ኖች ፡ ውስጥ ፡ በገጠር ፡ (የራቁ) ፡
ሊኾኑ ፡ ይመኛሉ ፤ ከወሬዎቻ
ችሁ ፡ ይጠይቃሉ ፤ በናንተ ፡



ውስጥ ፡ በነበሩም ፡ ኖሮ ፡ ጥቂ
ትን ፡ እንጂ ፡ አይዋጉም ፡ ነበር ።
21 ለናንተ ፡ አላህንና ፡ የመጨረሻ
ውን ፡ ቀን ፡ የሚከጅል ፡ ለኾነ ፡
ሰው ፡ አላህንም ፡ በብዙ ፡ ለሚያ
ወሳ ፡ በአላህ ፡ መልክተኛ ፡ መል
ካም ፡ መከተል ፡ አላችሁ ፤
22 አማኞቹም ፡ አሕዛብን ፡ ባዩ ፡
ጊዜ ፡ ይህ ፡ አላህና ፡ መልክተ
ኛው ፡ የቀጠሩን ፡ ነው ፤ አላህና ፡
መልክተኛውም ፡ እውነትን ፡
ተናገሩ ፡ (1) አሉ ። (ይህ) ፡ እም
ነትንና ፡ መታዘዝንም ፡ እንጂ ፡
ሌላን ፡ አልጨመረላቸውም ።
23 ከአማኞቹ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ለአ
ላህ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የገቡበትን ፡
በውነት ፡ የፈጸሙ ፡ ወንዶች ፡
አልሉ ፤ ከነሱም ፡ ስለቱን ፡ የፈ
ጸመ ፡ (ለሃይማኖቱ ፡ የተገደለ) ፡
አልለ ፤ ከነሱም ፡ ገና ፡ የሚጠባ
በቅ ፡ አልለ ፤ (የገቡበትን ፡ ቃል) ፡
መለወጥንም ፡ አልለወጡም ።
24 አላህ ፡ እውነተኞችን ፡ በውነተኛ
ነታቸው ፡ ሊመነዳ ፡ መናፍቃ
ንንም ፡ ቢሻ ፡ ሊቀጣ ፡ ወይም ፡
(ቢመለሱ) ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ጸጸታ
ቸውን ፡ ሊቀበል ፡ (ይህን ፡ አደ
ረገ) ፤ አላህ ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡
ነውና ።
25 እነዚያንም ፡ የካዱትን ፡ በቁጭ
ታቸው ፡ የተመሉ ፡ መልካምን ፡
ነገር ፡ ያላገኙ ፡ ኾነው ፡ አላህ ፡
መለሳቸው ፤ አማኞቹንም ፡ አላህ ፡
መጋደልን ፡ በቃቸው ፤ አላህም ፡
ብርቱ ፡ አሸናፊ ፡ ነው ።
26 እነዚያንም ፡ ከመጽሐፉ ፡ ባለ ፡
ቤቶች ፡ (አሕዛቦችን) ፡ የረዱዋ

1 የተናገሩት ፡ እውነት ፡ መኾኑ ፡ ተገለጠ ።

ቸውን ፡ (ቁረይዟን) ፡ ከምሽጎ
ቻቸው ፡ አወረዳቸው ፤ በልቦቻ
ቸውም ፡ ውስጥ ፡ መባባትን ፡
ጣለባቸው ፤ ከፊሉን ፡ ትገድላ
ላችሁ ፤ ከፊሉንም ፡ ትማርካላ
ችሁ ።
27 ምድራቸውንም ፡ ቤቶቻቸውንም ፡
ገንዘቦቻቸውንም ፡ ገና ፡ ያልረገጣ
ችኋትንም ፡ ምድር ፡ አወረሳችሁ ፤
አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ቻይ ፡ ነው ።
28 አንተ ፡ ነቢዩ ፡ ሆይ ! ለሚስቶ
ችህ ፡ (እንዲህ) ፡ በላቸው ፡— ቅር
ቢቱን ፡ ሕይወትና ፡ ጌጧን ፡ የም
ትፈልጉ ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ ኑ ፤
አጣቅማችኋለሁና ፤ መልካምንም ፡
ማሰማራት ፡ (በመፍታት) ፡ አሰ
ማራችኋለሁና ፤
29 አላህንና ፡ መልክተኛውን ፡ የመ
ጨረሻይቱን ፡ አገርም ፡ የምትፈ
ልጉ ፡ ብትኾኑም ፤ እነሆ ፡ አላህ ፡
ከናንተ ፡ ለመልካም ፡ ሠሪዎቹ ፡
ትልቅን ፡ ምንዳ ፡ አዘጋጅቷል ።
30 የነቢዩ ፡ ሴቶች ፡ ሆይ ! ከናንተ ፡
ውስጥ ፡ ግልጽ ፡ የኾነን ፡ መጥፎ ፡
ሥራ ፡ የምትሠራ ፡ ለርሷ ፡ ቅጣቱ ፡
ሁለት ፡ እጥፍ ፡ ኾኖ ፡ ይነባበር
በታል ፤ ይህም ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡
ገር ፡ ነው ።

★ ★ ★

31 ከናንተም ፡ ለአላህና ፡ ለመልክተ
ኛው ፡ የምትታዘዝ ፡ መልካም ፡
ሥራንም ፡ የምትሠራ ፡ ምንዳ
ዋን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ እንሰጣታ
ለን ፤ ለርሷም ፡ የከበረን ፡ ሲሳይ ፡
አዘጋጅተንላታል ።
32 የነቢዩ ፡ ሴቶች ፡ ሆይ ! ከሴቶች ፡
እንደ ፡ ማናቸው ፡ አይደላችሁም ፤

አላህን ፡ ብትፈሩ ፡ (ትበልጣላ
ችሁ) ፤ ያ ፡ በልቡ ፡ ውስጥ ፡
በሽታ ፡ ያለበት ፡ እንዳይከጅል ፡
በንግግር ፡ አትለስልሱም ፤ መል
ካምንም ፡ ንግግር ፡ ተናገሩ ።
33 በቤቶቻችሁም ፡ ውስጥ ፡ እርጉ ፤
እንደ ፡ ፊተኛይቱ ፡ መሃይምንነት ፡
ጊዜ ፡ መገለጥም ፡ በማጌጥ ፡
አትገለጡ ፤ ሶላትንም ፡ በደንቡ ፡
ስገዱ ፤ ዘካንም ፡ ስጡ ፤ አላህንና ፡
መልክተኛውንም ፡ ታዘዙ ፤ የነ
ቢዩ ፡ ቤተሰቦች ፡ ሆይ ! አላህ ፡
የሚሻው ፡ ከናንተ ፡ ላይ ፡ ርክሰ
ትን ፡ ሊያስወግድና ፡ ማጥራት
ንም ፡ ሊያጠራችሁ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
34 ከአላህ ፡ አንቀጾችና ፡ ከጥበቡም ፡
በቤቶቻችሁ ፡ የሚነበበውን ፡
አስታውሱ ፤ አላህ ፡ እዝነቱ ፡
ረቂቅ ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ፤
35 ሙስሊሞች፡ ወንዶችና፡ ሙስሊ
ሞች ፡ ሴቶች ፡ ምእምናንና ፡
ምእምናትም ፡ ታዛዦች ፡ ወንዶ
ችና ፡ ታዛዦች ፡ ሴቶችም ፡ እውነ
ተኞች ፡ ወንዶችና ፡ እውነተኞች፡
ሴቶችም ፡ ታጋሾች ፡ ወንዶችና ፡
ታጋሾች ፡ ሴቶችም ፡ አላህን ፡
ፈሪዎች ፡ ወንዶችና ፡ አላህን ፡
ፈሪዎች ፡ ሴቶችም ፡ መጽዋቾች ፡
ወንዶችና ፡ መጽዋቾች ፡ ሴቶ
ችም ፡ ጿሚዎች ፡ ወንዶችና ፡
ጿሚዎች ፡ ሴቶችም ፡ (ካልተፈ
ቀደ ፡ ሥራ) ፡ ብልቶቻቸውን ፡
ጠባቂዎች ፡ ወንዶችና ፡ ጠባቂ
ዎች ፡ ሴቶችም ፡ አላህን ፡ በብዙ ፡
አውሺዎች ፡ ወንዶችና ፡ አውሺ
ዎች ፡ ሴቶችም ፡ አላህ ፡ ለነርሱ ፡
ምሕረትንና ፡ ታላቅን ፡ ምንዳ ፡
አዘጋጅቶላቸዋል ።

36 አላህና ፡ መልክተኛውም ፡ ነገ
ርን ፡ በፈረዱ ፡ ጊዜ ፡ ለምእም
ናንና ፡ ለምእምናት ፡ ከነገራቸው ፡
ለነርሱ ፡ ምርጫ ፡ ሊኖራቸው ፡
አይገባም ! የአላህንና ፡ የመልክ
ተኛውንም ፡ ትእዛዝ ፡ የጣሰ ፡
ሰው ፡ ግልጥ ፡ የኾነን ፡ መሳሳት ፡
በእርግጥ ፡ ተሳሳተ ።
37 ለዚያም ፡ አላህ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
ለለገሰለትና ፡ (አንተም ፡ ነጻ ፡
በማውጣት) ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ለለገ
ስክለት ፡ ሰው ፡ (ለዘይድ) ፡ አላህ ፡
ገላጩ ፡ የኾነን ፡ ነገር ፡ በነፍስህ ፡
ውስጥ ፡ የምትደብቅና ፡ አላህ ፡
ልትፈራው ፡ ይልቅ ፡ የተገባው ፡
ሲኾን ፡ ሰዎችን ፡ የምትፈራ ፡
ኾነህ ፡— ሚስትህን ፡ ባንተ ፡
ዘንድ ፡ ያዝ ፤ (ከመፍታት) ፡ አላ
ህንም ፡ ፍራ ፤ በምትል ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ) ፤ ዘይድም ፡ ከርሷ ፡
ጉዳይን ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ (1) በም
እምናኖች ፡ ላይ ፡ ልጅ ፡ አድርገው፡
ባስጠጉዋቸው ፡ (ሰዎች) ፡ ሚስ
ቶች ፡ ከነሱ ፡ ጉዳይን ፡ በፈጸሙ ፡
ጊዜ ፡ (በማግባት) ፡ ችግር ፡ እንዳ
ይኖርባቸው ፡ እርሷን ፡ አጋባንህ፤
የአላህም ፡ ትእዛዝ ፡ ተፈጻሚ ፡
ነው ።
38 በነቢዩ ፡ ላይ ፡ አላህ ፡ ለርሱ ፡
በፈረደው ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ ችግር፡
ሊኖርበት ፡ አይገባም ፤ በነዚያ ፡
ከዚያ ፡ በፊት ፡ ባለፉት ፡ (ነቢ
ያት) ፡ አላህ ፡ ደነገገው ፤ የአላ
ህም ፡ ትእዛዝ ፡ የተፈረደ ፡ ፍ
ርድ ፡ ነው ።
39 ለነዚያ ፡ የአላህን ፡ መልክቶች ፡
ለሚያደርሱና ፡ ለሚፈሩት ፡ ከአ

1 ፍላጎቱን ፡ አርክቶ ፡ በፈታትና ፡ ዒዳዋን ፡
በጨረሰች ፡ ጊዜ ፡



ላህ ፡ በስተቀርም ፡ አንድንም ፡
ለማይፈሩት ፡ (ተደነገገ) ፤ ተቆ
ጣጣሪም ፡ በአላህ ፡ በቃ ።
40 ሙሐመድ ፡ ከወንዶቻችሁ ፡ የአ
ንድም ፡ ሰው ፡ አባት ፡ አይደለም ፡
ግን ፡ የአላህ ፡ መልክተኛና ፡ የነ
ቢዮች ፡ መደምደሚያ ፡ ነው ፤
አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።
41 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላ
ህን ፡ ብዙ ፡ ማውሳትን ፡ አው
ሱት ።
42 በቀኑ ፡ መጀመሪያና ፡ መጨረ
ሻም ፡ አጥሩት ።
43 እርሱ ፡ ያ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ እዝ
ነትን ፡ የሚያወርድ ፡ ነው ፤ መላ
እክቶቹም ፡ (እንደዚሁ ፡ ምሕረ
ትን ፡ የሚለምኑላችሁ ፡ ናቸው) ፤
ከጨለማዎች ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡
ያወጣችሁ ፡ ዘንድ ፡ (ያዝንላች
ኋል) ፤ ለአማኞችም ፡ በጣም ፡
አዛኝ ፡ ነው ።
44 በሚገናኙት ፡ ቀን ፡ መከባበሪ
ያቸው ፡ ሰላም ፡ መባባል ፡ ነው ፤
ለነርሱም ፡ የከበረን ፡ ምንዳ ፡
አዘጋጅቶላቸዋል ።
45 አንተ ፡ ነቢዩ ፡ ሆይ ! እኛ ፡ መስ
ካሪ ፡ አብሳሪና ፡ አስፈራሪም ፡
አድርገን ፡ ላክንህ ።
46 ወደ ፡ አላህም ፡ በፈቃዱ ፡ ጠሪ ፡
አብሪ ፡ ብርሃንም ፡ (አድርገን ፡
ላክንህ) ፤
47 አማኞችንም ፡ ከአላህ ፡ ዘንድ ፡
ለነርሱ ፡ ታላቅ ፡ ችሮታ ፡ ያላ
ቸው ፡ መኾኑን ፡ አብስራቸው ።
48 ከሓዲዎችንና ፡ መናፍቃንንም ፡
አትታዘዛቸው ፤ ማሰቃየታቸው
ንም ፡ (ለአላህ) ፡ ተው ፤ (1) በአላ
ህም ፡ ላይ ፡ ተጠጋ ፤ መጠጊያም ፡
በአላህ ፡ በቃ ።
49 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ምእ
ምናትን ፡ ባገባችሁና ፡ ከዚያም ፡
ሳትነኩዋቸው ፡ በፊት ፡ በፈታች
ኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ለናንተ ፡ በነሱ ፡
ላይ ፡ የምትቆጥሩዋት ፡ ዒዳ ፡ (2)
ምንም ፡ የላችሁም ፡ አጣቅሟቸ
ውም ፤ (ጉርሻ ፡ ስጡዋቸው) ፤
መልካም ፡ ማሰናበትንም ፡ አሰና
ብቷቸው ።
50 አንተ ፡ ነቢዩ ፡ ሆይ ! እኛ ፡ እነዚ
ያን ፡ መህሮቻቸውን ፡ (3) የሰጠ
ሃቸውን ፡ ሚስቶችህን ፡ አላህ ፡
ባንተ ፡ ላይ ፡ ከመለሰልህም ፡ እነ
ዚያን ፡ እጅህ ፡ የጨበጠቻቸውን ፡
ምርኮኞች ፡ እነዚያንም ፡ ከአን
ተ ፡ ጋር ፡ የተሰደዱትን ፡ የአጎት
ህን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ የአክስቶ
ችህንም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ የየሹ
ማህንም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ የየሹ
ሜዎችህንም ፡ (4) ሴቶች ፡ ልጆች ፡
(ማግባትን) ፡ ለአንተ ፡ ፈቅደን
ልሃል ፤ የአመነችንም ፡ ሴት ፡
ነፍሷን ፡ (ራሷን) ፡ ለነቢዩ ፡ ብት
ሰጥ ፡ ነቢዩ ፡ ሊያገባት ፡ የፈለገ ፡
እንደ ፡ ኾነ ፡ ከምእምናን ፡ ሌላ ፡
ላንተ ፡ ብቻ ፡ የጠራች ፡ ስትኾን ፡
(ፈቀድንልህ) ፤ በነርሱ ፡ (በምእ
ምናን) ፡ ላይ ፡ በሚስቶቻቸውና ፡

1 በምዕራፍ ፡ 22 ፡ አንቀጽ ፡ 39 ፡ ለሚገደሉ፡
ሰዎች ፡ መጋደል ፡ ተፈቀደላቸው ፡ በሚ
ለው ፡ ተሽሮአል ።

2 ሦስት ፡ ደም ፡ ጥራት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡
ወር ፡ መታገሥ ።

3 የቅጥር ፡ ገንዘቦቻቸውን ።

4 አጎት -የአባት፡ ወንድም፡ ብቻ፡ የሹማ
የእናት፡ ወንድም፤ አክስት -የአባት፡ እኅት
ብቻ የሹሜ፡ የእናት፡ እኅት፡ ናቸው።

እጆቻቸው ፡ በጨበጧቸው ፡ (ባ
ሮች ፡ ነገር) ፡ ግዴታ ፡ ያደረግን
ባቸውን ፡ በእርግጥ ፡ ዐውቀናል ፤
ባንተ ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ እንዳይኖር ፡
(ያለፉትን ፡ ፈቀድንልህ) ፤ አላ
ህም ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።

51 ከነሱ ፡ የምትሻትን ፡ ታቆያለህ ፤
የምትሻትንም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡
ታስጠጋለህ ፤ (በመፍታት) ፡ ከአ
ራቅሃትም ፡ የፈለግሃትን ፡ (በመ
መለስ ፡ ብታስጠጋ) ፡ በአንተ ፡
ላይ ፡ ኀጢአት ፡ የለብህም ፤ ይህ ፡
ዓይኖቻቸው ፡ ወደ ፡ መርጋት ፡
ወደ ፡ አለማዘናቸውም ፡ ለሁሉም፡
በሰጠሃቸው ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ መው
ደዳቸውም ፡ በጣም ፡ የቀረበ ፡
ነው ፤ አላህም ፡ በልቦቻችሁ ፡
ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ያው
ቃል ፤ አላህም ፡ ዐዋቂ ፡ ታጋሽ ፡
ነው ።

52 ከነዚህ ፡ በኋላ ፡ እጅህ ፡ ከጨበጠ
ቻቸው ፡ (ባሮች) ፡ በስተቀር ፡
ሴቶች ፡ ለአንተ ፡ አይፈቀዱል
ህም ፤ ከሚስቶችም ፡ መልካቸው ፡
ቢደንቅህም ፡ እንኳ ፡ በነርሱ ፡
ልታላውጥ ፡ (አይፈቀድልህም) ፤
አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ተጠባባቂ ፡ ነው ።

53 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! መድ
ረሱን ፡ የማትጠባበቁ ፡ ስትኾኑ ፡
ወደ ፡ ምግብ ፡ ካልተፈቀደላችሁ ፡
በስተቀር ፡ የነቢዩን ፡ ቤቶች ፡
(በምንም ፡ ጊዜ) ፡ አትግቡ ፤ ግን ፡
በተጠራችሁ ፡ ጊዜ ፡ ግቡ ፤ በተ
መገባችሁም ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡
ተበተኑ ፤ ለወግ ፡ የምትጫወቱ ፡
ኾናችሁም ፡ (አትቆዩ) ፤ ይሃችሁ ፡
ነቢዩን ፡ በእርግጥ ፡ ያስቸግራል ፤
ከናንተም ፡ ያፍራል ፤ ግን ፡ አላህ ፡
ከውነት ፡ አያፍርም ። ዕቃንም ፡
(ለመዋስ) ፡ በጠየቃችኋቸው ፡
ጊዜ ፡ ከመጋረጃ ፡ ኋላ ፡ ኾናችሁ ፡
ጠይቋቸው ፤ ይሃችሁ ፡ ለልቦቻ
ችሁ ፤ ለልቦቻቸውም ፡ የበለጠ ፡
ንጽሕና ፡ ነው ፤ የአላህንም ፡ መል
ክተኛ ፡ ልታስቸግሩ ፡ ሚስቶቹ
ንም ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ምንጊዜም ፡
ልታገቡ ፡ ለናንተ ፡ አይገባችሁም፤
ይሃችሁ ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡ ከባድ ፡
(ኀጢአት) ፡ ነው ።

54 ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ብትገልጹ ፡
ወይም ፡ ብትደብቁት ፡ (በርሱ ፡
ይመነዳችኋል) ፤ አላህ ፡ ነገሩን ፡
ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።

55 (የነቢዩ ፡ ሚስቶች) ፡ በአባቶቻ
ቸው ፡ በወንዶች ፡ ልጆቻቸውም ፡
በወንድሞቻቸውም ፡ በወንድሞ
ቻቸው ፡ ወንዶች ፡ ልጆችም ፡
በእኅቶቻቸው ፡ ወንዶች ፡ ልጆ
ችም ፡ (ምእምናት ፡ በኾኑት) ፡
በሴቶቻቸውም ፡ እጆቻቸው ፡
በጨበጧቸውም ፡ ባሮች ፡ (አጠ
ገብ ፡ በመገለጥ) ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
ኀጢአት ፡ የለባቸውም ፤ (ሴቶች ፡
ሆይ ! ታዘዙ) ፡ አላህንም ፡ ፍሩ ፤
አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ መስ
ካሪ ፡ ነውና ።

56 አላህና ፡ መላእክቱ ፡ በነቢዩ ፡
ላይ ፡ የአክብሮት ፡ እዝነትን ፡
ያወርዳሉ ፤ እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡
ሆይ ! በርሱ ፡ ላይ ፡ የአክብሮት ፡
እዝነትን ፡ አውርዱ ፤ የማክበር
ንም ፡ ሰላምታ ፡ ሰላም ፡ በሉ ።

57 እነዚያ ፡ አላህንና ፡ መልክተኛ
ውን ፡ የሚያስከፉ ፡ በቅርቢቱ ፡
ዓለም ፡ በመጨረሻይቱም ፡ አላህ፡
ረግሟቸዋል ፤ ለነርሱም ፡ አዋራ
ጅን ፡ ቅጣት ፡ ደግሶላቸዋል ።



58 እነዚያም ፡ ምእምናንንና ፡ ምእ
ምናትን ፡ ባልሠሩት ፡ ነገር ፡
(በመዝለፍ) ፡ የሚያሰቃዩ ፡ ዕብ
ለትንና ፡ ግልጽ ፡ ኀጢአትን ፡ በእ
ርግጥ ፡ ተሸከሙ ።

59 አንተ ፡ ነቢዩ ፡ ሆይ ! ለሚስቶ
ችህ ፡ ለሴቶች ፡ ልጆችህም ፡ ለም
እምናን ፡ ሚስቶችም ፡ ከመከናነ
ቢያዎቻቸው ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡
እንዲለቁ ፡ ንገራቸው ፤ ይህ ፡ እን
ዲታወቁና ፡ (በባለጌዎች) ፡ እንዳ
ይደፈሩ ፡ ለመኾን ፡ በጣም ፡ የቀ
ረበ ፡ ነው ፤ አላህም ፡ መሐሪ ፡
አዛኝ ፡ ነው ።

60 መናፍቃንና ፡ እነዚያ ፡ በልቦቻ
ቸው ፡ ውስጥ ፡ (የአመንዝራነት) ፡
በሽታ ፡ ያለባቸው ፡ በመዲናም ፡
ውስጥ ፡ (በወሬ) ፡ አሸባሪዎቹ ፡
(ከዚህ ፡ ሥራቸው) ፡ ባይከለከሉ ፡
በነርሱ ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ እንቀሰ
ቅስሃለን ፤ ከዚያም ፡ በርሷ ፡
ውስጥ ፡ ጥቂትን ፡ እንጂ ፡ አይጎ
ራበቱህም ።

61 የተረገሙ ፡ ኾነው ፡ እንጂ ፡ (አይ
ጎራበቱህም) ፤ በየትም ፡ ስፍራ ፡
ቢገኙ ፡ ይያዛሉ ፤ መገደልንም ፡
ይገደላሉ ።

62 (ይህቺ) ፡ በነዚያ ፡ በፊት ፡ ባለ
ፉት ፡ (ላይ ፡ የደነገጋት) ፡ የአ
ላህ ፡ ድንጋጌ ፡ ናት ፤ ለአላህም ፡
ድንጋጌ ፡ ፈጽሞ ፡ መለወጥን ፡
አታገኝም ።

63 ሰዎቹ ፡ ከሰዓቲቱ ፡ ይጠይቁሃል ፤
ዕውቀትዋ ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡
ነው ፤ በላቸው ፤ የሚያሳውቅህም፡
ምንድን ፡ ነው ! ሰዓቲቱ ፡ በቅ
ርብ ፡ ጊዜ ፡ ልትኾን ፡ ይከጀላል ።

64 አላህ ፡ ከሓዲዎችን ፡ በእርግጥ ፡
ረግሟቸዋል ፤ ለነርሱም ፡ የተጋ
ጋመችን ፡ እሳት ፡ አዘጋጅቷል ።

65 በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ዘለዓለም ፡ ዘው
ታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፤ ወዳጅም ፡ ረዳ
ትም ፡ አያገኙም ።

66 ፊቶቻቸው ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡
በሚገለባበጡ ፡ ቀን ፡ ዋ ፡ ምኞታ
ችን ! አላህን ፡ በተገዛን ፡ መልክ
ተኛውንም ፡ በታዘዝን ፡ ኖሮ ፡
እያሉ ፡ ይጸጸታሉ ፤

67 ይላሉም ፡— ጌታችን ፡ ሆይ !
እኛ ፡ ጌቶቻችንንና ፡ ታላላቆቻ
ችንን ፡ ታዘዝን ፤ መንገዱንም ፡
አሳሳቱን ፤

68 ጌታችን ፡ ሆይ ! ከቅጣቱ ፡ እጥ
ፍን፡ ስጣቸው፤ ታላቅን፡ እርግ
ማንም፡ እርገማቸው።

69 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! እን
ደነዚያ ፡ ሙሳን ፡ እንዳሰቃዩት ፡
ሰዎች ፡ አትኹኑ ፤ ካሉትም ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ አላህ ፡ አጠራው ፤
አላህም ፡ ዘንድ ፡ ባለሞገሥ ፡
ነበር ።

70 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላ
ህን ፡ ፍሩ ፤ ትክክለኛንም ፡ ንግ
ግር ፡ ተናገሩ ።

71 ሥራዎቻችሁን ፡ ለናንተ ፡ ያበጅ
ላችኋልና ፡ ኀጢአቶቻችሁንም ፡
ለናንተ ፡ ይምርላችኋል ፤ አላህ
ንና ፡ መልክተኛውን ፡ የሚታዘ
ዝም ፡ ሰው ፡ በእርግጥ ፡ ታላቅን ፡
ዕድል ፡ አገኘ ።

72 እኛ ፡ አደራን ፡ በሰማያትና ፡ በ
ምድር ፡ በተራራዎችም ፡ ላይ ፡
አቀረብናት ፤ መሸከሟንም ፡ እ
ንቢ ፡ አሉ ፤ ከርሷም ፡ ፈሩ ፤
ሰውም ፡ ተሸከማት ፤ እርሱ ፡
በጣም ፡ በደለኛ ፡ ተሳሳች ፡ ነውና፤

73 መናፍቃንንና ፡ መናፍቃትን ፡
ወንዶች ፡ አጋሪዎችንና ፡ ሴቶች ፡
አጋሪዎችንም ፡ አላህ ፡ ሊቀጣና ፡
በምእምናንና ፡ በምእምናትም ፡
ላይ ፡ አላህ ፡ ንስሓን ፡ ሊቀበል ፡
(አደራዋን ፡ ሰው ፡ ተሸከማት) ፤
አላህም ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡
ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 34 ፡ ሰበእ ። ክፍል ፡ 22 ።

34ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ሰበእ ፤ (የሰበእ ፡ ምዕራፍ) ፤ በመካ ፡ የወ
ረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 54 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 ምስጋና ፡ ለዚያ ፡ በሰማያትም ፡
ያለ ፡ በምድርም ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡
የርሱ ፡ ለኾነው ፡ ለአላህ ፡ ይገ
ባው ፤ በመጨረሻይቱም ፡ ዓለም ፡
ምስጋና ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤
እርሱም ፡ ብልሃተኛው ፡ ውስጠ ፡
ዐዋቂው ፡ ነው ።

2 በምድር ፡ ውስጥ ፡ የሚገባውን ፡
ሁሉ ፡ ከርሷም ፡ የሚወጣውን ፡
ከሰማይም ፡ የሚወርደውን ፡ በር
ሷም ፡ ውስጥ ፡ የሚያርገውን ፡
ሁሉ ፡ ያውቃል ፤ እርሱም ፡
አዛኙ ፡ መሓሪው ፡ ነው ።

3 እነዚያ ፡ የካዱትም ፡ ሰዓቲቱ ፡
አትመጣብንም ፡ አሉ ፤ በላቸው ፡
—አይደለም ፤ ሩቁን ፡ ሁሉ ፡
ዐዋቂ ፡ በኾነው ፡ ጌታዬ ፡ እምላ
ለሁ ፤ በእርግጥ ፡ ትመጣባችኋ
ለች ፤ የብናኝ ፡ ክብደት ፡ ያክል ፡
እንኳ ፡ በሰማያትና ፡ በምድር ፡
ውስጥ ፡ ከርሱ ፡ አይርቅም ፤
ከዚህ ፡ ያነሰም ፡ ኾነ ፡ የበለጠ ፡
የለም ፡ በግልጹ ፡ መጽሐፍ ፡
ውስጥ ፡ የተመዘገበ ፡ ቢኾን ፡
እንጅ ።

4 እነዚያን ፡ ያመኑትንና ፡ መልካ
ሞችን ፡ የሠሩትን ፡ ሊመነዳ ፡
(ሰዓቲቱ ፡ ትመጣባችኋለች) ፤
እነዚያ ፡ ለነሱ ፡ ምሕረትና ፡ የከ
በረ ፡ ሲሳይ ፡ አላቸው ።

5 እነዚያም ፡ የሚያመልጡ ፡ መስ
ሏቸው ፡ አንቀጾቻችንን ፡ ለማፍ
ረስ ፡ የጣሩ ፡ እነዚያ ፡ ለነርሱ ፡
ከመጥፎ ፡ ቅጣት ፡ የኾነ ፡ አሳ
ማሚ ፡ ስቃይ ፡ አላቸው ።

6 እነዚያም ፡ ዕውቀትን ፡ የተሰ
ጡት ፡ ያንን ፡ ከጌታህ ፡ ወዳ
ንተ ፡ የተወረደውን ፡ እርሱ ፡
እውነትና ፡ አሸናፊ ፡ ምስጉን ፡
ወደ ፡ ኾነው ፡ አላህ ፡ መንገድ ፡
የሚመራ ፡ መኾኑን ፡ ያውቃሉ ።

7 እነዚያም ፡ የካዱት ፡— (ሙታ
ችሁ) ፡ መበጣጠስን ፡ ሁሉ ፡ በተ
በጣጠሳችሁ ፡ ጊዜ ፡ እናንተ ፡
በአዲስ ፡ መፈጠር ፡ ውስጥ ፡ ትኾ
ናላችሁ ፡ ብሎ ፡ የሚነግራችሁን ፡
ሰው ፡ እናሳያችሁን ? አሉ ።



8 በአላህ ፡ ላይ ፡ ውሸትን ፡ ቀጠ
ፈን ? ወይስ ፡ በርሱ ፡ ዕብደት ፡
አለበትን ? (አሉ) ፤ እንዳሉት ፡
አይደለም ፤ እነዚያ ፡ በመጨረሻ
ይቱ ፡ (ዓለም) ፡ የማያምኑት ፡ (በር
ሷ) ፡ በቅጣት ፡ ውስጥ ፡ (አሁን) ፡
በራቀ ፡ ስሕተትም ፡ ውስጥ ፡
ናቸው ።

9 ከሰማይና ፡ ከምድር ፡ በፊታቸ
ውና ፡ በኋላቸው ፡ ወዳለው ፡
ሁሉ ፡ አይመለከቱምን ? ብንሻ ፡
በነርሱ ፡ ምድርን ፡ እንደረባባቸ
ዋለን ፤ ወይም ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡
ከሰማይ ፡ ቁራጭን ፡ እንጥልባቸ
ዋለን ፤ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ (ወደ ፡
ጌታው) ፡ ተመላሽ ፡ ለኾነ ፡ ባሪያ ፡
ሁሉ ፡ ምልክት ፡ አለበት ።

10 ለዳውድም ፡ ከኛ ፡ የኾነን ፡ ችሮታ
በእርግጥ ፡ ሰጠነው ፤ (አልንም) ፡
፡— ተራራዎች ፡ ሆይ ! ከርሱ ፡
ጋር ፡ ውዳሴን ፡ መላልሱ ፤ በራ
ሪዎችንም ፡ (ገራንለት) ፤ ብረት
ንም ፡ ለርሱ ፡ አለዘብንለት ።

11 ሰፋፊዎችን ፡ ጥሩሮች ፡ (1) ሥራ ፤
በአሠራርዋም ፡ መጥን ፤ መልካ
ምንም ፡ ሥራ ፡ ሥሩ ፤ እኔ ፡ የም
ትሠሩትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተመል
ካች ፡ ነኝና ፡ (አልነው) ።

12 ለሱለይማንም ፡ ነፋስን ፡ የቀትር ፡
በፊት ፡ ጉዞዋ ፡ የወር ፡ መንገድ ፡
የቀትር ፡ በኋላ ፡ ጉዞዋም ፡ የወር ፡
መንገድ ፡ ሲኾን ፡ ገራንለት ፤
የነሐስንም ፡ ምንጭ ፡ ለርሱ ፡
አፈሰስንለት ፤ ከጋኔኖችም ፡ በጌ
ታው ፡ ፈቃድ ፡ በፊቱ ፡ የሚሠ
ሩን ፡ (አደረግንለት) ፤ ከነሱም ፡
ውስጥ ፡ ከትእዛዛችን ፡ ገንፍ ፡

1 የብረት ፡ ቀሚሶች ።

የሚል ፡ ከነዲድ ፡ እሳት ፡ ቅጣት ፡
እናቀምሰዋለን ።

13 ከምኩራቦች ፡ ከምስሎችም ፡
እንደ ፡ ገንዳ ፡ ከኾኑ ፡ ገበታዎ
ችም ፡ ከተደላደሉ ፡ ታላላቅ ፡
ድስቶችም ፡ የሚሻውን ፡ ሁሉ ፡
ይሠሩለታል ፤ (አልናቸውም) ፡—
የዳውድ ፡ ቤተሰቦች ፡ ሆይ ! አመ
ስጋኞች ፡ ኾናችሁ ፡ (ለጌታችሁ) ፡
ሥሩ ፤ ከባሮቼ ፡ በጣም ፡ አመስጋ
ኞቹም ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ።

14 በርሱም ፡ ላይ ፡ ሞትን ፡ በፈጸም
ንበት ፡ ጊዜ ፡ መሞቱን ፡ በት
ሩን ፡ የምትበላ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡
ምስጥ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አላመለከታ
ቸውም ፤ በወደቀ ፡ ጊዜም ፡ ጋኔ
ኖች ፡ ሩቅን ፡ ምስጢር ፡ የሚያ
ውቁ ፡ በኾኑ ፡ ኖሮ ፡ በአዋራጅ ፡
ስቃይ ፡ ውስጥ ፡ የማይቆዩ ፡ እንደ
ነበሩ ፡ ተረዱ ።

15 ለሰበእ ፡ (1) በመኖሪያቸው ፡ በው
ነት ፡ አስደናቂ ፡ ምልክት ፡ ነበራ
ቸው ፡ ከግራና ፡ ከቀኝ ፡ ሁለት ፡
አትክልቶች ፡ (ነበሩዋቸው) ፤
ከጌታችሁ ፡ ሲሳይ ፡ ብሉ ፤ ለር
ሱም ፡ አመስግኑ ፤ (አገራችሁ) ፡
ውብ ፡ አገር ፡ ናት ፤ (ጌታችሁ) ፡
መሓሪ ፡ ጌታም ፡ ነው ፤ (ተባሉ) ።

16 (ከማመስገን) ፡ ዞሩም ፤ በነርሱም ፡
ላይ ፡ የግድቡን ፡ ጐርፍ ፡ ለቀቅን
ባቸው ፤ በአትክልቶቻቸውም ፡
ሁለትን ፡ አትክልቶች ፡ ባለ ፡
መርጋጋ ፡ ፍሬዎችን ፡ ባለ ፡
ጠደቻና ፡ ከቁርቁራም ፡ ባለ ፡
ጥቂት ፡ ዛፎችን ፡ ለወጥናቸው ።

17 በመካዳቸው ፡ ይህንን ፡ መነዳና
ቸው ፤ (እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ቅጣት)

1 የአገር ፡ ወይም ፡ ነገዶች ፡ ስም ።

በጣም ፡ ከሓዲን ፡ እንጂ ፡ ሌላ
ውን ፡ እንቀጣለን ?
18 በነርሱና ፡ በዚያች ፡ በውስጧ ፡
በረከትን ፡ ባደረግንባት ፡ አገር ፡
(በሻም) ፡ መካከልም ፡ ቅጥልጥል፡
ከተሞችን ፡ አደረግን ፤ በርሷም ፡
ጉዞን ፡ ወሰንን ፤ ጸጥተኞች ፡ ኾና
ችሁ ፡ በሌሊቶችም ፡ በቀኖችም ፡
ተጓዙ ፤ (አልን) ።
19 ጌታችን ፡ ሆይ ! በጉዞዎቻችን ፡
መካከል ፡ አራርቅልን ፡ አሉም ፤
ነፍሶቻቸውንም ፡ በደሉ ፤ (መገረ
ሚያ) ፡ ወሬዎችም ፡ አደረግና
ቸው ፤ መበታተንንም ፡ ሁሉ ፡
በታተንናቸው ፤ በዚህ ፡ ውስጥ ፡
በጣም ፡ ታጋሽና ፡ አመስጋኝ ፡
ለኾነ ፡ ሁሉ ፡ መገሠጫዎች ፡
አሉበት ።
20 ኢብሊስም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ምኞ
ቱን ፡ በእርግጥ ፡ ፈጸመ ፤ ከአመኑ
ትም ፡ የኾኑት ፡ ጭፍሮች ፡ በስ
ተቀር ፡ ተከተሉት ።
21 በመጨረሻይቱም ፡ ዓለም ፡ የሚ
ያምነውን ፡ ከዚያ ፡ እርሱ ፡ ከርሷ፡
በመጠራጠር ፡ ውስጥ ፡ ከኾነው ፡
ሰው ፡ ለይተን ፡ እንድናውቅ ፡
እንጅ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ለርሱ ፡
ምንም ፡ ሥልጣን ፡ አልነበረውም
ጌታህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ተጠባባቂ ፡ ነው ።
22 እነዚያን ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ (አማል
ክት ፡ ብላችሁ) ፡ የምታስቧቸ
ውን ፡ ጥሩ ፤ በሰማያትም ፡ በምድ
ርም ፡ ውስጥ ፡ የብናኝ ፡ ክብደት ፡
ያክል ፡ ምንንም ፡ አይችሉም ፤
ለነርሱም ፡ በሁለቱም ፡ ውስጥ ፡
ምንም ፡ ሽርክና ፡ የላቸውም ፤
ከነርሱም ፡ ለርሱ ፡ ምንም ፡
አጋዥ ፡ የለውም ፤ በላቸው ።
23 ምልጃም ፡ እርሱ ፡ ለፈቀደለት ፡
ሰው ፡ ብቻ ፡ ቢኾን ፡ እንጂ ፡
እርሱ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ አትጠ
ቅምም ፤ ከልቦቻቸው ፡ ላይ ፡
ድንጋጤው ፡ በተገለጠም ፡ ጊዜ ፡
(ተማላጆቹ) ፡ ጌታችሁ ፡ ምን ፡
አለ ? ይላሉ ፤ (አማላጆቹ) ፡ እውነ
ትን ፡ አለ ፤ እርሱም ፡ ከፍተኛው ፡
ታላቁ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ ይላሉ ።
24 ፡—ከሰማያትና ፡ ከምድር ፡ (ዝና
ምንና ፡ በቃይን) ፡ የሚሰጣችሁ ፡
ማነው ? በላቸው ፤ አላህ ፡ ነው ፡
እኛ ፡ ወይም ፡ እናንተ ፡ በትክክ
ለኛው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡
በግልጽ ፡ መሳሳት ፡ ውስጥ ፡
ነን ፡ በላቸው ።
25 ፡—ከአጠፋነው ፡ ጥፋት ፡ አትጠ
የቁም ፤ ከምትሠሩትም ፡ ሥራ ፡
አንጠየቅም ፤ በላቸው ።
26 ፡—ጌታችን ፡ በመካከላችን ፡ ይሰ
በስባል ፤ ከዚያም ፡ በመካከላችን ፡
በውነት ፡ ይፈርዳል ፤ እርሱም ፡
በትክክል ፡ ፈራጁ ፡ ዐዋቂው ፡
ነው ፡ በላቸው ።
27 ፡—እነዚያን ፡ ተጋሪዎች ፡ አድር
ጋችሁ ፡ በርሱ ፡ ያስጠጋችኋቸ
ውን ፡ (ጣዖታት) ፡ አሳዩኝ ፤
ተዉ ፡ (አታጋሩ) ፤ በውነቱ ፡
እርሱ ፡ አሸናፊው ፡ ብልሃተኛው ፡
አላህ ፡ ነው ፤ በላቸው ።
28 አንተንም ፡ ለሰዎች ፡ ሁሉ ፡
በመላ ፡ አብሳሪና ፡ አስፈራሪ ፡
አድርገን ፡ ቢኾን ፡ እንጂ ፡ አልላ
ክንህም ፤ ግን ፡ አብዛኞቹ ፡ ሰዎች፡
አያውቁም ።
29 ፡-እውነተኞችም ፡ እንደ ፡ ኾና
ችሁ ፡ ይህ ፡ ቀጠሮ ፡ መቼ ፡ ነው ?
ይላሉ ።



30 ለናንተ ፡ ከርሱ ፡ አንዲትንም ፡
ሰዓት ፡ የማትዘገዩበት ፡ የማትቀ
ድሙበትም ፡ የቀጠሮ ፡ ቀን ፡
አላችሁ ፡ በላቸው ።
31 እነዚያ ፡ የካዱትም ፡ በዚህ ፡
ቁርአን ፡ በዚያ ፡ ከበፊቱ ፡ ባለ
ውም ፡ (መጽሐፍ) ፡ በጭራሽ ፡
አናምንም ፡ አሉ ፤ በዳዮችም ፡
ከፊላቸው ፡ ወደ ፡ ከፊሉ ፡ ንግግ
ርን ፡ የሚመላለሱ ፡ ኾነው ፡ በጌ
ታቸው ፡ ዘንድ ፡ በሚቆሙ ፡ ጊዜ ፡
ብታይ ፡ ኖሮ ፤ (አስደናቂን ፡
ነገር ፡ ታይ ፡ ነበር) ፤ እነዚያ ፡
የተዋረዱት ፡ ለነዚያ ፡ ለኮሩት ፡
እናንተ ፡ ባልነበራችሁ ፡ ኖሮ ፡
አማኞች ፡ በኾን ፡ ነበር ፡ ይላሉ ።
32 እነዚያ ፡ የኮሩት ፡ ለነዚያ ፡ ለተዋ
ረዱት ፡ ከትክክለኛው ፡ እምነት ፡
ከመጣላችሁ ፡ በኋላ ፡ እኛ ፡ ከለከ
ልናችሁን ? አይደለም ፡ (እናን
ተው) ፡ ከሓዲዎች ፡ ነበራችሁ ፡
ይሏቸዋል ።
33 እነዚያም ፡ የተዋረዱት ፡ ለነዚያ ፡
ለኮሩት ፡ አይደለም ፤ በአላህ ፡
እንድንክድና ፡ ለርሱ ፡ ባላንጣዎ
ችን ፡ እንድናደርግ ፡ ስታዙን ፡
(የከለከለን) ፡ የሌሊትና ፡ የቀን ፡
ዱለታችሁ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፤ ቅጣ
ቱንም ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ጸጸትን ፡ ይገ
ልጣሉ ፤ በነዚያም ፡ በካዱት ፡
አንገቶች ፡ ላይ ፡ እንዛዝሎችን ፡
እናደርጋለን ፤ ይሠሩት ፡ የነበሩ
ትን ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡ ይመነዳሉን ?
34 በከተማዎ ፡ አስፈራሪን ፡ አልላክ
ንም ፡ ነዋሪዎችዋ ፡ እኛ ፡
በዚያ ፡ በርሱ ፡ በተላካችሁበት ፡
ከሓዲዎች ፡ ነን ፡ ያሉ ፡ ቢኾኑ ፡
እንጂ ።
35 እኛም ፡ በገንዘቦችና ፡ በልጆች ፡
ይበልጥ ፡ የበዛን ፡ ነን ፤ እኛም ፡
የምንቀጣ ፡ አይደለንም ፡ አሉ ።
36 በላቸው ፡— ጌታዬ ፡ ሲሳይን ፡
ለሚሻው ፡ ሰው ፡ ያሰፋል ፤ ያጠ
ባልም ፤ ግን ፡ አብዛኞዎቹ ፡
ሰዎች ፡ አያውቁም ።
37 ገንዘቦቻችሁና ፡ ልጆቻችሁም ፡
ያች ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ መቅረብን ፡
የምታቀርባችሁ ፡ አይደለችም ፤
ያመነና ፡ መልካምን ፡ የሠራ ፡
ብቻ ፡ ሲቀር ፤ እነዚያ ፡ ለነርሱ ፡
በሠሩት ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡
እጥፍ ፡ ምንዳ ፡ አላቸው ፤ እነ
ሱም ፡ በገነት ፡ ሰገነቶች ፡ ውስጥ ፡
ጸጥተኞች ፡ ናቸው ።
38 እነዚያም ፡ የሚያቅቱ ፡ መስሏ
ቸው ፡ አንቀጾቻችንን ፡ ለማበላ
ሸት ፡ የሚጥሩት ፡ እነዚያ ፡ በቅ
ጣቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚጣዱ ፡ ናቸው።
39 ፡—ጌታዬ ፡ ሲሳይን ፡ ከባሮቹ ፡
ለሚሻው ፡ ሰው ፡ ያሰፋል ፤ ለር
ሱም ፡ ያጠባል ፤ ከማንኛውም ፡
ነገር ፡ የምትለግሱትን ፡ እርሱ ፡
ይተካዋል ፤ እርሱም ፡ ከሲሳይ ፡
ሰጪዎች ፡ ሁሉ ፡ በላጭ ፡ ነው ፡
በላቸው ።
40 ሁሉንም ፡ በሚሰበስባቸውና ፡
ከዚያም ፡ ለመላእክቶቹ ፡ እነዚህ ፡
እናንተን ፡ ይግገዙ ፡ ነበሩን ?
በሚላቸው ፡ ቀን ፡ (የሚኾነውን ፡
አስታውስ) ።
41 (መላእክቶቹም) ፡ ጥራት ፡ ይገ
ባህ ፡ ከነሱ ፡ ሌላ ፡ ረዳታችን ፡
አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህ ፤ (እንደሚ
ሉት) ፡ አይደለም ፡ ይልቁንም ፡
ጋኔንን ፡ ይግገዙ ፡ ነበሩ ፤ አብዛኞ
ቻቸው ፡ በነርሱ ፡ አማኞች ፡
ናቸው ፡ ይላሉ ።

42 ዛሬም ፡ ከፊላችሁ ፡ ለከፊሉ ፡
መጥቀምንም ፡ ኾነ ፡ መጉዳትን ፡
አይችሉም ፤ ለነዚያም ፡ ለበደ
ሉት ፡ ያችን ፡ በርሷ ፡ ታስተባብ
ሉባት ፡ የነበራችሁትን ፡ የእሳት ፡
ቅጣት ፡ ቅመሱ ፡ እንላቸዋለን ።

43 በነርሱም ፡ ላይ ፡ አንቀጾቻችን ፡
ግልጽ ፡ ኾነው ፡ በተነበቡላቸው ፡
ጊዜ ፡ ይህ ፡ አባቶቻችሁ ፡ ይግገ
ዙት ፡ ከነበሩት ፡ ነገር ፡ ሊከለክ
ላችሁ ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አይደለም ፡ አሉ ፤ ይህም ፡
(ቁርአን) ፡ የተቀጣጠፈ ፡ ውሸት ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፡
አሉ ፤ እነዚያም ፡ የካዱት ፡ እውነ
ቱ ፡ በመጣላቸው ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡
ግልጥ ፡ ድግምት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አይደለም ፡ አሉ ።

44 የሚያጠኑዋቸው ፡ የኾኑ ፡ መጽሐ
ፎችንም ፡ ምንም ፡ አልሰጠናቸ
ውም ፤ ከአንተ ፡ በፊትም ፡ አስ
ፈራሪ ፡ ነቢይን ፡ ወደነርሱ ፡ አል
ላክንም ።

45 እነዚያም ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡ የነበ
ሩት ፡ አስተባብለዋል ፤ የሰጠናቸ
ውንም ፡ ከዐሥር ፡ አንዱን ፡
(እነዚህ) ፡ አልደረሱም ፤ መልክ
ተኞቼንም ፡ አስተባበሉ ፤ (ነቀፍኳ
ቸውም) ፤ መንቀፌም ፡ እንዴት ፡
ነበር !

46 የምገሥጻችሁ ፡ ባንዲት ፡ ነገር ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ (እርሷም) ፡ ሁለት ፡
ሁለት ፡ አንድ ፡ አንድም ፡ ኾና
ችሁ ፡ ለአላህ ፡ እንድትነሱ ፡
ከዚያም ፡ በጓደኛችሁ ፡ (ቢሙሐ
መድ) ፡ ምንም ፡ ዕብደት ፡ የሌለ
በት ፡ መኾኑን ፡ መርምራችሁ ፡
እንድትረዱ ፡ ነው ፤ እርሱ ፡ ለና
ንተ ፡ ከብርቱ ፡ ቅጣት ፡ በስተ
ፊት ፡ አስጠንቃቂ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አይደለም ፡ በላቸው ።

47 ከዋጋ ፡ ማንኛውም ፡ የጠየቅኋ
ችሁ ፡ ቢኖር ፡ እርሱ ፡ ለናንተው ፡
ነው ፤ ዋጋዬ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡
እንጂ ፡ በሌላ ፡ ላይ ፡ አይደለም ፡
እርሱም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ፡ በላቸው ።

48 ፡—ጌታዬ ፡ እውነትን ፡ ያወር
ዳል ፤ ሩቅ ፡ የኾኑትን ፡ ምስጢ
ሮች ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፡ በላ
ቸው ።

49 እውነቱ ፡ መጣ ፤ ውሸትም ፡ መነ
ሻም ፡ መድረሻም ፡ የለውም ፡ (ተ
ወገደ) ፡ በላቸው ።

50 ብሳሳት ፡ የምሳሳተው ፡ በራሴ ፡
ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ብምመራም ፡
ጌታዬ ፡ ወደኔ ፡ በሚያወርደው ፡
ነው ፤ እርሱ ፡ ሰሚ ፡ ቅርብ ፡
ነውና ፡ በላቸው ።

51 በደነገጡና ፡ ማምለጫ ፡ በሌላ
ቸው ፡ ጊዜ ፡ ከቅርብ ፡ ስፍራም ፡
በተያዙ ፡ ጊዜ ፡ (ኹኔታቸውን) ፡
ብታይ ፡ ኖሮ ፡ (አስደናቂን ፡ ነገር፡
ባየህ ፡ ነበር) ።

52 በርሱም ፡ (አሁን) ፡ አመንን ፡
ይላሉ ፤ ለነርሱም ፡ ከሩቅ ፡ ስፍራ፡
(እምነትን) ፡ በቀላል ፡ ማግኘት ፡
ከየታቸው ?

53 በፊትም ፡ በርሱ ፡ በእርግጥ ፡ ክደ
ዋል ፡ ከሩቅ ፡ ስፍራም ፡ በግምት ፡
ንግግርን ፡ ይጥላሉ ።

54 ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በመሰሎቻቸው ፡
እንደ ፡ ተሠራውም ፡ ብጤ ፡ በነር
ሱና ፡ በሚፈልጉት ፡ መካከል ፡
ተጋረደ ፤ እነርሱ ፡ በእርግጥ ፡
በአወላዋይ ፡ ጥርጣሬ ፡ ውስጥ ፡
ነበሩና ።



35ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ፋጢር ፤ (የፈጣሪ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 45 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው።

1 ምስጋና ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡
ፈጣሪ ፡ መላእክትን ፡ ባለ ፡ ሁለት፡
ሁለት ፡ ባለ ፡ ሦስት ፡ ሦስትም ፡
ባለ ፡ አራት ፡ አራትም ፡ ክንፎች ፡
የኾኑ ፡ መልክተኞች ፡ አድራጊ ፡
ለኾነው ፡ አላህ ፡ ይገባው ፤ በፍጥ
ረቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚሻውን ፡ ይጨ
ምራል ፤ አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ቻይ ፡ ነውና ።

2 አላህ ፡ ለሰዎች ፡ ከችሮታ ፡ የሚ
ከፍታት ፡ ለርሷ ፡ ምንም ፡ አጋጅ፡
የላትም ፤ የሚያግደውም ፡ ከርሱ ፡
በኋላ ፡ ለርሱ ፡ ምንም ፡ ለቃቂ ፡
የለውም ፤ እርሱም ፡ አሸናፊው ፡
ጥበበኛው ፡ ነው ።

3 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! በናንተ ፡
ላይ ፡ (ያለውን) ፡ የአላህን ፡ ጸጋ ፡
አስታውሱ ፤ ከአላህ ፡ ሌላ ፡
ፈጣሪ ፡ አልለን ? ከሰማይና ፡
ከምድርም ፡ ሲሳይን ፡ የሚሰጣ
ችሁ ፡ አልለን ? ከርሱ ፡ በስተቀር፡
አምላክ ፡ (ሰጪም) ፡ የለም ፤
ታዲያ ፡ ወዴት ፡ ትዞራላችሁ ።

4 ቢያስተባብሉህም ፡ ከአንተ ፡
በፊት ፡ የነበሩ ፡ መልክተኞች ፡
በእርግጥ ፡ ተስተባብለዋል ፤ ወደ ፡
አላህም ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ይመለ
ሳሉ ።

5 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! የአላህ ፡
ቀጠሮ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ የቅር
ቢቱም ፡ ሕይወት ፡ አትታታላችሁ ፤
አታላዩም ፡ (ሰይጣን) ፡ በአላህ ፡
(መታገሥ) ፡ አያታላችሁ ፤

6 ሰይጣን ፡ ለናንተ ፡ ጠላት ፡ ነው ፤
ስለዚህ ፡ ጠላት ፡ አድርጋችሁ ፡
ያዙት ፤ ተከታዮቹን ፡ የሚጠ
ራው ፡ ከእሳት ፡ጓዶች ፡ እንዲ
ኾኑ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

7 እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ለነርሱ ፡
ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ፤ እነዚ
ያም ፡ ያመኑትና ፡ በጎ ፡ ሥራ
ዎችን ፡ የሠሩት ፡ ለነርሱ ፡ ምሕ
ረትና ፡ ታላቅ ፡ ምንዳ ፡ አላቸው ።

8 መጥፎ ፡ ሥራው ፡ የተሸለመለ
ትና ፡ መልካም ፡ አድርጎ ፡ ያየው ፡
ሰው ፡ (አላህ ፡ እንዳቀናው ፡ ሰው ፡
ነውን ?) አላህም ፡ የሚሻውን ፡
ሰው ፡ ያጠምማል ፤ የሚሻው
ንም ፡ ያቀናል ፤ ስለዚህ ፡ በነርሱ ፡
ላይ ፡ (ባለመቅናታቸው) ፡ ስለመ
ቆላጨት ፡ ነፍስህ ፡ አትጥፋ ፤
አላህ ፡ የሚሠሩትን ፡ ሁሉ ፡
ዐዋቂ ፡ ነውና ።

9 አላህም ፡ ያ ፡ ነፋሶችን ፡ የላከ ፡
ነው ፤ ደመናዎችንም ፡ ትቀሰቅ
ሳለች ፤ ወደ ፡ ሙት ፡ (ድርቅ) ፡
አገርም ፡ እንነዳዋለን ፤ በርሱም ፡
ምድርን ፡ ከሞተች ፡ በኋላ ፡
ሕያው ፡ እናደርጋታለን ፤ ሙታ
ንንም ፡ መቀስቀስ ፡ እንደዚሁ ፡
ነው ።

10 ማሸነፍን ፡ የሚፈልግ ፡ የኾነ ፡
ሰው ፡ አሸናፊነት ፡ ለአላህ ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ (እርሱን ፡ በመግገ

ዛት ፡ ይፈልገው) ፤ መልካም ፡
ንግግር ፡ ወደርሱ ፡ ይወጣል ፤
በጎ ፡ ሥራም ፡ ከፍ ፡ ያደርገዋል ፤
እነዚያም ፡ መጥፎ ፡ ሥራዎችን ፡
የሚዶልቱ ፡ ለነሱ ፡ ብርቱ ፡
ቅጣት ፡ አላቸው ፤ የነዚያም ፡
ተንኮል ፡ እርሱ ፡ ይጠፋል ።

11 አላህም ፡ ከዐፈር ፡ ከዚያም ፡ ከፍ
ትወት ፡ ጠብታ ፡ ፈጠራችሁ ፤
ከዚያም ፡ ጐሳዎች ፡ አደረጋችሁ ፤
ሴትም ፡ አታረግዝም ፡ አትወል
ድምም ፡ በዕውቀቱ ፡ ቢኾን ፡
እንጂ ፤ ዕድሜው ፡ ከሚረዘምም ፡
አንድም ፡ አይረዘምም ፡ ከዕድ
ሜውም ፡ አይጐደልም ፡ በመጽ
ሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ያልለ ፡ ቢኾን ፡
እንጂ ፤ ይህ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ገር ፡
ነው ።

12 ሁለቱ ፡ ባሕሮችም ፡ አይተካከ
ሉም ! ይህ ፡ ጣፋጭ ፡ ጥምን ፡
ቆራጭ ፡ መጠጡ ፡ በገር ፡ ተዋጭ፡
ነው ፤ ይህኛውም ፡ ጨው ፡ መር
ጋጋ ፡ ነው ፤ (1) እርጥብ ፡ ስጋ
ንም ፡ ከሁሉም ፡ ትበላላችሁ ፤
(ከጨው ፡ ባሕር) ፡ የምትለብሷ
ትንም ፡ ጌጥ ፡ ታወጣላችሁ ፤
ከችሮታው ፡ ልትፈልጉና ፡ ልታ
መሰግኑም ፡ መርከቦችን ፡ በርሱ ፡
ውስጥ ፡ ውሃውን ፡ ቀዳጆች ፡
ኾነው ፡ (ሲንሻለሉ) ፡ ታያለህ ።

13 ሌሊትን ፡ በቀን ፡ ውስጥ ፡ ያስገ
ባል ፤ ቀንንም ፡ በሌሊት ፡ ውስጥ ፡
ያስገባል ፤ ፀሐይንና ፡ ጨረቃ
ንም ፡ ገራ ፤ ሁሉም ፡ እተወሰነ ፡
ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ይሮጣሉ ፤ ይሃችሁ ፡
ጌታችሁ ፡ አላህ ፡ ነው ፤ ንግሥ
ናው ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ እነዚ
ያም ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ የምትግገዟ
ቸው ፡ የተምር ፡ ፍሬ ፡ ሺፋን ፡
እንኳ ፡ አይኖራቸውም ።

14 ብትጠሩዋቸው ፡ ጥሪያችሁን ፡
አይሰሙም ፤ ቢሰሙም ፡ ኖሮ ፡
ለናንተ ፡ አይመልሱላችሁም ፤
በትንሣኤም ፡ ቀን ፡ (እነርሱን ፡
በአላህ) ፡ ማጋራታችሁን ፡ ይክ
ዳሉ ፤ እንደ ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂው ፡
ማንም ፡ አይነግርህም ።

15 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ! እናንተ ፡
(ሁል ፡ ጊዜ) ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ከጃ
ዮች ፡ ናችሁ ፤ አላህም ፡ እርሱ ፡
ተብቃቂው ፡ ምስጉኑ ፡ ነው ።

16 ቢሻ ፡ ያስወግዳችኋል ፤ አዲስ
ንም ፡ ፍጡር ፡ ያመጣል ።

17 ይህም ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡
አስቸጋሪ ፡ አይደለም ።

18 ኀጢአትን ፡ ተሸካሚም ፡ (ነፍስ) ፡
የሌላዋን ፡ ሸክም ፡ አትሸከምም ፤
የተከበደችም ፡ (ነፍስ) ፡ (1) ወደ ፡
ሸክሟ ፡ ብትጠራ ፡ (ተጠሪው) ፡
የቅርብ ፡ ዝምድና ፡ ባለቤት ፡
ቢኾንም ፡ እንኳ ፡ ከርሷ ፡ አን
ዳችን ፡ የሚሸከምላት ፡ አታገ
ኝም ። የምታስጠነቅቀው ፡ እነ
ዚያን ፡ ጌታቸውን ፡ በሩቅ ፡ የሚ
ፈሩትን ፡ ሦላትንም ፡ አስተካክ
ለው ፡ ያደረሱትን ፡ ብቻ ፡ ነው ፤
የተጥራራም ፡ ሰው ፡ የሚጥራ
ራው ፡ ለራሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ መመ
ለሻም ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

19 ዕውሩና ፡ የሚያየውም ፡ አይተ
ካከሉም ።

20 ጨለማዎችና ፡ ብርሃንም ፤ (እን
ደዚሁ) ።

21 ጥላና ፡ ሐሩርም ፤

1 ይህ ፡ ለምእምናንና ፡ ለከሐዲ ፡ ምሳሌ ፡
ነው ።

1 ከባድ ፡ ሸክም ፡ የተጫነች ።



22 ሕያዋንና ፡ ሙታንም ፡ አይስተካ
ከሉም ፤ አላህ ፡ የሚሻውን ፡ ሰው ፡
ያስሰማል ። አንተም ፡ በመቃብር ፡
ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ አስሰሚ ፡ አይ
ደለህም ።

23 አንተ ፡ አስጠንቃቂ ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አይደለህም ።

24 እኛ ፡ አብሳሪና ፡ አስፈራሪ ፡ አድ
ርገን ፡ በውነቱ ፡ (መምሪያ) ፡
ላክንህ ፤ ማንኛይቱም ፡ ሕዝብ ፡
በውስጧ ፡ አስፈራሪ ፡ ያላለፈባት ፡
የለችም ።

25 ቢያስተባብሉህም ፡ እነዚያ ፡ ከበ
ፊታቸው ፡ የነበሩት ፡ በእርግጥ ፡
አስተባብለዋል ፤ መልክተኞቻቸ
ው ፡ በግልጽ ፡ ማስረጃዎች ፡ በጽ
ሑፎችም ፡ አብራሪ ፡ በኾነ ፡ መጽ
ሐፍም ፡ መጥተዋቸዋል ።

26 ከዚያም ፡ እነዚያን ፡ የካዱትን ፡
ያዝኳቸው ፤ ቅጣቴም ፡ እንዴት ፡
ነበር ! (በስፍራው ፡ ነው) ።

27 አላህ ፡ ከሰማይ ፡ ውሃን ፡ ማውረ
ዱን ፡ አላየህምን ? በርሱም ፡
ዓይነቶቻቸው ፡ የተለያዩ ፡ ፍሬ
ዎችን ፡ አወጣን ፤ ከጋራዎችም ፡
መልኮቻቸው ፡ የተለያዩ ፡ ነጮች ፡
ቀዮችም ፡ በጣም ፡ ጥቁሮችም ፡
የኾኑ ፡ መንገዶች ፡ አሉ ።

28 ከሰዎችም ፡ ከተንቀሳቃሾችም ፡
ከቤት ፡ እንስሳዎችም ፡ እንደ
ዚሁ ፡ መልኮቻቸው ፡ የተለያዩ ፡
አሉ ፤ አላህን ፡ ከባሮቹ ፡ ውስጥ ፡
የሚፈሩት ፡ ዐዋቂዎቹ ፡ ብቻ ፡
ናቸው ፤ አላህ ፡ አሸናፊ ፡ መሐሪ ፡
ነው ።

29 እነዚያ ፡ የአላህን ፡ መጽሐፍ ፡
የሚያነቡ ፡ ሶላትንም ፡ አስተካ
ክለው ፡ ያደረሱ ፡ ከሰጠናቸውም ፡
ሲሳይ ፡ በምስጢርም ፡ ኾነ ፡ በግ
ልጽ ፡ የለገሱ ፡ በፍጹም ፡ የማት
ከስርን ፡ ንግድ ፡ ተስፋ ፡ ያደር
ጋሉ ።

30 ምንዳዎቻቸውን ፡ ሊሞላላቸው ፡
ከችሮታውም ፡ ሊጨምርላቸው ፡
(ተስፋ ፡ ያደርጋሉ) ፤ እርሱ ፡
በጣም ፡ መሓሪ ፡ አመስጋኝ ፡
ነውና ።

31 ያም ፡ ከመጽሐፉ ፡ ወዳንተ ፡ ያወ
ረድንልህ ፡ ከበፊቱ ፡ ላለው ፡ አረ
ጋጋጭ ፡ ሲኾን ፡ እርሱ ፡ እው
ነት ፡ ነው ፤ አላህ ፡ በርግጥ ፡ በባ
ሮቹ ፡ ውስጥ ፡ ዐዋቂ ፡ ተመል
ካች ፡ ነው ።

32 ከዚያም ፡ እነዚያን ፡ ከባሮቻችን ፡
የመረጥናቸውን ፡ መጽሐፉን ፡
አወረስናቸው ፤ ከነርሱም ፡ ነፍ
ሱን ፡ በዳይ ፡ አልለ ፤ ከነርሱም ፡
መካከለኛ ፡ አልለ ፤ ከነሱም ፡ በአ
ላህ ፡ ፈቃድ ፡ በበጎ ፡ ሥራዎች ፡
ቀዳሚ ፡ አልለ ፤ ያ ፡ (ማውረስ) ፡
እርሱ ፡ ታላቅ ፡ ችሮታ ፡ ነው ።

33 የመኖሪያ ፡ ገነቶችን ፡ በውስጧ ፡
የወርቅ ፡ አንባሮችን ፡ሉልንም ፡
የሚሸለሙ ፡ ኾነው ፡ ይገቡባ
ታል ፤ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ አልባሳ
ታቸውም ፡ ሐር ፡ ነው ።

34 ይላሉም ፡— ምስጋና ፡ ለዚያ ፡
ከኛ ፡ ላይ ፡ ሐዘንን ፡ ላስወገደ
ልን ፡ አላህ ፡ ይገባው ፤ ጌታችን ፡
በጣም ፡ መሐሪ ፡ አመስጋኝ ፡
ነውና ።

35 (እርሱም) ፡ ያ ፡ ከችሮታው ፡ የዘ
ላለም ፡ መኖሪያን ፡ አገር ፡ ያሰፈ
ረን ፡ ነው ፤ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ መከራ
አይነካንም ፤ በርሷም ፡ ውስጥ ፡
ድካም ፡ አይነካንም ።

36 እነዚያ ፡ የካዱትም ፡ ለነርሱ ፡ የገ
ሀነም ፡ እሳት ፡ አላቸው ፤ ይሞቱ ፡
ዘንድ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ (በሞት) ፡
አይፈረድም ፤ ከቅጣቷም ፡ ከነሱ ፡
አይቀለልላቸውም ፤ እንደዚሁ ፡
ከሓዲን ፡ ሁሉ ፡ እንመነዳለን ።
37 እነርሱም ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ እርዳ
ታን ፡ በመፈለግ ፡ በኀይል ፡ ይጮ
ሃሉ ፤ ጌታችን ፡ ሆይ ! ከዚያ ፡
እንሠራው ፡ ከነበርነው ፡ ሌላ ፡
በጎ ፡ ሥራን ፡ እንሠራ ፡ ዘንድ ፡
አውጣን ፡ (ይላሉ) ፤ በርሱ ፡ ውስጥ ፡
ያስታወሰ ፡ ሰው ፡ የሚገሠጥበትን ፡
ዕድሜ ፡ አላቆየናችሁምን ? አስ
ጠንቃቂውም ፡ መጥቶላችኋል !
(አስተባብላችኋልም) ፤ ስለዚህ ፡
ቅመሱ ፤ ለበደለኞችም ፡ ምንም ፡
ረዳት ፡ የላቸውም ፡ (ይባላሉ) ።
38 አላህ ፡ የሰማያትንና ፡ የምድርን ፡
ምስጢር ፡ በእርግጥ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ፤ እርሱ ፡ በልቦች ፡ ውስጥ ፡
ያለን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።
39 እርሱ ፡ ያ ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡
ምትኮች ፡ ያደረጋችሁ ፡ ነው ፤
የካደም ፡ ሰው ፡ ክሕደቱ ፡ በር
ሱው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ከሓዲ
ዎችንም ፡ ክሕደታቸው ፡ ከጌታ
ቸው ፡ ዘንድ ፡ መጠላትን ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ አይጨምርላቸውም ፤ ከሓዲ
ዎችንም ፡ ክሕደታቸው ፡ ከሳ
ራን ፡ እንጂ ፡ አይጨምርላቸውም ፤
40 በላቸው ፡— እነዚያን ፡ ከአላህ ፡
ሌላ ፡ የምትግገዟቸውን ፡ ተጋሪ
ዎቻችሁን ፡ አያችሁን ? ከምድር ፡
ምንን ፡ እንደ ፡ ፈጠሩ ፡ አሳዩኝ ፡
ወይስ ፡ ለነርሱ ፡ በሰማያት ፡ ው
ስጥ ፡ ሽርክና ፡ አላቸውን ? ወይስ ፡
መጽሐፍን ፡ ሰጥናቸውና ፡ እነ
ርሱ ፡ ከርሱ ፡ በግልጽ ፡ አስረጅ ፡
ላይ ፡ ናቸውን ? አይደለም ፡ በደ
ለኞች ፡ ከፊላቸው ፡ ከፊሉን ፡
ማታለልን ፡ እንጂ ፡ አይቀጥሩም ።
41 አላህ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡
እንዳይወገዱ ፡ ይይዛቸዋል ፤ ቢወ
ገዱም ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ አንድም ፡
የሚይዛቸው ፡ የለም ፤ እነሆ ፡
እርሱ ፡ ታጋሽ ፡ መሓሪ ፡ ነውና ።
42 አስፈራሪም ፡ ቢመጣላቸው ፡
ከሕዝቦቹ ፡ ሁሉ ፡ ከአንደኛዋ ፡
ይበልጥ ፡ የተመሩ ፡ ሊኾኑ ፡ የመ
ሐላቸውን ፡ ዲካ ፡ አድርሰው ፡
በአላህ ፡ ማሉ ፤ አስፈራሪም ፡
በመጣላቸው ፡ ጊዜ ፡ መበርገግን ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ አልጨመረላቸ
ውም ።
43 በምድር ፡ ላይ ፡ ኩራትንና ፡ በክፉ
(ተንኮል) ፡ መዶለትንም ፡ (እንጂ ፡
አልጨመረላቸውም) ፤ ክፉ ፡ ተን
ኮልም ፡ በባለ ፡ ቤቱ ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡
በሌላ ፡ ላይ ፡ አይሰፍርም ፤ የቀድ
ሞዎቹን ፡ ደንብ ፡ እንጂ ፡ ይጠባ
በቃሉን ? ለአላህ ፡ ደንብም ፡
መልለወጥን ፡ አታገኝም ፤ ለአ
ላህ ፡ ደንብም ፡ መዛወርን ፡ አታ
ገኝም ።
44 በምድር ፡ ላይ ፡ አይኼዱምና ፡ የነ
ዚያን ፡ ከነርሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩ
ትን ፡ ሰዎች ፡ መጨረሻ ፡ እን
ዴት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አይመለከቱ
ምን ? ከነርሱም ፡ በኀይል ፡ የበ
ረቱ ፡ ነበሩ ፤ አላህም ፡ በሰማያ
ትም ፡ ኾነ ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡
ምንም ፡ ነገር ፡ የሚያቅተው ፡
አይደለም ፤ እርሱ ፡ ዐዋቂ ፡ ቻይ ፡
ነውና ።
45 አላህም ፡ ሰዎችን ፡ በሠሩት ፡
ኀጢአት ፡ ቢይዝ ፡ ኖሮ ፡ በወ
ለሏ ፡ (በምድር) ፡ ላይ ፡ ምንም ፡



ተንቀሳቃሽ ፡ ባልተወ ፡ ነበር ፤
ግን ፡ እተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡
ያቆያቸዋል ፤ ጊዜያቸውም ፡ በ
መጣ ፡ ወቅት ፡ (በኀጢአታቸው ፡
ይቀጣቸዋል) ፤ አላህ ፡ በባሮቹ ፡
(ኹኔታ) ፡ ተመልካች ፡ ነውና ።

## ምዕራፍ ፡ 36 ፡ ያሲን ። ክፍል ፡ 22 ።

36ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ያሲን ፡ (የያሲን ፡ ምዕራፍ) ፤ በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 83 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በኾነው ።
1 የ. ሰ. (ያ ፡ ሲን) ፡ (1)
2 ጥበብ ፡ በተመላበት ፡ ቁርአን ፡
እምላለሁ ፤
3 አንተ ፡ በእርግጥ ፡ ከመልክተ
ኞቹ ፡ ነህ ።
4 በቀጥታው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡
ነህ ።
5 አሸናፊ ፡ አዛኝ ፡ ከሆነው ፡ አም
ላክ ፡ መወረድን ፡ ተወረደ ።
6 አባቶቻቸው ፡ ያልተስፈራሩትን ፡
ሕዝቦች ፡ ልታስጠነቅቅበት ፡
(ተወረደ) ። እነርሱ ፡ ዘንጊዎች ፡
ናቸውና ።
7 በአብዛኞቻቸው ፡ ላይ ፡ ቃሉ ፡
በውነት ፡ ተረጋገጠ ፤ ስለዚህ ፡
እነርሱ ፡ አያምኑም ።
8 እኛ ፡ በአንገቶቻቸው ፡ ላይ ፡ እን
ዛዝላዎችን ፡ አደረግን ፤ እርሷም ፡
(እንዛዝላይቱ) ፡ ወደ ፡ አገጮቻ
ቸው ፡ ደራሽ ፡ ናት ፤ እነርሱም ፡
ራሶቻቸውን ፡ ያንጋጠጡ ፡ ናቸው ።
(2)
9 ከስተፊታቸውም ፡ ግርዶን ፡ ከስ
ተኋላቸውም ፡ ግርዶን ፡ አደረ
ግን ፤ ሸፍፈንናቸውም ፤ ስለዚህ ፡
እነሱ ፡ አያዩም ።
10 ብታስጠነቅቃቸውም ፡ ባታስጠነ
ቅቃቸውም ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡
እኩል ፡ ነው ፤ አያምኑም ።
11 የምታስጠነቅቀው ፡ ግሣጼን ፡
የተከተለንና ፡ አልረሕማንን ፡
በሩቅ ፡ የፈራን ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡
ነው ፤ በምሕረትና ፡ በመልካም ፡
ምንዳም ፡ አብስረው ።
12 እኛ ፡ ሙታንን ፡ እኛ ፡ በእርግጥ ፡
ሕያው ፡ እናደርጋለን ፤ ያስቀደ
ሙትንም ፡ ሥራ ፡ ፈለጎቻቸው
ንም ፡ እንጽፋለን ፤ ነገሩንም ፡
ሁሉ ፡ ገላጭ ፡ መሪ ፡ በኾነ ፡
መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ አጠቃለል
ነው ።
13 ለነሱም ፡ የከተማይቱን ፡ (የአን
ጣኪያን) ፡ ሰዎች ፡ ምሳሌ ፡ መል

1 አንተ ፡ ሰው ፡

2 እጅካንገት ፡ የታሠረ ፡ ሰው ፡ ለመዘዟር ፡
እንደማይችል ፡ ወደ ፡ እምነት ፡ አያዘነብ
ሉም ።

ክተኞቹ ፡ በመጧት ፡ ጊዜ ፡ (የኾ
ነውን) ፡ ግለጽላቸው ።
14 ወደነርሱ ፡ ሁለትን ፡ ሰዎች ፡ በላ
ክንና ፡ ባስተባበሉዋቸው ፡ ጊዜ ፡
በሦስተኛም ፡ በአበረታንና ፡ እኛ ፡
ወደ ፡ እናንተ ፡ መልክተኞች ፡
ነን ፡ ባሏቸው ፡ ጊዜ ፡ (የኾነ
ውን ፡ ምሳሌ ፡ ግለጽላቸው) ።
15 እናንተ ፡ መሰላችን ፡ ሰዎች ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደላችሁም ፤
አልረሕማንም ፡ ምንም ፡ ነገር ፡
አላወረደም ፤ እናንተ ፡ የምት
ዋሹ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደላች
ሁም ፡ አሉዋቸው ።
16 (መልክተኞቹም) ፡ አሉ ፡— ጌታ
ችን ፡ ያውቃል ፤ እኛ ፡ ወደናንተ ፡
በእርግጥ ፡ መልክተኞች ፡ ነን ፤
17 በኛ ፡ ላይም ፡ ግልጽ ፡ የኾነ ፡
ማድረስ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የለብንም ።
18 (ሕዝቦቹም) ፡— እኛ ፡ በናንተ ፡
ገደ ፡ ቢሶች ፡ ኾን ፤ ባትከከለከሉ ፡
በእርግጥ ፡ እንወግራችኋለን ፤ ከኛ
ም ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ በእርግጥ ፡
ያገኛችኋል ፤ አሉ ።
19 ገደ ፡ ቢስነታችሁ ፡ ከናንተው ፡
ጋር ፡ ነው ፤ ብትገገሠጹ ፡ (ትዝ
ታላችሁን ?) በውነቱ ፡ እናንተ ፡
ወሰን ፡ አላፊዎች ፡ ሕዝቦች ፡
ናችሁ ፡ አሏቸው ።
20 ከከተማይቱም ፡ ሩቅ ፡ዳርቻ ፡
የሚሮጥ ፡ ሰው ፡ መጣ ፤ ወገኖቼ ፡
ሆይ ! መልክተኞቹን ፡ ተከተሉ ፡
አለ ።
21 እነርሱ ፡ ቅኑን ፡ መንገድ ፡ የተ
መሩ ፡ሲኾኑ ፡ ዋጋን ፡ የማይጠ
ይቁዋችሁን ፡ ሰዎች ፡ ተከተሉ ፡
(አላቸው) ።

★ ★ ★

22 ያንንም ፡ የፈጠረኝን ፤ ወደርሱም ፡
የምትመለሱበትን ፡ (ጌታ) ፡ የማ
ልግገዛ ፡ ለኔ ፡ ምን ፡ አለኝ ?
(አለ) ።
23 ከርሱ ፡ ሌላ ፡ አማልክትን ፡ እይ
ዛለሁን ? አልረሕማን ፡ በጉዳት ፡
ቢሻኝ ፡ ምልጃቸው ፡ ከኔ ፡ (ለመ
መለስ) ፡ ምንም ፡ አትጠቅመ
ኝም ፤ አያድኑኝምም ፤
24 እኔ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በግልጽ ፡ ስሕ
ተት ፡ ውስጥ ፡ ነኝ ፤
25 እኔ ፡ በጌታችሁ ፡ አመንኩ ፤ ስሙ
ኝም ፤ (አለ) ።
26 ገነትን ፡ ግባ ፡ ተባለ ፤ (እርሱም) ፡
አለ ፡— ወገኖቼ ፡ ቢያውቁ ፡
እመኛለሁ ፤
27 ጌታዬ ፡ ለኔ ፡ ምሕረት ፡ ያደረገል
ኝና ፡ ከተከበሩትም ፡ ያደረገኝ ፡
መኾኑን ።
28 ከርሱም ፡ በኋላ ፡ በሕዝቦቹ ፡
ላይ ፡ (ልናጠፋቸው) ፡ ሰራዊ
ትን ፡ ከሰማይ ፡ አላወረድንም ፤
(በማንም ፡ ላይ) ፡ አውራጆችም ፡
አልነበርንም ።
29 (ቅጣታቸው) ፡ አንዲት ፡ ጩኸት ፡
እንጂ ፡ ሌላ ፡ አልነበረችም ፤ ወዲ
ያውኑም ፡ እነርሱ ፡ ጠፊዎች ፡
ኾኑ ።
30 በባሮቹ ፡ ላይ ፡ ዋ ፡ ቁልጭት !
ከመልክተኛ ፡ አንድም ፡ አይመ
ጣቸውም ፡ በርሱ ፡ የሚሳለቁ
በት ፡ ቢኾኑ ፡ እንጅ ።
31 ከነሱ ፡ በፊት ፡ ከክፍለ ፡ ዘመ
ናት ፡ ሕዝቦች ፡ ብዙዎችን ፡
ማጥፋታችንንና ፡ እነሱ ፡ ወደነ
ርሱ ፡ የማይመለሱ ፡ መኾናቸ
ውን ፡ አላወቁምን ?



32 ሁሉም ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ የሚሰበ
ሰቡ ፡ የሚቀረቡ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡
አይደሉም ።
33 የሞተችውም ፡ ምድር ፡ ለነሱ ፡
ምልክት ፡ ናት ! ሕያው ፡ አደ
ረግናት ፤ ከርሷም ፡ ፍሬን ፡
አወጣን ፤ ከርሱም ፡ ይበላሉ ።
34 በርሷም ፡ ውስጥ ፡ ከዘምባባዎ
ችና ፡ ከወይኖች ፡ የኾኑ ፡ አትክል
ቶችን ፡ አደረግን ፤ በርሷም ፡
ውስጥ ፡ ምንጮችን ፡ አፈለቅን ።
35 ከፍሬውና ፡ እጆቻቸው ፡ ከሠሩ
ትም ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ (ይህን ፡
አደረግን) ፤ አያመሰግኑምን ?
36 ያ ፡ ምድር ፡ ከምታበቅለው ፡ ከነ
ፍሶቻቸውም ፡ ከማያውቁትም ፡
ነገር ፡ ዓይነቶችን ፡ ሁሏንም ፡
የፈጠረ ፡ (አምላክ) ፡ ጥራት ፡
ይገባው ።
37 ሌሊቱም ፡ ለነሱ ፡ ምልክት ፡
ነው ፤ ከርሱ ፡ ላይ ፡ ቀንን ፡ እንገ
ፍፋለን ፡ ወዲያውኑም ፡ እነሱ ፡
በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።
38 ፀሐይም ፡ ለርሷ ፡ ወደ ፡ ኾነው ፡
መርጊያ ፡ ትሮጣለች ፤ ይህ ፡ የአ
ሸናፊው ፡ የዐዋቂው ፡ አምላክ ፡
ውሳኔ ፡ ነው ።
39 ጨረቃንም ፡ የመስፈሪያዎች ፡ (1)
ባለቤት ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ ዘንባባ ፡
አሮጌ ፡ ቀንዘል ፡ እስኪኾን ፡
ድረስ ፡ (መኼዱን) ፡ ለካነው ።
40 ፀሐይ ፡ ጨረቃን ፡ ልትደርስበት ፡
አይገባትም ፤ ሌሊትም ፡ ቀንን ፡
(ያለ ፡ ጊዜው) ፡ ቀዳሚ ፡ አይኾ
ንም ፤ ሁሉም ፡ በመዞሪያቸው ፡
ውስጥ ፡ ይዋኛሉ ።
41 እኛም ፡ (የቅድም) ፡ ትውልዳቸ
ውን ፡ በተመላች ፡ መርከብ ፡
ውስጥ ፡ የጫን ፡ መኾናችን ፡
ለነርሱ ፡ ምልክት ፡ ነው ።
42 ከመሰሉም ፡ በርሱ ፡ የሚሳፈሩበ
ትን ፡ ለነርሱ ፡ ፈጠርንላቸው ።
43 ብንሻም ፡ እናሰጥማቸዋለን ፤ ለነ
ርሱም ፡ ረዳት ፡ የላቸውም ፤ እነ
ርሱም ፡ የሚድዳኑ ፡ አይደሉም ።
44 ግን ፡ ከኛ ፡ ለኾነው ፡ ችሮታና ፡
እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞታቸው ፡ ለማጣ
ቀም ፡ (አዳናቸው) ።
45 ለነርሱም ፡ በስተፊታችሁና ፡
በኋላችሁ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ተጠ
ንቀቁ ፡ ይታዘንላችኋልና ፡ በተ
ባሉ ፡ ጊዜ ፡ (ፊታቸውን ፡ ያዞ
ራሉ) ።
46 ከጌታቸውም ፡ ታምራት ፡ ማንኛ
ይቱም ፡ ታምር ፡ አትመጣላቸ
ውም ፤ ከርሷ ፡ የሚሸሹ ፡ ቢኾኑ ፡
እንጅ ።
47 ለነሱም ፡ አላህ ፡ ከሰጣችሁ ፡
ሲሳይ ፡ ለግሱ ፡ በተባሉ ፡ ጊዜ ፡
እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ለነዚያ ፡ ላመ
ኑት ፡— አላህ ፡ ቢሻ ፡ ኖሮ ፡ የሚ
ያበላውን ፡ ሰው ፡ እናበላለን ?
እናንተ ፡ በግልጽ ፡ ስሕተት ፡
ውስጥ ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ ላይ ፡
አይደላችሁም ፡ ይላሉ ።
48 እውነተኞችም ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡
ይህ ፡ቀጠሮ ፡ መቼ ፡ ነው ? ይላሉ ፤
49 እነርሱ ፡ የሚከራከሩ ፡ ሲኾኑ ፡
በድንገት ፡ የምትይዛቸው ፡ የኾነ
ችን ፡ አንዲትን ፡ ጩኸት ፡ እንጂ ፡
ሌላን ፡ አይጠባበቁም ።
50 (ያን ፡ ጊዜ) ፡ መናዘዝንም ፡ አይ
ችሉም ፤ ወደ ፡ ቤተሰቦቻቸውም ፡
አይመለሱም ።

1 በየሌሊቱ ፡ የሚሰፍርባቸው ።

51 በቀንዱም ፡ ይነፋፋል ፤ ወዲያው
ኑም ፡ እነርሱ ፡ ከመቃብሮቻ
ቸው ፡ ወደ ፡ ጌታቸው ፡ በፍጥ
ነት ፡ ይገሠግሣሉ ።
52 ወይ ፡ ጥፋታችን ! ከምኝታችን ፡
ማን ፡ ቀሰቀሰን ? ይህ ፡ ያ ፡ አዛኙ ፡
ጌታ ፡ (በርሱ) ፡ የቀጠረን ፡ መል
ክተኞቹም ፡ እውነትን ፡ የነገሩን፡
ነው ፡ ይላሉ ።
53 (እርሷ) ፡ አንዲት ፡ ጩኸት ፡
እንጂ ፡ አይደለችም ፤ ወዲያው
ኑም ፡ እነርሱ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ የሚ
ሰሰበሰቡ ፡ የሚቀርቡ ፡ ናቸው ።
54 ዛሬም ፡ ማንኛይቱም ፡ ነፍስ ፡
ምንም ፡ አትበደልም ፤ ትሠሩ
ትም ፡ የነበራችሁትን ፡ እንጂ ፡
ሌላን ፡ አትመነዱም ፡ (ይባላሉ)።
55 የገነት ፡ ሰዎች ፡ ዛሬ ፡ በእርግጥ ፡
በሥራዎች ፡ ውስጥ ፡ ተደሳቾች ፡
ናቸው ።
56 እነርሱም ፡ ሚስቶቻቸውም ፡
በጥላዎች ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ፤
ባለ ፡ አጐበር ፡ አልጋዎች ፡ ላይ ፡
ተደጋፊዎች ፡ ናቸው ።
57 በውስጧ ፡ ለነርሱ ፡ ፍራፍሬዎች፡
አሏቸው ፤ ለነርሱም ፡ የሚፈል
ጉት ፡ ሁሉ ፡ አላቸው ።
58 (ለነሱም) ፡ አዛኝ ፡ ከኾነው ፡
ጌታ ፡ በቃል ፡ ሰላምታ ፡ አላ
ቸው ።
59 (ይላልም) ፡ እላንተ ፡ አመጠ
ኞችም ፡ ሆይ ! ዛሬ ፡ (ከምእም
ናን) ፡ ተለዩ ፤
60 የአደም ፡ ልጆች ፡ ሆይ ! ሰይጣ
ንን ፡ አትግገዙ ፤ እርሱ ፡ ለናንተ፡
ግልጽ ፡ ጠላት ፡ ነውና ፡ በማለት፡
ወደናንተ ፡ አላዘዝኩምን ?
61 ተገዙኝም ፤ ይህ ፡ ቀጥተኛ ፡ መን
ገድ ፡ ነው ፤ (በማለትም) ፤
62 ከናንተም ፡ ብዙን ፡ ፍጡር ፡
በእርግጥ ፡ አሳስቷል ፤ የምታው
ቁም ፡ አልነበራችሁምን ?
63 ይህቺ ፡ ያቺ ፡ ትቀቀጠሩዋት ፡
የነበረችው ፡ ገሀነም ፡ ናት ፤
64 ትክዱ ፡ በነበራችሁት ፡ ምክን
ያት ፡ ዛሬ ፡ ግቡዋት ፡ (ይባ
ላሉ) ።
65 ዛሬ ፡ በአፎቻቸው ፡ ላይ ፡ እናት
ምና ፡ እጆቻቸው ፡ ያነጋግሩናል ፤
እግሮቻቸውም ፡ ይሠሩት ፡ በነ
በሩት ፡ ሁሉ ፡ ይመሰክራሉ ።
66 ብንሻም ፡ ኖሮ ፡ በዐይኖቻቸው ፡
ላይ ፡ በአበስን ፡ ነበር ፤ መንገ
ድንም ፡ (እንደ ፡ ልማዳቸው) ፡
በተሽቀዳደሙ ፡ ነበር ፤ እንዴ
ትም ፡ ያያሉ ?
67 ብንሻም ፡ ኖሮ ፡ በስፍራቸው ፡
ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ፍጥ
ረት ፡ በለወጥናቸው ፡ ነበር ፤
መኼድንም ፡ መመለስንም ፡ ባል
ቻሉም ፡ ነበር ።
68 ዕድሜውንም ፡ የምናረዝመውን ፡
ሰው ፡ በፍጥረቱ ፡ (ወደ ፡ ደካማ
ነት) ፡ እንመልሰዋለን ፤ አያው
ቁምን ?
69 (ሙሐመድን) ፡ ቅኔንም ፡ አላስተ
ማርነውም ፤ ለርሱም ፡ አይገባ
ውም ፤ እርሱ ፡ (መጽሐፉ) ፡ መገ
ሠጫና ፡ ገላጭ ፡ ቁርአን ፡ እንጅ ፡
(ቅኔ) ፡ አይደለም ።
70 (ግሣጼነቱም ፡ ልቡ) ፡ ሕያው ፡
የኾነን ፡ ሰው ፡ ሊያስፈራራበ
ትና ፡ ቃሉም ፡ በከሓዲዎች ፡
ላይ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ነው ።



71 እኛ ፡ እጆቻችን ፡ (ኀይሎቻችን) ፡
ከሠሩት ፡ ለነርሱ ፡ እንስሳዎችን ፡
መፍጠራችንን ፡ አያውቁምን ?
እነርሱም ፡ ለርሷ ፡ ባለ ፡ መብ
ቶች ፡ ናቸው ።
72 ለነርሱም ፡ ገራናት ፤ ስለዚህ ፡
ከርሷ ፡ ውስጥ ፡ የሚጋልቡት ፡
አልለ ፤ ከርሷም ፡ ይበላሉ ።
73 ለነርሱም ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ (ሌ
ሎች) ፡ ጥቅሞች ፡ መጠጦችም ፡
አሉዋቸው ፤ ታዲያ ፡ አያመሰግ
ኑምን ?
74 መረዳትንም ፡ በመከጀል ፡ ከአ
ላህ ፡ ሌላ ፡ አማልክትን ፡ያዙ ፤
75 መርዳታቸውን ፡ አይችሉም ፤
እነርሱም ፡ ለርሳቸው ፡ (ወደ ፡
እሳት) ፡ የተቀረቡ ፡ ሰራዊት ፡
ናቸው ።
76 ንግግራቸውም ፡ አያሳዝንህ ፤
እኛ ፡ የሚደብቁትንም ፡ የሚገል
ጹትንም ፡ እናውቃለንና ።
77 ሰውየው ፡ እኛ ፡ ከፍቶት ፡ ጠብታ
የፈጠርነው ፡ መኾናችን ፡ አላወ
ቀምን ? ወዲያውም ፡ እርሱ ፡
(ትንሣኤን ፡ በመካድ) ፡ ግልጽ ፡
ተከራካሪ ፡ ይኾናልን ?
78 ለኛም ፡ ምሳሌን ፡ አደረገልን ፤
መፈጠሩንም ፡ ረሳ ፤ አጥንቶችን፡
እነርሱ ፡ የበሰበሱ ፡ ሲኾኑ ፡
ሕያው ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ማነው ?
አለ ።
79 ያ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ (ከኢ
ምንት) ፡ ያስገኛት ፡ ሕያው ፡
ያደርጋታል ፤ እርሱም ፡ በፍጡሩ፡
ሁሉ ፡ (ኹነታ) ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፡
በለው ።
80 ያ ፡ ለናንተ ፡ ከእርጥብ ፡ ዛፍ ፡
እሳትን ፡ ያደረገላችሁ ፡ ነው ፤
ወዲያውኑም ፡ እናንተ ፡ ከርሱ ፡
ታቀጣጥላላችሁ ።
81 ያ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ የፈ
ጠረ ፡ ብጤያቸውን ፡ በመፍጠር ፡
ላይ ፡ ቻይ ፡ አይደለምን ? ነው ፡
እንጅ ፤ እርሱም ፡ በብዙ ፡ ፈጣ
ሪው ፡ ዐዋቂው ፡ ነው ።
82 ነገሩም ፡ አንዳችን ፡ በሻ ፡ ጊዜ ፡
ኹን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ወዲያው ፡
ይኾናልም ።
83 ያ ፡ የነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣን ፡
በእጁ ፡ የኾነው ፡ ጌታ ፡ ጥራት ፡
ይገባው ፤ ወደርሱም ፡ ትመለሳ
ላችሁ ።

## 37ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አልሷፍፋት ፡ (የተሰላፊዎቹ ፡ ምዕራፍ) ፤ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 182 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ፤

1 መሰለፍን ፡ በሚሰለፉት ፤

2 መገሠጽንም ፡ በሚገሥጹት ፤

3 ቁርአንንም ፡ በሚያነቡት ፡ እምላለሁ ።

4 አምላካችሁ ፡ በእርግጥ ፡ አንድ ፡ ነው ።

5 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ በመካከላቸው ፡ ያለውም ፡ ፍጡር ፡ ሁሉ፡ ጌታ ፡ ነው ፤ የምሥራቆችም ፡ ጌታ ፡ ነው ።

6 እኛ ፡ ቅርቢቱን ፡ ሰማይ ፡ በከዋክብት ፡ ጌጥ ፡ አጌጥናት ።

7 አመጠኛም ፡ ከኾነ ፡ ሰይጣን ፡ ሁሉ ፡ መጠበቅን ፡ ጠበቅናት ።

8 ወደላይኛው ፡ ሰራዊት ፡ አያዳምጡም ፤ ከየወገኑም ፡ ሁሉ ፡ ችቦ ፡ ይጣልባቸዋል ።

9 የሚባረሩ ፡ ሲኾኑ ፡ (ይጣልባቸዋል) ፤ ለነሱም ፡ ዘውታሪ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ።

10 ንጥቂያን ፡ የነጠቀ ፡ ወዲያውም፡ አብሪ ፡ ኮከብ ፡ የተከተለው ፡ ሲቀር ፤ (እርሱ ፡ ይሰማዋል) ።

11 ጠይቃቸውም ፤ እነርሱ ፡ በአፈጣጠር ፡ ይበልጥ ፡ የበረቱ ፡ ናቸውን ? ወይስ ፡ እኛ ፡ (ከነሱ ፡ በፊት) ፡ የፈጠርነው ? (ፍጡር) ፡ እኛ ፡ ከሚጣበቅ ፡ ጭቃ ፡ ፈጠርናቸው ።

12 ይልቁንም ፡ (በማስተባበላቸው) ፡ ተደነቅህ ፤ (ከመደነቅህ) ፡ ይሳለቃሉም ።

13 በተገሠጹም ፡ ጊዜ ፡ አይመለሱም ።

14 ታምርን ፡ ባዩም ፡ ጊዜ ፡ ለመሳለቅ ፡ ይጠራራሉ ።

15 ይላሉም ፡- ይህ ፡ ግልጽ ፡ ድግምት ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ።

16 በሞትንና ፡ ዐፈርና ፡ አጥንቶችም፡ በኾን ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ የምንቀሰቀስ፡ ነን ?

17 የቀድሞዎቹ፡ አባቶቻችንም? (ይላሉ)::

18 አዎን ፡ እናንተ ፡ ወራዶች ፡ ኾናችሁ ፡ (ትነሳላችሁ) ፡ በላቸው ።

19 እርሷም ፡ አንዲት ፡ ጩኸት ፡ ብቻ ፡ ናት ፤ እነርሱም ፡ ወዲያውኑ ፡ (ምን ፡ እንደሚፈጸምባቸው) ፡ ያያሉ ።

20 ዋ ፡ ጥፋታችን ! ይህ ፡ የፍርዱ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ይላሉም ።

21 ይህ ፡ ያ ፡ በርሱ ፡ ታስተባብሉ ፡ የነበራችሁት ፡ መለያው ፡ ቀን ፡ ነው ፡ (ይባላሉ) ።

22 (ለመላእክቶችም) ፡ እነዚያን ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ የበደሉትን ፡ ሰዎች ፡ ጓደኞቻቸውንም ፡ ይግገዟቸው ፡ የነበሩትንም ፡ (ጣዖታት) ፡ ሰብስቡ ፤



23 ከአላህ ፡ ሌላ ፡ (የሚገዙዋቸውን ፡ ሰብስቧቸው) ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ መንገድም ፡ ምሩዋቸው ፤

24 አቁሟቸውም ፤ እነርሱ ፡ ተጠያቂዎች ፡ ናቸውና ፡ (ይባላል) ።

25 (ለነርሱም) ፡ የማትረዳዱት ፡ ለናንተ ፡ ምን ፡ አላችሁ ? (ይባላሉ) ።

26 በእርግጥ ፡ እነርሱ ፡ ዛሬ ፡ እጃቸውን ፡ የሰጡ ፡ ወራዳዎች ፡ ናቸው ።

27 የሚወቃቀሱም ፡ ኾነው ፡ ከፊላቸው ፡ በከፊሉ ፡ ላይ ፡ ይመጣሉ ፤

28 (ለአስከታዮቹ) ፡ እናንተ ፡ ከስተቀኝ ፡ ትመጡብን ፡ ነበር ፡ (1) ይላሉ ።

29 (አስከታዮቹም) ፡ ይላሉ ፡— አይደለም ፡ ፈጽሞ ፡ ምእምናን ፡ አልነበራችሁም ፤

30 ለኛም ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ስልጣን ፡ አልነበረንም ፤ በእርግጥ ፡ እናንተ ፡ ጠማሞች ፡ ሕዝቦች ፡ ነበራችሁ ።

31 በኛም ፡ ላይ ፡ የጌታችን ፡ ቃል ፡ ተረጋገጠብን ፤ እኛ ፡(ሁላችንም ፡ ቅጣቱን) ፡ ቀማሾች ፡ ነን ።

32 ወደ ፡ ጥመት ፡ ጠራናችሁም ፤ እኛ ፡ ጠማሞች ፡ ነበርንና ፤ (ይላሉ) ።

33 ስለዚህ ፡ እነርሱ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ በቅጣቱ ፡ ተጋሪዎች ፡ ናቸው ።

34 እኛ ፡ በአመጠኞች ፡ ሁሉ ፡ እንደዚሁ ፡ እንሠራለን ።

35 እነርሱ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፡ በተባሉ ፡ ጊዜ ፡ ይኮሩ ፡ ነበሩ ።

36 እኛ ፡ ለዕብድ ፡ ባለቅኔ ፡ ብለን ፡ አማልክቶቻችንን ፡ የምንተው ፡ ነን ? ይሉም ፡ ነበር ።

37 አይደለም ፡ እውነቱን ፡ (ሃይማኖት) ፡ አመጣ ፤ መልክተኞቹንም ፡ እውነተኛነታቸውን ፡ አረጋገጠ ።

38 እናንተ ፡ አሳማሚውን ፡ ቅጣት ፡ በእርግጥ ፡ ቀማሾች ፡ ናችሁ ።

39 ትሠሩትም ፡ የነበራችሁትን ፡ እንጂ ፡ ሌላን ፡ አትመነዱም ።

40 ግን ፡ ምርጥ ፡ የኾኑት ፡ የአላህ ፡ ባሮች ፡ (ቅጣትን ፡ አይቀምሱም)፤

41 እነዚያ ፡ ለነርሱ ፡ የታወቀ ፡ ሲሳይ ፡ አልላቸው ።

42 ፍራፍሬዎች ፡ (አሏቸው) ፤ እነርሱም ፡ የተከበሩ ፡ ናቸው ፤

43 በድሎት ፡ ገነቶች ፡ ውስጥ ።

44 ፊት ፡ ለፊት ፡ የሚተያዩ ፡ ሲኾኑ፥ በአልጋዎች ፡ ላይ ፡ (ይንፈላሰሳሉ) ።

45 ከሚመነጭ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ በያዘ ፡ ብርጭቆ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ይዝዞርባቸዋል ።

46 ነጭ ፡ ለጠጪዎች ፡ ጣፋጭ ፡ ከኾነች ፤

47 በርሷ ፡ ውስጥም ፡ ምታት ፡ የለባትም ፤ እነርሱም ፡ ከርሷ ፡ የሚሰክሩ ፡ አይደሉም ።

48 እነርሱም ፡ ዘንድ ፡ ዓይናቸውን ፡ (በባሎቻቸው ፡ ላይ) ፡ አሳጣሪዎች ፡ የኾኑ ፡ (1) ዓይናማዎች ፡ አልሉ ።

49 እነርሱ ፡ ልክ ፡ የተሸፈነ ፡ (የሰጐን) ፡ ዕንቁላል ፡ ይመስላሉ ።

---

1 በደጎና ፡ ነገር ፡ መከሬ ፡ በመምሰል ፡ ታሳስቱን ፡ ነበር ።

1 ከባሎቻቸው ፡ ሌላ ፡ የማይመለከቱ ።

50 የሚጠያየቁም ፡ ኾነው ፡ ከፊላ
ቸው ፡ ወደ ፡ ከፊሉ ፡ ይመጣሉ ።
51 ከነሱ ፡ የኾነ ፡ ተናጋሪ ፡ ይላል ፦
እኔ ፡ ጓደኛ ፡ ነበረኝ ፤
52 በእርግጥ ፡ አንተ ፡ ከሚያምኑት ፡
ነህን ? የሚል ፤
53 በሞትንና ፡ ዐፈር ፡ አጥንቶችም ፡
በኾን ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ በእርግጥ ፡
እንመረመራለን ? (የሚል) ፤
54 እናንተ ፡ ተመልካቾች ፡ ናችሁን ?
ይላል ።
55 ይመለከታልም ፤ በገሀነም ፡ መካ
ከልም ፡ (ጓደኛውን) ፡ ያየዋል ።
56 ይላል ፡— በአላህ ፡ እምላለሁ ፤
በእርግጥ ፡ ልታጠፋኝ ፡ ቀርበህ ፡
ነበር ።
57 የጌታየም ፡ ጸጋ ፡ ባልነበረ ፡ ኖሮ ፡
ወደ ፡ እሳት ፡ ከሚቀርቡት ፡
እኾን ፡ ነበር ።
58 (የገነት ፡ ሰዎች ፡ ይላሉ) ፡—እኛ፡
የምንሞት ፡ አይደለንምን ?
59 የመጀመሪያይቱ ፡ መሞታችን ፡
ብቻ ፡ ስትቀር ፤ እኛም ፡ የምን
ቀቀጣ ፡ አይደለንምን? (ይላሉ) ።
60 ይህ ፡ (ለገነት ፡ ሰዎች ፡ የተወ
ሳው) ፡ እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ ታላቅ፡
ዕድል ፡ ነው ።
61 ለዚህ ፡ ብጤ ፡ ሠሪዎች ፡ ይሥሩ።
62 በመስተንግዶነት ፡ ይህ ፡ ይበል
ጣልን ? ወይስ ፡ የዘቁም ፡ ዛፍ ?
63 እኛ ፡ ለበዳዮች ፡ ፈተና ፡ አድር
ገናታል ።
64 እርሷ ፡ በገሀነም ፡ አዘቅት ፡
ውስጥ ፡ የምትወጣ ፡ ዛፍ ፡ ናት ።
65 እንቡጧ ፡ ልክ ፡ የሰይጣናት ፡
ራሶች ፡ ይመስላል ።
66 እነርሱም ፡ ከርሷ ፡ በይዎች ፡
ናቸው ፤ ሆዶችንም ፡ ከርሷ ፡
ሞይዎች ፡ ናቸው ።
67 ከዚያም ፡ ለነርሱ ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡
ከተኳሳ ፡ ውሃ ፡ ቅልቅል ፡ (መ
ጠጥ) ፡ አላቸው ።
68 ከዚያም ፡ መመለሻቸው ፡ ወደ ፡
ተጋጋመች ፡ እሳት ፡ ነው ።
69 እነሱ ፡ አባቶቻቸውን ፡ የተሳሳቱ፡
ኾነው ፡ አግኝተዋልና ።
70 እነሱም ፡ በፈለጎቻቸው ፡ ላይ ፡
ይገሠግሣሉና ።
71 ከነርሱ ፡ በፊትም ፡ የቀድሞዎቹ ፡
(ሕዝቦች) ፡ አብዛኞቻቸው ፡ በእ
ርግጥ ፡ ተሳስተዋል ፤
72 በውስጣቸውም ፡ አስፈራሪዎችን፡
በእርግጥ ፡ ልከናል ።
73 የተስፈራሪዎቹም ፡ መጨረሻ ፡
እንዴት ፡ እንደነበረ፡ ተመልከት።
74 ምርጥ ፡ የኾኑት ፡ የአላህ ፡ ባሮች፡
ብቻ ፡ ሲቀሩ ።
75 ኑሕም ፡ በእርግጥ ፡ ጠራን ፤ ጥሪ
ውን ፡ ተቀባዮቹም ፡ ምንኛ ፡
አማርን !
76 እርሱንም ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹንም ፡
ከከባድ ፡ ጭንቅ ፡ አዳንን ።
77 ዘሮቹንም ፡ እነርሱን ፡ ብቻ ፡
ቀሪዎች ፡ አደረግን ፤
78 በርሱም ፡ ላይ ፡ በኋለኞቹ ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ውስጥ ፡ (መልካም ፡ ዝናን)
ተውን ።
79 በዓለማት ፡ ውስጥ ፡ ሰላም ፡ በኑ
ሕ ፡ ላይ ፡ ይኹን ።
80 እኛ ፡ እንደዚሁ ፡ መልካም ፡
ሠሪዎችን ፡ እንመነዳለን ።
81 እርሱ ፡ ከምእምናን ፡ ባሮቻችን ፡
ነውና ።



82 ከዚያም ፡ ሌሎቹን ፡ አሰጠምን ።
83 ኢብራሂምም ፡ በርግጥ ፡ ከተከ
ታዮቹ ፡ ነው ።
84 ወደ ፡ ጌታው ፡ በቅን ፡ ልብ ፡
በመጣ ፡ ጊዜ ፡ (የኾነውን ፡ አስ
ታውስ) ።
85 ለአባቱና ፡ ለሕዝቦቹ ፡ ምንን ፡
ትግገዛላችሁ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፤
86 ለቅጥፈት ፡ ብላችሁ ፡ ከአላህ ፡
ሌላ ፡ አማልክትን ፡ ትሻላችሁን ?
87 በዓለማትም ፡ ጌታ ፡ ሐሳባችሁ ፡
ምንድን ፡ ነው ? (አለ) ።
88 በከዋክብትም ፡ መመልከትን ፡
ተመለከተ ።
89 እኔ ፡ በሺተኛ ፡ ነኝም ፡ አለ ።
90 ከርሱም ፡ የሸሹ ፡ ኾነው ፡ ኼዱ።
91 ወደ ፡ አማልክቶቻቸውም ፡ ተዘ
ነበለ ፤ አለም ፡— አትበሉምን ?
92 የማትናገሩት ፡ ለናንተ ፡ ምን ፡
አላችሁ ?
93 በኀይል ፡ የሚመታቸውም ፡ ኾኖ፡
በነርሱ ፡ ላይ ፡ በድብቅ ፡ ተዘ
ነበለ ።
94 ወደርሱም ፡ (ሰዎቹ) ፡ እየሮጡ ፡
መጡ ።
95 አላቸው ፦ የምትጠርቡትን ፡
ትግገዛላችሁን ?
96 አላህ ፡ እናንተንም ፡ የምትሠ
ሩትንም ፡ የፈጠረ ፡ ሲኾን ።
97 ለርሱም ፡ ግንብን ፡ ገንቡ ፤ በእ
ሳት ፡ ነበልባል ፡ ውስጥ ፡ ጣ
ሉትም ፡ አሉ ።
98 በርሱም ፡ ተንኮልን ፡ አሰቡ ፤
ዝቅተኞችም ፡ አደረግናቸው ።
99 አለም ፡—እኔ ፡ ወደ ፡ ጌታዬ ፡
ኼያጅ ፡ ነኝ ፤ በእርግጥ ፡ ይመራ
ኛልና ።
100 ጌታዬ ፡ ሆይ ! ከመልካሞቹ ፡ የኾ
ነን ፡ (ልጅ) ፡ ስጠኝ ።
101 ታጋሽ ፡ በኾነ ፡ ወጣት ፡ ልጅም ፡
አበሰርነው ።
102 ከርሱ ፡ ጋርም ፡ ለሥራ ፡ በደረሰ ፡
ጊዜ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ! እኔ ፡ በሕል
ሜእኔ ፡ የማርድህ ፡ ኾኜ ፡ አያ
ለሁ ፤ ተመልከትም ፤ ምን ፡ ታያ
ለህ ? አለው ፤ አባቴ ፡ ሆይ ! የታ
ዘዝከውን ፡ ሥራ ፤ አላህ ፡ ቢሻ ፡
ከታጋሾቹ ፡ ኾኜ ፡ ታገኘኛለህ ፡
አለ ።
103 ሁለቱም ፡ ትእዛዙን ፡ በተቀበ
ሉና ፡ በግንባሩም ፡ ጎን ፡ ላይ ፡
በጣለው ፡ ጊዜ ፡ (የኾነው ፡
ኾነ) ።
104 ጠራነውም ፤ (አልነው) ፦ኢብ
ራሂም ፡ ሆይ !
105 ራእይቱን ፡ በውነት ፡ አረጋገ
ጥክ ፤ እኛ ፡ እንደዚሁ ፡ መልካም፡
ሠሪዎችን ፡ እንመነዳለን ።
106 ይህ ፡ እርሱ ፡ በውነት ፡ ግልጽ ፡
ፈተና ፡ ነው ።
107 በታላቅ ፡ ዕርድም፡ (መሥዋዕት)፡
ተቤዠነው ።
108 በርሱም ፡ ላይ ፡ በኋለኞቹ ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ውስጥ ፡ መልካም ፡ ዝናን ፡
አስቀረንለት ።
109 ሰላም ፡ በኢብራሂም፡ላይ፡ ይኹን።
110 እንደዚሁ ፡ መልካም ፡ ሠሪዎችን፡
ሁሉ ፡ እንመነዳለን ።
111 እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ ካመኑት ፡
ባሮቻችን ፡ ነው ።
112 በኢስሐቅም ፡ አበሰርነው ፤ ከመ
ልካሞቹ ፡ የኾነ ፡ ነቢይ ፡ ሲኾን ።
113 በርሱና ፡ በኢስሐቅ ፡ ላይም ፡
ባረክን ፤ ከሁለቱም ፡ ዘሮች ፡

በጎ ፡ ሠሪ ፡ አልለ ፤ ለነፍሱ ፡ ግልጽ ፡ በዳይም ፡ አልለ ።

114 በሙሳና ፡ በሃሩን ፡ ላይም ፡ በእርግጥ ፡ ለገስን ።

115 እነርሱንም ፡ ሕዝቦቻቸውንም ፡ ከታላቅ ፡ ጭንቅ ፡ አዳንን ።

116 ረዳናቸውም ፤ እነርሱም ፡ አሸናፊዎች ፡ ነበሩ ።

117 በጣም ፡ የተብራራውንም ፡ መጽሐፍ ፡ ሰጠናቸው ።

118 ቀጥተኛውንም ፡ መንገድ ፡ መራናቸው ።

119 በሁለቱም ፡ ላይ ፡ በኋለኞቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ውስጥ ፡ መልካም ፡ ዝናን ፡ ተውንላቸው ።

120 ሰላም ፡ በሙሳና ፡ በሃሩን ፡ ላይ ፡ ይኹን ።

121 እኛ ፡ እንደዚሁ ፡ በጎ ፡ አድራጊዎችን ፡ ሁሉ ፡ እንመነዳለን ።

122 ሁለቱም ፡ በእርግጥ ፡ ከአመኑት ፡ ባሮቻችን ፡ ናቸው ።

123 ኢልያስም ፡ በእርግጥ ፡ ከመልክተኞቹ ፡ ነው ።

124 ለሕዝቦቹ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፤ አላህን ፡ አትፈሩምን ?

125 በዕልን ፡ (1) ትግገዛላችሁን ? ከሰዓሊዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ በጣም ፡ አሳማሪ ፡ የኾነውንም ፡ አምላክ ፡ ትተዋላችሁን ?

126 አላህን ፡ ጌታችሁንና ፡ የቀድሞዎቹ ፡ አባቶቻችሁን ፡ ጌታ ፡ (ትተዋላችሁን) ?

127 አስተባበሉትም ፤ ስለዚህ ፡ እነርሱ ፡ (ለቅጣት) ፡ የሚጣዱ ፡ ናቸው ።

128 ንጹሕ ፡ የተደረጉት ፡ የአላህ ፡ ባሮች ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ ፤

129 በርሱ ፡ ላይም ፡ በኋለኞቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ውስጥ ፡ መልካም ፡ ዝናን ፡ ተውንለት ።

130 ሰላም ፡ በኢልያሲን ፡ ላይ ፡ ይኹን

131 እኛ ፡ እንደዚሁ ፡ መልካም ፡ ሠሪዎችን ፡ እንመነዳለን ።

132 እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ ከምእምናን ፡ ባሮቻችን ፡ ነው ።

133 ሉጥም ፡ በእርግጥ ፡ ከመልክተኞቹ ፡ ነው ።

134 እርሱንና ፡ ቤተሰቦቹን ፡ ሁሉንም ፡ በአዳንናቸው ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፤

135 (በቅጣቱ ፡ ውስጥ) ፡ ከቀሪዎቹ ፡ የኾነችው ፡ አሮጊት ፡ ብቻ ፡ ስትቀር ።

136 ከዚያም ፡ ሌሎቹን ፡ አጠፋን ።

137 እናንተም ፡ ያነጋችሁ ፡ ስትኾኑ ፡ በነርሱ ፡ (መኖሪያዎች) ፡ ላይ ፡ (በቀን) ፡ ታልፉላችሁ ።

138 በሌሊትም ፡ (ታልፉላችሁ) ፤ ልብም ፡ አታደርጉምን ?

139 ዩኑስም ፡ በእርግጥ ፡ ከመልክተኞቹ ፡ ነው ።

140 ወደ ፡ ተመላው ፡ መርከብ ፡ በኰበለለ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ።

141 ዕጣም ፡ ተጣጣለ ፤ ከተሸነፉትም ፡ ኾነ ።

142 እርሱም ፡ ተወቃሽ ፡ ሲኾን ፡ ዐሣው ፡ዋጠው ፤

143 እርሱ ፡ ለጌታው ፡ ከአወዳሾቹ ፡ ባልኾነም ፡ ኖሮ ፡

144 እስከሚቀሰቀሱበት ፡ ቀን ፡ ድረስ በሆዱ ፡ ውስጥ ፡ በቆዩ ፡ ነበር ።

145 እርሱ ፡ በሺትኛ ፡ ኾኖ ፡ በቃይ ፡ በሌለው ፡ (በባሕር) ፡ ዳርቻ ፡ ላይ ፡ ጣልነውም ።

146 በርሱም ፡ ላይ ፡(በአጠገቡ) ፡ ከቅል ፡ የኾነችን ፡ ዛፍ ፡ አበቀልን ።

147 ወደ ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎችም ፡ (ዳግመኛ) ፡ ላክነው ፤ ከቶውንም ፡ ይጨምራሉ ።

148 አመኑም ፤ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ድረስም ፡ አጣቀምናቸው ።

149 (የመካን ፡ ሰዎች) ፡ ጠይቃቸውም ፤ ለጌታህ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ለነርሱም ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ይኖራልን ?

150 ወይስ ፡ እኛ ፡ እነሱ ፡ የተጣዱ ፡ ኾነው ፡ መላእክትን ፡ ሴቶች ፡ አድርገን ፡ ፈጠርን ?

151 ንቁ ፡ እነሱ ፡ ከቅጥፈታቸው ፡ (የተነሳ) ፡ ይላሉ ፡—

152 አላህ ፡ (መላእክትን) ፡ ወለደ ፤ እነርሱም ፡ በእርግጥ ፡ ውሸታሞች ፡ ናቸው ።

153 በወንዶች ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ይልቅ ፡ ሴቶችን ፡ ልጆች ፡ መረጥን ?

154 ለናንተ ፡ ምን ፡ (አስረጅ) ፡ አላችሁ ? እንዴት ፡ ትፈርዳላችሁ !

155 አትገነዘቡምን ?

156 ወይስ ፡ ለናንተ ፡ ግልጽ ፡ አስረጅ ፡ አላችሁን ?

157 እውነተኞች ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ መጽሐፋችሁን ፡ አምጡ ፡ (በላቸው) ።

158 በአላህና ፡ በአጋንንት ፡ መካከልም ፡ ዝምድናን ፡ አደረጉ ፤ አጋንንትም ፡ እነሱ ፡ (ይህን ፡ ባዮች ፡ በእሳት) ፡ የሚጣዱ ፡ መኾናቸውን ፡ በእርግጥ ፡ ዐውቀዋል ።

159 አላህ ፡ ከሚመጥኑት ፡ ሁሉ ፡ ጠራ ።

160 ግን ፡ የተመረጡት ፡ የአላህ ፡ ባሮች ፡ (በአላህ ፡ ላይ ፡ አይዋሹም) ።

161 እናንተም ፡ የምትግገዟቸውም ፡ ሁሉ ፤

162 በርሱ ፡ (በአላህ) ፡ ላይ ፡ አንድንም ፡ አጥማሚዎች ፡ አይደላችሁም ፤

163 ያንን ፡ እርሱ ፡ ገሀነምን ፡ ገቢ ፡ የኾነውን ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ እንጅ ።

164 (ጂብሪል ፡ አለ) ፡ ከኛም ፡ አንድም ፡ የለም ፤ ለርሱ ፡ የታወቀ ፡ ደረጃ ፡ ያለው ፡ ቢኾን ፡ እንጅ ።

165 እኛም ፡ (ጌታን ፡ ለመግገዛት) ፡ ተሰላፊዎቹ ፡ እኛ ፡ ነን ።

166 እኛም ፡ (አላህን) ፡ አጥሪዎቹ ፡ እኛ ፡ ነን ።

167 እነርሱም ፡ (ከሐዲዎቹ) ፡ በእርግጥ ፡ ይሉ ፡ ነበሩ ፡—

168 ከቀድሞዎቹ ፡ (መጻሕፍት) ፡ ገሣጭ ፡ መጽሐፍ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ በነበረን ፡ ኖሮ ፤

169 የአላህ ፡ ምርጦች ፡ ባሮች ፡ በኾን ፡ ነበር ።

170 ግን ፡ (ቁርአኑ ፡ በመጣላቸው ፡ ጊዜ) ፡ በርሱ ፡ ካዱ ፡ ወደፊትም ፡ በእርግጥ ፡ ያውቃሉ ፤

171 (የርዳታ) ፡ ቃላችንም ፡ መልክተኞች ፡ ለኾኑት ፡ ባሮቻችን ፡ በውነት ፡ አልፋለች ።

172 እነርሱ ፡ ተረጂዎቹ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ።

1 የጣዖት ፡ ስም ፡ ነው ።

173 ሰራዊቶቻችንም ፡ በእርግጥ ፡ አሸ
ናፊዎቹ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ።
174 ከነሱም ፡ (ከመካ ፡ ከሓዲዎች) ፡
እስከ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡
ዙር ፡ (ተዋቸው) ።
175 እያቸውም ፤ ወደፊትም ፡ (የሚደ
ርስባቸውን) ፡ ያያሉ ።
176 በቅጣታችንም ፡ ያቻኩላሉን?
177 በቀያቸውም ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡
የተስፈራሪዎቹ ፡ ንጋት ፡ ከፉ !
178 እነርሱንም ፡ እስከ ፡ (ጥቂት) ፡
ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ተዋቸው ።
179 ተመልከትም ፤ በእርግጥም ፡ ያ
ያሉ ።
180 የማሸነፍ ፡ ጌታ ፡ የኾነው ፡ ጌታህ
ከሚሉት ፡ ሁሉ ፡ ጠራ ።
181 በመልክተኞቹም ፡ ላይ ፡ ሰላም ፡
ይኹን ፡
182 ምስጋናም ፡ ለዓለማት ፡ ጌታ ፡
ለአላህ ፡ ይኹን ።

## ምዕራፍ ፡ 38 ፡ ሷድ ። ክፍል ፡ 23 ።

38ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ሷድ ፡ (የሷድ ፡ ወይም ፡ የዳውድ ፡ ምዕራፍ) ። በ
መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 88 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፤ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 ጸ. (ሷድ) ፡ (1) የክብር ፡ ባለ
ቤት ፡ በኾነው ፡ ቁርአን ፡ እም
ላለሁ ፡ (ብዙ ፡ አማልክት ፡
አልሉ ፡ እንደሚሉት ፡ አይደ
ለም) ።
2 ይልቁንም ፡ እነዚያ ፡ የካዱት ፡
ሰዎች ፡ በትዕቢትና ፡ በክርክር ፡
ውስጥ ፡ ናቸው ።
3 ከነሱ ፡ በፊት ፡ ከክፍለ ፡ ዘመ
ናት ፡ ሕዝቦች ፡ ብዙን ፡ አጥፍ
ተናል ፤ (ጊዜው) ፡ የመሸሻና ፡
የማምለጫ ፡ ጊዜ ፡ ሳይኾንም ፡
(ለርዳታ) ፡ ተጣሩ ።
4 ከነሱ ፡ የኾነ ፡ አስፈራሪም ፡
ስለ ፡ መጣላቸው ፡ ተደነቁ ፤ ከሓ
ዲዎቹም ፡ ይህ ፡ ድግምተኛ ፡
(ጠንቋይ) ፡ ውሸታም ፡ ነው ፡
አሉ ።
5 አማልክቶቹን ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡
አደረጋቸውን ? ይህ ፡ አስደናቂ ፡
ነገር ፡ ነው ፡ (አሉ) ።
6 ከነርሱም ፡ መኳንንቶቹ ፡-ኺዱ ፤
በአማልክቶቻችሁም ፡ (መግገዛት) ፡
ላይ ፡ ታገሡ ፤ ይህ ፡ (ከኛ) ፡ የሚ
ፈለግ ፡ ነገር ፡ ነውና ፡ እያሉ ፡
አዘገሙ ።
7 ይህንንም ፡ በኋለኛይቱ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ አልሰማንም ፡ ይህ ፡ ውሸ
ትን ፡ መፍጠር ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡
አይደለም ፡ (እያሉም) ፤
8 ከመካከላችን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
ቁርአን ፡ ተወረደን ? (አሉ፡) ፤
በውነት ፡ እነርሱ ፡ ከግሣጼዬ ፡
(ከቁርአን) ፡ በመጠራጠር ፡ ውስ
ጥ ፡ ናቸው ፤ በእርግጥም ፡ ቅጣ
ቴን ፡ ገና ፡ አልቀመሱም ፤
9 ይልቁንም ፡ የአሸናፊውና ፡ የለ
ጋሱ ፡ ጌታህ ፡ የችሮታው ፡ መካዚ
ኖች ፡ እነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ናቸውን ?
10 ወይስ ፡ የሰማያትና ፡ የምድር ፡
የመካከላቸውም ፡ ንግሥና ፡ የነሱ
ነውን ? (ነው ፡ ቢሉ) ፡ በመሰ
ላሎችም ፡ ይውጡ ።
11 እዚያ ፡ ዘንድ ፡ ከአሕዛብ ፡ የኾኑ፡
ተሸናፊ ፡ ሰራዊት ፡ ናቸው ።
12 ከነርሱ ፡ በፊት ፡ የኑሕ ፡ ሕዝ
ቦች ፤ ዓድም ፡ የችካሎች ፡ ባለ
ቤት ፡ የኾነው ፡ ፈርዖንም ፡
አስተባበሉ ።
13 ሠሙድም ፡ የሉጥ ፡ ሰዎችም ፡ የአ
ይከት ፡ ሰዎችም ፡ (አስተባበሉ) ፡
እነዚህ ፡ አሕዛቦቹ ፡ ናቸው ።
14 ሁሉም ፡ መልክተኞቹን ፡ ያስ
ዋሹ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደሉም ፤
ቅጣቴም ፡ ተረጋገጠባቸው ።
15 እነዚህም ፡ ለርሷ ፡ መመለስ ፡
የሌላትን ፡ አንዲትን ፡ ጩኸት ፡
እንጅ ፡ ሌላን ፡ አይጠባበቁም ።
16 ጌታችን ፡ ሆይ ! ከምርመራው ፡
ቀን ፡ በፊት ፡ መጽሐፋችንን ፡
አስቸኩልልን ፡ አሉም ።
17 በሚሉት ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ታገሥ ፤
የኀይል ፡ ባለቤት ፡ የኾነውን ፡
ባሪያችንንም ፡ ዳውድን ፡ አው
ሳላቸው ፤ እርሱ ፡ በጣም ፡ መላሳ፡
ነውና ።
18 እኛ ፡ ተራራዎችን ፡ ከቀትር ፡
በኋላና ፡ በረፋድም ፡ ከርሱ ፡
ጋር ፡ የሚያወድሱ ፡ ሲኾኑ ፡
ገራንለት ።
19 በራሪዎችንም ፡ (አእዋፍን) ፡ የሚ
ሰበሰቡ ፡ ኾነው ፡ (ገራንለት) ፤
ሁሉም ፡ ለርሱ ፡ (ማወደስ) ፡
የሚመላለስ ፡ ነው ።
20 መንግሥቱንም ፡ አበረታንለት ፤
ጥበብንም ፡ ንግግርን ፡ መለየት
ንም ፡ ሰጠነው ፤
21 የተከራካሪዎቹም ፡ ወሬ ፡ መጥ
ቶሃልን ? ምኩራቡን ፡ በተንጠ
ጠላጠሉ ፡ ጊዜ ፡
22 በዳውድ ፡ ላይም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡
ከነርሱም ፡ በደነገጠ ፡ ጊዜ ፡ አት
ፍራ ፤ (እኛ) ፡ ከፊላችን ፡ በከ
ፊሉ ፡ ላይ ፡ ወሰን ፡ ያለፈ ፡ ሁለት
ተከራካሪዎች ፡ ነን ፤ በመካከላ
ችንም ፡ በውነት ፡ ፍረድ ፤ አታ
ዳላም ፤ ወደ ፡ መካከለኛውም ፡
መንገድ ፡ ምራን ፤ አሉት ።
23 ይህ ፡ ወንድሜ ፡ ነው ፤ ለርሱ ፡
ዘጠና ፡ ዘጠኝ ፡ ሴቶች ፡ በጐች ፡
አሉት ፤ ለኔም ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡
በግ ፡ አለችኝ ፤ እርሷንም ፡ ዕድሌ
አድርጋት ፡ አለኝ ፤ በንግግርም ፡
አሸነፈኝ ፡ አለው ።
24 ሴት ፡ በግህን ፡ ወደ ፡ በጐቹ ፡
(ለመቀላቀል) ፡ በመጠየቁ ፡ በእ
ርግጥ ፡ በደለህ ፤ ከተጋሪዎችም ፡
(1) ብዙዎቹ ፡ ከፊላቸው ፡ በከ
ፊሉ ፡ ላይ ፡ ወሰን ፡ ያልፋሉ ፤
እነዚያ ፡ ያመኑትና ፡ መልካም
ችን ፡ የሠሩት ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ ፤
እነሱም ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡
ናቸው ፡ አለ ፤ ዳውድም ፡ የፈተ
ንነው ፡ መኾኑን ፡ ዐወቀ ፤ ጌታ
ውንም ፡ ምሕረትን ፡ ለመነ ፤
ሰጋጅ ፡ ኾኖ ፡ ወደቀም ፤ በመ
ጸጸት ፡ ተመለሰም ።

1 ሙሐመድ ፡ እውነትን ፡ ተናገረ ።

1 ከሸሪኮች ።

25 ለርሱም ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ መቅረብ፡ (ክብር) ፡ መልካም ፡ መመለሻም፡ አልለው ።

26 ዳውድ ፡ ሆይ ! እኛ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ምትክ ፡ አድርገንሃልና ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ በውነት ፡ ፍረድ ፤ ዝንባሌህንም ፡ አትከተል ፤ ከአላህ ፡ መንገድ ፡ ያሳስትሃልና ፤ እነዚያ ፡ ከአላህ ፡ መንገድ ፡ የሚሳሳቱ ፡ የምርመራውን፡ ቀን ፡ በመርሳታቸው ፡ ለነርሱ ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ።

27 ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በመካከላቸውም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ለከንቱ ፡ አልፈጠርንም ፤ ይህ ፡ የነዚያ ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡ ጥርጣሬ ፡ ነው ፤ ለነዚያም ፡ ለካዱት ፡ ሰዎች ፡ ከእሳት ፡ ወዮላቸው !

28 በውነቱ ፡ እነዚያን ፡ ያመኑትንና ፡ መልካሞችን ፡ የሠሩትን ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ እንደሚያጠፉት ፡ እናደርጋለን ? ወይስ ፡ አላህን ፡ ፈሪዎቹን ፡ እንደ ፡ ከሓዲዎቹ ፡ እናደርጋለን ?

29 (ይህ) ፡ ወዳንተ ፡ ያወረድነው ፡ ብሩክ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፤ አንቀጾቹን ፡ እንዲያስተነትኑና ፡ የአእምሮዎች ፡ ባለ ፡ ቤቶችም ፡ እንዲገሠጹ ፡ (አወረድነው) ።

30 ለዳውድም ፡ ሱለይማንን ፡ ሰጠነው ፤ ምን ፡ ያምር ፡ ባሪያ ! (ሱለይማን) ፤ እርሱ ፡ መላሳ ፡ ነው ።

31 በርሱ ፡ ላይ ፡ ከቀትር ፡ በኋላ ፡ በሦስት ፡ እግሮችና ፡ በአራተኛዋ ፡ ኮቲ ፡ ጫፍ ፡ የሚቆሙ ፡ ጮሌዎች ፡ ፈረሶች ፡ በተቀረቡለት ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፤

32 አለም ፡-እኔ ፡ (ፀሐይ) ፡ በግርዶ ፡ እስከ ፡ ተደበቀች ፡ ድረስ ፡ (1) ከጌታዬ ፡ ማስታወስ ፡ ፋንታ ፡ ፈረስን ፡ መውደድን ፡ መረጥኩ ፤

33 በኔ ፡ ላይ ፡ መልሷት ፡ (2) (አለ) ፤ አጋዶችዋንና ፡ አንገቶችዋንም ፡ ማበስ ፡ ያዘ ።

34 ሱለይማንንም ፡ በእርግጥ ፡ ፈተንነው ፤ በመንበሩም ፡ ላይ ፡ አካልን ፡ ጣልን ፤ ከዚያም ፡ በመጸጸት ፡ ተመለሰ ።

35 ጌታዬ ፡ ሆይ ! ለኔ ፡ ማር ፤ ከኔ ፡ በኋላ ፡ ለአንድም ፡ የማይገባንም፡ ንግሥና ፡ ስጠኝ ፤ አንተ ፡ ለጋሱ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህና ፡ አለ ።

36 ነፋስንም ፡ በትእዛዙ ፡ ወደፈለገበት ፡ ስፍራ ፡ ልዝብ ፡ ኾና፡ የምትፈስ ፡ ስትኾን ፡ ገራንለት ።

37 ሰይጣናትንም ፡ ገንቢዎችንና ፡ ሰጣሚዎችን ፡ ሁሉ ፡ (ገራንለት)፤

38 ሌሎችንም ፡ በፍንጆች ፡ ተቆራኞችን ፡ (ገራንለት) ።

39 ይህ ፡ ስጦታችን ፡ ነው ፤ ያለ ፡ ግምት ፡ ለግስ ፤ ወይም ፡ ጨብጥ ፡ (አልነው) ።

40 ለርሱም ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ መቅረብ ፡ መልካም ፡ መመለሻም ፡ በእርግጥ ፡ አለው ።

41 ባሪያችንን ፡ አዩብንም ፡ አውሳላቸው ፤ እኔ ፡ ሰይጣን ፡ በጉዳትና ፡ በስቃይ ፡ ነካኝ ፡ ሲል ፡ ጌታውን ፡ በተጣራ ፡ ጊዜ ፤

42 በእግርህ ፡ (ምድርን) ፡ ምታ ፤ ይህ ፡ ቀዝቃዛ ፡ መታጠቢያ ፡ መጠጥም ፡ ነው ፤ (ተባለ) ፤

---

1 እስከ ፡ ጠለቀች ፡ ድረስ ።

2 ፈረሶቹን ፡ መልሱ ።



43 ለርሱም ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ለችሮታ ፡ ባለ ፡ አእምሮዎችንም ፡ ለመገሠጽ ፡ ቤተሰቦቹን ፡ ከነሱም ፡ ጋር ፡ መሰላቸውን ፡ ሰጠነው ፤

44 በእጅህም ፡ ጭብጥ ፡ አርጩሜን፡ ያዝ ፡ በርሱም ፡ (ሚስትህን) ፡ ምታ ፤ ማላህንም ፡ አታፍርስ ፤ (አልነው) ፤ እኛ ፡ ታጋሽ ፡ ኾኖ ፡ አገኘነው ፤ ምን ፡ ያምር ፡ ባሪያ ! እርሱ ፡ በጣም ፡ መላሳ ፡ ነው ።

45 ባሮቻችንንም ፡ ኢብራሂምን ፡ ኢስሐቅንና ፡ ያዕቆብንም ፡ የኀይልና ፡ የማስተዋል ፡ ባለ ፡ ቤቶች የኾኑትን ፡ አውሳላቸው ።

46 እኛ ፡ ጥሩ ፡ በኾነች ፡ ጠባይ ፡ መረጥናቸው ፤ (እርሷም) ፡ የመጨረሻይቱን ፡ አገር ፡ ማስታወስ ፡ ናት ።

47 እነርሱም ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ ከመልካሞቹ ፡ ምርጦች ፡ ናቸው ።

48 ኢስማዒልንም ፡ አልየሰዕንም ፡ ዙልኪፍልንም ፡ አውሳ ፤ ሁሉም፡ ከበላጮቹ ፡ ናቸው ።

49 ይህ ፡ መልካም ፡ ዝና ፡ ነው ፤ ለአላህ ፡ ፈሪዎችም ፡ በእርግጥ ፡ ውብ ፡ የኾነ ፡ መመለሻ ፡ አላቸው ።

50 በሮቻቸው ፡ ለነርሱ ፡ የተከፈቱ ፡ ሲኾኑ ፡ የመኖሪያ ፡ ገነቶች ፡ አሏቸው ።

51 በርሷ ፡ ውስጥ ፡ የተደገፉ፡ ኾነው፡ በውስጧ ፡ በብዙ ፡ እሸቶችና ፡ በመጠጥም ፡ ያዝዛሉ ።

52 እነርሱ ፡ ዘንድም ፡ ዓይኖቻቸውን (በባሎቻቸው ፡ ላይ) ፡ አሳጣሪዎች ፡ እኩያዎች ፡ (ሴቶች) ፡ አሉ ።

53 ይህ ፡ ለምርመራው ፡ ቀን ፡ የምትቀጠሩት ፡ ተስፋ ፡ ነው ።

54 ይህ ፡ሲሳያችን ፡ ነው ፡ ለርሱ ፡ ምንም ፡ ማለቅ ፡ የለውም ።

55 ይህ ፡ (ለአማፆች ፡ ነው) ፤ ለጠማሞችም ፡ በጣም ፡ የከፋ ፡ መመለሻ ፡ አላቸው ።

56 የሚገቧት ፡ ስትኾን ፡ ገሀነም ፡ (አለቻቸው) ፤ ምንጣፊቱም ፡ ምንኛ ፡ ከፋች ።

57 ይህ ፡ (ለከሓዲዎች ፡ ነው) ፤ ይቅመሱትም ፤ የፈላ ፡ ውሃና ፡ እዥ ፡ ነው ።

58 ሌላም ፡ ከመሰሉ ፡ ዓይነቶች ፡ አሉ ።

59 ይህ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ በመጋፈጥ፡ ገቢ ፡ ጭፍራ ፡ ነው ፤ (ይባላሉ) ፡ ለነርሱ ፡ አይስፋቸው ፤ እነርሱ ፡ እሳትን ፡ ገቢዎች ፡ ናቸውና ፡ (ይላሉ) ።

60 (ተከታዮቹ) ፡ ይላሉ ፡-ይልቁን ፡ እናንተ ፡ አይስፋችሁ ፤ እናንተ ፡ (ክሕደቱን) ፡ ለኛ ፡ አቀረባችሁት ፤ መርጊያይቱም ፡ (ገሀነም)፡ ከፋች ።

61 ጌታችን ፡ ሆይ ! ይህንን ፡ ያቀረበልንን ፡ ሰው ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ እጥፍን ፡ ቅጣት ፡ ጨምርለት ፡ ይላሉ ።

62 ይላሉም ፡— ለኛ ፡ ምን ፡ አለን ? ከመጥፎዎች ፡ እንቆጥራቸው ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ (እዚህ) ፡ አናይምሳ ።

63 መቀለጃ ፡ አድርገን ፡ ያዝናቸውን ? ወይስ ፡ ዓይኖቻችን ፡ ከነሱ ዋለሉ ?

64 ይህ ፡ በእርግጥ ፡ እውነት ፡ ነው ፤
(እርሱም) ፡ የእሳት ፡ ሰዎች ፡
(የርስ ፡ በርስ) ፡ መካሰስ ፡ ነው ።
65 ፡—እኔ ፡ አስፈራሪ ፡ ብቻ ፡ ነኝ ፡
ኀያል ፡ አንድ ፡ ከኾነው ፡ አላህ ፡
በቀር ፡ ምንም ፡ አምላክ ፡ የለም ፡
በላቸው ።
66 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ በመካ
ከላቸውም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡
አሸናፊው ፡ መሓሪው ፡ ነው ።
67 በላቸው ፡— እርሱ ፡ (ቁርአን) ፡
ታላቅ ፡ ዜና ፡ ነው ።
68 እናንተ ፡ ከርሱ ፡ ዘንጊዎች ፡
ናችሁ ።
69 (በአደም ፡ ነገር) ፡ በሚከራከሩ ፡
ጊዜ ፡ በላይኛው ፡ ሰራዊት ፡
ለኔ ፡ ምንም ፡ ዕውቀት ፡ አልነ
በረኝም ።
70 ወደኔም ፡ አስፈራሪ ፡ ገላጭ ፡
መኾኔ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይወረ
ድልኝም ፡ (በል) ።
71 ጌታህ ፡ ለመላእክት ፡ እኔ ፡ ሰውን ፡
ከጭቃ ፡ ፈጣሪ ፡ ነኝ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ) ።
72 ፍጥረቱንም ፡ ባስተካከልኩና ፡
ከመንፈሴ ፡ በነፋሁበት ፡ ጊዜ ፡
ለርሱ ፡ ሰጋጆች ፡ ኾናችሁ ፡
ውደቁ ፡ (አልኩ) ።
73 መላእክትም ፡ መላውም ፡ ባን
ድነት ፡ ሰገዱ ።
74 ኢብሊስ ፡ ብቻ ፡ ሲቀር ፤ ኮራ ፤
ከከሓዲዎቹም ፡ ነበር ።
75 (አላህም) ፡ ኢብሊስ ፡ ሆይ ! በሁ
ለት ፡ እጆቼ ፡ (በኃይሌ) ፡ ለፈጠ
ርኩት ፡ ከመስገድ ፡ ምን ፡ ከለ
ከለህ ? (አሁን) ፡ ኮራህን ? ወይስ ፡
(ፊቱኑ) ፡ ከትዕቢተኞቹ ፡ ነበ
ርክ ፡ አለው ።
76 እኔ ፡ ከርሱ ፡ በላጭ ፡ ነኝ ፤ ከእ
ሳት ፡ ፈጠርከኝ ፤ ከጭቃም ፡
ፈጠርከው ፡ አለ ።
77 (አላህ) ፡ አለው ፡—ከርሷ ፡ ውጣ ፤
አንተ ፡ የተባረርክ ፡ ነህና ፤
78 ርግማኔም ፡ እስከ ፡ ፍርዱ ፡ ቀን ፡
ድረስ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ይኹን ።
79 ጌታዬ ፡ ሆይ ! እስከሚቀሰቀሱ
በት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ አቆየኝም ፡
አለ ።
80 (አላህም) ፡ አለው ፡— አንተ ፡
ከሚቆዩት ፡ ነህ ፤
81 እስከ ፡ ታወቀው ፡ ወቅት ፡ ቀን ፡
ድረስ ።
82 (እርሱም) ፡ አለ ፡-በአሸናፊነትህ ፡
ይኹንብኝ ፤ በመላ ፡ አሳስታቸ
ዋለሁ ፤
83 ከነርሱ ፡ ምርጥ ፡ የኾኑት ፡ ባሮ
ችህ ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ ።
84 (አላህ) ፡ አለው ፡-እውነቱም ፡
(ከኔ ፡ ነው) ፤ እውነትንም ፡ እላ
ለሁ ።
85 ከአንተና ፡ ከነርሱ ፡ ውስጥ ፡ ከተ
ከተሉህ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ገሀነምን ፡
በእርግጥ ፡ እመላታለሁ ።
86 በላቸው ፡—በርሱ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡
ዋጋ ፡ አልጠይቃችሁም ፤ እኔም ፡
ከተግደርዳሪዎቹ ፡ አይደለሁም ።
87 እርሱ ፡ (ቁርአን) ፡ ለዓለማት ፡
መገሠጫ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደ
ለም ።
88 ትንቢቱንም ፡ (እውነት ፡ መኾኑን) ፡
ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ በእርግጥ ፡ ታው
ቁታላችሁ ።



39ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ዙመር ፤ (የጭፍራዎች ፡ ምዕራፍ) ፤ በመ
ካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 75 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፤ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 የመጽሐፉ ፡ መወረድ ፡ አሸና
ፊው ፡ ጥበበኛው ፡ ከኾነው ፡
አላህ ፡ ነው ።
2 እኛ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ መጽሐፉን ፡
በውነት ፡ (የተመላ) ፡ ሲኾን ፡
አወረድነው ፤ አላህንም ፡ ሃይማ
ኖትን ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡ ያጠራህ ፡
ኾነህ ፡ ተገዛው ።
3 ንቁ ፤ ፍጹም ፡ ጥሩ ፡ የኾነው ፡
ሃይማኖት ፡ የአላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
እነዚያም ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ (ጣዖ
ታትን) ፡ ረዳቶች ፡ የያዙት ፡
ወደ ፡ አላህ ፡ ማቃረብን ፡ እንዲ
ያቃርቡን ፡ እንጅ ፡ ለሌላ ፡ አን
ግገዛቸውም ፡ (ይላሉ) ፤ አላህ ፡
በዚያ ፡ እነርሱ ፡ በርሱ ፡ በሚለ
ያዩበት ፡ ነገር ፡ በመካከላቸው ፡
ይፈርዳል ፤ አላህ ፡ እርሱ ፡ ውሸ
ታም ፡ ከሓዲ ፡ የኾነን ፡ ሰው ፡
አያቀናም ።
4 አላህ ፡ ልጅን ፡ መያዝ ፡ በፈለገ ፡
ኖሮ ፡ ከሚፈጥረው ፡ ውስጥ ፡
የሚሻውን ፡ ይመርጥ ፡ ነበር ፤
ጥራት ፡ ተገባው ። እርሱ ፡ አሸ
ናፊው ፡ አንዱ ፡ አላህ ፡ ነው ።
5 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ በውነት ፡
ፈጠረ ፤ ሌሊትን ፡ በቀን ፡ ላይ ፡
ይጠቀልላል ፤ ቀንንም ፡ በሌሊት ፡
ላይ ፡ ይጠቀልላል ፤ ፀሐይንና ፡
ጨረቃንም ፡ ገራ ፤ ሁሉም ፡
ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ይሮጣሉ ፤
ንቁ ፡ እርሱ ፡ አሸናፊው ፡ መሐ
ሪው ፡ ነው ።
6 ከአንዲት ፡ ነፍስ ፡ ፈጠራችሁ ፤
ከዚያም ፡ ከርሷ ፡ መቀናጆዋን ፡
አደረገ ። ለናንተም ፡ ከግመልና ፡
ከከብት ፡ ከፍየል ፡ ከበግ ፡ ስም
ንት ፡ ዓይነቶችን ፡ (ወንድና ፡
ሴት) ፡ አወረደ ፤ በእናቶቻችሁ ፡
ሆዶች ፡ ውስጥ ፡ በሦስት ፡ ጨለ
ማዎች ፡ ውስጥ ፡ (1) ከመፍ
ጠር ፡ በኋላ ፡ (ሙሉ) ፡ መፍጠ
ርን ፡ ይፈጥራችኋል ፤ (2) ይሃችሁ ፡
ጌታችሁ ፡ አላህ ፡ ነው ። ሥል
ጣኑ ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ከርሱ ፡
ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ ታዲያ ፡
ወዴት ፡ ትዞራላችሁ ።
7 ብትክዱ ፡ አላህ ፡ ከናንተ ፡ የተ
ብቃቃ ፡ ነው ። ለባሪያዎቹም ፡ ክህደ
ትን ፡ አይወድም ፤ ብታመሰግኑም ፤
እርሱን ፡ ይወድላችኋል ፤ ማንኛይ
ቱም ፡ ኃጢአትን ፡ ተሸካሚ ፡ ነፍ
ስ ፡ የሌላይቱን ፡ ኃጢአት ፡ አት
ሸከምም ፤ ከዚያም ፡ መመለሻ
ችሁ ፡ ወደ ፡ ጌታችሁ ፡ ነው ፤ ትሠ
ሩት ፡ የነበራችሁትንም ፡ ይነግራ
ችኋል ፤ እርሱ ፡ በልቦች ፡ ውስጥ ፡
ያሉትን ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።

---

1 በሆድ ፡ በማሕፀንና ፡ በእንግዴ ፡ ልጅ ።
2 ከፍትወት ፡ ጠብታ ፡ ከዚያም ፡ ከረጋ ፡ ደም ፡ ከዚያም ፡ ከቁራጭ ፡ ስጋ ፡ ለጥቆ ፡ ሙሉ ፡ ሰው ፡ ያደርጋችኋል ።

8 ሰውንም ፡ ጉዳት ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡
ጌታውን ፡ ወደርሱ ፡ ተመላሽ ፡
ኾኖ ፡ ይጠራል ። ከዚያም ፡
ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ጸጋን ፡ በሰጠው ፡
ጊዜ ፡ ያንን ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡
ወደርሱ ፡ ይጸልይበት ፡ የነበረ
ውን ፡ (መከራ) ፡ ይረሳል ፤ ከመ
ንገዱ ፡ ለማሳሳትም ፡ ለአላህ ፡
ባላንጣዎችን ፡ ያደርጋል ፤ በክ
ሕደትህ ፡ ጥቂትን ፡ ተጣቀም ፤
አንተ ፡ በእርግጥ ፡ ከእሳት ፡
ጓዶች ፡ ነህ ፡ በለው ።
9 እርሱ ፡ የመጨረሻይቱን ፡ ዓለም፡
(ቅጣት) ፡ የሚፈራ ፡ የጌታው
ንም ፡ ችሮታ ፡ የሚከጅል ፡ ሲ
ኾን ፡ በሌሊት ፡ ሰዓቶች ፡ ሰጋ
ጅና ፡ ቋሚ ፡ ኾኖ ፡ ለጌታው ፡
የሚገገዛ ፡ ሰው ፡ (እንደ ፡ ተስ
ፋ ፡ ቢሱ ፡ ከሓዲ ፡ ነውን? በለው) ፤
እነዚያ ፡ የሚያውቁና ፡ እነዚያ ፡
የማያውቁ ፡ ይተካከላሉን ? በላ
ቸው ፤ የሚገነዘቡት ፡ ባለ ፡ አእ
ምሮዎቹ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።
10 (ጌታችሁ) ፡ እናንተ ፡ ያመናችሁ፡
ባሮቼ ፡ ሆይ ! ጌታችሁን ፡ ፍሩ ፤
ለነዚያ ፡ በዚች ፡ በቅርቢቱ ፡
ዓለም ፡ መልካም ፡ ለሠሩት ፡
መልካም ፡ ምንዳ ፡ አላቸው ።
የአላህ ፡ ምድርም ፡ ሰፊ ፡ ናት ፤
(ብትቸገሩ ፡ ተሰደዱ) ፤ ታጋሾቹ፡
ምንዳቸውን ፡ የሚሰሰጡት ፡ ያለ
ግምት ፡ ነው ፤ (ይላል) ፡ በላ
ቸው ።
11 በል ፡-እኔ ፡ አላህን ፡ ሃይማኖትን ፡
ለርሱ ፡ ያጠራሁ ፡ ኾኜ ፡ እንድ
ግገዛው ፡ ታዘዝኩ ፤
12 የሙስሊሞችም፡ መጀመሪያ፡ እን
ድኾን ፡ ታዘዝኩ ።
13 እኔ ፡ ከጌታዬ ፡ ባምጥ ፡ የታላቁን፡
ቀን ፡ ቅጣት ፡ እፈራለሁ ፡ በል ።
14 አላህን ፡ ሃይማኖቴን ፡ ለርሱ ፡
ያጠራሁ ፡ ኾኜ ፡ እግገዛዋለሁ ፡
በል ።
15 ከርሱ ፡ ሌላ ፡ የሻችሁትን ፡ ተገዙ ፤
ከሳሪዎች ፡ ማለት ፡ እነዚያ ፡
በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ነፍሶቻቸው
ንና ፡ ቤተሰቦቻቸውን ፡ ያከሰሩ ፡
ናቸው ፤ ንቁ ፤ ይህ ፡ እርሱ ፡
ግልጽ ፡ ከሳራ ፡ ነው ፡ በላቸው ።
16 ለነርሱ ፡ ከበላያቸው ፡ ከእሳት ፡
የኾኑ ፡ (ድርብርብ) ፡ ጥላዎች ፡
አሏቸው ፤ ከበታቻቸውም ፡ ጥላ
ዎች ፡ አሏቸው ። ይህ ፡ አላህ ፡
ባሮቹን ፡ (እንዲጠነቀቁ) ፡ በርሱ ፡
ያስፈራራበታል ፤ ባሮቼ ፡ ሆይ !
ስለዚህ ፡ ፍሩኝ ።
17 እነዚያም ፡ ጣዖታትን ፡ የሚግገ
ዟት ፡ ከመኾን ፡ የራቁ ፡ ወደ ፡
አላህም ፡ የዞሩ ፡ ለነርሱ ፡ ብስ
ራት ፡ አላቸው ፤ ስለዚህ ፡ ባሮ
ቼን ፡ አብስር ።
18 እነዚያን ፡ ንግግርን ፡ የሚያዳ
ምጡትንና ፡ መልካሙን ፡ የሚ
ከተሉትን ፡ (አብስር) ፤ እነዚያ ፡
እነርሱ ፡ አላህ ፡ የመራቸው ፡
ናቸው ። እነዚያም ፡ እነሱ ፡ ባለ ፡
አእምሮዎቹ ፡ ናቸው ።
19 በርሱ ፡ ላይ ፡ የቅጣት ፡ ቃል ፡
የተረጋገጠችበት ፡ ሰው ፡ (ትመ
ራዋለህን?) ፡ አንተ ፡ በእሳት ፡
ውስጥ ፡ ያለን ፡ ሰው ፡ ታድና
ለህን ?
20 ግን ፡ እነዚያ ፡ ጌታቸውን ፡ የፈሩ፡
ለነርሱ ፡ ከበላያቸው ፡ የታነጹ ፡
ሰገነቶች ፡ ያሏቸው ፡ ሰገነቶች ፡
ከሥሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚ



ፈስሱባቸው ፡ የኾኑ ፡ አሏቸው ፤
(ይህንን) ፡ አላህ ፡ ቃል ፡ ገባላ
ቸው ፤ አላህ ፡ ቃሉን ፡ አያፈር
ስም ።
21 አላህ ፡ ከሰማይ ፡ ውሃን ፡ እንዳ
ወረደና ፡ በምድርም ፡ ውስጥ ፡
ምንጮች ፡ አድርጎ ፡ እንዳስገ
ባው ፡ አላየህምን ? ከዚያም ፡
በርሱ ፡ ዓይነቶቹ ፡ የተለያዩን ፡
አዝመራ ፡ ያወጣል ፤ ከዚያም ፡
ይደርቃል ፤ ገርጥቶም ፡ ታየዋ
ለህ ፤ ከዚያም ፡ ስብርብር ፡ ያደ
ርገዋል ፤ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ለባለ ፡
አእምሮዎች ፡ ግሣጼ ፡ አለበት ።
22 አላህ ፡ ደረቱን ፡ ለእስልምና ፡
ያሰፋለትና ፡ እርሱም ፡ ከጌታው ፡
ዘንድ ፡ በብርሃን ፡ ላይ ፡ የኾነ ፡
ሰው ፡ (ልቡ ፡ እንደ ፡ ደረቀ ፡
ሰው ፡ ነውን ?) ልቦቻቸውም ፡
ከአላህ ፡ መወሳት ፡ ለደረቁ ፡
ሰዎች ፡ ወዮላቸው ፤ እነዚያ ፡
በግልጽ ፡ መሳሳት ፡ ውስጥ ፡
ናቸው ።
23 አላህ ፡ ከዜና ፡ ሁሉ ፡ መልካምን፡
ተመሳሳይ ፡ ተደጋጋሚ ፡ የኾነን ፡
መጽሐፍ ፡ አወረደ ፤ ከርሱ ፡
(ግሣጼ) ፡ የነዚያ ፡ ጌታቸውን ፡
የሚፈሩት ፡ ሰዎች ፡ ቆዳዎች ፡
ይኮማተራሉ ፤ ከዚያም ፡ ቆዳዎ
ቻቸውና ፡ ልቦቻቸው ፡ ወደ ፡
አላህ ፡ (ተስፋ) ፡ ማስታወስ ፡
ይለዝባሉ ። ይህ ፡ የአላህ ፡ መም
ሪያ ፡ ነው ፤ በርሱ ፡ የሚሻውን ፡
ሰው ፡ ይመራበታል ፤ አላህም ፡
የሚያጠመው ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡
ምንም ፡ አቅኚ ፡ የለውም ።
24 በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ክፉን ፡ ቅጣት ፡
በፊቱ ፡ የሚመክት ፡ ሰው ፡ (ከቅ
ጣት ፡ እንደሚድን ፡ ነውን ?) ለበ
ዳዮችም ፡ ትሠሩት ፡ የነበራች
ሁትን ፡ (ቅጣቱን) ፡ ቅመሱ ፡
ይባላሉ ።
25 ከነሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ አስ
ተባበሉ ፤ ቅጣቱም ፡ ከማያው
ቁት ፡ በኩል ፡ መጣባቸው ።
26 አላህም ፡ በቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡
ውርደትን ፡ አቀመሳቸው ። የመ
ጨረሻይቱም ፡ ዓለም ፡ ቅጣት ፡
በጣም ፡ ትልቅ ፡ ነው ። የሚያ
ውቁ ፡ ቢኾኑ ፡ ኖሮ ፡ (አያስተባ
ብሉም ፡ ነበር) ።
27 በዚህም ፡ ቁርአን ፡ ውስጥ ፡ ለሰ
ዎች ፡ ይገሠጹ ፡ ዘንድ ፡ ከየም
ሳሌው ፡ ሁሉ ፡ በእርግጥ ፡ አብ
ራራን ፤
28 መዛባት ፡ የሌለበት ፡ ዐረብኛ ፡
ቁርአን ፡ ሲኾን ፡ (አብራራነው)፡
ሊጠነቀቁ ፡ ይከጀላልና ።
29 አላህ ፡ በርሱ ፡ ተጨቃጫቂዎች ፡
የኾኑ ፡ ተጋሪዎች ፡ ያሉትን ፡
ባሪያና ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡
ንጹሕ ፡ የኾነን ፡ ባሪያ ፡ (ለሚያ
ጋራና ፡ ባንድነቱ ፡ ለሚያምን ፡
ሰው) ፡ ምሳሌ ፡ አደረገ ፤ በም
ሳሌ ፡ ይተካከሉን ? ፤ ምስጋና ፡
ለአላህ ፡ ይገባው ። በውነቱ ፡
አብዛኞቻቸው ፡ አያውቁም ።
30 አንተ ፡ ሟች ፡ ነህ ፤ እነርሱም ፡
ሟቾች ፡ ናቸው ።
31 ከዚያም ፡ እናንተ ፡ በትንሣኤ ፡
ቀን ፡ እጌታችሁ ፡ ዘንድ ፡ ትከራ
ከራላችሁ ።

★ ★ ★

32 በአላህም ፡ ላይ ፡ ከዋሸ ፡ እውነ
ቱንም ፡ በመጣላት ፡ ጊዜ ፡ ከአ
ስተባበለ ፡ ሰው ፡ ይበልጥ ፡

በዳይ ፡ ማን ፡ ነው ? በገሀነም ፡
ውስጥ ፡ ለከሓዲዎች ፡ መኖሪያ ፡
የለምን ? (አልለ ፡ እንጅ) ።
33 ያም ፡ በውነት ፡ የመጣው ፡ በርሱ
ያመነውም ፡ እነዚያ ፡ እነርሱ ፡
አላህን ፡ ፈሪዎች ፡ ናቸው ።
34 ለነርሱ ፡ በጌታቸው ፡ ዘንድ ፡
የሚሹት ፡ ሁሉ ፡ አላቸው ፤ ይህ ፡
የበጎ ፡ አድራጊዎች ፡ ምንዳ ፡
ነው ።
35 አላህ ፡ ያንን ፡ (በስሕተት) ፡ የሠ
ሩትን ፡ መጥፎ ፡ ሥራ ፡ ከነርሱ ፡
ሊሰርይላቸው ፡ በዚያም ፡ ይሠ
ሩት ፡ በነበሩት ፡ በመልካሙ ፡
ሥራ ፡ ምንዳቸውን ፡ ሊመነዳ
ቸው ፡ (ይህንን ፡ አደረገ) ።
36 አላህ ፡ ባሪያውን ፡ በቂ ፡ አይደ
ለምን ? በነዚያ ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡
በኾኑትም ፡ (ጣዖታት) ፡ ያስፈ
ራሩሃል ፤ አላህ ፡ የሚያጠመ
ውም ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡ ምንም ፡
አቅኚ ፡ የለውም ።
37 አላህ ፡ የሚያቀናውም ፡ ሰው ፡
ለርሱ ፡ ምንም ፡ አጥማሚ ፡
የለውም ፤ አላህ ፡ አሸናፊ ፡ የመ
በቀል ፡ ባለ ፡ ቤት ፡ አይደለምን ?
38 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ የፈጠረ ፡
ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ብትጠይቃ
ቸው ፡ አላህ ፡ ነው ፡ ይሉሃል ።
ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የምትግገዟቸውን፡
(ጣዖታት) ፡ አያችሁን? (ንገሩኝ) ፡
አላህ ፡ በጉዳት ፡ ቢፈልገኝ ፡ እነሱ
ጉዳቱን ፡ ገላጮች ፡ ናቸውን ?
ወይስ ፡ በችሮታው ፡ ቢፈቅደኝ ፡
እነርሱ ፡ ችሮታውን ፡ አጋጆች ፡
ናቸውን ? በላቸው ። አላህ ፡
በቂዬ ፡ ነው ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡
ተመኪዎች ፡ ይመካሉ ፤ በል ።
39 (ሙሐመድ ፡ ሆይ !) በላቸው ፡—
ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ! ባላችሁበት ፡
ኹነታ ፡ ላይ ፡ ሥሩ ፤ እኔ ፡ ሠሪ፡
ነኝና ፤ ወደፊትም ፡ ታውቃላ
ችሁ ፤
40 ያንን ፡ የሚያሳፍረው ፡ ቅጣት ፡
የሚመጣበትንና ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
ዘውታሪ ፡ ቅጣት ፡ የሚሰፍር
በትን ፡ (ታውቃላችሁ) ?
41 እኛ ፡ መጽሐፉን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡
ለሰዎች ፡ (ጥቅም) ፡ በውነት ፡
አወረድነው ፤ የተመራም ፡ ሰው ፡
ለነፍሱ ፡ ነው ፤ የጠመመም ፡
ሰው ፡ የሚጠመው ፡ (ጉዳቱ) ፡
በርሷ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ አንተም ፡
(ታስገድዳቸው ፡ ዘንድ) ፡ በነርሱ ፡
ላይ ፡ ጠባቂ ፡ አይደለህም ።
42 አላህ ፡ ነፍሶችን ፡ በሞታቸው ፡
ጊዜ ፡ ይወስዳል ፤ ያችንም ፡ ያል
ሞተችውን ፡ በእንቅልፏ ፡ ጊዜ ፡
(ይወስዳታል) ፤ ታዲያ ፡ ያችን ፡
ሞትን ፡ የፈረደባትን ፡ ይይዛታል፤
ሌላይቱንም ፡ እስከ ፡ ተወሰነ ፡
ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ይለቃታል ፤ በዚህ ፡
ውስጥ ፡ ለሚያስተነትኑ ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ምልክቶች ፡ አሉበት ።
43 ይልቁንም ፡ (ቁረይሾች) ፡ ከአ
ላህ ፡ ሌላ ፡ አማላጆችን ፡ ያዙ ፤
እነርሱ ፡ ምንንም ፡ የማይችሉና ፡
የማያውቁ ፡ ቢኾኑም? በላቸው ።
44 ምልጃ ፡ መላውም ፡ የአላህ ፡ ብቻ፡
ነው ፤ የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ሥል
ጣን ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ከዚ
ያም ፡ ወደርሱ ፡ ትመለሳላችሁ ፤
በላቸው ።
45 አላህም ፡ ብቻውን ፡ በተወሳ ፡
ጊዜ ፡ የነዚያ ፡ በመጨረሻይቱ ፡
ዓለም ፡ የማያምኑት ፡ ሰዎች ፡



ልቦች ፡ ይሸመቀቃሉ ፤ (ይደነብ
ራሉ) ፤ እነዚያም ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡
የኾኑት ፡ (ጣዖታት) ፡ በተወሱ ፡
ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ይደሰ
ታሉ ።
46 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ የፈጠ
ርክ ፡ ሩቁንም ፡ ቅርቡንም ፡
ዐዋቂ ፡ የኾንክ ፡ አላህ ፡ ሆይ !
አንተ ፡ በባሮችህ ፡ መካከል ፡
በዚያ ፡ በርሱ ፡ ይለያዩበት ፡ በነበ
ሩት ፡ ነገር ፡ ትፈርዳለህ ፤ በል ።
47 ለነዚያም ፡ ለበደሉት ፡ በምድር ፡
ያለው ፡ ሁሉ ፡ መላውም ፡ ከርሱ ፡
ጋር ፡ መሰሉም ፡ ቢኖራቸው ፡
ኖሮ ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ከቅጣቱ ፡
ክፋት ፡ የተነሳ ፡ በርሱ ፡ ነፍሶቻ
ቸውን፡ በተበገዙበት፡ ነበር ። ለነ
ርሱም ፡ ከአላህ ፡ ዘንድ ፡ ያስቡት ፡
ያልነበሩት ፡ ሁሉ ፡ ይገለጽላቸ
ዋል ።
48 ለነሱም ፡ የሠሩዋቸው ፡ መጥፎ
ዎቹ ፡ ይገለጹላቸዋል ። በነርሱም፡
ላይ ፡ በርሱ ፡ ያላግጡበት ፡ የነበ
ሩት ፡ ቅጣት ፡ ይሰፍርባቸዋል ።
49 ሰውንም ፡ ጉዳት ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡
ይጠራናል ፤ ከዚያም ፡ ከኛ ፡ የኾነ
ውን ፡ ጸጋ ፡ በሰጠነው ፡ ጊዜ ፡
እርሱን ፡ የተሰጠሁት፥ ፡ በዕው
ቀት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ይላል ፤ ይልቁ
ንም ፡ እርሷ ፡ (ጸጋይቱ) ፡ መፈ
ተኛ ፡ ናት ፤ ግን ፡ አብዛኞቻቸው ፡
አያውቁም ።
50 እነዚያ ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩት፡
ሕዝቦች ፡ በእርግጥ ፡ ብለዋታል ፤
ይሠሩት ፡ የነበሩትም ፡ ነገር ፡ ከነ
ርሱ ፡ አልጠቀማቸውም ።
51 የሠሩዋቸውም ፡ መጥፎዎች ፡
(ቅጣት) ፡ አገኛቸው ። ከነዚህም ፡
እነዚያ ፡ የበደሉት ፡ የሠሩዋቸው ፡
መጥፎዎች ፡ (ፍዳ) ፡ በእርግጥ ፡
ይነካቸዋል ። እነርሱም ፡ አምላ
ጮች ፡ አይደሉም ።
52 አላህ ፡ ሲሳዩን ፡ ለሚሻው ፡ ሰው ፡
የሚያሰፋ ፡ የሚያጠብም ፡ መኾ
ኑን ፡ አያውቁምን ? በዚህ ፡
ውስጥ ፡ ለሚያምኑት ፡ ሕዝቦች ፡
ግሣጼዎች ፡ አሉበት ።
53 በላቸው ፡— እናንተ ፡ በነፍሶቻ
ችሁ ፡ ላይ ፡ ድንበር ፡ ያለፋችሁ ፡
ባሮቼ ፡ ሆይ ! ከአላህ ፡ እዝነት ፡
ተስፋ ፡ አትቍረጡ ፤ አላህ ፡ ኃጢ
አቶችን ፡ በመላ ፡ ይምራልና ፡
እነሆ ፡ እርሱ ፡ መሓሪው ፡ አዛኙ ፡
ነውና ።
54 ቅጣቱም ፡ ወደናንተ ፡ ከመምጣ
ቱና ፡ ከዚያም ፡ የማትረዱ ፡ ከመ
ኾናችሁ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ጌታችሁ፡
(በመጸጸት) ፡ ተመለሱ ፤ ለርሱም ፡
ታዘዙ ።
55 እናንተ ፡ የማታውቁ ፡ ስትኾኑም ፡
ቅጣቱ ፡ በድንገት ፡ ሳይመጣባ
ችሁ ፡ በፊት ፡ ከጌታችሁ ፡ ወደ
ናንተ ፡ የተወረደውን ፡ መልካ
ሙን ፡ (መጽሐፍ) ፡ ተከተሉ ።
56 (የካደች) ፡ ነፍስ ፡ እኔ ፡ ከሚሳለ
ቁት ፡ የነበርኩ ፡ ስኾን ፡ በአላህ ፡
በኩል ፡ ባጓደልኩት ፡ ዋ ፡ ጸጸቴ!
ማለቷን ፡ (ለመፍራት) ፤
57 ወይም ፡ አላህ ፡ በመራኝ ፡ ኖሮ ፡
ከሚጠነቀቁት ፡ እኾን ፡ ነበር ፡
ማለቷን ፡ (ለመፍራት) ፤
58 ወይም ፡ ቅጣቱን ፡ በምታይ ፡
ጊዜ ፡ ለኔ ፡ (ወደ ፡ ምድረ ፡ ዓለም)
አንድ ፡ ጊዜ ፡ መመለስ ፡ በኖረ
ኝና ፡ ከበጎ ፡ አድራጊዎቹ ፡ በኾ
ንኩ ፡ ማለቷን ፡ (ለመፍራት ፡
መልካሙን ፡ ተከተሉ) ።

59 የለም ፡ ተመርተሃል ፤ አንቀጾቼ ፡
በእርግጥ ፡ መጥተውልሃል ፤ በነ
ሱም ፡ አስተባብለሃል ፤ ኮርተሃ
ልም ፤ ከከሓዲዎቹም ፡ ኾነሃል ፤
(ይባላል) ።
60 በትንሣኤ ፡ ቀንም ፡ እነዚያን ፡
በአላህ ፡ ላይ ፡ የዋሹትን ፡ ፊቶቻ
ቸው ፡ የጠቆሩ ፡ ኾነው ፡ ታያቸዋ
ለህ ፤ በገሀነም ፡ ውስጥ ፡ ለትዕቢ
ተኞች ፡ መኖሪያ ፡ የለምን ?
61 እነዚያንም ፡ የተጠነቀቁትን ፡
በማግኛቸው ፡ ስፍራ ፡ ኾነው ፡
አላህ ፡ ያድናቸዋል ፤ ክፉ ፡ ነገር ፡
አይነካቸውም ፤ እነርሱም ፡ አያዝ
ኑም ።
62 አላህ ፡ የነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡
ነው ። እርሱም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ አስተናባሪ ፡ ነው ።
63 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ (ድልብ) ፡
መክፈቻዎች ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡
ናቸው ፤ እነዚያም ፡ በአላህ ፡ አን
ቀጾች ፡ የካዱት ፡ እነዚያ ፡ እነሱ ፡
ከሳሪዎቹ ፡ ናቸው ።
64 እላንተ ፡ መሃይማን፡ ሆይ !
ከአላህ ፡ ሌላን ፡ እንድግገዛ ፡ ታዙ
ኛላችሁን ? በላቸው ።
65 ብታጋራ ፡ ሥራህ ፡ በእርግጥ ፡
ይታበሳል ፤ በእርግጥም ፡ ከከሓዲ
ዎቹ ፡ ትኾናለህ ፡ ማለት ፡ ወደ ፡
አንተም ፡ ወደነዚያም ፡ ካንተ ፡
በፊት ፡ ወደነበሩት ፡ በእርግጥ ፡
ተወርዷል ።
66 ይልቅ ፡ አላህን ፡ ብቻ ፡ ተገዛም ፤
ከአመስጋኞቹም ፡ ኹን ።
67 አላህንም ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡
ምድር ፡ በመላ ፡ ጭብጡ ፡ (1)
ስትኾን ፤ ሰማያትም ፡ በኀይሉ ፡
የሚጠቀለሉ ፡ ሲኾኑ ፡ (ከርሱ ፡
ጋር ፡ ሌላን ፡ በማጋራታቸው) ፡
ተገቢ ፡ ክብሩን ፡ አላከበሩትም ።
ከሚያጋሩት ፡ ጠራ ፤ ላቀም ።
68 በቀንዱም ፡ ይነፋፋል ፤ በሰማያት ፡
ውስጥ ፡ ያለው ፡ ፍጡርና ፡ በምድ
ርም ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ፍጡር ፡
ሁሉ ፡ አላህ ፡ የሻው ፡ ሲቀር ፡
በድንጋጤ ፡ ይሞታል ፤ ከዚያም ፡
በርሱ ፡ ሌላ ፡ (መነፋት) ፡ ይነ
ፋል ፤ ወዲያውም ፡ እነርሱ ፡ (የሚ
ሠራባቸውን) ፡ የሚጠባበቁ ፡
ኾነው ፡ ቋሚዎች ፡ ይኾናሉ ።
69 ምድርም ፡ በጌታዋ ፡ ብርሃን ፡ ታበ
ራለች ፤ መጽሐፉም ፡ ይቀረባል ፤
ነቢያቱና ፡ ምስክሮቹም ፡ ይምመ
ጣሉ ፤ በመካከላቸውም ፡ በው
ነት ፡ ይፈረዳል ፤ እነርሱም ፡ አይ
በደሉም ።
70 ነፍስም ፡ ሁሉ ፡ የሠራችውን ፡
ሥራ ፡ ትሞላለች ፤ (ትሰፈራለች) ፤
እርሱም ፡ የሚሠሩትን ፡ ሁሉ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።
71 እነዚያ ፡ የካዱትም ፡ የተከፋፈሉ ፡
ጭፍሮች ፡ ኾነው ፡ ወደ ፡ ገሀነም ፡
ይነዳሉ ፤ በመጧትም፡ ጊዜ ፡ ደጃ
ፎችዋ ፡ ይከፈታሉ ፤ ዘበኞችዋም ፡
ከናንተ ፡ የኾኑ ፡ መልክተኞች ፡
የጌታችሁን ፡ አንቀጾች ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ የሚያነቡላችሁ ፡ የዚህንም ፡
ቀን ፡ መገናኘት ፡ የሚያስጠነቅቋ
ችሁ ፡ አልመጡዋችሁምን ? ይሏ
ቸዋል ፤ የለም ፡ መጥተውናል ፤
ግን ፡ የቅጣቲቱ ፡ ቃል ፡ በከሓዲ
ዎች ፡ ላይ ፡ ተረጋገጠች ፡ ይላሉ ።
72 የገሀነምን ፡ ደጃፎች ፡ በውስጧ ፡
ዘውታሪዎች ፡ ስትኾኑ ፡ ግቡ ፤
የትዕቢተኞችም ፡ መኖሪያ ፡ ምን ፡
ትከፋ ! ይባላሉ ።

1 አንድ ፡ ጭብጥ ።

73 እነዚያም ፡ ጌታቸውን ፡ የፈሩት ፡
የተከፋፈሉ ፡ ጭፍሮች፡ ኾነው ፡
ወደ፡ገነት፡ ይነዳሉ ፤ በመጧትም ፡
ጊዜ ፡ ደጃፎችዋ ፡ የተከፈቱ ፡
ሲኾኑ ፡ ዘበኞችዋም ፡ ለነርሱ ፡
ሰላም ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ይኹን ፤
ተዋባችሁ ፤ ዘውታሪዎች ፡ ኾና
ችሁ ፡ ግቧት ፤ ባሏቸው ፡ ጊዜ ፡
(ይገቧታል) ።
74 ምስጋና ፡ ለአላህ ፡ ለዚያ ፡ ተስፋ ፡
ቃሉን ፡ ለሞላልን ፤ የገነትን ፡
ምድር ፡ በምንሻው ፡ ስፍራ ፡ የም
ንሰፍር ፡ ስንኾን ፡ ላወረሰን ፡ ይገ
ባው ፡ ይላሉም ፤ የሠሪዎችም ፡
ምንዳ ፡ ምን ፡ ያምር !
75 መላእክትንም ፡ በጌታቸው ፡ ምስ
ጋና ፡ ቀላቅለው ፡ የሚያጠሩ ፡
ሲኾኑ ፡ በዐርሹ ፡ ዙሪያ ፡ ከባቢ
ዎች ፡ ኾነው ፡ ታያለህ ። በመካከ
ላቸውም ፡ (1) በውነት ፡ ይፈረ
ዳል ፤ ይባላልም ፤ ምስጋና ፡ ለአ
ላህ ፡ ለዓለማት ፡ ጌታ ፡ ይገባው ።

1 በፍጡሮች ፡ መካከል ።

## ምዕራፍ ፡ 40 ፡ አል-ሙእሚን ። ክፍል ፡ 24 ።

40ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሙእሚን ፡ (የምእምን ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 85 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው።
1 ሐ. መ. (ሓ. ሚም) ፤ (1)
2 የመጽሐፉ ፡ መወረድ ፡ አሸናፊ ፡
ዐዋቂ ፡ ከኾነው ፡ አላህ ፡ ነው ።
3 ኀጢአትን ፡ መሓሪ ፡ ጸጸትንም ፡
ተቀባይ ፡ ቅጣተ ፡ ብርቱ ፡ የል
ግስና ፡ ባለቤት ፡ ከኾነው ፡ (አላህ
የወረደ ፡ ነው) ፤ ከርሱ ፡ በቀር ፡
አምላክ ፡ የለም ፤ መመለሻው ፡
ወደርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
4 በአላህ ፡ አንቀጾች ፡ እነዚያ ፡
የካዱት ፡ ቢኾኑ ፡ እንጅ ፡ ማንም፡
(በመዝለፍ) ፡ አይከራከርም ።
በያገሮችም ፡ ውስጥ ፡ መዘዋወ
ራቸው ፡ አይሸንግልህ ።
5 ከነሱ ፡ በፊት ፡ የኑሕ ፡ ሕዝቦች ፡
ከኋላቸውም ፡ አሕዛቦቹ ፡ አስተ
ባበሉ ፤ ሕዝቦችም ፡ ሁሉ ፡ መል
ክተኛቸውን ፡ ሊይዙ ፡ አሰቡ ፤
በውሸትም ፡ በርሱ ፡ እውነትን ፡
ሊያጠፉበት ፡ ተከራከሩ ፤ ያዝ
ኳቸውም ፤ ታዲያ ፡ ቅጣቴ ፡ እን
ዴት ፡ ነበር ?
6 እንደዚሁም ፡ የጌታህ ፡ ቃል ፡
በነዚያ ፡ በካዱት ፡ ላይ ፡ እነሱ ፡
የእሳት ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ፡ ማለት፡
ተረጋገጠች ።
7 እነዚያ ፡ ዐርሹን ፡ የሚሸከሙት ፡
እነዚያም ፡ በዙሪያው ፡ ያሉት ፡
በጌታቸው ፡ ምስጋና ፡ ያወድሳሉ፤

1 የሚኾነው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ፍርዱ ፡ ተፈ
ጸመ ።

በርሱም ፡ ያምናሉ ፤ ጌታችን ፡
ሆይ ! ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ በእዝነትና ፡
በዕውቀት ፡ ከበሃል ፤ ስለዚህ ፡
ለነዚያ ፡ ለተጸጸቱት ፡ መንገድ
ህንም ፡ ለተከተሉት ፡ ምሕረት ፡
አድርግላቸው ፤ የእሳትንም ፡ ቅ
ጣት ፡ ጠብቃቸው ፡ እያሉ ፡
ለነዚያ ፡ ላመኑት ፡ ምሕረትን ፡
ይለምናሉ ።
8 ጌታችን ፡ ሆይ ! እነርሱንም ፡
ከአባቶቻቸውና ፡ ከሚስቶቻቸው
ም ፡ ከዝርዮቻቸውም ፡ የበጀውን ፡
ሁሉ ፡ እነዚያን ፡ ቃል ፡ የገባ
ህላቸውን ፡ የመኖሪያ ፡ ገነቶች ፡
አግባቸው ፤ አንተ ፡ አሸናፊው ፡
ጥበበኛው ፡ አንተ ፡ ነህና ።
9 ከቅጣቶችም ፡ ጠብቃቸው ፤ በ
ዚያ ፡ ቀንም ፡ የምትጠብቀውን ፡
ሰው ፡ በእርግጥ ፡ አዘንክለት ፤
ይህም ፡ እርሱ ፡ ታላቅ ፡ ማግ
ኘት ፡ ነው ።
10 እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡
እምነት ፡ በምትጥጠሩና ፡ በምት
ክዱ ፡ ጊዜ ፡ አላህ ፡ (እናንተን) ፡
መጥላቱ ፡ ነፍሶቻችሁን ፡ (ዛሬ) ፡
ከመጥላታችሁ ፡ የበለጠ ፡ ነው ፤
በማለት ፡ ይጥጠራሉ ።
11 ጌታችን ፡ ሆይ ! ሁለትን ፡ ሞት ፡
አሞትከን ፡ ሁለትንም ፡ ሕይወት ፡
ሕያው ፡ አደረግከን ፤ በኃጢአቶ
ቻችንም ፡ መሰከርን ፤ ታዲያ ፡
(ከእሳት) ፡ ወደ ፡ መውጣት ፡
መንገድ ፡ አለን ? ይላሉ ።
12 ይሃችሁ ፡ እነሆ ፡ አላህ ፡ ብቻውን
በተጠራ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ካዳችሁ ፡
በርሱም ፡ ተጋሪ ፡ ቢደረግ ፡ የም
ታምኑ ፡ ስለ ፡ ኾናችሁ ፡ ነው ፤
ስለዚህ ፡ ፍርዱ ፡ ከፍተኛ ፡ ታላቅ
ለኾነው ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
13 እርሱ ፡ ያ ፡ (ለአምላክነቱ) ፡ ምል
ክቶቹን ፡ የሚያሳያችሁ ፡ ለናን
ተም ፡ ከሰማይ ፡ ሲሳይን ፡ የሚ
ያወርድላችሁ ፡ ነው ፤ ወደርሱም ፡
የሚመለስ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ እንጂ ፡
ሌላው ፡ አይገሠጽም ።
14 አላህንም ፡ ከሓዲዎች ፡ ቢጠሉም
ሃይማኖትን ፡ ለርሱ ፡ አጥሪዎች ፡
ኾናችሁ ፡ ተገዙት ።
15 (እርሱ) ፡ ደረጃዎችን ፡ ከፍ ፡
አድራጊ ፡ የዐርሹ ፡ ባለቤት ፡
ነው ፤ የመገናኛውን ፡ ቀን ፡ ያስ
ፈራራ ፡ ዘንድ ፡ ከባሮቹ ፡ በሚ
ሻው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ከትእዛዙ ፡
መንፈስን ፡ (ራእይን) ፡ ያወር
ዳል ።
16 እነርሱ ፡ (ከመቃብር) ፡ በሚወ
ጡበት ፡ ቀን ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ከነሱ
ምንም ፡ ነገር ፡ አይደበቅም ፤
ንግሥናው ፡ ዛሬ ፡ ለማን ፡ ነው ?
(ይባላል ፤) ለአሸናፊው ፡ ለአ
ንዱ ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ (ይባ
ላል) ።
17 ዛሬ ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ በሠራችው ፡
ሥራ ፡ ትመነዳለች ፤ ዛሬ ፡ በደል ፡
የለም ፤ አላህ ፡ በእርግጥ ፡ ምር
መራው ፡ ፈጣን ፡ ነው ፡ (ይባ
ላል) ።
18 ቅርቢቱንም ፡ (የትንሣኤን) ፡ ቀን
ልቦች ፡ ጭንቀትን ፡ ይተመሉ ፡
ኾነው ፡ ላንቃዎች ፡ ዘንድ ፡ የሚ
ደርሱበትን ፡ ጊዜ ፡ አስጠንቅቃ
ቸው ፤ ለበዳዮች ፡ ምንም ፡ ወዳ
ጅና ፡ ተሰሚ ፡ አማላጅ ፡ የላቸ
ውም ።
19 (አላህ) ፡ የዓይኖችን ፡ ክዳት ፡
ልቦችም ፡ የሚደብቁትን ፡ ሁሉ ፡
ያውቃል ።



20 አላህም ፡ በውነት ፡ ይፈርዳል ፤
እነዚያም ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ የሚግ
ገዟቸው ፡ በምንም ፡ አይፈር
ዱም ፤ አላህ ፡ እርሱ ፡ ሰሚው ፡
ተመልካቹ ፡ ነው ።
21 የነዚያን ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡ የነበ
ሩትን ፡ ሕዝቦች ፡ ፍጻሜ ፡ እን
ዴት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ይመለከቱ ፡
ዘንድ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አይኼ
ዱምን ? በኀይልና ፡ በምድር ፡
ላይ ፡ በተውዋቸው ፡ ምልክቶች ፤
ከነሱ ፡ ይበልጥ ፡ የበረቱ ፡ ነበሩ ፤
አላህም ፡ በኀጢአቶቻቸው ፡ ያዛ
ቸው ፤ ለነሱም ፡ ከአላህ ፡ (ቅጣት)
ምንም ፡ ጠባቂ ፡ አልነበራቸ
ውም ።
22 ይህ ፡ (መያዝ) ፡ እነሱ ፡ መልክ
ተኞቻቸው ፡ በታምራቶች ፡ ይመ
ጡባቸው ፡ ስለ ፡ ነበሩና ፡ ስለ ፡
ካዱ ፡ ነው ፤ አላህም ፡ ያዛቸው ፤
እርሱ ፡ ኀያል ፡ ቅጣተ ፡ ብርቱ ፡
ነውና ።
23 ሙሳንም ፡ በታምራቶቻችንና ፡
በግልጽ ፡ ማስረጃ ፡ በእርግጥ ፡
ላክነው ።
24 ወደ ፡ ፈርዖንና ፡ ወደ ፡ ሃማን ፤
ወደ ፡ ቃሩንም ፡ (ላክነው) ፤ ድግ
ምተኛ ፡ ውሸታም ፡ ነው ፡ አሉም ።
25 ከኛ ፡ ዘንድ ፡ እውነትን ፡ ይዞ ፡
በመጣላቸውም ፡ ጊዜ ፡-የነዚያን ፡
ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያመኑትን ፡ ሰዎች ፡
ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ግደሉ ፤ ሴቶቻ
ቸውንም ፡ አስቀሩ ፡ አሉ ፤ የከሓ
ዲዎችም ፡ ተንኮል ፡ በጥፋት ፡ ው
ስጥ ፡ እንጅ ፡ አይደለም ።
26 ፈርዖንም ፡— ተዉኝ ፤ ሙሳን ፡
ልግደል ፤ ጌታውንም ፡ ይጥራ ፤
ያድነው ፡ እንደኾነ) ፤ እኔ ፡ ሃይ
ማኖታችሁን ፡ ሊለውጥ ፤ ወይም ፡
በምድር ፡ ውስጥ ፡ ጥፋትን ፡ ሊያስ
ራጭ ፡ እፈራለሁና ፡ አለ ።
27 ሙሳም ፡ እኔ ፡ በምርመራው ፡
ቀን ፡ ከማያምን ፡ ትዕቢተኛ ፡
ሁሉ ፡ በጌታየና ፡ በጌታችሁ ፡
ተጠበቅሁ ፡ አለ ።
28 ከፈርዖንም ፡ ቤተሰቦች ፡ አንድ ፡
እምነቱን ፡ የሚደብቅ ፡ ምእምን ፡
ሰው ፡ አለ ፡—ሰውየውን ፡ ከጌ
ታችሁ ፡ በታምራቶች ፡ በእር
ግጥ ፡ የመጣላችሁ ፡ ሲኾን ፡
ጌታዬ ፡ አላህ ፡ ነው ፡ ስለሚል ፡
ትገድላላችሁን ? ውሸታምም ፡
ቢኾን ፡ ውሸቱ ፡ በርሱው ፡ ላይ ፡
ነው ፤ እውነተኛ ፡ ቢኾን ፡ ግን ፡
የዚያ ፡ የሚያስፈራራችሁ ፡ ከፊሉ
ያገኛችኋል ፤ አላህ ፡ ያንን ፡ እርሱ
ድንበር ፡ አላፊ ፡ ውሸታም ፡ የኾ
ነውን ፡ አይመራምና ።
29 ወገኖቼ ፡ ሆይ ! በምድር ፡ ላይ ፡
አሸናፊዎች ፡ ስትኾኑ ፡ ዛሬ ፡
መንግሥቱ ፡ የናንተ ፡ ነው ፤
ታዲያ ፡ ከአላህ ፡ ቅጣት ፡ ቢመ
ጣብን ፡ የሚያድነን ፡ ማን ፡ ነው?
(አለ) ። ፈርዖን ፡ የማየውን ፡ ነገር
እንጅ ፤ አላመለክታችሁም ፤ ቅኑ
ንም ፡ መንገድ ፡ እንጅ ፡ አልመ
ራችሁም ፡ አላቸው ።
30 ያም ፡ ያመነው ፡ ሰው ፡ አለ ፡—
እኔ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ የአሕዛቦ
ቹን ፡ ቀን ፡ ብጤ ፡ እፈራላችኋ
ለሁ ።
31 የኑሕን ፡ ሕዝቦች ፡ የዓድንና ፡
የሠሙድንም ፡ የነዚያንም ፡ ከኋ
ላቸው ፡ የነበሩትን ፡ ልማድ ፡
ብጤ ፡ (እፈራላችኋለሁ) ፤ አላ
ህም ፡ ለባሮቹ ፡ መበደልን ፡ የሚ
ሻ ፡ አይደለም ።

32 ወገኖቼ ፡ ሆይ ! እኔ ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ የመጠራሪያን ፡ ቀን ፡ (1)
እፈራለሁ ።

33 ወደኋላ ፡ ዞራችሁ ፡ በምትሸሹበት ፡
ቀን ፤ ለናንተ ፡ ከአላህ ፡ (ቅጣት) ፡
ምንም ፡ ጠባቂ ፡ የላችሁም ፤ አላህ
ም ፡ የሚያጠመው ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡
ምንም ፡ አቅኚ ፡ የለውም ።

34 ዩሱፍም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ግልጽ ፡
ማስረጃዎችን ፡ በእርግጥ ፡ አመ
ጣላችሁ ፤ ከዚያም ፡ እርሱ ፡
ካመጣላችሁ ፡ ነገር ፡ ከመጠራ
ጠር ፡ አልተወገዳችሁም ፤ በጠ
ፋም ፡ ጊዜ ፡ አላህ ፡ ከርሱ ፡
ኋላ ፡ መልክተኛን ፡ በጭራሽ ፡
አይልክም ፡ አላችሁ ፤ አላህ ፡
እንደዚሁ ፡ ድንበር ፡ አላፊ ፡
ተጠራጣሪ ፡ የኾነን ፡ ሰው ፡
ያሳስታል ።

35 እነዚያ ፤ የመጣላቸው ፡ አስረጅ ፡
ሳይኖር ፡ በአላህ ፡ ታምራቶች ፡
የሚከራከሩ ፡ (ክርክራቸው) ፡
አላህ ፡ ዘንድና ፡ እነዚያም ፡ አመ
ኑት ፡ ዘንድ ፡ መጠላቱ ፡ በጣም ፡
ተለቀ ፤ እንደዚሁ ፡ አላህ ፡ በኩሩ ፡
ጨካኝ ፡ (ሰው) ፡ ልብ ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ያትማል ።

36 ፈርዖንም ፡ አለ ፡— ሃማን ፡ ሆይ !
መንገዶችን ፡ እደርስ ፡ ዘንድ ፡
ረገርም ፡ ሕንጻን ፡ ለኔ ፡ ካብልኝ ።

37 የሰማያትን ፡ መንገዶች ፡ (እደ
ርስ ፡ ዘንድ) ፤ ወደ ፡ ሙሳም ፡
አምላክ ፡ እመለከት ፡ ዘንድ ፡
እኔም ፡ ውሸታም ፡ ነው ፡ ብዬ ፡
በእርግጥ ፡ እጠረጥረዋለሁ ፡ (አለ) ፤
እንደዚሁም ፡ ለፈርዖን ፡ መጥፎ ፡
ሥራው ፡ ተሸለመለት ፤ ከቅን ፡
መንገድም ፡ ታገደ ፤ የፈርዖንም ፡
ተንኮል ፡ በከሳራ ፡ ውስጥ ፡
እንጅ ፡ አይደለም ።

38 ያም ፡ ያመነው ፡ አለ ፡— ወገ
ኖቼ ፡ ሆይ ! ተከተሉኝ ፤ ቀጥታ
ውን ፡ መንገድ ፡ እመራችኋለ
ሁና ።

39 ወገኖቼ ፡ ሆይ ! ይህቺ ፡ ቅርቢቱ ፡
ሕይወት ፡ (ጥቂት) ፡ መጣቀሚያ ፡
ብቻ ፡ ናት ፤ መጨረሻይቱም ፡
ዓለም ፡ እርሷ ፡ መርጊያ ፡ አገር ፡
ናት ።

40 መጥፎን ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ብጤ
ዋን ፡ እንጅ ፡ አይመነዳም ፤
እርሱ ፡ ምእምን ፡ ኾኖ ፡ ከወ
ንድ ፡ ወይም ፡ ከሴት ፡ በጎን ፡
የሠራም ፡ ሰው ፡ እነዚያ ፡ ገነትን ፡
ይገባሉ ፤ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ቁ
ጥጥር ፡ ይመገባሉ ።

41 ወገኖቼም ፡ ሆይ ! ወደ ፡ መዳን ፡
የምጠራችሁ ፡ ስኾን ፡ ወደ ፡ እሳ
ትም ፡ የምትጠሩኝ ፡ ስትኾኑ ፡
ለኔ ፡ ምን ፡ አለኝ ! (1)

42 በአላህ ፡ ልክድና ፡ በርሱም ፡
ለኔ ፡ ዕውቀት ፡ የሌለኝን ፡ ነገር ፡
በርሱ ፡ እንዳጋራ ፡ ትጠሩኛላ
ችሁ ፤ እኔም ፡ ወደ ፡ አሸናፊው ፡
መሓሪው ፡ (አላህ) ፡ እጠራች
ችኋለሁ ።

43 በእርግጥ ፡ ወደርሱ ፡ የምትጠ
ሩብኝ ፡ (ጣዖት) ፡ ለርሱ ፡ በቅር
ቢቱም ፡ ኾነ ፡ በመጨረሻይቱ ፡
ዓለም ፡ (ተሰሚ) ፡ ጥሪ ፡ የለውም ፤
መመለሻችንም ፡ በእርግጥ ፡ ወደ ፡
አላህ ፡ ነው ፤ ወሰን ፡ አላፊዎ
ቹም ፡ እነሱ ፡ የእሳት ፡ ጓዶች ፡
ናቸው ።

44 ወደ ፡ ፊትም ፡ ለናንተ ፡ የምላ
ችሁን ፡ ምክር ፡ (ቅጣትን ፡ በም
ታዩ ፡ ጊዜ) ፡ ታስታውሳላችሁ ፤
ነገሬንም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡
አስጠጋለሁ ፤ አላህ ፡ ባሮቹን ፡
ተመልካች ፡ ነውና ።

45 ከመከሩዋቸውም፡ መጥፎዎች፡
አላህ፡ ጠበቀው፤ በፈርዖን፡ ቤተ
ሰቦችም ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ቅጣት ፡
ሰፈረባቸው ።

46 እሳት ፡ በጧትና ፡ በማታ ፡ በርሷ ፡
ላይ ፡ ይቀርባሉ ፤ ሰዓቲቱም ፡
በምትኾንበት ፡ ቀን ፡ የፈርዖንን ፡
ቤተሰቦች ፡ ብርቱን ፡ ቅጣት ፡
(ገሀነምን) ፡ አግቡዋቸው ፡ (ይባ
ላል) ።

47 በእሳትም ፡ ውስጥ ፡ የሚከራከ
ሩበትን ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፡
ደካማዎቹም ፡ ለነዚያ ፡ ለኮሩት ፡
እኛ ፡ ለናንተ ፡ ተከታዮች ፡ ነበር
ንና ፡ እናንተ ፡ (አሁን) ፡ ከእ
ሳት ፡ ከፊሉን ፡ ከኛ ፡ ላይ ፡ ገፍ
ታሪዎች ፡ ናችሁን ? ይላሉ ።

48 እነዚያም ፡ የኮሩት ፡ እኛ ፡ ሁላ
ችንም ፡ በውስጧ ፡ ነን ፤ አላህ ፡
በባሮቹ ፡ መካከል ፡ በእርግጥ ፡
ፈረደ ፡ ይላሉ ።

49 እነዚያም ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡
ያሉት ፡ ለገሀነም ፡ ዘበኞች ፡ ጌታ
ችሁን ፡ ለምኑልን ፤ ከኛ ፡ ላይ ፡
ከቅጣቱ ፡ አንድን ፡ ቀን ፡ ያቃል
ልን ፤ ይላሉ ።

50 (ዘበኞቹም) ፡ መልክተኞቻችሁ ፡
በታምራቶች ፡ ይመጡላችሁ ፡
አልነበሩምን ? ይላሉ ፤ (ከሓዲዎ
ቹም) ፡ እንዴታ ፡ መጥተውናል ፡
እንጅ ፤ (ግን ፡ አስተባበልናቸው) ፡
ይላሉ ፤ እንግዲያውስ ፡ ጸልዩ ፡
የከሓዲዎችም ፡ ጸሎት ፡ በከንቱ ፡
እንጅ ፡ አይደለም ፡ ይሏቸዋል ።

51 እኛ ፡ መልክተኞቻችንን ፡ እነዚ
ያንም ፡ ያመኑትን ፡ በቅርቢቱ ፡
ሕይወት ፡ ምስክሮችም ፡ በሚ
ቆሙበት ፡ ቀን ፡ በእርግጥ ፡ እን
ረዳለን ።

52 በደለኞችን ፡ ምክንያታቸው ፡
በማይጠቅማቸው ፡ ቀን ፡ (እንረ
ዳለን) ፤ ለነርሱም ፡ ርግማን ፡
አላቸው ፤ ለነርሱም ፡ መጥፎ ፡
አገር ፡ አላቸው ።

53 ሙሳንም ፡ መምሪያን ፡ በእርግጥ ፡
ሰጠነው ፤ የእስራኤልንም ፡ ል
ጆች ፡ መጽሐፉን ፡ አወረስና
ቸው ።

54 ለባለ ፡ አእምሮዎች ፡ መሪና ፡
ገሣጭ ፡ ሲኾን ።

55 (ሙሐመድ ፡ ሆይ !) ታገስም ፤
የአላህ ፡ ተስፋ ፡ እውነት ፡ ነውና ፤
ለስሕተትህም ፡ ምሕረትን ፡ ለ
ምን ፤ ከቀትር ፡ በኋላም ፡ በማ
ለዳም ፡ ጌታህን ፡ ከማመስገን ፡
ጋር ፡ አጥራው ።

56 እነዚያ ፡ የመጣላቸው ፡ አስረጅ ፡
ሳይኖር ፡ በአላህ ፡ አንቀጾች ፡
የሚከራከሩ ፡ በልቦቻቸው ፡ ው
ስጥ ፡ እነርሱ ፡ ደራሾቹ ፡ ያልኾ
ኑት ፡ ኩራት ፡ ብቻ ፡ እንጅ ፡
ምንም ፡ የለም ፤ በአላህም ፡ ተጠ
በቅ ፤ እነሆ ፡ እርሱ ፡ ሰሚው ፡ ተ
መልካቹ ፡ ነውና ።

57 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ መፍ
ጠር ፡ ሰዎችን ፡ ከመፍጠር ፡
ይልቅ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤ ግን ፡
አብዛኞዎቹ ፡ ሰዎች ፡ አያውቁም ።

---

1 የእሳትና ፡ የገነት ፡ ሰዎች ፡ የሚጠራሩበ
ትን ፡ የትንሣኤን ፡ ቀን ።

1 ወደ ፡ መዳን ፡ ስጠራችሁ ፡ ወደ ፡ እሳት ፡
መጥራችሁ ፡ ይገርማል ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

58 ዕውርና ፡ የሚያይ ፡ እነዚያም ፡
አምነው ፡ መልካሞችን ፡ የሠ
ሩና ፡ መጥፎ ፡ ሠሪው ፡ አይተካ
ከሉም ፤ በጣም ፡ ጥቂትን ፡ ብቻ ፡
ትገሠጻላችሁ ።

59 ሰዓቲቱ ፡ በእርግጥ ፡ መጪ ፡ ናት፤
በርሷ ፡ ጥርጥር ፡ የለም ፤ ግን ፡
አብዛኞቹ ፡ ሰዎች ፡ አያምኑም ።

60 ጌታችሁም ፡ አለ ፡— ለምኑኝ ፤
እቀበላችኋለሁና ፤ እነዚያ ፡ እኔን፡
ከመገዛት ፡ የሚኮሩት ፡ ተዋራ
ጆች ፡ ኾነው ፡ ገሀነምን ፡ በእር
ግጥ ፡ ይገባሉ ።

61 አላህ ፡ ያ ፡ ለናንተ ፡ ሌሊትን ፡
በውስጡ ፡ ልታርፉበት ፡ (ጨ
ለማ) ፡ ቀንንም ፡ (ልትሠሩበት) ፡
የሚያሳይ ፡ ያደረገላችሁ ፡ ነው ።
አላህ ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡
የችሮታ ፡ ባለቤት ፡ ነውና ። ግን ፡
አብዛኞዎቹ ፡ ሰዎች ፡ አያመሰ
ግኑም ።

62 ይሃችሁ ፡ ጌታችሁ ፡ አላህ ፡ ነው ፤
የነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡ ነው ፤
ከርሱ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፤
ታዲያ ፡ (ከእምነት) ፡ ወዴት ፡
ትመለሳላችሁ ።

63 እንደዚሁ ፡ እነዚያ ፡ በአላህ ፡
አንቀጾች ፡ ይክዱ ፡ የነበሩት ፡
(ከእምነት) ፡ ይመለሳሉ ።

64 አላህ ፡ ያ ፡ ምድርን ፡ መርጊያ ፡
ሰማይንም ፡ ጣሪያ ፡ ያደረገላችሁ፡
ነው ፤ የቀረጻችሁም ፡ ቅርጻችሁ
ንም ፡ ያሳመረ ፡ ከጣፋጮችም ፡
ሲሳዮች ፡ የሰጣችሁ ፡ ነው ፤
ይሃችሁ ፡ ጌታችሁ ፡ አላህ ፡ ነው ፤
የዓለማትም ፡ ጌታ ፡ አላህ ፡ ላቀ ።

65 እርሱ ፡ ብቻ ፡ (ሁል ፡ ጊዜ) ፡
ሕያው ፡ ነው ፤ ከርሱ ፡ ሌላ ፡
አምላክ ፡ የለም ፤ ሃይማኖትንም ፡
ለርሱ ፡ ያጠራችሁ ፡ ስትኾኑ ፡
ምስጋና ፡ ለዓለማት ፡ ጌታ ፡ ለአ
ላህ ፡ ይኹን ፡ የምትሉ ፡ ኾና
ችሁ ፡ ተገዙት ።

66 እኔ ፡ ከጌታዬ ፡ አስረጃዎች ፡
በመጡልኝ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያን ፡
ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የምትገዙዋቸ
ውን ፡ እንዳልገዛ ፡ ተከልክያ
ለሁ ፤ ለዓለማት ፡ ጌታም ፡ እን
ድገዛ ፡ ታዝዣለሁ ፡ በላቸው ።

67 እርሱ ፡ ያ ፡ ከዐፈር ፡ ከዚያም ፡
ከፍትወት ፡ ጠብታ ፡ ከዚያም ፡
ከረጋ ፡ ደም ፡ የፈጠራችሁ ፡ ነው።
ከዚያም ፡ ሕጻናት ፡ አድርጎ ፡
ያወጣችኋል ፤ ከዚያም ፡ ጥንካ
ሬያችሁን ፡ ትደርሱ ፡ ዘንድ ፤
ከዚያም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ትኾኑ፡
ዘንድ ፡ (ያቆያችኋል) ፤ ከናንተም፡
ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የሚ
ሞት ፡ አለ ፤ (ይህንንም ፡ ያደረ
ገው ፡ ልትኖሩና) ፡ የተወሰነ ፡
ጊዜንም ፡ ልትደርሱ ፡ ታው
ቁም ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

68 እርሱ ፡ ያ ፡ ሕያው ፡ የሚያደርግ ፡
የሚያሞትም ፡ ነው ፤ አንዳችን ፡
ነገር ፡ በሻም ፡ ጊዜ ፡ ለርሱ ፡
የሚለው ፡ ኹን ፡ ነው ፤ ወዲያው
ም ፡ ይኾናል ።

69 ወደነዚያ ፡ በአላህ ፡ አንቀጾች ፡
ወደሚከራከሩት ፡ (ከእምነት) ፡
እንዴት ፡ እንደሚመለሱ ፡ አታ
ይምን ?

70 ወደነዚያ ፡ በመጽሐፉ ፡ በዚ
ያም ፡ መልክተኞቻችንን ፡ በርሱ፡
በላክንበት ፡ ወዳስተባበሉት ፡
(አታይምን?) ወደፊትም ፡ ያው
ቃሉ ።



71 እንዛዝላዎቹና ፡ ሰንሰለቶቹ ፡ በአ
ንገቶቻቸው ፡ ላይ ፡ በተደረጉ ፡
ጊዜ ፡ (በርሷ) ፡ ይጐተታሉ ።

72 በገሀነም ፡ ውስጥ ፡ (ይጐተታሉ)፤
ከዚያም ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ይማ
ገዳሉ ።

73 ከዚያም ፡ ለነርሱ ፡ ይባላሉ ፡—
(በአላህ) ፡ ታጋሩዋቸው ፡ የነበ
ራችሁት ፡ የታሉ ?

74 ከአላህ ፡ ሌላ ፡ (የምታጋሩዋ
ዋቸው) ፤ ከኛ ፡ ተሰወሩን ፤ ከቶ ፡
ከዚህ ፡ በፊት ፡ ምንንም ፡ የምን
ግዛ ፡ አልነበርንም፡ ይላሉ ፤
እንደዚሁ ፡ አላህ ፡ ከሓዲዎችን ፡
ያሳስታል ።

75 ይሃችሁ ፡ (ቅጣት) ፡ ያለ ፡ አግ
ባብ ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ትደ
ሰቱ ፡ በነበራችሁትና ፡ ትንበጣ
ረሩ ፡ በነበራችሁት ፡ ነው ፡ (ይባ
ላሉ) ።

76 የገሀነምን ፡ በሮች ፡ በውስጧ ፡
ዘውታሪዎች ፡ ስትኾኑ ፡ ግቡ ፡
(ይባላሉ) ፤ የትዕቢተኞችም ፡ መ
ኖሪያ ፡ (ገሀነም) ፡ ምን ፡ ትከፋ !

77 ታገሥም ፡ የአላህ ፡ ቀጠሮ ፡ እው
ነት ፡ ነውና ፤ የዚያንም ፡ የምናስ
ፈራራቸውን ፡ ከፊሉን ፡ (በሕ
ይወትህ) ፡ ብናሳይህ ፡ (መልካም ፡
ነው) ፤ ወይም ፡ ብንገድልህ ፡
ወደኛ ፡ ይመለሳሉ ።

78 ካንተ ፡ በፊትም ፡ መልክተኞችን፡
በእርግጥ ፡ ልከናል ፤ ከነሱ ፡ ባ
ንተ ፡ ላይ ፡ የተረክንልህ ፡ አልለ ፤
ከነሱም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ያልተረ
ክነው ፡ አልለ ። ለማንኛውም ፡
መልክተኛ ፡ በአላህ ፡ ፈቃድ ፡
ካልኾነ ፡ ታምርን ፡ ሊያመጣ ፡
አይገባውም ። የአላህም ፡ ትእ
ዛዝ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በውነት ፡
ይፈረዳል ፤ እዚያ ፡ ዘንድም ፡
አጥፊዎቹ ፡ ይከስራሉ ።

79 አላህ ፡ ያ ፡ ለናንተ ፡ ግመልን ፡
ከብትንና ፡ ፍየልን ፡ ከርሷ ፡
(ከፊሏን) ፡ ልትጋልቡ ፡ የፈጠረ
ላችሁ ፡ ነው ፤ ከርሷም ፡ ትበላላ
ችሁ ።

80 ለናንተም ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ጥቅ
ሞች ፡ አሏችሁ ፤ በርሷም ፡ ላይ ፡
(ዕቃን ፡ በመጫን) ፡ በልቦቻችሁ፡
ያሰባችሁትን ፡ ጉዳይ ፡ ትደርሱ ፡
ዘንድ ፡ (ፈጠረላችሁ) ፤ በርሷም ፡
ላይ ፡ በመርከቦችም ፡ ላይ ፡ ትሳ
ፈራላችሁ ።

81 ታምራቱንም ፡ ያሳያችኋል ፤ ታ
ዲያ ፡ ከአላህ ፡ ታምራት ፡ የትኛ
ውን ፡ ትክዳላችሁ ?

82 የነዚያን ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡ የነበ
ሩትን ፡ ሕዝቦች ፡ ፍጻሜ ፡ እን
ዴት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ይመለከቱ ፡
ዘንድ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አይኼዱ
ምን ? ከነሱ ፡ ይበልጥ ፡ ብዙዎች፡
በኀይልና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በተ
ውዋቸው ፡ ምልክቶችም ፡ በጣም
ብርቱዎች ፡ ነበሩ ። ያም ፡ ይሠ
ሩት ፡ የነበሩት ፡ ከነሱ ፡ ምንም ፡
አልጠቀማቸውም ።

83 መልክተኞቻቸውም ፡ ታምራቶ
ችን ፡ ባመጡላቸው ፡ ጊዜ ፡ እነ
ርሱ ፡ ዘንድ ፡ ባለው ፡ ዕውቀት ፡
ተደሰቱ ፤ በርሱ ፡ ይሳለቁበት ፡
የነበሩት ፡ ቅጣትም ፡ በነርሱ ፡
ላይ ፡ ሰፈረባቸው ።

84 ብርቱ ፡ ቅጣታችንንም ፡ ባዩ ፡
ጊዜ ፡ በአላህ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡
አምነናል ፤ በርሱም ፡ እናጋራ ፡
በነበርነው ፡ (ጣዖታት) ፡ ከደናል ፡
አሉ ።

85 ብርቱ ፡ ቅጣታችንን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡
ማመናቸውም ፡ የሚጠቅማቸው ፡
አልነበረም ፤ የአላህን ፡ ደንብ ፡
ያችን ፡ በባሮቹ ፡ ውስጥ ፡ ያለፈች
ውን ፡ (ተጠንቀቁ) ፡ በዚያ ፡
ጊዜም ፡ ከሓዲዎች ፡ ከሰሩ ።

## ምዕራፍ ፡ 41 ፡ ሐ ፡ ሚም ፡ አል-ሰጅዳህ ። ክፍል ፡ 24 ።

41ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ሐ ፡ ሚም ፡ አል-ሰጅዳህ ፤ (የሐ ፡ ሚም ፡ ስግደት ፡ ምዕራፍ) ፤ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 54 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 ሐ. መ. (ሐ ፡ ሚም) ፤
2 (ይህ ፡ ቁርአን) ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ ከሆ
ነው ፡ (አላህ) ፡ የተወረደ ፡ ነው ።
3 አንቀጾቹ ፡ የተብራሩ ፡ የኾነ ፡
መጽሐፍ ፡ ነው ፤ ዐረብኛ ፡ ቁር
አን ፡ ሲኾን ፡ ለሚያውቁ ፡ ሕዝ
ቦች ፡ (የተብራራ) ፡ ነው ።
4 አብሳሪና ፡ አስፈራሪ ፡ ሲኾን ፡
(ተወረደ) ፤ አብዛኛዎቻቸውም ፡
ተዉት ፤ እነሱም ፡ አይሰሙም ።
5 አሉም ፡— ልቦቻችን ፡ ከዚያ ፡
ወደርሱ ፡ ከምትጠራን ፡ እም
ነት ፡ በመሸፈኛዎች ፡ ውስጥ ፡
ናቸው፤ በጆሮዎቻችንም፡ ላይ ፡
ድንቁርና ፡ አለለ ፤ በኛና ፡ ባን
ተም ፡ መካከል ፡ ግርዶሽ ፡ አለለ ፤
(በሃይማኖትህ) ፡ ሥራም ፤ እኛ ፡
ሠሪዎች ፡ ነንና ።
6 (እንዲህ) ፡ በላቸው ፡— እኔ ፡
መሰላችሁ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነኝ ፤
አምላካችሁ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ ወደርሱም ፡ ቀጥ ፡
በሉ ፤ ምሕረትንም ፡ለምኑት ፡
ማለት ፡ ወደኔ ፡ ይወረድልኛል ።
ለአጋሪዎቹም ፡ ወዮላቸው ።
7 ለነዚያ ፡ ዘካን ፡ ለማይሰጡት ፡
እነሱም ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ዓለም፤
እነሱ ፡ ከሓዲዎች ፡ ለኾኑት ፡
(ወዮላቸው) ።
8 እነዚያ ፡ ያመኑትና ፡ በጎ ፡ ሥራ
ዎችን ፡ የሠሩት ፡ ለነርሱ ፡ የማይ
ቆረጥ ፡ ምንዳ ፡ አላቸው ።
9 በላቸው ፡— እናንተ ፡ በዚያ ፡
ምድርን ፡ በሁለት ፡ ቀኖች ፡
ውስጥ ፡ በፈጠረው ፡ አምላክ ፡
በእርግጥ ፡ ትክዳላችሁን ? ለር
ሱም ፡ ባላንጣዎችን ፡ ታደርጋላ
ችሁን ? ያ ፡ (ይህንን ፡ የሠራው) ፡
የዓለማት ፡ ጌታ ፡ ነው ።
10 በርሷም ፡ ከበላይዋ ፡ የረጉ ፡ ጋራ
ዎችን ፡ አደረገ ፤ በርሷም ፡ በረከ
ትን ፡ አደረገ ፤ በውስጧም ፡ ምግ
ቦችዋን ፡ (ካለፉት ፡ ሁለት ፡
ቀኖች ፡ ጋር) ፡ በአራት ፡ ቀናት ፡
ውስጥ ፡ ለጠያቂዎች ፡ ትክክል ፡
ሲኾኑ ፡ ወሰነ ።
11 ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እርሷ ፡
ጭስ ፡ ኾና ፡ ሳለች ፡ አሰበ ፤ ለር



ሷም ፡ ለምድርም ፡ ወዳችሁም ፡
ኹነ ፡ ወይም ፡ ጠልታችሁ ፡ ኑ ፤
አላቸው ። ታዛዦች ፡ ኾነን ፡
መጣን ፡ አሉ ።
12 በሁለት ፡ ቀኖችም ፡ ውስጥ ፡
ሰባት ፡ ሰማያት ፡ አደረጋቸው ፤
በሰማይቱም ፡ ሁሉ ፡ ነገሯን ፡
አዘጋጀ ፤ ቅርቢቱንም ፡ ሰማይ ፡
በመብራቶች ፡ አጌጥን ፤ (ከሰይ
ጣናት) ፡ መጠበቅንም ፡ ጠበቅ
ናት ፤ ይህ ፡ የአሸናፊው ፡ የዐዋ
ቂው ፡ (ጌታ) ፡ ውሳኔ ፡ ነው ።
13 (ከእምነት) ፡ እንቢ ፡ ቢሉም ፡
እንደ ፡ ዓድና ፡ ሠሙድ ፡ መቅሠ
ፍት ፡ ብጤ ፡ የኾነን ፡ መቅሠፍት፡
አስጠነቅቃችኋለሁ ፡ በላቸው ።
14 መልክተኞቹ ፡ አላህን ፡ እንጂ ፡
ሌላን ፡ አትግዙ ፡ በማለት ፡ ከስተ
ፊታቸውም ፡ ከስተኋላቸውም ፡
በመጡባቸው ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡
በሻ ፡ ኖሮ ፡ መላእክትን ፡ ባወ
ረደ ፡ ነበር ፤ ስለዚህ ፡ እኛ ፡ በዚያ፡
በርሱ ፡ በተላካችሁበት ፡ ከሓዲ
ዎች ፡ ነን ፡ አሉ ።
15 ዓድም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያለ ፡
አግባብ ፡ ኮሩ ፤ ከኛ ፡ ይበልጥ ፡
በኀይል ፡ ብርቱ ፡ ማን ፡ ነው ?
አሉም ፤ ያ ፡ የፈጠራቸው ፡ አላህ ፡
እርሱ ፡ በኀይል ፡ ከነርሱ ፡ ይበ
ልጥ ፡ የበረታ ፡ መኾኑን ፡ አያዩ
ምን ? በታምራታችንም ፡ ይክዱ ፡
ነበሩ ።
16 በቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡ የውርደ
ትን ፡ ቅጣት ፡ ልናቀምሳቸውም ፡
በነሱ ፡ ላይ ፡ የሚንሻሻን ፡ ብርቱ ፡
ነፋስ ፡ መናጢዎች ፡ በኾኑ ፡
ቀናት ፡ ውስጥ ፡ ላክንባቸው ፤
የመጨረሻይቱም ፡ (ዓለም) ፡
ስቃይ ፡ በጣም ፡ አዋራጅ ፡ ነው ፤
እነርሱም ፡ አይረዱም ።
17 ሠሙዶችማ ፡ መራናቸው ፡ ዕውርነ
ትንም ፡ በቅንነት ፡ ላይ ፡ መረጡ ፤
ይሠሩትም ፡ በነበሩት ፡ ኃጢአት ፡
አሳናሽ ፡ የኾነችው ፡ የመብረቅ ፡
ቅጣት ፡ ያዘቻቸው ።
18 እነዚያንም ፡ ያመኑትንና ፡ ይጠነ
ቀቁ ፡ የነበሩትን ፡ አዳንናቸው ።
19 የአላህም ፡ ጠላቶች ፡ ወደ ፡ እሳት ፡
የሚሰበሰቡበትን ፡ ቀን ፡ (አስታ
ውስ) ፤ እነሱም ፡ የሚከመከሙ ፡
ኾነው ፡ ይነዳሉ ።
20 በመጧትም፡ ጊዜ፥ ጆሮዎቻቸው፥
ዓይኖቻቸውና ፡ ቆዳዎቻቸውም ፡
ይሠሩት ፡ በነበሩት ፡ ነገር ፡ በነ
ርሱ ፡ ላይ ፡ ይመሰክሩባቸዋል ።
21 ለቆዳዎቻቸውም ፡ በኛ ፡ ላይ ፡
ለምን ፡ መሰከራችሁብን ፡ ይላሉ ፤
ያ ፡ አንዳቹን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያና
ገረው ፡ አላህ ፡ አናገረን ፤ እር
ሱም ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ፈጠ
ራችሁ ፤ ወደርሱም ፡ ትመለሳላ
ችሁ ፤ ይሏቸዋል ።
22 ጆሮዎቻችሁ፥ዓይኖቻችሁና፡ቆዳዎ
ቻችሁም ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ከመ
መስከራቸው ፡ የምትደበቁ ፡ አልነ
በራችሁም ፤ ግን ፡ አላህ ፡ ከምት
ሠሩት ፡ ብዙውን ፡ አያውቅም ፡
ብላችሁ ፡ ጠረጠራችሁ ።
23 ይሃችሁም ፡ ያ ፡ በጌታችሁ ፡ የጠ
ረጠራችሁት ፡ ጥርጣሪያችሁ ፡
አጠፋችሁ ፡ ከከሳሪዎቹም ፡ ኾና
ችሁ ፡ (ይባላሉ) ።
24 ቢታገሡም ፡ እሳት ፡ ለነርሱ ፡
መኖሪያቸው ፡ ናት ፤ ወደሚወ
ዱት ፡ መመለስንም ፡ ቢጠይቁ ፡

እነሱ ፡ ተቀባይ ፡ የሚያገኙ ፡ አይ
ደሉም ።
25 ለነርሱም ፡ ቁራኛዎችን ፡ አዘጋ
ጀንላቸው ፤ በፊታቸው ፡ ያለው
ንና ፡ በኋላቸው ፡ ያለውንም ፡
ሁሉ ፡ ለነርሱ ፡ ሸለሙላቸው ፤
ከጋኔንና ፡ ከሰውም ፡ ከነሱ ፡
በፊት ፡ በእርግጥ ፡ ካለፉት ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ጋር ፡ ኾነው ፡ ቃሉ ፡ በነ
ርሱ ፡ ላይ ፡ ተረጋገጠባቸው ፤
እነርሱ ፡ በእርግጥ ፡ ከሳሪዎች ፡
ነበሩና ።
26 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ይህንን ፡
ቁርአን ፡ አታዳምጡ ፤ ታሸን
ፉም ፡ ዘንድ ፡ (ሲነበብ) ፡ በርሱ ፡
ውስጥ ፡ ተንጫጩ ፡ አሉ ።
27 እነዚያንም ፡ የካዱትን ፡ ብርቱን ፡
ቅጣት ፡ እናቀምሳቸዋለን ፤ የዚ
ያንም ፡ ይሠሩት ፡ የነበሩትን ፡
መጥፎውን ፡ (ፍዳ) ፡ በእርግጥ ፡
እንመነዳቸዋለን ።
28 ይህ ፡ የአላህ ፡ ጠላቶች ፡ ፍዳ ፡
ነው ፤ እሳት ፡ በውስጧ ፡ ለነርሱ ፡
የዘላለም ፡ መኖሪያ ፡ አገር ፡ አላ
ቸው ፤ በአንቀጾቻችን ፡ ይክዱ ፡
በነበሩት ፡ ምንዳን ፡ (ይመነዳሉ) ።
29 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ (በእሳት ፡
ውስጥ ፡ ኾነው) ፡ ጌታችን ፡ ሆይ !
እነዚያን ፡ ከጋኔንና ፡ ከሰው ፡ ያሳ
ሳቱንን ፡ አሳየን ፤ ከታችኞቹ ፡
ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ከጫማዎቻችን ፡
ሥር ፡ እናደርጋቸዋለንና ፡ ይላሉ ።
30 እነዚያ ፡ ጌታችን ፡ አላህ ፡ ነው ፡
ያሉ ፡ ከዚያም ፡ ቀጥ ፡ ያሉ ፡-አት
ፍሩ ፤ አትዘኑም ፤ በዚያችም ፡
ተስፋ ፡ ቃል ፡ ትደረግላችሁ ፡
በነበራችሁት ፡ ገነት ፡ ተበሰሩ ፤
በማለት ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ መላእክት፡
ይወርዳሉ ።
31 እኛ ፡ በቅርቢቱም ፡ ሕይወት ፡
በመጨረሻይቱም ፡ ረዳቶቻችሁ ፡
ነን ! ለናንተም ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡
ነፍሶቻችሁ ፡ የሚሹት ፡ ሁሉ ፡
አልላችሁ ፤ ለናንተም ፡ በርሷ ፡
ውስጥ ፡ የምትፈልጉት ፡ ሁሉ ፡
አልላችሁ ፤
32 መሐሪ ፡ አዛኝ ፡ ከኾነው ፡ አላህ ፡
መስተንግዶ ፡ ሲኾን ፤ (ይባላሉ) ።
33 ወደ ፡ አላህ ፡ ከጠራና ፡ መልካ
ምንም ፡ ከሠራ ፡ እኔ ፡ ከሙስሊም
ች ፡ ነኝ ፡ ካለም ፡ ሰው ፡ ይበልጥ ፡
ቃሉ ፡ ያማረ ፡ ማን ፡ ነው ?
34 መልካሚቱና ፡ ክፉይቱም ፡ (ጠ
ባይ) ፡ አይተካከሉም ፤ በዚያች ፡
እርሷ ፡ መልካም ፡ በኾነችው ፡
ጠባይ ፡ (መጥፎይቱን) ፡ ገፍትር ፤
ያን ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ባንተና ፡ በርሱ ፡
መከከል ፡ ጠብ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ እ
ርሱ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ አዛኝ ፡ ዘመድ፡
ይኾናል ።
35 (ይህችንም ፡ ጠባይ) ፡ እነዚያ ፡
የታገሡት ፡ እንጅ ፡ ሌላው ፡ አያ
ገኛትም ፤ የትልቅም ፡ ዕድል ፡
ባለቤት ፡ እንጅ ፡ ማንም ፡ አይገጠ
ማትም ።
36 ከሰይጣንም ፡ ጉትጎታ ፡ ቢያገ
ኝህ ፡ (ከመልካም ፡ ጠባይም ፡
ቢመልስህ) ፡ በአላህ ፡ ተጠበቅ ፤
እነሆ ፡ እርሱ ፡ ሰሚው ፡ ዐዋቂው ፡
ነውና ።
37 ሌሊትና ፡ ቀንም ፡ ፀሐይና ፡ ጨረ
ቃም ፡ ከምልክቶቹ ፡ ናቸው ፤
ለፀሐይና ፡ ለጨረቃ ፡ አትስገዱ ፤
ለዚያም ፡ ለፈጠራቸው ፡ አላህ ፡
ስገዱ ፤ እርሱን ፡ ብቻ ፡ የምት
ግገዙ ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ (ለሌላ ፡
አትስገዱ) ።



38 ቢኮሩም ፡ እነዚያ ፡ በጌታህ ፡
ዘንድ ፡ ያሉት ፡ (መላእክት) ፡
በቀንም ፡ በሌሊትም ፡ ለርሱ ፡
ያወድሳሉ ፤ እነርሱም ፡ አይሰ
ለቹም ።
39 አንተ ፡ ምድርን ፡ ደረቅ ፡ ኾና ፡
ማየትህም ፡ ከምልክቶቹ ፡ ነው ፤
በርሷም ፡ ላይ ፡ ውሃን ፡ ባወረድን፡
ጊዜ ፡ (በቡቃያዎችዋ) ፡ ትላወ
ሳለች ፤ ትነፋለችም ፤ ያ ፡ ሕያው ፡
ያደረጋት ፡ ጌታ ፡ በእርግጥ ፡
ሙታንን ፡ ሕያው ፡ አድራጊ ፡
ነው ፤ እርሱ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ቻይ ፡ ነውና ።
40 እነዚያ ፡ አንቀጾቻችንን ፡ የሚያ
ጣምሙ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ አይደበ
ቁም ፤ (የሚያጣምምና) ፡ በእ
ሳት ፡ ውስጥ ፡ የሚጣለው ፡ ሰው ፡
ይበልጣልን ? ወይስ ፡ በትንሣኤ ፡
ቀን ፡ ጸጥተኛ ፡ ኾኖ ፡ የሚመ
ጣው ፡ ሰው ? የሻችሁትን ፡ ሥሩ ፤
(ዋጋችሁን ፡ ታገኛላችሁ) ፤ እርሱ፡
የምትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ተመል
ካች ፡ ነውና ።
41 እነዚያ ፡ በቁርአን ፡ እርሱ ፡ አሸ
ናፊ ፡ መጽሐፍ ፡ ሲኾን ፡ በመጣ
ላቸው ፡ ጊዜ ፡ የካዱት ፡ (ጠፊ
ዎች ፡ ናቸው) ።
42 ከኋላውም ፡ ከፊቱም ፡ ውሸት ፡ አይ
መጣበትም ፤ ጥበበኛ ፡ ምስጉን ፡
ከኾነው ፡ ጌታ ፡ የተወረደ ፡ ነው ።
43 ካንተ ፡ በፊት ፡ ለነበሩት ፡ መልክ
ተኞች ፡ የተባለው ፡ ብጤ ፡ እንጅ ፡
ለአንተ ፡ ሌላ ፡ አይባልም ፤ ጌታህ፡
የምሕረት ፡ ባለቤትና ፡ የአሳ
ማሚ ፡ ቅጣት ፡ ባለቤት ፡ ነው ።
44 በአዕጀምኛ ፡ የኾነ ፡ ቁርአን ፡
ባደረግነው ፡ ኖሮ ፡ አንቀጾቹ ፡
(በምናውቀው ፡ ቋንቋ) ፡ አይብ
ራሩም ፡ ኖሯልን ? (ቁርአኑ) ፡
አዕጀምኛና ፡ (መልክተኛው) ፡
ዐረባዊ ፡ ይኾናልን ? ባሉ ፡ ነበር ፤
እርሱ ፡ ለነዚያ ፡ ለአመኑት ፡
መምሪያና ፡ መፈወሻ ፡ ነው ።
እነዚያም ፡ የማያምኑት ፡ በጆሮዎ
ቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ድንቁርና ፡
ነው ፤ (አይሰሙትም) ፡ እርሱም ፡
በነርሱ ፡ ላይ ፡ ዕውርነት ፡ ነው ፤
እነዚያ ፡ ከሩቅ ፡ ስፍራ ፡ እንደሚ
ጥጠሩ ፡ ናቸው ።
45 ሙሳንም ፡ መጽሐፉን ፡ በእርግጥ ፡
ሰጠነው ፤ በርሱም ፡ ተለያዩበት ፤
ከጌታህም ፡ ያለፈች ፡ ቃል ፡ ባል
ነበረች ፡ ኖሮ ፡ በመካከላቸው ፡
በተፈረደ ፡ ነበር ፤ እነርሱም ፡
ከርሱ ፡ አወላዋይ ፡ በኾነ ፡ ጥር
ጣሬ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።
46 መልካም ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ለነፍሱ ፡
ነው ፤ ያጠፋም ፡ ሰው ፡ በርሷ ፡
ላይ ፡ ነው ፤ ጌታህም ፡ ለባሮቹ ፡
በዳይ ፡ አይደለም ።

★ ★ ★

47 ጊዜይቱን ፡ ማወቅ ፡ ወደርሱ ፡
ይመለሳል ፡ (1) ከፍሬዎችም ፡
ከሽፋኖቻቸው ፡ አይወጡም ፤
ከሴትም ፡ አንዲትም ፡ አታረግ
ዝም ፡ አትወልድምም ፡ በዕው
ቀቱ ፡ ቢኾን ፡ እንጅ ፤ ተጋሪዎቼ፡
የት ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ በሚጠ
ራቸው ፡ ቀንም ፡ ከኛ ፡ ውስጥ ፡
(ባላንጣ ፡ አልለ ፡ ብሎ) ፡ ምንም ፡
መስካሪ ፡ አለመኖሩን ፡ አስታወ
ቅንህ ፡ ይላሉ ።
48 ያም ፡ በፊት ፡ ይግገዙት ፡ የነበ
ሩት ፡ (ጣዖት) ፡ ከነርሱ ፡ ይጠፋ

1 የትንሣኤን ፡ ጊዜ ፡ መምጫ ፡ ያለርሱ ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ።

ቸዋል ፤ ለነሱም ፡ ምንም ፡ መሸሻ ፡
የሌላቸው ፡ መኾኑን ፡ ያረጋግ
ጣሉ ።
49 ሰው ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ ከመለመን ፡
አይሰለችም ፤ ክፉም ፡ ቢያገኘው ፡
ወዲያውኑ ፡ በጣም ፡ ተስፋ ፡
ቆራጭ ፡ ተበሳጭ ፡ ይኾናል ።
50 ካገኘችውም ፡ መከራ ፡ በኋላ ፡
ከኛ ፡ የኾነን ፡ እዝነት ፡ ብናቀ
ምሰው ፡ ይህ ፡ ለኔ ፡ (በሥራዬ ፡
የተገባኝ) ፡ ነው ፤ ሰዓቲቱም ፡
መጪ ፡ ናት ፡ ብዬ ፡ አላስብም ፤
ወደ ፡ ጌታየም ፡ ብመለስ ፡ ለኔ ፡
እርሱ ፡ ዘንድ ፡ መልካሚቱ ፡
(ገነት) ፡ በእርግጥ ፡ አለችኝ ፡
ይላል ፤ እነዚያንም ፡ የካዱትን ፡
ሥራዎቻቸውን ፡ በእርግጥ ፡ እንነ
ግራቸዋለን ፤ ከብርቱውም ፡ ስቃይ
በእርግጥ ፡ እናቀምሳቸዋለን ።
51 በሰውም ፡ ላይ ፡ ጸጋችንን ፡ በለ
ገስን ፡ ጊዜ ፡ (ከማመስገን) ፡ ይዞ
ራል ፤ በጐኑም ፡ ይርቃል ፤ መከ
ራም ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ የብዙ ፡
ልመና ፡ ባለቤት ፡ ይኾናል ።
52 በላቸው ፡— ንገሩኝ ፡ (ቁርአኑ) ፡
ከአላህ ፡ ዘንድ ፡ ቢኾን ፡ ከዚያም ፡
በርሱ ፡ ብትክዱ ፡ (ከውነት) ፡
በራቀ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ላይ ፡ ከኾነ ፡
ሰው ፡ ይበልጥ ፡ የተሳሳተ ፡ ማን ፡
ነው ።
53 እርሱም ፡ (ቁርአን) ፡ እውነት ፡
መኾኑ ፡ ለነርሱ ፡ እስከሚገለጽላ
ቸው ፡ ድረስ ፡ በአጽናፎቹ ፡ (1)
ውስጥና ፡ በነፍሶቻቸውም ፡ ው
ስጥ ፡ ያሉትን ፡ ታምራቶቻችንን ፡
በእርግጥ ፡ እናሳያቸዋለን ፤ ጌታ
ህም ፡ እርሱ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ዐዋቂ ፡ መኾኑ ፡ አይበቃቸው
ምን ?
54 ንቁ ፡ እነርሱ ፡ ከጌታቸው ፡ መገ
ናኘት ፡ በመጠራጠር ፡ ውስጥ ፡
ናቸው ፤ ንቁ ፡ እርሱ ፡ በነገሩ ፡
ሁሉ ፡ (ዕውቀቱ) ፡ ከባቢ ፡ ነው ።

1 በምድርና ፡ በሰማያት ፡ ቀበሌዎች ።

## ምዕራፍ ፡ 42 ፡ አል-ሹራ ። ክፍል ፡ 25 ።

42ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሹራ ፡ (የመመካከር ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 53 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 ሐ. መ. (ሐ ፡ ሚም) ።
2 ዐ. ሰ. ቀ. (ዓይን ፡ ሲን ፡ ቃፍ) ፤(1)
3 እንደዚሁ ፡ (በዚች ፡ ሱራ ፡ ውስጥ
እንዳለው) ፡ አሸናፊው ፡ ጥበበ
ኛው ፡ አላህ ፡ ወዳንተ ፡ ያወር
ዳል ፤ ወደነዚያም ፡ ከአንተ ፡
በፊት ፡ ወደ ፡ ነበሩት ፡ ሕዝቦች ፡
(አውርዷል) ።

1 በውቀቱ ፡ በልቅናዩ ፡ በችሎታዩ ፡ እም
ላለሁ ። በኔ ፡ ያመነ ፡ አይቀጣም ።



4 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡
ሁሉ ፡ የርሱ ፡ ነው ፤ እርሱም ፡
የበላዩ ፡ ታላቁ ፡ ነው ።
5 (ከአላህ ፡ ፍራቻ) ፡ ሰማያት ፡ ከበ
ላያቸው ፡ ሊቀደዱ ፡ ይቀርባሉ ፤
መላእክትም ፡ ጌታቸውን ፡ እያ
መሰገኑ ፡ ያወድሳሉ ፤ በምድርም ፡
ላለው ፡ ፍጡር ፡ ምሕረትን ፡ ይለ
ምናሉ ፤ ንቁ ፡ አላህ ፡ እርሱ ፡
መሓሪው ፡ አዛኙ ፡ ነው ።
6 እነዚያም ፡ ከርሱ ፡ ሌላ ፡ (የጣዖ
ታት) ፡ ረዳቶችን ፡ የያዙ ፤ አላህ ፡
በነርሱ ፡ ላይ ፡ ተጠባባቂ ፡ ነው ፤
አንተም ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ኀላፊ ፡
አይደለህም ።
7 እንደዚሁም ፡ የከተሞች ፡ እናት ፡
የኾነችውን ፡ (የመካን ፡ ሰዎች) ፡
በአካባቢዋ ፡ ያሉትንም ፡ ልታስ
ፈራራ ፡ የመሰብሰቢያውንም ፡
ቀን ፡ በርሱ ፡ ጥርጣሬ ፡ የሌለ
በት ፡ ሲኾን ፡ ልታስጠነቅቅ ፡
ዐረብኛ ፡ የኾነን ፡ ቁርአን ፡ ወደ ፡
አንተ ፡ አወረድን ፤ (ከነሱም) ፡
ከፊሉ ፡ በገነት ፡ ውስጥ ፡ ከፊ
ሉም ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ነው ።
8 አላህም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ (ባንድ ፡
ሃይማኖት ፡ ላይ) ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡
ባደረጋቸው ፡ ነበር ። ግን ፡ የሚ
ሻውን ፡ ሰው ፡ በእዝነቱ ፡ ውስጥ ፡
ያስገባል ፤ በዳዮችም ፡ ለነርሱ ፡
ወዳጅና ፡ ረዳት ፡ ምንም ፡ የላቸ
ውም ።
9 ከርሱ ፡ ሌላ ፡ ረዳቶችን ፡ ያዙን ?
(ረዳቶች ፡ አይደሉም) ፡ አላህም ፡
ረዳት ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ። እር
ሱም ፡ ሙታንን ፡ ሕያው ፡ ያደር
ጋል ፤ እርሱም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ።
10 ከምንም ፡ ነገር ፡ ያ ፡ በርሱ ፡ የተለ
ያዩበት ፡ ፍርዱ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡
ነው ፤ ይሃችሁ ፡ አላህ ፡ ጌታዬ ፡
ነው ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተጠጋሁ ፤
ወደርሱም ፡ እመለሳለሁ ፤ (በላ
ቸው) ።
11 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ ፈጣሪ ፡
ነው ፤ ከነፍሶቻችሁ ፡ (1) ሴቶ
ችን ፡ ከቤት ፡ እንስሳዎችም ፡
ዓይነቶችን ፡ (ወንዶችና ፡ ሴቶ
ችን) ፡ ለናንተ ፡ አደረገላችሁ ፤
በርሱ ፡ (2) ያበዛችኋል ፤ የሚመስ
ለው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ፤
እርሱም ፡ ሰሚው ፡ ተመልካቹ ፡
ነው ።
12 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ (ድልቦች) ፡
መክፈቻዎች ፡ የርሱ ፡ ናቸው ።
ሲሳይን ፡ ለሚሻው ፡ ሰው ፡ ያሰ
ፋል ፤ ያጠባልም ፤ እርሱ ፡ ነገ
ሩን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።
13 ለናንተ ፡ ከሃይማኖት ፡ ያንን ፡
በርሱ ፡ ኑሕን ፡ ያዘዘበትን ፡ ደነ
ገገላችሁ ፤ ያንንም ፡ ወዳንተ ፡
ያወረድነውን ፡ ያንንም ፡ በርሱ ፡
ኢብራሂምን ፡ ሙሳንና ፡ ዒሳ
ንም ፡ ያዘዝንበትን ፡ ሃይማኖትን ፡
በትክክል ፡ አቋቁሙ ፡ በርሱም ፡
አትለያዩ ፡ ማለትን ፡ (ደነገግን) ፤
በአጋሪዎቹ ፡ ላይ ፡ ያ ፡ ወደርሱ ፡
የምትጠራቸው ፡ ነገር ፡ ከበዳ
ቸው ፤ አላህ ፡ የሚሻውን ፡ ሰው ፡
ወደርሱ ፡ (እምነት) ፡ ይመርጣል ፤
የሚመለስንም ፡ ሰው ፡ ወደርሱ ፡
ይመራል ።
14 (የሃይማኖት ፡ ሰዎች) ፡ ዕውቀ
ቱም ፡ ከመጣላቸው ፡ በኋላ ፡ በመ

1 ከጐሶቻችሁ ።
2 በማድረጉ ።

ካከላቸው ፡ ለምቀኝነት ፡ እንጅ ፡
ለሌላ ፡ አልተለያዩም ፤ እስከ ፡
ተወሰነም ፡ ጊዜ ፡ (በማቆየት) ፡
ከጌታህ ፡ ያለፈች ፡ ቃል ፡ ባልነበ
ረች ፡ ኖሮ ፡ በነሱ ፡ መካከል ፡
(አሁን) ፡ በተፈረደ ፡ ነበር ። እነ
ዚያም ፡ ከኋላቸው ፡ መጽሐፉን ፡
እንዲወርሱ ፡ የተደረጉት ፡ ከርሱ ፡
በእርግጥ ፡ በአወላዋይ ፡ ጥርጣሬ ፡
ውስጥ ፡ ናቸው ።

15 ለዚህም ፡ (ድንጋጌ ፡ ሰዎችን) ፡
ጥራ ፤ እንደታዘዝከውም ፡ ቀጥ ፡
በል ፤ ዝንባሌዎቻቸውንም ፡ አት
ከተል ፤ በላቸውም ፡— ከመጽ
ሐፍ ፡ አላህ ፡ ባወረደው ፡ ሁሉ ፡
አመንኩ ፤ በመካከላችሁም ፡ ላስ
ተካክል ፡ ታዘዝኩ ፤ አላህ ፡ ጌታ
ችን ፡ ጌታችሁም ፡ ነው ፤ ለኛ ፡
ሥራዎቻችን ፡ አልሉን ፤ ለናን
ተም ፡ ሥራዎቻችሁ ፡ አልሏችሁ ፤
በኛና ፡ በናንተ ፡ መካከል ፡ ክር
ክር ፡ የለም ፤ አላህ ፡ በመካከላ
ችን ፡ ይሰበስባል ። መመለሻም ፡
ወደርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

16 እነዚያም ፡ በአላህ ፡ (ሃይማኖት) ፡
ለርሱ ፡ ተቀባይ ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡
የሚከራከሩት ፡ ማስረጃቸው ፡
በጌታቸው ፡ ዘንድ ፡ ብልሹ ፡
ናት ። በነርሱም ፡ ላይ ፡ ቁጣ ፡
አለባቸው ፡ ለነርሱም ፡ ብርቱ ፡
ቅጣት ፡ አልላቸው ።

17 አላህ ፡ ያ ፡ መጽሐፉን ፡ በእው
ነት ፡ ያወረደ ፡ ነው ፤ ሚዛንንም ፡
(እንደዚሁ) ፤ ሰዓቲቱ ፡ ምናል
ባት ፡ ቅርብ ፡ መኾንዋን ፡ ምን ፡
ያሳውቅሃል ?

18 እነዚያ ፡ በርሷ ፡ የማያምኑት ፡
በርሷ ፡ ያቻኩላሉ ፤ እነዚያም ፡
ያመኑት ፡ ከርሷ ፡ ፈሪዎች ፡ ናቸ
ው ፤ እርሷም ፡ እውነት ፡ መኾን
ዋን ፡ ያውቃሉ ፤ ንቁ ፡ እነዚያ ፡
በሰዓቲቱ ፡ የሚከራከሩት ፡ በእ
ርግጥ ፡ (ከውነት) ፡ በራቀ ፡ ስሕ
ተት ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።

19 አላህ ፡ በባሮቹ ፡ ርኅሩህ ፡ ነው ፤
ለሚሻው ፡ ሰው ፡ (በሰፊው) ፡
ሲሳይን ፡ ይሰጣል ፤ እርሱም ፡
ብርቱው ፡ አሸናፊው ፡ ነው ።

20 (በሥራው) ፡ የኋለኛይቱን ፡ ዓለም
አዝመራ ፡ የሚፈልግ ፡ የኾነ ፡
ሰው ፡ ለርሱ ፡ በአዝመራው ፡
ላይ ፡ እንጨምርለታለን ፤ የቅር
ቢቱንም ፡ ዓለም ፡ አዝመራ ፡ የሚ
ፈልግ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ከርሷ ፡
(የተወሰነለትን ፡ ብቻ) ፡ እንሰጠ
ዋለን ፤ ለርሱም ፡ በኋለኛይቱ ፡
ዓለም ፡ ምንም ፡ ፋንታ ፡ የለውም።

21 ከሃይማኖት ፡ አላህ ፡ በርሱ ፡ ያል
ፈቀደውን ፡ ለነርሱ ፡ የደነገጉ ፡
ተጋሪዎች ፡ ለነርሱ ፡ አልሏቸ
ውን ? የፍርዱ ፡ ቃል ፡ ባልነበረ ፡
ኖሮ ፡ በመካከላቸው ፡ (አሁን) ፡
በተፈረደ ፡ ነበር ፤ በደለኞችም ፡
ለነርሱ ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ በእ
ርግጥ ፡ አልላቸው ።

22 በደለኞችን ፡ ከሠሩት ፡ ሥራ ፡
(ዋጋ ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን) ፡ ፈሪ
ዎች ፡ ኾነው ፡ ታያቸዋለህ ፤ እር
ሱም ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ወዳቂ ፡
ነው ። እነዚያም ፡ ያመኑት ፡ መል
ካሞችንም ፡ የሠሩት ፡ በገነቶች ፡
ጨፌዎች ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።
ለነርሱ ፡ በጌታቸው ፡ ዘንድ ፡
የሚሹት ፡ ሁሉ ፡ አልላቸው ፤
ይህ ፡ እርሱ ፡ ታላቅ ፡ ችሮታ ፡
ነው ።

23 ይህ ፡ (ታላቅ ፡ ችሮታ) ፡ ያ ፡
አላህ ፡ እነዚያን ፡ ያመኑትንና ፡
መልካሞችን ፡ የሠሩትን ፡ ባሮ
ቹን ፡ የሚያበስርበት ፡ ነው ፤
በርሱ ፡ (መልክቴን ፡ በማድረሴ) ፡
ላይ ፡ በዝምድና ፡ (1) ውዴታን ፡
እንጅ ፡ ዋጋን ፡ አልጠይቃችሁም ፡
በላቸው ፤ መልካሚቱንም ፡ ሥራ ፡
የሚሠራ ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡ በርሷ ፡
መልካምን ፡ ነገር ፡ እንጨምር
ለታለን ፤ አላህ ፡ መሓሪ ፡ አመስ
ጋኝ ፡ ነውና ።

24 ይልቁንም ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ውሸ
ትን ፡ ቀጠፈ ፡ ይላሉን ? አላህም ፡
ቢሻ ፡ በልብህ ፡ ላይ ፡ ያትማል ፤
(2) አላህም ፡ ውሸቱን ፡ ያብብሳል ፤
እውነቱንም ፡ በቃላቱ ፡ ያረጋ
ግጣል ፡ እርሱ ፡ በልቦች ፡ ውስጥ ፡
ያለን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።

25 እርሱም ፡ ያ ፡ ከባሮቹ ፡ ንስሓን ፡
የሚቀበል ፡ ከኃጢአቶችም ፡ ይ
ቅር ፡ የሚል ፡ የምትሠሩትንም ፡
ሁሉ ፡ የሚያውቅ ፡ ነው ።

26 እነዚያንም ፡ ያመኑትንና ፡ መልካ
ሞችን ፡ የሠሩትን ፡ ልመናቸውን ፡
ይቀበላል ፤ ከችሮታውም ፡ ይጨ
ምርላቸዋል ፤ ከሓዲዎቹም ፡ ለነሱ
ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ።

27 አላህም ፡ ለባሮቹ ፡ (ሁሉ) ፡ ሲሳ
ይን ፡ በዘረጋ ፡ ኖሮ ፡ በምድር ፡
ውስጥ ፡ (ሁሉም) ፡ ወሰን ፡ ባለፉ ፡
ነበር ፤ ግን ፡ የሚሻውን ፡ በልክ ፡
ያወርዳል ፤ እርሱ ፡ በባሮቹ ፡
ውስጥ ፡ ዐዋቂ ፡ ተመልካች ፡
ነውና ።

28 እርሱም ፡ ያ ፡ ተስፋ ፡ ከቆረጡ ፡
በኋላ ፡ ዝናምን ፡ የሚያወርድ ፡
ችሮታውንም ፡ የሚዘረጋ ፡ ነው ፤
እርሱም ፡ ረዳቱ ፡ ምስጉኑ ፡
ነው ።

29 ሰማያትንና ፡ ምድርንም ፡ መፍ
ጠሩ ፡ ከተንቀሳቃሽም ፡ በሁለቱ ፡
ውስጥ ፡ የበተነውን ፡ (መፍጠሩ) ፡
ከአስደናቂ ፡ ምልክቶቹ ፡ ነው ።
እርሱም ፡ በሚሻ ፡ ጊዜ ፡ እነር
ሱን ፡ በመሰብሰብ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡
ነው ።

30 ከመከራም ፡ ማንኛውም ፡ ያገኛ
ችሁ ፡ ነገር ፡ እጆቻችሁ ፡ በሠ
ሩት ፡ (ኃጢአት) ፡ ምክንያት ፡
ነው ፤ ከብዙውም ፡ ይቅር ፡ ይላል።

31 እናንተም ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡
አስሳኞች ፡ አይደላችሁም ፤ ለና
ንተም ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ከዘመ
ድም ፡ ከረዳትም ፡ ምንም ፡ የላ
ችሁም ።

32 በባሕር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጋራዎች ፡
ኾነው ፡ ተንሻላዮቹም ፡ (መርከ
ቦች) ፡ ከአስደናቂ ፡ ምልክቶቹ፡
ናቸው ።

33 ቢሻ ፡ ነፋሱን ፡ የረጋ ፡ ያደርገ
ዋል ፤ በባሕሩም ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡
ረጊዎች ፡ ይኾናሉ ፤ በዚህ ፡
ውስጥ ፡ በጣም ፡ ታጋሽና ፡ አመ
ስጋኝ ፡ ለኾነ ፡ ሁሉ ፡ በእርግጥ ፡
ምልክቶች ፡ አልሉ ።

34 ወይም ፡ በሠሩት ፡ ኃጢአት ፡ ምክ
ንያት ፡ (በማስጠም) ፡ ያጠፋቸ
ዋል ፤ ከብዙም ፡ ይቅርታ ፡ ያደ
ርጋል ።

35 (ከነሱ ፡ ለመበቀል) ፤ እነዚያንም ፡
በአንቀጾቻችን ፡ የሚከራከሩትን ፡
ለማወቅ ፡ (ያጠፋቸዋል) ፤ ለነ
ርሱ ፡ ምንም ፡ መሸሻ ፡ የላቸ
ውም ።

1 በመካከላችን ፡ ባለው ፡ ዝምድና ፡ መዋ
ደድን ።

2 ልብህን ፡ በትእግሥት ፡ ያበረታል ።

36 ከምንም ፡ ነገር ፡ የተሰጣችሁት ፡
የቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡ መጠቀ
ሚያ ፡ ነው ፤ አላህ ፡ ዘንድ ፡ ያለ
ውም ፡ ምንዳ ፡ ለነዚያ ፡ ለአመ
ኑትና ፡ በጌታቸው ፡ ላይ ፡ ለሚ
ጠጉት ፡ በላጭና ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡
ነዋሪ ፡ ነው ።

37 ለነዚያም ፡ የኀጢአትን ፡ ታላላ
ቆችና ፡ ጠያፎችን ፡ የሚርቁ ፡
በተቆጡም ፡ ጊዜ ፡ እነሱ ፡ የሚ
ምሩ ፡ ለኾኑት ።

38 ለነዚያም ፡ የጌታቸውን ፡ ጥሪ ፡
ለተቀበሉት ፣ ሶላትንም ፡ ላዘወ
ተሩት ፡ ነገራቸውም ፡ በመካከላ
ቸው ፡ መመካከር ፡ ለኾነው ፡
ከሰጠናቸውም ፡ ሲሳይ ፡ ለሚለ
ግሱት ።

39 ለነዚያም ፡ በደል ፡ በደረሰባቸው ፡
ጊዜ ፣ እነሱ ፡ (በመሰሉ) ፡ የሚመ
ልሱ ፡ ለኾኑት ፣ (በላጭና ፡ ኗሪ ፡
ነው) ።

40 የመጥፎም ፡ ነገር ፡ ዋጋ ፡ ብጤዋ ፡
መጥፎ ፡ ናት ፤ ይቅርም ፡ ያለና ፡
ያሳመረ ፡ ሰው ፡ ምንዳው ፡ በአ
ላህ ፡ ላይ ፡ ነው ። እርሱ ፡ በደ
ለኞችን ፡ አይወድም ።

41 ከተበደሉም ፡ በኋላ ፡ (በመሰሉ) ፡
የተበቀሉ ፣ እነዚያ ፡ በነርሱ ፡
ላይ ፡ ምንም ፡ (የወቀሳ) ፡ መን
ገድ ፡ የለባቸውም ።

42 (የወቀሳ) ፡ መንገዱ ፣ በነዚያ ፡
ሰዎችን ፡ በሚበድሉት ፣ በም
ድርም ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡
ወሰን ፡ በሚያልፉት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡
ነው ፤ እነዚያ ፡ ለነሱ ፡ አሳማሚ ፡
ቅጣት ፡ አልላቸው ።

43 የታገሠና ፡ ምሕረት ፡ ያደረገም ፡
ሰው ፣ ይህ ፡ ከምርሮቹ ፡ (ከተፈላ
ጊዎቹ) ፡ ነገሮች ፡ ነው ።

44 አላህ ፡ የሚያጠመውም ፡ ሰው ፡
ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ለርሱ ፡ ምንም ፡
ረዳት ፡ የለውም ፤ በደለኞችንም ፡
ቅጣቱን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ መመ
ለስ ፡ መንገድ ፡ አልለን ? የሚሉ ፡
ሲኾኑ ፡ ታያቸዋለህ ።

45 ከውርደት ፡ የተነሳ ፡ ፈሪዎች ፡
ኾነው ፣ በዓይን ፡ ሥርቆት ፡ ወደ
ርሷ ፡ (ወደ ፡ እሳት) ፡ እያስተ
ዋሉ ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ የሚቀረቡ ፡
ሲኾኑ ፡ ታያቸዋለህ ፤ እነዚያም ፡
ያመኑት ፡— በእርግጥ ፡ ከሳሪ
ዎቹ ፣ እነዚያ ፡ ነፍሶቻቸውንና ፡
ቤተሰቦቻቸውን ፡ በትንሣኤ ፡
ቀን ፡ ያከሰሩት ፡ ናቸው ፡ ይላሉ ።

46 ንቁ ፡ በደለኞች ፡ በእርግጥ ፡ በዘ
ውታሪ ፡ ስቃይ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።
ለነሱም ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የሚረ
ዷቸው፡ ዘመዶች ፡ ምንም ፡ አልነ
በሩዋቸውም ፤ አላህም ፡ የሚያጠ
መው ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡ (ወደ ፡
እውነት) ፡ ምንም ፡ መንገድ ፡ የለ
ውም ።

47 ለርሱ ፡ መመለስ ፡ የሌለው ፡ ቀን ፡
ከአላህ ፡ ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡
ለጌታችሁ ፡ ታዘዙ ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡
ለናንተ ፡ ምንም ፡ መጠጊያ ፡
የላችሁም ፤ ለናንተም ፡ ምንም ፡
መካድ ፡ የላችሁም ።

48 ቢዞሩም ፡ (ወቀሳ ፡ የለብህም) ፤
በነሱ ፡ ላይ ፡ ጠባቂ ፡ አድርገን ፡
አልላክንህምና ፤ ባንተ ፡ ላይ ፡
ማድረስ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የለብ
ህም ፤ እኛም ፡ ሰውን ፡ ከኛ ፡ የኾ
ነን ፡ ጸጋ ፡ ባቀመስነው ፡ ጊዜ ፣
በርሷ ፡ ይደሰታል ፤ እጆቻቸው ፡
ባስቀደሙትም ፡ ኀጢአት ፡ ምክ
ንያት ፡ መከራ ፡ ብትደርስባቸው ፡



(ተስፋ ፡ ይቆርጣሉ) ፤ ሰው ፡ (ውለ
ታን) ፡ በጣም ፡ ከሐዲ ፡ ነውና ።

49 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ንግሥና ፡
የአላህ ፡ ነው ፤ የሚሻውን ፡ ይፈ
ጥራል ፤ ለሚሻው ፡ ሰው ፡ ሴቶ
ችን ፡ (ልጆች) ፡ ይሰጣል ፤ ለሚሻ
ውም ፡ ሰው ፡ ወንዶችን ፡ ይሰ
ጣል ።

50 ወይም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡
አድርጎ ፡ ያጠናዳቸዋል ፤ የሚሻ
ውንም ፡ ሰው ፡ መካን ፡ ያደርገ
ዋል ፤ እርሱ ፡ ዐዋቂ ፡ ቻይ ፡
ነውና ።

51 ለሰውም ፡ አላህ ፡ በራእይ ፡
ወይም ፡ ከግርዶ ፡ ወዲያ ፡ ወይም ፡
መልክተኛን ፡ (መልአክን) ፡ የሚ
ልክና ፡ በፈቃዱ ፡ የሚሻውን ፡
ነገር ፡ የሚያወርድለት ፡ ቢኾን ፡
እንጅ ፡ (በገሃድ) ፡ ሊያናግረው ፡
ተገቢው ፡ አይደለም ። እርሱ ፡
የበላይ ፡ ጥበበኛ ፡ ነውና ።

52 እንደዚሁም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ከት
እዛዛችን ፡ ሲኾን ፡ መንፈስን ፡
(ቁርአንን) ፡ አወረድን ፤ መጽሐ
ፉም ፡ እምነቱም ፡ ምን ፡ እንደ ፡
ኾነ ፡ የምታውቅ ፡ አልነበርክም ።
ግን ፡ (መንፈሱን) ፡ ከባሮቻችን ፡
የምንሻውን ፡ ሰው ፡ በርሱ ፡ የምን
መራበት ፡ ብርሃን ፡ አደረግነው ።
አንተም ፡ ወደ ፡ ቀጥተኛው ፡ መን
ገድ ፡ በእርግጥ ፡ ትመራለህ ።

53 ወደዚያ ፡ በሰማያትና ፡ በምድር ፡
ያለው ፡ ሁሉ ፡ የርሱ ፡ ወደ ፡
ኾነው ፡ አላህ ፡ መንገድ ፡ (ትመ
ራለህ) ፤ ንቁ ፡ ነገሮቹ ፡ ሁሉ ፡
ወደ ፡ አላህ ፡ ይመለሳሉ ።

## ምዕራፍ ፡ 43 ፡ አል-ዙኽሩፍ ። ክፍል ፡ 25 ።

43ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ዙኽሩፍ ፡ (የጌጣጌጥ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 89 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፣ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው።

1 ሐ. መ. (ሓ ፡ ሚም) ።

2 ገላጭ ፡ በኾነው ፡ መጽሐፍ ፡
እምላለሁ ።

3 እኛ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ዐረብኛ ፡
ቁርአን ፡ አደረግነው ።

4 እርሱም ፡ በመጽሐፎቹ ፡ እናት ፡
ውስጥ ፣ እኛ ፡ ዘንድ ፡ በእርግጥ ፡
ከፍተኛ ፣ ጥበብ ፡ የተመላ ፡ ነው ።

5 ድንበር ፡ አላፊዎች ፡ ሕዝቦች ፡
ለመኾናችሁ ፡ ቁርአኑን ፡ ከና
ንተ ፡ ማገድን ፡ እናግዳለን ?

6 በፊተኞቹም ፡ ሕዝቦች ፡ ውስጥ ፡
ከነቢይ ፡ ብዙን ፡ ልከናል ።

7 ከነቢይም ፡ አንድም ፡ የሚመጣ
ላቸው ፡ አልነበረም ፣ በርሱ ፡ ይሳ
ለቁበት ፡ የነበሩ ፡ ቢኾኑ ፡ እንጅ ።

8 ከነሱም ፡ በኀይል ፡ ይበልጥ ፡ የበ
ረቱትን ፡ አጥፍተናል ። የፊተኞ

ቹም ፡ (አጠፋፍ) ፡ ምሳሌ ፡ አል
ፏል ።

9 ሰማያትንና ፡ ምድርንም ፡ ማን ፡
ፈጠራቸው ፡ ብለህ ፡ ብትጠይ
ቃቸው ፡ አሸናፊው ፡ ዐዋቂው ፡
(አላህ) ፡ በእርግጥ ፡ ፈጠራቸው ፡
ይላሉ ።

10 (እርሱ) ፡ ያ ፡ ምድርን ፡ ለናንተ ፡
ምንጣፍ ፡ ያደረገላችሁ፣ በርሷም ፡
ውስጥ ፡ ትመሩ ፡ ዘንድ ፡ ለናንተ ፡
መንገዶችን ፡ ያደረገላችሁ ፡ ነው።

11 ያም ፡ ከሰማይ ፡ ውሃን ፡ በልክ ፡
ያወረደላችሁ ፡ ነው ፤ በርሱም ፡
የሞተችውን ፡ አገር ፡ ሕያው ፡
አደረግን ፤ እንደዚሁ ፡ (ከመቃብ
ራችሁ) ፡ ትውወጣላችሁ ።

12 ያም ፡ ዓይነቶችን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረ፣
ለናንተም ፡ ከመርከቦችና ፡ ከቤት፣
እንስሳዎች ፡ የምትጋልቧቸውን ፡
ያደረገላችሁ ፡ ነው ።

13 በጀርባዎቹ ፡ ላይ ፡ እንድትደላ
ደሉ ፣ ከዚያም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
በተደላደላችሁ ፡ ጊዜ ፣ የጌታች
ሁን ፡ ጸጋ ፡ እንድታስታውሱ ፤
እንድትሉም ፡— ያ ፡ ይህንን ፡
የማንችለው ፡ ስንኾን ፡ ለኛ ፡
ያገራልን ፡ ጌታ ፡ ጥራት ፡ ይገ
ባው ።

14 እኛም ፡ በእርግጥ ፡ ወደ ፡ ጌታ
ችን ፡ ተመላሾች ፡ ነን ፣ (እንድ
ትሉ) ።

15 ከባሮቹም ፡ ለርሱ ፡ ቁራጭን ፣ (ል
ጅን) ፣ አደረጉለት ፤ (1) ሰው ፡
በእርግጥ ፡ ግልጽ ፡ ከሓዲ ፡ ነው ።

16 ከሚፈጥረው ፡ ውስጥ ፡ ሴቶች ፡
ልጆችን ፡ ያዘን? በወንዶች ፡ ልጆ
ችም ፡ (እናንተን) ፡ መረጣችሁን ?

17 አንዳቸውም ፣ ለአልረሕማን ፡
ምሳሌ ፡ ባደረገው ፡ ነገር ፡ (በሴት፡
ልጅ) ፡ በተበሰረ ፡ ጊዜ ፣ እርሱ ፡
በቁጭት ፡ የተመላ ፡ ኾኖ ፡ ፊቱ ፡
የጠቆረ ፡ ይኾናል ።

18 በጌጥ ፡ (ተከልሶ) ፡ እንዲያድግ ፡
የሚደረገውን ? እርሱም ፡ (ለደካ
ማነቱ) ፡ በክርክር ፡ የማያብራራ
ውን ፡ ፍጡር ፡ (ሴትን) ፡ ለአላህ ፡
ያደርጋሉን ?

19 መላእክትንም ፡ እነሱ ፡ የአልረሕ
ማን ፡ ባሮች ፡ የኾኑትን ፡ ሴቶች ፡
አደረጉ ፤ ሲፈጠሩ ፡ ነበሩን ? መመ
ስከራቸው ፡ በእርግጥ ፡ ትጻፋ
ለች ፤ ይጠየቃሉም ።

20 አልረሕማንም ፡ በሻ ፡ ኖሮ ፡ ባል
ተገዛናቸው ፡ ነበር ፡ አሉ ፤ ለነ
ርሱ ፡ በዚህ ፡ ምንም ፡ ዕውቀት ፡
የላቸውም ፤ እነሱ ፡ የሚዋሹ ፡
እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደሉም ።

21 ከርሱ ፡ (ከቁርአን) ፡ በፊት ፡ መጽ
ሐፍን ፡ ሰጠናቸውን ? ስለዚህ ፡
እነሱ ፡ እርሱን ፡ የጨበጡ ፡
ናቸውን ?

22 ከቶውንም ፡ እኛ ፡ አባቶቻችንን ፡
በሃይማኖት ፡ ላይ ፡ አገኘናቸው ፤
እኛም ፡ በፈለጎቻቸው ፡ ላይ ፡
ተመሪዎች ፡ ነን ፡ አሉ ።

23 (ነገሩ) ፡ እንደዚሁም ፡ ነው ፤ ከበ
ፊትህ ፡ በማንኛይቱም ፡ ከተማ ፡
ውስጥ ፡ አስፈራሪን ፡ አልላክ
ንም ፣ ቅምጥሎችዋ ፡ እኛ ፡ አባ
ቶቻችንን ፡ በሃይማኖት ፡ ላይ ፡
አገኘን ፤ እኛም ፡ በፈለጎቻቸው ፡
ላይ ፡ ተከታዮች ፡ ነን ፡ ያሉ ፡
ቢኾኑ ፡ እንጅ ።

1 መላእክት ፡ የአላህ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡
ናቸው ፡ አሉ ።



24 (አስፈራሪው) ፡ አባቶቻችሁን ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ ካገኛችሁበት ፡
ይበልጥ ፡ ቀጥተኛን ፡ (ሃይማኖት)፡
ባመጣላችሁም ? አላቸው ፤ እኛ ፡
በርሱ ፡ በተላካችሁበት ፡ ነገር ፡
ከሓዲዎች ፡ ነን ፡ አሉ ።

25 ከነሱም ፡ ተበቀልን ፤ ያስተባባዮ
ቹም ፡ መጨረሻ ፡ እንዴት ፡
እንደ ፡ ነበረ ፡ ተመልከት ።

26 ኢብራሂምም ፡ ለአባቱና ፡ ለሕ
ዝቦቹ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፡
እኔ ፡ ከምትግገዙት ፡ ሁሉ ፡
ንጹሕ ፡ ነኝ ።

27 ከዚያ ፡ ከፈጠረኝ ፡ በስተቀር ፤
(አልግገዛም) ፡ እርሱ ፡ በእርግጥ ፡
ይመራኛልና ።

28 በዝርዮቹም ፡ ውስጥ ፡ ይመለሱ ፡
ዘንድ ፡ (ባንድ ፡ አምላክ ፡ ማመ
ንን) ፡ ቀሪ ፡ ቃል ፡ አደረጋት ።

29 ይልቅ ፡ እነዚህን ፡ (ቁረይሾችን) ፡
አባቶቻቸውንም ፡ ቁርአንና ፡
ገላጭ ፡ መልክተኛ ፡ እስከመጣላ
ቸው ፡ ድረስ ፡ አጣቀምኳቸው ።

30 እውነቱም ፡ በመጣላቸው ፡ ጊዜ ፣
ይህ ፡ ድግምት ፡ ነው ፤ እኛም ፡
በርሱ ፡ ከሓዲዎች ፡ ነን ፡ አሉ ።

31 ይህም ፡ ቁርአን ፡ ከሁለቱ ፡ ከተ
ሞች ፡ በታላቅ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ (1)
አይወረድም ፡ ኖሯልን ? አሉ ።

32 እነርሱ ፡ የጌታህን ፡ ችሮታ ፡ ያከ
ፋፍላሉን ? እኛ ፡ በቅርቢቱ ፡
ሕይወት ፡ኑሯቸውን ፡ በመካከ
ላቸው ፡ አከፋፍለናል ። ከፊላቸ
ውም ፡ ከፊሉን ፡ ሠራተኛ ፡ አድ
ርጎ ፡ ይይዝ ፡ ዘንድ ፡ ከፊላቸ
ውን ፡ ከከፊሉ ፡ በላይ ፡ በደረጃ
ዎች ፡ (በሀብት) ፡ አበለጥን ፣ የጌ
ታህም ፡ ጸጋ ፡ (ገነት) ፡ ከሚሰበስ
ቡት ፡ (ሃብት) ፡ በላጭ ፡ ናት ።

33 ሰዎችም ፡ (በክሕደት) ፡ አንድ ፡
ሕዝብ ፡ የሚኾኑ ፡ ባልነበሩ ፡
ኖሮ ፣ በአልረሕማን ፡ ለሚክዱት ፡
ሰዎች ፡ (በዚህች ፡ ዓለም) ፡ ለቤ
ቶቻቸው ፡ ከብር ፡ የኾኑን ፡ ጣራ
ዎች ፣ በነርሱ ፡ ላይ ፡ የሚወጡ
ባቸውንም ፡ (የብር) ፡ መሰላሎች ፣
ባደረግንላቸው ፡ ነበር ።

34 ለቤቶቻቸውም ፡ ደጃፎችን ፣ በነ
ርሱ ፡ ላይ ፡ የሚደገፉባቸውንም ፡
አልጋዎች ፣ (ከብር ፡ ባደረግን
ላቸው ፡ ነበር) ።

35 የወርቅ ፡ ጌጥንም ፡ (ባደረግንላ
ቸው ፡ ነበር) ፤ ይህም ፡ ሁሉ ፣
የቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡ መጣቀ
ሚያ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፤
(ጠፊ ፡ ነው) ፤ መጨረሻይቱም ፡
አገር ፡ በጌታህ ፡ ዘንድ ፡ ለጥን
ቁቆቹ ፡ ናት ።

36 ከአልረሕማን ፡ ግሣጼ ፡ (ከቁር
አን) ፡ የሚደናበርም ፡ ሰው ፣
ለርሱ ፡ ሰይጣንን ፡ እናስጠጋለን ፤
ስለዚህ ፡ እርሱ ፡ ለርሱ ፡ ቁራኛ ፡
ነው ።

37 እነሱም ፡ (ተደናባሪዎቹ) ፡ ተመ
ሪዎች ፡ መኾናቸውን ፡ የሚያስቡ፣
ሲኾኑ ፡ እነርሱ ፡ (ሰይጣናት) ፡
ከቀጥተኛው ፡ መንገድ ፡ በእር
ግጥ ፡ ያግዷቸዋል ።

38 (በትንሣኤ) ፡ ወደኛ ፡ በመጣም ፡
ጊዜ ፡ (ቁራኛዬ ፡ ሆይ !) በኔና ፡
ባንተ ፡ መካከል ፡ የምሥራቅና ፡
የምዕራብ ፡ ርቀት ፡ በኖረ ፡ ወይ ፡
ምኞቴ ! ምን ፡ የከፋህ ፡ ቁራኛ ፡
ነህ ፡ ይላል ።

1 ከመካ ፡ በወሊድ ፡ ላይ ፣ ወይም ፡ ከጧኢፍ፣
በዑርዋ ፡ ላይ ።

39 ስለ ፡ በደላችሁም ፡ ዛሬ ፡ እናንተ ፡ በቅጣት ፡ ተጋሪዎች ፡ መኾናችሁ ፡ አይጠቅማችሁም ፤ (ይባላሉ) ።

40 አንተ ፡ ደንቆሮዎችን ፡ ታሰማለህን ? ወይስ ፡ ዕውሮችንና ፡ በግልጽ ፡ ጥመት ፡ ውስጥ ፡ የኾኑን ፡ ሰዎች ፡ ትመራለህን ?

41 አንተንም ፡ (ቅጣታቸውን ፡ ሳታይ) ፡ ብንወስድህ ፡ እኛ ፡ ከነርሱ ፡ ተበቃዮች ፡ ነን ።

42 ወይም ፡ ያንን ፡ የቀጠርናቸውን ፡ ብናሳይህ ፡ እኛ ፡ በነርሱ ፡ (ቅጣት) ላይ ፡ ቻይዎች ፡ ነን ።

43 ያንንም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ የተወረደልህን ፡ አጥብቀህ ፡ ያዝ ፤ አንተ ፡ በቀጥተኛው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ነህና ።

44 እርሱም ፡ (ቁርአን) ፡ ለአንተ ፡ ለሕዝቦችሕም ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ፊትም ፡ (ከርሱ) ፡ ትጠየቃላችሁ ።

45 ከመልክተኞቻችንም ፡ ካንተ ፡ በፊት ፡ የላክናቸውን ፡ (ተከታዮቻቸውን) ፡ ከአልረሕማን ፡ ሌላ ፡ የሚገዙዋቸው ፡ የኾኑን ፡ አማልክት ፡ አድርገን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ጠይቃቸው ፤ (1)

46 ሙሳንም ፡ በታምራቶቻችን ፡ ወደ ፡ ፈርዖንና ፡ ወደ ፡ ሹማምንቶቹ ፡ በእርግጥ ፡ ላክን ፤ እኔ ፡ የዓለማት ፡ ጌታ ፡ መልክተኛ ፡ ነኝ ፡ አላቸውም ።

47 በታምራታችንም ፡ በመጣባቸው ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡ እነርሱ ፡ በርሷ ፡ ይስቃሉ ፤

1 ከአልረሕማን ፡ ሌላ ፡ አማልክትን ፡ እንዲያመልኩ ፡ ፈርደን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ጠይቃቸው ።

48 ከታምርም ፡ አንዲትንም ፡ አናሳያቸውም ፡ እርሷ ፡ ከብጤዋ ፡ በጣም ፡ የበለጠች ፡ ብትኾን ፡ እንጅ ፤ (ከክሕደታቸው) ፡ ይመለሱም ፡ ዘንድ ፡ በቅጣት ፡ ያዝናቸው ።

49 አንተ ፡ ድግምተኛ ፡ (ዐዋቂ) ፡ ሆይ ! ጌታህን ፡ አንተ ፡ ዘንድ ፡ ቃል ፡ በገባልህ ፡ ለኛ ፡ ለምንልን ፤ እኛ ፡ (ቅጣቱን ፡ ቢያነሳልን) ፡ ተመሪዎች ፡ ነን ፡ አሉም ።

50 ስቃዩን ፡ ከነሱ ፡ ላይ ፡ በገለጥንም ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡ ኪዳናቸውን ፡ ያፈርሳሉ ።

51 ፈርዖንም ፡ በሕዝቦቹ ፡ ውስጥ ፡ ተጣራ ፤ አለም ፤ ሕዝቦቼ ፡ ሆይ ! የምስር ፡ ግዛት ፡ የኔ ፡ አይደለምን ? እነዚህም ፡ ጅረቶች ፡ ከስሬ ፡ የሚፈሱ ፡ ሲኾኑ ፡ (የኔ ፡ አይደሉምን ?) አትመለከቱምን ?

52 በውነቱ ፡ እኔ ፡ ከዚህ ፡ ያ ፡ እርሱ ፡ ወራዳ ፡ ንግግሩንም ፡ ሊገልጽ ፡ የማይቀርብ ፡ ከኾነው ፡ በላጭ ፡ ነኝ ።

53 በርሱም ፡ ላይ ፡ የወርቅ ፡ አንባሮች ፡ ለምን ፡ አልተጣሉበትም ፤ ወይም ፡ መላእክት ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ተቆራኝተው ፡ ለምን ፡ አልመጡም ፤ (አለ) ።

54 ሕዝቦቹንም ፡ አቄላቸው ፤ ታዘዙትም ፤ እነርሱ ፡ አመጠኞች ፡ ሕዝቦች ፡ ነበሩና ።

55 ባስቆጡንም ፡ ጊዜ ፡ ከነሱ ፡ ተበቀልን ፤ ሁሉንም ፡ አሰጠምናቸውም ።

56 (በጥፋት) ፡ ቀዳሚዎችና ፡ ለኋለኞቹ ፡ (መቀጣጫ) ፡ ምሳሌም ፡ አደረግናቸው ።



57 የመርየም ፡ ልጅም ፡ ምሳሌ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቦችህ ፡ (ከሓዲዎቹ) ፡ ወዲያውኑ ፡ ከርሱ ፡ ይስቃሉ ።

58 አማልክቶቻችን ፡ ይበልጣሉን ? ወይስ ፡ እርሱ ፡ አሉም ፤ ለክርክርም ፡ እንጅ ፡ ላንተ ፡ እርሱን ፡ ምሳሌ ፡ አላደረጉትም ። በውነት ፡ እነርሱ ፡ ክርክረ ፡ ብርቱ ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ።

59 እርሱ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የለገስንለት ፡ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ታምር ፡ ያደረግነው ፡ የኾነ ፡ ባሪያ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ።

60 ብንሻም ፡ ኖሮ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ከናንተ ፡ ምትክ ፡ መላእክትን ፡ ባደረግን ፡ ነበር ።

61 እርሱም ፡ (ዒሳ) ፡ ለሰዓቲቱ ፡ (ማወቂያ) ፡ በእርግጥ ፡ ምልክት ፡ ነው ። በርሷም ፡ አትጠራጠሩ ። ተከተሉኝም ፤ ይህ ፡ ቀጥተኛ ፡ መንገድ ፡ ነው ፤ (በላቸው) ።

62 ሰይጣንም ፡ አያግዳችሁ ፤ እርሱ ፡ ለናንተ ፡ ግልጽ ፡ ጠላት ፡ ነውና ።

63 ዒሳ ፡ በታምራቶች ፡ በመጣ ፡ ጊዜም ፡ አላቸው ፡— በእርግጥ ፡ በጥበብ ፡ መጣኋችሁ ፤ የዚያንም ፡ በርሱ ፡ የምትለያዩበትን ፡ ከፊሉን ፡ ለናንተ ፡ ላብራራላችሁ ፡ (መጣሁ) ፤ አላህንም ፡ ፍሩ ፤ ታዘዙኝም ።

64 አላህ ፡ ጌታየ ፡ ጌታችሁም ፡ ነውና ፡ ተገዙት ፤ ይህ ፡ ቀጥተኛ ፡ መንገድ ፡ ነው ።

65 ከመካከላቸውም ፡ አሕዛቦቹ ፡ ተለያዩ ፤ ለነዚያም ፡ ለበደሉት ፡ ከአሳማሚ ፡ ቀን ፡ ቅጣት ፡ ወዮላቸው ።

66 ሰዓቲቱን ፡ እነሱ ፡ የማያውቁ ፡ ኾነው ፡ በድንገት ፡ ልትመጣባቸው ፡ እንጅ ፡ ይጠባበቃሉን ?

67 ወዳጆች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከፊላቸው ፡ ለከፊሉ ፡ ጠላት ፡ ነው ፤ አላህን ፡ ፈሪዎች ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ ፤

68 (ለነርሱስ) ፡— ባሮቼ ፡ ሆይ ! ዛሬ ፡ ቀን ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ፍርሃት ፡ የለባችሁም ፤ እናንተም ፡ የምታዝኑ ፡ አይደላችሁም ፡ (ይባላሉ) ።

69 እነዚያ ፡ በአንቀጾቻችን ፡ ያመኑና ፡ ፍጹም ፡ ታዛዦች ፡ የነበሩ ፡ (ባሮቼ ፡ ሆይ !)

70 ገነትን ፡ ግቡ ፤ እናንተም ፡ ሚስቶቻችሁም ፡ ትደሰታላችሁ ፤ ትከበሩም ፡ አላችሁ ፤ (ይባላሉ) ።

71 ከወርቅ ፡ የኾኑ ፡ ሰፋፊ ፡ ዝርግ ፡ ሳሕኖችና ፡ ኩባያዎች ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ይዝዞራሉ ፤ በርሷም ፡ ውስጥ ፡ ነፍሶች ፡ የሚከጅሉት ፡ ዓይኖችም ፡ የሚደሰቱበት ፡ ሁሉ ፡ አልለ ፤ እናንተም ፡ በውስጧ ፡ ዘላለም ፡ ዘውታሪዎች ፡ ናችሁ ።

72 ይህችም ፡ ያቺ ፡ ትሠሩት ፡ በነበራችሁት ፡ ዋጋ ፡ የተሰጣችኋት ፡ ገነት ፡ ናት ።

73 ለናንተ ፡ በውስጧ ፡ ብዙ ፡ ፍራፍሬዎች ፡ አሏችሁ ፤ ከርሷ ፡ ትበላላችሁ ።

74 አመጠኞች ፡ በገሀነም ፡ ስቃይ ፡ ውስጥ ፡ በእርግጥ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ናቸው ።

75 ከነሱ ፡ (ቅጣቱ) ፡ አይቀለልላቸውም ፤ እነርሱም ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ተስፋ ፡ ቆራጮች ፡ ናቸው ።

76 አልበደልናቸውምም ፤ ግን ፡ በዳዮቹ ፡ እነርሱው ፡ ነበሩ ።

77 ማሊክ ፡ ሆይ ! (1) ጌታህ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ (በሞት) ፡ ይፍረድ ፡ (2) እያሉ ፡ ይጣራሉም ፤ እናንተ ፡ (በቅጣቱ ፡ ውስጥ) ፡ ዘላለም ፡ ነዋሪዎች ፡ ናችሁ ፡ ይላቸዋል ።

78 እውነተኛውን ፡ መንገድ ፡ በእርግጥ ፡ አመጣንላችሁ ፤ ግን ፡ አብዛኞቻችሁ ፡ እውነቱን ፡ ጠይዎች ፡ ናችሁ ።

79 ይልቁንም ፡ (በነቢዩ ፡ ላይ ፡ በማደም) ፡ ነገርን ፡ አጠነከሩን ? እኛም ፡ (ተንኮላቸውን ፡ ወደነርሱ ፡ በመመለስ) ፡ አጠንካሪዎች ፡ ነን ።

80 ወይም ፡ እኛ ፡ ምስጢራቸውንና ፡ ውይይታቸውን ፡ የማንሰማ ፡ መኾናችንን ፡ ያስባሉን ? አይደለም ፤ መልክተኞቻችንም ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ ይጽፋሉ ።

81 ፡—ለአልረሕማን ፡ ልጅ ፡ (የለውም ፡ እንጅ) ፡ ቢኖረው ፡ እኔ ፡ (ለልጁ) ፡ የተገዢዎቹ ፡ መጀመሪያ ፡ ነኝ ፡ በላቸው ።

82 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ጌታ ፡ የዙፋኑ ፡ ጌታ ፡ ከሚሉት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጠራ ።

83 ተዋቸውም ፤ ያንን ፡ ይስፈራሩበት ፡ የነበሩትን ፡ ቀናቸውን ፡ እስከሚገናኙ ፡ ድረስ ፡ (በስሕተታቸው ፡ ውስጥ) ፡ ይዋኙ ፡ ይጫዎቱም ።

84 እርሱም ፡ ያ ፡ በሰማይ ፡ ውስጥ ፡ ሊገዙት ፡ የሚገባው ፡ በምድርም ፡ ውስጥ ፡ ሊገዙት ፡ የሚገባው ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ ብልሃተኛው ፡ ዐዋቂው ፡ ነው ።

85 ያም ፡ የሰማያትና ፡ የምድር ፡ በመካከላቸውም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ንግሥና ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ የኾነው ፡ አምላክ ፡ ላቀ ። የሰዓቲቱም ፡ (የመምጫዋ ፡ ዘመን) ፡ ዕውቀት ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ወደርሱም ፡ ትመለሳላችሁ ።

86 እነዚያም ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የሚግገዟቸው ፡ እነሱ ፡ የሚያውቁ ፡ ኾነው ፡ በውነት ፡ ከመሰከሩት ፡ በስተቀር ፡ ምልጃን ፡ አይችሉም ።

87 ማን ፡ እንደ ፡ ፈጠራቸውም ፡ ብትጠይቃቸው ፡ በእርግጥ ፡ አላህ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ታዲያ ፡ (ከእምነት) ፡ ወዴት ፡ ይዞራሉ ።

88 (ነቢዩ) ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ! እነዚህ ፡ የማያምኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ፡ የማለቱም ፡ (ዕውቀት ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡ ነው) ።

89 እነርሱንም ፡ ተዋቸው ፤ ነገሬ ፡ ሰላም ፡ ነው ፡ በልም ፤ ወደፊትም ፡ (የሚመጣባቸውን) ፡ ያውቃሉ ።

---

1 የገሀነም ፡ መልአክ ፡ ስም ፡ ነው ።

2 እንሙትና ፡ ከስቃዩ ፡ እንድናርፍ ፡ ይላሉ ።



44ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ዱኻን ፡ (የጭስ ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፡ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 59 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው።

1 ሐ. መ. (ሓ ፡ ሚም) ።

2 አብራሪ ፡ በኾነው ፡ መጽሐፍ ፡ እንምላለን ።

3 እኛ ፡ (ቁርአኑን) ፡ በተባረከች ፡ ሌሊት ፡ ውስጥ ፡ አወረድነው ፤ እኛ ፡ አስፈራሪዎች ፡ ነበርንና ።

4 በውስጧ ፡ የተወሰነው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይለያል ።

5 ከኛ ፡ ዘንድ ፡ የኾነ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲኾን ፡ (አወረድነው) ፤ እኛ ፡ (መልክተኞችን) ፡ ላኪዎች ፡ ነበርን ።

6 ከጌታህ ፡ በኾነው ፡ ችሮታ ፡ (ተላኩ) ፡ እነሆ ፡ እርሱ ፡ ሰሚው ፡ ዐዋቂው ፡ ነውና ።

7 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ በመካከላቸውም ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ ከኾነው ፡ (ተላኩ) ፤ የምታረጋግጡ ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ (ነገሩ ፡ እንዳልነው ፡ መኾኑን ፡ ዕወቁ) ።

8 ከርሱ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ ሕያው ፡ ያደርጋል ፤ ያሞታልም ፤ ጌታችሁ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ አባቶቻችሁም ፡ ጌታ ፡ ነው ።

9 በውነቱ ፡ እነሱ ፡ የሚጫወቱ ፡ ሲኾኑ ፡ በመጠራጠር ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።

10 ሰማይም ፡ በግልጽ ፡ ጭስ ፡ የምትመጣበትን ፡ ቀን ፡ ተጠባበቅ ።

11 ሰዎችን ፡ የሚሸፍን ፡ (በኾነ ፡ ጭስ) ፡ ይህ ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ ነው ።

12 ጌታችን ፡ ሆይ ! ከኛ ፡ ላይ ፡ ቅጣቱን ፡ ግለጥልን ፤ እኛ ፡ አማኞች፡ እንኾናለንና ፡ (ይላሉም) ።

13 (ቅጣቱ ፡ በወረደ ፡ ጊዜ) ፡ ለነርሱ ፡ መገሠጽ ፡ እንዴት ፡ ይኖራቸዋል ፤ አስረጅ ፡ መልክተኛ ፡ የመጣቸው ፡ ሲኾን ፡ (የካዱም ፡ ሲኾኑ) ።

14 ከዚያም ፡ ከርሱ ፡ የዞሩ ፤ (ከሰው) ፡ የተስተማረ ፡ ዕብድ ፡ ነው ፡ ያሉም ፡ ሲኾኑ ።

15 እኛ ፡ ቅጣቱን ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ገላጮች ፡ ነን ፤ እናንተ ፡ (ወደ ፡ ክሕደታችሁ) ፡ በእርግጥ ፡ ተመላሾች ፡ ናችሁ ።

16 ታላቂቱን ፡ ብርቱ ፡ አያያዝ ፡ በምንይዝበት ፡ ቀን ፤ እኛ ፡ ተበቃዮች ፡ ነን ።

17 ከነርሱም ፡ በፊት ፡ የፈርዖንን ፡ ሕዝቦች ፡ በእርግጥ ፡ ሞከርን ፤ ክቡር ፡ መልክተኛም ፡ መጣላቸው ።

18 የአላህን ፡ ባሮች ፡ ወደኔ ፡ አድርሱ ፤ እኔ ፡ ለናንተ ፡ ታማኝ ፡ መልክተኛ ፡ ነኝና ።

19 በአላህም ፡ ላይ ፡ አትኩሩ ፤ እኔ ፡ ግልጽ ፡ የኾነን ፡ አስረጅ ፡ ያመጣሁላችሁ ፡ ነኝና ፡ (በማለት ፡ መጣላቸው) ።

20 እኔም ፡ እንዳትወግሩኝ ፡ በጌታዬና ፡ በጌታችሁ ፡ ተጠብቂያለሁ ።

21 በኔም ፡ ባታምኑ ፡ ራቁኝ ፤ (ተውኝ አለ) ።

22 ቀጥሎም ፡ (ስለ ፡ ዛቱበት) ፡ እነዚህ ፡ አመጠኞች ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ፤ (አጥፋቸው) ፡ ሲል ፡ ጌታውን ፡ ለመነ ።

23 (ጌታው) ፡ ባሮቼንም ፡ ይዘህ ፡ በሌሊት ፡ ኺድ ፤ እናንተ ፡ የሚከተሉዋችሁ ፡ ናችሁና ።

24 ባሕሩንም ፡ የተከፈተ ፡ ኾኖ ፡ ተወው ፤ እነርሱ ፡ የሚሰጥጠሙ ፡ ሰራዊት ፡ ናቸውና ፡ (አለው) ።

25 ከአትክልቶችና ፡ ከምንጮችም ፡ ብዙ ፡ ነገሮችን ፡ ተዉ ።

26 ከአዝመራዎችም ፡ ከመልካም ፡ መቀመጫም ።

27 በርሷ ፡ ተደሳቾች ፡ ከነበሩባትም ፡ ድሎት ፡ (ብዙን ፡ ነገር ፡ ተዉ) ።

28 (ነገሩ) ፡ እንደዚሁ ፡ ኾነ ፤ ሌሎችንም ፡ ሕዝቦች ፡ አወረስናት ።

29 ሰማይና ፡ ምድርም ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ አላለቀሱም ፤ የሚቆዩም ፡ አልነበሩም ።

30 የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ አዋራጅ ፡ ከኾነ ፡ ስቃይ ፡ በእርግጥ ፡ አዳንናቸው ።

31 ከፈርዖን ፤ እርሱ ፡ የኮራ ፡ ከወሰን ፡ አላፊዎቹ ፡ ነበርና ።

32 ከማወቅም ፡ ጋር ፡ በዓለማት ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡ መረጥናቸው ።

33 ከታምራቶችም ፡ በውስጡ ፡ ግልጽ ፡ የኾነ ፡ ፈተና ፡ ያለበትን ፡ ሰጠናቸው ።

34 እነዚህ ፡ (የመካ ፡ ከሓዲዎች) ፡ በእርግጥ ፡ ይላሉ ፡—

35 እርሷ ፡ የፊተኛይቱ ፡ ሞታችን ፡ እንጅ ፡ አይደለችም ፤ እኛም ፡ የምንቀሰቀስ ፡ አይደለንም ።

36 እውነተኞችም ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ አባቶቻችንን ፡ አምጡልን ።

37 እነርሱ ፡ በላጮች ፡ ናቸውን ? ወይስ ፡ የቱብበዕ ፡ ሕዝቦችና ። እነዚያ ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ? አጠፋናቸው ፤ እነሱ ፡ አመጠኞች ፡ ነበሩና ።

38 ሰማያትንና ፡ ምድርንም ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ ቀላጆች ፡ ኾነን ፡ አልፈጠርንም ።

39 ሁለቱንም ፡ በምር ፡ እንጅ ፡ አልፈጠርናቸውም ፤ ግን ፡ አብዛኞቻቸው ፡ አያውቁም ።

40 የመለያው ፡ ቀን ፡ ለሁሉም ፡ ቀጠሯቸው ፡ ነው ።

41 ዘመድ ፡ ከዘመዱ ፡ ምንንም ፡ የማይጠቅምበት ፡ እነሱም ፡ የማይረዱበት ፡ ቀን ፡ ነው ።

42 አላህ ፡ ያዘነለት ፡ ሰውና ፡ ያመነ ፡ ብቻ ፡ ሲቀር ፤ (እርሱስ ፡ ይረዳል) ፤ እርሱ ፡ አሸናፊው ፡ አዛኙ ፡ ነውና ።

43 የዘቁም ፡ ዛፍ ፡ (1)

44 የኀጢአተኛው ፡ ምግብ ፡ ነው ።

45 እንደ ፡ ዘይት ፡ አተላ ፡ ነው ፤ በሆዶች ፡ ውስጥ ፡ የሚፈላ ፡ ሲኾን ።

46 እንደ ፡ ገነፈለ ፡ ውሃ ፡ አፈላል ፡ (የሚፈላ ፡ ሲኾን) ።

47 ያዙት ፤ ወደ ፡ ገሀነም ፡ መካከልም ፡ በኀይል ፡ ጉትቱት ።

---

1 በገሀነም ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ዛፍ ፡ ስም ፡ ነው ።



48 ከዚያም ፡ ከራሱ ፡ በላይ ፡ ከፈላ ፡ ውሃ ፡ ስቃይ ፡ አንቧቡበት ።

49 ቅመስ ፤ አንተ ፡ አሸናፊው ፡ ክቡሩ ፡ (፩) ነህና ፡ (ይባላል) ።

50 ይህ ፡ ያ ፡ በርሱ ፡ ትጠራጠሩበት ፡ የነበራችሁት ፡ ነው ፤ (ይባላሉ) ።

51 ጥንቁቆቹ ፡ በእርግጥ ፡ በጸጥተኛ ፡ መኖሪያ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።

52 በአትክልቶችና ፡ በምንጮች ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።

53 ፊት ፡ ለፊት ፡ የተቅጣጩ ፡ ኾነው ከስስ ፡ ሐርና ፡ ከወፍራም ፡ ሐር ፡ ይለብሳሉ ።

54 (ነገሩ) ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፤ ዓይናሞች ፡ የኾኑን ፡ ነጫጭ ፡ ሴቶችም ፡ እናጠናዳቸዋለን ።

55 በርሷም ፡ ውስጥ ፡ የተማመኑ ፡ ኾነው ፡ ከፍራፍሬ ፡ ሁሉ ፡ ያዛሉ ።

56 የፊተኛይቱን ፡ ሞት ፡ እንጅ ፡ (ዳግመኛ) ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ሞትን አይቀምሱም ፤ የገሀነምንም ፡ ቅጣት ፡ (አላህ) ፡ ጠበቃቸው ።

57 ከጌታህ ፡ በኾነ ፡ ችሮታ ፡ (ጠበቃቸው) ፤ ይህ ፡ እርሱ ፡ ታላቅ ፡ ዕድል ፡ ነው ።

58 (ቁርአኑን) ፡ በቋንቋህም ፡ ያገራነው ፡ (ሕዝቦችህ) ፡ ይገነዘቡ ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

59 ተጠባበቅም ፡ እነርሱ ፡ ተጠባባቂዎች ፡ ናቸውና ።

---

1 ይህን ፡ የሚባለው ፡ ለቅጥጥብ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 45 ፡ አል-ጃሢያህ ። ክፍል ፡ 25 ።

45ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ጃሢያህ ፡ (የተንበርካኪ ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 37 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው።

1 ሐ. መ. (ሓ ፡ ሚም) ።

2 የመጽሐፉ ፡ መወረድ ፡ አሸናፊ ፡ ጥበበኛ ፡ ከኾነው ፡ አላህ ፡ ነው ።

3 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ለምእምናን ፡ ሁሉ ፡ (ለችሎታው) ፡ እርግጠኛ ፡ ምልክቶች ፡ አልሉ ።

4 እናንተንም ፡ በመፍጠር ፡ ከተንቀሳቃሽም ፡ (በምድር ፡ ላይ) ፡ የሚበትነውን ፡ ሁሉ ፡ (በመፍጠሩ) ፡ ለሚያረጋግጡ ፡ ሕዝቦች ፡ ታምራቶች ፡ አልሉ ።

5 በሌሊትና ፡ መዓልት ፡ መተካከትም ፡ ከሲሳይም ፡ (ከዝናም) ፡ አላህ ፡ ከሰማይ ፡ ባወረደው ፡ በርሱም ፡ ምድርን ፡ ከሞተች ፡ በኋላ ፡ ሕያው ፡ በማድረጉ ፡ ነፋሶችንም ፡ (በያቅጣጫቸው) ፡ በማዘዋወሩ ፡ ለሚያውቁ ፡ ሕዝቦች ፡ ማስረጃዎች ፡ አልሉ ።

6 እነዚህ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ በውነት ፡ የምናነባቸው ፡ ሲኾኑ ፡ የአላህ ፡

ማስረጃዎች ፡ ናቸው ፣ ከአላህና ፡
ከማስረጃዎቹም ፡ ወዲያ ፡ በየት
ኛው ፡ ንግግር ፡ ያምናሉ ?
7 ውሸታም ፡ ኀጢአተኛ ፡ ለኾነ ፡
ሁሉ ፡ ወዮለት ። (ጥፋት ፡ ተገ
ባው) ።
8 የአላህን ፡ አንቀጾች ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
የሚነበቡለት ፡ ሲኾኑ ፡ ይሰማል ፣
ከዚያም ፡ የኩራ ፡ ሲኾን ፡ እንዳል
ሰማት ፡ ኾኖ ፡ (በክሕደቱ ፡ ላይ) ፡
ይዘወትራል ፣ በአሳማሚም ፡ ቅ
ጣት ፡ አብስረው ።
9 ከአንቀጾቻችንም ፡ አንዳችን ፡
ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ መሳለቂያ ፡ አድ
ርጎ ፡ ይይዛታል ፣ እነዚያ ፡ ለነ
ርሱ ፡ አዋራጅ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው።
10 ከፊታቸውም ፡ ገሀነም ፡ አለች ፣
የሰበሰቡትም ፡ ሀብት ፡ ከነርሱ ፡
ላይ ፡ ምንንም ፡ አይመልስላቸ
ውም ፣ ከአላህ ፡ ሌላም ፡ ረዳቶች ፡
አድርገው ፡ የያዙዋቸው ፡ (አይጠ
ቅሟቸውም) ፣ ለነርሱም ፡ ታላቅ ፡
ቅጣት ፡ አላቸው ።
11 ይህ ፡ (ቁርአን) ፡ መሪ ፡ ነው ፣
እነዚያም ፡ በጌታቸው ፡ አንቀ
ጾች ፡ የካዱት ፡ ለነሱ ፡ ከብርቱ ፡
ቅጣት ፡ የኾነ ፡ አሳማሚ ፡ ስቃይ ፡
አላቸው።
12 አላህ ፡ ያ ፡ ባሕርን ፡ በውስጡ ፡
ታንኳዎች ፡ በፈቃዱ ፡ እንዲን
ሻለሉበት ፡ ከችሮታውም ፡ እንድ
ትፈልጉበት ፡ እንድታመሰግኑት
ም ፡ ለናንተ ፡ የገራላችሁ ፡ ነው ።
13 ለናንተም ፡ በሰማያት ፡ ያለው
ንና ፡ በምድርም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡
በመላ ፡ ከርሱ ፡ ሲኾን ፡ የገራላ
ችሁ ፡ ነው ፣ በዚህ ፡ ለሚያስተን
ኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ታምራት ፡ አለበት ።
14 ለነዚያ ፡ ለአመኑት ፡ ሰዎች ፡
(ምሕረት ፡ አድርጉ) ፡ በላቸው ፣
ለነዚያ ፡ የአላህን ፡ ቀኖች ፡ ለማ
ይፈሩት ፡ ይምራሉና ፡ ሕዝቦችን ፡
ይሠሩት ፡ በነበሩት ፡ ነገር ፡ ይመ
ነዳ ፡ ዘንድ ፡ (ምሕረት ፡ አድርጉ ፡
በላቸው) ።
15 መልካምን ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ለነ
ፍሱ ፡ ነው ፣ ያከፋም ፡ ሰው ፡
በርሷ ፡ ላይ ፡ ነው ፣ ከዚያም ፡
ወደ ፡ ጌታችሁ ፡ ትመለሳላችሁ ።
16 ለእስራኤል ፡ ልጆችም ፡ መጽሐ
ፍንና ፡ ሕግን ፡ ነቢይነትንም ፡
በእርግጥ ፡ ሰጠናቸው ፣ ከመል
ካም ፡ ሲሳዮችም ፡ ለገስንላቸው ፡
በዓለማት ፡ ላይም ፡ አበለጥና
ቸው ።
17 ከትእዛዝም ፡ ግልጾችን ፡ ሰጠና
ቸው ፣ ዕውቀቱም ፡ ከመጣላቸው ፡
በኋላ ፡ በመካከላቸው ፡ ለምቀኛ
ነት ፡ እንጅ ፡ ለሌላ ፡ አልተለያ
ዩም ፣ ጌታህ ፡ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡
በዚያ ፡ በርሱ ፡ ይለያዩበት ፡ በነ
በሩት ፡ ነገር ፡ በመካከላቸው ፡ በእ
ርግጥ ፡ ይፈርዳል ።
18 ከዚያም ፡ ከነገሩ ፡ (ከሃይማኖት) ፡
በትክክለኛይቱ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡
አደረግንህ ፣ ስለዚህ ፡ ተከተላት ፣
የነዚያንም ፡ የማያውቁትን ፡ ሕዝ
ቦች ፡ ዝንባሌዎች ፡ አትከተል ።
19 እነርሱ ፡ ከአላህ ፡ (ቅጣት) ፡ ምን
ንም ፡ ከአንተ ፡ አይገፈትሩልህ
ምና ፣ በደለኞችም ፡ ከፊላቸው ፡
የከፊሉ ፡ ረዳቶች ፡ ናቸው ፣ አላ
ህም ፡ የጥንቁቆቹ ፡ ረዳት ፡ ነው ።
20 ይህ ፡ (ቁርአን) ፡ ለሰዎች ፡ የልብ ፡
ብርሃኖች ፡ ነው ። ለሚያረጋግ
ጡም ፡ ሕዝቦች ፡ መሪና ፡ እዝነት ፡
ነው ።



21 እነዚያ ፡ ኀጢአቶችን ፡ የሠሩ ፡
ሕይወታቸውም ፡ሞታቸውም ፡
ትክክል ፡ ሲኾን ፡ እንደነዚያ ፡
እንደ ፡ አመኑትና ፡ መልካሞችን ፡
እንደሠሩት ፡ ልናደርጋቸው ፡
ይጠረጥራሉን ? (አይጠርጥሩ) ፣
የሚፈርዱት ፡ ምንኛ ፡ ከፋ !
22 አላህም ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡
(ለችሎታው ፡ እንዲያመለክትባ
ቸውና) ፡ ነፍስም ፡ ሁሉ ፡ በሠ
ራችው ፡ ሥራ ፡ ትመነዳ ፡ ዘንድ ፡
በትክክል ፡ ፈጠረ ፣ እነሱም ፡
አይበደሉም ።
23 ዝንባሌውን ፡ አምላኩ ፡ አድርጎ ፡
የያዘውን ፡ አላህም ፡ ከዕውቀት ፡
ጋር ፡ ያጠመመውን ፡ በጆሮውና ፡
በልቡ ፡ ላይም ፡ ያተመበትን ፡
በዓይኑም ፡ ላይ ፡ ሺፋን ፡ ያደረገ
በትን ፡ ሰው ፡ አየህን ! ታዲያ ፡
ከአላህ ፡ ኋላ ፡ የሚያቀናው ፡
ማነው ? አትገሠጹምን ?
24 እርሷም ፡ (ሕይወት) ፡ የቅርቢቱ ፡
ሕይወታችን ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደ
ለችም ፣ እንሞታለን ፣ ሕያውም ፡
እንኾናለን፣ [1] ከጊዜም ፡ (ማለፍ) ፡
በስተቀር ፡ ሌላ ፡ አያጠፋንም ፡
አሉ ፣ ለነርሱም ፡ በዚህ ፡ (በሚ
ሉት) ፡ ምንም ፡ ዕውቀት ፡ የላ
ቸውም ፣ እነርሱ ፡ የሚጠራጠሩ ፡
እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደሉም ።
25 አንቀጾቻችንም ፡ ግልጾች ፡ ኾነው ፡
በነሱ ፡ ላይ ፡ በተነበቡላቸው ፡
ጊዜ ፡ ክርክራቸው ፡ እውነተኞች ፡
እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ አባቶቻችንን ፡
አምጡ ፡ ማለት ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡
አልነበረም ።

1 ከፊላችን ፡ ሲሞት ፡ ከፊላችን ፡ ሕያው ፡
ይሆናል ፡ ይተካል ።

26 ፡—አላህ ፡ ሕያው ፡ ያደርጋች
ኋል ፣ ከዚያም ፡ ያሞታችኋል ፣
ከዚያም ፡ ወደ ፡ ትንሣኤ ፡ ቀን ፡
ይሰበስባችኋል ፣ በርሱ ፡ ጥርጥር ፡
የለበትም ፣ ግን ፡ አብዛኞዎቹ ፡
ሰዎች ፡ አያውቁም ፡ በላቸው ።
27 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ግዛት ፡
የአላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፣ ሰዓቲቱም ፡
በምትቆምበት ፡ ቀን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡
አጥፊዎች ፡ ሁሉ ፡ ይከስራሉ ።
28 ሕዝብንም ፡ ሁሉ ፡ ተንበርካኪ ፡
ኾና ፡ ታያታለህ ፣ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡
ወደ ፡ መጽሐፏ ፡ ትጠራለች ፣
ዛሬ ፡ ትሠሩት ፡ የነበራችሁትን ፡
ነገር ፡ ትመነዳላችሁ ፡ (ይባላሉ) ።
29 ይህ ፡ መጽሐፋችን ፡ ነው ፣ በና
ንተ ፡ ላይ ፡ በውነት ፡ ይናገራል ፣
እኛ ፡ ያንን ፡ ትሠሩት ፡ የነበራች
ሁትን ፡ እናስገለብጥ ፡ ነበርን ፡
(ይባላሉ) ።
30 እነዚያ ፡ ያመኑትና ፡ መልካም
ችን ፡ የሠሩትማ ፡ ጌታቸው ፡ በእ
ዝነቱ ፡ ውስጥ ፡ ያገባቸዋል ፣
ይህ ፡ እርሱ ፡ ግልጽ ፡ የኾነ ፡ ማግ
ኘት ፡ ነው ።
31 እነዚያም ፡ የካዱትማ ፡ (ለነርሱ ፡
ይባላሉ) ፡— አንቀጾቼ ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ ይነበቡ ፡ አልነበሩምን ?
ኮራችሁም ፣ ከሓዲዎች ፡ ሕዝቦ
ችም ፡ ነበራችሁ ።
32 የአላህ ፡ ቀጠሮ ፡ እውነት ፡ ነው ፣
ሰዓቲቱም ፡ በርሷ ፡ (መምጣት) ፡
ጥርጥር ፡ የለም ፣ በተባለ ፡ ጊዜም ፡
ሰዓቲቱ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡
አናውቅም ፣ መጠራጠርን ፡ የምን
ጠራጠር ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለ
ንም ፣ እኛም ፡ አረጋጋጮች ፡ አይ
ደለንም ፡ አላችሁ ።

33 የሠሩዋቸውም ፡ ኀጢአቶች ፡
ለነርሱ ፡ ይገለጹላቸዋል ፤ ያም ፡
በርሱ ፡ ይሳለቁበት ፡ የነበሩት ፡
ቅጣት ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ይወርድ
ባቸዋል ።
34 ይህንንም ፡ ቀናችሁን ፡ መገና
ኘትን ፡ እንደ ፡ ረሳችሁ ፡ ዛሬ ፡
እንረሳችኋለን ፤ (እንተዋችኋለን) ፤
መኖሪያችሁም ፡ እሳት ፡ ናት ፤
ለናንተም ፡ ከረዳቶች ፡ ምንም ፡
የላችሁም ፡ ይባላል ።
35 ይህችሁ ፡ እናንተ ፡ የአላህን ፡ አን
ቀጾች ፡ መቀለጃ ፡ አድርጋችሁ ፡
በመያዛችሁና ፡ ቅርቢቱም ፡ ሕይ
ወት ፡ ስለ ፡ አታለለቻችሁ ፡ ነው ፡
(ይባላሉ) ። ዛሬ ፡ ከርሷ ፡ አይወ
ጥጡም ፤ እነሱም ፡ በወቀሳ ፡
አይታለፉም ።
36 ምስጋናም ፡ ለአላህ ፡ ለሰማያት ፡
ጌታ ፡ ለምድርም ፡ ጌታ ፡ ለዓለ
ማት ፡ ጌታ ፡ የተገባው ፡ ነው ።
37 ኩራትም ፡ በሰማያትም ፡ በምድ
ርም ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ እር
ሱም ፡ አሸናፊው ፡ ጥበበኛው ፡
ነው ።

ምዕራፍ ፡ 46 አል-አሕቃፍ ። ክፍል ፡ 26 ።

★ ★ ★

46ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-አሕቃፍ ፡ (የአሸዋዎች ፡ ምዕራፍ) ። በመ
ካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 35 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 ሐ. መ. (ሓ ፡ ሚም) ።
2 የመጽሐፉ ፡ መወረድ ፡ አሸናፊ ፡
ጥበበኛ ፡ ከኾነው ፡ አላህ ፡ ነው ።
3 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ በመካከ
ላቸው ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ በም
ርና ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜንም ፡ በመለ
ካት ፡ እንጅ ፡ (ለቀልድ) ፡ አልፈ
ጠርናቸውም ። እነዚያ ፡ የካዱ
ትም ፡ ከተስፈራሩት ፡ ነገር ፡
(ትተው) ፡ ዘዋሪዎች ፡ ናቸው ።
4 ከአላህ ፡ ሌላ ፡ የምትግገዟቸውን ፡
አያችሁን ? ከምድር ፡ ምንን ፡
እንደ ፡ ፈጠሩ ፡ አሳዩኝ ፤ ወይም ፡
በሰማያት ፡ ለነሱ ፡ (ከአላህ ፡ ጋር) ፡
መጋራት ፡ አላቸውን ? (ያማልዱ
ናል ፡ በማለታችሁ) ፡ እውነተ
ኞች ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ ከዚህ ፡
(ቁርአን) ፡ በፊት ፡ የኾነን ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ወይም ፡ ከዕውቀት ፡ የኾነ ፡
ቅርስን ፡ አምጡልኝ ፡ በላቸው ።
5 እስከ ፡ ትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ድረስም ፡
ለርሱ ፡ የማይመልስለትን ፡ (ጣ
ዖት) ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ከሚጠራ ፡
ሰው ፡ ይበልጥ ፡ የተሳሳተ ፡
ማነው ? እነርሱም ፡ ከጥሪያቸው ፡
ዘንጊዎች ፡ ናቸው ።



6 ሰዎችም ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡
(ጣዖቶቹ) ፡ ለነርሱ ፡ ጠላቶች ፡
ይኾናሉ ፤ (እነሱን) ፡ መገዛታቸ
ውንም ፡ ከሓዲዎች ፡ ይኾናሉ ።
7 በነሱም ፡ ላይ ፡ አንቀጾቻችን ፡
ግልጾች ፡ ኾነው ፡ በተነበቡ ፡ ጊዜ ፡
እነዚያ ፡ እውነቱን ፡ በመጣላቸው
ጊዜ ፡ የካዱት ፡ ይህ ፡ ግልጽ ፡ ድግ
ምት ፡ ነው ፡ አሉ ።
8 ይልቁንም ፡ ቀጠፈው ፡ ይላሉን ?
ብቀጥፈው ፡ ለኔ ፡ ከአላህ ፡ (ቅጣት
ለማዳን) ፡ ምንንም ፡ አትችሉም ፤
እርሱ ፡ ያንን ፡ በርሱ ፡ የምትቀ
ባጅሩበትን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፤ በኔና ፡
በናንተ ፡ መካከል ፡ መስካሪ ፡
በርሱ ፡ በቃ ። እርሱም ፡ መሓሪው ፡
አዛኙ ፡ ነው ፡ በላቸው ።
9 ከመልክተኞች ፡ ብጤ ፡ የሌለኝ ፡
አይደለሁም ፤ በኔም ፡ በናንተም ፡
ምን ፡ እንደሚሠራም ፡ አላው
ቅም ፤ ወደኔ ፡ የሚወረደውን ፡
እንጅ ፡ ሌላን ፡ አልከተልም ፤
እኔም ፡ ግልጽ ፡ አስፈራሪ ፡ እንጅ ፡
ሌላ ፡ አይደለሁም ፡ በላቸው ።
10 (ሙሐመድ ፡ ሆይ !) በላቸው ፡—
እስቲ ፡ ንገሩኝ ፤ (ቁርአኑ) ፡ ከአ
ላህ ፡ ዘንድ ፡ ቢኾን ፤ በርሱም ፡
ብትክዱ ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆችም ፡
መስካሪ ፡ በብጤው ፡ (በርሱ) ፡
ላይ ፡ ቢመሰክር ፤ ቢያምንም ፤
(ከእምነት) ፡ ብትኮሩም ፤ (በዳይ ፡
አትኾኑምን ?) አላህ ፡ በእርግጥ ፡
በደለኞችን ፡ ሕዝቦች ፡ አያቀ
ናም ።
11 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡
ስለነዚያ ፡ ስለ ፡ አመኑት ፡ ሰዎች ፡
(እምነቱ) ፡ መልካም ፡ ነገር ፡
በኾነ ፡ ኖሮ ፡ ወደርሱ ፡ ባልቀደ
ሙን ፡ ነበር ፡ አሉ ፤ በርሱም ፡
ባልተመሩ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ (ቁር
አን) ፡ ጥንታዊ ፡ ቅጥፈት ፡ ነው ፡
ይላሉ ።
12 ከበፊቱም ፡ የሙሳ ፡ መጽሐፍ ፡
መሪና ፡ ጸጋ ፡ ሲኾን ፡ አልለ ፤
ይህም ፡ እነዚያን ፡ የበደሉትን ፡
ሊያስፈራራ ፡ በዐረብኛ ፡ ቋንቋ
ሲኾን ፡ (የፊቶቹን ፡ መጻሕፍት) ፡
አረጋጋጭ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፤
ለበጎ ፡ አድራጊዎችም ፡ ብስ
ራት ፡ ነው ።
13 እነዚያ ፡— ጌታችን ፡ አላህ ፡
ነው ፡ ያሉ ፡ ከዚያም ፡ ቀጥ ፡ ያሉ ፡
በነርሱ ፡ ላይ ፡ ፍርሃት ፡ የለባቸ
ውም ። እነሱም ፡ አያዝኑም ።
14 እነዚያ ፡ የገነት ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ፤
በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ዘውታሪዎች ፡
ሲኾኑ ፤ በዚያ ፡ ይሠሩት ፡ በነበ
ሩት ፡ ምክንያት ፡ ታላቅን ፡ ምንዳ ፡
(ይመነዳሉ) ።
15 ሰውንም ፡ በወላጆቹ ፡ በጎ ፡ መዋ
ልን ፡ በጥብቅ ፡ አዘዝነው ፤ እናቱ ፡
በችግር ፡ ላይ ፡ ኾና ፡ አረገዘችው ፤
በችግርም ፡ ወለደችው ፤ እርግዝ
ናውና ፡ ከጡት ፡ መለያውም ፡
ሠላሳ ፡ ወር ፡ ነው ። ጥንካሬው
ንም ፡ ወቅት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡
(ከዚያ ፡ አልፎ) ፡ አርባ ፡ ዓመት
ንም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ጌታዬ ፡
ሆይ ! ያችን ፡ በኔ ፡ ላይና ፡ በወ
ላጆቼ ፡ ላይ ፡ የለገስካትን ፡ ጸጋ
ህን ፡ እንዳመሰግን ፡ የምትወደው
ንም ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ እንድ
ሠራ ፡ ምራኝ ፤ ዘሮቼንም ፡ ለኔ ፡
አብጅልኝ ፤ እኔ ፡ ወዳንተ ፡ ተመ
ለስኩ ፤ እኔም ፡ ከሙስሊሞች ፡
ነኝ ፡ አለ ። (1)

1 ይህ ፡ ስለ ፡ አቡ ፡ በክር ፡ የተነገረ ፡ ነው ፡
ይባላል ።

16 እነዚህ ፡ (ይህንን ፡ ባዮች) ፡ በገ
ነት ፡ ጓዶች ፡ ውስጥ ፡ ሲኾኑ ፡
እነዚያ ፡ ከሠሩት ፡ ሥራ ፡ መልካ
ሙን ፡ ከነሱ ፡ የምንቀበላቸውና ፡
ከኀጢአቶቻቸውም ፡ የምናልፋ
ቸው ፡ ናቸው ። ያንን ፡ ተስፋ ፡
ይስሰጡት ፡ የነበሩትን ፡ እውነተኛ ፡
ቀጠሮ ፡ (እንሞላላቸዋለን) ።

17 ያንንም ፡ ለወላጆቹ ፡ ፎህ ፡ ለና
ንተ ፡ ከኔ ፡ በፊት ፡ የክፍል ፡ ዘመ
ናት ፡ ሰዎች ፡ (ሳይወጡ) ፡ በእር
ግጥ ፡ ያለፉ ፡ ሲኾኑ ፡ (ከመቃ
ብር) ፡ እንድወጣ ፡ ታስፈራሩ
ኛላችሁን ? ያለውን ፡ ሁለቱም ፡
(ወላጆቹ) ፡ አላህን ፡ የሚለምኑ ፡
ሲኾኑ ፡ (ባታምን) ፡ ወዮልህ ፤
እመን ፤ የአላህ ፡ ቀጠሮ ፡ እርግ
ጠኛ ፡ ነው ፡ (ሲሉት) ፡ ይህ ፡
የፊተኞቹ ፡ ሰዎች ፡ ጽሑፍ ፡ ተረ
ቶች ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፡
የሚለውንም ፡ ሰው ፡ (አስታውስ) ።

18 እነዚህ ፡ እነዚያ ፡ ከጋኔንም ፡ ከሰ
ውም ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡ ካለፉት ፡
ሕዝቦች ፡ ጋር ፡ ቃሉ ፡ በነሱ ፡
ላይ ፡ የተረጋገጠባቸው ፡ ናቸው ፤
እነርሱ ፡ ከሳሪዎች ፡ ነበሩና ።

19 ለሁሉም ፡ ከሠሩት ፡ ሥራ ፡ ደረ
ጃዎች ፡ አሏቸው ። ሥራዎቻቸ
ውንም ፡ ይሞላላቸው ፡ ዘንድ ፡
(ይህንን ፡ መነዳቸው) ፡ እነርሱም ፡
አይበደሉም ።

20 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ በእሳት ፡
ላይ ፡ በሚጋፈጡ ፡ ቀን ፡ ጣፋጮ
ቻችሁን ፡ በአነስተኛይቱ ፡ ሕይ
ወታችሁ ፡ አሳለፋችሁ ፤ በር
ሷም ፡ ተጣቀማችሁ ፤ ስለዚህ ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡
ትኮሩ ፡ በነበራችሁትና ፡ ታምጡ ፡
በነበራችሁት ፡ ዛሬ ፡ የውርደትን ፡
ቅጣት ፡ ትመነዳላችሁ ፤ (ይባ
ላሉ) ።

21 የዓድንም ፡ ወንድም ፡ (ሁድን) ፡
ሕዝቦቹን ፡ በአሕቃፍ ፡ (1) ባስ
ጠነቀቀ ፡ ጊዜ ፡ አውሳላቸው ፤
በስተፊቱና ፡ በስተኋላውም ፡
ብዙ ፡ አስፈራሪዎች ፡ በእርግጥ ፡
አልፈዋል ። ከአላህ ፡ በስተቀር ፡
አትገዙ ፡ እኔ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
የከባድ ፡ ቀንን ፡ ቅጣት ፡ እፈራ
ላችኋለሁና ፡ በማለት ፡ (ባስጠ
ነቀቀ ፡ ጊዜ) ።

22 ከአማልክቶቻችን ፡ ልታዞረን ፡
መጣህብን ? ከውነተኞቹም ፡
እንደኾንክ ፡ የምትዝትብንን ፡
(ቅጣት) ፡ አምጣው ፡ አሉ ።

23 ዕውቀቱ ፡ (2) አላህ ፡ ዘንድ ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ ያንን ፡ በርሱ ፡ የተላ
ክሁበትንም ፡ አደርስላችኋለሁ ፤
ግን ፡ እኔ ፡ የምትሳሳቱ ፡ ሕዝቦች ፡
ኾናችሁ ፡ አያችኋለሁ ፡ አላቸው ።

24 ሸለቆዎቻቸውን ፡ ተቅጣጪ ፡
አግዳሚ ፡ ደመና ፡ ኾኖ ፡ ባዩ
ትም ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ አዝናቢያችን ፡
የኾነ ፡ ደመና ፡ ነው ፡ አሉ ፤
(ሁድም) ፡ አይደለም ፤ እርሱ ፡
ያ ፡ በርሱ ፡ የተቻኮላችሁበት ፡
መዐት ፡ ነው ፤ በውስጧ ፡ አሳ
ማሚ ፡ ስቃይ ፡ ያለባት ፡ ነፋስ ፡
ናት ።

25 በጌታዋ ፡ ትእዛዝ ፡ አንዳቹን ፡
ሁሉ ፡ ታጠፋለች ፡ (አላቸው) ፤
ከመኖሪያዎቻቸውም ፡ በስተቀር ፡
ምንም ፡ የማይታዩ ፡ ኾኑ ፤ እንደ
ዚሁ ፡ አመጠኞችን ፡ ሕዝቦች ፡
ሁሉ ፡ እንቀጣለን ።

---

1 በአሸዋማዎቹ ፡ ስፍራዎች ፤
2 የመምጫውን ፡ ጊዜ ፡ ማወቅ ።



26 በዚያም ፡ እናንተን ፡ በርሱ ፡ ባላ
ስመቸንበት ፡ (ድሎት) ፡ በእር
ግጥ ፡ አስመቸናቸው ፤ ለነርሱም ፡
መስሚያንና ፡ ማያዎችን ፡ ልቦ
ችንም ፡ አደረግንላቸው ፡ ግን ፡
መስሚያቸውና ፡ ማያዎቻቸው ፡
ልቦቻቸውም ፡ ከነሱ ፡ ምንም ፡
አልጠቀሟቸውም ፤ በአላህ ፡ አን
ቀጾች ፡ ይክዱ ፡ ነበሩና ፤ በነር
ሱም ፡ ላይ ፡ ያ ፡ በርሱ ፡ ይሳለ
ቁበት ፡ የነበሩት ፡ ቅጣት ፡ ወረ
ደባቸው ።

27 ከከተሞችም ፡ እነዚያን ፡ በአካባ
ቢያችሁ ፡ የነበሩትን ፡ በእርግጥ ፡
አጠፋን ፤ (ከክሕደታቸው) ፡ ይመ
ለሱም ፡ ዘንድ ፡ አስረጂዎችን ፡
መላለስን ።

28 እነዚያም ፡ መቃረቢያ ፡ ይኾኑ ፡
ዘንድ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ አማልክት ፡
አድርገው ፡ የያዙዋቸው ፡ አይረ
ዷቸውም ፡ ኖሯልን ? በእርግጥ ፡
ከነሱ ፡ ራቁ ፤ ይህም ፡ ውሸታቸ
ውና ፡ (በልማድ) ፡ ይቀጥፉት ፡
የነበሩት ፡ ነው ።

29 ከጋኔን ፡ የኾኑን ፡ ጭፍሮች ፡ ቁር
አንን ፡ የሚያዳምጡ ፡ ሲኾኑ ፡
ወዳንተ ፡ ባዞርን ፡ ጊዜም ፡ (አስ
ታውስ) ፤ በተጣዱትም ፡ ጊዜ ፡
ዝም ፡ ብላችሁ ፡ አዳምጡ ፡ ተባ
ባሉ ፤ በተጨረሰም ፡ ጊዜ ፡ አስ
ጠንቃቂዎች ፡ ኾነው ፡ ወደ ፡
ሕዝቦቻቸው ፡ ተመለሱ ።

30 አሉም ፡— ሕዝቦቻችን ፡ ሆይ !
እኛ ፡ ከሙሳ ፡ በኋላ ፡ የተወረደን ፡
መጽሐፍ ፡ በፊቱ ፡ ያለውን ፡ (መ
ጽሐፍ) ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ወደ ፡
እውነትና ፡ ወደ ፡ ቀጥተኛ ፡ መን
ገድ ፡ የሚመራ ፡ የኾነን ፡ ሰማን ።

31 ወገኖቻችን ፡ ሆይ ! የአላህን ፡
ጠሪ ፡ ተቀበሉ ፤ በርሱም ፡ እመኑ ፤
(አላህ) ፡ ከኀጢአቶቻችሁ ፡ ለና
ንተ ፡ ይምራልና ፤ ከአሳማሚ ፡
ቅጣትም ፡ ያድናችኋልና ።

32 የአላህንም ፡ ጠሪ ፡ የማይቀበል ፡
ሰው ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ የሚያ
መልጥ ፡ አይደለም ፤ ከርሱም ፡
ሌላ ፡ ለርሱ ፡ ረዳቶች ፡ የሉትም ፤
እነዚያ ፡ በግልጽ ፡ ስሕተት ፡
ውስጥ ፡ ናቸው ፡ (አሉ) ።

33 ያ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ የፈ
ጠረ ፡ እነርሱንም ፡ በመፍጠሩ ፡
ያልደከመው ፡ አላህ ፡ ሙታንን ፡
ሕያው ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡
መኾኑን ፡ አላስተዋሉምን ? (በማ
ስነሳት) ፡ ቻይ ፡ ነው ። እርሱ ፡
በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ ነውና ።

34 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ሰዎች ፡
በእሳት ፡ ላይ ፡ በሚቀረቡ ፡ ቀን ፡
ይህ ፡ እውነት ፡ አይደለምን ? (ይ
ባላሉ) ፤ እውነት ፡ ነው ፤ በጌታ
ችን ፡ ይኹንብን ፤ ይላሉ ፤ (አላ
ህም) ፡ ትክዱ ፡ በነበራችሁት ፡
ምክንያት ፡ ቅጣቱን ፡ ቅመሱ ፡
ይላቸዋል ።

35 ከመልክተኞችም ፡ የቆራጥነት ፡
ባለቤቶች ፡ የኾኑት ፡ እንደ ፡ ታ
ገሡ ፡ ሁሉ ፡ ታገሥ ፤ ለነርሱም ፡
(ለሕዝቦችህ ፡ ቅጣት) ፡ አትቻ
ኮል ፤ ያንን ፡ የሚስፈራሩበትን ፡
ቅጣት ፡ በሚያዩ ፡ ቀን ፡ እነሱ ፡
ከቀን ፡ አንዲትን ፡ ሰዓት ፡ እንጅ ፡
እንዳልቆዩ ፡ ይኾናሉ ፤ (ይህ ፡
ቁርአን) ፡ በቂ ፡ ግሣጼ ፡ ነው ፤
አመጠኞችም ፡ ሕዝቦች ፡ እንጅ ፡
(ሌሎች) ፡ ይጥጠፋሉን ?

47ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ሙሐመድ ፡ (የሙሐመድ ፡ ምዕራፍ) ። በመ
ዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 38 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 እነዚያ ፡ የካዱ ፡ ከአላህ ፡ መንገ
ድም ፡ የከለከሉ ፡ (አላህ) ፡ ሥራዎ
ቻቸውን ፡ አጠፋባቸው ።
2 እነዚያም ፡ ያመኑ ፡ በጎዎችንም ፡
የሠሩ ፡ በሙሐመድ ፡ ላይም ፡
በተወረደው ፡ እርሱ ፡ ከጌታቸው ፡
ሲኾን ፡ እውነት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡
ያመኑ ፡ ከነርሱ ፡ ላይ ፡ ኀጢአቶ
ቻቸውን ፡ ያብብሳል ፤ ኹኔታቸ
ውንም ፡ ሁሉ ፡ ያበጃል ።
3 ይህ ፡ እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ውሸ
ትን ፡ የተከተሉ ፡ በመኾናቸውና ፡
እነዚያም ፡ ያመኑት ፡ ከጌታቸው ፡
የኾነን ፡ እውነት ፡ ስለ ፡ ተከተሉ ፡
ነው ። እንደዚሁ ፡ አላህ ፡ ለሰ
ዎች ፡ ምሳሌዎቻቸውን ፡ ያብራ
ራል ።
4 እነዚያንም ፡ የካዱትን ፡ (በጦር ፡
ላይ) ፡ ባገኛችሁ ፡ ጊዜ ፡ ጫንቃ
ዎችን ፡ በኀይል ፡ ምቱ ፤ ባደከማ
ችኋቸውም ፡ ጊዜ ፡ (አትግደሏ
ቸው ፡ ማርኳቸው) ፤ ማሠሪያው
ንም ፡ አጥብቁ ፤ በኋላም ፡ ወይም ፡
በነጻ ፡ ትለቋቸዋላችሁ ፤ ወይም ፡
ትበዡቸዋላችሁ ፤ (ይህም) ፡ ጦሪ
ቱ ፡ መሣሪያዋን ፡ እስከምትጥል ፡
ድረስ ፡ ነው ፤ (ነገሩ) ፡ ይህ ፡ ነው ፤
አላህም ፡ ቢሻ ፡ ከነሱ ፡ (ያለጦር) ፡
በተበቀለ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ከፊላች
ሁን ፡ በከፊሉ ፡ ሊሞክር ፡ (በዚህ ፡
አዘዛችሁ) ፤ እነዚያንም ፡ በአ
ላህ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ የተገደሉ
ትን ፡ ሥራዎቻቸውን ፡ ፈጽሞ ፡
አያጠፋባቸውም ።
5 በእርግጥ ፡ ይመራቸዋል ፤ ኹኔታ
ቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ያበጃል ።
6 ገነትንም ፡ ያገባቸዋል ፤ ለነሱ ፡
አስታውቋታል ።
7 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላ
ህን ፡ (ሃይማኖቱን) ፡ ብትረዱ ፡
ይረዳችኋል ፤ ጫማዎቻችሁንም ፡
ያደላድላልል ።
8 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ለነሱ ፡
ጥፋት ፡ ተገባቸው ፤ ሥራዎቻቸ
ውንም ፡ አጠፋባቸው ።
9 ይህ ፡ እነሱ ፡ አላህ ፡ ያወረደውን ፡
ስለጠሉ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ሥራዎ
ቻቸውን ፡ አበላሸባቸው ።
10 የነዚያ ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡
(ከሓዲዎች) ፡ መጨረሻ ፡ እን
ዴት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ አልኼዱምን ?
አላህ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ (ያላቸውን ፡
ሁሉ) ፡ አጠፋባቸው ፤ ለከሐዲ
ዎችም ፡ ሁሉ ፡ ብጤዎችዋ ፡
አልሏቸው ።
11 ይህ ፡ አላህ ፡ የነዚያ ፡ ያመኑት ፡
ሰዎች ፡ ረዳት ፡ ስለ ፡ ኾነና ፡ ከሓ
ዲዎችም ፡ ለነሱ ፡ ረዳት ፡ ስለሌላ
ቸው ፡ ነው ።
12 አላህ ፡ እነዚያን ፡ ያመኑትንና ፡
መልካሞችን ፡ የሠሩትን ፡ ከሥ
ሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱባ



ቸውን ፡ ገነቶች ፡ ያገባቸዋል ፤
እነዚያም ፡ የካዱት ፡ (በቅርቢቱ ፡
ዓለም) ፡ ይጣቀማሉ ፤ እንስሳዎ
ችም ፡ እንደሚበሉ ፡ ይበላሉ ፤
እሳትም ፡ ለነርሱ ፡ መኖሪያቸው ፡
ናት ።
13 ከከተማም ፡ እርሷ ፡ ከዚያች ፡
ካወጣችህ ፡ ከተማህ ፡ ይበልጥ ፡
በኀይል ፡ ጠንካራ ፡ የኾነች ፡
(ባለቤቶችዋን) ፡ ያጠፋናቸው ፡
ብዙ ፡ ናት ፤ ለነርሱም ፡ ረዳት ፡
አልነበራቸውም ።
14 ከጌታው ፡ በኾነች ፡ አስረጅ ፡
ላይ ፡ የኾነ ፡ ምእምን ፡ ክፉ ፡
ሥራቸው ፡ ለነርሱ ፡ እንደ ፡
ተሸለመላቸውና ፡ ዝንባሌዎቻቸ
ውን ፡ እንደ ፡ ተከተሉት ፡ ነውን?
15 የዚያች ፡ ጥንቁቆቹ ፡ ተስፋ ፡ የተ
ሰጧት ፡ ገነት ፡ ምስል ፡ በው
ስጧ ፡ ሺታው ፡ ከማይለውጥ ፡
ውሃ ፡ ወንዞች ፡ ጣዕሙ ፡ ከማይ
ለወጥ ፡ ወተትም ፡ ወንዞች ፡
ለጠጪዎች ፡ ሁሉ ፡ ጣፋጭ ፡
ከኾነች ፡ የወይን ፡ ጠጅም ፡
ወንዞች ፡ ከተነጠረ ፡ ማርም ፡
ወንዞች ፡ አሉባት ፤ ለነሱም ፡
በውስጧ ፡ ከፍሬዎች ፡ ሁሉ ፡
(በያይነቱ) ፡ ከጌታቸው ፡ ምሕ
ረትም ፡ አላቸው ፡ (በዚች ፡ ገነት ፡
ውስጥ ፡ ዘውታሪ ፡ የኾነ ፡ ሰው) ፡
እርሱ ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ዘው
ታሪ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሰው ፡ ሞቃ
ትንም ፡ ውሃ ፡ እንደ ፡ ተጋቱ ፡
አንጀቶቻቸውንም ፡ ወዲያውኑ ፡
እንደ ፡ ቆራረጠው ፡ ነውን ?
(አይደለም) ።
16 ከነሱም ፡ ወዳንተ ፡ የሚያዳምጡ ፡
አሉ ፤ ከአንተም ፡ ዘንድ ፡ በወ
ጡ ፡ ጊዜ ፡ ለነዚያ ፡ ዕውቀት ፡
ለተሰጡት ፡ አሁን ፡ ምን ፡ አለ ?
ይላሉ ። እነዚህ ፡ እነዚያ ፡ በል
ቦቻቸው ፡ ላይ ፡ አላህ ፡ ያተመ
ባቸው ፡ ዝንባሌዎቻቸውንም ፡
የተከተሉ ፡ ናቸው ።
17 እነዚያም ፡ የተመሩት ፡ (አላህ) ፡
መመራትን ፡ ጨመረላቸው ፤
(ከእሳት) ፡ መጠበቂያቸውንም ፡
ሰጣቸው ።
18 ሰዓቲቱንም ፡ ድንገት ፡ የምት
መጣባቸው ፡ መኾንዋን ፡ እንጅ ፡
ይጠባበቃሉን ? ምልክቶችዋም ፡
በእርግጥ ፡ መጥተዋል ፤ በመጣ
ቻቸውም ፡ ጊዜ ፡ ማስታወሳ
ቸው ፡ ለነርሱ ፡ እንዴት ፡ ይጠ
ቅማቸዋል ?
19 እነሆ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡
አለመኖሩንም ፡ ዕወቅ ፤ ስለ ፡
ስሕተትህም ፡ ለምእምናንም ፡
ምሕረትን ፡ ለምን ፤ አላህም ፡
መዘዋወሪያችሁን ፡ መርጊያችሁ
ንም ፡ ያውቃል ።
20 እነዚያም ፡ ያመኑት ፡ ሰዎች ፡
(መታገል ፡ ያለባት) ፡ ሱራ ፡
አትወርድም ፡ ኖሮአልን ? ይላሉ ፤
የጠነከረችም ፡ ሱራ ፡ በተወረ
ደችና ፡ በውስጧም ፡ መጋደል ፡
በተወሳ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያን ፡ በልቦ
ቻቸው ፡ ውስጥ ፡ (የንፍቅና) ፡
በሺታ ፡ ያለባቸውን ፡ ሰዎች ፡
ከሞት ፡ የኾነ ፡ መከራ ፡ በርሱ ፡
ላይ ፡ እንደ ፡ ወደቀበት ፡ ሰው ፡
አስተያየት ፡ ወዳንተ ፡ ሲመለ
ከቱ ፡ ታያቸዋለህ ፤ ለነሱም ፡
ወዮላቸው ።
21 ታዛዥነትና ፡ መልካም ፡ ንግ
ግር ፡ (ይሻላቸዋል) ፡ ትእዛዙም ፡
ቁርጥ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ለአላህ ፡

(ትእዛዝ) ፡ እውነተኞች ፡ በኾኑ ፡
ኖሮ ፡ ለነሱ ፡ የተሻለ ፡ በኾነ ፡
ነበር ።
22 ብትሸሾሙም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ማበላሸትን ፡ ዝምድናችሁንም ፡
መቁረጥን ፡ ከጀላችሁን ?
23 እነዚህ ፡ እነዚያ ፡ አላህ ፡ የረገ
ማቸው ፤ ያደነቆራቸውም ፡ ዓይ
ኖቻቸውንም ፡ ያወራቸው ፡ ና
ቸው ።
24 ቁርአንንም ፡ አያስተነትኑምን ?
በውነቱ ፡ በልቦቻቸው ፡ ላይ ፡
ቁልፎቿ ፡ አሉባትን ?
25 እነዚያ ፡ ለነሱ ፡ ቅኑ ፡ መንገድ ፡
ከተብራራላቸው ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡
ኋላቸው ፡ የተመለሱት ፡ ሰይ
ጣን ፡ ለነሱ ፡ መመለሳቸውን ፡
ሸለመላቸው ፤ ለነሱም ፡ አዝዘ
ናጋቸው ።
26 ይህ ፡ እነሱ ፡ ለነዚያ ፡ አላህ ፡
ያወረደውን ፡ ለጠሉት ፡ በነገሩ ፡
ከፊል ፡ እንታዘዛችኋለን ፡ ያሉ ፡
በመኾናቸው ፡ ነው ፤ አላህም ፡
መደበቃቸውን ፡ ያውቃል ።
27 መላእክትም ፡ ፊቶቻቸውንና ፡ ጀር
ባቻቸውን ፡ የሚመቱ ፡ ሲኾኑ ፡
በገደሉዋቸው ፡ ጊዜ ፡ (ኹኔታቸ
ው) ፡ እንዴት ፡ ይኾናል ?
28 ይህ ፡ እነርሱ ፡ አላህን ፡ ያስቆጣ
ውን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ተከተሉ ፡ ውዴ
ታውንም ፡ ስለ ፡ ጠሉ ፡ ነው ።
ስለዚህ ፡ ሥራዎቻቸውን ፡ አበላ
ሸባቸው ።
29 እነዚያ ፡ በልቦቻቸው ፡ ውስጥ ፡
በሽታ ፡ ያለባቸው ፡ አላህ ፡ ቂሞ
ቻቸውን ፡ አለማውጣቱን ፡ ጠረ
ጠሩን ?
30 በሻንም ፡ ኖሮ ፡ እነሱን ፡ ባሳየ
ንህና ፡ በምልክታቸውም ፡ በእ
ርግጥ ፡ ባወቅሃቸው ፡ ነበር ፤ ንግግ
ርንም ፡ በማሸሞራቸው ፡ በእር
ግጥ ፡ ታውቃቸዋለህ ። አላህም ፡
ሥራዎቻችሁን ፡ ያውቃል ።
31 ከናንተም ፡ ታጋዮቹንና ፡ ታጋሾ
ቹን ፡ እስከምናውቅ ፡ ወሬዎቻ
ችሁንም ፡ እስከምንገልጽ ፡ ድረስ
በእርግጥ ፡ እንሞክራችኋለን ።
32 እነዚያ ፡ የካዱና ፡ ከአላህም ፡ መን
ገድ ፡ ያገዱ ፡ ለነርሱም ፡ ቅኑ ፡
መንገድ ፡ ከተገለጸላቸው ፡ በኋላ ፡
መልክተኛውን ፡ የተከራከሩ ፡ አላ
ህን ፡ በምንም ፡ አይጐዱትም ፤
ሥራዎቻቸውንም ፡ በእርግጥ ፡
ያበላሻል ።
33 እናንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ፡ አላ
ህን ፡ ተገዙ ፤ መልክተኛውንም ፡
ታዘዙ ፤ ሥራዎቻችሁንም ፡ አታ
በላሹ ።
34 እነዚያ ፡ የካዱ ፡ ከአላህም ፡ መን
ገድ ፡ ያገዱ ፡ ከዚያም ፡ እነሱ ፡
ከሓዲዎች ፡ ኾነው ፡ የሞቱ ፡
አላህ ፡ ለነሱ ፡ በፍጹም ፡ አይም
ርም ።
35 እናንተም ፡ አሸናፊውቹ ፡ ስት
ኾኑ ፡ አላህም ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡
ሲኾን ፡ አትድከሙ ፤ ወደ ፡ ዕር
ቅም ፡ አትጥሩ ፤ ሥራዎቻችሁ
ንም ፡ ፈጽሞ ፡ አያጐድልባች
ሁም ።
36 ቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡ ጫወታና ፡
ዛዛታ ፡ ብቻ ፡ ናት ፤ ብታምኑም ፡
ብትጠነቀቁም ፡ ምንዳዎቻችሁን ፡
ይሰጣችኋል ፤ ገንዘቦቻችሁንም ፡
(ሁሉ) ፡ አይጠይቃችሁም ።



37 እርሷን ፡ ቢጠይቃችሁና ፡ ችክ ፡
ቢልባችሁ ፡ ትሰስታላችሁ ፤ ቂሞ
ቻችሁንም ፡ ያወጣል ።
38 ንቁ ፡ እናንተ ፡ እነዚያ ፡ በአላህ ፡
መንገድ ፡ ትለግሱ ፡ ዘንድ ፡ የም
ትጠሩ ፡ ናችሁ ፤ ከናንተም ፡
ውስጥ ፡ የሚሰስት ፡ ሰው ፡ አለ ፤
የሚሰስትም ፡ ሰው ፡ የሚሰስ
ተው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤
አላህም ፡ ከበርቴ ፡ ነው ፤ እናን
ተም ፡ ድኾች ፡ ናችሁ ፤ ብትሸ
ሹም ፡ ሌሎችን ፡ ሕዝቦች ፡ ይለ
ውጣል ፤ ከዚያም ፡ (ባለመታዘዝ)
ብጤዎቻችሁ ፡ አይኾኑም ።

## ምዕራፍ ፡ 48 ፡ አል-ፈትሕ ። ክፍል ፡ 26 ።

48ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ፈትሕ ፡ (አገር ፡ የመክፈት ፡ ምዕራፍ) ። በመ
ዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 29 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅ ፡ በጣም ፡ ርኅ
ሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 እኛ ፡ ላንተ ፡ ግልጽ ፡ የኾነን ፡
መክፈት ፡ ከፈትንልህ ።
2 አላህ ፡ ከኃጢአትህ ፡ ያለፈው
ንና ፡ የሚመጣውን ፡ ላንተ ፡
ሊምር ፡ ጸጋውንም ፡ ባንተ ፡
ላይ ፡ ሊሞላ ፡ ቀጥተኛውንም ፡
መንገድ ፡ ሊመራህ ፡ (ከፈተልህ) ።
3 አላህ ፡ ብርቱን ፡ እርዳታ ፡ ሊረዳ
ህም ፡ (ከፈተልህ) ።
4 እርሱ ፡ ያ ፡ በምእምናን ፡ ልቦች ፡
ውስጥ ፡ ከእምነታቸው ፡ ጋር ፡
እምነትን ፡ ይጨምሩ ፡ ዘንድ ፡
እርጋታን ፡ ያወረደ ፡ ነው ፤ ለአላ
ህም ፡ የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ሰራ
ዊቶች ፡ አልሉት ፤ አላህም ፡
ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።
5 ምእምናንንና ፡ ምእምናትን ፡
ከሥሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈ
ሱባቸውን ፡ ገነቶች ፡ በውስጣ
ቸው ፡ ዘውታሪዎች ፡ሲኾኑ ፡ ሊያ
ገባቸው ፡ ከነሱም ፡ ኃጢአቶቻ
ቸውን ፡ ሊያብስላቸው ፡ (በት
ግል ፡ አዘዛቸው) ፤ ይህም ፡ ከአ
ላህ ፡ ዘንድ ፡ የኾነ ፡ ታላቅ ፡ ማግ
ኘት ፡ ነው ።
6 በአላህም ፡ ክፉ ፡ ጥርጣሬን ፡
ተጠራጣሪዎቹን ፡ መናፍቃንና ፡
መናፍቃትን ፡ ወንዶች ፡ አጋሪ
ዎችንና ፡ ሴቶች ፡ አጋሪዎችንም ፡
(1) ያሰቃይ ፡ ዘንድ ፡ (በትግል ፡
አዘዘ) ፤ በነሱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ከባቢ ፡
አለባቸው ፤ በነሱም ፡ ላይ ፡ አላህ ፡
ተቆጣባቸው ፤ ረገማቸውም ፤ ለነ
ሱም ፡ ገሀነምን ፡ አዘጋጀላቸው ፤
መመለሻነትዋም ፡ ከፋች ።
7 ለአላህም ፡ የሰማያትና ፡ የምድር ፡
ሰራዊቶች ፡ አልሉት ፤ አላህም ፡
አሸናፊ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።
8 እኛ ፡ መስካሪ ፡ አብሳሪና ፡ አስ

1 ጣዖታትን ፡ በአላህ ፡ የሚያጋሩትን ።

ፈራሪም ፡ አድርገን ፡ በእርግጥ ፡
ላክንህ ።
9 በአላህ ፡ ልታምኑ ፡ በመልክተኛ
ውም ፡ (ልታምኑ) ፡ ልትረዱትም
ልታከብሩትም ፡ (አላህን) ፡ በጧ
ትና ፡ ከቀትር ፡ በኋላ ፡ ልታወድ
ሱትም ፡ (ላክነው) ።
10 እነዚያ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የሚጋ
ቡህ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የሚጋቡት ፡
አላህን ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ የአላህ ፡
እጅ ፡ (ኀይሉ) ፡ ከእጆቻቸው ፡
በላይ ፡ ነው ፤ ያፈረሰም ፡ ሰው ፡
የሚያፈርሰው ፡ በነፍሱ ፡ ላይ ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ አላ
ህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የተጋባበ
ትን ፡ የሞላም ፡ ሰው ፡ ታላቅ ፡
ምንዳን ፡ በእርግጥ ፡ ይሰጠዋል ።
11 ከአዕራብ ፡ ሰዎች ፡ (1) እነዚያ ፡
(ከዘመቻ) ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀሩት ፡
ለአንተ ፦ ገንዘቦቻችንና ፡ ቤተ ፡
ሰቦቻችን ፡ አስቸገሩን ፤ ስለዚህ ፡
ምሕረትን ፡ ለምንልን ፤ ይሉ
ሃል ፤ በልቦቻቸው ፡ ውስጥ ፡
የሌለውን ፡ ነገር ፡ በምላሶቻቸው ፡
ይናገራሉ ፤ (አላህ) ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ ጉዳትን ፡ ቢሻ ፡ ወይም ፡
በናንተ ፡ መጥቀምን ፡ ቢሻ ፡ ከአ
ላህ ፡ (ለማገድ) ፡ ለናንተ ፡ አን
ዳችን ፡ የሚችል ፡ ማነው ? በው
ነቱ ፡ አላህ ፤ በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡
ውስጥ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፡ በላቸው ።
12 ይልቁንም ፡ መልክተኛውና ፡
ምእምናኖቹ ፡ ወደ ፡ ቤተሰቦቻ
ቸው ፡ ፈጽሞ ፡ አለመመለሳቸ
ውን ፡ ጠረጠራችሁ ፤ ይህም ፡
በልቦቻችሁ ፡ ውስጥ ፡ ተሸለመላ
ችሁ ፤ መጥፎንም ፡ መጠርጠር ፡
ጠረጠራችሁ ፤ ጠፊዎች ፡ ሕዝ
ቦችም ፡ ኾናችሁ ።
13 በአላህና ፡ በመልክተኛው ፡ ያላ
መነም ፡ ሰው ፡ እኛ ፡ ለከሓዲ
ዎች ፡ እሳትን ፡ አዘጋጅተናል ።
14 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ንግሥ
ናም ፡ የአላህ ፡ ነው ፤ ለሚሻው ፡
ሰው ፡ ይምራል ፤ የሚሻውንም ፡
ይቀጣል ፤ አላህም ፡ መሓሪ ፡
አዛኝ ፡ ነው ።
15 ወደ ፡ ዘረፋዎች ፡ ልትይዟት ፡
በኼዳችሁ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ ወደ ፡
ኋላ ፡ የቀሩት ፡ ሰዎች ፡ ተዉን ፡
እንከተላችሁ ፡ ይሏችኋል ፤ (በዚህ
ም) ፡ የአላህን ፡ ቃል ፡ ሊለውጡ ፡
ይፈልጋሉ ፤ ፈጽሞ ፡ አትከተ
ሉንም ፤ እንደዚሃችሁ ፡ (ቃል) ፡
ከዚህ ፡ በፊት ፡ አላህ ፡ ብሏል ፡
በላቸው ፤ ይልቁንም ፡ ትመቀኙ
ናላችሁ ፡ ይላሉም ፤ በውነት ፡
እነርሱ ፡ ጥቂትን ፡ እንጅ ፡ የማ
ያውቁ ፡ ነበሩ ።
16 ከአዕራቦች ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ለቀ
ሩት ፡ በላቸው ፦ የብርቱ ፡
ጭካኔ ፡ ባለ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ኾኑ ፡
ሕዝቦች ፡ (ውጊያ) ፡ ወደፊት ፡
ትጥጠራላችሁ ፤ ትጋደሏቸዋላች
ሁ ፤ ወይም ፡ ይሰልማሉ ፤ ብት
ታዘዙም ፡ አላህ ፡ መልካም ፡
ምንዳን ፡ ይሰጣችኋል ፤ ከአሁን ፡
በፊት ፡ እንደ ፡ ሸሻችሁ ፡ ብት
ሸሹም ፡ አሳማሚን ፡ ቅጣት ፡
ይቀጣችኋል ።
17 በዕውር ፡ ላይ ፡ (ከዘመቻ ፡ በመቅረ
ቱ) ፡ ኃጢአት ፡ የለበትም ፤ በአንካ
ሳም ፡ ላይ ፡ ኃጢአት ፡ የለበትም ፤ በበ
ሽተኛም ፡ ላይ ፡ ኃጢአት ፡ የለበት
ም ፤ አላህንና ፡ መልክተኛውንም ፡
የሚታዘዝ ፡ ሰው ፤ ከሥሮቻቸው ፡

1 ከዐረብ ፡ ዘላኖች ።



ወንዞች ፡ የሚፈሱባቸውን ፡ ገነቶች ፡
ያገባዋል ፤ የሚሸሸውንም ፡ ሰው ፡
አሳማሚውን ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣዋል ።
18 ከምእምናኖቹ ፡ በዛፊቱ ፡ ሥር ፡
ቃል ፡ ኪዳን ፡ በሚጋቡህ ፡ ጊዜ ፡
አላህ ፡ በእርግጥ ፡ ወደደ ፤ በልቦ
ቻቸውም ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡
ዐወቀ ፤ በነሱም ፡ ላይ ፡ እርጋ
ታን ፡ አወረደ ፤ ቅርብ ፡ የኾነንም
መክፈት ፡ መነዳቸው ።
19 ብዙዎች ፡ ዘረፋዎችንም ፡ የሚ
ወስዷቸው ፡ የኾኑን ፡ (መነዳ
ቸው) ፤ አላህም ፡ አሸናፊ ፡ ጥበ
በኛ ፡ ነው ።
20 አላህ ፡ ብዙዎችን ፡ ዘረፋዎች ፡
የምትወስዷቸው ፡ የኾኑን ፡ ተ
ስፋ ፡ አደረገላችሁ ፤ ይህችንም ፡
ለናንተ ፡ አስቸኰለላችሁ ፤ ከና
ንተም ፡ የሰዎችን ፡ እጆች ፡ ከለ
ከለላችሁ ፤ (ልታመሰግኑትና) ፡
ለምእምናንም ፡ ምልክት ፡ እንድ
ትኾን ፤ ቀጥተኛውን ፡ መንገድ ፡
ይመራችሁም ፡ ዘንድ ፡ (ይህንን ፡
ሠራላችሁ) ።
21 ሌላይቱንም ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ገና ፡
ያልቻላችኋትን ፡ አላህ ፡ ያወቃ
ትን ፡ (ለናንተ ፡ አዘጋጃት) ፤
አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ቻይ ፡ ነው ።
22 እነዚያም ፡ የካዱት ፡ (የመካ ፡
ሰዎች ፡ በሑደይቢያ) ፡ በተዋጉ
ዋችሁ ፡ ኖሮ ፡ (ለሺሺት) ፡ ጀር
ባዎችን ፡ ባዞሩ ፡ ነበር ፤ ከዚያም ፡
ዘመድም ፡ ረዳትም ፡ አያገኙም ።
23 አላህ ፡ ያችን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡
በርግጥ ፡ ያለፈችውን ፡ ልማድ ፡
ደነገገ ። ለአላህም ፡ ልማድ ፡
ለውጥን ፡ አታገኝም ።
24 እርሱም ፡ ያ ፡ በመካ ፡ ውስጥ ፡
በነሱ ፡ ላይ ፡ ካስቻላችሁ ፡ በኋላ ፡
እጆቻቸውን ፡ ከናንተ ፡ ላይ ፡
እጆቻችሁንም ፡ ከነሱ ፡ ላይ ፡ የከ
ለከለ ፡ ነው ። አላህም ፡ የምትሠሩ
ትን ፡ ሁሉ ፡ ተመልካች ፡ ነው ።
25 እነሱ ፡ እነዚያ ፡ የካዱ ፡ ከተከበ
ረው ፡ መስጊድም ፡ የከለከሏችሁ ፡
መሥዋዕቱንም ፡ የታሰረ ፡ ሲኾን ፡
በስፍራው ፡ እንዳይደርስ ፡ (የከ
ለከሉ) ፡ ናቸው ፤ የማታውቋቸው ፡
የኾኑ ፡ ምእመናን ፡ ወንዶችና ፡
ምእመናት ፡ ሴቶች ፡ (ከከሓዲ
ዎቹ ፡ ጋር) ፡ ባልነበሩ ፡ ያለ ፡
ዕውቀት ፡ እነርሱን ፡ መርገጣች
ሁና ፡ ከነርሱ ፡ (በኩል) ፡ መከ
ፋት ፡ የሚነካችሁ ፡ ባልኾነ ፡
ኖሮ ፡ (እጆቻችሁን ፡ ባላገድን ፡
ነበር) ፤ አላህ ፡ የሚሻውን ፡ ሰው ፡
በእዝነቱ ፡ ውስጥ ፡ ያገባ ፡ ዘንድ ፡
(እጆቻችሁን ፡ አገደ) ፤ በተለዩ ፡
ኖሮ ፡ እነዚያን ፡ ከነሱ ፡ ውስጥ ፡
የካዱትን ፡ አሳማሚን ፡ ቅጣት ፡
በቀጣናቸው ፡ ነበር ።
26 እነዚያ ፡ የካዱት ፡ ደራይቱን ፡
የመሃይምነቲቱን ፡ ደራ ፡ በልቦ
ቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡
(በቀጣናቸው ፡ ነበር) ፤ አላህም ፡
በመልክተኛው ፡ ላይና ፡ በምእም
ናኖቹ ፡ ላይ ፡ እርጋታውን ፡ አወ
ረደ ፤ መጥጠበቂያይቱንም ፡ ቃል ፡
አስያዛቸው ፤ በርሷም ፡ ተገቢ
ዎች ፡ ባለቤቶችዋም ፡ ነበሩ ፤
አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።
27 አላህ ፡ ለመልክተኛው ፡ ሕልሙን ፡
(1) እውነተኛ ፡ ሲኾን ፡ አላህ ፡

1 እርሱና ፡ ወዳጆቹ ፡ በደህና ፡ መካ ፡ ሲገቡ ፡
ያየውን ።

የሻ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ጸጥተኞች ፡ ኾና
ችሁ ፡ ራሶቻችሁን ፡ ላጭታችሁ ፡
አሳጥራችሁም ፡ የማትፈሩ ፡ ስት
ኾኑ ፡ የተከበረውን ፡ መስጊድ ፡
በእርግጥ ፡ ትገባላችሁ ፤ ያለውን ፡
በእርግጥ ፡ እውነት ፡ አደረገለት ።
(ከዕርቁ) ፡ ያላወቃችሁትንም ፡
ነገር ፡ ዐወቀ ፤ ከዚህም ፡ በፊት ፡
ቅርብን ፡ መክፈት ፡ (1) አደረገ ።

28 እርሱ ፡ ያ ፡ መልክተኛውን ፡
በመሪ ፡ መጽሐፍና ፡ በውነተኛ ፡
ሃይማኖት ፡ በሃይማኖት ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ሊያልቀው ፡ የላከ ፡ ነው ፤
መስካሪም ፡ በአላህ ፡ በቃ ።

29 የአላህ ፡ መልክተኛ ፡ ሙሐመድ ፡
እነዚያም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያሉት ፡
(ወዳጆቹ) ፡ በከሓዲዎቹ ፡ ላይ ፡
ብርቱዎች ፡ በመካከላቸው ፡ አዛ
ኞች ፡ ናቸው ፤ አጎንባሾች ፡ ሰጋ
ጆች ፡ ኾነው ፡ ታያቸዋለህ ፤
ከአላህ ፡ ችሮታንና ፡ ውዴታን ፡
ይፈልጋሉ ፤ ምልክታቸው ፡ ከስ
ግደታቸው ፡ ፈለግ ፡ ስትኾን ፡
በፊቶቻቸው ፡ ላይ ፡ ናት ፤ ይህ ፡
በተውራት ፡ (የተነገረው) ፡ ጠባ
ያቸው ፡ ነው ፤ በኢንጂልም ፡
ውስጥ ፡ ምሳሌያቸው ፡ ቀንዘ
ሉን ፡ እንደአወጣ ፡ አዝመራና ፡
(ቀንዘሉ) ፡ እንዳበረታው ፡ እንደ ፡
ወፈረምና ፡ ገበሬዎቹን ፡ የሚያ
ስደንቅ ፡ ኾኖ ፡ በአገዳዎቹ ፡ ላይ ፡
ተስተካከሎ ፡ እንደ ፡ ቆመ ፡ (አዝ
መራ) ፡ ነው ፤ (ያበረታቸውና ፡
ያበዛቸው) ፡ ከሓዲዎችን ፡ በነሱ ፡
ሊያስቆጭ ፡ ነው ፤ አላህም ፡
እነዚያን ፡ ያመኑትንና ፡ ከነሱ ፡
በጎዎችን ፡ የሠሩትን ፡ ምሕረት
ንና ፡ ታላቅ ፡ ምንዳን ፡ ተስፋ ፡
አድርጎላቸዋል ።

1 የኸይበርን፡ መክፈት፡ (ድል)።

## ምዕራፍ ፡ 49 ፡ አል-ሑጁራት ። ክፍል ፡ 26 ።

49ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሑጁራት ፡ (የቤት ፡ ክፍሎች ፡ ምዕራፍ) ።
በመዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ አንቀጾችዋ ፡ 18 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በኾ
ነው ።

1 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! በአ
ላህና ፡ በመልክተኛው ፡ ፊት ፡
(ነፍሶቻችሁን) ፡ አታስቀድሙ ፤
አላህንም ፡ ፍሩ ፤ አላህ ፡ ሰሚ ፡
ዐዋቂ ፡ ነውና ።

2 እናንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ፤ ድም
ጾቻችሁን ፡ ከነቢዩ ፡ ድምፅ ፡
በላይ ፡ ከፍ ፡ አታድርጉ ፤ ከፊ
ላችሁም ፡ ለከፊሉ ፡ እንደሚ
ጮህ ፡ በንግግር ፡ ለርሱ ፡ አት
ጩሁ ፤ እናንተ ፡ የማታውቁ ፡
ስትኾኑ ፡ ሥራዎቻችሁ ፡ እንዳ
ይበላሹ ፡ (ተከልከሉ) ።



3 እነዚያ ፡ በአላህ ፡ መልክተኛ ፡
ዘንድ ፡ ድምጾቻቸውን ፡ ዝቅ ፡
የሚያደርጉ ፡ እነዚህ ፡ እነዚያ ፡
አላህ ፡ ልቦቻቸውን ፡ ለፍርሃት ፡
የፈተናቸው ፡ ናቸው ። ለነሱም ፡
ምሕረትና ፡ ታላቅ ፡ ምንዳ ፡
አላቸው ።

4 እነዚያ ፡ ከክፍሎቹ ፡ ውጭ ፡
ኾነው ፡ የሚጠሩህ ፡ አብዛኞቻ
ቸው ፡ አያውቁም ።

5 ወደነርሱም ፡ እስክትወጣ ፡ ድረስ
እነርሱ ፡ በታገሡ ፡ ኖሮ ፡ ለነርሱ ፡
በላጭ ፡ በኾነ ፡ ነበር ፤ አላህም ፡
እጅግ ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።

6 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ፡ ነገ
ረኛ ፡ ወሬን ፡ ቢያመጣላችሁ ፡
በስሕተት ፡ ላይ ፡ ኾናችሁ ፡ ሕዝ
ቦችን ፡ እንዳትጎዱና ፡ በሠራ
ችሁት ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ተጸጸቾች ፡
እንዳትኾኑ ፡ አረጋግጡ ።

7 በውስጣችሁም ፡ የአላህ ፡ መል
ክተኛ ፡ መኖሩን ፡ ዕወቁ ፤ ከነ
ገሩ ፡ በብዙው ፡ ቢከተላችሁ ፡
ኖሮ ፡ በእርግጥ ፡ በተቸገራችሁ ፡
ነበር ፤ ግን ፡ አላህ ፡ እምነትን ፡
ወደናንተ ፡ አስወደደ ፤ በልቦ
ቻችሁም ፡ ውስጥ ፡ አጌጠው ፤
ክሕደትንና ፡ አመጥንም ፡ እን
ቢተኛነትንም ፡ ወደናንተ ፡ የተ
ጠላ ፡ አደረገ ፤ እነዚያ ፡ (እምነ
ትን ፡ የወደዱና ፡ ክሕደትን ፡
የጠሉ) ፡ እነርሱ ፡ ቅኖቹ ፡ ናቸው ፡

8 ከአላህ ፡ በኾነው ፡ ችሮታና ፡
ጸጋ ፡ (ቅኖች ፡ ናቸው) ፤ አላ
ህም ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።

9 ከምእምናንም ፡ የኾኑ ፡ ሁለት ፡
ጭፍሮች ፡ ቢጋደሉ ፡ በመካከላ
ቸው ፡ አስታርቁ ፤ ከሁለቱ ፡ አን
ደኛይቱም ፡ በሌላይቱ ፡ ላይ ፡
ወሰን ፡ ብታልፍ ፡ ያችን ፡ ወሰን ፡
የምታልፈውን ፡ ወደ ፡ አላህ ፡
ትእዛዝ ፡ እስከምትመለስ ፡ ድረስ ፡
ተጋደሉ ፤ ብትመለስም ፡ በመካ
ከላቸው ፡ በትክክል ፡ አስታርቁ ፤
በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ አስተካክሉም ፤
አላህ ፡ አስተካካዮችን ፡ ይወዳ
ልና ።

10 ምእመናኖች ፡ ወንድማማቾች ፡
ናቸው ፤ በሁለት ፡ ወንድሞቻ
ችሁም ፡ መካከል ፡ አስታርቁ ፤
ይታዘንላችሁም ፡ ዘንድ ፡ አላህን ፡
ፍሩ ።

11 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ፡ ወን
ዶች ፡ ከወንዶች ፡ አይቀልዱ ፤
ከነርሱ ፡ የበለጡ ፡ ሊኾኑ ፡ ይከጀ
ላልና ፤ ሴቶችም ፡ ከሴቶች ፡ (አይ
ሳለቁ) ፤ ከነሱ ፡ የበለጡ ፡ ሊኾኑ ፡
ይከጀላልና ፤ ነፍሶቻችሁንም ፡ (1)
አታነውሩ ፤ በመጥፎ ፡ ስሞችም ፡
አትጠራሩ ፤ ከእምነት ፡ በኋላ ፡
የማመጥ ፡ ስም ፡ ከፋ ፤ ያልተጸ
ጸተም ፡ ሰው ፡ እነዚያ ፡ እነሱ ፡
በዳዮቹ ፡ ናቸው ።

12 እናንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ፡ ከጥ
ርጣሬ ፡ ብዙውን ፡ ራቁ ፤ ከጥር
ጣሬ ፡ ከፊሉ ፡ ኃጢአት ፡ ነውና ፤
ነውርንም ፡ አትከታተሉ ፤ ከፊ
ላችሁም ፡ ከፊሉን ፡ አይማ ፤
አንደኛችሁ ፡ የወንድሙን ፡ ስጋ ፡
የሞተ ፡ ኾኖ ፡ ሊበላው ፡ ይወ
ዳልን ? (መብላቱን) ፡ ጠላችሁ
ትም ፤ (ሐሜቱንም ፡ ጥሉት) ፤
አላህንም ፡ ፍሩ ፤ አላህ ፡ ጸጸትን ፡
ተቀባይ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።

13 እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፡ እኛ ፡
ከወንድና ፡ ከሴት ፡ ፈጠርናችሁ ፤

1 ከፊላችሁ ፡ ከፊሉን ፡ አይዝለፍ ።

እንድትተዋወቁም ፡ ጐሳዎችና ፡
ነገዶች ፡ አደረግናችሁ ፤ አላህ ፡
ዘንድ ፡ በላጫችሁ ፣ በጣም ፡ አላ
ህን ፡ ፈሪያችሁ ፡ ነው ፤ አላህ ፡
ግልጽን ፡ ዐዋቂ ፣ ውስጥንም ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።

14 የዐረብ ፡ ዘላኖች ፡ አምነናል ፡
አሉ ፤ አላመናችሁም ፤ ግን ፡
ሰልመናል ፡ በሉ ፤ እምነቱም ፡
በልቦቻችሁ ፡ ውስጥ ፡ ገና ፡ (ጠ
ልቆ) ፡ አልገባም ፤ አላህንና ፡
መልክተኛውንም ፡ ብትታዘዙ ፣
ከሥራዎቻችሁ ፡ ምንንም ፡ አያ
ጐድልባችሁም ፤ አላህ ፡ መሓሪ ፡
አዛኝ ፡ ነውና ፡ በላቸው ።

15 (እውነተኛዎቹ) ፡ ምእምናን ፣ እነ
ዚያ ፡ በአላህና ፡ በመልክተኛው ፡
ያመኑት ፣ ከዚያም ፡ ያልተጠራ
ጠሩት ፣ በገንዘቦቻቸውና ፡ በነ
ፍሶቻቸውም ፡ በአላህ ፡ መን
ገድ ፡ የታገሉት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፤
እነዚያ ፡ እነሱ ፡ እውነተኞቹ ፡
ናቸው ።

16 አላህ ፡ በሰማያት ፡ ውስጥ ፡ ያለ
ውንና ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ያለ
ውን ፡ ሁሉ ፡ የሚያውቅ ፡ ሲኾን ፡
አላህን ፡ በሃይማኖታችሁ ፡ ታስታ
ውቁታላችሁን ? በላቸው ፤ አላ
ህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።

17 መስለማቸው ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡
ይመጻደቃሉ ፤ በስልምናችሁ ፡
በኔ ፡ ላይ ፡ አትመጻደቁ ፤ ይል
ቁንም ፡ አላህ ፡ ወደ ፡ እምነት ፡
ስለ ፡ መራችሁ ፡ ይመጻደቅባች
ኋል ፤ እውነተኞች ፡ ብትኾኑ ፣
(መመጻደቅ ፡ ለአላህ ፡ ነው) ፤
በላቸው ።

18 አላህ ፡ የሰማያትንና ፡ የምድርን ፡
ሩቅ ፡ ምስጢር ፡ ያውቃል ፤ አላ
ህም ፡ የምትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡
ተመልካች ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 50 ፡ ቃፍ ። ክፍል ፡ 26 ።

50ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ቃፍ ፤ (የቃፍ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡
ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 45 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፣ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።

1 ቀ. (ቃፍ) ፡ (1) በተከበረው ፡
ቁርአን ፡ እምላለሁ ፤ (በሙሐ
መድ ፡ አላመኑም) ።

2 ይልቁንም ፡ ከነሱ ፡ ጐሳ ፡ የኾነ ፡
አስፈራሪ ፡ ስለ ፡ መጣላቸው ፡
ተደነቁ ፤ ከሓዲዎቹም ፡— ይህ ፡
አስደናቂ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ አሉ ።

3 በሞትንና ፡ ዐፈር ፡ በኾን ፡ ጊዜ ፡
(እንመለሳለን ?) ይህ ፡ ሩቅ ፡
የኾነ ፡ መመለስ ፡ ነው ፤ (አሉ) ።

1 የሚኾነው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተፈርዷል።



4 ከነሱ ፡ (አካል) ፡ ምድር ፡ የምታ
ጐድለውን ፣ በእርግጥ ፡ ዐውቀ
ናል ፤ እኛም ፡ ዘንድ ፡ ጠባቂ ፡
መጽሐፍ ፡ አልለ ።

5 (አልተመለከቱም) ፤ ይልቁንም ፡
በቁርአን ፡ በመጣላቸው ፡ ጊዜ ፡
አስተባበሉ ፤ እነርሱም ፡ በተማታ ፡
ነገር ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።

6 ወደ ፡ ሰማይም ፣ ከበላያቸው ፡
ስትኾን ፡ ለርሷ ፡ ምንም ፡ ቀዳ
ዳዎች ፡ የሌሏት ፡ ኾና ፡ እንዴት ፡
እንደ ፡ ገነባናትና ፡ (በከዋክብት)
እንዳጌጥናት ፡ አልተመለከቱምን ?

7 ምድርንም ፣ ዘረጋናት ፤ በርሷም ፡
ውስጥ ፡ ጋራዎችን ፡ ጣልንባት ፤
በውስጧም ፡ ከሚያስደስት ፡ ዓይ
ነት ፡ ሁሉ ፡ አበቀልን ።

8 (ይህንን ፡ ያደረግነው) ፣ ተመ
ላሽ ፡ ለኾነ ፡ ባሪያ ፡ ሁሉ ፡ ለማ
ሳየትና ፡ ለማስገንዘብ ፡ ነው ።

9 ከሰማይም ፡ ብሩክን ፡ ውሃ ፡ አወ
ረድን ፤ በርሱም ፡ አትክልቶ
ችንና ፡ የሚታጨድን ፡ (አዝ
መራ) ፡ ፍሬ ፡ አበቀልን ።

10 ዘምባባንም ፡ ረዣዦርም ፣ ለርሷ ፡
የተደራረበ ፡ እንቡጥ ፡ ያላት ፡ ስት
ኾን ፡ (አበቀልን) ።

11 ለባሮቹ ፡ሲሳይ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡
(አዘጋጀናት) ፤ በርሱም ፡ የሞተ
ችን ፡ አገር ፡ ሕያው ፡ አደረግን
ንበት ፤ (ከመቃብር) ፡ መውጣት
ም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።

12 ከነርሱ ፡ በፊት ፡ የኑሕ ፡ ሕዝ
ቦችና ፡ የረስስ ፡ ሰዎች ፤ ሠሙ
ድም ፡ አስተባበሉ ።

13 ዓድም ፣ ፈርዖንም ፤ የሉጥ ፡ ወን
ድሞችም ፤ (1)

14 የአይከት ፡ ሰዎችም ፤ የቱብበዕ ፡
ሕዝቦችም ፡ ሁሉም ፡ መልክተ
ኞቹን ፡ አስተባበሉ ፤ ዛቻዬም ፡
ተረጋገጠባቸው ።

15 በፊተኛው ፡ መፍጠር ፡ ደከምን ?
በውነቱ ፡ እነሱ ፡ ከአዲስ ፡ መፍ
ጠር ፡ (1) በመጠራጠር ፡ ውስጥ ፡
ናቸው ።

16 ሰውንም ፡ ነፍሱ ፡ (በሐሳቡ) ፡
የምታጫውተውን ፡ የምናውቅ ፡
ስንኾን ፣ በእርግጥ ፡ ፈጠርነው ፤
እኛም ፡ ከደም ፡ ጋኑ ፡ ጅማት ፡
ይበልጥ ፡ ወደርሱ ፡ ቅርብ ፡ ነን ።

17 ሁለቱ ፡ ቃል ፡ ተቀባዮች ፡ (መላ
እክት) ፣ ከቀኝና ፡ ከግራ ፡ ተቀ
ማጮች ፡ ኾነው ፡ በሚቀበሉ ፡
ጊዜ ፡ (አስታውስ) ።

18 ከቃል ፡ ምንም ፡ አይናገርም ፣
በአጠገቡ ፡ ተጠባባቂና ፡ ዝግጁ ፡
የኾኑ ፡ (መላእክት) ፡ ያሉበት ፡
ቢኾን ፡ እንጅ ።

19 የሞትም ፡ መከራ ፡ እውነቱን ፡
ነገር ፡ ታመጣለች ፤ (ሰው ፡ ሆይ)፡
—ይህ ፡ ያ ፡ ከርሱ ፡ ትሸሸው ፡
የነበርከው ፡ ነው ፡ (ይባላል) ።

20 በቀንዱም ፡ ውስጥ ፡ ይነፋል ፤
ያ ፡ (ቀን) ፡ የዛቻው ፡ (መፈጸ
ሚያ) ፡ ቀን ፡ ነው ።

21 ነፍስም ፡ ሁሉ ፡ ከርሷ ፡ ጋር ፡
ነጂና ፡ መስካሪ ፡ ያለባት ፡ ኾና ፡
ትመጣለች ።

22 ከዚህ ፡ ነገር ፡ በእርግጥ ፡ በዝን
ጋቴ ፡ ውስጥ ፡ ነበርክ ፤ ሺፋን
ህንም ፡ ካንተ ፡ ላይ ፡ ገለጥንልህ ፤
ስለዚህ ፡ ዛሬ ፡ ዓይንህ ፡ ስለ
ታም ፡ ነው ፡ (ይባላል) ።

1 የተላከባቸው ፡ ሰዎች ፡

1 ከበሰበሱ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ከመፈጠራ
ቸው ።

23 ቁራኛውም ፡ (መልአክ) ፡ ይህ ፡ ያ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ቀራቢ ፡ ነው ፡ ይላል ።

24 ሞገደኛ ፡ ከሓዲን ፡ ሁሉ ፡ በገሀነም ፡ ውስጥ ፡ ጣሉ ።

25 ለበጎ ፡ ሥራ ፡ ከልካይ ፡ በዳይ ፡ ተጠራጣሪ ፡ የኾነን ፡ ሁሉ ፤ (ጣሉ) ።

26 ያንን ፡ ከአላህ ፡ ጋር ፡ ሌላን ፡ አምላክ ፡ ያደረገውን ፡ በብርቱ ፡ ቅጣት ፡ ውስጥ ፡ ጣሉት ፤ (ይባላል) ።

27 ቁራኛው ፡ (ሰይጣን) ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ አላሳሳትኩትም ፤ ግን ፡ (ራሱ) ፡ በሩቅ ፡ ስሕተት ፡ ውስጥ ፡ ነበር ፡ ይላል ።

28 (አላህ) ፡ ወደናንተ ፡ ዛቻን ፡ በእርግጥ ፡ ያስቀደምኩ ፡ ስኾን ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ አትጨቃጨቁ ፡ ይላቸዋል ።

29 ቃሉ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ አይለወጥም ፤ እኔም ፡ ለባሮቼ ፡ ፈጽሞ ፡ በዳይ ፡ አይደለሁም ፡ (ይላቸዋል) ።

30 ለገሀነም ፡ ሞላሽን ? የምንልበትንና ፡ ጭማሪ ፡ አለን ? የምትልበትን ፡ ቀን ፡ (አስጠንቅቃቸው) ።

31 ገነትም ፡ አላህን ፡ ለፈሩት ፡ እሩቅ ፡ ባልኾነ ፡ስፍራ ፡ ትቅቀረባለች ።

32 ይህ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ተመላሽና ፡ (ሕግጋቱን) ፡ ጠባቂ ፡ ለኾነ ፡ ሁሉ ፡ የተቀጠራችሁት ፡ ነው ፡ (ይባላሉ) ።

33 አልረሕማንን ፡ በሩቁ ፡ ኾኖ ፡ ለፈራና ፡ በንጹሕ ፡ ልብ ፡ ለመጣ፡ (ትቅቀረባለች) ።

34 በሰላም ፡ ግቧት ፡ ይህ ፡ የመዘውተሪያ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ (ይባላሉ) ።

35 ለነርሱ ፡ በውስጧ ፡ ሲኾኑ ፡ የሚሹት ፡ ሁሉ ፡ አላቸው ፤ እኛም ፡ ዘንድ ፡ ጭማሪ ፡ አልለ ።

36 ከነርሱም ፡ (ከቁረይሾች) ፡ በፊት፡ ከክፍለ ፡ ዘመናት ፡ ሕዝቦች ፡ ብዙዎችን ፡ እነርሱ ፡ በኀያልነት ፡ ከነርሱ ፡ ይበልጥ ፡ የበረቱ ፡ የኾኑትን ፡ (ማምለጫ ፡ ፍለጋ) ፡ በየአገሮቹም ፡ የመረመሩትን ፡ አጥፍተናል ፤ ማምለጫ ፡ አለን ?

37 በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ለርሱ ፡ ልብ ፡ ላለው ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ (በልቡ)፡ የተጣደ ፡ ኾኖ ፡ (ወደሚነበብለት) ፡ ጆሮውን ፡ ለጣለ ፡ ሰው ፡ ግሣጼ ፡ አለበት ።

38 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ በመካከላቸው ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ በስድስት ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ በእርግጥ ፡ ፈጠርን ፤ ድካምም ፡ ምንም ፡ አልነካንም ።

39 በሚሉትም ፡ ላይ ፡ ታገሥ ፤ ጌታህንም ፡ ከማመስገን ፡ ጋር ፡ ፀሐይ ከመውጣቷ ፡ በፊት ፡ ከመግባቷም በፊት ፡ አወድሰው ።

40 ከሌሊቱም ፡ አወድሰው ፡ ከስግደቶችም ፡ በኋላዎች ፡ (አወድሰው) ።

41 (የሚነገርህን) ፡ አዳምጥም ፤ ጠሪው ፡ ከቅርብ ፡ ስፍራ ፡ በሚጠራበት ፡ ቀን ፡ (ከመቃብራቸው ፡ ይወጣሉ) ።

42 ጩኸቲቱን ፡ በውነት ፡ የሚሰሙበት ፡ ቀን ፡ ያ ፡ (ከመቃብር) ፡ የመውጫው ፡ ቀን ፡ ነው ።

43 እኛ ፡ እኛው ፡ ሕያው ፡ እናደርጋለን ፤ እንገድላለንም፤ መመለሻም ፡ ወደኛ ፡ ብቻ ፡ ነው ።



44 የሚፈጥኑ ፡ ኾነው ፡ ምድር ፡ ከነርሱ ፡ ላይ ፡ የምትሰነጣጠቅበት ፡ ቀን ፡ (የመውጫው ፡ ቀን ፡ ነው) ። ይህ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ገር ፡ የኾነ ፡ መሰብሰብ ፡ ነው ።

45 እኛ ፡ የሚሉትን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነን ፤ አንተም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ አስገዳጅ ፡ አይደለህም ፤ ስለዚህ ፡ ዛቻየን ፡ የሚፈራን ፡ ሰው ፡ በቁርአን ፡ አስታውስ ።

## ምዕራፍ ፡ 51 ፡ አል-ዛሪያት ፡ ክፍል ፡ 26 ።

51ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ዛሪያት ፡ (የበታኞች ፡ ምዕራፍ) ፤ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 60 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው፡

1 መበተንን ፡ በታኞች ፡ በኾኑት ፡ (ነፋሶች) ፤

2 ከባድ ፡ (ዝናምን) ፡ ተሸካሚዎች፡ በኾኑትም ፡ (ደመናዎች) ፤

3 ገር ፡ (መንሻለልን) ፡ ተንሻላዮች ፡ በኾኑትም ፡ (መርከቦች) ፤

4 ነገርን ፡ ሁሉ ፡ አከፋፋዮች ፡ በኾኑትም ፡ (መላእክት) ፡ እምላለሁ ።

5 የምትቀጠሩት ፡ (ትንሣኤ) ፡ እውነት ፡ ነው ።

6 (እንደየሥራው) ፡ ዋጋን ፡ ማግኘትም ፤ ኋኝ ፡ ነው ፤ (የማይቀር ፡ ነው) ።

7 የ(ከዋክብት) ፡ መንገዶች ፡ ባለ ፡ ቤት ፡ በኾነችው ፡ ሰማይ ፡ እምላለሁ ።

8 እናንተ ፡ (የመካ ፡ ሰዎች) ፡ በተለያየ ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ ናችሁ ፤

9 ከርሱ ፡ የሚዝዞር ፡ ሰው ፡ ይዝዞራል ።

10 በግምት ፡ የሚናገሩ ፡ ውሸታሞች ተረገሙ ፤

11 እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ በሚሸፍን ፡ ስሕተት ፡ ውስጥ ፡ ዘንጊዎች ፡ የኾኑት ።

12 የዋጋ ፡ መስጫው ፡ ቀን ፡ መቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይጠይቃሉ ።

13 (እነርሱ) ፡ በእሳት ፡ ላይ ፡ በሚፈተኑበት ፡ ቀን ፡ ነው ።

14 መከራችሁን ፡ ቅመሱ ፤ ይህ ፡ ያ ፡ በርሱ ፡ ትቻኮሉበት ፡ የነበራችሁት ፡ ነው ፡ (ይባላሉ) ።

15 አላህን፡ፈሪዎቹ፡በአትክልቶችና፡ በምንጮች ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።

16 ያንን ፡ ጌታቸው ፡ የሰጣቸውን ፡ ተቀባዮች ፡ ኾነው ፤ (በገነት ፡ ውስጥ ፡ ይኾናሉ) ። እነርሱ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ መልካም ፡ ሠሪዎች ፡ ነበሩና ።

17 ከሌሊቱ ፡ ጥቂትን ፡ ብቻ ፡ ይተኙ ፡ ነበሩ ።

18 በሌሊቱ ፡ መጨረሻዎችም ፡ እነሱ ፡ ምሕረትን ፡ ይለምናሉ ፤

19 በገንዘቦቻቸውም ፡ ውስጥ ፡ ለለማኝና ፡ (ከልመና) ፡ ለተከለከለም ፡ (በችሮታቸው) ፡ መብት ፡ አልለ ።

20 በምድርም ፡ ውስጥ ፡ ለሚያረጋግጡ ፡ ሰዎች ፡ ምልክቶች ፡ አልሉ ።

21 በነፍሶቻችሁም ፡ ውስጥ ፡ (ምልክቶች ፡ አልሉ) ፣ ታዲያ ፡ አትመለከቱምን ?

22 ሲሳያችሁም ፡ የምትቀጠሩትም ፡ (ፍዳና ፡ ምንዳ) ፡ በሰማይ ፡ ውስጥ ነው ።

23 በሰማይና ፡ በምድር ፡ ጌታም ፡ እምላለሁ ፡ እርሱ ፡ እናንተ ፡ እንደምትናገሩት ፡ ብጤ ፡ እርግጠኛ ፡ ነው ። (1)

24 የተከበሩት ፡ የኢብራሂም ፡ እንግዶች ፡ ወሬ ፡ መጥቶሃልን ?

25 በርሱ ፡ ላይ ፡ በገቡና ፡ ሰላም ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፣ ሰላም ፣ ያልታወቃችሁ ፡ ሕዝቦች ፡ ናችሁ ፣ አላቸው ።

26 ወደ ፡ ቤተሰቡም ፡ ተዘነበለ ፣ ወዲያውም ፡ የሰባ ፡ወይፈንን ፡ አመጣ ።

27 ወደነርሱም ፡ (አርዶና ፡ ጠብሶ) ፡ አቀረበው ፣ አትበሉምወይ ? አላቸው ።

28 ከነርሱ ፡ መፍራትንም ፡ በልቡ ፡ አሳደረ ። አትፍራ ፡ አሉት ፣ በዐዋቂ ፡ ወጣት ፡ ልጅም ፡ አበሰሩት ።

29 ሚስቱም ፡ እየጮኸች ፡ መጣች ፣ ፊቷንም ፡ መታች ፣ መካን ፡ አሮጊት ፡ ነኝ ፡ አለችም ።

1 በንግግራችሁ ፡ እንደማትጠራጠሩ ፡ አትጠራጠሩበት ።

30 እንደዚኸሽ ፡ ጌታሽ ፡ ብሏል ፣ እነሆ ፡ እርሱ ፡ ጥበበኛ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ፡ አሏት ።

★ ★ ★

31 እላንተ ፡ መልክተኞች ፡ ሆይ ፡ ታዲያ ፡ ነገራችሁ ፡ ምንድን ፡ ነው ? አላቸው ።

32 (እነርሱም) ፡ አሉ ፡—እኛ ፡ ወደ ፡ አመጠኞች ፡ ሕዝቦች ፡ ተልከናል ።

33 በነርሱ ፡ ላይ ፡ ከጭቃ ፡ የኾኑን ፡ ደንጊያዎች ፡ ልንለቅባቸው ፡ (ተላክን) ።

34 በጌታህ ፡ ዘንድ ፡ ለድንበር ፡ አላፊዎቹ ፡ (በየስማቸው) ፡ ምልክት ፡ የተደረገባት ፡ ስትኾን ።

35 ከምእምናንም ፣ በርሷ ፡ (በከተማቸው) ፡ ውስጥ ፡ የነበሩትን ፡ አወጣን ።

36 በውስጧም ፡ ከሙስሊሞች፡ ከአንድ ፡ ቤት ፡ (ቤተሰቦች) ፡ በስተቀር ፡ አላገኘንም ።

37 በውስጧም ፡ ለነዚያ ፡ አሳማሚውን ፡ ቅጣት ፡ ለሚፈሩት ፡ ምልክትን ፡ አስቀረን ።

38 በሙሳም ፡ (ወሬ) ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ፊርዖን ፡ በግልጽ ፡ ማስረጃ ፡ በላክነው ፡ ጊዜ ፡ (ምልክትን ፡ አደረግን) ።

39 ከድጋፉ ፡ (ከሰራዊቱ) ፡ ጋርም ፡ (ከእምነት) ፡ ዞረ ፣ (እርሱ) ፡ ድግምተኛ ፡ ወይም ፡ ዕብድ ፡ ነው ፡ አለም ።

40 እርሱንም ፡ ሰራዊቱንም ፡ ያዝናቸው ፣ እርሱ ፡ ተወቃሽ ፡ ሲኾን በባሕር ፡ ውስጥም ፡ ጣልናቸው ።



41 በዓድም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ መካንን ፡ ነፋስ ፡ በላክን ፡ ጊዜ ፡ (ምልክት ፡ አልለ) ።

42 በላዩ ፡ ላይ ፡ የመጣችበትን ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ በሰበሰ ፡ አጥንት ፡ ያደረገችው ፡ ብትኾን ፡ እንጂ ፡ አትተወውም ።

43 በሠሙድም ፡ ለነርሱ፡ እስከ፡ ጊዜ፡ (ሞታችሁ) ፡ ድረስ ፡ ተጣቀሙ ፡ በተባሉ ፡ ጊዜ ፡ (ምልክት ፡ አልለ) ።

44 ከጌታቸው ፡ ትእዛዝም ፡ ኰሩ ፣ እነርሱም ፡ እያዩ ፡ ጩኸት ፡ ያዘቻቸው ።

45 መቆምንም ፡ ምንም ፡ አልቻሉም፣ የሚረዱም ፡ አልነበሩም ።

46 የኑሕንም ፡ ሕዝቦች ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ (አጠፋን) ፣ እነርሱ ፡ አመጠኞች ፡ ሕዝቦች ፡ ነበሩና ።

47 ሰማይንም ፡ በኀይል ፡ ገነባናት ፣ እኛም ፡ በእርግጥ ፡ ቻዮች ፡ ነን ።

48 ምድርንም ፡ ዘረጋናት ፣ ምን ፡ ያማርንም ፡ ዘርጊዎች ፡ (ነን !)

49 ትገነዘቡም ፡ ዘንድ ፡ ከነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ሁለት ፡ (ተቃራኒ) ፡ ዓይነትን ፡ ፈጠርን ፣

50 ወደ ፡ አላህም ፡ ሺሹ ፣ እኔ ፡ ለናንተ ፡ ከርሱ ፡ ግልጽ ፡ አስጠንቃቂ ፡ ነኝና ፡ (በላቸው) ።

51 ከአላህም ፡ ጋር ፡ ሌላን ፡ አምላክ ፡ አታድርጉ ፣ እኔ ፡ ለናንተ ፡ ከርሱ፡ (የተላክሁ) ፡ ግልጽ ፡ አስፈራሪ ፡ ነኝና ።

52 (ነገሩ) ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፣ እነዚያን ፡ ከነርሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩትን፡ ከመልክተኛ ፡ ማንም ፡ አልመጣቸውም ፡ (እርሱ) ፡ ድግምተኛ ፡ ወይም ፡ ዕብድ ፡ ነው ፡ ያሉ ፡ ቢኾኑ ፡ እንጂ ።

53 በርሱ ፡ (በዚህ ፡ ቃል) ፡ አደራ ፡ ተባብለዋልን ? አይደለም ፣ እነርሱ ፡ ጥጋበኞች ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ።

54 ከነሱም ፡ (ክርክር) ፡ ዘወር ፡ በል ፣ (ተዋቸው) ፣ አንተ ፡ ምንም ፡ ተወቃሽ ፡ አይደለህምና ።

55 ገሥጽም ፣ ግሣጼ ፡ ምእምናንን ፡ ትጠቅማለችና ።

56 ጋኔንንና ፡ ሰውንም ፡ ሊግገዙኝ ፡ እንጅ ፡ ለሌላ ፡ አልፈጠርኋቸውም ።

57 ከነሱም ፡ ምንም ፡ ሲሳይ ፡ አልፈልግም ፣ ሊመግቡኝም ፡ አልሻም ።

58 አላህ ፡ እርሱ ፡ ሲሳይን ፡ ሰጪ ፡ የብርቱ ፡ ኀይል ፡ ባለ ፡ ቤት ፡ ነው ።

59 ለነዚያም ፡ ለበደሉት ፡ እንደ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ፋንታ ፡ ብጤ ፡ (የቅጣት) ፡ ፋንታ ፡ አላቸው ፣ ስለዚህ ፡ አያስቸኩሉኝ ።

60 ለነዚያም ፡ ለካዱት ፡ ከዚያ ፡ ከሚቀጠሩት ፡ ቀናቸው ፡ ወዮላቸው ።

52ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ጡር ፡ (የጡር ፡ ምዕራፍ) ፤ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 49 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 በጡር ፡ (ጋራ) ፡ እምላለሁ ።

2 በተጻፈው ፡ መጽሐፍም ።

3 በተዘረጋ ፡ ብራና ፡ ላይ ፤ (በተጻፈው) ።

4 በደመቀው ፡ ቤትም ።

5 ከፍ ፡ በተደረገው ፡ ጣራም ።

6 በተመላው ፡ ባሕርም ፡ እምላለሁ ።

7 የጌታህ ፡ ቅጣት ፡ በእርግጥ ፡ ወዳቂ ፡ ነው ፤ (የማይቀር ፡ ነው) ።

8 ለርሱ ፡ ምንም ፡ ገፍታሪ ፡ የለውም ።

9 ሰማይ ፡ ብርቱ ፡ መዞርን ፡ በምትዞርበት ፡ ቀን ፡ (ይኾናል) ።

10 ተራራዎችም ፡ መኼድን ፡ በሚኼዱበት ፡ (ቀን) ።

11 ለአስተባባዮችም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ወዮላቸው ።

12 ለነዚያ ፡ እነርሱ ፡ በውሸት ፡ ውስጥ ፡ የሚጫወቱ ፡ ለኾኑት ።

13 ወደ ፡ ገሀነም ፡ እሳት ፡ በኀይል ፡ መግገፍተርን ፡ በሚግገፈተሩበት ፡ ቀን ፤

14 ይህች ፡ ያቺ ፡ በርሷ ፡ ታስተባብሉባት ፡ የነበራችሁት ፡ እሳት ፡ ናት ።

15 ይህ ፡ (ፊት ፡ ትሉ ፡ እንደነበራችሁት) ፡ ድግምት ፡ ነውን ? ወይስ ፡ እናንተ ፡ አታዩምን ?

16 ግቧት ፤ ታገሡም ፤ ወይም ፡ አትታገሡ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ እኩል ፡ ነው ፤ የምትመነዱት ፡ ትሠሩት ፡ የነበራችሁትን ፡ (ፍዳ) ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ (ይባላሉ) ።

17 አላህን ፡ ፈሪዎቹ ፡ በእርግጥ ፡ በገነቶችና ፡ በጸጋ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።

18 ጌታቸው ፡ በሰጣቸው ፡ ፀጋ ፡ ተደሳቾች ፡ ኾነው ፡ (በገነት ፡ ውስጥ ፡ ናቸው) ። የገሀነምንም ፡ ስቃይ ፡ ጌታቸው ፡ ጠበቃቸው ።

19 ትሠሩት ፡ በነበራችሁት ፡ ምክንያት ፡ ተደሳቾች ፡ ኾናችሁ ፡ ብሉ ፤ ጠጡም ፤ (ይባላሉ) ።

20 በተደረደሩ ፡ አልጋዎች ፡ ላይ ፡ ተደጋፊዎች ፡ ኾነው ፡ (በገነት ፡ ይኖራሉ) ። ዓይናማዎች ፡ በኾኑ ፡ ነጫጭ ፡ ሴቶችም ፡ እናጠናዳቸዋለን ።

21 እነዚያም ፡ ያመኑትና ፡ ዝርያቸውም ፡ በእምነት ፡ የተከተለቻቸው ፡ ዝርያቸውን ፡ በነሱ ፡ እናስጠጋለን ፤ ከሥራቸውም ፡ ምንንም ፡ አናጐድልባቸውም ፤ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ተያዢ ፡ ነው ።

22 ከሚሹትም ፡ ሁሉ ፡ እሸትንና ፡ ስጋን ፡ እንጨምርላቸዋለን ።

23 በውስጧ ፡ መጠጥን ፡ ይሰጣጣሉ፤ በውስጧ ፡ ውድቅ ፡ ንግግርና ፡ መውወንጀልም ፡ የለም ።



24 ለነርሱም ፡ የኾኑ ፡ ወጣቶች ፡ ልክ ፡ የተሸፈነ ፡ ሉል ፡ መስለው ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ (ለማሳለፍ) ፡ ይዘዋወራሉ ።

25 የሚጠያየቁ ፡ ኾነውም ፡ ከፊላቸው ፡ በከፊሉ ፡ ላይ ፡ ይዞራል ።

26 እኛ ፡ ፊት ፡ በቤተሰቦቻችን ፡ ውስጥ ፡ (ከቅጣት) ፡ ፈሪዎች ፡ ነበርን ፡ ይላሉ ።

27 አላህም ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ለገሰ ፤ የመርዛም ፡ እሳት ፡ ቅጣትንም ፡ ጠበቀን ።

28 እኛ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንለምነው ፡ ነበርን ፤ እነሆ ፡ እርሱ ፡ በጎ ፡ ዋይ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ፡ (ይላሉ) ።

29 (ሰዎችን) ፡ አስታውስም ፤ አንተም ፡ በጌታህ ፡ ጸጋ ፡ ምክንያት ፡ ጠንቋይም ፡ ዕብድም ፡ አይደለህም ።

30 ይልቁንም ፡ የሞትን ፡ አደጋ ፡ በርሱ ፡ የምንጠባበቅበት ፡ የኾነ፡ ባለ ፡ ቅኔ ፡ ነው ፡ ይላሉን ?

31 ተጠባበቁ ፤ እኔም ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ከሚጠባበቁት ፡ ነኝ ፡ በላቸው ።

32 አእምሮዎቻቸው ፡ በዚህ ፡ ያዟቸዋልን ? አይደለም ፡ በውነቱ ፡ እነርሱ ፡ ወሰን ፡ አላፊዎች ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ።

33 ወይም ፡ ቀጠፈው ፡ ይላሉን ? አይደለም ፤ በውነቱ ፡ አያምኑም ።

34 እውነተኞችም ፡ ቢኾኑ ፡ መሰሉ ፡ የኾነን ፡ ንግግር ፡ ያምጡ ።

35 ወይስ ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ (ፈጣሪ) ፡ ተፈጠሩን ? ወይስ ፡ እነርሱ ፡ ፈጣሪዎች ፡ ናቸውን ?

36 ወይስ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ ፈጠሩን ? አይደለም ፡ አያረጋግጡም ።

37 ወይስ ፡ የጌታህ ፡ ግምጃ ፡ ቤቶች ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ ናቸውን ? ወይስ ፡ እነሱ ፡ አሸናፊዎች ፡ ናቸውን ?

38 ወይስ ፡ ለነሱ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ (ከሰማይ) ፡ የሚያዳምጡበት ፡ መሰላል ፡ አላቸውን ? አድማጫቸውም ፡ (ሰማሁ ፡ ቢል) ፡ ግልጽን ፡ አስረጅ ፡ ያምጣ ።

39 ወይስ ፡ ለርሱ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ አሉትን ? ለናንተም ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ አሏችሁን ?

40 ወይስ ፡ ዋጋን ፡ ትጠይቃቸዋለህን ? ስለዚህ ፡ እነሱ ፡ ከዕዳው ፡ የተከበዱ ፡ ናቸውን ?

41 ወይስ ፡ ሩቁ ፡ ምስጢር ፡ እነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ነውን ? ስለዚህ ፡ እነሱ ፡ ይጽፋሉን ?

42 ወይስ ፡ ተንኮልን ፡ (ባንተ) ፡ ይሻሉን ? እነዚያም ፡ የካዱት ፡ እነሱ ፡ በተንኮል ፡ ተሸናፊዎች ፡ ናቸው።

43 ወይስ ፡ ለነርሱ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አላቸውን ? አላህ ፡ ከሚያጋሩት ፡ ሁሉ ፡ ጠራ ።

44 ከሰማይም ፡ ቁራጭን ፡ (በነሱ ፡ ላይ) ፡ ወዳቂ ፡ ኾኖ ፡ ቢያዩ ፡ ኖሮ ፡ ይህ ፡ የተደራረበ ፡ ደመና ፡ ነው ፡ ይሉ ፡ ነበር ።

45 ያንንም ፡ በርሱ ፡ የሚግገደሉበትን ፡ ቀናቸውን ፡ እስከሚገናኙ ፡ ድረስ ፡ ተዋቸው ።

46 ተንኮላቸው ፡ ከነርሱ ፡ ምንንም ፡ የማይጠቅማቸውንና ፡ እነሱም ፡ የማይረዱበትን ፡ ቀን ፡ (እስከሚገናኙ ፡ ተዋቸው) ።

47 ለነዚያ ፡ ለበደሉትም ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ቅርብ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ፤ (1) ግን ፡ አብዛኛዎቻቸው ፡ አያውቁም ።

48 ለጌታህ ፡ ፍርድም ፡ ታገሥ ፤ አንተ ፡ በጥበቃችን ፡ ውስጥ ፡ ነህና ፤ ጌታህንም ፡ በምትንነሳ ፡ ጊዜ ፡ ከማመስገን ፡ ጋር ፡ አወድሰው ።

49 ከሌሊቱም ፡ አወድሰው ፤ በከዋክብት ፡ መደበቂያ ፡ ጊዜም ፡ (እንጋት ፡ ላይ ፡ አወድሰው) ።

1 በድርቅ ፡ በረኃብ ፡ በጦር ፡ ይሞክራሉ ።

## ምዕራፍ ፡ 53 ፡ አል-ነጅም ። ክፍል ፡ 27 ።

53ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ነጅም ፤ (የኮከብ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 62 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 በኮከብ ፡ እምላለሁ ፡ በወደቀ ፡ (በገባ) ፡ ጊዜ ።

2 ነቢያችሁ ፡ (ሙሐመድ) ፡ አልተሳሳተም ፤ አልጠመመምም ።

3 ከልብ ፡ ወለድም ፡ አይናገርም ።

4 እርሱ ፡ (ንግግሩ) ፡ የሚወረድ ፡ ራእይ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ።

5 ኀይሎቹ ፡ ብርቱው ፡ (መልአክ) ፡ አስተማረው ።

6 የዕውቀት ፡ ባለቤት ፡ የኾነው ፡ (አስተማረው ፤ በተፈጥሮው ፡ ቅርጹ ፡ ኾኖ ፡ በአየር ፡ ላይ) ፡ ተደላደለም።

7 እርሱ ፡ በላይኛው ፡ አድማስ ፡ ኾኖ ።

8 ከዚያም ፡ ቀረበ ፤ ወረደም ።

9 (ከርሱ) ፡ የሁለት ፡ ደጋኖች ፡ ጫፍ ፡ ያህል ፡ ወይም ፡ (ከዚህ) ፡ ይበልጥ ፡ የቀረበ ፡ ኾነም ።

10 ወደ ፡ ባሪያውም ፡ (አላህ) ፡ ያወረደውን ፡ አወረደ ።

11 (ነቢዩም ፡ በዓይኑ) ፡ ያየውን ፡ ልቡ ፡ አልዋሸም ።

12 ታዲያ ፡ በሚያየው ፡ ላይ ፡ ትከራከሩታላችሁን ?

13 በሌላይቱም ፡ መውረድ ፡ ጊዜ ፡ በእርግጥ ፡ አይቶታል ።

14 በመጨረሻይቱ ፡ ቁርቁራ ፡ (1) አጠገብ ፤

15 እርሷ ፡ ዘንድ ፡ መኖሪያይቱ ፡ ገነት ፡ ያለች ፡ ስትኾን ።

16 ቁርቁራይቱን ፡ የሚሸፍን ፡ ነገር ፡ በሚሸፍናት ፡ ጊዜ ፡ (አየው) ።

17 ዓይኑ ፡ (ካየው) ፡ አልተዘነበለም፤ ወሰንም ፡ አላለፈም ።

1 የዕውቀት ፡ ዲካ ፡ በኾነ ፡ ስፍራ ።



18 ከጌታው ፡ ታምራቶች ፡ ታላላቆቹን ፡ በእርግጥ ፡ አየ ።

19 አል-ላትንና ፡ አል-ዑዛን ፡ አያችሁን ?

20 ሦስተኛይቱንም ፡ አነስተኛዋን ፡ መናትን ፡ (1) (አያችሁን ? የምትግገዟቸው ፡ ኃይል ፡ አላቸውን ?)

21 ለናንተ ፡ ወንድ ፡ ለርሱም ፡ ሴት ፡ (ልጅ) ፡ ይኖራልን ?

22 ይህቺ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አድላዊ ፡ ክፍያ ፡ ናት ።

23 እነርሱ ፡ እናንተና ፡ አባቶቻችሁ፡ (አማልክት ፡ ብላችሁ) ፡ የጠራችኋቸው ፡ ስሞች ፡ ብቻ ፡ እንጅ ፡ ምንም ፡ አይደሉም ። አላህ ፡ በርሷ ፡ (መግገዛት) ፡ ምንም ፡ ማስረጃ ፡ አላወረደም ፤ ከጌታቸውም ፡ መምሪያ ፡ የመጣላቸው ፡ ሲኾኑ ፡ ጥርጣሬንና ፡ ነፍሶች ፡ የሚዘነበሉበትን ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይከተሉም ።

24 ለሰው ፡ የተመኘው ፡ ሁሉ ፡ አለውን ?

25 መጨረሻይቱም ፡ መጀመሪያይቱም ፡ (ዓለም) ፡ የአላህ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

26 በሰማያት ፡ ውስጥ ፡ ካለ ፡ መልአክም ፡ ብዙዎች ፡ (ሊማለዱለት) ፡ ለሚሻውና ፡ ለሚወደው ፡ ሰው ፡ ከፈቀደ ፡ በኋላ ፡ ቢኾን ፡ እንጅ ፡ ምልጃቸው ፡ ምንም ፡ አትጠቅምም ።

27 እነዚያ ፡ በመጨረሻይቱ ፡ ዓለም ፡ የማያምኑት ፡ መላእክትን ፡ በሴት ፡ አጠራር ፡ ይጠራሉ ።

1 እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ የጣዖታት ፡ ስሞች ፡ ናቸው ።

28 ለነሱም ፡ በርሱ ፡ ምንም ፡ ዕውቀት ፡ የላቸውም ፤ ጥርጣሬን ፡ እንጅ ፡ ሌላን ፡ አይከተሉም ፤ ጥርጣሬም ፡ ከእውነት ፡ ምንም ፡ አያብቃቃም ።

29 ከግሣጼያችንም ፡ (ከቁርአን) ፡ ከሸሸና ፡ አነስተኛይቱን ፡ ሕይወት ፡ እንጅ ፡ ሌላን ፡ ከማይሻ ፡ ሰው ፡ ዙር ፡ (ተወው) ።

30 ይህ ፡ (አነስተኛይቱን ፡ ሕይወት ፡ መምረጥ) ፡ ከዕውቀት ፡ ዲካቸው፡ ነው ፤ ጌታህ ፡ እርሱ ፡ ከመንገዱ ፡ የተሳሳተውን ፡ በእርግጥ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ የቀናውን ፡ ሰው፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

31 በሰማያት ፡ ያለውና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ የአላህ ፡ ነው ። እነዚያን ፡ ያጠፉትን ፡ በሠሩት ፡ ሊቀጣ ፡ እነዚያን ፡ ያሳመሩትንም ፡ በመልካሚቱ ፡ (ገነት) ፡ ሊመነዳ ፡ (የጠመመውንና ፡ የቀናውን ፡ ያውቃል) ።

32 (እነርሱ) ፡ እነዚያ ፡ የኃጢአትን ፡ ታላላቆችና ፡ አስጠያፊዎቹን ፡ የሚርቁ ፡ ናቸው ፤ ግን ፡ ትናንሾቹ ፡ የሚማሩ ፡ ናቸው ። ጌታህ ፡ ምሕረተ ፡ ሰፊ ፡ ነውና ፤ ከምድር ፡ በፈጠራችሁ ፡ ጊዜ ፡ እናንተም ፡ በእናቶቻችሁ ፡ ሆዶች ፡ ውስጥ ፡ ሽሎች ፡ በኾናችሁ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ በናንተ ፡ (ኹኔታ)፡ ዐዋቂ ፡ ነው ። ነፍሶቻችሁንም ፡ አታወድሱ ፡ እርሱ ፡ የሚፈራውን ፡ ሰው ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

33 ያንን ፡ (ከእምነት) ፡ የዞረውን ፡ አየህን ?

34 ጥቂትን ፡ የሰጠውንና ፡ ያቋረጠውንም ፡ (አየህን?)

35 የሩቁ ፡ ምስጢር ፡ ዕውቀት ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡ አልለን ? ስለዚህ ፡ እርሱ ፡ ያያልን ?

36 ይልቁንም ፡ በዚያ ፡ በሙሳ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ አልተነገረምን ?

37 በዚያም ፡ (የታዘዘውን) ፡ በፈጸመው ፡ በኢብራሂም ፡ (ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ አልተነገረምን ?)

38 (እርሱም ፡ ኃጢአት) ፡ ተሸካሚ፡ ነፍስ ፡ የሌላይቱን ፡ ነፍስ ፡ ኃጢአት ፡ አትሸከምም ።

39 ለሰውም ፡ ሁሉ ፡ የሠራው ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ የለውም ።

40 ሥራውም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይታያል ።

41 ከዚያም ፡ ሙሉውን ፡ ምንዳ ፡ ይመነዳዋል ።

42 መጨረሻውም ፡ ወደ ፡ ጌታህ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

43 እነሆ ፡ እርሱም ፡ አስሳቀ ፤ አስለቀሰም ።

44 እነሆ ፡ እርሱም ፡ ገደለ ፤ አስነሳም ።

45 እርሱም ፡ ሁለቱን ፡ ዓይነቶች ፡ ወንድንና ፡ ሴትን ፡ ፈጠረ ።

46 ከፍትወት ፡ ጠብታ ፡ (በማኅፀን ፡ ውስጥ) ፡ በምትፈሰስ ፡ ጊዜ ፤

47 የኋለኛይቱም ፡ ማስነሳት ፡ በርሱ፡ ላይ ፡ ነው ።

48 እነሆ ፡ እርሱም ፡ አከበረ ፤ ጥሪተኛም ፡ አደረገ ።

49 እነሆ ፡ እርሱም ፡ የሺዕራ ፡ (1) ጌታ ፡ ነው ።

50 እነሆ ፡ እርሱም ፡ የፊተኛይቱን ፡ ዓድ ፡ አጥፍቷል ።

51 ሠሙድንም ፡ (አጥፍቷል) ፤ አላስቀረምም ።

52 በፊትም ፡ የኑሕን ፡ ሕዝቦች ፡ (አጥፍቷል) ፤ እነሱ ፡ በጣም ፡ በደለኞችና ፡ እጅግ ፡ የጠመሙ ፡ እነሱ ፡ ነበሩና ።

53 የተገለበጠችውንም ፡ ከተማ ፡ ደፋ ።

54 ያለበሳትንም ፡ አለበሳት ።

55 ከጌታህም ፡ ጸጋዎች ፡ በየትኛው ፡ ትጠራጠራለህ ?

56 ይህ ፡ ከፊተኞቹ ፡ አስፈራሪዎች ፡ (ጐሳ) ፡ የኾነ ፡ አስፈራሪ ፡ ነው ።

57 ቀራቢይቱ ፡ (ኀልፈተ ፡ ዓለም) ፡ ቀረበች ።

58 ለርሷ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ገላጭ ፡ የላትም ።

59 ከዚህ ፡ ንግግር ፡ ትደነቃላችሁን ?

60 ትስቃላችሁምን ? አታለቅሱምን?

61 እናንተም ፡ ዘንጊዎች ፡ ናችሁ ።

62 ለአላህም ፡ ስገዱ ፡ ተገዙትም ።

---

1 የሚያመልኩባት ፡ ደማቅ ፡ ኮከብ ፡ ናት ።



54ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ቀመር ፤ (የጨረቃ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 55 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 ሰዓቲቱ ፡ (የትንሣኤ ፡ ቀን) ፡ ተቃረበች ፤ ጨረቃም ፡ ተገመሰ ፤

2 ታምርንም ፡ ቢያዩ ፡ (ከእምነት) ፡ ይዞራሉ ፤ (ይህ) ፡ ዘውታሪ ፡ ድግምት ፡ ነውም ፡ ይላሉ ።

3 አስተባበሉም ፤ ዝንባሌዎቻቸውንም ፡ ተከተሉ ፤ ነገርም ፡ ሁሉ ፡ (ወሰን ፡ አለው) ፤ ረጊ ፡ ነው ።

4 ከዜናዎችም ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ መገሠጥ ፡ ያለበት ፡ ነገር ፡ በእርግጥ ፡ መጣላቸው ።

5 ሙሉ ፡ የኾነች ፡ ጥበብ ፡ (መጣቻቸው) ፡ ግን ፡ አስፈራሪዎቹ ፡ አያብቃቁም ።

6 ከነርሱም ፡ ዙር ። ጠሪው ፡ (መልአክ) ፡ ወደ ፡ ፡ አስደንጋጭ ፡ ነገር የሚጠራበትን ፡ ቀን ፡ (አስታውስ) ።

7 ዓይኖቻቸው ፡ ያቀረቀሩ ፡ ኾነው፡ ፍጹም ፡ የተበተነ ፡ አንበጣ ፡ መስለው ፡ ከመቃብሮቹ ፡ ይወጣሉ ።

8 ወደ ፡ ጠሪው ፡ አንገቶቻቸውን ፡ ሳቢዎች ፡ ቸኳዮች ፡ ኾነው ፡ (ይወጣሉ) ፤ ከሓዲዎቹ ፡ (ያን ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ይላሉ ?) ፡ ይህ ፡ ብርቱ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

9 ከነሱ ፡ በፊት ፡ የኑሕ ፡ ነገድ ፡ አስተባበለች ። ባሪያችንንም ፡ (ኑሕን) ፡ አስተባበሉ ፤ ዕብድ ፡ ነውም ፡ አሉ ፤ ተገለመጠም ።

10 ጌታውንም ፡ እኔ ፡ የተሸነፍኩ ፡ ነኝና ፡ እርዳኝ ፡ ሲል ፡ ጠራ ።

11 ወዲያውም ፡ የሰማይን ፡ ደጃፎች ፡ በሚንቧቧ ፡ ውሃ ፡ ከፈትን።

12 የምድርንም ፡ ምንጮች ፡ አፈነዳን ፤ ውሃውም ፡ (የሰማዩና ፡ የምድሩ) ፡ በእርግጥ ፡ በተወሰነ ፡ ኹነታ ፡ ላይ ፡ ተገናኘ ።

13 ባለ ፡ ሳንቃዎችና ፡ ባለሚስማሮች ፡ በኾነችም ፡ ታንኳ ፡ ላይ ፡ ጫነው ።

14 በጥበቃችን ፡ ሥር ፡ ኾና ፡ ትንሻለላለች ። ተክዶ ፡ ለነበረው ፡ ሰው ፡ ምንዳ ፡ (ይህንን ፡ ሠራን) ።

15 ታምር ፡ አድርገንም ፡ በእርግጥ ፡ ተውናት ፤ ከተገሣጭም፡ አልለን ?

16 ቅጣቴና ፡ ማስጠንቀቂያዎቼም ፡ እንዴት ፡ ነበሩ ?

17 ቁርአንንም ፡ ለመገንዘብ ፡ በእርግጥ ፡ አገራነው ፤ ተገንዛቢም ፡ አልለን ?

18 ዓድ ፡ አስተባበለች ፤ ቅጣቴና ፡ ማስጠንቀቂያዎቼም ፡ እንዴት ፡ ነበሩ !

19 እኛ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ዘወትር ፡ መናጢ ፡ በኾነ ፡ ቀን ፡ በኀይል ፡ የምትንሻሻ ፡ ነፋስን ፡ ላክንባቸው ።

20 ሰዎቹን ፡ ልክ ፡ ከሥሮቻቸው ፡ የተጐለሰሱ ፡ የዘንባባ ፡ ግንዶች ፡ መስለው ፡ (ከተደበቁበት) ፡ ትነቅላቸዋለች ።

21 ቅጣቴና ፡ ማስጠንቀቂያዎቼም ፡ እንዴት ፡ ነበሩ ?

22 ቁርአንንም ፡ ለማስታወስ ፡ በእርግጥ ፡ አገራነው ፤ ተገሣጭም ፡ አልለን ?

23 ሠሙድ ፡ በአስፈራሪዎቹ ፡ አስተባበለች ።

24 ከኛ ፡ የኾነን ፡ አንድን ፡ ሰው ፡ እንከተለዋለን ? እኛ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በስሕተትና ፡ በዕብደት ፡ ውስጥ፡ ነን ፡ አሉ ።

25 ከኛ ፡ መካከል ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ (ብቻ) ፡ ማስገንዘቢያ ፡ (ራእይ) ፡ ተጣለለትን ? አይደለም ፡ እርሱ ፡ ውሸታም ፡ ኩሩ ፡ ነው ፡ (አሉ) ።

26 ውሸታሙ ፡ ኩሩው ፡ ማን ፡ እንደ ኾነ ፡ ነገ ፡ በእርግጥ ፡ ያውቃሉ ።

27 እኛ ፡ ሴት ፡ ግመልን ፡ ለነርሱ ፡ መፈተኛ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ላኪዎች ፡ ነን ፤ ተጠባበቃቸውም ፤ ታገሥም ።

28 ውሃውም ፡ በመካከላቸው ፡ የተከፈለ ፡ መኾኑን ፡ ንገራቸው ፤ ከውሃ ፡ የኾነ ፡ ፋንታ ፡ ሁሉ ፡ (ተረኞቹ) ፡ የሚጣዱት ፡ ነው ።

29 ጓደኛቸውንም ፡ ጠሩ ፤ ወዲያውም ፡ (ሰይፍን) ፡ ተቀበለ ፤ ወጋትም ።

30 ቅጣቴና ፡ ማስጠንቀቂያዎቼም ፡ እንዴት ፡ ነበሩ ?

31 እኛ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ አንዲትን ፡ ጩኸት ፡ ላክንባቸው ፤ ወዲያውም ፡ ከበረት ፡ አጣሪ ፡ (አጥር) ፡ እንደ ፡ ተሰባበረ ፡ ርግጋፊ ፡ ኾኑ ።

32 ቁርአንንም ፡ ለመገንዘብ ፡ አገራነው ፤ ተገሣጭም ፡ አልለን ?

33 የሉጥ ፡ ሕዝብ ፡ በአስፈራሪዎቹ ፡ አስተባበለች ።

34 እኛ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ጠጠርን ፡ ያዘለች ፡ ነፋስን ፡ ላክን ። የሉጥ ፡ ቤተሰቦች ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ ፤ (እነሱንስ) ፡ በሌሊት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ አዳንናቸው ።

35 ከኛ ፡ በኾነ ፡ ጸጋ ፡ (አዳንናቸው)፤ እንደዚሁ ፡ ያመሰገነን ፡ ሰው ፡ እንመነዳለን ።

36 ብርቱይቱን ፡ አያያዛችንንም ፡ በእርግጥ ፡ አስጠንቀቃቸው ፤ በማስጠንቀቂያዎቹም ፡ ተከራከሩ ።

37 ከእንግዶቹም ፡ እንዲያስመቻቸው ፡ ደጋግመው ፡ ፈለጉት ፤ ወዲያውም ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ አበስን ፤ ቅጣቴንና ፡ ማስጠንቀቂያዎቼንም ቅመሱ ፡ (አልናቸው) ።

38 በማለዳም ፡ ዘውታሪ ፡ የኾነ ፡ ቅጣት ፡ በእርግጥ ፡ ማለደባቸው ።

39 ቅጣቴንና ፡ ማስጠንቀቂያዎችንም ቅመሱ ፡ (ተባሉ) ።

40 ቁርአንንም ፡ ለመገንዘብ ፡ በእርግጥ ፡ አገራነው ፤ ተገሣጭም ፡ አልለን ?

41 የፈርዖንንም ፡ ቤተሰቦች ፡ ማስጠንቀቂያዎች ፡ በእርግጥ ፡ መጡዋቸው ።

42 በታምራቶቻችን ፡ በሁሏም ፡ አስተባበሉ ፤ የብርቱ ፡ ቻይንም ፡ አያያዝ ፡ ያዝናቸው ።

43 ከሓዲዎቻችሁ ፡ ከነዚሃችሁ ፡ በላጮች ፡ ናቸውን ? ወይስ ፡ ለናንተ ፡ በመጽሐፎች ፡ ውስጥ ፡ (የተነገረ) ፡ ነጻነት ፡ አላችሁን ?



44 ወይስ ፡ እኛ ፡ የተረዳን ፡ ክምቹዎች ፡ ነን ፡ ይላሉን ?

45 ክምቹዎቹ ፡ በእርግጥ ፡ ድል ፡ ይመታሉ ፤ ጀርባዎችንም ፡ ያዞራሉ ።

46 ይልቁንም ፡ ሰዓቲቱ ፡ (ትንሣኤ) ፡ ቀጠሮዋቸው ፡ ናት ፤ ሰዓቲቱም ፡ በጣም ፡ የከበደችና ፡ የመረረች ፡ ናት ።

47 አመጠኞች ፡ በስሕተትና ፡ በእሳቶች ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።

48 በእሳት ፡ ውስጥ ፡ በፊቶቻቸው ፡ በሚጐተቱበት ፡ ቀን ፡ የሰቀርን ፡ (1) መንካት ፡ ቅመሱ ፡ (ይባላሉ) ።

49 እኛ ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ በልክ ፡ ፈጠርነው ።

50 ትእዛዛችንም ፡ እንደ ፡ ዓይን ፡ ቅጽበት ፡ አንዲት ፡ (ቃል) ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ።

51 ብጤዎቻችሁንም ፡ በእርግጥ ፡ አጠፋን ፤ ተገሣጭም ፡ አልለን ?

52 የሠሩትም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በመጽሐፎች ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

53 ትንሹም ፡ ትልቁም ፡ ሁሉ ፡ የተጻፈ ፡ ነው ።

54 አላህን ፡ ፈሪዎቹ ፡ በአትክልቶችና ፡ በወንዞች ፡ ውስጥ ፡ ናቸው።

55 (እነሱም ፡ ውድቅ ፡ ቃልና ፡ መውወንጀል ፡ በሌለበት) ፡ በውነት ፡ መቀመጫ ፡ ውስጥ ፡ ቻይ ፡ እሆነው ፡ ንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ ናቸው ።

---

1 ሰቀር ፡ የገሀነም ፡ ስም ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 55 ፡ አል-ረሕማን ። ክፍል ፡ 27 ።

55ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ረሕማን ፤ (የርኅሩሁ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 78 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 አል-ረሕማን ፤

2 ቁርአንን ፡ አስተማረ ።

3 ሰውን ፡ ፈጠረ ።

4 መናገርን ፡ አስተማረው ።

5 ፀሐይና ፡ ጨረቃ ፡ በተወሰነ ፡ ልክ ፡ (ይኼዳሉ) ፤

6 ሐረግና ፡ ዛፍም ፡ (ለርሱ) ፡ ይሰግዳሉ ።

7 ሰማይንም ፡ አጓናት ፤ ትክክለኛነትንም ፡ ደነገገ ።

8 በሚዛን ፡ (ስትመዝኑ) ፡ እንዳትበድሉ ።

9 መመዘንንም ፡ በትክክል ፡ መዝኑ፤ ተመዛኙንም ፡ አታጉድሉ ።

10 ምድርንም ፡ ለፍጡሩ ፡ አደላደላት ።

11 በውስጧ ፡ እሸት ፡ ባለ ፡ ሺፋኖች ፡ የኾኑ ፡ ዘንባባዎችም ፡ ያሉባት ፡ ስትኾን ፤

12 የገለባ ፡ ባለቤት ፡ የኾነ ፡ ቅንጣ
ትም ፤ ባለ ፡ መልካም ፡ መዐዛ ፡
ቅጠሎችም ፡ (ያሉባት ፡ ስትኾን)፡
13 (ሰዎችና ፡ ጋኔኖች ፡ ሆይ) ፡ ከጌ
ታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየትኛው ፡
ታስተባብላላችሁ ?
14 ሰውን ፡ እንደ ፡ ሸክላ ፡ ከሚቅ
ጨለጨል ፡ ደረቅ ፡ ጭቃ ፡ ፈጠ
ረው ።
15 ጃንንም ፡ (1) ከእሳት ፡ ከኾነ ፡
ነበልባል ፡ ፈጠረው ።
16 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
17 የሁለቱ ፡ ምሥራቆች ፡ ጌታ ፤
የሁለቱ ፡ ምዕራቦችም ፡ ጌታ ፡
ነው ።
18 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት ፡
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
19 ሁለቱን ፡ ባሕሮች ፡ የሚገናኙ ፡
ሲኾኑ ፡ ለቀቃቸው ።
20 (እንዳይዋሐዱ) ፡ በመካከላቸው ፡
ጋራጅ ፡ አልለ ፤ (አንዱ ፡ ባንዱ ፡
ላይ) ፡ ወሰን ፡ አያልፉም ፤
21 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት ፡
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
22 ሉልና ፡ መርጃን ፡ ከሁለቱ ፡
(2) ይወጣል ።
23 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
24 እንደ ፡ ጋራዎች ፡ ኾነው ፡ በባ
ሕር ፡ ውስጥ ፡ የተሠሩት ፡ ተን
ሻላዮቹም ፡ (ታንኳዎች) ፡ የርሱ ፡
ናቸው ።
25 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?

1 የጋኔንን ፡ አባት ።
2 ከአንደኛው ፡ ከጨዋማው

26 በርሷ ፡ (በምድር) ፡ ላይ ፡ ያለው ፡
ሁሉ ፡ ጠፊ ፡ ነው ።
27 የልቅናና ፡ የልግሥና ፡ ባለቤት ፡
የኾነው ፡ የጌታህ ፡ ፊትም ፡ ይቀ
ራል ። (አይጠፋም) ።
28 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
29 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡
ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ይለምኑታል ፤
በየቀኑ ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ በሥራ ፡
ላይ ፡ ነው ።
30 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
31 እናንተ ፡ ሁለት ፡ ከባዶች ፡ (ሰዎ
ችና ፡ ጋኔኖች) ፡ ሆይ ፡ ለናንተ ፡
(መቆጣጠር) ፡ በእርግጥ ፡ እና
ስባለን ። (1)
32 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
33 የጋኔንና ፡ የሰው ፡ ጭፍሮች ፡
ሆይ ፡ ከሰማያትና ፡ ከምድር ፡
ቀበሌዎች ፡ መውጣትን ፡ ብት
ችሉ ፡ ውጡ ፤ በስልጣን ፡ እንጅ ፡
አትወጡም ። (ግን ፡ ስልጣን ፡
የላችሁም) ።
34 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
35 በሁለታችሁም ፡ ላይ ፡ ከእሳት ፡
ነበልባል ፡ ጭስም ፡ ይላክባች
ኋል ፤ (ሁለታችሁም) ፡ አትረ
ዱምም ።
36 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
37 ሰማይም ፡ በተሰነጠቀችና ፡ እንደ፡
ጽጌ ፡ ረዳ ፡ እንደታረበ ፡ ቆዳ ፡

1 ሆነ ፡ ብለን ፡ እናስብበታለን ፡ ይህ ፡ ብርቱ ፡
ዛቻ ፡ ነው ።



በኾነች ፡ ጊዜ ፤ (ጭንቁን ፡ ምን፡
አበረታው) ።
38 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
39 በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰውም ፡ ጃንም ፡
ከኃጢአቱ ፡ ገና ፡ አይጠየቅም ።
40 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
41 ከሓዲዎች ፡ በምልክታቸው ፡
ይታወቃሉ ። እናቶቻቸውንና ፡
ጫማዎቻቸውንም ፡ ይያዛሉ ።
42 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ።
43 ይህቺ ፡ ያቺ ፡ አመጠኞች ፡ በርሷ፡
ያስተባብሉባት ፡ የነበረችው ፡
ገሀነም ፡ ናት ፡ (ይባላሉ) ።
44 በርሷና ፡ በጣም ፡ ሞቃት ፡ በኾነ ፡
ፍል ፡ ውሃ ፡ መካከል ፡ ይመላ
ለሳሉ ።
45 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
46 በጌታውም ፡ ፊት ፡ መቆምን ፡
ለፈራ ፡ ሰው ፡ ሁለት ፡ ገነቶች ፡
አሉት ።
47 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
48 የቀንዘሎች ፡ ባለ ፡ ቤቶች ፡ የኾኑ ፡
(ገነቶች ፡ አሉት) ።
49 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
50 በሁለቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚፈሱ ፡
ሁለት ፡ ምንጮች ፡ አልሉ ።
51 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
52 በሁለቱ ፡ ውስጥ ፡ ከፍራፍሬዎች ፡
ሁሉ ፡ ሁለት ፡ ዓይነቶች ፡ (እር
ጥብና ፡ ደረቅ) ፡ አልሉ ።

53 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
54 የውስጥ ፡ ጉስጉሳቸው ፡ ከወፍ
ራም ፡ ሐር ፡ በኾኑ ፡ ምንጣፎች ፡
ላይ ፡ የተመቻቹ ፡ ሲኾኑ፡ (ይን
ፈላሰሳሉ) ፤ የሁለቱም ፡ ገነቶች ፡
ፍሬ ፡ (ለለቃሚ) ፡ ቅርብ ፡ ነው ።
55 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
56 በውስጣቸው ፡ ከበፊታቸው ፡
(ከባሎቻቸው ፡ በፊት) ፡ ሰውም ፡
ጃንም ፡ ያልገሠሣቸው ፡ ዓይናቻ
ቸውን ፡ (በባሎቻቸው ፡ ላይ) ፡
አሳጣሪዎች ፡ (ሴቶች) ፡ አልሉ ።
57 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
58 ልክ ፡ ያቁትና ፡ መርጃን ፡ (1)
ይመስላሉ ።
59 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
60 የበጎ ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ በጎ ፡ እንጅ ፡
ሌላ ፡ ነውን ?
61 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
62 ከሁለቱ ፡ ገነቶችም ፡ ሌላ ፡ ሁለት
ገነቶች ፡ አልሉ ።
63 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
64 ከልምላሜያቸው ፡ የተነሳ ፡ ወደ ፡
ጥቁረት ፡ ያዘነበሉ ፡ ናቸው ።
65 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየት
ኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?
66 በውስጣቸው ፡ ሁለት ፡ የሚን
ፏፏ ፡ ምንጮች ፡ አልሉ ።

1 ለጌጥ ፡ የሚኾኑ ፡ የሚያንጸባርቁ ፡ ክብር ፡
ድንጊያዎች ፡ ናቸው ።

67 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየትኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?

68 በውስጣቸው ፡ ፍራፍሬ ፡ ዘምባባም ፡ ሩማንም ፡ አልለ ።

69 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየትኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?

70 በውስጣቸው ፡ ጠባየ ፡ መልካሞች ፡ መልከ ፡ ውቦች ፡ (ሴቶች) ፡ አልሉ ።

71 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየትኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?

72 በድንኳኖች ፡ ውስጥ ፡ የተጨጐሉ ፡ የዓይኖቻቸው ፡ ጥቁረትና ፡ ንጣት ፡ ደማቅ ፡ የኾኑ ፡ ናቸው ።

73 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየትኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?

74 ከነሱ ፡ በፊት ፡ ሰውም ፡ ጃንም ፡ አልገሠሣቸውም ።

75 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየትኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?

76 በሚያረገርጉ ፡ አረንጓዴ ፡ ምንጣፎችና ፡ በሚያማምሩ ፡ ስጋጃዎች ፡ ላይ ፡ የተደላደሉ ፡ ሲኾኑ ፡ (ይቀመጣሉ) ።

77 ከጌታችሁም ፡ ጸጋዎች ፡ በየትኛው ፡ ታስተባብላላችሁ ?

78 የግርማና ፡ የመክበር ፡ ባለቤት ፡ የኾነው ፡ ጌታህ ፡ ስም ፡ ተባረከ ።

## ምዕራፍ ፡ 56 ፡ አል-ዋቂዓህ ። ክፍል ፡ 27 ።

56ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ዋቂዓህ ፤ (የመከራይቱ ፡ ቀን ፡ ምዕራፍ) ።
በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 96 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 መከራይቱ ፡ በወደቀች ፡ ጊዜ ።

2 ለመውደቋ ፡ አስተባባይ ፡ (ነፍስ) የለችም ።

3 ዝቅ ፡ አድራጊና ፡ ከፍ ፡ አድራጊ ፡ ናት ።

4 ምድር ፡ መናወጥን ፡ በተናወጠች ፡ ጊዜ ።

5 ተራራዎችም ፡ መፍፈርፈርን ፡ በተፈረፈሩ ፡ ጊዜ ፡ (እንደተፈጨ ፡ ዱቄት ፡ በኾኑ ፡ ጊዜ) ።

6 የተበተነ ፡ ብናኝ ፡ በኾኑም ፡ ጊዜ ፡

7 ሦስት ፡ ዓይነቶችም ፡ በኾናችሁ ፡ ጊዜ ፡ (ታዋርዳለች ፤ ታነሳለችም) ።

8 የቀኝ ፡ ጓዶችም ፡ ምን ፡ (የተከበሩ) ፡ የቀኝ ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ።

9 የግራ ፡ ጓዶችም ፡ ምን ፡ (የተዋረዱ) ፡ የግራ ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ።

10 (ለበጎ ፡ ሥራ) ፡ ቀዳሚዎቹም ፡ (ለገነት) ፡ ቀዳሚዎች ፡ ናቸው ።

11 እነዚያ ፡ ባለሟሎቹ ፡ ናቸው ።

12 በመጠቀሚያ ፡ ገነቶች ፡ ውስጥ ፡ ሲኾኑ ።

13 ከፊተኞቹ ፡ ብዙ ፡ ጭፍሮች ፡ ናቸው ።



14 ከኋለኞቹም ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ።

15 በተታቱ ፡ አልጋዎች ፡ ላይ ፡ ይኾናሉ ።

16 በርሷ ፡ ላይ ፡ የተመቻቹና ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የተቅጣጩ ፡ ሲኾኑ ።

17 በነሱ ፡ ላይ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የማያረጁ ፡ ወጣቶች ፡ ልጆች ፡ ይዘዋወራሉ ።

18 ከጠጅ ፡ ምንጭም ፡ በብርጪቆዎችና ፡ በኩስኩስቶች ፡ በጽዋም ፡ (በነሱ ፡ ላይ ፡ ይዞራሉ) ።

19 ከርሷ ፡ የራስ ፡ ምታት ፡ አያገኛቸውም ፤ አይሰክሩምም ።

20 ከሚመርጡትም ፡ ዓይነት ፡ በእሸቶች ።

21 ከሚሹትም ፡ በኾነ ፡ የበራሪ ፡ ሥጋ ፡ (ይዞሩባቸዋል) ።

22 ዓይናማዎች ፡ የኾኑ ፡ ነጫጭ ፡ ቆንጆዎችም፡ አሏቸው።

23 ልክ ፡ እንደተሸፈነ ፡ ሉል ፡ መሰሎች ፡ የኾኑ ።

24 በዚያ ፡ ይሠሩት ፡ በነበሩት ፡ ምክንያት ፡ ዋጋ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ (ይህንን ፡ አደረግንላቸው) ።

25 በውስጥዋ ፡ ውድቅ ፡ ንግግርንና ፡ መውወንጀልን ፡ አይሰሙም ።

26 ግን ፡ ሰላም ፡ መባባልን ፡ (ይሰማሉ) ።

27 የቀኝም ፡ ጓዶች ፡ ምንኛ ፡ (የከበሩ) ፡ የቀኝ ፡ ጓዶች !

28 በተቀፈቀፈ ፡ (እሾህ ፡ በሌለው) ፡ ቁርቁራ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።

29 (ፍሬው) ፡ በተነባበረ ፡ በሙዝ ፡ ዛፍም ።

30 በተዘረጋ ፡ ጥላ ፡ ሥርም ።

31 በሚንቧቧ ፡ ውሃ ፡ አጠገብም ።

32 ብዙ ፡ (ዓይነት) ፡ በኾኑ ፡ ፍራፍሬዎችም ።

33 የማትቋረጥም ፡ የማትከለከልም ፡ የኾነች ።

34 ከፍ ፡ በተደረጉ ፡ ምንጣፎችም ፡ (ሴቶችም ፡ መካከል) ።

35 እኛ ፡ አዲስ ፡ ፍጥረት ፡ አድርገን ፡ (ለነሱ) ፡ ፈጠርናቸው ።

36 ደናግሎችም ፡ አደረግናቸው ።

37 ለባሎቻቸው ፡ ተሽሞርሟሪዎች ፡ እኩያዎች ፡ (አደረግናቸው) ።

38 ለቀኝ ፡ ጓዶች ፡ (አዘጋጀናቸው) ።

39 ከፊተኞቹ ፡ ብዙ ፡ ጭፍሮች ፡ ናቸው ።

40 ከኋለኞቹም ፡ ብዙ ፡ ጭፍሮች ፡ ናቸው ።

41 የግራ ፡ ጓዶችም ፡ ምንኛ ፡ (የተዋረዱ) ፡ የግራ ፡ ጓዶች ! ናቸው ።

42 በመርዛም ፡ ነፋስ ፡ በጣም ፡ በፈላ ፡ ውሃም ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።

43 ከጥቁር ፡ ጭስም ፡ በኾነ ፡ ጥላ ፡ ውስጥ ።

44 ቀዝቃዛም ፡ መልካምም ፡ ያልኾነ ።

45 እነርሱ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ቅምጥሎች ፡ ነበሩና ።

46 በታላቅ ፡ ኀጢአትም ፡ ላይ ፡ ይዘወትሩ፡ ነበሩና ።

47 ይሉም ፡ ነበሩ ፡— በሞትንና ፡ ዐፈር ፡ ዐጥንቶችም ፡ በኾን ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ በእርግጥ ፡ የምንቀሰቀስ ፡ ነን?

48 የፊተኞቹ ፡ አባቶቻችንም ?

49 በላቸው ፡— ፊተኞቹም ፡ ኋለኞቹም ።

50 በተወሰነ ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ በእርግጥ ፡ ተሰብሳቢዎች ፡ ናቸው ።

51 ከዚያም ፡ እናንተ ፡ ጠማሞች ፡ አስተባባዮች ፡ ሆይ ፤

52 ከዘቁም ፡ ዛፍ ፡ በእርግጥ ፡ በይዎች ፡ ናችሁ ።

53 ከርሷም ፡ ሆዶቻችሁን ፡ሞይዎች ፡ ናችሁ ።

54 በርሱ ፡ ላይም ፡ ከፈላ ፡ ውሃ ፡ ጠጪዎች ፡ ናችሁ ።

55 የተጠሙንም ፡ ግመሎች ፡ አጠጣጥ ፡ ብጤ ፡ ጠጪዎች ፡ ናችሁ ።

56 ይህ ፡ በፍርዱ ፡ ቀን ፡ መስተንግዷቸው ፡ ነው ።

57 እኛ ፡ ፈጠርናችሁ ፤ አታምኑምን?

58 (በማኅፀኖች) ፡ የምታፈሱትን ፡ አያችሁን?

59 እናንተ ፡ ትፈጥሩታላችሁን? ወይስ ፡ እኛ ፡ ፈጣሪዎቹ ፡ ነን ።

60 እኛ ፡ ሞትን ፡ (ጊዜውን) ፡ በመካከላችሁ ፡ ወሰንን ። እኛም ፡ ተሸናፊዎች ፡ አይደለንም ።

61 ብጤዎቻችሁን ፡ በመለወጥና ፡ በዚያ ፡ በማታውቁትም ፡ (ቅርጽ)፡ እናንተን ፡ በመፈጠር ፡ ላይ ፡ (አንሸነፍም) ።

62 የፊተኛይቱንም ፡ አፈጣጠር ፡ [1] በእርግጥ ፡ ዐውቃችኋል ፤ አትገነዘቡምን?

63 የምትዘሩትንም ፡ አያችሁን?

64 እናንተ ፡ ታበቅሉታላችሁን ? ወይስ ፡ እኛ ፡ አብቃዮቹ ፡ ነን ?

65 ብንሻ ፡ ኖሮ ፡ ደረቅ ፡ ስብርብር ፡ ባደረግነውና ፡ የምትደነቁም ፡ በኾናችሁ ፡ ነበር ።

66 እኛ ፡ በዕዳ ፡ ተያገሮች ፡ ነን ።

67 በእርግጥም ፡ እኛ ፡ (ከመጠቀም) ፡ የተከለከልን ፡ ነን ፡ (ትሉ ፡ ነበር)።

68 ያንንም ፡ የምትጠጡትን ፡ ውሃ ፡ አያችሁን?

69 እናንተ ፡ ከደመናው ፡ አወረዳችሁትን ? ወይስ ፡ እኛ ፡ አውራጆቹ ፡ ነን ?

70 ብንሻ ፡ ኖሮ ፡ መርጋጋ ፡ ባደረግነው ፡ ነበር ። አታመሰግኑምን ?

71 ያቺንም ፡ የምትሰብቋትን ፡ እሳት፡ አያችሁን ?

72 እናንተ ፡ ዛፏን ፡ ፈጠራችሁን ? ወይስ ፡ እኛ ፡ ፈጣሪዎችዋ ፡ ነን ?

73 እኛ ፡ (ለገሃነም) ፡ ማስታወሻ ፡ ለመንገደኞችም ፡ መጠቀሚያ ፡ አደረግናት ።

74 የታላቁን ፡ ጌታህንም ፡ ስም ፡ አወድስ ።

75 በከዋክብትም ፡ መጥለቂያዎች ፡ እምላለሁ ።

76 እርሱም ፡ ብታወቁ ፡ ታላቅ ፡ መሐላ ፡ ነው ።

77 እርሱ ፡ የከበረ ፡ ቁርአን ፡ ነው ።

78 በተጠበቀ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

79 የተጥራሩት ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይነካውም ።

80 ከዓለማት ፡ ጌታ ፡ የተወረደ ፡ ነው ።

81 በዚህ ፡ ንግግር ፡ እናንተ ፡ ቸልተኞች ፡ ናችሁን ?

82 ሲሳያችሁንም ፡ (ዝናምን) ፡ እናንተ ፡ የምታስተባብሉት ፡ ታደርጋላችሁን ?

83 (ነፍስ) ፡ ጉረሮንም ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ።

1 የአዳምን ፡ ዐፈርነት ፡ የሔዋንን ፡ ሥጋነት፡ የናንተን ፡ ከፍትወት ፡ ጠብታ ፡ መገኘት ።



84 እናንተ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የምታዩ ፡ ስትኾኑ ።

85 እኛም ፡ ግን ፡ አታዩም ፡ እንጅ ፡ ከናንተ ፡ ይልቅ ፡ ወደርሱ ፡ የቀረብን ፡ ስንኾን ።

86 የማትዳኙም ፡ ከኾናችሁ ።

87 እውነተኞች ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡ (ነፍሲቱን ፡ ወደ ፡ አካሉ) ፡ ለምን፡ አትመልሷትም ።

88 (ሟቹ) ፡ ከባለሟሎቹ ፡ ቢኾንማ ።

89 (ለርሱ) ፡ ዕረፍት ፡ መልካም ፡ ሲሳይም ፡ የመጠቀሚያ ፡ ገነትም፡ አልለው ።

90 ከቀኝ ፡ጓዶችም ፡ ቢኾንማ ።

91 ከቀኝ ፡ ጓዶች ፡ ስለ ፡ ኾንክ ፡ ላንተ ፡ ሰላም ፡ አልለህ ፡ (ይባላል) ።

92 ከሚያስዋሹት ፡ ጠማማዎችም ፡ ቢኾንማ ።

93 ከፈላ ፡ ውሃ ፡ የኾነ ፡ መስተንግዶ ፡ አልለው ።

94 በገሀነም ፡ መቃጠልም ፡ (አልለው) ።

95 ይህ ፡ እርሱ ፡ እርግጠኛ ፡ እውነት ፡ ነው ።

96 የታላቁንም ፡ ጌታህን ፡ ስም ፡ አወድስ ።

## ምዕራፍ ፡ 57 ፡ አል-ሐዲድ ። ክፍል ፡ 27 ።

57ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሐዲድ ፤ (የብረት ፡ ምዕራፍ) ። በመዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 29 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው።

1 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ለአላህ ፡ አሞገሰ ፤ እርሱም፡ ሁሉን ፡ አሸናፊው ፡ ጥበበኛው ፡ ነው ።

2 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ንግሥና ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ሕያው ፡ ያደርጋል ፤ ይገድላልም ፤ እርሱም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ።

3 እርሱ ፡ ፊትም ፡ ያለ ፡ ኋላም ፡ ቀሪ ፡ ግልጽም ፡ ስውርም ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

4 እርሱ ፡ ያ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ በስድስት ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ የፈጠረ ፡ ከዚያም ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ፡ (ሥልጣኑ) ፡ የተደላደለ ፡ ነው ፤ በምድር ፡ ውስጥ ፡ የሚገባውን ፡ ከርሷም ፡ የሚወጣውን ፡ ከሰማይም ፡ የሚወርደውን ፡ በርሷም ፡ ውስጥ ፡ የሚያርገውን ፡ ያውቃል ፤ እርሱም ፡ የትም ፡ ብትኾኑ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ነው ፤ አላህም ፡ የምትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ተመልካች ፡ ነው ።

5 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ንግሥና ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ነገሮችም ፡

(ሁሉ) ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡ ይመ
ለሳሉ ።
6 ሌሊትን ፡ በቀን ፡ ውስጥ ፡ ያስገ
ባል ፤ ቀንንም ፡ በሌሊት ፡ ውስጥ ፡
ያስገባል ፤ እርሱም ፡ በልቦች ፡
ውስጥ ፡ የተደበቁትን ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።
7 በአላህና ፡ በመልክተኛው ፡ እ
መኑ ፤ (አላህ) ፡ በርሱ ፡ ተተኪ
ዎች ፡ ባደረጋችሁም ፡ ገንዘብ ፡
ለግሱ ፤ እነዚያም ፡ ከናንተ ፡ ው
ስጥ ፡ ያመኑትና ፡ የለገሱት ፡
ለነርሱ ፡ ታላቅ ፡ ምንዳ ፡ አልላ
ቸው ።
8 መልክተኛው ፡ በጌታችሁ ፡ እን
ድታምኑ ፡ የሚጠራችሁ ፡ ሲኾን ፡
(ጌታችሁ) ፡ ኪዳናችሁንም ፡ የያ
ዘባችሁ ፡ ሲኾን ፡ በአላህ ፡ የማ
ታምኑት ፡ ለናንተ ፡ ምን ፡ አላ
ችሁ ? የምታምኑ ፡ ብትኾኑ ፡
(ወደ ፡ እምነት ፡ ቸኩሉ) ።
9 እርሱ ፡ ከጨለማዎች ፡ ወደ ፡
ብርሃን ፡ ሊያወጣችሁ ፡ ያ ፡ ግል
ጾች ፡ የኾኑን ፡ አንቀጾች ፡ በባሪ
ያው ፡ ላይ ፡ የሚያወርድ ፡ ነው ፤
አላህም ፡ ለናንተ ፡ በእርግጥ ፡
ርኅሩኅ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።
10 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ውርስ ፡
ለአላህ ፡ ሲኾን ፡ በአላህ ፡ መን
ገድ ፡ የማትለግሱትም ፡ ለናንተ ፡
ምን ፡ አልላችሁ ? ከናንተ ፡
ውስጥ ፡ (መካን) ፡ ከመክፈት ፡
በፊት ፡ የለገሰና ፡ የተጋደለ ፡
ሰው ፡ (ከተከፈተች ፡ በኋላ ፡ ከለ
ገሰና ፡ ከተጋደለ ፡ ጋር) ፡ አይተ
ካከልም ፤ ከነዚያ ፡ በኋላ ፡ ከለ
ገሱትና ፡ ከተጋደሉት ፡ እነዚህ ፡
በደረጃ ፡ በጣም ፡ የላቁ ፡ ናቸው ፤
ሁሉንም ፡ አላህ ፡ መልካሚቱን ፡
ተስፋ ፡ ቃል ፡ ገብቶላቸዋል ፤
አላህም ፡ በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡
ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
11 ያ ፡ ለአላህ ፡ መልካም ፡ ብድ
ርን ፡ የሚያበድር ፡ ለርሱም ፡
(አላህ) ፡ የሚያነባብርለት ፡ ሰው ፡
ማነው ? ለርሱም ፡ መልካም ፡
ምንዳ ፡ አልለው ።
12 ምእምናንንና ፡ ምእምናትን ፡ በስ
ተፊቶቻቸው ፡ በቀኞቻቸውም ፡
ብርሃናቸው ፡ የሚሮጥ ፡ ሲኾን ፡
በምታያቸው ፡ ቀን ፡ (ምንዳ ፡
አልላቸው) ። ዛሬ ፡ ብስራታችሁ ፡
በውስጦቻቸው ፡ ዘውታሪዎች ፡
ስትኾኑ ፡ ከሥሮቻቸው ፡ ወን
ዞች ፡ የሚፈሱባቸው ፡ ገነቶች ፡
ናቸው ፡ (ይባላሉ) ። ይህ ፡ እርሱ ፡
ታላቁ ፡ ዕድል ፡ ነው ።
13 መናፍቃንና ፡ መናፍቃት ፡ ለነ
ዚያ ፡ ለአመኑት ፡ ተመልከቱን ፤
ከብርሃናችሁ ፡ እናበራለንና ፡
የሚሉበትን ፡ ቀን ፡ (አስታውስ) ፤
ወደ ፡ ኋላችሁ ፡ ተመለሱ ፤ ብር
ሃንንም ፡ ፈልጉ ፡ ይባላሉ ፤ በመ
ካከላቸውም ፡ ለርሱ ፡ ደጃፍ ፡
ባለው ፡ አጥር ፡ ይከለላል ፤ ግቢው
በውስጡ ፡ ችሮታ ፡ (ገነት) ፡ ያለ
በት ፡ ውጭውም ፡ ከበኩሉ ፡
ስቃይ ፡ (እሳት) ፡ ያለበት ፡ የኾነ ፡
(ደጃፍ ፡ ባለው ፡ አጥር) ።
14 ከናንተ ፡ ጋር ፡ አልነበርንምን ?
በማለት ፡ ይጠሩዋቸዋል ፡ እውነት ፡
ነው ፤ ግን ፡ እናንተ ፡ ነፍሶቻች
ሁን ፡ አጠፋችሁ ፤ (በነቢዩ ፡
አደጋዎችን) ፡ ተጠባበቃችሁም ፤
ተጠራጠራችሁም ፤ የአላህም ፡
ትእዛዝ ፡ እስከ ፡ መጣ ፡ ድረስ ፡
ከንቱ ፡ ምኞቶች ፡ አታለሏችሁ ፤



አታላዩም ፡ (ሰይጣን) ፡ በአላህ ፡
(መታገሥ) ፡ ሸነገላችሁ ፤ ይሏ
ቸዋል ።
15 ዛሬም ፡ ከናንተ ፡ ቤዛ ፡ አይወሰ
ድም ፤ ከነዚያ ፡ ከካዱትም ፤ መኖ
ሪያችሁ ፡ እሳት ፡ ናት ፤ እርሷ ፡ ተ
ገቢያችሁ ፡ ናት ፤ ምን ፡ ትከፋም ፡
መመለሻ ! (ይሏቸዋል) ።
16 ለነዚያ ፡ ለአመኑት ፡ ለአላህ ፡
ተግሣጽና ፡ ከቁርአንም ፡ ለወረ
ደው ፡ ልቦቻቸው ፡ ሊፈሩ ፡ እንደ
ነዚያም ፡ በፊት ፡ መጽሐፍን ፡
እንደ ፡ ተሰጡትና ፡ በነርሱ ፡
ላይ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ረዘመባቸው ፡
ልቦቻቸውም ፡ እንደ ፡ ደረቁት ፡
ላይኾኑ ፡ (ጊዜው) ፡ አልቀረበ
ምን ? ከነርሱም ፡ ብዙዎቹ ፡
አመጠኞች ፡ ናቸው ።
17 አላህ ፡ ምድርን ፡ ከሞተች ፡
በኋላ ፡ ሕያው ፡ የሚያደርጋት ፡
መኾኑን ፡ ዕወቁ ፤ ታውቁ ፡
ዘንድ ፡ አንቀጾችን ፡ ለናንተ ፡ በእ
ርግጥ ፡ አብራራንላችሁ ።
18 የመጸወቱ ፡ ወንዶችና ፡ የመጸ
ወቱ ፡ ሴቶች ፡ ለአላህም ፡ መልካ
ምን ፡ ብድር ፡ ያበደሩ ፡ ለነርሱ ፡
ይደራረብላቸዋል ፤ ለነርሱም ፡
መልካም ፡ ምንዳ ፡ አላቸው ።
19 እነዚያም ፡ በአላህና ፡ በመልክ
ተኞቹ ፡ ያመኑት ፡ እነዚያ ፡ እነሱ ፡
በጣም ፡ እውነተኞቹ ፡ በጌታቸ
ውም ፡ ዘንድ ፡ መስካሪዎቹ ፡
ናቸው ፤ ለነርሱ ፡ ምንዳቸው ፡ ብ
ርሃናቸውም ፡ አልላቸው ፤ እነዚ
ያም ፡ የካዱት ፡ በአንቀጾቻች
ንም ፡ ያስተባበሉት ፡ እነዚያ ፡
የእሳት ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ።
20 ቅርቢቱ ፡ ሕይወት ፡ ጨዋታና ፡
ዛዛታ ፡ ማጌጫም ፡ በመካከላች
ሁም ፡ መፎካከሪያ ፡ በገንዘቦ
ችና ፡ በልጆችም ፡ ብዛት ፡ መበ
ላለጫ ፡ ብቻ ፡ መኾንዋን ፡ ዕወቁ ፤
(እርሷ) ፡ በቃዩ ፡ ገበሬዎችን ፡
እንደሚያስደስት ፡ ዝናም ፡ ከዚ
ያም ፡ በቃዩ ፡ እንደሚደርቅና ፡
ገርጥቶ ፡ እንደምታየው ፡ ከዚ
ያም ፡ የተሰባበረ ፡ እንደሚኾን ፡
ብጤ ፡ ናት ፤ በመጨረሻይቱም ፡
ዓለም ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ ከአላ
ህም ፡ ምሕረትና ፡ ውዴታ ፡
አልለ ፤ የቅርቢቱም ፡ ሕይወት ፡
የመታለያ ፡ ጥቅም ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡
አይደለችም ።
21 ከጌታችሁ ፡ ወደ ፡ ኾነች ፡ ም
ሕረት ፡ ወርዱ ፡ እንደ ፡ ሰማ
ይና ፡ ምድር ፡ ወርድ ፡ ወደ ፡
ኾነችም ፡ ገነት ፡ ተሽቀዳደሙ ፤
ለነዚያ ፡ በአላህና ፡ በመልክተ
ኞቹ ፡ ላመኑት ፡ ተዘጋጅታለች ።
ይህ ፡ የአላህ ፡ ችሮታ ፡ ነው ፤
ለሚሻው ፡ ሰው ፡ ይሰጠዋል ፤
አላህም ፡ የታላቅ ፡ ችሮታ ፡ ባለ
ቤት ፡ ነው ።
22 በምድርም ፡ በነፍሶቻችሁም ፡
መከራ ፡ (ማንንም) ፡ አትነካም ፡
ሳንፈጥራት ፡ በፊት ፡ በመጽሐፍ ፡
የተመዘገበች ፡ ብትኾን ፡ እንጅ ፤
ይህ ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡ ገር ፡ ነው ።
23 (ይህ ፡ ማሳወቃችን) ፡ ባመለጣ
ችሁ ፡ ጸጋ ፡ ላይ ፡ እንዳታዝኑ ፡
አላህም ፡ በሰጣችሁ ፡ ነገር ፡
(በትዕቢት) ፡ እንዳትደሰቱ ፡ ነው ፤
አላህም ፡ ኩራተኛን ፡ ጉረኛን ፡
ሁሉ ፡ አይወድም ።
24 (እነርሱም) ፡ እነዚያ ፡ የሚሰስ
ቱና ፡ ሰዎችንም ፡ በስስት ፡ የሚ
ያዙ ፡ ናቸው ፤ (ከውነት) ፡ የሚ
ሸሽም ፡ ሰው ፡ (ጥፋቱ ፡ በራሱ ፡

ላይ ፡ ነው) ፤ አላህም ፡ እርሱ ፡
ተብቃቂ ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

25 መልክተኞቻችንን ፡ በግልጽ ፡
ማስረጃዎች ፡ በእርግጥ ፡ ላክን ፤
ሰዎችም ፡ በትክክል ፡ ቀጥ ፡ እን
ዲሉ ፡ መጽሐፎችንና ፡ ሚዛንን ፡
ወደነርሱ ፡ አወረድን ፤ ብረት
ንም ፡ በውስጡ ፡ ብርቱ ፡ ኀይ
ልና ፡ ለሰዎችም ፡ መጠቃቀሚ
ያዎች ፡ ያሉበት ፡ ሲኾን ፡ አወ
ረድን ፤ (እንዲጠቀሙበት) ፡ አላ
ህም ፡ ሃይማኖቱንና ፡ መልክተኞ
ቹን ፡ በሩቅ ፡ ኾኖ ፡ የሚረዳውን ፡
ሰው ፡ ሊያውቅ ፡ (ሊገልጽ ፡ አወ
ረደው) ፤ አላህ ፡ ብርቱ ፡ አሸ
ናፊ ፡ ነውና ።

26 ኑሕን ፡ ኢብራሂምንም ፡ በእር
ግጥ ፡ ላክን ፤ በዘሮቻቸውም ፡
ውስጥ ፡ ነቢይነትንና ፡ መጽሐ
ፎችን ፡ አደረግን ፤ ከነሱም ፡ ቅን ፡
አልለ ፤ ከነሱም ፡ ብዙዎቹ ፡ አመ
ጠኞች ፡ ናቸው ።

27 ከዚያም ፡ በዱካዎቻቸው ፡ ላይ ፡
መልክተኞቻችንን ፡ አስከታተልን
የመርየምን ፡ ልጅ ፡ ዒሳንም ፡
አስከተልን ፤ ኢንጂልንም ፡ ሰጠ
ነው ፤ በነዚያም ፡ በተከተሉት ፡
(ሰዎች) ፡ ልቦች ፡ ውስጥ ፡ መለ
ዘብንና ፡ እዝነትን ፡ አዲስ ፡ የፈ
ጠሩዋትንም ፡ ምንኩስና ፡ አደረ
ግን ፤ በነርሱ ፡ ላይ ፡ (ምንኩስ
ናን) ፡ አልጻፍናትም ፤ ግን ፡ የአላ
ህን ፡ ውዴታ ፡ ለመፈለግ ፡ ሲሉ ፡
(ፈጠሩዋት) ፤ ተገቢ ፡ አጠባበ
ቋንም ፡ አልጠበቋትም ፤ ከነር
ሱም ፡ ለነዚያ ፡ ላመኑት ፡ ምንዳ
ቸውን ፡ ሰጠናቸው ፤ ከነሱም ፡
ብዙዎቹ ፡ አመጠኞች ፡ ናቸው ።

28 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላ
ህን ፡ ፍሩ ፤ በመልክተኛውም ፡
እመኑ ፤ ከችሮታው ፡ ሁለትን ፡
ክፍሎች ፡ ይሰጣችኋልና ፤ ለናን
ተም ፡ በርሱ ፡ የምትኼዱበት ፡
የኾነ ፡ ብርሃንን ፡ ያደርግላችኋል ፤
ለናንተም ፡ ይምራል ፤ አላህም ፡
መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነው ።

29 (ይህም) ፡ የመጽሐፉ ፡ ሰዎች ፡
ከአላህ ፡ ችሮታ ፡ በምንም ፡ ላይ ፡
የማይችሉ ፡ መኾናቸውን ፡ ችሮ
ታም ፡ በአላህ ፡ እጅ ፡ ነው ፤ ለሚ
ሻው ፡ ሰው ፡ ይሰጠዋል ፡ ማለ
ትን ፡ እንዲያውቁ ፡ ነው ፤ አላ
ህም ፡ የታላቅ ፡ ችሮታ ፡ ባለቤት ፡
ነው ።



★ ★ ★

58ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሙጃደላህ ፤ (የመከራከር ፡ ምዕራፍ) ። በመ
ዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 22 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።

1 አላህ ፡ የዚያችን ፡ በባሏ ፡ (ነገር) ፡
የምትከራከርህንና ፡ ወደ ፡ አላህ ፡
የምታሰሙተውን ፡ (ሴት) ፡ ቃል ፡
በእርግጥ ፡ ሰማ ። አላህም ፡ (በን
ግግር) ፡ መመላለሳችሁን ፡ ይሰ
ማል ። አላህ ፡ ሰሚ ፡ ተመልካች ፡
ነውና ።

2 እነዚያ ፡ ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ ከሚስ
ቶቻቸው ፡ እንደናቶቻችን ፡ ጀር
ባዎች ፡ ይኹኑብን ፡ በማለት ፡
የሚምሉ ፡ እነሱ ፡ እናቶቻቸው ፡
አይደሉም ፤ እናቶቻቸው ፡ እሊያ ፡
የወለዱዋቸው ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።
እነርሱም ፡ (በዚህ ፡ ቃል) ፡ ከን
ግግር ፡ የተጠላንና: ውሸትን ፡
በእርግጥ ፡ ይናገራሉ ፤ አላህም ፡
(ለሚጸጸት) ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ መሓሪ
ነው ።

3 እነዚያም ፡ ከሚስቶቻቸው ፡ እንደ
ናቶቻችን ፡ ጀርባዎች ፡ ኹኑብን ፡
በማሉት ፡ የሚምሉ ፡ ከዚያም ፡
ወደ ፡ ተናገሩት ፡ የሚመለሱ ፡
ሳይነካኩ ፡ በፊት ፡ ጫንቃን ፡
ነጻ ፡ ማውጣት ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
አለባቸው ። ይሃችሁ ፡ በርሱ ፡
ትገሠጹበታላችሁ ፤ አላህም ፡
በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ውስጠ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።

4 ያላገኘም ፡ ሰው ፡ ከመነካካታ
ቸው ፡ በፊት ፡ ሁለት ፡ የተከታ
ተሉ ፡ ወሮችን ፡ መጾም ፡ አለ
በት ። ያልቻለም ፡ ሰው ፡ ስድሳ ፡
ድኾችን ፡ ማብላት ፡ (አለበት) ፤
ይህ ፡ በአላህና ፡ በመልክተኛው ፡
እንድታምኑ ፡ ነው ። ይህችም ፡
የአላህ ፡ ሕግጋት ፡ ናት ፡ ለከሓ
ዲዎችም ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡
አልላቸው ።

5 ግልጾች ፡ ማስረጃዎችን ፡ ያወ
ረድን ፡ ስንኾን ፡ እነዚያ ፡ አላህ
ንና ፡ መልክተኛውን ፡ የሚከራ
ከሩ ፡ እነዚያ ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡
የነበሩት ፡ እንደተዋረዱ ፡ ይዋ
ረዳሉ ፤ ለከሓዲዎችም ፡ አዋ
ራጅ ፡ ቅጣት ፡ አልላቸው ።

6 አላህ ፡ ሁላቸውንም ፡ በሚቀሰ
ቅሳቸው ፡ ቀን ፡ (ይቀጣቸዋል) ፤
የሠሩትንም ፡ ሁሉ ፡ ይነግራቸ
ዋል ፤ የረሱት ፡ ሲኾኑ ፡ አላህ ፡
ዐውቆታል ። አላህም ፡ በነገሩ ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

7 አላህ ፡ በሰማያት ፡ ውስጥ ፡ ያለ
ውን ፡ በምድርም ፡ ውስጥ ፡ ያለ
ውን ፡ ሁሉ ፡ የሚያውቅ ፡ መኾ
ኑን ፡ አታይምን ? ከሦስት ፡
ሰዎች ፡ መሾካሾክ ፡ አይኖርም ፡
እርሱ ፡ አራተኛቸው ፡ ቢኾን ፡
እንጅ ፤ ከአምስትም ፡ (አይኖ
ርም) ፡ እርሱ ፡ ስድስተኛቸው ፡

ቢኾን ፡ እንጅ ፤ ከዚያ ፡ ያነሰም ፡
የበዛም ፡ (አይኖርም) ፡ እርሱ ፡
የትም ፡ ቢኾኑ ፡ አብሮዋቸው ፡
ቢኾን ፡ እንጅ ፤ ከዚያም ፡ በትን
ሣኤ ፡ ቀን ፡ የሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ይነ
ግራቸዋል ። አላህ ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።
8 ወደነዚያ ፡ (በመጥፎ) ፡ ከመሾካ
ሾክ ፡ ወደ ፡ ተከለከሉት ፡ ከዚ
ያም ፡ ከርሱ ፡ ወደ ፡ ተከለከሉት ፡
ነገር ፡ ወደሚመለሱት ፡ በኃጢ
አትና ፡ ድንበርን ፡ በማለፍ ፡
መልክተኛውን ፡ በመቃወም ፡
ወደሚንሾካሾኩት፡ አላየህምን?
(ሰላም ፡ ሊሉ) ፡ በመጡህም ፡
ጊዜ ፡ አላህ ፡ በርሱ ፡ ባላናገረህ ፡
ቃል ፡ ያናግሩሃል ። በነፍሶቻቸ
ውም ፡ ውስጥ ፡ (ነቢይ ፡ ከኾ
ንክ) ፡ በምንለው ፡ ነገር ፡ አላህ ፡
አይቀጣንም ፡ ኖሮአልን ? ይላሉ ።
ገሀነም ፡ የሚገቧት ፡ሲኾኑ ፡ በቂ
ያቸው ፡ ናት ፤ ምን ፡ ትከፋም ፡
መመለሻ !
9 እላንተ፡ ያመናችሁ፡ ሆይ! በተን
ሾካሾካችሁ ፡ ጊዜ ፡ በኃጢአትና ፡
ወሰንን ፡ በማለፍ ፡ መልክተኛ
ውንም ፡ በመቃወም፡ አትንሾካ
ሾኩ ፤ ግን ፡ በበጎ ፡ ሥራና ፡ አላ
ህን ፡ በመፍራት ፡ ተወያዩ ፤ ያን
ንም ፡ ወደርሱ ፡ የምትሰበሰቡበ
ትን ፡ አላህን ፡ ፍሩ ።
10 (በመጥፎ)፡ መንሾካሾክ፡ ከሰይ
ጣን ፡ ብቻ ፡ ነው ። እነዚያ ፡ ያመ
ኑት ፡ ያዝኑ ፡ ዘንድ ፡ (ይቀሰቅሰ
ዋል) ፤ በአላህ ፡ ፈቃድ ፡ ካል
ኾነ ፡ በቀር ፡ በምንም ፡ አይጐዳ
ቸውም ፤ በአላህ ፡ ላይም ፡ አማ
ኞች ፡ ይጠጉ ።
11 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ለና
ንተ ፡ በመቀመጫዎች ፡ ስፍራ ፡
ተስፋፉ ፡ በተባላችሁ ፡ ጊዜ ፡ (ስ
ፍራን) ፡ አስፉ ፤ አላህ ፡ ያሰፋላች
ኋልና ። ተነሱ ፡ በተባለም ፡ ጊዜ ፡
ተነሱ ። አላህ ፡ ከናንተ ፡ እነዚ
ያን ፡ ያመኑትንና ፡ እነዚያንም ፡
ዕውቀትን ፡ የተሰጡትን ፡ በደረጃ
ዎች ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፤ አላህም ፡
በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ውስጠ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።
12 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! መል
ክተኛውን ፡ በተወያያችሁ ፡ ጊዜ ፡
ከመወያየታችሁ ፡ በፊት ፡ ምጽ
ዋትን ፡ አስቀድሙ ፤ ይህ ፡ ለና
ንተ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ አጥሪም ፡
ነው ። ባታገኙም ፡ አላህ ፡ መሐሪ ፡
አዛኝ ፡ ነው ።
13 ከውይይታችሁ ፡ በፊት ፡ ምጽ
ዋቶችን ፡ ከማስቀደም ፡ (ድህነ
ትን) ፡ ፈራችሁን ? ባልሠራች
ሁም ፡ ጊዜ ፡ አላህ ፡ ከናንተ ፡
ጸጸትን ፡ የተቀበለ ፡ ሲኾን ፡ ሶላ
ትን ፡ ስገዱ ፤ ዘካንም ፡ ስጡ ፤
አላህንና ፡ መልክተኛውንም ፡
ታዘዙ ፤ አላህም ፡ ውስጥ ፡ ዐዋቂ፡
ነው ።
14 ወደነዚያ ፡ አላህ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡
የተቆጣባቸውን ፡ ሕዝቦች ፡ ወደ ፡
ተወዳጁት ፡ (መናፍቃን) ፡ አላ
የኸምን ? እነርሱ ፡ ከናንተ ፡ አይ
ደሉም ፤ ከነርሱም ፡ አይደሉም ።
እነሱም ፡ የሚያውቁ ፡ ሲኾኑ ፡
በውሸት ፡ ላይ ፡ ይምላሉ ።
15 አላህ ፡ ለነርሱ ፡ ብርቱን ፡ ቅጣት ፡
አዘጋጀ ፤ እነሱ ፡ ይሠሩት ፡ የነ
በሩት ፡ ሥራ ፡ ምንኛ ፡ ከፋ !
16 መሐሎቻቸውን ፡ ጋሻ ፡ አድር
ገው ፡ ያዙ ፤ ከአላህም ፡ መንገድ ፡



አገዱ ፤ ስለዚህ ፡ ለነሱ ፡ አዋራ
ራጅ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ።
17 ገንዘቦቻቸውና ፡ ልጆቻቸው ፡
ከአላህ ፡ (ቅጣት) ፡ ምንንም ፡
ከነሱ ፡ አያድኗቸውም ። እነዚያ ፡
የእሳት ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ። እነሱ ፡
በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ዘውታሪዎች ፡
ናቸው ።
18 አላህ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ኾነው ፡ በሚ
ያስነሳቸው ፡ ቀን ፡ ለናንተ ፡ እን
ደሚምሉላችሁም ፡ እነሱ ፡ (በሚ
ጠቅም) ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ መኾናቸ
ውን ፡ የሚያስቡ ፡ ኾነው ፡ ለርሱ ፡
በሚምሉበት ፡ ቀን ፡ (አዋራጅ ፡
ቅጣት ፡ አላቸው) ፤ ንቁ ፡ እነሱ ፡
ውሸታሞቹ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ።
19 በነርሱ ፡ ላይ ፡ ሰይጣን ፡ ተሾመ
ባቸው ፤ አላህንም ፡ ማስታወስን ፡
አስረሳቸው ፤ እነዚያ ፡ የሰይ
ጣን ፡ ጭፍሮች ፡ ናቸው ፤ ንቁ ፤
የሰይጣን ፡ ጭፍሮች ፡ ከሳሪዎቹ ፡
እነርሱ ፡ ናቸው ።
20 እነዚያ ፡ አላህንና ፡ መልክተኛ
ውን ፡ የሚከራከሩት ፡ እነዚያ ፡
በጣም ፡ በወራዶቹ ፡ ውስጥ ፡
ናቸው ።
21 አላህ ፡—እኔ ፡ በእርግጥ ፡ አሸን
ፋለሁ ፤ መልክተኞቼም ፡ (ያሸን
ፋሉ ፡ ሲል) ፤ ጽፏል ። አላህ ፡
ብርቱ ፡ አሸናፊ ፡ ነውና ።
22 በአላህና ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡
የሚያምኑትን ፡ ሕዝቦች ፡ አላህ
ንና ፡ መልክተኛውን ፡ የሚከራ
ከሩትን ፡ ሰዎች ፤ አባቶቻቸው ፡
ወይም ፡ ልጆቻቸው ፤ ወይም ፡
ወንድሞቻቸው ፡ ወይም ፡ ዘመ
ዶቻቸው ፡ ቢኾኑም ፡ እንኳ ፡
የሚወዳጁ ፡ ኾነው ፡ አታገኛቸ
ውም ፤ እነዚያ ፡ በልቦቻቸው ፡
ውስጥ ፡ እምነትን ፡ ጽፏል ፤
ከርሱም ፡ በኾነ ፡ መንፈስ ፡ ደግ
ፏቸዋል ፤ ከሥሮቻቸውም ፡ ወን
ዞች ፡ የሚፈሱባቸውን ፡ ገነቶች ፡
በውስጣቸው ፡ ዘውታሪዎች ፡
ሲኾኑ ፡ ያገባቸዋል ፤ አላህ ፡ ከነ
ርሱ ፡ ወዷል ። ከርሱም ፡ ወደ
ዋል ፤ እነዚያ ፡ የአላህ ፡ ሕዝቦች ፡
ናቸው ፤ ንቁ ፡ የአላህ ፡ ሕዝቦች ፡
እነሱ ፡ ምኞታቸውን ፡ የሚያገኙ፡
ናቸው ።

59ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሐሽር ፤ (ከአገር ፡ የማውጣት ፡ ምዕራፍ) ፡ በ
መዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 24 ፡ ናቸው ።

ርአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ፡
1 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡
ያለው ፡ ሁሉ ፡ ለአላህ ፡ አሞገሰ ፤
እርሱም ፡ አሸናፊው ፡ ጥበበኛው ፡
ነው ።
2 እርሱ ፡ ያ ፡ ከመጽሐፉ ፡ ሰዎች ፡
እነዚያን ፡ የካዱትን ፡ ከቤቶቻ
ቸው ፡ ለመጀመሪያው ፡ ማው
ጣት ፡ ያወጣቸው ፡ ነው ፤ መው
ጣታቸውን ፡ አላሰባችሁም ፤ እነ
ሱም ፡ ምሽጎቻቸው ፡ ከአላህ ፡
(ኀይል) ፡ የሚከላከሉላቸው ፡ መኾ
ናቸውን ፡ አሰቡ ፤ አላህም ፡ ካላ
ሰቡት ፡ ስፍራ ፡ መጣባቸው ፤
በልቦቻቸውም ፡ ውስጥ ፡ መርበ
ድበድን ፡ ጣለባቸው ፤ ቤቶቻቸ
ውን ፡ በእጆቻቸውና ፡ በምእም
ናኖቹ ፡ እጆች ፡ ያፈርሳሉ ፤ አስ
ተውሉም ፡ የአእምሮ ፡ ባለቤ
ቶች ፡ ሆይ !
3 በነሱም ፡ ላይ ፡ አላህ ፡ ከአገር ፡
መውጣትን ፡ ባልጻፈ ፡ ኖሮ ፡
በቅርቢቱ ፡ ዓለም ፡ በቀጣቸው ፡
ነበር ፤ ለነርሱም ፡ በመጨረሻ
ይቱ ፡ (ዓለም) ፡ የእሳት ፡ ቅጣት ፡
አላቸው ።
4 ይህ ፡ እነርሱ ፡ አላህንና ፡ መልክ
ተኛውን ፡ በመከራከራቸው ፡
ነው ። አላህንም ፡ የሚከራከር ፡
ሰው ፡ (ይቀጣዋል) ፤ አላህ ፡
ቅጣተ ፡ ብርቱ ፡ ነውና ።
5 ከዘንባባ ፡ (ከተምር ፡ ዛፍ) ፡ ማን
ኛዋም ፡ የቆረጣችኋት ፡ ወይም ፡
በግንዶቿ ፡ ላይ ፡ የቆመች ፡ ኾና ፡
የተዋችኋት ፡ በአላህ ፡ ፈቃድ ፡
ነው ፤ አመጠኞችንም ፡ ያዋርድ ፡
ዘንድ ፡ (በመቁረጥ ፡ ፈቀደ) ።
6 ከነርሱም ፡ (ገንዘብ) ፡ በመልክተ
ኛው ፡ ላይ ፡ አላህ ፡ የመለሰው ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ ፈረሶችንና ፡ ግመ
ሎችን ፡ አላስጋለባችሁበትም ፤
(1) ግን ፡ አላህ ፡ መልክተኞ
ቹን ፡ በሚሻው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡
ይሾማል ። አላህም ፡ በነገሩ ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ ነው ።
7 አላህ ፡ ከከተሞቹ ፡ ሰዎች ፡
(ሀብት) ፡ በመልክተኛው ፡ ላይ ፡
የመለሰው ፡ (ሀብት) ፡ ከናንተ ፡
ውስጥ ፡ በሀብታሞቹ ፡ መካከል ፡
ተዘዋዋሪ ፡ እንዳይኾን ፡ ለአላ
ህና ፡ ለመልክተኛው ፡ ለዝም
ድና ፡ ባለቤትም ፡ አባት ፡ ለሌ
ላቸው ፡ ልጆችም ፡ ለድኾችም ፡
ለመንገደኛም ፡ (የሚሰጥ) ፡ ነው ፤
መልክተኛውም ፡ የሰጣችሁን ፡
(ማንኛውንም) ፡ ነገር ፡ ያዙት ።
ከርሱም ፡ የከለከላችሁን ፡ ነገር ፡
ተከልከሉ ። አላህንም ፡ ፍሩ ፤
አላህ ፡ ቅጣተ ፡ ብርቱ ፡ ነውና ።
8 ለነዚያ ፡ የአላህን ፡ ችሮታና ፡
ውዴታውን ፡ የሚፈልጉ ፡ አላ
ህንና ፡ መልክተኛውንም ፡ የሚ
ረዱ ፡ ኾነው ፡ ከአገሮቻቸውና ፡

1 በጦር ፡ ኃይል ፡ አልደከማችሁበትም ።



ከገንዘቦቻቸው ፡ ለተወጡት ፡
ስደተኞች ፡ ድኾች ፡ (ይሰጣል) ፤
እነዚያ ፡ እነሱ ፡ እውነተኞቹ ፡
ናቸው ።
9 እነዚያም ፡ ከበፊታቸው ፡ አገሪ
ቱን ፡ መኖሪያ ፡ ያደረጉት ፡ እምነ
ትንም ፡ የለመዱት ፡ ወደነርሱ ፡
የተሰደዱትን ፡ ሰዎች ፡ ይወዳሉ ፤
(ስደተኞቹ) ፡ ከተሰጡትም ፡ ነገር ፡
በልቦቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ቅሬታን ፡
አያገኙም ። በነሱ ፡ ላይ ፡ ችግር ፡
ቢኖርባቸውም ፡ በነፍሶቻቸው ፡
ላይ ፡ ሌላውን ፡ ይመርጣሉ ። የነ
ፍሱንም ፡ ንፍገት ፡ የሚጠበቅ ፡
ሰው ፡ እነዚያ ፡ እነሱ ፡ ምኞታቸ
ውን ፡ አግኚዎች ፡ ናቸው ።
10 እነዚያም ፡ ከበኋላቸው ፡ የመ
ጡት ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ ለኛም ፡
ለነዚያም ፡ በእምነት ፡ ለቀደ
ሙን ፡ ወንድሞቻችን ፡ ምሕረት ፡
አድርግ ። በልቦቻችንም ፡ ውስጥ ፡
ለነዚያ ፡ ለአመኑት ፡ (ሰዎች) ፡
ጥላቻን ፡ አታድርግ ። ጌታችን ፡
ሆይ ! አንተ ፡ ርኅሩኅ ፡ አዛኝ ፡
ነህና ፡ ይላሉ ።
11 ወደነዚያ ፡ ወደ ፡ ነፈቁት ፡ አላ
የህምን ? ከመጽሐፉ ፡ ሰዎች ፡
ውስጥ ፡ ለነዚያ ፡ ለካዱት ፡ ወን
ድሞቻቸው ፡ (ከአገር) ፡ ብትባ
ረሩ ፡ አብረናችሁ ፡ እንወጣለን ፤
በናንተም ፡ (ጉዳይ) ፡ አንድንም ፡
በፍጹም ፡ አንታዘዝም ። ብትገ
ደሉም ፡ በእርግጥ ፡ እንረዳች
ኋለን ፡ ይሏቸዋል ፤ አላህም ፡
እነሱ ፡ ውሸታሞች ፡ መኾናቸ
ውን ፡ ይመሰክራል ።
12 ቢወጥጡ ፡ አብረዋቸው ፡ አይ
ወጡም ፤ ቢገደሉም ፡ አይረዱ
ዋቸውም ፤ ቢረዷቸውም ፡ (ለሺ
ሺት) ፡ ጀርባዎችን ፡ ያዞራሉ ፤
ከዚያም ፡ እርዳታን ፡ አያገኙም ።
13 እናንተ ፡ በልቦቻቸው ፡ ውስጥ ፡
በማስፈራት ፡ ከአላህ ፡ ይልቅ ፡
የበረታችሁ ፡ ናችሁ ፤ ይህ ፡
እነርሱ ፡ የማያውቁ ፡ ሕዝቦች ፡
በመኾናቸው ፡ ነው ።
14 በተመሸጉ ፡ ከተሞች ፡ ውስጥ ፡
ወይም ፡ ከአጥሮች ፡ ጀርባ ፡
ኾነው ፡ እንጅ ፤ የተሰበሰቡ ፡
ኾነው ፡ አይዋጉዋችሁም ። ኀይ
ላቸው ፡ በመካከላቸው ፡ ብርቱ ፡
ነው ። ልቦቻቸው ፡ የተበታተኑ ፡
ሲኾኑ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ናቸው ፡
ብለህ ፡ ትጠረጥራቸዋለህ ። ይህ ፡
እነሱ ፡ አእምሮ ፡ የሌላቸው ፡
ሕዝቦች ፡ በመኾናቸው ፡ ነው ።
15 (ብጤያቸው) ፡ እንደነዚያ ፡ ከነሱ
በፊት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የነገራ
ቸውን ፡ ቅጣት ፡ እንደ ፡ ቀመ
ሱት ፡ ብጤ ፡ ነው ፤ ለነርሱም ፡
አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ።
16 እንደ ፡ ሰይጣን ፡ ብጤ ፡ ለሰው
የው ፡ ካድ ፡ ባለው ፡ ጊዜና ፡ በካ
ደም ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ከአንተ ፡
ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ እኔ ፡ አላህን ፡ የዓ
ለማትን ፡ ጌታ ፡ እፈራለሁ ፡ እን
ዳለው ፡ ነው ።
17 መጨረሻቸውም ፡ እነርሱ ፡ በው
ስጡ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡
በእሳት ፡ ውስጥ ፡ መኾን ፡ ነው ።
ይህም ፡ የበዳዮች ፡ ዋጋ ፡ ነው ።
18 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላ
ህን ፡ ፍሩ ፤ ማንኛይቱም ፡ ነፍስ ፡
ለነገ ፡ ያስቀደመችውን ፡ ትመ
ልከት ፤ አላህንም ፡ ፍሩ ፤ አላህ ፡
በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ውስጠ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።

19 እንደነዚያም ፡ አላህን ፡ እንደረ
ሱትና ፡ ነፍሶቻቸውን ፡ እንዳስ
ረሳቸው ፡ (ሰዎች) ፡ አትኹኑ ።
እነዚያ ፡ እነሱ ፡ አመጠኞቹ ፡
ናቸው ።
20 የእሳት ፡ ጓዶችና ፡ የገነት ፡ ጓዶች ፡
አይተካከሉም ፤ የገነት ፡ ጓዶች ፡
እነሱ ፡ ምኞታቸውን ፡ አግኚዎች ፡
ናቸው ።
21 ይህንን ፡ ቁርአን ፡ በተራራ ፡
ላይ ፡ ባወረድነው ፡ ኖሮ ፡ ከአላህ፡
ፍራቻ ፡ (የተነሳ) ፡ ተዋራጅ ፡
ተሰንጣቂ ፡ ኾኖ ፡ ባየኸው ፡
ነበር ፤ ይህችንም ፡ ምሳሌ ፡ ይገ
መግሙ ፡ ዘንድ ፡ ለሰዎች ፡ እንገ
ልጻታለን ።
22 እርሱ ፡ አላህ ፡ ነው ፤ ያ ፡ ከርሱ ፡
በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የሌለ ፡
ሩቁንና ፡ ቅርቡን ፡ ዐዋቂ ፡ የኾነ ፡
ነው ፤ እርሱ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ ነው ።
23 እርሱ ፡ አላህ ፡ ነው ፤ ያ ፡ ከርሱ ፡
በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የሌለ ፡
ንጉሡ ፤ ከጉድለት ፡ ሁሉ ፡
የጠራው ፡ የሰላም ፡ ባለቤቱ ፡
ጸጥታን ፡ ሰጪው ፡ ባሮቹን ፡
ጠባቂው ፡ አሸናፊው ፡ ኀያሉ ፡
ኩሩው ፡ ነው ። አላህ ፡ ከሚያ
ጋሩት ፡ ሁሉ ፡ ጠራ ።
24 እርሱ ፡ አላህ ፡ ፈጣሪው ፡ (ከኢ
ምንት) ፡ አስገኚው ፡ ቅርጽን ፡
አሳማሪው ፡ ነው ፤ ለርሱ ፡ መል
ካሞች ፡ ስሞች ፡ አሉት ፤ በሰማያ
ትና ፡ በምድርም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡
ለርሱ ፡ ያሞግሳል ፤ እርሱም ፡
አሸናፊው ፡ ጥበበኛው ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 60 ፡ አል-ሙምተሒናህ ። ክፍል ፡ 28 ፡

60ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሙምተሒናህ ፡ (የፈታኚቱ ፡ ምዕራፍ) ፤
በመዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 13 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ጠላ
ቶቼንና ፡ ጠላቶቻችሁን ፡ ወዳ
ጆች ፡ አድርጋችሁ ፡ አትያዙ ፤
ከውነቱ ፡ የመጣላችሁን ፡ ሃይማ
ኖት ፡ በእርግጥ ፡ የካዱ ፡ ሲኾኑ ፡
ውዴታን ፡ ወደነርሱ ፡ ታደርሳ
ላችሁ ። መልክተኛውንና ፡ እና
ንተን ፡ በአላህ ፡ በጌታችሁ ፡
ስላመናችሁ ፡ (ከመካ) ፡ ያወ
ጣሉ ፤ በመንገዴ ፡ ለመታገልና ፡
ውዴታዬን ፡ ለመፈለግ ፡ የወጣ
ችሁ ፡ እንደኾናችሁ ፡ (ወዳጆች ፡
አድርጋችሁ ፡ አትያዙዋቸው) ፤
እኔ ፡ የምትደብቁትንና ፡ የምት
ገልጹትን ፡ ሁሉ ፡ የማውቅ ፡
ስኾን ፡ ወደነርሱ ፡ በፍቅር ፡
ትመሣጠራላችሁ ፤ ከናንተም ፡
(ይህንን) ፡ የሚሠራው ፡ ሰው ፡
ቀጥተኛውን ፡ መንገድ ፡ በእር
ግጥ ፡ ተሳሳተ ።
2 ቢያሸንፏችሁ ፡ ለናንተ ፡ ጠላ
ቶች ፡ ይኾናሉ ፤ እጆቻቸውንና ፡
ምላሶቻቸውንም ፡ ወደናንተ ፡
በክፉ ፡ ይዘረጋሉ ፤ ብትክዱም ፡
ተመኙ ።
3 ዘመዶቻችሁም ፡ ልጆቻችሁም ፡
በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ አይጠቅሟ
ችሁም ፤ (አላህ) ፡ በመካከላችሁ ፡
ይለያል ፤ አላህም ፡ የምትሠሩ
ትን ፡ ሁሉ ፡ ተመልካች ፡ ነው ።
4 በኢብራሂምና ፡ በነዚያ ፡ ከርሱ ፡
ጋር ፡ በነበሩት ፡ (ምእምናን) ፡
መልካም ፡ መከተል ፡ አለቻ
ችሁ ። ለሕዝቦቻቸው ፡—እኛ ፡
ከናንተ ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡ ከምትግገ
ዙትም ፡ ንጹሖች ፡ ነን ፤ በናንተ ፡
ካድን ፤ በአላህ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡
ሲኾን ፡ እስከምታምኑ ፡ ድረስ ፡
በኛና ፡ በናንተ ፡ መካከል ፡ ጠብና፡
ጥላቻ ፡ ዘወትር ፡ ተገለጸ ፤ ባሉ ፡
ጊዜ ፡ (መልካም ፡ መከተል ፡
አለቻችሁ) ፤ ኢብራሂም ፡ ለአ
ባቱ ፡ እኔ ፡ ለአንተ ፡ ከአላህ ፡
(ቅጣት) ፡ ምንም ፡ የማልጠቅም ፡
ስኾን ፡ ለአንተ ፡ በእርግጥ ፡ ምሕ
ረትን ፡ እለምንልኻለሁ ፡ ማለቱ ፡
ብቻ ፡ ሲቀር ፤ ጌታችን ፡ ሆይ !
በአንተ ፡ ላይ ፡ ተመካን ፡ ወደ ፡
አንተም ፡ ተመለስን ፥ መመለ
ሻም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤
(ባለው ፡ ተከተሉት) ።
5 ጌታችን ፡ ሆይ! ለነዚያ ፡ ለካዱት ፡
ሰዎች ፡ መሞከሪያ ፡ አታድርገን ፤
ለኛም ፡ ምሕረት ፡ አድርግልን ፤
ጌታችን ፡ ሆይ ! አንተ ፡ አሸና
ፊው ፡ ጥበበኛው ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡
ነህ ።
6 ለናንተ ፡ አላህንና ፡ የመጨረሻ
ውን ፡ ቀን ፡ ለሚፈራ ፡ ሰው ፡
በነርሱ ፡ መልካም ፡ መከተል ፡
አላችሁ ። የሚዞርም ፡ ሰው ፡
(ራሱን ፡ ይጎዳል) ፤ አላህ ፡ ተብ
ቃቂው ፡ ምስጉኑ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡
ነውና ።
7 በናንተና ፡ በነዚያ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡
በተጣላችሁት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡
አላህ ፡ መፋቀርን ፡ ሊያደርግ ፡
ይችላል ፤ አላህም ፡ ቻይ ፡ ነው ።
አላህም ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ ነው ።
8 ከነዚያ ፡ በሃይማኖት ፡ ካልተጋ
ደሏችሁ ፡ ከአገሮቻችሁም ፡ ካላ
ወጡዋችሁ ፡ (ከሓዲዎች) ፡ መል
ካም ፡ ብትውሉላቸውና ፡ ወደነ
ርሱ ፡ ብታስተካክሉ ፡ አላህ ፡
አይከለክላችሁም ፤ አላህ ፡ ትክ
ክለኞችን ፡ ይወዳልና ።
9 አላህ ፡ የሚከለክላችሁ ፡ ከነዚያ ፡
በሃይማኖት ፡ ከተጋደሉዋችሁ ፡
ከቤቶቻችሁም ፡ ካወጡዋችሁ ፡
እናንተንም ፡ በማውጣት ፡ ላይ ፡
ከረዱት ፡ (ከሓዲዎች) ፡ እንዳት
ወዳጁዋቸው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ወ
ዳጅ ፡ የሚያደርጓቸውም ፡ ሰዎች ፡
እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ በዳዮቹ ፡ ና
ቸው ።
10 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ምእ
ምናት ፡ ስደተኞች ፡ ኾነው ፡
በመጧችሁ ፡ ጊዜ ፡ (ለሃይማ
ኖት ፡ መሰደዳቸውን) ፡ ፈትኑ
ዋቸው ፤ አላህ ፡ በእምነታቸው ፡
ይበልጥ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ። አማ
ኞችም ፡ መኾናቸውን ፡ ብታ
ውቁ ፡ ወደ ፡ ከሓዲዎቹ ፡ አት
መልሱዋቸው ። እነርሱ ፡ (ሴቶቹ)
ለነርሱ ፡ የተፈቀዱ ፡ አይደሉ
ምና ። እነርሱም ፡ (ወንዶቹ) ፡ ለነ
ርሱ ፡ አይፈቀዱምና ። ያወጡ
ትንም ፡ ገንዘብ ፡ ስጧቸው ፤ መህ
ራቸውንም ፡ በሰጣችኋቸው ፡

ጊዜ ፡ ብታገቡዋቸው ፡ በናንተ ፡
ላይ ፡ ኃጢአት ፡ የለባችሁም ።
የከሓዲዎቹንም ፡ ሴቶች ፡ የጋ
ብቻ ፡ ቃል ፡ ኪዳኖች ፡ አትያዙ ፤
(1) ያወጣችሁትንም ፡ ገንዘብ ፡
ጠይቁ ፤ ያወጡትንም ፡ ይጠ
ይቁ ፤ ይሃችሁ ፡ የአላህ ፡ ፍርድ ፡
ነው ፤ በመካከላችሁ ፡ ይፈርዳል ፤
አላህም ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበበኛ ፡ ነው ።
11 ከሚስቶቻችሁም ፡ ወደ ፡ ከሓዲ
ዎቹ ፡ አንዳቸው ፡ ቢያመልጧ
ችሁ ፡ ቀጥሎም ፡ ብትዘምቱባ
ቸው ፡ ለነዚያ ፡ ሚስቶቻቸው ፡
ለኼዱባቸው ፡ (ሰዎች) ፡ ያወጡ
ትን ፡ ብጤ ፡ ስጧቸው ፤ ያንንም ፡
እናንተ ፡ በርሱ ፡ ያመናችሁበ
ትን ፡ አላህን ፡ ፍሩ ።
12 አንተ ፡ ነቢዩ ፡ ሆይ ! ምእምና
ቶቹ ፡ በአላህ ፡ ምንንም ፡ ላያ
ጋሩ ፡ ላይሰርቁም ፡ ላያመነዝ
ሩም ፡ ልጆቻቸውን ፡ ላይገድ
ሉም ፡ በእጆቻቸውና ፡ በእግሮ
ቻቸው ፡ መካከልም ፡ የሚቀጣ
ጥፉት ፡ የኾነን ፡ ኃጢአት ፡
ላያመጡ ፡ (ላይሠሩ) ፡ በበጎም ፡
ሥራ ፡ ትእዛዝህን ፡ ላይጥሱ ፡
ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሊገቡልህ ፡ በመ
ጡህ ፡ ጊዜ ፡ ኪዳን ፡ ተጋባቸው ።
ለነርሱም ፡ አላህን ፡ ምሕረት ፡
ለምንላቸው ፤ አላህ ፡ በጣም ፡
መሓሪ ፡ አዛኝ ፡ ነውና ።
13 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! አላህ
በነሱ ፡ ላይ ፡ የተቆጣባቸውን ፡
ሕዝቦች ፡ አትወዳጁ ፤ ከሓዲዎች፣
ከመቃብር ፡ ሰዎች ፡ ተስፋ ፡ እን
ደቆረጡ፥ ከመጨረሻይቱ ፡ ዓለ
ም ፡ (ምንዳ) ፡ በእርግጥ ፡ ተስፋ ፡
ቆርጠዋል ።

1 እናንተ ፡ እምናችሁ ፡ እነርሱ ፡ ካላመኑ ፡ ጋብ
ቻው፡ ይፈርሳልና።

## ምዕራፍ ፡ 61 ፡ አል-ሶፍ ፡ ክፍል ፡ 28 ።

61ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሶፍ ፤ (የሰልፍ ፡ ምዕራፍ) ። በመዲና ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 14 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው።
1 በሰማያት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ በም
ድርም ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡
ለአላህ ፡ አሞገሠ ፤ እርሱም ፡
አሸናፊው ፡ ጥበበኛው ፡ ነው ።
2 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! የማ
ትሠሩትን ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ ትና
ገራላችሁ ?
3 የማትሠሩትን ፡ ነገር ፡ መናገራ
ችሁ ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡ መጠላቱ ፡
ተለቀ ።
4 አላህ ፡ እነዚያን ፡ እነርሱ ፡ ልክ ፡
እንደ ፡ ተናሰ ፡ ግንብ ፡ የተሰለ
ለፉ ፡ ኾነው ፡ በመንገዱ ፡ (በሃ
ይማኖቱ) ፡ የሚጋደሉትን ፡ ይወ
ዳል ።
5 ሙሳም ፡ ለሕዝቦቹ ፡ ሕዝቦቼ ፡
ሆይ ! እኔ ፡ ወደናንተ ፡ የአላህ ፡



መልክተኛ ፡ መኾኔን ፡ በእርግጥ ፡
የምታውቁ ፡ ስትኾኑ ፡ ለምን ፡
ታሰቃዩኛላችሁ ? ባለ ፡ ጊዜ ፡
(አስታውስ ፤ ከውነት) ፡ በተዘ
ነበሉም ፡ ጊዜ ፡ አላህ ፡ ልቦቻቸ
ውን ፡ አዘነበላቸው ፤ አላህም ፡
አመጠኞችን ፡ ሕዝቦች ፡ አያቀ
ናም ።
6 የመርየም ፡ ልጅ ፡ ዒሳም ፡—የእ
ስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡
ከተውራት ፡ በፊቴ ፡ ያለውን ፡
የማረጋገጥና ፡ ከኔ ፡ በኋላ ፡ በሚ
መጣው ፡ መልክተኛ ፡ ስሙ ፡
አሕመድ ፡ በኾነው ፡ የማበስር፡
ስኾን ፡ ወደናንተ ፡ (የተላክሁ) ፡
የአላህ ፡ መልክተኛ ፡ ነኝ ፡ ባለ ፡
ጊዜ ፡ (አስታውስ) ፤ በግልጽ ፡ ታም
ራቶች ፡ በመጣቸውም ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡
ግልጽ ፡ ድግምት ፡ ነው ፡ አሉ ።
7 ኀርሱ ፡ ወደ ፡ ኢስላም፡ የሚ
ጥጠራ ፡ ሲኾን ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡
ውሸትን ፡ ከቀጣጠፈ ፡ ሰውም ፡
ይበልጥ ፡ በደለኛ ፡ ማን ፡ ነው ?
አላህም ፡ በዳዮችን ፡ ሕዝቦች ፡
አይመራም ።
8 የአላህን ፡ ብርሃን ፡ በአፎቻቸው ፡
ሊያጠፉ ፡ ይሻሉ ፤ አላህም ፡ ከሓ
ዲዎቹ ፡ ቢጠሉም ፡ እንኳ ፡
ብርሃኑን ፡ ገላጭ ፡ ነው ።
9 እርሱ ፡ ያ ፡ አጋሪዎቹ ፡ ቢጠ
ሉም ፡ መልክተኛውን ፡ በመም
ሪያ ፡ (መጽሐፍ) ፡ በውነተኛው ፡
ሃይማኖትም ፡ (በኢስላም) ፡
ከሃይማኖት ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ይፋ ፡
ሊያደርገው ፡ የላከ ፡ ነው ።
10 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ከአ
ሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ የምታድናችሁ፡
የኾነችን ፡ ንግድ ፡ ላመላክታች
ሁን ? (በላቸው) ።
11 (እርሷም) ፡ በአላህና ፡ በመል
ክተኛው ፡ ታምናላችሁ ፤ በአላህ ፡
መንገድም ፡ በገንዘቦቻችሁ ፡ በነ
ፍሶቻችሁም ፡ ትታገላላችሁ ፤
ይሃችሁ ፡ የምታውቁ ፡ ብትኾኑ ፡
ለናንተ ፡ የተሻለ ፡ ነው ።
12 ኃጢአቶቻችሁን ፡ ለናንተ ፡ ይም
ራል ፤ ከሥሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡
የሚፈሱባቸውንም ፡ ገነቶች ፡
ያገባችኋል ፤ በመኖሪያ ፡ ገነቶችም
በሚያማምሩ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡
(ያስቀምጣችኋል) ፤ ይህ ፡ ታላቅ ፡
ዕድል ፡ ነው ።
13 ሌላይቱንም ፡ የምትወዷትን ፡
(ጸጋ ፡ ይሰጣችኋል) ፤ ከአላህ ፡
የኾነ ፡ እርዳታና ፡ ቅርብ ፡ የኾነ ፡
የአገር ፡ መክፈት ፡ ነው ፤ ምእም
ናንንም ፡ አብስር ።
14 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ፡
የመርየም ፡ ልጅ ፡ ዒሳ ፡ ለሐዋ
ርያቶቹ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡ ረዳቴ ፡
ማነው ? እንዳለ ፡ ሐዋርያቶቹም ፡
እኛ ፡ የአላህ ፡ ረዳቶች ፡ ነን ፡
እንዳሉት ፡ የአላህ ፡ ረዳቶች ፡
ኹኑ ፡ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡
አንደኛዋ ፡ ጭፍራ ፡ አመነች ፤
ሌላይቱም ፡ ጭፍራ ፡ ካደች ፤
እነዚያን ፡ ያመኑትንም ፡ በጠላ
ታቸው ፡ ላይ ፡ አበረታናቸው ፤
አሸናፊዎችም ፡ ኾኑ ።

62ኛ : ሱረቱ : አል-ጁሙዓህ ፡ (የዐርብ : ምዕራፍ) ። በመ
ዲና:የወረደች፡ናት፤አያትዋ፡(አንቀጾችዋ) : 11 : ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።

1 በሰማያት ፡ ያለው ፡ በምድርም ፡
ያለው ፡ ሁሉ ፡ ለአላህ -ንጉሥ፥
ቅዱስ ፡ አሸናፊ ፡ ጥበበኛ - ለኾ
ነው ፡ ያሞግሣል ።

2 እርሱ ፡ ያ ፡ በመሃይሞቹ ፡ ውስጥ፡
አንቀጾቹን ፡ (ቁርአንን) ፡ በነርሱ ፡
ላይ ፡ የሚያነብላቸው ፡ (ከማ
ጋራት) ፡ የሚያጠራቸውም ፡ መጽ
ሐፍንና ፡ ጥበብን ፡ የሚያስተም
ራቸውም ፡ የኾነን ፡ መልክተኛ ፡
(ሙሐመድን) ፡ ከነሱው ፡ ውስጥ፡
የላከ ፡ ነው ፤ እነርሱም ፡ ከርሱ ፡
በፊት ፡ በግልጽ ፡ስሕተት ፡ ው
ስጥ ፡ ነበሩ ።

3 ከነሱም ፡ ሌሎች ፡ ገና ፡ ያልተጠ
ጉዋቸው ፡ በኾኑት ፡ ላይ ፡ (የላ
ከው ፡ ነው) ፤ እርሱም ፡ አሸና
ፊው ፡ ጥበበኛው ፡ ነው ።

4 ይህ ፡ የአላህ ፡ ችሮታ ፡ ነው ፤
ለሚሻው ፡ ሰው ፡ ይሰጠዋል ፤
አላህም ፡ የታላቅ ፡ ችሮታ ፡ ባለ
ቤት ፡ ነው ።

5 የነዚያ ፡ ተውራትን ፡ የተጫኑ
ትና ፡ ከዚያም ፡ ያልተሸከሟት ፡
(ያልሠሩባት) ፡ ሰዎች ፡ ምሳሌ ፡
መጽሐፎችን ፡ እንደሚሸከም ፡ አ
ህያ ፡ ብጤ ፡ ነው ፤ የነዚያ ፡ በአ
ላህ ፡ አንቀጾች ፡ ያስተባበሉት ፡
ሕዝቦች ፡ ምሳሌ ፡ ከፋ ፤ አላህም ፡
በዳዮችን ፡ ሕዝቦች ፡ አይመ
ራም ።

6 እላንተ ፡ ይሁዳውያን ፡ የኾና
ችሁ ፡ ሆይ ! ከሰው ፡ ሁሉ ፡ በስተ
ቀር ፡ እናንተ ፡ ብቻ ፡ ለአላህ ፡
ወዳጆች ፡ ነን ፡ ብትሉ ፡ እውነተ
ኞች ፡ እንደኾናችሁ ፡ ሞትን ፡
ተመኙ ፡ በላቸው ።

7 እጆቻቸውም ፡ ባስቀደሙት ፡
ኃጢአት ፡ ምክንያት ፡ በፍጹም ፡
አይመኙትም ፤ አላህም ፡ በዳዮ
ቹን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።

8 ያ ፡ ከርሱ ፡ የምትሸሹት ፡ ሞት ፡
እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ አግኛችሁ ፡
ነው ፤ ከዚያም ፡ ሩቁንና ፡ ቅር
ቡን ፡ ዐዋቂ ፡ ወደ ፡ ኾነው ፡
ጌታ ፡ ትመለሳላችሁ ፤ ትሠሩ
ትም ፡ የነበራችሁትን ፡ ሁሉ ፡
ይነግራችኋል ፡ በላቸው ።

9 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! በዐ
ርብ ፡ ቀን ፡ ለስግደት ፡ ጥሪ ፡
በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አላህ ፡
ማውሳት ፡ ኺዱ ፤ መሸጥንም ፡
ተዉ ፤ ይሃችሁ ፡ የምታውቁ ፡
ብትኾኑ ፡ ለናንተ ፡ በጣም ፡ የተ
ሻለ ፡ ነው ።

10 ሶላቲቱም ፡ በተፈጸመች ፡ ጊዜ ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ ተበተኑ ፤ ከአላ
ህም ፡ ችሮታ ፡ ፈልጉ ፤ አላህንም፡
በብዙ ፡ አውሱ ፤ ልትድኑ ፡ ይከ
ጀላልና ።



11 ንግድን ፡ ወይም ፡ ዛዛታን ፡ ባዩ ፡
ጊዜም ፡ ቆመህ ፡ የተዉህ ፡ ሲ
ኾኑ ፡ ወደርሷ ፡ ይበተናሉ ፤ አላህ
ዘንድ ፡ ያለው ፡ ዋጋ ፡ ከዛዛታም ፡
ከንግድም ፡ በላጭ ፡ ነው ፤ አላ
ህም ፡ ከሰጪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ይበ
ልጥ ፡ ሲሳይን ፡ ሰጭ ፡ ነው ፡
በላቸው ።

ምዕራፍ ፡ 63 ፡ አል-ሙናፊቁን ፡ ክፍል ፡ 28 ።

63ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሙናፊቁን ፤ (የመናፍቃን ፡ ምዕራፍ) ።
በመዲና፡የወረደች፡ናት፤አያትዋ፡(አንቀጾችዋ)፡ 11 ፡ናቸው ።

1 በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው፡
መናፍቃን ፡ በመጡህ ፡ ጊዜ ፡
አንተ ፡ የአላህ ፡ መልክተኛ ፡
መኾንህን ፡ በእርግጥ ፡ (ምለን) ፡
እንመሰክራለን ፡ ይላሉ ፤ አላህም፡
አንተ ፡ በእርግጥ ፡ መልክተኛው ፡
መኾንህን ፡ ያውቃል ፤ አላህም ፡
መናፍቃን ፡ (ከልብ ፡ እንመሰክራ
ለን ፡ በማለታቸው)፡ ውሸታሞች፡
መኾናቸውን ፡ ይመሰክራል ።

2 መሐሎቻቸውን ፡ ጋሻ ፡ አድር
ገው ፡ ያዙ ፤ ከአላህም ፡ መንገድ ፡
ከለከሉ ፤ እነሱ ፡ ይሠሩት ፡ የነ
በሩት ፡ ነገር ፡ ከፋ ።

3 ይህ ፡ እነሱ ፡ (በምላስ) ፡ ያመኑ ፡
ከዚያም ፡ (በልብ) ፡ የካዱ ፡ በመ
ኾናቸው ፡ ነው ፤ በልቦቻቸውም፡
ላይ ፡ ታትመባቸው ፤ ስለዚህ ፡
እነሱ ፡ አያውቁም ።

4 ባየሃቸውም ፡ ጊዜ ፡ አካሎቻቸው፡
(ግዙፍነታቸው) ፡ ያስደንቁሃል ፤
ቢናገሩም ፡ ለንግግራቸው ፡ ታዳ
ምጣለህ ፤ (ከዕውቀት ፡ ባዶ ፡
በመኾን) ፡ እነርሱ ፡ ልክ ፡ በግ
ድግዳ ፡ የተጠጉ ፡ ግንዶችን ፡
ይመስላሉ ፤ ጩኸትን ፡ ሁሉ ፡
በነሱ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ብለው ፡
ያስባሉ ፤ እነሱ ፡ ጠላቶች ፡ ናቸ
ውና ፡ ተጠንቀቃቸው ፤ አላህ ፡
ይጋደላቸው ፤ (ከእምነት) ፡ እን
ዴት ፡ ይመለሳሉ !

5 ለነሱም ፡— ኑ ፡ የአላህ ፡ መል
ክተኛ ፡ ለናንተ ፡ ምሕረትን ፡ ይለ
ምንላችኋል ፤ በተባሉ ፡ ጊዜ ፡
ራሶቻቸውን ፡ ያዞራሉ ፤ እነሱም፡
ትዕቢተኞች ፡ ኾነው ፡ ሲሸሹ ፡
ታያቸዋለህ ።

6 ምሕረትን ፡ ብትለምንላቸው ፡
ወይም ፡ ምሕረትን ፡ ባትለምን
ላቸው ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ እኩል ፡
ነው ፤ አላህ ፡ ለነሱ ፡ በፍጹም ፡
አይምርም ፤ አላህ ፡ አመጠኞችን ፡
ሕዝቦች ፡ አይመራምና ።

7 እነሱ ፡ እነዚያ ፡—አላህ ፡ መል
ክተኛ ፡ ዘንድ ፡ ላሉት ፡ ሰዎች ፡
እስከሚበታተኑ ፡ ድረስ ፡ አት
ቀልቡ ፡ የሚሉ ፡ ናቸው ፤ የሰማ
ያትና ፡ የምድር ፡ ድልቦችም ፡

የአላህ ፡ ናቸው ፤ ግን ፡ መናፍ
ቃን ፡ አያውቁም ።
8 ወደ ፡ መዲና ፡ ብንመለስ ፡ አሸ
ናፊው ፡ ወራዳውን ፡ በእርግጥ ፡
ከርሷ ፡ ያወጣል ፡ ይላሉ ፤ አሸ
ናፊነትም ፡ ለአላህ ፡ ለመልክተ
ኛውና ፡ ለምእምናን ፡ ነው ፤
ግን ፡ መናፍቃን ፡ አያውቁም ።
9 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ፡ ገንዘ
ቦቻችሁና ፡ ልጆቻችሁ ፡ አላህን ፡
ከማስታወስ ፡ አያታሉዋችሁ ፤ ይ
ህንንም ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ እነ
ዚያ ፡ እነሱ ፡ ከሳሪዎቹ ፡ ናቸው ።
10 አንዳችሁንም ፡ ሞት ፡ ሳይመ
ጣውና ፡—ጌታዬ ፡ ሆይ ! እንድ
መጸውትና ፡ ከደጋጎቹም ፡ ሰዎች
እንድኾን ፡ ወደ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡
ብታቆየኝ ፡ ኖሮ ፡ እመኛለሁ ፡
ከማለቱ ፡ በፊት ፡ ከሰጠናችሁ ፡
ሲሳይ ፡ ለግሱ ።
11 ማንኛይቱንም ፡ ነፍስ ፡ (የሞት) ፡
ጊዜዋ ፡ በመጣባት ፡ ጊዜ ፡ አላህ ፡
በፍጹም ፡ አያቆያትም ። አላህም፡
በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ውስጠ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 64 ፡ አል-ተጋቡን ። ክፍል ፡ 28 ።

64ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ተጋቡን ፤ (የመኰዳዳት ፡ ምዕራፍ) ። አብዛኞቹ ፡ እንደሚሉት ፡ መዲናዊ ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 18 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 በሰማያት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡
በምድርም ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡
ሁሉ ፡ ለአላህ ፡ ያሞግሳል ፤ ንግ
ሥናው ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤
ምስጋናም ፡ ለርሱ ፡ ነው ፤ እር
ሱም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡
ነው ።
2 እርሱ ፡ ያ ፡ የፈጠራችሁ ፡ ነው ፤
ከናንተም ፡ ከሓዲ ፡ አልለ ፤ ከናን
ተም ፡ አማኝ ፡ አልለ ፤ አላህም ፡
በምትሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ተመልካች ፡
ነው ።
3 ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ በውነት ፡
ፈጠረ ፤ ቀረጻችሁም ፡ ቅርጻችሁ
ንም ፡ አሳመረ ፤ መመለሻችሁም ፡
ወደርሱ ፡ ነው ።
4 በሰማያትና ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡
ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል ፤ የም
ትደብቁትንም ፡ የምትገልጡት
ንም ፡ ያውቃል ፤ አላህም ፡ በል
ቦች ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።
5 የነዚያ ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡ የካዱ
ትና ፡ የክሕደታቸውን ፡ ቅጣት ፡
ቅመሱ ፡ የተባሉት ፡ ሕዝቦች ፡
ወሬ ፡ አልመጣላችሁምን ? ለነ
ሱም ፡ አሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ አል
ላቸው ።
6 ይህ ፡ (ቅጣት) ፡ እርሱ ፡ መልክተ
ኞቻቸው ፡ በአስረጂዎች ፡ ይመጡ



ባቸው ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ሰዎችም ፡
ይመሩናልን ? ስላሉና ፡ ስለካዱ ፡
(ከእምነት) ፡ ስለ ፡ ዞሩም ፡ ነው ፤
አላህም ፡ (ከነሱ ፡ እምነት) ፡
ተብቃቃ ፤ አላህም ፡ ተብቃቂ ፡
ምስጉን ፡ ነው ።
7 እነዚያ ፡ የካዱት ፡ በፍጹም ፡
የማይቀሰቀሱ ፡ መኾናቸውን ፡
አሰቡ ፤ አይደለም ፡ በጌታዬ ፡
እምላለሁ ፤ በእርግጥ ፡ ትቀሰቀ
ሳላችሁ ፤ ከዚያም ፡ በሠራችሁት፡
ሁሉ ፡ ትነገራላችሁ ፤ ይህም ፡
በአላህ ፡ ላይ ፡ ቀላል ፡ ነው ፤
በላቸው ።
8 በአላህና ፡ በመልክተኛውም ፤
በዚያም ፡ ባወረድነው ፡ ብርሃን ፡
እመኑ ፤ አላህም ፡ በምትሠሩት ፡
ሁሉ ፡ ውስጠ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፡
(በላቸው) ።
9 ለመሰብሰቢያው ፡ ቀን ፡ የሚሰበ
ስብባችሁን ፡ ቀን ፡ (አስታውሱ) ፤
ይህ ፡ የመኰዳዳት ፡ (መግለጫ) ፡
ቀን ፡ ነው ፤ (1) በአላህም ፡ የሚ
ያምን ፡ ሰው ፡ መልካምንም ፡
የሚሠራ ፡ ከርሱ ፡ ኀጢአቶቹን ፡
ይሰርይለታል ፤ (ይፍቅለታል) ፤
ከሥሮቻቸውም ፡ ወንዞች ፡ የሚ
ፈሱባቸውን ፡ ገነቶች ፡ በውስጣ
ቸው ፡ ዘለዓለም ፡ ዘውታሪዎች ፡
ሲኾኑ ፡ ያገባዋል ፤ ይህ ፡ ታላቅ ፡
ማግኘት ፡ ነው ።
10 እነዚያም ፡ የካዱና ፡ በአንቀጾ
ቻችን ፡ ያስተባበሉ ፡ እነዚያ ፡
በውስጡ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡
የእሳት ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ፤ መመ
ለሻቸውም ፡ ከፋ !
11 ከመከራም ፡ (ማንንም) ፡ አይነ
ካም ፡ በአላህ ፡ ፈቃድ ፡ ቢኾን ፡
እንጅ ፤ በአላህም ፡ የሚያምን ፡
ሰው ፡ ልቡን ፡ (ለትዕግሥት) ፡
ይመራዋል ፤ አላህም ፡ ነገሩን ፡
ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
12 አላህንም ፡ ተገዙ ፤ መልክተኛ
ውንም ፡ ታዘዙ ፤ ብትዞሩም ፡
(መልክተኛውን ፡ አትጐዱም) ፤
በመልክተኛውም ፡ ላይ ፡ ያለ
በት ፡ ግልጽ ፡ ማድረስ ፡ ብቻ ፡
ነው ።
13 አላህ ፡ ከርሱ ፡ በቀር ፡ አምላክ ፡
የለም ፤ በአላህም ፡ ላይ ፡ አማ
ኞቹ ፡ ይመኩ ።
14 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ! ከሚ
ስቶቻችሁና ፡ ከልጆቻችሁ ፡ (ከአ
ላህ ፡ መንገድ ፡ በማስተጓጐል) ፡
ለናንተ ፡ ጠላቶች ፡ የኾኑ ፡ አል
ሉ ፤ ስለዚህ ፡ ተጠንቀቋቸው ፤
ይቅርታ ፡ ብታደርጉ ፡ ብታል
ፉቸውም ፡ ብትምሩዋቸውም ፡
አላህ ፡ በጣም ፡ መሐሪ ፡ አዛኝ ፡
ነው ።
15 ገንዘቦቻችሁና ፡ ልጆቻችሁ ፡ ለና
ንተ ፡ መፈተኛ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፤
አላህም ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡
ምንዳ ፡ አልለ ።
16 አላህንም ፡ የቻላችሁትን ፡ ያክል ፡
ፍሩት ፤ ትእዛዙን ፡ ስሙም ፤
ታዘዙም ፤ ለግሱም ፤ ለነፍሶቻ
ችሁ ፡ መልካምን ፡ (ይሰጣችኋ
ልና) ፤ የነፍሱንም ፡ ንፍገት ፡
የሚጠበቅ ፡ ሰው ፡ እነዚያ ፡
እነሱ ፡ ፍላጐታቸውን ፡ የሚያ
ገኙ ፡ ናቸው ።
17 ለአላህ ፡ መልካም ፡ ብድርን ፡
ብታበድሩ ፡ (ምንዳውን) ፡ ለና

---
1 ምእምናን ፡ የከሓዲዎችን ፡ ቤቶች ፡ ይወር
ሳሉ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከሓዲዎቹም ፡ ጉዳታ
ቸው ፡ ስለሚገለጥ ፡ ይቆጫሉ ።

ንተ ፡ ይደራርበዋል ፤ ለናንተም ፡
ይምራል ፤ አላህም ፡ አመስጋኝ ፡
ታጋሽ ፡ ነው ።
18 ሩቁን ፡ ምስጢር ፡ ግልጹንም ፡
ሁሉ ፡ ዐዋቂው ፡ አሸናፊው ፡
ጥበበኛው ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 65 ፡ አል-ጠላቅ ። ክፍል ፡ 28 ።

65ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ጠላቅ ፡ (የፍች ፡ ምዕራፍ) ፤ በመዲና ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 12 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 አንተ ፡ ነቢዩ ፡ ሆይ ! ሴቶችን ፡
መፍታት ፡ ባሰባችሁ ፡ ጊዜ ፤
ለዒዳቸው ፡ (1) ፍቱዋቸው ፤
ዒዳንም ፡ ቁጠሩ፤ አላህንም ፡
ጌታችሁን ፡ ፍሩ ፤ ግልጽ ፡ የኾነ
ችን ፡ ጠያፍ ፡ ካልሠሩ ፡ በስተ
ቀር ፡ ከቤቶቻቸው ፡ አታውጡ
ዋቸው ፤ አይውጡም ፤ ይህችም ፡
የአላህ ፡ ሕግጋት ፡ ናት ፤ የአላ
ህንም ፡ ሕግጋት ፡ የተላለፈ ፡
ሰው ፡ በእርግጥ ፡ ነፍሱን ፡
በደለ ፤ ከዚህ ፡ (ፍች) ፡ በኋላ ፡
አላህ ፡ (የመማለስ) ፡ ነገርን ፡
ምናልባት ፡ ያመጣ ፡ እንደ ፡
ኾነ ፡ አታውቅም ።
2 ጊዜያቸውንም ፡ በመዳረስ ፡ በተ
ቃረቡ ፡ ጊዜ ፡ በመልካም ፡ ያዙ
ዋቸው ፤ ወይም ፡ በመልካም ፡
ተለያዩዋቸው ፤ ከናንተም ፡ ው
ስጥ ፡ ሁለት ፡ የትክክለኛነት ፡
ባለቤቶችን ፡ አስመስክሩ ፤ ምስ
ክርነትንም ፡ ለአላህ ፡ አስተካ
ክሉ ፤ ይሃችሁ ፡ በአላህና ፡ በመ
ጨረሻው ፡ ቀን ፡ የሚያምን ፡
የኾነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡
ይገሠጽበታል ፤ አላህንም ፡ የሚ
ፈራ ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡ መውጫን ፡
ያደርግለታል ።
3 ከማያስበውም ፡ በኩል ፡ ሲሳ
ይን ፡ ይሰጠዋል ፤ በአላህም ፡ ላይ፡
የሚጠጋ ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡ በቂው ፡
ነው ፤ አላህ ፡ ፈቃዱን ፡ አድራሽ ፡
ነው ፤ አላህ ፡ ለነገሩ ፡ ሁሉ ፡ የተ
ወሰነ ፡ ጊዜን ፡ በእርግጥ ፡ አድ
ርጓል ።
4 እሊያም ፡ ከሴቶቻችሁ ፡ ከአደፍ፡
ያቋረጡት ፡ (በዒዳቸው ፡ ሕግ) ፡
ብትጠራጠሩ ፡ ዒዳቸው ፡ ሦስት ፡
ወር ፡ ነው ፤ እሊያም ፡ ገና ፡ አደ
ፍን ፡ ያላዩት ፡ (ዒዳቸው ፡ እንደ
ዚሁ ፡ ነው) ፤ የእርግዝና ፡ ባለቤ
ቶችም ፡ ጊዜያቸው ፡ እርጉዛቸ
ውን ፡ መውለድ ፡ ነው ፤ አላህ
ንም ፡ የሚፈራ ፡ ሰው ፡ ከነገሩ ፡
ሁሉ ፡ ለርሱ ፡ መግራትን ፡ ያደ
ርግለታል ።
5 ይህ ፡ የአላህ ፡ ፍርድ ፡ ነው ፤ ወደ
ናንተ ፡ አወረደው ፤ አላህንም ፡

1 በንጽሕና ፡ ወራታቸው ፡ መጀመሪያ ፡ ከአ
ደፋቸው ፡ እንደ ፡ ጠሩ ፡ ሳትነኳቸው ፡
ፍቷቸው ።



የሚፈራ ፡ ሰው ፡ ኀጢአቶቹን ፡
ከርሱ ፡ ይሰርይለታል ፤ ምንዳንም፡
ለርሱ ፡ ያተልቅለታል ።
6 ከችሎታችሁ ፡ ከተቀመጣችሁበት፡
ስፍራ ፡ አስቀምጧቸው ፤ በነሱም፡
ላይ ፡ ልታጣብቡ ፡ አትጉዷቸው ፤
የእርግዝና ፡ ባለቤቶችም ፡ ቢኾኑ ፡
እርጉዛቸውን ፡ እስኪወልዱ፡ ድ
ረስ ፡ በነሱ ላይ ቀልቡ ፤ ለናን
ተም (ልጆቻችሁን) ቢያጠቡ
ላችሁ ፡ ምንዳዎቻቸውን ፡ ስጧ
ቸው ፤ በመካከላችሁም ፡ በመል
ካም ፡ ነገር ፡ ተመካከሩ ፤ ብትቻ
ጋገሩም ፡ ለርሱ ፡ ሌላ ፡ (ሴት) ፡
ታጠባለታለች ።
7 የችሎታ ፡ ባለቤት ፡ ከችሎታው ፡
ይቀልብ ፤ በርሱም ፡ ላይ ፡ሲሳዩ ፡
የተጠበበበት ፡ ሰው ፡ አላህ ፡
ነፍስን ፡ የሰጣትን ፡ እንጅ ፡ አያ
ስገድድም ፤ አላህ ፡ ከችግር ፡
በኋላ ፡ ምቾትን ፡ በእርግጥ ፡
ያደርጋል ።
8 ከከተማም ፡ ከጌታዋ ፡ ትእዛዝ ፡
ከመልክተኞቹም ፡ ያመጠች ፡
ብርቱንም ፡ ቍጥጥር ፡ የተቆጣጠ
ርናት ፡ መጥፎንም ፡ ቅጣት ፡ የቀ
ጣናት ፡ ብዙ ፡ ናት ።
9 የነገርዋንም ፡ ቅጣት ፡ ቀመሰች ፡
የነገርዋም ፡ መጨረሻ ፡ ከሳራ ፡
ኾነ ።
10 አላህ ፡ ለነሱ ፡ ብርቱን ፡ ቅጣት ፡
አዘጋጀ ፤ እናንተም ፡ የአእምሮ ፡
ባለ ፡ ቤቶች ፡ ሆይ ፡ አላህን ፡
ፍሩ ፤ እነዚያ ፡ ያመኑ ፡ (ሆይ)!
አላህ ፡ ወደናንተ ፡ ግሣጼን ፡
በእርግጥ ፡ አወረደ ፤ መልክተ
ኛን ፡ (ላከ) ።
11 እነዚያን ፡ ያመኑትንና ፡ መልካ
ሞችን ፡ የሠሩትን ፡ ከጨለማ
ዎች ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ያወጣ ፡
ዘንድ ፡ የአላህን ፡ አንቀጾች ፡ ገላ
ጮች ፡ ሲኾኑ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡
የሚያነብላችሁን ፡ (ላከ) ፤ በአላ
ህም ፡ አንቀጾች ፡ የሚያምን ፡
መልካምን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራም ፡
ከሥሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈ
ሱባቸውን ፡ ገነቶች ፡ በውስጣ
ቸው ፡ ዘለዓለም ፡ ዘውታሪዎች ፡
ሲኾኑ ፡ ያገባዋል ፤ አላህ ፡ ለ
ርሱ ፡ ሲሳይን ፡ በእርግጥ ፡ አሳ
መረ ።
12 አላህ ፡ ያ ፡ ሰባትን ፡ ሰማያት ፡
የፈጠረ ፡ ነው ፤ ከምድርም ፡ መሰ
ላቸውን ፡ (ፈጠረአል) ፤ በመካከ
ላቸው ፡ ትእዛዙ ፡ ይወርዳል ፤
አላህ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡
መኾኑን ፡ አላህም ፡ በነገሩ ፡
ሁሉ ፡ በዕውቀት ፡ ያካበበ ፡ መኾ
ኑን ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ (ይህንን ፡
አሳወቃችሁ) ።

66ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ተሕሪም ፤ (የማውገዝ ፡ ምዕራፍ) ። በመ
ዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 12 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።

1 አንተ ፡ ነቢዩ ፡ ሆይ ፡ አላህ ፡ ለአ
ንተ ፡ የፈቀደልህን ፡ ነገር ፡ ሚስ
ቶችህን ፡ ማስወደድን ፡ የምትፈ
ልግ ፡ ስትኾን ፡ (ባንተ ፡ ላይ) ፡
ለምን ፡ እርም ፡ ታደርጋለህ ፤ አላ
ህም ፡ እጅግ ፡ መሓሪ ፡ አዛኝ ፡
ነው ።

2 አላህ ፡ ለናንተ ፡ የመሓላዎቻች
ሁን ፡ መፍቻ ፡ ደነገገላችሁ ፤ አላ
ህም ፡ ረዳታችሁ ፡ ነው ፤ እርሱም፡
ዐዋቂው ፡ ጥበበኛው ፡ ነው ።

3 ነቢዩ ፡ ከሚስቶቹ ፡ ወደ ፡ አንዷ ፡
ወሬን ፡ በመሠጠረ ፡ ጊዜ ፡ (አስ
ታውስ) ፤ እርሱንም ፡ በነገረችና ፡
አላህ ፡ እርሱን ፡ (ማውራትዋን) ፡
ባሳወቀው ፡ ጊዜ ፡ ከፊሉን ፡ አስ
ታወቀ ፤ ከፊሉንም ፡ ተወ ፤ በር
ሱም ፡ ባወራት ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡
ማን ፡ ነገረህ ? አለች ፤ ዐዋቂው ፡
ውስጠ ፡ ዐዋቂው ፡ ነገረኝ ፡ አላት፤

4 ወደ ፡ አላህ ፡ ብትመለሱ ፡ ልቦቻ
ችሁ ፡ በእርግጥ ፡ ተዘንብለዋልና ፡
(ትስሰማላችሁ) ፤ በርሱም ፡ ላይ ፡
ብትረዳዱ ፡ አላህ ፡ እርሱ ፡ ረዳቱ ፡
ነው ፤ ጂብሪልም ፡ ከምእምናንም፡
መልካሙ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መላ
እክቱ ፡ ረዳቶቹ ፡ ናቸው ።

5 (መላችሁንም) ፡ ቢፈታችሁ ፡ ከና
ንተ ፡ የበለጡ ፡ ሚስቶችን ፡ እስላ
ሞች ፡ አማኞች ፡ ታዛዦች ፡ ተጸ
ጸቾች ፡ (ለአላህ) ፡ ተገዢዎች ፡
ጿመኞዎች ፡ ፈቶች ፡ ደናግልም ፡
የኾኑትን ፡ ጌታው ፡ ሊለውጠው ፡
ይከጀላል ።

6 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ ፡ ነፍሶ
ቻችሁንና ፡ ቤተሰቦቻችሁን ፡
መቀጣጠያዋ ፡ ሰዎችና ፡ ደንጊያ
ዎች ፡ ከኾነች ፡ እሳት ፡ ጠብቁ ፤
በርሷ ፡ ላይ ፡ ጨካኞች ፡ ኀይለ
ኞች ፡ የኾኑ ፡ መላእክት ፡ አልሉ ፤
አላህን ፡ ያዘዛቸውን ፡ ነገር ፡
(በመጣስ) ፡ ኢያምጡም ፤ የሚታ
ዘዙትንም ፡ ሁሉ ፡ ይሠራሉ ።

7 እላንተ ፡ የካዳችሁ ፡ ሆይ! ዛሬ ፡
አታመካኙ ፤ የምትመነዱት ፡
ያንን ፡ ትሠሩት ፡ የነበራችሁትን ፡
ብቻ ፡ ነው ፡ (ይባላሉ) ።

8 እላንተ ፡ ያመናችሁ ፡ ሆይ! ንጹሕ፡
የኾነችን ፡ ጸጸት ፡ በመጸጸት ፡
ወደ ፡ አላህ ፡ ተመለሱ ፤ ጌታችሁ፡
ከናንተ ፡ ኀጢአቶቻችሁን ፡ ሊሰ
ርይላችሁ ፡ ከሥሮቻቸው ፡ ወን
ዞች ፡ የሚፈሱባቸውንም ፡ ገነ
ቶች ፡ ሊያስገባችሁ ፡ ይከጀላልና ፤
አላህ ፡ ነቢዩን ፡ እነዚያንም ፡
ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያመኑትን ፡ በማያሳ
ፍርበት ፡ ቀን ፡ ብርሃናቸው ፡ በፊ
ቶቻቸውና ፡ በቀኞቻቸው ፡ የሚ
ሮጥ ፡ ሲኾን ፡ ጌታችን ፡ ሆይ !
ብርሃናችንን ፡ ሙላልን ፤ ለኛ ፡
ምሕረትም ፡ አድርግልን ፤ አንተ ፡
በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ ነህና ፡
ይላሉ ።



9 አንተ ፡ ነቢዩ ፡ ሆይ ! ከሓዲዎ
ችንና ፡ መናፍቃንን ፡ ታገል ፡
በነሱም ፡ ላይ ፡ በርታ ፤ መኖሪያ
ቸውም ፡ ገሀነም ፡ ናት ፤ ምን ፡
ትከፋም ፡ መመለሻ !

10 አላህ ፡ ለነዚያ ፡ ለካዱት ፡ ሰዎች፡
የኑሕን ፡ ሴትና ፡ የሉጥን ፡ ሴት ፡
ምሳሌ ፡ አደረገ ፤ ከባሮቻችን ፡
ከኾኑ ፡ ሁለት ፡ መልካም ፡ ባሪ
ያዎች ፡ ሥር ፡ ነበሩ ፤ ከዱዋቸ
ውም ፤ ከአላህም ፡ (ቅጣት ፡
ኑሕና ፡ ሉጥ) ፡ ከሚስቶቻቸው ፡
ምንም ፡ አልገፈተሩላቸውም ፤ ከገ
ቢዎቹም ፡ ጋር ፡ እሳትን ፡ ግቡ ፡
ተባሉ ።

11 ለነዚያ ፡ ለአመኑትም ፡ የፈርዖ
ንን ፡ ሴት ፡ አላህ ፡ ምሳሌ ፡ አደ
ረገ ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ ! አንተ ፡ ዘንድ ፡
በገነት ፡ ውስጥ ፡ ለኔ ፡ ቤትን ፡ ገን
ባልኝ ፤ ከፈርዖንና ፡ ከሥራውም ፡
አድነኝ ፤ ከበደለኞቹ ፡ ሕዝቦችም ፡
አድነኝ ፡ ባለች ፡ ጊዜ ።

12 የዒምራንን ፡ ልጅ ፡ መርየምንም፡
ያችን ፡ ብልቷን ፡ የጠበቀችውን ፡
(ምሳሌ ፡ አደረገ) ፤ በርሱም ፡
ውስጥ ፡ ከመንፈሳችን ፡ነፋፋን፤
በጌታዋ ፡ ቃላትና ፡ በመጻሕፍ
ቱም ፡ አረጋገጠች ፤ ከታዛዦ
ቹም ፡ ነበረች ።

ምዕራፍ ፡ 67 ፡ አል-ሙልክ ። ክፍል ፡ 29 ።

★ ★ ★

67ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሙልክ ፤ (የንግሥና ፡ ምዕራፍ) ። በ
መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 30 ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።

1 ያ ፡ ንግሥና ፡ በእጁ ፡ የኾነው ፡
አምላክ ፡ ችሮታው ፡ በዛ ፤ እር
ሱም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡
ነው ።

2 ያ ፡ የትኛችሁ ፡ ሥራው ፡ ይበ
ልጥ ፡ ያማረ ፡ መኾኑን ፡ ሊሞ
ክራችሁ ፡ ሞትንና ፡ ሕይወትን ፡
የፈጠረ ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ አሸ
ናፊው ፡ መሓሪው ፡ ነው ።

3 ያ ፡ ሰባትን ፡ ሰማያት ፡ የተነባ
በሩ ፡ ኾነው ፡ የፈጠረ ፡ ነው ።
በአልረሕማን ፡ አፈጣጠር ፡ ው
ስጥ ፡ ምንም ፡ መዛነፍን ፡ አታ
ይም ። ዓይንህንም ፡ መልስ ፤
ከስንጥቆች ፡ አንዳችን ፡ ታያለ
ህን ?

4 ከዚያም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዓይን
ህን ፡ መላልስ ። ዓይንህ ፡ ተዋ
ርዶ ፡ እርሱም ፡ የደከመ ፡ ኾኖ ፡
ወዳንተ ፡ ይመለሳል ።

5 ቅርቢቱን ፡ ሰማይም ፡ በእርግጥ ፡
በመብራቶች ፡ (በከዋክብት) ፡
አጌጥናት ፤ ለሰይጣናትም ፡ መቀ

ጥቀጫዎች ፡ አደረግናት ። ለነ
ርሱም ፡ (ለሰይጣናች) ፡ የእሳ
ትን ፡ ቅጣት ፡ አዘጋጀን ።
6 ለነዚያም ፡ በጌታቸው ፡ ለካዱት ፡
የገሀነም ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ፤
መመለሻይቱም ፡ ከፋች !
7 በውስጧ ፡ በተጣሉ ፡ ጊዜ ፤ እርሷ ፡
የምትፈላ ፡ ስትኾን ፡ ለርሷ ፡
(እንደ ፡ አህያ) ፡ ማናፋትን ፡
ይሰማሉ ።
8 ከቁጭትዋ ፡ የተነሳ ፡ ልትቆራ
ረጥ ፡ ትቀርባለች ፤ በውስጧ ፡
ጭፍሮች ፡ በተጣሉ ፡ ቍጥር ፡
ዘበኞችዋ ፡ አስፈራሪ ፡ (ነቢይ) ፡
አልመጣችሁምን ? በማለት ፡
ይጠይቋቸዋል ።
9 አይደለም ፡ በእርግጥ ፡ አስፈራሪ ፡
መጥቶናል ፤ አስተባበልንም ፤
አላህም ፡ ምንንም ፡ አላወረደ ፡
እናንተ ፡ (አውርዷል ፡ ስትሉ) ፡
በትልቅ ፡ ስሕተት ፡ ውስጥ ፡
እንጅ ፡ አይደላችሁም ፡ አልን ፡
ይላሉ ።
10 የምንሰማ ፡ ወይም ፡ የምናስብ ፡
በነበርንም ፡ ኖሮ ፡ በነዳጅ ፡ እሳት
ጓዶች ፡ ውስጥ ፡ ባልኾን ፡ ነበር ፡
ይላሉ ።
11 በኀጢአታቸውም ፡ ያምናሉ ፡
ለእሳት ፡ ጓዶችም ፡ (ከእዝነት) ፡
መራቅ ፡ ተገባቸው ።
12 እነዚያ ፡ ጌታቸውን ፡ በሩቁ ፡
የሚፈሩ ፡ ለነሱ ፡ ምሕረትና ፡
ታላቅ ፡ ምንዳ ፡ አላቸው ።
13 (ሰዎች ፡ ሆይ !) ቃላችሁንም ፡
መሥጥሩ ፤ ወይም ፡ በርሱ ፡
ጩሁ ፤ እርሱ ፡ በልቦች ፡ ውስጥ ፡
ያለን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
14 የፈጠረ ፡ አምላክ ፡ እርሱ ፡ ዕው
ቀት ፡ ረቂቁ ፡ ውስጥ ፡ ዐዋቂው ፡
ሲኾን ፡ (ምስጢርን ፡ ሁሉ) ፡
አያውቅምን ?
15 እርሱ ፡ ያ ፡ ምድርን ፡ ለናንተ ፡
የተገራች ፡ ያደረገላችሁ ፡ ነው ፤
በጋራዎችዋና ፡ በመንገዶችዋም ፡
ኺዱ ፡ ከሲሳዩም ፡ ብሉ ፤ (ኋላ) ፡
መመለሻውም ፡ ወደርሱ ፡ ብቻ ፡
ነው ።
16 በሰማይ ፡ ውስጥ ፡ ያለን ፡ (ስራ
ዊት) ፡ በናንተ ፡ ምድርን ፡ ቢደረ
ባባችሁ ፡ ወዲያውም ፡ እርሷ ፡
የምታረገርግ ፡ ብትኾን ፡ ትተማ
መናላችሁን ? (አትፈሩምን ?)
17 ወይም ፡ በሰማይ ፡ ውስጥ ፡ ያለን ፡
በናንተ ፡ ላይ ፡ ጠጠርን ፡ ያዘለች ፡
ነፋስን ፡ ቢልክባችሁ ፡ ትተማ
መናላችሁን ? (አትፈሩምን ?) ማ
ስጠንቀቄም ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡
ኾነ ፡ ወደፊት ፡ ታውቃላችሁ ።
18 እነዚያም ፡ ከነሱ ፡ በፊት ፡ የነበ
ሩት ፡ በእርግጥ ፡ አስተባበሉ ፤
ጥላቻዬም ፡ እንዴት ፡ ነበር !
19 ወደ ፡ አዕዋፍ ፡ ከበላያቸው ፡ ክን
ፎቻቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ተንሳ
ፋፊዎች ፡ የሚሰበስቡም ፡ ሲኾኑ
አላዩምን ? ከአልረሕማን ፡ በቀር ፡
(ባየር ፡ ላይ) ፡ የሚይዛቸው ፡
የለም ። እርሱ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡
ተመልካች ፡ ነው ።
20 በውነቱ ፡ ያ ፡ እርሱ ፡ ከአልረሕ
ማን ፡ ሌላ ፡ የሚረዳችሁ ፡ ለና
ንተ ፡ የኾነ ፡ ሰራዊት ፡ ማነው ?
ከሓዲዎች ፡ በመታለል ፡ ውስጥ ፡
እንጅ ፡ በሌላ ፡ ላይ ፡ አይደሉም ።
21 ወይም ፡ ሲሳዩን ፡ ቢይዝባችሁ ፡
ያ ፡ ሲሳይን ፡ የሚሰጣችሁ ፡
ማነው ? በውነቱ ፡ እነርሱ ፡ በም
ገድና ፡ በመደንበር ፡ ውስጥ ፡
ችክ፡ አሉ።



22 በፊቱ ፡ ላይ ፡ ተደፍቶ ፡ የሚ
ኼድ ፡ ሰው ፡ ይበልጥ ፡ የቀና ፡
ነውን ? ወይስ ፡ በቀጥተኛ ፡ መ
ንገድ ፡ ላይ ፡ ተስተካክሎ ፡ የሚ
ኼድ ?
23 እርሱ ፡ ያ ፡ የፈጠራችሁ ፡ ለናን
ተም ፡ መስሚያና ፡ ማያዎችን ፡
ልቦችንም ፡ ያደረገላችሁ ፡ ነው ፤
ጥቂትንም ፡ አታመሰግኑም ፡ በላ
ቸው ።
24 እርሱ ፡ ያ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የበ
ተናችሁ ፡ ነው ፤ ወደርሱም ፡ ትሰ
በሰባላችሁ ፡ በላቸው ።
25 እውነተኞችም ፡ እንደኾናችሁ ፡
ይህ ፡ ቀጠሮ ፡ መቼ ፡ ነው ? ይላሉ ።
26 ዕውቀቱ ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡
ነው ። እኔ ፡ ግልጽ ፡ አስፈራሪ ፡
እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለሁም ፡
በላቸው ።
27 (ቅጣቱን) ፡ ቅርብ ፡ ኾኖ ፡ ባዩ
ትም ፡ ጊዜ ፡ የነዚያ ፡ የካዱት ፡
ሰዎች ፡ ፊቶች ፡ ይከከፋሉ ፤ ይህ ፡
ያ ፡ በርሱ ፡ ትከራከሩበት ፡ የነበ
ራችሁት ፡ ነው ፡ ይባላሉም ።
28 አያችሁን ? አላህ ፡ ቢገድለኝ ፡
ከኔ ፡ ጋር ፡ ያሉትንም ፡ (እንደ
ዚሁ) ፡ ወይም ፡ (በማቆየት) ፡
ቢያዝንልን ፡ ከሓዲዎችን ፡ ከአ
ሳማሚ ፡ ቅጣት ፡ የሚያድን ፡
ማን ፡ ነው ? በላቸው ።
29 እርሱ ፡ (እመኑበት ፡ የምላችሁ) ፡
አልረሕማን ፡ ነው ፤ (እኛ) ፡ በርሱ ፡
አመንን ፤ በርሱም ፡ ላይ ፡ ተጠ
ጋን ፤ ወደ ፡ ፊትም ፡ በግልጽ ፡
መሳሳት ፡ ውስጥ ፡ የኾነው ፡
እርሱ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በእ
ርግጥ ፡ ታውቃላችሁ ፡ በላቸው ።
30 አያችሁን ? ውሃችሁ ፡ ሠራጊ ፡
ቢኾን ፡ ፈሳሺን ፡ ውሃ ፡ የሚያ
መጣላችሁ ፡ ማን ፡ ነው ? በላ
ቸው ። (አላህ ፡ የዓለማት ፡ ጌታ ፡
ያመጣዋል) ።

## ምዕራፍ ፡ 68 ፡ አል-ቀለም ። ክፍል ፡ 29 ።

68ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ቀለም ፡ (የብርዕ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 52 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 ኑ. (ኑን) ፤ (1) በብርዕ ፡ እምላ
ለሁ ፡ በዚያም ፡ (መልአኮች) ፡
በሚጽፉት ።
2 አንተ ፡ በጌታህ ፡ ጸጋ ፡ የተጐና
ጸፍክ ፡ ስትኾን ፡ ዕብድ ፡ አይደ
ለህም ።
3 ላንተም ፡ (ከጌታህ) ፡ የማይቋረጥ ፡
ዋጋ ፡ በእርግጥ ፡ አልለህ ።
4 አንተም ፡ በታላቅ ፡ ጠባይ ፡
ላይ ፡ ነህ ።

1 የዐማ ፡ ስም ፡ ነው ።

5 ወደፊትም ፡ ታያለህ ፤ ያያሉም ፤
6 ዕብደት ፡ በማንኛችሁ ፡ እንዳ
ልለ ።
7 ጌታህ ፡ እርሱ ፡ ከመንገዱ ፡ የተ
ሳሳተውን ፡ ሰው ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፤
እርሱም ፡ ተመሪዎቹን ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ።
8 ለአስተባባዮችም ፡ አትታዘዝ ።
9 ብትመሳሰላቸውና ፡ ቢመሳሰሉህ፡
ተመኙ ።
10 መሓለኛ ፡ ወራዳንም ፡ ሁሉ ፡
አትታዘዝ ።
11 ሰውን ፡ አነዋሪንና ፡ በማሳበቅ ፡
ኼያጅን ።
12 ለበጎ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ከልካይን ፤
ወሰን ፡ አላፊን ፤ ኃጢአተኛን ፤
13 ልበ ፡ ደረቅን ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡
ዲቃላን ፡ (ሁሉ ፡ አትታዘዝ) ።
14 የገንዘብና ፡ የልጆች ፡ ባለቤት ፡
በመኾኑ ፡ (ያስተባብላል) ።
15 በርሱ ፡ ላይ ፡ አንቀጾቻችን ፡
በሚነበቡ ፡ ጊዜ ፡ የመጀመሪያ
ዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ተረቶች ፡ ናቸው ፡
ይላል ።
16 በአፍንጫው ፡ ላይ ፡ በእርግጥ ፡
(የሚነወርበት) ፡ ምልክት ፡ እና
ደርግበታለን ።
17 እኛ ፡ የአትክልቲቱን ፡ ባለ ፡
ቤቶች ፡ እንደ ፡ ሞከርን ፡ (የመ
ካን ፡ ሰዎች) ፡ ሞከርናቸው ፤
ማልደው ፡ (ፍሬዋን) ፡ ሊለቅ
ሟት ፡ በማሉ ፡ ጊዜ ።
18 (በመሓላቸው) ፡ አያስቀሩምም ።
(1)
19 እነርሱ ፡ የተኙ ፡ ኾነውም ፡ ሳሉ ፡
ከጌታህ ፡ የኾነ ፡ ዟሪ ፡ በርሷ ፡
ላይ ፡ ዞረባት ።
20 እንደ ፡ ሌሊት ፡ ጨለማም ፡ ኾና ፡
አነጋች ፤ (ከሰለች) ።
21 ያነጉም ፡ ኾነው ፡ ተጠራሩ ።
22 ቆራጮች ፡ እንደ ፡ ኾናችሁ ፡
በእርሻችሁ ፡ ላይ ፡ ማልዱ ፡ በማ
ለት ።
23 እነሱ ፡ የሚንሾካሾኩ፡ ኾነው ፡
ኼዱም ።
24 ዛሬ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ድኻ ፡ እን
ዳይገባት ፡ በማለት ።
25 (ድኾችን) ፡ በመከልከልም፡ ላይ ፡
(በሐሳባቸው) ፡ ቻዮች ፡ ኾነው ፡
ማለዱ ።
26 (ተቃጥላ) ፡ ባዩዋትም ፡ ጊዜ ፡
እኛ ፡ በእርግጥ ፡ ተሳሳቾች ፡ ነን ፡
አሉ ።
27 ይልቁንም ፡ እኛ ፡ የተከለከልን ፡
ነን ፡ አሉ ።
28 ትክክለኛቸው ፡ ለናንተ ፡ አላህን፡
ለምን ፡ አታጠሩም ፡ አላልኳች
ሁምን ? አላቸው ።
29 ጌታችን ፡ ጥራት ፡ ይገባው ፤ እኛ ፡
በዳዮች ፡ ነበርን ፤ አሉ ።
30 የሚወቃቀሱም ፡ ኾነው ፡ ከፊሎ
ቻቸው ፡ በከፊሉ ፡ ላይ ፡ መጡ ።
31 ዋ ፡ ጥፋታችን ! እኛ ፡ ድንበር ፡
አላፊዎች ፡ ነበርን ፤ አሉ ።
32 ጌታችን ፡ ከርሷ ፡ የተሻለን ፡ (አት
ክልት) ፡ ሊለውጠን ፡ ይከጀላል ፤
እኛ ፡ ወደ ፡ ጌታችን ፡ ከጃዮች ፡
ነን ፤ (አሉ) ።
33 ቅጣቱ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። የመ
ጨረሻይቱም ፡ ዓለም ፡ ቅጣት ፡
ታላቅ ፡ ነው ፤ የሚያውቁ ፡ በኾኑ፡
ኖሮ ፡ (በተጠነቀቁ ፡ ነበር) ።

---
1 አላህ ፡ ቢሻ ፡ አይሉም ፤ የድኾችን ፡ ፈንታ ፤
አያስተርፉም ።



34 ለጥንቁቆቹ ፡ በጌታቸው ፡ ዘንድ ፡
መጠቀሚያ ፡ ገነቶች ፡ አሏቸው።
35 ሙስሊሞቹን፡ እንደ፡ ከሓዲዎች፡
እናደርጋለን ?
36 ለናንተ ፡ ምን ፡ (አስረጅ) ፡ አላ
ችሁ ? እንዴት ፡ ትፈርዳላችሁ ።
37 በውነቱ ፡ ለናንተ ፡ በርሱ ፡ የም
ታጠኑበት ፡ መጽሐፍ ፡ አላች
ሁን ?
38 በውስጡ ፡ ለናንተ ፡ የምትመር
ጡት ፡ አላችሁ ፡ (የሚል) ።
39 ወይስ ፡ ለናንተ ፡ የምትፈርዱት ፡
አላችሁ ፡ በማለት ፡ (ቃል ፡ ኪዳን
የገባንላችሁ) ፡ እስከ ፡ ትንሣኤ ፡
ቀን ፡ ደራሽ ፡ የኾኑ ፡ መሓላዎች፡
ለናንተ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ አሏችሁን ?
40 በዚህ ፡ ማንኛቸው ፡ ተያዥ ፡
እንደ ፡ ኾነ ፡ ጠይቃቸው ።
41 ወይስ ፡ ለነሱ ፡ (በፍርዳቸው ፡
ተስማሚ) ፡ ተጋሪዎች ፡ አሏቸ
ውን ? እውነተኞችም ፡ እንደ ፡
ኾኑ ፡ ተጋሪዎቻቸውን ፡ ያምጡ ።
42 ባት ፡ የሚገለጥበትን ፡ (ከሓዲ
ዎች) ፡ ወደ ፡ መስገድም ፡ የሚ
ጥጠሩበትንና ፡ የማይችሉበትን ፡
ቀን ፡ (አስታውስ) ።
43 ዓይኖቻቸው ፡ የፈሩ ፡ ውርደት ፡
የምትሸፍናቸው ፡ ሲኾኑ ፤ (ወደ ፡
ስግደት ፡ የሚጠሩበትን) ፤ እነ
ሱም ፡ (በምድረ ፡ ዓለም) ፡ ደህና ፡
ኾነው ፡ ሳሉ ፡ ወደ ፡ ስግደት ፡ በእ
ርግጥ ፡ ይጠሩ ፡ ነበሩ ።
44 በዚህም ፡ ንግግር ፡ ከሚያስተባ
ብሉት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ተዎኝ ፤
(እነሱን ፡ እኔ ፡ እበቃሃለሁ) ።
ከማያውቁት ፡ ስፍራ ፡ አዘናግተን
እንይዛቸዋለን ።
45 እነርሱንም ፡ አዘገያለሁ ፤ ዘዴዬ፡
ብርቱ ፡ ነውና ።
46 በውነቱ ፡ ዋጋን ፡ ትጠይቃቸዋለ
ህን ? ስለዚህ ፡ እነሱ ፡ ከዕዳ ፡
የተከበዱ ፡ ናቸውን ?
47 ወይስ ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ የሩቁ ፡
ምስጢር ፡ ዕውቀት ፡ አልለን ?
ስለዚህ ፡ እነርሱ ፡ ይጽፉሉን ?
48 ለጌታህም ፡ ፍርድ ፡ ታገሥ ፤
(በመበሳጨትና ፡ ባለ ፡ መታ
ገሥ) ፡ እንደ ፡ ዓሣው ፡ ባለቤ
ትም ፡ (እንደ ፡ ዮናስ) ፡ አትኹን ፤
እርሱ ፡ በጭንቀት ፡ የተመላ ፡
ኾኖ ፡ (ጌታውን) ፡ በተጣራ ፡
ጊዜ ።
49 ከጌታው ፡ የኾነ ፡ ጸጋ ፡ ባላገ
ኘው ፡ ኖሮ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡
ተወቃሽ ፡ ኾኖ ፡ በተጣለ ፡ ነበር።
50 ጌታውም ፡ (በነቢይነት) ፡ መረ
ጠው ፡ ከደጋጎቹም ፡ አደረገው ።
51 እነሆ ፡ እነዚያም ፡ የካዱት ፡ ሰዎች
ቁርአኑን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በዓይ
ኖቻቸው ፡ ሊጥሉህ ፡ (ሊያጠ
ፉህ) ፡ ይቃረባሉ ፤ እርሱም ፡ በእ
ርግጥ ፡ ዕብድ ፡ ነው ፡ ይላሉ ።
52 ግን ፡ እርሱ ፡ (ቁርአን) ፡ ለዓለ
ማት ፡ መገሠጫ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡
አይደለም ።

69ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሓቅቃህ ፤ (የአረጋጋጪቱ ፡ ምዕራፍ) ።
በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 52 ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 እውነትን ፡ አረጋጋጪቱ ፡ (ትንሣኤ) ።
2 አረጋጋጪቱ ፡ (እርሷ) ፡ ምንድን ፡ ናት !
3 አረጋጋጪቱም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ምን ፡ አሳወቀህ ?
4 ሠሙድና ፡ ዓድ ፡ በቆርቋሪይቱ ፡ (ትንሣኤ) ፡ አስተባበሉ ።
5 ሠሙድማ ፡ ወሰን ፡ በሌላት ፡ ጩኸት ፡ ተጠፉ ፤ (ተወደሙ) ።
6 ዓድማ ፡ በኀይል ፡ በምትንሻሻ ፡ ብርቱ ፡ ነፋስ ፡ ተጠፉ ።
7 ተከታታይ ፡ በኾኑ ፡ ሰባት ፡ ሌሊቶችና ፡ ስምንት ፡ መዓልቶች ፡ ውስጥ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ለቀቃት ። ሕዝቦቹንም ፤ በውስጧ ፡ (1) ፡ የተጣሉ ፡ ኾነው ፡ ልክ ፡ ክፍት ፡ የኾኑ ፡ የዘንባባ ፡ ግንዶች ፡ መስለው ፡ ታያቸዋለህ ።
8 ለነሱም ፡ ቀሪን ፡ ታያለህን ?
9 ፈርዖን ፡ ከበፊቱ ፡ የነበሩትም ፡ ሰዎች ፡ ተገልባጮቹም ፡ (ከተሞች) ፡ በኀጢአት ፡ (ሥራዎች) ፡ መጡ ።
10 የጌታቸውንም ፡ መልክተኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ጣሱ ፤ የበረታችንም ፡ አያያዝ ፡ ያዛቸው ።
11 እኛ ፡ ውሃው ፡ ባየለ ፡ ጊዜ ፡ በተንሻላይቱ ፡ ታንኳ ፡ ውስጥ ፡ ጫንናችሁ ።
12 ለናንተ ፡ መገሠጫ ፡ ልናደርጋት ፡ አጥኚ ፡ የኾነችም ፡ ጆሮ ፡ ታጠናት ፡ ዘንድ ።
13 በቀንዱም ፡ አንዲት ፡ መነፋት ፡ በተነፋች ፡ ጊዜ ።
14 ምድርና ፡ ጋራዎችም ፡ (ከስፍራቸው) ፡ በተነሱና ፡ አንዲትን ፡ መሰባበር ፡ በተሰባበሩ ፡ ጊዜ ።
15 በዚያ ፡ ቀን ፡ ኋኝቱ ፡ (ትንሣኤ) ፡ ትኾናለች ።
16 ሰማይም ፡ ትቀደዳለች ፡ ስለዚህ ፡ እርሷ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ደካማ ፡ ናት ።
17 መላእክትም ፡ በየጫፎችዋ ፡ ላይ ፡ ይኾናሉ ፤ የጌታህንም ፡ ዐርሽ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ስምንት ፡ መላእክት ፡ ከበላያቸው ፡ ይሸከሙታል ።
18 በዚያ ፡ ቀን ፡ ከናንተ ፡ ተደባቂ ፡ (ነገሮች) ፡ የማይደበቁ ፡ ሲኾኑ ፡ ትቅቀረባላችሁ ።
19 መጽሐፉን ፡ በቀኙ ፡ የተሰጠ ፡ ሰውማ ፡ (ለጓደኞቹ) ፡ እንኩ ፤ መጽሐፌን ፡ አንብቡ ፡ ይላል ።
20 እኔ ፡ ምርመራዬን ፡ የምገናኝ ፡ መኾኔን ፡ አረጋገጥኩ ፤ (ተዘጋጀሁም ፡ ይላል) ።
21 እርሱም ፡ በተወደደች ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ ይኾናል ።
22 በከፍተኛይቱ ፡ ገነት ፡ ውስጥ ።
23 ፍሬዎችዋ ፡ ቅርቦች ፡ የኾኑ ።

1 በቀኖቹ ፡ ወይም ፡ በነፋሲቱ ፡ ውስጥ ።



24 በአለፉት ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ (በምድረ ፡ ዓለም) ፡ ባስቀደማችሁት ፡ ምክንያት ፡ ብሉ ፤ ጠጡም ፤ (ይባላሉ) ።
25 መጽሐፉንም ፡ በግራው ፡ የተሰጠማ ፡ ዋ ፡ ጥፋቴ ! ምነው ፡ መጽሐፌን ፡ ባልተሰጠሁ ፡ ይላል ።
26 ምርመራዬንም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባላወቅሁ ።
27 እርሷ ፡ (ሞት ፡ ሕይወቴን) ፡ ምነው ፡ ፈጻሚ ፡ በኾነች ። (1)
28 ገንዘቤ ፡ ከኔ ፡ ምንንም ፡ አላብቃቃኝ ፤ (አልጠቀመኝም) ።
29 ኀይሌ ፡ ከኔ ፡ ላይ ፡ ጠፋ ፡ (ይባላል) ።
30 ያዙት ፤ እሰሩትም ።
31 ከዚያም ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ አግቡት ።
32 ከዚያም ፡ ርዝመቷ ፡ ሰባ ፡ ክንድ ፡ በኾነች ፡ ሰንሰለት ፡ ውስጥ ፡ አግቡት ።
33 እርሱ ፡ ታላቅ ፡ በኾነው ፡ አላህ ፡ አያምንም ፡ ነበርና ።
34 ድኾችንም ፡ በማብላት ፡ ላይ ፡ አያግባባም ፡ ነበርና ።
35 ለርሱም ፡ ዛሬ ፡ እዚህ ፡ ዘመድ ፡ የለውም ።
36 ምግብም ፡ ከእሳት ፡ ሰዎች ፡ ቁስል ፡ እጣቢ ፡ (እኽ) ፡ በስተቀር ፡ የለውም ።
37 ኀጢአተኞች ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይበላውም ፤ (ይባላል) ።
38 በምታዩትም ፡ ነገር ፡ እምላለሁ ።
39 በማታዩትም ፡ ነገር ።
40 እርሱ ፡ (ቁርአን) ፡ የተከበረ ፡ መልክተኛ ፡ ቃል ፡ ነው ። (1)
41 እርሱም ፡ የባለቅኔ ፡ ቃል ፡ (ግጥም) ፡ አይደለም ። ጥቂትን ፡ ብቻ ፡ ታምናላችሁ ።
42 የጠንቋይም ፡ ቃል ፡ አይደለም ፤ ጥቂትን ፡ ብቻ ፡ ታስታውሳላችሁ ።
43 ከዓለማት ፡ ጌታ ፡ የተወረደ ፡ ነው ።
44 በኛ ፡ ላይም ፡ ከፊልን ፡ ቃላት ፡ (ያላልነውን) ፡ በቀጠፈ ፡ ኖሮ ፤
45 በኀይል ፡ በያዝነው ፡ ነበር ።
46 ከዚያም ፡ ከርሱ ፡ የልቡን ፡ ስር ፡ (የተንጠለጠለበትን ፡ ጂማት) ፡ በቆረጥን ፡ ነበር ።
47 ከእናንተም ፡ ውስጥ ፡ ከርሱ ፡ ላይ ፡ ከልካዮች ፡ ምንም ፡ አይኖሩም ።
48 እርሱም ፡ (ቁርአን) ፡ ለጥንቁቆቹ ፡ መገሠጫ ፡ ነው ።
49 እኛም ፡ ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ አስተባባዮች ፡ መኖራቸውን ፡ በእርግጥ ፡ እናውቃለን ።
50 እርሱም ፡ (ቁርአን) ፡ በከሓዲዎቹ ፡ ላይ ፡ ጸጸት ፡ ነው ።
51 እርሱም ፡ የተረጋገጠ ፡ እውነት ፡ ነው ።
52 የታላቁን ፡ ጌታህንም ፡ ስም ፡ አወድስ ።

1 እንደ ፡ ሞትኩ ፡ ሳልነሳ ፡ በቀረሁ ፡ ማለት ፡ ነው ።

1 ከጌታ ፡ ተልኮ ፡ ያመጣው ፡ ቃል ፡ ነው ።

70ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-መዓሪጅ ፤ (የመሰላሎች ፡ ምዕራፍ) ። በ
መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 44 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 ወዳቂ ፡ ከኾነው ፡ ቅጣት ፡ ጠያቂ ፡ ጠየቀ ።

2 በከሓዲዎች ፡ ላይ ፡ (ወዳቂ ፡ ከኾነው) ፡ ለርሱ ፡ መላሽ ፡ የለውም ።

3 የ(ሰማያት) ፡ መሰላሎች ፡ ባለቤት ፡ ከኾነው ፡ አላህ ፡ (መላሽ ፡ የለውም) ።

4 መላእክቱና ፡ መንፈሱም ፡ ልኩ ፡ አምሳ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ በኾነ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ወደርሱ ፡ ያርጋሉ ፤ (ይወጣሉ) ።

5 መልካምንም ፡ ትእግሥት ፡ ታገሥ ።

6 እነርሱ ፡ (ያንን ፡ ቀን) ፡ ሩቅ ፡ አድርገው ፡ ያዩታል ።

7 እኛም ፡ ቅርብ ፡ ኾኖ ፡ እናየዋለን ።

8 ሰማይ ፡ እንደ ፡ ዘይት ፡ አተላ ፡ በምትኾንበት ፡ ቀን ።

9 ጋራዎችም ፡ በተለያዩ ፡ ቀለማት ፡ እንደ ፡ ተነከረ ፡ ሱፍ ፡ (ነፋስ ፡ እንደሚያበረው) ፡ በሚኾኑበት ፡ ቀን ።

10 ዘመድም ፡ ዘመድን ፡ በማይጠይቅበት ፡ ቀን ፤ (መላሽ ፡ የለውም) ።

11 (ዘመዶቻቸውን) ፡ ያዩዋቸዋል ፤ አመጠኛው ፡ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ስቃይ ፡ (ነፍሱን) ፡ በልጆቹ ፡ ሊበዥ ፡ ይመኛል ።

12 በሚስቱም ፡ በወንድሙም ።

13 በዚያችም ፡ በምታስጠጋው ፡ ጎሳው ።

14 በምድርም ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ሁሉ ፡ (ሊበዥ) ፡ ከዚያም ፡ ሊያድነው ፡ (ይመኛል) ።

15 ይተው ! እርሷ ፡ (እሳቲቱ) ፡ ለዟ ፡ ናት ። (1)

16 የራስን ፡ ቅል ፡ ቆዳ ፡ የምትሞሽልቅ ፡ ስትኾን ።

17 (ከእምነት) ፡ የዞረንና ፡ የሸሸን ፡ ሰው ፡ (ወደርሷ) ፡ ትጠራለች ።

18 ገንዘብን ፡ የሰበሰበንና ፡ (ዘካውን ፡ ሳይሰጥ) ፡ የቆጠረንም ፤ (ትጠራለች) ።

19 ሰው ፡ ቅጠ ፡ ቢስ ፡ ኾኖ ፡ ተፈጠረ ።

20 ክፉ ፡ ነገር ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ ብስጩተኛ ።

21 መልካምም ፡ ነገር ፡ (ድሎት) ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ከልካይ ፡ (ኾኖ ፡ ተፈጠረ) ።

22 ሰጋጆቹ ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ ።

23 እነዚያ ፡ እነርሱ ፡ በስግደታቸው ፡ ላይ ፡ ዘውታሪዎች ፡ የኾኑት ።

24 እነዚያም ፡ በገንዘቦቻቸው ፡ ላይ ፡ የታወቀ ፡ መብት ፡ ያለባቸው ፡ የኾኑት ።

---
1 ነዲድ ፡ እሳት ፡ ናት ።



25 ለለማኝ ፡ ከልመና ፡ ለሚከለከልም ፡ (መብት ፡ ያለባቸው ፡ የኾኑት) ።

26 እነዚያም ፡ በፍርዱ ፡ ቀን ፡ እውነት ፡ የሚሉት ፡ (የሚያረጋግጡት) ።

27 እነዚያም ፡ እነሱ ፡ ከጌታቸው ፡ ቅጣት ፡ ፈሪዎች ፡ የኾኑት ።

28 የጌታቸው ፡ ቅጣት ፡ (መምጣቱ) ፡ የማያስተማምን ፡ ነውና ።

29 እነዚያም ፡ እነሱ ፡ ብልቶቻቸውን ፡ ጠባቂዎች ፡ የኾኑት ።

30 በሚስቶቻቸው ፡ ወይም ፡ እጆቻቸው ፡ በያዙዋቸው ፡ (ባሮች) ፡ ላይ ፡ ሲቀር ። እነሱ ፡ (በነዚህ) ፡ የማይወቀሱ ፡ ናቸውና ።

31 ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ (1) የፈለገ ፡ ሰው ፡ እነዚያ ፡ እነሱ ፡ ድንበር ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ።

32 እነዚያም ፡ እነሱ ፡ አደራዎቻቸውንና ፡ ቃል ፡ ኪዳናቸውን ፡ ጠባቂዎች ፡ የኾኑት ።

33 እነዚያም ፡ እነሱ ፡ በምስክርነታቸው ፡ ትክክለኞች ፡ የኾኑት ።

34 እነዚያም ፡ እነሱ ፡ በሶላቶቻቸው ፡ ላይ ፡ የሚጠባበቁት ።

35 እነዚህ ፡ (ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተወሱት ፡ ሁሉ) ፡ በገነቶች ፡ ውስጥ ፡ የሚከበሩ ፡ ናቸው ።

36 ለነዚያም ፡ ለካዱት ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ በኩል ፡ አንገቶቻቸውን ፡ መዘዘው ፡ የሚያተኩሩት ፡ ምን ፡ አላቸው ?

37 ከቀኝና ፡ ከግራ ፡ ክፍልፍል ፡ ጭፍሮች ፡ ሲኾኑ ፤

38 ከነሱ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የጸጋይቱን ፡ ገነት ፡ መግባትን ፡ ይከጅላልን ?

39 ይከልከል ፤ እኛ ፡ ከሚያውቁት ፡ ነገር ፡ (ከፍቶት ፡ ጠብታ) ፡ ፈጠርናቸው ።

40 በምሥራቆችና ፡ በምዕራቦችም ፡ ጌታ ፡ እምላለሁ ፤ እኛ ፡ በእርግጥ ፡ ቻዮች ፡ ነን ፤

41 ከነሱ ፡ የተሻለን ፡ በመለወጥ ፡ ላይ ። እኛም ፡ ተሸናፊዎች ፡ አይደለንም ።

42 ያንንም ፡ የሚስፈራሩበትን ፡ ቀናቸውን ፡ እስከሚገናኙ ፡ ድረስ ፡ ተዋቸው ፤ ይዋኙ ፡ ይጫወቱም ።

43 ወደ ፡ ጣዖቶች ፡ እንደሚሸቀዳደሙ ፡ ኾነው ፡ ከመቃብሮቻቸው ፡ ፈጥነው ፡ የሚወጡበትን ፡ ቀን ፡ (እስከሚገናኙ ፡ ድረስ ፡ ተዋቸው) ።

44 ዓይኖቻቸው ፡ ያፈሩ ፡ ኾነው ፡ ውርደት ፡ ትሸፍናቸዋለች ። ይህ ፡ ቀን ፡ ያ ፡ ይስፈራሩበት ፡ የነበሩት ፡ ነው ።

---
1 ከሚስቶቹና ፡ እጁ ፡ ከጨበጣቸው ፡ ባሮች ፡ ሌላ ።

71ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ኑሕ ፡ (የኖሕ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወ
ረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 28 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 እኛ ፡ ኑሕን ፡ ሕዝቦችህን ፡ አሳ
ማሚ ፡ ቅጣት ፡ ሳይመጣባቸው ፡
በፊት ፡ አስጠንቅቅ ፡ በማለት ፡
ወደ ፡ ሕዝብቹ ፡ ላክነው ።
2 (እርሱም) ፡ አለ ፡— ሕዝቦቼ ፡
ሆይ ! እኔ ፡ ለናንተ ፡ ገላጭ ፡ የኾ
ንኩ ፡ አስጠንቃቂ ፡ ነኝ ።
3 አላህን ፡ ተገዙት ፤ ፍሩትም ፤
ታዘዙኝም ፡ በማለት ፤ (አስጠ
ንቃቂ ፡ ነኝ) ።
4 ለናንተ ፡ ከኀጢአቶቻችሁ ፡ ይም
ራልና ፤ ወደ ፡ ተወሰነው ፡ ጊዜም፡
ያቆያችኋል ፤ የአላህ ፡ (የወሰነው) ፡
ጊዜ ፡ በመጣ ፡ ወቅት ፡ አይቅ
ቆይም ። የምታውቁ ፡ ብትኾኑ ፡
ኖሮ ፡ (በታዘዛችሁ ፡ ነበር) ።
5 (ስለ ፡ ተቃወሙትም) ፡ አለ ፡—
ጌታዬ ፡ ሆይ ! እኔ ፡ ሌሊትም ፡
ቀንም ፡ ሕዝቦቼን ፡ ጠራሁ ።
6 ጥሪየም ፡ መሸሽን ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡
አልጨመረላቸውም ።
7 እኔም ፡ ለነርሱ ፡ ትምር ፡ ዘንድ ፡
(ወደ ፡ እምነት) ፡ በጠራኋቸው ፡
ቁጥር፥ ጣቶቻቸውን፡ በጆሮዎቻ
ቸው ፡ ውስጥ ፡ አደረጉ ፤ ልብሶቻ
ቸውንም ፡ ተከናነቡ ፤ (በመጥፎ ፡
ሥራቸው ፡ ላይ) ፡ ዘወተሩም ።
(ያለ ፡ ልክ) ፡ መኩራትንም ፡ ኮሩ ።
8 ከዚያም ፡ እኔ ፡ በጩኸት ፡ ጠራ
ኋቸው ።
9 ከዚያም ፡ እኔ ፡ ለነሱ ፡ ገለጽኩ ፡
ለነሱም ፡ መመስጠርን ፡ መሰጠ
ርኩ ፡ (1)
10 አልኳቸውም ፡— ጌታችሁን ፡
ምሕረትን ፡ ለምኑት ፤ እርሱ ፡
በጣም ፡ መሓሪ ፡ ነውና ።
11 በናንተ ፡ ላይ ፡ ዝናምን ፡ ተከታ
ታይ ፡ አድርጎ ፡ ይልካል ።
12 በገንዘቦችና ፡ በልጆችም ፡ ይለግ
ስላችኋል ፤ ለናንተም ፡ አትክል
ቶችን ፡ ያደርግላችኋል ። ለናን
ተም ፡ ወንዞችን ፡ ያደርግላች
ኋል ።
13 ለአላህ ፡ ልቅናን ፡ የማትሹት ፡
ለናንተ ፡ ምን ፡ አላችሁ ።
14 በልዩ ፡ ልዩ ፡ ኹኔታዎች ፡ በእር
ግጥ ፡ የፈጠራችሁ ፡ ሲኾን ።
15 አላህ ፡ ሰባትን ፡ ሰማያት ፡ አንዱ፡
ካንዱ ፡ በላይ ፡ ሲኾን ፡ እንዴት ፡
እንደ ፡ ፈጠረ ፡ አታዩምን ?
16 በውስጣቸውም ፡ ጨረቃን ፡ አብሪ፡
አደረገ ፤ ፀሐይንም ፡ ብርሃን ፡
አደረገ ።
17 አላህም ፡ ከምድር ፡ ማብቀልን ፡
አበቀላችሁ ።
18 ከዚያም ፡ በውስጧ ፡ ይመልሳች
ኋል ። ማውጣትንም ፡ ያወጣች
ኋል ።
19 አላህም ፡ ምድርን ፡ ለናንተ ፡
ምንጣፍ ፡ አደረጋት ።

1 በግልጽም ፡ በምስጢርም ፡ ወደ ፡ እምነት ፡ ጠራኋቸው ።



20 ከርሷ ፡ ሰፋፊዎችን ፡ መንገዶች ፡
ትገቡ ፡ ዘንድ ።
21 ኑሕ ፡ አለ ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ !
እነሱ ፡ አምመጡብኝ ፤ ገንዘቡና፡
ልጁም ፡ ከጥፋት ፡ በስተቀር ፡ ያል
ጨመረለትን ፡ ሰው ፡ ተከተሉ ።
22 ታላቅንም ፡ ተንኮል ፡ የመከሩ
ትን ፡ ሰዎች ፡ (ተከተሉ) ።
23 አሉም ፡— አምላኮቻችሁን ፡
አትተዉ ፤ ወድንም ፡ ሱዋዕንም ፡
የጉሥንም ፡ የዑቅንም ፡ ነስርንም
አትተዉ ። (1)
24 በእርግጥም ፡ ብዙዎችን ፡ አሳ
ሳቱ ፤ ከሓዲዎችንም ፡ ጥመትን ፡
እንጅ ፡ ሌላን ፡ አትጨምርላቸው ፡
(አለ) ።
25 በኀጢአቶቻቸው ፡ ምክንያት ፡
ተሰጠሙ ፤ እሳትንም ፡ እንዲገቡ፡
ተደረጉ ፤ ለነሱም ፡ ከአላህ ፡ ሌላ ፡
የኾኑ ፡ ረዳቶችን ፡ አላገኙም ።
26 ኑሕም ፡ አለ ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ !
ከከሓዲዎቹ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
አንድንም ፡ አትተው ።
27 አንተ ፡ ብትተዋቸው ፡ ባሮችህን፡
ያሳስታሉና ፤ ኀጢአተኛ ፡ ከሓ
ዲንም ፡ እንጅ ፡ ሌላን ፡ አይወ
ልዱም ።
28 ጌታዬ ፡ ሆይ ! ለኔም ፡ ለወላጆ
ቼም ፡ ምእምን ፡ ኾኖ ፡ በቤቴ ፡
ለገባም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለምእም
ናንና ፡ ለምእምናትም ፡ ምሕረት፡
አድርግ ፤ ከሓዲዎችንም ፡ ከጥ
ፋት ፡ በቀር ፡ አትጨምርላቸው ፤
(አለ) ።

1 እነዚህ ፡ የአማልክቶቻቸው ፡ ስሞች ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ 72 ፡ አልጂን ። ክፍል ፡ 29 ።

72ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ጂን ፡ (የጋኔን ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 28 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 (ሙሐመድ ፡ ሆይ !) በል ፡—
እነሆ ፡ ከጂን ፡ የኾኑ ፡ ጭፍሮች ፡
(ቁርአንን) ፡ አዳመጡ ፤ እኛ ፡
አስደናቂ ፡ የኾነን ፡ ቁርአን ፡ ሰማ
ንም ፡ አሉ ፡ ማለት ፡ ወደኔ ፡ ተወ
ረደ ።
2 ወደ ፡ ቀጥታ ፡ መንገድ ፡ የሚመ
ራን ፡ (ቁርአን ፡ ሰማን) ፤ በር
ሱም ፡ አመንን ፤ በጌታችንም ፡
አንድንም ፡ አናጋራም ።
3 እነሆም ፡ የጌታችን ፡ ክብር ፡
ላቀ ፤ ሚስትንም ፡ ልጅንም ፡
አልያዘም ።
4 እነሆም ፡ ቂላችን ፡ በአላህ ፡ ላይ ፡
ወሰን ፡ ያለፈን ፡ (ውሸት) ፡ ይና
ገር ፡ ነበር ።
5 እኛም ፡ ሰዎችና ፡ ጋኔኖች ፡ በአ
ላህ ፡ ላይ ፡ ውሸትን ፡ (ቃል) ፡
አይናገሩም ፡ ማለትን ፡ ጠረጠ
ርን ።

6 እነሆም ፡ ከሰዎች ፡ የኾኑ ፡ ወን
ዶች ፡ በጋኔን ፡ ወንዶች ፡ ይጠ
በቁ ፡ ነበሩ ፤ ኩራትንም ፡ ጨመ
ሩዋቸው ።

7 እነሱም ፡ አላህ ፡ አንድንም ፡
አይቀሰቅስም ፡ ማለትን ፡ እንደ ፡
ጠረጠራችሁ ፡ ጠረጠሩ ።

8 እኛም ፡ ሰማይን ፡ (ለመድረስ) ፡
ፈለግን ፤ ብርቱ ፡ ጠባቂዎችንና ፡
ችቦዎችንም ፡ ተሞልታ ፡ አገኘ
ናት ።

9 እኛም ፡ ከርሷ ፡ (ወሬን) ፡ ለማዳ
መጥ ፡ በመቀመጫዎች ፡ እንቀ
መጥ ፡ ነበርን ፤ አሁን ፡ ግን ፡
የሚያዳምጥ ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡ ተጠ
ባባቂ ፡ ችቦን ፡ ያገኛል ።

10 እኛም ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ባልሉ ፡
ሰዎች ፡ ክፉ ፡ ተሽቷል ? ወይስ ፡
በነሱ ፡ ጌታቸው ፡ ደግን ፡ ነገር ፡
ሽቷል ? ማለትን ፡ አናውቅም ።

11 እኛም ፡ ከኛ ፡ ውስጥ ፡ ደጎች ፡
አልሉ ፡ ከኛም ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡
የኾኑ ፡ አልሉ ፤ የተለያዩ ፡ መን
ገዶች ፡ (ባለ ፡ ቤቶች) ፡ ነበርን ።

12 እኛም ፡ አላህን ፡ በምድር ፡
ውስጥ፡ ፈጽሞ፡ የማናቅተው፥
ሽሽተንም፡ ፈጽሞ፡ የማናመል
ጠው ፡ መኾናችንን ፡ አረጋገ
ጥን ።

13 እኛም ፡ መሪውን ፡ በሰማን ፡ ጊዜ ፡
በርሱ ፡ አመንን ። በጌታውም ፡
የሚያምን ፡ ሰው ፡ መግጐደል
ንም ፡ መጭጨመርንም ፡ አይፈ
ራም ።

14 እኛም፡ ከኛ፡ ውስጥ፡ ሙስሊሞች፡
አልሉ ፤ ከኛም ፡ ውስጥ ፡ በዳዮች፡
አልሉ ፤ የሰለሙም ፡ ሰዎች ፡ እነ
ዚያ ፡ ቅንን ፡ መንገድ ፡ መረጡ ።

15 በዳዮቹማ ፡ ለገሀነም ፡ ማገዶ ፡
ኾኑ ።

16 እነሆም ፡ በመንገዲቱ ፡ ላይ ፡
ቀጥ ፡ ባሉ ፡ ኖሮ ፡ ብዙ ፡ ዝና
ምን ፡ ባጠጣናቸው ፡ ነበር ፡ (ማለ
ትም ፡ ተወረደልኝ) ።

17 በርሱ ፡ ልንሞክራቸው ፡ (ባጠ
ጣናቸው ፡ ነበር) ፤ ከጌታውም ፡
ማስታወሻ ፡ የሚያፈገፍግ ፡ ሰው፡
አስቸጋሪን ፡ ቅጣት ፡ ያገባዋል ።

18 እነሆ ፡ መስጊዶችም ፡ የአላህ ፡
ብቻ ፡ ናቸው ፡ (በውስጣቸው) ፡
ከአላህ ፡ ጋር ፡ አንድንም ፡ አት
ገዙ ፡ (ማለትም) ።

19 እነሆም ፡ የአላህ ፡ ባሪያ ፡ (ሙሐ
መድ ፡ አላህን) ፡ የሚጠራው ፡
ኾኖ ፡ በተነሳ ፡ ጊዜ ፡ (ጋኔኖች) ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ ድርብርቦች ፡ ሊኾኑ ፡
ቀረቡ ፡ (ማለትም) ።

20 እኔ ፡ የምግገዛው ፡ ጌታየን ፡ ብቻ፡
ነው ፤ በርሱም ፡ አንድንም ፡ አላ
ጋራም ፡ በል ።

21 እኔ ፡ ለናንተ ፡ ጉዳትንም ፡ ቀጥታ
ንም ፡ አልችልም ፡ በላቸው ።

22 እኔ ፡ ከአላህ ፡ (ቅጣት) ፡ አንድም፡
አያድነኝም ፤ ከርሱም ፡ ሌላ ፡
መጠጊያን ፡ አላገኝም ፡ በላቸው ።

23 ከአላህ ፡ የኾነ ፡ ማድረስን ፡ መል
ክቶቹንም ፡ በስተቀር ፡ (አልች
ልም) ፤ አላህንና ፡ መልክተኛው
ንም ፡ የሚያምጥ ፡ ሰው ፡ ለርሱ ፡
የገሀነም ፡ እሳት ፡ አልለው ፤ በው
ስጧ ፡ ዘላለም ፡ ዘውታሪዎች ፡
ሲኾኑ ።

24 የሚስፈራሩበትንም ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡
ረዳቱ ፡ ደካማ ፡ ቍጥሩም ፡ አነ
ስተኛ ፡ የኾነው ፡ ማን ፡ እንደ ፡
ኾነ ፡ በእርግጥ ፡ ያውቃሉ ።



25 የምትስፈራሩበት ፡ ነገር ፡ ቅርብ ፡
ወይም ፡ ጌታየ ፡ ለርሱ ፡ የተወ
ሰነ ፡ ጊዜን ፡ የሚያደርግለት ፡
(ሩቅ) ፡ መኾኑን ፡ አላውቅም ፡
በላቸው ።

26 (እርሱ) ፡ ሩቁን ፡ ምስጢር ፡ ዐዋቂ ፡
ነው ፡ በምስጢሩም ፡ ላይ ፡ አንድ
ንም ፡ አያሳውቅም ።

27 ከመልክተኛ ፡ ለወደደው ፡ ቢኾን
እንጅ ፡ (ለሌላ ፡ አይገልጽም) ፤
እርሱም ፡ ከስተፊቱም ፡ ከስተኋላ
ውም ፡ ጠባቂዎችን ፡ ያደርግለ
ታል ።

28 እነሱ ፡ ዘንድ ፡ ባለው ፡ ነገር ፡
ዕውቀቱ ፡ የከበበና ፡ ነገሩንም ፡
ሁሉ ፡ በቍጥር ፡ ያጠቃለለ ፡
ሲኾን ፡ የጌታቸውን ፡ መልክ
ቶች ፡ ያደረሱ ፡ መኾናቸውን ፡
ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ (ጠባቂ ፡ ያደር
ጋል) ።

## ምዕራፍ ፡ 73 ፡ አል-ሙዘሚል ። ክፍል ፡ 29 ።

73ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሙዘሚል ፤ (የተከናናቢው ፡ ምዕራፍ) ። በ
መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 20 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።

1 አንተ ፡ ተከናናቢው ፡ ሆይ ።

2 ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ጥቂት ፡ ሲቀር ፡
ቁም ፤ (ስገድ)።

3 ግማሹን ፡ (ቁም) ፤ ወይም ፡ ከርሱ
ጥቂትን ፡ ቀንስ ።

4 ወይም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ጨምር ፤
ቁርአንንም ፡ በዝግታ ፡ ማንበ
ብን ፡ አንብብ ።

5 እኛ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ቃልን
እንጥላለንና ።

6 የሌሊት ፡ መነሳት ፡ እርሷ ፡ (ሕዋ
ሳትንና ፡ ልብን) ፡ ለማስማማት ፡
በጣም ፡ ብርቱ ፡ ናት ፤ ለማንበ
ብም ፡ ትክክለኛ ፡ ናት ።

7 ላንተ ፡ በቀን ፡ ውስጥ ፡ ረገጅም ፡
መዘዋወር ፡ አልለህ ።

8 የጌታህንም ፡ ስም ፡ አውሳ ፤ ወደ
ርሱም ፡ (መግገዛት) ፡ መቋረጥን፡
ተቋረጥ) ። (1)

9 (እርሱም) ፡ የምሥራቅና ፡ የም
ዕራብ ፡ ጌታ ፡ ነው ፤ ከርሱ ፡ ሌላ ፡
አምላክ ፡ የለም ፤ መጠጊያ ፡ አድ
ርገሀም ፡ ያዘው ።

10 (ከሓዲዎች) ፡ በሚሉትም ፡ ላይ፡
ታገሥ ፤ መልካምንም ፡ መተው ፡
ተዋቸው ።

11 የድሎት ፡ ባለቤቶችም ፡ ከኾኑት፡
አስተባባዮች ፡ ጋር ፡ ተዎኝ ፤
ጥቂትንም ፡ ጊዜ ፡ አቆያቸው ።

12 እኛ ፡ ዘንድ ፡ ከባድ ፡ ማሠሪያ
ዎች ፡ እሳትም ፡ አልለና ።

13 የሚያንቅ ፡ምግብም ፤ አሳማሚ ፡
ቅጣትም ፡ (አልለ) ።

14 ምድርና ፡ ጋራዎች ፡ በሚርገፈ

1 ለጌታህ ፡ ፍጹም ፡ አገልጋይ ፡ ኹን ።

ገፉበት ፡ ጋራዎችም ፡ ፈሳሽ ፡
የአሸዋ ፡ ክምር ፡ በሚኾኑበት ፡
ቀን ።
15 እኛ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ መስካሪ ፡
መልክተኛን ፡ ወደናንተ ፡ ላክን ፤
ወደ ፡ ፈርዖን ፡ መልክተኛን ፡
እንደላክን ።
16 ፈርዖንም ፡ መልክተኛውን ፡ አ
መጠ ፤ ብርቱ ፡ መያዝንም ፡ ያዝ
ነው ።
17 ብትክዱ ፡ ልጆችን ፡ ሽበቶዎች ፡
የሚያደርገውን ፡ ቀን ፡ (ቅጣት) ፡
እንዴት ፡ ትጠበቃላችሁ !
18 ሰማዩ ፡ በርሱ ፡ (በዚያ ፡ ቀን) ፡
ተሰንጣቂ ፡ ነው ። ቀጠሮው ፡
ተፈጻሚ ፡ ነው ።
19 ይህቺ ፡ መገሠጫ ፡ ናት ፤ (መዳ
ንን)፡ የሻም ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ጌታው፡
መንገድን ፡ ይይዛል ።
20 አንተ ፡ ከሌሊቱ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡
ያነሰን ፡ ግማሹንም ፡ ሢሶውንም፡
የምትቆም ፡ መኾንህን ፡ ጌታህ ፡
በእርግጥ ፡ ያውቃል ። ከነዚያም ፡
አብረውህ ፡ ካሉት ፡ ከፊሎች ፡
(የሚቆሙ ፡ መኾናቸውን ፡ ያው
ቃል) ፤ አላህም ፡ ሌሊትንና ፡
ቀንን ፡ ይለክካል ፡ (ሌሊቱን) ፡
የማታዳርሱት ፡ መኾናችሁን ፡
ዐወቀ ፤ በናንተ ፡ ላይም ፡ (ወደ ፡
ማቃለል) ፡ ተመለሰላችሁ ፤ ስለ
ዚህ ፡ ከቁርአን ፡ (በስግደት) ፡ የተ
ቻላችሁን ፡ አንብቡ ፤ ከናንተ ፡
ውስጥ ፡ በሺተኞች ፡ ሌሎችም ፡
ከአላህ ፡ ችሮታ ፡ ለመፈለግ ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ የሚጓዙ ፡ ሌሎ
ችም ፡ በአላህ ፡ መንገድ ፡ (ሃይ
ማኖት) ፡ የሚጋደሉ ፡ እንደሚ
ኖሩ ፡ ዐወቀ ፤ (አቃለለላቸውም)።
ከርሱም ፡ የተቻላችሁን ፡ አንብቡ
ሶላትንም ፡ ስገዱ ፤ ዘካንም ፡
ስጡ ፤ ለአላህም ፡ መልካም ፡
ብድርን ፡ አበድሩ ፤ ከመልካም ፡
ሥራም ፡ ለነፍሶቻችሁ ፡ የም
ታስቀድሙትን ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡
የተሻለና ፡ በምንዳም ፡ ታላቅ ፡
ኾኖ ፡ አላህ ፡ ዘንድ ፡ ታገኙታ
ላችሁ ፤ አላህንም ፡ ምሕረትን ፡
ለምኑት ፤ አላህ ፡ በጣም ፡ መሐሪ፡
አዛኝ ፡ ነውና ።

## ምዕራፍ ፡ 74 ፡ አል-ሙደሢር ። ክፍል ፡ 29 ።

74ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሙደሢር ፤ (የልብስ ፡ ደራቢው ፡ ምዕራፍ) ።
በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 56 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 አንተ ፡ (ልብስህን) ፡ ደራቢው ፡
ሆይ !
2 ተነሳ ፡ አስጠንቅቅም ።
3 ጌታህንም ፡ አክብር ።
4 ልብስህንም ፡ አጥራ ።
5 ጣዖትንም ፡ ራቅ ።
6 ማብዛትንም ፡ የምትፈልግ ፡ ኾነህ ፤



(በረከትን) ፡ አትለግስ ። (1)
7 ለጌታህም ፡ (ትእዛዝ) ፡ ታገሥ ።
8 በቀንዱም ፡ በተነፋ ፡ ጊዜ ፡ (ነገሩ
ይበረታል) ።
9 ይህም ፡ (ጊዜ) ፡ ያ ፡ ቀን ፡ አስቸ
ጋሪ ፡ ቀን ፡ ነው ።
10 በከሓዲዎች ፡ ላይ ፡ ገር ፡ ያል
ኾነ ፡ ነው ።
11 አንድ ፡ ኾኖ ፡ ከፈጠርኩት ፡ ሰው ፡
ጋር ፡ ተዎኝ ፡ (እኔ ፡ እበቃሃለሁ)።
12 ለርሱም ፡ የተዘረጋን ፡ ገንዘብ ፡
(በያይነቱ) ፡ ያደረግሁለት ።
13 (በያደባባዩ) ፡ ተገኝዎች ፡ የኾኑ ፡
ወንዶች ፡ ልጆችንም ።
14 ለርሱም ፡ (ኑሮውን) ፡ መዘርጋ
ትን ፡ የዘረጋሁለት ፡ (ከኾነ ፡
ሰው ፡ ጋር ፡ ተዎኝ) ።
15 ከዚያም ፡ ልጨምርለት ፡ ይከጅ
ላል ።
16 ይከልከል ፤ እርሱ ፡ ለአንቀጾቻ
ችን ፡ በእርግጥ ፡ ተቃዋሚ ፡
ነበር ።
17 በእርግጥ ፡ ችግርን ፡ አስገድደ
ዋለሁ ።
18 እርሱ ፡ (በቁርአን ፡ ነገር) ፡ ሐሰበ ፤
ገመተም ።
19 ተረገመም ፤ እንዴት ፡ ገመተ !
20 ከዚያም ፡ (ከሞት ፡ በኋላ) ፡ ተረ
ገመ ። እንዴት ፡ ገመተ !
21 ከዚያም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ (በቁርአኑ፡
ነገር) ፡ ተመለከተ ።
22 ከዚያም ፡ ፊቱን ፡ አጨፈገገ ፤
አኮማተረም ።
23 ከዚያም ፡ (ከማመን) ፡ ዞረ ፤ ኮ
ራም ።
24 አለም ፡—ይህ ፡ (ከሌላ) ፡ የሚ
ቀዳ ፡ ድግምት ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡
አይደለም ።
25 ይህ ፡ የሰው ፡ ቃል ፡ እንጅ ፡ ሌላ፡
አይደለም ።
26 በሰቀር ፡ ውስጥ ፡ በእርግጥ ፡
አገባዋለሁ ።
27 ሰቀር ፡ ምን ፡ እንደኾነች ፡ ምን
አሳወቀህ ? ፡
28 (ያገኘችውን፡ ሁሉ)፡ አታስቀርም፡
አትተውምም ።
29 ቆዳን ፡ በጣም ፡ አክሳይ ፡ ናት ።
30 በርሷም ፡ ላይ ፡ አሥራ ፡ ዘጠኝ ፡
(ዘበኞች) ፡ አሉባት ።
31 የእሳትንም ፡ ዘበኞች ፡ መላእክት፡
እንጅ ፡ ሌላ ፡ አላደረግንም ።
ቍጥራቸውንም ፡ ለነዚያ ፡ ለካ
ዱት ፡ መፈተኛ ፡ እንጅ ፡ አላደረ
ግንም ፤ እነዚያ ፡ መጽሐፍን ፡ የተ
ሰጡት ፡ እንዲያረጋግጡ ፡ እነ
ዚያም ፡ ያመኑት ፡ እምነትን ፡ እ
ንዲጨምሩ ፡ እነዚያም ፡ መጽሐ
ፍን ፡ የተሰጡትና ፡ ምእምናኖቹ፡
እንዳይጠራጠሩ ፡ እነዚያም ፡
በልቦቻቸው ፡ ውስጥ ፡ በሽታ ፡
ያለባቸው ፡ (መናፍቃን) ፡ ከሓዲ
ዎችም ፡ አላህ ፡ በዚህ ፡ (ቍጥር)፡
ምን ፡ ምሳሌ ፡ ሻ ! ል ? እንዲሉ ፡
(እንጅ ፡ አላደረግንም) ። እንደ
ዚሁ ፡ አላህ ፡ የሚሻውን ፡ ያጠ
ማል ፤ የሚሻውንም ፡ ያቀናል ፤
የጌታህንም ፡ ሰራዊት ፡ (ልክ) ፡
ከርሱ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ አያው
ቅም ፤ እርሷም ፡ (የሰቀር፡ እሳት)፡
ለሰዎች ፡ መገሠጫ ፡ እንጅ፡ ሌላ፡
አይደለችም ።
32 (ከክሕደት) ፡ ይከልከሉ ፤ በጨ
ረቃ ፡ እምላለሁ ።

1 ጥቂት ፡ ሰጥተህ ፡ ብዙ ፡ እንዲሰጡህ ፡
አታድርግ ።

33 በሌሊቱም ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ።
34 በንጋቱም ፡ ባበራ ፡ ጊዜ ።
35 እርሷ ፡ (ሰቀር) ፡ ከታላላቆቹ ፡ (አደጋዎች) ፡ አንዷ ፡ ናት ።
36 ለሰዎች ፡ አስፈራሪ ፡ ስትኾን ።
37 ከናንተ ፡ (ወደ ፡ በጎ ፡ ነገር) ፡ መቅደምን ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መቅረትን ፡ ለሻ ፡ ሰው ፡ (አስፈ ራሪ ፡ ስትኾን) ።
38 ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ በሠራችው ፡ ሥራ ፡ ተያዥ ፡ ናት ።
39 የቀኝ ፡ ባለቤቶች ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ።
40 (እነርሱስ) ፡ በገነቶች ፡ ውስጥ ፡ ይጠያየቃሉ ፤
41 ከአመጠኞቹ ፡ ኹነታ ።
42 (ይሏቸዋልም) ፡— በሰቀር ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ አገባችሁ ?
43 (እነርሱም) ፡ ይላሉ ፡— ከሰ ጋጆቹ ፡ አልነበርንም ።
44 ለድኾችም ፡ የምናበላ ፡ አልነበ ርንም ።
45 ከዘባራቂዎቹም ፡ ጋር ፡ እንዘባ ርቅ ፡ ነበርን ።
46 በፍርዱ ፡ ቀንም ፡ እናስተባብል ፡ ነበርን ፤
47 እርግጠኛው ፡ (ሞት) ፡ እስከ መጣን ፡ ድረስ ።
48 የአማላጆችም ፡ ምልጃ ፡ አትጠ ቅማቸውም ።
49 ከግሣጼም ፡ (ከቁርአን) ፡ የሚያ ፈገፍጉት ፡ ለነርሱ ፡ ምን ፡ አላ ቸው ?
50 እነሱ ፡ ልክ ፡ ደንባሪዎች ፡ የሜዳ፡ አህዮች ፡ ይመስላሉ ።
51 ከዐንበሳ ፡ የሸሹ ።
52 ይልቁንም ፡ ከነርሱ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የተዘረጉ ፡ ጽሑፎ ችን ፡ እንዲሰሰጥ ፡ ይፈልጋል ።
53 ይከልከሉ ፤ ይልቁንም ፡ የመጨ ረሻይቱን ፡ ዓለም ፡ (ቅጣት) ፡ አይፈሩም ።
54 ይከልከሉ ፤ እርሱ ፡ (ቁርአን) ፡ መገሠጫ ፡ ነው ።
55 ስለዚህ ፡ የሻ ፡ ሰው ፡ ይገሠጽ በታል ።
56 አላህም ፡ ካልሻ ፡ በስተቀር ፡ አይገሠጹም ፤ እርሱ ፡ (አላህ) ፡ የመፈራት ፡ ባለቤት ፡ የምሕረ ረትም ፡ ባለቤት ፡ ነው ።



75ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ቂያማህ ፤ (የትንሣኤ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 40 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ ነው ።
1 (ነገሩ ፡ ከሓዲዎች፡ እንደሚሉት)፡ አይደለም ፤ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ እምላለሁ ።
2 (ራሷን) ፡ ወቃሽ ፡ በኾነች ፡ ነፍ ስም ፡ እምላለሁ ፤ (በእርግጥ ፡ ትቀሰቀሳላችሁ) ።
3 ሰው ፡ አጥንቶቹን ፡ አለመሰብሰ ባችንን ፡ ያስባልን ?
4 አይደለም ፡ ጣቶቹን ፡ (ፊት ፡ እንደ ፡ ነበሩ) ፡ በማስተካከል ፡ ላይ ፡ ቻዮች ፡ ስንኾን ፡ (እንሰበ ስባቸዋለን) ።
5 ይልቁንም ፡ ሰው ፡ በፊቱ ፡ ባለው ነገር ፡ (በትንሣኤ) ፡ ሊያስተባ ብል ፡ ይፈልጋል ።
6 የትንሣኤው ፡ ቀን ፡ መቼ ፡ ነው ? ሲል ፡ ይጠይቃል ።
7 ዓይንም ፡ በዋለለ ፡ ጊዜ ፤
8 ጨረቃም ፡ በጨለመ ፡ ጊዜ ፤
9 ፀሐይና ፡ ጨረቃም ፡ በተሰበሰቡ፡ ጊዜ ፤
10 ሰው ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ መሸሻው ፡ የት ፡ ነው ? ይላል ።
11 ይከልከል ፤ ምንም ፡ መጠጊያ ፡ የለም ።
12 በዚያ ፡ ቀን ፡ መርጊያው ፡ ወደ ፡ ጌታህ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
13 ሰው፡ በዚያ፡ ቀን፡ ባስቀደመውና ፡ ባስቆየው ፡ ሁሉ ፡ ይነገራል ።
14 በእርግጥም ፡ ሰው ፡ በነፍሱ ፡ ላይ ፡ አስረጅ ፡ ነው ። (አካሎቹ ፡ ይመሰክሩበታል) ።
15 ምክንያቶቹን ፡ ሁሉ ፡ ቢያመ ጣም ፡ እንኳ ፡ (አይሰማም) ።
16 በርሱ ፡ (በቁርአን ፡ ንባብ) ፡ ልት ቸኩል ፡ ምላስህን ፡ በርሱ ፡ አታ ላውስ ።
17 (በልብህ ፡ ውስጥ) ፡ መሰብሰቡና ፡ ማንበቡ ፡ (1) በኛ ፡ ላይ ፡ ነውና።
18 ባነበብነውም ፡ ጊዜ ፡ (ካለቀ ፡ በኋላ) ፡ ንባቡን ፡ ተከተል ።
19 ከዚያም ፡ ማብራራቱ ፡ በኛ ፡ ላይ፡ ነው ።
20 (ከመጣደፍ) ፡ ተከልከል ፤ ይልቁ ንም ፡ (ሰዎች) ፡ ፈጣኒቱን ፡ (ዓለም) ፡ ትወዳላችሁ ።
21 መጨረሻይቱንም ፡ (ዓለም) ፡ ትተዋላችሁ ። (አትዘጋጁላትም)።
22 ፊቶች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ አብሪዎች ፡ ናቸው ።
23 ወደ ፡ ጌታቸው ፡ ተመልካቾች ፡ ናቸው ፡
24 ፊቶችም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ጨፍጋ ጊዎች ፡ ናቸው ።
25 በርሳቸውም ፡ ዐደጋ ፡ እንደሚ ሠራባቸው ፡ ያረጋግጣሉ ።
26 ንቁ ፡ (ነፍስ) ፡ ብሪዎችን ፡ (2) በደረሰች ፡ ጊዜ ፤

1 ለማንበብ ፡ እንድትችል ፡ ማድረግ ።
2 የአንገት ፡ አጥንቶችን ።

27 አሻሪው ፡ ማነው ? በተባለም ፡
ጊዜ ፤

28 (ሕመምተኛው) ፡ እርሱ ፡ (የሠ
ፈረበት ፡ ነገር ፡ ከዚህ ፡ ዓለም) ፡
መለየት ፡ መኾኑን ፡ ባረጋገጠም፡
ጊዜ ፤

29 ባትም ፡ በባት ፡ በተጣበቀች ፡
ጊዜ ፤

30 በዚያ ፡ ቀን ፡ መነዳቱ ፡ ወደ ፡
ጌታህ ፡ (ፍርድ) ፡ ነው ።

31 አላመነምም ፡ አልሰገደምም ።

32 ግን ፡ አስተባበለ ፤ (ከእምነት) ፡
ዞረም ።

33 ከዚያም ፡ እየተንጐባለለ ፡ ወደ ፡
ቤተሰቡ ፡ ኼደ ።

34 የምትጠላውን ፡ ነገር ፡ (አላህ) ፡
ያስከትልህ ፤ ለአንተ ፡ ተገቢህም፡
ነው ።

35 ከዚያም ፡ ጥፋት ፡ ይጠጋህ ፡ ለአ
ንተ ፡ የተገባህም ፡ ነው ።

36 ሰው ፡ ስድ ፡ ኾኖ ፡ መትተውን ፡
ይጠረጥራልን ?

37 የሚፈሰስ ፡ ከኾነ ፡ የፍትወት ፡
ጠብታ ፡ አልነበረምን ?

38 ከዚያም ፡ የረጋ ፡ ደም ፡ ኾነ ፤
(አላህ ፡ ሰው ፡ አድርጎ) ፡ ፈጠ
ረውም ፤ አስተካከለውም ።

39 ከርሱም ፡ ሁለት ፡ ዓይነቶችን ፡
ወንድና ፡ ሴትን ፡ አደረገ ።

40 ይህ ፡ (ጌታ) ፡ ሙታንን ፡ ሕያው ፡
በማድረግ ፡ ላይ ፡ ቻይ ፡ አይደ
ለምን ?

## ምዕራፍ ፡ 76 ፡ አል-ደህር ። ክፍል ፡ 29 ።

76ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ደህር ፤ (የዘመናት ፡ ምዕራፍ) ። አብዛኞቹ ፡ እን
ደሚሉት ፡ መዲናዊ ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 31 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።

1 በሰው ፡ ላይ ፡ የሚታወስ ፡ ነገር ፡
ሳይኾን ፡ ከዘመናት ፡ የተወሰነ ፡
ጊዜ ፡ በእርግጥ ፡ አልፎበታል ።

2 እኛ ፡ ሰውን ፡ (በሕግ ፡ ግዳጅ) ፡
የምንሞክረው ፡ ስንኾን ፡ ቅልቅ
ሎች ፡ ከኾኑ ፡ የፍትወት ፡ ጠብታ
ፈጠርነው ፤ ሰሚ ፡ ተመልካችም፡
አደረግነው ።

3 እኛ ፡ ወይ ፡ አመስጋኝ ፡ ወይም ፡
ከሓዲ ፡ ሲኾን ፡ መንገዱን ፡ መራ
ነው ፤ (ገለጽንለት) ።

4 እኛ ፡ ለከሓዲዎች ፡ ሰንሰለቶች
ንና ፡ እንዛዝላዎችን ፡ እሳትንም ፡
አዘጋጅተናል ።

5 በጎ ፡ አድራጊዎች ፡ መበረዣዋ ፡
ካፉር ፡ ከኾነች ፡ ጠጅ ፡ ይጠ
ጣሉ ።

6 ከርሷ ፡ የአላህ ፡ ባሮች ፡ የሚጠ
ጡላት ፡ (ወደፈለጉበት) ፡ ማን
ቧቧትን ፡ የሚያንቧቧት ፡ ከኾ
ነች ፡ ምንጭ ፡ (ይጠጣሉ) ።



7 (ዛሬ) ፡ በስለታቸው ፡ ይሞላሉ ፤
መከራው ፡ ተሰራጪ ፡ የኾነንም ፡
ቀን ፡ ይፈራሉ ።

8 ምግብንም ፡ ከመውደዳቸው ፡
ጋር ፡ ለድኻ ፡ ለየቲምም ፡ ለም
ርኮኛም ፡ ለእስረኛም ፡ ያበላሉ ።

9 የምናበላችሁ ፡ ለአላህ ፡ ውዴታ ፡
ብቻ ፡ ነው ፤ ከናንተ ፡ ዋጋንም ፡
ማመስገንንም ፡ አንፈልግም ።

10 እኛ ፡ (ፊትን) ፡ የሚያጨፈግግን ፡
ብርቱን ፡ ቀን ፡ ከጌታችን ፡ እን
ፈራለንና ፤ (ይላሉ) ።

11 አላህም ፡ የዚያን ፡ ቀን ፡ ክፉት ፡
ጠበቃቸው ፤ (ፊታቸው) ፡ ማ
ማርንና ፡ መደሰትንም ፡ ገጠማ
ቸው ።

12 በመታገሣቸውም ፡ ገነትንና ፡
የሐር ፡ ልብስን ፡ መነዳቸው ።

13 በውስጧ ፡ በባለ ፡ አጎበር ፡ አል
ጋዎች ፡ ላይ ፡ ተደጋፊዎች ፡ በው
ስጧ ፡ ፀሐይንም ፡ ጨረቃንም ፡
የማያዩ ፡ ሲኾኑ ።

14 ዛፎችዋም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ የቀረ
በች ፡ ፍሬዎችዋም ፡ (ለለቃሚ
ዎች) ፡ መገራትን ፡ የተገራች ፡
ስትኾን ፡ (ገነትን ፡ መነዳቸው) ።

15 በነሱም ፡ ላይ ፡ ከብር ፡ በኾኑ ፡
ዕቃዎች ፡ (ሰሐኖች) ፡ የብርጭ
ቆዎች ፡ በኾኑ ፡ ኩባያዎችም ፡
ይዝዞርባቸዋል ።

16 መለካትን ፡ የለኳቸው ፡ በኾኑ ፡
የብር ፡ ብርጭቆዎች ፡ (ይዝዞርባ
ቸዋል) ።

17 በርሷም ፡ መበረዣዋ ፡ ዘንጀቢል ፡
የኾነችን ፡ ጠጅ ፡ ይጠጣሉ ።

18 በውስጧ ፡ ያለችውን ፡ ሰልሰቢል
ተብላ ፡ የምትጠራውን ፡ ምንጭ ።

19 በነሱም ፡ ላይ ፡ (ባሉበት ፡ ኹነታ) ፡
የሚዘወትሩ ፡ ወጣት ፡ ልጆች ፡
ይዘዋወራሉ ፤ ባየሃቸው ፡ ጊዜ ፡
የተበተነ ፡ ሉል ፡ ናቸው ፡ ብለህ ፡
ታስባቸዋለህ ።

20 እዚያም ፡ በተመለከትክ ፡ ጊዜ ፡
ጸጋንና ፡ ታላቅ ፡ ንግሥናን ፡
ታያለህ ።

21 አረንጓዴዎች ፡ የኾኑ ፡ የቀጭን ፡
ሐር ፡ ልብሶችና ፡ ወፍራም ፡
ሐርም ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ አልለ ።
ከብር ፡ የኾኑ ፡ አንበሮችንም ፡
ይሸለማሉ ፤ ጌታቸውም ፡ አ
ጥሪ ፡ የኾነን ፡ መጠጥ ፡ ያጠጣቸ
ዋል ።

22 ይህ ፡ በእርግጥ ፡ ለናንተ ፡ ዋጋ ፡
ኾነ ፤ ሥራችሁም ፡ ምስጉን ፡
ኾነ ፤ (ይባላሉ) ።

23 እኛ ፡ ቁርአንን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡
ማውረድን ፡ እኛው ፡ አወረድ
ነው ።

24 ለጌታህ ፡ ፍርድም ፡ ታገሥ ፤
ከነሱም ፡ ኃጢአተኛን ፡ ወይም ፡
ከሓዲን ፡ አትታዘዝ ።

25 የጌታህንም ፡ ስም ፡ በጧትና ፡ ከቀ
ትር ፡ በላይ ፡ አውሳ ።

26 ከሌሊቱም ፡ ለርሱ ፡ ስገድ ፤ በረ
ዥም ፡ ሌሊትም ፡ አወድሰው ።

27 እነዚህ ፡ ፈጣኒቱን ፡ ዓለም ፡
ይወዳሉ ፤ ከባድን ፡ ቀንም ፡ በስ
ተፊታቸው ፡ ኾኖ ፡ ይተዋሉ ።

28 እኛ ፡ ፈጠርናቸው ፤ መለያልያ
ቸውንም ፡ አጠነከርን ፤ በሻንም ፡
ጊዜ ፡ መሰሎቻቸውን ፡ መለወ
ጥን ፡ እንለውጣለን ።

29 ይህቺ ፡ መገሠጫ ፡ ናት ፤ የሻም ፡
ሰው ፡ ወደ ፡ ጌታው ፡ መንገድን ፡
ይይዛል ።
30 አላህም ፡ ካልሻ ፡ በስተቀር ፡
አትሹም ፤ አላህ ፡ ዐዋቂ ፡ ጥበ
በኛ ፡ ነውና ።
31 የሚሻውን ፡ ሰው ፡ በእዝነቱ ፡
ውስጥ ፡ ያገባዋል ፤ በዳዮቹንም ፡
(ዝቶባቸዋል) ፤ ለነሱ ፡ አሳማሚ ፡
ቅጣትን ፡ አዘጋጅቶላቸዋል ።

## ምዕራፍ ፡ 77 ፡ አል-ሙርሰላት ። ክፍል ፡ 29 ።

77ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሙርሰላት ፤ (የተላኪዎች ፡ ምዕራፍ) ። በ
መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 50 ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 ተከታታይ ፡ ኾነው ፡ በተላኩት ፤
2 በኀይል ፡ መንፈስን ፡ ነፋሾች ፡
በኾኑትም ፤
3 መበተንን ፡ በታኞች ፡ በኾኑትም ፤
(ነፋሶች) ፤
4 መለየትን ፡ ለይዎች ፡ በኾኑትም ፤
5 መገሠጫን ፡ (ወደ ፡ ነቢያት) ፡
ጣይዎች ፡ በኾኑትም ፤
6 ምክንያትን ፡ ለማስወገድ ፡ ወይም
ለማስፈራራት ፡ (ጣይዎች ፡ በኾ
ኑት ፡ መላእክት) ፡ እምላለሁ ።
7 ያ ፡ የምትስፈራሩበት ፡ (ትንሣኤ)
በእርግጥ ፡ ኋኝ ፡ ነው ።
8 ከዋክብትም ፡ (ብርሃንዋ) ፡ በታ
በሰች ፡ ጊዜ ።
9 ሰማይም ፡ በተከፈተች ፡ ጊዜ ።
10 ጋራዎችም ፡ በተንኮተኮቱ ፡ ጊዜ ።
11 መልክተኞቹም ፡ ወቅት ፡ በተደ
ረገላቸው ፡ ጊዜ ።
12 ለየትኛው ፡ ቀን ፡ ተቀጠሩ ፡ (የሚ
ባል ፡ ሲኾን) ፤
13 ለመለያው ፡ ቀን ፡ (በተባለ ፡
ጊዜ ፤ በፍጡሮች ፡ መካከል ፡
ይፈረዳል) ።
14 የመለያውም ፡ ቀን ፡ ምን ፡ እን
ደኾነ ፡ ምን ፡ አሳወቀህ ?
15 ለአስተባባዮች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡
ወዮላቸው ።
16 የፊተኞቹን ፡ (ሕዝቦች) ፡ አላጠ
ፋንምን ?
17 ከዚያም ፡ የኋለኞቹን ፡ እናስከ
ትላቸዋለን ።
18 በአመጠኞች ፡ ሁሉ ፡ እንደዚሁ ፡
እንሠራለን ።
19 ለአስተባባዮች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡
ወዮላቸው ።
20 ከደካማ ፡ ውሃ ፡ አልፈጠርናችሁምን ?
21 በተጠበቀ ፡ መርጊያ ፡ ውስጥም ፡
(በማሕፀን) ፡ አደረግነው ፤
22 እስከ ፡ ታወቀ ፡ ልክ ፡ ድረስ ።
መጠንነውም ፤ ምን ፡ ያማርንም ፡
23 መጣኞች ፡ ነን ።



24 ላስተባባዮች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ወዮ
ላቸው ።
25 ምድርን ፡ ሰብሳቢ ፡ አላደረግና
ትምን ?
26 ሕያዋን ፡ ኾናችሁ ፡ ሙታንም ፡
ኾናችሁ ።
27 በውስጧም ፡ ከፍተኛዎችን ፡
ተራራዎች ፡ አደረግን ፤ ጣፋጭ ፡
ውሃንም ፡ አጠጣናችሁ ።
28 ለአስተባባዮች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡
ወዮላቸው ።
29 ወደዚያ ፡ በርሱ ፡ ታስተባብሉ ፡
ወደ ፡ ነበራችሁት ፡ (ቅጣት) ፡
አዝግሙ ።
30 ባለ ፡ ሦስት ፡ ቅርንጫፎች ፡ ወደ ፡
ኾነው ፡ ጥላ ፡ አዝግሙ ፤ (ይባ
ላሉ) ።
31 አጠላይ ፡ ያልኾነ ፡ ከእሳቱም ፡
ላንቃ ፡ የማይደግን ፡ ወደ ፡ ኾነው ፡
(አዝግሙ) ።
32 እርሷ ፡ እንደ ፡ ታላላቅ ፡ ሕንጻ ፡
የኾኑን ፡ ቃንቄዎች ፡ ትወረው
ራለች ።
33 (ቃንቄውም) ፡ ልክ ፡ ዳለቻዎች ፡
ግመሎችን ፡ ይመስላል ።
34 ለአስተባባዮች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡
ወዮላቸው ።
35 ይህ ፡ የማይናገሩበት ፡ ቀን ፡ ነው ።
36 ይቅርታም ፡ ይጠይቁ ፡ ዘንድ ፤
ለነርሱ ፡ አይፈቀድላቸውም ።
37 ለአስተባባዮች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡
ወዮላቸው ።
38 ይህ ፡ መለያው ፡ ቀን ፡ ነው ፤
እናንተንም ፡ የፊተኞቹንም ፡
ሰበሰብናችሁ ።
39 ለናንተም ፡ (ለማምለጥ) ፡ ብል
ሃት ፡ እንዳላችሁ ፡ ተተናኮሉኝ ።
40 ላስተባባዮች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ወዮ
ላቸው ።
41 ጥንቁቆቹ ፡ በጥላዎችና ፡ በምን
ጮች ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።
42 ከሚከጅሉትም ፡ ሁሉ ፡ በፍራ
ፍሬዎች ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።
43 ትሠሩት ፡ በነበራችሁት ፡ ዋጋ ፡
የምትደሰቱ ፡ ኾናችሁ ፡ ብሉ ፤
ጠጡም ፤ (ይባላሉ) ።
44 እኛ ፡ እንደዚሁ ፡ መልካም ፡
ሠሪዎችን ፡ ሁሉ ፡ እንመነዳለን ።
45 ላስተባባዮች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ወዮ
ላቸው ።
46 ብሉ ፤ ጥቂትንም ፡ (ጊዜ) ፡ ተጠ
ቀሙ ፤ እናንተ ፡ አመጠኞች ፡
ናችሁና ።
47 ላስተባባዮች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ወዮ
ላቸው ።
48 ለነሱ ፡ስገዱም ፡ በተባሉ ፡ ጊዜ ፡
አይሰግዱም ።
49 ላስተባባዮች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ወዮ
ላቸው ።
50 ከርሱም ፡ ሌላ ፡ በየትኛው ፡ ንግ
ግር ፡ ያምናሉ ?

* * *

78ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ነበእ ፤ (የዜናው ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 40 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 ከምን ፡ ነገር ፡ ይጠያየቃሉ ?

2 ከታላቁ ፡ ዜና ፡ (ከቁርአን ፡ ይጠያየቃሉ) ።

3 ከዚያ ፡ እነሱ ፡ በርሱ ፡ የተለያዩበት ፡ ከኾነው ።

4 ይከልከሉ ፤ ወደፊት ፡ (የሚደርስባቸውን) ፡ በእርግጥ ፡ ያውቃሉ ።

5 ከዚያም ፡ ይከልከሉ ፤ ወደፊት ፡ ያውቃሉ ።

6 ምድርን ፡ ምንጣፍ ፡ አላደረግንምን ?

7 ጋራዎችንም ፡ ችካሎች ፡ አላደረግንምን ?

8 ብዙ ፡ ዓይነቶችም ፡ አድርገን ፡ ፈጠርናችሁ ።

9 እንቅልፋችሁንም ፡ ዕረፍት ፡ አደረግን ።

10 ሌሊቱንም ፡ ልባስ ፡ አደረግን ።

11 ቀኑንም ፡ (ለኑሮ) ፡ መሥሪያ ፡ አደረግን ።

12 ከበላያችሁም ፡ ሰባትን ፡ ብርቱዎች ፡ (ሰማያት) ፡ ገነባን ።

13 አንጸባራቂ ፡ ብርሃንንም ፡ አደረግን ።

14 ከአረገዙት ፡ ደመናዎችም ፡ ተንቧቢ ፡ ውሃን ፡ አወረድን ።

15 በርሱ ፡ እኽልንና ፡ ቅጠላ ፡ ቅጠልን ፡ እናወጣ ፡ ዘንድ ፡ (አወረድን) ።

16 የተቆላለፉ ፡ አትክልቶችንም ።

17 የመለያው ፡ ቀን ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

18 በቀንዱ ፡ በሚነፋና ፡ የተለያዩ ፡ ጭፍሮች ፡ ኾናችሁ ፡ በምትመጡ ፡ ቀን ፡ ነው ።

19 ሰማይም ፡ በምትከፈትና ፡ (ባለ) ፡ ደጃፎችም ፡ በምትኾንበት ።

20 ጋራዎችም ፡ በሚነዱበት ፡ (እንደ) ሲራብዱም ፡ በሚኾኑበት ፡ (ቀን) ፡ ነው ።

21 ገሀነም ፡ መጠባበቂያ ፡ (ስፍራ) ፡ ናት ።

22 ለሕግ ፡ ተላላፊዎች ፡ መመለሻ ፡ ስትኾን ።

23 በውስጧ ፡ ብዙን ፡ ዘመናት ፡ ነዋሪዎች ፡ ሲኾኑ ፤

24 በውስጧ ፡ ቅዝቃዜንም ፡ መጠጥንም ፡ አይቀምሱም ።

25 ግን ፡ሙቅ ፡ ውሃንና ፡ እዥን ፡ (ይቀምሳሉ) ።

26 ተስማሚን ፡ ምንዳ ፡ ይመነዳሉ ። (1)

27 እነሱ ፡ ምርመራን ፡ የማይፈሩ ፡ ነበሩና ።

1 የየሥራቸውን ፡ ዓይነት ፡ ዋጋ ፡ ያገኛሉ ።



28 በአንቀጾቻችንም ፡ማስተባበልን ፡ አስተባበሉና ።

29 ነገሩንም ፡ ሁሉ ፡ የተጻፈ ፡ ሲኾን ፡ አጠቃለልነው ።

30 ቅመሱም ፤ ቅጣትንም ፡ እንጅ ፡ (ሌላን) ፡ አንጨምራችሁም ፡ (ይባላሉ) ።

31 ለጥንቁቆቹ ፡ መዳኛ ፡ ስፍራ ፡ አላቸው ።

32 አትክልቶችና ፡ ወይኖችም ።

33 እኩያዎች ፡ የኾኑ ፡ ጡተ ፡ ጉቻማዎችም ።

34 የተሞሉ ፡ ብርጭቆዎችም ።

35 በውስጧ ፡ ትርፍ ፡ ቃልንም ፡ ማስዋሸትንም ፡ አይሰሙም ።

36 ከጌታህ ፡ የኾነን ፡ ምንዳ ፡ በቂ ፡ ስጦታን ፡ (ተሰጡ) ።

37 የሰማያትና ፡ የምድር ፡ በመካከላቸውም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ ከኾነው ፡ (ተመነዱ) ፤ ከርሱ ፡ ጋር ፡ መነጋገርን ፡ አይችሉም ።

38 መንፈሱ ፡ (ጂብሪል) ፡ መላእክቶቹም ፡ የተሰለፉ ፡ ኾነው ፡ በሚቆሙ ፡ ቀን ፡ አል-ረሕማን ፡ ለርሱ የፈቀደለትና ፡ ትክክለኛን ፡ ቃል ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ እንጅ ፡ (መነጋገርን ፡ አይችሉም) ።

39 ይህ ፡ የተረጋገጠው ፡ ቀን ፡ ነው ። የሻም ፡ ሰው ፡ ወደጌታው ፡ መመለስን ፡ ይይዛል ።

40 እኛ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እጆቹ ፡ ያስቀደሙትን ፡ በሚያይበትና ፡ ከሓዲውም ፡ ዋ ፡ ምኞቴ ፡ ምንነው ፡ ዐፈር ፡ በኾንኩ ፡ በሚልበት ፡ ቀን ፡ ቅርብ ፡ የኾነን ፡ ቅጣት ፡ አስጠነቀቅናችሁ ።

ምዕራፍ ፡ 79 ፡ አል-ናዚዓት ። ክፍል ፡ 30 ።

79ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ናዚዓት ፤ (የአውጪዎች ፡ ምዕራፍ ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 46 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩህ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 በኃይል ፡ አውጪዎች ፡ በኾኑት ፤

2 በቀስታ ፡ መምዘዝንም ፡ መዛዦች ፡ በኾኑት ፤

3 መዋኘትንም ፡ ዋኚዎች ፡ በኾኑት ፤

4 መቅደምንም ፡ ቀዳሚዎች ፡ በኾኑት ፤

5 ነገርንም ፡ አስተናባሪዎች ፡ በኾኑት ፡ (መላእክት) ፡ እምላለሁ ፤ (በእርግጥ ፡ ትቀሰቀሳላችሁ) ።

6 ተርገፍጋፊይቱ ፡ (ምድር) ፡ በምትርገፈገፍበት ፡ ቀን ፤

7 ለጣቂይቱ ፡ የምትከተላት ፡ ስትኾን ፡ (ትቀሰቀሳላችሁ) ።

8 በዚያ ፡ ቀን ፡ ልቦች ፡ ተሸባሪዎች ፡ ናቸው ።

9 ዓይኖቻቸው ፡ ተዋራጆች ፡ (አቀርቃሪዎች) ፡ ናቸው ።

10 እኛ ፡ ወደ ፡ መጀመሪያይቱ ፡ ኹነታ ፡ ተመላሾች ፡ ነን? ይላሉ ።
11 የበሰበሱ ፡ አጥንቶች ፡ በኾን ፡ ጊዜ ፡ (እንቀሰቀሳለን ?)
12 ይህቺ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ባለ ፡ ከሳራ ፡ መመለስ ፡ ናት ፡ ይላሉ ።
13 እርሷም ፡ አንዲት ፡ ጩኸት ፡ ብቻ ፡ ናት ፤
14 ወዲያውኑም ፡ እነሱ ፡ እንቅልፍ ፡ በሌለባት ፡ (ምድር) ፡ ላይ ፡ ይኾናሉ ።
15 የሙሳ ፡ ወሬ ፡ መጣልህን ?
16 ጌታው ፡ በተቀደሰው ፡ ሸለቆ ፡ በጡዋ ፡ በጠራው ፡ ጊዜ ፤
17 ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ኺድ ፤ እርሱ ፡ ወሰን ፡ አልፏልና ።
18 በለውም ፦ ወደ ፡ መጥራራትህ ፡ ላንተ ፡ (መንገድ) ፡ አለህን ?
19 ወደ ፡ ጌታህም ፡ ልመራህ ፡ ትፈራውም ፡ ዘንድ ፤ (መንገድ ፡ አለህን ?) አለው ።
20 ታላቂቱንም ፡ ታምር ፡ አሳየው ።
21 አስተባበለም ፤ አመጠም ።
22 ከዚያም ፡ (ለማጥፋት) ፡ የሚተጋ ፡ ኾኖ ፡ ዞረ ።
23 (ሰራዊቶቹን) ፡ ሰበሰበም ፤ ተጣራም ።
24 አለም ፦ እኔ ፡ ታላቁ ፡ ጌታችሁ ፡ (1) ነኝ ።
25 አላህም ፡ በኋለኛይቱና ፡ በፊተኛይቱ ፡ (ቃል) ፡ ቅጣት ፡ ያዘው ።
26 በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ለሚፈራ ፡ ሰው ፡ በእርግጥ ፡ መገምገሚያ ፡ አለበት ።
27 ባፈጣጠር ፡ እናንተ ፡ ይበልጥ ፡ የበረታችሁ ፡ ናችሁን ? ወይንስ ፡ ሰማይ ? (አላህ) ፡ ገነባት ።
28 ከፍታዋን ፡ አጓነ ፤ አስተካከላትም ።
29 ሌሊቷንም ፡ አጨለመ ፤ ቀንዋንም ፡ ገለጸ ።
30 ምድርንም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዘረጋት ።
31 ውሃዋንና ፡ ግጦሿን ፡ ከርሷ ፡ አወጣ ።
32 ጋራዎችንም ፡ አደላደላቸው ።
33 ለናንተና ፡ ለእንስሶቻችሁ ፡ መጠቀሚያ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ (ይህን ፡ አደረገ) ።
34 ታላቂቱም ፡ መዐት ፡ በመጣች ፡ ጊዜ ፤
35 ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሠራውን ፡ በሚያስታውስበት ፡ ቀን ፤
36 ገሀነምም ፡ ለሚያይ ፡ ሰው ፡ በተገለጠች ፡ ጊዜ ፤
37 የካደ ፡ ሰውማ ፤
38 ቅርቢቱንም ፡ ሕይወት ፡ የመረጠ ፤
39 ገሀነም ፡ እርሷ ፡ በእርግጥ ፡ መኖሪያው ፡ ናት ።
40 በጌታው ፡ ፊት ፡ መቆምን ፡ የፈራ ሰውማ ፡ ነፍሱንም ፡ ከዝንባሌዋ ፡ የከለከለ ፤
41 ገነት ፡ እርሷ ፡ በእርግጥ ፡ መኖሪያው ፡ ናት ።
42 ከሰዓቲቱ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ መኾኛዋ ? ሲሉ ፡ ይጠይቁሃል ።
43 አንተ ፡ እርሷን ፡ ከማስታወስ ፡ በምን ፡ ውስጥ ፡ ነህ ?
44 (የዕውቀት) ፡ መጨረሻዋ ፡ ወደ ፡ ጌታህ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
45 አንተ ፡ የሚፈራትን ፡ ሰው ፡ አስፈራሪ ፡ ብቻ ፡ ነህ ።
46 እነርሱ ፡ በሚያዩዋት ፡ ቀን ፡ ያንዲት ፡ ቀን ፡ ምሽትን ፡ ወይም ፡ ረፋዷን ፡ እንጅ ፡ ያልቆዩ ፡ ይመስላሉ ።

1 የበላይ ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝ ።



80ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ዐበሰ ፤ (የማጨፍገግ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 42 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 ፊቱን ፡ አጨፈገገ ፤ ዞረም ፤
2 ዕውሩ ፡ ስለ ፡ መጣው ።
3 ምን ፡ ያሳውቅሃል ? (ከኀጢአቶቹ) ፡ ሊጥራራ ፡ ይከጀላል ።
4 ወይም ፡ ሊገሠጽ ፡ ግሣጼይቱም ፡ ልትጠቅመው ፡ (ይከጀላል) ።
5 የተብቃቃው ፡ ሰውማ ፤
6 አንተ ፡ ለርሱ ፡ (ለእምነቱ ፡ በመጓጓት) ፡ በፊገግታ ፡ ትቀበለዋለህ ፤
7 ባይጥራራ ፡ (ባያምን) ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ የሌለብህ ፡ ስትኾን ፤
8 እየገሰገሠ ፡ የመጣህ ፡ ሰውማ ፤
9 እርሱ ፡ (አላህን) ፡ የሚፈራ ፡ ሲኾን ፤
10 አንተ ፡ ከርሱ ፡ ትዝዘናጋለህ ።
11 ተከልከል ፤ እርሷ ፡ ማስገንዘቢያ ፡ ናት ።
12 የሻም ፡ ሰው ፡ (ቁርአኑን) ፡ ያስታውሰዋል ።
13 በተከበሩ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ነው ፤
14 ከፍ ፡ በተደረገች ፡ ንጹሕ ፡ በተደገረች ፡ (ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ነው) ።
15 በጸሐፊዎቹ ፡ (መላእክት) ፡ እጆች ፡ (ንጹሕ ፡ የተደረገች) ።
16 የተከበሩና ፡ ታዛዦች ፡ በኾኑት ፤ (ጸሐፊዎች ፡ እጆች) ።
17 ሰው ፡ ተረገመ ፤ ምን ፡ ከሓዲ ፡ አደረገው ?
18 (ጌታው) ፡ ከምን ፡ ነገር ፡ ፈጠረው ? (አያስብምን ?)
19 ከፍትወት ፡ ጠብታ ፡ ፈጠረው ፤ መጠነውም ።
20 ከዚያም ፡ (መውጫ) ፡ መንገዱን ፡ አገራው ።
21 ከዚያም ፡ ገደለው ፤ እንዲቀበርም ፡ አደረገው ፤
22 ከዚያም ፡ (ማንሳቱን) ፡ በሻ ፡ ጊዜ ፡ ያስነሳዋል ።
23 በውነት ፡ ያንን ፡ (ጌታው) ፡ ያዘዘውን ፡ ገና ፡ አልፈጸመም ።
24 ሰውም ፡ ወደ ፡ ምግቡ ፡ ይመልከት ፤
25 እኛ ፡ ውሃን ፡ ማንቧቧትን ፡ ያንቧቧን ፡ መኾናችንን ፤
26 ከዚያም ፡ ምድርን ፡ (በደካማ ፡ ቡቃያ) ፡ መሰንጠቅን ፡ የሰነጠቅን ፤
27 በውስጧም ፡ እኽልን ፡ ያበቀልን ፤
28 ወይንንም ፤ እርጥብ ፡ ሳርንም ፤
29 የዘይት ፡ ወይራንም ፡ ዘንባባንም ፤
30 ጭፍቆች ፡ አትክልቶችንም ፤
31 ፍራፍሬንም ፡ ገለባንም ፤ (ያበቀልን ፡ መኾናችንን ፡ ይመልከት) ።
32 ለናንተም ፡ ለእንስሶቻችሁም ፡ መጠቀሚያ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ (ይህን ፡ ሠራን) ።

33 አደንቋሪይቱም ፡ (መከራ) ፡ በመጣች ፡ ጊዜ ፤
34 ሰው ፡ ከወንድሙ ፡ በሚሸሽበት ፡ ቀን ፤
35 ከናቱም ፤ ካባቱም ፤
36 ከሚስቱም ፤ ከልጁም ፤
37 ከነሱ ፡ ለየሰው ፡ ሁሉ ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ (ከሌላው) ፡ የሚያብቃቃው ፡ ኹነታ ፡ አልለው ። (1)

1 ለራሱ ፡ ብቻ ፡ ማሰብና ፡ መጨነቅ ፡ ይኖርበታል ።

38 ፊቶች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ አብሪዎች ፡ ናቸው ፤
39 ሳቂዎችም ፡ ተደሳቾችም ፡ ናቸው ።
40 ፊቶችም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ ትቢያ ፡ አልለባቸው ፤
41 ጥቁረት ፡ ትሸፍናቸዋለች ፤
42 እነዚያ ፡ እነሱ ፡ ከሓዲዎቹ ፡ አመጠኞቹ ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ 81 ፡ አል-ተክዊር ። ክፍል ፡ 30 ።

81ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ተክዊር ፤ (የመጠቅለል ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 29 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፤ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 ፀሐይ ፡ በተጠቀለለች ፡ ጊዜ ፤
2 ከዋክብትም ፡ በረገፉ ፡ ጊዜ ፤
3 ተራራዎችም ፡ በተነዱ ፡ ጊዜ ፤
4 የዐሥር ፡ ወር ፡ እርጉዞች ፡ ግመሎችም ፤ (ያለጠባቂ) ፡ በተተዉ ፡ ጊዜ ፤
5 እንስሳትም ፡ ሁሉ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፤
6 ባሕሮችም ፡ በተቃጠሉ ፡ ጊዜ ፤
7 ነፍሶችም ፡ (በየአካሎቻቸው) ፡ በተቆራኙ ፡ ጊዜ ፤
8 በሕይወቷ ፡ የተቀበረችውም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፤ በተጠየቀች ፡ ጊዜ ፤
9 በምን ፡ ወንጀል ፡ እንደ ፡ ተገደለች ፤
10 ጽሑፎችም ፡ በተዘረጉ ፡ ጊዜ ፤
11 ሰማይም ፡ በተገሸለጠች ፡ ጊዜ ፤
12 ገሀነምም ፡ በተነደደች ፡ ጊዜ ፤
13 ገነትም ፡ በተቀረበች ፡ ጊዜ ፤
14 ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ (ከሥራ) ፡ ያቀረበችውን ፡ ታውቃለች ፤
15 ተመላሾችም ፡ በኾኑት ፡ (ዐዋድያት) ፡ (1) እምላለሁ ።
16 ኺያጆች ፡ ገቢዎች ፡ በኾኑት ፤ (ከዋክብት) ።
17 በሌሊቱም ፤ (ጨለማውን) ፡ በጠነሰሰ ፡ ጊዜ ፤
18 በንጋቱም ፤ (በብርሃን) ፡ በተነፈሰ ፡ ጊዜ ፤ (እምላለሁ) ።
19 እርሱ ፡ (ቁርአን) ፡ የክቡር ፡ መልክተኛ ፡ ቃል ፡ ነው ።

1 ዐዋድያት ፡ ማለት ፡ ዘዋሪ ፡ ፕላኔት ፡ ማለት ፡ ነው ።



20 የኀይል ፡ ባለቤት ፡ በዙፋኑ ፡ ባለቤት ፡ ዘንድ ፡ ባለሟል ፡ የኾነ ፤
21 በዚያ ፡ ስፍራ ፡ ትእዛዙ ፡ ተሰሚ ፤ ታማኝ ፤ የኾነ ፡ (መልክተኛ ፡ ቃል) ፡ ነው ።
22 ነቢያችሁም ፡ በፍጹም ፡ ዕብድ ፡ አይደለም ።
23 በግልጹ ፡ አድማስም ፡ በእርግጥ ፡ አይቶታል ።
24 እርሱም ፡ በሩቁ ፡ ወሬ ፡ ላይ ፡ ሰሳች ፡ (ንፉግ) ፡ አይደለም ።
25 እርሱም ፡ (ቁርአን) ፡ የርጉም ፡ ሰይጣን ፡ ቃል ፡ አይደለም ።
26 ታዲያ ፡ ወዴት ፡ ትኼዳላችሁ ?
27 እርሱ ፡ የዓለማት ፡ መገሠጫ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ።
28 ከናንተ ፡ ቀጥተኛ ፡ መኾንን ፡ ለሻ ፡ ሰው ፡ (መገሠጫ ፡ ነው) ።
29 የዓለማት ፡ ጌታ ፡ አላህ ፡ ካልሻም ፤ አትሹም ።

## ምዕራፍ ፡ 82 ፡ አል-ኢንፊጣር ። ክፍል ፡ 30 ።

82ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ኢንፊጣር ፤ (የመሰንጠቅ ፡ ምዕራፍ) ፡ በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 19 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፤ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 ሰማይ ፡ በተሰነጠቀች ፡ ጊዜ ፤
2 ከዋክብትም ፡ ተበታትነው ፡ በወደቁ ፡ ጊዜ ፤
3 ባሕሮችም ፡ በተከፈቱና ፡ በተደበላለቁ ፡ ጊዜ ፤
4 መቃብሮችም ፡ በተገለባበጡና ፡ (ሙታን) ፡ በተነሱ ፡ ጊዜ ፤
5 ማንኛይቱም ፡ ነፍስ ፡ ያስቀደመችውንና ፡ ያቆየችውን ፡ ታውቃለች ።
6 አንተ ፡ ሰው ፡ ሆይ ፤ በቸሩ ፡ ጌታህ ፡ ምን ፡ አታለለህ?
7 በዚያ ፡ በፈጠረህ ፤ አካለ ፡ ሙሉም ፡ ባደረገህ ፤ ባስተካከለህም ።
8 በማንኛውም ፡ በሻው ፡ ቅርጽ ፡ በገጣጠመህ ፡ (ጌታህ ፡ ምን ፡ አታለለህ) ።
9 ተከልከሉ ፤ በውነቱ ፡ በፍርዱ ፡ ቀን ፡ ታስተባብላላችሁ ።
10 በናንተ ፡ ላይ ፡ ተጠባባቂዎች ፡ ያሉባችሁ ፤ ስትኾኑ ፤
11 የተከበሩ ፤ ጸሐፊዎች ፡ የኾኑ ፤ (ተጠባባቂዎች) ፤
12 የምትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ የሚያውቁ
13 እውነተኞቹ ፡ ምእምናን ፡ በእርግጥ ፡ በገነት ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።
14 ከሓዲዎቹም ፡ በእርግጥ ፡ በገሀነም ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።
15 በፍርዱ ፡ ቀን ፡ ይገቧታል ።
16 እነርሱም ፡ ከርሷ ፡ ራቂዎች ፡ አይደሉም ።

17 የፍርዱ ፡ ቀን ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ምን ፡ አሳወቀህ ?
18 ከዚያም ፡ የፍርዱ ፡ ቀን ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ምን ፡ አሳወቀህ ?
19 (እርሱ) ፡ ማንኛይቱም ፡ ነፍስ ፡ ለሌላይቱ ፡ ነፍስ ፡ ምንም ፡ ማድረግን ፡ የማትችልበት ፡ ቀን ፡ ነው ። ነገሩም ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ለአላህ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 83 ፡ አል-ሙጠፊፊን ። ክፍል ፡ 30 ።

83ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሙጠፊፊን ፤ (የሰላቢዎች ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፤ (አንቀጾችዋ) ፡ 36 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 ለሰላቢዎች ፡ ወዮላቸው ፤
2 ለነዚያ ፡ ከሰዎች ፡ ባስሰፈሩ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስሞሉ ፤
3 ለነሱም ፡ (ለሰዎቹ) ፡ በሰፈሩ ፡ ወይም ፡ በመዘኑላቸው ፡ ጊዜ ፡ የሚያጎድሉ ፡ (ለኾኑት) ።
4 እነዚያ ፡ እነሱ ፡ ተቀስቃሾች ፡ መኾናቸውን ፡ አያውቁምን ?
5 በታላቁ ፡ ቀን ፤
6 ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለዓለማት ፡ ጌታ ፡ (ፍርድ) ፤ በሚቆሙበት ፡ ቀን ፡ (ተቀስቃሾች ፡ መኾናቸውን) ።
7 በውነት ፡ የከሓዲዎቹ ፡ (የሰላቢዎቹ) ፡ መጽሐፍ ፡ በእርግጥ ፡ በሲጂን ፡ ውስጥ ፡ ነው ።
8 ሲጂንም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ምን ፡ አሳወቀህ ?
9 የታተመ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ።
10 ለአስተባባዮች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ወዮላቸው ።
11 ለነዚያ ፡ በፍርዱ ፡ ቀን ፡ ለሚያስተባብሉት ።
12 በርሱም ፡ ወሰን ፡ አላፊ ፡ ኀጢአተኛ ፡ ሁሉ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አያስተባብልም ።
13 አንቀጾቻችን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ በተነበቡ ፡ ጊዜ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ተረቶች ፡ ናቸው ፡ ይላል።
14 ይከልከል ፤ ይልቁንም ፡ በልቦቻቸው ፡ ላይ ፡ ይሠሩት ፡ የነበሩት ፡ (ኀጢአት) ፡ ደገደገባቸው ፤
15 ይከልከሉ ፤ እነሱ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከጌታቸው ፡ (ማየት) ፡ ተጋራጆች ፡ ናቸው ።
16 ከዚያም ፡ እነሱ ፡ በእርግጥ ፡ ገሀነምን ፡ ገቢዎች ፡ ናቸው ።
17 ከዚያም ፡ ይህ ፡ ያ ፡ በርሱ ፡ ታስተባብሉበት ፡ የነበራችሁት ፡ ነው ፡ ይባላሉ ።
18 በውነቱ ፡ የውነተኞቹ ፡ ምእምናን ፡ መጽሐፍ ፡ በዒሊዮን ፡ ውስጥ ፡ ነው ።
19 ዒሊዮንም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ምን ፡ አሳወቀህ ?



20 የታተመ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ።
21 ባለሟልዎቹ ፡ ይጣዱታል ።
22 እውነተኞቹ ፡ ምእምናን ፡ በእርግጥ ፡ በድሎት ፡ (ገነት) ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።
23 በባለ ፡ አጎበር ፡ አልጋዎች ፡ ላይ ፡ ኾነው ፡ ይመለከታሉ ።
24 በፊቶቻቸው ፡ ላይ ፡ የድሎትን ፡ ውበት ፡ ታውቃለህ ።
25 ተጣርቶ ፡ ከታተመ ፡ ጠጅ ፡ ይጠጣሉ ።
26 ማተሚያው ፡ ምስክ ፡ ከኾነ ፤ በዚህም ፡ ተሽቀዳዳሚዎች ፡ ይሽቀዳደሙ ።
27 መበረዣውም ፡ ከተስኒም ፡ ነው ።
28 ባለሟሎቹ ፡ ከርሷ ፡ የሚጠጡላት ፡ ምንጭ ፡ ናት ።
29 እነዚያ ፡ ያምመጡት ፡ በነዚያ ፡ ባመኑት ፡ በእርግጥ ፡ ይስቁ ፡ ነበሩ ።
30 በነሱም ፡ ላይ ፡ ባለፉ ፡ ጊዜ ፡ ይጠቃቀሱ ፡ ነበር ።
31 ወደ ፡ ቤተሰቦቻቸውም ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ (በመሳለቃቸው) ፡ ተደሳቾች ፡ ኾነው ፡ ይመለሱ ፡ ነበር ።
32 ባዩዋቸውም ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ በእርግጥ ፡ ተሳሳቾች ፡ ናቸው ፡ ይሉ ፡ ነበር ።
33 በነሱ ፡ ላይ ፡ ተጠባባቂዎች ፡ ተደርገው ፡ ያልተላኩ ፡ ሲኾኑ ።
34 ዛሬ ፡ (በትንሣኤ ፡ ቀን) ፡ እነዚያ፡ ያመኑት ፡ በከሓዲዎቹ ፡ ይስቃሉ ።
35 በባለ ፡ አጎበር ፡ አልጋዎች ፡ ላይ፡ ኾነው ፡ የሚመለከቱ ፡ ሲኾኑ ፡ (ይስቃሉ) ፤
36 ከሓዲዎች ፡ ይሠሩት ፡ የነበሩትን፡ (ዋጋ) ፡ ተመነዱን ? (ይላሉ) ።

## ምዕራፍ ፡ 84 ፡ አል-ኢንሺቃቅ ። ክፍል ፡ 30 ።

84ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ኢንሺቃቅ ፤ (የመቀደድ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፤ (አንቀጾችዋ) ፡ 25 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 ሰማይ ፡ በተቀደደች ፡ ጊዜ ፤
2 ለጌታዋም ፡ (ትእዛዝ) ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፤ (ልትሰማ) ፡ ተገባትም ፤
3 ምድርም ፡ በተለጠጠች ፡ ጊዜ ፤
4 በውስጧ ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ በጣለችና ፡ ባዶ ፡ በኾነች ፡ ጊዜ ፤
5 ለጌታዋም ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፤ (መስማት) ፡ ተገባትም ፤ (ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሥራውን ፡ ይገናኛል) ።
6 አንተ ፡ ሰው ፡ ሆይ ! አንተ ፡ ጌታህን ፡ (በሞት) ፡ እስከምትገናኝ ፡ ድረስ ፡ ልፋትን ፡ ለፊ ፡ ነህ፤ ተገናኚውም ፡ ነህ ።
7 መጽሐፉን ፡ በቀኙ ፡ የተሰጠ ፡ ሰውማ ፡

8 በእርግጥ ፡ ቀላልን ፡ ምርመራ ፡ ይመረመራል ፤
9 ወደ ፡ ቤተሰቦቹም ፡ ተደሳች ፡ ኾኖ ፡ ይመለሳል ።
10 መጽሐፉን ፡ በጀርባው ፡ ኋላ ፡ የተሰጠ ፡ ሰውማ ፤
11 (ዋ ፡ ጥፋቴ ፡ በማለት) ፡ ጥፋትን ፡ በእርግጥ ፡ ይጠራል ።
12 የተጋጋመች፡ እሳትንም፡ ይገባል ።
13 እርሱ ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ተደሳች ፡ ነበርና ።
14 እርሱ ፡ (ወደ ፡ አላህ) ፡ የማይመለስ ፡ መኾኑን ፡ አስቧልና ።
15 አይደለም ፡ (ይመለሳል) ፤ ጌታው በርሱ ፡ (መመለስ)፡ ዐዋቂ ፡ ነበር ፤ (ነውም) ።
16 አትካዱ ፤ በውጋገኑ ፡ (1) እምላለሁ ፡
17 በሌሊቱም ፡ በሰበሰበውም፡ ሁሉ ፤
18 በጨረቃውም ፡ በሞላ ፡ ጊዜ ፡ (እምላለሁ) ።
19 ከኹነታ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ኹነታ ፡ ትለዋወጣላችሁ ።
20 የማያምኑት ፡ ለነርሱ ፡ ምን ፡ አላቸው ?
21 በነሱም ፡ ላይ ፡ ቁርአን ፡ በተነበበ ፡ ጊዜ ፡ የማይሰግዱት ፤ (ምን፡ አላቸው ?)
22 በእርግጡ ፡ እነዚያ ፡ የካዱት ፡ (በትንሣኤ) ፡ ያስተባብላሉ ።
23 አላህም ፡ (በልቦቻቸው) ፡ የሚቆጥሩትን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ።
24 በአሳማሚ ፡ ቅጣትም ፡ አብስራቸው ።
25 ግን ፡ እነዚያ ፡ ያመኑና ፡ መልካሞችን ፡ የሠሩ ፡ ለነርሱ ፡ የማይቆረጥ ፡ ምንዳ ፡ አላቸው ።

1 በፀሐይ ፡ ግባት ፡ ቀይ ፡ ኾኖ ፡ በሚታየው ፡ ውጋገን ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 85 ፡ አል-ቡሩጅ ። ክፍል ፡ 30 ።

85ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ቡሩጅ ፤ (የቡርጆች ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ)፡ 22 ፡ ናቸው ።

በአላህ፡ ስም፡ እጅግ፡ በጣም፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 የቡርጆች ፡ ባለቤት ፡ በኾነችው ፡ ሰማይ ፡ እምላለሁ ፤
2 በተቀጠረው ፡ ቀንም ፤
3 በተጣጅና ፡ በሚጣዱትም ፤ (1) ፡ (እምላለሁ) ፤
4 የጉድቡ ፡ ባለቤቶች ፡ ተረገሙ ፤
5 የማገዶ ፡ ባለቤት ፡ የኾነቿው ፡ እሳት ፡ (ባለቤቶች) ።
6 እነርሱ ፡ በርሷ ፡ (አፋፍ) ፡ ላይ ፡ ተቀማጮች ፡ በኾኑ ፡ ጊዜ ፤ (ተረገሙ) ።
7 እነሱም ፡ በምእምናኖቹ ፡ በሚሠሩት ፡ (ማስቃየት) ፡ ላይ ፡ መስካሪዎች ፡ ናቸው ።

1 በቀራቢና ፡ በሚቀረብበትም ።



8 ከነሱም ፡ በአላህ ፡ አሸናፊው ፡ ምስጉኑ ፡ በኾነው ፡ (ጌታ) ፡ ማመናቸውን ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ አልጠሉም ።
9 በዚያ ፡ የሰማያትና ፡ የምድር ፡ ንግሥና ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡ በኾነው፡ (አላህ ፡ ማመናቸውን) ፡ አላህም ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ መስካሪ ፡ ነው ።
10 እነዚያ ፡ ምእምናንንና ፡ ምእምናትን ፡ ያሰቃዩ ፡ ከዚያም ፡ ያልተጸጸቱ ፡ ለነርሱ ፡ የገሀነም ፡ ቅጣት ፡ አላቸው ፤ ለነሱም ፡ የመቃጠሉ ፡ ስቃይ ፡ አላቸው ፤
11 እነዚያ ፡ ያመኑና ፡ መልካም ፡ ሥራዎችንም ፡ የሠሩ ፡ ለነሱ ፡ ከሥሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱባቸው ፡ ገነቶች ፡ አሏቸው ፤ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ማግኘት ፡ ነው ።
12 የጌታህ ፡ በኀይል ፡ መያዝ ፡ ብርቱ ፡ ነው ።
13 እነሆ ፡ እርሱ ፡ መፍጠርን ፡ ይጀምራል ፤ ይመልሳልም ።
14 እርሱም ፡ ምሕረተ ፡ ብዙ ፡ ወዳድ ፡ ነው ።
15 የዙፋኑ ፡ ባለቤት ፡ የላቀው ፡ ነው ።
16 የሚሻውን ፡ ሁሉ ፡ ሠሪ ፡ ነው ።
17 የሰራዊቶቹ ፡ ወሬ ፡ መጣልህን ?
18 የፈርዖንና ፡ የሠሙድ ፤ (ወሬ) ።
19 በውነቱ ፡ እነዚያ ፡ የካዱት ፡ በማስተባበል ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።
20 አላህም ፡ በዙሪያቸው ፡ (በዕውቀቱ) ፡ ከባቢ ፡ ነው ።
21 ይልቁንም ፡ እርሱ ፡ የከበረ ፡ ቁርአን ፡ ነው ።
22 የተጠበቀ ፡ በኾነ ፡ ሰሌዳ ፡ ውስጥ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 86 ፡ አል-ጣሪቅ ። ክፍል ፡ 30 ።

86ኛ ፡ ሱረቱ፡ አል-ጣሪቅ ፤ (የሌሊት ፡ መጪው ፡ ምዕራፍ)። በመካ፡ የወረደች፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 17 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 በሰማዩ ፡ በሌሊት ፡ መጪውም ፡ እምላለሁ ፤
2 የሌሊት ፡ መጪውም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ምን ፡ አሳወቀህ ?
3 ጨለማን ፡ ቀዳጁ ፡ ኮከብ ፡ ነው ።
4 ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ጠባቂ ፡ ያለባት ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይደለችም ።
5 ሰውም ፡ ከምን ፡ እንደተፈጠረ ፡ ይመልከት ።
6 ከተስፈንጣሪ ፡ ውሃ ፡ ተፈጠረ ።
7 ከጀርባና ፡ ከእርግብግብቶች ፡ መካከል ፡ የሚወጣ ፡ ከኾነ ፡ (ውሃ) ።
8 እርሱ ፡ (አላህ) ፡ በመመለሱ ፡

ላይ ፡ በእርግጥ ፡ ቻይ ፡ ነው ።
9 ምስጢሮች ፡ በሚገለጡበት ፡
ቀን ።
10 ለርሱም ፡ (ለሰው) ፡ ኀይልና ፡
ረዳት ፡ ምንም ፡ የለውም ።
11 የመመለስ ፡ ባለቤት ፡ በኾነችው፡
ሰማይም ፡ (1) እምላለሁ ።
12 (በበቃይ) ፡ የመሰንጠቅ ፡ ባለ
ቤት ፡ በኾነችው ፡ ምድርም ፤
13 እርሱ ፡ (እውነትን ፡ ከውሸት) ፡
የሚለይ ፡ ቃል ፡ ነው ።
14 እርሱም ፡ ቀልድ ፡ አይደለም ።
15 እነሱ ፡ በርግጥ ፡ ተንኰልን ፡ ይሠ
ራሉ ።
16 (እኔ) ፡ ተንኰልንም ፡ እመልሳ
ለሁ ፤
17 ከሓዲዎችንም ፡ ቀን ፡ ስጣቸው ፤
ጥቂትን ፡ ጊዜ ፡ አቆያቸው ።

1 ዝናምን ፡ ወይም ፡ ፀሐይንና ፡ ከዋክብትን ፡ የምትመላልስ ፡

## ምዕራፍ ፡ 87 ፡ አል-አዕላ ። ክፍል ፡ 30።

87ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-አዕላ ፤ (የበላይ ፡ አሸናፊው ፡ ምዕራፍ) ።
በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 19 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 ከሁሉ ፡ በላይ ፡ የኾነውን ፡ ጌታ
ህን ፡ ስም ፡ አጥራ ፤
2 የዚያን ፡ (ሁሉን ፡ ነገር) ፡ የፈ
ጠረውን ፡ ያስተካከለውንም ፤
3 የዚያንም ፡ የወሰነውን ፡ (ለተፈ
ጠረለት ፡ ነገር) ፡ የመራውንም ፤
4 የዚያንም ፡ ግጦሽን ፡ (ለምለም ፡
አድርጎ) ፡ ያወጣውን ፤
5 (ከዚያ) ፡ ደረቅ ፡ ጥቁር ፡ ያደረገ
ውንም ፡ (አምላክ ፡ ስም ፡ አጥ
ራ) ።
6 (ቁርአንን) ፡ በእርግጥ ፡ እናስነ
ብብሃለን ፤ አትረሳምም ፤
7 አላህ ፡ ከሻው ፡ ነገር ፡ በስተቀር ።
እርሱ ፡ ግልጹን ፡ የሚሸሸገው
ንም ፡ ሁሉ ፡ ያውቃልና ።
8 ለገሪቱም ፡ (ሕግጋት) ፡ እንገጥ
ምሃለን ።
9 ግሣጼይቱ ፡ ብትጠቅም ፡ (ሰዎ
ችን) ፡ ገሥጽም ።
10 (አላህን) ፡ የሚፈራ ፡ ሰው ፡ በእ
ርግጥ ፡ ይገሠጻል ።
11 መናጢውም ፡ ይርቃታል ፤
12 ያ ፡ ታላቂቱን ፡ እሳት ፡ የሚገ
ባው ።
13 ከዚያም ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ አይ
ሞትም ፡ ሕያውም ፡ አይኾንም ።
14 የተጥራራ ፡ ሰው ፡ በእርግጥ ፡
ዳነ ፤
15 የጌታውንም ፡ ስም ፡ ያወሳና ፡
የሰገደ ።



16 ይልቁንም ፡ ቅርቢቱን ፡ ሕይ
ወት ፡ ትመርጣላችሁ፤
17 መጨረሻይቱ ፡ (ሕይወት) ፡ በ
ላጭ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ዘውታሪም ፡
ስትኾን ።
18 ይህ ፡ በፊተኞቹ ፡ መጻሕፍት ፡
ውስጥ ፡ ያለለ ፡ ነው ።
19 በኢብራሂምና ፡ በሙሳ ፡ ጽሑ
ፎች ፡ ውስጥ ።

## ምዕራፍ ፡ 88 ፡ አል-ጋሺያህ ፡ ክፍል ፡ 30።

88ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ጋሺያህ ፤ (የሸፋኝቱ ፡ ምዕራፍ) ። በ
መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 26 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 የሸፋኝቱ ፡ (1) (ትንሣኤ) ፡ ወሬ ፡
መጣህን ?
2 ፊቶች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ተዋራጆች፡
ናቸው ፤
3 ሠሪዎች ፡ ለፊዎች ፡ ናቸው ።
4 ተኳሳን ፡ እሳት ፡ ይገባሉ ፤
5 በጣም ፡ ከፈላች ፡ ምንጭ ፡ ይጋ
ታሉ ፤
6 ለነሱ ፡ ዶሪዕ ፡ ከሚባል ፡ (እሾ
ሃም) ፡ ዛፍ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ ምግብ ፡
የላቸውም ፤
7 የማያሰባ ፡ ከረኃብም ፡ የማያብ
ቃቃ ፡ ከኾነው ።
8 ፊቶች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ተቀማጣ
ዮች ፡ ናቸው ፤
9 ለሥራቸው ፡ ተደሳቾች ፡ ናቸው ፤
10 በከፍተኛ ፡ ገነት ፡ ውስጥ ፡ ናቸው
11 በውስጧ ፡ ውድቅን ፡ ነገር ፡
አይሰሙም ።
12 በውስጧ ፡ ፈሳሾች ፡ ምንጮች ፡
አልሉ ።
13 በውስጧ ፡ ከፍ ፡ የተደረጉ ፡ አል
ጋዎች ፡ አልሉ ።
14 በተርታ ፡ የተኖሩ ፡ ብርጭቆዎችም ፤
15 የተደረደሩ ፡ መከዳዎችም ፤
16 የተነጠፉ ፡ ስጋጃዎችም ፡ (አልሉ) ።
17 (ከሓዲዎች) ፡ አይመለከቱምን ?
ወደ ፡ ግመል ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡
ተፈጠረች !
18 ወደ ፡ ሰማይም ፡ እንዴት ፡ ከፍ ፡
እንደ ፡ ተደረገች !
19 ወደ ፡ ተራራዎችም ፡ እንዴት ፡
እንደ ፡ ተቸከሉ !
20 ወደ ፡ ምድርም ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡
ተዘረጋች ፡ (አይመለከቱምን ?)
21 አስታውስም ፤ አንተ ፡ አስታዋሽ፡
ብቻ ፡ ነህና ።
22 በነሱ ፡ ላይ ፡ ተቈጣጣሪ ፡ (አስገዳጅ)፡
አይደለህም ፤

1 በድንጋጤና ፡ በጭንቀት ፡ ሁሉን ፡ የምት ሸፍነው ።

23 ግን ፡ (ከውነት) ፡ የዞረና ፡ የካደ ፡
ሰው ፤
24 አላህ ፡ ታላቁን ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣ
ዋል ።
25 መመለሻቸው ፡ ወደኛ ፡ ብቻ ፡
ነው ።
26 ከዚያም ፡ ምርመራቸው ፡ በኛ ፡
ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 89 ፡ አል-ፈጅር ። ክፍል ፡ 30 ።

89ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ፈጅር ፡ (የጎህ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 30 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 በጎህ ፡ እምላለሁ ፤
2 በዐሥር ፡ ሌሊቶችም ፤
3 በጥንዱም ፡ በነጠላውም ፤
4 በሌሊቱም ፡ በሚኼድ ፡ ጊዜ ፤
5 በዚህ ፡ (መሐላ) ፡ ለባለ ፡ አእ
ምሮ ፡ ታላቅ ፡ መሐላ ፡ አለበትን?
6 ጌታህ ፡ በዓድ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡
ሠራ ፡ አታውቅምን ?
7 በኢረም ፡ በባለ ፡ ረዣዥሚቱ ፡
አዕማድ ፤
8 በዚያች ፡ ብጤዋ ፡ በአገሮች ፡
ውስጥ ፡ ያልተፈጠረ ፡ በኾነችው ፤
9 በሠሙድም ፡ በነዚያ ፡ በሸለቆው
ቋጥኝን ፡ የቆረጡ ፡ በኾኑት ፤
10 በፈርዖንም ፡ ባለ ፡ ችካሎች ፡
በኾነው ፡
11 በነዚያ ፡ በአገሮች ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡
የሠሩ ፡
12 በርሷም ፡ ውስጥ ፡ ጥፋትን ፡ ያ
በዙ ፡ በኾኑት ፡ (እንዴት ፡ እን
ደሠራ ፡ አታውቅምን ?)
13 በነሱ ፡ ላይም ፡ ጌታህ ፡ የቅጣ
ትን ፡ አለንጋ ፡ አወረደባቸው ።
14 ጌታህ ፡ በመጠባበቂያ ፡ ላይ ፡
ነውና ።
15 ሰውማ ፡ ጌታው ፡ በሞከረው ፡
ጊዜ ፡ ባከበረውና ፡ ባጣቀመ
ውም ፡ (ጊዜ) ፡ ጌታዬ ፡ አከበ
ረኝ ፡ (አበለጠኝ) ፡ ይላል ።
16 በሞከረውና ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ሲሳ
ዩን ፡ ባጠበበ ፡ ጊዜማ ፡ ጌታዬ ፡
አሳነሰኝ ፡ ይላል ።
17 ይከልከል ፤ ይልቁንም ፡ የቲምን ፡
አታከብሩም ፤
18 ድኻንም ፡ በማብላት ፡ ላይ ፡ አት
ተዛዘዙም ፤
19 የውርስንም ፡ ገንዘብ ፡ የመሰብ
ሰብን ፡ አበላል ፡ ትበላላችሁ ፤
20 ገንዘብንም ፡ ብዙን ፡ መውደድ ፡
ትወዳላችሁ ።
21 ተዉ ፤ ምድር ፡ ደጋግማ ፡ በተሰ
ባበረች ፡ ጊዜ ፤
22 መላእክትም ፡ ሠልፍ ፡ ሠልፍ ፡
ኾነው ፡ ጌታህ ፡ (ትእዛዙ) ፡ በ
መጣ ፡ ጊዜ ፤



23 ገሀነምም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ በተ
መጣች ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡
ሰው ፡ (ጥፋቱን) ፡ ይገነዘባል ፤
መገንዘብም ፡ ለርሱ ፡ ከየት ? (1)
24 ዋ ፡ እኔ ! ምነው ፡ በሕይወቴ ፡
(መልካምን ፡ ሥራ) ፡ ባስቀደ
ምኩ ፡ ኖሮ ፡ ይላል ።
25 በዚያ ፡ ቀንም ፡ የርሱን ፡ አቀጣጥ ፡
አንድም ፡ አይቀጣም ።
26 የርሱንም ፡ አስተሳሠር ፡ አን
ድም ፡ አያሥርም ፤
27 (ለአመነች ፡ ነፍስም) ፡ አንቺ ፡
የረካሺው ፡ ነፍስ ፡ ሆይ !
28 ወዳጅ ፡ ተወዳጅ ፡ ኾነሽ ፡ ወደ ፡
ጌታሽ ፡ ተመለሺ ።
29 በባሮቼም ፡ ውስጥ ፡ ግቢ ፡
30 ገነቴንም ፡ ግቢ ፤ (ትባላለች) ።

1 ከየት ፡ ይጠቅመዋል ።

## ምዕራፍ ፡ 90 ፡ አል-በለድ ። ክፍል ፡ 30 ።

90ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-በለድ ፤ (የሀገር ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 20 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 በዚህ ፡ አገር ፡ (በመካ) ፡ እምላ
ላለሁ ፤
2 አንተ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ሰፋሪ ፡
ስትኾን ፤
3 በወላጂም ፡ በወለዳቸውም ፡ ሰ
ዎች ፡ (በአዳምና ፡ በዘሮቹ ፡ ሁሉ ፡
እምላለሁ) ፤
4 ሰውን ፡ ሁሉ ፡ በእርግጥ ፡ በል
ፋት ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ፈጠርነው ፤
(1)
5 በርሱ ፡ ላይ ፡ አንድም ፡ የማይ
ችል ፡ መኾኑን ፡ ይጠረጥራልን ?
6 ብዙን ፡ ገንዘብ ፡ አጠፋሁ ፡
ይላል ፤
7 አንድም ፡ ያላየው ፡ መኾኑን ፡
ያስባልን ?
8 ለርሱ ፡ ሁለት ፡ ዓይኖችን ፡ አላደ
ረግንለትምን ?
9 ምላስንና ፡ ሁለት ፡ ከንፈሮችንም ፤
10 ሁለትን ፡ መንገዶችም ፡ (1)፣ አል
መራነውምን ?
11 ዓቀበቲቱንም ፡ አልወጣም ።
12 ዓቀበቲቱም ፡ (መውጣቷ) ፡ ምን
እንደኾነች ፡ ምን ፡ አሳወቀህ ?
13 (እርሱ) ፡ ጫንቃን ፡ መልቀቅ ፡
ነው ።
14 ወይም ፡ የረኃብ ፡ ባለቤት ፡ በኾነ ፡
ቀን ፡ ማብላት ፤
15 የዝምድና ፡ ባለቤት ፡ የኾነን ፡
የቲም ፤

1 ልፋት ፡ ምንጊዜም ፡ አይለየውም ።

1 የደግና ፡ የክፉን ፡ ወይም ፡ የናቱን ፡ ሁለት ፡
ጡቶች ።

16 ወይም ፡ የዐፈር ፡ ባለቤት ፡ የኾ
ነን ፡ ድኻ ፡ (1) (ማብላት ፡ ነው) ።

17 (ዐቀበቲቱን፡ አልወጣም)፡ ከዚያም፡
ከነዚያ፡ ከአመኑትና፡ በመታገሥ፡
አደራ፡ ከተባባሉት፥ በማዘንም፡ አደ
ራ፡ ከተባባሉት፡ ሰዎች፡ አልኾነም።

1 የሚያነጥፈው ፡ አጥቶ ፡ ዐፈር ፡ ላይ ፡ የሚ ተኛን ፡ ድኻ ።

18 እነዚያ ፡ (ይህንን ፡ የፈጸሙ) ፡
የቀኝ ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ።

19 እነዚያም ፡ በአንቀጾቻችን፡ የካ
ዱት ፡ እነሱ ፡ የግራ ፡ ጓዶች ፡
ናቸው ።

20 በነሱ ፡ ላይ ፡ የተዘጋች ፡ እሳት ፡
አለለች ።

## ምዕራፍ ፡ 91 ፡ አል-ሸምስ ። ክፍል ፡ 30 ።

91ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሸምስ ፤ (የፀሐይ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 15 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።

1 በፀሐይና ፡ በብርሃኗ ፡ እምላለሁ ።

2 በጨረቃውም ፡ በተከተላት ፡
ጊዜ ፤

3 በቀኑም ፡ (ፀሐይን) ፡ በገለጻት ፡
ጊዜ ፤

4 በሌሊቱም ፡ በሸፈናት ፡ ጊዜ ፤

5 በሰማይቱም ፡ በገነባትም ፡ (ጌታ) ፤

6 በምድሪቱም ፡ በዘረጋትም ፤

7 በነፍስም ፡ ባስተካከላትም ፤

8 አመጥዋንና ፡ ፍርሃትዋንም ፡ ባሳ
ወቃት ፡ (አምላክ ፡ እምላለሁ) ፤

9 (ከኀጢአት) ፡ ያጠራት ፡ ሰው ፡
ፍላጎቱን ፡ በእርግጥ ፡ አገኘ ።

10 (በኀጢአት) ፡ የሸፈናትም ፡ ሰው ፡
በውነት ፡ አፈረ ።

11 ሠሙድ ፡ ወሰን ፡ በማለፍዋ ፡ አስ
ተባበለች ፤

12 ጠማማዋ ፡ በተንቀሳቀሰ ፡ ጊዜ ።

13 ለነሱም ፡ የአላህ ፡ መልክተኛ ፡
(ሷሊህ) ፡ የአላህን ፡ ግመል ፡ የመ
ጠጥ ፡ ተራዋንም ፡ (ተጠንቀቁ) ፡
አላቸው ።

14 አስተባበሉትም ፤ (ቋንጃዋን) ፡
ወጓትም ፤ በኀጢአታቸውም ፡
ምክንያት ፡ ጌታቸው ፡ (ቅጣትን) ፡
በነሱ ፡ ላይ ፡ ደመደመባቸው ፤
አስተካከላትም ።

15 ፍጻሜዋንም ፡ (የምታስከትለውን) ፡
አይፈራም ።



92ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ለይል ፤ (የሌሊት ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 21 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ሀም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።

1 በሌሊቱ ፡ እምላለሁ ፡ (በጨለ
ማው) ፡ በሚሸፍን ፡ ጊዜ ፤

2 በቀኑም ፤ በተገለጸ ፡ ጊዜ ።

3 ወንድንና ፡ ሴትን ፡ በፈጠረውም ፡
(አምላክ ፡ እምላለሁ) ፤

4 ሥራችሁ ፡ በእርግጥ ፡ የተለያየ ፡
ነው ።

5 የሰጠ ፡ ሰውማ ፡ ጌታውን ፡ የፈ
ራም ፤

6 በመልካሚቱም ፡ (እምነት) ፡ ያረ
ጋገጠ ፤

7 ለገሪቱ ፡ ሥራ ፡ እናዘጋጀዋለን ።

8 የሰሰተ ፡ ሰውማ ፡ የተብቃቃም ፤
(በራሱ ፡ የተመካ) ፤

9 በመልካሚቱ ፡ (እምነት) ፡ ያስተ
ባበለም ፤

10 ለክፉይቱ ፡ ሥራ ፡ እናዘጋጀዋ
ለን ።

11 በወደቀም ፡ ጊዜ ፡ ገንዘቡ ፡ ከርሱ ፡
ምንም ፡ አይጠቅመውም ።

12 ቅኑን ፡ መንገድ ፡ መግለጽ ፡ በኛ ፡
ላይ ፡ አለብን ።

13 መጨረሻይቱም ፡ መጀመሪያይ
ቱም ፡ ዓለም ፡ የኛ ፡ ናቸው ።

14 የምትንቀለቀልንም ፡ እሳት ፡ አስ
ጠነቀቅኋችሁ ፡ (በላቸው) ።

15 ከጠማማ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የማይ
ገባት ፡ የኾነችን ፤

16 ያ ፡ ያስተባበለና ፡ ከትእዛዝ ፡
የሸሸው ።

17 አላህን ፡ በጣም ፡ ፈሪውም ፡
በእርግጥ ፡ ይርቃታል ።

18 ያ ፡ የሚጥራራ ፡ ኾኖ ፡ ገንዘቡን ፡
(ለድኾች) ፡ የሚሰጠው ።

19 ለአንድም ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡
የምትመለስ ፡ ውለታ ፡ የለችም ።
(1)

20 ግን ፡ የታላቅ ፡ ጌታውን ፡ ውዴታ ፡
ለመፈለግ ፡ (ይህንን ፡ ሠራ) ።

21 ወደፊትም ፡ በእርግጥ ፡ ይደሰ
ታል ።

1 የሚለግሰው ፡ ለአላህ ፡ ውዴታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ውለታ ፡ ለመመለስ ፡ ወይም ፡ ለመ ፈለግ ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 93 ፡ አል-ዱሓ ። ክፍል ፡ 30 ።

93ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ዱሓ ፤ (የረፋድ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 11 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 በረፋዱ ፡ እምላለሁ ፤

2 በሌሊቱም ፡ ጸጥ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፤

3 ጌታህ ፡ አላሰናበተህም ፤ አልጠላህምም ።

4 መጨረሻይቱም ፡ (ዓለም) ፡ ከመጀመሪያይቱ ፡ ይልቅ ፡ ላንተ ፡ በላጭ ፡ ናት ።

5 ጌታህም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ (ብዙን ፡ ስጦታ) ፡ በእርግጥ ፡ ይሰጥሃል ፤ ትደሰታለህም ።

6 የቲም ፡ ኾነህ ፡ አላገኘህምና ፡ አላስጠጋህምን ? (አስጠግቶሃል) ።

7 የሳትክም ፡ ኾነህ ፡ አገኘህ ፤ መራህም ።

8 ድኻም ፡ ኾነህ ፡ አገኘህ ፤ አከበረህም ።

9 የቲምንማ ፡ አትጨቁን ።

10 ለማኝንም ፡ አትገላምጥ ።

11 በጌታህም ፡ ጸጋ ፡ አውራ ፤ (ግለጸት) ።

## ምዕራፍ ፡ 94 ፡ አል-ኢንሽራሕ ። ክፍል ፡ 30 ።

94ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ኢንሽራሕ ፤ (የልብ ፡ መስፋት ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 8 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 ልብህን ፡ ለአንተ ፡ አላሰፋንልህምን ? (አስፍተንልሃል) ።

2 ሸክምህንም ፡ ካንተ ፡ አውርደንልሃል ።

3 ያንን ፡ ጀርባህን ፡ ያከበደውን ፡ (ሸክም) ።

4 መወሳትህንም ፡ ላንተ ፡ ከፍ ፡ አድርገንልሃል ።

5 ከችግርም ፡ ጋር ፡ ምቾት ፡ አልለ ።

6 ከችግር ፡ ጋር ፡ በእርግጥ ፡ ምቾት ፡ አልለ ።

7 በጨረስክም ፡ ጊዜ ፡ ልፋ ። (ቀጥል) ።

8 ወደ ፡ ጌታህም ፡ ብቻ ፡ ከጅል ፤

## ምዕራፍ ፡ 95 ፡ አል-ቲን ። ክፍል ፡ 30 ። 

95ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ቲን ፤ (የበለስ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 8 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 በበለስና ፡ በዘይት ፡ ወይራ ፡ እምላለሁ ፤

2 በሲኒን ፡ ተራራም ፤

3 በዚህ ፡ በጸጥተኛው ፡ አገርም ፡ (እምላለሁ) ።

4 ሰውን ፡ በጣም ፡ በአማረ ፡ አቋም ፡ ላይ ፡ ፈጠርነው ።

5 ከዚያም ፡ (ከፊሉን) ፡ ከዝቅተኞች ፡ ሁሉ ፡ በታች ፡ አድርገን ፡ መለስነው ።

6 ግን ፡ እነዚያ ፡ ያመኑት ፡ መልካሞችንም ፡ የሠሩት ፡ ለነሱ ፡ ተቆራጭ ፡ ያልኾነ ፡ ምንዳ ፡ አላቸው ።

7 ታዲያ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በፍርዱ ፡ ምን ፡ አስተባባይ ፡ አደረገህ ?

8 አላህ ፡ ከፈራጆች ፡ ሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ፈራጅ ፡ አይደለምን ? (ነው) ።

## ምዕራፍ ፡ 96 ፡ አል-ዐለቅ ። ክፍል ፡ 30 ።

96ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ዐለቅ ፤ (የረጋ ፡ ደም ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 19 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 አንብብ ፡ በዚያ ፡ (ሁሉን) ፡ በፈጠረው ፡ ጌታህ ፡ ስም ።

2 ሰውን ፡ ከረጋ ፡ ደም ፡ በፈጠረው ፡ (ጌታህ ፡ ስም) ።

3 አንብብ ፤ ጌታህ ፡ በጣም ፡ ቸር ፡ ሲኾን ፤

4 ያ ፡ በብርዕ ፡ ያስተማረ ፤

5 ሰውን ፡ ያላወቀውን ፡ ሁሉ ፡ ያሳወቀ ፡ ሲኾን ።

6 በውነቱ ፡ ሰው ፡ ወሰንን ፡ ያልፋል ፤

7 ራሱን ፡ የተብቃቃ ፡ (ባለ ፡ ሀብት) ኾኖ ፡ ለማየቱ ።

8 መመለሻው ፡ ወደ ፡ ጌታህ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

9 አየህን ? ያንን ፡ የሚከለክለውን ፡

10 ባሪያን ፡ በሰገደ ፡ ጊዜ ፤

11 አየህን ? ንገረኝ ፡ (ተከልካዩ) ፡ በትክክለኛ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ቢኾን ፡

12 ወይም ፡ (ፈጣሪውን) ፡ በመናራት ፡ ቢያዝ ፤

13 አየህን ? ንገረኝ ፡ (ከልካዩ) ፡ ቢያስተባብልና ፡ (ከእምነት) ፡ ቢሸሽ ፤

14 አላህ ፡ የሚያይ ፡ መኾኑን ፡ አያውቅምን ?

15 ይተው ፡ ባይከለከል ፡ አናቱን ፡ ይዘን ፡ እንጎትተዋለን ።

16 ውሸታም ፡ ስሕተተኛ ፡ የኾነችውን ፡ አናቱን ።

17 ሸንጎውንም ፡ ይጥራ ፤

18 (እኛም) ፡ ዘበኞቻችንን ፡ እንጠራለን ።

19 ይከልክል ፤ አትታዘዘው ፤ ስገድም ፤ (ወደ ፡ አላህ) ፡ ተቃረብም ።

## ምዕራፍ ፡ 97 ፡ አል-ቀድር ። ክፍል ፡ 30 ።

97ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ቀድር ፤ (የውሳኔ ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 5 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 እኛ ፡ (ቁርአኑን) ፡ በመወሰኛይቱ ፡ ሌሊት ፡ (1) ፡ አወረድነው ።

2 መወሰኛይቱም ፡ ሌሊት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ምን ፡ አሳወቀህ ?

3 መወሰኛይቱ ፡ ሌሊት ፡ ከሺሕ ፡ ወር ፡ በላጭ ፡ ናት ።

4 በርሷ ፡ ውስጥ ፡ መላእክትና ፡ መንፈሱ ፡ በጌታቸው ፡ ፈቃድ ፡ በነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ይወርዳሉ ።

5 እርስዋ ፡ እስከ ፡ ጎህ ፡ መውጣት ፡ ድረስ ፡ ሰላም ፡ ብቻ ፡ ናት ።

1 የመወሰኛ ፡ ሌሊት ፡ ወይም ፡ የከበረች ፡ ሌሊት ፡ ትባላለች ።

## ምዕራፍ ፡ 98 ፡ አል-በይናህ ። ክፍል ፡ 30 ።

98ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-በይናህ ፤ (የግልጽ ፡ አስረጅ ፡ ምዕራፍ) ። በመዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 8 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 እነዚያ ፡ ከመጽሐፉ ፡ ባለቤቶች ፡ ከአጋሪዎቹም ፡ የካዱት ፡ ግልጹ ፡ አስረጅ ፡ እስከ ፡ መጣላቸው ፡ ድረስ ፡ (ከነበሩበት ፡ ላይ) ፡ ተወጋጆች ፡ አልነበሩም ።



2 (አስረጁም) ፡ ከአላህ ፡ የኾነ ፡ መልክተኛ ፡ የተጥራሩን ፡ መጽሐፎች ፡ የሚያነብ ፡ ነው ።

3 በውስጧ ፡ ቀጥተኛ ፡ የኾኑ ፡ ጽሑፎች ፡ ያሉባት ፡ የኾነችን ።

4 እነዚያም ፡ መጽሐፉን ፡ የተሰጡት ፡ ሰዎች ፡ ግልጽ ፡ አስረጅ ፡ ከመጣላቸው ፡ በኋላ ፡ እንጅ ፡ አልተለያዩም ፤

5 አላህን ፡ ሃይማኖትን ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡ አጥሪዎች ፡ ቀጥተኞች ፡ ኾነው ፡ ሊገዙት ፡ ሶላትንም ፡ አስተካክለው ፡ ሊሰግዱ ፡ ዘካንም ፡ ሊሰጡ ፡ እንጅ ፡ ያልታዘዙ ፡ ሲኾኑ ፡ (ተለያዩ) ። ይህም ፡ የቀጥተኛይቱ ፡ (ሃይማኖት) ፡ ድንጋጌ ፡ ነው ።

6 እነዚያ ፡ ከመጽሐፉ ፡ ሰዎች ፡ የካዱት ፡ አጋሪዎቹም ፡ በገሀነም ፡ እሳት ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ፤ በውስጧ ፡ ዘውታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፤ እነዚያ ፡ እነሱ ፡ ከፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ክፉ ፡ ናቸው ።

7 እነዚያ ፡ ያመኑትና ፡ መልካሞችንም ፡ የሠሩት ፡ እነዚያ ፡ እነሱ ፡ ከፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በላጭ ፡ ናቸው ።

8 በጌታቸው ፡ ዘንድ ፡ ምንዳቸው ፡ ከሥሮቻቸው ፡ ወንዞች ፡ የሚፈሱባቸው ፡ የመኖሪያ ፡ ገነቶች ፡ ነው ፤ በውስጣቸው ፡ ዘለዓለም ፡ ዘውታሪዎች ፡ ሲኾኑ ፡ (ይገቡባቸዋል) ። አላህ ፡ ከነሱ ፡ወደደ ፤ ከርሱም ፡ ወደዱ ፤ ይህ ፡ ጌታውን ፡ ለፈራ ፡ ሰው ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ 99 ፡ አል-ዘልዘላህ ። ክፍል ፡ 30 ።

99ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ዘልዘላህ ፤ (የምድር ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ምዕራፍ) ። በመዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 8 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 ምድር ፡ (በኀይል) ፡ መንቀጥቀጥን ፡ በተንቀጠቀጠች ፡ ጊዜ ፤

2 ምድር ፡ ሸክሞችዋን ፡ ባወጣችም ፡ ጊዜ ፤

3 ሰውም ፡ ምን ፡ ኾነች ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፤

4 በዚያ ፡ ቀን ፡ ወሬዎችዋን ፡ ትናገራለች ፤

5 ጌታህ ፡ ለርሷ ፡ በማሳወቁ ፡ ምክንያት ።

6 በዚያ ፡ ቀን ፡ ሰዎች ፡ ሥራዎቻቸውን ፡ (ምንዳዋን) ፡ እንዲያዩ ፡ ይደረጉ ፡ ዘንድ ፡ (እንደየሥራቸው) ፡ የተለያዩ ፡ ኾነው ፡ (ከመቆሚያው ፡ ስፍራ) ፡ ይመለሳሉ ፤

7 የብናኝ ፡ ክብደት ፡ ያክልም ፡ መልካምን ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ያገኘዋል ።

8 የብናኝ ፡ ክብደት ፡ ያክልም ፡ ክፉን ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ያገኘዋል ።

100ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ዓዲያት ፡ (የሩዋጮች ፡ ምዕራፍ) ። በ
መካ ፡ የወረደችናት ፡ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 11 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 እያለከለኩ ፡ ሩዋጮች ፡ በኾኑት ፡
(ፈረሶች) ፡ እምላለሁ ።
2 (በሰኮናቸው) ፡ እያጋጩ ፡ እሳ
ትን ፡ አውጪዎች ፡ በኾኑትም ፤
3 በማለዳ ፡ ወራሪዎች ፡ በኾኑትም ።
4 በርሱ ፡ አቧራን ፡ በቀሰቀሱትም ፤
5 በ(ጠላት) ፡ ክቢ ፡ (1) መካከል ፡
በርሱ ፡ (በጧት) ፡ በተጋፈጡ
ትም ፡ እምላለሁ ።
6 ሰው ፡ ለጌታው ፡ ብርቱ ፡ ከሓዲ ፡ ነው ።
7 እርሱም ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ መስካሪ ፡
ነው ።
8 እርሱም ፡ ገንዘብን ፡ ለመውደድ ፡
በጣም ፡ ብርቱ ፡ ነው ።
9 (ሰው) ፡ አያውቅምን ? በመቃብ
ሮች ፡ ያሉት ፡ (ሙታን) ፡ በተ
ቀሰቀሱ ፡ ጊዜ ፤
10 በልቦች ፡ ውስጥ ፡ ያለውም ፡ ሁሉ ፡
በተገለጸ ፡ ጊዜ ፡ (እንዴት ፡ እን
ደሚኾን) ።
11 ጌታቸው ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ በነሱ ፡
(ነገር) ፡ በእርግጥ ፡ ውስጠ ፡
ዐዋቂ ፡ ነው ።

1 የጦር ፡ ሰራዊት ፡ ልዩ ፡ ሰፈር ።

## ምዕራፍ ፡ 101 ፡ አል-ቃሪዓህ ። ክፍል ፡ 30 ።

101ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ቃሪዓህ ፤ (የቆርቋሪይቱ ፡ ምዕራፍ) ። በ
መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 11 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፤ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 ቆርቋሪይቱ ፡ (ጩኸት) ፤
2 ምን ፡ አስደናቂ ፡ ቆርቋሪ ፡ ናት !
3 ቆርቋሪይቱም ፡ ምን ፡ እንደ ፡
ኾነች ፡ ምን ፡ አሳወቀህ ?
4 ሰዎች ፡ እንደ ፡ ተበታተነ ፡ ቢራ
ቢሮ ፡ (ወይም ፡ ኩብኩባ) ፡ (1)
በሚኾኑበት ፡ ቀን ፤
5 ጋራዎችም ፡ እንደ ፡ ተነደፈ ፡
ሱፍ ፡ በሚኾኑበት ፡ (ቀን ፡ ልበ
ችን ፡ በድንጋጤ ፡ ትቆረቁራለች።
6 ሚዛኖቹ ፡ የከበዱለት ፡ ሰውማ ፤
7 እርሱ ፡ በምትወደድ ፡ ኑሮ ፡
ውስጥ ፡ ይኾናል ።
8 ሚዛኖቹም ፡ የቀለሉበት ፡ ሰውማ ፤
9 መኖሪያው ፡ ሃዊያህ ፡ ናት ፡ (1)
10 እርሷም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡
ምን ፡ አሳወቀህ ?
11 (እርሷ) ፡ በጣም ፡ ተኳሳ ፡ እሳት ፡ ናት ።

1 ገና ፡ ያልበረረ ፡ ግልገል ፡ አንበጣ ።

1 ሃዊያህ ፡ አዘቅትዋ ፡ በጣም ፡ የራቀ ፡ የእ
ሳት ፡ ጉድጓድ ፡ ናት ።



102ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ተካሡር ፤ (በብዛት ፡ የመፎካከር ፡ ምዕራፍ) ።
በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 8 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።
1 በብዛት ፡ መፎካከር ፡ (ጌታች
ሁን ፡ ከመገዛት) ፡ አዘነጋችሁ ፤
2 መቃብሮችን ፡ እስከ ፡ ጐበኛችሁ ፡
ድረስ ።
3 ተከልከሉ ፤ ወደፊት ፡ (ውጤ
ቱን) ፡ ታውቃላችሁ ፤
4 ከዚያም ፡ ተከልከሉ ፤ ወደ ፡ ፊት ፡
ታውቃላችሁ ።
5 በውነቱ ፡ (የሚጠብቃችሁን) ፡
እርግጠኛ ፡ ዕውቀትን ፡ ብታውቁ ፡
ኖሮ ፤ (ባልዘናጋችሁ ፡ ነበር) ።
6 ገሀነምን ፡ በእርግጥ ፡ ታያላችሁ ።
7 ከዚያም ፡ እርግጠኛን ፡ ማየት ፡
ታዩዋታላችሁ ፤
8 ከዚያም ፡ ከድሎታችሁ ፡ ሁሉ ፡
በዚያ ፡ ቀን ፡ ትጠየቃላችሁ ።

## ምዕራፍ ፡ 103 አል-ዐስር ። ክፍል ፡ 30 ።

103ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ዐስር ፤ (የጊዜያት ፡ ምዕራፍ) ። በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 3 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 በጊዜያቱ ፡ እምላለሁ ፤
2 ሰው ፡ ሁሉ ፡ በእርግጥ ፡ በከሳራ ፡
ውስጥ ፡ ነው ።
3 እነዚያ ፡ ያመኑትና ፡ መልካሞ
ችን፡ የሠሩት፥ በውነትም፡ አደራ፡
የተባባሉት፥ በመታገሥም፡ አደ
ራ፡ የተባባሉት፡ ብቻ፡ ሲቀሩ።

## ምዕራፍ 104 ፡ አል-ሁምዛህ ፡ ክፍል ፡ 30 ፡፡

104ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ሁመዛህ ፤ (የአሚተኛ ፡ ምዕራፍ) ፡፡ በ
መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 9 ፡ ናቸው ፡፡

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ፡፡
1 ለአሚተኛ ፡ ለዘላፊ ፡ ሁሉ ፡ ወዮ
ለት ፡፡
2 ለዚያ ፡ ገንዘብን ፡ የሰበሰበና ፡
የቆጣጠረው ፡ (ያደለበውም) ፡
ለኾነ ፤ (ወዮለት) ፡፡
3 ገንዘቡ ፡ የሚያዘወትረው ፡ መኾ
ኑን ፡ ያስባል ፡፡
4 ይከልከል ፤ በሰባሪይቱ ፡ (እሳት) ፡
ውስጥ ፡ በእርግጥ ፡ ይጣላል ፡፡
5 ሰባሪይቱም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡
ምን ፡ አሳወቀህ ?
6 የተነደደችው ፡ የአላህ ፡ እሳት ፡ ናት ፡፡
7 ያቺ ፡ በልቦች ፡ ላይ ፡ የምትዘ
ልቅ ፡ የኾነችው ፡፡
8 እርሷ ፡ በእርግጥ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡
የተዘጋች ፡ ናት ፡፡
9 በተዘረጋች ፡ አዕማድ ፡ ውስጥ ፤
(የተዘጋች ፡ ናት) ፡፡

## ምዕራፍ 105 ፡ አል-ፊል ፡፡ ክፍል ፡ 30 ፡፡

105ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ፊል ፤ (የዝሆን ፡ ምዕራፍ) ፡፡ በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 5 ፡ ናቸው ፡፡

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ፡፡
1 በዝሆኑ ፡ ባለቤቶች ፡ ጌታህ ፡ እን
ዴት ፡ እንደሠራ ፡ አላወቅህምን ?
2 ተንኮላቸውን ፡ በጥፋት ፡ ውስጥ ፡
(ከንቱ) ፡ አላደረገምን ? (አድር
ጓል) ፡፡
3 በነሱም ፡ ላይ ፡ መንጋዎች ፡ የኾ
ኑን ፡ ወፎች ፡ ላከ ፡፡
4 ከተጠበሰ ፡ ጭቃ ፡ በኾነ ፡ ደን
ጊያ ፡ የምትወረውርባቸው ፡ የኾ
ነችን ፤ (አዕዋፍ) ፡፡
5 ቅጠሉ ፡ እንደ ፡ ተበላ ፡ አዝመ
ራም ፡ አደረጋቸው ፡፡



## ምዕራፍ ፡ 106 ፡ ቁረይሽ ፡፡ ክፍል ፡ 30 ፡፡

106ኛ ፡ ሱረቱ ፡ ቁረይሽ ፤ (የቁረይሾች ፡ ምዕራፍ) ፡፡ በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 4 ፡ ናቸው ፡፡

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ፡፡
1 ቁረይሽን ፡ ለማላመድ ፡ (ባለዝ
ሆኖቹን ፡ አጠፋ) ፡፡
2 የብርድንና ፡ የበጋን ፡ ወራት ፡
ጉዞ ፡ ሊያላምዳቸው ፡ (1) (ይህ
ንን ፡ ሠራ) ፡፡
3 ስለዚህ ፡ የዚህን ፡ ቤት ፡ (የከዕ
ባን) ፡ ጌታ ፡ ይግገዙ ፡፡
4 ያንን ፡ ከረኃብ ፡ ያበላቸውን ፡
ከፍርሃትም ፡ ያረካቸውን ፡ (ጌታ ፡
ያምልኩ) ፡፡

1 በብርድ ፡ ወራት ፡ ወደ ፡ የመን ፡ በበጋ ፡ ወራት ፡ ወደ ፡ ሻም ፡ ለንግድ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ጉዞ ፡ ሊያላምዳቸው ፡፡

## ምዕራፍ ፡ 107 ፡ አል-ማዑን ፡፡ ክፍል ፡ 30 ፡

107ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ማዑን ፤ (የዕቃ ፡ ትውስት ፡ ምዕራፍ) ፡፡
በመካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 7 ፡ ናቸው ፡፡

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ፡፡
1 ያንን ፡ በምርመራው ፡ የሚያስተ
ባብለውን ፡ አየህን ? (ዐወቅከ
ውን ?)
2 ይህም ፡ ያ ፡ የቲምን ፡ በኀይል ፡
የሚገፈትረው ፤
3 ድኻንም ፡ በማብላት ፡ ላይ ፡ የማ
ያግባባው ፡ ሰው ፡ ነው ፡፡
4 ወዮላቸው ፡ ለሰጋጆች ፤
5 ለነዚያ ፡ እነሱ ፡ ከሰግዳታቸው ፡
ዘንጊዎች ፡ ለኾኑት ፤ (ሰጋጆች) ፡፡
6 ለነዚያ ፡ እነሱ ፡ ይውልኝ ፡
ባዮች ፡ ለኾኑት ፤
7 የዕቃ ፡ ትውስትንም ፡ (ሰዎችን) ፡
የሚከለክሉ ፡ ለኾኑት ፡ (ወዮ
ላቸው) ፡፡

108ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ከውሠር ፤ (የበጎ ፡ ነገሮች ፡ ምዕራፍ) ። በ መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 3 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ ነው ።

1 እኛ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ በጎ ፡ ነገሮ ችን ፡ ሰጠንህ ።

2 ስለዚህ፡ለጌታህ፡ስገድ ፤ (በስሙ)፡ ሠዋም ።

3 ጠይህ ፡ (የሚጠላህ) ፡ እርሱ ፡ በእርግጥ ፡ (ዘሩ) ፡ የተቆረጠው ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ 109፡ አል-ካፊሩን ። ክፍል ፡ 30 ።

109ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ካፊሩን ፤ (የከሓዲዎች ፡ ምዕራፍ) ። በ መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 6 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ፡ በጣም ፡ አዛኝ፡ በሆነው ።

1 በላቸው ፡—እላንተ ፡ ከሓዲዎች ፡ ሆይ ፡

2 ያንን ፡ የምትግገዙትን ፡ (ጣዖት ፡ አሁን) ፡ አልግገዛም ።

3 እናንተም ፡ እኔ ፡ የምግገዛውን ፡ (አምላክም፡ አሁን)፡ ተገገርዎች፡ አይደላችሁም ።

4 እኔም ፡ ያንን ፡ የተገዛችሁትን ፡ (ወደፊት) ፡ ተገገር ፡ አይደለሁም።

5 እናንተም ፡ እኔ ፡ የምግገዛውን ፡ (ወደፊት) ፡ ተገገርዎች ፡ አይደላ ችሁም ።

6 ለናንተ ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ አላ ችሁ ፤ ለኔም ፡ ሃይማኖቴ ፡ አለኝ ።



110ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ነስር ፤ (የእርዳታ ፡ ምዕራፍ) ። በመዲና ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ ፫ ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፤ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ ነው ።

1 የአላህ፡ እርዳታና፡ (መካን)፡ መክ ፈት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤

2 ሰዎችንም ፡ ጭፍሮች ፡ እየኾኑ ፤ በአላህ ፡ ሃይማኖት ፡ ውስጥ ፡ ሲገቡ ፡ ባየህ ፡ ጊዜ ፤

3 ጌታህን ፡ ከማመስገን ፡ ጋር ፡ አጥ ራው ፤ ምሕረትንም ፡ ለምነው ፤ እርሱ ፡ ጸጸትን ፡ በጣም ፡ ተቀ ባይ ፡ ነውና ።

ምዕራፍ ፡ 111 ፡ አል-ለሀብ ። ክፍል ፡ 30 ።

111ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ለሀብ ፤ (የመንቀልቀል ፡ ምዕራፍ) ። በ መካ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 5 ፡ ናቸው ።

በአላህ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ ነው ።

1 የአቡ ፡ ለሀብ ፡ ሁለት ፡ እጆች ፡ ከሰሩ ፡ (ጠፉ ፤ እርሱ) ፡ ከሰረም ።

2 ከርሱ ፡ ገንዘቡና ፡ ያም ፡ ያፈ ራው ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ አልጠቀ መውም ።

3 የመንቀልቀል ፡ ባለቤት ፡ የኾነ ችን ፡ እሳት ፡ በእርግጥ ፡ ይገባል ።

4 ሚስቱም ፡ (ትገባለች) ፤ እንጨት፡ ተሸካሚ ፡ ስትኾን ፤

5 በአንገትዋ ፡ ላይ ፡ ከጭረት ፡ የኾነ ፡ ገመድ ፡ ያለባት ፡ ስት ኾን ።

112ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ኢኽላስ ፤ (የፍጹምነት ፡ ምዕራፍ) ። በ
መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 4 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 በል ፡-እርሱ ፡ አላህ ፡ አንድ ፡
ነው ።
2 አላህ ፡ (የሁሉ) ፡ መጠጊያ ፡ ነው ።
3 አልወለደም ፤ አልተወለደምም ።
4 ለርሱም ፡ አንድም ፡ ብጤ ፡ የለ
ውም ።

## ምዕራፍ ፡ 113 ፡ አል-ፈለቅ ። ክፍል ፡ 30 ፡

113ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ፈለቅ ፤ (የተፈልቃቂው ፡ ምዕራፍ) ። በ
መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 5 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 በል ፡—በተፈልቃቂው ፡ ጐህ ፡
ጌታ ፡ እጠበቃለሁ ፤
2 ከፈጠረው ፡ ፍጡር ፡ ሁሉ ፡
ክፋት ።
3 ከሌሊትም ፡ ክፋት ፡ ባጨለመ ፡
ጊዜ ፤
4 በተቋጠሩ ፡ (ክሮች) ፡ ላይ ፡ ተፊ
ዎች ፡ ከኾኑት ፡ (ደጋሚ) ፡ ሴቶ
ችም ፡ ክፋት ፤
5 ከምቀኛም ፡ ክፋት ፡ በተመቀኘ ፡
ጊዜ ፤ (እጠበቃለሁ ፡ በል) ።



114ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ናስ ፤ (የሰዎች ፡ ምዕራፍ) ፤ በመካ ፡
የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 6 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆ
ነው ።
1 በል ፡—በሰዎች ፡ ፈጣሪ ፡ እጠ
በቃለሁ ።
2 የሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ንጉሥ ፡ በኾ
ነው ፤
3 የሰዎች ፡ አምላክ ፡ በኾነው ።
4 ብቅ ፡ እልም ፡ ባይ ፡ ከኾነው ፡
ጐትጓች ፡ (ሰይጣን) ፡ ክፋት ፤
5 ከዚያ ፡ በሰዎች ፡ ልቦች ፡ ውስጥ ፡
የሚጐተጉት ፡ ከኾነው ፤
6 ከጋኔኖችም ፡ ከሰዎችም ፡ (ሰይ
ጣናት ፡ እጠብቃለሁ ፡ በል) ።

(ተፈጸመ) ።

# ማውጫ ።


| ተ፡ቁ፡ | ሱራህ ፡ | ገጽ፡ቁ፡ |
|---|---|---|
| 1 | ሱረቱ ፡ አል-ፋቲሐህ ፡ | 1 |
| 2 | ሱረቱ ፡ አል-በቀራህ ፡ | 1 |
| 3 | ሱረቱ ፡ አሊ-ዒምራን ፡ | 33 |
| 4 | ሱረቱ ፡ አል-ኒሳእ ፡ | 51 |
| 5 | ሱረቱ ፡ አል-ማኢዳህ ፡ | 70 |
| 6 | ሱረቱ ፡ አል-አንዓም ፡ | 84 |
| 7 | ሱረቱ ፡ አል-አዕራፍ ፡ | 100 |
| 8 | ሱረቱ ፡ አል-አንፋል ፡ | 118 |
| 9 | ሱረቱ ፡ አል-ተውባህ ፡ | 125 |
| 10 | ሱረቱ ፡ ዩኑስ ፡ | 138 |
| 11 | ሱረቱ ፡ ሁድ ፡ | 148 |
| 12 | ሱረቱ ፡ ዩሱፍ ፡ | 158 |
| 13 | ሱረቱ ፡ አል-ረዕድ ፡ | 167 |
| 14 | ሱረቱ ፡ ኢብራሂም ፡ | 172 |
| 15 | ሱረቱ ፡ አል-ሒጅር ፡ | 177 |
| 16 | ሱረቱ ፡ አል-ነሕል ፡ | 181 |
| 17 | ሱረቱ ፡ አል-ኢስራእ ፡ | 191 |
| 18 | ሱረቱ ፡ አል-ከህፍ ፡ | 200 |
| 19 | ሱረቱ ፡ መርየም ፡ | 209 |
| 20 | ሱረቱ ፡ ጣሃ ፡ | 214 |
| 21 | ሱረቱ ፡ አል-አንቢያ ፡ | 222 |
| 22 | ሱረቱ ፡ አል-ሐጅ ፡ | 229 |
| 23 | ሱረቱ ፡ አል-ሙእሚኑን ፡ | 236 |
| 24 | ሱረቱ ፡ አል-ኑር ፡ | 242 |
| 25 | ሱረቱ ፡ አል-ፉርቃን ፡ | 250 |
| 26 | ሱረቱ ፡ አል-ሹዓራእ ፡ | 255 |
| 27 | ሱረቱ ፡ አል-ነምል ፡ | 263 |
| 28 | ሱረቱ ፡ አል-ቀሶስ ፡ | 270 |
| 29 | ሱረቱ ፡ አል-ዐንከቡት ፡ | 277 |
| 30 | ሱረቱ ፡ አል-ሩም ፡ | 283 |
| 31 | ሱረቱ ፡ ሉቅማን ፡ | 287 |
| 32 | ሱረቱ ፡ አል-ሰጅዳህ ፡ | 290 |
| 33 | ሱረቱ ፡ አል-አሕዛብ ፡ | 293 |
| 34 | ሱረቱ ፡ ሰበእ ፡ | 300 |
| 35 | ሱረቱ ፡ ፋጢር ፡ | 305 |
| 36 | ሱረቱ ፡ ያሲን ፡ | 309 |
| 37 | ሱረቱ ፡ አል-ሳፍፋት ፡ | 314 |
| 38 | ሱረቱ ፡ ሷድ ፡ | 320 |
| 39 | ሱረቱ ፡ አል-ዙመር ፡ | 325 |
| 40 | ሱረቱ ፡ አል-ሙእሚን ፡ | 331 |
| 41 | ሱረቱ ፡ ሐ ፡ ሚም ፡ አል ሰጅዳህ ፡ | 338 |
| 42 | ሱረቱ ፡ አል-ሹራ ፡ | 342 |
| 43 | ሱረቱ ፡ አል-ዙኽሩፍ ፡ | 347 |
| 44 | ሱረቱ ፡ አል-ዱኻን ፡ | 353 |
| 45 | ሱረቱ ፡ አል-ጃሢያህ ፡ | 355 |
| 46 | ሱረቱ ፡ አል-አሕቃፍ ፡ | 358 |
| 47 | ሱረቱ ፡ ሙሐመድ ፡ | 362 |
| 48 | ሱረቱ ፡ አል-ፈትሕ ፡ | 365 |
| 49 | ሱረቱ ፡ አል-ሑጁራት ፡ | 368 |
| 50 | ሱረቱ ፡ ቃፍ ፡ | 370 |
| 51 | ሱረቱ ፡ አል-ዛሪያት ፡ | 373 |
| 52 | ሱረቱ ፡ አል-ጡር ፡ | 376 |
| 53 | ሱረቱ ፡ አል-ነጅም ፡ | 378 |
| 54 | ሱረቱ ፡ አል-ቀመር ፡ | 381 |
| 55 | ሱረቱ ፡ አል-ረሕማን ፡ | 383 |
| 56 | ሱረቱ ፡ አል-ዋቂዓህ ፡ | 386 |
| 57 | ሱረቱ ፡ አል-ሐዲድ ፡ | 389 |
| 58 | ሱረቱ ፡ አል-ሙጃደላህ ፡ | 393 |
| 59 | ሱረቱ ፡ አል-ሐሽር ፡ | 396 |
| 60 | ሱረቱ ፡ አል-ሙምተ ሒናህ ፡ | 398 |
| 61 | ሱረቱ ፡ አል-ሶፍ ፡ | 400 |
| 62 | ሱረቱ ፡ አል-ጁሙዓህ ፡ | 402 |
| 63 | ሱረቱ ፡ አልሙናፊቁን ፡ | 403 |
| 64 | ሱረቱ ፡ አል-ተጋቡን ፡ | 404 |
| 65 | ሱረቱ አል-ጠላቅ ፡ | 406 |
| 66 | ሱረቱ ፡ አል-ተሕሪም ፡ | 408 |
| 67 | ሱረቱ ፡ አል-ሙልክ ፡ | 409 |
| 68 | ሱረቱ ፡ አል-ቀለም ፡ | 411 |
| 69 | ሱረቱ ፡ አል-ሓቃህ ፡ | 414 |
| 70 | ሱረቱ ፡ አል-መዓሪጅ ፡ | 416 |
| 71 | ሱረቱ ፡ ኑሕ ፡ | 418 |
| 72 | ሱረቱ ፡ አል-ጂን ፡ | 419 |

# ማውጫ ።


| ተ፡ቍ፡ | ሱራህ ፡ | ገተ፡ቍ፡ |
|---|---|---|
| 73 | ሱረቱ፡ አል-ሙዘሚል፡ | 421 |
| 74 | ሱረቱ፡ አል-ሙደሢር፡ | 422 |
| 75 | ሱረቱ፡ አል-ቂያማህ፡ | 425 |
| 76 | ሱረቱ፡ አል-ደህር፡ | 426 |
| 77 | ሱረቱ፡ አል-ሙርሰላት፡ | 428 |
| 78 | ሱረቱ፡ አል-ነበእ፡ | 430 |
| 79 | ሱረቱ፡ አልናዚዓት፡ | 431 |
| 80 | ሱረቱ፡ ዐበሰ፡ | 433 |
| 81 | ሱረቱ፡ አል-ተክዊር፡ | 434 |
| 82 | ሱረቱ፡ አል-ኢንፊጣር፡ | 435 |
| 83 | ሱረቱ፡ አል-ሙጠፊፊን፡ | 436 |
| 84 | ሱረቱ፡ አል-ኢንሺቃቅ፡ | 437 |
| 85 | ሱረቱ፡ አል-ቡሩጅ፡ | 438 |
| 86 | ሱረቱ፡ አል-ጣሪቅ፡ | 439 |
| 87 | ሱረቱ፡ አል-አዕላ፡ | 440 |
| 88 | ሱረቱ፡ አል-ጋሺያህ፡ | 441 |
| 89 | ሱረቱ፡ አል-ፈጅር፡ | 442 |
| 90 | ሱረቱ፡ አል-በለድ፡ | 443 |
| 91 | ሱረቱ፡ አል-ሸምስ፡ | 444 |
| 92 | ሱረቱ፡ አል-ለይል፡ | 445 |
| 93 | ሱረቱ፡ አልዱሓ፡ | 446 |

| ተ፡ቍ፡ | ሱራህ ፡ | ገጽ፡ቍ፡ |
|---|---|---|
| 94 | ሱረቱ፡ አል-ኢንሺራሕ፡ | 446 |
| 95 | ሱረቱ፡ አል-ቲን፡ | 447 |
| 96 | ሱረቱ፡ አል-ዐለቅ፡ | 447 |
| 97 | ሱረቱ፡ አል-ቀድር፡ | 448 |
| 98 | ሱረቱ፡ አል-በይናህ፡ | 448 |
| 99 | ሱረቱ፡ አል-ዘልዘላህ፡ | 449 |
| 100 | ሱረቱ፡ አል-ዓዲያት፡ | 450 |
| 101 | ሱረቱ፡ አል-ቃሪዓህ፡ | 450 |
| 102 | ሱረቱ፡ አል-ተካሡር፡ | 451 |
| 103 | ሱረቱ፡ አል-ዐስር፡ | 451 |
| 104 | ሱረቱ፡ አል-ሁመዛህ፡ | 452 |
| 105 | ሱረቱ፡ አል-ፊል፡ | 452 |
| 106 | ሱረቱ፡ ቁረይሽ፡ | 453 |
| 107 | ሱረቱ፡ አልማዑን፡ | 453 |
| 108 | ሱረቱ፡ አል-ከውሠር፡ | 454 |
| 109 | ሱረቱ፡ አል-ካፊሩን፡ | 454 |
| 110 | ሱረቱ፡ አል-ነስር፡ | 455 |
| 111 | ሱረቱ፡ አል-ለሀብ፡ | 455 |
| 112 | ሱረቱ፡ አል-ኢኽላስ፡ | 456 |
| 113 | ሱረቱ፡ አል-ፈለቅ፡ | 456 |
| 114 | ሱረቱ፡ አል-ናስ፡ | 457 |